# መረቅ



አዳም ረታ

# መረቅ

## አዳም ረታ

ተርበቻችን በመኪ. ተቱ.ር ፈ.ር
ይሞቱሉ.

© አዳም ረታ

አምስተኛ ህትመት 2012

## ስጦታ:

ለማንያዘዋል እንደሻው/ለተፈሪ አለሙ/ለሐረገወይን ከበደ

ሕይወት እንደ በግኩል አገዶ ነው ፣ ማን ነው ያለው?

እንዳሁን ተክሎ [illegible] ያስቸግረኛ

ተቆጥሮን እግር ከራብ በንሆን ያኔ በግኩራው መለስ ሰት ነው።

**በእርትእት ስራ ላገዘኝ ለማንያዘዋል እንደሻው ምስጋናዬን አቀርባለሁ።**

ዘሮን በዘዘ ተሽቶኛሎ መሬቱ ይፎጋል [illegible]

የሕይወታችን እንቆ [illegible]

[illegible]

መቼ በራብቶችን መቃተ [illegible]

[illegible]

[illegible]

ደግሞ መሬት እንደዘታችንን በደበ ይሞቁል

ወደም

**ትርቦቻችን በመክ. ተቆ.ር ፌር ይሞቁሉ...**

ደግ

የጎንቻችን ተሕይወት ትንሽ የለውም።

# ይዘት


ክፍል ፩ ................................ 7

ሁረቱ ዓላዛር ................................ 9

መዋዕለ ላይፐዚግ ................................ 159

ተባረኪ፡ 'ሁለት ፍቅር ያመናቅር' ................................ 213

መዋዕለ አዋሳ ................................ 289

ክፍል ፪ ................................ 329

ጥብስና ጠበል ................................ 331

መዋዕለ ቃዚና ................................ 411

ማከዳ፡ 'ሰዶ ማሳደድ ሲያምረኝ' ................................ 439

መዋዕለ አየር ጤና ................................ 545

ክፍል ፫ ................................ 585

እንጓና መለልታ ................................ 587

ስለ እንጀራ ባለጣ፡ መግቢያ ................................ 595

መውጫ ................................ 603

# ክፍል ፩

ቸርቦቻችን በመኪ። ቸቀር ፈር ጀምቱሉ።

# ሁረቱ ዓላዛር



## የፍቅሬ ፍልስፍና

እይ!......ተራሮቹ ሰማዩን ሲስሙ
የባሕር ማዕበሎችም ሲተቃቀፉ::
የሆነች አበባ ወንድምዋን ብታርቀው
‘ጎሽ’ የሚላት ማነው:::
የፀሐይ ብርሃን ምድርን ይጨብጣል
እግረ—ጨረቃ ባህሩን ይጨመጭማል
የነዚህ ሁሉ ‘እሟ’ ትርፉ ለምንድነው?
አንተ እኔን ካልሳምከኝ?
አብረን ካልታየርነው::

(የፐርሲ ሼሊ *የፍቅር ፍልስፍና* (love's philosophy)
በተባለው ግጥሙ ላይ (ሁለተኛው ክፍል) የተመሠረተ
ሉንዶን፣ ሃይድ ፓርክ 1980 እም
ትርጉም በፀናፅል ተ. ማርያም

## የመዲባ ኡሪ

ከዕለታት አንድ ቀን 'ጣይቱ' የተባሉ እተጌ እዛች ፍልውሃ የምትባለው የምትጤስ ቦታ፣ እዛች እርጥብ ፊንፊኔ ገላቸውን ተታጣጥበው ጨርሰው፣ ከተቀመጡበት በርጬማ ብድግ ሲሉ፣ እንደ ደንግ የምታበራ የሕልም እንቁላላቸው የምትሞቅ ግልገል ኩሬ ውስጥ ወደቀች:: ከዛም ወደ ተሰራላቸው ማረፊያ ጎጆ አቀበቱን ሲያዘግሙ፣ ስሟ የተጠራ ከተማ የመቆርቆር ምኞታቸው በሚያልፉበት ጎዳና ላይ ከአንደበታቸውና ከረጠበ ጉንጉናቸው ተንጠባጠበ:: ባለቤታቸው ንጉሠ ነገሥት ሚኒሊክን ጨምሮ ሕዝቦች ያን ከፍልውሐ ጉም እስከ ባዕታ ወይራዎች ድረስ የተዘራውን የእመቤታቸውን ምኞት አተኩረው እንደ ጥሬ ለቀሙ (ምንም እንኳን በንግርት ባላቸው እንጦጦ ላይ የታፈረ መንግስት እንዲያቆሙ ንግርት አለ ቢባልም):: ቅጠል በልቶ ከተነበየ ባሕታዊና አውቃለሁ ባይ የአምደ ዕዮን ዘመን ደብተራ ይልቅ ጎርጎራ ከተማ በጣና ዳር በመረጋጋት የሰለጠነ የንግሥት ጣይቱ ድምቡሼ ገላ ትንቢትን አሸነፈ:: ብዙም ሳይቆይ ሚኒሊክ እንጦጦ ማርያም ግቢ ጉባኤ ጠርተው መኳንንቶቻቸውን እንዲህ አሉ:

«አዲስ አባን እንካችሁ:: ተጠራርታችሁ ሙኗት»

እነሱም እንደ ተባሉት ሠራዊቶቻቸውን እየመሩ ፍል ውሃ ዙሪያ ሳርና ጭቃ ላይ እንደ ጨርቅ ተጣፉ፤ እንደ ድንጋይ ተኮለኮሉ: ሽጎሌ፣ አባ ኮራን፣ ጉለሌ፣ ጎላ፣ ቶረት ሰፈር፣ ሠራተኛ ሰፈር፣ አራዳ......እንዲያ እንዲያ እያለ በጅረትና በወንዝ የተሸረሸረች፣ አፈርና ሳር የነበረችው የፊንፊኔ ሜዳ በሰውና በጎጆ፣ በሰንሰልና በባሕር ዛፍ ሞላች:: ዘመናዊ ለመሆን ማሽቃበጥ ስትጀምር በ1928 ጣሊያን ገባና በሲሚንቶ፣ በዘረኛነት፣ በአስፋልት......ይሄንንም እንዲያዳምቁ ጦርነት የበተናቸውን ወይዛዝርት ሰብስቦና አደፋፍሮ በመለኮ (እዝራ እንዳለው) አጎለበታት:: 1933እም ላይ ትቷት ሲሄድ የምንወደውን፣ የሚቀርበንንና የምንችልበትን ጠበቅን: ጥቂት ትምህርት ቤቶችን፣ አልሞት ያለ የአስፋልት መንገዱን፣

ለገሃርን፣ ፖፖላሬን፣ ካዛንቺስን፣ ፒያሳን፣ መርካቶን አረቄና ሽርሙጥናን (ልጅን ሲወዱ ከነንፍጡ)፡፡

ያኔ ይሄ ሁሉ ሲሆን ሽሮሜዳ፡ በእግር መንገዶች የተሸነሸኑ አረንጓዴ አራዳ ሜዳዎች የገነኑባት፣ ጥቁርና ቀይ አፈራቸው በዝናብና በኅርፍ የፈረሱ ተረተሮችና አረሆች የተቀረፁባት፣ በጋ በጋ የሚደርቁ ጭቃማ ጅረቶች የሚሰርቡባት፣ ሚዳቋዎች ከተራራው እየዘለሉ መጥተው እየዘለሉ የሚሸሿት፣ በአጋም፣ በቀጋ፣ በቁጥቋጦና በዕድ ደኖች መሃል አሾልከው የሚያዩ ጎጆዎች የፈሉባት፣ ዝግባ ዛፍ ስር ያደፈጡ መንገደኛ መቀበያ ኮሳሳ ማደሪያዎች የተጎለቱባት፣ የቄስ የደብተራና የገበሬ ቅልሳቶች ያፈጠጡባት፣ የበግና የበሬ ነጋዴዎች ጉሮኖዎች የተነቀሱባት፣ ልብሳቸውን ሳር ላይ የሚያሰጡ ወይዘሮዎች የሚያንጎራጎሩባት፣ ጠዋት ማታ የሚንጋጋ ጅብ እዚህና እዚያ በነጭ ኩሱ የነቀሳት ቦታ ነበረች፡፡

እኔም ነጋ ጠባ ባሰፈፈ የእንጨት ጭስና የባሕር ዛፍ ድምድማት ተከልሎ ይኑር አይኑር በማይታወቀው የአዲስ አባ ማዕከልና በዝናብ እየታጠበ፣ የሊሊት ዝምታው ቋጠሮ አሁንም አሁንም በጅብ እሙኝታ፣ በውሾች የሊሊት ሃዝ ሃዝ፣ በሚፈታው የእንጦጦ ተራራ መሃል፣ ከኋለኛው ቀርቤ ከፊተኛው ዕርቄ ተወለድኩ፡፡ የከተማችን ቀያሾች ‘መዲባ’ ይሏታል፡፡ በመዲናና በባላገር መሃል ናችሁ ሊሉን፡፡ እየሰደቡን ይሆን እየመደቡን ይህቺ ማርያም ታውቃለች፡፡

ሽሮሜዳ ‘ሽሮሜዳ’ የተባለችው የአረጋሽ ባል ጋሼ ሰይፉ ሲያወራ እንደሰማሁት እዚህ አካባቢ በድሮ በድሮ ጊዜ ሰዎች አፈሩን ሽሮ መስሎአቸው ወጥ ሰርተው በልተውታል ተብሎ ነው አሉ፡፡ ስለ *የድንጋይ ዳቦ ዘመን* ከተወራ ስለ *የአፈር ሽሮ ዘመን* አይቻልም?

ሽሮን (ስናቆላምጣት) የአዲስአባ ፕላን አውጪዎች ከሚያዳሉላቸው ቦሌና አሮጌው አይሮፕላን ማረፊያ ውበቷ ይበልጣል፡፡ የመስከረም አረንጓዴና ቢጫነቷን? በመንገዶች ግራና ቀኝ ከእንጦጦ የሚወርደውን ወርቅማ ውሃዋን......እንጦጦ ወጥተን በላስቲክ ኮሮጆ ሰብስበን የምናመጣቸውን ልጋምና ቀጋዋን ማን ይስተካከላታል?

ሽሮሜዳ እያደገች ብዙ ሰዎች ሊኖሩባትና ሊሰሩባት መጡ፡፡ የአልማዝ ጉርጉሱም ሆቴልና ተራራ ካፌቴርያ ተከፈቱ፡፡ ግራና ቀኝ በየመንገዱ ዳርና ዳር ቡና፣ ጠላና አረቄ ቤቶች ተደረደሩ፡፡ ጥቂት ልብስ ሰፊዎችና የልብስ ሱቆች እዛ እዛ ተተከሉ፣ የሚያምር አጂፕ ነዳጅ ማደያ ከተራራ ሆቴል ዝቅ ብሎ ተከፈተ፡፡ ጫማ ሰሪዎች ትናንሽ መጠለያቸው ውስጥ መዶሻቸውን ይዘው ተቀመጡ፡፡ በዚያች ጥቁር ሰረሰር በመሰለች

እስፋልት መንገዳችን ጠርዝ ሸንኮራ ሻጩ ዋሕድ እየተጎማለለ መዘየር ጀመረ፡

*የዚህ ሰፈር ሰዎች ሕብስት አያምራቸው፣*
*አጅሬ ሸንኮራ ገብቶ ከቤታቸው!!*

ቅልብጭ ባለችው ለግላጋ የመንደራችን ካርታ ላይ ሰካራም በረታ፡፡ እኔም እንደ በአካባቢዬና እንደ አካባቢዬ ብዙ አለማዊ ዕውቀት ተማርኩ፡፡ ጊዜ አልወሰደብኝም በጉጉቴ ስፋትና በቀልቃላነቴ ጥልቀት ከከተማውም ከገጠሩም የደባለቀ የመዲባ ዜጋ፣ ደህና ዲቃላ ሆንኩ፡፡

## መግነጢስ አንድ፡ እኔ በአገሬ እንኳን ሰው ኢሊ አለምጻለሁ

ዝርዝሮቹ ትዝ የሚሉኝ አልፎ አልፎ ቢሆንም፣ የልጅነት ጊዜዬን በአጠቃላይ፣ በተንጠባጠበ መልክ አስታውሳለሁ......

አያቴ እናኑን ለማየት ከሞግዚቴ ከፀሐይ ጋር መስፍን ሃረር መንገድ (ዛሬ በላይ ዘለቀ የተባለው) ለመሄድ ብቻ ካልሆነ ከቤቴ ወጥቼ ከማንም ጋር ሰፈር ውስጥ እንድውል፣ ከሰፈር ልጆች እንድቀላቀል አይፈቀድልኝም ነበር:: የማይረሱኝ ነገሮች አሉ:: የማይረሱኝ ገጠመኞች አሉ:: የማይረሱኝ ሰዎች አሉ:: የማይረሱኝ ነገሮች፣ የማይረሱኝ ገጠመኞችና የማይረሱኝ ሰዎች አሉ::

በፍፁም የማልረሳቸው ልክ ዛሬ እንደሆኑ ሁሉ ትዝ የሚሉኝ ጥቂት ቀኖች አሉ......በሆን አጋጣሚ እንደ ውሻ ቡችላ በሞግዚቴ በፀሐይ እግሮች መሃል ሾልኬ አምልጬ ወደ ሰፊዋ ሸሮሜዳ ካመለጥኩ በኋላ አልተመለስኩም:: ከታዚና ሆቴል የሚወጡ ሰካራሞች አየሁ:: ዋሻ ከሚመስሉ የመጠጫ ዛኒጋባዎች ሰምቼው የማላውቅ ሙዚቃ ሰማሁ:: የእኔ ዕድሜ እኩያ ልጆች ባዶ እግራቸውን ሲሮጡና ሲዘሉ አየሁ:: በቁምጣው ቀዳዳ፣ በኋላ ጓደኛዬ የሆነው የቸርነትን አፍረት ታዘብኩ:: ያን ቀን ፀሐይ በቁጣና በእርግማን ደጋግማ ወደ ቤት እንድገባ ብትጠራኝም ሆን ብዬ አልሰማኋትም:: እዛ መንገድ ዳር በመገረም አፌን ከፍቼ እንደቆምኩ ቄስ ታዚና የሚባሉ የታዚና ሆቴል ባለቤት ብስክሌት ከሚገፉ ልጃቸው ጋር በአጠገቤ ሲያልፉ እንዲህ አሉ፡

«ልጅት አንተን ነው የምትጠራው አይደል?»

«አይደለም» አልኩዋቸው::

ከት ብለው ሳቁ:: ከዛ ፊታቸውን ኮስተር አድርገው፡

«ዋሸኸኝ:: በል ሰበብ ሆነህ አታስቆጣት:: ግባላት»

እጆቼን ከሱሪ ኪሶቼ ሳላወጣ አባትዬውንና ልጅዬውን እያቀያየርኩ አየኋቸውና፡

«ብስክሌቱ የአንተ ነው?» አልኩት ልጁን::

«አዎ ምነው መጋለብ ፈለግህ?» አለኝ

«አልችልም»

«ምን መሆኑ ነው ይሄ ቀልቃላ የሰው ልጅ ልትገል ነው?» አሉና ቄሱ ልጃቸውን እናቱ ላይ ከሁዋላው በጥፊ መቱት::

ያኔ እናቴ በፀሐይ ተጠርታ ከግቢ ወጥታ በንዴት እያጉተመተመች ወደ መንገዱ ዳር መጣች::

«ጤና ይስጥልኝ እትዬ ሮዛ!» አሉ ቄሱ፤ ቀና ብለው ወደ ሁዋላዬ እያዩ

«እንደምን አሉ መሪጌታ!»

«እሱ ይመስገን፡ ይሄ ደቦል የታሰረበትን እየፈታ ይወጣ ጀመር»

'ደቦል' ምን እንደሆነ አላውቅም ነበር:: የቃሉ እንግዳ መሆኑ ትውስታዬ ውስጥ ተዝናንቶ እንዲቀመጥ አድርጎታል::

«አልቻልኩትም:: (አጠገቤ ደረሰችና ተግሳፅ በተቀላቀለበት ስልት እጄን ነጠቅ አድርጋ ያዘችኝ) አንድ ነገር የሆነብኝ መሰሉኝ ኡኡ ማለት ነው የቀረኝ»

«እማማ ብስክሌት እፈልጋለሁ» አልኩ ሳላመነታ ቀና ብዬ እያየኋት

«ብዙ ልጆች እኮ የሉም ሰፈራችን:: ምናለበት ይጫወት:: ለልጅ የተመቸ ሁሉ የሚያምር ነገር ነው ያለው:: ይሄም የእኔው እዝራ ትልቅ ነው ይጠብቀዋል፣ ቢጫወት:: ልጄ ብስክሌት መጋለብ ያለማምደዋል» አሉ ፈገግ ብለው

«ገና አቅም የለውም እኮ:: ይሄ አፉ ተንቀለቀለ እንጂ፣ አደግሁ አደግሁ ብሎ» አለች እማዬ::

«ለመሆኑ እናኑ ደህና ናት? እንዳመማት እሰማለሁ:: አስታማሚዋ ደሞ ይሄ ጎረምሳ ነው አሉ»

«እሱን ካላየች አትተኛም፤ ያለ እሱ አይሆንላትም»

«እናኑ ጆሮ ቢያገኙ ብዙ ነገር፣ ብዙ ብዙ ነገር ያውቃሉ:: መገናኛው ጊዜው የለም እንጂ:: እንደው ያኔ......ሌላ ጊዜ እንጫወታለን፣ ብዙ ነገር......ብዙው ነገር የእግዜር ነው:: አየሽ? ሌላ ጊዜ እናወራዋለን:: ለማንኛውም ዛሬ ይዘሽው ግቢ:: ሲቻል ከእዝራ ጋር ይጫወት:: እዝራ ዲያቆን ነው እኮ:: ዜማ እየተማረ ነው:: ታውቂ የለ? ልጄ ስለሆነ ሳይሆን ብሩህ ነው፣ ወደ ተንኮሉ ያደላል እንጂ:: ቤተ ክርስቲያንም ይወስደዋል:: አንቺ ብቻ ነሽ እንዴ? ልጅሽም ማርያምን ይሳለም»

* * *

የሚነቀፍ፣ የሚደገፍ፣ የሚያስቅና የማያስቅ ኩሸት እየጠጣሁና እየበላሁ አደግሁ……

ይሄ እዝራ ታዚናና በሁዋላ ያወቅሁዋቸው የእሱ ጓደኞች በእናቴ ፈሪነትና በአባቴ የሃብታምነት ኩራት የተጋረዱትን ዐይኖቼን ገልጠው አለምን ያሳዩኝ መሪዎቼ ነበሩ:: ብዙ ጊዜ እደጅ ተገናኝተን የምንጫወተው እየመሸ የአየሩ ጣዕም የገነት ነገር ነኝ ሲል ነው:: ነፃነቱን ማወጅ የሻተ ጅብ የመጀመሪያውን ደንገዝጋዛ እሙጓ ከሩቅ ሲለቅ:: ያኔ አስፋልቱ ጭር ስለሚል ልባችን እስከሚጠፋ ብስክሌቶቻችንን በመንገዱ ላይና ታች እንጋልባለን:: በዚህ እብደታችን አስፋልት ላይና የአስፋልት ዳር የእግር መንገዶች ላይ ደጋግሜ ወድቄአለሁ:: ይሄን የሚመሰክሩ ግራ ቀርጭምጭምቴና ሁለቱም ጉልበቶቼ ላይ ድርብርብ ጠባሳዎች ዛሬ ድረስ አሉ:: ጎንበስ ብዬ ባይ መስታወት በመሰለው የጠባሳዎቹ ቆዳ ላይ የሚንፀባረቀው የሽሮሜዳ ልጆች ፊት ነው::

አስፋልቱን ይዘው ወደ እንጦጦ ሲወጡ በስተቀኝ ልጃገረዶች በስኞ ማክሰኞ፣ በገመድ ዝላይ፣ በቅልልቦሽ ለራሳቸው የከለሉት፣ በእግሮቻቸው ሳሩን ያቃጠሉትና አፈሩን የደቀደቁት መሬት ሶስት አራት ቦታ አለ:: ይሄ መላከፊያችን፣ ማልቀሻና ማስለቀሻችን ነበር:: እናትና አባቴን ሳላስፈቅድ ሳንቲም ከፍዬ ሸንኮራ መብላት ለመድኩ:: ጥርሶቼ እሱን በመላጥ ጡንቻ አበቀሉ:: ከዋሕድ ስር ስር እየሄድኩ በዘፈኑ ማሾፍ ሰለጠንኩ::

*ይሄው በአምስት ሳንቲም ያማረ ወለላ፣*
*ሰውን የሚያዋድድ ሰው የማያጣላ፣*
*ዋሕድ ጋ አለላችሁ የሸንኮር መለላ!!*

ከምኖርባት ቅንጃ የሽሮሜዳ ቪላ ውጭ አባትና እናቴ ከሚያጠጡኝ ሾርባ፣ ቺዝ ሳንድዊች፣ በእሳት የጠቆረ የበግ ጥብስ፣ በቢላ ጫፍ ሲነኩት ከሚበታተን የበግ አሮስቶ፣ ተቋጥሮ ከሚፈታ ነጭ እንጀራ፣ አርፎ ሲቀመጥ መረቅ ከሚጋርደው ቀይ ወጥ የበለጠ የሚያንዘረዝር ደስታ የሚሰጡ ነገሮች እንዳሉ አየሁ:: ስትኖ የሚናፍቀኝ ነግቶልኝ እዳሪ መሰደዴ ሆነ:: ይሄ ከቤቴ ውጭ ዕጣዬ ያዘዘችልኝ መግነጢስ ነበር::

ብዙ ጊዜ እሁድ እሁድ ከእዝራ፣ ከቸርነት፣ ከተስፋዬ፣ ከዳኜ፣ ከደበበ፣ ከበፍቃዱ፣ ከአማን፣ (ሰፈሩን ወደ ታች ሳይለውጥ በፊት) ጋር ሆነን እንጦጦ እንወጣለን:: የማንጫወተው የጨዋታ አይነት አልነበረም:: ዳኜ ጢብ ጢብ አሰለጠነኝ:: እሱን ነገር ስለምወድ ከረምት ካለፈ በሁዋላ ተሰብስበው የታሰሩ መዓት የደረቁ የቅጠል ኳሶች ቤቴ ግቢ በየቦታው

ወድቀው ይገኙ ነበር:: በእጅ ቦምብ ጨዋታ የተጠለዙ መዓት የሸራ ኳሶች እንጦጦ ማር ዋሻ ገደል ስር ጠፍተውብኛል፤ በሌባና ፖሊስ ልፊያ ቁልፉ ያልተበጠሰ ሸሚዝ፣ ማንገቻቸው ያልተበጠሰ ሱሪዎች አልነበሩኝም፤ በመሃረቦሽ ሩጫ ተጠልፌ ደጋግሜ ወድቄአለሁ፤ አይኖቼም ተዘነቁለዋል፣ ክንዶቼ ተቧጨረው ደምተዋል:: የማዘጋጀ እግር ኳስ ገንዘብ አስይዘን ያልተራኮትንበት የአስፋልት ዳር የቱ ነው? ከፍታ ላይ ተቀምጠን፣ ተከሉች መሃል ተደብቀን በተሰበረ የፊት መስታወት፣ ስንት ወደ ገጠር የሚነዳ ሾፌር በብልጭታው አበሳጭተናል:: ጨዋ ከተባሉ ጎልማሶችና አዛውንት በልባቸው ደብቀው የያዙትን አስቃቂና አስቂኝ እርግማንና ስድብ አፍርጠን አውጥተናል:: ተዳክመን ስናርፍ ደበበ ሞፎ በሚያምር ድምፁ የጊታቸው ካሳን ትዝታ ሊያንቀረቁርልን ይለፉል:: ዳገት ላይ ቆመን እንዳሻችን 'የማን ይገናል?' ፉክክር የምንለቃቸው ባዶ ትርጉም የለሽ የኩሽት እሪታዎች ከዛፎቹ ጋር በቅለዋል፣ ከቅጠሉች ጋር ተንዠርግዋል::

ዛፍ ስትቆርጥ

ከቅጠሎቻቸው እሪታና ሳቅ

ከእንጨቶቻቸው ሁካታና ዘፈን ከሰማህ

የእኛ ናቸው

የውጭው ጨዋታ ሲሰለቸን እኔ ቤት ገብተን ዳማና ቼዝ እንጫወታለን:: እነዚህ ሲሰለቹን ደሞ ከቴፕ ሙዚቃ እየሰማን አብረን እያንጎራጎርን በተሚምፕቴሽን ላይ ዶሽ ሊት ዉድ ሬይን፣ በሞንኪስ ላይ ላም ኤ ቢሊቨር፣ በሮሊንግ ስቶንስ ጃምፒንግ ጃክ ፍላሽ፣ በካፒቶልስ ኩል ጀርክ፣ በቢግ ጆና በሉዊ ጆርዳን ቡጊ ዉጊ፣ በስኮት ጆፒሊን ሉገር ሌን ራግ እንደንሳለን:: እየቀደሰኩ ይሄን አላደርግም ስለሚለን ከእዝራ በስተቀር ሁላችንም እንደንሳለን:: ይሄ ደሞ ሲደክመን፣ በአሌ ቡም እጆቻችንን እናነዳለን:: እማዬ ይሄ ሁካታችን ረብሿት እንዳትነዘንዘን እዝራ ብልጡ ከመሃል እንዲህ ይላታል:

«እትዬ ሮዛ የሕኒሱን ዘፈን እርሺና ልቀድስልሽ?»

ልታዳምጠው በስርአት ትቀመጣለች:: ከማንም ዘፋኝ አፍ ወጥቶ ሰምቼው በማላውቅ የሚያምር ድምፅ(እሱ 'የኢዩኤል ዮሐንስን ይመስላል' ይለናል) እስኪያልበው ትክክለኛ ግዕዝ ይሁን አይሁን ይቀድስላታል:: ሲጨርስ፣ እማማም ደስ ስለሚላት (ምን እንደቀደሰ ባታውቅም)፣ ቤት ያፈራው ምግብ ሁሉ ጠረጴዛ ላይ ይደረድርልናል::

ጨዋታ ብቻ አልነበረም:: ትንንሽ የልጅነት ሴራዎች ውስጥ በፍስሃ ታላላቆቼ ነክረውኛል:: የላይኛው እንዱን ጥርሴን ማውለቅ ፈርቼ ማንም

ሲያደርገው ያላሁትንና ብዙ ሰው የማያውቀውን ልዩ ጥበብ ያሳየኝ እዝራ ነው:: የተነቃነቀችውን ጥርስ ከበቀለችበት ስር በረዥም ክር አስሮ 'ሄደህ ከልጆች ጋር ተደባልቀህ ተጫወት' አለኝ:: ቀይ ክር ከከንፈሮቼ መሃል እስከ ሆዴ እንደ ሽረሪት ድር እየተንሳፈፈ ልጆች መሃል ለጨዋታ ገባሁ:: አንድ ደቂቃ ሳልቆይ ቸርነት:

«ምንድነው ይሄ!?» ብሎ ተንቀልቅሎ ክሩን ሲጎትት ጥርሴን ነቀለውና ተገላገልኩ:: ይሄን ለእናቴ ነግሬአት ዕንባ ከአይኖቿ እስኪወርድ ሳቀች::

አደቦቃ ጢንዚዛ ከዕጌሬዳ ዛፍ ላይ ለቅሞ እግሮቿን በክር አስሮ ለሳምንት በሰፈርና በትምህርት ቤት እያበረርኩ በተደናቂ ልጆች ተራ ያስመዘገበኝ እዝራ ነው:: በዚህ ጢንዚዛ ስኮራ ቆይቼ አንድ ቀን መኝታ ቤቴ ብርድ ልብስ ስር ገብቶ ጨፍልቄ ገደልኩት::

አባቴ እሱን ወደሚመስሉ የተማሩ ሃብታም ዘመዶቹና ጓደኞቹ አጣጥቦና አለባብሶ ሲወስደኝ ከንፅሕናና ከጥሩ ምግብ በቀር ምንም አያጋጥመኝም:: ብጫወትም ከልቤ አይደርስም:: እዛ ካሉት አስርና አስራ አምስት ሕፃናት የምቀርባቸው ጥቂት ነበሩ:: ሐብታሞች ግቢ ወንበር ላይ ተደርድረን ወይ በተከረከመ ሳር ላይ ያልቆሸሸ ኳስ ስናንከባልል (ጭቃ ሲነካበት 'ኳሴ ቆሸሸ!' ብሎ የሚያለቅስ አለ) እና ደሞ 'ዞር በሉ ከአበባው ጋ' እየተባልን፣ ምሁራኑና ዘናጭ ሚስቶቻቸው ሲነጅሱኝ ሰፈሬ ይናፍቀኛል:: ብዙ ጊዜ ተደብሬ እቀመጣለሁ:: ከእዝራና ከዳኜ ጋር ጨጎጎት እየተወራወርን ልብሳችንን አበላሽተን፣ ሰፈር ከመድረሳችን በፊት ደሞ በወላጆቻችን ላለመተረብ እንደ ዝንጀሮ ተከባበን የተጣበቁብንን ከልብሳችን ላይ ስንለቅም ትዝ ይለኛል::

ሳንድዊች ተሰርቶ በስርአት ተደርድረን ስንበላ ትዝ የሚለኝ እንጦጦ እዝራ ማር ዋሻ የወረዛ ገደል ላይ ተንጠላጥሎ ከተንዠረገጉ ሃረጎች ላይ ለቅሞ ያመጣው ሐምራዊ ቀለም ያለው የሚያምር አበባ ነው:: የእሱን ጎድጓዳ በአጋምና በእንጆሪ ሞልተን እንደ ዳቦ የገመጥነው:: አፉን በዚህ ሞልቶ:

'ይሄን ሁልጊዜ ብትበዪ አታረጂም' ያለኝ ትዝ ይለኛል:: አበባዎቹን እናፍቃለሁ:: የእዝራን ኩሽት እናፍቃለሁ::

*

አንድ ክረምት ነው:: ነሐሴ ወይም ሐምሌ:: ብቻ ዝናብ ዘንቦ ሊያልቅ አንዳንድ ነጠብጣብ ይወድቃል:: ትንሽ ቅዝቃዜ አለ:: ሰማዩ እንደ መስኮት በስተምስራቅ ተከፍቶ ደስ የሚል ወጋገን ይወርዳል:: አስፋልቱ ንፁሕ የመሰለ ጥቁር ነው:: አልፎ አልፎ መኪናዎች ይወጣሉ ይወርዳሉ::

እላይ ሱቅ በረንዳ ላይ አንድ ሰው ቆሞ ሲጃራ አተማትኳል። የሚያምር ነጭ ጭስ ወደ መንገዱ እየተሳበ እስፋልቱ ጋ ሳይደርስ በነፋስ ይበታተናል። ታዚና ሆቴል ፊት ለፊት አንድ የአባቴን የመሰለች ነጭ ታኑስ መኪና ቆማለች። መንገድ ተሻግሬ ትልቅ ምንጭ ሽር የመሰለ ውሃ የሞላ ቦይ መርጬ አረንጓዴ የላስቲክ ኳሴን ከላይ እየወረወርኩ ከታች እየለቀምኩ ስጫወት፣ እዝራ ከእንጦጦ አቅጣጫ ከዳገቱ አስገራሚ ነገር እያደረገ ሲመጣ አየሁት። የመንገዱን ቀኝ ደርዝ ይዞ ትልቅ ጭቃ የመሰለ ኢሊ ላይ ተቀምጧል። ኢሊው አራት እግሮቹን ወጥሮ ቆሞ በፍጥነት ይራመዳል። እንደዛ ትልቅና እንደዛ ፈጣን የሆነ ኢሊ አይቼ አላውቅም። እዝራ ኢሊው ጀርባ ላይ ጎበጥ ብሎ የተለመደ ነገር እየሰራ እንደሆነ ሁሉ እየሳቀ ቁጭ ብሏል። የኢሊው አንገት ዙርያ ገመድ አለ። ገመዱን እዝራ እንደ ልጓም ይዞታል። እኔ ብቻ ሳልሆን በመንገድ ላይ የነበሩ ጥቂት ሰዎች በመገረም ከጉዞአቸው ተገ ብለው አፋቸውን ከፍተው በመሆን ላይ ያለውን ጉድ ያያሉ። የምንገበገብላት ኳሴን እነበረችበት ውሃ መሃል ትቼአት እዝራ ወደ አለበት በሩጫ ዳገቱን መውጣት ጀመርኩ። እዝራ ቁልቁለቱን እንደጨረሰ ደረስኩበት። ተጠግቼ ቆሜ ሳየው ከውስጡ እንዳለ እንኳን የማላውቀው ታላቅ ሳቅ ፈንቅሎኝ ወጣ። ሆዴን ይዤ በሳቅ ስንፈራፈር ከተቀመጠበት ሳይነቃነቅ:

«እዛ ዋሻ ውስጥ አገኘሁት» አለኝ።

ሳቁን አላቆምኩም።

«ምን ያስቅሃል?» አለኝ።

ለእኔ እዝራ በዚያን ሰአት አስቀያሚ፣ ገጣጣ፣ ጎባጣ የደስታ ፈላስፋ ነበር።

በሳቁ ተደናብሮ መሰለኝ ኢሊው አንገቱን ወደ ድንጋዩ ለማስገባት ሲጥር፣ እዝራ ከሳዱ ዙርያ ያሰረበት ወፍራም ገመድ አቆመው። የኢሊው አይኖች ጭንቀት ውስጥ እንዳሉ ሁሉ ፈጠዋል። ሽርታታ ንቅናቄአቸው ነገር የሚፈልግ ተንኮለኛ ልጅ ያስመስሉታል። ገመዱ የሚያልፍበት የኢሊው ሽካራ ቆዳ አመድ መስሏል። አፉን እየከፈተ የሚያስጠላና የሚያስፈራ ቀይ ጉድጓድ ያሳየኛል።

«መሳፈር ትፈልጋለህ?» አለኝ እዝራ።

ስለፈራሁ በእምቢታ ራሴን ነቀነቅሁ። ኢሊው አጠገብ ስቆም ከፍታው ከወገቤ ይደርስ ነበር።

«አትፍራ ና፣ አይሮጥም አይጥልህም። ከመኪና ይመቻል» አለ። መራመድ የጀመረውን ኢሊ ልጓሙን ሳበና አቆመው።

ልቤ ተከፈለ። እዝራ ልጓሙን ለቀቅ ሲያደርግለት ኢሊው ጉዞውን ጀመረ። ጎን ጎን እየተከተልኩ እስቃለሁ። ትንሽ እንደሄደ አብሬው

እንድሳፈር በድጋሚ በአይኖቹ ጠቀሰኝ:: በድፍረት ወስኜ ኤሊውን ልወጣው ስጠጋ የእዝራ አባት ቄስ ታዜና ያለ ጥምጥማቸው ከሆቴላቸው እየተመናጨቁ ሲወጡ አየሁ:: ፈራሁ:: የደነገጡ ዐይኖቼን ተከትሎ እዝራ ፊቱን ሲያዞር አባቱ በሩጫ ወደ እሱ ሲመጡ አየ:: ከተቀመጠበት አልተነሳም::

«አንተ ቀልቃላ ምን እየሰራህ ነው?!»

እዝራ ግራ እንደ ተጋባ፣ መልካም ስራ እየሰራ እያለ እጅ ከፍንጅ እንደ ተያዘ ጨዋ ሁሉ አባቱን እየሳቀ ያያል::

«የቀረህ ይሄ ነበር!»

«ምነው አባባ!?»

«ከየት አመጣሃት?» አሉ

መንገድ ተሻግረው ወደ ነበርንበት መጡ:: በመገረም ኤሊዋን፣ ኤሊዋ ላይ የተቀመጠውን ልጃቸውን፣ በኤሊዋ አንገት የገባውን ልጓም ሲያዩ ቆዩና:

«ጉድ! እያመጣው የለ! በል ውረድ፣ ገመዱንም አውጣላት፣ ይሄ ማርያም ጋ ትኖር የነበረችው ደጀ ሰላም ጠባቂ ኤሊ አይደለችም? ተንኮልህ ወሰን አጣ»

እዝራ አንገራገረ::

«ውረድ አልኩህ!»

ኤሊ እንዴት ማርያምን እንደሚጠብቅ አስባለሁ:: እዝራ ከኤሊዋ ጀርባ ላይ በልግመት ወረደ::

«በል አሁን ወደ አመጣህበት መልስ»

«የት ነው የምመልሰው? ባለቤት እንዳላት የት አውቃለሁ? እላይዋ ላይ እንደ ታርጋ ተፅፏል?»

«መለፍለፍህን አቁምና በል ገመዱን አውጣላት!»

እንዲህ ጭቅጭቅ ላይ እያሉ የሰፈሩ ሰዎችና አላፊ አግዳሚዎች ኤሊዋ ዙርያ ተሰበሰቡ::

እዝራ ገመዱን ከኤሊዋ አንገት ላይ አወለቀና አስፋልት መሃል ጣለው:: ኤሊዋ ያኔውኑ አንገቷን ድንጋዩ ውስጥ አስገባችና ተድቦልቡላ ቁጭ አለች::

«ኤሊው ደሞ ወንድ ነው» አለ ድምፁን ዝቅ አድርጎ

«ምን አገባህ ወንድ ሆነ ሴት፣ በምን አወቅሽው? አሁን አገኘህበት መልሰው:: ከሰው አልፈህ ኤሊ መረበሽ ጀመርክ?»

«እንዴት እወስደዋለሁ? ራሱ ይሄዳል»

«ተሸከመህም ይሁን አገኘክበት መልስ:: ይሄን ገደል በምኑ ይወጣዋል:: ኤሊ እኮ ነው ወፍ አይደለም»

«እየጋለብኩ ልውሰደው......ፊቱን አዙሬ»

«ቆይማ አንተ አስቸጋሪ:: እንዳዋረድከኝ ነው ሁልጊዜ» አሉና በችኮላ ወደ ታች ወደ ሆቴላቸው ወረዱ::

እንዲህ ሲቆጡና ሲቸኩሉ አይቼአቸው አላውቅም:: ወደ ዕንብርታቸው የሚሳበው ጢማቸው ከመሃል በነፋስ ተከፍሎ ግራጫ መንታ ክንፎች መስሏል:: እዛው ቆመን ኤሊውን ስንዳብስ፣ ስንገፋና በፍርሃት ወደ ድንጋዩ ያስገባውን ፊቱን ለማየት ስናጎነብስ፣ ጫጫታ በጫጫታ ስንሆን፣ ሆቴሉ ፊት ለፊት የነበረችው ታኑስ መኪና እየሳለች፣ እያማጠች መጥታ አጠገባችን ከመንገዱ በወዲያ በኩል ቆመች:: እውስጥዋ ከራቫት ያደረገ፣ ከግራ የአፉ ጠርዝ ተቆርጦ ሊያልቅ አንድ ዕፅቅ የቀረው የሐረር መፋቂያ የነከሰ ሰው ተቀምጧል:: ኤሊውን አተኩሮ ሲያይ ቆየ:: ከዚያ አሰልቺ ፈጣጣ በኋላ ጭንቅላቱን እየነቀነቀ መኪናዋን ወደ ፊት ነድቶ የኋልዮሽ በእኛ አቅጣጫ አመጣትና ቂጥዋን ወደ ኤሊው አስጠግቶ አቆማት::

ይሄ ሃብታም የመሰለ ሰውዬ መላጣ አናቱን እያሸ ከታኑሷ ወጣና:

«ከየት ተገኘች በእግዜር?» አለ

«እዝራ ነው ያገኘው:: ደሞ ኤሊው ወንድ ነው» አልኩ

የሰማኝ አልመሰለኝም::

ቆሞ ኤሊውን ሲያይ ቆየና:

«ትረዱኛላችሁ እንጫነው?» አለ

እዝራ ኤሊውን ሲጋለብ ያየ የተገረመ ሰው፣ እዝራን የሚያውቅ ሰው፣ ታዚናን የሚያውቅ፣ ጠቅላላ የኤሊው እዛ መኖርና አንድ ጌኛ መጋ'ለብ ያስደመማቸው መንገደኞችና ሰፈሩ ቴኞች ተረዳድተው መኪናዋ ጀርባ ሰፊ ባዶ ቦታ ላይ ኤሊውን አስገቡት::

መኪናዋ ያኔውኑ ከቂጥዋ ተኛች:: ባለቤቱ ራቅ ብሎ ቆሞ ከአፍንጫዋ ወደ ላይ የተፈነረቸውን መኪና አየና:

«ይቅርታ:: ይሄን ነገር መጫን አልችልም: ባሌስትራዬን ይሰብርብኛል:: ወደ ጫካ አስገቡትና ይሂድ:: ማውረድ እርዱኝ» አለ::

ኤሊው በሰዎች እርዳታ ከታኑሷ በሆሆታ ታጅቦ ወረደና መንገድ ዳር ተጎለተ:: ዙሪያውን የተሰበሰቡት ሰዎች ቢጮሁ፣ ቢረግጡትና ቢጎነትሉት

ኤሊው አንገቱን ለአፍታ እንኳን አላወጣም:: ቄስ ታዚና ከሆቴላቸው ተመልሰው መጥተው የሚያደርጉት ጠፍቷቸው ይራገማሉ:: ብዙ ሰዎች እዝራ እየጋለበ እንዳመጣው፣ እየጋለበ ወደ አመጣበት ቦታ እንዲመልሰው ይመክራሉ:: ሳንጠብቀው ኤሊው ቀጭን አረንጓዴ ቅዘን እመሃላችን ሸር አደረገ:: እዛ የነበረው ሰው ሁሉ በሳቅ አወካ:: ቄስ ታዚና ወዲያ ወዲህ እየተቁነጠነጡ ለብቻቸው:

«ዕብድ ሁሉ፣ ዕብድ ሁሉ» ይላሉ

የሚሰማቸው እኔ ብቻ ነበርኩ::

«ይሄ ኤሊ ማርያም ደጅ ሰላም ልጅ ሆኜ ሁሉ የነበረ ነው:: ለእሷ ክብር የሚኖር ነው:: ታቦት የሚጠብቅ ነው:: የሚወስድልኝ የጭነት መኪና ማግኘት አለብኝ......»

እዝራ አባቱ የፈለጉት ሳይሳካላቸው ቀርቶ ‘መልሰህ እየጋለብክ ወስደው’ እንዲሉት ይጠብቃል መሰለኝ ፈገግ ብሎ አይኖቹን እያርገበገበ መሬት መሬት እያየ ቆሟል::

ቄስ ታዚና ሰዎች ዞር እንዲሉና ኤሊውን እንዳይረብሹት ቁጣ በተደባለቀበት ድምፅ ማዘዝ ሲጀምሩ፣ በማርጀቱ የሚንገዳገድ የመሰለ ዚታዎ ከታች ከተራራ ሆቴል (በኋላ ‘አረንጓዴ ሆቴል’ የተባለው) ከሚገነባበት ቦታ ብቅ አለ:: የእዝራ አባት ያለማመንታት መሃል መንገድ ላይ ወጥተው መኪናው እንዳያልፋቸው እጆቻቸውን ግራ ቀኝ ዘርግተው መጠበቅ ጀመሩ:: ዚታዎው አጠገባቸው ሲደርስ ሞተሩን ሳያጠፋ ቆመ:: አንድ ቀይ፣ ጠማማ አፍሮው እንደ ጭራሮ የቆመ ሾፌር መስኮት ከፍቶ:

«ምን ሆኑ ጋሼ?!» አለ

«አንድ ጊዜ ልጄ እርዳን እዚህ......ያን አየህ?.....» አሉ ኤሊውን እያሳዩ:: ሰዎች ጋርደውታል::

«ዞር በሉ በራጉኤል!» ለዚታዎው ሾፌር ኤሊው እንዲታይ ሰዎች ጠባብ ቀዳዳ ከፈቱ::

«እከፍልሃለሁ ያን ኤሊ ማርያም ታወጣልኛለህ?»

ሰውዬው የሚያስብ መሰለና:

«ምን አመጣው እዚህ?»

«እሱን እየሄድን እናወራለን በኋላ»

«ሁለት ብር:: ራሳችሁ ጫኑ» የዚታዎው ሞተር ጠፋ

«ግድ የለም ግድ የለም፣ እዛ ጋ አንተ ጠብደል!» አሉ ቄስ ታዚና ከሁሉ በቁመቱና በአካሉ ጎላ ያለ ሰውዬ እያሳዩ:: አያውቁትም::

«አንተ! አንተ!» ልክ እንደሚያውቋቸው ሁለት ሌሎች ሰዎች እየመረጡ::

በአምስት ደቂቃ ውስጥ ኤሊው ዚታዎው ጀርባ ተጭኖ ታዚና ጋቢና ገቡ:: ሾፌሩን አሻግረው ጣታቸውን እዝራ ላይ አወዛወዙ:: እዝራ እኔን አየኝ:: አባቱና የጫናቸው መኪና ዞር ሲሉ ተያይዘን በሳቅ ፈረስን:: እዛ የቆሙትን ሰዎች ከነወሬአቸው ትተን ከእዝራ ጋር ትከሻ ለወገብ ተያይዘን ለሌላ ኩሽትና ፌሽታ፣ ለሌላ ቻቻ፣ ለሌላ ቡጊ ውጊ ወደታች ወደ ሰፈር መሃል ወረድን:: ያን ማታ በጣም ደስተኛ ስለነበርኩ ራት መብላት እንደ ነበረብኝ ትዝ አላለኝም……

……ዕድሜዬ ከፍ ሲል በዝግመተ ለውጥ ኩሽትን ተውኩ፣ የልጅ ከመሰሉ ነገሮች ሸሸሁ፡ ማበጥ ለጀመረው የጉርምስና ደረቴ *ስዊት ሆም ሽሮሜዳ*[1] ጠበበች:: የቋንጃዬን እርዝመት የእናቴ ኩታ፣ የአባቴ ቁጣ ሊያቆሙት አልቻሉም:: የሽሮሜዳ አንዲት አስፋልት ጠበበችኝ:: ከብብቴና ከብሽሽቴም የሚተነውን የጉርምስና ላቤን መጥረጊያ ደህና ጨርቅ አልነበራትም:: ከእናቴ ሳንቲም ለምኜ ወይም ሸውጄ ወደ ከተማ መሃል መሰደድን ለመድኩ:: በጥልቅ ባይሆንም፣ የትላልቅ ሰዎች ስራ ገባኝ:: በዕድሜ የሚበልጡኝ ሰዎች የሚያደርጉትን አየሁ:: የበሰለ ባይሆንም ከለቃቀምኩዋቸውና ከተነገሩኝ እሴቶች ያለሁበት አካባቢ የሚቀበለውን መልካሙንና የሚነቅፈውን ከፉ ተረዳሁ:: ከደጉም ከከፉውም ተሻሽሁ:: አለም ሰፋች:: አንዳንዶቹን ለመረዳት አልከበደኝም:: አንዳንዶቹ ሚስጢራቸው ረበሸኝ::

[1] Sweet home shiromeda (ሽሮ ሜዳ የምታምረው ቤቴ)

## መግነጢስ ሁለት፡ ገበር

አባቴ በዕውቀቱና በብሩህነቱ ብቻ ሳይሆን በሚስቱ ጨዋነትና በተጠራ መልኳ የተከበረ ነበር፡፡ የአባቴን የብርሃን መስቀልን የየቀኑን ክሱት ድርጊት ያየ ትዳሩን ለማሻሻል እንቅልፍ እንደማይተኛ በአርባ አራት ታቦታት ምሎ መናገር ይችላል፡፡ ግን እንደ ገበር የለበሰው አደባባይ የማያየው ተቃራኒ ገፅም ነበረው፡፡

አንድ እሁድ የልደት ቀኑን ለማክበር ፓርቲ/ድግስ አዘጋጅቷል፡፡ ብዙ እንግዶች ነበሩ፡፡ የሚበላና የሚጠጣው ነገር እንደ ልብ ነው፡፡ ከሰፈር ቄስ ታዚና፣ የተባረኪ እናት ትደነቂያለሽ፣ ግርማቸው፣ አባቱ መክብብና እናቱ ስመኝ፣ አማንና ወላጅ አባቱ መረሳ፣ ገንዘብ ሚኒስቴር ከአባቴ ጋር የሚሰራ 'በልሁ' የተባለ ሰውዬና ሌሎች ስማቸውን የማላውቃቸው አራት ሰዎች፣ የአባቴ ፀሐፊ (ፀጉሯን ሳትተኩስ አይቼአት የማላውቅ 'መስታወት' የምትባል ወፍራም ሴት)፣ ኢያን የሚባል አጭር ቀጫጫ አይሪሽ ፈረንጅ ማርጋሬት ከተባለች እሱን ከመሰለች ሚስቱ ጋር፣ ከጃማይካ የመጡ፣ አባቴ ለትምህርት እንግሊዝ አገር እያለ የተወዳጃቸው ሁለት ድሬድ ሎክ የተሰሩ ወጣት ራስ ተፈሪያኖችና ሌሎችም ብዙ የማላውቃቸው ሰዎች መጥተዋል፡፡ ከነዚህ ከራስታዎቹ በስተቀር ሌሎቹ ብሄራዊ በዓል እንደሚያከብሩ ሁሉ ዘንጠዋል፡፡ የሞዳ ኖቫ፣ የሳሶና የቺኮ ልብሶች ያልሰፈሩበት ትከሻ የለም፡፡ ከተጎነጎነችው እማማ በተቀር ሴቶቹ በሙሉ ፀጉራቸውን ፍራንቼስካ የተሰሩ ናቸው፡፡ መብያና መጠጫው እቃ ከሞዝቮልድና ከኖቪስ የተገዛ ነው፡፡ ምሳ ከተበላ በኋላ ቡናውንም አልኮሉንም ለመሕጣች ያመቻል ቅካሎ ከቤት ጀርባ ሎሚና ትርንጎ ዛፎች ስር ጠረጴዛዎችና ወንበሮች ተደርድረዋል፡፡ ከትልቅ ፓርክ ዣንጥላ ስር ከተቀመጠ ሸክላ ማጫወቻ አንዴም ያላቋረጠ ሙዚቃ ግቢውን ያደነቁራል፡፡ እየተበላ፣ እየተጠጣና የተለያየ አይነት ሙዚቃ እየተሰማ በሚያምር መልክ መሸ፡፡ ያልሰከረ ሰው አልነበረም፡፡ እናቴ ብቻ ከሁሉ ተገልላ ዋናው ቤት ሳሎን ከመስታወት ጋር (እሷም ሞቅ ብሏታል) ታወራለች፡፡ አባቴ ከተቀመጠበት ተነስቶ በስካር እያንጎራጎረ ይንገላወዳል፡፡ እየደነሰ እማማን «ሮዛ! ማይ ላቭ ሮዛ!» እያለ ይጣራል፡፡ ከመሃልም የማሪዮ ኮሞን የፍቅር ዘፈን ያንጎራጉራል፡፡ ወዳጆቹ ሁሉ ከበው

ጣቶቻቸውን እያጮሁ በድምፁ ስልትና በማስመሰል ችሎታው ያደንቁታል:: ልጆች ሰርቪስ ቤት ጥግ ዕድሜያችን ያበጀልን ክልል ዙርያ እንጫፋለን:: ወላጆች ስለረሱን የሆነ ነፃነት ነበረው:: አንዳንዶቻችን የተሰረቀ ውስኪ፣ ረምና ፋሽኬት ጠጥተን ሞቅ ብሎናል::

በዚህ ጊዜ 'በልሁ' የተባለው የአባቴ የስራ ጓደኛው ከተቀመጠበት ተነስቶ መደነስ ጀመረ:: እንዲህ እየሆነ እያለ እናቴና መስታወት እየተሳሳቁ ከዋናው ቤት ወጡ:: እማማ አባባን እንዳየችው በማዘን ራሷን ነቀነቀች:: ልትናገር አስባ መሰለኝ ወይም እየተናገረች ከንፈሮቿ ተንቃነቁ:: ራቅ ስላልኩ አይሰማኝም:: በልሁ እየደነሰ በብርጭቆ ከያዘው አረቄ ከፊሉ እየተፈናጠረ፣ በሚንገዳገድ፣ ይሉኝታውን በሰረዘ የሰካራም አማርኛ፣ የሰራተኛ ሰፈር እንግሊዝ:

«ብርሃን ዛሬ ሌላ ሆነሃል:: የአስመራዋ ምስራቅ አሁን ብታይህ ዲግ ታደርግህ ነበር......»

ሲያሾፍ፣ ሲጫወትና በድምፁ ማማር ሲንበላጠጥ የነበረው አባቴ የበልሁን ስም በቁጣ ጠርቶ እላዩ ላይ የሚጠጣውን ደፋበት::

«ምን ታወራለህ? አርፈህ ጠጣ!» አለው አባቴ

«ምን ሆንክ?! ምን ልሁን ነው?!» አለ ሰውዬው በቁጣ፣ እየተንገዳገደና የሚጠጣበትን ብርጭቆ አባቴ ላይ እየወረወረ:: ሊመታው ፈልጎ ከነበረ አላገኘውም::

በሆነ የቀን አጋጣሚ እዛ ነበርኩ:: ምንም ሳያመልጠኝ ሁሉን ሰማሁ፣ አየሁ::

በሁለቱ መለካከፍ ሰበብ እዛ አትክልት ቦታ ውስጥ ሰማይና መሬት የሚውጥ የፀጥታ ቀዳዳ ተፈለፈለ:: እዛች እናቴ ፊት፣ ማንም ትሁት ናት ብሎ የመሰከረላት እናቴ ፊት፣ በሌላ ሴት መጠርጠር ይሄም እዛች እሷ እየሰማች ሲወራ ውርደት አይደለም? ከፊሎቹ ተጋባዦች አንገታቸውን በማፈር ደፉ:: ምን እየተደረገ እንደሆነ አስተርጓሚ ፍለጋ ወደ ሌላ አበሻ አፍ በጆሮአቸው ያጎነበሱ ፈረንጆች የገጠማቸው ዝምታ ነበር:: እማማ ነጠላዋን እያጣፋች አፏን ይዛ መስታወትን ወደ ጎን ገፍታ በመጣችበት ወደ ትልቁ ቤት ተመልሳ ገባች:: አባቴ ኮቱን በንዴት አውልቆ መሬት ላይ ወርውሮ ገለል ያለ ወንበር ላይ ተቀመጠና አንገቱን ደፋ:: ዝምታው እየጠለቀ እስከ ዛሬ የፀጥታ ደረጃ መለኪያ ያደረግሁት ፍፁም ጭርታ ነገሰ:: የመደፋፈር ጥልቀት የማይገባው የሕፃናት ጫጫታ ይሄን በወንጀለኛነት ስሜት የተፈጠረ የፀጥታ ጉድጓድ ሊሞላው አልቻለም::

በዚህ መሃል ከጓደኞቼ ስብስብ ተነጥዬ ወጣሁና እናቴ ወደ ነበረችበት ሄድኩ:: ይህቺ በልጅነቴ ያደረኳት ቀላል የጥቂት ሜትሮች ጉዞ፣ ከአባቴ ጋር የነበረኝን ግንኙነት ልዩ ይዘት ሰጠችው:: እናቴ ሳሎን ወይም

ለምግባችን የቀረበው የሚጣፍጥ ሽሮ ወጥ ነው:: ሌላ የለም:: ድንች የለም:: ሁልጊዜ ከሽሮ ጋር የሚቀርበው ዕልበት የለም:: ሁልጊዜ ለምሣ በተለይ በቀትር በክብር ዘበኛ ብርጭቆ የሚቀርበው የሱፍ ውሐ የለም:: እንደ ክርስቶስ የተሰቀሉ ሁለት እንጀራዎች ሳፋ ላይ በብቸኝነት ተዘርግተዋል:: መሐሉ ላይ የጣቶቼን ጫፍ እንደ ከሰል ፍም የሚነድፍ ሽንኩርቱ ያልሞተ ትኩስ ሽሮ:: የእንጀራውን ዳር ዳር እኛ የተራብን፣ በፊጣን ቧጠጣ ወርዱን እያጠበብነው::

ፀጥታ:: አባቴ ብቻ ሲያላምጥ:: ሁሌ ሲያላመጥ እሰማው ነበር:: ያባቴ ማላመጥ ብቻ ፀጥታው ውስጥ ብቸኛ ሞገድ ሆኖ:: የአባቴ ጉርሻ እንደ አደገሁበት አገር መልክምድር አይረሳኝም:: የጉርሻዎች ጉርሻ ነበር:: ሲበላ ደስተኛ ነበር:: የጉንጩ እብጠት ቱሉዋለልን ነበር:: በሁለት ሜትር እርዝመቱና በዛ ስፋቱ የበይዎች ንጉሥ ነበር::

ወጡ ሲያልቅ በብረት ጭልፋ እሱን የመሰለ ትሪው መሃል ይደፋል:: በቅባ ኑግ እያብረቀረቀ:: ጥርሴ ደሞ ይጠዘጥዘኛል::

የምበላበትን እጄን ዝቅ ብዬ አየሁ::

የገበጣውን ጠጠሮች የደመርኩበትና የቀነስኩበት ሒሳብ ቁጥሮቹ ይታያሉ:: ደነገጥኩ:: እጄ ላይ አፈጠጥኩ::

«ምን እጅህን ታያለህ? አትበላም እርፌህ» አለኝ አባቴ

«በኋላ ራበኝ ብትል ላንተ ለብቻህ አላቀርብም:: ጠስቀህ ብላ» አለች እናቴ::

የኖርኩት ነገር፣ የከረመው ሁሉ ተመልሶ የሚመጣ ይመስለኛል:: ነገም ኪላላይሶ የምል፣ ነገም አባቴ ሴትዮዋን የሚደበድብ፣ ነገም የሚያስፈራ አሞራ የማይ፣ ነገም በሌላ መጠጥና ወጥ ያልታጀበ ነጠላ ሽሮ የምበላ፣ ነገም ይኸው ዓይነት ቀን ተመልሶ የሚመጣ......

*

ሁለት ቀኖች ያህል ከቤት ውስጥ ቢብስ ከደጃፍ አልፈን አልወጣንም:: ፍርሃት ሁለመናችን ላይ ነግሶአል:: ከሰማይ እስከ መሬት ፍርሃት ነው:: ቤቱንም አፉንም ከድኖ የዋለ አለ:: ሐይለሥላሴ የሚወደዱ ንጉሥ እንደሆኑ ያወቅሁት ያኔ ነው:: ጐረቤቴንና ጓደኛዬን እመቤትን ካገኘኋት ሁለት ቀናት ማለፋቸው ነው:: ለሁለት ቀናት የጓሮዋ የባቄላ እሸት ናፍቆኛል:: የረሻም አባቷ የአባባ እምቢበል(ከአባቴ ጋር 'ማን ይረዝማል' ይፎካከራሉ) የውሸት ቁጣና ተረብ ናፍቆኛል:: አልጋዬ ላይ ተቀምጬ የደብተሬን ፊት ለፊት አያለሁ:: የሐይለሥላሴን ፎቶ አያለሁ:: ስለ 'መንግሥት መፈንቀል' አስባለሁ:: ስለ መሬት መፈንቀል አስባለሁ:: ስለ እተጌ አስባለሁ:: ስለ ልጆቻቸው አስባለሁ:: አሊጋ ወራሽ ባቄላ እሸት ይበላሉ? እተጌ ልብሳቸውን የሚያጥቡት እንደ እማማ ወንዝ ወርደው ነው? ማታ ማታ እልበት ይበላሉ?

ያልጠበቅሁትን አምስት ሰአት ያህል ተኝቼ ተነሳሁ:: አባቴ ቤት አልነበረም:: እናቴ ጎረቤታችን 'ትደነቂያለሽ' ጋ ሄዳለች:: ፀሐይ የምበላውን ስታቀርብልኝ ከእማማ ጋር ምን እንዳጨቃጨቃት ጠየቅሁዋት::

«ምንም» አለችኝ:: ቀና ብዬ አየሁዋት:: ደስ ያላት አትመስልም፣ ለምቦጭዋን ጥላ መልሳ አየችኝ::

«ስለትናንትናው ነገር ለእናኑ ደውለሽ እንዳይሆን» አልኩዋት

«አላደረኩትም እንጂ ባደርገውስ ምን አለበት......ይሄ ባለጌ» አለች

ምንም መናገር አልፈለኩም:: ምሳዬን በልቼ ጨርሼ ውሃ ስጠጣ፣ ፀሐይ ሃያ ብር አምጥታ ፊት ለፊቴ ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠች

«በል ጠጣበት እዛ አልማዝ ጋ ሂድና»

«አንቺ ምን መሆንሽ ነው?»

«ደሞ እዛ እየሄድክ እንደምትጠጣ ለእታታ እነግራታለሁ»

«ምን አደረኩሽ? ብታደርጊ ጥርስሽ ምናምን ረገፈ ማለት ነው» ብሩን ኪሴ ከትቼ ከማዕደ ተነሳሁ::

«የያዝከው ገንዘብ ለአመት ሸንኮራ ይሆናታል:: ያ ዋሕድ ደሞ ጉንፋን አሞታል:: ሸንኮራውን ስትሰጣት እንድታጥበው፣ አሮጊቷን በተስቦ እንዳትገላት»

«ሸንኮራው ሻወር ይውሰድ ልትይ ምንም አልቀረሽ»

«ቀልደህ ሞተሃል»

ልመታት ተጠጋሁዋት:: ዞራ ልትሮጥ ስትል ወንበር አደናቅፎ አዘገያትና ማጅራቷ ላይ ያዝኳት::

«ልቀቀኝ ነገርኩህ:: እንዳላጮልህ» እየሳቅሁ ትቼአት ወደ ውጭ ስወጣ፣ አድብታ መጥታ ጀርባዬ ላይ በቦክስ ደቃችኝ::

## የእናኑ መልዕክት ለሸሮሜዳ ዜጋዎች

'እናኑ' ወይም 'እናና' የምንላት አያቴ የምትኖረው መስፍን ሃረር መንገድ ነው:: በትክክል የደም ግንኙነት የለንም፤ ግን ከሴት አያቴ ከሰብለ መሸሻ ጋር እንደ እህትማማቾች ነበሩ:: የምትናገረው ነገር ሁሉ እንዲደመጥ፣ የሚሰ'ራ ከሆነ እንዲፈፀም የምትፈልግ ቀልድ የማታውቅ ሴትዮ ናት:: ብዙ ጊዜ ወደዚህ ወደ ሸሮሜዳ ነይና ኑሪ እያልናት 'ያረጀሁበትን ቤቴን አለቅም' ብላን ሁልጊዜም እዛ ናት:: ቤቷ ለመድረስ በታክሲ ግማሽ ሰአት ይወስድብኛል:: ሁልጊዜ እሷ ጋ ስሄድ ከሸሮሜዳው ዋሕድ ሸንኮራ እገዛላታለሁ:: *ጥሩ ሸንኮራ የሚያውቀው ዋሕድ ነው፤ ከሌላ እንዳትገዛብኝ* ትላለች:: አንድ ሁለቴ ሸውጄአት፣ እንደሸወድኳት ገብቷታል::

ሳንቲሜን ሱሪ ኪሴ ከትቼ ከግቢ ወጣሁ:: ወደ ላይ እየሁ:: እህል ፈሶበት አስፋልቱ በዕርግቦች ተሸፍኗል:: መኪና ሲጠጋቸው ይነሱና ካለፈ በኋላ ወደ ለቀማቸው ይመለሳሉ:: ከእነሱ ዝቅ ብሎ ዋሕድ መንገድ ዳር እንጀራና ቂጣ ከምትነግደው ማልደያ ከተባለች ሴትዮ ጋ ቆሞ ያወራል:: ስጠራው ቢሰማኝም ወሬውን ማቋረጥ አልቻለም፣ ወይም ሴትዮዋ ልትለቀው አልፈለገችም:: ቢሰማኝም ባይሰማኝም መንገድ አሻግሬ የስሙኒ ሸንኮራ እንዲሰጠኝ በጩኸት ጠየቅሁት:: ከሴትዮዋ ጋ እያወራ ሴንጢውን ከደረት ኪሱ አውጥቶ ሸንኮራ መቁረጥ ጀመረ::

«ስራ አላስፈታሁህ፣" ጀሀኝ ዋል!»

«ደህና ዋይ ማልዴ፣ ብቅ እላለሁ ወደ ማታ:: ጠብቀኝ በይው»

«እለዋለሁ»

መንገድ ሳቋርጥ ከሴትዮዋ ጋር ተላለፍን:: የተቆላ ስንዴ ጠረን ወይም የቆሎ ጠረን ትሸታለች:: ስህተት እንዳጋጠመኝ ሁሉ ዞር ብዬ አየሁዋት:: እኔን እንዳለፈች ከጀርባዬ በኩል ወደ አለው የኮረኮንች መንገድ ቶሎ ቶሎ እየተራመደች ገባች:: ከሆነ አባራሪ የምትሸሽ ትመስላለች::

«ዓላዛር እናት ጋ ነህ መሰለኝ?» አለ ገና ሳልጠጋው ዋሕድ

«እዎ»

«እሳቸው ከንአንጓው ነው የሚወዱት አይደለም? አንጓውን ለሁለት መሰንጠቅ አዳጋች እኮ ነው፣ እንዴት አንድ መለልታ ሁለት አንጓ ይኖረዋል?»

«አድርግልኝ ያለችውን አድርግላት»

«የምትሞት አሮጊት አትርገምህን ተረት ፈርተህ ነው» አለ እየሳቀ

«በተረት አትዶክክኝ ባክህ»

«ጨዋታ ነው፤ ውሰድ ይሄውልህ፣ ላጥ ነው የማደርጋት እኔ ዋሕድ:: በምንህ ትይዘዋለህ?»

«ከተማም ሱቅ ላስቲክ እወስዳለሁ»

«ተማም የላስቲክ ፋብሪካ አለው? እዛ ድረስ በምን ትወስደዋለህ?»

«ምን አገባህ?»

ዋሕድ የተሰባበሩ ሶስት የሸንኮራ ዘንጎች አቀበለኝና እጁን ዘረጋ:: ሰሙኒውን ሰጠሁት:: ሴንጢና ሸንኮራ እያጋጨ እንጉርጉሮውን ጀመረ......

ለእናኑ የገዛሁላት ሁለት ዘንጎች እያንዳንዳቸው ሁለት መለልታና ሶስት [redacted] አላቸው:: ዋሕድ ብዙ ጊዜ አንጓውን በትክክል ከመሃል መቁረጥ ስላለበት፣ ያማርራል:: ማንም ሰው ከእናኑ በስተቀር እንዲህ እንዲቆረጥለት አይጠይቅም::

ሸንኮራዬን ይገፔ ልክ ዘጠኝ ሰአት ላይ መስፍን ሐረር መንገድ ደረስኩ:: የእናናን የግቢ በር ሳንኳኳ እንዳላበኝ አወቅሁ:: ጃኬቴን አወለቅሁና በትከሻዬ ያዝኩት:: ገና እንደተከፈተልኝ እናናን ከቤቷ በረንዳ ታች ደረጃ ላይ ተቀምጣ አየሁዋት::

«የእኔ ጌታ መጣህ! የእኔ ደራሼ! የእኔ መኳንንት!»

ላስቲኬን እንጠልጥዬ እንደተጠጋሁዋት ፊቷን በሁለቱ እጆቿ ይዛ አፌን፣ ግንባሬን ፊቴን ሳመችኝ::

«ስትጣፍጥ፤ አቤት ስትጣፍጥ» አለች አፏን እየዳበሰች::

ቀዝቃዛ ነው ፊቷ:: ምናልባት የግቢው ዛፎች ሳያቋርጡ ከሚፈጥሩት ጥላ የተቀበለው ይሆናል:: ብዙ ጊዜ እዚህ ስትቀመጥ ወይ ጥፍሯን ትቆርጣለች ወይ ሸንኮራ ትበላለች:: ሸንኮራዋን በልታ ጨርሳ ጣቶቿን ተራ በተራ ታያለች:: ጥፍሯ ያደገ ከሆነ እሱን ትከረክማለች:: ከሶስቱ ደረጃዎች አንዱ ላይ ሁልጊዜ ጥፍር መቁረጫ አይጠፋም:: የደረጃዎች መጋጠሚያ ላይ መዓት የእናና የጥፍር ቁርጥራጮች ነፋስና [redacted]

እየገፉና እየሰበሰቧቸው የደቃቃ አጥንት ስብርባሪዎች መስለው ይቀመጣሉ:: የሚጠርጋቸው የለም:: ጣቶቿን አየሁ……ንፁህ ሆነው ተከርክመዋል:: ጥፍር መቀረሚ፣ ዱባ ወጥና ሽንኩሩዋን ካገኘች እናና አትጨቃጨቅም:: የቁሳቁስ ፍቅሯ በነዚህ ብቻ መወሰኑ አንዳንዴ ይገርመኛል::

«በል አምጣ ሽንኩሩዬን»

ግቢው በረዣዥም ያረጁ ዛፎች ተከልሏል:: በማይጨው ጦርነት ጊዜ የአንድ ጣሊያን መኮንን መኖሪያ የነበረ ነው:: ከፊት ለፊቱ ያለው ቦታ በአበቦችና በትላልቅ የኮባ ተክሎች ግርማ የተሸፈነ ነው:: ላስቲኩን ስሰጣት ተቀበለችኝና ከቂጡ ይዛ ዘቀዘቀችው:: ሽንኩሩዎቹ እየተንከባለሉ ወጡ:: እተጋደሙበት ለአፍታ ተራ በተራ ስታያቸው ቆየችና፣ አንዱን አነሳች:: አገላብጣ አይታ በነጠላዋ ጠራርጋ ትላልቅ ጥርሶቿን አንጓው ላይ ተክላ መቆፈርና እየላጠች ስኳሩን ስታጣጥም ቆየችና:

«እኔ እናትህ ቀላል አልምሰልህ……» በግራ እጇ ጎኗ እንድቀመጥ ደረጃውን ተመተመች:

«ና እዚህ……ፊቴ አትቁም»

ሽንኩሩውን በደቂቃ ላጠችና ማላመጥ ጀመረች:: ወለላው ከአፏ ሲወጣ ለምቦጭዋን በመዳፏና በነጠላዋ ትጠርጋለች:: ዞር ብላ እያየችኝና:

«ገለህ እኮ አያትህን ሰብልዬን ቁጭ» አለች::

ሁልጊዜ የምትለኝ፣ የማይሰለቻት ግን እኔን ያማረረኝ መረጃ ነው::

«ልጅ ብዙ ጊዜ እናቱን ወይም አባቱን ነው የሚመስለው:: አያት ጋ ምን አስኬደ? አያትህ ሰብለ እርግብግብ ነበረች:: ለትንሹ ነገር 'የዱማው ያለህ'፣ 'የዱማው ድረስ'፣ ምንስ ፈረሰኛ ቢሆን ከብቸና እዚህ……ይቅር በለኝ……ሁሉ ነገር ያሳስባታል እምጠ አይ ሽንኩሩ እቴ:: እንደው መመሳሰላችሁ የእግዜር ስራ ይመስለኛል:: እናትህን ሮዛን ሞጆ ነው የወለደቻት፣ ያን ጊዜ አራስ ሆና ያየሁት አይደን አሁን እዚህ ቆመህ አየሁት:: በልቤ አይ መመሳሰል አልኩ:: እሷን እንዳልረሳት ነው እግዜር በጥበቡ አንተን ያበጀው:: የምረሳት መስሎታል፣ ቂሉን ይፈልግ:: ታዲያ አያት ድረስ ይኬዳል? ሊያባባ ካልሆነ? ሁሉን ነገር ካስተዋለት ያስገርማል:: የኑሮ ትንሽ የለውም:: እዛ የወደቀችው ደረቅ ሳር አስገራሚ ናት:: ወፍ ለትሞ ጎጆ ይሰራባታል:: ይሄን ሳር አጭዶ ያመጣው ማጭዱ አስገራሚ ነው:: ሰዎቹ ማጭድ ማሰባቸው:: የሚያስገርመው ጉዳይ እልፍ ነው:: ሳሩን አጭዶ ያመጣልኝ ሰውዬ 'ዘገየ' ይባላል ጨዋታ ያውቃል:: እሱ ሲያወራኝ የሚገርም ነው ታሪኩ:: 'ለምን?' ብትል እንደው ወንድ ሆነ እንጂ ታሪኩ ተእኔ አንድ ነው:: የእኔ ታሪክ ምንም ብለፋ ምንም ብተባጥር የእኔ ብቻ አይሆን:: ለካ የእሱ የእኔን ይመስላል ብለህ መታዘብ አለ:: ያንተ የአንተ ብቻ ተሆነ፣ የእናትህ የእናትህ ብቻ ተሆነ

የሰብለ የሰብለ ብቻ ተሆነ እንዴት እዝህ ደረስን? እሱ እኮ ነው፡፡ ጠዋት እዚህ ፀሐይ ሰሞቅ የቆረጥኩት የአውራጣቴ ጥፍር ለስንት ጉንዳን እራት ይሆናል? ባላርስም አበላሁ ማለት ነው……ሂሂሂ»

'ግድ የለኝም' እንዳልላት ነጭናጫነቷን መቀስቀስ አልፈለኩም፡፡

«ትሰማኛለህ?» አለች

መሬት መሬት እያየሁ ራሴን በአወንታ ነቀነቅሁ፡፡ የሸንኮራው መረቅ በነካቸው ጣቶቿ ፀጉሬን ደባበሰችና

«እይ ፀጉር እቴ…….እንዳልኩህ አገዞ…….ሰሚ ታገኝ የማንም ታሪክ ይገርማል፡፡ እንደው እየመረጥን እንጂ……ሰብለ የሚነገር ታሪክ ነው ያላት፡፡ እግዜር በመጣፉ ጫር ጫር ያደርጋል እኛ እንኖራለን፡፡ ዝም ብለን መኖር……የሰብለ ታሪኳን ተረት በለው፡፡ ምን ሌላ ስም አለው? እሷ የፊታውራሪ ልጅ ነበረች፡፡

«በእናትህ በኩል ቅድመ አያትህ ፊታውራሪ መሸሻ የሚባሉ አጥንተ ጥሩ የጎጃም ሰው ነበሩ፡፡ ሰብለ ዲማ ነው እንግዲህ የተወለደችው፣ ለአቅመ ሔዋን የደረሰችውም እዛ ነው……አባቷ ባል ሲመርጡ መዳሪያ ጊዜዋ ተላለፋት……እና ፊደል የሚያስቆጥራትን በዛብህ የሚባል ጎረምሳ ዲያቆን ወደደች፡፡ ያኔ እንደዛሬ ዘመን ማንም ከማንም አይጋባም፡፡ ዘር አለ ምን አለ……

«አባቷ ከሚንቁት ሰው የመዋደድዋ ወሬ ሲደርሳቸው 'ይሄን ቅማላም ካልገደልኩ' ሲሉ ይሰማና በዛብህ ነፍሱን ሊያድን ወደ ሸዋ ይሰደዳል፡፡ ቆየት ብሎ እሷ መሸሹን ስትሰማ ሳትውል ሳታድር……እስረዋት አልነበር ……ተእስር አምልጣ……እግሩን ተከትላ ወደ ሸዋ፡፡ ብቻዋን……ብዙ ብዙ ችግር አጋጠማት እሷ እንደምትለው፡፡ አንደዬው 'ሀይኑን እዪው' ሲላት ሽፍቶች ደብድበውት በጠና ታሞ ሊሞት ሲያጣጥር አንድ ባላገር ቤት ተኝቶ ትደርሳለች፡፡ እንደው ማጥጥሞሽ አይገርምም? ምን ይደረጋል እግዜር ያቀደውን?……አይታገሉት፡፡ ከንድዋ ላይ ደም መቶት ይሞታል፡፡ እንዲህ ስታወራኝ በጉንጭዋ ዕንባ እየወረደ ነው፡፡ ታሪኳን የሰማት ሁሉ ነው 'ሚያለቅስ……ያቺ ልጅ አልመጣችም? መድሃኒቴን የት ነው ያስቀመጠችው? ጊዜው ተላለፈ. እኮ፡፡ ሰዓት ስንት ሆነ? ሐምጣ

«……ስለ አያትህ ስለ ሰብለ ልቀጥልልህ፡፡ በዛብህ ሲሞትባት 'ምን ቀረኝ ዲማ አልመለስም' ብላ እሱን ደጀሰላም ቀብራ ነጋዴ ተከትላ አዲስአባ መጣች፡፡ አራዳው ጊዮርጊስ ነው ያገኘሁዋት እንደ ነዳይ አፈር ላይ ተኝታ፡፡ ከግንባሯ፣ ቀን የጣላት እንደሆነች ማንም ይገባዋል፡፡ ቤቴ ወሰድኳት፡፡ እኔ ምን ነበረኝ ያኔ? ምንም፡፡ ሴት ነኝ የሁለታችንንም ሆድ መሙላት አልችል፡፡

«አገሩን እንደለመደች 'በይ ተነሺ አሁን' አልኩና ነጋዴ አደረኳት፡፡ ቅጠላቅጠል፣ ሸንኮራአገዳ፣ ዱባና ቅል እሸጥ ነበር፡፡ እብረን መነገድ

ጀመርን......በተለይ የቅል ስራችን ጠነከረ:: አሁን እርጅቼ አልሰራውም እንጂ ቅል መንቀስ፣ ማስማመር፣ ማሸመልመል እችል ነበር:: በቅል ላይ በወስፌውም በካራውም ስዕልና ቅርጥ መስራት:: ሐረጉን መከየን:: መጻፌ በስለት ተቆራርጦ እንደው ወንፊት ይመስል ነበር......::

«ገበያችን ተአራዳው ጊዮርጊስ ስር ነበር የተነጠፈው፣ ትንሽ ፈቀቅ ብሎ:: ሰብለ ለመሸከም ወገቧ አይችል በዛ ላይ ተእኔ የባሰች ባላገር:: ግን ቆንጆ ነችና የማይወዳት አልነበረም:: ቆንጆ ስልህ ይህቺ እዚህ ተግሮሰሪው ዝቅ ብሎ የሚኖሩ አለማየሁ ሀዲስ የሚባሉ ሰውዬ የሉም? 'እንቆጳ' የምትባል ልጅ አለቻቸው፤ እሷን አይተህ ማየት ነው:: እንቆጳ ጠቆር ትላለች እንጂ:: ገበያተኛው የሚያውቃት 'የሸንኮሬዋ ልጅ' እያለ ነበር:: እና ዱባችንን፣ ሸንኮራችንን መሸጥ ቀጠልን:: ደምበኛችን በዛ:: ዱባው ካልደረሰ ጎመኑን:: ሸንኩርቱን እንላለን:: ሁልጊዜም ግን ሸንኮራ አለን:: 'እዛ ሰብለ ጋ' 'ያቺ ቀይ ዳማዋ ጋ' 'ሸንኮሬት ጋ ሒዱ' ይባላል:: ተዓይን የማይደበቅ ምን እንደ ሆነ ታውቃለህ? ተራራና ቆንጆ......

*ሸሽተሽ ተአራዳው ብትገቢ እምጃ*

*ከዓይን አይሸሸግም ተራራና ቆንጆ ......*

አለ ነገር አላለም ያገሬ አንጎራጉዋሪ:: እኔ ለማጣራት ቀንና ሁለት ቀን የሚወስድብበኝን እሷ ቁጭ አድርጋት ምጥት:: አንዳንዴ መደቤን እየተውኩላት ቤት ቀርቼ ምግባችንን እሰራለሁ::

«እንዲህ እንዳለን አንድ ሰርኪን የተባለ አርመን አራዳ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሊሳለም ሲሄድ በዚያ በገበያው ሲያልፍ በየቀኑ ያያታል፤ እና ይወዳታል:: ሲመጣ፣ የያዘችውን ከዛም ከዛም ቀላቅሎ ይገዛትና ይሄዳል፤ አገሩ ሃብታም አርመን ነበር አሉ:: የኛ ሰው ወሬውን ተየት እንደሚለቃቅመው:: አንድ ቀን ሽቀጥዋን በጀርባዋ አዝላ ስትሄድ ይገጣጠማትና ይቆጣል...... 'ምን ይላል?' 'ምን ይቀባጥራል?' እያልኩ ገና ገበያ ዘርግተን እፎይ እንዳልን አንዲት አህያ አምጥቶ እንኪ አላት:: በቃ አምጥቶ ይሄው:: እኔ 'ምን ማለቱ ነው? ጨዋ የጨዋ ልጅ ናት' እላለሁ:: አስተርጉዋሚ እሱን የመሰለ መጥቶ 'ታርባኒ' የሚባል ተዚህ ተአራዳ የማይጠፋ—ያኔ፣ ቢያሳ የለም. እሱስ—እሱ እኮ የሰጣት ስጦታ ነው......ክፉ አይደለም ያደረገው......ቆንጆ ልጅ ናትና ገላዋ እንዳይጎዳ አስቦ ነው' አለን:: እሷ መሬት መሬት እያየች 'አልቀበልም':: 'ያገባሽ መሰለሽ? በይ የሰው ስጦታ እምቢ አይባልም' ብለን እዛ የተሰበሰብን ሴቴ ሁሉ ጮህንባትና አስቀበልናት:: 'አህያ ሰጥቶ ሌላ ነገር አምጪ የለም እንዴ?!' አልኩ......ገበያተኛው አፌን ይወደዋል:: ያልኩት ተተረጎመለት ......ሳቀ:: የሚያምር ጥርስ ነበረው:: ኸረ እሱ እቴ በየቀኑ የማያስተጉዋጉል ጊዮርጊስ የሚሳለም ክርስቲያን ነው በሁዋላ ስንሰማ:: ብረት ሁሉ ተባህር ማዶ ያመጣል እና ውሎው ተመኪንንት ነው......

በመንገድ ተተገማጠሞን ከበቅሎው ወርዶ ተግቢያችን ድረስ ይሸኘናል፡፡ ታዲያ ምን ይደረጋል? 'ቤት ግባ' ይባላል፡፡ እሷ መቼም እሷ፡ ዝግ ነው፤ አንድ ቀን 'ግባ' አልኩት፡፡ ከዛ ለመደ፡፡ ስንላመድ በተንተባተበ አማርኛ 'እህ' አለ፡፡ 'እንዴት እህ?' 'ሰብለን ወድጄአታለሁና ጻፉኝ' ብሎ ፈረንጁ ሽማግሌ ሳከ፡፡ አንድ ቀን አስቀመጥኩና 'ስሚ ሰብልዬ በዛብህ አዝጊር ጋ ነው፡፡ አንቺ ዘመድ የለሽ ምን የለሽ፡፡ ይሄን ሰው አንድ በይው፡፡ 'እሺ' ወይም 'እምቢ' አንድ ነገር፡፡ ጡር ይሆናል፡፡ በዛብህ ጎጃሜው ሞቶ ስደተኛው አርመን ምን በወጣው ይሰቃይ እቴ፡፡ ሰብለ ስታገነግን እንደው ያ ደብተራ በድግመቱ አበለኛሽቶአት እንደሁ እያልኩ እቀልጻለሁ፡፡ ጎጃሜን በዚህ ጠርጥር፡፡

«ጠዋት እንዲያ አላልኩዋትም? ማታ ላይ፡ 'እናንዬ ነማብኝ' አትለኝ......'እንዴ እኔ የዘውዲቱ አሽከር፡ ይህቺ ጅል ጎጃሚ ምን ቢያደርጉዋት ይሻላል፡፡ ነማብኝ ብሎ ነገር፡፡ እንደው አንቺን ሁለት ቀን ሽከምሽን ትተሽ ባማጥብሽ ተእሱም አትፈግጊ? ዋናው ልብሽ መከጀሉ ነው'

«እያትህ ሳርኪስ ምን ይመስላል መሰለህ? ረዥም፣ ፊቱ መጠጥ ያለ፣ አገጬም---አገጬምነቱ እንኳን ተእኔ አይብስም፣ ጠጉሩ የሚልፈሰፈስ ጥቁር ነው......በነፋስ እንደተልቆሰቆሰ፡፡ ሲመጣ 'ቡና አፍሉልኝ' ብሎ እዛ ኮባው ስር ይቀመጣል፡፡ ነፋስ አለና እየተመሳቀለ ያስቸግረዋል ጠጉሩ፡፡ 'ምነው እንደ ሴት ጠጉሩ ለስልሶ ምናለ ለእኔ በሰጠኝ' ስል ሰምቶ ሳቀ ......ይሄ ድንጋይ ቤት አልነበረም......ጣሊያን ገብቶ መች ሰራው......

«ልጅ ዓላዛር......ሰማኸኝ?......'አለመታደል' ትርጉሙ የትም መቸም ያው 'አለመታደል' ነው፡፡ ብዙ ሳይቆይ ገና ልድራት ዳር ዳር ስል ጣሊያን መጣ፡፡ እስኪ ሁሉን እንየውና ሰላም ሲሆን እናስብበታለን ብለን ቆየን፡፡ ብዙ ሳይቆይ 'ማይጨው ላይ ተሸነፍን' ተብሎ ተወራ ባገሩ፡፡ ሬድዮ የለ ጋዜጣ የለ ብቻ ወሬ፡፡ ታመስን ታመስን፡፡ ሳርኪስና አንድ ባልንጀራው ቤታችን መጥተው 'ሁሉን ነገር አዘጋጅተናል ወደ ታች ወደ አዋሽ እንሸሽ' አሉ፡፡ ዘመዳችን አይደሉ---ብናውቃቸው፡፡ ስናገነግን ሳርኪስ እንደው ሰብለ እግር ስር በርከክ ብሎ 'በይ እንሂድ እሺ በይኝ ......ብትሞችብኝ ምን ልሆን ነው' አለ፡፡ ብዙ ሳይቆይ ሽብሱ ተሸንፈው ገቡ አዲስአባ፡፡ እላመንኩም፡፡ ጎበና ቢኖር እላለሁ፡፡ ጎበና ቢኖር ሮማ ይገባ ነበር......አዲስ አይደለም መንከራተት ለእኔ......መቸም፡፡ አይ ጣሊያኑ ይገለናል ወይ ያግዘናል እያልን እንጠብቃለን፡፡ ሰው ፈርቶ ወደ ታች ወደ ሲዳሞ ይጎርፋል ነፍሴን ላድን ብሎ፡፡ አንድ ቀን ያ ሳርኪስ ከቸች አይል......በቅሎውን ጭኖ......'በሉ ልወስዳችሁ ነው'......'ለመሆኑ የት ልትወስደን ነው?' አልኩት፡፡ 'ሐረር ወይ ድሬዳዋ ዘመዶች አሉኝ እዛ፡፡ ከዛ እናስብበታለን......' እኔ በተፈሪ ሐረርን አልወደውም፡፡ ተፈሪ ሲመጣ ነገር መጣ፡፡ ሁሉ ተንኮለኛ ሆነ፡፡ እጁን አጣምሮ የፈረንጅ ካቲካላ

ለመደና አገሩን ረሳ:: ይሄው አስወረረን:: ፈረንጆቹ ሲያቆላብጡት ጊዜ ያ ቀጫጫ የተከበረ መስሎታል:: ቀን ጠብቀው ልክ አበጁለት......ለኛ ተረፈ እንጂ:: ሊለማመጣቸው ተሰደደ አሉ:: እሱ ወገኖቹ ላይ ነው ጠመንጃውን አጉርሶ የሚጠብቀው:: ወንድ ወንዶቹን እየመረጠ ካ ካ ካ አደረገ:: በቃው:: ምን ይደረግ ታዲያ......

'ጣልያን ተገባ ሰውን አይምረውም' አለን ሳርኪስ:: 'ሴትም አይምርም' አለን:: አይ እዚችው ሞቼ እቀራለሁ የትም አልሄድም:: ......ግን የእኔ ሃሳብ የእኔ ነው:: አይደለ:: አዎ የእኔ የእኔ ነው:: ሰብለን እረሳሁዋት:: ሳርኪስ የተግደረደርንም መሰለው:: 'እሺ ሰብለ እንኳን ትዳን' አለ አፍ አውጥቶ፤ መች ገብቶኝ:: አይ አሁን በዓይኔ መጣህ አልኳ:: አይ የሊላም ነፍስ አላበላሽ ብዬ በመጨረሻ ተረታሁ:: እኔ ነበርኩ እምቢተኛዋ:: እንግዲህ ተሸሽን ሳይቀር በሞጆ እንሂድ ብለን ለስንቅም ለምንም እንዲያመች ተያይዘን እዛ:: ሞጆ ትንሽ እንደከረምን ጣልያን አዲስ አባ ገባ የሚል ወሬ መጣ:: ያለቀስኩት ለቅሶ:: ለሰው እንደማልቀስ:: ጎበና እንዲያ ለፍቶ ለፍቶ እንዲያ በባዶ እግሩ ለፍቶ እንዲያ ሆኖ እንዲህ ይሁን?

«አያትህ ሰብለ ነጋ ጠባ 'ዲማ ምን ሆኖ ይሆን?' ትለኛለች:: ዲማማ ምን ይሆናል ቀጭኑ በላይ መጠለት:: ምንም አይሆን:: አርመኑ ሞጆ ከረመና ጅቡቲ የሚባለው አገር......የት አቃለሁ እቴ እንሂድ በሉ ተነሱ ይላል:: አይ በቃን አልኩ እኔ:: ብንሮጠው የት እንደርሳለን:: አገር ሲወሰድ ምን ይደረጋል? ጡብ ሲል ተጉያ፣ ዞር ብሎ ይለቀማል እንጂ:: ሰተት ብሎ አይኬድም:: አገር ሲወሰድ ደንቡ 'አምጣው መልስ' ይባላል:: በነገር ሲባል በነገር፣ በጦር ሲሉ በጦር ነው:: ተአምላክ ቀጥሎ አገር እኮ ነው:: ንክች አልኩ......ይግረምሽ ሲለኝ ሰብለ 'እሄዳለሁ' አለች:: 'ምን?' 'እሄዳለሁ' 'ምነው ልጄ አሳፈርሽኝ?' ለሁለታችንም ነዋ የምከራከረው:: ደሞ ተባዕድ ጋር ሄዳ ድምፅዋ ቢጠፋ እጠየቅበታለሁ በምድርም በሰማይ:: 'ምን በወጣሽ?' 'አብሬው ልሂድ::' እኔም ነገረኛ ነኝ ብሽቅ ስታደርገኝ 'ምነው ሰብለ በዛብህን ረሳሽው?' አልኳት:: ካወቅሁዋት ጀምሮ እስከትሞት ድረስ ይህቺን ከፉ ቃል ብቻ ተናግሬአታለሁ:: ጊዮርጊስ ምስክሬ ነው...እንጀቴ ተንሰፈሰፈ:: አስለቀስኳት:: ዛሬ ሁልጊዜ የምመኘው ነገር ያ ቃል ተአፌ ባይወጣ:: የተተፋ አይመለስ:: እኔ መች አወቅሁ......ለካ ከሳርኪስ ጋር እዛው ሞጆ፣ እዛው አፍንጫዬ ስር ነገር ጀማምረዋል::

«ሞጆ እንደዛሬ ሳይሆን ሰማይና ደን ነበር:: ዛሬ ገደል ብቻ ነው:: ልባችን ገደል ሆኖ:: ልቡ የለመለመ ሰው ለምለም ይወጣለታል:: ገደለ-ልብ አገርን በገደል ይሞላል:: ልቡ የደረቀ አገር ላይ ግራሩ ይደርቃል::

ቅንነት ካለህ ደረቅ እንጨት መሬት ብትከት ውሃ ባታጠጣውም ይፀድቃል......

«......ሰብለን ትቼ የት ልሂድ? በሁዋላ ብጠየቅ ምን እመልሳለሁ? ተነስተን ወደ ሐረር:: ብዙ ቀን ተጉዘን ድሬዳዋ ገባን:: እዛ ድሬዳዋ ልንደርስ ስንል ሳርኪስን ወባ ጣለችው:: የእኔ ወንድም......ጠናችበት ......ብንፀልይ ብናማትብ እሱ ያለው አይቀር ሰብለ ክንድ ላይ ዛ ብሎ ቀረ:: አይ የእኔ ጌታ:: ዓይኔ ላይ አለ አሁንም:: ሳርኪስ ሁሌ ዓይኔ ላይ አለ:: በኖርኩበት ዘመን ሰው በፊት ለፊት ክፉ ተናግሮኝ፣ ነጅሶኝ አያውቅም:: ግን እንዲህ እንዲህ ያለ ነገር ይደርስብኛል:: ለምን? በአገር ስለመጣ:: በእኔ ሳይሆን በአገር ስለመጣ:: ሰብለ የስድስት ወር እርጉዝ ሆና ሞጆ ተመለስን:: ሰው 'ምነው?' አለ:: 'ሞተ' ለቅሶ ተቀመጥን:: ሰብለ ይህቺን ሲቢርቶ መሰለች:: አመዲትን:: ለምን አትሁን...... ሲያሸበለብላት ሲያስብላት ነበር:: እናትህን ወለደች:: እራስ በችግር ከወለደች ሕፃኑ ይደክማል:: ክስት ብላ ነበር እናትህ ስትወለድ:: 'ስምዋ ማን ይሁን?' ሲባል ሰብለ 'ሮዛ' አለች:: 'ምንድነው ይሄ ደሞ፣ ከየት መጣ?' ስል:: ለካስ ሳርኪስ አድርጊ ብሏት ነው:: 'ወንድ ቢሆንስ ኖሮ?' 'ወንድ ተሆነ 'ዓላዛር' በይው' አያትህ ነው ሊሞት ሲል ስም ያወጣልህ:: ታሪክ ነው አይደል:: 'ምን ማለት ነው?' ስል፣ 'ትርጉሙ ጥጌሬዳ ማለት ነው' አሉ:: እሱ ልክ፣ ብትከሳም ጥጌሬዳ ትመስል ነበረ:: አሁንስ ልጄ ጥጌሬዳ አይደለች:: ሳንክ የሌላት፣ የእናቷ ልጅ::

«ያን ሰሞን ሞጆ የሚያስገርም ነገር ሆነ:: ነሐሴ መሃል ፍልሰታ ማለቂያ ላይ ሌሊት ከሰማይ ወለላ ዘነበ:: ልጆች ናቸው እየተጯጯሁ መጥተው 'ኸረ ማር ከሰማይ ዘነበ' እያሉ:: ካደርንበት ቤት ስብሳብ ውሃ ያጠራቀመ ቀራሩ ነበር፣ እዛ ያቋረውን ዝናብ ጣቴን ነክሬ ቀመስኩት:: ስኳር ስኳር ይላል:: አላመንኩም:: ያካፋል ገና......አላቆመም:: ወጣ ብዬ እጄን ዘርግቼ ዝናቡን አስነክቼ መዳፌን ስልሰው ስኳር:: ሳርኪስ አቅምሶን ስኳር አቃለሁ:: ልጆች አፈር በልተው ሊሞቱ፣ ቦይ ውስጥ ያቋረ ውሃ አልቀረም:: ተጠጣ:: አራው ሁሉ ሰከረ አልኩህ:: ዝናቡ አቁሞም ለሁለት ቀኖች፣ አፈር እየጠባና ሳር እየጋጠ በስርአት የሚተኛ ልጅ ጠፋ:: እኔ የእናትህ ስም 'ማሬ' ወይም 'ስኳሬ' ቢባል እወድ ነበር:: ሳርኪስ በዘሩ ታሪክ አስቀምጦ ሄደ፣ ሞጆስ በልጁ ታሪክ አይኖራትም? ዘመኑስ? በዛ ሰሞን የተወለዱ ሞጄዎች ስማቸው 'ማር'፣ 'ማርዬ' 'ስኳር' 'ሽኳር' 'ወለላ' 'ወለላዬ' ነው የሚባሉት:: ሳርኪስ ሰብለን ብቻ ሳይሆን እንደበታችንንም ነው የወሰደብን:: ያን የሰማይ መረቅ የቀመሱ ወንዶቹ ሴቶቹ ብዙዎቹ ዛሬ በሕይወት የሉም:: ያን ቀምሰው እርበኛ ያልሆኑ ጥቂት ናቸው:: ዘፈን ስምተህ ተሆነ ***አካም ነጉማ ፊዮማ አካም ነጉማ ፊዮማ ያ ዳሜ ያ ዳሜ ያ ዳሜ ቡልቡላ*** የሚል ያኔ ነው የተዘፈነው::

ቡልቡላ የተባለች ከተማ ስሚ ያኔ ነው የወጣላት አሉ:: ምን ታሪክ ታውቅና......ፈረንጅ ሆነህ::

«ነፃነት ተመለሰ:: ያም ወሬኛ ንጉስ ነኝ ብሎ:: እንግሊዝ እየነዳ አመጣው:: ገሪሱን አያረጉትም ነበረ? በላይን አያደርጉትም ነበር? አበበ አረጋይስ? ዞሮ ዞሮ ማን? እሱ:: እድሮው መሬቴና ቤቴ ተመለሰን:: ጎጆዬ ፈርሳ የጣሊያን መኮንን ይሄን ሕንፃ ሰርቶበት አገኘሁ:: ቤቱ ይበርደኛል ይሸተኛል......አየር አያስገባ:: ይኼው አድሬበት አላውቅም:: ከጀርባ ያለው ጭቃ ቤት ነው የምተኛው:: ሽሮሜዳ የሚባለው ብዙው ከንግሥት ዘውዲቱ የተሰጠኝ መሬት ነበር:: ሸጥኩት:: እሱን እየሸጥኩ ቤት ገዛሁ:: ቤት እየሰራሁ ማከራየት ጀመርኩ:: አይቸግረንም:: ሮዛን ደሞ ሰው እየሰደበ አስቸገረን:: 'ክልስ አህያ መልስ' እያለ:: ክፋት ሳይሆን ተጣልያን የተደቀለች እየመሰላቸው:: እንደ አሁኑ ተፈረንጅ መደቀል አይወደድም:: ገና ብዙ ነገር አልተረሳማ:: አንዳንዴ ሲያስ ለቅሏት ሽመሌን ይዤ እወጣና ያንን ኡሪ መቀጥቀጥ......አባቷ አርመን ነው ስንል ሰዉ ታገሰ:: ዕድሜዋ ደሞ ጨመር ሲል ወንድ አለ እሷ አላይ አለ:: ረጋ በሉ እንዴ!!! እሷ ብቻ ሴት ተፈጠረች አሏችሁ እንዴ?!! ትናንት ስድብ ዛሬ ደሞ ዐይን ማፈጠጥ ምን የሚሉት ዘዬ ነው!......ሰብለ ከሳርኪስ በሁዋላ ማግባት አልፈለገችም:: ሁሉ ነገር ልቧን ደፈነው መሰል:: የበዛብህ ነገር የሳርኪን ነገር የወላጆቿ ነገር......ጣሊያን የእንገላታን ነገር......ብቻ ሁሉ ነገር ተጫጭኖአት በሁዋላ ሃብት ብናገኝም ልቧን አልመለሰውም:: ውስጥዋ እህህእህህ ነው መቸም:: ደሞ......ዝምተኛ ሆነች:: ሚስጠረኛም:: ልትደብቀኝ አይደለም:: 'ብናገረው ምን ይረባል' ብላ ነው እሱስ:: እህህእህህ ነው ኑጋ ጠባ:: 'ማርከሽ ልጻርሽ' ብላት እምቢ:: እምቢ አለች:: ደጅ ያልጠና አለ እንዴ? ለነጋ ድራስ ተሰማ ልጅ ልድራት ሁሉ፣ ማነው ይድነቃቸው ለሚባለው......ያለ ወተት አትጠጣም:: ውሃ አትነካ ምን:: ያቺን በቅባ ኑግ የተሰራች ዱባ ወጥ በነጭ እንጀራ ትበላለች......እህህ እህህ እህህ እያለች፣ ከወጡ የሚቀረውን ሰሃን ላይ ያለውን መረቅ በጣትዋ ስትዘነቁል፣ በእሱ ስትጫወት ትውላለች:: እኛ አገር ከአመት አመት ጦርነት ነበር ልጄ:: ስንቷ በሙሽርነቷ ቆማ ቀርታለች፣ እኔም እንዷ አይደለሁ:: ስንቷ ባሏን ስንቷ የከንፈር ወዳጇን አጥታለች:: ቤት ይቆጠረው:: ሰንቱ ሎጋ አካለ ስንኩል ሆነ? ባሌ የነበረው የአሰፋ አባት ሱባ ተጠናሁ በሁዋላ አግብቼው......ማግባት ነው እንዴ? የእኛው አላንስ ብሎ በሌላ ሰው ነገር ገብተን፣ ኮርያ ሄዶ ታሞ መጣ:: ብዙ አልቆየም ሞተ......

«እናልህ......ለሌላ ቆስሎ መሞት ምን የሚሉት ዘዬ ነው? እኔ አሁን 'ኮርያ' የሚባል አገር ይኑር አይኑር የት አውቃለሁ:: ለራሳችን አንሶ ለሰው ተርፈን:: ወንድ በዝቶብን ነው እንደ ቡና ወደ ውጭ እንልክ የነበረው? ትሰማኛለህ? ኮርያ ለእኔ ምኔ ነው? ስንቱ ገበሬ በጥልያን

ቡዋንብ ተመታ:: ዓይኑ ታወረ? ስንቱ ነው 'መሶሎኒ' የሚባል ፈረንጅ የሚያውቅ? እንደው በመንገድ ተላልፈው 'ኖር' 'ኖር' 'ወያ' 'ወያ' ተባብለው ያውቃሉ? ተዚያ በሶማል በኩል ተዚያ በሐማሴን በኩል በየቦታው ጦርነት:: ማን አዘዘ ይሄን ሁሉ? አሁን ደሞ......በየትምህርት ቤቱ ተማሪ ይራበሻል:: እኔ ይኼን አልወድም:: ባለፈው እዚህ የተወረወረ ድንጋይ አንድ የቦሊስ ዓይን አጠፋ:: አንድ ዓይኑ ፈረጠ:: እንዲህ እኛ ስፈር ተንጋሎ ደሙ ፈሶ ሲያንራ ነው ያየሁት:: የተመታበት ድንጋይ ልጅ የወረወረው አይመስልም:: ተመሃል ሆሆሆ እያለን የስንት ሰው ቤት ይፈርሳል? እስቲ ንገረኝ:: ፈታውራሪ መሸሻ ስብለን አባረሩ:: ጣልያን እኔን፣ ሰብለንና ሳርኪስን አባረረ:: ሳርኪስ ሞተ:: በዛብህ ሞተ:: በመሸሻና በሞሶሎኒ መሃል ልዩነቱ ምንድነው? በኮርያና በተማሪ ድንጋይ መሃልስ? የዕውን ላስብ ብትለው አያሳስብም?

«በዚህ በዚህ በመሳሰለው ተዳከመችና የእኔ እመቤት ታመመች:: በሽታዋ ምን እንደሆነ ሃኪሙም አያውቅ:: አልጋ ላይ ብዙ አልቆየችም ያውም:: ሞተችብኝ......ለእኔ ቀረችብኝ እንጂ እሷማ ተእዝጌር ጋር ናት:: እንደተወለደች ነው የተመለሰችው ወደ እሱ ወደ ፈጣሪ:: ወደደች አዘነች:: ወደደች ወለደች:: ጎጃሜም ሆነ አርመን:: እግዜር ምን ምን ያህል ወደፊት እንደምናዝን ያውቃል:: እና የዕንባ መጠን ተመድቦልናል:: አንድ ኩባያ የተመደበለት አለ:: አንድ ጋን የተመደበለት አለ:: የእኔ አንድ እንስራ ሳይሆን አይቀርም:: እሱን በአያትህ ጨረስኩ:: እሷን አስቤ ከንፈሬን ያልመጠጥኩበት፣ ዘለላ ዕንባ ያልጣልኩበት ጊዜ አለ? እሱው ጊዮርጊስ ያውቃል:: ምናል ስትወለድ አንተንም አይታህ ብታልፍ:: አየህ አለማለቅ:: ተዚህ ነው የጀመርከው:: የእዝጌርን ሚስጢር ማን ይፈታል? የማን አማርኛ?

«የሱባ ልጅ አሰፋና እናትህ ሮዛ ብቻ ቀሩኝ:: ያ ሁሉ ዘመድ አልቆ እነሱ ብቻ:: አየህ እሱ ሰው በሞላበት አገር እንዲህ ብቻን ሲያደርግ:: ለወሬውማ ሰው ሞልቶአል:: ለወሬማ ሰው መች ቸገረ......አሰፋ ለእናትህ ወንድምዋ ነበር:: እንደዓይኑ ብሌን ነበር እናትህን የሚጠብቃት:: ትሞግድ ነበር:: እሱስ እኔም አጥግቢያት ነው:: አባትህ ብርሃን የአሰፋ ጓደኛው ነበር:: እንደሚወራው ትስተካካይ ተማሪ አልነበረውም:: ፈረንጅኛውን ሲነዳው:: ግዕዝም ያውቃል አሉ:: እስጢፋኖስ ነበር ሰፈሩ:: ተዛ እዝህ መስፍን ሐረር ይመጣል:: ደጋግሞ ይመጣል:: ቆቅ የነበርኩት ቤት ምን እንዳፈዘዘኝ አላውቅም ተሮዛ ለካ ነገር አለው:: ለእሷ አይሆንም አፈ ጮሌ ነው:: ያው የረባ ጉዋደኛም የላት:: 'ምነ?' ብትለኝ፣ ቅናታቸው:: የእኛ ሰው ቅናት እኮ ደርዝ የለውም......እግዜር በስራው መልከ ምን ተብሎ ይቀናል?......አንድ ቀን አፍረቷን ነገረችኝ:: ያ ወመኔ አባትህ ብርሃን ለካ አስረግዞአታል:: እኔ ሳያት ሮዛ የት ትደርስ

አልኩ እንጂ ሌላ ምን አሰብኩ? እሱ ደሞ የሚገዝግዝ ይገዝግዘውና እንግሊዝ የሚባለው አገር ለትምህርት ሂዶአል:: በደብዳቤ ላይ ደብዳቤ ተፃፈለት:: ደብዳቤ በደብዳቤ ላይ:: እሱ እቴ ሊመልስ ነው? እንዴ ምን ዓይነት ነገር ነው? 'ደስ አለኝም አይባል? ጦርን መፍራት ደግ፤ ደሞ ዘርን መፍራት መጣ?

«በክረምት አገሩ ይገባል ተብሎ ቢጠበቅ ቢጠበቅ......በሁዋላ ስሰማ እሱ በየፈረንጅ አገሩ 'ጠሐዩ ያምራል' እያለ ሲዞር ነበር አሉ:: ተአመት ተአመት አዲስአባ ጣይ አይደል:: ብልግና እንጂ:: ንገረኝ እስኪ የተለየ ጣይ ይወጣል? ሁሉ የእግዜር አገር አይደለ? አዘንኩ:: እሷም ተመሃል አንተን በደህና ተገላገለች:: እግዜር ይመስገን:: እሷ ዲቃላ ወለድኩ ብላ እንቅልፍ አጥታ::......ሲመለስ ቢጋቡም እንኳን ሮዛ ቂምዋን አልረሳችም:: ትወደዋለች ግን ቂምዋን አልረሳችም:: ተሰብለ አባት ተመሸሻ ያልተሻለ ነበር:: 'ብርሃን' አሉት ስሙን ሲያወጡ:: 'ድቅድቅ ጨለማ' አይሉትም? አሰፋ አሁን ድረስ አያናግረውም:: ብንል ብንል:: አሰፋ ሁሉ ነገሩ እንደ አባቱ ፊት ለፊት ነው:: አሽሙር አያውቅ፣ ቅኔ አያውቅ:: ወዳጅ እኮ ነበሩ.....አባትህን እያማሁት አይደለም፣ ልጄም ነው:: እንደ ሮዛ አይነት ሴቶች በብርሃን ማግኘት ይከብዳል:: ወዳጆቹ እንዴት እንደሚቀኑበት:: እስተዛሬ ያደረጋትን አነሳበታለሁ:: ቂም ነገር የመሰለ ነገር ሊያወራ ሲል 'አይተነው' እለዋለሁ:: 'አንቺ ደሞ አትረሺም' ይላል:: 'ወግድልኝ ጃን'......

«......እንደ ብርሃን ዓይነቶች ጠባያቸው እኮ ከንጉሱ ይከፋል:: ሰለጠንን ብለው ልባቸው ተደፈነ:: 'እከሌ የሚያምር ማቀዝቀዣ አለው' ይሉኛል የት ነው የምትሰሩት? ይሄ አቃቂ አገሬ እኮ ነው፣ 'አቃቂ በረታ' ስል:: 'አይ ተውጭ ነው የመጣው' ብለው ይስቃሉ:: በራሳቸው ይሳቁ፣ በእኔ ይሳቁ እሱ አልገባኝም:: 'ጀት ያበራሉ' ይሉኛል:: 'የት?' ስል 'ቢሾፍቱ'......'አይ ቢሾፍቱ......የማትሰራው የለም' ስል 'እዛ እኮ ማረፊያዋ ነው የተገዛችውማ ተውጭ ነው' ይሉኛል:: 'ትልቅዋ እማማ ቀልደኛ ናት፣ የዋህ ናት' ይላሉ:: 'ኸረ መቀለዴ አይደለም!' ብል ማን ሰምቶኝ:: *አትበላውም፣ እንዴ? ሽንኩራህን አንቁርፌህ ታየኛለህ?*

ለምን እናና ይሄን ሁሉ እንደ ምታወራኝ አልገባኝም:: ብዙውን ድሮ ሰምቼዋለሁ:: እንዲህ ሳስብ:

«ምን ልልህ ነበር? ይሄን ሁሉ ያደነቀርኩህ?» አለች እንደምታስብ ሁሉ አላምጣ የተፋችውን፣ መሬት ያልወደቀ የሽንኩራ ቃጫ ከቀሚሷ ላይ ለማራገፍ እየሞከረች::

«እንደ አያትህ ባትሆን፣ መልኳን አይሁን እንጂ ዐይንህ ጠቅላላ የእሷ ነው:: ዐይን ብዙ ብዙ ነገር አለው:: እንደ ዕጌ ልቤ-ስስ አትሁን:: ፅናት

አይሆናትም። ታገስኩ ስትል ሆዷን እየበላት አትችልበትም። እራስህን ጥንካሬ አስተምር። የከብት ጥንካሬ ሳይሆን የሰው። የአህያ ሳይሆን የሰው። ፅናትና ስራ አንድ ላይ ጎን ለጎን ካልሆኑ ድንጋይ መሆን ነው። አለዛ ትገፋለህ፣ ገድ ይርቅሃል። ሰማኸኝ?»

«እ»

«እ ትለኛለህ?»

«ምን ልበል እማማ»

«ልክ ነህ ካልደረሰብን አይታወቀንም፣ በል ብላት እሷን እያየሁህ»

በእጄ የያዝኩትን አምሮ የተላጠ ነጭ የ[redacted] እርሳስ ማኘክ ጀመርኩ።

«ያ ጥግ ይታይሃል? እዛ ሶስት ጉልቻ ነበር። አንዱ ድንጋይ አሁንም አለ። ሰው ከድንጋይ ያንሳል፣ አንዳንዴ። ያስቀመጡት ቦታ አይገኝም። ሰብልዬ ግን አስቀመጧት የምትገኝ ናት። ከሳርኪስ ወልዳ በዛብህን አልረሳችም። ሳስብ አንዳንዴ 'አርጅተሽ ነው' አልባልና [redacted]ው በታምር ከበዛብህ ጋር ዲማ እያለች ሳርኪስን ታልም ነበር? እላለሁ። ሂሂ። እንዴት ሁለት ፍቅር በአንድ [redacted] ይቀመጣል? እንዴት አንዱ [redacted] ሳያጣፋ ይሰፍራሉ? እናልህ ያ ድንጋይ አለ። ሁለቱ የት እንደሄዱ እንጃ።»

ጣትዋን ቆጠረችና፡

«እስከዛሬ ድረስ አራት ሰራተኛ ነበረኝ፣ አንዷ ጥላው ይሆናል። ከሰብልዬ ጋር ነፋስ እንዳያስቸግረን አሮጌ ጠረጴዛ አጋድመን በእሱ ጋርደን ቡና እናፈላ ነበር። እዛ ጋ እወዲያ [redacted] መሬት ነበረች......ባዶ ናት እና እሷ ላይ ለክረምት ዘንጋዳ እንተክላለን ለጥንቅሹ ነው ታዲያ። ውልቢኙን በልበላውን በያይነቱ። ክረምቱ ሲያልቅ ቁመቱን ከአጥሩ በላይ ከውጭ ታየዋለህ። ሲደርስልን እሱን መምጠጥ ነው። ማር ማር ነው የሚል። እጃችን በልጣጩ ሲቀደድ ነበር የሚውል። የመለመልነው ቅጠሉና የጣልነው ልጣጩ ከቦን እንደው ጠረኑ ውል ይለኛል። ዝንጀሮ ያመሰው ይመስላል። ሂሂ......አራት በልተህ ትሄድ?»

«አይ......እላይ ቤት እበላለሁ»

«ጥሩ ዱባ ወጥ አለ»

«አልፈልግም»

«በቅቤ የተሰራ»

«አልፈልግም እማማ አላሰኘኝም»

«የአባትህ ነገር አያስጨንቅህ:: ተፈጥሮ ነው:: የእውነት:: መጥማጥን ዶሮ መሃል ብታደርጋት ያስችላታል? ዶሮንስ ጥሬ በትነህላት 'አትንኪ' ብትላት የሚሰማህ አለ?»

«ሂሂ»

«አታስብ፣ አዎ የውሸት ሳቅህ እንጂ. እንደ እናትህ አልረሳህም:: ሰው መሃል እንዳዋረዳት ጠሐይ ነግራኛለች:: ልኩን እንደመንገር 'ማርያም ሂደች' አለችኝ:: ማርያም ምን ታድርጋት:: የእኔ ሸንኮራ አትለስልስ:: ከቻልክ ነው እንግዲህ:: ተፈጥሮን ምን ይሰሩታል?......እንደ እናትህ አትሁን......ደሞ ዱባ አማትበላው ንቀኸው ነው?»

«ምኑ ይበላል?»

«እንዲህ እድሜዬን ያረዘመው ምኑ መሰለህ?»

«ዱባ ስለበላሽ ነው?»

«ወይ ዱባው ነው......ወይ ሸንኮራው ነው......ወይ የመረቀኝ ደግ አለ:: እግዜር የእኔን ፀሎት አይሰማም:: ያከረመኝ አንተንና ጠሐይን በጤና እንዳያችሁ ነው:: ስልዬዋለሁ ብዙ:: ተለማምጬዋለሁ:: ይኮራብኛል:: በሰው ነው የሚሰጠኝ»

«አይ እማማ»

«አሁን ደክሜአለሁ:: ይህቺን ደረጃ እንዴት እንደወረድኳት አንተን ላይ:: እዚህ ስሆን ነው የምትታየኝ:: ተዳገት ተደረጃው ስሆን»

መድረክ የጀመረው የሸንኮራው መረቅ እጄን ስላጣበቀኝ በጃኬቴ እየጠረግኩ ላዳርቀው ሞከርኩ::

«እቤት ስትሄድ አታኩርፈው አባትህን:: እሷ አሁን ማርያም ጋ ሄዳ ለእሱ ነው የምትፀልየው:: ምን ላድርጋት? አሁን ስትሄድ ፊትህን ኅምዘዝ አድርግ:: አትደበት፣ ኅምዘዝ በል:: ያላማረህ ነገር እንዳለ ንገር:: ተረግጠህም አትሳቅ:: ጥርሳምና ጅል ነው እንዲያ የሚያደርግ:: ጠሐይ ደውላ ትናንት የሆነውን ነግራኝ ማታ አልተኛሁም:: መሳቂያ ሆነ......እሷም መሳቂያ ሆነች:: አሁን ማን ተጠቀመ? ወዳጆችህ ሁሉ ነበሩ አሉ»

«ለምን ትደውልልኛለች? አፏ አያርፍም»

«እንዴ? ልጄ ምን እንደደረሰባት ማወቅ አለብኝ:: ደሞ ምን ሳደርግስ? ዝም ብዬ ልስማ እንጂ:: የማወራው ካንተ ነው:: ምነ ተነሳህ?»

«ልሂድ:: ነገ እመጣለሁ»

«ኸረ አትመላለስ እቴ»

«ግድ የለም:: እዚህ ፒያሳ ለሲኒማ ስለምመጣ እግረመንገዴን ብቅ እላለሁ»

«ነገ ከመጣህ......ይሁን አላቆይህ:: ሽንኮራዬንም ማምጣት አትርሳ»

«ይሄን መቼ በላሽው:: አልጨረሽውም»

«ያደረ አልበላም:: ብላው አንተ:: ሞክረው አንተ፣ ለጥርስ ጥሩ ነው......ለመሆኑ ለኪስ ከሚሰጥህ ገንዘብ ነው ሽንኮራውን የምትገዛልኝ? ወይስ 'ለእናኑ' ብሎ ይሰጥሃል አባትህ?»

እሱ እንደማይሰጠኝ ታውቃለች:: እንደማይወዳት ለሺህኛ ጊዜ ልትነግረኝ ነው:: የቀረውን የአገዳ ቁራጭ ተንዘርፍፎ ደረጃ ላይ እንደ ነጭ ፏፏቴ ከተኛው ቀሚሷ ላይ አነሳሁና:

«እየበላሁ ልሂድ» አልኳት

«መልስልኝ እንጂ፣ የጠየኩህን:: የኪስ ገንዘብ በደንብ ይሰጥሃል?»

«አንዳንዴ:: ከእማማ ወይ ከፀሐይ እወስዳለሁ»

«ይሁን እሺ......ይሄ ቤት ከበደኝ:: ብርዱን አልቻልኩትም:: ቁርጥማቱ አላስተኛኝ አለ:: ጭቃ ቤት ነው ለእኔ የሚሆነኝ:: ገና ለገና ፈረንጅ የሰራው ቤት ልኑር ብዬ ዕድሜዬን አላሳጥርም:: አንተን ሳልድርማ አልሄዳትም:: ሂሂሂ:: ላከራየው አስቤአለሁ:: እዛ የትደነቂያለሽ ዘመድ ማልደያ ያለችበት ጎላ ሚካኤል እሄዳለሁ:: ሚካኤል ክፍሌ ነው፣ ስሳለውም ይሰማኛል:: እዛው አጠገቡ እሆናለሁ:: እዛ ያለን ቤት ጥሩ ነው:: እሱን እንዲለቁልኝ ንገሪልኝ ብዬአት እምቢ አለች ሮዛ:: ትርቂኛለሽ ትላለች:: ምን ላድርጋት:: ንገራት:: የኪስ ገንዘብ ያስፈልግሃል:: ሲከራይ አንተ ትቀበላለህ......አድገሃል አሁንማ:: ሽንኮራዬንም መግዣ ይሆንሃል:: ሂሂ:: ወደ ጠሐይ ሆስፒታል አካባቢ ያለውን ልብ ስትገዛ፣ ትዳር ስትይዝ ቆንጆህን ይዘህ እዛ ትገባለህ:: ትጠረኛለህ:: እኔ እንደሆነ መሬት ካልተንቀጠቀጠች አልሞታትም ሂሂሂ ......ሃኪሙ 'እንደ ልጅ ነሽ' አለ:: የዞረበት ሐኪም:: ይሄ ቤት እድሳት ይጠይቃል:: ሲያንቀለቅለኝ መጥቼ:: ድሮም ሰብለ ስለምትወደው ነው የቆየሁት:: የድንጋይ ቤት አልወድም እኮ:: ለመሆኑ ባውቶቡስ ነህ?»

«በታክሲ ነው የምሄደው»

«በል ሳመኝ»

እጆቼን ግራና ቀኝ ዘርግቼ ስጠጋት፣

«ወስላታ እንደ ባዕድ ልታቅፈኝ ነው:: እጁን ያንከረፍፋል»

«እኔ ልስምሽ ነበር»

«አፍህን አምጣ......እንካ»

«እምጳ……ማር ማር ስትል ሸንኮራው ነህ አንተ……ሂሂሂ እንዳትጥለው ……ወይ መንገድ ላይ ለሰው እንዳትሰጠው:: እንደነገርኩህ የአባትህን ነገር:: ለባለጌ አይሸከረመሙም፣ ለፈሪ አይሮጡም»

«እሺ እሺ ሰማሁ»

«አድርቄ እሰድሃለሁ»

«ገባኝ:: አሁን ግቢና እረፊ»

«ደከመኝ አልኩ?»

«ደስ እንዳለሽ»

«ደብርዬ ሰማሽ!……አይ ይቺ»

«ደብሬ! እናና ትጠራሻለች!»

ደብሬ ምናልባት ጎረቤት ሄዳለች::

እናናን በዝምታ ከተቀመጥኩበት አየሁዋት:: እጅግ እንዳረጀች ተረዳሁ:: ገፅዋ አራት ምዕራፎች ያሉት መጽሐፍ ነው:: ግራና ቀኝ ቅንድቦቿ መሃል ጎድጓዳ ሰንበር አለ:: ከዚህ በስተሰሜን ሁለት አግዳሚ መስመሮች አሉ:: እነዚህ መስመሮች ላይ ከክንብንብዋ ያመለጠ ሽበት ጥላውን ጥሎአል:: አንደኛው ምዕራፍ ይሄ የግንባርዋ ነገር ነው:: አደባባይ የሚያየው:: ግራና ቀኝ ጉንጮቿ ወድቀዋል:: ፊኛ መምሰል ብቻ ሳይሆን የቀለጠ የወንጂ ስኳር ባስቲክ ይመስላሉ:: ቶሎ በሚታዩና በረቂቅ ሰንበሮች ተሞልተዋል:: እነዛ ጅረቶች ስለሰማይና ስለምድር የተናገረችው የተረት ወለላዋ የፈሰሰበት ነው:: ከጓሮዋ ሰብራ የበላችው ዘንጋዳና ከሰማይ የወረደው ስኳር:: እዛ የአደባባይና የወዳጅ ንባብ ይካሄድበታል:: ወዳጆቿ እንስመዋለን:: ሁለተኛው ምዕራፍ ይሄ ነው:: የታች ከንፈሯ ላይ ሁልጊዜ ሁለት የፊት ጥርሶቿ ይታያሉ:: የላይኛው ከንፈርዋ እርጅና የከተፈው ነው:: ከሌላ መልኪ ይጠቁራል:: ከንፈሮቿተሸብሽበዋል:: ባልታወቀ ምክንያት ሁልጊዜ ይንቃነቃሉ:: ተረቷ በዚህ በኩል ይወጣል:: አፏን የሳምነው አሰፋ፣ እማማ፣ እኔና ሱባ ብቻ ነን:: ከንፈሮቿ ሁልጊዜም ሁለት ጣዕም አላቸው: የዱባ ወጥና የስኳር:: እዚህ እንደደረስኩ የሳምኳት ትዱባውን ነው:: ስሰናበቷት የሟሟመው ስኳሩን ነው:: ከንፈሮቿ ቀስላሳና ቀዝቃዛ ናቸው:: ይሄ የመፅሐፉ ሶስተኛ ምዕራፍ ነው:: አራተኛ መልኪ ኩልኩልትዋ ነው:: ልጅ እያለሁ ከጥቂት አመታት በፊት አቅፋኝ ስትተኛ ቀና ስል የማየው ይሄን አገጩ-ቢስ ያደረጋትን ኩልኩልት ነው:: እሱን እየጎተትኩ፣ እብጠቱን በጣቴ እየዘነቆልኩ እረፍትና እንቅልፍ እነሳት ነበር:: አሁን ኩልኩልቷ የበለጠ ወደ ታች ወርዷል:: ጠፍጣፋም ይመስላል::

በሚቁለጨለጩ ትናንሽ አይኖቿ በትኩረትና በማዘን አየችኝ:: ከዛ ሆዴ እንደደከማት ሁሉ ጨፈነች:: እንዲህ ስታደርግ እባባለሁ::

ይፈራል:: ለምን እንደምፈራ አላውቅም:: ምናልባት እንዲህ ሆና ይሆን የምትሞተው? አይኖቿን ሳትገልጥ በፊት ቶሎ ብዬ አፏንና አይኗን ደግሜ ሳምኩዋትና ወጣሁ::

«ደህና ግባ» አለች

ዞር ብዬ አየሁዋት::

አይኖቿን አልገለጠችም::

ፀሐይ አዘቅዝቃለች:: የመስፍን ሀረር መንገድ ጥላ በጥላ ነው:: እስከ ስድስት ኪሎ ታክሲ፣ ከስድስት ኪሎ ወደ ሰፈር ሌላ ታክሲ ያዝኩ:: ሁለተኛው ታክሲ ውስጥ እንዳለሁ ተዝናንቼ ለመቀመጥ ጃኬቴ ኪስ እጄን ስከት፣ ከእናና የወሰድኩትን [redacted] አገኘሁት:: አወጣሁና አገላብጬ አየሁትና በቀስታ ነከስኩት::

«ወንድሜ ልጣጩን እንዳትጥ[redacted]ኝ ታክሲ ውስጥ» አለ ሾፌሩ

«ግድየለም» አልኩ::

በአፌ የያዝኩትን [redacted] ልጣጭ ጃኬቴ ኪስ ከተትኩ

«እግዜር ይስጥልኝ»

«ግድየለም»

«ሳይህ ሸንኮራ የምትበላ አትመስልም»

«እንዴት?»

«የአራዳ ልጅ ትመስላለህ»

«አራዳነት ሸንኮራ በመብላት ባለመብላት ይለካል? እያቴ 'ካልበላህ እረግምሃለሁ' ብላኝ ነው»

«ሃሃሃሃሃሃ ጥሩ ጨዋታ»

«እውነቴን ነው»

«ለምን?»

«እይ......ሸንኮራው ምን ይመስላል?»

የመኪናውን ፍጥነት በረድ አድርጎ ዞር ብሎ አየኝ::

«ያው ሸንኮራ ነዋ»

«በደንብ እየው»

«ኸረ ባክህ እንጋጫለን»

ከዛ በድጋሚ ዞር ብሎ አየና፡

«ያው ነው»

«ሁለት እንጓ አለው»……

«እና አዎ» አለ ለሶስተኛ ጊዜ አይቶ

«አንጓ አስቆርጦ ነው ብዙ ሰው የሚገዛው»

«ገባኝ እና»

«እሷ ደሞ አንጓ ከሌለው አትበላም:: ለምን እንደሆነ ታውቃለህ? መጀመሪያ ለጥርስ ጥሩ ነው፣ ከዛ ደሞ እንደ ሕይወት ነው ትላለች:: ሁልጊዜም 'እንዲህ ካልበላህ ሰነፍና ፈሪ ነህ' ትለኛለች:: እስኪ ልየው ብዬ እየታገልኩ ነው»

«ሆነ ብሎ ችግር መፍጠር አይደለ ይሄማ……ሴትዮዋ ፈላስፋ ናቸው?»

«ግራ ገብቶኛል እኔም»

«እንደምታየው አንድ አንጓ መላጥ ከብዶኛል:: እሷ ሰከንድ አይወስድባትም»

«ስንት አመታቸው ነው?»

«በግምት ሰማንያ ውስጥ ይመስለኛል፤ የድሮ ሰው ዕድሜው አይታወቅም»

«ጥርሳቸው ይችላል?»

«ይሄው በሸንኮራው ሂሳብ ከሆነ ጠንካራ ነው ማለት ነው»

«ይገርማል:: አልሞከርም እኔ:: ለመሆኑ የሽሮሜዳ ልጅ ነህ?»

«ተወልጄ ያደኩት»

«የት ጋ?»

«ታዚና ፊት ለፊት»

«የባለቤቱን ልጅ ታውቀዋለህ?»

«ወንድሜ በለው እ……ይሄ ነገር ጥርስ ያማል አቦ:: ታውቀዋለህ?»

«ትተዋወቃላችሁ?»

«እንዴ ታዲያስ»

«እንተዋወቅ» በግራ እጁ እየነዳ ቀኝ እጁን ለሰላምታ ዘረጋ ጨበጥኩት::

«ዘውግ እባላለሁ:: ሲመቸኝ ራቴን የምበላው 'በርዴን' የምወስደው እሱ ቤት ነው:: ጥሩ ልጅ ነው:: በጣም ንግድ ያውቃል ደሞ»

«እዝራ እሳት ነው»

«እሳት ትላለህ ሰው ሲወድስ? ዘውገ ሰላም ብሎሃል በልልኝ»

«እነግረዋለሁ»

«አንተ ስምህን......»

«አ......ዓላዛር......በነገራችን ላይ እንዳታስከፍለኝ»

«ሃሃሃሃ በቃ ልክ ነህ:: አሁን በደንብ አመንኩህ፣ የእሱ ጓደኛ ነህ»

«ይደርቃል አይደል?»

«ሃሃሃሃሃ ታች ወወክማ ነው የማውቀው......በሳቅ ይገለናል:: ተንኮሉ ተንኮል መሰለህ፣ ወላ ደሞ ቼዝ የሚያሸንፈው የለም፣ አላጋጠመኝም ያሸነፈው»

«ደብተራ አይደለ:: ሃሃ:: እንዴት አላየኸኝም አንዳንዴ እመጣ ነበር ወወክማ»

«ባንገጣጠም ነው:: አንድ ነገር......በተራራ ሆቴል ወደ ቀኝ እታጠፋለሁ:: የቀረውን በአስራ አንድ ቁጥር ሂድ»

«ግድ የለም፣ ታውቃለህ? የዚህ ሽንኮራ ነገር እንጓውን በልተህ መለልታውን ስትበላ የበለጠ ይጣፍጣል»

«አየህ አዋቂ ሴትዮ ናቸው»

«በል አውርደኝ ሲጋራ ገዝቼ ነው የምገባው፣ ጊዜ ካለህ ስትመለስ ታዚና ብቅ በል፣ ካፌ በእኔ ሂሳብ»

«አሁን እምሄድበት አመሻለሁ:: እዚህ ዘመድ እጠይቃለሁ:: ደጃዝማች አስጋኸኝን ታውቃቸዋለህ?»

«ዘመዴ ናቸው እንዴትለኝ?»

«አጎቴ ናቸው:: ትልቁ አጎቴ»

«ከባድ ቪላ ነው አቦ»

«ማርትሬዛ በደንብ አለው ሰውዬው:: እዝራን ላገኘው ብችል ደስ ይለኛል:: ከተማው ስለሚርቅብኝ እዚህ ድረስ ግዴታ ካልሆነ አልመጣም:: ሌላ ቀን......»

«ጥሩ......ከመጣህ እኔንም ከቤት አስጠራኝ፣ ቤቴ ታዚና ፊት ለፊት ነው:: ቤቱ ራሱ 'የዓላዛር ቤት ነኝ' 'የዓላዛር ቤት ነኝ' ምናምን ይላል:: ሃሃህ ካለሁ እመጣለሁ»

«ሃሃሃሃህ ጥሩ»

«የማን ታክሲ ነው?»

«የቤት ነው፣ ግን ልሰራበት አልነበረም ያወጣሁት:: ሾፌራችን የለም:: አባባና እማማ የቤት መኪናውን ይዘው ጅማ ሄደዋል:: ትራንስፖርት ያስፈልገኛል:: ስመጣ ሳይህ በቃ ልጫነው አልኩ»

«አይገርምም......?»

«ይሄ ራሱ አሪፍ ታሪክ ምናምን ነው፣ ወሳ ጳውሎስ ኞኞ ቢያገኝት»

ዳገቱን ጨርሰን ሽሮሜዳ ማዕከል ከመግባታችን በፊት እንዲያቆምልኝ ጠየቅሁት::

«እሺ እንጠፋፋ» አለ

«አልጠፋም:: ቻው»

በሩን ከፍቼ ከወጣሁ በሁዋላ በእጅ ሰላምታ ዘውገን በድጋሚ ተሰናበትኩት:: ሲጋራ ለመግዛት መንገድ ተሻግሬ ቦይ ዘልዬ አለምነህ ሱቅ ሄድኩ:: በደንቤ በጀርባ በኩል ወደ ሱቁ ገባሁ:: አለምነህ በክርኑ ባንኮኒ ተደግፎ የአዝማሪ ዘፈን እያንጎራጎረ ቆሟል:: በማታው የፀሐይ ብርሃን ቀይ ዳማነቱ ቦግ ብሎ ይበራል:: አፍሮው የአፍንጫው ድልድይ ላይ ጥላ ጥሎአል:: እንደመፋቂያ የያዘው ክብሪት እንጨት ወፋፍራም ከንፈሮቹ መሃል ድኙ ረጥቦ እየተሰባበረ ነው:: ሰላም ብዬው ተቀመጥኩ:: አለምነህ ሱቅ ሲጋራ ተደብቄ ማጤስ እችላለሁ::

«ዊንስተን ጨርሼአለሁ፣ ኬንት አጢስ»

«የዶና ሲጋራ ነው አቦ»

«ጉሬዛ ይሻልሻል?» አለ

«ግደለው ተብለሃል?»

አንድ ኬንት አመጣና ሰጠኝ:: ሳንቲሙን ሰጠሁት:: የአለምነህ ጣቶቹም ጥፍሩም ረዣዥሞች ናቸው:: ጥፈሮቹ ቆሽሸዋል:: በእያንዳንዳቸው ውስጥ ቀጫጫ ጥቋቁር መቀነቶች አሉ:: የጣቶቹ አርማ ነው::

«ፓርቲ እንዴት ነበር ትናንት?»

«አሪፍ ነበር» አልኩት:: ምን ወሬ ፈለገ?

«አባትህ እንዳስፎገረ ሰማሁ» አለ የማጅራቱን ፀጉር እየነተተ:: ማጅራቱ ላይ ያለው ፀጉር በሙሉ የተቆጣጠረ ነው::

«ከየት ሰማህ? ወሬኛ»

«መደበቅሽ ነው?»

«ማን ነገርህ?»

«ምን ያደርግልሃል? ጉዳት ልታደርስበት ነው የነገረኝ ሰው ላይ?»

«በጣም ቀላል ነው አቦ ይሄ ሲጋራ»

«ሁለት አጢስ»

«በሳንባዬ ትነግዳለህ? ምናባቱን»

ለሶስተኛ ጊዜ ከሲጋራው ስስብ የሱቁ መስኮት ተጋረደ:: ሲጋራዬን ደበቅሁና ቀና አልኩ:: ከእኛ ቤት ጀርባ ሜዳው አጠገብ የምትኖረው ማልደያ የተባለችው ሴት ናት:: ዛሬ በጥቂት ሰአታት ዕርቀት ሁለተኛ ሳገኛት ነው::

«ደህና ዋላችሁ?»

«ደህና ታዲያስ ማልደያ:: ምን ፈለግሽ?»

«እስኪ ዘይት ስጠኝ»

ከወደታች ምናልባት ከነጠላዋ ስር፣ ከጉያዋ፣ ከተቀመጥኩበት ሊታየኝ ከማይችል ስፍራ ቡናማ ሊሆን ትንሽ የቀረው ጠርሙስ አውጥታ ባንኮኒው ላይ አቆመችው:: አለምነህ ጠርሙሱን ወስዶ ጎንበስ አለ:: ከእግሩ ስር ታኒካ፣ የዘይት ጭልፋና ፈኔል አወጣ:: ሁሉም ጥቁር ሊሆኑ ምንም አልቀራቸው:: ከአፉ የሚያላምጠውን የከብሪት እንጨት አውጥቶ:

«ታዲያስ እንዴት ነው ወንዴ?» አለ

«ደህና ነው ምን ይሆናል? ያደርቀኛል እንጂ:: ታውቀዋለህ የእሱን ነገር»

«ሃሃሃ የስንት ነበር አልሽኝ?»

«የስሙኒ አድርገው»

«ጥጋበኛ በዪው፣ የዕውነት ጠላሽና ፊልቴርሽ ይናፍቀኛል:: ሙያ እኮ አለች»

«አይ አንተ ብዙ እንደዛ ይላል:: መቼም ምኑም ከትዳር አይበልጥም»

«እሱስ አዎ»

ቀና ብሎ፣ በቀስታ ጠርሙሱን ከወለል ላይ አነሳና ባልኮኒ ላይ አስቀመጠው::

«መርቅበት እንጂ አንተ ደሞ፣ አሁን ይህቺን ከአንገቷ በላይ መሙላት ምን ያስቀርብሃል?»

«ታውቂያለሽ እኔ አሪጂናሌ ዘይት ነው የምሸጠው:: አይገኝም የትም:: ሙች እዪ ቀለሙ ራሱ ወርቅ የመሰለ»

«እህት ላይ አይነገድም አንተዬ፣ ምን ላድርገው?» አለች ወደ እኔ እየሳቀች እያየች:: ሳቋ የሚገርም ውበት አለው:: ሲጋራ መምጠጤን ትቼ አተኩሬ እየሁዋት::

«በል አንተን መከራከር አያዋጣም፣ ያቺ እህትህን ሰላም በልልኝ»

አንድ ክርንዋን ባልኮኒ ላይ ጣል አድርጋ፣ ልታናግረኝ የፈለገች አይነት አተኩራ አየችኝ:: ከዛ ዞር ብላ የዘይቷን ጠርሙስ ቀለብ አድርጋ ጉያዋ ከተተችና ወደ ታች ወደ ደረጃው ወረደች:: አለምነህ ወንበሩ ላይ ተመለሰና እየሳቀ አየኝ......

«ምነው ጂሚ ፈጣጣ አደረከብኝ?» አልኩት

«ደስ ትላለች አይደለ? እ?»

«እና ምን ይጠበስ?»

«ባሏ በቅናት ሊገላት ነው»

«እና»

«አይገባሽም:: በጣም ቆንጆ ናት:: ጥሩ ጠላ ትነግድ ነበር:: በቅናት አስተዋት»

«በደንብ አላየሁዋትም:: በደንብ ስላላየሁዋት መፍረድ አልችልም:: ስትስቅ ደስ ትላለች:: ደሞ አሁን አባቴን ስትስድበው አልነበረም?»

«አልሰደብኩትም ምነው?»

«ስይዝህ አልሰደብኩትም ትላለህ:: አራዳ መሆንሽ ነው?»

«ከዋሕድ ጋር አንድ ነገር አላቸው»

«ዋሕድ? ይሄ ባለ ሸንኮራው? በምን አገናኘሃቸው አቦ? ወንድና ሴት ሰላም መባባል ሊያቆሙ ነው በወሬኞች ትርጉም ተደናግጠው»

«አንተ ምን ነገር ነገር ይልሃል:: ሲጋራውን አማረርክ:: ጨምር»

«በነፃ ከሰጠኸኝ»

«ለሃብታም ልስጥ እንዴ? እውነቴን ነው:: ሲገናኙ እንደ ሴባ ዙሪያቸውን ያያሉ:: እያደረገላት ይሆናል»

«ወንዴ ማነው?»

«የሴትዮዋ ባል»

«ቢቀና ልክ ነው ማለት ነው እንግዲህ:: ያየው ቢኖር ነው»

«ቢቀናም፣ ቀንቶ ጠላ ጠመቃ ቢያስተዋትም፣ አላመለጠም ማለት ነው ሃሃሃ»

«ሃሃሃ ስለዚህ ቅናቱ ቢቀጥል ትክክል ነው ማለት ነው ሃሃሃሃ:: ምናባቱን አንድ ሲጋራ ጨምርልኝ፣ ሳላጤሰው እያዋራኸኝ ነዶ አለቀ»

«ከየት ነው የምትመጣው?»

«ከእናና ጋ»

«ደህና ናቸው?»

«ደህና ናት»

«ሽንኩራ በላህ?»

«መቼ ይቀርልኛል»

«ኪስህ ያበጠው በእሱ ሳይሆን አይቀርም፣ ለመጠርጠር ይፈቀድልኝ»

«አዎ ምነው? ከፈለክ እሱን እስጥሃለሁ አንድ ሲጋራ አምጣ»

«ልየው መጀመሪያ»

ከጃኬቴ ኪስ ወፍራም ሽንኩራ አወጣሁና አሳየሁት

«አሪፍ ነው አቦ»

«እንስማማ»

ፊቱን ዞር አድርጎ የኪንት ሲጋራ ከለማጣ ፓኮ ውስጥ ፈልፍሎ አወጣና ዘረጋልኝ::

«ሲጋራውን ተቀብዬ ከዛ ሽንኩራውን ሰጠሁት»

አለምነህ አንዳንዴ ውሸትን አራዳነት ያደርጋል:: በክህደት ይፎግራል::

«ጠረጠርከኝ እ? ምናባቱን»

«አንተ ያልተጠረጠርክ:: ሽንኩራዬን ይዘህ መጭ ብትልስ? እ?»

«ሃሃሃ:: እናልህ ይሄ ዋሕድ አንድ ነገር አለው:: እዚህ ደርሳ እሱን ሳታይ አትሄድም:: እሷ ካልመጣች እሱ ይመጣና፣ 'ዛሬ ማልደያ ብቅ አላለችም?' ይላል:: አይኖቹ ውስጥ እንደቆላው አያለሁ»

«አንተ ታናሽህ ነኝ እንዲህ ያለ ነገር ለእኔ አታወራም ሃሃሃ፣ ደሞ በዋሕድ ቀንተህበታል መሰለኝ:: ሲትዮዋ ዘጋችህ እንዴ?»

«ማን አንተ? ዱርዬ»

«ለምን እንደዛ አልክ? ለእንደዚህ ያለ ነገር ገና ነኝ ታውቃለህ:: ዱርዬ ይለኛል?»

«ከፀናዕል ጋር 'የሆነ' ነገር አለሽ ይባላል»

«ማን አለ ደሞ:: ከቤት ሲወጡ የዚህ ሰፈር ሴቶች ከሞግዚት ጋር ምናምን ነው:: ጥቂት ቆይቶ ከአራተኛ ክፍለጦር አጃቢ ሳይቀጥሩ አይቀርም»

«ህሃሃሃህ»

«ፉገራሽ በጣም ነው የሚጥመኝ»

«ፀናዕል ከቤቷ አትወጣም እንኳዋን ሌላ ልታስብ:: ዝም ብለህ ወሬ ትቀዳለህ:: መንገድ ዳር ስቅህ ሲስፍር ነው የተበላሸኸው አንተ»

«ሃሃሃሀ አይ አንቺ፣ የዋሕድን ግን ልክ ነኝ»

አልመለስኩለትም፡፡ ይሄን አውርተን በዝምታ እሱ ሽንኮራውን እየጋጠ፣ እኔም ሲ.[redacted]ዬን እያጤስኩ ቆየን፡፡ የጠራ አመልማሎ ደመና የተኛበት መምሸት የጀመረ ሰማይ እያየሁ፣ በዝምታ በመረጋጋት ያሳለፍኩትን እያሰብኩ ሰስተኛ ሲጋራ ለኮስኩ……ቀኑ አርጅቶ የጨለማ ሸበቱን በሰፊሬ ማንኩዋተት ሲጀምር ወደ ቤቴ ሄድኩ፡፡

ቤት ስገባ፣ የበለጠ መቃቃሩ እንዳይሰፋ ፈርቼ ጥፋቱን አንስቼ አባቴን አልተጋፈጥኩትም፡፡ ማግስቱን [redacted] ሳይሆን ለሳምንታት ቤታችን በሚያስፈራ ደርዝ የለሽ ፀጥታ ተወጥሮ እንደ ነበር አስታውሳለሁ፡፡ የልቡና ነገር ሲጠም፣ ሲጣመም፣ ልክ እንደ ቁስ ሚዛን ያለው አይመስለኝም ነበር፡፡ ክብደቱ ዛሬ ድረስ ይሰማኛል፡፡

እናኑን ላያት የተመላለስኩት እስከ የካቲት 1967 አማሃይ አካባቢ ድረስ ነበር፡፡ የካቲት 19 የገብሬል እለት ማታ አልጋዋ ላይ ልረፍ ብላ ጋደም እንዳለች ከዚህ አለም ሞት ነጠቃት፡፡ እኔና እማማ ተጠርተን ቤቷ ስንሄድ (አባባ ለስራ ጉዳይ ኖርዌይ የተባለ አገር ነበር) አልጋዋ ላይ የምናውቀው ጋቢዋን ከላይዋ ጣል አድርጋ አገኘናት፡፡ መሞቷን ስላላመንኩ (ያውም ዘጠና የተጠጋት ሴትዮ) ጋቢዋን ገለል አድርጌ ፊቷን አየሁት፡፡ ዐይኖቿ ተከድነዋል፡፡ አፏ በትንሹ ተከፍቷል፡ የመጨረሻዋ እስትንፋስ የወጣችበት ቀዳዳ ይመስላል፡፡ የፊትዋ ቆዳ ለስላሳና ቀዝቃዛ ነው፡፡ ሽበቷ እንዲህ ነጭ አይመስለኝም ነበር፡፡ ከሁለመናዋ የሚወጣው ጠረን የሽንኮራ፣ የዱባና የእረቲ ነው፡፡ [redacted] እናኑ ያሉ እውነቱንና ልዋጩን የማያምታቱ፣ በማጋነንና በማኮሰስ ከትክክለኛ እውነቱ የማያሸሹን ይመጣሉ፡፡ የተመደበላቸውን ጊዜ ጨርሰው ወደ ሚሄዱበት ይሄዳሉ፡፡ ውስጤ ለቅሶ ይሰበስባል፣ አፌ ሊስማት ይቋምጣል፡፡ ጉንጭዋ ላይ ጉንጬን አስቀመጥኩ፡፡ ሁሉ ነገሯ ትዝ አለኝ፡፡ ቀስ ብላ አንስታ አናቴ ላይ የምታስቀምጠው ቆዳው የተጨማደደ የደከመ እጇ፣ በኮረዳነቷ ቅል ስትፍቅ የተጎዱት መዳፎቿ፡፡ በቀስታ የሚፈሰው የሚያስቀኝና የሚያስገርመኝ ጨዋታዋ፡፡ ሳይጠፉቀ አብረው የማገኛቸው እውነተኛነቷና ቧልቷ፡፡ እንደፈለጓችው ብትኖርም፣ ብዙ ያየች ናት፡፡ የሚያሳዝን ቢሆንም መታደልም ነው፡፡ ጋቢዋን በቀስታ እነበረበት መለስኩት፡፡ እማማ ከጀርባዬ ወዲያ ወዲህ እያለች እጆቿን አናቷ ላይ አድርጋ በፀጥታ ታለቅሳለች፡፡ ዕንባዋ በጉንጮቿ ላይ መንታ ጅረቶች ሆኖ ይወርዳል፡፡ ነጠላዋ በከፊል ገላዋን ለቆ መሬት ላይ ይጎተታል፡፡ ቀጭን ቁመናዋ ይንቀጠቀጣል፡፡ እንደ [redacted] ልጅ ታለቅሳለች፡፡ ለጥቂት ደቂቃዎች በማልቀሷ ብትቀጥል እማዬ ተበታትና ወለል ላይ እንደምትወድቅ እርግጠኛ ነበርኩ፡፡ እሷን ደግፌ ለመቀመጥ ተቸገርኩ፡፡ ሁለመናዋ ተልቆሰቆሰ፡፡ ከተቀመጠችበት ወርዳ እየዳኸች ወደ እማ አልጋ ሄደች፡፡

ከዛ ማልቀስ ጀመርኩ:: ከአያቴ ሞት የበለጠ የእማማ ሁኔታ ሁሉን ነገር ወደ ቀለጠ የመርዶ አለም ለወጠው:: ብዙም አልቆየችም:: የእናኑን እጅ እንደያዘች ራሷን ሳተች:: እናኑ በሞት ከተሰናበተችን ሁለት ሳምንታት ቢያልፍም እማማ ተዳክማ ከአልጋ አልተነሳችም::

አለመስማማትና መስማማት፣ ፍቅርና ፊንታ፣ ጠማማነትና ቀጥተኛነት፣ ገፅና ገበር፣ እናና እንደምትለው እንደ እንጓና መለሌቃ በቤቴ አህጉር ተቀራርበው የሚኖሩ አይመስለኝም ነበር:: እንዲህ እያየነው አበባ የመሰለው ነገር እሾህ ሆኖ እንደሚወጋን አልገመትንም:: ሊታየን የሚገባው ክፉ ቶሎ የማይታየን የዋሃን ነበርን:: መልካሙ ያልፋል:: ክፉውም ይቀመጣል:: ክፉውም ያልፋል፣ መልካሙም ይቀመጣል:: የአበባውንና የእሾሁን ወሰን የሚሰብር አደጋ ባልተጠበቀ ቀን እንደሚመጣም ገባኝ:: በዚህች አይነት አለም ውስጥ ነበርኩ:: ሽሮሜዳ ባኗት መዲባ:: እጣ ክፍሌ ካስቀመጠኝ ከዚህች ቦታ የትንሿ አለሜን ወጣ ገባዋ በትንሽ ነፍሴ ሸመደድኩ:: ቸኩላ የመጣች የዞረባት ጉርምስናዬን በጠባብ ደረቴ ተቀበልኩ:: እየበላሁ፣ እየተፋሁ፣ እያሰብኩ፣ እየረሳሁ፣ ጃርክ፣ ቻቻና ቡጊ ውጊ እየደነስኩ በለግላጋ ቁመናዬ ደቃቃ ሰድሜያትን ሰበሰብኩ......

# የሽሮሜዳ ቡጊ ዉጊ

በግድየለሽ ፌሽታ እየተነዳሁ......በዘመኑ የመዘየን ስልት ራሴን አበጀሁ፡ ልሳኔ በአራት ቋንቋዎች የተኳለ ጉራማይሌ ነበር፡ እንግሊዘኛ፣ ጀርመንኛ፣ አማርኛና አራድኛ:: ስራመድ በዳንስ ነው:: የምለብሰው እንደ ሆሊውድ አክተሮች ነበር:: ከላዬ ላይ እንደ ቆዳ ልክክ የሚል ጀርሲ ሸሚዝ ካልለበስኩ (ያውም ባለ ሪጋ)፣ ረዥም ኮሌታዎቹንም ነፋስ እንደ ኮባ ሐመልማል እየገለበ አይኖቼ ስር ካላርገበገባቸው፣ የቤልቦተሙ ሱሪዬ ስፋት አቧራ እያስነሳ ተላላፊ ካልረበሸ፣ በዚህም ትዕምርት እንደ እኔ ዘመነኛ ነን ባይ ልጃገረዶች ከወረዳ ወረዳ አይተው ካልማለሉልኝ (ከብልቶቻችን ሁሉ ዓይናችን ሳይበረታ ይቀራል?)፣ አፍሮዬ በየአቅጣጫው እንደ ጭራሮ ቆሞ ሳበጥረው ቀለምሲስ ካላፍለቀለቀ ያማረብኝ አይመስለኝም ነበር......የዘመኑ ቀለም እንደዛ ነው:: እያንዳንዱ ዘመን የራሱ መረብ አለው--ወጣት ጠልፎ አባላት የሚያረባበት......ይሄን አላመለጥኩም፣ ለማምለጥም አላሰብኩም፣ ለማምለጥም ማሰቢያው አልነበረኝም::

በሚመች ጊዜ ከመሰሎቼና ከዕድሜ እኩዮቼ ጋር ብዙ ጊዜ ፒያሳ ትሪያኖን ካፊቴርያ፣ ወይ ክሪያዚስ ተያይዘን እንሄዳለን:: በቂጥ ልመው የበለዙ/በልዘው የላሙ የጣሊያን እንጨት ወንበሮች ላይ ተቀምጠን ሆዳችንን በቡና በወተት እየነፋን......ብዙዎቻችን ገና አስራ ሰባት ያልሞላን የጎረምሳ ጅር፡ እኔ፣ ዳንኤል (ጠዋት ማታ ስለሪቮሉሽን የሚያወራን ማርክሲስት ነኝ ባይ)፣ ናትናኤል(ፊልም አምላኪ፤ 'ፊልሚስት ነው' እንለው ነበር)፣ ደብተራው እዝራ (ያለ ቡና አይጠጣም:: ቡና ያስለመደኝ እሱ ሳይሆን አይቀርም) እስማኝኝ(እንደ አሜሪካው ተዋናይ እንደ የል ብራይነር የሚራመድ፣ እንደ የል ብራይነር የሚናገር፣ እንደ የል ብራይነር ጭንቅላቱን የሚላጭ፤ አማን 'ምነው ሽንት የወጠረሽ ትመስያለሽ?' ያለው)፣ ደበበ (ጄምስ ብራውን ነኝ የሚል ሃ!ሃ!ሃ!ሂ!ሂ! እያለ በተለይ ሞቅ ካለው በኮፒ ጩኸቱ የሚያደነቁረን)፣ ግርማቸው (እጅግ በጣም ጉዋደኛዊ የሆነ ጉዋደኛ፣ የቢትልሶችን ዘፋኝ ብርያን ጆንስን ለመምሰል ፒጃማው እንኳን የቢትልስ ሹራብ የሆነ)፣ የዝናሽ ወንድም ጥላዬ(ትንሽ ጥፍሩን አሰድጎ በእሱ አናቱን እያከከ በዝምታ ተቀምጦ አብሮን የሚጠጣ እና 'እስኪ ካሽ ግፊ' ሲባል ሳይከራከር

ጠረጴዛ ላይ የተጠቀለለች ባውንድዋን ቁጭ የሚያደርግ፣ ተስፋዬ(ቤቱ ግቢ ሁለት ሶስት ባስኬት ቦል የማያጣ--የስፖርት ወሬ የሚወድ)፣ ቸርነት ጣጤ(ካልሰከረ ቅዳሜ ቶሎ የማያልፍለት)፣ አማን ቶራ(የሆነ በዚህ ስም የሚጠራ የሁለተኛው ዓለም ጦርነት ፊልም ነበር:: በሬድዮ 'ቶራ! ቶራ!' እያለ ማስታወቂያ የሚናገረውን ሰውዬ ሴት ልጅ ሊጠብስ ሲለፋ ደርሰንበት የአባቱን ስም መረሳን ቀንሰን 'አማን ቶራ' አልነው፤ በተጨማሪም አፉን ሞልቶ 'በፖለቲካ ከእናንተ የበሰልኩኝ ነኝ' የሚል)፣ ልዑል (እጅግ በጣም ብሪሊያንት የተባለ የእንግሊዝ ስኩል ተማሪ)፣ እና ገርማሜ (በቅፅል ስሙ 'ሼክስፒር' የምንለው፣ የፀጋዬ ገብረመድህንን 'ሃምሌት' በቃሉ የሚያንቸለችልልን የተፈሪ መኮንን ተማሪ......አለቃ ገብረሃናን የሚያዳንቅ፣ ንጉሠነገሥት ኃይለስላሴን የሚያጣጥል ስንት ስንት ቀልዶች ከምላሱ አሸንዳ ፈሰሱ?)--እሱን የማያውቅ ማን ነበር?

በሽሚዜ ደረት ኪስ ሲጋራችንን ያዝ እኔ ነበርኩ:: ሌሎች ወላጆ ቻቸውን፣ የወላጆቻቸውን ዘመዶች፣ የወላጆቻቸውን ወዳጆችና ራሳቸውን ይፈራሉ:: አንዳንዴ ደፋርነትና 'ምን አገባችሁ' ማለት ሲያምረኝ ጆሮዬ ላይ ግራና ቀኝ ያልተለኮሱ ዊንስተን ሲጋራዎች እሰንግና በፒያሳ፣ በቸርችል ጎዳና፣ በቼንትሮ፣ በኤንሪኮ፣ በፒኮክ፣ በፍላሚንጎና በመሳሰሉ ቦታዎች ሳንጅብ ቆይቼ ('ገና ከአሁኑ ያጤሳል? ምን ልሁን ብሎ ነው?' ብለው የሚያስቡ ባዕዳን እንደ ልጅ ገላምጠውኛል) ሰፈሬ ስመለስ ግን ያው ቡካቴ ይመጣብኝና አወርዳቸዋለሁ::

ታዲያ ቡና በወተታችንንና ማኪያቶአችንን እየለጠጥን፣ ሲርበን በተዋጣ ገንዘብ ታሳቴሊና ቦሎኛ እየበላን......የተቀመጥንበት ቂጣችን እስኪደክም የማያልቅ ወሬአችንን እናወራለን......

ወሬያችንም የተደገፋቸው የድምፅ መደቦች፡ የአጄይስ ሳቮ ትሬይን የላቤል ሌዲ *ማርመላት ('ማርመላታ ማርመላታ/ቴቢ ማርመላታ'* ተብሎ በሁዋላ በሞዛዛ የወጠጤ ዜማ እንዴት እንደተሾፈብኝ)......የዶን ማክሌን *አሜሪካን ፓይ*፣ የሙሉቀን *ቼ በለው*፣ የአለማየሁ *እንዳምራ*፣ የጌታቸው ካሳ *ትዝታ*፣ የሆት ቸኮላት *ሴክሲ ቲንግ*......የጂሚ ክሊፍ *ፓወር ኤንድ ግሎሪ*.....የፎንቴኝ ካሽ *ሬስክዩ ሚ* (ይህቺን ዘፈን ስወዳት የነበረው *ሬስኩዩ ሚ ዳዳዳዳዳ*) የሰይፉ ዮሃንስን *መላ መላ*፣ የሙላቱን ጃዝ፣ የአይቤክስ ባንድ ትራምፔት፣ የሚኒሊክ ወስናቸው *አደረች አራዳ*፣ የጌታቸው መኩሪያ ሳክስ፣ የጥላሁን *ስትሄድ ስከተላት*፣ የተክሌ አድሃኖም ጊታር......እና......ሌላ መዓት መዓት......እየሰማን ወይም እያልሰማን...... ወይ ለማንጎራጎር አንዱ ሞክሮ ስንተራረብ፡ '/ዘፍንሽ ሞተሻል/ዕንጥልሽን ተመርመሪ/ለማልቀሻ እሳትሚው/ሀሀሀሀሀ!!ጂሰስ አሳመምከን/ ምን አደረግንህ? ምን በደልንህ?/' ምናምን ምናምን......

ወሬአችን ሲከስም የሶልና የብሉስ ዜማ ተከትለን በጋራና ለየብቻችን ስንሶሉሱልና ስናቦልል......ወይ ጠረጴዛ ስንቆረቁር......ስንተመትም...... የተጨለጠ ካፌላቴና ሻይ ስንጨልጥ......

ያ አገሬ ነበር......

ያ ስፔሹ[2] ጊዜ......

ትሪያኖን[3] ሲሰለቸን ጣቢያ ቀይረን ቼንትሮ ባር፣ ወይ ኖሃ ባር ወይ ክሬመሪ ተቀምጠን በመንገድና በበረንዳ ላይ የሚያልፉትን 'ዶናዎች' በየመልካቸውና በአለባበሳቸው ገርማሚ ባስተማረን ቴንፕ መድበናል:: እዛ የምታልፈው ጂንስ ቤልቦተም የለበሰች አፍሮዋ የሚያምር ወይ ፀጉሯ እስከ ጀርባዋ የወረደ 'ታንጀሪና' ነበረች:: ባላቸው ከመሰለ ጋር የሚሄዱ ቆነጃጅት *እነዚህ ጩጬዎች ምን ያፈጣሉ?* አይነት የሚያጤኑን 'ፋንታ' ነበሩ:: ቀለብላባዎች፣ ልጅነት አፋቸው ላይ የሚፈላ፣ ወሬኛነታቸውና ቂሌታምነታቸው የሚያምታታ ከማንም 'ቶክ'[4] ማድረግ የሚወዱ 'ስፐራይት' ነበሩ፤ ነጭናጫዎቹ፣ አስቀያሚዎችና ፋራዎቹ 'ጠላ' ነበሩ:: ፈረንጆች ወይም የጣሊያን ክልሶች 'ባናና ሼክ' ነበሩ:: አንዳንዴም አገር ሰላም ነው ብለው በመንገድ የሚያልፉ ልጃገረዶችን በጋራ የሹፈት ቁልምጫ: 'ቆንጂት!' 'ሳራ!' 'የእኔ እህት!' ብለን ተጣርተን፣ የተናገርነው ተረባችን መስጠን ፊቶቻችንን በአንዱ ወዳጃችን ደረት ጋርደን በሳቅ ስንንፈራፈር......

ያበቀለና ያላበቀለ ጢም እያስተያየን እንደ ቁም ነገር ስንበሻሸቅበት:: ስለ ብሪቲሽ እግር ኳስ ስለ እነ ጆርጅ ቤስት፣ ቦብ ቻርልተንና ዴኒስ ሎው እያወራን፣ ራስ መኮንን ባር እርጎ በማንኪያ እየቀረፋን፣ ቦክሰኛ ኬክ እያፈረጥን፣ ቸኮላት ኬክ እየላስን፣ ባልተገደበም የድርጊት ቧልት የሲጋራ ገበር ወረቀት ልጠን፣ ሚጢጢ ዋንጫ ሰርተን፣ ጣራ ላይ የሰቀልናቸው ብርማ ወረቀቶች እስከ ቅርብ ቀን ድረስ ነበሩ......ሃ!ሃ!ሃ! እያልኩ የማያቸው......ከመልካም ዘመን የተፈለፈሉ ጨዋታዎች ነበሩ......

**ዛሬ ካሉ ሂድና**
**እነሱን እያየህ**
**ብትችልበት**
**እንደ እኛ**
**እንደ ፌሽታ ዘመን ልጆች**
**ሃ!ሃ!ሃ! በል**
**ያልታደልክ::**

---

[2] 'ስፔሻል' የተባለው ቃል ሲቆላመጥ

[3] ፒያሳ ሲኒማ ኢትዮጵያ ጎን ያለ ሆቴል/ካፌቴርያ

[4] ማውራት(እንግሊዘኛ)

ክረምት ሆኖ ዶካኪንቱ ከቤት አላስወጣ ሲለኝ፣ አልጋዬ ላይ ተጋድሜ የታደሰ ሊበንን አጫጭር ታሪኮች (መስከረምን እና ሌላው መንገድን--ማን ይረሳል 'ተሰማ......ተሰማ......ተሰምዬ'ን[5]) አጋታ ክሪስቲንን፣ ኢያን ፍሌሚንግን፣ ሃሮልድ ሮቢንሰንን፣ የቶማስ ማንን ማጂክ ማውንቴይን፣ የሲድኒ ሼልደንን ሴክሲ[6] ዕሑፎች፣ የቴድ አልበሪን ልቦለዶች) እነዚህ ሲሰለቹኝ ወይም ሲያልቁብኝ ያረጁ ያፈጁ የፀደይ መፅሔቶች ላይ የወጡ የስርግና(ሙሹሮች ለምን በቀላሉ ይስቃሉ? ይሄ ሁሉ ስንክሮዓት ነገ ለመፋታት ይሆን? ይህቺ ቆንጆ ምን ልሁን ብላ ያን አውራሪስ ታገባዋለች?) የልጆች የልደት ፎቶግራፎች (ለዚያ ሕፃን አጠገቡ ያቆሙለት የኬክ ፎቅ ነው? ወይስ የእንጨት ሐውልት? ለሕፃንዋ እናቷ ላይ ያስቀመጡላት ባርኔጣ ነው ድስት?) እያየሁ አሾፍ ነበር:: ፀሐይም በማያቆም ንጭንጭዋ፣ በማያልቅ መሳምዋ፣ በማያልቅ ልፊያዋ ቀኔን ስታዝንረጉረው......ሁሌም ክረምት የማይቀረው እንጨት እየፈለጠ ኩቢ. ሜትር የሚደረድርልን ወንድወሰን ሲያምጥና ሲያፋዋጭ......አንዳንዴ አብራው የምትመጣ መልአክ ልትመስል ችንሽ የቀራት ስድስት ሰባት ወይም ስምንት አመት የሚሆናት ሴት ልጁን 'መክዲ ዞር በይልኝ ልስራበት!' እያለ ሲጮህባት......የቡሄ ጅራፍ እንደ ጥፊ እያንባረቀ ያለፈ ዘመኔን ሲቀሰቅስ:: ሳናውዝ፣ ስነቃ፣ ስጠጣና ስበላ......

የዚህ ክረምት ዕረፍትና መሠረተ ልማቱ ወሬ ሰልችቶኝ ቁዋቅ ሊለኝ ሲጀምር ግማሹን ቀን የማሳልፈው ከሞጆ ሊታይ የሚችል የፈረደበት ታላቁን አፍሮዬን ሳስተካክል ነው:: እንዴት ብሎ ዞማ ያማይበላሽ ክብ አፍሮ ይሆናል? ምንስ በቢራ ቢታጠብ? ሁለት የሚቀናባቸው፣ ስማቸው የተጠራ፣ በማክሳም ቅባት ያዳለጡ፣ እንደ ቅቤ ቅል የጠየሙ፣ ዘግነው የሚበትኑ ትላልቅ የእንጨት ሚዶዎች ነበሩኝ:: እናቴ ነገረ ስራዬን እያየች ራሷን እየነቀነቀች 'ያለ ዕድሜው አደገ' ብላ ድምፅዋን ዝቅ አድርጋ ለሰው ስታማኝ ሰማኋት::

ቤት መዘፍዘፍና የአራዳው ወጣ ገባ ሲያደክመኝ ጓደኞቼን ጠርቼ ስፈራችን ሽሮሜዳ መረት አንባቢዋ አልማዝ ቤት ጉርጉሱም ሆቴል ተያይዘን እንሄዳለን

---

[5] የመስከረም <u>ዕውነት</u>(አጭር ታሪክ)

[6] ወሲብ የተመለከተ

## አልማዜ

በመሰላቸትና በመደበር ብቻ ሳይሆን መሃል ከተማው ሲርቀንና ረኃ ብሉ መዝናናት ሲያምረን ምሽትና ጨለማ ተገን አድርገን እዛው ሰፈራችን ያለው ጉርጉሱም ሆቴል ወይም በደንበኞች ስያሜ 'አልማዜ ቤት' እንሄዳለን፡፡ ፍልቅልቅ አልማዝ ባለጌ ወንበሯ ላይ ተተክላ የሚያምሩ ዓይኖቿን እያንከባለለች 'ሂሂሂ' ስትል፣ በጎ ጎ ጫማዋ፣ በሚሪ ካንት ሚኒ ቀሚሷ፣ በሰፊ ቂጥዋ አየር እያመሰች ስትንቆራጠጥ፣ ጎረምሶችና ጎልማሶች የሚሻሙባት እትዬ ትሆናለች፡፡ በዚህ ሰበብ መሰለኝ (እኔ ባይገባኝም) ሰው 'አልማዜ' እያለ የሚጠራት፡፡ የአልማዜን ቤትን ያልረገጠ የአዲስአባ አራዳ አለ? ሚሾ የአልኮል ቤት፣ ሚሾ የሴት ቤት፣ ሚሾ የጠንቋዋይ ቤት፡፡ ኩል የመሰለ ጠይምነቷን እንዲያስተጋባላት ነው መሰለኝ ሁልጊዜ ነጭ ቀሚስ ትለብስ ነበር፡፡ ይሄም ቀሚስ የመነኩሴ ድግ በሚያክል ቀበቶ ወገቧ ዙሪያ ይያዛል፡፡ በዚያ አይነት አሰናነግ እንኳን ጨርቅ አየር አያመልጥም፡፡ እንዴት እንደሆን አላውቅም ይሄ የተሰላ ቅንብሯ ቆንጆ ሳይሆን ቆሻሻ ያስመስላታል፤ እና አንዳንዴ አተኩሬ ባይ ከላይዋ ላይ ትንኝ የሚነሳ ይመስለኛል......አልማዜ የት ጠፋሽ? ብለን ስንጠይቃት 'እየተግጠብኩ ነበረ' ብላ ስትመልስልን ጥርጣሬዬን አምነዋለሁ፡፡

የአልማዜ ሆቴል ንፁሕ ነበረች፡፡ ከጀርባ ያለው ኮረኮንችና የቤርጎዎቹ ፊት ለፊት ሁልጊዜ ከባሊ በሚወረወር ውሃ ይታጠባሉ፡፡ ከውስጥ የቡና ቤቱ ግድግዳዎች በሙሉ ነጭ፣ ዋናዎቹና መተላለፊያ በሮቹ ደማቅ አረንጓዴ የተቀቡ ናቸው፡፡ በጀርባ በኩል ከውጭ ግድግዳ ላይ በተለያየ ጊዜ ከተለያዩ የበጎች ሆድቃ አስገፍፋ፣ ከሰው ዓይኖች በትንሹ ሸሸት አድርጋ የምትለስነው፣ የማይደርቅ፣ ቀለሙ የሚለዋወጥ የመሰለ የሞራ ሰሌዳ አለ፡፡ ሁልጊዜ ዓይኖቼ እዛ ላይ ሲያተኩሩ በአቧራና በጢስ የቆሸሸ ሞራና ሞራው ላይ የሰፈሩትን ጥቁዋቁር ትንኞችና ዝንቦች አይ ነበር፡፡

ቡና ቤቱ ውስጥ ካሉት ከሁሉ ጠባብ እሆነችው በስተጀርባ አለችው ክፍል ደብዛዛ ብርሃን ውስጥ ተወሽቀን፣ ገንዘብ ካለን ጂን፣ ወይ ግሪን ፋየር፣ ካሌለን ደሞ ግንበኛ አስከፍተን እንጠጣለን፡፡ ከቡና ቤቱ ቴፕ

የሚለቀቀውን ሙዚቃ የሚያስማን በቆሸሹ የሽረሪት ድሮች የተከለለ አንድ ስፒከር ኮርኒሱ ስር አለ:: ከዚህ ሚጢጢ ሳጥን ዘመኑ በጉጉት የሚያዳምጠው ዜማ ይወረወራል:: እዚህ ሆኜ 'ኢትዮጵያ ትቅደም፣ አቆርቋዥዋ ይውደም' ሲባል 'ያለምንም ደም'......ሲባል ደም ስሮቼ በአልኮል ትኩሳት አብጠው የደም ፈረሰኞቹ ሲጋርፍ ነበር......ቆዳዬም በጉርምስናዬ እሳት ሲግል'......ኢትዮጵያ ሃዱርሲቱ......' ሲሉ '...... እንዴት በነጠቅል ተራብሽ ኢትዮጵያ' ሲል......ማመልከቻ የያዘ......ትልቅ ኤንቬሎፕ በዘንጉ ፍንጭት የሰነገና በኩታ የተጠቀለለ ምስኪን 'እስኪ ይሄን ተቀበሉኝ' የሚል......ስለ ገረጣ ሰማይና ስለ ፀሐይ እቶን እየተዜመ......ከጥላሁን ገሠሠ የሚጣፍጥ አንደበት 'ዋይ ዋይ ሲሉ' እየነፈሰ......ከደባሪ ሎሚ ተራ ተራ[7] ጀምሮ እስከ መሳሰሉ መዐት ነገሮች ......ጥልቅ እንቅልፍ ተኝቼ እንደማዳምጥ ሁሉ ከፋቶ ሲነካኩኝ......በስካር ሞቅ ያለው የደም ፏፏቴዬ ላይ አፍጥጬ አተኩሬ አልሰማኋቸውም::

ባለቤቷ ልጅ እግር አልማዝ፣ ስላምታ ልትለን ወደ የምትሰራውን ጠፍቷት......ያለንበት ስትገባ......አማን ሁሌ የሚጠይቃት በማይገባን ትግረኛ አዲስ ቆንጆ ደና አምጥታ እንደሆነ ነበር::

እሱ በጋራ ቋንቋቸው ቢጠይቃትም ለሁላችን በአማርኛ ትመልሳለች:

«ምን የመሰለች አዲስ ልጅ መጥታለች፣ ዋናው መድፈር ነው» ትለዋለች ባያስቅም፣ ሁሌ የምትለው ቢሆንም፣ ልክ አዲስ እንደሰማናት ሁሉ እንስቃለን:: የሚንቀለቀለው አፌ ጮሌነታችን አልማዜ የምትናገረው ቀዝቀዝ ያለ ዕውነት ሲነፍስበት ተኮማትሮ እሚቀመጥበት ይቀመጣል::

ብዙ ሳይቆይ እሷ ጠርታት ሳይሆን አይቀርም አዲስ የተባለችው ልጅ እግር ሴት አለንበት ክፍል ትመጣለች:: አማን እዛ ጋ እሷን ጎኑ አስቀምጦ ይላፋል:: እኔና ልዑል 'ለዚህ አልደረስንም' ስለምንልና ስለምንባል፣ ልባችን እየጓጓ፣ ሚስጢሩ እያብሰለሰለን፣ በጎሪጥ እሱንና እሷን እያየን የምንማረውን እንማራለን:: እዚህ እኔ ነኝ፣ እዛ ልዑል ስገድ ነው፣ ወይ ቸርነት፣ ወይ ገርማሜ፣ ወይ ግርማቸው፣ በፕሪሞ ወይ በስኮንዶ፣ ወይ በቴርሶ ሲጋራ እየታፈንን:: እዛ ጋ ደሞ ከፊት ለፊታችን አልማዝ ከአማኚና ከልጅቷ ጎን ተቀምጣ መቼ ዕለት ያወራችንን ደግማ ታወራናለች......

አልማዝ ወደ ሰፈሩ ቆንጃጅት በማምጣት ላጤዎችንና ባለትዳሮችን በማስከርና በማማለል የታወቀች ብቻ ሳትሆን በጠንቋይነቷም የሚወራላት ነበረች:: ጥንቆላዋ የግዕዝ ማወቅ ችሎታ ወይም የደብተራ አይነት ድግምት ሳይሆን እሷ እንደምትለውና እኛም በኋላ እንዳየነው መረቅ

---

[7] ትንቢት አለው ተብሎ በዚያን ጊዜ ይመለከ የነበረ ፍካሬ የሱሳዊ ዘፈን

በማንበብ[8] ነው:: አማን እንደሚለን ከሆነ ቆሌዋ ላልወደደው ሰው አትጠነቁልም:: አልፎ አልፎ እሁድ እዛች ቤቷ ጠባብ ክፍል ስገባ፣ መረቅ አስነብበው የጨረሱ ሰዎች ቀይ ወጥ ያረጠበው እጃቸውን አንቀርፈው ለመታጠብ ወደ ቧንቧ ሲሄዱ፣ ወይ ገንዘብ ሰጥተዋት ሲወጡ አይቼአለሁ:: ያን ሁሉ አሕዛብ ቀልቧ ወዶታል? 'መረቅ ማንበብ' ወይም 'ትሪ ማንበብ' እሷ እንደምትለውና ኮስተር ብላ እንዳወራችን ከጠጠር መጣል፣ በቡና አተላ ከመጠንቆል፣ ወይ ኮከብ ከመቁጠር የሚለይ አይደለም::

አንድ ጊዜ የደመወዝ ገንዘብ አልቆ፣ ሴተኛ አዳሪዎቿ ወንድ ተሰውሮባቸው በየወንበሩ ላይ ተወዝፈው፣ የአልማዜም ገቢ ከስቶ የምትሰራው ቢጠፋት 'ዛሬ በእኔ ሂሳብ ላሳያችሁ' ብላን፣ 'እንይ እንይ' ተባብለን፣ ባልገባኝ ምክንያት እኔ እንዲነበብልኝ ተመረጥኩና ያኔውኑ መጠንቆያ አንድ ቀይ ወጥ እንድበላ ታቀደ:: 'ምን ይደርስብኛል?' ብዬ እሺ አልኩ::

እጄን እንድታጠብ ተነገረኝና ታጥቤ ተመለስኩ:: አልማዝ እና እኔ ጎን ለጎን ተቀመጥን:: ከላይዋ ማራኪ የፍራፍሬ መዐዛ ይነሳል:: ቸርነት፣ አማንና ልዑል ያልተለኮሰ ሲ[redacted] ወደ ሰማይ እየወረወሩ በአፋቸው ለመቅለብ ይለፋሉ:: እየወደቀባቸው ተያይዘው ይስቃሉ፣ ይተራረባሉ......

«እንጀራው መቼም በትሪ ነው የሚመጣው:: እንጀራው ትሪ ላይ ሁልጊዜም ተዘርግቶ ይመጣል:: ትሪው ነጭና ንፁሕ መሆን አለበት:: ገባህ? እሺ? አለበለዚያ ትርጉሙ ይበላሻል:: መረቁ ትሪው ላይ እንዴት [redacted]ተሰራጨ በማየት ነው አየህ የማነበው:: [redacted] ቀላል ነገር አይምሰልህ:: የሁሉ ነገር [redacted] አንድ ላይ ተሰብስቦና ተጨምቆ ነው: የሽንኩርቱ፣ የስጋው፣ የቅመሙ፣ የበርበሬው የቅልጥሙ ምን አለፋህ የሁሉ ነገር:: እ? ገባህ? አታምንም አይደል? በዝምታ መብላት አለብህ:: ዝምታ [redacted]ህን ያረጋጋል፣ ታተኩራለህ:: ገባህ?»

ትሪ ላይ የሚያምር እጅግ ስስ የሆነ አይናማ ነጭ እንጀራ ተዘርግቶበት መጣ:: አንዴ እንኳን አልታጠፈም:: ከእንጀራው ጋር መረቁ የጠፈፈ ቀይ ወጥ፣ ጠርዙ ተከርክፎ ባለቀ የተዝጎረጎረ የለቅሶ ቤት የኒኬል ሳህን መጣ::

«በል ትሪህ ላይ ገልብጠው:: ገባህ? አንተነህ የምትበላው ወጡንም የምታደርገው» አለችኝና አንስቼ ወጡን የተዘረጋው እንጀራ ላይ ገለበጥኩት::

«ጥሩ አደረግህ:: ልክ መሃል ላይ ነው ያፈሰስከው:: ገብቶሃል» አለች

[8] (ስለዚህ ማብረሪያ አባሪ እንበብ)

በልቤ *'ምን አስቸኮላት?'* እላለሁ:: *'የእኔን የወደፊት ዕጣ ለማወቅ ምን አስቸኮላት?'* እላለሁ:: ግራ ገብቶኝ አየሁዋት:: ትሪውን ወደ እኔ ገፉችውና እንድበላ በእጇ ጠቀሰችኝ:: መብላት ጀመርኩ::

«ቶሎ ብዪና እስኪ ሚሊየነር ስትሆኚ እንይ» ይሉኛል ልዑልና አማን

ግን የእንጀራ በወጡ ፀባይ ገና አንድ አራት ጉርሻ እንደ በላሁ ተለወጠብኝ:: ወጡ ቢጥምም ጥንቆላ የበላሁ መሰለኝ፤ ከሰይጣን ጋር የተካፈልኩ......የሆነ ከተደገመበት ነገር ጋር የተገናኘሁ::

እንደ በቃኝ ነገርኳት::

«ግድ የለም በዚህ ለማንበብ እሞክራለሁ» አለችና ካልተበላው እንጀራ፣ ወጥ ያልነካውን በአመልካችና በአውራጣቷ ይዛ በቀስታ ገልባ አነሳችውና ጎድጓዳው ሳህን ላይ አስቀመጠችው:: በእንጀራው ዓይኖች ሰርጎ ትሪው ንጣት ላይ የፈሰሰውን የሚያምር ቀይ መረቅ በፍቅር ስታየው ቆየችና ወደ እሷ ሳበችው:: ጓደኞቼ ጨዋታቸውን አቆሙ:: ሰሃኑን እያገላበጠች በመስኮት በሚገባ ብርሃን እያጠናችው ቆየችና ብዙ ተጉዛ እንደ መጣች ሁሉ ከውስጥ ተንፍሳ ትሪውን ወደ ጠረጴዛው መለሰችው::

ሁላችን በጉጉት አየናት::

አማን:

«ስንት ልጅ ይወልዳል?» አላት እየሳቀ:: አልመለሰችለትም::

አንድ እጇን አፏ ላይ፣ ሌላ እጇን ብብቷ ከታ ትሪውን፣ እኔን፣ ትሪውን፣ እኔን ስታይ ቆየችና:

«አንዲት ልጅ ትወዳለህ፣ ግን እሷ አታውቅም:: ልጅቷ ትወድሃለች ግን ትፈራለች:: ጥሩ አይሆንም:: ልጅ ነህ ምንም አይደል:: ልጅቷ ግን አጠገብህ ናት......»

አማን:

«ረድኤትን ይሆናል» አለ እየሳቀ፣ ንግግሯን አቋርጦ:: በመስኮት ወዲያ ወዲህ ስትል የምናያትን በቅርብ ከአስመራ የመጣች ጨጬ ልጅ በአገጩ እያሳየን::

«ዝም በል አማን:: በደንብ የሚነበብ ነው፤ ግልፅ ነህ ማለት ነው:: አዎ ማለት ነው:: እግር አለ፣ እግር አያለሁ ያውም ሁለት:: ቦት የመሰለ ያጠለቀ:: ጉዞ አለብህ:: ውጭ አገር ትሄዳለህ:: ሩቅ አገር ትሄዳለህ» አተኩራ ትሪውን ስታይ ቆየች::

«አንድ አዘን አለብህ ጥሩ አይደለም:: እንጃ......እዚህ ጋ» አለችና ትሪውን በብርሃን ውስጥ ስታገላብጠው ቆየች::

«ለመሆኑ የልጅቷ ስም አለ? ተፅፏል?» ይላታል አማን

«ሌላ ቀን ብናደርገውስ? እናንተ ልጆች በተለይ አማን አታስሩም እኮ:: ማተኮር አልቻልኩም:: በልቶ ቢጨርሰው ኖሮ ይታይ ነበር:: ሁለተኛ ከእናንተ ጋር»

«ጀርመንኛ ትችላለች?» አለ ልዑል

«ለምን?» አለችው

«ጀርመን ስኩል የተማረ እኮ ነው! የጉዋደኛዬን እህት በጀርመንኛ ሊጠብስ ይሞክራል፣ ግን እሷ ያለ አይመስላትም:: በጣም ሃብታም ናት፣ ለክረምት ለእረፍት ለንደን ነው የምትሄደው» አለ ልዑል

«ልጅቷ ግን ጥራት አላት?» አለችው እሱንም ሳታየው

«ምን ትፈልጊያለሽ ከዚህ በላይ? አንቺ ከየት ነው የመጣሽው? ከአባሻውል ነው ከደቀመሃሪ አይደለም እንዴ የመጣሽው? ለንደንን ዕድሜሽ 900 እስኪሆን አታዪውም»

«አንተ አፍህን ያዝ አልማዜን አትንካ» አለና አማን አልማዝን ሊያቅፋት እጁን ዘረጋ:: ከትከሻዋ ላይ እጁን ፈቀቅ አደረገችውና:

«የልጅቷ ነገርና የጉዞው ነገር ነው በደንብ የታየኝ» አለችና የበላሁበትን ዕቃ ማነሳሳት ጀመረች::

በድንገት ማተኮሯና ጥልቅ ዝምታዋ እዛች አካባቢ ለተሰራው ጥንቆላ ለተባለው ነገር እንግዳ ክብደት ሰጠው:: ከላይ እስከ ታች በትኩረት አየኋት::

«ማየት ፈለክ?» አለች ትሪውን ወደ እኔ ዘርግታ::

ቢረባም ባይረባም የተጠራጠርኩዋትና የምታደርገውንም ያመንኩ እንዳይመስልብኝ

«አይ ግድየለም» አልኩዋት

አይኖቼ ውስጥ ያለውን አሻሚ መልዕክት አነበበች መሰለኝ

«እየው» አለችና ትሪውን ወደ እኔ ዘረጋች::

*መተርጎም ካልቻልኩ ባየው ምን ይጠቅማል::* አልማዝ አራዳ ናት:: በይሉኝታና በጉጉት ትሪውን ተቀበልኩዋት:: ሰሃኑ ላይ ተጠርጎ ያላለቀ ቀይ ወጥና ግማሹ ተበልቶለት እዛና እዛ በወጥ የተነካካ እንጀራ አለበት:: ቂል የሆንኩ መሰለኝ:: በመሀይም የተፎገርኩ:: ከመሃል ልክ ከሳህኑ ደርዝ

በደንብ በጉልህ የሚታይ ይሄ ምስል አለ:: ጉርሻዬን የምበላው እያሽከረከርኩ ነው እንዴ?

# 9

እሱን ዐይቼ ቀና ብዬ አየሁዋት:: ዐይኖቿን መለሰች:: የሆነ የገባኝ ነገር እንዳለ የጠረጠረች መሰለኝ:: ትሪውን ከእጇ ላይ ቶሎ ወሰደችው:: አይኖቿ ውስጥ ያጋጠመኝ ሁኔታና ትሪውን ከእኔ አነጣጠቋ፣ ሁሉን የነገረችኝ ሳይሆን በጓደኞቼ ረባሽነት አሳባ ከፊሉን ትርጉም በመዋጥ ላይ ያለች መሰለኝ:: ድርጊቷ የመዋጥ ድርጊት መሰለኝ:: በሞቀው ቧልት መሃል ትርጉም የሚጠይቅ ምን እንደማደርገው ያልገባኝ ዝምታ ነበር ......እውጭ ከወጣች በኋላ በመስኮት ከወገቧ በላይ ጉርዷን አየኋት የበላሁበትን ትሪ ደግማ ስታይ......ስትሰርቅ እንደ ተያዘች ሁሉ እኔና ጓደኞቼ ወደ ተቀመጥንባት ወደ ዛች ደብዛዛ ክፍል ተገላመጠች......

*

በልጅነቱ ጉርጉሱም መስከር ያልጀመረ የሽሮሜዳ ጎረምሳ መኖሩን እንጃ:: ይሄ ከወላጆችና ከአንዳንድ 'ያገባናል' ከሚሉ ሰዎች አልማዝ ላይ ብዙ ተረብና ትችት አምጥቶባታል:: ደንበኞችን ከማስተናገድ ሌላ አንድ ስራዋ ታዲያ ድንገት ጓዳ ካለን የሚያውቁን ጎረቤቶቻችን፣ ወላጆቻችን፣ ወይም ዘመዶቻችን ሆቴሏ ሊጠጡ ሲገቡ ካየች፣ አለንበት ክፍል በቶሎ መጥታ እንድንሄድላት መለመን ነው:: በዚህ ሩጫና ትርምስ መሃል ጨርሰን ሳንጠጣቸው ብዙ ፋሽኬቶቻችን ሆቴሏ ቀርተውብናል:: ብታስቀምጥልንም፣ ሌላ ጊዜ ተመልሰን ስንመጣ ነፍሰበት ተበላሽቶ እንደርሳለን::

አንድ ቀን ከዚህ ከዚህ አይነት አማራሪ ጉዳይ ለመሸሽ ከግሮሰሪ ግንበኞችንን ገዝተን እንጦጦ ተራራ ላይ ወጥተን፣ ማንም ሳያየን ትልቅ ዛፍ ጥላ ስር ተቀምጠን፣ ጠጥተን በሞቅታ ስፈር ስንገባ......

እኔና ደበበ ጄምስ ብራውንንና ፍሬዲ ጃክሰንን ለመዝፈን እየሞከርን......ወይም ሌላ......አማንና ልዑል 'ሪቮሉሽናሪ' ነን ብለው ሳይሆን አይቀርም:

*ማርታ ለምን ለምን ሞተች!?*
*ጥላሁን ለምን ለምን ሞተ!?*
*ዋለልኝ ለምን ለምን ሞተ!?*
*በሃይል በትግል ነው ነፃነት የሚገኘው!*

በሳዳና የተማረ ሰልፍ የተካኑበትን የሐይለስላሴን መንግሥት የሚገፉበትን ዘፈን አብረናቸው በማላገጥ ስንዘምር......እየጮሁ ሲያቋር ጡን፣ *ስክርው ዜም*[9] እያልናቸው......እየተበሳጩ......ሰዎቹን በዓይኔ ስጋ አይቼአቸው ስለማላውቅ፣ በየፎቶ ቤቱ የተሰቀሉት ምስሎቻቸው......

‘ማርታ’ በአፍሮዋ ትክክለኛ ማንነቷን የደበቀች ቢች[10] ትመስለኝ ነበር፣

‘ጥላሁን ግዛው’ የተባለው ደሞ ለምን እንደሆነ ጥቁር ያረጀ ባለ ቀጭኔ ጥንጥላ ያስታውሰኛል፣

‘ዋለልኝ’ ቁጭራ ፀጉሩን በምላጭ ከፍሎ የሚያበጥር የባንክ አካውንታንት (ከትደነቂያለሽ ጋር አብሮ አንድ ቢሮ ውስጥ የሚሰራ) ይመስለኛል::

ግምቴን ለአማን ስነግረው ከልዑል ጋር ተጻብለው ሊመቱኝ ያባርሩኛል::

«ቤተሰቦቻቸው ቬሪ ሪች[11] ናቸው ለአገር መስዋዕት መሆን ያሰድባል?» ብሎ ይጮኻል::

«ማን ግድ አለው? ሃብት አይደለም አየሽ ክላስ ነው ዋናው፤ ይታይህ ፀጉሩን በምላጭ የሚከፍል ሰው፣ ፕሬዝዳንት ቢሆን ‘ጋሜ ተሰራ’ ይልሃል ሃሃሃ»

በዚህ መጋጨት ተዳክመን የእንጦጦን ተዳፋት ጨርሰን ሽሮሜዳ ስንገባ፣ ያው የዚያን ጊዜ በአለም ተወዳጅ ዘፈን የነበረውን *ሰዊት ሆም አላባማን* እያፈራረቅን እየዘፈንን፣ (ከመሃል ልዑል ፉገራ ሲያምረው *ሰዊት ሆም ሽሮሜዳ* ብሎ ይዘፍናል) እየተላፋንና እየተተራረብን......

በዚያ ፀሐይዋን ባልገደለች ለስላሳ የግንቦት ማታ......የፋሽኬት ሞቅታ ገና ባላንበረከካቸው ዓይኖቼ......ጎረቤቴ ተባረኪ ከታዚና ወረድ ብሎ ብዙ ጊዜ ልጃገረዶች እሚሰበሰቡበት ሜዳ አጠገብ በጉንጉንዋ እየተጫወተች፣ ጠብደል ጭኖቿ ላይ ሚጢጢ ረጋ ሰራሽ የቤት ልብሷ እንደ ውሃ እየፈሰሰች......ጎንበስ እያለች ድንጋይ እያነሳች......ብዙም እንዳትገለብ ቀሚሷን እግሮቿ መሃል እየሰበሰበች......ለእሷ ብቻ እንጂ ለሌላ ሰው የማይታይ ነገር ለመምታት ስትወረውር......እጆቿን ከአቧራ ለማፅዳት እርስ በእርስ እያማታች ስታራግፍ......ተቆጥተው እንደ ጠሩአት ሁሉ ሮጣ ቤቷ ግቢ ስትገባ......ቀሚሷ በነፋስ ውስጥ የሚያምር ቂጥዋን ተከትላ ስትቦን......ልስላሴአቸው ሰመመን የሚከቱ እግሮቿን ሳይ......ይሄ ጠዋት ማታ የማየው የለመድኩት ቁመና በፍቅር እንዳሰረኝ ገባኝ::

---

[9] ተኛቸው(screw them)

[10] ጨቅጫቃ፣ ትርቡት(bitch)

[11] በጣም ሃብታም(very rich)

አይኖቼን ሁለመናዋ ላይ ተክዬ ያውም ከእርቀት......እየተደነቃቀፍኩ ......ወፍራም ምራቅ ደጋግሜ ዋጥኩ::

የአልማዜ ትንቢት ትዝ አለኝ::

ለመጀመሪያ ጊዜ ጥንቆላን አምኜ ፈራሁ::

## መልመድና ፍቅር

እነዚህ ሁለቱ ያላንከረባበቱኝ ገና ሳተና......

በቀላሉ በሚረሳ የለመድኩት አስልቺ ዓይነት ክረምት፣ ግን ልረሳው ባልቻልኩት በአንዱ፣ ጎረቤቴ ተባረኪ(ቴቢ) እኔን ለማጫወት ቦይ አቋርጣ (የዚህም ስፋት እንደ ተከዜ ነው) ጭቃ በለበሰ አስፋልት ላይ ተረማምዳ፣ እንደ ገና ሌላ ሁለተኛ ቦይ አቋርጣ ቤቴ መጣች:: በሚኒሊክ ሁለተኛ ደረጃ ከላይ እስከ ታች በትምህርቷ አንደኛ የምትወጣ ሁሉ የሚያውቃት ተማሪ ነበረች:: ትዝ ከሚለኝ የልጅነት ዕድሜዬ ጀምሮ አብረን አድገናል:: ስለ እናቷና ስለ እሷ ሲወራ:

«ትደነቂያለሽ እኮ አንድም ብትሆን በልጅ ተባርካለች፣ ሰው በስሙ ይወጣል ይሏችኋል......» የሚባልላት ናት::

አልጋዬ ላይ ተጋድሜ መስኮት ከፍቼ መስታወቱን ግን ዘግቼ የሚጣፍጥ የዝናብ አወራረድ አዳምጣለሁ:: ጃኪ ዊልሰን ኖ ባዲ ባት ዩ[12]ን ያቀነቅናል:: ሶል ይሶለሰላል:: ሃ ሃ ሃ ሀ ሀ ሀ ሀ ሀ ሁ ሁ እንጉርጉሮው በቴፑ ወንፊት ሾልኮ ከክፍሌ ወደ ውጭ ወደ ክረምቱ እየተተረተረ......በትከዛ የማያቸው የዝናብ ነጠብጣቦች እንደ መቀነት ታጥቀውት......ቀዝቀዛ የፀሐይ ውጋጋን በመስኮት እየገባና አልጋዬ መሃል እያረፈ......በመልከመልካምነቱ እያማለለ......ከቤቴ እንድወጣና ቼንትሮ ወይም ትሪያኖን ተዘፍዝፌ ቡና በወተት እንድለጥጥ ይጠራኛል:: የፀዳሉ ለስላሳነት የአንሶላዬን ቆሻሻነት እያጋለጠው ቡናማ አንሶላ ስለመግዛት አስባለሁ:: ይሄንንም ችግሬን እንዲቀልድበት ለቸርነት አሹዋፊው እነግረዋለሁ:: እንዴሁ እንዴሚለኝ በሁሉ እገምታለሁ:

*አንሶላህ ምን አጠፋ፣ አንሶላህ ምን አጠፋ*
*አንሶላማ ግዑዝ ነገር ነው እሱ ምን አጠፋ*
*አፍህ ነው አጉዳፊ ልጋግ እየደፋ*

ሰማይ ላይ ያቆለጡትን ግራጫ ደመናዎች(ይሄን አባባል ግርማቸው ኩ ወንድ አያቱ ሰምቶ ነው የነገረን---አንድ ጊዜ በሚያስገርም መልክ ነፋስ

---

12 ማንንም አይደለም አንቺን ብቻ (Nobody but you)

የቆራረስው ቁልል ደመና አይቶ 'ምን ዓይነት ቆለጣም ደመና ነው?' ያለው ትዝ ይለኛል) የከስዓት በሁዋላ ዙረቴን እንደማያበላሹ እየተለማመጥኩ ሳለሁ በር በለሆሳስ ተንኳኳ::

(ምነው ለሆሰሰ?)

ዞር ስል የተባረኪ ፊትና ክብ ፊቷን የከበበው ጉንጉን:: ፊቷ ዙሪያ ነጭ ግድግዳ......ጠይምነቷን ያጎላው ፍካት......በጀርባዬ ያው አልጋ ላይ ነኝ......

«አሌክስ! አልተነሳህም እስከ አሁን?» ብላ ሳቀች:: ሳልመልስላት አንሶላና ብርድልብሴ ስር ተርመጠመጥኩ:: የምረሳት አረፍተነገር አይደለችም:: ከምንም ተነስታ ሳቀች:: ሳቂ ነበረች:: ትንፋሽዋ እስኪጠፋ ትስቅ ነበር:: እተቀመጠችበት ዓይኖቿ ዕንባ እስኪያቀሩ የምትርገፈገፍ::

ታዲያ እንዲህ ብላኝ: 'አሌክስ! አልተነሳህም እስከ አሁን?' ክፍሌ ገባች::

እንደሌላው ጊዜ ቢሆንም ውስጤ ልረዳው ያቃተኝ፣ ልሰይመው የማልችል ለየት ያለ ስሜት ይፈላ ነበር:: ሹራቧን አልጋዬ ላይ ጥላ ከጉያዋ ትልቅ፣ ቅጠሎቹ የበጨፈጨ 'አንድ ለእናቱ' የተባለ መጽሐፍ አወጣች:: እሱን ሽክም ነጭ ቀለም የተቀባ ዕድሜዬ አስር ዓመት ሳለ አልጋዬን እንዲያጅብ የተገዛልኝ አጭር የእንጨት ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠችውና በቁሟ አልጋ ላይ ዘጭ አለች::

አንዳንድ ፊዐሞ የማልረሳቸው ነገሮች አሉ: ዘጭ አባባሏ ለምሳሌ አይረሳኝም:: ዛሬ ዓይኖቼን ስጨፍን ያኔ በገላዋ ክብደት የቀሰቀሰችው የአልጋ ንቅናቄ ትዝታው በለጋ አጥንቶቼ ታስሮ አሁን እንደሆነ ሁሉ ይሰማኛል::

በመስኮት የሚገባው ለስላሳ የፀሐይ ጨረር በግራ ትከሻዋ ላይና በግራ ክንድዋ ላይ፣ በግራ ሽንጥዋ ላይ፣ ሐምራዊ ጀርባዋ ላይ አር ፎባታል(ይሄን አልረሳሁም):: ባለማንገቻ ሐምራዊ ቀሚስ ነው የለበሰችው (ይሄንንም አልረሳሁም):: ሁልጊዜ የምትለብሰው ቢጫ ዕምብርት ያላቸው ትናንሽ ነጫጭ አበባዎች የተሳሉበት ሐምራዊ ቀለም ያለው ቀሚስ ስለነበር፣ ሌላ ለብሳ ካጋጠመችኝ ወይ እደነግጣለሁ ወይ እሷ መሆንዋ ለአፍታ ይሳተኛል:: ቀሚሱ በውሃ፣ በሳሙና፣ በነፋስና በልፊያ አለማለቁ ይገርመኛል:: ጡቶቿ ያለመያዣ ተራርቀው ቆመው ጫፎቻቸው ረቂቅ የነቁጥ ጉብታዎች ሆነዋል:: ከጠይም ቆዳዋ ስር የተደበቀ ቅላት ያለ ይመስላል:: ጥርሶቿ ከላይ እስከታች ከዳር እዳር ኖራ የተቀቡ ይመስላሉ:: የድድዋን ንፅሕና አደነቅሁ:: በነዚህ ምልክቶች ልቤ ተንፈራፈረች:: በዝምታ የተገራሚ ወይም የተማራኪ ትኩረት አየሁዋት:: በትክክል የትኛው ዓይነት ትኩረት እንደሆነ እንጃ:: እሷም ታዲያ:

«ምነው?» አለችኝ

'ምን ታየኛለህ?' ዓይነት ነገር

«ምንም» አልኩ:: ምን ልበል?

«ቁርስ በልተሃል?»

«ፀሐይ የተነሳሁ አልመስላትም»

«ልንገራት:: እኔም አልበላሁም» አለችና ከመኝታ ቤት ስትወጣ ከጀርባዋ አየሁዋት:: ፈርጠም ያለ ቂጥ አውጥታለች:: ሴት ከሆነች በሁዋላ ከሌላ ገላዋ የበለጠ እያበጠ «ቂጣም» ያሰኛት:: ፀጉሯ ተራርቆ የበቀለ እናቷን ለቀው ሊሄዱ እንደሚፈልጉ ሁሉ የሚወናጨፉ አስራ አራት ወፋፍራም ጉንጉኖች ናቸው:: ከማድ ቤት ተመልሳ መጥታ እንቁላል እየተፈረፈረ እንደሆነ ነገረችኝና አልጋዬ ዳር ወደ ጭኔ ጠጋ(ጠጌ) ብላ ተቀመጠች:: ምን ላድርግ?

«አልጋው ስለሚሞቅ አልወጣም» አልኩ

«ጥሩ አይደለም ብዙ መተኛት» አለች

«ጋደም በይ፣ ይመቻል»

«ምን?» አለች እንደምትቆጣ ሁሉ ጎላ አድርጋ:: ተቆጥታ ሳይሆን እስከዚያን ጊዜ ከምንነጋገርበት ቀስስተኛው አሮጌ የድምፃችን መደብ ላይ ስላረፈ መሰለኝ::

«ስቀልድ ነው» አልኩ ቶሎ፤ ተንቦቅቡቄ::

«ምነው ሙዚቃ አላደረግህም ዛሬ?»

«አሁን ጠምጥሞ ጨርሶ እኮ ነው:: እስኪ ያን የማርቪንጌይን ዘፈን አድርጊልኝ»

«አይሰለችህም?»

«ደስ ይለኛል:: አለማየሁ እሸቴን አደረግሽው? እንዳሞራ ምናምን:: የአገራችን ዘፋኝ ለምን አሞራና ዶሮ ይወዳል?»

«ምን ወጣው? አለማየሁ ደስ ይላል:: የት ጋ ነው ካሴቱ?»

«እሱ እስክሪፕቶ ጋን»

«የት? እ»

ካሴቱን ቴፕ ውስጥ አስገብታ ዘፈኑ ከስፒከሩ እስኪወጣ ጠበቀች......

*ላቭ ዩ ገርል*
*ላቭ ዩ ገርል*
*ማይ ሚስቴክ......*

እቆመችበት ፊቷን ሳታዞር ዘፈኑን ለመጀመሪያ እንደሰማችው ሁሉ አተኩራ ስታስብ ቆየች። ከሁዋላዋ ባቷን እየሰረቅሁ አያለሁ። ልጅነት የቀበተተው ጠብደልነቱ፣ ደሞም ሌላ ነገር ለማሰብ ስዳዳ......በድንገት ዞር ብላ፡

«ይበቃናል እንዴ?» አለች ሳቅና ቀልድ አድርጋ።

«ምን? እ......እዎ»

በጀርባዋ በቀኝ ጎኔ በኩል ጠርዝ ላይ ጋደም አለች። እንዲበቃት ወደ ግድግዳ ሸሸት አልኩላት። (ይሄም ለብቻው ትዝ የሚለኝ እውስጤ ተጣብቆ የቀረ ዝርዝር ጠቃሚነቱ አጠራጣሪ የሆነ ትውስታ ነው)

አንድ እጇን አናቷ ስር ሌላ እጇን ሆድዋ ላይ እንዳደረገች ትዝ ይለኛል። የጣቶቿ ጥፍሮች እንደ ጨረቃ የነጡ።

ነገሩ ረብሾኛል። እናም አስፈርቶኛል። ብዙ ጊዜ እንሳፋ ነበር። ያን ዕለት የተለየ የሆነበት ምክንያት ግን ዛሬም ቢሆን አልበራልኝም። ልክ በዚያን ዕለት የመዳሪያ ዕድሜዬ ደርሶ ይሆን? ለመሆኑ ጎረምሳና ኮረዳ የሚሻሻቱበት ትክክለኛ ዕድሜ፣ ሰዓትና ደቂቃ ይታወቃል? ገላዬን ማነቃነቅ ፈርቼ ትንፋሼን ውጬ ለደቂቃዎች ዝም አልኩ......ሰንድ ለአናቱ የተባለውን መጽሐፍ በኮርኒሱ አቅጣጫ ገልጣ ለመጀመሪያ እንዳየችው ሁሉ በፀጥታ ስታነብ ቆየች......ምናልባት ከግማሽ ሰአት በሁዋላ......

እኔም እሷም ከተኛንበት ለማውራት ፊታችንን ስናዙዋዙር ትንፋሽ ለትንፋሽ ተቀራረብን (ከሌላው ሁሉ ጎልቶ ትዝ የሚለኝ)። ገላዋ በስልት ተነቃነቀ። ማየት የሚከብድ እጅግ ቀስስተኛ ግን ምሉዕ ንቅናቄ ነበር። ቀሚሷ ላይ የተሳሉት አበባዎች ነፋስ የነካቸው ዓይነት የተከፈቱ የተከደኑ መሰሉ......

ሞግዚቴ/ሰራተኛችን ፀሐይ ክፍሌ ገብታ፣ ሁኔታችን አስደንግጧት መሰለኝ ተንደፋድፋ፣ ያልተሰማኝን ነገር አጉተምትማ፣ የማጥኛ ጠረጴዛዬ ላይ ፍርፍሩን አስቀምጣ ተመልሳ ሄደች።

እኔ ከአልጋዬ ሳልወጣ ከተባረኪ ጋር ቁርሳችንን በዝምታ በላን።

ለምን ዝም አልን?

እንደለመድኩት አልተበላልኝም። ሆዴ በሆነ ባልገባኝ ጉዳይ ተደፍኖ ነበር። ከጉሮሮዬ እስከ ፊኛዬ ቀላል ክብደት ያለው የተላቆጠ ሲሚንቶ ወይም የዳቦ ሊጥ የተቀመጠ ይመስለኛል። ከቁርስ በሁዋላ ተራ ንክኪያችን ዳብሮ እጅ ለእጅ ተያያዝን። አያያዛችን እንደሌላው ጊዜ አልነበረም። ትከሻ ለትከሻ ተደጋግፈን አልጋ ዳር እንደተቀመጥን ሰመመን ውስጥ ወደቅን። መሳም አላውቅም። ከወዳጆቼ ጋር ካፌ ውስጥ እየተሰበሰብን በአፍ እራቀቃለሁ እላከፋለሁ እንጂ. ከቸርነት፣ ከተስፋዬ

ፓስታና ከአማን በስተቀር ስለ ሴት የምናውቅ አልነበርንም:: ሁሉን የማደርገው በወሬ እንደሰማሁት ነበር:: ገላዋ አቅፌ ሳረጋጋው ያልቻልኩት ነፍስ ያለው ሐምራዊ ንጋት የለበሰ ወጨጫ፣ ሁለመናዋ የሚያሙዋልጭ ታላቅ ድመት:: ስንተራመስ፣ በማይገባኝ፣ ቅኔ በሆነብኝ የመሳሳም ስፖርት መሃል የጭኖቿን መገናኛ ጥቁር ወሽመጥ ሳይ እንዴት ተርበደበድኩ? የፀጉሯ ስብርባሪ በአፌ ሰረገ:: ትንፋሽ እስኪያጥረን አንገት ለአንገት ተቃቅፈን ግማሽ ሰአት ያህል ቆየን:: በዓለም የተደነገገ አገር ያወቀው ነፋስ የመታው ደንብ እንደሆነ ሁሉ......

ያን ዕለት ማታ የአንበሳ አውቶቡስ በደርግ መንግስት መወረሱን ሰማሁ::

ጳጉሜን በፍቅር ስመመን አልፌ፣ የካይዘር ሐይለስላሴ ከዙፋን መውረድ ማታ ላይ ተነገረኝ:: ያን ቀን ጠዋት ከተባረኪ ጋር እንጦጦ እየተንተትን ስንወጣ ካልተጉመጠመጠችው አፏ ላይ የቀመስኩት የቁርስዋን ትዝታ ነበር:: ያን ቀን ከነጫማዬ ዛፍ ላይ ልወጣ እየሞከርኩ ሳልችልበት ስቀር--ስትስቅብኝ......ቦይ ልትዘል ሞክራ አንሸራቷት ስትወድቅ--ስስቅባት......ለግላጋ የለጋ ባህር ዛፎችን ብርማ ዱቄት በእጃችን እየጠረግን እሷ ፊቴን ልትቀባኝ፣ እኔም ፊቷን ልቀባት ስንሯሯጥ......ገደል ቆንጥጦ የተተከለ ጠፍጣፋ ድንጋይ ላይ ተንጋላ ሰማዩንና የሚፈስ ደመናውን......ቆማ ደሞ በጢስና በሐመልማል የተጋረደች የአዲስ አባን ኩርማን ፈትሻ 'የት ነው ቀሐሥ ቲያትር?' ብላ ፈልገን ፈልገን አላገኘነውም......ቀሚሷ ወደ ላይ ተሰብስቦ የጭኖቿን ከፊል ቀዝቃዛ ሳር ላይ ሙጥኝ ያለ ጤዛ እየሳመው......እነሱን ለመሸፈን ስትለፋ......የገላዋ መግነጢሱ ስቦኝ አጠገቧ ቁጭ ብዬ ወደ ታች በፀጥታ የምትጤስ ከተማችንን አያየሁ......የገጠር ከተሞች ሞጆና ቢሸፍቱና ሰበታና አቃቂና ሌሎች......ማህበራዊ ረብሻ ፈርተው ካሉበት እየሮጡ መጥተው ጥቂት ፎቆች ዙርያ እየተንቀጠቀጡ የተሰበሰቡ እየመሰሉኝ ......አጎንብሼም እሷን ለመሳም ስንጠራራ......በሚጣፍጠኝ፣ በጣፈጠኝ መግደርደር፡ 'ሂድዛ!'......

እናቴ የምወደውን የዕንቁላል ወጥ ሰርታ የፓስታ ምሳዬን ስበላ፡

«ሐይለስላሴ ከዙፋናቸው ወረዱ» አለች......ዕንባ እየተናነቃት (እናቴ ለምታውቀውም ይሁን ለማታውቀው ዕድለቢስ ታዝናለች)

«መቼ?»

«እንዴት አልሰማህም? የት ነበርክ?» (እየተናፈጠች)

እንደ ተረት አልናገረው ታሪኬን፣ እንደ ዙፋን የሚያበሩ እርጥብ የቴቢ ከንፈሮች ላይ ነበሩ ከንፈሮቼ......ቀልቤም::

እነዛ ጊዜዎች......ነጋ ጠባ 'ተነሳ ተራመድ' ሲባል፣ የተማሩ ፖለቲከኞች ፎቶ በየቦታው ሲሰቀል፣ ለእኔ ምንም አልነበሩም:: 'አማን

አማን አንዶም' ሲባል:: 'አቆርቁዋዥዋ ይውደም' ሲባል:: ሁሉ ሲባል ......ልቤ በመውደድ ቀጭን ገመድ አዲስ አባ ሰማይ መሃል ተሰቅላ ነበር::

ሲባል 'ተነሳ' ከአልጋዬ ቀና ብዬ መስኮት ከፍቼ በጠዋት ፀሐይ ስር ወዳጄ ቴቢን ደብቆ የያዘውን የእናቷን የትደነቂያለሽን ቤት ማየት:: በችኮላ ፊቴን መተጣጠብ፣ ልብሴን መልበስ......

ሲሉ 'ተራመድ' ቁርሴን ሳልጨርስ መንገድ አቋዋርጬ ቀዝቃዛ ሃረጎች ያቆፈነኑት በረንዳ ላይ በር እያንኳኳሁ......እሷም በሩን ከእናቷ ቀድማ ከፍታ እጅ ለእጅ ተያይዘን ወደ ቤቷ ጀርባ አልፈን፣ የጎረቤቷን የሰይፉን ቤት እያየን ጥቁር ቆዳዋን ከእናቷ ደብቃ ስስማት ሉሚ ሉሚ አለኝ አፌን......

*

አንድ ምሽት ከተማም ከሲታ ሱቅ አንዲት ሲጋራ ገዝቼ እሷን መንገድ ጓሮ ተደብቄ ስገል......አልማዝን አገኘሁዋት:: ስለ እኔና ስለ አማን ስለ ጓደኞቼ ጠየቀችኝና ቶሎ ቅላዬዋን ለውጣ:

'የት ጠፋህ አንተ? እንዳንተ ግን የጠፋ የለም' አለችኝ:: እነአማን ስለ እኔና ስለ ተባረኪ ተያይዞ መፍሰስ ወይም መንዘላዘል፣ በዚህም ሰበብ ከአለም እንደተሰወርኩ እንዳላወሯት ሁሉ......

መንገድ ዳር አቁማኝ እየሳቀች......በፍቅር የሚቀቀል የሚፋጅ ግንባሬን በቀዝቃዛ ጣቶቿ እንደጨዋታ እየነካች (ግራና ቀኝ መንገደኛ እየሰለለች)......ጆሮዬ ላይ ያረፋትንም የፀጉሬን አሻራዎች ፈቀቅ እያደ ረገች......በለሰለሰ ድምፅ......የላይ ከንፈሯን (ሁልጊዜ ከርፈፍ ብሎ ለመናደፍ እንደሚንጠራራ) ወደ ገጼ እንደ ሚስጢር አቅርባ......የምስበው አክሲጅኔ የእሷን የሽቶ ጥብቆ ለብሶ.....ደሞ አፏን ሸርመም አድርጋ ፈገግ እያለች......በቀላል ነፋስ የሚከለባበስ አጭር ስስ ሚኒ ቀሚሷን በቀኝ እጇ እየጨበጠች እየለቀቀች......አንገቷን እየሰበቀች:

«ብቅ በልና በእኔ ኪሳራ ጂን ቶኒክ እገዛልሃለሁ......» አለችኝ

እዛ ከዚህ እስከ ስድስት ኪሎ የሚንሽረሽረው የደርግ ጂፕ ቢአፉን አቁሞ ያልፈናል:: ታች ከግሮሰሪው ጎን አዲስ ሕንፃ ለማቆም ሰዎች በፈዘዘ ትጋት ከቆፈሩት መሬት የአፈር ሽታ ይመጣል:: ይሄም ጠረን የተከበበበት የቆርቆሮ አጥር ንጣቱ በደብዛዛው ጨለማ የተዘረጋ አንሶላ ይመስላል::

......ደሞም እያረገረገች፣ (በአንድ እግሯ ሁለመናዋን እያስደነሰች ......አንድ እጅዋን ወግባ) የተከመሩ ጡቶቿ ደረቷ ላይ እየዋለሉ......

የተጋጠሙበትን ስፍራ ለሞላ አይኖቼ አቅርባ እያሳየች አለች ያኔ አልማዜ:

«ብቅ በል ጂን እጋብዝሃለሁ፣ ሙት ጠፋህ:: ስትናፈቅ አትኩራ:: ካልፈለክም ካፌ ላቴ እሰራልሃለሁ»

*

እነዚያን ወራት......ለስላሳ ሹል መንከሻ ያለው......ልቤ ላይ እንደ አልቅት የተለጠፈ......ከአፍ ማውጣት የከበደኝ......የክርታስ ቁምጣ ያጠለቀ.....ሞፈር ቀምበር የተሸከመ......የሚንኳኳ ድንቁርናዬ ነበር::

ይሄ ድንቁርናዬ አስፈራኝ:: ድንቁርናዬ ደበረኝ::

አንዳንዴም ተባረኪን የመውደዴን ነገር አልማዜ ራሷ በድግምት የፈጠረችው ይመስለኛል:: ካልሆነ ለምን እሷ 'ወደሃል' ያለችኝ ሰሞን ተባረኪን እንደ ወደድኳት ገባኝ? ይልቁን ከእሷ የበለጠ የማከብራት የምፈራት በእቃ እቃ ጨዋታ ከተባረኪ ያላነሰ የማውቃት የዶክተር አሰፋ ልጅ ፀናዕል፣ አሳጥረን 'ፂ' የምንላት ነበረች አይደል:: አሻንጉሊት የሞላበት ክፍሏ ተቀምጠን ስንጫወት እጄን ጭኗ ላይ ሳስቀምጥ እንዳልሰማች እንዳላየች ሁሉ፣ በተከፈተ መስኮት በዝምታ ወደ ውጭ የምታይ? በዚህ ፈቃዷ ተማርኬ ወደ ሌላ እንዳላልፍ ምንም ሳትናገር እጆቼን በቆራጥ ውሳኔ ጉልበቷ ላይ ጨምድዳ የምትይዝ:: ሌሎች ልጃገረዶች ሲነጫነጩ፣ እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ ሲፎካከሩ በዝምታ ተቀምጣ የምታዳምጥ:: አይኖቿን ከፍታ ስትከድን ሁለት አመታት የሚወስድባት:: የሆነች ጠንበለል (እዝራ እንዲያ ይላት ነበር):: ከንፈሮቿ የበሰለ ኮክ የመሰሉ:: ለመጫወትና ለማሾፍ ስለፋ ጥርሱ የማይታይ ፈገግታ ብቻ የምታሳየኝ:: እንድትደበር በእግዚአብሄር የተፈቀደላት የመሰለ:: ኮስታራነቷ የሚያሸሽ:: እንደገና ከዝምታዋ ስትወጣ ገፆዋ ንቅናቄ የሚሞላው:: ያኔ ካልታቀፈች፣ ካልተያዘች፣ የምትበታተን የምትመስል:: ግን እንደምመኘው እንደፍላጎቴ መጠን የማታስጠጋኝ:: ብታስጠጋኝም ወደ አፏ የማታሳልፈኝ:: (በዚህ ላይ አሉ በደርባባነታቸው የሚያስፈሩ እናቷ፣ እንደ 'ሮያል' የሚሰራቸው፣ አፍ አውጥተው ባይናገሩም በሰላም ቅቅምጠን ጆያወራን ሲያዩን መስመር የታለፈ ስለሚመስላቸው፣ ወይም የታቀደ፣ ቶሎ ብለው 'ምን እያደረጋችሁ ነው?!' ብለው እንደ ወጥ ቤት ሰራተኛ የሚጠይቁን) ስጨብጣት ደሞ የሚሰማኝ ቀዝቃዛና ደረቅ ነገር:: በዚህ ተገርሜ ፊቷን ሳየው ገላዋ ለሁለት የተከፈለ እየመሰለኝ የምታስደነግጠኝ......

ይኼ ይኼ ሁኔታዋ ሳላውቀው አስፈርቶኝ ይሆን? ምናልባት ይሄ አርቆኝ ይሆን? እናቷ? ድብርቷ? ወዘተ ወዘተ

ለምን ተባረኪን?

ተባረኪ ማሾፍ ትችላለች፡፡ ይሄ አንድ ችሎታዋ ነው፡፡ ልጅ ሆነው ካላሾፉ በልብ ድካም ይጠፋ፡፡ እናቷ ስንላሉ 'በቆረጣ' ታየናለች እንጂ ጥያቄ አትጠይቀንም፡፡ ስንሯሯጥ ካየችን 'እንዳትወድቁ' ብላ የመከረች መስላ መከታተልዋን ትደብቃለች እንጂ አታስደነግጠንም፡፡ ከተባረኪ ጋር መሆን በትንሹ መፍዘዝ ነው፡፡ ጊዜ ይበራል፡፡ እንደበረረ አይታወቅም፡፡ ተባረኪ ፊት ላይ ሁልጊዜ ልሙጥ ፀጥታ አለ፡፡ መልኳ ወይም ፀባይዋ ያለው ምናልባት ከቆዳዋ ስር ነው፡፡ ምናልባት ያኔ ሕይወታችን የተራራቁ ስሜቶች ያልነበሩበት ጊዜ ይሆናል፡፡ ስታከካትና ስትሽኮረመም ከንፈሮቿን ሰብስብ አድርጋ አይኖቿን ለረቂቅ አፍታ ከአይኖቼ ዞር ታደርጋለች፡፡ ስትራመድ ንቅናቄዋ ውስጥ የሆነ ቋንቋ አለ፡ 'በሉ ደረስኩ፣ አድርጉኝ' የሚል፡፡ አስራ አምስት ባልደረሰች በዚያ ልጅነቷ በመንገድ ዳር ስትሄድ ካለፈቻቸው በኋላ ስንቶች ጎረምሶች በቁሊታቸው ጥርስ ኋላዋን ግጠዋታል? ስንት ባለትዳሮች ቀድመው በመወለዳቸው ጢማቸውን በቁጭት ነትተዋል? የፀናዕል ከላይና ከታች መከፈል፣ የተባረኪ በውስጥና በውጭ መከፈል ተመሳሳይ አያደርጋቸውም ነበር? ፍቅር ሚስጥር ይሆናል ትንታኔና መረጃዎች የማይደርሱበት፡፡

ድንቁርናዬ ሲያብሰለስለኝ ከረመ፡፡ በደረቅ ሌሊት አይኖቼን ስከድን ሁለመናዋን ሳስብ ከሚቆመው የአፍሪቴ አድማስ ወዲያ ያለው ግቢ እንዴ መግነጢስ ይስበኛል፡፡ ልቤ ይፈራል፡፡ ለመሆኑ የሚፋጅ እሷ የሚቀባኝን እርጥበት ያስለመለመኝን የመሳምን ድርጊት ሳልፍ የሚቀጥለውን እንዴት ልሆን ነው? እንዴትስ ላደርግ ነው?

## ግቡ እናንተ ተስፋ ያልቆረጣችሁ[13]

እሁድ እሁድ የአልማዝን ጉርጉሱም ሆቴል ደንበኞቿና እንግዶች ይርቁታል:: ከዋናው ሕንፃ ጀርባ በ«ገ» ቅርፅ በሰልፍ ከተደረደሩት 13 አልቤርጎዎች በደንበኞች የሚሞሉት ግማሾቹ ቢሆኑ ነው:: ከግቢው ግራና ቀኝ 'ኑና አዳምጡኝ' እያለ በድርቅና የሚጮህ ግን የሚያዳምጠው ያጣ የመሰለ ስስ አቧራ የሸፈነው ናሽናል ቴፕ ሪከርደር አለ:: የምታሰራቸው ቆነጃጅት ግማሾቹ ፈቃድ እየሰጠቻቸው ወደ ግል ጉዳያቸው ይሄዳሉ::

እንደ ልጆች በሰልፍ ሁዋላ ፊት ሆነው ይደረደራሉ:

«የት መሄድ አለብሽ አንቺ?»

«ታች ገዳም ሰፈር አንድ ዘመዴ ዘንድ»

«ያንቺ ዘመድ አያልቅ......ያ ወዳጅሽ መጥቶ ቢያጣሽ የለሁበትም»

«አይመጣም ነግሮኛል»

«አንቺስ?»

«ከአንድ ጉዋደኛዬ ጋር ቀጠሮ አለኝ»

ከፍ ዝቅ አድርጋ ታያትና ዓይኖቿ ቡናማ ውስጥ መዓት አይነት ቀለም ያለው ቅናት እየነደደ......

«አውቀዋለሁ እዚህ ይመጣል? ዕውነት አንቺ ዕድሜሽ 20 ነው?»

«ምነው አልማዜ እስከዛሬ አታምኚኝም?»

«ማመን?......እሺ አምንሻለሁ:: ጥሩ ጎበዝ አንቺን ቢያገኝ ሚስት ቢያደርግ......ወይ ማማር»

«ሂሂ......»

«በይ አትቁሚ ከፊቴ......»

«አንቺ ደሞ የት ልትሄጂ ነው? ስራ እኮ ነው»

---

[13] ከዳንቴ አሊጊሂሪ (Divine Comedy)መንፈሳዊው ጨዋታ

«በእናትሽ አልማዚ.......»

አተኩራ አይታት አፏን ጠረግ አድርጋ የማንባሯን ቆዳ ወደ ላይ ሰብስባ የፀጉሯን ደርዝ ፋት ፋት አድርጋ እንደሚያስብ ሁሉ አሰባ......

ባታስብም......

«ማንም መጥቶ እንዳያስቸግረኝ፣ ከአሁን በሁዋላ ፈቃድ የለም»

ሲያብሰለስለኝ የከረመውን ነገር ለማድረግ ተጣጥቤና ቁርሴን እንደነገሩ በልቼ አንድ እሁድ ጠዋት አምስት ሰዓት አካባቢ ከቤቴ ወጣሁ:: በአገሪቷ የሰፈነው ገጭ ገው ያስደነገጣቸው ምዕመናን ከእንጦጦ ማርያም ከራራይስአቸውን አፍስሰው ይመለሳሉ:: ቤቷ በጠዋት እርይታ ውስጥ ተኝታለች:: አልኮል፣ ትዝታዚና ምንም ይሸታል:: አልማዜ ባንኮኒ ጀርባ ተቀምጣ አገኘሁዋት:: ከቡና ቤቷ ስፒከር የሚንጨረጨረው የጃክሰን ፋይቭ አቤሲ (ሀሁ ወይም አቡጊዳ) ዘፈን ነበር:: እነዛ ጎፈሪያም የጃክሰን ወንድማማቾች ካልጠፋ ዘፈን ይሄን ሲያቀንቅኑ ለምን ያን ቀን በዛች ደቂቃ ተገጣጠሙኝ? ሰላምታ ብዬአት አፍጥጬ ፊት ለፊቷ ቆምኩ:: አንዳንድ አጋጣሚ ስድብ ይመስላል:: ሰማይና ምድር ፕላን ያደረጉት:: ውስጤ የሣፍኩትን እንዳነበበች ሁሉ ፈገግ ብላ (ወይስ የልቤ ደብተር ግንባሬ ላይ ነበር?)

«አሁን አይመችም ማታ ና» አለችኝ::

'ማታ ና' ስትለኝ ሁለመናዬን እፍረት አነደደው:: ይሄ ሰውቀቷ ነበረ:: ወይ ድሬዳዋ ወይ ናዝሬት ወይ አንዱ ከተማ የተማረችው:: ቀጠሮዬን ወስጄ አመዴን እያቦነንኩና እያራገፍኩ (ለራሴ ብቻ የሚታየኝ) ቀኑን ሙሉ ስርበተበት ቆየሁ:: መሽቶ ተባረከ እቤቴ መጥታ ራት ስንበላ፣ ራሴን ስታዘብና ስራገም፣ እንደተለመደው ብዙ አላጫወትኳትም:: መኝታቤቴ ገብተን ሙዚቃ እየሰማን 'ምን ሆንክ?' እያለች ስትደባብሰኝ ያቀድኩት ሐጢያቴ ሲፍቀኝና ሲግጠኝ:: መሽት ሲል እሷን ቤቷ ሸኘሁና......የጨለማ ጥቁረትና የመንገደኛ ትራፊክ ብዛት ስለካ ቆይቼ (በደንብ ጠቁሮአል ወይስ አልጠቆረም? እታይ ይሆን?)......

ጉርጉሱም ስደርስ አልማዚ ተደብራ ነበር:: ልጅ ነኝና መዳራትን ብርቅ አድርጌ መሀይምነት ውስጤ ፈንድቶ ሆሮብኝ ስንከወከው......ረስታኝ ነው? የረሳችኝ ለመምሰል ነው? የመርሳት ችሎታዋ የሰውቀቷ አንዱ ምዕራፍ እንደሆነስ? ማስመሰሉ ደሞ አንዱ ሌላው ምዕራፍ::

ከጀርባ ትንሽዋ ክፍል ገብቼ በፍርሃት ተኮማትሬ፣ ግድግዳ ተደግፌ ስቀመጥ፣ አልማዝ የነበርኩ አልመሰላትም:: የምሆነውን እንደጠበቀች ሁሉ ቸለል ብላ ነበር:: ምናልባት ድልድዩን ራሴ እንድሰራው

ከአበላሺነት ሐላፊነቷ ለመራቅ ያደረገችው ይሆናል:: 'ከፈለገ ምን ላደርግ' ልትል:: 'አሳዬኝ ካለ ምናለ የእግዜር ስራን ባሳየው' ዓይነት::

እያስጠበቀችኝ ብትሆንም፣ በቅራጥነት፣ ውስጤ የሚጮኸውን ፍርሃትና ቡና ቤቱ ውስጥ ያለውን (ጃክሰኖች ሲጠፉ) ጢም ያለ ፀጥታ እያዳመጥኩ ተደብሬ ተቀምጬአለሁ:: ፈቃድ ያልወሰዱት ወይም መሄጃ የሌላቸው ሴቶች በሚያድሩባቸው የጋራ ክፍሎች የየራሳቸውን ቡና እያፈሉ፣ ነፃ ሆኖ በማያንቀሳቅሰው ጨለማ እየደከመ በሚጠነክር፣ እየጠነከረ በሚደክም ሳቃቸው ፀጥታው አልፎ አልፎ እየተቀደደና እየተጣፈ......የስጣንና የወይራ ጢስ በቢጫ ብርሃን ከደመቁ ክፍሎች ስፌቱ እንደ ፈረስ አሮጌ ነጠላ በተገረበበ በር እየተጣጠፈ እየተዘረጋጋ እየተሳበ ሲወጣ......ከእናቴ ከፍ ብሎ ሁለት ግድግዳዎች መገናኛ ጣራ ጥግ በአቡዋራ ቡላ የሆነ የሸረሪት ድር የተከናነበ ስፒከር ከአፍታ ፀጥታ በሁዋላ የሙሐመድ አህመድን 'የሺ ሐረጊቱን' በቀስታ እያወረደ...... የመጀመሪያዬን ብራንዲ ጨርሼ ሌላ ለማዘዝ ወደ ዋናው የቡና ቤት ክፍል ስገባ አልማዝን ከባንኮኒ ጀርባ ተቀምጣ አየሁዋት:: ከባንኮኒው ጀርባ እንደተቀመጠች ያወቅሁት በፀጉሯ ጉልላት ነው:: ከየረር የሚታይ የሾጣጣዎች ሾጣጣ አፖሎ ትሰራለች:: ጉልላቱ የእኔን ቡጢ ያክላል:: ግራና ቀኝ በተከፈተው ጋባዥ በር ቀዝቃዛ አየር እየተንዘላዘለ ይገባል:: ይከረስሳል:: በስተግራዬ ሁለት ጎልማሶች ሻይ አዘው በፀጥታ ግድግዳና መሬት እያዩ ይጠጣሉ:: ከአልማዝ በስተግራ ከባንኮኒው በር ከፍ ብሎ የጥላሁን ግዛውና የማርታ መብራቱ ፎቶዎች ተሰቅለዋል:: ከእሱ በስተግራ በሚያምር ትልቅ መስታወት ነጫጭ አሸዋ ውስጥ የሰመጡ የመሰሉ ቤቶች ያሉበት ፎቶ አለ:: ከስሩ በእንግሊዘኛ 'ማሳዋ' ይላል:: ከጥቂት ሳምንታት በፊት የጄኔራል አማን አንዶምን ፎቶግራፍ በኩራት የሰቀለችበት ቦታ በጨርቅ ሰሌዳ ላይ በክር ተጠልፋ በመስታወት የገባች የአንድ ዕጌሬዳ አበባ ስዕል ያለችበት ፍሬም አለ::

ወደ ባንኮኒው ስጠጋ ተራ በተራ ከላይ ወደ ታች ያየሁት: ጥቁር የፀጉር ኳስ......ፍጭጭ ያለ ቢጫ ላስቲክ ዙሪያውን የተጠመጠመበት ለጭር የፀጉር ዘንግ......በቅባት የሚያንፀባርቅ የተለጠሰ ፀጉር ......ፈጠጥ ያለ ግንባር......በመጨረሻ ቡናማ ዓይኖቿና እነሱ የታጠሩበት የሰባት ከተሞችን ነፋስ ደቁመ ቅንድብ......

ቀና ብላ በዝምታ አየችኝ:: ቀና አባባሏ ሰመመን ውስጥ እንዳለች ሁሉ ነበር:: የግቢዋ መብረድ እሷንም ሊያስተኛት እንደ ዳዳ:: አፏን ጠመም አድርጋ እንዳዘነች ሁሉ ፈገግ አለች:: ልብ የሚሰብር ፈገግታ ነው:: ልጅ ትሆናለች:: አልማዜ የምትማርከው ስትደበር ነው:: ትላልቅ ቡናማ አይኖቿ ውስጥ አውቆ የተኛ ግን ሳይጠብቁት የሚያንቅ የመሰለ ጉጉት አለ:: የሆነ ገብጋባ ስሜት:: በዚህ ሁኔታ ውስጥ ስምዋ ሲጠራ 'እመት!' የምትልበት......'አቤት!' የምትልበት ቅላፄ እንደ ላስቲክ የሚሳብ ነው::

መጀመሪያውና መጨረሻው የማይታወቀው ዝግመቱ ይሰበኛል:: ይኼ ዝግመቱ ስቦኝስ ይሆን የመጣሁት?

«ብራንዲ መጨመር ፈልጌ ነበር» እንደተምታታብኝ ለራሴም ይገባኛል

«አንድም አሳሳፊ አልመጣልህም?» አለች ፊቷን እያበሰች

«ማንም......ማድ ቤት ቡና ላይ ናቸው»

«ምን ላድርጋቸው?......» አተኩራ አየችኝ:: ዓይኖቼን ሰበርኩ::

«መጣሁ ቆየኝ» አለችና ባልጠበቅሁት ፍጥነት ከተቀመጠችበት ተነስታ ከባንኮኒው ጀርባ ወጣችና አልፋኝ ሄደች:: እንደ ጥርኝ ምናምን ትንፋ-ሽዋን......ጠረንዋን ልበል እላዬ ላይና ባንኮኒ ዙርያ ከንብላ......

መጀመሪያ ወደ ነበርኩበት ማድፈጫዬ ክፍል ስመለስ፣ ቃሉ ባይወጣኝም እንዳወጣሁት ሁሉ አፍሬ ነበር:: ገና እንደ ተቀመጥኩ የማደርገው ሳጣ ያለቀ መለኪያዬን አንስቼ እንጥፍጣፊ ጨለጥኩ:: እንዴት ብዬ ላስታውሳት? መለኪያውን ወደ ጠረጴዛው ስመለስ ቴፑ ዝም አለ:: ፍርሃቴን ልጅነቴ ላይ ላሳብብ እፈልጋለሁ:: ሰው አልግደል እንጂ በዚያ ዕድሜዬ ሲያል ሊያስገቡ የሚችሉ ብዙ ሐጢያቶች ሰርቼአለሁ:: አሁን የምመኘውን ሐጢያት የተለየ የሚያደርገው ምንድነው? ያዘዝኩት ብራንዲ እስኪመጣ ጊዜ እንደሚወስድ አውቃለሁ:: እሁድ እሁድ አልማዜና ቤቷ ፈጣን አይደሉም::

በግራ ቀኝ እጇ ሁለት መጠጥ ያለባቸውን መለኪያ ይዛ አለሁበት ክፍል መግቢያ በር ጋ በቀኝ እግሯ ቆም ብላ በግራ ጫማዋ ደረት ወለል እየመታች፣ ከወገቧ በላይ ያለው ገላዋ ችላ ያልኩትን ሙዚቃ ተከትሎ በቀስታ እየተንቃነቀ......ወደ ውጭ እያየች:

«እናንተ ልጆች......ስራችሁን ረሳችሁ» ከዚያ ወደ እኔ ዞር ብላ ድምፅዋን ዝቅ አድርጋ፣ ትክክለኛ ከእኔ ጋር ነጋ ጠባ የምንፈትለው የተለመደ ሴራ እንዲመስል አድርጋ ተናገረች:

«እኔ ክፍል ሄደን እንጠጣ?»

ከእኔ መልስ ሳትጠብቅ ጭር ያለውን ኮሪደር በሚጮሁ ገብረክርስቶስ ጫማዋ እያደነቆረች በጀርባ ወጣች:: በመስኮት እያታለሁ ወደ ሁዋላ እንኳን ሳታይ(መከተሌን እንኳን ለማረጋገጥ ሳትሞክር) ወደ ክፍሏ ስትሄድ:: የአልማዜ ክፍል ከአልቤርጎዎቹ ድርድር በስተግራ መጨረሻ ላይ ነው:: በወሬ በወሬ ከሌሎች ክፍሎች እንዲተልቅ አድርጋ ነው ያሰራችው ይባላል:: ሺህ ጊዜ እዚህ ሆቴል ብመጣም እስከ ማስታውሰው ወደ'ዛ አልፌ ሄጄ አላውቅም:: ጨለማ ባይሆንም ጨለም ያለ፣ ሩቅ ባይሆንም ሩቅ የሆነ ስፍራ እንደሆነ ይሰማኝ ነበር:: እየተጫወትን፣ እየተቃለድንና፣ እየተገባበዝን፣ እንጀራ እየገለብን አንዲት ቀን እንኳን

በዛ አቅጣጫ ጎራ ብዬ አላውቅም:: ይሄ በእኔና በቡና ቤቱ ብቻ ሳይሆን በሴቶቹ መሃል ያለውን ዕርቀት ማሳያ ምልክት መሰለኝ:: ይሄን መሬት አብሬአቸው እየረገጥኩ፣ እየሩን በትብብር ተንፍሼ፣ የገዛችውንና የሰራችውን በልቼ ሌላ ነገር ጋ ሲደርስ ግን አውቄም ይሁን ሳላውቅ ስገለልና ሳገል......

ግራና ቀኝ የተለየ ወጋገን ባለው ደብዛዛ ምሽት እሷ ጫማዋ ላይ ቆማ አፖሎዋ እንደ እስራኤል ሚሳይል ቆሞ......በቀስታ ስትራመድ አያታለሁ:: ወገቧ በአካሄድዋ ይሁን በምትሄድበት መሬት አለመስተካከል ምክንያት ቂጥዋን እያቀዘፈ:: እተቀመጥኩበት እግሮቼ በቀስታ ይንዘረዘራሉ:: 'ካሴት ልገለብጥ' እያለች አንዷ ሰራተኛ ወደ ቡና ቤቱ ስታልፍ እየሁዋት:: ሁሉ ነገር ጭር ማለቱን ጠበቅሁ:: *ግን ሌላ ማድረግ የቻለውን ዓላዛር ማድረግ አይችልም ማን አለ?* ደግሜ እንድትጠራኝ አልፈለግሁም:: የምትጠራኝ ባይመስለኝም:: በሄደችበት አቅጣጫ የጃኬቴን ኮሌታ አቁሜ በእሱ በከፊል ተከልዬ (ያውቁኛል እኮ ግን) ስሄድ መኝታ ቤቷ በር ፊት ለፊት መጠጦቿን ይዛ ቆማ አገኘሁዋት:: ከአናቷ ከፍ ብሎ ጉማም አምፖል ይበራል:: ስታየኝ እንደደከማት ሁሉ የበረንዳ ምሰሶ ተደገፈች:: ይሄ አቁዋቁዋምዋ ልጃገረድ ያስመስላታል:: የሆነች ተባረኪ:: ምናልባት እያንዳንድዋ አሮጊት ገላ ውስጥ ተጠጥቶ ያላለቀ ማንም ያልነካው የደበቀችው የወጣትነት መረቅ ይኖራል:: ያሰበችበት ወይ ያላሰበችበት ይሁን አይገባኝም:: ወይም በወይዘሮነት ዘመንዋ ልትገለገልበት ከልጅነቷ መርጣ ያስቀረችው የመቄነጥ ጥበብ ነው:: ጥላዋ ነጭ ወረቀት ላይ በእርሳስ ወይ በከሰል ንድፍ የወጣ የመሰለ ጥቁረትና ውበት አለው:: ፈገግ ብላ ዓይታኝ አንገቷን ወደ መሬት ሰበረች......

«ቦርሳዬ ወደቀብኝ:: ቁልፍ እዛ ውስጥ አለልህ በሩን ክፈተው» አሁንም በሚጎተት ግን ጠንከር ባለ ድምፅ......

ጎንበስ ብዬ ጥቁር ባለ ዚፕ የቆዳ ቦርሳ ከሲሚንቶ ወለል ላይ አነሳሁ:: አፏራውን አረጋግፌ ዚፑን ከፈትኩት::

«ደስ አይልም?......» አለች

«እ»

«ደስ አይልም?»

ብዙ ቁልፎች ከቦርሳው አወጣሁ:: ምኑን ማለቷ እንደሆነ አልገባኝም:: ምን ደስ እንዳላት አልተረዳሁም:: ያተኮርኩት በብርማ ቀለበቶችና ሰንሰለቶች የተያያዙት ቁልፎቹ ላይ ነው:: ብዛታቸው ራስ ምታት ይቀሰቅሳል:: ግራ መጋባቴን ስታይ......በያዘችው አንዱ መለኪያ ትክክለኛውን ቁልፍ መታ አድርጋ አሳየችኝና......በሩ ላይ የተንጠለጠለውን ጉዋጉንቸር መዳፌ መሃል አስተኝቼ ቁልፉን አስገባሁ::

ቾኮል ባለ ድምፅ:

«ቶሎ ገባልህ?» አለችኝ

«አዎ»

«በደንብ ከተትከው?» አለች

«አዎ»

«በደንብ አዙረው»

«ይኼው ከፈትኩት» አልኩና ቀና ብዬ በመገረም አየኋት:: ቀድማኝ እንድትገባ በሩን ወደ ውስጥ ገፋ አድርጌ ያዝኩላት:: ፈገግ እያለች ገብታ ብርጭቆ በያዘችበት ቀኝ እጇ መጻፍ ግድግዳ መታች:: በቆሻሻ ውሃ ቆቃ ተለቅልቆ የመጣ ምጥን ሽሮ የመሰለ ብርሃን በራ:: ወይም ሰልቫጅ ብርሃን፣ ሌላ ከተማ የሆነ ሕዝብ ወደ አንድ ዲታ አገልግሎ ወደዚህ የተመራ:: ያኔውኑ የሽቶ ጠረን አፍንጫዬን መታኝ:: በዚህ ዓይነት መጠን ስፋትና ሐይል ሽቶ ሽቶኝ አያውቅም:: የቆሻሻ ብርሃን ጠረን ነገር:: ጭንቅላቴ በር እንዳለው ሁሉ በሽቶው መዐዛ ተከፈተ:: አናቴ መሃል ላይ ቀዳዳ ነገር የተሰራ መሰለኝ:: ዛሬ አንዳንዴ ደብዛዛ አርባ ቁጥር ሻማ አምፖል ሲያጋጥመኝ አልማዚና እንደ ለስላሳ ዘንግ በጉሮሮና በትናጋ የሚሰነቀር ሽቶ ትዝ ይለኛል::

መኝታ ቤቷ ጠባብ ብትሆንም ሁሉ ነገር ያለባት ትመስላለች:: በስተግራ ጥግ ለጉዞ እንደምትዘጋጅ ሁሉ ሶስት ጥቁዋቁር ሻንጣዎች ተረባርበው ተቆልለዋል:: ከእነሱ ጎን ትልቅ የፊት መስታወት ያላት መጠነኛ ቢፌ አለች:: ይህቺ በቅባት፣ በሽቶ፣ በሚዶ (ላስቲክ...... እንጨት......ብረት)፣ በተዘረገፉ ፀጉር ማስያዣዎች፣ የተለያየ ቀለም ባላቸው ቦጎዲዎች፣ በተበተኑ ዝርዝር ሳንቲሞች፣ ባረጁ የእጅ ቦርሳዎች ተሞልታለች:: ከቢፌው ጎን የእንጨት ወንበር አለች:: እንጨት ወንበሯ ፒጃማ፣ ቀሚስ፣ ሻሽ፣ ፎጣና ሌላ ሌላ ዓይነት ጨርቃ ጨርቆች ተሸክማለች:: በአልጋውና በቢፌው መሃል ባዶ ቦታ አለ:: እዚህ ባዶ ቦታ ላይ አንድ እግር ነጠላ ጫማ አያለሁ:: አልጋዋ ትልቅ ነው:: በቀይ የጥልፍ ስራ ተሸፍኖአል:: ግድግዳው ከላይ እስከ ታች በፎቶዎችና በፖስተሮች ሞልቷል:: ፎቶ ያሊለበት መደብ ውሃ አረንጉዋዴ ቀለም አለው:: ይሄ አረንጓዴ ከተቀጠፈ ሶስት ቀን የሆነው የጠወለገ ሰላጣ ያስታውሳል:: አራት ትራሶች ቦታቸውን ለቀው አልጋው ላይ በየቦታው ተወርውረዋል:: ከአልጋው ትራስጌ ትንሽ መሳቢያ ያላት በዘይት የታሸች የመሰለች የእንጨት ጠረጴዛ አለች:: በስተቀኝ በአልጋው ግርጌና በግድግዳው መሃል ረዥም የልብስ ቁምሳጥን አለ::

ብራንዲያችንን ራስጌ ያለው ኮመዲኖ ላይ አስቀመጠች:: እኔ ግራ በተጋባ ሁኔታ የምቀመጥበትን ቦታ ስመርጥ አልፋኝ ሄዳ በር ዘጋች::

«ተቀመጥ»

የቀረው ልቀመጥበት የምችለው ነገር አልጋው ነው:: አልጋው ደሞ ሌላ ነገር አሳሰበኝ:: አልፋኝ ሄዳ የራሷን ብራንዲ አነሳችና አልጋው ዳር ተቀመጠች:: አንድ እግሯን ሌላ እግሯ ላይ አነባብራ አተኩራ አየችኝ:: ጥያቄዋን መፈፀም ነበረብኝ::

«ብራንዲ እኮ እስከዚህ አልወድም» አለች

«ለምን ትጠጪያለሽ?»

«ና ተቀመጥ መጀመሪያ:: ለምን ትፈራኛለህ? አልባላም»

«እኔ? እኔ አንቺን እፈራለሁ?»

መለኪያ ባልያዘ እጇ አልጋውን መታ መታ አደረገች፣ ጎንዋ እንድቀመጥ:: እጇ የመታው ቦታ መጎድጎዱ ሳይሆን ለእሷ ጭን የነበረው ቅርበት ረበሸኝ:: ቶሎ ተቀመጥኩ ('ይሄው ፈራኸኝ አይደል' እንዳትለኝ):: ፈገግ አለች:: ነቃች? ቸርነት አለ ነገር 'ሱፐር ሹሼ' አላላትም:: ከዚህ በሁዋላስ? (እያንዳንድዋ ያልተያያዘች ብቻዋን የተፈጠረች የመሰለች ድርጊቷ በትልቅ አጀንዳ የተሳሰረች መሆኑ የገባኝ ከርሞ ነው) እንደ ተቀመጥኩ በነዚያ አፍዛዥ ቡናማ ዓይኖቿ (አይተውኝ የማያወቁ ይመስላሉ) ፊቴን ከፍ ዝቅ አድርጋ አይታ......

«ጋራህ ያምራል» አለች

«ምን?»

«ፀጉርህ ያምራል»

«እ......ሁልጊዜም ትያለሽ ማዋስ አልችልም፣ ብራንዲ ካልፈለግሽ ታዲያ ምን መጠጣት ትፈልጊያለሽ?»

«ቢራሪት»

«ንገሪያቸው ያምጡልሻ»

«ተወው አይገፋኝም ብራንዲ»

ይሄን ብላ የያዘችውን ብራንዲ(የእኔን መጠጣት ረስቼአለሁ) ሰጠችኝና ጎንበስ ብላ......

«ይሄ ጫማ ገመዱ ይገለኛል......ሲያጌጡ ይመላለጡ» አለች ጎንበስ ብላ እየፈታች::

ተረትና ምሳሌ እንደምጠላ ምን ብዬ ልንገራት? ከማጠሩ ከዕውነት መራቁ:: አስፈቶ የሚያስብ ላጥብበው ሲል የዘባርቀው ሁሉ ይመስለኛል:: የጋቢ ቲሸርት::

ከዛ:

«ግን ያምራል» አለች::

ጥፍሮቻቸው በእንሶስላ የጠየሙ እግሮቿን ከጫማዎቹ አወጣችና (ያስፈራኛል እንሶስላ) እያንቃነቀች እያዝናናች አየቻቸው:: ዓይኖቼ ወደ ላይ ማተሩ:: ቀሚሷ እየተሰበሰበ ጠቃጠቆ የመሰለ ነገር ያለባቸው ከፊቷ የቀሉ ቀይ ጭኖቿን አየሁ:: ሰባት ከተሞች (ድሬዳዋ፣ ናዝሬት፣ ሐረር፣ ደብረዘይት፣ አቃቂ፣ ሞጆ፣ አዲስአባ) አልፎ የመጣ ጭን እንዲህ ይለሰልሳል? ልምምድ ድክመት ይለግሳል ወይስ ውበት? አንዳንዴ ጨዋታ መሃል 'ብዙ አየሁ' ብላ ስትናገር የሆነ አተነፋፈስ ነበራት ሽክም እንደጣለች: ሁሁሁሁሁ:: ምን ማየቷን ባታብራራም:: እንገምታለን ከአሁን ሙያዋ ተነስተን ሁሁሁሁሁ ያሰኛትን:: ዕውቀቷ ግን ከማየው ዓይንዋ የሚያልፍ የመሰለ ነበር:: የጥልቀቱን ቅርፅ አይ ነበር:: የሚያሰምጥ ውሃ ይሁን የሚያፍን አየር ሳላውቅ:: መ'ደበር ዕውቀት ሊሆን አይችልም? አደባበር......ለመ'ደበር መድረስ? አንዳንዴ 'ታማለች' 'ታማ ተኝታለች' ሲባል ሕመምዋ የሚመዘምዝ፣ የሚቆረጥም፣ የሚቆርጥ ያ ብዙ ብዙ ዕውቀት ነበር?

«ሲጋራ አለህ?» አለችና ሁለት እግሮቿን ገጥማ ሰብስባ ወደ ሁዋላ ዘለል ብላ አልጋ ላይ ሙሉ በሙሉ ወጣች::

እንደ ተጋደመች ሲጋራዋን ለኮሰኩላት::

«መተርኮሻ መሬት ላይ አለ» አለች:: አይኖቿን ሳትገልጥ እኔም መሬት መሬት ሳይ::

«ጃኬትህን አታወልቀውም?» አለች ቀጠለችና:: የጃኬቱን ጉዳይ እንዳልሰማሁዋት ሁሉ ከወለል ላይ ትንሽ ወደ አልጋ ስር ገባ ብሎ የተቀመጠ የመስታወት መተርኮሻ አነሳሁ:: መተርኮሻውን እንደ ልዩ ዕቃ ማየት ቀጠልኩ:: ከመተርኮሻው መሃል ላይ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ አርማ አለ:: የጊዮርጊስ ፊት በእሳት ተቃጥሎአል:: ጊዮርጊስ በጦሩ የሚወጋው ዘንዶ ጅራቱ የለም:: መተርኮሻውን ጠረጴዛዋ ላይ በቀስታ አስቀመጥኩ:: የአልማዝ አንድ እግሯ በሸሚዜና በጃኬቴ ስር በቀስታ ተስቦ መጣ::

«ዊንስተን እወጻለሁ» አልኳት

አልመለሰችልኝም:: እግሯ ወደ ብብቴ መጣ:: ፊቷን ሳላይ......

«እግርሽ......ኮረኮረኝ» አልኳት:: አልኮረኮረኝም::

«እየኝ እስኪ» አለች በቀስታ ሳቅ ባፈናቸው ሁለት ቃላት::

ቀና ስል የሲጋራ ጉም ፊቴ ላይ ተደፋ:: ያደረገችበት ምክንያት ባይገለፅልኝም ለመሳቅ ሞከርኩ:: ሲጋራው ጢስ ውስጥ ለስስ ያለ የሽቶ ጠረን አለ:: ልክ ኢ.ሴ.ኒ. ሲጋራ እንደ ማጤስ:: እሷን ሳላይ በእጄ ጉም

ሳባርር ሌላ እግሯ በጀርባዬ አለፈ:: ወደ ቀኝ ዞር ብዬ አየሁ:: ጭኖቿ ግራና ቀኝ ተከፍተው......ስቤ በአፌ የያዝኩት የሲጋራ ጢስ አሳለኝ::

«ሮዝማን ነው የምወደው» አለች

የተረጋጋሁ ብመስልም በአእምሮዬ የመዘገብኩትን ቀይ ዳማ ጭንቀን ፎቶ ሳላቋርጥ አያለሁ:: ከዚያ ወዲያ ስላለው ስለማላውቀው ነገር አስባለሁ:: የማላውቀውን ነገር እያሰብኩ ከተባረኪ ጋር አነፃፅራለሁ:: ሁለት የማይታወቁ ነገሮች እንዴት ይነፃፀራሉ?

በጭኖቿ እንደ አቀፈችኝ ተንጠራርታ ተነስታ ከጠረጴዛው ላይ የነበረውን መተርኮሻ ወደ እኔ አስጠጋችና ያላለቀ ሲጋራዬን እንዳስቀምጥ ጋበዘችኝ: ሲጋራውን ሳላጠፋ አጋደምኩት:: ልክ ከረሜላ ስትመጥ እንደ ነበረች ሁሉ አፏን እያጣጣመች የራሷን ተረኮሰች::

«ጃኬትህን አታወልቅም?» አለች

«ልክ ነሽ ይሞቃል አይደል......በተለይ ቤት ውስጥ ስትሆኚ»

«አዎ»

«እም»

ጃኬቴን ለማውለቅ ወደ ሁዋላ ስስብ ቀና ብላ አንገቴን አቀፈችኝ:: መልሼ እንዳልለብሰው በግራ ክንድዋ መጋፊያዎቼ መሃል ግድብ ሰርታለች:: ለመከራከር አፌን ስከፈት አፌን በአፏ ከድና ለሰከንዶች ያህል መተንፈስ ከለከለችኝ:: ከማጤሰው ትንባሆ የበለጠ ክብደት ያለው የትንባሆ ጠረን የለበሰ የሚፋጅ ምላስ ትናጋዬን ነክቶ ተመለሰ:: የምታነቅ መስሎኝ ነበር:: ፍጥነቱ የሚገርምና የሚያስደንቅ ነው:: ይሄ ሁሉ ዕውቀቷ የእኔ መሀይምነት ነው......ፊቴን እዛ እዛ አፏ እየዘለለ ሳመኝ::

«የእኔ ኮርማ በዚህ ጨለሚታ......» ወደ ሁዋላዋ አልጋ ላይ እየወደቀች በቀኝ እጇ ማብሪያና ማጥፊያ መታች:: በጨለማ ጃኬቴን ስባ አወለቀች:: አናቴ ውስጥ እሳት ተለኩሶአል:: አንጎሌ ወደ አዙዋሪት ውስጥ እየወረደ ነው:: የሚመስጥና የሚያስፈራ ጨለማ:: የተሰጠኝን አጠቃላይ አመራር በስርዓት ተከትልኳት:: ገላዋ የሚሞቅ የሸቶ ኩሬ:: ፊቴ ላይ የዕጣንና የብርጉድ በር:: ገንትና ሲያል እንደ ተምታታብኝ:: ራቁቴን አልጋ ላይ ስወደቅ ወደ እግሮቿ መሃል ሳበችኝ:: በእጆቿ ደባብሳ ከአፏ ተኩስ ፊቴ ላይ እንደ መሃረብ የሚወድቅ ትኩስ ነፋስ እየደፋች እንደገና በማይገባኝ ቋንቋዋ እየተንተባተበች......

«አትያ ጎሜ የእኔ ፍርር ውስጥ» አለች

ፈራሁዋት:: ግን መላቀቅ እንደማልችል አውቃለሁ:: በወሬ እንደ ሰማሁት የሚመች ሙቀት ነው:: እዚህ ከመድረሴ በፊት ሐጢያተኛ

ነበርኩ:: ርጥብ አፏ ደረቴን ያጥባል:: ደረቴን ትነክሳለች:: የሚያምና የሚመስጥ::

«በዚህች ጨለሚታ የእኔ አንበሳ እዚህ ጣሩጪት......በዚህ ጨለሚታ የእኔ ፋርዳ ጮሪት እስክትወጣ......ሰባ ጊዜ ሰባ ጊዜ ሰባ ሰባት» የታመመችኝም መሰለኝ:: አልጋው ልቆጣጠረው በማልችል መፈራገጥ ተሞላ::

ትላልቅ ጭኖቿ መሃል......ግን አጠር ያሉ......በሰባት ከተሞች ንትርክ የጠነከሩ......እነዚህ ሁሉ ከተሞች ባለፉበት......ሁለመናዬ እየተቀጣጠለ በአስራ ስድስት ዓመት ጉልበቴ ተወረወርኩ......

«ባስ ማ አብ......እ»

በሚያምር መልክ፣ የትኛውንም አይነት ሙዚቃ መርታት የሚችል ከሰው ላንቃ ሊወጣ ያልመሰለ *ባ ስ መ አብብ* ነው:: ቴስ እንኳዋን እንዲህ ሲጠራው አልሰማሁም:: ከተለመደው አነባብ ውጭ የመጀመሪያዋ 'በ' 'ባ' ተብላ የተጠራችበት የከናፈርት ጥብቀት፣ 'ስ' የተጠራችበት የጥርስ ፉጨት 'ማ' የተዘየረችበት የምንጭርና ለምቦጭ የተጠበበ ውሁድ-ነት፣ ሁለቱ ሆሄያት 'አ' እና 'ብ' ተደርበው የተጠሩበት በፈሳሽ የታጀበ ምጧ:: ድምፀ መልካሙ እዝራ እንኳን እንደዛ አልቀረፀውም:: አዲስ የአምላክ ስም ይመስላል፣ በቅርብ ኢትዮጵያ የገባ:: በሆነ መልክ በሆነ በተጣመመ ትርጉም ድርጊቴን መለኮታዊ ያደረገችው መሰለኝ:: ወይ ስትፎግረኝ ነው? የእኔ አብሮኝ የተወለደው ሰለሞን ('ሰለሞን' ነበር የምለው እንትኔን) ከመፅሃፍ ቅዱሱ ሰለሞን የበለጠ ተጠባቢ መሰለኝ:: ተሰልቤው ሚዳ ቢወድቅ እንኳን እየዳኸ ተነስቶ መጽሐፍ ምሳሌን የሚፅፍ:: የተንዠረገገ ፍሬው ስኩዋኑና መረቁ ያልተነካ:: ይሄ ዝየራዋ ከቀኝ አንጎሌ ኪነትና ኪነቶች ከሚዘፈዘፉበት፣ ጥንቆላና ሃይማኖት ከተከበረበት፣ ሰይጣንና መላዕክት ከሚንፈላሰሱበት ግራጫ ስብ ውስጥ ተጠብሶ ቀረ::

*

በተባወዘ ሕመምና በደስታ እንቀጠቀጣለሁ:: ጥርሶቼ አልፎ አልፎ ይንቀጫቀጫሉ:: በተከናነብኩት ብርድ ልብስ ስር አጮልቄ አያታለሁ...... ፍርሃቴ ወደ ሚተንበት ተኖ፣ ብዙ የሚወራለት ነገር ቀሎ ሳገኘው፣ ግን የሆነ ውበት ነበረው፣ ትንሽ የቆሸሸ:: በልጅነት መረቂ ረጥባ በጨለማ ተነስታ ከእኔ በእጥፍ ያረጀ ራቁት ገላዋን እንዳናወዛት ሁሉ እያንጎራ ደደች......በየወለሉ የረገፉ ልብሶቻችንን ስታነሳ:: እንደ እንጉርጉሮ ነገር፣ ልጅ እያለች ታረገው እንደ ነበር ጨረቃ ድምቡለቃዋን......ድምፅዋ ሳዱላ ነበረው:: ለአፍታ ኮስታራ ባልና ሚስት የምንጫወት መሰለኝ......

ተመልሳ ወደ አልጋዋ መጥታ ሚስጥሬ ተገልጦላት፣ ሁለመናው የረገበ ገላዬን እንዳይበርደው ቀስ አድርጋ ኩታ እላዬ ላይ ስትጥል......የሆነ ውበት ነበረው ከዛ ስር ገብታ ከጀርባዬ አቅፋኝ በማጅራቴ በኩል ተሰባ አፏን ወደ ጆሮዬ አስጠግታ 'አይዞህ እንዲህ አልመሰለኝም' ስትለኝ:: 'አይዞህ እንዲህ አልመሰለኝም' ባዘነ ድምፅ ደጋግማ ስትለኝ የሆድዋን ንቅናቄና ሙቀት ጀርባዬ ላይ በከፊል እየሰማሁ......ወንድነቴን አደጋ እንዳይደርስበት ገና እንደ ተወለደ ቡችላ በእጇ እንደመከታ ይዛው......ፊቷን ፀጉሬ ውስጥ እያስገባችና እያስወጣች (ተባረኪ እንደምታደርገው) ትከሻዬን በቀስታ ስትስመኝ......በከፊል እንቅልፍ፣ ሕመምና ጣዕም ወደ ተደበላለቁበት ሰመመን ገባሁ::

......ስባንን፣ በሙቅ እንደ ተነከረ ወረቀት የተጣበቀችበት ጀርባዬን አልቦኛል:: ግራ እጇ እግሮቼ መሃል እንዳረፈ ነው:: ምኞቱን ሳዳምጥ ቆየሁና የተኛች መስሎኝ በቀስታ ግራ እጄን ከብርድልብስ ስር አውጥቼ ሰዓቴን በጨለማ አየሁ:: ከምሽቱ አራት ሰዓት:: አንጎሌ የተከፈተ መሰለኝ:: በጨለማ የማይ መሰለኝ:: መንቃቴን እንዳወቀች ከጀርባዬ አንገቴ ላይ ሆና......

«ወላ ሴት የምታውቅ መስሎኝ ነበር»

ዝም አልኳት

«ወላ ሽርሙጣ ስለ ሆንኩ ብቻ የፈራኸኝ መስሎኝ ነበር»

ራሴን በአሉታ ነቀነቅሁ::

«አይዞህ......አመመህ?»

«ትንሽ»

አጥብቃ አቀፈችኝ:: ከጀርባዬ እንድትነሳ አልፈለግሁም:: የሆነ ልሰይመው የማልችል ፍርሃት ተሰማኝ:: ቤቴ ቶሎ መግባትም አለብኝ:: ጊዜው ሰላም ስላልሆነ ወላጆች ሁሉ ልጆቻቸው ላይ በቶሎ እንዲገቡ የሚጮሁበት ሰዓት ነው:: ሮዛን የመሰለች ቆንጂት የወለደችው ይኼ ልጅ ጠጅ ሳርና ሂና ከምትቀባ በብርጉድ ጉም ከተከበበች ቂጠ--ዝቋላ ሽርሙጣ ጋር......

«ቤት ልሂድ» አልኳት:: አልመለሰችልኝም

ባልነሳ ደስ ይለኛል......በሆቴሉ በኩል መሄድ ደበረኝ፣ ፈራሁ:: እዚህ የተኛንበት ቦታ ምናለበት ከሆቴሉ እጅግ ቢነጠል:: በእርኩሰት የጀመርኩ መሰለኝ:: ማንም የሚያወግዘውን (እኔን ጨምሮ) ትክክል ያልሆነ ነገር እንዳደረግሁ......

«አንድ ነገር ልጠይቅሽ?»

«ምን?»

«ዛሬ ያደረግነውን ነገር ለማንም አትነግሪም?»

ክትክት ብላ ሳቀች:: መጋሬያዬ ላይ ሳም ሳም አደረገችኝ::

«ሂሂሂሂ በቃ መጀመሪያ ውል እናድርግ» አለች

«የምን ውል?»

«በየወሩ እዚህ ትመጣለህ»

«እንዴት?»

«በየወሩ ከእኔ ጋር ትተኛለህ»

«ገንዘብ ከየት አገኛለሁ?»

«ገንዘብ ትከፍላለህ አልኩህ?»

«እሺ ምን ቸገረኝ» ሳቅ አለች:: ሳም ሳም:: መብራት በራ

«እንካ» አለች

«ምን?» የግራ እጇን ትንሽ ጣት ቀስራ ከብርድ ልብስ ስር አወጣች

«እንዲህ ነው የምታደርጉት አይደል» ብርድ ልብስ ከላዬ ገፍፌ ቁጭ አልኩና ትንንሽ ጣቶቻችንን አቆላለፍን::

«እንኳን ይሄ ዳዊት ይደገማል» አለችና እጇን መልሳ እግሮቼ መሃል አስቀመጠች.............................................

ልብሴን ለብሼ ተነሳሁ:: ባለዚፕ ቆዳ ጫማዬን እየዘጋሁ ካለሁበት እንዴት እንደምወጣ አሰባለሁ::

«እኔ እወጣና ዙሪያውን ሰልዬ በር ሳንኳኳልህ ቀስ ብለህ ትወጣለህ» አለች:: አእምሮዬን አነበበች? ወይስ ዕውቀቷ የሰጣት ንቃት? ፈራሁዋት:: በውስጥ ሱሪ ብቻ ወዲያ ወዲህ አለች:: ቁመናዋን ልታሳየኝ እንደሆነ እንጃ:: ጫማዋ ላይ ቆማ ክፍሉን በመኖሯ ሞላችው:: ጨርቅ የለበስኩ ትንሽ ነገር የሆንኩ መሰለኝ:: በግዙፍ ቂጥዋ ሽለቆ የተነከሰ ጠባብ ሙታንታዋ? ግዙፍ የቡና ፍሬ መስሎ የማየው አፍረቷ:: ያለፍኩት ወጣ ገባ ሁሉ ይሄ ነው? ነጠላዋን ተከናነበችና ፀጉሯን በመስታወት አስተካከላ በር ከፍታ እውጭ ቆመች:: ተመልሳ ገባች::

«ሰው አለ በወዲያ በኩል፣ የሰፈር ሰው ሊሆን ይችላል ስትወጣ ያይሃል»

ወንበር ሳበችና የተሸከመው ጨርቅ ላይ ተቀመጠች:: አተኩራ አየችኝ:: ኮስተር ባለ ድምፅ የሚሰማን ሰው አጠገባችን እንዳለ ሁሉ::

«በዚህ በኩል ሂድ......በቀኝ በኩል ይቀርብሃል አይደል?»

'አዎ' ለማለት አፈርኩ::

ተነስታ ወደ በሩ ሄደችና ተመልሳ መጣች::

«አልሄዱም:: ቆመው ያወራሉ» አለችና ወደ ሲጋራው መተርኮሻ አየች::

«ሌላ ሲጋራ አለህ?» አለች

የሲጋራ ፓኮውን ከጃኬቴ ኪስ ፈልጌ አውጥቼ ስሰጣት እጄን ያዘችኝ:: በሩን አየሁ::

«ካለ እኔ በስተቀር እዚህ የሚገባ የለም» ሲጋራዋን በከንፈሮቿ ነክሳ ጎኔ ተቀመጠች:: ለኮስኩላት:

«እሺ ቃልህን ባትጠብቅስ?» አለች ሳቅ ብላ

«እንዴት?»

«ብትረሳኛ፣ ባትመጣ»

«ቢራ እቀጣለሁ»

«አንተ ከቢራ እኩል ነህ?»

«ምን ላድርግ?»

«እኔ እቀጣሃለሁ በፈለግሁት»

«በምን?»

«አይቀጡ ቅጣት»

«ምን?»

«የራሴ የፍየል ወጠጤ አለኝ» ሳቅ ብላ አየችኝ

«ማን ይፈራል»

«ትወደኛለህ?»

«እ»

«ማለቴ ደስ እልሃለሁ?»

ዘገየሁ ለመመለስ

«አዎ»

«አትዋሸኝ»

«ደስ ትያለሽ......» አልኳት (የጥርሷን ዘርዘራነት---በደንብ ልሳቅ ስትል ፈገግታዋን ከሽሉ ገሎ የሚጥለውን፣ ወይም የአንገቷን ማጠር፣ የሚያስጠላ አንዳንዴ የምትሰራው ቀጭን ጉንጉኗን፣ የተደሰተች ለመምሰል የውሸት ስትስቅ፣ ገመድ የበዛው ገብረክርስቶስ ጫማዋ......ይኼን ይኼን አልነገርኳትም)

«ቢቃ?»

«ፀጉርሽ»

«ቢቃ?»

«እ»

«ተው አላስቸግርህም:: ልምከርህ? ምን መሰለህ ለሴት ከፈለግሃት በደንብ ዋሻት:: ሴት ውሸት ትወዳለች:: 'ከማንም ትበልጫለሽ' በላት:: እውነትና እንትን አይገናኙም:: ዛሬ ሕይወቴ እዚህ የደረሰው በመጀመሪያ ስለ ተደለልኩ ነው:: ቆይቶ ግን ገባኝ:: ቢሆንም ወንዶች በፈጠሩት የራሳቸው ወሬ ቆንጆ ተብዬ ወንድ አደባድቤአለሁ:: ስንት ከእኔ የሚያምሩ ሴቶች ነበሯቸው በየቤታቸው? ወንድ አበጀኝ፣ ወንድ ተደባደበብኝ......ሂሂሂ አያስቅም?»

ዝም

«አባትህ እዚህ መሆንህን ቢያውቅ መከራ ነው የማየው»

«እ»

«ስፈራችን አንጎል የለውም፣ ባይገባውም ያድማል»

«ጠባብ ስፈር ናት»

«የሰው እንጂ የስፈር ጠባብ የለውም»

«ስፈር ስለሚጠብ ነው አንጎል የሚጠበው»

«ሰባት ከተሞች ነበርኩ ነግሬአችሁዋለሁ አይደል......ከተወሰነ ዕድሜህ በሁዋላ ሁሉ አንድ ነው......አዲስ ዕውቀት የለም:: ላንተ አዲስ ነኝ ለእኔ ግን አይደለህም»

«የምትደበሪው ለዚህ ነው?»

ራሴን ዳበሰችኝ

«ገና አስራ ሰባት አልሞላህም......ስለ መደበር አታስብ......ቃሉንም ማወቅ አያስፈልግም......የድብርት ጊዜማ ይመጣል አይቀርም......ግን ሲደብርህ እኔ ጋ ና:: አንተም ደስ ይልሃል......እኔንም ልጅ ታደርጋለህ ሂሂሂ:: ዕዳህን ትምህርትህን ስትጨርስ ትከፍላለህ»

አየሁዋት

«ዕውነቴን መስለሁ ደነገጥክ? ቆይ ልይልህ......»

ከክፍሏ ወጣች:: በረንዳ ላይ ቆማ ስታጤስና ስትተነፍስ እሰማታለሁ:: በር በረገደችና:

«ና አሁን ቶሎ»

በፍጥነት ተነሳሁና በሩን ሰፋ አድርጌ ገፍቼ ዞር ብዬም ሳላያት ወደ ቀኝ ታጥፌ ጨለማው ባሕር ገባሁ:: በኮረኮንች ላይ እየተደነቃቀፍኩ ስሮጥ......

ጆሮዬ ላይ የቢሊ ጁልን ፒያኖ ማን የሰማሁ መሰለኝ::

ግራ ገብቶኝ ቆም አልኩ::

*ያለምንም ደም ኢትዮጵያ*......ይሄ መዝሙር አየር ሃይሎች የሰሩት ቅመም ነበር ከኤፍ ፋይቭና ከበርበሬ የተሰራ::

ዋናው መንገድ ስገባ ታች እሚታየኝ የበረንዳው መብራት በቅሎች የተከበበ ቤት ሳላቋርጥ እየሮጥኩ መግባት ፈለኩ:: የተማርኳትን ትንሽ ሂሳብ ተባረኪ መደብ ላይ ለመፃፍ......ጎድርግ ብል ያቺ ሚጥሚጣ ትሞጣመጥ ይሆን?

ሳቅሁ......

# የጓሮ በርበሬ

አባቴ ደብረዘይት ከእናቴ ጋር ዊክ ኤንድ[14] ወርዶአል:: የቴቢ እናት ትደነቂ ያለሽም ከአቶ አባይነህ ጋር የሚሄዱበት ቦታ ሄደዋል:: ሰፈር በእኔና በተባሪኪ ቁጥጥር ስር ናት:: ወላጆቻችን እኛን መፈተኛ ያቀናበሩት መሰናክል ይሁን አይገባኝም:: ማታ ላይ ተባረኪ ጋ ቆይቼ ለመተኛት ቤቴ ስመለስ የአጥሬን በር እያንኳኳሁ ፀሐይ እንድትከፍትልኝ አጠብቃለሁ:: ለስለስ ያለ የሚበርድ ካፊያ ይወርዳል:: አይኖቼን ብጨፍንና ባተኩር ፊቴ ላይ የሚያርፉትን ነጠብጣቦች መቁጠር የምችል ይመስለኛል:: ቴቤ ጋ እያለሁ በሰበሰብኩት ትኩሳት ገላዬ ግሎ እንደሆነ ይገባኛል:: *እስከ መቼ?* አልኩ:: *እስከ መቼ?* ከገላዬ ትኩሳት የተለየ እሳት ከውስጤ እንደ ቀላል ገሞራ ሲነሳ ተሰማኝ:: የቤቴን በር ማንኳኳት ትቼ ተመልሼ ወደ ተባረኪ ቤት መሮጥ ጀመርኩ:: እሷም እኔን ሽንታ የአጥር በሩን ዘግታ ምናልባት ገና ሳሎን ማረፏ ነበር:: በር አንኳኩቼ የአጥሩን በር ከፍታልኝ ገና 'ምነው ተመለስክ?' ብላ ስትጠይቀኝ በሩን ቶሎ በእግሬ ዘጋሁና ምንም ሳልናገር ዓይኖቼን ጨፍኜ አቀፍኳት:: ካፊያ መሃል ቆመን አንገት ለአንገት ተያይዘን ነበር:: ውሐ የተመተመው የተልፈሰፈሰ ፀጉሯ ግንባሯ ላይ ተጣብቆ......ፊቶቻችን ከውስጣችን በሚወጣ እርጥበትና ከሰማይ በሚወርድ ማይ ረጥበው:: እየተንገዳገድን፣ እየተያያዝን፣ እየተላቀቅን ሳሎን ገባን:: ያን የተረገመ ሶፋ ስተን እንደ መንታ አሶች ወለል ላይ እያብለጨለጭን አረፍን:: ያቺ ከአልማዝ በለቃቀምኳት ትንሽ ሰውቀቴ፣ አፍረቴን ከነሐጢያቴ እየዋጥኩ፣ ከሃዲነቴንም፣ እዚህች ጎረቤቴ፣ እዚህች እህቴ፣ እዚህች ፍቅረኛዬ፣ እዚህች አብሮ አደጌ ውስጥ ሳርፍ፣ በትኩሳቷ ስነከስ፣ በድልኳ ስላስ ከእኔም ከእሷም አፍ የወጣው ዘፈን፣ የሆነ ጣት ያለው ዝማሬ፣ አውቃለሁ በረቂቅነቱ ጤፍ እንደሚጠረጥር......

ሁሉ ቶሎ አልቆ የተበታተኑ ልብሶቻችን ላይ በጀርባችን ፈዘን እንደተኛን ደረቴ ላይ ፊቷን አሳርፋ......ቋጠሮውን ሰብሮ የተበተነ

---

[14] ቅዳሜና እሁድ(weekend)

እርጥብ ከርዳዳ ፀጉሯ ውስጥ ፊቴን ቀብሬ፣ የላቧን ጎምዛዛነት እየመገመግሁ ራሴን አልኩት፡ *ዓላዛር ወደድክ*......

እዛ ሰርከ ሶፋ ላይ ተቀምጠን የምናየው እንደ ፈሪ ግድግዳ ተደግፎ የሚታዘበን የመሰለ ቲቪ......እዛ ዳንቴል የለበስ በቀለም የተሰራ ሞሰብ (ዳንቴሉ ወደ ጀርባ ተንሸራቷል--አልረሳም)......ደ'ሞ እዛ ግድግዳ ላይ እናቷ፣ አባቷ ዘርዓይ ሌሎችም *የቤተዘመዱ ይታያል ፊቱ* በሰልፍ የተደረደሩ አራት ሰዎች የተነሱት ፎቶ......

ከባሎኒ ጡቶቿ......የፍቅርን መረቅ ጠባሁ......የለጋ ገላዋ ሴትነት...... የዕጣንዋ እረግረግ አስከሮኝ......በደከመ ልብ......በሚንገዳገድ ምላስ...... አልኳት የጓሮዬን በርበሬ.....የእኔን ቴቢ......የእኔን ሀ፡

«ቴቢሽ እወድሻለሁ»

ዐይኖቿን እንደከደነች በዝምታ አጥብቃ አቀፈችኝ::

*

ለአንዲት ቀን እሷን አለማየት እንደ አንድ ዓመት ሲረዝምብኝ:: ልጠግባት አልቻልኩም:: በእንጀራ ወጥ አልተካት ነገር እሷን:: ሰው በተሰበሰበበት በዜሮ እፍረት (የአፍረት ደረጃዎች ከዜሮ እስከ አስር ናቸው፤ አስር ድብን ያለ ዐይን አውጣነት ነው) ማንም ሳያይ እጇን ስይዘው ሁለመናዬ ሲንቀጠቀጥ::

እኔ ቤት ሰው ካለ ('እሷ ቤት ለማጥናት እንሄድ' ብለን) እሷ ቤት ሰው ካለ('እኔ ቤት ለማጥናት እንሂድ' ብለን):: በየቴፖቻችን *ቢ ጂስን፣ ሳጣን* እና በእሷ ግፊት *አሰፋ ተሰማን* እናዳምጣለን (የማይገባኝ ዘፋኝ) እንዲህ እያለ ያስቀኝ ነበር ይሄ አሰፋ የሚሉት፡

*ቱጭ ብዬ ግራዋ፣ ቆሜ ክሰ ጠማሁ*

('ማን ጠጣ አለው?' 'ማን ቆመህ ጠጣ አለው?' ምናምን እያልኩ ቴቢን ሳበሽቃት:: እንደ አውሬ ጥሬ ስጋ ይበሉና እንጀታቸው ውስጥ የትል ኪንደር ጋርተን ይሰራሉ)

*ምን ያለው አሞራ ከዛፍ ይሙዋገታል*

('ይታይሽ አሞራ ከዛፍ ጋር ቶክ[15] ሲያደርግ')

*ጠይሙ ጎፈሬ ሸዋ ላይ ነው ቤቱ*

('እንደ አይዛክ ሄይስ ለምን ኒውዮርክ አይኖርም?' 'ለምን ጠይሙ ባለአፍሮ ዋሽንግተን ቤቱ አይልም?' 'ይታይሽ አይዛክ ሄይስ የሸዋ ሰው

[15] ሲያወራ

ቢሆን? እ? ደስ አይልም? ሂሂሂሂ' በተረቤም ተበሳጭታ ለቅጣት ፀጉሬን ስትጎትተኝ......እኔ ፊቴን ረቂቅ ጠይም ጡቶቿ መሃል ደግኜ የደፋሁት ወዜን ስሰበስብ......)

ብዙ ጊዜ ከምሽቱ አንድ ሰዓት በኋላ ታዚና ሆቴል ካሉት አልቤርጎዎች የሰፈር ሰው እንዳያየን በጀርባ ገብተን በጀርባ የምንወጣበት የተመቸ ክፍል እንይዛለን:: እዝራ 'የዓላዛር መጎናፀፊያ' ብሎ እኔ ብቻ እንድጠቀምበት አግልሎ ያስቀመጠው አንሶላና ብርድ ልብስ ላይ የልጅነታችንን ገብጋባ በሮች እንከፍታለን:: ሆቴሉ ጀርባ በፍቅርና በስጋ ጉዳይ ተቀጣጥለው ከተከፈቱ ቀዳዳዎቻችን ጢስ እየወጣ......እዝራና አስተናጋጁ ጌታቸውን አዳምጣቸው ነበር ሲያወሩ--ሊደብቁት የሚጥሩት ድምፅ በመስኮትና በበር ቀዳዳ እያመለጣቸው:

ጌቾ: 'ሁለት ሰዎች ለአጭር ጊዜ አልጋ ፈልገው መለስኩ:: ዓላዛርን ውጣ ልበለው?'

እዝራ: 'በራሱ ከወጣ ይውጣ:: ቢሰማንስ እዚህ ጋ የምትጠይቀኝ?'

ከውጭ ጨለማ ሰብሮ በበር መቃን ሾልኮ የሚመጣው ዓይኖቼ ላይ የሚቆመው ሰንበር የመሰለ ቢጫ መብራት......

በማላውቀው ምክንያት ተባረኪ ሁልጊዜ ሁለት የውስጥ ሱሪዎች ደራርባ ትለብስ ነበር:: 'ምነው ሁለት?' እንኳን አላልኳትም---ሁሉ ልጃገረዶች ተመካክረው የሚያደርጉት ስለሚመስለኝ ......

ክንዴ ላይ ተጣጥፋ እንደ በግ ጥብስ የምትሸት ተባረኪ......(ምናልባት የፋሲካ ዕለት ነው ወይ የገና፣ ምን አውቃለሁ? ወይ የሆቴሉ ማድቤትና ነፋስ ተመሳጥረው የተራቆተ የዋሀ ልጅነታችን ላይ የስብ መዓዛቸውን እያፈሰሱብን)......ገና ያልተገራ ብርቅ የሆነብን ወሲብ እንደ ባርያ አስሮን......

የመከረም ጉም በወደቀበት የደበዘዘ ትውስታዬ ውስጥ ችኩል ገላዋ ትዝ ይለኛል:: ድምቡሽኗ እንደ ትንሽ አኮርድዮን ተሰብስቦ ደረቴ ላይ ሲለጠፍ:: ዕንባ የፈሰሰባቸው የመሰሉ ወዛም ጭኖቿ ትዝ ይሉኛል የልጅ ነታችንን ናርዱ ተቀብተው......እንዴት ጣዕም ነበረው......ዝማሬአችን ከክፍል ፈሶ እንዳይወጣ አፍ ለአፍ ተከዳድነን......እንደ ድኝ ስንፈነዳ......

አምናለሁ ያን ሰሞን የዋጥኩት የተባረኪ ቅላዬ ከኦፔራ እንደሚያስንቅ ......ጭር ባለው በዚህ ጎዳና ላይ ዛሬ ከሆዴ ባገሳው፣ እንደ ጣያስ እየተንሸረሸረ እንደሚሄድ......

ስንቴ እሷ እኔን፣ እኔም እሷን በፍቅር ዘንግ ሰበርን? እሷ ማሕፀን ውስጥ ስንት 'ቴቢ ማይ ላቭ'[16] ዎች ነበሩ? እንደ መረቅ የነጠሩ……እኔስ ደረት ላይ ስንት 'ወይኔዎች' ነበሩ? እንደ ዕንቁ የሚያበሩ?

እንዲህ ሆኖ……እንዲህ ያማረ መስሎ……እንዲህ ሁሉ ነገር እነሁላይ ሆኖ……ግን ምንም አላጋጠመኝም:: የወሬ ሰውቀቴ ጥራት አጥሮት ይመስለኝ ነበር:: ምንም አላጋጠመኝም:: ኬላ አልነበረም:: እንደሚባለው እንደምሰማው ኬላ መኖር ነበረበት:: የሆነ ቢአር የሚነዳ ወይ ኦዚ ያነገተ፣ ደርግ የመሰለ:: ቸርነት ሲጠይቀኝ ዋሸሁት:

«ቨርጂን[17] ነች?»

«እዎ……ታዲያስ»

ብቸኛ ውሸቴ ስለ እሷ ይሄ ነበር:: ምናልባትም መሀይምነቴን የደበቅሁበት:: ስለጣመኝ ብቻ ያገኘሁትን ላለማበላሸት፣ እርካታዬ እንዳይደፈርስ:: እሷን መውደዴም እንዳይረክስ……

ጥቂት ጓደኞቼ 1967 ላይ ለዕድገት በሕብረት ዘመቻ ተመልምለው በየቦታው የሄዱ አሉ:: 'አንድ ነገር ይሆንብኛል ልጄ' ብላ እናቴ ስላመፀች ሂያጅ አልነበርኩም:: በፖለቲካ አቋማቸው 'አንሄድም' ካሉና ምደባቸውን ከሚጠብቁ ልጆች ጋር የማያልቅ የመሸኛ ድራፍት እየጠጣን፣ ስለ እድገት በሕብረት ዘመቻ እየተወራና 'ሶሻሊዝም ታወጀ' ተብሎ ውይይትና አሉባልታ ሲደምቅ፣ ልቤ ሌላ ቦታ ነበር:: በለመድኳቸው፣ በምወዳቸው፣ ባሳደጉኝ የከተማዬ መዝናኛዎች ተቀምጬ ሽሮሜዳ ተባረኪ ጋ ለመሄድ ሳላቋርጥ እናፍቃለሁ::

ይጠይቁኛል:

«ጂሚ ምነው ተዶከከሽ? ለምን አንዱ ጋ አትዘምቺም? ቦካሽ እ?» አለ የዝናሽ ወንድም ጥላዬ

«ስለያችሁ ነዋ»

«ውሸቱን ነው:: ፉጌ:: ፍቅር ይዞታል:: ገርሉን እያሰበ ነው» አለ ተስፍሽ

«ማን ናት? እናውቃታለን?»

«ቴቢሽ»

[16] ቴቢ የእኔ ፍቅር

[17] ድንግል (Virgin)

«ቴብሽ? ተባረኪ? ታድለሻል ጆ:: ፖስቸሯ ሊሳ እኮ ነው:: ለመሆኑ ያን ነገር አደረግሽ?»

«ይሄ ልብ የለውም»

«ብትዘምቺ ኖሮ 'ልሞት ነው የምሄደው፣ ሳልመለስ እችላለሁ' ብለሽ ይበጠስልሽ ነበር:: ያልታደለ»

«ባክህ ተወኝ:: ምን ያወራል፣ ምናባቱን» *ሊላ ምን እላለሁ?*

«አልቆረጥሽም?»

«አንተ አፍህን ያዝ:: እንደዛ አትበል»

«ናይስ ናት አይደል ተባረኪ? እግሯ ይጀነጅናል:: ጭንዋ የትልቅ ሴት ያክላል ጆ፣ እኔን ግን እናቷ ትመስጠኛለች:: *ጎርጀስ*[18] ናት»

ይሄ በማንም አይካድም: የትደነቂያለሽ ልጃገረድ መምሰል:: ብዙ ጊዜ ከተባረኪ ጋር ተያይዘው ወደ ገበያ ይሄዳሉ:: ሁለቱም ነጠላ ይለብሳሉ (ቴቢ ነጠላ መልበሷ ያናድደኛል):: የማያያቸው ማነው? አይኖቹ ከአንዷ ወደ አንዷ ሲዘል የሚያየው: ሁለት ዘንቢል የያዙ ከጥቁር አፈር ተፈልቅቀው የወጡ ጠይማንና ጠይማት እግ መሳያት......ፀሐይ ጠልቃ ከርሞ ውጋገን ብቻ ሲቀር የመሰሉ ጥቁራት......የባቄላ አበባ የመሰሉ አይናት......ድግምታት......አስማታት......ወይዘሮና ወይዘራት:: አስባለሁ ......ጀርባቸው ላይ መዓት ፈጣጣ ብሌኖች እንደ ምስማር ተቸንክረው ......አስባለሁ እቤት ገብተው ያን ሁሉ ቱሌታም የብሌን ጨጎጎት ከኩታቸው ላይ ሲያራግፉ......

«አንተ ገርሊን እንደዛ አትበል፣ ልትዘመት እንጂ ልትሞት አይደለም የምትሄደው»

«በነገራችን ላይ! ዓሳዘር......*ኦብጀክቲቭ ሪያሊቲ*[19]......ቴቢሽ ቨርጂን ናት? ንገረኝ፣ ፋይናል፣ አንጠይቅህም ከአሁን በሁዋላ»

«በመጀመሪያ ገርሊ ፊውዳሊዝም ወይም ኢምፔሪያሊዝም አይደለችም:: ስዊት[20] ነገር ናት:: ስዊት አታውቅም:: በቆሎ ጥብስ መስሎሃል:: ለየት ያለ ነገር ነው:: የምትዘናናው በታስቴ አይደለ አይፈረድብህም:: ደሞ *ፐርሰናል*[21] ጉዳይ ነው:: ለምን እንደሆነ ታውቃለህ? ብነግርህ አይገባህም፣ ይልቁን የማነው የእንትናን *አዳራሽ ቤቱን* እየዘፈንክ ጨርጨር ዝመት»

---

[18] ቆንጆ

[19] ተጨባጭ ሁኔታ (objective reality)

[20] ጣፋጭ ( sweet)

[21] የግል ጉዳይ ( personal)

«ካልክስ እሱን ሲያፋዋጭ ነው የሚውለው ሃሃሃ»

«ምናለበት......ምናለበት ተሾመ ደምሴ ከማን ያንሳል? በኢሪክ ክላፕቶን ጊታር እንድንዘምት ትፈልጋለህ? የማይረባ ኢምፔሪያሊስት:: ይልቁን ይነገረን ያሳሰበን እናቱ እንኩዋን ገና ጡት እንደጣለ ገብቶአቸው ከቀሚሴ ስር አይሄድብኝም ያሉት ትንሽ ልጅ ነው......የእኛ ቆንጆ፣ የእኛ ቴክስ......ሴቶች የሚያባልግ እንጂ የሚያምር አይፈልጉም፣ ጠይቅ ከዩንቨርሲቲ ምሁር ሃሃሃ መጥፎ የሃይ ስኩል ተማሪ»

«ሃሃሃ አንዱ ኡላ ቀድሞ በትኖላታል፣ አፍራ ነው፣ ፐርሰናል ምናምን ትላለች» አለ ናትናኤል:: *ዝም ብሎ ቆይቶ ምን አናገረው?*

«ዝም ብለህ ጠጣ ስለማታውቀው ሆሆ አትበል:: 'ነይ እርግብ አሞራ' መዝፈን መሰለህ:: ደባሪ ዘማች:: እዛ ይቆላህና ላም ትጠብሳለህ ከዛ በሬ ምናምን ትወልዳለህ»

«ምናባቱን እኔ እኮ ነኝ:: *ሌዲስ ማን*[22] ጂሚ! በቃ አደገች አይደለ ዓላዛር:: እንኩዋን አንቺን ማርሎን ብራንዶን ቺክ ማውረድ አስተምራለሁ:: ግን እግዜር ይመስገን አሌክስ ለጠበሳ ደረሰች፣ ከእኛ ጋር ሁሉ መጠጣት ቻለች አደለ? ልዝፈንልሽ? እ? *ዝንጀሮ በገደል አድጦት አይወድቅም፣ እንዳንተ ያለ ጤባ አጋጥሞኝ አያውቅም......ሃሃሃሃሃሃ* ልክሽን ነገርኩሽ»

«ምናለበት? ከሽማግሌ ጋር ብቀመጥ እንደዚህ እጠቀማለሁ:: ትመርቁኛላችሁ፣ ተረትና ምሳሌ እማራለሁ፣ ስለ ዝንጀሮም እሰማለሁ:: ዝንጀሮ ምን ይመስላል? ሃሃ እኔ ኤሌክትሪክ ትሬይን[23] ምናምን ነው የማውቀው»

«ምናባቱን ይላል ይሄ:: መጥበስ እኮ ብርቅ አይደለም»

«ስክሩው ዩ»

«ሾትሪ ያቺን ልጅ:: ቤቶቹ የዘመቻውን ሱሪ ደግመው እያሰፉ:: ቁሌታም መሰሉ፣ ጡት ነው ያ ወይስ ጎጆ ቤት ነው?»

«አንተ ራስህ አላስፈራህም?»

«ምን ታደርገዋለህ? በጣም ደባሪ ነገር እኮ ነው:: ማስጠበብ አለብህ፣ አለበለዚያ በጨርቅ ተከበህ የምትሄድ ነው የምትመስለው»

......ከመሃል አንዱ የዘመቻ ዘፈን ሊዘፍን ይፈልጋል:: ከማርማቸው የበለጠ አሳምሮ እንደሚዘፍን ለማሳየት ይጥራል:: አይችልበትም::

[22] ሴት አውል (Womanizer)

[23] የኤሌክትሪክ ባቡር ( electric train)

ልተርበው አልፈልግም፡፡ ጉልበት የለኝም፡፡ ስመልስለት በብድር ለምድር ስለ ተባረኪ እንዳያነሳብኝ፡፡

«ግብታዊ ዘፈን ነው?» አለ አስማኸኝ

«ስሚ ገብረ መስቀል የት ጠፋች?» ገርማሚ

«ገብሬ ኡላው አልሄድም ብላ የለ እንዴ? ከአማን ቶራ ጋር 'ፋሺሽት አያዘምተንም' እያሉ ያነጅባሉ፡፡ የጦፈ ጓደኛ ሆነዋል ደሞ»

«ትልቁ ጆኒ እኮ በቃ ገርሌን ልሰናበት እያለ ልክ እንደሚሞት ሁሉ አልገኝ አለ»

«እንደ አሌክስ ሆናለቻ፡፡ ፔሲ እንደ ካልሲ ያልቃል ጂሚ፡፡ ሀያ አራት ሰአት ስትጎለትባት ተማራ እንዳትከስህ......» አለ ናትናኤል ወደ እኔ ዞሮ፡፡

«ምን ሆንሽ አሌክስ? ዘመቻ አትሄድ ምን እንዲህ አደረገህ? ለእሷ ብዬ ነው የቀረሁት እንዳትለኝ»

«ልጅ አይደለ ሃሃሃ......ገና ለዚህ አልደረሰም»

«አፍህን ያዝ! ሳይጠይቁት»

«ምነው? ፍቅር በአንቺ አልተጀመረም እኮ፡፡ ስለዚህ ትልቅ ጉዳይ አታድርጊው»

«ስሜቴ ይከበር»

«ዘመቻ ልሄድ ነው፡፡ ልሞት እችላለሁ፡፡ አፌ ያመጣልኝን ልናገር፣ አትቀየሚኝ» አለ አሰማኸኝ

«ነው እንዴ? አማረልኝ ብለሃል»

«አማርኛውን ሰማህ? 'አማረልኝ ብለሃል' ከእናትህ ጋር ነው የምትውለው? ወይስ በጎን ገረድሽን ላሸር አድርገሻል?»

«አትደብሩ»

«ይቅርታ ሮሚእ ሮሚእ ሮሚእ......»

«ኖኖ ቴቢዬ ቴብዬ የልቤ ወለላ......»

«የናንተ ገርሎች ጠንፌዎች ስለ ሆኑ ቀንታችሁ ነው አደለ? ከወፍጮ ቤት ሲወጡ መጠበቅ ስለቻችሁ»

«የናዝሬት ስኩል ቺክ ናት......ከሴንት ሜሪ ምናምን ነው እኛ፡፡ ስማቸው ደሞ ሐና ቲቲ ኩኩ ምናምን ነው፡፡ እንዳንተ ኣስካለ በቀለች ኣሰለፈች ወርቂቱ ምናምን አይደለም፡፡ ሲሰናበቱን 'ኦ ሃኒ' ምናምን ተብለን ነው፡፡ አኬ? እንዳንቺ 'በል ማርያም ትከተልህ'......ሺት፡፡ ወላ

እጣን አጢሰው ምናምን። ከሚኒሊክ ትምህርት ቤት ምናምን ትጠብሳለህ? እዛ ያለው ቺክ ሹሩቡ ጋቢ ነው ጂሚ። ፋራ። ሁለት አይነት ገርልስ አሉ ማለት ነው። የጠላና የሚልክ ሼክ። ገባሽ?»

«ዝጋ በቃ። ያንተ ገርል ምንድናት? አላውቃትም? የሆነች የጥያቄ ምልክት የመሰለች ነገር። ሃሃ በአጠገቧ ስትሄድ ነፋስ ገልቦት ትንድፋ በጥሬ ይመታሃል። በጣም እርግጠኛ ነኝ እንጦጦ ከጉሬዛ ጋር አስር አመት የኖረች ናት። እንዴት ጤም ያላት ቺክ ትጠብሳለህ? አሰዳቢ። ፋክ የአባቷን መኪና»

......ተረቢን ሰምተው እንዳልሰሙኝ ወይ በፌጣን ሳቅ ረስተው ሌላ ወሬ ይቀጥላሉ። እኔም በፀጥታና በትንሽ ቅሬታ ቲቢን አስባታለሁ። የተገለበጡ የቡና ሲኒዎች የመሰሉ ጡቶቿንም አስባለሁ። እግሮቿ መሃል ስላለው እግዜር በጥበበኛ ሽረሪቱ ያደራውን እርጥብ ረባዳ......

ስለ ኬላው ግን እሷን መጠየቅ አፍራለሁ። አንድ፡ ከፍቅር ያነሰ ጥያቄ ይመስለኛል። እሷን አለማክበር ይመስለኛል። ሁለት፡ ተባረኪ ከላይ ለስላሳ፣ ዝምተኛ፣ የዋህ፣ የመሰለች ናት። ካላማራት ትቆጣለች ትሳደባለች። ካላማራት እንዳዛ ናት። ከተከፋፈተች አስቀያሚ ነገር ትናገራለች። እናቷ 'ይህቺ በርበሬ ጆመራት' አለነገር አትልም። የኬላ ጥያቄዬ የማያምራት ይመስለኛል። እንደ ድፎ እጠበሳለሁ......ከላይ እሳ ናት፣ ከውስጥ ቁጭቴ......

*

«እነዚህ ሰዎች አይደክማቸውም እንዴ?» ይለዋል ጊቾ።

«ሃሃሃ» ይላል እዝራ በቸልታ።

በደስታ እሳት ተለኩሰን ፍም እያዝረበረብን፣ ሁለመናችን እየጤሰ ከቤርጎ እንወጣለን። ቃጠሎው ለሁለታችንም ቢከብደንም ደስታው ግን እንደ ገነት ሃያል ነበር።

የሚያበሽቀው ሁሉ ነገር ግን እያለፈ አያልፍም......

## እሳት ቀኖች

ለእድገት በህብረት ዘመቻ የሄዱት ወጣቶች ቶሎም ይምጡ ዘግይተው በትንሹ አርጅተው ነው:: ብዙ ነገር በፍጥነት እየተለዋወጠ አገሩ የተለየ ሆነ:: አዲስአባ በፖለቲካ ጉዳይ ትታመሳለች:: 'ብዙው ወጣት ለማህበራዊ ለውጥ በመታገል ላይ ነው' ይባላል:: ብዙ ነገሮች ሆነዋል:: መሬት የሕዝብ ሆነ ተብሏል:: ፋብሪካዎች ተወርሰዋል:: ኅዳር 67 ውስጥ እናና የምታውቃቸው ጥቂት ባለስልጣናት ተረሽነዋል:: 'አይ እቴ ባለጌ ቢሆኑም የሚያስገድል ምን ሰሩ?' ያለችው ትዝ ይለኛል:: ሁለት የዐናዕል ዘመዶች እርምጃ ተወሰዶባቸው ለቅሶ ተቀምጠናል:: የመሬት ለአራሹ አዋጅና የትርፍ ቤት አዋጅ የእናናንና የእማማን የኑሮ ደረጃ ዝቅ አደረገ:: ሁለቱም የቆጫቸው ለሆነ ኤምባሲ ያከራዩት የነበረው የጣሊያን ቤትና አሮጌው አይሮፕላን ማረፊያ የሰሩት በጣም ዘመናዊ ቪላ መወረሳቸው ነው:: በግድ የሁዋለኛውን ምግብ ቤት ወይም መስሪያ ቤት ለማድረግ መረጡ::

በየቀበሌው ወጣቶች ውይይትና ስብሰባ ያካሂዳሉ:: የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ማኦሴቱንግ ፍልስፍና ይጠናል፣ መፈክር ይለፈለፋል:: (*መፈክር ምንድነው? መፈክር የት እንደተተነተነ የማይታወቅ ሰፊ ሃሳብን አሳጥሮ ስድብ ወይም ተረብ ማድረግ ይመስለኛል*) ከደበበ ጀምሮ በተስፋዬ አድርጎ በተማም በኩል በአማን እና በራሷ በተባረኪ በቀጥታና በተዘዋዋሪ ስብሰባ እንድመጣ እስኪሰለቸኝ ተደጋግሞ ይነገረኛል:: 'ዝም ብለህ ከምትቀመጥ......ተደበርበት' እየተባልኩ እንዳነብ በራሪ ወረቀት ይሰጠኛል::

አንድ ቀን ተባረኪ 'ትንሽ ጉጉት እንኳዋን የለህም? ወጣት ሆኖ ከወጣት መለየት ደስ አይልም በእናትህ፣ በሮዛ ሞት፣ ደሞ ኔክስት[24] ቅዳሜ ቲያትር እናሳያለን:: አኔም ተዋናይ ሆኜ እሰራለሁ' ብላኝ የእሷ ነገር ሆኖ ትንሽ ስለከበደኝ አንድ ከሰአት በኋላ እሷ የምትሳተፍበት የወጣቶች ማሕበር ስብሰባ እዛው ቀበሌአችን ሄድኩ......

---

[24] የሚቀጥለው

የተጋበዝኩት ቲያትር የሚሰራበት አዳራሽ የእህል መጋዘን የነበረ ነው:: ገና ከውጭ ሲያዩት በዐይን፣ መግቢያውን እንዳለፉ በጠረን እህል ይታጎርበት እንደነበር ይታወቃል:: ሕንፃው ከብሎኬት የተሰራ፣ 'እህል ደብቀሃል' ተብሎ የተረሸነ፣ ከነፀናዕል ጋር የቅርብ ዝምድና ያለው ሰውዬ ሀብት ነው:: ገና አዳራሹ ስገባ የእህል ዱቄትና ብዙ ያገለገለ የቃጫ ጆንያ ሸተተኝ:: ወለሉ በፊራረስ የሲሚንቶ ቂጣ የተሸፈነ ነው:: ከመጋዘኑ አራት ሰፋፊ የብረት በሮች ሁለቱ ተዘግተዋል:: የአዳራሹ አንድ አራተኛ በጠጅ ቤት አግዳሚ ወንበሮችና በዕድር ወንበሮች ተሞልቷል:: ከጥቂት መቀመጫዎች በስተቀር በሙሉ በተመልካች ወጣቶች ተይዘዋል:: አዳራሹ ከነፋስ የተገለለ ቢመስልም ይበርዳል:: ምናልባት ሌሊት የገባው ብርድ ጨርሶ አልወጣም:: እንደ አስተናጋጅ የሚሰራት ልጅ በስሜ ጠርታኝ 'እድለኛ ነህ ጥሩ ወንበር አገኘሁልህ' ብላ አዳራሹ መግቢያ አጠገብ መደገፊያ ያለው አንድ ታጣፊ የላስቲክ ወንበር አምጥታ እንድቀመጥ ጋበዘችኝ:: ወንበሩ እሳት ውስጥ ገብቶ እንደወጣ ሁሉ የተጨማደደ ነው:: ስቀመጥበት ተንጋደደ::

አንድ አስር ደቂቃ እንደቆየሁ ፊት ለፊት አንድ ወጣት መጣና እንዳላየነው ሁሉ ወደ መድረኩ በእጁ እያሳየ፣ ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በፈቃደኞች ተሰርቶ እንዳለቀና ሃላፊነቱም የ......(ያልተሰማኝን ስም ጠርቶ) መሆኑን ተናገረ:: ፊት ለፊት ካሉ መቀመጫዎች አንድ ሰው ተነሳና ከፊት ለፊታችን ቆመ:: ማጨብጨብ ተጀመረ:: ከሁዋላ የነበርነው ልጆች እኔንም ጨምሮ የተጀመረውን ጭብጨባ ተከተልን:: ጎኔ የተቀመጠውን አንዱን ማብራሪያ ጠየቅሁት:: 'መድረኩን የሰራው ሰውዬ ነው' አለኝ:: ሰውዬው በከፊል ወደ ተሰብሳቢው ፊቱን ዞሮ ለማያቋርጠው ጭብጨባና አጨብጫቢ እየተሽኮረመመ ከወገቡ ጎንበስ ጎንበስ እያለ ምስጋናውን አቀረበ::

አስተዋዋቂው ልጅ ሰውዬውን (አናጢ ይሁን መሃንዲስ እንጃ) አመስግኖና እንዲቀመጥ ጋብዞት ንግግሩን ቀጠለ:

«ቲያትሩ ከጥቂት ደቂቃዎች በሁዋላ ይጀመራል:: ይሄን ሁሉ ለማቀናበር ጊዜና ገንዘብ ስለወጣ የተቻላችሁን ያህል እንድትረዱ ቲያትሩ ሲያልቅ፣ አሁንም ሊሆን ይችላል፣ በሩ አጠገብ ለምትቀመጠው ልጅ ለጓድ--እዩአት (ወደ በሩ እያሳየ)--ለአሷ ትሰጡናላችሁ (የሆነች ቀጫጫ መልከመልካም እጆቿን ደረቷ ላይ አጣምራ ፈገግ አለች):: የቻላችሁትን ብታደርጉ ደስ ይለኛል» አለና ማራኪ ሳቅ ሳቀ::

ቀጥሎም ትንሽ አሰብ አደረገና:

«ቲያትሩ 'ቱሉ ፎርሳ' በተባለው አጭር ታሪክ ላይ የተመሠረተና ለመድረክ እንዲመጥን ሆኖ የተዘጋጀ ነው:: ወደ ድራማ የለወጠው አሸብር መልካም ሲሆን መሪ ተዋንያኖቹ ደሞ ታባረኪ ዘርአይ እና ተመስገን ዝናቡ ናቸው:: ተመስገንን ሚኒሊክ የምታውቁት እትጠፉም::

ተመስገን የፀጋዬ ገብረመድሕንን *የእሾህ አክሊል* ድራማ በትምህርት ቤት የሰራ ነው:: ተባረኪም እንዲሁ የተፈጥሮ ችሎታ የታደለች ናት:: በሉ ተማሩ ተዝናኑ» በማጎንበስ ሰላምታ ሰጥቶን ከመድረኩ ዞር ሲል ሞቅ ያለ ጭብጨባ ሸኘው::

መድረኩ የተዘጋው በአንሶላ ነው:: ከጀርባ እቃ ሲዘገጃጅ ሰዎች ሲያንጎዳጉዱ ይሰማል:: መድረኩ ቆንጆ ቢሆንም ወለሉ የተሰራበት እንጨት ይሁን አሰራሩ የሚያወጣው ድምፅ ለቲያትር የሚያመች አል መሰለኝም:: ግን ማንም ባለው ነው:: ለደቂቃዎች ፀጥታ ነገሰና መጋረጃው ተከፈተ:: ጭብጨባውና ፉጨቱ ቀለጠ:: ተባረኪን በረዥም የተቦዳደሰ ቀሚስና በኮንጎ ጫማ ከቱሉ ጋ እጅ ለእጅ ተያይዛ ብቅ አለች:: አንድን ወርቅ አባራ ውስጥ ከተን ብናወጣው ያው ወርቅ ነው:: የማየው እሷን ብቻ ነበር ማለት እችላለሁ:: ቱሉ ሆኖ የሚሰራው ቴቢን 'ባለቤቴ' እያለ ሲጠራት ደሜ ይፈላል:: ልጅ ሁሉ ወልዳለታለች:: አልባሌነቷን ማየት አልቻልኩም:: የማየው ከጨርቁ ስር ያለውን ነው:: እሷ መድረክ ላይ ስታለቃቅስ እኔ ራቁትዋን በሆዷ አስተኛታለሁ:: እሷ 'ውዱ ባለቤቴ' 'ጓዴ' 'እኛ ላብ አደሮች' ምናምን ስትል እግሮቿ መሃል ነኝ:: ስለ ፋሺሽቶች ስታወራ አፏን ጎርሼ ከንፈሮቿን እመጣለሁ:: ለገቢር መድረክ ሲዘጋ ጠባብ ጂንስ ሱሪዬ ሊፈነዳ ያህል አብጧል:: እሱን አባጣ ሰው እንዳያይብኝ በእጄ ጋረድኩ:: አጠር ባለ ሁለተኛ ገቢር ቲያትሩ ተጠናቀቀ:: በምን ሃሳብ እንደተጠናቀቀ እርግጠኛ አልነበርኩም:: ብቻ ቲያትሩ እንዳለቀ ቴቢና ቱሉን ሆኖ የሰራው ላብ አደሩ ልጅ ግራና ቀኝ ቆመው እጆቻቸውን ወደ ላይ ዘረጉ:: እሷ በግራ እጅዋ ማጭድ፣ እሱ በቀኝ እጁ መዶሻ ይዘዋል:: መዶሻውና ማጭዱ ተደራርበው የኮሚኒስቶችን አርማ ሰሩ:: እንደዚህ እንደዘረጉ ምንም ሳይንቃነቁ ምናልባት ለአንድ ደቂቃ ቆዩና ለዚያን ጊዜ ያህል ጭብጨባው ቀለጠ:: የሚተነፍሱ አይመስልም:: የተጨበጨበው ላለመተንፈሳቸው ይሁን ለኪነቱ ግራ ያጋባል:: ለጠላቂ ዋናተኛ ከማጨብጨብ የተለየ አልነበረም:: ይሄን 'ኪነት ነው' ብሎ የተማረከ የታመመ ነው::

*በሐምሌ*ትና *በሀሁ በስድስት ወር* የተጀነጀንኩ ልጅ፣ 'ላብ አደር' ናቸው የተባሉ አንድ ወንድና ሴት አክተሮች፣ ሴቷ ከግራ፣ ወንዱ ከቀኝ፣ እሷ ማጭድ እሱ መዶሻ ይዘው፣ እሷ ግራ እጇን እሱ ቀኝ እጁን ወደ ላይ ዘርግተው አየር ውስጥ መዶሻና ማጭድ አነባብረው የፓርቲያቸውን አርማ ሰሩና ኪነት ነው? በትክክል መጨብጨብ የነበረበት ለቴቢ ቁመናና እግር ነው:: ቴቢ የድራማውን ደራሲ 'አሪፍ' ልጅ ነው ብላ ነግራኝ ነበር:: ለምን 'አሪፍ' እንዳለችው እንጃ:: ውይይት ክበብና ድርጅት ተጋርተው ደርግን ስለጠሉ መካከቢያ ነው? የሰፈር ፐርሰናሊቲ ክልት ነው? የማይሆን ጌታ ለሰፈሩ ኡሪ ሲያዘጋጁለት ነው? ለመሆኑ ያልሆነውን እንደሆነ ሲነግሩት የሚቀበል ምን አይነት የኪነት ሰው ነው?

ላብ አደር ተብሎ የሚሰራው ልጅ ቶሎ ቶሎ የሚቆጣ ገፀባሕርይ ነው:: ምን አስቆጣው? ሲቋን ሆና የሰራችው ቴቢ ደሞ ድራማው ሲያልቅ አካባቢ ከወንድ ጓዶቿ ጋር በመሆን እነግራዚያኒን እንደምትታገል ስትለፈልፍ ነበር:: ኮሚኒስት መሆን አለመሆኗ ሳይሆን በጣም በመጥፎ ሰውና በመጥፎ መድረክ ምናልባትም ምንም ለማያውቁ ሰዎች የተሰራ ነው:: ያላቸውን ደካማ ዕውቀት ሰብስበው ጠማማ ፍቅርና ጠማማ ጥላቻ በመፈልሰፍ ላይ እንደሆኑ መገመት አይከብድም:: ቲያትሩ አልቆ ተዋንያኖቹ የሚንጣጣው ወደ መድረክ ተመልሰው ወጥተው እጅ ለእጅ ተያይዘው ተመልካቹን ሲሰናበቱ፣ ቴቢ በአይኗ ፈለገችኝ:: እንደ-ማልወደው ትጠረጥራለች:: የተወለደችው ለእኔ ነው:: ለማርክስ ወይም ለቱሉ ፎርሳ አይደለም:: ከባምቢስ ወደ ሰፈሬ የመጣችው ለእኔ ነው:: የጎዷትና የጎዱኝ መሰለኝ: በትግል በምናምን አዋክበው፣ ታጋይ ሴት ምናምን አስመስለው መድረክ ላይ አውጥተው በሴትነቷ እንዲያፄአት:: 'መዋቅሯ ደስ አይልም?' ምናምን እንዲሉአት:: ይሄ ሁሉ ጎረምሳ በቁሌት እንዲያፈጥባት:: አንዳንድ ስድ ይህቺን ከሁዋላ ማድረግ ነው ሊል ይችላል:: መድረክ ላይ ያወጧት ግብግ ሲያደርጉዋት ነው:: 'ያላያችሁዋት ካላያችሁ ይህቺትና ተባረኪ አሌክስን ኑና ፈንግሉ' የመሰለ እሰማለሁ::

ወጣቶቹ ቲያትሩን ሲያደንቁ ግንባራቸው ላይ ይሁን ድምፃቸው ውስጥ የመፎጋገር ቅላፄ እንኳን የለም:: ከልባቸው ነው:: ወደ ውጭ ስወጣ አንድ ብር በሩ ጋ ላለችው ልጅ ሰጠኋት:: የሚያስደንግጥ ውብ ጥርስና ፈገግታ አላት:: አውቀው የመደባት ይመስላል:: ፖለቲካና ንግድ ቤት የሚመሳሰሉበት ጉዳይ አንዱ ይሄ ነው::

ከአዳራሹ ወጥቼ ከአንድ ሰለሞን ከተባለ ልጅ ጋር እውጭ ቆሜ አወራለሁ:: ለልጁ በቲያትሩ መደበሬን እየነገርኩት ነበር: 'አቦ ይሄ ምንድነው? ደህና ቲያትር አትሰሩም?' የመሳሰለ::

ቴቢ ወደ እኛ እየሳቀች መጣች:: በእጅዋ ወረቀት ይዛለች:: እሷ ወደ ቆምኩበት ስትመጣ ስራዋን እንደማደንቅላት ገምታ ስትፍለቀለቅ፣ እኔ ጋ ከመድረሷ በፊት ሰለሞን ወደ እሷ ሮጥ ሮጥ ብሎ ሄዶ ከመሃል መንገድ አቆማትና አንድ አስቸኳይ ነገር እንደሚነግራት ሁሉ ከጀርባዋ ደግፎ ይዞ ከእኔ ራቅ አድርጎ ወሰዳት::

«መጣሁ!» ብላኝ ከሰለሞን ጋር 'ተቃቅፋ' ቆመች:: ወደ ጆሮዋና ወደ ትከሻዋ ተጠግቶ የሆነ ነገር ሹክ አላት:: ሹክታው ረዘመብኝ:: በሹክታው መሃል ፊቷ ተኮሳትሮ ዞር ብላ አየችኝ:: ከእሱ ጋር አንሾካሾካ ከጨረሰች በሁዋላ፣ እንድጠብቃት ወይ እንዳልጠብቃት ማስጠንቀቂያ እንኳን ሳትሰጠኝ ወደ አዳራሹ ተመልሳ ገባች:: ልጁ እሷን ተከትሎ አብሮአት ከመሰወሩ በፊት ሌላ ቦታ የሚያይ መስሎ 'በቆረጣ' አየኝ:: እጄን

አንሳሁለት:: እጅ ማንሳቴን ያላየ መስሎ አዳራሹ ገባ:: እንደተሳሳትኩ የገባኝ ከዚህ በሁዋላ ነው::

ከአዳራሹ እስክትወጣ ከውጭ ዱቄትና አቧራ የለበሰ ዛፍ ስር አሩብ ስአት ያህል በትዕግስት ቆሜ ጠበቅሁዋት:: ሰለሞን ስለ ቲያትሩ ያለኝን ግምት ቢያወራት እራሱም የምንነግራት ጉዳይ ነውና ሺህ ቢዘባርቅላት አታምነውም ብዬ በመገመት ተረጋጋሁ:: በከፉ አላማሁዋትም:: ሰለሞን እያንሾካሾከ ስለሚናገር ትችቴን የሐሜት ፀባይ እንዲይዝ ሊያደርገው ይችላል:: የህብረተሰባችን ስልጣን ውይይትን በተቻለ መጠን ወደ ሃሜት አውርዶ ደባሪ ገፅ የመስጠት ነው:: የስራ ቀዳዳውን እንዲሰፋበት መርፌ ስታሳየው ቂጭ ብሎ ሹልነቱን እንደ አስገራሚ ግኝት እየፈተሸ ቂጥህን ሊወጋበት ቀን የሚጠብቅ አይጠፋም:: ተባረኪ አዳራሹ ውስጥ ስትቆይብኝ እንዳከረፈችኝ ተረዳሁ:: ፖለቲካ ባይገባኝም በአራዳ ደንብ ጠማማነትን ገና ሳያት አውቃታለሁ:: የነገርን ምስማር በፖለቲካ፣ በወዛደር፣ በቁጩ መደብ ትግል፣ በሆነ መሬት ላራሹ በተባለ ምናምን ብትከናነብ አውቃ-ታለሁ:: ውሸት አልተናገርኩም:: ምናልባት እኔ የዋህ ነበርኩ:: ግልፅ መሆን በፓርቲ ፖለቲከኞች ባህል ብልሃት አልነበረም:: ያየሁት ቲያትር ግን በአስቀያሚነቱ ልዩ እንደሆነ ከእኔ ሌላ ትርፍ ምስክር አልጠራም::

ቴቢ በመዘግየቷ ልታበሳጨኝ እንደፈለገች፣ ከእኔ ይልቅ በፖለቲካ የተዋወቀችው ልጅ ወሬ እንደበለጠባት ገምቼ አለችበት አዳራሽ ገባሁና፣ ከበዋት ከሚያወሩ 'ኢምፖርታንት' ካደረጓት ሰዎች መሃል እንደቆመች ከአርቀት:

«እቤት ነኝ እጠብቅሻለሁ!» ብዬ ከአዳራሽ ወጣሁ::

አብረዋት ከነበሩ ልጆች የማውቃቸው ቢኖሩም ሰላም አላልኩዋቸ-ውም:: እነዚህ ትንንሽ ልጆች በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዴት እንዲህ ሃይለኛና ጠማማ ሊሆኑ እንደቻሉ መረዳት አልቻልኩም:: ባህላችን ተጠ-ልፎ ነው? አዳራሹ ደሞ ደርግ የወረሰው ነው:: በዚህ ወረሳ ተደስተውና ተስማምተው ከተሰበሰቡበት ለምን በዙፋኑ አይስማሙም? ፉከ ዜም::

ቴቢ ሁለት ሰአት ያህል አርፍዳ ቤት መጣች:: ቆጥሬአለሁ ሰአቴን:: ከነደቂቃው:: ሁለት ስአት ከሃያ:: የመጣችው የነበረችበት ቦታ እንደ ጫማ ስላለቀ ወይም በመሬት መንቀጥቀጥ ስለተዋጠ ይመስላል:: ክፍሉ እንደገባች የያዘችውን ወረቀትና ፋይል የምታስቀምጥበት ቦታ ያጣች መስላ ወንበር ስባ ከእኔ ራቅ ብላ ተቀመጠች:: ጉልበቶቿን ገጥማ የያዘችውን ወረቀትና ምናምን ጭኗ ላይ አደረገችና አተኩራ አየችኝ:: ስትፈልገኝ እግሮቿን ታነባብራለች:: አሁን እንዲህ ስታደርግ እኔም ልብ አልኩ:: የመጀመሪያዬ ስለሆነ መሰለኝ:: አልጠፋኝም ስለሞን ቆልፎ እንደላካት::

«መዓት የሚሰራ ነገር ነበር ለዚህ ነው የዘገየሁት:: ለመሆኑ ወደድከው ድራማውን?» አለችኝ:: ይሄ ጥያቄዋ ራሱ ቅንነት አልነበረበትም:: ልጄ እንደነገራት ገብቶኛል:: *ንቃት* የተባለው ይሄ ይሄ ተጠረቃቅሞ መሰለኝ:: በእሷና በቀጣፊ ዱርዬ መሃል ያለው ልዩነት ምንድነው? ይሄ ንቃት ከተባለ ከነ ማእ ምን አስለቀመ? ወይም ሌኒን ምናምን? አገራችን ውስጥ በመዓት መልክ በየሰፈሩ እንደ ጠጠር ሬግፎ ይገኝ የለ? ቤቴም ይሁን አሜሪካን ግቢ::

«ኖ» በቁርጥ ነገርኳት:: የፊቷ መልክአምድር ሲለዋወጥ አየሁት::

«ለመን?» አለች ከንፈሮቿን በንዴት ነክሳ:: ቃሉ ራሱ በከፊል ተቆርጦ ነው የወጣው:: *ለመን*

«ልደብርሽ አይደለም:: ምንም የድራማ ነገር የለውም ውስጡ:: ሕይወት የለውም:: ሁለታችሁም ምን እንዳማረራችሁ ግልፅ አይደለም:: አማረረኝ እንዳትዪ እሱም ስለመዶሻና ማጭድ ያወራል:: ለማማረር ገና አልደረሰም:: ተበሳጭቶ እንዲማረር ከዛ እሱ እንዲያማርረን እቅድ ካለ ሹር:: አንድን ስርአት......ሲመስለኝ ደርግ ስርአት አይደለም፡ ምክንያቱም በለውጥ ሐዋርያ ስርአት አይፈጠርም:: መጥላት ብቻ ሞቲቭ አይደለም:: ይመስለኛል:: ወዛደሮቹ ተናደዱ:: ገበሬዋ ተናደደች:: እንደዛ የሚያኑ ጫንጭ መዶሻና ማጭድ የሚያስነሳ ምን ነገር አለ? ካለ፣ ድራማው ውስጥ አልተገነባም:: ሞቲቭ ያስፈልጋል:: በቃ ተናደዱ:: *ሁ ኬርስ*[25]»

«እም......ታዲያ አንተ አትፅፍም አሪፍ ከሆንክ?» አለች

'እም' ማለቷን ያዝኩ::

«ምን ማለት ነው? አልችልም:: ስለማልችል አልፅፍም:: እናንተ መፃፍ አትችሉም፡ ግን ቻልን ትላላችሁ»

«ቻልን አላልንም፣ ደሞ በመልካም ፈቃደኝነት ነው እንጂ ፖለቲካ ምናምን የለውም:: አንዳንዶቹ ድርጅት ያለበት ይመስላቸዋል»

«ግድ የለኝም:: ድርጅት ኖረ አልኖረ፣ ቅዱስ ኖረ አልኖረ:: ትንሽ ጴንጤ ነገር ትመስላላችሁ:: አንቺን ብዬ ነው የመጣሁት:: ጥሩ ልምድ ነው ያገኘሁት:: ደ ሰለሞን ለምን እንደሆነ ጠየቀኝ፡ ልክ አሁን ያልኩሽን ነገርኩት:: ነገረሽ?»

«እ......አልነገረኝም......ምን ብሎ ይነግረኛል? ምን አሳሰበህ?»

«አሳሰቦኝ አይደለም:: እንደገባኝ ወይም እንደጠረጠርኩት ልበል ትንሽ ወሬ እኔ ጋ መጥቶ የለቃቀመ መሰለኝ ሃሃሃ»

«ታሾፋለህ»

---

[25] ማን ግድ አለው(who cares)

ለዚህ አባባሏ ልመልስ አልፈለኩም:: እንዳላሾፍኩ ታውቃለች:: አንዳንዴ በሰፈሬ እንዳየሁት ስብቀት ቶሎ ይታመናል:: ድራፍት እስደ-ግፌው የስጡን ሐሜት ከክርስቶስ ቃል ትበልጣለች:: ከቄስ ግዝት ትከራለች:: የሃሜት ችሎታው ቅር ሳይለው በሬ ማስወለድ መቻሉ ነው:: 'እም' ማለቷን አልረሳሁም:: በከፊል ልቦናዬ ቃሉን ከተቀመጠበት የእንጎሌ ጓዳ አውጥቼ እየተረጎምኩት ነበር:: 'እም' መንጠቆ ናት:: ከቅርብ የትውስታዋ ባሕር ሰለሞን የሰበቃትን ጎትታ የምታወጣበት:: ስታነፃዕር:: የአሁኑ ማነፃፀሪያዋ ግን የይስሙላ ነው:: ቢጋሩ ተለውጧል:: ከፖለቲካው በፊት በቀላሉ እንግባባለን:: አብሮ ማደግ፣ አብሮ መጠጣትና መብላት፣ መዋደድና መዳራት......ወዘተ ፈርሰው ፖለቲካው ቢጋር ሲሆን አንድን ቲያትር መተቸት እንደ ታላቅ ግድፈት ይቆጠራል:: 'እም' ስትል 'ሰለሞን ያሳበቀልኝ ትክክል ነበር' ማለቷ ነው:: ይሄ ደሞ ጥሩ አይ-ደለም:: ከዚህች እምነቷ ተነስታ ሌላ ጊዜ ሌላ ውሸቱን ታምንለታለች:: የተቀመጥኩበትን አልጋ በመዳፌ እየተመተምኩ ስጠራት ያላየች መስላ ስለ እማማና ስለ እናቷ የማያገባኝንና የማያገባትን አወራች:: ግድ አልሰጠኝም:: ደጋግሜ አልጋውን ተመተምኩ:: ሲሰለቸኝ ወደ ተቀመጠችበት ሄድኩና የያዘችውን ወረቀት ምናምን ከጭንዋ ላይ አንስቼ ወለል ላይ ሳስቀምጠው ስል:

«ተው እንጂ. ምን ሆንክ ይሄን ያህል አስጠላህ እንዴ?»

አልመለስኩላትም::

*ማን? ቲያትሩ? ድርሰቱ? አክተርነቷ? ሁሉ ሁሉ?*......ፍቅረኞች እንዲህ በሆዳቸው ቡራቡሬ ነገር ማውራት አለባቸው?

ከእኔ ተቀብላ ለማስቀመጥ ደህና ቦታ ብትፈልግ ከወለሉ በስተቀር ሌላ የተሻለ አማራጭ አላገኘችም:: መደርደሪያው አይሆንም:: እወዲያ መስኮቱ አጠገብ ያለ ጠረጴዛ ላይ ለማስቀመጥ ልትሄድ ስትል ያዝኳት:: ይሄ ለእኔ ቀላል ንቅናቄ አልነበረም:: በመርከብ ወደ ሌላ አህጉር ለመሄድ ትኬት የቆረጠች ነው የመሰለኝ:: ከሁዋላዋ ያዝኳት:: ቀሚሷን ገበሬ ስታይል:: ድሮ ስናሾፍ 'እንትና ሲጠብስ እንደ ሱሉልታ ገበሬ ቀሚስ ይጎትታል ምናምን' እንል ነበር:: ከዚህ የበለጠ የላብአደሩ ሕዝብ ርዕዮተ ፍቅር ምናምን አለ? አጎታተቴ ራሱ ሕዝባዊ ስታይል ምናምን ይመስላል:: ከዚህ የበለጠ ሪቮነት አለ? ቶሎ ዞር ብላ አየችኝ:: ድልድይ ላይ ናት:: ትፈልገኛለች ደሞ ብቁ አይደለሁም::

«አንቺ ብቻ ነበርሽ የምታምሪው እዛ» አልኩዋት

«አትዋሽ»

«ዕጌ ትሙት:: የዚህ አይነት ቲያትር ግን አትስሪ» አልኩና ከሁዋላዋ ቆምኩ:: ተጠግቼ ቀሚሷን ከፍ አደረኩ:: ረቂቅ ሙቀት አብራኪን መታኝ::

«ውሸታም» አለች:: ቀሚሷ እንደተገለበ ተያይዘን ወደ ጠረጴዛው ሄድን

«የምን ውሸት?»

«ተወው በቃ»

*ምን አገባኝ ቢ ቀር::* ዞረች:: አፏ ላይ ሳምኩዋት:: እንደ ቀደሞው አልተሳተፈችም:: እንዲህ ሲሆን በመሳሳም ትርምሳችን ውስጥ ሊያጋጨን የሚችለውን ቀላል የመሰለ ታምራት በትክክል አስፍቼ ማሰብ አልቻ. ልኩም:: የሆነ ነገር ለመናገር እየፈለገች ራሷን የምትቆጣጠር ይመስላል:: እንደ እርጥብ ጨርቅ ብጠመዝዛት ግን አንድ ቃል አይወጣትም:: ቴቢን ዋሽቼአት አላውቅም:: ስለ አልማዝ ብቻ ነው የዋሸሁዋት:: የስጋ ፍላጎቴ አይሎ ሁኔታዋን ችላ ብለውም፣ እውስጤ እንደ ስንጥር ተሰንቅሮ ተቀመጠ:: አሁን ችላ እለው ይሆናል:: ፀጉሯን እያፈራረስኩ ስስማት ሙቀት ከላይዋ ሲነሳ እንደ መጋዘን መሽተት ጀመረች:: ፊቴን እንዳታይ አድርጌ ለራሴ ሳቅሁ::

•

በሬድዮ ያውም በመንገድ ሳልፍ ከምሰማው ወይም ማታ አባዬ ቲቪ ሲከፍት አንዳንድ ነገር እግረ መንገዴን ሳይ ካልሆነ ስለዚህ ስለፖለቲካው የጠለቀ ዕውቀት አልነበረኝም:: ግድም አይሰጠኝም:: ተባረኪ በተገናኘን ቁጥር ደርግን እያማረረች ስታወራ ፖለቲካ በአጠቃላይ እንደሚደብረኝ ከመናገር ውጪ አልቀናቀናትም:: ለምን ልነዛነዝ? አብረን ሚኒሊክ ስንሄድ የንቃት መፅሃፍ ለመግዛት ቅድስት ማርያም ፊት ለፊት ያለ መፃህፍት ቤት ስትገባ ተከትዬአት መግባት ቢደብረኝም፣ በአጋጣሚ የእነ ጎጎልንና የእነ ዶዮስቶቪስኪን ጥሩ ሆነው የተጠረዙ መፃህፍት እገዛለሁ:: አንዳንዴ በአማራሪ ወሬዋ 'ፋሽሽት' 'ፋሽሽት' 'ባንዳ' ስትል በልቤ 'ምን አገባሽ?' እላለሁ:: መንግስቱ ሃይለማርያምን 'ይሂ ጨፍጫፊ' ስትል ለብዙ ጊዜ አብራው ኖራ ስለሰውዬው በጥልቅ የምታውቅ ትመስላለች:: 'ሰውዬው ክራቫች ለብሶ መንገድ ላይ ባየው አላውቀውም' እላታለሁ:: በአባባሌ በጣም ታዝናለች:: እሷና እሷን የመሰሉ አብዮተኛ የሚባሉት የሚጠቀሙባቸው ቃላቶች ቶሎ አይገቡኝም:: አንዳንዴ እነዛን ቃላቶች በአጭር ጊዜ ማን ፈጠራቸው እላለሁ? 'ባንዳ' 'መኢሶን' 'ኢህአፓ' 'ፊዩዳሊስት' 'ጠቆረ' 'ቀላ' 'ቀይ ባንዲራ' 'አብዮት' 'ዲሞክራሲያ' ምናምን ስትልና ሲባል የስሞቹ አፈጣጠር፣ የአፈጣጠራቸው ፍጥነትና ምህዋሮቹ ሲበተኑ የማገኘው አንዳንድ ጉድ ያስቀኛል:: ከማላውቀው ወደ ማላውቀው፣ ከማይገባኝ ወደ ማይገባኝ:: የእናና ወሬ ስርጎብኝ እንጎሊን

*ላይ ተለስኖ ይሆናል፡ ‘ይኼ ንጉሱን የመስደብ ወሬ እኮ የወጪ ት ሰባሪዎች ነው……አባትህን የመሰሉ ናቸው……ቂል ቢሰበሰብ ወጥ ያበላሻል እንጂ ድግስ አያስተካክልም:: የትም አይደርስ……በል ዓላዛር እንዳህን ጀምር……’ ከዛ መለሊታውን……*

*

ትምህርቴን ለመቀጠል አራት ኪሎ ዩንቨርሲቲ ተመዘገብኩ:: በፖለቲካ ውጥረት ምክንያት ብዙ ተማሪ ስላልመጣ አራት አልጋ ያለበት ዶርም ብቻዬን ተመድቤ ነበር:: ከሰኞ እስከ አርብ ትምህርት ከሌለኝ ሽፍቷን ጨርሳ ከሚኒሊክ ትምህርት ቤት የምትወጣውን ቴቢን ጳሽን ካፌቴርያ ውስጥ ሻይ እየጠጣሁ ወይም ፊት ለፊት ሲሚንቶ ደረጃ ላይ ተቀምጬ ሲጋራ እያጤስኩ እጠብቃታለሁ:: ገንዘብና ጊዜ ካለን መክሰስ ሳንድዊች በልተን ወይ ጁስ ጠጥተን፣ እንዲህ ካልሆነም በቀስታ በእግር እየተጓዝን ሰፈር እንገባለን:: ሰፈር ካለንም እሷ ወይም እኔ ግቢ ዛፍ ስር ተቀምጠን የባጥ የቆጡን እናወራለን:: የትምህርት ሳምንት ሲሆን ማታ ማታ ብቻዬን ማደር ስለሚደብረኝ ካልደከመኝ ሽሮሜዳ እሄዳለሁ:: የትምህርት ሳምንት ሲያልቅ ጥናት ካሌለኝና ትምህርትን በሚመለከት የሚቸግረኝ ነገር ካላጋጠመኝ ሁልጊዜ ተባረኪን ፍለጋ ሰፈሬ እወጣለሁ::

ግን ሁኔታዋ ሁሉ ተለወጠ:: እንደምፈልጋት አላገኛትም:: ብዙ ሰበብ ትደረድራለች:: ሰበቦቹ ቢያልቁም ትደጋግማቸዋለች:: ያለእሷ መዝናናት ስለማይሆንልኝ ላገኛት ቤቷ እየደጋገምኩ እሄዳለሁ::

«አሁን ወጣ አለች:: አንተ ጋ አይደለችም እንዴ?» ትለኛለች ትደኑቂያለሽ (ዓይኖቿ ውስጥ በማበብ ላይ ያለው ግራ መጋባት ትዝ ይለኛል)

ታዚና ቤት እሄድና ከአዝራ ጋር አሁን በከተማውና በአገሪቷ ስለሚሆነው ፖለቲካ እናወራለን:: ወሬዬን እያቋረጥኩ ደጋግሚ እውጭ እየወጣሁ የተባረኪን ቤት መግባት ‘ቼክ’[26] አደርጋለሁ:: ሳላገኛት ስቀር በደንብ ፋታ ሳልወስድ ስላልጠበቅሁዋት የራሴ ጥፋት አድርጌ…… ውስጤ በወንጀለኛነት ይታመሳል:: አንዳንዴም ብቻዬን ብርድ ውስጥ ቆሜ የእንጦጦ ጅብ ሽታዬን በጠኔ እየነከሰ፣ ከእዛ ገደላ ገደል ፋደት የነሰነሰውን ጠረን አፌን ከፍቼ እየመጠጥኩ፣ አጥር ስር ድንጋይ ላይ ከቁራ ሬብ እንደ ወለቀ ኩስ እዛ ተለጥፌ (ትዝ ይለኛል ከጀርባዬ ነጭ የተቀባ የብሎኬት ግንብ ነበር:: እዚህ ግንብ ላይ ቀይና ጥቁር የፖለቲካ እርግማን ፅሑፎቹ ነበሩ:: ቀያይና ጥቋቁር ጋማድዮኖች[27]:: የተፃፉበት ቀለም አፈሳሰስ ከቫምፓየር ፊልሞች ሬክላም መፃፊያ ቴክኒክ የተቀዳ የመሰለ):: ሳልሰላች የግቢ በሯን እያየሁ ብጠብቃትም ፈፅሞ አትመጣም::

---

[26] አረጋግጣለሁ (Check)

[27] ስዋስቲካ (卐)

ሾልካ ገብታ እንደሆነ ብዬ ብጠረጥርም፣ በዛ ምሽት ደግሜ የቢቷን በር አንኳኩቼ መጠየቅ አፍራለሁ:: ትደነቂያለሽ በልቧ ትለኝ ይሆናል ምነው እቴ አላበዛውም?

ትዕግስቴ አልቆ ወደ ትምህርት ቤት እመለሳለሁ:: የቁጥር ደብተሬ ላይ አጎንብሼ የውሸት እመሰጣለሁ……በቀን ቅዤት ወደ አሳለፍኩት የቅርብ ልጅነቴ እሰደዳለሁ……እንቅልፍ እምቢ ሲለኝ ብቻዬን በሌሊት ከመኝታ ቤቴ ወጥቼ ቂጤ ቁርጥማት እስኪይዘው ሲሚንቶ ግንብ ላይ እቀመጣለሁ:: የራቀብኝ እንቅልፌን ላቀርበው ስለማመጥና በእግረ መንገድ ትከዛም በእኔና በእሷ መሃል የገባው ቀዝቃዛ አየር እንዴት እንደ ሚያደርገኝ ላዳምጥ……እዛ ጋ የጨለማ ኳስ የመሰሉ ያለ እንክብካቤ ያደጉትን ዕጌሬዳዎች አጠናለሁ (አትክልተኞችም ቸልተኛ በመሆን አምፀዋል መሰል):: በድንግዝግዝ ከዛ ፎቅ ላይ የሰከረ ተማሪ የመፈክር ጩኸት በመስኮት ወደ መሬት እንደ ትውከት ይደፋል: 'ደርግ ይውደም!':: ጥላ ሞቶች ግቢው ውስጥ እየተሩዋሩዋጡ ሉቢዎች ወለል ላይ ፍም የመሰለ ወረቀት ይበትናሉ……ግድግዳ ላይ ይዕፋሉ:: ቀልጣፋ መሳዮች ስፕሬይ ጣሳቸውን እየነቀነቁ ገላምጠው ያልፉኛል:: አንዳንዶቹ ያጉተመትማሉ……እንዲህ እያሉ ይሆን?: 'ይሄ አክቲቭ ያልሆነ ማነው?' ይኼም በአየር ውስጥ የሚንሳፈፈው፣ ላስቆመው አቅም ያሌለኝ፣ በሚታዘበን ጨለማ የተዋጠ ዝም ያለ መጥረቢያ ነው……በእኔና በወዳጆቼ መሃል ቀን ጠብቆ ስተት ብሎ የሚገባ……ሁሉ ያልጠበኩትና ያልለመድኩት ነውና የምሰራው ይጠፋኛል:: ብርድ የሚገላምጥ መጥፎር ቢጫ የቆዳ ጃኬቴን ለብሼ ቴቤን በትዕግስት እስባለሁ……

አንዳንድ ጊዜ ተባረኪ አድርጋ የማታውቀውን ሳትነግረኝ አባቷ ጋ ደብረዘይት ትሄዳለች:: የምትመጣበትን ሰአት እናቷ ትነግረኝና ቤቴ ተጋድሜ ሙዚቃ እየሰማሁ እጠብቃታለሁ:: እንዲህ ማድረግ ሲሰለቸኝና ስማረር ደሞ እውጭ በረንዳ ላይ ወጥቼ የግቢዋን በርና ግቢዋን እያየሁ እቀመጣለሁ:: በረንዳዬ ሲሰለቸኝ መንገድ ዳር ወጥቼ ወዲያ ወዲህ እያልኩና ከባለሱቁ ከተማም ጋር እያወራሁ፣ ጎዳና ላይ እያፈጠጥኩ እጠብቃታለሁ:: አንዳንዴ ደሞ ደብረዘይት አርብ ሄዳ ወደ ትምህርት ቤት ከተመለስኩ በኋላ ሰኞ ጠዋት ላይ ትመጣለች::

ግለሰቦች አቅም ያጠራቸው ልዩ ዘመን እንደደረስኩ አልገባኝም:: ከዛ ወይ ከዛ ከወዲያና ከወዲህ ከጠላና ከቡና ቤቶች የጥላሁን ገሠሠ ዘፈኖች፣ ያረጁ ሰላምከምቾ፣ የፈረሱ ያገኔዎች፣ እዛ እዛና እዛ የሸገኔዎች እንጉርጉሮ፣ ከትናንሽ ጠላና መሸታ ቤቶች እዛ ገዳዳ ሕንፃቸው ውስጥ የተጨነቀ ወንድ አልበው የሚጥሉ……ከእነሱ ሲናዱ እየሰማሁ፣ ወይ ከማላውቀው አቅጣጫ ብቻ ከሆነ ከየትም ይሁን ብቻ የእስቴር አወቀና የውብሸት ክራር……የሙሐመድ እንጉርጉሮ……የሰፈሬን ጆግራፊ እንዳልረሳው ደግሜ ደጋግሜ አጠናሁ በዛ ማታ……

*'በሸዋ ላይ ደሴ ታቹን በቦረና፣ ኑይ ኑይ እንደገና'*

ሲል ሙሃመድ የሚባለው ዘፋኝ……

'ቦረና' የደነዘዘ እግሬ ነው ተስፋ ሳይቆርጥ ታጥፎ ቦረቦርና ኮረኮንች ውስጥ ሚስቱን ሲጠብቅ ለሰዓታት የተጋደመ……

(እባ እንጦጦ ላይ መብራት ቦግ ብሎ ሲጨልም አስባለሁ ጆከሩ አለቃ ገብረሃና እንኩዋን ራጉኤል ግቢ ቀዝቃዛው የዕድ ጥላ ስር ተለማምጠው ሆኖላቸው ነበር ያኔ ('ሙች ብዬሻለሁ ነገርኩሽ፣ እንዳልኩሽ ወደ ማታ እመጣለሁ፣ ያቺ ቶላ ማዘንጊያሽ የለችም')……

'ደሴ' ሳይመጠጥ የተረሳ በራሱ ፍም የተደመሰሰ ሲጋራ ነው……

'ሸዋ' ግድግዳ ተደግፌ በእግሬ የምመታው አሸዋ ነው……

ከየሬድዮው የአብዮት ዘፈን ጋሻና ጦሩን ይዞ ሲፎስ ሲፎራና ሲያስፎራ……

'ኢህአፓ' ሲል የሆኑ ቄስ ነበሩ የሚታዩኝ ጥቁር የለበሱ፣ ታች ትልቁ ዛፍ ስር የፈረሰ ቆርቆሮ ቤት ውስጥ የሚኖሩ፣ ወይም እዝራ ቤት ያየሁት የአባቱ የቄስ ታዚና ፎቶ (ሳይሞቱ በሰፈሩ 'አባ' የሚባሉት)፡፡ ቀልድ አይደለም……

'ኢድዩ' የአንድ ሰው አይዲካርድ ይመስለኛል ደርዙ በዕድሜ የባተለ፣ ጥቁርና ነጭ ፎቶው ላይ ያለችው ሴት አንድ አይናማ ናት፡፡ እማምላክን……

'ሻቢያ' የሆነ ደረት ላይ ያለ የፀጉር ሽበት ይመስለኛል እስከ ፑንት[28] ከተከፈተ ሸሚዝ በጭገር ጥቅጣቆ ዐይን የሚረብሽ፡፡ ቀልድ አይደለም……

'መኢሶን' ልጅ እያለሁ ሶደሬ ወርጄ ያየኋቸው፣ የፊት ጥርሱ የወለቀ ሕፃን ቢጫ ድንጋዮች መሃል ቆሞ፣ በሽቦ ያንጠለጠላቸው የሚሸቱ አሳዎች ትዝ ይሉኛል፡፡ የሞተ አሳ ለምን ዐይኖቹ አይጨፈኑም? ወላ አቦ ያጠያይቃል……

ቲጤ በተቀመጥኩበት ድንጋይ ደንዝዞ ወይም በብርድ ፈዞ ወይ በድካም ላሽቆ ሲመሽ ቴቢ ከመኪና ወይ ከታክሲ ትወርዳለች፡፡ ልክ አሁን ከቤት እንደወጣሁ፣ ሳፈጥ እንዳላመሽሁ በደስታ ተጠግቼ ሳቅፋት፣

«አንተ ምነው? አትተኛም እንዴ? ሌላ ጊዜ እንዳትጠብቀኝ»

እንዲህ ብላ፣ በችኮላ ጉንጬን ጨምጭማ ገፋፍታኝ ቤቷ ልትገባ ትቸኩላለች፡፡

---

[28] አዝራሮቹ እስከ ዕንብረት ድረስ የተከፈቱ

(ገፋፍታ እንዳይመስልባት፣ እያቃቀፈች፣ እያዛጋች፣ 'ሂድዛ ሂድዛ' የውሽቷን እያለች:: ጠጥተን የጨረስነውን መሽከርመም፣ የማውቀውን፣ የምናውቀውን ያውም ሰሌን ላይ እንደ ቃሪያ አስጥተነው ደርቆ የበቃለት አፏን ቱና ላይ አስቀምጣ)

«ምናለበት ነገ አብረን ሲኒማ ብንገባ» እና «የተስፍሽ ልደት ነው እንገናኛለን ተባብለናል:: ለምን አብረን አንሄድም? ክሬመሪ ነው ደሞ» ......እንዲህ ያለ ጨዋታ የምትሰማበት ጆሮዋ አልነበረም:: ማን ወሰደባት?

## ማን ወሰደብሽ?

ትንሽ እንደተናቅሁ ዓይነት ተሰማኝ:: እንግዳ በሆነ ታሪክና እግዚአብሄር ሊተነብዩት ባልቻሉት መንገድ ያ እንደ እጄ ጋል የማውቀው ጡጦ ከጣልኩ ጀምሮ ያደግሁባት ሽሮሜዳ፣ የሰጠችኝን ፍቅሬን፣ የሰጠችኝን ቀላል እርጋታ የነጠቀችኝ መሰለኝ......

አንድ ቀን ማታ 1969 ውስጥ መሰለኝ እንዲህ ሆነ......አንዳንድ ነገር ሲደራረብና ቁርጡን ስናውቅ የበለጠ ይገባናል መሰለኝ:: የተረሳ መረጃ ሰብስበን ከዛሬ ጋር ደምረን ስናስበው:: ቤቴ ተንቀልቅላ መጥታ፣ እየጎተተች መኝታ ቤቴ አስገብታ እኔ ልደባብሳት ክንፌን ሳራግብ፣ ሊነድፋት የሚያንዣብብ የተቆጣ ተርብ እንደሆንኩ ሁሉ እየተከላከለች:

«በምሽት ሰላማዊ ሰልፍ ይደረጋል ተሳተፍ» አለችኝ::

«የምን ሰላማዊ ሰልፍ? ለምን በጨለማ?» አልኳት

«ማንም ይመጣል:: ምን አስፈራህ? የአገር ጉዳይ ነው:: የሕዝብ ጉዳይ ነው» አለችኝ:: በከንፈሮቿ ከንፈሬን ልትነካኝ እየተጠጋችኝ:: ይሄ አጠጋግ የማፍቀር ሳይሆን የማባበል ነበር:: ቴቢን እንደ እናቴ አደረጋት::

«በጨለማ ምን ይታያል? ማን ምን እንደሆነ ይታወቃል? ብሞት እንኳዋን ማን እንደሆነ አውቄው ልሙት......ሀሀሀሀ አይሆንም:: እነዚያ ማንሞች ደሞ እነማን ናቸው?» ስላት ልትስመኝ ያሸቋበበችው ልጅ (ከንፈሯ ጉቦ ሆኖ) እየተቆናጠረች ከክፍሌ ወጣች......

ሰላማዊ ሰልፍ ተጀምሮ ምሽት ላይ ታች ተራራ ሆቴል አካባቢ መፈክር ሲዘመር ስሰማ ቴቢ ትዝ ብላኝ፣ ምን ላደርግላት እንደሆነ አላውቅም......ከቤት ልወጣ ስል፣ አባቴ በሩን ዘግቶ ይዞ ፊት ለፊቴ ቆመ::

«የት ነው?» አለኝ

«አንድ ነገር ሆና እንደሆነ ቴቢን ልያት አባዬ......»

«አሁን ጥሩ ጊዜ አይደለም:: ተባረኪን ደሞ አሁን ብትወጣ አታድናትም:: ማንነው አንተን ለአዳኝነት የመረጠህ? እንዴት እስከዛሬ አልገባህም? አሁን እሷ ለማንም ግድ የላትም:: ለብቸኛ እናቷ ግድ የላትም:: ለብዙ ነገር ግድ የላትም:: ምርጫዋ ነው:: ማንንም የማዳን አቅም፣ ማንንም የመከላከል አቅም የለህም:: እንደ እናትህ አልቀርብህም:: ሮዛ በአንተ ሳንባ ነው የምትተነፍሰው:: ገባህ? በአንተ ልብ ነው ደም የምታገኘው:: እንደ እሷ ባታቀርበኝም እ? ለእናትህ በልና ስማኝ:: እኬ? ደሞም ቴቢ ብትወጣና አንድ ነገር ብትሆን የራሷ ምርጫ......ፐርሰናል ቾይስ[29] ነው» አለኝ::

በግራ እጁ ረም በብርጭቆ ይዞአል:: ተፋጠን ቆምን:: ፀሐይ ኩታዋን ለብሳ ወደማድ ቤት የሚያሳልፈውን በር ተደግፋ ቆማለች:: እናቴ ከተኛችበት ተነስታ ዐይኖቿን እያሸች 'ምን ሆናችሁ?' እያለች መጣች:: ብዙም ሳልከራከር፣ በአባቴ እውነት ተረትቼ፣ ወደ ክፍሌ ተመልሼ አልጋ ላይ በጀርባዬ ተጋድሜ አለምኩ......ቀይ ካባ የለበሰ ጥቁር ሞት ሽሮሜዳ ሰማይ ላይ እየሳቀ ሲንበለበል:: ካባው ጀርባ ላይ የልብ ስዕል ጥልፍ ነበር......

የጥይቶችን ጃዝ ሰማሁ......

ጣጣጤጥ

ጣጣጥ

ጡጠጢጡጡ

ጣጠ

ጣጣ

ጢጥ

ጠ

እንቅልፍ በአይኖቼ ሳይዞር አድሮ በጠዋት ተባረኪ ጋ ስሄድ 'ተኝታለች' ተባልኩ:: ዘልዬ መግባት እንደ ፈለግሁ:: በር ሰባብሬ አልፌ እተኛችበት ውጭእሷ መጥፋት እንደፈለግሁ:: በጎሕ ብርሃን አየሁ ሰፈሬን......በመንገድ ላይ አስፋልት መሃልና ዳር ትልቅ የደም ፊርማ ነበር:: ወሬው ሲቀርልኝ የአንድ ወጻጂ ሬሳ ከመንገድ ላይ ተነስቶ ደረስኩ:: መንገደኛ ቆሞ ከንፈሩን ይመጠምጣል:: ቃል ሳይተነፍሱ እያ-ማተቡ ወደ ከተማ መሃል ይንሸራተታሉ:: ነገሩኝ:: ደበበ ሞተ አሉ:: ደበበ ግንቡ:: ደበበ ጂምስ ብራውን:: የሞተበት ቦታ ከአስፋልቱ መሃል

[29] የግል ምርጫ (personal choice)

በግራ በኩል እስካለው ቦይ ድረስ የፈሰሰው ደሙ ውሃ ቢሆን የአንድ ጋሻ መሬት ሸንኮራ ያለመልማል:: ከአስፋልቱ መሃል በግራ በኩል እስካለው ቦይ ድረስ:: መንገዳችን ዘማማ አይመስለኝም ነበር:: አስታውሳለሁ እንጠጠ ወጥተን ስንመለስ ወይ ስንደበር የጂምስ ብራውንን ፐሊዝ ፐሊዝ ሲዘፍን......እንደ ጦር የሚወጉ ትናንሽ ዐይኖች ነበሩት......

ማታ ላይ አባቱን ሃምሳ አለቃ ጥላሁንን እናቱን እትዬ ምንትዋብን እና ሁለት እህቶቹን ላይ ሄድኩ:: ቤታቸው ጭር ብሎ ነበር:: የደበበ ቤት የተሰራው እኔ ሳውቅ በቆርቆሮ፣ በጭቃ፣ በእንጨት፣ በሳቅና በጫጫታ ነበር:: አንድ ጠባብ ሳሎን ውስጥ ብቻቸውን እየተያዩ ተቀምጠዋል:: አልቅሰው የደከሙና ለመቀጠል ቀጠሮ ያላቸው ይመስላል:: ስመጣ በቀያይ ስምንት አይኖቻቸው አዩኝ:: እህቱ ማሚ ዘላ አቀፈችኝ:: እያለቀሰች:: እኔም ሁሉ ነገር ተጨማምሮ ማልቀስ ጀመርኩ:: አሩብ ሰአት እያለቀስን እየተናፈጥን ምንም መናገር ሳንችል ቆየን::

ከመሃል አባቱ በፀጥታ የሚወርድ ዕንባቸውን ከፊታቸው ላይ እየጥረጉ......

«ሁለት ጥይት ነው የመታው:: ሁለቱም ሽጉጥ ነው:: አንዱ ከሩቅ የተተኮሰ ክሊበር ነው:: ግራ እግሩን ባቱ ላይ ሞድርፎታል:: ይሄ የጠላት በትር ነው:: ሁለተኛው ከጎኑ ነው:: በግራ ጎኑ ከነመረቁ ነው የተተኮሰበት:: የወዳጅ መሳይ ጥይት ነው:: የሚታመን ሰው:: ዓላዛር ምንድነው?»

«እንጃ» ትከሻዬን ከፍ ዝቅ አደረኩ

«ብልጥ አደርገው ነበር:: ደቢ ብልጥ ነበር»

*ያ አይነት ቲያትር መስጠአቸው ያጨበጨቡ ብልጥነት የላቸውም* ልበላቸው? ዝም አልኩ:: ማሚ ከንዴን ጨምድዳ ይዛ ተጠጋችኝ:: አቀፍኳትና አንገቴን አናቷ ላይ ደፋሁ:: የመልካም ዘመን ዞማዋ ውስጥ ፎሮፎርና አቧራ አለ:: ይሄም ሆኖ ያብለጨልጫል:: ስርቅታዋ ይንጠኛል:: ሁሉ ነገር ሲሰበሰብ የእሳት ገሞራ ፍንዳታ እንደመዋጥ ነው:: ብዙ ለቅሶና የትም የማይደርስ ውይይት ከመከሰቱ በፊት የማላውቀውን ተናግሬ የበለጠ ደማቸውን እንዳላፈላው ሃዘናቸውንም እንዳላጠልቀው ተነስቼ ወጣሁ::

*

የቴቢን መሰወር እየለመድኩት ብመጣም፣ ለብቻዬ ስሆን በተለይ ቅዳሜና እሁድ......ሱስና ተስፋ አለመቁረጥ እያብከነከኑኝ ከበረንዳዬ ላይ ወደ ተባረኪ ቤት እሁንም እሁንም እያለሁ......

……ጠዋት ላይ የተሰጡት ቢጫና ቀይ ቀለም ያለው ፎጣና ሁለት ነጭ አንሶላዎች የደረቁ ቢሆንም አልወረዱም። የተሰጡበት ሽቦ ረግቦ አንሶላው መሃሉ ላይ ተሰብስቦአል። ፎጣው ወደ ግራ ተንሸራቶ ወርዶ አንሶላውን ተጠግቶአል……

ቁና ቁና እየተነፈስኩ አልጋ ላይ እንጋለላለሁ……የምጠጣው ውሃ እቀዳለሁ(ግን አልጠማኝም) የቀዳሁትን እረሳለሁ፣ ረስቼም አንስቼ ለመጠጣት እያሰብኩ ተመልሼ አልጋ ላይ በጀርባዬ እወድቃለሁ (ዓይኖቼን የውሃ ብርጭቆ ሳይሆን ነጭ ኮርኒስ ሲያጤኑ አገኛቸዋለሁ)

የካሴት ሙዚቃ አስገባለሁ (የ ቢ ጂስ *ስቴይንግ አላይቭ*)

አእምሮዬ በሻሞ ሙሉ ነው።

አብሬ ልዘፍን እየሞከርኩ የቀዳሁትን ውሃ ለመጠጣት አስታውሳለሁ (*ቴቢ በጠራራ ፀሐይ ወደ ቤቷ የሚወስደውን ዳገት አንገቷን ወደ መሬት ሰበር አድርጋ ስትወጣ*……)……

ውሃውን ወንበር ላይ ተቀምጬ ስጠጣ(*ቴቢ ቀና ብላ ቤቴን ታያለች* ……)……

ሳሎን ሄጄ በመስኮት ወደ ውጭ አያለሁ……አስፋልት ላይ ልጆች ኳስ ያለፋሉ……እንደሚቻል ሁሉ ወደ አጥር ስር ተንጠራርቼ አያለሁ…… ***ስቴይንግ አላይቭ……ስቴይንግ አላይቭ***……

*አሁን ቤቷ ገብታ ይሆን እንዴ?* በግራና በቀኝ አፌ ጠርዞች ውሃ መንገድ ሰቶ ይፈሳል። እሱን እየጠረግሁ መስታወት አያለሁ። የደረቁ ከንፈሮች፣ መስመሮች የተረገዙበት ግንባር……***ስቴይንግ አላይቭ……አአ አአ***……መኝታ ቤቴ ተመልሼ በሆዴ ወድቄ ቴቢን አስታውሳለሁ። *እዚህ ቤቷ፣ እዚህ ጋ ናት*። የክፍሏ ግድግዳ እዛ ጋ በሰባት ዓመቷ የተነሳችው የወላቃነቷ ፎቶ……ወደዚህ ያረጀ ፀጥታ ድምጼን አጥፍቼ አፈተልካለሁ። ካሴቱን እገለብጣለሁ……እጅ ይኑረኝ ጣት ይኑረኝ ምን ልብ ብዬ……*የቴቢ ጣቶች የቀይ ወጥ መረቅ የመሰለ የቀለም ቆብ ደፍተው*……

ከተደረደሩት መፃሕፍት አንዱን አውርጄ አርዕስቱን አነባለሁ፡ *ይሄን መግለጥ ትወድ ነበር*……

በጀርባዬ ሆኜ እግሮቼን አያለሁ……

ግራ እግሬን አያለሁ (የግራ እግሬ ካልሲ አፍንጫው ላይ ረጥቦአል) *ከየት መጣ ውሃው?* የምጠጣበት ብርጭቆ ተከንብሎ መሬት ላይ የረገፈ ጀርሲ ሱሪዬ ላይ ወድቆ……በአፉም የወጣው ውሃ ሳይመጠጥ ሸረር ብሎ ……*ለምን ውሃው ወደ ታች ይወርዳል? የተኛሁት ዳገት ላይ ነው?*

በጠርሙስ ፍሪጅ ውስጥ የተቀመጠው ውሃ አልቆአል *መቼ ጠጣሁት?*

ውሃውን ለመሙላት ወደ መታጠቢያ ቤት ሳልፍ በተከፈተው ዋና በር የደረቀ ቅጠል በነፋስ እየተገፋ ወደ ቤት ውስጥ ይገባል *የባሕር ዛፍ አይደለም*......ብርጭቆውን ጠረጴዛ ላይ አስቀምጬ ቅጠሉን ከወለል ላይ አንስቼ ወደ ውጭ እወጣለሁ......*አሁን መጥታ ይሆናል*

አንሶላውን በሃሳቤ ዘርግቼ ጠይምነቷን እዛ ላይ አፈስዋለሁ (በጎን ተኝታ)......ከርዳዳ ፀጉሯ ጡቶቿ ላይ ከርፈፍ ብሎ:: የሴትነቷ አፍሮ:: በቀስታ ስገባና ስወጣ:: ዐይኖቿ በኩርማን ተከድነው፣ አፏ ሳያቋርጥ ተከፍቶ......ደቃቃ መላዕክት ከሆዷ በአየር ተመስለው ይወጣሉ...... የማያቸው እኔ ብቻ ነኝ......*መጥታ ይሆን?*

ወደ ቤቷ እያለሁ......

የአንሶላው ነጣ ያለ በረኪና ያነደደው መሃል......*ሁለተኛው የት ሄደ?*

የቀረው ብቸኛው አንሶላ ከሽቦው ጋር እንደ ተሰፋ ሁሉ በፀጥታ ተጣብቆ......በጀርባዬ አልጋ ላይ እንደ ተመታ ሁሉ ወድቄ......

የተጨበጠ እጄን ስከፍት መዳፌ መሃል በላቤ የተሰባበረች ከቤት ውስጥ የለቀምኳት ስደተኛ ቅጠል......

እንዳንዴ ምናልባት ልረሳት እችል እንደሆን ብዬ ጀርመን ኢኒስቲትዩት ላይብረሪ እሄዳለሁ (ከቅድስት ማርያም ቀዝቃዛ የዕድ ጥላ ሞቶች ሰላም መች ወርዶልኝ)፣ የጎይተን ፎስት በከፊል ልቦና አነባለሁ (ግልብ ዕውቀት በጥቁር ቡጢው እየደጋገመ ይቀጠቅጠናል):: እዛ አልፎ አልፎ የማገኘው ተፈሪ መኮንን ት/ቤት ክላስሜቴ የነበረ፣ ድምፁን በቀን ያጠፋ፣ በሌሊት ፓራሹት የሚሰቅል ኮሚኒስት ሙላት......ሙላት ተመስገን፣ ሙላት ጆሊው:: ጆሊነቱን፣ የልጅነት ፌዝና ፊንታውን ለፖለቲካ የለገሰ......ምን አይነት አስማት ነው? ምን አይነት መስተፋቅር ነው? *የተደገመብህ በልብህ ላይ ነው በምላስህ ላይ?*

«የት ጠፋሽ ግን ሙሌ? ቡና ውሰጅ»

«ምን እባክህ ቀበሌ ሊገለን ነው:: አንድ ነገር ላውራሽ:: ግድ የለህም መቼም......»

«ምን?»

«የሚኒሊክ ትምህርት ቤትን ዳይሬክተር ታውቂዋለሽ? ያ ባንዳ ሽንኑ እርምጃ ተወሰደበት:: ልወደድ ባይ ቆማጣ......»

ምን ልበለው? ልውደደው? እሱን ልምሰለው? ልጣላው?

«ስምቼ አለሁ……ልሂድ ቤት ማዘርን እመጣለሁ ብዬአት ነበር (ውሸቴን ነው)»

«በአንተ ዕድሜ ማዘር ትላለህ?»

«ሃሃ በብብቴ ምን እንደቀረቀርኩ ታውቃለህ? ጡጦ»

«በቃ አንተ እንደ ፎገርክ ልታረጅ ነው»

«ቻው ቺፍ……እዚህ ነኝ አልጠፋም እንገናኝ»

«በል ቻው»

በየግድግዳው ላይ የተፃፉትን የፖለቲካ ወለሎታት እያንቸለቸልኩ፣ ልቤ አልቆርጥ ብሎ(የልብ ፀባዩ አይለወጥም እንዴ?) ጌታው እንደ ጠፋበት ስደተኛ ውሻ ተመልሼ ቴቢ ቤት ቆርቆሮ አጥር ስር በዝምታ እያላዘንኩ መምጫዋን እጠብቃለሁ:: አፌን አውጥቼ ባልናገረውም ልቤ ይፈራል ገና ለገና *ብትሞትስ?* እያለ:: ገና ለገና *ብትታሰርስ?* እያለ::

ማስታወስ ማስታወስን ኮርኩሮ ያስነሳዋልና አንድ ቀን ምን አለችኝ?

ጠዋት እቤቷ መጣሁ---አልነበረችም:: ከሰዓትም በምሽትም---አልነበረችም:: ማታ ላይ እንደገና ለአራተኛ ጊዜ ተመልሼ መጥቼ አገኘሁዋትና (እንዴት ደስ ብሎኝ ነበር!) ስፈልጋት እንደዋልኩ ስነግራት ከአምስት ደቂቃዎች በኋላ ቤቷ መሄድ እንዳለባት ስትነግረኝ ደሜ ፈላ::

«እኔን ጠልተሽኛል» አልኳት

«ለምን?»

«እንጃ»

«ሌላ ሌላ የምሰራው ነገር አለ:: መሰለህ እንጂ.»

«ምን?»

«ብዙ የሚያሳስበኝ ነገር አለ»

ፀጉሯን ሰብስባ ወደ ኋላ አስራለች:: በዚህም አንገቷ ቀጥ ብሎ የወጣ ሰንደቅ ይመስላል:: የመንገጭላዋ ቅንፍ:: የአገጭዋ አሾዋሾዋል:: ከንፈሮቿ ደብዛዛ ቅላት አላቸው:: ከተሳሳምን በኋላ እንደሚሆኑት:: ከፊቱ ተካፋች የሆነ የገርዳሜ ቀሚስ ለብሳለች:: እግሮቿ ብልጭ ድርግም ይላሉ:: ትታኝ ለመሄድ ስትሞክር እጅዋን ያዝኳት:: የያዛት እጇንና ግራ የገባው ፊቴን በመገረም እየቸኘና:

«በእናትህ የምሄድበት አለ:: ለምን ልጅ ትሆናለህ!! ወጣቱ እየተረሸነ እንዲህ ሳደርግ ቅር ይለኛል፣ አንተ ደሞ ከዚህ የተለየ ሌላ ነገር

*አታስብም?» ከዚህ? ፍቅረኞች ከመጓተት በላይ ምን መስራት አለባቸው? ወረቀት መበተን?*

ተገርሜ እጅዋን ለቀቅሁት:: አንገቴን ሰብሬ በእፍረትና በዝምታ ዓላባርን ጠየቅሁት:

***ምን አደረግሁ?***

***ምን አጠፋሁ?***

***ምንህ የልጅ ስራ ነው?***

የተባረኪ ከእቅፌ መሸሽ ከጠበቅሁትና ልቤ ከሚቀበለው በላይ ሰላም ነሳኝ:: በሆነ መልክ ግልፅ ባልሆነ ሰበብ ከእጆቼ መሃል ደስታዬ እንደ አሸዋ እየሾለከ፣ እንደ ጭድ እየተቃጠለ እጄን ብዘረጋው መዳፌ ላይ አመድ የማገኝ ይመስለኛል:: ብጠጣም አልሰከርም ነበር:: መስከር ጀመርኩ:: ለመሆኑ ሳይነጫነጩ አገርን መለወጥ አይቻልም? ከባ እንደዚያ የሚያድገው፣ አገዳ የሚረዝመው፣ ገበሬዎች ከስሩ አጎንብሰው ስለ ጮሁበት ነው?

ብዙ ሳይቆይ አንድ ማታ ወደምሸሸው ስህተት እንዳልመለስ አድርጋ ነዳችኝ፣ በከፊል የእልህ ነዳጅ ሞልታ:: ወደ አልማዜ:: ደስታ በትሪ መዘንጋትን በመሶብ ወደምትሰጠኝ:: ተፈቅፍቃ ከላመች ጉድጓዷ እረፍትን ለመጠጣት ማርኩ:: ስንቴ ትን አለኝ? በተኮማተረ ልቦና በተሸበሸበ ግንባር የአሮጊት ማሕፀን አለመለምኩ……የልጅነት መረቴን የማይሆን ስፍራ ደፋሁ……ትራሷ ላይ ተጋድሜ……የበረደ ***** መዳፏ ላይ እንደ እባብ አርፎ፣ ገና ባልጠገበ ጉጉት እሱን እያጫወተች ……አስባለሁ ደሞ ቴቢን……ወደ ተኛሁበት ክፍል በተገኘው ቀዳዳ ዘፈን ይመጣል……*የሐረር ልጅ ናት ወጣቷ ጀጎል ነው ቤቷ*……ግራና ቀኝ ተከፍላ እላዬ ታርፋለች:: 'ቃል ገብተህ ምነው ጠፋህ? ያቺ ፋራ ደበረችህ?' '*እስኪ ዘም እንበል አለ ገርማሜ*'……በሰባት ከተሞች ወደ ላመው ማድጋዋ እሄዳለሁ……'እህ እህ እህ ገርማሜ ጋር ትገናኛላችሁ? ምነው ጋግርታም ሆንክ?'……

……በከፊል ትምህርት፣ በከፊል ትከዛ፣ በከፊል በሚያስጮህ ስካር ……ግራ ቀኝ ሕይወት በሕቡዕነት በሰለጠነችበት ዘመን……እኔን መሰል ልጅ እግሮች በየጎዳናው እንደ ቆሸሸ ጨርቅ ሲወድቁ……ራሳቸውን ሲያቀጣጥሉ……በተፈሩ ጎዳናዎች ላይ እጆቼን ሰሪ ኪሶቼ ከትቼ በግድ የለሽነት ተራመድኩ……ፖለቲካ ባልወድም ጎዳና ላይ ከሚፈስ የአብዮት ዘፈን ተበድሬ አፏጨሁ……

……እንግዳ የሆነ አዲስ አለም ነበር:: እንዲህ ሲጣጣል ያለፈውን ዘመን የኖርንበት አይመስልም:: ባለፈው ዘመን አባቶቻችን የኖሩበት፣ እኛም ልጅ ሆነን ጭቃ ያቦካንበት አይመስልም::

# ሲቃጠል አንድ

አንድ አርብ ምሽት ላይ (ቀኑን ልረሳው አልችልም) ከትምህርት ቤት መጥቼ ዕቃዬን አልጋዬ ላይ ወርውሬ ከእዝራ ጋር ለመጫወት ታዚና ሆቴል ሄድኩ:: ታዚና በብዙ የክፍለ ሃገር ከተሞች የምናያቸውን ምስኪን ሆቴሎችን ብትመስልም፣ የተወዳጅነቷ መሠረት ከከተማው መሃል ወጣ ያለችና ደንበኞች ማንም ሳይታዘባቸው፣ የፈለጉትን ማድረግ የሚችሉባት ቦታ በመሆኗ ነው:: የክፍሎቿና የአልጋዎቿ ንፅሕና ትልልቅና ዝነኛ ከተባሉ ሆቴሎች እንደማያንስ ብዙ ባለጌና እንግዳ መስክሮላታል:: ልጃገረዶች እዚህች ቦታ መጥተው ሴቶች ሆነዋል--ሴቶች እዚህች ገላ የመንገድ ዳር ሆቴል ከውሽሞቻቸው ፀንሰው ሄደዋል:: ነጠላ ተከናንበው ገብተው ነጠላ ተከናንበው የሚወጡ ጀማሪዎች......ማጅራት ባበቀሉ አቶዎች እዚህ ተሰብረዋል......ራሳቸውን ደፍተው እያለቀሱ......ወደ ማይጋርዳቸው ጨለማ ሲጠፉ ታዝቤአለሁ......

......የተወራውን ሁሉ አይቼአለሁ::

ሆቴሏ 12 መኝታ ክፍሎች፣ አንድ ትልቅ አዳራሽና ባር አላት:: ባሩ ውስጥ ስድስት አዳዲስ ባለጌ ወንበሮች አሉ:: የተቀሩት ወንበሮች የዛገ የብረት ቢጋር ያላቸው፣ ጣውላ ወለል ላይ ሲንፏቀቁ የሚረብሹ፣ ብዙ ጊዜ ሰው የማይጠቀምባቸው ነበሩ:: እንግዶች ብዙውን ጊዜ ምግብ የሚያዙት መኝታ ክፍል ገብተው ነው:: ሁሉም ያሉት ከሆቴሉ ጀርባ ሲሆን ከፊት ለፊታቸው የመኪና ማቆሚያ ስፈ ኮረኮንች አለ:: በስተቀኝ አልጋ አከራዩ ጌቾ የማይለቀውን ጦር ማስቲካ እያላመጠ ደንበኛ የሚጠብቅባት ቢሮ አለች:: እዚህች ነጠላ ክፍል መቃን ላይ በአማርኛ 'ቢሮ' በእንግሊዘኛ ደሞ office የተፃፈባት ማስመሪያ የመሰለች የቆርቆሮ ስሌዳ ተሰቅላለች:: የቢሮዋ ስፋት ሶስት በአራት ቢሆን ነው:: በስተግራ አንድ ጠቆር ያለች የእንጨት ወንበርና ከጎኗ ደሞ የእሷን ዓይነት መልክ ያላት አሮጌ ጠረጴዛ አለች:: እዚህች ጠረጴዛ መሃል ትልቅ የክርታስ ልባስ ያለው መዝገብ አለ:: የመዝገቡ የወረቀት ቅጠሎች ሁልጊዜ ደርቦቹ የባዘቱ አመዳም ናቸው:: አንደኛው ግድግዳ ላይ ሁለት

አመት ያለፈው በጥቁር ጠቃጠቆዎች የተሸፈነ የአየር መንገድ ካሌንደር አለ:: ግድግዳዎቹ ሁሉ በየአመቱ ቢጫ ቀለም ይቀባሉ:: ጌች ኪሱ በየጊዜው እየተዘነተረ በየጊዜው በመርፌ የሚሰፋው አረንጓዴ የቴትሮን ካፖርት ከጠዋት እስከ ማታ ይለብሳል:: ከእሱ ቢሮ ጎን እዝራ ሆቴል ስራ ላይ ከሆነ ቀይና ጥቁር ቀለም ያላት (በሁዋላ ሐምራዊ ቀለም የቀባት) የስፖርት ብስክሌት ቆማ ትታያለች:: ከጅርባ በኩል ጠባብ የሆነች ስፈረተኛና ቤት-አወቅ የሚያልፍባት እንደነገሩ የተሰራች በቆርቆሮ በር የተከለለች ቀዳዳ አለች:: እኔና ተባረኪ ጨለማ ተገን አድርገን እንመጣ የነበረው በዛ በኩል ነው::

ጌች ያን ዕለት ቢሮው ፊት ለፊት በረንዳ ላይ ቆሞ ሲሽ[30] ይለብጣል:: የማይቀረውን ማስቲካ እያኘከ:: ጌቾ ታች አምስት ኪሎ የቅድስት ማርያም መዘምራን ሆኖ ነው እዝራን የሚያውቀው:: የጌቾ አንዱ ፀባይ በሰው ለመታመን መጣር ነው:: ደንበኞቹን ሲያነጋግር ቆሞ እንደሆነ ጎንበስ ብሎ፣ ተቀምጦ እንደሆነ ተነስቶ ነው:: የነጋዴ ብልጠት ሳይሆን ያደገበት ነው:: ሁልጊዜ ስንሮግረው ('ቱ ታይምስ ታጥፌሽ ወይም እንደዛ ያጎነበስሽው የሴትዮዋን ፓንት ልታዪ ነበር?' ስንለው 'ከቅድስት ማርያም መዘምራንነት የተረፈኝ አንዱ ስነስርዐት ነው' ይላል:: ያለ ደረሰኝ ገንዘብ ተቀብሎ ሳያጎድል ለጓደኛው ለእዝራ ማታ ላይ ያስረክባል::

«እዚዬ ዛሬ ለምን አልመጣሽም?» አለ ዜማ ባለው አማርኛ ሰላምታ ተባብለን እንደ ቆምን

«ቢራ ልግዛልሽ፣ አንዱ ደንበኛ ሃያ ብር ቲፕ ገፋልኝ» አለኝ ቀጠለና

«ሃያ ብር? አባትህ ነው ምንድነው? ማን ይጠላል፣ አምጣው አቦ...... ይበርዳል አይደል:: አያምርብህም 'ግፋልኝ' ስትል»

«ተወኝ እባክህ ዘመኑ ያስጤሳል ያናግራልም:: አንድ አሮጌ የኤሌክትሪክ ማሞቂያ ገዝቼአለሁ አሮጌ ነው ግን:: እሷን ተግ አደርግልሃለሁ»

«እዝራን አይቼው መጣሁ......ቢራውንም ይገፌ» አልኩና ብር ተቀብዬው ወደ ቡና ቤቱ ሄድኩ

እዝራ ማድ ቤት ከሁለት ሴት ሰራተኞች ጋር ቆሞ ስለ አረረ ወጥ ያወራል:: ሰላም ተባባልን፣ ግን ሊያወራኝ ፋታ አልነበረውም:: ወደ ባር ሄድኩና አንዷን አሳላፊ ቢራ እንድትሰጠኝ ጠይቄ እሱን እስኪታመጣልኝ

---

[30] ሲጋራ

እየጠበቅሁ ዞር ስል፣ በቀኝ ጥግ ቴሌቭዥን ከተሰቀለበት ግድግዳ ስር አንድ መላጣ ቀጭን ሰውዬ ለብቻው ካርታ ሲጫወት አየሁ:: ከፊት ለፊቱ ሙሉ ቡጥሌ ቢራና ባዶ ብርጭቆ አለ::

ልጅቷ የከፈተችልኝን ቢራ ይዤ ወደ ጌቾ ልሄድ መንገድ ጀመርኩና:

«ወንድም!» አልኩ

ቀና ብሎ አየኝ

«ካርታ እዛ ጋ ለምን አንጫወትም አብረን?» አልኩት

በዝምታ ለአፍታ ከላይ እስከ ታች አየኝና:

«ምን ትጫወታላችሁ?» አለ

«የፈለከውን:: ቁማር አይደለም ግን»

«ትንሽ ሳንቲም ይኑርበት»

«እናያለን»

እየሳቀ ከተቀመጠበት ቡጥሌውን ብቻ ይዞ ተነሳ:: ያልጠበቅሁት ዓይነት ቀጭን ረዥም ሰው ነው:: ሲቆም እንደ አንቴና ተዘረጋጋ:: ከቡጥሌው ጋር ብርጭቆውንም ደርቦ ለመያዝ አስቦ ከራሱ ጋር አንገራገረና ተወው:: እንደ ተጠጋኝ ካርታውን ኪሱ ከተተና:

«አለማየሁ እባላለሁ» አለኝ:: ካርታውን ኪሱ ከተተና ሊጨብጠኝ እጁን ዘረጋ::

«ዓሳዛር» አልኩት:: በጣም ጠንካራ እንደ እንጨት የከረረ እጅ አለው::

«ስማችን አንድ ነው:: በአ ይጀምራል» አለ:: ቀሽም ቀልድ ብትሆንም ሳቅሁለት:: ተያይዘን በጀርባ ወጣን::

«እዚህ አካባቢ ነህ?»

«ከባሕር ዳር ነው የመጣሁት:: አዲስ አባ ቀስ ብዬ ልግባ ብዬ ነው»

*('ቀስ ብዬ ልግባ ነው' ብሎ ነገር ምንድነው? ገብቶ የለም?)*

«ሰፈሬ እዚህ ነው» አልኩት

«ጥሩ እንግዳ አስተናጋጅ ናችሁ»

«እዚህ ሽሮሜዳ የእግዚአብሄር ሌላው ስሙ 'እንግዳ' ነው:: አዲስ 'ቀበሌ' የሚባል ነገር አለ አይደለ? በአብዮቱ የመጣ፣ የእኛ ቀበሌ ነው ለመጀመሪያ ለነዳያን መጠለያ የሰራው:: መንገድ ላይ የሚያድር የለም እዚህ» በዚህ አባባሌ የተገረመ አይመስልም::

«ፍትህ ያለበት ቦታ ነው በለኝ» አለ እየሳቀ፡፡ አፉ ውስጥ ብዙ ጥርስ ያለ ይመስላል፡፡ ማለት ውስጡ ጥርስ ብቻ ያለ ይመስላል፡፡ ሰልካካ መልከ መልካም ፊቱ በነዚህ በተከማቹ ጥርሶቹ ይዋጣል፡፡ ይሄ በትንሹ የሚያስደነግጥ ስሜት ይፈጥራል፡፡

«እውነቴን ነው ስፈሬ ስለሆነ አይደለም፡፡ እስከ ዛሬ ሊሳ ነው»

ጎን ለጎን ሆነን ልክ ለረዥም ጊዜ እንደምንተዋወቅ ሁሉ እየተፎጋገርን ወደ ጌቾ ቢሮ አመራን፡፡ እዛ ከመድረሴ በፊት ጮክ ብዬ፡

«ስማ ጌቾ! ካርታ የሚጫወት እንግዳ አምጥቼአለሁ!» አልኩት

ጌቾ ከቢሮው ብቅ ብሎ ዐየንና፡

«ደግ» ብሎ የጨረሰውን ሲጋራ ቡሽ በልማድ ወደ ሚወረውርበት ወርውሮ ካልተያዘ መኝታ ቤት ሌላ ወንበር ሊያመጣ ሄደ፡፡ ተቀምጥን (ጌቾ አንዳንዴ እንግዳ ሲመጣ ለማከራየት መነሳቱ አልቀረም) ካርታ እየተጫወትን ወሬአችንን ቀጠልን፡፡ ሰውዬው በአለም ላይ የሚወደው ቦታና አገር ባሕርዳር ይመስላል፡፡ የጣና ሐይቅ አሳ ጥብስ በዐይኑ እየመጣ የካርታ ጨዋታውን እንዳበላሸበት ይነግረናል፡፡ ከመሃል ቸርነት ካመሸበት አምሽቶ ወደ ቤቱ ሲያልፍ ነፃ ቢራ ስለተገኘ ብቻ አብሮን ሆነና ስንሳሳቅ፣ ስንተራረብ፣ ስንጫጫህ ቆየን፡፡ አለማየሁ ባሸነፈው በበላን በራሳችን አምስት ብር የ 'ደህና እደሩ' ቢራ ገዛልን፡፡ እኩለ ሌሊት ሩብ ጉዳይ ላይ ሰአት እላፊ ከመድረሱ በፊት ሞቅ ብሎን ተለያየን፡፡

*

በሁለተኛው ቀን ላይ ማታ ተባረኪ 'ጓደኛዬን እጠይቃለሁ' ብላ ወጥታ አምሽታ ከትደነቂያለሽ ጋር በረንዳ ላይ ቆመን እያወራን እስክትመጣ እንጠብቃታለን፡፡ ከምሽቱ ሁለት ሰአት አልፏል፡፡ 'ይሄ የማታ መቀጣጠር አይሆንም ብላት አትሰማም፡፡ ልጇ ጊዜው ተለውጧል' እያለችኝ ተባረኪ የአጥር በር ከፍታ ገባች፡፡ እናቷ ድምፅዋን ዝቅ አድርጋ እየተራገመች ሁለታችንንም ለበረንዳው ትታን ቤት ስትገባ፣ ከመናኸሪያ ሆቴል አቅጣጫ የሰው ጩኸት ሰማሁ፡፡ ቀላል ጩኸት አልነበረም፡፡ ሽሮሜዳዊ ዓይነቱ ነገር የለውም፡፡ የለመድኩት ጩኸት አይደለም፡፡ ሽሮሜዳ የለመድኩት ጩኸት በአብዛኛው እናትና አባት ያመሸ ልጃቸውን ቤት እንዲገባ ወይ ለምሳ የዘገየ ልጃቸውን ምሳውን እንዲበላ ሲጠሩት ነው፡፡ ይሄ ከኡኡታ በላይ ነው፡፡ 'ኡኡታ እንዴት ከኡኡታ በላይ ይሆናል?' ተብዬ አልጠየቅ፡፡ ብቻ እንደዛ ነው፡፡ በሆነ ተአምረኛ የተፈጥሮ እብደት የእንጠጠ አየር የቀጠነ ይመስላል፡፡

«ምንድነው?» ብዬ ደንግጬ ልወጣ ስል ተባረኪ የኮቴን እጅጌ ጎትታ ይዛ ወደ እሷ አስጠጋችኝና፡

«ተው» አለችኝ

«ልይ ምን እንደ ሆነ»

«ለምን?»

ኡኡታው ይንቀለቀላል:: ኡኡታው ቃል ሆነ:

«ወይኔ! ወይኔ! ወንድሜን!» የሚል

ተባረኪ እስጠግታ አቀፈችኝና እንደ እኔ በጉጉት ጩኸቱን መከታተል ጀመረች:: እንዲህ አስጠግታ ስታቅፈኝ ብዙ ጊዜ ሆነኝ:: ጠጋ ብዬ አንገቷን መንከስ ፈለኩ:: ነክሼአት ቆዳዋን እየመጠጥኩ ለሰአታት መቆየት:: ግን ሽሮሜዳ እንዲህ ተጩሆ አያውቅም:: በዝምታ ቆሜ ማዳመጥ ደስ አላለኝም:: ያደግሁበት ሰፈር ነው:: በዚህ ዓይነት ድምፅ የሚያለቅስ ሰው ባይቀርበኝም የማውቀው ሰው ነው:: 'ቴቢሽ ቆዩ' አልኩና ከእቅፏ ወጥቼ ደረጃውን ሳልወስድ ከበረንዳው አምባ ላይ ዘልዬ የአጥር በር ከፍቼ ወጣሁ:: ጩኸቱን ወደ ሰማሁበት ወደ ግራ ታጠፍኩ:: የእነ ተባረኪን ግቢ አጥር አልፌ ወደ አስፋልቱ ስሻገር ኡኡታው ከዋናው ጎዳና ተገንጥላ ከተሰራች መንገድ እየመጣ እንደሆነ አየሁ:: አንድ ሰስት መኪናዎች በእኔና በሚጮኸው ሰው መሀል ቆመው ማን እንደሚጮህ እንዳላይ ከለሉኝ:: የመጀመሪያውን የተባዕት ጩኸት ሴት ተቀላቀለችው:: በቆመው የአንዱ መኪና ጀርባ ዞሬ አስፋልቱን አቋርጬ ስጨርስ መንገድ ዳር እግሮቹ ወደ አስፋልቱ ጭንቅላቱ ደሞ ወደ በይ ሆኖ የወደቀ ሰው አየሁ:: ከአስፋልቱ በኩል ስለ መጣሁ በደብዛዛው የመንገድ ብርሃን የወደቀው ሰው ማን እንደሆነ መለየት አልቻልኩም:: ቆሞ የሚጮኸውን ሰውዬና የምታለቅሰውን ሴትዮ ግን አውቃቸዋለሁ:: እነሱን እንዳየሁ የልቤ ምት ለአፍታ ሲቆም ተሰማኝ:: እነዚህን ሰዎች ሲጮሁ ከዚህ በፊት አይቼአቸው አላውቅም:: ሌላ ፕላኔት፣ ሌላ አህጉር የገባሁ መሰለኝ:: ሕልም መሰለኝ:: ለአፍታ ቀጥ ያለው ልቤ በፍጥነት መንተክተክ ጀመረና አቅለሸለሸኝ:: አዞረኝ:: በቀስታ እየተራመድኩ በሆዴ 'ጂሰስ ጂሰስ ጂሰስ'[31] እያልኩ ወደ ወደቀው ሰውዬ ተጠጋሁ:: ከአናታቸው ስር ደም ይወርዳል፣ አፋቸውን ወደ ሰማይ ከፍተዋል:: ሁለቱም እጆቻቸው ተጨብጠዋል:: ጭንቅላታቸው አጠገብ መሬት ላይ ተንበረከኩና ጠራሁዋቸው:

«ጋሼ መክብብ! ጋሼ መክብብ!»

በልቤ መሞታቸውን ሙሉ በሙሉ አምኜአለሁ:: ግን ደሞ ማመን አልፈለግሁም::

---

[31] ኢየሱስ ኢየሱስ ኢየሱስ

«ወዬ!» ብለው ከተዘረሩበት ተነስተው ሁሉ ልጅም ሆኚ ይሁን አድጊ እንደሚያደርጉት እናቴን በሁለት እጆቻቸው እየነቀነቁ ግንባሬን የሚስሙኝ መሰለኝ:: ግን «ጋሼ መክብብ!» እያልኩ መጮኼን አላቆምኩም:: እነዚህ ቃላቶች ስሜታቸውንና ጉላታቸውን ሳይለውጡ በራሳቸው ጉልበት ከውስጤ መውጣት ቀጥለዋል......

በዚህ መሃል ግርማቸው ከጨለማ እየሮጠ መጥቶ እኔና ሬሳው አጠገብ ቆመና እንዴ ባልጠበቅሁት አይነት ከፍታ 'አባባ!' ብሎ ጮሆ እላያቸው ላይ ወደቀ:: ሁላችንም መጮህም ይባል ማልቀስ አንችልም:: ሁላችንም እያጓራን ዓይነት ነበርን:: ልምድ ይጠይቃል መሰለኝ:: እኔን ሳለቅስ አይቶኝ አያውቅም:: እኔም ከዛን ቀን በፊት ሲያለቅስ አላየሁትም:: ሁላችንም ድምፃችን ከፍ ብሎ አልቅሰን አናውቅም:: ማን ይሆን እንዲህ በማያምር መልክ ስናለቅስ ተደብቆ እያየ የሚስቅብን? አራት ሆነን እዬዬአችንን ስናቀልጥ ሰው እየተሰበሰበ የሆነውን እያየ......እየተያያዘ ......እየተጋባ......ማን እንደሞተ ሲታወቅ አገር በኡኡታ ቀለጠ::

እንደዛ እያለቀስኩ በሃሳቤ ሜዳ የሚመላለሱት መክብብ እጃቸውን ሱሪ ኪሳቸው ከተው እየተራመዱ ቆም ሲሉ፤ ዞር ዞር ብለው አይተው ሲራመዱ፤ ልጅ ጠርተው ከኮት ኪሳቸው ከረሜላ አውጥተው ሲሰጡ (ከረሜላ ለልጆች ሊሰጡ መንገድ ላይ ይወጡ ነበር) ከሱሪ ኪሳቸው መሃረብ አውጥተው የግንባራቸውን ላብ ሲጠርጉ:: እና ቤት መጥተው ከአባቴ ጋር ወሬ እያወሩ ከመኝታ ቤቴ እንድወጣ እየጮሁ ሲጠሩኝ፣ እናቴን ሲተርቡ፡

«የእኔ ቆንጆ የሚጠጣ አምጪልን እንጂ፤ ምናለ አንዲት ቀን አብረሽን ብትቀመጪ አትሞች» ሲሉ እማማ ትንሹ ነገር ሁሉ ያስቃታልና ከት ከት ስትል::

ይኼም ነው:: ያለቀስኩበት ጊዜ ትዝ አይለኝም:: ያለቀስንባቸው የማይታወሱን ቀላልና ምክንያታቸው ደካማ ስለነበር ይሆናል:: ባልችል በትም ነፍሴ የምትወጣ እስኪመስለኝ ምርር ብዬ አነባሁ:: አባቴ ቤት አልነበረም:: መኪና ያለው ሰው ፍለጋ ሰፈር ገባሁ:: ከሩብ ሰአት ሩጫ በኋላ ስመለስ መንገዱ ሁሉ በተሰበሰበ ሰው ተዘግቷል::

«በጥይት ተመተው ነው አሉ»

«ድምፅ የሌለው»

አፋፍሰን አንስተን ወደ የካቲት አስራ ሁለት (ቀኃሥ ሆስፒታል) ይዘናቸው ወረድን:: እግሮቼ የዚያን ሆስፒታል ግቢ ሲረግጡ

የመጀመሪያ ጊዜዬ ነበር። በግማሽ ሰአት ውስጥ መሞታቸው ተረጋግጠ ተመለስን።

ለሰባት ቀኖች ትምህርት ቤት ሳልሄድ ለቀስተኛ ሆኜ ተቀመጥኩ። እንኳን መማር ስለ መማር ማሰብ አስጠላኝ። ግርማቸው ተላጭቶ ጥቁር ባርኔጣ ሲያደርግ መከብብ እንደ አባቴ ነበሩና እኔም አደረግሁ። ድሮ ባርኔጣ ማድረግና ፀጉሬን መላጨት አልወድም፡ ግን እንዲህ በሕይወቴ መለልታ የመክብብ መሞት እንጓ ሆኖ ሲሰነቀር፣ ሞት ፋሽን አስለወጠኝ።

# 7 ቀኖች

አንድ ቀን እማዬ እንደልማዷ ማርያም ደርሳ ቁርስ ለመቁረስ ሳሎን ተቀምጣለች፣ እኔም መኝታ ቤት ፀሐይ እንድታጥብልኝ የቆሸሸና ያልቆሸሸ ልብሴን ስለያይ፣ እማማ 'ምንድነው?' ብላ ተናግራ ወደ በረንዳ ስትወጣ ሰማሁ። አጠያየቋና የድምፅዋ ቅላፄ የተለየ መሆኑ እስኪገባኝ ደቂቃዎች ወሰደብኝ። የምሰራውን ጨርሼ ምን ሆና እንደሆነ ልጠይቃት የመኝታ ቤቴን በር ከፍቼ ስወጣ፣ የወታደር ዩኒፎርም የለበሰ ሰው ኡዚ ማሺንገን ነገር ይዞ ኮሪዶር ላይ ቆሞ አየሁ። የማልም መሰለኝ።

«ምንድነው ወንድም?» አልኩት።

አልመለሰልኝም። አተኩሮ በጥንቃቄ ያየኛል።

ከግራ በኩል ከሳሎን፣ እናቴ ከነበረችበት፣ የሲቪል ካፖርት የደረበ ከዚህ ድራቢ ስር አረንጓዴ የካኪ ዩኒፎርም ሸሚዙ የሚታይ ሰውዬ ብቅ አለ። ያኔ እናቴ ጮኸች። ወደ ሳሎን ለማለፍ ስሞክር ኮሪዶር ላይ የነበረው ወታደር መንገዱን ዘግቶ ኡዚውን ወደ እኔ ደግኖ አቆመኝ። እናቴ ለመጮህ አልተፈጠረችም። እናቴ ድምፅ አልነበራትም። ከእሷ ሶስት ሜትሮች እርቆ የሚቀመጥ ስትናገር ሊሰማት አይችልም። በከባድ ተቆጣሁ ስትል እንኳ እጇን ወደ ሰማይ በመመረር ማንሳት ነው።

«እማማ ደህና ነሽ?!!» ብዬ ጮህኩ። የሚሰማኝ አልነበረም።

ባለ ካፖርቱ ሰውዬ ረጋ ባለ አዛዥ ድምፅ፡ «ዓላዛር በፀጥታ ትተባበረኛለህ። ጫማህን ታጠልቃለህ፣ የምልህን እየሰማህ ማድረግ ነው»

«ምን አጠፋሁ?»

«እሱን ሌላ ቦታ እንነጋገራለን»

«እኔ ሰላማዊ ሰው ነኝ»

«ወሬ አያስፈልግም፣ ልበስ»

«እማማ ደህና ነሽ?!»

«ምንም አትሆንም:: በዚህ ዘመን የእናቶች ስራ ማልቀስ ነው:: ልበስ! የምንሄድበት አለ»

የእናቴ ድምፅዋ ለአፍታ ጠፋና እንደገና ለቅሶዋን ቀጠለች:: ጫማዬን አድርጌ ጃኬቴን ደርቤ ታጣቂዎቹን ተከተልኳቸው:: መሳሪያ የያዘ ወታደር ከመሃላችን እንደ ኮረብታ ቆሞ ከእናቴ ጋር እንዲህ እየተያየን፣ እጇን ዘርግታ እጄን ዘርግቼ ሳንነካካ ከግቢያችን ወጣሁ:: ፊት ለፊት በከፊል አስፋልት በከፊል እግረኛ መንገድ ላይ ጥቁር አረንጓዴ ላንድሮቨር ቆሟል:: ከሁዋላዬ እየተገፋሁ መኪናው ጋ እንደተጠጋሁ፣ ምን ማድረግ እንደጠፋኝ ሁሉ ቆምኩ:: ሰፈር አንጉል ፀጥ ብሏል:: የለመድኩትን ጨለማና የእንጦጦን ቀዝቃዛ ዘነጋሁ:: ሁለመናዬ ያተኩሳል:: ከወደ ጀርባዬ በሚመጣ የመንገድ መብራት የላንድሮቨሩ ጎን ተፍቆ መሰለኝ ኪ ሜ ወይም ኬ ሜ ወይም ካ ማ ወይም ኪ ማ ወይም ኬ ማ የሚል ፅሁፍ አየሁ:: ከቀኜ በኩል ተጠንቅቆ ቆሞ የነበረ አንድ ቀጫጫ ግን ከራራ የሆነ ወታደር ከቂጤ አንስቶ ወደ መኪናው ውስጥ ወረወረኝ:: ከፊት ለፊቴ ከእነ ሾፌሩ ሁለት ሲቪል የለበሱ መልካቸው የማይታየኝ ሰዎች ነበሩ:: ገብቼ እንደተቀመጥኩ፣ ግራና ቀኜን፣ ፊቶቻቸው ላይ የስሜት ሩሕ የሌለባቸው ላብ ላብ የሚሸቱ ሁለት ወታደሮች ተቀመጡ:: የመኪናው ውስጥ ቆዳ፣ ፕላስቲክ፣ ላብና ብረት እንደሚሸት ልብ አልኩ:: በዚያ ሁኔታ ውስጥ እያለሁ ጠረን መገምገሜ ደደብነት መሰለኝ:: ባለ ካፖርቱ ሰውዬ ከጀርባዬ ካሉ ሁለት አግዳሚዎች ላይ በስተቀኝ ካለው ተቀመጠና ሲጋራ ለኮሰ::

«ቀጥል» አለ ጭሱን እየተፋ

መኪናው ተነስቶ ትንሽ እንደሄድን፣ ከኋላዬ እሱ ራሱ 'ይህቺን አድርጋት' አለ:: ዞር ብዬ ሳየው ጥቁር ጨርቅ ወረወረልኝ:: ጨርቁ በትከሻዬ ላይ ተንሳፎ አልፎ ጭኖቼ ላይ አረፈ:: አልገባኝም:: አንስቼ አየሁት:: ጥቁር ሻሽ ነው:: ጎኔ ከተቀመጡት አንደኛው ወታደር ነጠቀኝና አይኖቼን በእሱ ጋረደኝ:: ምናልባት ሃያ ደቂቃዎች ያህል በአስፋልት ላይ ቆይተን ኮረኮንች ውስጥ ገባን:: ኮረኮንቹ ላይ መኪናው ለጥቂት ደቂቃዎች 'ያህል' እየተንገጫገጨ ሲሄድ ቆየና ቆመ:: የብረት በር ሲከፈት እሰማለሁ:: መኪናው እንደገና ተነስቶ ለሰከንዶች በቀስታ ተንከባለለና ቆመ:: ብዙ ሳይቆይ በስተቀኜ የነበረው ሰውዬ 'በል ውረድ' አለኝና ቀኝ እጄን ያዘኝ:: እጁ እንደ ብረት ጠንካራ ነው:: የጣቶቹ አጥንቶች ድርቀት ሰአት ማሰሪያዬ ላይ ይሰማኛል:: 'ተከተለኝ' ብሎ እየሳበኝ መራመድ ጀመረ:: እየተደነቃቀፍኩ ተከተልኩት:: ባላየውም ያለሁበት ቦታ ድንጋያማና ቀዝቃዛ እንደሆነ ሁሉ ለእግሬ ይሰማኛል::

«ደረጃ ጋ ደርሰናል እግርህን አንሳ» አለ የሚመራኝ ሰው

ቀኝ እግሬን በቀስታ አንስቼ ጣል አደረኩት። የደረጃ ምንጣፍ አጋጠመኝ።

«ጎበዝ ነህ አቦ ዕውር ነበርክ? ልምድ ያለህ ትመስላለህ ሃሃሃ» አለ የሚመራኝ ሰው። እኔ የሚያስቅ ሁኔታ ውስጥ አልነበርኩም።

ደረጃውን እንደጨረስኩ የሚጣፍጥ የሲጋራ ጭስ ሰነፈጠኝ። እንግዳ አይነት የማላውቀውና የማውቀው አይነት ጣዕም አለው። ከአንድ ሶስት እርምጃ በሁዋላ ቤት ውስጥ የገባሁ ይመስለኛል። የሚያስጠላ የእምግ ጠረን አለው። ሻሹ ያኔውኑ ከአይኖቼ ላይ ተነሳ። ባለ ካፖርቱ ሰውዬ የሲጋራውን ጢስ ፊቴ ላይ እየተፋ፣ በዚያ ደብዛዛ ብርሃን ውስጥ አተኩሮ ያየኛል። ፊቴ ላይ የሆነ ነገር የሚፈልግ ይመስላል።

«ና» አለኝ። ግራና ቀኝ ሁለት ወይም ሶስት በሮች ካለፍን በኋላ በስተግራ ያለች በደንብ የማትታየኝ ግን መግቢያ መሆኗ የሚታወቅ አንድ ትንሽ የተገረበበች በር ጋ ሲደርስ ቆመ። በሯን በእግሩ መታና ከፈተ።

«ላልተወሰነ ጊዜ ቤትህ እዚህ ነው» አለኝ

«ምን አደረግሁ ጋሼ?»

አተኩሮ አየኝና፡

«ለምን እንደሆነ አታውቅም? ብዙ ሳትቆይ ታውቀዋለህ፣ ይልቁን ግባ። ፈትሸው!» አለ የጠየቅሁትን ሳይመልስ

ከኋላዬ የሚከተለኝ ወታደር ኡዚውን በትከሻው አንጠልጥሎ ተጠጋኝና ከጃኬት ኪሴ አንድ የእርሳስ መቅረጫ፣ አንድ መሃረብ፣ ሁለት ሲጋራዎች ያሉበት አንድ የዊንስተን ፓኬት፣ ከሱሪዬ ኋላ ኪስ የካምፓስ መታወቂያ ካርድና የካፌቴርያ መታወቂያ፣ ከሸሚዝ ኪሴ መቅለጥ የጀመረች ቢክ ስክሪፕቶ፣ ከሱሪዬ የፊት ኪስ አስራ ሁለት ብርና ዝርዝር ሳንቲሞች፣ ከአንገቴ ላይ እናቴ የሰጠችኝን የመስቀል ድምብል ያለው የወርቅ ሐብል፣ ከግራ እጄ ላይ አንድ የኦሪስ ሰዓት፣ እነዚህን ሁሉ አውጥቶ እንደ ጉልት ነጋዴ ወለል ላይ እግሩ ስር ደረደራቸው።

«በቃ ይሄ ነው?»

«አዎ» አለ ፈታሼ

«የቀበሌ መታወቂያ የለህም?»

«ካምፓስ ነው የምውለው። ስፈሬ ውስጥ ድንጋዩ ሁሉ ያውቀኛል»

«መታወቂያ አለህ ወይ? ለምን አላወጣህም? ስለ መታወቅ አላወራሁም»

«የለኝም»

«ለምን?»

«በጣም ሰፈሬ ነው»

«እንዴት ነው 'ሰፈር በጣም ሰፈር' የሚሆነው? መታወቂያው እኮ ለአገር የሚያገለግል ነው:: ዛፍ ነህ ከሰፈር የማትወጣው?»

ጥያቄውን ከመመለሴ በፊት ደረቴ ላይ ገፍቶ ወደ ክፍሉ አስገባኝና በሩን ስቦ ዘጋው::

«ጋሼ!» 'ጓድ' ማለት ገና አለመድኩም::

ከውስጥ በሩ ስር ቆሜ ደጋግሜ እየተጣራሁ መልስ ስጠብቅ ምናልባት ሩብ ሰአት ያህል ቆየሁ:: ማንም እንዳሌለ፣ ወይም መልስ የሚሰጠኝ እንደማይኖር ሲገባኝ ወደ ኋላ ዞር ብዬ አየሁ:: ያለሁበት ክፍል የሰውነት ወና ነው:: ምላስ ላይ የሚሰማ መራራ የሽንት፣ የላብና ልሰይመው ያልቻልኩ ሌላ ጠረን አለው:: ኮሪዶሩ ላይ ያጋጠመኝ አስቀያሚ ሽታ እዚህ ብርድ ለብሶ እያከከ ተቀምጧል:: ክብደት አለው:: ከክፍሉ ግራ ጥግ የተላላጠ፣ የዛገ ነጭ ሰሃንና የተበጣጠሰ፣ የቆሸሸ፣ ልባስ የሌለው መላጣ፣ መፈርፈር የጀመረ የስፖንጅ ፍራሽ አለ:: እነዚህን ዕቃዎች እንደ አንድ ትልቅ ግኝት አተኩሬ አየኋቸው:: ግድግዳው ከርብርብ ሸክላዎች የተሰራ ነው:: በዕሑሮች ተሞልቷል:: እንደ ጨፈቃ የቆሙ፣ ወገባቸው ላይ ማገር የተሰመረባቸው ቀን መቁጠሪያ ነጫጭ ጭረቶች አራቱም ግድግዳዎች ላይ አሉ:: ጣሪያው ኮርኒስ የለውም:: ከመሃሉ በበራሪ ዓይነምድርና በሸረሪት ድር የተሸፈነች ቢጫ ቀለም ያላት አምፖል አለች:: አምፖሏ በቀስታ ትነቃነቃለች:: በጣርያውና በግድግዳው መገናኛ ቀጭን ክፍተት አለ:: በዛ ክፍተት የሚያስፈራ ፀጥታና ምናልባት አምፖሏን የሚያነቃንቀው አየር ይገባል:: ፍራሹ ጋ ሄጄ ተቀመጥኩ:: ሁሉ ነገር ከበደኝ:: 'ምንድነው?' እያልኩ አይኖቼን ጨፈንኩ:: በትክክል ማሰብ አልቻልኩም::

ምንም አላደረግሁም:: ምን እንደሆንኩ ካልተረዳሁስ ምን ማድረግ እንደሚገባኝ እረዳለሁ? ይሄ ቅዠት ሳይሆን እንዳልቀረ እጠረጥራለሁ:: ታፍሶ የመታሰር ድርጊት ብቻ ማን እንደሆንኩ፣ ምን ስህተት እንደሰራሁ ይነግረኛል? እናቴን በእጆቼ መሃል ይገፔ የማላስበው ነገር አልነበረም:: የማያልቀው ሰአት ሳያልፍ በተጎተተ ቁጥር ጭንቅላቴን የሆነ ነገር የሚፈተፍተው መሰለኝ:: ከውስጥ ያሳክከኛል:: እናቴን እቆፍራለሁ:: የሚያሳክከኝን ግን ጣቶቼ አይደርሱበትም:: አዲስአባ እንዲህ አድርጋኝ አታውቅም:: ሽሮሜዳ እንዲህ ሰርታኝ አታውቅም:: ሁለመናዬን ስለደከመኝ ያገኘሁት ፍራሽ ላይ ተጋደምኩ......እየተጋደምኩ እነሳለሁ......እየተነሳሁ እጋደማለሁ:: ሌሊት ላይ አጠገቤ ያገኘሁትን ሰሃን ራቅ አድርጌ አንድ ጥግ ወሰድኩና ሽንቴን ሸናሁ:: ሽንቴ ስጨርስና የሱሪዬን ዚፕ ስዘጋ በር ተከፈተ::

አንድ ልጅ እግር ወታደር አንድ ጋቤጣና ጋቤጣው አፍ ላይ ፉርኖ አድርጎ ወለል ላይ አስቀመጠ:: እንደ ራበኝ አወቅሁ::

«ጋሼ! ጓድ! ማንን ላነጋገር?!» አልኩት ጮኼ

አልመለሰልኝም:: በሩ ሲቆለፍ እሰማለሁ:: መቀርቀሪያውና መቆለፊ-ያው ከውጭ ነው:: ጋቤጣው ውስጥ ለዝ ያለ ሻይ ነበር:: ዳቦውን እየቆረስኩ በሻይ እያጠቀስኩ ትንሽ በላሁ:: አቅለሸለሸኝ:: ሽንት መሽኛዬ ላይ የበላኋትን አስመለስኩ:: እንዲህ ከሆነ ምናልባት ከሩብ ሰአት በኋላ በር ተከፈተና አጠር ቀጠን ያለ፣ ግራ አገጩ ላይ በደብዛዛው ብርሃን የሚታይ ደማቅ ጠባሳ ያለበት ሰው ገባ::

ከተቀመጥኩበት ፍራሽ ላይ በፍጥነት ተነሳሁ:: ወንበር የያዘ ቀድሞ ራቴን ያመጣልኝ ጎረምሳ ሰውዬውን ተከትሎ ገባና ቂጡ ስር ወንበሩን አስቀምጦለት ያኔውኑ ወጣ:: አዲሱን ሰው አተኩሬ አየዋለሁ:: በመንገድ ችላ ብዬ የማልፈውን ማንኛውንም አይነት ሰው ይመስላል:: የአየር ሃይል ጃኬት ለብሶአል:: ፀጉሩን በአጭር የተቆረጠ ነው:: አፍንጫው ባይተልቅ መልከ መልካም ይሆን ነበር:: ግንባሩ ለአምፖሉ ስለተጋለጠ ሳይሆን አልቀረም በጉልህ ከፊቱ ይቀላል::

አይኖቹን ከእኔ ላይ ሳያነሳ እጆቹን ጃኬቱ ኪሶች ከቶ በመዝናናት በዝምታ ተቀመጠ:: ከላይ እስከ ታች ሲያየኝ ቆየና:

«ስምህ ዓላዛር ነው»

«አዎ»

«ዓላዛር ብርሃነ መስቀል»

«አዎ»

«ለምን እዚህ እንደመጣህ ታውቃለህ?»

«አላቅም»

አረፍ አለና ከንፈሮቹን በመረጋጋት መጠ:

«ለምን ከእኔ አንጀምርም? እኔ ማን ነኝ?»

ቀልድ ይመስላል::

ለአመል ትከሻዬን ከፍ ዝቅ አደረግሁ:: ጃኬቱ ኪስ የከተተውን ግራ እጁን አወጣና አሳየኝ:: የመሀል ሁለት ጣቶቹ የሉም:: ይኼን ድኩማንነቱን ዛሬ ከእኔ ጋር ማየት እንደጀመረ ሁሉ ለአፍታ እያገላበጠ አጠናውና:

«ምን የቆረጠኝ ይመስልሃል?»

መልስ ከእኔ ሳይጠብቅ ቀጠለ:

«ሆን ተብሎ የተደረገ አይመስልም? ብዙ ሰው እጄን ሲያይ 'ሁለት ጣት የለውም' ነው የሚለው:: 'ሁለት ጣቶቹ የተቆረጡ ናቸው' ነው የሚለው:: ምክንያቱም ብዙ ሰው ደደብ ነው:: ምን ዓይነት አቆራረጥ ነው ሲመስልህ አመልካች ጣትና ትንሽ ጣትን ስቶ የመሃሎቹን ብቻ የሚቆርጠው? አስበኸዋል?»

ራሴን ነቀነቅሁ

«ተቀመጥ»

በፍጥነት ወደ ፍራሼ ተመለስኩ::

«አባቴ አንድ ጉልተኛ ቤት አገልጋይ ነበር:: ይሄ ጉልተኛ ከባድ ስህተት ይሰራል:: ስህተቱ ጉልተኛ ወይም ፊውዳል መሆኑ አይደለም:: ፊውዳሊዝም ስርአት ነው:: የእሱ ጥፋት አይደለም:: ስህተቱ ምንድነው? ይሄ ጉልተኛ ጥጋበኛ ነበር:: ቀላል ጥጋበኛ እንዳይመስልህ:: ጥጋበኝነት የግል ባህርይ ነው:: በዛ ባህርዩ ብቻ ደሞ መክሰስ እችላለሁ:: ለሕሊና:: በከፊል ጦም የሚያሳድረው ደሃ ላይ በመሞላፈጥ የእግዚአብሄርንና የተፈጥሮን ሕግ ያፈርሳል:: ሰው ሆኖ ሰው ይንቃል:: ሰው ሆኖ ሰው የናቀውን ቀን ጠብቀህ ወደ እንስሳ ለውጠው:: እንዲገባው:: ከዛ ወደ ሰውነት መልሰው:: እንዲገባው:: በዚህ አይነት ከማንም ያልተለየ ሰው መሆኑ ካልተረዳ፣ ከምድር ላይ ይሰረዛል:: ከአወላለድህ ብልህ ካልሆንክ፣ ከአስተዳደግህ ብልህ ካልሆንክ የተፈጥሮ ጠላት ነህ:: ቢያንስ በአንዱ ና::

«እግዚአብሄር ሁሉን እኩል አይደለም የፈጠረው እንዴ? ያ ሁሉ ደደብ ሃይማኖተኛ፣ አምላኩ በአምሳሉ የፈጠራቸውን ወገኖቹን ለምን ዝቅ እንዳሉ ፍጡራን ይቆጥራል? ይሄ የአምላክን ሕግ ማፍረስ ነው:: እሱና እሱን የመሰሉት ሰው ላይ ያላቸው ንቀት ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ የሚያይዛቸው የሰባዊነት ሙጫ ባለመኖሩ አመት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ተበታተኑ:: ያልገባቸው ስለሆኑ በቀላል ጥፊ ተጠናቀቁ:: እና አባቴ ለዚህ ሰው መሳይ በሸንጎ አገልጋይ ነበር:: በስራ ብዛት ገላው ስለሚደክምና ስለሚዝል ቆንጆ እናቴን ወይም ሚስቱን ለጌታው ፍትወት ይገብራል:: አየህ ትክክለኛው አባቴ ጉልተኛው ነው:: ትክክለኛው አባትህ ማን እንደሆነ በሹክሹክታ ሲነገርህ ምን አይነት ስሜት እንደሚሰማህ ታውቃለህ?......ቀልቃላ ዲቃላ ነበርኩ:: ወሬ ሰማሁና ለማረጋገጥ ደሃው አባቴን 'ማነው አባቴ?' አልኩት:: ስላፈረ ሳይነግረኝ አባረረኝ:: ፊውዳሉ ቤት ገብቼ 'ማነው አባቴ?' አልኩት:: ስለናቀኝ እሱም አባረረኝ:: መናቅ ብቻ አይደለም፣ መሳሪያም ተኮሰብኝ:: ልጅ ላይ:: ከእሱ ደንባራ በቅሎ ክብር የልጅ ሕይወት ቢጠፋ ምንም አይደለም አየህ:: ጀርባዬን እንዲቀድ የተላከው ጥይት እጄን መታኝ:: ሁለቱ ጣቶቼ ተቆረጡ:: የተቆረጡት ጣቶቼ ጠፉ? አልጠፉም:: ልቤ ገቡና ጦር ሆነው በቀሉ:: ልጅ ላይ ያስተኩሳል? ሰውዬውን ብቻ ሳይሆን የሚሰግዱለትን፣ የሚያከብሩትን

ሰዎች ሁሉ ጠላሁ። ደሃ አባቴንም ጠላሁት። ሲተኩሱብኝ ለምን አልተኮሰበትም? ምን ዓይነት ባህል ነው ልጅህን ለመጠበቅ ጦር እንዳትመዝ የሚያስርህ? ወይስ ልጁ እንዳልሆንኩ ያውቅ ነበር? ዱቃላ በመሆኔ ቂም ይዞ ነበር? በስድስት አመቴ አዲስአባ መጣሁ። ከሻሸመኔ ነው። አዲስ አበባ ስንከራተት ኖሬ እድሜዬ ከፍ ሲል በዕድሊና በብልጠቴ አገሬን ጠባቂ ለመሆን በቃሁ። ዛሬ ወታደር እንዲጠላ የሚሹሁት፣ ከየት እንደመጣ የማያውቁ፣ የሚበሉት ወጥ ቅባቱ እያዳለጠ የሚያሳስታቸው፣ ቀሽሞችና ሽረኞች ናቸው። ይሄ አብዮት ሲነሳ ደስ አለኝ፣ 'ብጥብጥ' ነው የምትሉት አይደለ? ስም ለማጥፋት? ሚሊዮኖች ለአገራቸው እየሞቱ የሚያመርቱበትን መሬት ብቻ ሳይሆን መቀበሪያውንም ለራሳችሁ ታደርጋላችሁ። አፍረተቢሶች ናችሁ። ከጦርነት ተርፎ ሲመጣ መልሳችሁ ባርያ ታደርጉታላችሁ»

እጁን ወደ ጀርባው ላከና ሽጉጥ አወጣ። እንደዚህ በቅርብ ሽጉጥ አይቼ አላውቅም። እዛና እዛ የሚፈልቅ ጥቁር አፈር ይመስላል። እጁ ላይ እንደ እንግዳ እቃ አጋድሞ እያየው፡

«መሳሪያ አለኝ። ጥላቻ አለኝ። ልጅነቴን ያበላሹብኝን ሲበላሽባቸው ምን እንደሚሰማቸው ማየት እፈልጋለሁ። ደስ እንደማይል አሳያቸዋለሁ። አስበው ካልደረሱበት ይመታሉ። አንተን የመሳሰሉ። የአገሮች ዋናው ሕልም ታላቅ የመሆን ነው። ደቃቃ ለመሆን እንቅልፍ አያጡም። የፈለከውን አገር ታሪክ እይ። አንተና አንተን የመሰላችሁት ግን ኢትዮጵያን ትንሽ ለማድረግ የማትሰሩት የለም። ምን ይጠቅማችኋል? አገሪቷ እያስተማረችህ፣ ከማንም ባላነሰ ምቾት እያኖረችህ ልታጠፋት ትፈልጋለህ። የአያትህን መሬት ስለ ወሰድንብህ ከፋህ? ምንስ ቢከፋችሁ እንደልጅ የሚያዩአችሁን፣ እንደ አባት ልትቆጥሯቸው የሚገባችሁን መክብብን መግደልና ማስገደል አለባችሁ?»

«ምን?» አልኩት

«ቆይ! ትደርሳለህ። አዲስአባ መጣሁ አላልኩህም? ለሁለት አመታት መንገድ ላይ ነበርኩ። እንጀታቸውን የበላሁዋቸው ሲትዮ ጩሉ አድርገው ወሰዱኝ። ጩሉ ሆኜ ተማርኩ። ጩሉ ነኝ። ጩሉ። ቃሉ አማርኛ አይመስለኝም፣ ኦሮምኛ አይደለም። ምንም አይደለም። ስድብኛ ነው። ስድቦች ብቻ ያሉት ቋንቋ አለ? ካለ ከዛ የተወሰደ ነው። እነዛ ደካማ፣ ኋላ ቀር፣ ግን ብዙ እናውቃለን የሚሉ ዘመዶቻችሁ ስለሚያወሩት ትራቅንቦ ብቻ ሳይሆን የውስጥ ሱሪዎቻቸውን ቀለም፣ የውሽሞቻቸውንና የቁባቶቻቸውን ስልፍ አውቃለሁ። በግልፅ እንነጋገር ቁልፍ ጉዳይ እጠይቅሃለሁ!»

«እኔ ይሄን ዓይነት ነገር......በፍፁም ተሳስተዋል»

«'አንተ' በለኝ ልጠይቅህ»

«አለማየሁ የሚባል ሰው ታውቃለህ?»

«አለማየሁ? ወጣት?»

«የፈለገው ዓይነት»

ሽጉጡን ኪሱ ከተተ::

«አዎ የአንድ ጓደኛዬ አባት»

«ካንተ የባሰ የአራዳ ልጅ አይቼአለሁ፣ የዚህ አይነት ቁጭበሉ አልሰማም:: በትክክል መልስልኝ:: እደግመዋለሁ......»

«ሌላ?»

«እንደገና ሳድርገው ጥያቄውን:: አለማየሁ የሚባል ሰው ታውቃለህ?»

«ብዙ አለማየሁ አውቃለሁ:: ትምህርት ቤት? ሰፈር? በየቦታው?»

«ካርታ መጫወት የሚወድ»

«እ»

«እ......ካርታ......አለማየሁ፣ ትዝ አለህ?»

«በቅርብ የማውቀው ሰው ነው:: ታዚና ሆቴል»

«አሁን ጓደኛ ልንሆን ነው:: አየህ እኛ ያለችንን ደሃ አገር ልንጠብቅ ስንለፋ በአጭር ሊያስቀሩን የሚፈልጉ ከባዕዳን ጋር ነጋ ጠባ የሚያሴሩ ከሃዲዎች አሉ:: አንዱ እሱ ነው:: ለእሱ ጭሎ አጨብጫቢ ምናልባትም መንገድ መሪ የሆንከው አንተና መሰሎችህ ናቸው»

'መሰሎችህ' ላይ ጠበቅ አድርጎ

«ጋሼ እኔ የዚህ ዓይነት ነገር አላውቅም»

«አትፍራ፣ ምን እንዳወራችሁ ዘርዝረህ ትነግረኛለህ:: ሁሉ ይስተካከላል:: ደሞ አትገሽሽኝ: ጋሼ ብሎ ነገር:: ጆ ማለት አይበቃም? ግን ጆ አይደለሁም:: ለአንተ አሁን ምንም አይደለሁም»

«ካርታ ተጫወትን፣ ተጯጋገርን:: በቃ»

«ምን ተጯጋገራችሁ? ይሄ መሀይም ወታደራዊ መንግስት አገር ይበጠብጣል? ገበሬ መሬት ብትሰጠው የሚሰራበትን አያውቅም? ምን? ዲሞክራሲ አሁኑኑ? ምን? የሰራተኛው አምባገነን መንግስት ይቋቋም? ለዚህ ሁሉ ግድ የለኝም:: ግድ የሚሰጠኝ የአገሬ ወሰን ነው:: የአገሬ አካል ነው:: ተግባባን? የሰለጠንኩት እሷን የሚነካብኝን በተገኘው መንገድ ከምድረ ገፅ ማጥፋት ነው:: የፈለከውን ዓይነት ሶሻሊስት ወይ ኮሚኒስት ሁን የአገሬን ድንበር የሚደፍረውን እቃጥለዋለሁ:: ተግባባን?......ስሜን

አጥፉ ከፈለጋችሁ ፋሺሽት ከፈለጋችሁ ግራዚያኒ በሉ ምን በሉ አይ ዊል ፋክ ዩ»

«ያወራነው ምንም ትዝ አይለኝም። ትዝ የሚለኝ ፖለቲካ እንዳላወራን ነው»

«አየህ አገሬ በጦር ቢመጡባት ትመልሳለች። ከልጆቻችን ጋር አብሮ ከበላ ከጠጣ ቦርቧሬ ጋር መታገል ግን ትንሽ አያስቸግርም? እኔ የዋህ አይደለሁም። እንዲህም አይነት አፍራሾች በአንተ አይነቱ ቀዳዳ ተጠቅመው ነው የሚመጡት። ኑሳች የሚመጡት ከሰሊጥ ተደባልቀው ነው። ያን ቀዳዳ መድፈን አለብኝ። አሁን እተውሃለሁ። አንዳንዴ ቂል መመታት አለበት። 'አውቃለሁ' የሚል ቂል ከጠላት ያላነሰ አደገኛ ነው። ደደብነት ከቦንብ ሊብስ ይችላል። አስብበት። ካልተጠነቀቅህ እንደ ኑግ ትወቀጣለህ። ከዛ በኋላ ስህተቱ የእኔ አይደለም። ፋሺሽት ፋሺሽት ብትለኝ አይገባኝም። የሚገባቸው ቢኖሩ በአንተ አይነት ክብት የሚጠቀሙ ናቸው። ትክክለኛ ዜጋ ነህ? ወይስ ማንም አገር ቆራሽ የሚነዳው ክብት? 'ክብት አይደለሁም' ካልክ ማረጋገጫ እፈልጋለሁ። ተግባባን? የአገር ሕልውና ላይ ዲሞክራሲ ሰባዊ መብት ቀባጢሶ አይሰራም»

«ኸረ እኔ……ነገርኩህ ፖለቲካ አላወራንም»

«አስብበት። ማንም ከሕግ አያመልጥም። የአገሬ ሕልውና ነጋሪት ጋዜጣ ውስጥ አይደለም ያለው። ታሪክና ጥይት ውስጥ ነው። 'ወታደር መሀይም ነው' አይደለም የምትሉት? የእናንተን ትምህርት አላየን። ፖለቲካል ሳይንስ ባችለር ዲግሪ አለኝ። ትከሻዬ ላይ የምታየው ምልክት የመቶ አለቃ ሊሆን ይችላል። ምሁር ለመሆን አትሞክርብኝ። አሁን ወረቀት ይመጣልሃል። እዛ ወረቀት ላይ ሆቴል ተቀምጣችሁ ያወራችሁትን ትዝ የሚልህን አንድ ሳታስቀር ታስፍራለህ። እኔ 'ሰላማዊ አይደለህም' እላለሁ። አንተ 'ነኝ' ትላለህ። ቀላል ነው። የምናመሳክረውን እናመሳክራለን። እኔ ስላጋጠምኩህ እድለኛ ነህ። መተባበር ካላማረህ መንገድ መንገድ አለ። ከምትነግረንና ከምትፅፈው ኑግ ወይም ሰሊጥ መሆንህን ማወቅ አለብን። ይገባሃል የምልህ? ማርክሲዝም ስለ ኑግና ስለ ሰሊጥ አያውቅም። አንድ ቦታ አሳየኝ ማርክሲስቶች ስለ ኢትዮጵያ የፃፉበትን ቦታ። ላእኔ ጋቢ የለበሰ አድሃሪ ሱፍ ከለበሰው ማርክስ የሚሻል አይመስለኝም። አንተ ማርክሲስት ሆንክ አልሆንክ ግድ የለኝም። ዕውነቱን እፈልጋለሁ። ተግባባን? መግባባት ማለት እኔ የማዝህን ማድረግ ማለት ነው። መግባባት ማለት እውነቷን ሳታስቀር መናገር ማለት ነው። ይሄን እዚህ ላይ ማፈንዳት እችላለሁ……» አለና ባልጠበቅሁት ፍጥነት ሽጉጡን ከጃኬቱ ኪስ አውጥቶ ግንባሬ ላይ ደገነው። ባይነካኝም፣ የአፈሙዙ ብረት ቅዝቃዜ ቆዳዬ ላይ ይሰማኛል።

«ኸረ እፅፋለሁ……»

«አታቋርጠኝ:: መክብብ ጥሩ ኢትዮጵያዊ ብቻ አልነበረም:: ደግ ሰው ነበር:: ለአንዱ እንኳ አትምሩትም? በደግነቱ ወይም በኢትዮጵያዊነቱ? ለመሆኑ ምን ድርጅት ውስጥ ነህ?......»

«አታቋርጠኝ:: እውነቱ እስኪወጣ ድረስ እዚህ ትቆያለህ:: አንተ የእኔ ነህ:: ወንጀለኛው መያዙ አይቀርም:: እንዳትረሳ ምን ድርጅት ውስጥ እንዳለህ? ኢሕአፓ፣ መኢሶን፣ ኢኤልኤፍ፣ ኢጭአት፣ ቀይ ባንዲራ ምናምን የፈለከውን:: ያለህበትን:: ማንም ከአገሬ አንድነት አይበልጥም:: ገባህ? እሸውዳለሁ ብትል ግን እዚህ እየሸናህና እያራህ የምትወጣው ዕድሜህ ሰባ ሲሆን ነው:: ከዛ በልብህም ይሁን በአፍህ ጩካኝ እንዳት. ለኝ:: አገር የምትሰራው በጦር ነው:: በወሬና በመከዳዳት አይደለም:: መጀመሪያ አገሬን ከዛ ዲሞክራሲ:: ጋሪውን አስቀድማችሁ ልታጠፉን ነው? ሲበላሽ በእኛ ልታመሃኙ?»

ሽጉጡን ከግንባሬ ላይ አነሳና በቀስታ ወደ ኪሱ መለሰው:

«ኸረ ምንም......»

«ከጊዜው ውጭ ነኝ ነው? ፋሽን አልከተልም ማለትህ ነው? የሚጎዳ ነገር የለውም ወጣት ሆነህ ወጣት መምሰል:: አፍሮህ ፋሽን ነው አይደል? አፍሮ ነው ጎፈሬ? 'ጎፈሬ' ከተባለ ኋላ ቀር ይመስላል አይደል? እ? ከብቶች ነን አይደለ? እንዲህ የሚነዳችሁን እረኛ አታዩትም ግን ያው ይነዳችኋል:: ፋሽን ጤነኛ ነው መከተል:: የጠላቶቼን ብልጥነት አደንቃለሁ:: የአንተ አይነቱ በትንሽ ጎደለብኝ ብዙ በሚበጠብጠው ቂል ግን አዝናለሁ:: ፈሪ ነህ?»

«እ»

«ዘመናይ ሰው አይደለህም? ወይስ ፈሪ ነህ?»

«እኔ ከሰው መቀያየም አልፈልግም:: ሁሉ ሰው ሸርኬ ነው:: ማለት እንዳዛ ነው:: ለምን እጣላለሁ? ፋን[32] ነው የምወደው:: በማላውቀው ነገር አልገባም»

«በወጣትነትህ አይቀርልህም:: ፋሽን ካለ ባታደርገውም ትታማበታለህ:: ባትፈልግም አይቀርም:: ዕውነታው ይሄ ነዋ:: ወጣት ላይ እየተሴረ እንደሆነ አልገባህም፣ ማምለጥ አትችልም:: የሴራው ሃይል ነው:: ባትፈልግም ያስገባሃል:: አይደለ? ይመጣል ባትፈልገውም:: ሰማህ? ለምን መጣህ እዚህ? እ? አታመልጥም»

ከተቀመጠበት በፍጥነት ተነስቶ በር ከፈተና እጁን ብቻ ወደ ውጭ አወጣ:: ያኔውኑ ከማይታየኝ ሰው እጁ ላይ አንድ ደብተር ከስክሮንቶ

[32] ጨዋታ (Fun)

ጋር ተቀመጠ። ከቆመበት ሳይጠጋኝ ደብተሩንና እስክሪፕቶውን ወደ እኔ ወረወረ። ስክሪፕቶው ወደ ቀኜ፣ ማስታወሻው ወደ ግራዬ ተለያይተው ወደቁ። ከወደቁበት ለማንሳት ሳጎነብስ በሩ ተዘጋ......

ያለሁበት ጉዳይ ከባድ እንደሆነ ተረዳሁ። እንድፅፍባት የተሰጠችኝ ቢክ ስክሪፕቶ ስገባ በበርባሪ የተወሰደችብኝ የራሴው ናት። ልዩ ነገር ከእሷ እንደማገኝ አተኩሬ አየኋት። ብዕሩን በጥርሴ ነክሼ ይገፎ 'አለማየሁ' ስለሚባለው ሰው ትዝ የሚለኝን ነገር ሁሉ በሃሳቤ ማደራጀት ጀመርኩ። ይሄ ሰውዬ 'አድርገሃል' ያለኝን እንዳላደረኩ ባውቅም የሚሆነው ስለማይታወቅ ተጨነቅሁ። ማስታወሻ ደብተሩን ለሁለት አጥፌ መፃፍ ጀመርኩ። የቤቱ ጣሪያ ከፍ ያለ ስለሆነ የአምፖሉ መብራት ወጋጋኑ በደንብ አይደርሰኝም። እጅ ፅሑፌን ለመተንተን ለሚፈልግ ተመራማሪ ማንበብ በሚያስቸግሩ፣ መስመር በሳቱና በተንጋደዱ ቃላት አራት ገጾች ሞላሁ። የመጀመሪያው ገፅ ላይ አለማየሁ ስለተባለው ሰውዬው መልክ፣ ቁመናና የተገነዘብኩትን ፀባዩን፤ በቀሩት ገፆች ደ'ሞ ተቀምጠን ያወራናቸውን ጉዳዮች፣ ቀልዶች፣ ተራ የሚባሉ ነገሮችን ሁሉ በተቻለኝ አቅም እያስታወስኩ አሰፈርኩ። ፍራሼ ላይ ተጋድሜ የሚያስጨንቀኝን ነገር ሳስብ እንቅልፍ ወሰደኝ። ሌሊት ላይ በር ተበረገደ። የክፍሉ መብራት ጠፍቷል። ለአፍታ የት እንዳለሁ ተደነጋገረኝ። ሽሮሜዳ መኝታ ቤቴ ያለሁ ይመስለኛል። ወይም በልጅነቴ ቤተክርስቲያን ለቁርባን ሄጄ ወለል ላይ እንቅልፍ ወስዶኝ የሆነ ዲያቆን ወይም ደብተራ ወይም ጓደኛዬ የሚቀሰቅሰኝ።

ሶስት ወይም አራት የሚሆኑ ሰዎች ገቡ። ቁጥራቸውን እርግጠኛ አልነበርኩም። ከኮሪዶር በሚገባ የብርሃን መደብ ላይ ያየኋቸውን እግሮች ለሁለት ለማካፈል እየጣርኩ ነበር። ከኋላቸው በር ተዘጋና:

«ያ የተበዳ ጥጋበኛ ይሄ ነው?» አለ አንድ ጡንቻ ያለው የመሰለ ድምፅ።

ከፍራሼ ላይ ለመነሳት ወለል ይገፎ ሳጎነብስ የሆነ እግር እጄ ላይ መታኝ። ጣቶቼ ሲሰበሩ ሰማሁ። ከባድ ውጋት በክንዴ በትከሻዬ በሁለመናዬ እንደ ጎርፍ ፈሰሰ። ጮሁኩና የናቅኋት ፍራሽ ላይ በፊቴ ተደፋሁ።

«አይ! ሙቼ ተጀመረ! ድሮ የበላሽውን ሾርባ አስጨርሰን ነው የምን-ተውሽ። ገና ምን ተነካሽ። እ? ጥጋበኛ!»

የተሰበረ እጄን ጭኖቼ መሃል አድርጌ ስጮህ፣ ትልቅ አጥንታም ጠንካራ እጅ መጥቶ ከጀርባ አንገቴ ላይ ያዘኝ። ጎትቶ አነሳኝ። የጎተተኝን እጅ ባለቤት ለማየት ስታገል እንደ ብረት የከረረ ቴስታ አፍ-ንጫዬና ዐይኖቼ መሃል አረፈ። አንገቴ ላይ የያዘኝ እጅ በሐይል ገፍቶ

ለቀቀኝ፡፡ ከግድግዳ ጋር ተላተምኩና ሲሚንቶ ወለል ላይ ወደቅሁ፡፡ ለመጨረሻ በደብዛዛው ብርሃን ውስጥ ያየሁት በተርታ የተሰለፉ እግሮች ነው……

ስባንን ነግቷል፡፡ የወደቅሁበትና በዛው ራሴን ስቼ የተኛሁበት ፍራሽ በደም ረጥቧል፡፡ ፊቴና አፍንጫዬ ይጠዘጥዘኛል፡፡ ግራ ክንዴ፣ ግራ ጉንጩና ግንባሬ ላይ በቃል መግለፅ የሚከብድ ውጋት ይሰማኛል፡፡ የጃኬቴና የሱሪዬ ፊት ለፊት በደም ረጥቧል፡፡ ፊቴን ለማጨማደድና ለመዘረጋጋት ስሞክር የደረቀው ደም እንደ ቅርፊት ሲሰነጣጠቅ ይሰማኛል፡፡ ስዳብሰው እንደ ደረቀ አፈር ይሻክረኛል፡፡ ግራ እጄና ስርኔ አልፎ አልፎ በከባድ ውጋት ይመታሉ፡፡ በግንባሬ ተደፍቼ አሁን ያለሁበት ሁኔታ ከልጅነቴ ጀምሮ አንድ ክፋት፣ እንደ ጥላ፣ እግር እግሬን ሲከታተለኝ ኖሮ ዛሬ ሊያጠምደኝ የተከሰተ መሰለኝ፡፡ በውጋቴ መሃል ማዘሬን አሰባለሁ፡፡ ፋዘርን አስባለሁ፡፡ ቴቢን አስባለሁ፡፡ በየተራ እያፈራረቅሁ ሳስብ፣ እየደረደርኩ ሳስብ እዝራ ትዝ አለኝ፡፡ በድንጋጤ ፍራሹ ላይ ተቀመጥኩና ጭንቅላቴን በሁለት እጆቼ ያዝኩ፡፡ ‘አለቀልን’ አልኩ በግድ በሚነቃነቅ፣ ቁስል ባጣመመው፣ ደም በሸፈነው አፌ፡፡ ወቅቱ መሰለኝ፡፡ የሆነ መርዝ እንደ ሰደድ ወይም ወረርሽኝ ሸሮሜዳ የገባ፡፡ ከእንጦጦ ገደል ስር አዲስ የዘመኑ ዘንዶ የበቀለ፡፡ እንደ ፋደት ከቂጡ ስር ቅርኔ መርዝ የሚነሰንስ፡፡ እዚያች የአዲስአባ ትንሽ ቁራጭ መሬት ላይ እንደብሳና በግድየለሽነት ያደግን፣ ቀስ በቀስ ስንሰነስን፡፡ እዝራንና ቤተሰቦቼን እያቀያየርኩ እያሰብኩ ማልቀስ ጀመርኩ፡፡ ለመከብብ እንዳለቀስኩት ዓይነት አልነበረም፡፡ እናቴን ይገፍ ፊቴን ደም የተነከረ እጄ ውስጥ ቀብሬ ድምፄን አጥፍቼ ለራሴ ብቻ እንዲሰማ፡፡ ጥልቀት አለው፡፡ የመጀመሪያው የመከብብ ሞት፣ መድረሱ ለማይቀር ለዚህኛው ጣጣ ሊያለማምደኝ የመጣ ጉዳይ መሰለኝ፡፡ ሞት ዐይነአፋር ይሆናል ‘ዓላዛርን ከምመነትፈው በፊት ሌላ መንትፌ የስራዬን ጨካኝነት ቢያጠና’ አይነት ብሎ የሚነሳ፡፡ ልቅሶዬ የጨመረው ነገር አልነበረም፣ የቀነሰውም አልነበረም……

……የቀኑ ፍሰት ታስቶኛል……ሲነጋ አለቅሳለሁ……ሲጨልም አለቅሳለሁ……ፀጥታው ውስጥ የምሰማው አዝማቼ ለቅሶ ነው፡፡ ቁስሌ ቀስ በቀስ ቢሻለኝም፣ ምን ሁኔታ ላይ እንዳለሁ ሊጠይቀኝ የመጣ ሰው አልነበረም፡፡ አንድ ቀን መጀመሪያ ያነጋገረኝ ሰው መጣና ቃል ሳይወጣው ማስታወሻውን ከነስክሪፕቶው ወስዶ ሄደ፡፡ ደብተሩ ላይ የሚያየው የደም ነጠብጣብ እንደማይረብሸው አውቃለሁ፡፡ ስራው ነው፡፡ ዳቦ በሻይ እየበላሁ እየተኛሁ እያለቀስኩ፡፡ እናቴ እየባበለችኝ፡፡ የእናቴ ሳቅ……የእናቴ ሐዘን……ያ የምሽት አየር እንደሰው……ያ የቀትር ፀሐይ እሱም በልጅነቴ ስጠጣው እንደ ፊጀኝ ትኩስ ወተት ትዝ አለኝ፡፡ እነዛን

ተራ የመሰሉ ተፈጥሮዎች እንዳላያቸው እከለከላለሁ ብዬ ያሰብኩበት ጊዜ እንዳልነበረ፣ ግን ሊሆን እንደሚችል ስረዳ፣ ጊዜ ተሰጠኝ ትቼአቸው ከመሄዴ በፊት እጆቼን ወደ እነሱ ዘርግቼ አንጋጥጬ 'ደህና ሁኑ' ልላቸው ፈለግሁ......የሰፈሬ ሰዎችም: *ጌቾ፣ እዝራ፣ ቻርነት፣ አባባ ምናልባት እዛ የሚያውቁኝ በሙሉ እነሱ ሁሉ ታስረው ይሆን?* እያልኩ ......ሰፍራውም፣ ነገሮችም እቻ ለእቻ ናፈቁኝ......የእጅ ጣቶቼ የሞቀ ወጥ የተነከረ እርጥብ እንጀራ መጠቅለል ናፈቃቸው......ነፋስ ሲነፍስ በጃኬታቸው ሲጋራቸውን ጋርደው ለማጤስ የሚማስኑት የምቀርባቸውና የማልቀርባቸው የሰፈሬ ጎረምሶች ናፈቁኝ......ቴቢና ማሚ ዳማ ሲጫወቱ የሚያደክመን ንጭንጫቸው ናፈቀኝ......ሊያልቅ የደረሰ ሎሚ የገባበት ውሃ አረንጓዴ የአባቴ ረም ባካርዲ ቢፌ ጠርዝ ላይ የተቀመጠው እሱም ናፈቀኝ......እዝራ ጋ ምሳ ልበላ ስሄድ ወጥ የሚያወጣበት ብርማ ቀለም ያለው ትልቅ የብረት ጭልፋ እንኳን እንደ አርቦሼ ትዝ አለኝ......ከልብስ ማስጫ ላይ ወድቆ በጤዛ ረጥቦ አንድ ጠዋት ሳር መሃል ያየሁት ቤት ሳይገባ የተረሳ የተባረኪ ጥቁር የውስጥ ሱሪ እንደ ዘመድ ትዝ አለኝ......የአልማዜ ወገብ በስፌ ነጭ ቀበቶ የታሰረው፣ እሱም ከነስቡ ናፈቀኝ......ቤቷ ሳሎን መሃል ሁልጊዜ የወይራ ጢስ እየሞቀች የማገኛት የተባረኪ እናት ትደነቂያለሽ ናፈቀችኝ......በመንገድ ዳር ክረምት ክረምት እየገነፈሉ የሚወርዱት ወርቅማ ቀለም ያላቸው የቦይ ውሃዎች ናፈቁኝ......ኩመካው የማይጥመኝ መላጣው የማትስ 101 አስተማሪ...... ሚጢጢ ከንፈሮቻቸው ላይ አረፋ የተለደሰ የጆሊ ባር የማኪያቶ ብር ጭቆዎች......ቻርነትና እዝራ ከእንጦጦ እስከ ሰፈር የሚያደርጉት የብስክሌት ውድድር (በከፊል እየተሸከሙ)......እነዚህ ሁሉ ናፈቁኝ:: እሁድና ቅዳሜ በሙዚቃ የምትሞላው ሙቅ የሆነች ክፍሌ እንደ አክስት ናፈቀችኝ......'አልፈልግም' ያልኩዋትን ምግብ እንድበላላት ፀሐይ የም-ታደርገው ልምምጥ ('እይ እኔ ስበላው') ናፈቀኝ......የተባረኪ ሁለመና እያብላላኝ: *ምናልባት እሷንም አስረዋት ይሆን?* እያልኩ......ከዋለችበት በምሽት ስትመጣ ላገኛት በጉጉት ስጠብቃት......ከፊት ለፊቴ እግሬ ስር የረገፉት የሲጋራ ቁሩዎች (በጨለማ ውስጥ እቆጥራቸው ነበር) ናፈቁኝ ......ተባረኪ የአፍንጫ ቀዳዳ፣ ስናደርግ የምታሰማው ወለልታና በሴትነት መረቅዋ የወረዛች ምንትሷ......ስገባና ስወጣ (ሲሚንቶና ካልቾ ያበረደው ******እዛው ያለ እፍረት እየቆመ)......ቴቢ በጣቶቿ ቅንድቤን ስትነካካ ......በሞቀ እርጥብ አፏ አይኖቼን ስትስመኝ......ፀሐያማው የዳሸን በረንዳ ......የሚጥም ነፋስ በካናቴራዬ አልፎ ቆዳዬን ሲያቅፈኝ......እና ተባረኪ እኔን እያየች ፈገግ ብላ መንገድ ስታቋርጥ......ያስከፋችኝና ያስኮረፈችኝ ነገር ትርጉሙ ጠፍቶኝ ናፈቀችኝ......ቅሬታዬ እንዴት በኖ ጠፋ? እዚህ

ስለ እሷ ብጠየቅ ምን እላለሁ? ከማላውቀው ሰው ጋር 'ትተዋወቃለህ' ያሉኝ የእሷ ነገር ቀላል አይሆንም? ጨለማው እንደበር ተከፍቶ የበለጠ ወደ ጨለማው ስገባ ይታወቀኛል:: ዐይኖቼን ብገልጥም ብጨፍንም የሚታየኝ እሱ ጨለማ ነው:: ዐይኖቼን ገልጬ የማየው ጨለማ ዐይኖቼን ስከፈትም አየዋለሁ:: ከነውዜ እየወጣሁ ወደ ነውዜ እመለሳለሁ:: ከመንጎላጀጅ እየተላቀቅሁ እንደገና እንጎላጃለሁ:: ሕልሜ በቅዠት የቀለመ ነው:: የቸርነት ተረብ ትዝ ሲለኝ አለቅሳለሁ:: እማማ ነጠላዋን ለብሳ የአቋቋሚን ማማር፣ የቀሚሷን አወራረድ፣ የወገቧን አያያዝ፣ ተጠግታኝ ያልተበላሸ ፀጉሬን ስታስተካክል፣ እንዲህ ሳስታውስ አለቅሳለሁ ......የፒያሳን ምሽት ሳስብ አለቅሳለሁ......ትውስታዬና ለቅሶዬ እንደ ጉንጉን ተሸርበው......ሳላቋርጥ አለቅሳለሁ......ሳላቋርጥ እናፍቃለሁ...... ምሽት ሳይሆን አይቀርም ሆያ ሆዬ እሰማለሁ......አሲዮ ቤሌማ እሰማለሁ ......ከሌላ አገር ሆኜ በሬድዮ የሚተላለፍልኝ ይመስለኛል...... አገሬ ላይ ሆኜ አገሬ ላይ አይደለሁም:: ድምፅ ይመጣል ብዬ ወደ አሰብኩበት አቅጣጫ ወደ ጣርያው ቀና እላለሁ......እንዴት ይጥማል? ይህቺ ተራ ነፋስ ሸው ብላ ያመጣቻት ዜማ የማልወደውን፣ የምስቅበትን የስንዴ ጥቢኛ አስታወሰችኝ......(ልጅ እያለሁ ሆያ ሆዬ ማለት ስለ ማይፈቀድልኝ እነ ቸርነት ዘፍነው ሲጨርሱ ተደብቄ በወጥ አበስብሰው ሲበሉ ለልፊያ አብሬአቸው ለመብላት ሞክሬ አልወደድኩትም) ያኔ ቤቴ ታስሬ የምሰማውን አሁንም እዚህ ታስሬ እሰማዋለሁ......ያኔ የምርቀው የልጆች ሆሆታ፣ ዛሬ ሃይማኖተኛ ሰዎች ያሉበት ምድር ላይ እንዳለሁ ይሰብከኛል......በነፋስ እየተዋጡ፣ እየተተፉና እየተደፋፈቁ ብቅ ጥልቅ የሚሉትን አስዮ ቤሌማዎችና ሆያ ሆዬዎች በጀርባዬ ተንጋልዬ እየሰማሁ ......ሲሰወሩ በረሃብ የተጣበቀ አንጀቴን እየዳበስኩ በጨጨዎች የሚዘፈንለት ሙልሙል እንደጠዋቴ ዕንቁላል ፍርፍር ናፈቀኝ......

ውስጤ የሚፈራረቀውን የሚያዘቅጥ ስሜት ለመግለፅ ገለልተኛ የሆነ ጥቅስ ግድግዳ ላይ በቀበቶዬ የብረት ዘለበት በእንግሊዘኛ ጫርኩ፡ hoping is hopeless.........

......ለእኔ አመታት ያለፉ በመሰለኝ ቀን፣ አንድ ሰው በር ከፍቶ እንደ ቀላል ነገር:

«በል ውጣ!» አለኝ

«ምን?»

«ውጣ! መቆየት ፈለግህ?»

«ወደ የት?»

«ቤትህ መሄድ አትፈልግም?»

«እ»

ውሻ ምናምን እንደሚጠራ ሁሉ እጁን አራገበ:: በፍርሃት ኩሰስ እያልኩ ወጣሁ:: ኮሪደሩ በአንዲት ዜሮ ሻማ አምፖል ብርሃን ውስጥ የተነከረ ነው:: ለአፍታ ወደ ውጭ አየሁ:: ድቅድቅ ጨለማ ነው:: በልቤ ወደ ቤቴ ልለቀቅ ሳይሆን ልረሽን የምወሰድ መሰለኝ:: ፈዝዤ እንደቆምኩ ሰውዬው ከኋላዬ ዞረና አመቻችቶ አቁሞ ጨርቅ ፊቴ ዙርያ ጠመጠመ:: ከኋላዬ ሆኖ እየገፋኝ ጥቂት ከሄድኩ በኋላ እንድቆም አዘዘኝ::

«ወደ ግራ ግባና ፊትህን ታጠብ» አለና ወደ አንድ ክፍል ውስጥ ገፋኝ:: የሚዘገንን ጠረን ተቀበለኝ:: ክፍሉ እንደ ሽንት ቤትና ስም ልሰጠው እንዳልቻልኩት ሌላ ነገር ይሸታል:: ወለሉ ከጫማዬ ስር እንደ ብርጭቆ ወረቀት ይንኳኳል:: ቦታው ዝም ያለ በጠረንና በኳኳታ ብቻ የምረዳው ሽብር ነው::

«ጨርቁን ፍታና ታጠብ» አለኝ ከሁዋላዬ የቆመ ከዚህ በፊት ያልሰ-ማሁት እንግዳ ድምፅ:: ቀስ ብዬ ፈታሁት:: ተቃራኒ ትዕዛዝ የሚያስተላልፍ መሰሉኝ ፈራሁ:: አይኖቼን በቀስታ ገለጥኩ:: ሁሉ ነገር የሚታየኝ ደብዛዛ ነው:: ፊት ለፊቴ ሁለት ሜትሮች ያህል እርቆ በዕንብርቱ አኳያ ቧንቧ የተንጠለጠለችበት አንድ የፊት መታጠቢያ ሳህን፣ ከእሱ ቀኝ ለቁጢጥ መፀዳጃ የሚያገለግል በዝገት፣ በዐይነምድርና በብርሃን እጦት የጠቆረ የሴራሚክ ሰሃንና በስተቀኝ ከፍ ብሎ ደሞ በብረት ጨፈቃ የታጠረ ሰፊ የመስታወት መስኮት አለ:: ከክፍሉ ጣርያ ላይ ከተሰቀለች በተባይ ዐይነምድር ከተዥጎረጎረች አጭር የፍሎረሰንት ዘንግ የሚቆራረጥ ደብዛዛ ወተትማ ብርሃን እየተንቀጠቀጠ ይበራል:: አልፎ አልፎ እንደ ጥፊ ይጮሃል:: ፊት ለፊቴ ከነበረው ቧንቧ ከፍ ብሎ፣ ጥላ ብቻ ማሳየት የሚችል ያደፈና ብሩ የተላላጠ የፊት መስታወት አለ:: ፊቴን ለማየት ስሞክር:

«ስማ የውበት ሳሎን አይደለም:: ጊዜ የለንም:: እዚህ መቆየት ትፈልጋለህ?»

ቶሎ ጎንበስ ብዬ ቧንቧውን ከፈትኩ:: ማዞሪያው በዝገት ይጮኻል:: ቀጭን ለመቆም የሚዳዳ ውሃ መውረድ ጀመረ:: የሚወርድ የቧንቧን ውሃ ውበት ያወቅሁት ያኔ ነው:: በእፍኜ ውሃ እያጠራቀምኩ ፊቴን መታጠብ ጀመርኩ:: ቆዳዬ እንደ ብርጭቆ ወረቀት ይጮኻል:: ደርቆ የተጣበቀውን ደም ማዕዳት ከበደኝ:: ፊት መታጠቢያ ሰሃኑ ላይ የጠቆረ ውሃ ተቀላቅሎ ይወርዳል:: በዚህ ቀዝቃዛ መታጠቢያ ቤት፣ በዚህ ቀዝቃዛ ውሃ፣ በዚህ በዐይነምድር ጠረን የተሞላ ሽንት ቤት፣ በዚህ በር ላይ ቆሞ እንዴት

በፍጥነት መታጠብ እንዳለብኝ የሚነግረኝ ጠባቂ፣ በዚህ ምን ያህል ቀን እንደታሰርኩ እንኳን የማላውቅ የመታሸት መሀይም:: ሁሉ ነገር ሕልም የሚመስል ነገር አለው:: ፊቴ ትንሽ ሲፀዳልኝ፣ በጃኬቴ ገበር እየጠረግሁ ዝቅ ብዬ ሳይ፣ ወለሉ ጥልቅና የተሰነጣጠቀ ጥቁር መሆኑን አየሁ:: በጫማዬ ስነካካው ደረቅ ነው:: የደረቀ ደም ላይ ቆሜ እንደምታጠብ ጠረጠርኩ:: ይሄ ደም ጨለም እስካለው ቀኝ የግድግዳ ጥግ ድረስ እንደ ጭቃ ተለጥፏል:: ለአፍታ እዚህ ገብቼ እንድታጠብ የታዘዝኩት ታዝኖልኝ ሳይሆን ይሄን እንዳይ ተፈልጎ መሰለኝ::

«ውጣ!!» የሚል የትዕዛዝ ጩኸት ሰማሁ

በድንጋጤና በችኮላ የተገረበበውን በር ስከፍት፣ ከታሰርኩበት ክፍል ያወጣኝ ሰው ፊት ለፊቴ ቆሞ፣ ፊቱን በቁጣ አጣሞ ሊመታኝ መሳሪያውን ቃጣብኝ:

«ማለት ነበር በዚህ! ሽቶ ትፈልጋለህ?!»

በረንዳ ላይ የአንድ ሰው ጥላ አያለሁ:: ከእሱ አናት በላይ ከፍ ብሎ የማውቀው ጥቂት ከዋክብት የሚቁለጨለጩበት የአዲስ አባ ሰማይ ቁራጭ:: ሰማይ ያውም ከፊሉ እንዲህ የሚያምር አይመስለኝም ነበር:: ከዚህ በፊት ያላየሁት ቀጫጫ ሰውዬ አንገቴ ላይ በአንድ እጁ ያዘኝና በፍጥነት አዙሮ ቀድሞ የታሰረብኝን ጨርቅ ፊቴ ላይ ማሰር ጀመረ:: የተገለጠው ቀኝ ዐይኔ ገና አልተጨፈነም ነበር:: ካሰረኝ በሁዋላ እሱን ለማስተካከል ስሞክር እጄን በጥፊ መታኝ:: (የዚህ ዓይነት ቀልጣፋነት አጋጥሞኝ አያቅውም) ይሄ ቅልጥፍናና ጥንካሬው እስከ ዛሬ ድረስ ይገርመኛል:: ይሄ ጥንካሬ ለብቻው ተገልሎ ስራ ላይ የሚሳተፍበትን ጊዜ እየጠበቀ ሰውዬውን ከቦት የሚሄድ፣ ሲፈልገው እንደ ጋኔን የሚሰፍርበት ይመስላል::

«ቀስ እያልክ በእግርህ እየፈተሽክ ተራመድ:: ብትወድቅ ያንተ ጥርስ ነው»

ከኋላዬ እየገፋኝ ከቤቱ አስወጣኝ:: ደረጃ በቀስታ ወርጄ ጠፍጣፋ መሬት ላይ እንደቆምኩ:

«እጅህን ወደ ፊት ዘርጋ» አለኝ:: በቀስታ ዘረጋሁ:: ጉልበቶቼ ብረት ነኩ:: ጠንካራ እጅ ከኋላዬ መጣና እንደ ቀላል እቃ አንስቶ መኪና ውስጥ ሲጥለኝ ከማላየው ሰው ጋር በጭንቅላቴ ተላተምኩ::

«እንዴ ቀስ» አለ የተላተምኩት ሰው

ያኔውኑ የመኪናው ሞተር ተነሳ:: በግራ በኩል ከጋቢና:

«እድለኛ ነው አቦ......ከጉድጓድ አመለጠ:: አመለጥክ እ? ማን ፀልዮልህ ነው?» አለኝ የማላውቀው ድምፅ:: ሾፌሩም እሱ መሆን አለበት::

«የምልህን ትሰማለህ:: ትከታተላለህ:: ዝንፍ ማለት የለብህም:: ገባህ?» አለ ቀጠለና:: መልዕክቱ ለእኔ እንደሆነ ከድምፁ ይገባኛል:: ራሴን በአወንታ ነቀነቅሁ:: ጎኔ ያለው ሰውዬ ከአቀማመጡ ከራራነት እንደ-ታጠቀና እንደተጠነቀቀ መገመት አልከበደኝም:: ከእኔ ሌላ ሁለት ሰዎች ብቻ ነበሩ::

'እሺ!' ተከትዬው እንድል እየነገረኝ ነው::

«እሺ!» አልኩ:: ቃሉ የእኔ አልመሰለኝም:: ቃሉ ከአገር ውጭ የመጣ ይመስላል:: ያለ ድምፅ ቃሉን ደገምኩ:: እሺ እሺ......

ምናልባት እሩብ ሰአት ያህል ከነዳን በኋላ ዳገት ቦታ ቆምን:: የሰበት ሃይል ከጀርባዬ ይሰማኛል:: መሃረቡ ከዐይኔ ላይ ሲነሳ ዐይኖቼ ያጋጠማቸው ጨለማ ነው:: የት እንዳለሁ ማወቅ አልቻልኩም:: ግራና ቀኝ ብገላመጥም የማየው ጥቁር ደንና መሬት ነው:: ደስ የሚል የአፈርና የተክል ጠረን ሸተተኝ::

«የት ነው?»

«ሰፈርህ»

«እ»

እየተቁለጨለጭኩ ዙሪያዬን አየሁ:: መልከአምድሩ ትንሽ ገባኝ:: ፊት ለፊቴ ጨለማና የመኪናው የፊት መብራት ያረፈበት የደን ፍራክሽን ነው:: ከጀርባዬ አዲስ አበባ ናት--ሁሌ ከሸርሜዳ እዚህ ወጥቼ የማያት:: ካለሁበት ዳገት በእግር ታች ለመድረስ ምናልባት ግማሽ ሰአት ይወስድብኛል:: ደሞ አውሬ አይጠፋም:: በር ተከፈተልኝና ወጣሁ:: በጨለማ የመንገድ ጠርዝ ይገፔ መሮጥ ስጀምር የጣለኝ መኪና ተጠምዞ ወደ ከተማ መሃል ተመለሰ:: የመኪናው ፍሬቻ የሄደበትን አጠቃላይ አቅጣጫ እየተከተልኩ ወዲያ ወዲህ ሳልል የደከሙ፣ የተራቡ፣ የናፈቁ እግሮቼ በሚችሉት አቅም ቁልቁለቱን እየተንደረደርኩ፣ ትንፋሼ እየተቆራረጠና ሁለመናዬን እያላበኝ ሰፈሬ ገባሁ:: እዛ ታች ገና የእዝራን ሆቴል ጣሪያ ሳይ፣ የንተባረኪን የቆርቆሮ አጥር ሳይ፣ እንደ እጂ መዳፍ የማውቃቸውን ኮረኮንች መንገዶቼን ሳይ፣ የተማምን ሱቅ ሳይ፣ የበፍቃዱ ሱቅ ያለበትን የባንክ ሕንፃ ሳይ፣ ወደ አልማዜ ቤት የሚወስደውን መንገድ ሳይ ማልቀስ ፈለግሁ......የቤቴን ግቢ በር እንደዛ ደብድቤ አላውቅም:: በር እንደ እብድ ሳንኳኳ ቆየሁና ዞር ብዬ ሁሉን አየሁ:: ዛፎቹን አየሁ:: ነፋሱን ተነፈስኩ፣ መሬቱን በትክክል መሬት እንደሆነ ለማረጋገጥ መሰለኝ እንደ ፈረስ በእግሬ ጫርኩት:: ስለ አብዮትና ስለ መገንጣጠል አላውቅም ግን እዚህች መሬት ላይ ነፃ ነበርኩ:: ዐይኖቼ

ዕንባ አቅረው ግንባሬን የብረቱ በር ላይ አስደግፌ በቅዝቃዜው ትኩሳቱን ሳበርድ በር ተከፈተ::

«ዓላዛር!!» ብላ ጮኸችና ፀሐይ አንገቴ ላይ ተጠመጠመች:: ከመሬት አቅፌ አነሳሁዋት:: ገላዋ እንዳዛ ቀላል አይመስለኝም ነበር:: ሁሉ አይነት ጣፋጭ ጠረን አላት: የክክ፣ የሳልሳ፣ የጥብስ፣ የቤት ጠረን:: ያለገደብ ጨምድጄ ሳቅፋት ገላዬ እንደ ተራበ፣ ሰው እንደ ራበው ገባኝ:: እንደ ተሸከምኳት አፏን፣ ፊቷንና አንገቷን እየሳምኩ:

«ደህና ነሽ? ደህና ናችሁ? አባባስ? እማዬስ?» አልኳት::

ከአንገቴ ላይ ወረደችና እጄን እየጎተተች በሩጫ በር ከፍታ ቤት ገባን::

አባቴ ምግብ ጠረጴዛው ጋ ተቀምጧል:: የግርማቸው እናት እትዬ ትንሳኤ ሶፋ ውስጥ ራቅ ብላ ተቀምጣለች:: አባቴ ገና ሲያየኝ ፊቱን እጆቹ ውስጥ ቀበረ:: ማዘር እተቀመጠችበት እጆቿን ወደ ጣሪያ ሰቅላ እዬዬዋን ለቀቀችው......

......የፌሽታ ቅመም የጎደላቸው፣ ቢነገርላቸው የማያምሩ ደባሪ ጊዜያት ካልታወቀ የባዕድ ስፍራ ወደ ሕይወቴ ቀዬ መንቆርቆር ጀመሩ:: መጀመሪያ እንዲህ አልፎ ሂያጅ ጎርፍ መስለው መጡ፤ ብዙ ሳይቆይ ትተውኝ የማይሄዱ ነጋ ጠባ የሚፈሱ፣ ወገባቸውን በብረት ድግ የታጠቀ ቅመማቸው የሰነሰነ፣ በርበሬአቸው የተሰለበ ጭጋጋማ አልጫ ቀኖችና ሳምንታት ሆኑ::

## አልጫ ጊዜያት

ከእስር በሁዋላ ለሳምንት ያህል ቤት አርፌ ትምህርት ቤት ተመለስኩ:: ተባረኪ ለጥቂት ቀኖች አብራኝ ቆይታ መታሰሬን እንደቲም ወስጄ አብሬአት እንድፖተልክ ሞክራ ስላልሆንላት መሰለኝ እንደ ቀድሞዋ ተሰወረች:: ልቆጣጠረው የማልችል ከባድ ድብርት ተጫጫነኝ:: እንደ ነገሩ የያዝኩት ትምህርት ሲያደክመኝ፣ አራት ኪሎ ከመልከስከስና የማትመጣልኝን ተባረኪ ከመጠበቅ ሽሮሜዳ እወጣለሁ:: ታዚና እገባለሁ:: ባለኝ ሳንቲም መጠን የምፈልገውን አዝዤ እዝራ በስራ ከተጠመደና የማጫውተው ሰው ከሌለ በዕድ ማዕዘኖች የተከፈፈ የሆቴሷ በረንዳ ላይ ወጥቼ መንገድ መንገድ እያየሁ እቀመጣለሁ:: የሽሮሜዳ ምሽት ፀጥታ አይኖቼን ጨፍኜ የምሰማው፣ የማይገባኝ አይነት ሆኗል:: ፀጥታው ልዩ ጥልቀት ነበረው:: ልክ ሰፈሬ በጥቂት አመታት እንዳረጀች ሁሉ:: በትልቅ በርሜል ንፁሕ ውሃ ሞልተን ፀሐይ ብርሃን ውስጥ አስቀምጠነው ወደ ታች ስናይ እየጨለመ ቲጡን ለማየት የሚያዳግተን ዓይነት:: መንገድ እያሳበሩ በየቤቱ ጓሮ ውሾች ከሆነ ነገር ለማምለጥ እየተገላመጡ ይንሸራተታሉ:: ዝም ያለ መርዝ በሰፈሯ ደም ስሮች እንደ ተደፋ አጃ ይድሃል:: ያልለመድነው አዲስ ሰው ቡና ቤት ሲገባ ከምንጫወትበት ቦታ ከእኛው ፍላጎት ውጪ በጋራ በሚጠራጠሩ ዐይኖቻችን እንፈትሸዋለን:: በአስተያየታችን ግራ ገብቶት መቆየት ቢፈልግ እንኳን፣ ያሌለ ነገር ጠይቆ 'የለም' የተባለውን 'እስኪ ሌላ ቦታ ልፈልግ' ብሎ ይሸሻል:: ለታዚና ሆቴል ብቻ ሳይሆን ለሁላችን እንግዳ ልምድ ነበር:: ከእዝራ ሆቴል ደጋግሜ ወደ ውጭ እየወጣሁ በልማድ የተባረኪን ቤት አያለሁ:: በውጪው ነገር ሽስላች ቤቴ እገባና መደበሬን ማስተናገድ የለመደች አልጋዬ ላይ እጋደማለሁ:: ወይ ሶፋ ላይ ተንጋልዬ ሙዚቃ እሰማለሁ::

ከተጋደምኩበት ወይም ከተቀመጥኩበት ስነሳ ሁለመናዬ ይደክማል:: የሚያነጋግረኝ ሰው እፈልግና ስወጣ ባገኝም ዝም እላለሁ:: ትምህርት ቤት ከተመለስኩ፣ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ወይም ካለቀ በኋላ ከክፍሌ ልጆች ጋር በአፍ መላፋት የምወደው ልጅ ተዘግቼ ወጥቼ ተዘግቼ የምገባ ሆንኩ:: የማየው ነገር ሁሉ ምንም አልጥምህ አለኝ:: ቀጥ ያለ ዕንቅልፍ መተኛት አልቻልኩም:: ከተኛሁ እስኪነጋ ቢያንስ ሶስቴ

እባንናለሁ:: አንዳንዴ ድንገተ፣ እጅግ ጠንቃቃ እሆንና ከዛ ብሞትም ግድ የማይሰጠኝ ሰው እሆናለሁ::

ውስጤ ውሃ እንደ ገባ ሕብስት ፈረሰ......

*

ከአንዳንድ የትምህርት ቤት ጉዋደኞቼ ጋር የለመድኳቸው የድሮ መዝናኛ ቤቶች ስንሄድ ቦታዎች የተሸሹ ይመስላሉ:: 'የት ጠፋ?' እላለሁ እኛ እዛ ወንበር ጋ ቀልድ ስንተረትር ጮክ ብሎ 'እሱን ጆክ ሰምቼው ነበር' የሚለው ያልተጠየቀ ተሳታፊ:: ማን መከረው እንዲሰወር? እኔ ከተባረኪ ሊላ ባዶ ነኝ:: ያለጉዋደኞቼ--ያለ እሱ ያለ እሷ ያለ ሊላውም ባዶ ነበርኩ:: ሳፊ ወተት ተደግፈን የዊንስተንና የኬንት ቁና እየተቀባበልን ያጤስነው ጉዋደኞቼ በሙሉ ሕይወቴ ናቸው:: ምንም መኳኳል ባበዛ ጎፈሬዩን ባረዝም ትንሽ መኖር አውቃለሁ:: ከዚህችም የሚሸውደኝ አይኖርም::......ከትናንት ወዲያ የልጅነት ንፍጥዋን አብራኝ በሶፍት ፔፐር ነፋስ ውስጥ የቀበረች፣ እስከ እያቷ መቁጠር የማትችል ዕውቀት የሌላት ምን ገብቷት ነው ጣቷን ለቃታና ለውስብስብ ትችት ያሰለጠነችው? አካሄዳችን መስመሩ ተለያየ እንጂ ቴቢሽ በፖለቲካው መንገድ (የረቀቀች እየመሰላት) እኔ ብዙ ወደ ማላውቀው ወደ ተስፋ መቁረጥ ጨለማ ስነ'ዷ:: ጠዋት ማታ ጭንቅላቴ በጭንቀት ጉም ታፍኖ ሊፈነዳ ይደርሳል:: ለራሴ አልፈራሁም:: የመፍራት ነገር አይደለም:: በዛ ሰሞን ከምሽቱ አራትና አምስት ሰአት በእግሬ ከአራት ኪሎ ቤቴ እሄድ ነበር:: አንድ ሁለት ቀን አብዮት ጠባቂዎች አቁመውኛል:: ተበርብሬአለሁ:: አቆሙኝ ቦታ ቢረሽኑኝ ግድ አልነበረኝም:: በግድየለሽነት ድፍረት......የተዘረፍኩትን መረቅ......እረፍትንና መዘንጋትን ፍለጋ በከተማው ጉራንጉር ተሯሯጥኩ......

......ከጭቁን ሕዝቦች ጋር ወይ ከብኩናን ጋር ጠጅ በብርሌ ነፋሁ......

......በሲኒማ ቤቶች የሸራ ወጋገን የቀያይ ልጃገረዶችን ምላስ......በቀይ መብራት ፍም የቀዘቀዘች ሴት ግንባር ጠባሁ......

......ገብረ ተንሳይ ኬክ ቤት በረንዳ ላይ በወንበር ስር ጭን ያዝኩ:: ገጻጻ ጣሊያንኛ በሚናገሩ ጎፈሪያም የአስመራ አሳላፊዎች 'ባለጌ! ሌላ ቦታ ሂድ' ተባልኩ:: የባቅለቫ ኩርማን በጥርሶቻችን መሃል ወሽክን ርካሽ አልጋ ላይ ከምንመሳሰል እህቴ ጋር ወደቅሁ......

ምንም ከማይገባት፣ የተደበረች ለግላጋ ጋር ወይም በደረቅ ሌሊት ከሆነች ዓይኖቿ በስካር ከፈጠጡ ሽሌ ጋር ተጋድሜ እልፎ እልፎ የምሰማው የጠመንጃና የሽጉጥ ተኩስ እንደእነሳው የሚገፋፉኝ ጥያቄ፡ ለመሆኑ ማን ነው የተኮሰው? ለምን ተኮሰው? ተኩሱ ማን እለ?

እንዲተኩሱ የነገራቸው ማን ነው? እኔ ከተኳሹና ከተተኳሹ የተለየሁ ኖሬአለሁ? እስከ ዛሬ ጠላቴ ማን ነበር? እስከ ዛሬ ጠላቴ ሳይሆን እንዴት በአንድ ዓመት ወይም በሁለት አመት ውስጥ ጠላቴ መሆኑን አወቅሁ? እንዴት ሊሆን ቻለ? እንዴት አስራአምስት አመት 'እስኪ ልጁ ናና' ብለው ከመኮርኮር እስከ መፎገር ያለፉኝ የግርማቸው አባት እንዴት በአንድ ዓመት ጊዜ ደመኛዬ ይሆናሉ? ያልገባኝ ቀሽም ነኝ ማለት ነው? አንድ ጥይት በራ መጥታ እዚህ እኔና ልጅቷ መሃል እየጤሰች ብታርፍ፣ የምትጤሰዋን የምትንፈራፈረዋን ጥይት በንፁሕ ጣቶቼ ሳይበክል አንስቶ፣ ወዲያ ወዲህ በቀስታ አገላብጦ፣ ጉምዋን በትንፋሹ እያባረረ፣ እዛ ላይ ያለውን ቴምብር አንብቦ፣ ከየት እንደ ተላከች የሚነግረኝ ብልህ ይኖራል?

*

*ጉንታላ 1* እንዲህ ብላኝ ነበር እናቴ ሮዛ ልክ ትንሽ ልጅ እንደሆንኩ ሁሉ እጄን ይዛ፣ ሚስጢር እንደምታወራኝ ሁሉ ድምፅዋን ዝቅ አድርጋ፡

«ዓላዛር እባክህ እዛ ታዚና ቤት አትሂድ፣ ሲመሽ ሲመሽ አትሂድ፣ የጠጣ አንድ ነገር ያደርግሃል»

የጠጣ ግን አልጎዳኝም:: መደበሬን ያዩ፣ ገብቶናል ያሉ፣ እንዲህ ያወራሉ፡

'ደርግ ባያስርህ እንዲህ አትደበርም' ያኔ ይህ መልስ ዕውቀት የወለደው ዕውነት መስሎኝ ነበር:: ዕውነቱ ግን የት ነው? ስበብ ፍለጋ በጊዜ ወደ ሁዋላ ብንሄድ የምንቆመው የት ነው? ምክንያት ፍለጋ ወደ ሁዋላ እየሸሸን በሄድን ቁጥር መጨረሻ ላይ የምንለው ነገር ቢኖር *ለምን ተወለድኩ? አይሆንም? ለምን ተጠነሰስኩ? ታዲያ የት ጋ ላቁም? መቆሚያ ፊርማታዬንስ የሚመርጥልኝ ማነው?*

እዝራ ጓደኛዬ ነውና አብሬው ብሆን ምን አለበት? እዝራ ጋ ባልሄድ ኖሮ የዚያን የግርማን አባት የገደለውን ሰው ታዚና ቤት አልጋ ይዞ ማደሩን ላስቆመው እችል ነበር? ግን እዝራ ቤት እምሽቼ ከሰውዬው ጋር ካርታ በመጫወቴ መልካም ሽፋን አልሆንኩለትም? መልካም ሽፋን በመሆኔስ ምናልባት የመንግሥት ተከታታዮች እንዳያገኙት ስፈረተኛ አላስመሰልኩትም? ታዲያ በሆነ መልክ የወዳጄን አባት ገደላ ላይ ተባባሪ አልሆንም? ደሞስ እናቴን ሰምቼ ካርታ ባልጫወት ኖሮ(ምን ይጎልብኛል?) እዚህ እደርስ ነበር?

እንደገናስ ሰውዬው እኛ ሰፈር ካደረ ላይቀር ለምን አልማዚ አልቤርጎ አያድርም ነበር? ደሞስ ለምን ገዳይ ሆነ? ማነው ገዳይ ያደረገው? ማነው

መንገድ የመራው? ማንን ሊጠቅም ነው? ከእኔ ጋር ኮንከር ሲጫወት እንደሚቀራረቡ ወዳጆች ሆነን እየተሳሳቅን ሳለ ወንጀል ሊሰራ እንደሆነ ያውቅ ነበር?

ደርግ ዞርበትና የሚያደርገው ጠፍቶት ቢያስረኝ ደርግን ስህተተኛ ያደርገዋል? የፖሊስ ስራ ዋናው መጠርጠር አይደለም እንዴ? እንደ ዜጋው ሊገደል ሲል ዕርዳታ የማያደርግ መንግሥት አለ? ሁሉ ነገር ድብቅ በመሆኑ መንግሥት እኔን ቢጠረጥረኝ ስህተት ነው? ለምን ቢያንስ አድራጊዎቹ ገና መንግሥት እንደያዘንና እንዳሰረን እኛ እንዳሌለንበት በሚስጢር መልዕክት አይልኩም ነበር? እኛ ሰላማዊ ሰዎች ተማርረን ደርግን እንድንጠላ ነው? ደርግንስ ስንጠላ እንዲህ በመሰለ ቴክኒክ ነው?

እናቴ እርግብግብ፣ ቶሎ ዕንባ የሚተናነቃት፣ ፈሪ፣ ችግር ቢኖርም ባይኖርም፣ ገና በይሆናል ድምፅዋ ሳያቀዋርጥ ምሕረት የሚለማመጥ ነበረች:: ከተፈታሁ በሁዋላ እንደተነገረኝ፣ ታስሬ የሄድኩ ዕለት ራሷን ሳተች:: እስከፈታ ድረስ በየቀኑ ራሷን ትስት ነበር:: እናቴ እንዲህ ስትሆን ነገሩ አሳሳቢ መሆኑን ተረድተው ለምን ታጋይ ነን ባዮች 'እኛ ነን መክብብን የገደልነው' ወይ በዚያ ጊዜ አማርኛ 'እርምጃ የወሰድነው' 'የደፋነው' ምናምን አይሉም ነበር? ምን አስፈራቸው? ለምን ሌላ ሌላ ነገር ብዙ ከሚያወሩን ይህቺን ዕውነት አይነግሩንም ነበር? እማማንስ ማነው 'ደርግ ልጅሽን ከወሰደው ይገለዋል' ያላት? ሳልሞት እንዴት ይታወቃል? ለምን በሰፈሩ ያሉ ወይዛዝርትና ወይዘሮዎች አስፈሪ ወሬ ለእማማ እያመጡ የነገሯት ሁሉ የግርማን አባት ከገደለው አሸባሪ (ወይስ 'ነፃ አውጪ' ነው የሚባለው?) ጋር በጥይት ደረጃ እንኳን ባይሆን በመረጃ ደረጃ አንድ አይሆኑም? ቃታ የሳበ ብቻ ነው ገዳይ? ራሷን ካሳታት ድንጋጤ ስትባንን 'ደርግ ከያዘው በቃ ጨረሰው' እያሉ ተስፋ እንድትቆርጥና ደጋግማ ራሷን እንድትስት አላደረጉም? የእሷ መልክና ቁመና ብትጎዳ ይጋባላቸው ወይ ይላከክላቸው መሰላቸው? በዚህ ድርጊታቸው ትንሽ በልባቸው ለማንም ሳይነግሩ በመታሰሬና በዚህም ሰበብ እሷ በመጨነቋ ሳይደሰቱስ ይቀራሉ? እነዚሁ ወሬኞች ቤቴ መጥተው 'እንኳን ተፈታህ' አላሉኝም? 'ተአምር ነው መፈታትህ' ብለው የእነሱን በአፍ ሰውበላነት በደርግ ላይ አላሳበቡም? እኔ እስር ቤት እያለሁ እናቴን በወሬ እንዳልበሏት? እነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች በዝምታ ይከተሉኛል:: ብቀላውጥ ባንጋጥጥ መልሱን የሚሰጠኝ ግን የለም:: በስንስለት ሳልተነተነ የሚሰወሩ፣ የነገሮችን የግንኙነት ካቴና ሳጤን ግን እንደማይደበቁ ታውቋቸዋል? እኔስ እንደ ብሩህ የሚያደርገኝ፣ ብሩህ ወዳጆቼ 'አራዳ ነን' የሚሉ ውስብስቡን ነገር ቆመን ከመፍታት ተንጋለን በአጭሩ አላሰብንም? እንደው ለመሆኑ የግርማ አባት መገደል ሁላችንንም በተለያየ ደረጃ ወንጀለኛ አያደርገንም? የሚቀረን ነገር መልሱን

ደርስንበት ሃላፊነት እንደነበረብን ስንረዳና የተገለጠልንም ዕውነት አሳፍሮን ተያይዘን ዝም ማለት ብቻ አይደለም? ማን ማንን ይወርፋል?

በምኞትና ባለመታዘዝ በተገነባ አካባቢ፣ ባለመግባባትና ባለመደማመጥ በተገነባ አካባቢ የግርማ አባት መሞት እንግዳ ነው? የእኔስ መታሰር እንግዳ ነገር መሆን አለበት? እኔስ ብዙ ጥያቄዎችን ጠይቄ ለእናቴ መጎዳት ተጠያቂ የመሰሉኝን በሙሉ ከማኩረፍና ከመዝጋት ይልቅ የግርማ አባት ገዳዮች ላይ ብቻ ለምን አፈጠጥኩ? መያያዙ የሚያቆመው የት ላይ ነው? 'ሁሉ ነገር የተያያዘ ነው' ይባላልና እያንዳንዱን ሁኔታ በመተንተን የሁኔታዎችን የግንኙነት ሰፋትና ጥልቀት በማጥናት ለምን ውሳኔ አልደረስኩም? ምን ያዘኝ? ለአእምሮዬ ነገሩ ሰፋበት? ወይስ ቀስ ብሎ እንጎሌ ውስጥ በሰረፀ በሰዎች አባባል ተመራሁ? ወይስ የሁሉም ተሳትፎ አስፈራርቶኝ ከሁሉ መሸሽ እንደማልችል ገብቶኝ ደካማ ሃሳባቸውን ተቀበልኩት? ለምን ትንታኔዬ በአጭር ቀረ?

ምንም እንኳን ትውስታዬን ከሌላው ቁጥጥር ነፃ ለማውጣት ብታገልም በትንሹም ቢሆን በምትቆነጥጥ ስሜት እናቴን የበደልኩ ይመስለኛል። ዕርግብግብና፣ አንጀቷ ጣጣ እንደማይችል ስለማውቅ፣ ለምን የምትለኝን አልሰማም ነበር? እንኳን እኔን አንድ ልጇን ትልቁ የሚሰራውን የሚያውቅ አባቴ አምሽቶ ከመጣ 'ቢያንስ ስልክ አትደውልም እንዴ?' እያለች ትነዘንዘው አልነበር? ስንት ጊዜ ነው እሱስ ደጓ ፀባይዋ ሰልችቶት 'ምናለበት እግዜር ካንቺ በገላገለኝ' ይል የነበረው? እራሷን ስታ ሕይወቷ ቢያልፍ ኖሮ ምኞቱ ተሳካለት አይባልም? በአባቴ ሌላ ፀባይ ብዙ ጊዜ ቅር ቢለኝም በዚህ በዚህ የእሱ ክፋት ተባባሪ ሆንኩ ማለት አይደለም?

*

*ጉንተላ 2:* ዙሪያ ገባዬን ሳይ የጦርነት ዘፈን ይዘፈናል። አጋዴን በሶማልያ ተይዞ ይፎከራል። በዚህ ፉከራ መሃል መሃል ድሮ እስኪመሽ የምንጫወትበት መንገድ በፀጥታ ገመድ የታነቀ ይመስላል። ፀጥታው እንደ ቫይረስ ነበር። እያንዳንዱ ሜትር ፍርሃትና ጥርጣሬን ተንከርአል። አየሩ በትዝታችን ውስጥ ብቻ በምንሰማው የተጎረደ የልጅነታችን ድምፅ የሞላ ነው። ጆሮዬን በዕጥና ስከፍት በሰፈሩ ውስጥ ከአየሩ ጋር የሚመሳሰስ የሆነ ዝም ያለ ኡ! ኡ! አለ። ከዋናው መንገድ ተሻግሮ በዩዳር የተንጠላጠሉት ጠላና አረቄ ቤቶች በሮቻቸው ተገርብበው የትም የማይደርሰው ፌሽታቸው እንኳን የለም። በኤሌክትሪክ ገመዶች ላይ የተንጠለጠሉት ፓራሹቶች ያማላውቀውንና ያላየሁትን የሰይጣን ቆለጥ ያስታውሱኛል። በልጅነቷ ስትጫወትበት የነበረ ግቢዋ ፊት ለፊት ያለው ቦታ ላይ ቆሚ ተባረኪን አሰብኳት። ሩቅ አልነበረም። በምኔ ፈጥኜ ተጠፋፋን? እንዴት በችኮላ አረጀን? ዳገቱ ወደ እንጦጦ መውጫ እየተባረርን የምንወጣና የምንወርድበት። አንዳንዴ ከርዳዳ ፀጉሯን እየፎተትኩ እሷን የማስሞሀበት። ያ የሚያምር ልመና። 'በማርያም

ልቀቀኝ!' እዛ ዳገት ላይ እዛ ደን ውስጥ በፍርሃት የወደቅንበት:: ሰንባዬን በዝምታ ጠረግሁ:: የእንጦጦ ብርድ የለም:: እሱም ሕቡዕ ገብቶ በታሳሽ ታስሮ ወይ በሽብር ተመቶ ይሆናል:: አስፋልቱ መሃል ላይ የሚደማ አየር አግድም ተዘርሮ:: ደርዞ ላይ በፖለቲካ ሩካቤ የደከመች ተባረኪ ከደረቷ ደም ሲፈስ:: ሳላቋርጥ እናፈጣለሁ:: ከእዝራ ፔንሲዮን የሚገባ የሚወጣ የለም:: የሰላም መኖርና አለመኖር መለኪያ አንዱ ቱሌታምነት ነበር?

ራሴን በሁለት እጆቼ መሃል ይዤ እኔ የማላውቀውና የማይገባኝ፣ ሊገባኝ ያልቻለ እቅድ እንዳለስ? እላለሁ:: መክብብን በሚመለከት ተባረኪ እንደ ቀልድ ያወራቻቸውን ነገሮች ከተሰወሩበት የትውስታዬ ሚዳ እንቅልፍ አጥቼ መልቀም ጀመርኩ:: አንዱ የክፍል ጓደኛዬ 'ጂሚ ምነው በአንድ ሳምንት አስር ተደበርሽ፣ ለመርሳት ሞክሪ' እያለኝ......

በጨዋታ መሃል ትለኝ ነበር ተባረኪ አንዳንዴ:

«ጋሼ መክብብ ከከረን አልመጡም?»

«አስመራ ናቸው፣ ከተማው በሻቢያ ተከቦ መውጣት አይቻልም ይላሉ:: ባለቤታቸው ትንሳኤ ሁሌ እንዳለቀሰች ነው»

«ለምን ስራውን ትተው አዲስ አባ አይገቡም?»

«እንጀራ ነው»

«የሆነ ጥቅም ይኖረዋል:: ትተው ቢመጡ ምን ይሆናሉ?»

«ምን ማለት ነው ጥቅም ይኖረዋል? ቤተሰብ ማስተዳደር ጥቅም ሳይሆን ግዴታ ነው:: በልቶ ማደር ጥቅም አይደለም:: ግርማን ጠይቂ፣ አላውቅም:: አባትሽ ለምን ከደብረዘይት እዚህ አይመጣም? ወታደር እኮ ናቸው:: በኮማንድ ነው የሚሰራው:: ተዘፍዘፌ ከተባልሽ መዘፍዘፍ ነው»

«እሱ ንጭንጩ:: ሚስጢር ማድረግህ ነው?......የዘርአይ ጉዳይ የተለየ ነው ደሞ»

«የምን ሚስጢር? ግርማ ይነጫነጫል? ምናባቷ» ብዬ ትከሻዋን እመታታለሁ:: ያን ጊዜ ልምታት እንጂ:: ግን ልማድ አለኝ:: ወሬ መሃል ያልጣመኝ ነገር ሰው ሲናገርና ስቀኖቀን ትከሻ እገፋለሁ:: ብቻ ከእሷ ጋር እንደዚህ ዓይነት ወሬ ማውራት አይከይፈኝምና ወደ ልፊያዬ እወስዳታለሁ::

«እርሺያቸውና የራስሽን አባት አስታውሺ:: ዘርኡ ደህና ነው? እ» ብዬ ወገቧን ይዤ ወደ እኔ እስባታለሁ::

«ተው በእናትህ እዛ ጋ አትኅንትለኝ» 'አትኅንትለኝ':: ቃሉ አስቆኛል:: የሆነ ጎንደርኛ ነገር:: ቃሉን ያወቅሁት ያን ቀን ነበር:: ሁልጊዜም ግን የምነካት እንደዛ ነው:: ለምን ያን ጊዜ ገፋችኝ? ለምን ተናግራ

የማታውቀው ቃል ከአፏ ወጣ? በእንግዳ መዝገበ ቃላት......ለምን አሾረችብኝ? ስለ ነካካኋት ደብሯት ነው? ወይስ የወሬ ምንጭነቴ ስለ ቆመ? ብቻ ቃሉ ትዝ ይለኛል:: ስላፋት ወሬ ለቀማዋን እያበላሸሁ ከነበረስ? ከእሷ ይልቅ ለእኔ ቢቀርቡኝም እንደ እሷ አክርሬ ስለ መክብብ ጠይቄ አላውቅም:: ልጆች ከልጆች ጋር ነበር ግንኙነታችን:: ከልጅነታችን አባቶቻችንንና እናቶቻችንን የምንሸሻቸው ትንንሽ መንግስታት ነበሩ:: ይሄ የወሬ ለቀማዋ ጥበብ ግቡ አልገባኝ ይሆን? ግን እኮ የአገራችንን አባቶች መሰለል ቀላል ነው:: ጠና ብሎ አድር ያሌለው:: ጠና ብላ ማርያም የማትጠጣ የለችም:: ቡና አፍልተው ገበናቸውን ሲገላለቡ ነው የሚውሉት:: እርፍናም የለውም:: በጥርጣሬ የሚሞሉኝን ነገሮችንም አሰላስላለሁ:: መክብብ የተገደለ ዕለት እቤቷ በረንዳ ላይ አብረን ነበርን:: ለምን እጄን እየጎተተች 'አትሂድ' አለችኝ? ለምን ያን ዕለት ተከትላኝ አልመጣችም?

ሌላ ሌላም አውርተናል፣ ግን እንደተለመዱ ተራ ነገሮች ከኮስታራ የጉዳይ ማህደር ያልገቡ ሆነዋል:: ይሄም ያስፈራኛል:: ምናልባት እሳቸው እንዲገደሉ የሚያደርግ መረጃ አቀብዬ ከሆንስ? ለእኔ ተራ የመሰለች ከሌላ መረጃ ጋር ተቀላቅላ ወይም የሆነ ሰው ቀላቅሎ ሲጠቀምባት የምትከብድ? ምናልባትስ በሆነ መቶኛ እኔ የመክብብ ገዳይ እንደ ሆንኩስ?

መክብብ ከሞቱ በኋላ ግርማን አላየሁትም:: ወር ቆይቼ ላየው ስሄድ (ከእስር ቤት ወጥቼ ለመጀመሪያ ጊዜ) የቤቱ አጥር በር እንደተቆለፈ ነበር:: ሳንኳኳ ሰው ይወጣል ግን ሳይከፍቱልኝ እየተውኝ ይመለሳሉ:: ይሄ ድርጊት ራሱ ሁለመናዬን በንዴት በላው:: እንደውም አንድ ቀን ከአጥር ውጭ ቆሜ 'ክፈቱ!' እያልኩ ጮህኩ:: የመለሰልኝ አልነበረም:: ከጥቂት ወራት በኋላ መኖሪያቸውን ለወጡ:: ይሄም ያሳፍራል፣ ደም ያፈላል:: የጓደኛን ዕቃ ተሸክሞ እየተተራረቡ ቤት መለወጥ ደስ አይልም?

ደሞስ እንዴት ነው ለአስርና ለአስራ አምስት ዓመታት ያህል የተገነባ የልጅነት ወዳጅነት በአጭር ጊዜ የተናደው? ፍልስፍናው ምን ዓይነት ነው? ከቴቢ ድርጊት ቶችስቼ የምወደውን ሰው የዕውነት መውደዴ አጠራጠረኝ:: 'እናንተን እወዳለሁ' ብዬ ወደ ጎረቤቶች እያመለከትኩ ብናገር ቀፎ መሰለኝ:: ለዓመታት አብሮ መኖር ባዶ አጋጣሚ ሊሆን ነው? ለመጣላት ጊዜ እየጠበቅን ነበር ማለት ነው? ይሄም ጥያቄ በሆነ የአእምሮዬ ጉድጓድ ከከተሙት የግርማቸው፣ የመክብብ፣ የራሷ የተባረኪና የሌሎች ጉዋደኞቼ ብዙ ትዝታዎች የሚያነዱኝንና የሚያበርዱኝን እያነሳና እየጣለ:: በትዝታቸው ብቻ እዛ አንጎሌ ውስጥ አንዱ ቦታ እንደጠባሳ አርፈው ግን ሰፈሬ መስክ ላይ የዕውን ሳይኖሩ::

ለጋ እድሜዬ ወደማያውቀው ስፍራ የሚያስገባውን በር እየተንቀጠቀጠ ከፍቶ ገባ።

ኖር......

•

*ጉንተላ 3፡* አባቴ አንድ ቀን ማታ ከመኝታ ቤቴ ጠራኝ። እነበረበት ሳሎን ሄድኩ። ባካርዲውን በአምቦ ውሃ እየጠጣ አንድ እግሩን ጠረጴዛ ላይ አጋድሞ መለኪያ ባልያዘ እጁ ፊት ለፊቱ እንድቀመጥ ጠቀሰኝ። ከቴፕ (ማንም የማይነካበት የራሱ ቴፕ ነው) የሚሰማውን የሃይሌ መርጊያ ኢንስትሩመንታል ሙዚቃ ቀና ብሎ እኔን በጠቀሰበት እጁ ስቶፕ ተጭኖ ዝም አሰኘና፡

«ስማ ምን አስበሃል?» አለ ኮስተር ብሎ

«ስለምኑ?» አልኩት

«ይገባሃል ምን ማለቴ እንደሆነ። አውቀህ አትደናቆር። ስለ አብዮቱና ስለ ተባረኪ»

«ምንም»

«አይመስለኝም። መደባበቅ ጥሩ አይደለም። 'በሽታውን የደበቀ መድሃኒት አይገኝለትም' ትል ነበር እናኑ። ተረትና ምሳሌ አልወድም ግን ትንሽ ያግባባል። ትንሽ ያስፈራራል። በግልፅ እንነጋገር። መሸፋፈን የትም አያደርስም። ጉዳዬ እንዲህ ነው......»

መለኪያውን ከጠረጴዛ ላይ አንስቶ አንዴ ተጎንጩና እያጣጠመ እነበረበት መለሰው፡

«ትክክል ልንገርህ......ተባረኪ ለአንተ ግድ የላትም። ሁላችንም የምንፈልገውን ማግኘት አለብን። ረም ቶኒኬን ማግኘት አለብኝ። የምትፈልገውን ካላገኘህ ትጠይቃለህ። ማን የምፈልገውን ከለከለኝ? መልስ ለማግኘት ጠይቅ ያን። ሁሉ የፈለገውን ያገኛል። ሰክረህ ወድቀህ ጥርስህ ቢሰበር የፈለግኸው ነውና አትበሳጭ። ለምንድነው ፖለቲካ ያልገባሁት? አቅም አንሶኝ ነው? ላገሬ ስለማላስብ ነው? ኖ። ሁሉ ነገር ውዥንብር ነው። ገባህ? ኢኮኖሚስት ሆኜ ውጭ አገር ወይም ለውጭ ድርጅት ወይም ባንክ መስራት እችላለሁ። ጉራ አይደለም። የአገሬን የዋህነት እወዳለሁ፣ ይቅርታዋን እወዳለሁ፣ አየሩን እወዳለሁ። ሕይወት በቪላና በመኪና ብቻ አትገመገምም። አውሮፓ በል ሰሜን አሜሪካ ያላየሁት አገር የለም። ሽሮሜዳን የሚያክል አታገኝም። ባቡር የለምና ሺህ ፎቅ የለምና ምን ይጠበስ? ከዚህ በፊት ላላወራህ እችላለሁ። ምክንያቱም እውነቱ ጋ አንተ በራስህ ልምድ እንድትደርስ ነው። ከማየት እንጂ ከእኔ

ወሬ እንድትማር አይደለም:: አባትም ወሬኛ ሊሆን ይችላል:: አባትም ይሳሳታል:: ግን......ዛት ኢዝ ዘ ትሩዝ[33]:: ሽሮሜዳ የማገኘው የሰለጠነ ደሃነት ነው:: የምፈልገው ያ ነው፣ የምፈልገውን ነው ያገኘሁት:: በግድ ካባረሩኝ እሄዳለሁ:: በየቢሮው ፖለቲካቸው ውስጥ ካልገባህ ደማቸው የሚፈላ መዓት ናቸው:: ለአንተና ለአገሪቷ አዝነው ነው? አይደለም:: በሚያነዱት እሳት የተማረው ጥቂት ወጣት እንዲነድ ነው:: ፖለቲከኛ ባትሆን እንኳ በወታደር አስጠምደው ሊያጠፉህ የሚፈልጉ መዓት ናቸው:: አገሪቷ አሁን ጥምዝዝ ያለ የወሬ በሽታ ውስጥ ናት:: ‘ምሁሩ በመሰደድ ላይ ነው’ ይላሉ:: አገራችን ብዙ ምሁር የላትም የሚንጋጋም:: የፖለቲካውን አለም ያሽከረክራሉ የሚባሉትን አንዳንዶቹን አውቃለሁ:: ማክረር ይወዳሉ:: በግድ ቼ ጉቬራን እንሁን ብሎ ነገር:: አገሪቷ ቬትናም ብትሆን ደስ ይላቸዋል:: ‘ለምን?’ ብትል ሆ ቺ ሚንን ለመሆን ይቀላቸዋል:: ሌላው አለም ያሉ ግለሰቦች ጀግና የተባሉበትን ነገር ባያስፈልግም እዚህ ቢያደርጉ ደስ ይላቸዋል:: በዚህ ብናደንቃቸው ይወዳሉ:: ሺህ አይነት የአገርና የኢትዮጵያ ካባ ቢያለብሱት አንድ ነገር አውቃለሁ ቂል አይደለሁም......አይ አም ኖት ኤ ፉል[34]:: አንተም እንድትሆን አልፈልግም:: በግድ ‘እንጣላ’ ብሎ ነገር ፍለጋ አለ? ኢትዮጵያ ጠላቶቿ ላይ እንኳን አክራሪ አይደለችም:: ሃይማኖታችንና ቋንቋችን የተጻቀለ ነው:: ይሄ ልዩ ሊበራሊዝም ነው:: የትም አገር የለም:: ምን ማለት ነው? እንዲህ የሚያባላ ነገር የለም ማለት ነው:: አንዳንድ አለባበስ አበላልን ምናምን የመሰለ ከባዕድ እንደሚቀዳ ልክ እንደ ጆሊ ጃኪዝም ምናምን በለው ፖለቲካውን......:: መተማማት መጋደልና መሰዳደብ አኮሳተረው እንጂ ውስጡ ያው ነው:: የፖለቲካ ጆሊ ጃኮች ናቸው:: ወደ ፓስታ ሊለወጡ የሚለፉ ድፎ ዳቦዎች ናቸው:: አሁን የማየውና የምሰማው ሁሉ ልክ አይደለም:: አንድን ነገር ሳይመረምር በተራ ልዩነት ላይ ተመስርቶ ሺት የሚሰጥህ ገና ያላደገ ልጅ ነው:: ያውም ሬታርድድ የሆነ:: ልዩነትን በቋንቋ በማግነን በማይሆን ነገር ቶሎ ተገዳድሎ መስዋዕት በመፍጠር የአላማ ነገር ተትቶ (ቀድሞም የለም) በነዚህ በፈጠሩአቸው ሰማዕታት ስም ለዘላለም እንድንቀያየም የሚፈልጉ ይመስላል ሞር ሺት ዊል ኪም[35]:: የፀናዕል አባት ቤተሰቡን ይዞ የተሰደደው የዕውነት ከ60ዎቹ ውስጥ ዘመድ ስላለው ፈርቶ ነው? እንደውም ለሮዛና ለአያትህ የሚቀርቡ ሰዎች አሉበት:: እንግዳ ነገር ስለሆነ ነው:: ስለዚህ ጊዜህን አታጥፋ፣ ለተባረኪ አትጨነቅ:: ማታ ማታ

---

[33] ያ ነው እውነቱ (That is the truth)

[34] ቂል አይደለሁም (I am not a fool)

[35] መዓት ቆሻሻ ነገር ይከተላል (more shit will come)

እሷን ስትጠብቅ አይሃለሁ:: ያላየሁ ይመስልሃል? የምናውቅ እናውቃለን:: ፍቅር ከሁለት በኩል ሲመጣ ነው:: በአንተነትህ ሳይሆን በፖለቲካ አቋምህ የምትወደድ ከሆነ እርሳው:: የተለወጠችው እሷ ናት:: ቆንጆ ባገሩ ሞልቷል:: የሆነች ዘጠዘጥ ቂጣም:: ሶሪ ሽ. ደዝንት ሃቭ ክላስ[36]:: እኔ እንደውም ድሮ ከፀናዕል ጋር ነበር የጠረጠርኩህ:: ለማንኛውም በፍቅር መፍረድ አልችልም:: ግን ለራስህ ብቶሎ ስለ ላይፍህ[37] መወሰን ካልቻልክ፣ ጣልቃ መግባት አለብኝ:: ሁለተኛ በሃሳብ ባክነህ በመንገድ ላይ ብቻህን እያወራህ ስትሄድ ማየት አልፈልግም:: የተሸነፈችው ተባረኪ ናት:: ጌም[38] የለወጠችው እሷ ናት:: ግን ራስህን ሁን:: ሁሉ የፈለገውን ያገኛል:: መክብብ ገንባይ ተዋጋና ተባረኪን ምን አገባት? ለአባቷ ማዳላቷ ነው? አባቷ ትቷት ሄዶ እኛ ነን ያሳደግናት:: አይደለ? ግን መርጣለች:: ምን ማድረግ ይቻላል?»

ረሙን ይዞ ከተቀመጠበት ተነሳና ቴፑን ዘጋ:: ያኔውኑ ዞር ብሎም ሳያየኝ sl 1200 የማትሱሺታ ግራማፎኑ ላይ ፑቺኒ የደረሰውን የማርያ ካላስን ቶስካ ኦፔራ አስገባ:: ትንሽ ቆይቶ ፒተር ቶሽን ይከታል:: ተቀመጠና በትኩረት እያየኝ፣ ባላስለመደኝ ኮስታራነት:

«ከአሁን በኋላ እዚህ አገር መኖር አትችልም:: እርሳው:: በባዶ የሚጣላ ቦታ ለዘላለም ረብሻ ነው የሚሆነው:: ስኮላርሺፕ ሂድ:: ከእናትህ ጋር ተነጋግረናል ኢስት ጀርመኒ አገኝልሃለሁ:: ትምህርት ከሚሸን የሚሰሩ የማውቃቸው ሰዎች አሉ:: በአጭር ጊዜ ይሰናዳልሃል:: ምን ይመስልሃል? በትርምስ ውስጥ አንድ ነገር እንዲደርስብህ አልፈልግም:: እንግባባ»

አስቦበት እንዳናገረኝ ይታወቃል:: በሚገርም መልክ የትም አገር የመሄድ ፍላጎት እያደረብኝ ነበር:: የአባቴ ሃሳብ በዚህ ጊዜ መምጣቱ እና ከእኔ ምኞት ጋር ግጥጥሙ ትንሽ አስደነገጠኝ:: አፌ እንዳመጣው:

«ኢስት ኢሮፕ አይደብርም?»

«አስብበት:: ምዕራብ ትንሽ ጊዜ ይወስዳል:: ሁለመናቸው የሚመሳሰሉ ሰዎች ሲደባደቡ ቲያትር ይመስላል:: ተመሳስለህ ከተጣላህ የሆነ ነገር አለ ማለት ነው:: ሰላም አይኖርም:: በዚህ ሁኔታ ውስጥ ምኑን ተማርከው? ደሞ ኢስት ኢሮፕ ከማን ያንሳል? ቢያንስ ከእኛ ይበልጣሉ:: ከጠቀመህ በቂ ነው:: ፕሮሰሱን በስድስት ወር እንጨርሰዋለን:: በዚህ ሳምንት ውስጥ ብትመዘገብ ነሐሴ ወይም መስከረም ትሄዳለህ:: የኢ ኤስ ኤል ሲ

[36] ጥራት የላትም (she has no class)
[37] ስለ ሕይወትህ (life)
[38] ጨዋታ (game)

ዶኪመንትህን አዘጋጅ:: ቀበሌ ቶሌራ እንዲፅፍልህ እነግረዋለሁ:: አስብ:: እኬ?»

ወፍራም ጥልቅ ድምፅ ያለው ሰው በጣሊያንኛ ማቀንቀን ጀመረ:: ከመሃልም:

«ብፅጥታ አገር ለቀህ ትሄዳለህ......» ዞር ሳይል የግራማፎኑን ዜማ በማያምር ድምፁ ማጀብ ጀመረ::

ወደ መኝታ ቤቴ በዝምታ ተመለስኩ:: በእርግጥ ጥያቄዬን መልሷል? ችግሬን አቃሏል? የመለሰልኝ አልመሰለኝም:: ከችግሬ ነው የምሸሸው:: መተከዜ አልቀረም......ከዛም በፊት ከዛም በኋላ ከአባቴ ጋር ብዙ ኮስታራ ነገር አውርተን አናውቅም:: ግን ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት የተናገረውን አንድ አባባሉን ወስጄ አሰብኩ: 'ሁሉ የመረጠውን ያገኛል'

ሁሉ የመረጠውን ያገኛል:: (ያው በልቤ) በጨለማ የጮኸ በጨለማ ይወድቃል፣ (ይሄንንም በልቤ):: መስዋዕት መሆን የፈለገ መስዋዕት ይሆናል:: ፍቅር የፈለገስ ፍቅር አያገኝም? (ይሄንንም በልቤ)

በሚቀጥለው ቀን ከእማማ ጋር ተነጋግረን ከአገር መውጣቴን እንደ ምትደግፍ ሁሉ 'እሺ' አለች:: ተደብቃ እንደምታለቅስ አውቃለሁ::

*

ወደ ምስራቅ ጀርመን ልሄድ ሁለት ቀኖች ሲቀረኝ ተባረኪን ላገኛት ስላልቻልኩ፣ ለእናቷ በቀጥታ መልዕክት መተው ስፍሳፋ ስለሚያስመስለኝ እናቴ ለእናቷ ለትደነቂያለሽ ነግራ እንዳያት የእጅ አዙር አሳፋሪ ሙከራ አደረኩ:: እንደዚህ መብለጥለጥ ነበረብኝ? በዚህ ስልት ጠርቼአት፣ ተባረኪ ልትሸኘኝ እቤት መጣች:: ገና ያን ቀን የተዋወቅን አይነት እንግዳ ሆነችብኝ:: ግራ ያጋባል:: በትክክል ለብቻችን አንድ ክፍል ውስጥ ተቀምጠን እንዴት ራሴን መቆጣጠር ይቻለኛል? ያሳለፍኩትና የማላውቀው፣ ገና የማሳልፈውና የማላውቀው ጉዳይ እላዬ ላይ እንደ ቍዝቃዛ፣ ደኑ እንዳለቀ የየረር ገመገም ተጫነኝ:: ግን የፍቅረኛዬ ገላ በሆነ መልክ የእኔ አይደለም? ዐይኖቼን ጨፍኜ የማሕፀንዋን ፀባይ መዘርዘር የምችለው እኔ ብቻ ነኝ እላለሁ:: እንኳ በፖለቲካ ቢዘጋም ገላዋ ግን የእኔ ነው:: እየተነጫነጨች እየተፈራገጠች የምወዳቸው በግድ የተከፈቱ እግሮቿን አልፌ ውስጥዋ ሳርፍ የተቀበለኝ እንደ ዘመድና ወዳጅ ነው:: ደጃፏ እርጥብ ነበር:: እንደበት ቢኖረው 'እንኳዋን መጣህልኝ' ይለኛል:: ምክንያትና ሳይንስ የማይደርሱበት እውነት አለ:: የፖለቲከኞች ሴንጢ የማይቆርሰው ቅቤ ይሄው:: ከአፍቃሪ ስርአት ተጣልቼ በግዴታ ስተኛት ደስ አላለኝም:: አዎ ያኔ ያገኘሁት ትርፍ መደበርና ውድ ካናቴራዬን በቀይ ወጥ ማበላሸት ነው:: ሌላም ድብርት አለው: ከስሬ እንደሚሞቅ የቄራ ስጋ ተኝታ ገላዋን በትክክል ሳልነካውና ሳልስመው

የምገባበት ገብቼ መውጣት:: ግን የሚወዳት ሲሰናበታት ችላ እንድትል ንቃቱንና ብልጠቱን (ከተባለ) ማን አስተማራት? ከሳይዋ ሰነሳ፣ ልቤ ውስጥ ከባድ ሐዘን ነበር:: ሐዘኑ በመድፈሬ ሳይሆን ከእኔ የራቀች መሆኑን መረዳቴ ነው:: ሱሪዬን ወደ ላይ ሰብስቤ ጅራቴን ሸጉቤ አልጋ ዳር ተቀምጬ ወለል ወለል እያየሁ የምትናገረውን ስጠብቅ፣ በዝምታ ቀሚሷን አስተካክላ ከክፍሌ ወጣች:: 'ደህና ግባ' እንኳዋን አላለችኝም:: አልፋ ሂዳ ሳሎን ስትደርስ 'ደህና እደሩ!' ስትል ሰማሁዋት:: የገረመኝ የድምፅዋ ጉላት ነው:: ከእኔ ጋር ያልነበረች፣ ብትኖርም አብራኝ ስትቀልድና ስትስቅ ብቻ ቆይታ የምትሄድ ትመስላለች:: እንደውም 'የሆነ ነገር አድርገዋል' ተብላ እንዳትጠረጥር ድምፅዋን ንቁ እንዳደረገችው ጠረጠርኩ:: እነዛ ጊዜዎች የት ጠፉ......አይኖቿን ጨፍና እላዬ ላይ የምትንበለበልበት?

[redacted] ሃላፊነት ተሰምቶኝና ትንሽ ደሞ 'አልተኮራረፍንም' ለማለት ስንታገል ካናቴራዬን የቀባችው ወጥ እንዳይታይ ጃኬቴን ደርቤ በችኮላ ከክፍሌ ወጥቼ ተከተልኳት:: ፀሐይ የግቢውን በር ስትዘጋ ደረስኩ::

«ምን ሆናለች?» አለችኝ

«ምን?» አልኩ በድንጋጤ

«ምን አልካት?»

«ምን አገባሽ አንቺ?»

«የት ልትሄድ ነው?»

«ቤቷ ላስገባት»

«እስከአሁን ገብታለች»

«በምኔው?»

«እየሮጠች ነው የሄደችው:: ምን አደረካት?»

«ምን አደረኳት?»

«ታውቅ ይሆናል»

«ምን ታውቃለች?»

«የምታውቀውን»

«ምን ታወሪያለሽ?»

«ምን ታደናቁራለህ?»

«አልገባኝም» አልኩ ብደነግጥም:: በሩን ከፍቼ ወጣሁ::

«መሽቷል የት ልትሄድ ነው?»

«ነፋስ ለመቀበል»

«እዚህ ግቢ ውስጥ ነፋስ የለም አሉ እንዴ?»

«የለም»

«መጥፎ ጊዜ ነው፣ ብትታሰርስ? እውጭ የምትላከው እኮ እዚህ እንድትታሰር አይደለም:: እንዴት አይገባህም»

«እንዴ ሰፈሬን ልየው ከመሄዴ በፊት»

«እሩብ ሰአት ሰጥቼሃለሁ:: ካልመጣህ በሩብ ሰአት ለዕጌ እነግራታለሁ፣ ወይ እጮሃለሁ:: ምረጥ»

«ትቀልጃለሽ»

«አዎ የማላደርግ መሰለህ? ሂድ ለአስራ አምስት ደቂቃ» አገጬን ይዛ አፌ ላይ እንደ ፍቅረኛ ሳመችኝ:: በልጅነቴ እንደዚህ ነበር የምትስመኝ:: አገጬን ትይዝና በቀስታ ቀና አድርጋ የታችኛው ከንፈሬን ከአገጬ ጋር:: ሌላ ጊዜ እንዳታደርግ ባባርራትም ከዚህ አገር ለመሄድ ጥቂት ሰአቶች ስለቀሩኝ ግድ አልሰጠኝም::

«እፍህ ሴት ሴት ይላል ተሳስማችሁዋል ሂሂ»

«ምናባቷን» አልኩና ከግቢ ወጣሁ::

ሰፈሩ ፀጥታ ነው:: ፀጥታው የማይቆም እንደሆነ ገብቶኛል:: ከታች ከአለምነህ ሱቅ ውሻ መንገድ ያቋርጣል:: አንድ ጋቢ የለበሰ ሰው ወደ እኔ አቅጣጫ ይመጣል:: የክሊኒኩ ሁለት የበረንዳ መብራቶች የወላቃ ሳቅ ይመስላሉ:: እዛ ጋ በድቅድቅ ጨለማ ቀሌታም አህያ አህያ ይወጣል፡ የንፊያ ማሚቶ እየተጋጨ በየስርቻው ይወድቃል:: የእንጦጦን ገደል እየቧጠጥኩ ወጥቼ ሰፈሬን ወደ ታች ማየት ፈለኩ:: እዚያ ድንጋይ ላይ ተባረኪ ተጋድማ ተስማለች:: እዚህ ድንጋይ ላይ ጢንዚዛ አስረን እኛ እንደ አብርሃም ሆነን እሱን እንደ ይሥሐቅ ሰውተናል:: ከዛ ላይ ድንጋይ ወረውረን ወራጅ መንገደኛ ረብሸናል:: አስፋልት ዳር በቁም እየቃዠሁ:: ሁለት የደመና ንጣፎች ላይ ከታች ይተላለፋሉ:: ምን እቻኮላቸው? ያልተናገርነው ቁል ነገር ነበር? ርጥብ አረንጉዋዴ ጠረን:: ነፋስ የላይተሬን እሳት ሰስቴ ገደለ:: ሲጋራው እንኳን እንደ ቁምነገር ይከዳል:: እዛ እዛ እዛ ያልረገጥኩት ቦታ ነበረ? መፍዘዜን አቁሜ ቶሎ ቶሎ እየተራመድኩ ወደ ግራ ወደ አልማዝ ቤት ታጠፍኩ:: ከአልማዝ ጋር ያያዘኝ የየዋህነቴ ቃል ኪዳን ብቻ አይመስለኝም:: በሚያምር መልክ፣ የትኛውንም አይነት ሙዚቃ መርታት የሚችል ከሰው ላንቃ ሊወጣ ባልመሰለ ሁሌ የምታሰማኝ በ ስ መ አ ብ ነው:: ይሄን ዘፈንዋን በኋላ አልፎ አልፎ ብሰማውም እንደ መጀመሪያው የረቀቀ አልነበረም:: ወደ አልማዝ

የሚወስደኝን የ[redacted]ቆት ኅዳና ያበረታሁት እኳን በማፍቅሬ ወይም የገባሁት ቃል ኪዳን አስሮኝ ሳይሆን ያን ቃል ደግሜ ስታዜመው ለመስማት ይመስለኛል::

የጉርጉስም ሆቴል መብራት መንገድ ድረስ ወጥቶ ተኝቷል:: እሱን መቀስቀስ የፈራሁ አይነት (ግን እንዳልታይ ነው) በጎኑ አለፍኩ:: [redacted] ሄጄ ስደርስ በውስጡና በአካባቢው የሚለቀቀው የተለመደ ሙዚቃ እንኩዋን በደንብ አይሰማም:: ጭር ያለ ነው:: በጓሮ በኩል ገባሁና መኪና ማቆሚያው ሆኜ የት እንደምፈልጋት ሳወጣ ሳወርድ በስተቀኜ አንድ የተዘጋ ክፍል ተከፈተ:: 'ረድኤት' የተባለች ለብዙ ጊዜ ከአልማዝ ጋር የሰራች ቀይ ሴት ከዛ ወጥታ ግራና ቀኝ እና እኔን አየችና ፈገግ አለች:: ከነበረችበት ክፍል 'ወንድ ወሰን' የተባለው የክሊኒኩ ዘበኛ ካኪ ኮቱን እየቆለፈ ወጣ:: ወገቡ ላይ ትጥቅ ያየሁ መሰለኝ:: ሰውዬው በዝምታ ወደ መውጫው ሲሄድ:

«ታዲያስ! አልማዝን ነው?» አለችኝ ረድኤት

ትኩረቴን ሰብስቤ:

«አዎ:: የት ናት?»

«አልገባችም»

«ለዚህ ነው ጭር ያለው?»

«እም......ልትሄድ [redacted]ሆነ ሰማሁ»

«ይታይሽ እናንተን ትቼ ስሄድ»

«ሰላም ሳትለን የምትሄድ መስሎኝ ሳዝን ነበር» አለች

«ሰላም ልል ነው የመጣሁት»

«መቼ ልትሄድ ነው?»

«ነገ በጠዋት»

«ቀደም ብለህ ብቅ አትልም ነበር?»

«ሳስብ ነበር:: አልተመቸኝም»

«ካልጠፋ ቡታ ሕዛ አገር ትሄዳለህ?» አለች ሳቅ ብላ፣ ትችት እንዳይመስልባት መሰለኝ የሳቀችው

«ታዲያ እንደ እኛ እርስ በርሱ የሚባላ ሕዝብ ካሌለባት አገር አይባልም?»

እየተቁለጨለጨች አየችኝ::

«እዛ ደርሰህ ደህና አገር አስበህ ሂድ:: እግርህ ከወጣ በሁዋላ ማለቴ ነው»

«ከእንግዳ ጋር ነሽ መሰለኝ» አልኩዋት

«ከአንድ ሰአት በሁዋላ ና» አለች ሳቅ ብላ።

በጨለማ ውስጥ አይኗን እንኳን ሳላይ ስለ እኔና ስለ አልማዝ የግንኙነት ታሪክ ወይም ተረት እንደምታውቅ ገባኝ።

«ልተኛ እባክሽ ሄጄ፣ ደህና ሁኚ በይልኝ»

«እልልሃለሁ»

ከሆቴሉ ስወጣ የግቢው በር ላይ ወንድወሰን እምቢ ያለውን ቀበቶውን ወይ ያልበረደለት ሰለሞኑን እያፅናና ይሁን እንጃ እቆመበት ሲቁነጠነጥ አገኘሁት፡

«አንተ ጎረምሳ መጥፎ ጊዜ ነው ቶሎ ቶሎ ሂድ። እንዳለፈው ጊዜ እንዳትሆን» አለ ትንሽ ተራምጄ ዞር ብዬ አየሁ። *ምን አገባው?* የረድኤት ጥርሶች በጨለማ ውስጥ ረጋ እንደተሰራለት ባትሪ ያበራሉ። ወደ ቀኝ ታጥፌ ወደ ታች ስወርድ አልማዝ ትዝ አለችኝ። *እንጀራ ስትገልጥ የተናገረችላት አፍቃሪ እሷ ራሷ ትሆን?* አልኩ። ይሄ ሃሳብ አስደነገጠኝ። ወደ ሁዋላ ዞር ብዬ አየሁ። የተዘባረቀ ስሜት እየወጣና እየወረደብኝ የቤቴን አጥር በር ስገፋ ፀሐይን በረንዳ ላይ ቆማ አየሁዋት።

«ምናባትክን አየሁህ የት እንደሄድክ»

«የት ሄድኩ?»

«ጉርጉሱም»

«እና? ምን ይጠበስ?»

«ከአልማዝ ቤት ነገር አለህ፣ ሰምቼአለሁ»

«እናስ?»

«ተባረኪ ሰምታ ይሆናል»

ግድ አልነበረኝም። ግድ ቢኖረኝስ? የመጨረሻ መሰናበቻ ቃሌ ከልቤ ወጥቶ ምላሴ ላይ እንደ ሎቲ ከተንጠለጠለ ቆየ። ከአፌ በሰልፍ ከወጡት መሰናበቻ ቃሎች ብዙዎቹን ከሽሮሜዳ ፒያሳ ከፍተኛ ትምህርት ኮሚሽን ስመላለስ ታክሲ ውስጥ፣ እፍንጮ በር ጋ፣ አራዳው ጊዮርጊስ አካባቢ፣ አቡነ ጴጥሮስ ሐውልት ስር፣ ገዳም ሰፈር ጂን ቶኒክ ቤት፣ ክሪያዚስ፣ ቼንትሮ፣ ቸርችል ጎዳና ላይ (ቸርችል ላይ የምጥላቸው ጥቂቶቹ እየተንከባለሉ ባቡር ጣቢያ ይገባሉ፡ *ቻው ቢፌ ደ ላጋር!*) እንጠባጥቤ ጨርሼአቸዋለሁ። የቀረው ያልወጣኝ ቃል ምን ይሆን?

# አዲዮስ ሽሮሜዳ

ጠዋት 12 ሰአት ላይ ካፊያ እየረገፈ ወደ ቦሌ አይሮፕላን ማረፊያ መንገድ ጀመርን:: ሆዴ መሃል በትክክል እምብርቴና ዙሪያዋን ሊሟሟ ያልፈለገ ቅሬታ አለ:: ለአስራ ስድስት አመታት በአንጀቴ የገባው ደስታ አንድ አመት በማይሞላ ወጣ ገባ ጎርፍ ታጥቦ ወጥቷል:: በአፌ ብቻ ሳይሆን በነፍሴ ፀጥታ ገብታለች:: ከግቢ እንደወጣን የተባረኪን ቤት አየሁ:: እማና ፀሐይ ዞር ብለው እኔንና የተባረኪን ቤት አፈራርቀው አዩ:: ብንግባባም ያልተግባባን ለመምሰል ሞከርን:: መናገር የሚገባን ቢሆንም አለመናገርን መረጥን:: እኔም በከፊል አፍረት አንገቴን ቀሎ ሰበርኩ:: አባቴ በዝምታ ይነዳል:: እማማ በነጠላዋ ዕንባ የሚያመነጩ አይኖቿን ትጠርጋለች:: ፀሐይ ቀኝ እጄን ይዛ ትከሻዬን ተደግፋለች:: በዛ ጭር ያለ ጠዋት ግራ በገባው ብቻ ሳይሆን፣ በረቀቀ የብቸኝነት ስሜት ፀሐይን አቀፍኳት:: አጥብቄ ስለያዝኳት ባብታ ወደ ብብቴ ጎስጉሳ ገብታ ድምፅ አውጥታ ማልቀስ ጀመረች:: አባቴ ይሳደባል::

«ምን ቢያደርጓት ይሻላል»

«ዝም በል» አለች እየተናፈጠች

እማዬ ስለማትመልስለት፣ ትላት ነበር: 'ልኩን ንገሪልኝ'

ዛሬ አልወጣትም:: ምናልባት ለመናገር አቅሙ አልነበራትም:: እነዚህን ሁለት ቃላት መደጋገም ሰልችቷት ይሆናል:: የፀሐይን [redacted] ጭንቅላት በእቅፌ ይዤ ሳምኩት:: ፀጉሯ [redacted] ወተት ይሸታል:: ሁልጊዜ የሆነ አይነት ምግብ ነው የምትሸተው:: በመኪናው ውስጥ ያለው ድምፅ የሞተር፣ የነፋሰና የመናፈጥ ብቻ ነበር:: ቀኝ ጎኔ ፀሐይ ስለተጋደመችበት ሞቆኛል:: ባትነሳ እወዳለሁ:: እየሰነጠቅን በምንሄድበት የቦሌ መንገድ ያለው ፀጥታ ጥልቀቱ በአገሪቷ የፖለቲካ ረብሻ አለ ብሎ ለመጠርጠር አያመችም:: ይህቺ የተደበቀች ሁለተኛ አዲስአባ ናት:: እኔ የምኖረው ሶስተኛው ውስጤ አለ:: አዲስአባ እንደ አምላክ ሶስት ባሕርይ አላት:: ድሮ የማውቃቸውን ቦታዎች እየገላመጥኩ አለፍኩ:: የፍላሚንጎ ነጭ የቆሸሸ እንሰሳ ይመስላል:: ፒኮክ በሆዱ የተኛ እንቅልፋም ውሻ ነው:: እንቅልፋም ነበር? እዚህ ከመጣሁ ብዙ ጊዜ እንደሆነኝ ታወቀኝ:: ከማሽ

ሰአት በሁዋላ ቦሌ ደረስን። እንዴት ያን ሁሉ መንገድ ልብ ሳልል እንደመጣሁ ገረመኝ። እንደገረመኝም አልተናገርኩም።

አይሮፕላን ማረፊያው ተጓዥ መሸኛ ውስጥ ወደ ተለያዩ የሰሜሊስት አገሮች የሚሄዱ ተማሪዎችና የመንግስት ሰዎች ነበሩ። ሁሉም በጋቢውና በጃኬቱ ተጠቅለሎ እንዳይታይ የተደበቀ ይመስላል። ከቤተሰቦቼ ጋ መቆም አልፈለኩም። የሁላችንም ዝምታ፣ የአባቴ የፉገራ ሳቅ፣ የፀሐይ ለቅሶ በእኔ መሳም ደጋግሞ መሳምና መታቀፍ ስላልተመቸኝ፣ ግን ለምን እንዳልተመቸኝ ሳልነግራቸው ተሰናብቼአቸው ሄድኩ። ወደ አይሮፕላኑ ለመግባት አስፋልቱን ስሻገር ለአፍታ ቆሜ መሸኛ ሰገነት ላይ ያሉትን ቤተሰቦቼን አየሁ። አባባ በዝምታ እጁን ያነሳል። እማማ አፏን ይዛ ቆማ ታያለች። ፀሐይ የለችም። ፀሐይን ተጣራሁ። እማና አባቴ ይሰሙኝ አይሰሙኝ አላውቅም። አባቴ 'ዝም ብለህ ሂድ' አይነት እጁን እያራገበ ወደ አይሮፕላኑ እንድገባ ያባብለኛል። አንድ ተሳፋሪ ልጅ ከሁዋላዬ መጥቶ ገፋኝና አለፈኝ። ዞር ብሎ ይቅርታ ጠየቀኝ። አይሮፕላን ላይ መሳፈሬ ብርቅ አልሆነብኝም። በዛ ስመላለስ የኖርኩ ይመስለኛል። ወደ አይሮፕላኑ ውስጥ ስገባ ሆስተሷ ሰላምታ ስትለኝ አልሰማሁዋትም። ሰላምታ እንደምትሰጥ ያየሁት ተቀምጩ ወደ መግቢያው ሳይ ነው። የተመደበልኝ መቀመጫ ከሰገነቱ ወዲያ ቢሆንም የፀሐይ ነገር አሳስቦኝ ተመለስኩ። አባቴ እማማና ፀሐይ ቆመው አየሁዋቸው። ባያዩኝም እጄን አወዛወዝኩ። አባቴ የኮቱን ኮሌታ አነሳና ወደ ሲቶቹ አየ። እዛ እንግዶች መቀበያ ላይ ተባረከ፣ የለችም። እንዲህ ሆኜ ስሄድ ለእኔ ብቻ ነው ያሌለችው ወይስ ለሌላም?

እንዲት ሆስተስ ወደ መቀመጫችን ተመልሰን የወንበር ቀበቶአችንን እንድንታጠቅ ትእዛዝ አስተላለፈች። እኔን እያየች ነበር። አይሮፕላን ውስጥ ሳይሆን ትልቅ መኪና የተሳፈርኩ እንደመሰለኝ ነው። ወደ ወንበሬ ተመለስኩ። እውጭ ገፍቶኝ ያለፈው ልጅ ከእኔ በስተቀኝ ተቀምጦ በፈገግታ አየኝ። ራሴን ለሰላምታ ዝቅ አድርጌ አለፍኩት። አይሮፕላኑ ብዙ ሳይቆይ ተንቀሳቀሰ። እጄን ማውለብለብ ጀመርኩ። አውሮፕላኑ እየተንሸራተተ ሲሄድ ሰገነት ላይ አባቴ፣ እማማንና ፀሐይን ግራና ቀኝ ይዞ ወደ ሁዋላ ሲዞር አየሁት። ማውለብለቤን ትቼ ከፊት ለፊቴ ያለውን ወንበር እያየሁ ተከዝኩ። ከመሃል:

«ይቅርታ ቅድም ገፍቼህ አለፍኩ፣ አላየሁህም» አለኝ እውጭ ገፍቶኝ የሄደው ልጅ። ከእኔ አንድ ረድፍ ወደፊት ራቅ ብሎ ተቀምጧል።

አልመለስኩለትም። ፊቱን እንደማላውቀው ባውቅም የማውቀው መሰለኝ። ወደ ውጭ አየሁ። ማማው ተሰውሯል። ቤተሰቦቼን ለመጨረሻ ሰላም አለማለቴ ቅር አለኝ። ፊጁ አበሳጨኝ። ዞር ብዬ አየሁት። ይገለፍጣል።

«ይበርዳል አይደለ?» አለ:: ምንም አልመለስኩም:: ልጁ ወደ ሆነ የመጨፈር ተስፋ ወደአለበት ፓርቲ የሚሄድ ይመስላል::

«ሰማኸኝ?» እንደ ባነንኩ ሁሉ አየሁትና ትከሻዬን ምን ችገረኝ አይነት ነቀነቅሁ:: አውሮፕላኑ ተነስቶ ሰማይ ላይ እየተንቀጠቀጠ ሲበር ለመጨረሻ ወደ ታች አየሁ:: ዳገት የሚወጣ ሰው አየሁ......ቦሌ ሜዳ ላይ ላሞችና እርኛ አየሁ......እዛና እዛ የተኙ ጭብጥ የሚሞሉ አይነት ጉች ጉች ያሉ የጉም ደሴቶች አየሁ......በጠዋት እንጠጠ ተራራ ወርቅማ አረንጓዴ ሜዳ ትመስላለች......ሰፈሬ የአዲስአባ ትዕይንት ውስጥ ኢምንት ሆና ጠፍታለች......እያሉ ግን እንዳሌሉ መሰወር የሚያሳዝን ነገር አለው:: በህይነ ህሊናዬ የማውቃቸው እንዲሁም የማላውቃቸው ሰዎች በመንገዶች ላይ ሲሄዱ አያለሁ:: ዝምተኛ ጉዞአቸው ዳና የለውም:: ወንበሬ ጎን ሰው እንዳልተቀመጠ አየሁ:: ዙሪያ ገባዬን አየሁ:: ብዙ ሰው የለም:: ብዙ ተንገር የለም::

«ሰላም!» አለኝ ልጁ:: አለቀቀኝም::

«ምነው?» አልኩት በፊቴ ጥቅሻ

«ወደ የት ነህ?»

*«የት ነው የምሄደው?»* ራሴን እንደ ጅል ጠየቅሁ:: መመለስ አልፈለኩም:: ሁሉ ነገር ቀዝቃዛ ብቻ ሳይሆን ቀለም የለውም:: ሁሉ ነገር እንዲጠሉት የሚለፋ ይመስላል:: አየሩ ራሱ የሚተፋበት አይነት ደባሪ ነው:: አይኖቼ ላብ የመሰለ ዕንባ አቅርረዋል::

«ደብሮሃል?......እ አይዞህ» አለ ልጁ

ዞር ብዬ አየሁት:: ለአባባሉ ይቅርታ የሚጠይቀኝ ይመስላል::

«አልደበረኝም» አልኩት 'ምን ፈለክ?' አይነት ቅላፄ ጨምሬ

«እ ጥሩ:: የት ነህ? እኔ ሃንጋሪ ነው የምሄደው»

«ምስራቅ ጀርመን» አልኩት:: ብዙ ቃላት የሚወጣኝ መሰለኝ::

«የአዲስ አባ ልጅ ነህ?» ልጁ ሊለቀኝ ያቀደ አይመስልም:: ከሁኔታዬ ወሬ እንደማልፈልግ ቢገባውም ያልገባው ይመስላል:: ወይስ አልገባውም? እጄን ሰጠሁ::

«አዎ»

«ከደብረዘይት ነኝ፣ ስለ ናቪጌሽን ላጠና ነው የምሄደው......ስለ መርከብ ማለቴ ነው»

«ጥሩ»

«አንተስ?»

«ኬሚካል ኢንጂነሪንግ»

«ናይስ ነው። ቴክኒሺያን ነኝ። ከመስሪያቤት ነህ ወይስ……»

«ከትምህርት ቤት»

«ለስንት አመት ነው የምትሄደው?»

«አራት ወይም አምስት አመት»

«እኔ ለሁለት አመት ነው የምቆየው። ይታይህ በኢትዮጵያ አየር መንገድ መሄድ ኢት ኢዝ ዘ ቤስት ኢን ዘ ወርልድ[39]፡ ቀና ብሎ እዛ በሩ ጎን ወንበር ላይ ተቀምጣ እጅዋን የምታሻሽውን ቆቅ የመሰለች አስተናጋጅ እያየ። «አሁን ግን በደንብ የሚይዘው ጠፍቶ እየተበላሸ ነው»

ለልጅቷ ቀና ብሎ ፈገግ አለ። ፊቷን አዞረች።

«በነገራችን ላይ ከአሁኑ ዘመዶቼ ናፍቀውኛል»

እንዳስገደድኩትና ትቼው ለመሄድ እንደዛትኩበት ሁሉ በችኮላ ያወራል።

«ትንሽ መደበሩ ሲሻልህ እናወራለን። መለያየት ይደብራል አይደለ?»

ያለንን የበረራ ሰአት ደመርኩና ቀነስኩ። ለራሴ ፈገግ አልኩ።

«በነገራችን ላይ……» ይተወኛል መስሎኝ ነበር

ዞር አልኩ

«ስሜ 'በረከት ነጋሽ' ይባላል። አንተስ?»

«ዓላዛር»

«ናይስ ስም ነው»

«መተኛት ፈለክ? ረበሽኩህ? እኔም ማታ የወጪ ስጠማ ነበር»

«መተኛት ከቻልኩ» *ስክሬአለሁ አልኩት?*

«ለመተኛት ሞክር በሁዋላ እናወራለን»

ያ 'በሁዋላ' ከ20 ቀኖች ወይም ከ20 አመታት በሁዋላ ቢሆን ደስ ይለኛል። ማምረሬን እንዳያይ ፊቴን ከእሱ ዞር አደረኩና አይኖቼን ጨፈንኩ። ማስመሰሌ ሰውን ሆኖ……ስባንን ከአንድ ሰአት በላይ አልፏል።

በረከት ቦታ ለውጦ ከፊቱ ለፊቱ አለው ወንበር ላይ ከተቀመጠች አንዲት ወጣት ሴትዮ ጋ ተቀምጧል። እጅዋን እየነካካ አንገቱን ወደ

[39] (በአለም ድንቅ የሆነ ነው) (It is the best in the world)

እሷ ሰብሮ ያዋራታል:: በሳቅ ክትክትክት ትላለች:: እዚሁ አይሮፕላን ላይ ቢጋቡ ደስ ይለኛል:: *አምላክ ገላግለኝ*......

ሰዎች ቢፋቀሩም ባይፋቀሩም አጨራረሱ ያው መጣለዝ እንደሆነ የገባው ሳይሆን አይቀርም ጆኒ በረከት:: መተሳሰብ ዳብሮ ፍቅር ሳድርግህ ቢሉት ጊዜ መጨረስ ይሆን? አጉል መካተን? አጉል መራቀቅ? ምናልባት አለም በድርሳኗ 'ጨዋነት አለ' እያለች ታወራለች እንጂ አለም ራሷ ጠቅላላ ሹሼ ከሆነችስ? ሹሼነቱ ከሆነስ ጨዋነት የሚባለው? ብሳሳላትም፣ ባፈቅራትምና አስቤላት ባፈቅራትም የፈለገውን አይነት ብደበላልቅ ፈረንጆች ዋንስ '*ኤ ሆር ኢዝ ኦልዌይስ ኤ ሆር*' እንደሚሉት ከሆነችስ አለም ራሷ? ወድጄአታለሁ፣ አስቤላታለሁ፣ ሁለት ዙር አልቆየሁም፣ ተባረኪ ስትዘርረኝ ሪንጉ ውስጥ ሳይሆን በመውደቅ ላይ ያለሁት በአውሮፓ አቅጣጫ ወደ ጀርመን ነው::

# መዋዕለ ላይፕዚግ



*(ከፀሎት አይነቶች አንደኛው)*: ብችል ይህቺን አለምን ሶስቴ እገላታለሁ:: ጠዋት፣ ከሰአት ላይና ማታ:: በስመ አብ......ወወልድ...... ወመንፈስ ቅዱስ::

•

•

•

......የላይፕዚግ ከተማ በሳክሶኒ ክፍለ ሃገር፣ ከበርሊን በስተደቡብ ምዕራብ 150 ኪ.ሜ እርቃ ሶስት ወንዞች መገናኛ ላይ ያለች ከተማ ናት:: ለእኔ ያልተለመደ አይነት መልክአምድር ነው:: እንግዳ ለእንግዳ:: እንዲህ ፈዞ የቆመ ውሃ ያለበት ቦታ አልኖርኩም:: የአገሬ ውሃዎች ቀልቃሎች ናቸው፣ ለስደት ይፈጥናሉ:: አዲስአባና ይህቺ ከተማ የሚመሳሰሉት እኔ እዚህ ስላለሁ ብቻ ነው:: ከዚህም በላይ ሌሊቱ ሽሮሜዳ በጥቅምት የሚያጋጥመኝ፣ ግን ሙሉ ቀን ከቦኝ የሚውል ብርድ......

በከተማዋ በ1165 አካባቢ የተገነባው የቅዱስ ኒኮላይና የቅዱስ ቶማስ ቤተክርስቲያኖች፣ የፕሮቴሪዝም ዘመን ሕንፃዎች፣ የማርቲን ግረፒየስ ፈጠራ የሆነው የግዋንድ ሃውስ የሙዚቃ አዳራሽ፣ ባለ ስድስት ፎቁ የማዘጋጃ ቤቱ ሆህ ሃውስ አይነት ብዙ ባለታሪክ ሕንፃዎች ይገኛሉ::

በዚህ ዩንቨርሲቲ ጎይተ፣ ቫግነር፣ ኒቼና ታኮ ብሃ ተምረውበታል:: ሁሉንም ታላላቅ ሰዎች በመጽሐፍ ስለማውቃቸው እዛ መማሬ አልከፋኝም:: እ.አ.አ በ1953 አም 'ላይፕዚግ ዩንቨርሲቲ' የተባለው ስሙ ተለውጠ 'ካርል ማርክስ ዩንቨርሲቲ' ተባለ:: እንዲህ የተሰየመ ዩንቨርሲቲ ለመማር በመምጣቴ በማልወደው የዕውቀት መስመር የምሰለጥን ካድሬ የሆንኩ መሰለኝ:: በቤቶቨን ጎዳና ላይ የሚገኘው የዩንቨርሲቲው ላይብረሪ በአውሮፓ ካሉት ብዙዎቹ ረዥም እድሜ ያለው ነው::

አዲስአባንና የተባረኪን ትዝታ ይህቺ ላይፕዚግ አታውቅም:: ላይፕዚግ ከእኔ የምታገኘው ጥቅም የለም:: ምናልባት አእምሮዬን ወይም ልቤን ሶሻሊስት አድርጌላት ወደ አገሬ መመለሴን ነው (በዚህም ግድ ያላት አይመስለኝም):: ውስጤ የያዝኩትን ከላሽ ትዝታ በሰማያዊ አይኖቿ ማንበብ አትችልም:: ብትችልም ባትችልም፣ ግድ [redacted]ማይሰጠኝም

አታውቅም:: ጥበብ መቀበል የለመደው ሰፍነግ አንጎሌ ዛሬ ዕብነበረድ ሆኗል:: ላይፕዚግ ይሄንን አታውቅም:: ላይፕዚግ ብዙ አታውቅም:: 'ከአፍሪካ የመጣ' በሚል ጅምላ ምደባ ሙቀት እንደሚያግልለኝ ትገምታለች:: የእንጦጦ ብርድ እየከነተኝ እንዳደግሁ አታውቅም:: ላይፕዚግ ስለ እኔ መሀይም ናት፣ በምን ሂሳብ ይሆን እኔም ይሁን እሷ ስለአለም አቀፍ ወዝ አደሮች ማሰብ የምንችለው? ላይፕዚግ አነጣጣሪ ቅልጥም ሰባሪ አይደለችም::

•

•

•

*(ሀሁሁሀሀሸሸሸሹሺ)*: ከተኛሁበት ተነስቼ አልጋ ዳር ተቀምጬ ቀና ስል፣ እንደ ጥጥ የሚሰራቸው አመልማሎ በረዶዎች ከሰማይ ሲወርዱ አየሁ:: አይኖቼና ልቦናዬ በትዕንግርት ተገሰሱ:: በረዶዎቹን ቆሜ ሳይ፣ የምሰምጥም የምንሳፈፍም ይመስለኛል:: ሰማይ የለመድኩት አይነት ነጭ ነው:: ታች በረዶው አስፋልትና ድንጋዮች ላይ እያረፈ ይሰወራል:: የከተማው መልክአምድር በሰሱ የቆሸሸ ወረቀት ይመስላል:: ስለበረዶኝ አልጋዬ ውስጥ ተመልሼ ገባሁ:: አናቴን ትራስ ላይ አስደግፌ ቀና ብዬ በትኩረት እየቦነኑ የሚወርዱትን በረዶዎች እያየሁ እንቅልፍ ወሰደኝ:: በሕልሜ በለስላሳ ረግረግማ መስክ ላይ እሮጣለሁ:: እዛ መስክ ላይ ከእኔ ሌላ ፍጡር የለም:: የምሰማው የትንፋሼን ሀሀሁሁሀ እና በባዶ እግሮቼ የምረግጣቸውን የአከርማ ሳሮች ሸሸሸሹሺሸሸሸ ነው:: እንደዚህ አልም ነበር ልጅ እያለሁ:: አውሮፓ ላይፕዚግ ተኝቼ ይሄን ህልም ማለሜ ለምንድነው?

•

•

•

*ሆደ ሰፊ ነኝ*: አንዳንዴ ሆዴን እንደ ኮት ስከፍተው ከውስጤ አንድ ጋሻ መሬት፣ ሁለት ቸርቸብታዎች፣ አንድ ጅረት፣ ስድስት ሚዳቆአዎች፣ አራት ኤሊዎች፣ መዓት ንቦች፣ ሰላሳ ላሞች፣ አንድ የበግ ወጥ፣ አንድ ካፌ ላቴ እና መዓት ኩበት ተዘርግፎ ይወጣል:: ለምጠላው ትዝታ አለኝ::

•

•

•

**ሚሉስ ዘባራቂ፡** ትናንት ማታ የደረሰኝን ደብዳቤ እያዘንኩ አገላብጣለሁ:: ተባረክ 'ታስራ ነበር' ሲሉኝ ተከዝኩ:: ምንም እንዲደርስባት አልፈልግም:: እዛ አጠገቧ ብኖር ምን አደርግ ነበር ግን?

አብሮኝ የሚኖረው ሚሉስ ደብተሩን አስቀምጦ ሊወጣ ሲል አየኝና:

«ምን ሆንክ?» አለ

የሆነ ነገር ሲያጋጥመኝ ሳልነግረው ያውቃል:: ደብዳቤዬ በሴኩሪቲ እየተነበበ የሚደርሰኝ እስከሚመስለኝ::

«የተደበርኩ እመስላለሁ?»

«አዎ አይኖችህ ሰንባ አቅርረዋል» ይሄን ልብ አላልኩም

የተሻፈልኝን ነገርኩት:: ከጀርባ የነበረውንም ታሪክ፣ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ::

'እዛ አይነት ድርጅት ውስጥ ገብተው የሚሳተፉ ግለሰቦች ከራሳቸው ልምድ የወጣ ሃሳብና እምነት የላቸውም:: አንተንም እሷንም የሚያሸፍታችሁ ምክንያት የለም:: ሰበቡ ቅዱስ እንዲመስል 'ለተጨቆኑት ነው የቆምነው' ይሉሃል:: ያን የሌሎችን የመጨቆን ታሪክ የሚያውቁበት የሕይወት ልምድ የላቸውም:: እንደነገርከኝ ጓደኛህ ገና ልጅ አልነበረችም? አስራ አምስት ወይ አስራ ስድስት አመቷ አልነበረም? ብቻ የሆነ ጊዜ የየትም አገር ወጣቶች መንግስት ላይ መሸፈትን ፋሽንና ግዴታ ያደርጉታል:: ዋናው ሰበብ በቤተሰብ አለመደሰት ሊሆን ይችላል፣ ወይም መሰረታዊ የልጅነት ፍቅር ማጣት ሊሆን ይችላል፣ ይሄ አይነት የግል ስነልቦናዊ ችግር በምሬት ትርጉም በኩል አልፎ በአተረጓጎም ይዛነትና መንግስት የመቀናቀን ፖለቲካ ይሆናል:: የተፋቀራችሁት ወይም ያፈቀረችህ የመሰላት ምናልባት መልከመልካም ከሆንክ ሌሎች ስለሚወዱህ ልትሻማህ ሊሆን ይችላል:: አንተን ሳይሆን በሌሎች መወደድህን ይሆናል የወደደችው:: እሷም እርግጠኛ አይደለችም:: አንድ የማታመልጠው ጉዳይ ግን ከሰር መንጋ መሆኗ ነው:: አንተስ ራስህ የራስህን ሃሳብ ነው የኖርከው? ላይሆንም ይችላል:: አሁን ያለን ሃሳብ የእኛ ነው? ወይስ ሳናውቅ የተበደርነውና የተማርነው ነው? ብዙ አናውቅም:: ልዩነቱ እሷ ከማታያቸውና ከማታውቃቸው ሰዎች ነው ሃሳብ የወሰደችው:: አብዮት ወጣቶችን አትጠላለዙ ይላል? ከሆነ አብዮት አይደለም:: ከአንተ ጋር የምታጠፋውን ጊዜና ስሜት እነሱ ሊጠቀሙበት ስለፈለጉ ነው:: ከአፈቀሩት ተኝተው የተረጋጉ ወጣቶች በድርጅት አይደረስባቸውም:: ወሲብ ትልቅ ጉልበት ነው:: የወሲቡን ስልጣን ወጣቶቹ ልብ ውስጥ እንዳይወጣ አድርገህ አምቀህ ለሚጫታ ትጠቀምበታለህ:: በየአቅጣጫው ታፍነውና አንድ የፖለቲካ መውጫ ብቻ ቀዳዳ ካበጀህለት ባሪያ አገኘህ ማለት ነው:: አታስባት:: መስለህ እንጂ

የአንተ አልነበረችም፡፡ ምናልባት እድሜዋ ገፋ ቢል፣ ወይም በራሷ ስታስብ ይገባታል'

«ይሄን ሁሉ አባትህ ነገረህ?»

«በሃያ ስድስት አመቱ ፕሮፌሰር ነበር፡፡ የታሪክ ፕሮፌሰር፣ እኔ አይደለሁም እንጂ አባቴ ጂነስ ነው»

«እ»

«እንደ ዕብድ ታስባለህ ተብሎ በሙያው የሚተዳደርበት ስራ እንኳን አያገኝም፡፡ መስኮት ሲጠርግ ይውላል፡፡ ከአገር እንዳይወጣ ተከልክሏል፡፡ መስኮት የመጥረግ ስራ ከፈለክ አገናኝሃለሁ»

«ታዲያ ባለስልጣኖች ከእኔ ጋር መገናኘትህን ሲያዩ......»

«እዚህ ከመግባትህ በፊት ማን እንደሆንክ ያውቃሉ፡፡ ከዛ በሩቁ ሳይጠጉ ያዩሃል፡፡ ዲሞክራሲ ያለ ይመስልሃል? ዲሞክራሲ ጨረቃ ላይ ያለች አመድ ላይ እየተንከባለለች ሊፒስቲክ የምትቀባ የዞረባት ቺክ[40] ናት»

•

•

•

የክፍል ጓደኞቼ ባልታዛርና ሚሎስ ጥሩ ጠጪ በመሆኔ ሸርክ አድርገውኛል፡፡ በያዝኳት ዶላር ተሻርኬአቸው አብሮ አደግ መሰልን፡፡ ከትምህርት በሁዋላ ስራዬ መጠጣት ነው፡፡ አንድ ከተቋቋመ መቶ አመት የሚያልፈው ቡና ቤት ተቀምጠናል፡፡ ቤቱ ትንባሆና ቢራ ይሸታል፡፡ ልዩ ማንነት አለው፡፡ ጠረኑ ደስ ይለኛል፡፡ ይሄ ቡና ቤት ኢትዮጵያ ውስጥ ቢሆን ነፃ አውጪ ድርጅት ይቋቋምለት ነበር፡፡

«የእውነት ለምን ትደበራለህ?» አለኝ ባልታዛር

«ፍቅር፡፡ ነገርኩህ፡፡ ከወደድኩዋት ስለተለየሁ»

ልክ እዚህ በመምጣቴ ምክንያት የተለየሁዋት አይነት፡፡ ተለይቼአት እንዳልመጣሁ ጀርመን በፊት ጀርሙ እንዳልሰፈረብኝ አይነት፡፡

«ምንድን ነበር ውበቷ?» አለኝ

«ውበቷ የሚታየው ስታወልቅ ነው»

[40] ሴት

«ስትዋኝ ነው ያየሃት? ወይስ ተደብቀህ እንዳታይህ አድርገህ ገላዋን ስትታጠብ? ቮየር[41] ነህ እንዴ?»

«ሃሃሃሃ እኛ አንዋኝም:: አንድ ስዊሚንግ ፑል ነው ያለን በከተማው:: የተራራ ላይ ሰዎች ነን:: ውሃው ትቶን ይሄዳል እንጂ አይቆምም:: እግሯ ያምራል:: የሚያምር ጭን ነበራት.....ወደ ውስጥ እየቀላ ይሄዳል ካፌ ላቴ ነገር.....ልዩ ተስፋ ይሰጣል:: ልክ ነበርኩ:: ውበቷ ያለው ስታወልቅ ነው፣ ላንስማማ እንችላለን»

«ሃሃሃ ዮቶፕያ/ተምኔት አስበህ ነበር:: ተምኔትህ ሆነልህ:: ሌኒን እንኳዋን አልቀናውም:: ግን በማርክስ ስም እምላለሁ፣ ውበት አላፊ ነው፣ ገላ ያልቃል:: እንደ ደመና፣ ስጋ በጊዜ ነፋስ ይወሰዳል» አለና ሳቀ

«ፋክ ኒቼ» አልኩት

«ጀርመንኛህ ደስ ይለኛል፣ አለ አይደለ......»

እንኳን አነጋገሬ አሽናኔ ሁሉ ጀርመናዊና ሶሻሊስት እንዲመስል ይፈልጋሉ:: ሂትለርን ልሸና? ላይብኒስን ላንፎልፉል? ወይስ ታኮን ላዛጋ?

•

•

•

ተባረኪን መዓት ጊዜ ከግርማቸው ጋር እጅ ለእጅ ተያይዛ አስባታለሁ:: እያወሩ ወደ ሁዋላ እያዩ የእኔን መምጣት ሲጠብቁ......በግራው እሷን፣ በቀኙ ሴት ጉዋደኛውን ማሜን እንዳቀፈ......ፊታቸውን ወደ እኔ ሲያዞሩ (የማታ ፀሐይ ቀይ ዳማው መልከመልካሙ ግርማቸው ላይ፣ የደስ ደስ ያላት ተባረኪ ደረት ላይ፣ ዞማዋ ማሜ ገፅ ላይ)፣ ጀርባቸውን ወደ እኔ ሲመልሱ (በኮቱ ኮሌታ ወደ ላይ የተገፋና የሚያምረው ግን ክቡ የተበላሸ አፍሮው፣ አስደናቂ ቅርፅ ያላቸው የተባረኪ ባቶችና የማሜ ቂጥዋ የሚደርስ ፀጉር)......ተባረኪን እንዳአስለመዳት እሱንም እንደ አስለመደችው ተረብ ተርቦአት ከእጁ ተላቃ ትከሻው ላይ በውሸት ጥፊ ስትመታው:: እና ዞር ብላ፡ 'ይሄ ስድ የሚለውን ትሰማለህ?' ስትለኝ:: ያን ጊዜ ሳልቀና የእነሱ ጓደኝነት ጉዋደኞች እንዳሉኝ ውስጤ ይኮራ እንደ ነበር መች ነገርኳቸው?

•

•

•

[41] በማየት ብቻ የሚደሰት ወይም የምትደሰት

***ርዕዮተ አለም ኑፋቄ ነው:*** ርዕዮተ አለም ስስ ነው:: ርዕዮተ አለም ክሲታ ነው:: ስራው የተወሰኑ ዕውነት አላቸው ብሎ የሰየማቸውን ነገሮች መርጦ ስርአት መገንባት ነው:: ርዕዮተ አለም ተስፋ እንደቆረጡ አሮጊት 'ያልኩት ካልሆነ ከልኩ አያልፍም' ነገር አለው:: ወይም አከታትሎ ሶስት ሚስቶቹን እንደፈታ ምሬት ፈጥኖ እንዲደምደም ያስተማረው አቶ:: ብዙ ጊዜ ስለ ርዕዮተአለም ትክክለኛነት የሚጮሁት ብሩህ የተባሉ ሴረኞች ናቸው:: የስሜት ብሩህነት የላቸውም:: ርዕዮተ አለም ስሜትን የተጠየቅ ባሪያ ያደርጋል:: ስሜትን የደካሞች ያደርጋል:: ከስሜቶች አንዱ በግለሰቦች መሃል ያለ ፍቅር ነው:: ሰዎች ያለ ፍቅር መኖር ስለሚሳናቸው፣ የፍቅርን ቦታ የሚሞላ አሰራር ይፈጠራል:: ይሄም የአላማና የድርጅት ፍቅር ነው:: ፍቅር ፍርጅ ይሆናል:: መጀመሪያ የሚያደርጉት 'ጎረቤትህን እንደራስህ አድርገህ ውደድ' የሚለውን በሰበብ ሰርዞ፣ በጓሮ በር ሰው ሳያይ መጣል ነው:: የድርጅትን ጠባብ መዋደድ ከበቀለና ከበቀለች በፍቅር መውደቅ ጋር ያምታቱታል::

•

•

•

***ወልዶ ቀሎ:*** ሐምሌ ሰባ አመተምሕረት ውስጥ ተባረኪ ልጅ እንደወለደችልኝ የሚያብራራ፣ እንደ አዲስአባ ዘመዶቼ አባባል 'የሚያበስር' ደብዳቤ ደረሰኝ:: በቀኛዝማችና በግራዝማች:: ሁለት ደብዳቤዎች:: በምክር እንደተበጁ ሁሉ ተከታትለው:: ከአንዱ ደብዳቤ ጋር የተባረኪና የልጅቷ ፎቶ አለ:: የሕፃንዋ ስም 'ምስክር' ይባላል::

***እስኪ እንቆጠር:*** ልጆች የሚመጡት ከሶስት ቦታ ነው:: አንድ ከማሕፀን፣ ሁለት ከልብ፣ ሶስት ከልብና ከማሕፀን ነው:: የመጨረሻው ቀን ተባረኪ በመለያየታችን አዝና አይኖቿ እንዲት ዘለላ ዕንባ እንኳን አላቀረሩም:: አውሮፕላን ማረፊያ መጥታ አልሸኘችኝም:: አቅፋኝ 'ያላንተ ምን እሆናለሁ' አላለችኝም (እንድትለኝ እፈልጋለሁ):: ምን አለበት ብትለኝ? እንዲህ ብታደርግ ፓርቲዋ ለደርግ ነግሮ ያስገጫታል? አገር በምለቅበት ዋዜማ ውስጤ በእርሷ ነገር ፈርሶ ሳልፈልግ በግድ ነበር የተኛሁዋት:: በዚህ አይነት ሩካቤ የተወለደ ልጅ በእርግጥ የእኔ ልጅ አይደለም:: እንደማንም ትዝ ትለኛለች:: አዎ የሚጣፍጡ ትዝታዎች አሉኝ አዎ፣ እወዳት ነበር አዎ፣ እወዳታለሁ አዎ:: ለማላገኛት ለማትፈልገኝ ከእርግዝናው ቀድሞ ለከሸፈ ፍቅሬ ባርያ ልሆን ግን አልፈልግም::

•

•

•

***ዮሴፍ ዶሮታ ዲክ*** ሚሎስ የኮሌጁ አትሌት ስለሆነ በጠዋት ለሩጫ ይወጣል:: እዛው እንደተጋደምኩ ሩጫውን ጨርሶ ይመጣል:: ገላውን ታጥቦ ወዲያ ወዲህ ይላል:: አይበርደውም:: ፀጉሩን እያበጠረ ዴስኬን አየ:: የአይቤክስ ስዕል ያለበት ቴምብር ቀኝ ጎኑ ከለጠፈ፣ ከወርዱ ከተቀደደና ከላይ ከተሸነተረ ኤንቬሎፕ የወጣ አንድ ፎቶ ፈቀቅ ብሎ ተቀምጧል:: ፎቶውን አንስቼ ለሁለት ቀደድኩና እዛው ጠረጴዛ ላይ መለስኩት:: እንደገና ከነበረበት አንስቼ ለአራት ቀደድኩና እነበረበት መለስኩት:: ሚሎስ አተኩሮ አየኝና::

«የልጅህ አይደለም እንዴ?» አለኝ

«ይላሉ»

«አንተ ነህ ያልከኝ»

«ያሉኝን አልኩህ:: እንጃ አይመስለኝም፣ የአንዱ ምናምን ትሆናለች:: ምናልባት 'ዮሴፍ' የሚባል ሰውዬ ወይም የሚሎስ ልጅም ልትሆን ትችላለች»

«ክሬዚ ነህ»

«ታድዬአለሁ»

«ይሄን 'ዶሮታ' ብቻ የምትደሰትበት መረጃ ነው»

«ምን አገባት ዶሮታ»

«ትወድሃለች»

«ዲክ የለኝም:: ዲክ ካሌለኝ እንዴት እወልዳለሁ? ስለዚህ ነው ፎቶውን የቀደድኩት»

«በሽተኛ ነህ»

•

•

•

***ያኮረኮሩ ጉብኣን ሩሕ:*** እኛ ያኮረኮሩ ጉብኣን በአራድነት ደንብ አምባሳደር ቲያትር በተለይ ቅዳሜ ከሰዓት ጦር ማስቲካችንን እያላመጥን፣ የበረዶ ኮካ ጠርሙስ በእጆቻችን አቅፈን......አፍረተቢስ ነኝና የቴቢ አስራ አምስት አመት ያልሞላት ግን ፈርጣማ ቂጥዋ ላይ እጄን አስቀምጬ ከአንጀቴ ስኮራባት፣ እናም በዚህች [redacted] ነገር ስደሰት(ግን እሷ 'እጅህን በእግዚአብሄር አንሳው ያሳፍረኛል' ስትለኝ)፣ በጨለመ የሲኒማ አዳራሽ ውስጥ ከሌሎች ተመልካቾች እርቀን በሚፈልቅ ሸራ ላይ ጆን ዌይን ሲታኮስ እኛ እንሳሳም ነበር (ከአፏ የሚወጣው የኮረዳ አየር

በተዝቃዛ ፋንታ ጣፍጦ):: ስሜቴ ገናናው ሲነዳኝ እሷ ነበረች እጄን ከጭንዋ ላይ አንስታ 'ወይኔ አሊክስ ሰው ቢያየንስ?' የምትለኝ:: ያ እኔን ላለማስከፋት፣ ሰው እንዳይሰማና እንዳያይ ለማድረግ ንግግሯን ያጀበችበት አፋርታም ድምፅዋና ትንፋሽዋ ሐጢያተኛ ሊፈውስ ከገነት እንደ መጣ መስከረም ነበር::

•

•

•

***ምዕራብ ብትል ምስራቅ ብትል:*** 'የምስራቅም የምዕራብም ፖለቲከኞች ማቴሪያሊስቶች ናቸው:: በአካሄድ ቴንጥ ነው የሚባሉት:: የሁሉም የመጨረሻ ግብ ገንዘብ ነው:: በመጀመሪያ ይሄን እወቅ:: ፍቅር በገንዘብና በገንዘብ አስረጫጨት እኩልነት ላይ የተመሠረተ ነው:: ፍቅር ከዛ ግኑኝነት ረግፎ የሚመጣ ተከታይ ጉዳይ ነው:: ሲያወሩለት ግን መዓት ይመስላል:: ሁሉ የፖለቲካ ርዕዮት ገንዘብ የማሳደድ አፋርታም ቲያትር ነው' ***ሚሎስ***

•

•

•

***ደብዳቤዎች እንደ ሐምሌ ዝናብ:*** ደብዳቤዎች ያለገደብ እየተንጋጉ ይመጣሉ:: በተለያየ መልክ ተገላልጠው ዙሪያዬን ከበውኛል:: ሻንጣዬ በኤሮግራም ባህር መስሏል:: ልብሶቼም እንደ ተስፋቢስ ጀልባ ይተራመሰ ሰብታል:: ሚሎስ 'ለምን መልስ አትፅፍም?' ይለኛል:: 'እንደሰማሁ ለመጠቆም ፃፍ እንጂ' ይለኛል:: ትደነቂያለሽ 'ባልወልድህም ልጄ ነህ' ብላ ፅፋለች:: ላይፕዚግ አደባባይ ቆሜ ወደ ታች ሳይ እንኳን ትደነቂያለሽ፣ እንኳን ሽሮሜዳ፣ እንኳን አዲስአባ፣ እንኳን ኢትዮጵያ፣ አፍሪካም አትታየኝም::

•

•

•

***እዛው በዛው ቻው:*** የቦዙ ዓይኖቻችን ወጨጫ ከናፈቃት ለመጥለቅ በረቂቁ ከምትሳብ የፀሐይ ጨረር ጋር እየታገሉ......በአንድ እጇ ቸርነትን ይዛ፣ ትከሻዬን ተደግፋ በቀልደኛ ስትስቅ ወይ በግርማ ቀልድ......'ሌላ እርጎ ግዙልኝ በእናታችሁ' ብላ ራስ መኮንን ባር ጫፉ ቀይ ቀለም በተነከረ ጣቷ (አይ ጣት) ወደ ብርጭቆ እያሳየች:: አራት ኪሎ ቱሪስት ሆቴል ፋንታ ይዛ 'እበጂ' ያላት ቀን ለፈተና 'ከእፊ ትጠጣለህ?'

ስትለኝ:: (ደቤ ግንቡ: 'አሌክስ ቦካሽ?' ብሎ በሳቅ ሲንፈራፈር) ወሬ አልቆብን ፀሐይ አደይ ያስመሰለችውን መንገድ እያየን ራስ ለራስ በዝምታ ተደጋግፈን እኔ እሷን፣ እሷ እኔን እያሰብን......እዛው በዛው...... (በእርግጥ እዛው ነበርን?)::

•

•

•

ዶሮታ አይኖቿ ቀይ ባህርን የሚመስሉ ድንቡሼ ናት:: ብሌኖቿን እያሰሩች እያጠበበች በርቀት ትጸራኛለች:: እሷ ያለችበት ከምሆን ሳይፕዚግ አትክልት ሙዚየም ሄጄ አበባ ባይ፣ ንብ ቢነድፈኝ ይሻለኛል:: ለሚሎስ ስነግረው 'ኮሚክ ነህና ቢራ ልጋብዝህ' አለኝ:: እሱ የማይወዳት በማርክዋ ሬከርድ ያላት ስለሆነ ነው::

•

•

•

***ዕውቀቱ ከሌለህ እረፍ:*** :'ራስህን ማወቅ አስፈላጊ ነው:: ግዴታ ነው:: እንደ አወራኸኝ ከሆነ አገራችሁ ደካማ የስነዕሁፍ ባህል ነው ያላት:: ድሮ ስለተፃፉ የሃይማኖት መፃህፍት አይደለም የማወራው:: ስለዛሬ ነው:: አገርህን በሚመለከት እዚህ ሳይብረረ ብፈልግ አንድ ነገር አላገኘሁም:: ያሉት ጥቂቶቹ መጽሐፍት ፖለቲካ ብቻ ናቸው:: ሲመስለኝ ፖለቲካ ብላችሁ የተባላችሁት በባዶ ሜዳ ነው:: ስነዕሁፍ ራስህን ለማወቅ ይረዳሃል:: እንዴት አንድ ሰው ሊለውጠው የሚፈልገውን ሳያውቅ ሊለውጠው ይፈልጋል? ካላወቀውስ እንዴት ይፈልገዋል? ምኞታችሁ ከዕውቀት ውጭ ነው:: ከዕውቀት ውጭ ውሳኔ የሚሰጠው ልጅ ነው:: ልጅ የተለኮሰውን ክብሪት ልብላ ይልሃል፣ አረቄው ውሃ ይመስላልና ልጠጣው ይልሃል ወዘተ:: ልጁ አረቄውን ቢጠጣው ደፋር ወይም ጎበዝ አይደለም:: ደንቆሮ ነው:: እንዲህ ያለ ነገር ሲያጋጥም የሚመጣልኝ ምክንያት አንድ ነው:: ቁሎችን ለመምሰል መፈለግ:: በሙሉ የአገራችሁ አብዮተኞች ኢሚቴተርስ[42] ናቸው:: ዕውቀቱ ከሌለህ ታዲያ ነገሮችን እንዴት ታነቃንቃለህ? እንደዚህ አይነት ሰዎች ዕውቀቱ ከሌላቸው ምኞቶቻቸውን በግድ ዕውን ማድረግ አለባቸውና እሱን በስራ ላይ ለማዋል የሚቀራቸው የመጨረሻ አማራጭ ሴራና ጉልበት ነው:: አይመስልህም? በዚህ አይነት ሁኔታ የተገነባ ርዕዮተ አለም ነጭናጫ የሆነች ደህና ማሕፀን የሌላት ቆንጆ ሴት ናት:: ሺህ ጊዜ ብተተኛት አንተም

[42] ቀጂ (Imitators)

አትጠግብም እኳም አትወልድም:: ማንም አልነካትም ግን ረግባለች:: ብትወልድም የምትወልድልህ ልጆች አይምቧቹ እግር የላቸው፣ አይጠቡ አፍ የላቸው:: ልጆች አይደሉም፣ ገና ስም የሚሰጣቸው ፍጡራን ናቸው:: ይሄን ስል 'አገራቸው ውስጥ ያሉት ቤተ መፃሕፍት በጠቅላላ ሶስት ናቸው እንዴ?' ብዬ ራሴን እጠይቃለሁ' ሚሉስ

•

•

•

***አረንጓዴው ጎርፍ:*** 1972 የላይፐዚግ በጋ:: የሞስኮ ኦሊምፒክስ:: ጁላይ 31 ሐሙስ የ5000 ሜትር እሩጫ ሚሉስ ከሶስት ቀን በፊት በ10000 ሜትር ትራክ ያሸነፈውን ምሩፅ ይፍጠርን በድጋሚ ሲያሸንፍ ሲያይ:

«ሰው አይደለም……ደማችሁ የጥንት ስለሆነ ይሆናል:: የበሰለ ደም:: በሶሻሊዝም ሞቅ ይለዋል ደሞ ሃሃሀ»

«ይለማመዳሉ በጣም:: በሰፈሬ ሌሊት ሌሊት ሲሮጡ አያለሁ»

«እውነት? አንተ እንዴት አትሮጥም? እኛ አገር ጎበዝ ዋናተኞች አሉን፣ ለምን መሰለህ? ብዙዎቻችን እንዋኛለን:: ስለዚህ አሪፍ ለመባል በጣም አሪፍ መሆን አለብህ:: እዚህ ካሉት ተማሪዎች አንድ ኢትዮጵያዊ ሲሮጥ አላይም»

«ህይወታችን በሩጫ የተሞላ ነው:: ብዙዎቻችን ስንሮጥ ነው የምናድገው:: ከትምህርት ቤት ወደ ቤት፣ ከገበያ ወደ ቤት፣ ከአባታችን ኩርኩም ወደ እናታችን ጥፊ፣ ከዝናብ ለማምለጥ ስንሮጥ:: እዚህ ላይፐዚግ የመጣሁት በአይሮፕላን እንዳይመስልህ እየሮጥኩ ነው:: ስንወለድ እንኳን በፍጥነት ነው፣ ተወርውረን ስንወጣ ሊቀልቡን አዋላጅ ሐኪሞች ፎጣ ይዘው ነው የሚጠብቁን ሃሃሃ:: አዋላጅ ሐኪሞቻችን ጎል ኪፐሮች ናቸው ሃሃሆሆ»

«ሃሃሃ:: በጣም ፋኒ ነህ»

•

•

•

***የታደለው ብርሃን መስቀል:*** የድሮ ወዳጆቼን ስም፣ ፊት፣ አነጋገር፣ አለባበስ፣ የመሳሰለ እያፈራረቅሁ አስባለሁ:: እማን ትዝ የሚለኝ ዞር ብሎ ቴቢን ከሁዋላዋ ሲያያት ነው:: እግሮቿን በአይኖቹ ሲሰርቅ:: እቋቋሟንና አካሂድዋን ፈዞ ሲያይ ያየሁት አይመስለውም:: ያን ፊቱን አልረሳም::

ምን ሆኖ ይሆን? የትኛው ውብ ነው ብሎ ጠይቋል? ሁሉንም እየበላ:: ፖለቲካውንም እሷንም:: የድርጅት አባል መሆን ከማፍቀር እንደሚበልጥ ያየሁበት ዘመን ነው:: አባቴ በዛ ጎዳና አልፏል? አባቴ ያለፈው በራሱ የስድነት ጎዳና ነው:: ቢበላሽበት ማሳበቢያ የለውም:: ሰበቡ ራሱ ነው:: ይሄ 'መታደል' ይባላል:: አባቴ የታደለ ነው::

•

•

•

'አፍቃሪ መሆን አቁመሃል:: የፍቅር ቅኝ ግዛት ነህ:: ቡናማዋን ልጅ ተዋት' እ ሚሉስ! ምን አገባህ ግን?

•

•

•

ፀናዕል ከአሜሪካን ዋሽንግተን ዲሲ ደብዳቤ ፃፈች:: በምኔው ከለንደን ወደ ዲሲ ተሻገረች? ሶስት ፎቶዎች አሉ ፖስታዋ ውስጥ:: ገፅዋ ያኔ ልጅ እያለች የጀመረችውን ሃሳብ እንዳልጨረሰች ይናገራል:: የምታስበውንም የራሷን ሃሳብ የምትታዘብ ይመስላል:: ሌላ ጊዜ መልስ ልፅፍላት ወስኜ ደብዳቤዋን ሻንጣዬ ውስጥ ደበቅሁት:: በትክክል አጠፋሁት ማለት እችላለሁ:: ከተባረኪ ጋር እስክጣላ ስትጠብቅ የኖረች መሰለኝ:: የፀናፀል ብልጠት ዝምታዋ ውስጥ ነው:: ልክ ነኝ ግን? ብጠረጥር ምን አለበት? wer nich zweifelen kann, ist ein dummer man ይላል ተረትና ምሳሌው:: 'የማይጠረጥር ሰው ደደብ ነው' ማለት ነው:: አልጠረጠርኩምና ተመነጠርኩ::

•

•

•

'ሕይወት እኮ ምለዋጥ እንደምትችል በየጊዜው አንድ የተለየ ነገር እያደረክ ማረጋገጥ ነው:: ማፍቀር እንደምትችል አረጋግጠሃል:: መርሳት እንደምትችል አረጋግጥ:: ይሄ የጣጣህን ፋይል ባንክ አድርገው:: ከተመቸህና ከፈለክ ቀኑ ሲደርስ ፍሙን እየመዘዝክ ተቃጠል' ሚሉስ

•

•

•

የሮበርት ሙሲልን *ማን ዊዝ አውት ኳሊቲስ*[43] የተባለ ልብወለድ እያነበብኩ ነበር:: ዴብራና ማክስ በር ከፍተው መጥተው ከጀብዱዬ አላቀቁኝ:: ያን የሚያክል መጽሐፍ ማንበብ የእውነት ጀብድ አለው:: ማርያምን:: *'ፍቅር ልክ እንደ አንዳንድ መጥፎ ሃይማኖቶች አደገኛ ልምድ ተደርጎ መቆጠር አለበት:: ምክንያቱም በፍቅር የወደቁ ሰዎች አመክንዮ ቢስ ናቸው:: በዚህ ሰበብ እነዚህ ሰዎች ነገረ ስራቸው ሁሉ ከእውነታ የተላቀቀ ነው'* እንደኛ ቅዕ......ገዕ......ምናምን......በተረትና ምሳሌያቸውም ጀርመኖች liebe is eine krankheit, die man haben will ይላሉ:: አጥሮ ሲነገር 'ፍቅር በሽታ ነው' እንደ ማለት ነው::

•

•

•

የፍቅር ግኑኝነት በቦታና በጊዜ ገዋ ውስጥ ይኖራል? የሚረብሸው ወይም የሚያሳምረው አውድ የለም? የረበሸኝ ፖለቲካው አይደለም? የተባረኪ ጀርባ ለእኔ ፊቷ ለአብዮት፣ ፊቴ ወደ እሷ ጀርባዬ ለአብዮት:: በዚህ ክብ የሚተያዩት ሰዎች አይደሉም:: ዕንብርትና ቂጥ ናቸው:: ለመሆኑ አውድ እንደ ወንበር እንደ ድልድይ እንደመሳሰሉት በመሐንዲስ ይነደፋል? በዕደጥበብ ይወቀራል? በብልጣብልጦች ይገመዳል?

•

•

•

አድቫንስድ ሊኒየር አልጄብራ ተምረን ስንወጣ:

«አባቴን አስተዋውቅሃለሁ» አለኝ ሚሉስ

ግራ ገባኝና አተኩሬ አየሁት:: ከእኔ የመቅረብ የቀስ በቀስ ዝንባሌውን ሳላይ እዚህ መደምደሚያ በመድረሱ መሰለኝ::

«ደስ አላለህም» አለ ፈገግ ብሎ

«ደስ ይለኛል:: እንዴት ጠየቅኸኝ ዛሬ?»

«በቃ ደስ አለኝ:: እሺ......ቅዳሜ ይመችሃል?»

«ማለቴ ከስንት አመት በሁዋላ ላስተዋውቅህ ትላለህ?»

«መሸፈት እንድትማር»

---

[43] Man without qualities

«መሽፈት እንዴት ትማራለህ? ዝም ብለህ ከፈላስፋው አባቴ ጋር ላላፋህ አትለኝም? ሃሃ»

«ትደበራለህ፣ ትሸሻለህ እንጂ አትሸፍትም አንተ»

«እሱን እንተወውና ቮድካ አለ?......ደስ ይለኛል......እንዲህ የምልህ ካልጠጣሁ ስለማይበራልኝ ነው»

«ስታስበው እንዴት ያለ እሱ ራሴስ እሄዳለሁ? ምን መሆንህ ነው? ምሳ እኔ እሰራለሁ:: በነገራችን ላይ የአገርህ ልጆች ፈልገውህ ነበር:: 'ለስብሰባ ነው' አለኝ አንዱ:: ሁለት ሆነው መጥተው ነበር»

«ስለአረንጓዴው ዘመቻ ሊጠዘጥዙኝ ነው:: ለሌላ አይደለም:: ደሞ አርመናዊ እንደሆንኩ ንገርልኝ:: እሱን ካላመኑህ 'ትናንትና ሞተ' በላቸው»

«ሃሃሃሃ»

•

•

•

የእዝራና የሕዝቡ ኤሮግራም ደረሰኝ፡

**ወንድሜ ወዳጄ ዓላዛር እንደ ምን አለህ? እግዚአብሄር ይመስገን እኛ ደህና ነን:: ቤተሰብ ሁሉ ደህና ናቸው:: የማሳስብህ ነገር ትምህርትህን ስትጨርስ በቀጥታ አገርህ እንድትመለስ ነው:: 'አውሮፓ' 'ምዕራብ' እያሉ ቤተሰብ መደበር እዚህ ፋሽን ሆኗል፤ እና አትደብረን:: የሮዛ አክሲጂን ነህ:: ሮዛ በቀን አምስቴ ማርያም ትሄዳለች:: ብዙ ጊዜ ባይመችኝም እሸኛታለሁ:: መነኩሴ ትሁን አለማዊ አሁን አሁን እየተምታታብን ነው:: አንዳንድ ሰው ሃይማኖተኛ ለመሆን የተፈጠረ ነው:: ይሄ ያየሁት ነው ዓላዛር:: ገና ሲወለድ ሰይጣን የመለመለው አለ:: የተቀባና የተረገመ አለ:: እንደ እናቴና እህቴ እንደምወዳት ታውቃለህ:: ድሮ አስቃት ነበር አይደለ? ዛሬ አንድ ነገር አትስቅም:: ተባረኪ እዋላ ናት፤ ቁርጥህን እወቅ ከአንድ ፋሲል ከሚባል ምሁር ሰውዬ ጋር ደጋግሜ አያታለሁ:: ሰፈር ይመጣል:: ተባረኪ ብትደብርህ እኛን አትዝጋን:: ደሞ በዚህ በላኩልህ አድራሻ ፃፍላት:: ባለፈና ባለቀ ነገር አትበሳጭ:: ልጅህ ደሞ**

አድጋለች:: በጣም ታምራለች:: ስልህ የዕውነት ማለቴ ነው:: እዚህ ሽሮ ስትመጣ ላንሸራሸራት ብዬ አወጣትና እንድታውቅህ ፎቶህን አሳያታለሁ:: ያንተ ካድሬ ነገር ሆኜአለሁ ማርያምን:: በቃ በፎቶህ ብቻ ወዳሃለች:: አይኗ ፀጉሯ በቃ አንተ ነህ:: ግን እንደ እናቷ ሞጥሟጣ ናት:: ወሬዋ ይገልሃል:: ለማንኛውም ፃፍ:: ሳትፅፍ ብትቀር መዓት ነገር ትቀጣለህ:: የሽሮ ልጆች ሁሉ ሰላም ይሉሃል:: ነገር እንዳያበዙ ጠባብ ቦታ ትቼላቸዋለሁ::

አንተ ምናባትክን አትፅፍም የጀርመን ድንች እንደዚህ ያጠግባል? *ቻርነት ነኝ::*

ቮድካ እንዴት ነው? ደህና ተመለስልን አቦ:: *ዘኔው ነኝ::*

እንዴት ነው ያ ቁመናና ፀባይሽ ከሆነች ናታሻ ጋር አላላፋሽም? ሙላትም ሰላም በልልኝ ሲል ነበር:: *ጎ ሶዌይ* ብዬልሃለሁ:: ከርቸሌ ገብታ ከፋይ ጫማ መስላ ወጥታ ካድሬ ሆና ምናምን ታሳዝናለች:: ነገደ ነኝ:: እንዳንቺ ሳይንስ እየተማርኩ ነው:: ከቻልሽ ወደ ምዕራብ መጭ በይ፣ ጤይባ አትሁኚ ሀሰን ነኝ

ወንድሜ ደህና ነህ? ደህና ናልን:: ለሲጋራ የገባውን ዱቤ አንሳበት ይሉኛል እነዚህ ሰይጣኖች:: በርጫ ልቀመጥ ነው:: ደሞ ንጭንጭሽ ይናፍቀኛል:: *ተማም*

እንደምነህ? ደህና ነህ? ናፈቅኸን:: ኸረ ባክህ ደስ ይበላቸው ብለህ እንኳን እዛ ስላለው ነገር ፃፍልን? አምላክ ወደ አገርህ በሰላም ይመልስህ:: *ወንድምህ ጌታቸው ዘ ታዚና::*

በቃ ፈርማዬን መፈረሚያ እስካጣ ሞሉት:: በእግዜር ፈቃድ እንደምንገናኝ አምናለሁ:: ወንድምህ *እዝራ ታዚና ዘብሄረ ሽሮሜዳ::*

አዋሳ? አዋሳ ሄደች? አዋሳን አላውቃትም:: መዓት ሜዳና መዓት ሳር ያለው ሶደሬ ይመስለኛል:: አልዋኝ፣ ሳር ልግጥ አልሰማራ:: አዲስአባ ብኖር ኖሮ ሙላትን ታላቴሊ በትልቅ ሳህን ይገኔ እስር ቤት

ሂጄ እጠይቀው ነበር:: አይ ስዌር:: ሙላት ወዝ ዋን ኩል ዱድ......"
ጆሊ ባር ትመስክር:: ያ ግድ የሌለው ተጫዋች እንዴት ኢተጫዋች ሆነ?

•

•

•

***«ጌታ ሆይ ይህን እንጀራ ዘወትር ስጠን አሉት» የዮሐንስ ወንጌል 6:34---***

***ለቁርስ:***

ሌፕዚንገር ለርቸን፣ ፊልሰን፣ ፕሬትዜል

***ምሳ:***

ሱፕ ኮምፕሊካሲዮን

(*ኮምፕሊካሲዮን የተወሳሰበ ማለት ነው:: ሾርባ ሰፊ ቦታ የሚይዝ* መረቅ ነው፣ ብዙ ተፃራሪ የመሰሉ የንጥረነገር ባህርያትን የሰበሰበ:: ሾርባ አገር ነው:: ከከብት ግጦሽ ያመለጠ ጎመንና በግጦሹ የዳበረ የከብት ስጋ፣ በቦምብ ከሚደበደብ ሶስተኛው አለም የመጣ ቅመም:: መረቁን ብንሰባብረው ሉላችን ተቀምጣ እናገኛታለን)

ብለትዎርስት፣

ሳቨር ቭራተን በድንች፣

ቀይ ጎመን፣

ክኖዴል፣

ከፈራረሰ ድንች ተድቦልቡሎ የተሰራ የድንች ኳስ፣

ስፓዝል፣

የተቀቀለ ድንች በሎወንሶፍ መስታርድ፣

ብላክ ፎሬስት ኬክ

አንድ ትፏሕ

ቪታ ኮላ::

***እራት:***

አይስቤይን፣

44 እምላለሁ......ሙላት ደስ የሚል ልጅ ነበር......

ኬት ወርስት(ሆት ዶግ)፣

ግሪሊታስ፣

ክሩስታ (ፒዛ)፣

***ማታ ከአራት በሁዋላ:***

ቡልጋርያን ዶንኪ ሚልክ (የቡልጋርያ የአህያ ወተት) ወይን

ሃንጋርያን ቡልስ ብለድ (የሃንጋሪ የኮርማ ደም) ወይን

ሮትካፕቾን፣ ሮትስተርን፣

***ከመስኮት ጠረጋ መልስ:***

በትራባንት መኪና......

ቀይ ኮኮብ ቾኮላት

•

•

•

***የሌሊት ሩጫ:*** ሚሎስ ከፊት ለፊቴ እየሳቀ ያስከትለኛል:: በሬሃ ስፖርት ጫማ:: ባይመችም፣ ባለው:: በቀዝቃዛ ነፋስ ውስጥ እሮጣለሁ:: ጥርሴን ነክሼአለሁ:: እዛ እንዳለ ይገባኛል:: ግን አድማሱ አይታየኝም-- እንደምመኘው:: 'አለ' ወደ ተባልኩት እስክደክም እሮጣለሁ:: በተስፋ መኖር ቀልነት ነው::

•

•

•

***ሕቡዕ ምንድነው?*** ከስሜት ሕዋሳት ብርበራ የራቀ? ሕቡዕ ያልሆነ ነገር ምንድነው? የሆነ ይሄ ጎኔ ለራሴ እንኩዋን ሕቡዕ ነው:: ይሄ ጀርባዬ ለራሴ ህቡዕ ነው:: ህቡዕነት ብርቅ አይደለም:: የተባረኪ መታባት፣ የውሸት ተከፍቶ የሆነ የመሳደጃ ሰበብ ፈጥሮ ከሚያፈቅራት የመሸሸግ ነው:: ግመል ሸርቆ አጎንብሶ:: ስልቱ ሳይበረዝ ቢነገር፣ እየተያዩ 'ተደብቀናል' ማለት::

•

•

•

***ወረቀትና ዝምታ:*** አንድ ማታ ለፀናዕል ደብዳቤ ልፅፍ አሰብኩ:: *ምን ልበላት?* እያልኩ ስጨነቅ አመሸሁ:: *ምን ልበላት?* ወረቀት ሳነሳና

ስጥል፣ የፃፈችልኝን ከሻንጣዬ አውጥቼ ደግሜ ደጋግሜ እያነበብኩ መልስ ሳሰላስል:: ከመሃል ልጅነታችን ገለልተኛ ጊዜ ስለመሰለኝ ስለ እሱ መቸክቸክ ጀመርኩ:: (ግን ልጅነታችን ምኑ ገለልተኛ ነው? ምን ያህል ከልቦናችን የራቀ ነው?) ስለ ፒያኖ ጨዋታዋ አነሳሁ:: ስለዝምታዋ አነሳሁ:: ጨዋንትም ስለሆነ 'ትናፍቂኛለሽ' አልኩ:: የማስባት በመዓት የሽሮሜዳ ግብስብስ ሃሳቦች መሃል አንድ ተራ ንጥረ ነገር ሆና ብቻ ነው:: አትናፍቀኝም:: ካልረሳሁት እውቀቴ የፀናፅል ፀናፅልነት የተመሠረተው በእቅድ የተያዘ የመሰለ ቅጥነቷና ዝምታዋ መሆኑን አውቃለሁ:: ቀጫጫነቷን ገፋ ብታደርገው የምታስፈራ ነጭናጫ ሴት እንደምትመስል ልናገር አልችልም:: ዝምታዋ ላይ ሌላ አምስት ግራም ዝምታ ብትጨምር አብሬአት መቀመጥ ይከብደኛል:: ጠርዝ ላይ ያለች ናት:: ወደ የት እንደምትሻገር የሚያውቅ የለም:: ቢሆንም አብረን ያየናቸውና የምናውቃቸው ነገሮች ነበሩና አንድ ገፅ ሞልቼ ላኩላት:: ደብዳቤውን ስልከው ግን በሆዴ ቅሬታ አለ: *የፃፍኩት ልክ ነው ወይስ አይደለም? ምን አስፈራኝ?*

•

•

•

***ፅናት: ይሄን ቃል ልረሳው ስል:*** ፅናቴ ተላትሞ የመቆም ሳይሆን አጎንብሶ የማሳለፍ ነው (ጎበጥ ማለት እንደሚያደክም ጀርባ ያላቸው ሁሉ ያውቃሉ):: እማማ ከዚህ አለም በሞት እንደተለየች ሁለት ደብዳቤዎች ተፃፉልኝ:: ካነበብኩት በሁዋላ ወደ ፓርክ ብቻዬን ሄድኩ:: *ወንድ ልጅ ብቻውን ነው የሚያለቅስ::* ስርቅ ሳይለኝ አለቀስኩ ይባላል? የአብሮ አደጌን ትከሻ ሳልደገፍ ባለቅስ ለቅሶዬ ጥራት አለው ይባላል? ተባረኪ እጄን ሳትይዢኝ? እኔ እናቴን እመስላለሁና፣ ለስላሳነቴ ይሆን ያስለቀሰኝ? እማማ ከማለፏ በፊት የሰከንድ አፍታ ቢኖራት ስሜን እንደምትጠራ አውቃለሁ:: ለአባባ፣ ለፀሐይና ለእዝራ ደብዳቤዎች ፃፍኩ:: ለሶስቱም የፃፍኩት እያለቀስኩ ነው:: ከዚህ ቀድሜ ለምን አልፃፍኩም? ድምጼ በመጥፋቱ እንደተጎዳች እጠረጥራለሁ::

እዝራም አባባም ፀሐይም ሶስቱም: ***ፅናቱን ይስጥህ*** ብለው ደብዳቤአቸውን ይደመድማሉ:: ይሄን ቃል መቼም ተጠቅሜበት አላውቅም:: ከሰማሁት ዘመን አለፈኝ:: እንግዳና ከባድ ሆነብኝ::

ከአርባ ሰአታት በላይ አለቀስኩ:: የሆነ የዕንባ ሁዳዴ::

•

•

•

***አንዱ ባንዱ ውስጥ፡*** እዚያች ሽሮሜዳ የተባለች ድስት ውስጥ ስገባ፣ በ**ሕይወት** ጎዳና ስጓዝ፣ ፈጥኜም ይሁን ተንቀራፍፌ፣ ቢያምርብኝም ባያምርብኝም፣ ስጋጭ፣ ስዋደድና ስጣላ፣ ስስቅና ሳለቅስ፣ ሁሌም ያበጀኝ እሆናለሁ:: ውስጤ ያ አለ:: ውስጤ ያቺ አለች:: ተራራውም:: ወንዙም ('ዕንባው እንደ ወንዝ ፈሰሰ' ለምን እንላለን?)

**ባታምነኝም እነዚሁና አሉ::**

**ብትጎዳኝም የምትጎዳው ራስህን ነው::**

**የምትሰነዝሪብኝ ጥፊ፣ ከተሰማሽ**

**አንቺም ፊት ላይ በሰከንድ አፍታ ያርፋል::**


ዐየን......ተፋቀርን......ተጫወትን:: ሁለት አመት እንኳን አልሞላም፣ የሚያስወጣኝ በር አምስት ሺህ ኪሎ ሜትሮች ያህል ወደ ጀርመን ተከፈተ::

•

•

•

***ዩክሊድና ሕይወት፡*** በጂኦሜትሪ ቀላል ከርቭ ወይም ቀላል ቅንፍ የሚባል አለ:: ይሄ ማለት አንድ መስመር ከራሱ ይገጥምና ሁለት ክፋሎች ይፈጥራል:: ከውስጥና ከውጭ:: እንዲህ ለምሳሌ፡




ክቡ የተሰራው 'የአንድ መስመርን አናት ወስዶ ከራሱ ጅራት ጋር በመግጠም ነው:: በዚህ ድርጊት 'ሀ' የተባለው የተቀነበበ ቦታና ከ 'ሀ' ውጭ ያለ 'ለ' የተባለ ቦታ ይፈጠራል:: 'ሀ' አሁን እኔ ያለሁበት ይሆናል:: ከውጭ ያለው 'ለ' ይሆናል:: 'ሀ' ውስጥ እኔና የተባረኪ ትዝታ ነን:: እየቆየ ሲሄድ እዛ አካባቢ ያለው አየር ስለማይነፍስበት መሽተት ይጀምራል::

**አየሽ በሆነ ሂሳብ ትዝታ ዝገት ነው::**

በተነቃነቅሁ ቁጥር ግድግዳው ግንባሬና ሁለመናዬን ይገጨኛል፡፡ ስለዚህ ከዚህ ጣጣ ለመላቀቅ ከሰፊው አለም ጋር በቅንነት መገናኘት አለብኝ፡፡ ነፋስ መግባት አለበት፡፡ ያደረኩት እንዲህ ነው፡፡




ያኔውኑ 'ሀ' ውጭም ውስጥም ይሆናል፡፡

•

•

•

*ዝርግ……ግዙፍ……ዐይናማ፡* ሚሉስ እግሩን ወለም ብሎት ከክፍል አልወጣም፡፡ እኔና ዶሮታ፡፡ በበድራልዋሽ ቢራ ወረዳ እየተደሰቱ ለመዋረድ፣ እየተዋረዱ ለመደሰት፡፡ ዶሮታ ሁለመናዋ እንደ ተባረኪ ነው፡፡ ወፍራም ለመባል ትንሽ የቀራት ድምቡሼ፡፡ መልኳ በአገሯ ሰዎች ብዙ አይወደድም፡፡ ክብ ፊት፡፡ ሳቋ እንደ ሕፃን ልጅ፡፡ 'ለምን ወደድከኝ?' ስትለኝ አልነገርኳትም፡፡ 'ቴቢን ትመስያለሽ' አልላትም፡፡ በተለያዩ አህጉራት ያሉ ሰዎች እንዴት ይመሳሰላሉ? ይሄን ሳስብ፡

'ምን ታስባለህ?' አለችኝ፡፡

*ምን ልመልስ?*

'ስለ አይኖችሽ'……'

'ሂሂሂ……አላምንም'

ሞቅ ብሎን ወጣን፡፡ መንገድ ላይ ማንም አልነበረም፡፡ ዶሮታ ግዙፍ ናት፡፡ ደረተ ዝርግ ናት፡፡ የቀረው ሁሉ ነገሯ በስብ የተሞላ ነው፡፡ የዳሮታ እንደ ደም የቀላ ከንፈሯ አፌ ላይ፣ ምራቋ የፕሬትዜል ጨው ነው፡፡ ኒቼን ነትቼ እንደማወጣ ሁሉ እሱን እየመጠጥኩ፡፡ ከባሩ የሚሰማ የሮይ ኦርቢሰን ፕሪቲ ምማን በጆሮአችን፡፡ ከቴም፡፡ በጋ ነው እዚህ፡፡ ከላይፐዚግ ሰማይ ቢጫ መረቅ ይወርዳል፡፡ ከዚህች ጮማ ልጅ ጋር፡፡ በትፋህ የጠረኝ የኩሽ ብብቴ፡፡ ፍቅርና ወሲብ ርዕዮተ አለም አይደሉም፤ ማን ይቀነብበኛል? ባህሩ ሰፊ ነውና እሷን አቅፌ ዘልዬ ገባሁ……ወደ ካስፒያን ወደ ኤልባ፡፡ ከለመዱት ባሕርም ይደክላል፡፡

•

•

•

ዛሬም......ነገም......ከነገወዲያም......የሚመጣው አመትም......የእኔን ነገር የሚገልፀው ፍልስፍናና ዲሞክራሲ አይደለም:: ልቤ ነው:: ለምን በተባረከ ነገር አልቀና? 'ቅናት ጥሩ አይደለም' ምናምን......ጋዴሚት! ......መቅናቴ አያሳፍረኝም:: ጣቶቿ አጥቅ መሃል ያለው ሳብ፣ ደረቷን ሞልተው የሚገፉኝ ጡቶቿ:: ተሽከርምማ የምታነሳልኝ እግሮቿ፣ (እነሳስ ብቻ አይደለም፣ ከካሮል ካምፕቤል ዳንስ ያማረ ነበር) ስስ ከንፈሮቿ ሲሳቀቁ እየፈሰሰ የሚወጣው ትንፋሿ፣ ከከንፈሮቿ ጀርባ የማየው የጥርስዋ ሰልፍ፣ ስሜን እየጠራች ስትንቀጠቀጥ፣ ለምን አልቀናም? ና ልሳምህ ብላ ለምትነክሰኝ፣ (ሕመሙ ከቪታ ኮላ ይጥማል እማምላክን):: ታዲያ ብቀና ለምን ስህተት ይሆናል? ለምን ግድፈት ሊያደርጉት ይለፋሉ?

•

•

•

የሚመጣው አመት ፒኤችዲዬን ስለምሰራ ትንሽ ንባብ በዝቶብኛል:: ማርኬ እየተሻሻለ ስለመጣ እነ ሚሎስ 'ታዲያስ ጂነስ' ይሉኛል:: 'ከዶሮታ ተጋብቶብኝ ነው' እላቸዋለሁ:: ምንም 'ሶሻሊስት ነን' ቢሉ በጎን በስልት የሚሄድ አምልጦአቸው ይሁን ሳያመልጣቸው ቅር የሚያሰኝ ዘረኛነት ብቅ ይላል:: 'ጂነስ' ሲሉኝ ቅላፄው ውስጥ የማሳቅ ብቻ ሳይሆን የመናቅ ድምፅ አለ:: ልክም ናቸው:: 'ኅበዝ አገር የተወለድኩ ነኝ' ለማለት ምን ላሳያቸው? የአድዋ ጦርነት? ግን ሉአላዊነት ማሽንና ገንዘብ አይደለም:: በገንዘብም አይሰላም:: ነፃነት ስንት አይሮፕላን ያወጣል? የባቡር ሃዲድህ ምን ያህል ማይል መርዘም አለበት ባርያነት ለመድረስ? ስንት ደናግልት ባዕዳን መደብ ላይ መስዋዕት መሆን አለባቸው ለአንድ ትልቅ ድልድይ?

ፀናዕል ደግሜ ደብዳቤ ላከች:: በጣም ቀልታለች:: ከፎቶው ይሁን እንጃ ትንሽ ወፍራለች:: በጣም ትስቃለች:: ሁለቴ ደብዳቤዋ ውስጥ 'ውይ እንደናፈቅሽኝ' ትላለች:: ቀላል 'ውዮች' አይደሉም:: ይህቺ ልጅ ፍቅርና ፋክ[45] ፈልጋለች:: የዚህ አይነት ሁለት ክፍፍል መገመቴ ትክክል ነው? በሁለቱ መሃል አይሆንም? አንድ አራተኛ አንዴ ሶስት አራተኛው ሌላ? የልጅቷን 'ውይ' በሁለት መክፈሌ አእምሮዬን ወይም ስሜቴን የመሀይም

[45] ፋክቤ ሰጋ (እንግሊዘኛ)

ኩሊ ያደርገዋል:: ግን ሁለቱም ባይኖር አንዱ ወይም ፍራክሽኑ አይጠፋም:: ያኔውኑ መልስ ፃፍኩ:: ፎቶ ቢኖረኝም ከዶሮታና ከሚሉስ ጋር የተነሳነው ብቻ ነው::

ሚሉስን ትንሽ ተቀይሚዋለሁ:: 'ታዲያስ ጂነስ'ን አልረሳም:: ምናልባት የራሴ አደማመጥ ይሆናል አባባሉን ደባሪ ያደረገው:: መርሳት እሞክራለሁ:: ካለው በሁዋላ እንኩዋን የተሳሳተ አልመሰለውም:: ወይስ አራዳ ሲሆንብኝ ነው?

የፀናፅልን 'ውይ እንደናፈቅሽኝ' ያለበትን ደብዳቤ አስራ ሁለት ጊዜ አነበብኩት::

•

•

•

*ፊክን*[46]*......*

*'ችግርን አትሸሸው......*

*ላታመልጠው......*

*ሲጀመር አለመወለድ ነበር......*

*ሶ ላ ዛ ር'* ይሄን ብላኝ ነበር እናኑ:: ያኔ አባባሏ የመሰጠኝ ፈጣን ግጥም በመሆኑ ብቻ ነበር::

•

•

•

*ቢራና አባት፡* የሚሉስ አባት ስለ 'ግሮዘ' ቢራ ያወራሉ:: ስለ 'አትላንቲስ' የሚተርኩ እንጂ ስለ ድሮ ቢራ አይመስልም::

'አንድ ልጄ ነው' አለ ሚሉስን እያየ:: ዓይኖቹ በዕንባ ይፈልቃሉ:: ጊታር ይነቅስበት የነበረ ግራ እጁን አንስቶ የሚሉስን ቡናማ ፀጉር እየዳሰሰ አመሳቀለበት:: ሚሉስ ተበሳጨ:: ሁኔታው ያሳዝናል:: ብርሃን እንዲህ አድርጎ ያውቃል? ትዝ አልል አለኝ:: ሚሉስ እንደ ቀናሁበት አላወቀም::

«ወንድምና እህት አለህ?» አለኝ አባቱ ቀና ብለው:: ራሴን በአሉታ ነቀነቅሁ::

«እዛ ልጅ መውለድ ትወዳላችሁ አይደለ?»

---

[46] ዝኒ ከማሁ (ጀርመንኛ)

«እኔን ከወለደች በሁዋላ ሃኪም ሁለተኛ መውለድ አትችይም አላት»

አስብኩ፡ ተባረክ፣ እኔ፣ እዝራ፣ አንድ ለእናቱዎች ነበርን። የሽሮሜዳ የበኩር ልጆች። ሚሎስን የቀረብኩት ለዚህ ይሆን? ሽማግሌው ሚሎስ ሳያቋርጥ ለአንድ ሰአት ልብ የሚበላ ሙዚቃ በቡናማ አኩስቲክ ጊታሩ ተጫወተ። ከስንት አመታት በሁዋላ ሙሉ በሙሉ፣ ከላይ እስከታች ደስ ያለኝ ያን ቀን ነው።

•

•

•

ፀናዕል በአንድ አረፍተነገር ምን እንደምትፈልግ ፃፈች። 'ለምን አሜሪካ አትመጣም?' ሳይግደረደሩ ሲተረጉሙት፡ 'ለምን አብረን አንሆንም?' ማለት ነው። ቶሎ መወሰን አለብኝ። ለሁለት ቀኖች አልተኛሁም። 'ለምን አትተኛም?' ሲለኝ ሚሎስ 'ቴሲስ' እለዋለሁ። 'አይዞህ' ምናምን ይለኛል። ጠዋት ላይ ከእሱ ጋር የማደርገውን ሩጫ አቋሜአለሁ። እተኛሁበት ሰድቦኝ ይሄዳል። እማማ ናፈቀችኝ። ፀሐይ ናፈቀችኝ። ለፀናዕል *ለማንኛውም ሌላ ጊዜ በሰፊው እፅፍልሻለሁ* ብዬ አንድ ጥቁርና ነጭ ፎቶዬን ለደብዳቤዋ መልስ ላክሁ።

•

•

•

«ታሪክ የተለያዩ ደረጃዎች አሏት። አንደኛው ሁሉ የሚማረው የኩነቶች ክትትል ነው። የተከየነ ምክንያታዊነት በጥናት የተገጠመለት። ይሄ ማንም የሚያውቀው ግን ብዙው ውሸት የሆነ ታሪክ ነው። ይህቺ የመጀመሪያዋ ክፍል ብቻ ላይ ከቆምክ *ታሪክ ሴተኛ አዳሪ ናት* ትላለህ። ሁለተኛው ኮሌጅ የምትማረው፣ ከፊል ሚስጢር ያለበት፣ አመራር ላይ ያሉ ፖለቲከኞች የሚያውቁት፣ በመጠኑ የአንድ አገር ትክክለኛ ቦታ የሚታይበት ታሪክ አለ። ይሄ ለጉራ የሚሆን ዕውቀት ነው። ሶስተኛው ግን ሚስጢር ነው። ሶስተኛውን እንዲያነቡና እንዲያውቁ የሚመረጡት የተወሰኑ ሰዎች ናቸው። ያልተፈቀደለት ልወቅ ቢል ይቀጣል። ከዚህ በተጨማሪ ደሞ ግለሰቡን በሚመለከት ግለታሪክን የማወቂያና የመመዝገቢያ ሶስት ደረጃዎች አሉ፡ ሁሉ ሰው የሚያውቀው ጉዳይ፣ የቅርብ ሰዎች የሚያውቁትና አንተ ብቻ የምታውቀው። አንድን ነገር ለመረዳት በነዚህ ሁለት ክፍሎች ስድስት ንዑስ ክፍሎች ውስጥ መመላለስ ግድ ነው። እንደሚመስለኝ አንተ የትኛውንም በትክክል አታውቅም። በቀላሉ ስለሮጮችህ እንኳንም አታውቅም»

«ስህተት ነው?»

«ደንቆሮ መሆንህን አለመደበቅህ ደስ ይላል እንጂ. ስህተት ብቻ ሳይሆን ድክመትም ነው፡፡ በነገራችን ላይ ይሄ 'በክለ' 'በክለች' ያልክው ማነው? ሁልጊዜ 'በክለ' 'በክለች' ትላለህ»

«ወንድም ሚሉስ ሆይ አቶ ሴዝላው ሚሉስን ጠይቀው»

«ቬርዳምት!......አንተ እንዴት ከሶሻሊስት አገር መጣህ?»

•

•

•

ለሚሉስና ለአባቱ የሽሮሜዳን የእንጀራ ገለጣ ጥንቆላ አሳየሁዋቸው፡፡ የስፌሬ ባለ ቡና ቤት (ሴተኛ አዳሪ መሆንዋን ደብቄ) ይሄን አይነት ሾርባ ተጠቅማ መተንበይ ትችላለች አልኩዋቸው፡፡ ወሬዬ ከትንግርት እንዲላቀቅ አልፈለኩም፡፡

«ሕዝቦች ከጭንቀታቸው ለመላቀቅ የማያደርጉት የለም፡፡ ያፅናናል፡፡ ደመና ይነበባል፣ የቡና አተላ ይነበባል፣ የከብት ሞራ ይነበባል፡፡ በሳይኮሎጂ ሮሻሽ ቴስት አለ፡፡ ከዚህ ካልከኝ . በምን ይለያል? ሳይንስ ተብሎ ስንት ቀልድ አለ፡፡ ፍሩድያን ሳይኮአናሊሲስ አንዱ ቀልድ ነው፡፡ ፍሩድ የሳይኮአናሊሲስ ቴክኒኩን ሲያቀናብር አለምን ጠቅላላ በአንድ የኦዲፐስ ተረት ለመግለፅ ሞክሯል፡፡ እንደውም ይሄንን ያልከውን ነገር ትንሽ ለውጬ እጠቀምበታለሁ፡፡ የትም ባያደርስ ጥሩ ጨዋታ ነው፡፡ አሰራሩን በዝርዝር ታውቃለህ?»

የተናገረው በደንብ ባይገባኝም፣ ላስታውስ የምችለውን ያህል እንዴት እንደምትጠነቁል አብራራሁላቸው፡፡

«በቂ ነው፣ የቀረውን እራሴ እፈጥረዋለሁ፡፡ ሁሉ ነገር በንፅፅር የሚታይ ነው፡፡ ብቸኛ ነገር የለም፡፡ ሰው በል ቁስ፡፡ አንዱ የአንዱ ልዋጭ ነው፡፡ አንዱ አንዱን ይገልፃል፡፡ ውስብስብ ነገሮችን ለመረዳት ከቀላሉ መጀመር ማለት ውስብስብ መሆኑን መርሳት አይደለም፡፡ የአቅም እጥረት ነው፡፡ ሰው ራሱ የሰራውን ስርአት መረዳት ይከብደዋል፡፡ ይታይህ ለላም ጅራቷ ሲከብዳት፡፡ ፈላስፎች የማይገባቸው ይሄ ነው፡፡ በስርአት ያስሩናል፣ ይገርፉናል፡፡ ማርክሲዝምና ሊበራሊዝም ከዚህች ሴትዮ ጥንቆላ አይሻሉም፡፡ የዘመናዊነት በሽታዎች ናቸው»

በመንቦቅቦቅ እሰማለሁ፡፡ *ልፖተልክ አልመጣሁም ጂሚ፡፡*

ሚሉስ ሲጋራውን ኮስተር አድርጎ እየሳበ ያዳምጣል፡፡

«ሴትዮዋ ያደረገችው ኪነት ነው፡፡ ኪነት ምኑ ከጥንቆላ ይለያል? ኪነቱን ተወው፣ በስልት እየተሰራ ነው የሚሉን የአንዳንድ አገር ኢኮኖሚ እኮ ከጥንቆላ ስራ የተለየ አይደለም፡፡ ሃሃሃሀ»

ሳህኑ ላይ የቀረውን መረቅ በዳቦ ጥርግ አድርጌ በላሁ፡፡

«እርቦህ ነበር»

«መስኮት ጠረጋው ያደክማል፣ ቀኝ ከንዴ ዝሏል:: መልመድ ከብዶኛል»

«ያለው ይሄ ነው......በርታ:: መስኮት ትጠርጋለህ፣ ሰሃን ትጠርጋለህ:: የተዋጣለት ጠራጊ ይሉሃል ዓላዛር ነው ሃሃ»

«ሀው አብ[47]:: አላማረርኩም»

«ጀርመንኛው ደስ አይልም?»

«እኬ አሁን እንሂድ ቶሎ ስራውን እንጨርስ......»

•

•

•

አእምሮዬ ውስጥ ካለ ኮረብታ የላይፕዚግ ማርያምን ጉብታ አያለሁ:: ጉልላቱ እንደ ተፋቀ እርጥብ የሰብነበረድ ጥርስ ይፈልቃል:: የሚሉስ ዶቅዶቂ ድምፅ ከዛ የሚመጣ ይመስላል:: ይህቺን አለም የሚያነቃንቃት ሞተር የት ነው? እኔንስ እስሬ ባላቀድኩት ጎዳና እየነዳ አላወቅሁት ቦታ የሚጥለኝ እሱስ የት ነው? በጣም ከመርቀቁ የተነሳ በግጥምም በስነ መለኮትም የማይያዝ ከጥንት የተገጠመልን ሁላችንንም የሚነዳን ሞተር አለ? አድፍጦ የሚነዳኝ:: መኖሩን በወንጌሉ ያልነገረኝ:: የታለ መጽሐፍ ሞተር?

•

•

•

'ወደ ቦን ከተማ የሚወስዱህ ሰዎች ፈልግ:: ደሞ አምሮብሃል:: ሁልጊዜ ታምር ነበር:: ሁልጊዜ እወድህ ነበር:: አልገባህም:: ይቅርታ ይሄን ስላልኩ:: እንደነገርኩህ እንደምንም ምዕራብ ጀርመን ግባ፣ ለዶኪመንቱ ተፈራርመን አሜሪካ ይገቢህ እመጣለሁ:: መፈራረም እንዳያስፈራህ:: ቀላሉ እንደዛ ነው'

*ፀናፅል ተ/ ማርያም*

ምን ይጎልብኛል? ሰዎች አሜሪካ ሊገቡ አይሮፕላን ይጠልፉ የለም? የማውቃት ልጅ ስትጋብዘኝ ምን ጎደለ?

---

[47] ጥሩ ከዚህ (haw ab)

•

•

•

'ጥናት ከሌለ ዕውቀት የለም። ዕውቀት ከሌለ መለወጥ የለም። ልበሙሉነት ብቻውን ያለ ትክክለኛ መረጃ ምንም ነው። ሳታውቅ 'አውቀሃል' ካለህ አገልግሎትህ መስዋዕት መሆን ብቻ ነው። ማወቅ ሲገባህ ካላወቅህ ደደብ ነህ። ዕውቀት ስሜትን መቆጣጠር አለበት። ስሜት እውቀትን መያዝ ወይም ማሰር የለበትም። የለውጥ ስሜትህን አይተው፣ እሱንም ከዕውቀት አምታተው ሳታውቅ አውቀሃል ካሉህ፣ ጠላቶችህ ናቸው። ሹራቡ ላይ 'ጠላትህ ነኝ' ብሎ ዕሮ እንዲመጣ ትጠብቃለህ?'

ሰማሽ

ይሄ ሚሎስ ያለኝን?

ተባረኪ

ሰማሽ?

•

•

•

ማስታወስ የማንችላቸው ነገሮች አሉ። ማስታውስ እየቻልን ማስታወስ የማንፈልጋቸው ነገሮች አሉ። ማስታወስ የማንችላቸው ማስታወስ የማንፈልጋቸው ነገሮች አሉ። ማስታወሳችንንም የሚያስተዳድሩ ፖለቲከኞች፣ ታሪክ ፀሐፊዎች፣ አለባልተኞች፣ ስህተታቸው ያልጣማቸው ስህተተኞች አሉ። እነሱ ማስታወሳችንን ያርማሉ፤ አታለውም ይሁን አስፈራርተው የማስታወሳችንን ጆሮል ጥሰው ገብተው የፈለጋቸውን ይነቅላሉ፣ የፈለጋቸውን ይተክላሉ፤ ማፈሪያችንን ይኮተኩታሉ፣ መጠንከሪያችንን ውሃ ያጠጣሉ። የምታገለው ተፈጥሮ ከአሳቀፈችኝ የማስታወስ ችሎታዬና ድክመቴ ጋር ብቻ ሳይሆን ከስሜቴ ወጣ ገባና ከድርጅታዊ መዋቅሮችም ጋር ነው። የመከራው ስንሰለታማ ገቢር አንዱ ትዕይንት ይሄ ነው። በምን ይታገሉታል? እንዴት ይጋፉታል?

•

•

•

በርሊን አይሮፕላን ማረፊያ የጎማ ካፖርቴ ውስጥ ንፋጥ የሚያዝረበርብ ፊቴን ደብቄ እጠብቃታለሁ። ጉንፋን ሲይዘኝ አለምን

እጠላለሁ:: ምሽቱ ለዐይን ያምራል:: ልቤ እንደ ከበሮ ይመታል:: ሩብ ሰአት ዘግይታለች:: ስለመምጣትዋና እሷን ስለማግኘቴ እንጂ ስለሌላ ስለምንም አላስብም:: በር በር አያለሁ:: መዓት ሰው ዙሪያዬን ቢሆንም አልተሰወርኩም:: በቀኜ በኩል ስሜ ተጠራ:: ዞር ብዬ አየሁ:: ፀናዕል አይኖቿ ዕንባ አቅረው ፈገግ ብላ ቆማለች:: ቃል አልወጣኝም:: እዛ የቆመችው ፀናዕል አልነበረችም:: ሽሮሜዳ......አዲስአባ......አገሬ...... ተራራ......ሜዳ......የምበላው......የምጠጣው......ጠዋቱ......ደሞ ጠዋቱ ......ደሞ መዓት ፀሐይ......እማማ......እናኑ......አባባ......እዝራ......ፀናዕል ......የምትያዝ የምትጨበጥ ፀናዕል፣ በአእምሮዬ የሚወጣና የሚወርደው አልበሜ ናት:: ሳቅፋት......ሊወጣ የሚታገለኝን ለቅሶ ወደ ሚደበቅበት የሆዴ ጎድጓዳ ዋጥኩት::

•

•

•

ወደ ተዘባረቀ ወደ ደፈረሰ በተገኘው መንገድ መናከሻ በሚፈልግ አካሄዱን ወደ ማያውቅ መጋጋጥ ባህሉ እንዲሆን ወደ ተደረገ ኩሬ ተመልሼ አልገባም:: አሳው ውሃውን እየበላ ነው::

•

•

•

***ማይ ጎድ***: በታክሲ ወደ ቤቷ ስንሄድ እጄን ያዘችኝ:: ዝቅ ብዬ እያየሁ በእጅዋ ጣቶች ስጫወት ቆየሁ:: ተንጠራርቼ ጉንጭዋን ሳምኩዋት::

«እዛ አገር እንድትሄድ አልፈልግም» አለችና የተናገረችው ምን ተፅዕኖ እንዳሳደረብኝ ለማየት መሰለኝ ዞር ብላ አየችኝ::

«ምን ብዬ እሄዳለሁ?»

እጄን አጥብቃ ያዘችኝ:: መናገር እንደከበዳት ሁሉ ምራቋን ዋጠች:: ጉሮሮዋ ከፍ ዝቅ ሲል አያለሁ::

«እዚህ ሆኜ አገሬን ሳስብ በአንተ ውስጥ ብቻ ነበር የማስባት፣ ዮ *ኖው በጣም ፒይንፉል*[48] ነው:: *አይ ዱ ኖት ኖው*[49] ያንተን ስሜት:: ጀርመን ሄድክ ሲባል *ዩ ኖው*[50] ጀርመንን አላውቅም ግን ስለማላውቀው

---

[48] ያማል

[49] አላውቅም (I do not know)

[50] ታውቃለህ (you know)

ጀርመን አስባለሁ:: የራሴን መልከአምድር *ክሪኤት*[51] አደርጋለሁ:: በባቡር ስትሄድ አስባለሁ:: በበረዶ የበረዶ ልብስ ለብሰህ ስትሄድ አስባለሁ:: ቀይ ባንዲራ ሲያሸክሙህ *ሰምቲንግ ላይክ ዛት*[52] ሂሂ:: ሁልጊዜ እፀልይልሃለሁ:: አባባና እማማ አይገባቸውም:: ምን ብዬ ልንገራቸው? ትምህርትቤት *ለዝቢያን*[53] ያደርጉኛል:: አበሾችም:: እኔ ብቻ ነኝ እንደምወድህ የማውቀው:: ልረሳህም አልፈልግም:: ብፈልግም አልችልም:: አሜሪካ ደስ ካላለህ ግሪን ካርድህን ስታገኝ ለብቻህ መሆን ትችላለህ:: ብቻ አጠገቤ ሁን:: አሁን ጎበዝ ተማሪ እሆናለሁ:: *አይ ሃድ ኤ ባድ ይር......ይርስ*[54] ልበል እንጂ.»

*ማንም እንዲህ አላወራኝም:: የያዝኩትን እጅዋን ሳምኩት:: ለምን ሳምኩት? የምናገረው ስላልነበረኝ? መናገር ስላልቻልኩ? ተባረኪ እንዲህ አይነት ቃል ወጥቷት አያውቅም:: ሞጥሙዋጣ ናት ግን አልወጣትም::*

ከጥቂት ፀጥታ በሁዋላ ሾፌሩ በሚሰባበር የሕንድ እንግሊዘኛ ተናገረ:

«የየት አገር ቋንቋ ነው የምታወሩት?»

ፀናፅል እንደተሰላቸች ሁሉ አንገቷን እየነቀነቀች:

*«አአአ ማይ ጎድ*[55] *የድርቅና የረሃብ ወሬ ሊያመጣ ነው»* አለች::

•

•

•

*ሄንሪ ዋደስዎርዝ ሎንግ ፌሎ እንዲህ ይላል:*

In this world a man must either be an anvil or a hammer...(እዚህ ምድር ላይ ሲኖር የሰው ልጅ *መዶሻ* ወይም *መስፍ* ነው) በተሰነዘረው *መዶሻና* በሚጠብቀው *መስፍ* *መሃል* ያለ አየር አይሆንም? ሂደት አይሆንም? ወይ ጎዳና ብቻ? መነሻ መድረሻ የሌለው?

•

•

•

***መኖር አለመኖር፦እዚህ ላይ፣ነው ሚስጢሩ/ የዕድል፣ፈተና አለንጋ ሲወነጨፍ ወስፈንጥሩ:*** ፀናፅል አፓርትመንት ቢራ ስንጠጣ ቆየንና ራት ልንበላ የሆነ ሬስቶራንት ይዛኝ ሄድን:: ትርምሱ ከአውሮፓ ይበልጣል::

---

[51] መፍጠር (Create)

[52] እንደዛ የመሰለ (Something like that)

[53] ግብረሰዶም(Lesbian)

[54] መጥፎ አመት......ምን መጥፎ አመቶች (I had bad year.......years)

[55] እግዚአብሄርዬ (My God)

ለምን ይተራመሳል? እዚህና እዛ ተቀመጥን:: ቤቱ የድሮ ይመስላል:: የድሮ ዘፈን ይዘፈናል:: ዶን ማክሊይን መሰለኝ:: በስተቀኜ ትልቅ ማስታወቂያ የተለጣጠፈበት በር የመሰለ ቦርድ አለ:: ከተቀመጥኩበት፣ የመላጣ ሰው ፎቶ፣ ከመላጣው ሰው አናት ላይ በእንግሊዘኛ ፊደላት ሼክስፔር ከግርጌው ደሞ *ሐምሌት* የሚል በአግድም የተፃፉ ፅሁፎች አያለሁ:: ገርማሚ ጠዋት ማታ በተለይ ሞቅ ሲለው የሚያነበንባት የፀጋዬ ገብረመድህን ግጥም ትዝ አለችኝ: *መኖር አለመኖር እዚህ ላይ ነው ሚስጢሩ/ የዕድል ፈተና አለንጋ ሲወነጨፍ ወስፈንጥሩ::* የቤቱ ቡና ቤትነት ይገናል ከሬስቶራንትነቱ:: ቀላል የትንባሆና የወይን መዐዛ አለው:: ወንበሮቹ በሙሉ የእንጨት ናቸው:: ብዙ ሰው ስለተገለገለባቸው ያብለጨልጫሉ:: ጠረጴዛዎቹ ጨርቅ አለበሱም:: በብርጭቆ ቂጥ እርጥበት የተሰሩ ቀለበቶች ጠለሉን ሸፍነውታል:: የአዲስአባው ትሪያኖን ትዝ አለኝ::

«ምን እያሰብክ ነው? ወይን ጠጣ» አለች

ወይንና ስፓጌቲ አዘዘች:: እኔም እንደ እሷ አዘዝኩ::

የገባኝ ዛሬ ብቻ አይደለም ድሮም እንደማላውቃት ነው:: የመጣሁት ከማላውቃት ወደ ማላውቃት ልጅ ነው:: ደሞም ወደ ማላውቀው አገር:: ትልቁ የጋራ እውቀታችን ሽሮሜዳ ነው:: አንዳንዴም ሲኒማ በአንድ መስመር ተቀምጠን:: ፊልም ላይ ተዋንያኖች ሲሳሳሙ ፊቷን ታዞር፣ አይኖቿን በእጆቿ ትጋርድ ነበር::

«ታውቂያለሽ......ቤቱ ትሪያኖንን አስታወሰኝ» አልኩዋት

«ትሪያኖን ትዝ አይለኝም:: አውሮራ ብትል አዎ:: ያውም ከአባቴ ጋር ካልሆነ አልሄድም ነበር እዛም» አለች አተኩራ እያየችኝ:: የተናገረችው የሚያሳድርብኝን ስሜት ለመፈተሽ መሰለኝ አተኩራ አየችኝ::

«ገረመህ?»

'ደነገጥኩ' ልላት አልፈለኩም::

«አታምንም አይደል? ያለ ቤተሰቦቼ የትም በራሴ መሄድ አይፈቀድልኝም:: እማማ-ማ ጉረኛ ናት:: ......አሁን......አይ አም አልሬዲ ድረንክ......አይ ካን ኖት ኢቨን ሲት......ማይ አስ ጀስት ዲስአፒርስ...... አይ ዱ ኖት ኖው ዌር......ጀስት ሜልትስ......አይ ፊል ፍሎቲንግ[56] ግልፅ እሆናለሁ»

---

[56] ከአሁኑ ሰክሬአለሁ:: መቀመጥ እንኳዋን ደክሞኛል:: ቂጤ የጠፋ ይመስለኛል:: የት እንደሆነ እንጃ:: ዝም ብሎ ቀልጧል:: የምንሳፈፍ ይመስለኛል:: (I am already

*ምን ልበል?* እሷ በፀጥታና በፍጥነት በላች:: እንዲህ በፍጥነት የምትበላላ እንደሆነ እንኳዋን አላውቅም:: ወይ ትዝ አይለኝም:: ወይ አሜሪካ ከመጣች በሁዋላ መፍጠን ለምዳለች:: ማታ አራት ሰአት ተኩል አልፎ ሁለታችንም ሞቅ ብሎን ከሬስቶራንቱ ወጣን:: አፓርትመንቷ እስክንደርስ እጅዋን ያዝኩዋት:: በትክክል ስለ ፍቅር አላውቅም:: ስለ ፍቅር ለማወቅ በትክክል ከተፈቃሪው ጋር ትክክለኛ ስሜት መለዋወጥ ያስፈልጋል:: ቅን በቅን:: እንዴት ነው መውደዴን የማውቀው? መውደዴንስ? እጅዋን የያዝኩዋት የተናገረችው ነገር ስቦኝ ነው ወይስ ልጠጋት ፈልጌ ነው?

*መኝታ ቤቷን ለእኔ ለቃለች::*

*ያን ማታ መተኛት* አቅቶኝ ስገላበጥ አደርኩ:: ስንቶቹ በሆዳቸው ማፍቀራቸውን ይዘው ሳያወሩት ሳይነካኩ ተለያይተዋል? እየተብሰለሰሉ፣ እየተማደረደሩ፣ እያፈሩና እየፈሩ በወግ አጥባቂ ባህል ታስረው:: ይሄን የማይታይ ግጭት ዕድሜ ሊሰብረው ሲል ከመሃል የተሰነቀረው ፖለቲካ ነው:: ብዙ ወጣት የተጠለፈው ልክ እዚህ ፍቺ ያልተገኘለት የስሜት ነጥብ ላይ ከሆነስ? የተመኘው ግን ያላገኘው ፍቅሩን ለሚያቅፈው ድርጅት የሰጠው? ፖለቲከኞች በሽብር እንደተጠሩፉ ፀናዕልም እኔ ላይ ሽብር ወስዳለች:: አገርህን ትተህ *እዚህ* ና ስትለኝ የሽብሩ አንዱ ጎኑ አይሆንም? የተባረኪ ስራ ሽብር አይደለም? የቀለሙ አይነት አያጣላም::

•

•

•

*?????????:* ጠዋት ከፉቶኗ ተነስታ ወዲያ ወዲህ ትላለች::

«ደህና አደርሽ?»

*«ሃይ»*

እንደወጣሁላት፣ ወደ ነበርኩበት መኝታ ቤት ገብታ ጂንስ ሱሪዋን ለብሳ ተመልሳ መጣች:: ዝምታዋ ኩርፊያ ይመስላል:: ***ማድረግ*** ነበረብኝ? ወደ ማድቤት አለፈች::

«ስማሽ ፂ»

ቀና ብላ አየችኝ:: አንድ የድሬድ ሉክ ዘለላ ከፊቷ ላይ በቀስታ መለስ አድርጋ አተኩራ አየችኝ:: ከንፈሮቿ ደርቀዋል::

---

drunk. I can not even sit. My ass just disappears......I do not know where. Just melts. I feel floating...)

«ተባረኪ. አትወደኝም»

ውሃ በጀበና እየሞላች:

«አውቃለሁ» አለች

«ታውቂያለሽ?» አልኩ በመገረም

«እ ያ[57]......መሰላት እንጂ.»

«እንዴት አወቅሽ?»

«ኢቭሪ ገርል ላቭድ ዩ:: ዜን ሺ. ላቭድ ዩ:: ኖት ኮምፕሊኬትድ::[58] አንተን ሳይህ ድንገት ካየችኝ ትገላምጠኝ ነበር:: እፈራታለሁ ደሞ:: በትንሹ ጉዳይ ሁሉ ነገር ነገር ይላታል:: ዌን ኢቨር ዩ ተችድ ሚ ኢንአፕሮፕሪዬትሊ ዲድ አይ ሰይ ኖ[59]

«እም......ኖ»

*ከልክለሽኛል* ልላት አስቤ ተውኩት:: ረስታ ነው ወይስ ሆን ብላ እየዋሸች ነው? 'አላስታውስም' ልላት አልፈልግም:: ከባድ ነገር ጀምራለች::

«ትወጃታለህ አሁንም?»

«አይመስለኝም»

«ኢፍ አይ ወንት ሲክስ ዜር አር መዓት ቦይስ ሁ አር ሬዲ ቱ ስክሩው ሚ ዘ ካች ኢዝ አይ ላቭድ ዩ ሲንስ አይ ወዝ ቴን አን ቢሊቭብል አደለ?????????? ግን ይሆናል አይ ኔቨር ላቭድ አፍተር ዛት አይ ሃቭ ቱ ጎ አይ ቶክድ ቱ ማች[60]

---

[57] እምን

[58] ብዙ ልጃገረዶች ይወዱህ ነበር:: ከዛ እሷ ወደደችህ:: የተወሳሰበ አይደለም(every girl loved you. Then she loved you. Not complicated)

[59] (ያልሆነ ቦታ ስትነካኝ የከለከልኩህ ጊዜ አለ? (when ever you touched me inappropriately did I say no?)

[60] ወሲብ ብፈልግ መዓት ልጆች ሊያደርጉኝ ይፈልጋሉ:: ግን አስር አመቴ ከነበረ ጀምሮ አንተን ነው የወደድኩት:: አይታመንም አደለ? ግን ይሆናል:: ከዛ በኋላ ሌላ አልወደድኩም...... ልሂድ፣ ብዙ አወራሁ

(if I want sex there are መዓት boys who are ready to screw me....the catch is I loved you since I was 10............unbelievable አደለ? ግን ይሆናል I never loved after that.........have to go. I talked too much)

እደግመዋለሁ፡ ዓ. ከስምንት አመት በፊት የማውቃት ልጅ አይደለችም።

ወደ ማድቤት እያየች፡

«ሻይ ጥጄአለሁ ሲደርስ ጠጣ። ሶስት ሰአት ላይ እመጣለሁ። ቁልፍ ኮፒ እስከናሰራ አትጥፋብኝ። የስራ ቦታዬን ስልክ ቁጥር እዛ ጋ ትቼልሃለሁ (በአመልካች ጣትዋ ስልክ የተቀመጠበት ጠረጴዛ እያሳየች)። እኬ? ከፈለክ ናና ከምሰራበት ውሰደኝ። አብረን ብንመጣ ደስ ይለኛል፣ ደውልልኝ» ጃኬቷን ለብሳ ወደ በሩ በፍጥነት ሄደች። ቀና ብላ ልታየኝ አልፈለገችም። በር ሲዘጋ በእርጅና የዘቀጠ አንዱ ሶፋ ላይ ከቆሚ ተቀመጥኩ......በግራ በኩል ግድግዳ ላይ ትልቅ የቫዮሊን ፎቶ አለ። ከጎኑ del gesa ይላል። እሱ ላይ ያለምንም አላማ ሳፈጥ ቆየሁ። ደሞ የባ ከአፓርትመንት አወጣጥዋ ላይ። በር አዘጋግዋ ላይ። ለመጨረሻ ያየሁት ግራ ጉንጯ ላይ። አገጭዋን የሚያከው የአሊጌተር ሸሚዝ ኮሌታዋ ላይ። እዛ ማድቤት መጤስ የጀመረው ጀበና ጎን ያለ እውስጡ ያልተለኮሰ ሰንደል ያለበት ሰማያዊ ብርሌ ላይ። በቀስታ(?) ዘግታው ስትሄድ በሩ ጀርባ ላይ ያለው እስከ አሁን በቀስታ የሚንቃነቀው የዪንና የያንግ ጥልፍ ያለበት የቀርከሃ መጋረጃ ላይ። ማስታወሻ የምትለጥፍበት የቡሽ ሰሌዳ ላይ። ምን አለ እዛ? በቀይ como esta todo?[61] የሚል በጥቁር የወረቀት እሪባን ላይ ተፅፎ ተለጥፏል። ምን ማሰብ ነበረብኝ? ምን? ፊቴን በእጆቼ መሃል ቀበርኩና ብዙ ቆየሁ። ምን እንደማስብ አላውቅም። ብዙ የተዘባረቀ ነገር......የሻይው ጀበና ሲያፏዋጭብኝ ነቃሁ።

•

•

•

ሌሊ፡ ነገን እንደ ወራሪ ጀርም ብጠረጥረው የሚገርመው ይኖራል? ዛሬን እንደ ቫይረስ ብጠረጥረው የሚደንቀው ይኖራል? ትናንትንም። የኖርኩት ሕይወት የሌላ ሰው ሕይወት መሆኑን ማወቄ ድብርት ለቀቀብኝ። የእውነት ቂል የሆንኩ መሰለኝ። የሆነ ግድግዳ ላይ፣ መንገድ ላይ የተንጠለጠለ የሽቀጥ ማስታወቂያ።

ፀናፅል ድሮ የምታውቀኝ ልጅ አይደለሁም። ሁለመናዬ ተለውጧል። የሆነ ጉም ከቦኝ የሚሄድ ይመስለኛል። ጭማቂዬ በአጭር ጊዜ በዕድሜና በኑሮ እንደ ከረመ ጠላ ኮምጥጧል። እስዋ ስትወደኝ የነበርኩት ዓላዛርና አሁን አንድ አይደለሁም። ለእሷ እንዴት ሁለት አልሆንም? የድሮውና የአሁኑ። ይሄ የአሁኑን እንዴት አታየውም? 'ፍቅር ዕውር ነው' ሳይሆን

[61] እንዴት ነው ሁሉ ነገር (ስፓኒሽ)

'ፍቅር አያረጅም' ቢሉት ትክክል ነው:: ፖለቲካችን የሰራው ወንጀል መግደል፣ መሳደድና ማሳደድ አይደለም:: ቢገደል ቢሳደድ ያለበት ሲብላላበት ነው:: መገናኘት የማይገባቸውን ሰዎች በአንድ አስሮአቸዋል:: አብረው መሆን ያለባቸውን ነጣጥሉአል::

ማታ ሁለት ሰአት ላይ የምትሰራበት አካባቢ ሄጄ ወዲያ ወዲህ እያልኩ ግንብና ትርምስ፣ መኪናና ተላላፊ፣ ሃሳቢንና ሃሳቧን እና ስማዩን: ስማዩ ስማያዊ ነው፣ እንደ ጆርጅ ቡሽ አይኖች......በደፈረሰ የአመልማሎ ንጣፍ......ጥየራዎች ስማዩን ቢታቸው ያደረጉበት፣ እኔም ፀናዕልም ምናልባት አለባልታ ጠጥቶ ባደገ አጻናቂ ሕልማችን የምንወለውለውን እያለሁ:: ወደ አፈጠጠ፣ ማምለጫ ወደ ሚያሳጣ እውነት እንዲህ ስቀርብ ስንተኛዬ ነው? ከተለያየ አቅጣጫ ተመሳሳይ ነፋስ የነፈሰብን፣ የተለያየ ብልታችን ጋ የተመታን የዘመኑ ልጆች::

አጠገቤ የለማዳ እንስሳት ሱቅ አለ:: ከመስኮት ጀርባ በመስታወት ሳጥን እንሽላሊት፣ እባብ፣ ጊኒ አሳማዎች፣ እባቦችና ውሃ በተሞላ የብርጭቆ ታኒካ ደሞ ደቃቃ ኢሲዎች አሉ:: ኢሲ እወድ ነበር:: በቅርበት ላያቸው ሱቁ ገባሁ:: ነጭ ባርኔጣ ያደረገች ደረተ ሰፊ ልጅ ሃይ! አለችኝ:: ሃይዋን በደማቅ ሃይ!! መልሼ ወደ ቀኝ ታጠፍኩና ኢሲዎቹ ያሉበት ጋ ሄድኩ:: በፎቶና በሲኒማ ካልሆነ የሚዋኝ ኢሲ አይቼ አላውቅም:: አንድ አስር የሚሆኑ አውራጣት የሚያካክሉ ኢሲዎች በተፈጥሮ የሚኖሩበት አይነት መልክአምድር በጠባብ ቦታ ተቀንብቦላቸው ጉራጅ እንጨት ላይና ድንጋዮች ላይ ተረባርበው ያናውዛሉ:: ሲዋኙ ለማየት ቆሜ ጠበቅሁ:: እዛው አሉበት ይላወሳሉ:: ሲስለቸኝና ዟ ደሞ ፊልጋ እንዳታጣኝ ከሱቁ ስወጣ ዞር ብዬ አየሁ:: ባለ ሱቋ ቦታዋ የለችም:: በር ስከፍት በሌላ አቅጣጫ ከሁዋላዬ መጣች:: በድንገት ብቅ አባባሏ ብደናገጥም (የእሷን አላውቅም) ፈገግ አልኩ:: በኑ ከሁዋላዬ ሊዘጋ ሲል: 'ሲ ዩ' ስትል ሰማሁዋት:: ቀዝቃዛ አየር ሲነካኝ እዝራና ያ የእንጦጦ ማርያም ኢሲ ትዝ አሉኝ:: ከዚህ ጋርም ቁልቁለት......ገመድ ......ቄስ ታዚና......የተሰበሰቡ ሰዎች......አሮጌ ዚታዎ......የእንጦጦ ነጫጭና አረንጉዋዴ ዛፎች......ይሄን የእንስሳት ቤት ጉብኝት ከተራ አጋጣሚ አላቅቄ ሌላ ፍቺ ልሰጠው ጣርኩ:: ከትውስታ በላይ ምንም አላጋጠመኝም:: የእዝራ ኢሲ ግልቢያ ትዝ ብሎኝ ለራሴ ሳቅሁ:: ለፀናዕል ያን ጀብድ ልነግራት አቀድኩ:: ፂ ጠፍቼባት ስትገላመጥ አየሁዋት:: ከሁዋላዋ ነበርኩ:: የሚቁነጠነጥ ሁኔታዋ አማረኝ:: ሁኔታዋን አብራርቼ ላቆላምጣት ዳዳኝ:: ገፅዋ ላይ ያለው የጠፋ ፍለጋ የሚማትረው ገፅዋ ገና አስራ ስምንት አመቱ ይመስላል:: የሆነች ቢቢ:: እሷን እዚህ እያየሁ እንዴት የአፍረቷን ፀጉር ሹሩባ የምትሰራ ቴቢ ትዝ ልትለኝ ትችላለች? ባቆላምጣት ደሞ ችኩልነት መሰለኝ:: እንደ ኢሲዎቹ እየሰራኝ እሆን ከሜዳ ወጥቼ የሚያምር የውሃ ታንኳ ውስጥ የገባሁት? ነፃነቴ የት ነው?

ዒን ሳልጠራት ከሁዋላዋ ቆሜ ለአፍታ በአይኖቼ ላንቃ በዝምታ ላስኩዋት:: እንዴት ነው የማታምር፣ እስከዚህም ናት የምትባል ልጅ ገፅዋ ጉጉት ለብሶ ስትቁነጠነጥ ልብ የምትበላው? ጉጉትና ኪኒቲክስ ከመቼ ወዲህ አምባገነን ሆኑ? ምን ነበር ልነግራት የነበረው? የምነግራትን ረሳሁ::

•

•

•

ስራዋን ጨርሳ ስትወጣ ገና በር ስትከፍት አየችኝ:: እዛ ተደንቅሬአለሁዋ! ስታየኝ ፈርጠም አለች:: ሹራብዋን እየለበሰች መጣች:: የጀርባ ቦርሳዋን ተቀበልኩና በትከሻዬ ላይ አንጠለጠልኩት::

«ያምርብኛል?» አልኩዋት

«ያምርብሃል፣ ግን የሴት ነው ሂሂሂ»

ክንዴን ይዛ ጎንበስ ቀና እያለች ሳቀች::

«ምነው አየኸኝ?»

«ማየት ተከለከልኩ?»

«ሂሂሂሂ……አጎቴ ትምህርት ቤት ድረስ መጥቶ ሰላም ብሎኝ ሄደ:: አጎቴ ስልህ የአባቴ የቅርብ ጓደኛ ማለቴ ነው:: ካሳ ይባላል:: አንዳንዴ ቤቴ ብቅ ይላል:: ትንሽ ዶላር ሰጠኝ:: ላዝናናህ? ሂሂ:: አስተዋውቅሃለሁ:: ግን ፖለቲካ ያበዛል:: አኬ? ሻለቃ ምናምን ነው:: የሚያሳዝን ታሪክ አለው:: ስለሚያሳዝነኝ ነው የምወደው መሰለኝ:: የሐረር ሰው ነው:: ምን መሰለህ? ሰብለ የምትባል የሃብታም ፊውዳል ልጅ ይወዳል:: ማለቴ ይዋደዳሉ:: እንዳይጋቡ እንቅፋት ሲሆኑባቸው ልጅቷ ተበሳጭታ እዚህ ለትምህርት ትመጣለች:: አብዮት ይነሳል:: እሱ ደርግ ሆነ:: 120ዎቹ ምናምን የሚባሉ የሉም:: ከዛ ለስራ ጉዳይ ዩጎዝላቪያ ሲላክ ትቶ እዚህ እሷ ጋ መጣ:: ከሁለት አመት በፊት ማታ ላይ አምሽታ ከስራ ስትወጣ ጋንጎች ይደበድቡና ይዘርፉና ይጎዷታል:: ከወገቧ በታች ታነክሳለች አሁን:: አንዲት ትንሽ ልጅ አለቻቸው:: ሻለቃ አሁንም አብሯት አለ:: ኮርኒር ስቶር ስለምትሰራ አንዳንዴ ልጃቸውን ቤቢሲት አደርጋለሁ:: በጣም ያሳዝናል:: ላብ እንደዛ ሲሆን ደስ ይላል ደሞ ያሳዝናል:: አደለ?»

ታሪኩን ከዚህ በፊት የሰማሁት መሰለኝ::

«ያሳዝናል»

«ታውቀው ይሆናል:: ፍላሚንጎ አካባቢ ነበር የሚኖረው:: አባይነህን ታውቀዋለህ:: የተባረኪ እናት ጓደኛ? ከእሱ ጋር ይቀራረባሉ»

«ምናልባት በዐይን»

«አባይነህና ትደነቂያለሽ የሚጋቡ ይመስለኝ ነበር»

«ይወዳታል ግን 'ትነጫነጫለች' ይላታል ሂሂሂ»

«ይታይሽ ሚስቱ ከሆነች ገደለችው ማለት ነው:: ለመሆኑ ነጭናጫ ነሽ?»

«በዝምታዬ:: አይ አም ቱ ኩዋይት ዊዝ ዩ[62]»

«ቤት ደብዳቤ መፃፍ እፈልጋለሁ»

«አባትህን እስከአሁን ተቀይመኸዋል?»

«ማን ተቀይሜአለሁ አለ?»

«ብርሃን ራሱ ሲያወራ ሰምቼአለሁ:: የሆነ የልደት ጊዜ ምናምን ብቻ ኢንፊደሊቲ[63] አይተህ»

«አባቴ አወራ? ረስቼዋለሁ»

«ምን ትረሳለህ:: አይመስለኝም:: ሁኔታው መጠርጠርን፣ አለማመንን በልቦናህ ከቶ ይሄዳል:: ፐሎቱ[64] ይጠፋና መረቁ በልብህ ይቀራል:: ያ ልምድ ሜታሞርፎስ[65] አድርጎ ሃሳብ ይሆናል:: የራስህ ሃሳብ ይመስልሃል፣ የመጠርጠር ፍልስፍና:: ለምን ፒዛ በልተን አንሄድም? እዚህ አንድ ቦታ አለ:: ደክሞኛል:: ራት መስራት አልችልም:: ደሞ እዛ ስለዋልኩ ማድቤት ማየት እንዴት እንደጠላሁ:: ደሞ ያንተ ፓስታ ሰልችቶኛል:: ሂሂሂ»

«እኬ»

«ስትነግረኝ ዕፈህለት አታውቅም:: ስንፍና አይደለም»

«እም»

«በጣም ይወድሃል:: ዳድህ[66]......ተወው በቃ ሌላ ቀን እናወራለን»

እውስጥ ገባንና እንድቀመጥ ቦታ ጠቁማኝ ፒዛውን ለማምጣት ሄደች:: መስኮት ጋ ነኝ:: የጎዳናው ከፊል ጫጫታ በር በተዘጋና በተከፈተ ቁጥር ጆሮባዬ ላይ ይወድቃል:: ለምን ስለአባቴ ብዙ እንዳወራች አልገባኝም:: እራት ነው ምንድነው? አሜሪካ ቀላል ይመስላል:: አሜሪካ ከባድ ይመስላል:: አሜሪካ ሁሉን ይመስላል:: ግድግዳው የሚነበብ ነው::

---

[62] (ብዙ ዝም እላለሁ አንተ ጋ ሲሆን አይደለም" (I am too quite......not with you)

[63] ክህደት (Infidelity)

[64] ታሪኩ

[65] ተለውጦ

[66] አባትህ

የግድግዳው ሽክላና ሰብነበረድ የገንዘብ ተስፋ ይሰጣል። የፍቅር ተስፋ ይሰጣል። ተስፋውን አነባለሁ።

ፀናዕል የምንበላውን በፕላስቲክ ትሪ ላይ አምጥታ ከእኔ ትይዩ ተቀመጠች። ከአንገቷ ላይ እርግብግቢቷ ውስጥ ላለመስመጥ የምትለፋ ደቃቃ የብር አንክ[67] አለች። የእኔን የፒሳ ሽብልቅ ወደ ፊቴ ገፋች፣ ቀጥሎ በክርታስ ዋንጫ ያለውን ኮካ ገፋች። ሳል ሳለችና:

«ሳልጠይቅህ፣ ሻለቃ......ካሳ እንደታሰርክ ነግሮኝ ነበር እውነት ነው?»

«ጠረጠርሽው?» ፒሳውን አነሳሁና መሃል ለመሃል በቁሙ አጥፌ የሾለ ጫፉን በአፌ አስገባሁ

«ከአንተ መስማት አለብኝ። ፖለቲከኛ ስለሆነ ሊያዳላ ይችላል......»

«ታስሬአለሁ። ለሳምንት ነው። ለብቻዬ......»

ለአፍታ የታሰርኩበት ቦታ ትዝ አለኝ። በትክክል ትዝ ያለኝ ግን ዛሬ በተለየ መልክ ጎልቶ ነው። ያን ጊዜ አይኖቼ በጨርቅ በመጋረዳቸውና ጨለማ በመሆኑ ያላየሁት። ቀድሞ ያላወቅሁት የማውቀው ያህል ተሰማኝ። ጎልቶ የታየኝ በሩ ነው። ያን ቀን ያየሁዋቸው ግን ችላ ያልኩዋቸው ወይም ያላተኮርኩባቸው ዝርዝሮቹ ተጠረቃቅመው ተከሰቱ። ፀናዕል አተኮረች:

«ምነው? ላሳስብህ አይደለም»

«የሆነ ነገር ትዝ ብሎኝ ነው» አልኩና የያዝኩትን ቁራጭ ፒሳ ትሪው ላይ መለስኩ።

«ምን?»

«የታሰርኩበትን ቦታ»

«አልገባኝም»

«የታሰርኩት የት ቦታ እንደሆነ ታውቂያለሽ? እናኑ ቤት። የተወረሰ ቤት ነበራት። የሆነ የጣልያን ቤት»

«እና ያኔ አላወቅኸውም?» አለች በመገረም አይነት

«አሁን ማወቄ ነው። ጨለማ ነበር። ደሞ ፈርቼአለሁ፣ ደንግጬአለሁ። እንጂ። መታጠቢያ ቤቱ ውስጥ ነበርኩ። ትዝ የሚለኝ ቆሻሻነቱ ነው። መስኮቱ የብረት ፍርግርግ ገብቶለታል። ባኞ ነበረው። ባኞው ተነቅሏል። የታሰርኩበት ክፍል በር አሁን ትዝ አለኝ፣ ግን በሩን የማውቀው ሁልጊዜ ተከፍቶ ነው። ማለት በከፊል ነበር የማውቀው።

[67] የጥንት ግብፃውያን መስቀል

የዕቃ ቤት ነበር:: ከሰራተኛዋ መኝታ ክፍል ፊት ለፊት:: በሩን ተዘግቶ አይቼው አላውቀውም:: እናቱን......ደርግ ራሴ ቤት ውስጥ ነው ያሰረኝ»

«ይገርማል:: በቃ እርሳው»

«የእናናን ቤት ባልረሳው ኖሮ የታሰርኩበትን ቤት አውቅ አልነበር:: ቤቷን የረሳሁት ገና ሳልታሰር ነው»

«ሃሃሃ አልፏል አሁን»

«ጂስስ:: ደደብ መሆኔ አልፏል? ከአለፈ በሁዋላ አንድን ነገር መረዳት የደደብነትን ጊዜ ማስታወስም ይመስላል:: ደደብነት ብዙ ጊዜ መሸነፊያውን ይሸፍናል:: እያስታወሱ መርሳት:: አለ አይደለ የመሸፋፈን ብልጠት»

«እህም:: አሪፍ ፔፔሮኒ ነው»

«ትሰሚኛለሽ?»

«አልፏል!»

«ምንም አላለፈም:: ድንቁርናዬን ባወቅሁ ቁጥር ያላለፉ ነገሮች ትዝ ይሉኛል:: ግን መቼ ነው ልክ መሆኔን የማውቀው?»

አተኩራ አየችኝና ፒሳዋን አንቀርፋ ይዛ:

«ልብህን ስማው:: ለእኔ ቀላል ነው:: በቃ አልፏል:: ቀሽም ስለሆንን አይደለም:: ይመስለኛል:: በቃ ይሆናል:: ብቻ ልብህ ከሚነግርህ አትጣላ:: ማለት ከራስህ አትጣላ:: ደሞ ራስህን አላሰርክም:: አይደለ? በሰላም ጊዜና ሰላም ባልሆነ ጊዜ የዐይንና የልቦና ችሎታ ይለያያል:: ያ ያንተ ስህተት አይደለም:: ብዙ ጊዜ የግለሰቦች ስህተት አይደለም:: ፖለቲካ እየጠላህ ፖለቲካ አታስታውስ:: አሁን ራታችንን እንብላና እንረጋጋ:: ወክ እናደርጋለን:: ጥሩ ፓርክ አለ:: ምን ይመስልሃል? ቺዙ በረደብህ ብላ»

ስለመታሰሬ አንስታ ነገሩ ወደ አልጠበቀችው አቅጣጫ ቢሄድባት ማባበሏ ነው: ፖለቲከኛ ሳልሆን ፖለቲካ ሲያሸኝ አስገራሚ ነው:: ሳር አይደለሁም ግን ለምን በሬው ይበላኛል? የጀመርኩትን ፒሳ አነሳሁ:: ምንም ያልያዘ እጄን ምንም ባልያዘ እጅዋ በቀስታ ዳበሰችው:: *ያለፈቃዴ ፖለቲካ ውስጥ ነኝ እንዴ? ሕይወቴ ውስጥ ታሪክ የገነባው ፖለቲካ እንድናገር የሚገፋፋኝ የሆነ ግዴታ አለ? የት ሸሸሁ? የማን ተረት ነው?* ዒ የእጄን ጀርባ በትኩረት ትዳብሳለች::

•

•

•

ለአራት ስፓጌቲ ሰርቼ እየጠበቅሁዋት ነው:: የበር ቁልፍ ሲጮህ ደስ አለኝ:: መደሰቴን መቀበል ባልፈልግም:: ቶሎ ደስ እንዲለኝ

አልፈለኩም? እንደዛ የሚያምር የቁልፍ ኳኳታ ከዛ በፊት የሰማሁ አይመስለኝም:: የክራር ጨዋታ ማለት ነው:: መቼ እለት ትክክል ከተናገረች በሁዋላ አሳሰባኛለች: ሳይጠበቅ እንደፈነዳ እሳት ገሞራ:: ሁልጊዜ ጠዋት አርፍጄ ስለምተኛ ግን አላገኛትም::

«ሃይ! ደህና ዋልክ? ምን ይሸተኛል?»

«ፓስታ»

ከተቀመጥኩበት ተነሳሁና ወደ ማድቤት ሄጄ ምግብ የመስራት ችሎታዬንና ጥርጣሬዬን ነገርኩዋት::

«ማሰብህ ነው፣ የቻልከውን ከሰራህ ምን ማድረግ ይቻላል:: ፎ ኖመለ የሆነ ኮሜዲ ሾው ትኬት አገኘሁ:: አንድ ጓደኛዬ ጋብዛናለች:: ኮሜድያኑ ሪቻርድ ፕራየር ነው:: ታውቀዋለህ?»

«አላውቀውም»

«ትንሽ ሰድ ሰድ ነገር ይናገራል:: ለእኔም ይከብደኛል:: ግን ፋኒ ነው:: አሽሊ የምላት ጓደኛዬ ጋብዛናለች:: ብዙ ጊዜ ስልክ የማወራት:: አይ አም ኢክሳይትድ[69]:: ትተዋወቃላችሁ»

ቦርሳዋን አስቀምጣ፣ ወደ ማድ ቤት አልፋ የሰራሁትን ፓስታ ያለ ሳልሳው አነሳችና አንድ ዘለላ በላች::

«አሪፍ ነው:: ታጥቤ መጣሁ:: የሚለበስ አለህ?»

«የምስራቅ ጀርመን ነው:: አይተሽዋል?»

«አጉል ጊዜ:: ፔይ ደይ[70] ነገ ነው:: በቃ ያለህን ለብሰህ እንሄዳለን:: ጆሊነትህን አልነጥቅህም:: ከነገ ወዲያ ኦፍ[71] ነኝ:: አሜሪካዊ የሚያደርግህን እንገዛለን:: አገርህ አሜሪካዊ መስለህ እዚህ የሰንጋ ተራ ልጅ አትመስልም:: ሃሃሃሃ:: አሽሊና ጓደኞቿ ኔትወርክ[72] አላቸው ይረዱናል......ስራ ለማግኘት ሂሂሂ:: የማያውቁት ሰው የለም፣ እከተር በል ኮንግረስ ማን:: እዚህ አገር ለስራ ኔትወርክ ኢምፖርታንት[73] ነው:: ትንሽ ችሎታ ጥሩ ኔትወርክ:: የዘመድ ስራ እንደማለት ነው:: ኦብጀክትስ ቼንጅ ዚይር ከለር ኖት ዚይር ኢሰንስ[74]

---

[68] ታውቃለህ? ( you know)

[69] ደስ ብሎኛል (I am excited)

[70] የደመወዝ ቀን

[71] ስራ የለኝም

[72] Network (የትውውቅ መረብ እንደማለት)

[73] አስፈላጊ ( important)

[74] ነገሮች ቀለማቸውን እንጂ ይዘታቸውን አይለውጡም(objects change their color not their essence)

«ከፍልስፍናው ቀንስ እናድርግና፣ ታጥበሽ እስክትመጪ አዘጋጅቼ እጠብቅሻለሁ»

ትከሻዬን እንደጨዋታ ገፍታኝ አለፈች:: በአምስት ደቂቃ ውስጥ ሰሃኖችንና ለእኔ ሰሸን እና፣ ለእሷ ውሃ አድርጌ ጠረጴዛ አዘጋጅቼ ግድግዳና ነጭ ፓስታ እያየሁ ጠበቅሁዋት:: በሃያ ደቂቃ ተጣጥባ ልብሷን ለውጣ ተመለሰች:: 'ሀ' አንገትጌ ያለው አረንጉዋዴ ሹራብ፣ ከጉልበቷ ከፍ ያለ ደብዛዛ አረንጉዋዴ ቀሚስ ለብሳለች:: ባዶ እግሯን ናት:: ለዐይኑ ቀለለችኝ:: ከላይ እስከታች አንድ ናት:: ሁለመናዋ ቀጥኖ የተሰራ ነው:: አጠገቤ ስትሆን ከእኔ ትጠር እንጂ ረዥም ትመስላለች:: *ምን ትመስላለች?*

«ሰላጣ መስልኩ አይደለ?» አለች ከት እያለች

«ያምራል» የሰላጣውን ነገር እንዳልሰማ አለፍኩት::

«ተው በእናትህ»

«እውነት»

*ጥንቅሽ ጥንቅሽ ነው የምትመስለው:: የተመለመለ::* ልነግራት አልፈለኩም:: እናና ትዝ አለችኝ:: ልቦናዬ በአሮጊቷ ናፍቆት ባከነ::

«ምን ታስባለህ? ለመናገር የፈለከው ነገር አለ»

*ስለምን ልንገራት? ስለ ጥንቅሹ? ስለ እናና?*

«ለአፍታ እናና ትዝ አለችኝ»

«እንዴት?»

«በቃ ዝም ብሎ»

«ደግ ሴት ነበሩ:: ትዝ ይለኛል አንዴ ሄደን:: ትንሽ ይነጫነጫሉ አይደል ሂሂ:: የሆነ እንትን በላን ሸንኮራ የመሰለ:: ስሙ ጠፋኝ ሸንኮራ አይደለም......»

«ጥንቅሽ»

«ታንክ ዩ[75]፦ ደሟ ፈልቶ ነበር ስለረሳሁት:: እእእእእ»

«አትጎጂም እዚህ አገር ብትረሺው»

«ለሜታፎር[76] ይሆናል»

«ለምን?» አልኩ

---

[75] አመሰግናለሁ ( thank you )

[76] ልዋጭ ( metaphor )

ሳትመልስልኝ ከመቀመጫዋ ተነሳች:: ሳልሳ ያልነካው ሃባ ፓስታ አፏ ላይ፣ ከንፈሮቿ መሃል ይንጀለጀላል::

ግራና ቀኝ ዞር እያለች: «አይ ሉክ ላይክ[77] ጥንቅሽ» አለች

«ያያያያ» አልኩ እየሳቅሁ:: በድፍረቷ ስለተደመኝኝ፣ በልቤ አፍሬአለሁ:: ንቅናቂዋን አቁማ:

«በደንብ አዘጋጅተሃል ራታችንን» አለችና እኔ ከመቀመጤ በፊት ወንበር ስባ እየተቀመጠች:

«አይ አም ስታርቪንግ[78] አሌክስ»

ሳልሳና ፓስታውን መደባለቅ ስትጀምር፣ ጌጥ ያልተደረገበት ገጋው የወጣ የማር ወለላ የመሰለ አንገቷ ላይ ከእኔ በስተቀኝ ሁለት ሳንቲሜትሮች ስፋትና ግማሽ ሳንቲሜትር ያህል እርዝመት ያለው ጠባሳ አየሁ::

«አትበላም?» አለች አንዴ ጎርሳ

እጄን ሰደድኩና ጠባሳውን እየዳበስኩ:

«ምንድነው?» አልኩ

«ልጅ እያለሁ......» አለች እተቀመጠችበት እንደመደነስ እያደረጋት

«ሽልማት አደረግሽው?»

«እውነት ዌን አይ ወዝ ፋይቭ[79] አካባቢ መሰለኝ እንጃ:: ትዝ ይልሃል ግቢያችን ውስጥ የነበረው የወይኑ ቦታ? እዛ ወይኑን ለመደገፊያ አልጋ ሲሰ'ራ እንጨት የሚፈልጥ ሰው ይመጣል:: እንጨት በቅርብ ሲፈለ'ጥ አይቼ አላውቅም:: እና ብርቅ ሆኖብኛል:: 'ዞር በይ' ቢሉኝ አልሰማሁም:: እሺ ብዬ እሄድና ተመልሼ እመጣለሁ»

«መጥረቢያ እንዳትይኝ»

«አይ አም ቴሊንግ ዩ[80]......ልነግርህ ነው:: የሰፈራችን ሰው ነው፣ ፈላጨ:: ስሙ ጠፋኝ......»

«ወንድወሰን መሆን አለበት»

«ያ ያ ሁለት ቤት ልጆች አሉት:: በመንገድ አየው ነበር:: ሁልጊዜ ቤታችን ማገዶ ያመጣ ነበር:: እሱ አላየኝም፣ እኔ ደረጃ ላይ ሆኜ አየዋለሁ:: ሲፈልጥ ሽራፊው ተፈናጥሮ አንገቴ ላይ ተሰካ:: ቆዳዬ ላይ

[77] እመስላለሁ (I look like)

[78] ብጣም እርቦኛል ( I am starving )

[79] ዕድሜዬ አምስት እያለ (when I was five)

[80] ልነግርህ ነው (I am telling you)

እንደዚህ ተንጠለጠለ:: አንዴ ብቻ ሙህኩ:: ከዛ ምን እንደተደረገልኝ ትዝ አይለኝም:: ቶሎ ዳነ:: ግን ጠባሳው ቀረ:: በመንገድ ሳየው እሱን እፈራው ነበር:: ሂሂሂ:: ትልቅ ልጁን ሳያት እንኳን መጥረቢያ የያዘች እየመሰለኝ እፈራት ነበር:: ያስጠላል?»

«አይ» አንገቷን በእጄ ይገፎ ቆየሁ::

በጉንጭዋ ዳበሰችኝና:

«ይጠብቁናል:: የሀበሻ ቀጠሮ ምናምን የለም:: ፖላይት[81] መሆን ጥሩ ነው:: ደሞ ከቲያትር ቤቱ ስንወጣ ልጆቹን መጋበዝ አለብን:: ትንሽ ሳንቲም እይዛለሁ:: ገንዘብ ለማውጣት ባንክ እንሰለፍ ይሆናል»

ቶሎ ቶሎ መብላት ጀመረች:: ጠባሳውን ቀልድ አስመሰለችው::

«ሪቻርድ ፕራየር ስድ ቀልድ ይቀልዳል» ቶሎ ቶሎ እየበላች

«በጣም እርቦሻል የእውነት»

«በጣም:: ከክላስ እንደወጣሁ አንድ የፒነት ሳንድዊች[82] በላሁ:: ከዛ ጥናት ላይ ነበርኩ:: እምልህ፣ የአንድ ጓደኛዬ ወንድም አለ:: ይመጣ ይሆናል:: እንጃ:: ከእኔ ጋር ግንኙነት ይፈልጋል:: ምንም ጉዳይ የለንም:: ሌላ እንዳይመስልህ»

«አምንሻለሁ»

«የማይሆን ነገር ይናገራል:: ስለ ሴክስ[83] ምናምን»

«ይገባኛል»

ቀና ብላ አይታ: «አልገባህም» አለች

ዝም አልኩ:: ፓስታዬን እየጠቀለልኩ ጠበቅሁዋት:: አላየችም::

«ወንድ የሚባል አላውቅም» አለችኝ ቀና ብዬ እንዳያት ትጠብቀኝ ነበር:: ቀና ብዬ አየሁዋት::

«እዎ:: አን ቢሊቨብል[84]......እ»

«እእእ አዎ...ደስ የምትይ ልጅ ነሽ» ምን ልበል? ምን ይባላል?

አፏን በናፕኪን ጠረገች:: ችኩል ችኩል ያለች መሰለኝ::

«እም እሱን አላውቅም»

---

[81] ጨዋ (Polite)

[82] የለውዝ ቅቤ ሳንድዊች (peanut sandwich)

[83] ወሲብ( sex)

[84] አይታመንም (unbelievable)

«ኦኬ»

«ኦኬ አይደለም። አይታመንም። ሽማግሊት ሆኜአለሁ»

«አሮጊት»

«ሂሂ አሮጊት። አማርኛ ትንሽ እየጠፋኝ ነው መሰለኝ። አንድ ጓደኛዬ ነበረች ለንደን 'ሽማግሊት' ማለት አስለመደችኝ። በቃ ልማዴ ሆነ። በጣም ጉራዬን የምነፋበት ቃል ምንድነው መሰለህ? 'መታየር'። 'መታየር' ሲል 'አየር ያለበት፣ የገባው' ምናምን ይመስለኝ ነበር። 'መደባለቅ' ማለት ነው። ሚክስ ሲያደርግ። ሂሂ። ምናልባት አንድ ነገር ሲደባለቅ አለ አደለ ስታደባልቅ ያው አየር ይገባው የለ? እንርሳው ይሄንን። ብቻ የምልህ......'አላውቅም የዚህ አይነት ነገር' ስላቸው የሚያምነኝ የለም። ሊያዩህ ይፈልጋሉ። 'ለዚህ ልጅ ነው ወይ ያስቀመጥሽው?' ምናምን ሊሉ»

ፓስታዋን በሹካዋ ቆፈር ቆፈር አደረገች። ከንፈሮቿ በስጎው ረጥበዋል። አናቷን ይገፔ ጎትቼ ልስማት ፈለግኩ። ሹካዋን ወርውራ ተነሳች።

«ይቅርታ አስቀየምኩሽ»

«ምን አስቀየምከኝ?......እየቆየ ሲሄድ በአንተ ሳይሆን በመፈጠርህ። ማለት በእግዚአብሄር። ባለጌ ስለሆኑ ሊጠይቁኝ ይችላሉ። አደለ 'ያን ነገር አደረግሽ ወይ?' ምናምን»

ወዲያ ወዲህ እያለች ጫማ እየለወጠች። የት ነበረች በፊት? ስትገለጥ አታልቅም።

«ገረመህ?»

«ምኑ?»

«ግልፅ መሆኔ?»

«አዎ»

«አለመሆኔ ጎዳኝ። ፈሪነቴ ጎዳኝ። እዚህ አገር የተማርኩት ይመስልሃል? አይደለም» ወገቧን ይዛ ፊት ለፊቴ ቆመች።

«አገራችን እያለሁ እኔን የመሰሉ ወጣቶች፣ ትክክልም ይሁን አይሁን ለአላማቸው ሲሞቱ ሳይ......ለብቻዬ ከመሰቃየት ለአንተ መጥቼ ብነገርህ ቀላል መሆኑ ገባኝ። አንድ ቀን ቤትህ መጣሁ። እትዬ ሮዛ ነበሩ። እንደምፈልግህ ነገርኳቸው። 'የለም' አሉኝ። ከዛ ተመለስኩ ወደ ቤት። እንደገና መጥቼ መፈለግ ፈራሁ። እትዬ ሮዛ እንዳልነገሩህ አውቃለሁ። መምጣቴን ቢነግሩህም ግድ አይሰጥህም። ልስናበትህ

እንኩዋን ፈራሁ:: ከዛ አባቴ ጄኔቫ መጣ:: አይ አም ስቱፕድ[85]:: አዲስአባን ስንለቅ አለቀስኩ:: በደደብነቴ አዝኜ ነው:: *የሚያጋድል ነገር መስራት ሲደፍሩ እኔ ሞት የሌለበትን ነገር ልፍራ?* ብዬ ነው:: ራሴ አስጠላኝ:: ከዛ ለራሴ ማልኩ:: የፈለኩትን ማግኘት አለብኝ:: ከሕይወቴ ነው የተማርኩት:: አንዳንድ ሰዎች ቤተሰቦቼም እዚህ የለመድኩ ይመስላቸዋል:: 'አሜሪካ መጥታ ተለወጠች':: አገሬ ነው የጀመርኩት እንደዛ አይነት ነገር:: ስራ ላይ አላዋልኩትም እንጂ:: ከዛ ከአገሬ እዚህ ይገፄው የመጣሁት ጥሩ ነገር ራሴ ደካማነት ላይ ቂም መያዜን ነው:: ራሴን ይቅር አልለውም»

አርዕስት መለወጥ ፈለኩ:: ደጋግሜ ቂልነቴን ቀሽምነቴን ማየትና መስማት ባለመፈለጌ መሰለኝ:: ግን እንዴት ሊገባኝ ይችላል? አሳው ባሕር ውስጥ እያለ ባሕር ውስጥ እንዳለ ያውቃል? ወደ አሸዋው ሲወረወር ወይ ሲጠመድ ይሆናል አሳነቱን የሚያውቀው:: እንዲህ በማሰብ ራሴን ትንሽ አታለልኩ::

«አትበይም?»

«በቃኝ፣ ሌላ ጊዜ ስትሰራ ጨው ቀንስ»

«ሃሃሃሃ»

የእንገት ጌጥ፣ አምባር፣ ቀለበት፣ ስካርፍ ምናምን ከየቦታው እየለቃቀመች ስታደርግ ቶሎ ቶሎ ፓስታዬን በላሁ::

«የበላንበትን ስንመጣ እናጥበዋለን» አለች እኔን ሳታይ::

በሩብ ሰአት ውስጥ እጅ ለእጅ ተያይዘን ከአፓርትመንቱ ወጣን:: ለገንዘብ ባንክ ማሺን ጋ ትንሽ ተሰልፈን በባቡርና በእግር ከአንድ ሰአት ተኩል በሁዋላ ደረስን:: ከሌሎች ሰዎች ጋር እየተጋፋን፣ አዳራሹ ሳንገባ በፊት ዞር ብላ:

«እንደምትወደኝ አውቃለሁ» አለች ከንፈሮቿ እየተንቀጠቀጡ:: ይሄን የልቤን ነገር ባለመናገሬ ልትቆጣኝ መሰለኝ:: አፌ የሚናገረው ጠፍቶት ተርበተበተ::

«ሃው?[86] ስራ ቦታ ልገባ ስል፣ ከሁዋላዬ ስታየኝ ነበር:: ፊትህ ይናገራል:: ዐይንህ ይናገራል:: እሱን ፊትህን እሱን አስተያየትህን ሳስብ ነው የዋልኩት:: ደስ ብሎኛል:: የተባረኪ አይነት አይደለሁም:: ግን ወደኸኛል ሂሂ»

---

[85] ደደብ ነኝ (I am stupid)

[86] እንዴት? (How)

«ፖለቲካና ኮሬንቲ እንጂ ፍቅርና ኮሬንቲ አልተባለማ»

ትናንሽ አይኖቿ በጣም ተርገበገቡ:: ሰዎች እንዲህ ሲለወጡ አላየሁም::

መለ'ወጤን (ከተለወጥኩ) አይቶ የሚነግረኝ ይኖራል? ቃዛቢ አያሳጣ እንደ ማለት::

•

•

•

***ትንሽ ማየት ትንሽ ማፍጠጥ:*** እዚህ አልጋ ላይ ሶስተኛ ሳምንቴ ነው:: ሴት ልጅ ሳሎን ፉቶን ላይ እያስተኛሁ ስተኛበት:: ዒ እምቢ ብላኝ ነው:: የተኛሁበት ክፍል ከመጋረጃው በተጋባ የቀይ ብርሃን ድባብ ውስጥ ይዋኛል:: አንዱ ግድግዳ በሙዚቃ ሰዎች ፎቶና የተለያየ ዝርያ ባላቸው የተሰባበሩ ጊታሮች የተሞላ ነው:: ክፍሉ እንደ ሴት ይሸታል:: የሆነ ሽቶ የሆነ ንፅሕና:: አልጋው ሰፊ ስለሆነ ግራና ቀኜ ያለው ቦታ ተጨማሪ ሁለት ቀጫጫ ሰዎች ያስተኛል:: እዛ ጋ የፀናዕል ልብሶች በስርአት የተደረደሩበት ኮመዲና ነው:: ከፊት ለፊት ግድግዳው ላይ የአብዱ ማትያስ ክላዋይን የምሥራች/አነንሲዬሽን Annunciation የተባለው ስዕል ኮፒ ተሰቅሏል:: ስዕሉ ውስጥ በስተግራ አንዲት ጥቁር ሴት ራቁቷን ተንጋላለች፣ ወይም ተቀምጣለች:: እግሮቿ ግራና ቀኝ ተከፍተዋል:: ከጭኖቿ መሃል ነጭ እርግብ ተቀምጣለች:: ሴትዮዋ ሁለመናዋ ተባረኪን ይመስላል:: ባየሁዋት ቁጥር አይኖቿን አሸሻለሁ:: ፀናዕልን (ካልነቃችብኝ) የምጠይቃት አንዱ ውለታ ይሄን እንድታነሳልኝ ነው:: ሰበብ እስባለሁ ('ለምን?' ብትለኝስ) ከአልጋ ወጣሁ:: ግራና ቀኝ እጆቼን መስቀልኛ ዘረጋሁና አይኖቼን ጨፈንኩ:: የክፍሉ በር ገርበብ ተደርጓል:: ለስላሳ ሙዚቃ ምናልባት የፈረደበት *ባሀ* ከሳሎን ይመጣል:: ሱሪዬን ለብሼ ካናቴራ ደርቤ ከመኝታ ቤት ስወጣ ተኝታ የነበረበትን የሶፋ አልጋ አጎንብሳ ስታመቻች አየሁዋት:: ሳሎኑን ፈሳሽ ወርቅ የመሰለች የጠዋት ፀሐይ ወራዋለች:: ፀናዕልን በውስጥ ሱሪ እንዲህ አጎንብሳ አይቼአት አላውቅም:: እንዳላሳፍራት ወይም እንዳላስደነግጣት እንዳላየ ሆኜ በር በቀስታ መለስኩ:: የሆነ ነገር እንኳንሁና መልሼ በር በቀስታ ከፈትኩ:: ቆማ በር በር በሩን ስታይ አገኘሁዋት::

«ተስማማህ? በደንብ ተኛህ?» አለች ወገቧን ይዛ:: የየቀኑ ጥያቄዋ ነው:: ትንሽ ሊሰለቸኝ ጀምሯል::

«በጣም»

ፀጉርዋን እየላገች አስተካከለችና በምታስርበት አስራ ፈገግ ብላ አየችኝ:: ስለተስማማኝ መርካቷን ልትገልፅልኝ ነው:: ይሄም ትንሽ ሊሰለቸኝ ጀምሯል::

«አሁን ጠዋት ሁለት ክላስ አለኝ ከዛ ስራ እሄዳለሁ:: እየሮርክ ከተማውን ተለማመድ:: ዋሽንግተን ሸሮሚዳ ወይም ላይፕዚግ አይደለም ሂሂሂ» ላጅባት አንድ አምስት ሐሐሐሐሐ ሰጠሁዋት:: ተከትላኝ ከት ብላ ሳቀችና አንገቷን እያሻሸች ወደ መስኮቱ ሄደች::

«ጠዋት ጠዋት ዋሽንግተን ያምራል፣ ደስ ይለኛል፣ እንጃ» አለች

በስስ ነጭ ፒጃማዋ ስር ቅርፁ ሰንበሌጥ የመሰለ ቂጥ የሌለው ጡት የሌለው ቁመናዋን አያለሁ:: እርግብግብ ነው:: ቀላል ነው:: ከጥቂት ደቂቃዎች በሁዋላ ለመቀንጠስ የተዘጋጀ ይመስላል:: ግራና ቀኝ በትንሹ በተከፈቱት እግሮቿ የሚመጣው ወተት የመሰለ ጨረር ቀፎ ያወጣው የገላዋ ቅርፅ ለልቦናዬ የተላከ እሷ ያዘጋጀችው አጠር ያለ ፈተና መሰለኝ:: የውስጥ ሱሪዋን ቢጋር አያለሁ:: መስኮት ከፈተች:: መስኮት መክፈት እንዲህ አያንጠራራም:: የመስኮቱ አከፋፈትና የአልጋው አነጣጠፍ ስልት ግባቸው አንድ ሳይሆን አልቀረም:: እነዚህን ሳያይዝ *ሆን ብላ ያደረገችው ይሆን?* ብዬ ጠረጠርኩ:: የሚያሳዝን ነገር አለው:: ተባረኪ ብትሆን ኖሮ ሁሉን ነገር ትቼ እላይዋ ላይ እዘረገፍ ነበር:: ዞር አለች:: ለምን ፈጠነች? አሏሏሯ አያት እንደነበረ እጅ ከፍንጅ ልትይዘኝ አቅዳ መሰለኝ:: (መቼ ዕለት 'ከሁዋላዬ ስታየኝ አየሁህ' ያለችኝን አልረሳሁም:: ማስጠጣት የሚያሳፍር ነው?) ሄጄ ላቅፋት ፈለኩ:: ሁሉ ነገሯ ይጥማል ግን አላፈቅራትም:: ጥቁር ዶሮታ ናት:: እንዲህ ሳስብ:

«ምን ትበላለህ ቁርስ?» አለች

«እም......ያለውን»

አየችኝ::

«ምነው አየሽኝ?»

«የእውነት?»

«ያ ያ»

«እኬ»

እሷ እየሰራች ገንዘቡን ስለምታመጣ የጎዳሁዋት እየመሰለኝ ልቆጥብላት ይመስላታል:: የወንጀለኛነት ስሜት አይነት ነገር:: በስተግራ ወዳለው ማድቤት በፍጥነት ሄደች:: እንዲህ ስትፈጥን አላውቃትም:: *አዲስአባ የተረጋጉ ሰዎች አገር ነበረች?* በአምስት ደቂቃ እመሌት፣ ቶስትና ቡና ሰርታ እየተያየን ጠረጴዛ ከበን ተቀመጥን:: አይኖቿ ቀላ

ብለዋል:: የታቹ ከንፈሯ በግራ በኩል የተሰነጠቀ ቦታ አለው:: እስከዛሬ ያላየሁት ቀለም ስለምትቀባው ነው:: ቀደም ሲል በትዕይንት የሰጠችኝ የገላ ስጦታ ደስ እንዳለኝና እንደማስብላት ለማሳየት ስንጥቁን በአመልካች ጣቴ በቀስታ ነካሁና:

«ምን ሆነ?» አልኩ

ምን እንደሆነ መገመት ከብዶኝ፣ ወይም ጥያቄውን ራሴ መልሼ ዝም ማለት አቅቶኝ አልነበረም:: እንዲህ ስጠይቃት ግን አልተመቻትም:: ያን ሁሉ አድርጌለት የተጎዳ፣ የማያምር ከንፈሬን ያያል አይነት::

«ከሰብዌይ ስወጣ አንዱ ሲጋራ እንደመጣለት ሲወረውር......»

ከዛ በሁዋላ አልሰማሁዋትም:: እጅዋን ያዝኩዋት:: የተያያዙ እጆቻችንን ማየት ጀመረች:: እጅዋን አነሳሁና ሳምኩት:: ለስህተቴ ይቅርታ ለመጠየቅ ነው:: ከአንድ የተሳሳተ የምላስ ጻጥ ወደ ሌላ ሽርተቴ መሸጋገር ያደክማል:: እጄን አንስታ በአንገቷና በትከሻዋ ይዛ አይኖቿን ለአፍታ ጨፈነች::

«በጣም አፈራሃለሁ» አለች:: አይኖቿን ገለጠችና:

«አሁን ሳይሆን፣ አሁን አልፈራህም»

ሹካው ከእጇ አመለጠና ነጩ ሳህን ላይ የአመሌት ቂጣ ተደግፎ ተኛ:: ቀና ብላ አይታ እጄን ለቀቀች:: ሹካው ከእጅዋ በማምለጡ አፍራ ሳይሆን አይቀርም ራሷን ነቅንቃ ሹካዋን አነሳች::

«አንድ ሰአት ነው የቀረኝ:: ብሄድ ይሻላል»

«ለመሆኑ ስልክ ቁጥር የተውሽልኝ ብጠፋ......»

የጀመርኩትን ሳታስጨርሰኝ:

«ታዲያስ......» ልትጠጣ የጀመረችውን ቡና ከአፏ መለሰችና ሲኒዋን አስቀምጣ በሳቅ ፈረሰች::

«ጤይባ አደረግሽኝ?»

«ሳይሆን አለ አደለ......»

«ምን?»

«አይታወቅም»

'አይታወቅም' ያለችው ቃል ትርጉሙ ግልፅ ቢሆንም:: መሰለ:: በሚጣፍጥ መልክ ስላለችው መሰለ:: ድምፅዋ ብቻ ሳይሆን አንገት አሰባበሯ፣ የእጅዋ ንቅናቄ፣ የከንፈሮቿ አለዋወስ አባባሏን አጥር ላይ አስቀመጠው:: በዝምታ ቶሎ ቶሎ በላችና ቡናዋን ለመጨረሻ ፉት ብላ ከተቀመጠችበት ተነሳች:: ወደ መኝታ ቤት ገብታ በሶስት ደቂቃዎች

ውስጥ ጂንስ ሱሪዋን፣ ነጭ ሸሚዝ በጥቁር ሰደርያ ለብሳ ወጣች:: ቫዮሊንዋን ከተቀመጠበት ዴስክ ላይ፣ ቦርሳዋን ከአንድ ካሬጆ የቀርከሃ ላብ ሲት ላይ አንሳችና ወደ በር ሄደች:: ቡናዬን እየጠጣሁ እያታለሁ:: የተለወጠች ፀናዕል ናት:: በር ስር ያገኘችውን ባለተረከዝ ጫማ አድርጋ ቆማ አየችኝ:: የትንሽ ቂጥዋ ፈጣጣ ክቡ በኮምፓስ የወጣ ይመስላል:: ወፍራም ቀበቶው የዞረበት ወገቧ በጣቶች መሃል እንደ ሲጋራ የሚያዝ ነው::

«ለምን አልሸኘሽም?» አልኩዋት የዕውነቴን::

«ባላገር አልጎትትም» አለችና አፏን ወደ ላይ ሰቅላ ሳቀች::

ወደ እሷ ሄድኩና ላቅፋት እጆቼን ግራና ቀኝ ዘረጋሁ:: ይሄ የፍቅር አዘረጋግ ሳይሆን ደንብ ይመስላል:: ቆማ የምትጠብቀው ይሄን መሰለኝ:: ከነንዝሂ እላዬ ላይ ወደቀች::

«ፀናዕል» አልኩ በቀስታ፣ ድምፄን ላሳምር እየሞከርኩ

«እህም......» አለች

ከዛ ሁለታችንም ምንም አልተናገርንም:: ነገር የሚያስበው አናቴ እሷንም እኔንም አንድ መስመር ላይ የሚያቆም ቃል ማውጣት አልቻለም:: እላዬ ላይ ለ 15 ሰኮንዶች ያህል ቆይታ ቀና ብላ ሳታየኝ በር ዘግታ ወጣች:: ከከንፈሮቿ ቅርፅ ዕንባዋን እየያዘች እንደሆነ ይታወቃል:: ሆዴ ሲነድ እሰማዋለሁ::

•

•

•

እግሬን ስለበረደኝ ቆዳ ቦት ጫማ አድርጌአለሁ:: ስዞር ውዬ ስለ ራበኝ የሆነ ነገር በልቼ ፀናዕል ስራ ቦታ ለመሄድ በር ስር አወለቅሁት:: ካልሲዬ የረጠበ ይመስለኛል:: እንዲህ ሲሆን ማወዳደሪያ ዋቤ-- መልካምድሬ ሽሮሜዳ ትዝ ትለኛለች:: ላይፐዚግ ሳይሆን ሽሮሜዳ:: ለማምለጥ ስጥር ለማምለጥ አልችልም:: ማምለጥ ሳልችል ትዝ የሚለኝ ብዙ ጊዜ አልባሌ የመሰለ ነገር ነው:: ፀሐይን ሳስታውስ ከፊቷ ሌላ ምንም ትዝ አይለኝም:: እዝራን ሳስታውስ ትዝ የሚሉኝ ጥቂት ነገሮች ናቸው:: ረድኤትም ትዝ ትለኛለች:: ከገላቸውና ከልብሳቸው አንዳንዱ ትዝ ይለኛል:: ያን ሁሉ ጊዜ አውርተን፣ አንሶላ ተጋትተን ትዝታው ከአንድ አረፍተነገር በላይ አይረዝምም? ማለት ታሪክ የለኝም:: ታሪኬ 'ትዝታ' የተባለ አንድ ቃል ውስጥ ተሰንቅሯል:: ብጥስጣሽ ኩነቶች እንደ ክር ተገማምደውና እንደ ጥንግ ከረው ውስጤ ይኖራሉ:: ታሪኬ ያ ነው:: ላስበውና ልዘፍነው እችላለሁ:: ልናገረውና ልፅፈው አልችልም:: አልማዝ

ትዝ ስትለኝ የጉርጉስም ግቢና 'እንጀራ ገለጣ' ትዝ ይለኛል። ስለቡትና እግር ተነበይኩ ያለችው ትዝ ይለኛል። እሱም ትዝ ያለኝ ቡት ጫማ ስላደረኩ ነው። አለም ላይ ሁለት ነገር ታደርጋለህ ጂ.ሚ: ወይ ትቆማለህ ወይ ትጓዛለህ። ቀላል ነው። ጠንቋይ አያስፈልገውም። ደሞስ እትዬ አልማዝን ማን ይፈራታል? የፒነት ሳንድዊች እየበላሁ ዝም ብዬ በሃሳብ እከንፋለሁ። የእኔና የፀናዕል ጠላት የትዝታችን መለያየት ይመስለኛል። ሳንተዋወቅ እንተዋወቃለን ብለን ወደ ሁዋላ ስናይ ሁሉ ነገር መልክ መልክ የሌለው ጠፍጣፋ ይሆናል። ሁሉ ነገር ያንሳል። ለእኔ እንዲያ ነው። ቋንጣ ፍርፍር በበርበሬና በቅቤ ከበላሁስንት ጊዜዬ! ፉክ ኢት።

•

•

•

ቤት ውስጥ ወዲያ ወዲህ እያልኩ የማስበው ከፀናዕል ጋር ስሆን የተሳሳትኩትን ነው። ባልሳሳትም የተሳሳትኩ የመሰለኝን ነው። ስትሄድ ላያት ወደ መስኮቱ ተጠጋሁ። ዌስት ሚኒስቴር ስትሪት ሞቅ ብሏል። ቀላል ነፋስ ሽሚዜን እየገለጠ በአሜሪካን ድሪም መርፌ የሽንገላ ክትባቱን ይወጋኛል። ከአፓርትመንቱ ወጥታ መንገድ ስትገባ አየሁዋት። ቀኝ እግርዋ ትንሽ ሸፈፍ ያለች ናት። አረማመዷን አሳዛኝ ያደርገዋል። ያለ ዕድሜዋ ያደገች ወይም የረዘመች የ 11 አመት ልጃገረድ ትመስላለች። ፀናዕል አሜሪካ አርትኦት የሰራችባት የከበደ ሚካኤል ግጥም ናት። ረዥም ቀሚሷን ገፎ ጠባብ ጂንስ ያለበሳት፣ ሚኒ አፍሮዋን ላጭቶ ድሬድሎክ የሰጣት፣ ከሜሪ ጂንስ ጫማ አውጥቶ ተረከዛሙ ላይ የሰቀላት፣ ከቀለጠ አማርኛ ወደ ቀለጠ ጉራማይሌ ያሰደዳት። ከአገሯ የተያያዘችው በእኔና በልጅነቷ ትዝታ ይሆናል። ያልተሰረዝኩት እኔ ብቻ እሆናለሁ። እኔ ብሰረዝ የሚቀራት ምንድነው? ራሷን ማስታወስ? ወደ አፓርትመንቷ ቀና ብላ አየች። ገፅዋ ወደ ስላሳ አመታት ሊሆነው ነው። እጄን አነሳሁላት። ስለምን ትፈራኝ ነበር? ሁለተኛ መንገድ ስታቋርጥ ዞር ብላ አየችኝ። ደግሜ እጄን አነሳሁላት። እየሳቀች እጅዋን አነሳች። አይኖቼን መለስ አድርጌ ሲጋራ ለኮስኩ። ኡጓዴ መጥጬ ወደ ውጭ ጭሱን እየተፋሁ መንገዱን ቃኘሁ። ፀናዕል በትርምሱ መሃል ታልፋለች። እሷ ብቻ ወደዛ የምታልፍ ይመስላል። አካሄዷ የተዛነቀ አይነት። ቆም ብላ ከሆነ ሱቅ አንድ ነገር ገዛች። ወደ ነበርኩበት ዞር ብላ አየች። የገዛችውን አፏ አስገብታ እጅዋን አነሳች። እጄን አነሳሁ። አሁንም መንገድዋን ቀጠለች። አናቷን ወደ ሁዋላ ወርውራ ድሬድዋን አስተካከለች። ሃዋርድ ዩንቨርሲቲ የምትሄደው በእግሯ ነው። በሚተራመስ ጎዳና መሃል ጠፋች። ለደቂቃዎች ቆሜ የዘመን አለም ላይ ቆየሁ። በጥርሳም ፎቆቹ፣ በሲሚንቶው ደንደስ፣ በሚፈልቅ መስታወቱ፣

በሆሆታው ይስቅብኛል:: ከቆምኩበት አድማሴን እፈልጋለሁ:: ዐይን እስከሚይዝ መጀመሪያ ፎቅ፣ ቀጥሎ ፎቅና ከዛ ፎቅ ነው ከዛ......በከንፈሮቼ ጠፍሬ ከያዝኩት ደንሂል ጢስ ሳያቋርጥ ይቦናል:: ፀናዕል ሲጋራዬን አትወድም:: ጠረኑን ለማባረር እጅዋን ታርገበግባለች::

•

•

•

ኢትዮጵያ እዚያ አፍሪካ ያለች ትንሽ አገር አይደለችም:: አለም ራሷ ሆናለች:: ለምን እዛ ያጋጠመኝ እዚህ ያጋጥመኛል?

•

•

•

እሁድ ጠዋት ባልኮኒ አጠገብ ጠረጴዛውን አምጥተን ቡና እየጠጣን የምትወደውን አልተርኔቲቭ ሙዚቃ እንሰማለን:: ከእሷ ቀኝ ጠረጴዛው ደርዝ ቢጫ የሙዝ ልብስ ተፈራክሶ ተቀምጧል:: እሱን እያየች 'ማርያምን እወዳታለሁ ግን ማርያም የሳመችው ሙዝ አልወድም......ቢጫ ብቻ ነው የምበላው......ሙዙ የቆሸሸ ስለሚመስለኝ ነው......አይ አም ስፖይልድ[87] አደለ? ሂሂ' እሷ ታወራለች......ብዙ አልናገርም......በመመሰጥ እሰማታለሁ......ሁለታችንም በቁምጣ ነን:: ከላይ አረንጉዋዴ ታንክ ቶፕ ለብሳለች:: ቁምጣዋ ቢጫ ሾርት ሾርት ጂንስ ነው:: እግሮቿ ነጭ የጎማ ነጠላ ጫማ ላይ አርፈዋል:: ጣቶቿን ታንቃንቃለች:: ግራ ፊቷ ላይ የፀሐይ ብርሃን አርፎበታል፣ ለስላሳ ነው......ካስረችው ባንዳና ስር ድሬዷ ትከሻዋ ላይ ተረፍርፏል.....እኔ ነጭ ካናቴራና በብዙ አይነት ቀለማት የተዝጎረጎረ ቢች ቁምጣ አድርጌአለሁ:: የጭኔ ግማሽ ራቁቱን ነው:: ጉልበቴ ላይ ያሉትን ጠባሳዎች አይታ እየጠቆመች 'ኳስ ነው አይደል?' አለች:: እንደማላውቀው ሁሉ ተረቧን ተከትዬ አየሁት:: አንዱ ጉልበቴ ላይ ሶስት አራት ጠባሳዎች ተደርተውበታል:: ዐይኖቼን ጨፍኚ በዐይነ-ሕሊናዬ ሽሮሜዳ ሄድኩ......ስንቴና የት ቦታ ወድቄ እንዲህ እንደሆንኩ ትዝ ሊለኝ አልቻለም:: 'ወይ ብስክሌት ወይ ኳስ ነው' አልኩዋት:: ግራና ቀኝ ጉልበቶቼ ላይ ያሉትን ጠባሳዎች ቆጠርኩና (ሰባት) 'ሰባት ጊዜ ወድቄ ይሆናል፣ ስድስቴ ሊሆን ይችላል፣ አራቴ ሊሆን ይችላል፣ ግን ሁለት ወይም አንዴ አይደለም:: ብዙ ቁም ነገርም እንዲህ ነው የሚረሳው' አልኩዋት እየሳቅሁ:: አባባሌን ወደ ተባረከ እንደምታዞረው ይገባኛል:: ለማባበል መሰለኝ ቀኝ እጅዋን በጠረጴዛ ላይ ሳከችና

[87] ጥጋበኛ ነኝ (I am spoiled)

ያልተለኮሰ ሲጋራ የያዘ እጄን ዳበሰችው:: ሲጋራውን መተርኮሻ ላይ ጥዩ መልሼ ዳበስኳት:: 'አንድአንዴ በደንብ የምጫወተው ስኮር[88]፣ ገና ስጀምረው ይጠፋኛል:: አንድ አምስት ደቂቃ ሜዲቴት ማድረግ አለብኝ:: አንዳንዴ የማላውቀውን ያላሰብኩትን አይነት ጥሩ እጫወታለሁ:: መቼ በትክክል እንደምናስታውስ አናውቅም:: ሰውነት መሰለኝ:: ኢት ኢዝ ሁማን[89]:: ሶስተኛው አለም ሄጄ ፊልድ መስራት እፈልጋለሁ:: ብሄድ አብረኸኝ አትሄድም? ምናለበት......ደን ለምጄ አለሁ:: ብርድ ለምጄአለሁ:: በረሃ አይሁን እንጂ.' በፎክ ሚዩዚክ ስፔሻላይዝ ለማድረግ እንደምትፈልግ ነገረችኝ......ሙዚቃ ኮንሰርት እንደ ምንሄድ ደግማ አነሳች......አንድ የምታውቃት ብሉስ ዘፋኝ ተጋብዛ ለመጀመሪያ ፓብሊክ እንደምትዘፍን ተናግራ መሄድ እንዳለብን ሳይታለም እንደተፈታ ተናገረች:: (''ሳይታለም የተፈታ' ነው አይደለ የሚባለው? እንአቮይደብል[90] ሲሆን? ሂሂ ውይ! አይ አም አን ኢድየት'[91]) እጄን ብቻ ግድ የለኝም አይነት አነሳሁ:: ደስ እንዳለሽ ማለት ይመስላል:: 'አብረን እንደንሳለን አደል?'......ትለኛለች:: 'ሳር ላይ ተቀምጠን......አደለ? ክላፕቶን ነው......ኦሎምፒክስ በይኮት ተደርጓል፡ እዛ እንዳንሄድ......ብሉስ ትወዳለህ አሁንም? የቢል ዊዘርስን ኤይንት ኖ ሰንሻይን[92] እጫወት ነበር ትዝ ይልሃል? ain't no sunshine when she's gone......It's not warm when she's away ድምጼ ያምራል? ሂሂሂ'......ከምታወራው ከይዘቱ ተላቅቄአለሁ......አጥንታም ደረቷ ላይ በመድቀቃቸው የተበሳጩ የመሰሉ ጡቶች መሃል የብር መስቀሏ ቦግ እልም ይላል......እሱ ጉዳዬ እንደሆነ ሁሉ ሳፈጥበት ቆየሁ:: እጅ ለእጅ እንደተያያዝን ነው......

«የእማማ መስቀል ነው»

«ደስ ይላል አልኩ» በደከመ ድምፅ

«ከመቼ ወዲህ መስቀል ወዳጅ ሆንክ? ለፆም እየበላህ ትሄድ ነበር አደል ለማስቀደስ ሂሂሂ......ነጠላህ ውስጥ ከነቸርነት ጋር ዳቦ ደብቀህ ታስቀድስ ነበር:: አይቼአለሁ ሂሂሂ ሰይጣን የሚባለው አይነት ሂሂ»

አልመለስኩላትም::

«ዩ አር ደፕረስድ?[93]»

---

[88] score

[89] የሰው ነገር (It is human)

[90] የማይመለጥ (Unavoidable)

[91] ዘገምተኛ ነኝ (I am an idiot)

[92] የፀሐይ ብርሃን የለም (Ain't no sunshine)

[93] ደበረህ? (are you depressed?)

«አይ:: ከሽሮሜዳ ላይፕዚግ፣ ከላይፕዚግ እዚህ ዋሽንግተን ......ያስፈራል በፍጥነት አለዋወጡ»

.........................................................................................................

«በጣም ደስ ይለኛል እዚህ ስላለሁ:: እማማ ትሙት»

መስቀልዋን ከተንጠለጠለበት ቀና አድርጋ ሳመችው:: ዐይኖቿን ጨፍና በቀስታ ከንፈሮቿን አሞጥሙጣ:: ብሩን ከነካች በሁዋላ ለምቦጩዋን ነከሰች:: ዐይኖቿ ከመስኮት ወዲያ ተተክለው ቀሩ:: መስቀል እንዲህ ሲሳም አላየሁም:: ውስጤ ተነቃነቀ:: ምናልባት እንዲህ ተንጋላ የተቀመጠች ቀይ ልጅ መስቀል ስትስም አላየሁም:: ከውበት በላይ ነው ያየሁት:: ከሃይማኖት በላይ:: ንፁሕ ፍቅር ነው:: ሃይማኖቶች ብልጥ ሲሆኑ ነው? እንዱ እንዱን ያገላል:: አተኩሬ አየሁዋት:: እኔን ግን አታየኝም:: እጅዋን ፈልጌ ያዝኩት:: ዐይኖቿ ከረምት መሆን ጀምረዋል:: እጄን አላቃ ተነሳች:: ቀና ብዬ አየሁዋት:: ልከተላት ዳዳኝ:: ዞር ብላም ሳታየኝ 'ውሃ ጠማኝ' አለች:: ዕንባዋን መዋጫ የተደበቀ ቦታ ፍለጋ ነው::

*ምን ልበላት? ምን ላድርጋት?*

•

•

•

ሲጋራዬ አልቆ የነከሱት ጣቶቼ መሃል ሲሞቀኝ ደነገጥኩ:: ቡሹን ፍም ሊበላው ጀምሯል:: ልጅ ሳለሁ ከፀናዕል የራቅሁት ሌሎችን ስለማትመስል ነበር? አጠገቤ እያለች አልነበረችም:: ቴቢ ሌሎችን ቆነጃጅት ስለምትመስል ቢያንስ ሁኔታዋ ስለሚቀራረብ እና ሌሎች ስለሚወዷት እየተሻማሁዋት ነበር? ከመንጋ ጋር አንዷት ልጅ አፍቃሪ ነበርኩ:: 'ቴቢ ደስ ትላለች' እየተባለ የተነዛውን ወሬ ነበር የተከተልኩት? የሌሎችን ግምገማ ተደግፌ ነው የነደድኩት? ሲጋራዬን ሳላስበው እንደተረኮስኩት አየሁ:: ለመጀመሪያ ጊዜ ጠየቅሁ ራሴን፣ በእርግጥ ቴቢ ማን ናት? ከዚህ ሆኜ ሳስባት በድንቁርናዬ ዕንቁ ያደረኳት፣ በመልኬና በመላመዷ ብቻ ያሸነፍኳት፣ ከጸቃላ ፖለቲካዋ ያነስኩ አፍቃሪ ነበርኩ:: ግን ከአንድ ዝናብ የጠጣን ነንና በሆነ ትርጉም ጓዶች ነን:: እሷ ከመንጋ ጋር የመንጋ ፖለቲካ እኔም ከመንጋ ጋር በእሷ ቁመና መለከፍ:: ሳንግባባ ተግባብተናል:: ተግባብተን አልተግባባንም::

በዐይነሕሊናዬ ፀናዕል በሰዎች መሃል እየተጋፋች ስታልፍ አስባታለሁ:: ከቤተሰቦቿ ውጭ ናት:: የሚያስብላት ማንም የለም:: የመንገዱን ካርታ ያሳያት የለም:: ሰው በተጠቀጠቀበት ጎዳና ላይ እንደ መቀስ እየተከፈተች እየተከደነች ትሄዳለች:: እኔ በወሬ፣ ተባረኪ በፓምፍሌት የነቃን ነበርን:: ለፀናዕል ድል የሚያጨበጭብላት፣

ድክመቷን የሚያቃናላት የለም:: ድሮም አልነበረም:: አባቷ ሙዚቃ የሚያስተምሯት እሷ አፈልጋለሁ ስላለች ነው:: እናቷ 'ይሄን ነገር ከመቀጥቀጥ ሌላ ስራ የለሽም?' ይሏት ነበር:: እኛ ፒያኖውን ተጠግተን እያየነው ነክተነው ግን አናውቅም:: ወሬ አውርተን፣ ዳማ ተጫውተን፣ ተላፍተን፣ እየጮህን ገብተን ከቤቷ እየጮህን እንወጣለን:: ብቸኛ ነበረች:: ሳንቀርባት 'ከሰው አትቀርብም' ብለናት ነበር:: 'አርቀናት' ግን 'አራቀችን' እያለን:: ያሳዝናል::

ወደ አንድ እንጨት መደርደሪያ ሄድኩና ፊት ለፊቱ ቆምኩ:: ምን እንደምፈልግ አላውቅም:: መደርደሪያው አምስት ረድፎች አሉት:: ሁለቱ የመደርደሪያ ረድፎች በካሴት ሙሉ ናቸው:: አንገቴን ሰበር አድርጌ ሰረሰራቸው ላይ የተፃፈውን ሳነብ ቆየሁ:: የማውቃቸው ሙዚቃና ሙዚቀኞች ጥቂት ናቸው:: ክላሲካል ሙዚቃ ይበዛል:: አንድ መዘዝኩና አየሁ John Adams *two fanfares for orchestra* እሱን መለስኩና አጠገቡ የነበሩ ሁለት ካሴቶች አወጣሁ:: አንደኛው john cage *cheap imitation* ይላል፤ ሁለተኛው Variations I, II,III,IV,V,VI, VII,VIII ይላል:: ከት ብዬ ሳቅሁ::

ካሴቶቹን በታቸው መልሼ የተኛሁበትን አልጋ አነጠፍኩ:: ማድቤቱን አፀዳሁ:: መታጠቢያ ቤት ገብቼ ለአምስት ደቂቃ በቁም ታጠብኩ:: ገንዳ አልወድም:: ሁለመናዬን በሽቶ አጠርንኜ (ቻርነት እንደዛ ይል ነበር) ለማረፍ ተቀመጥኩ:: ከተቀመጥኩበት ሳይ በግድግዳዎቿ ላይ ከሙዚቃ መሳሪያዎች በተቀር የሰቀለቻቸው ጌጦቿ ሁሉ የትንሽ ልጅ ናቸው:: ዕድሜዋ የሴትዮ ይሁን እንጂ ፀናዕል ገና አላደገችም:: ለአፍታ ሽፋፋዋና አሳዛኝ አካሄዷ ትዝ አለኝ:: ከተቀመጥኩበት ተነስቼ ሲጋራ ለኩሼ ወደ መስኮቱ ሄድኩ:: ከፊት ለፊቴ በቀጫጫ ገመድ የተያዙ ብዙ የላስቲክ ባሉኖች ዝቅ ብለው እየተንሳፈፉ መጥተው የምኖርበትን ሕንፃ ተጠግቶ በቆመ የዛፍ ቅርንጫፎች ተይዘው ቆሙ:: ባሉኖቹ ቁጥራቸው መዓት ቢሆንም፣ ቀለማቸው ሰማያዊ፣ ቀይና ቢጫ ብቻ ነው:: ነፋስ በቀስታ እየገፋቸው ይልመጠመጣሉ:: እነሱን ሳይ ከሁዋላዬ በስተግራ በኩል አንድ ነገር ወደቀ:: ደነገጥኩና ዞር ብዬ አየሁ:: ከመደርደሪያው ስር አንድ ትልቅ የክርታስ ሽፋን ያለው መጽሐፍ ተጋድሟል:: ከመሃከለኛው እርከን ላይ ነው የወደቀው:: ሲጋራውን በመስኮት ወርውሬ መፅሐፉን ላነሳው ሄድኩ:: ጃዝ ቫዮሊን የሚል አርዕስትና የቫዮሊን ስዕል ሽፋኑ ላይ ያለበት መፅሃፍ ነው:: የወደቀበትን እርከን አየሁት:: የነበረበት ቦታ ሰፊ ክፍተት አለ:: ሰው ካልገፋው በስተቀር እንዲሁ ሊወድቅ የሚችል አይመስልም:: ላነሳው ስል ከውስጡ ሰማያዊ ወረቀት እንደ ምላስ ወጥቶ አየሁ:: መፅሃፉን አነሳሁና ወረቀቱን መዘዝኩት:: በአበባ ሞኖግራም አምሮ ለሁለት ታጥፏል:: እጥፋቱን ስገልጠው በአማርኛ የተፃፈ ግጥም አየሁ:: የተፃፈው በጥቁር እስክሪፕቶ

ነው:: አርዕስቱ፡ ***የፍቅር ፍልስፍና*** ይላል:: በጉጉትና በዝምታ አነበብኩት:: አስር መስመሮች አሉት:: ግጥሙን የፃፈችው ፀናዕል ናት:: ሃሳቡን ከፔርሲ. ሼሊ. እንደተዋሰችው ግጥሙ ማለቂያ ላይ ሳትደብቅ አስፍራለች:: በ1980 (እ.አ.አ) ለንደን ከተማ ሃይድ ፓርክ የተፃፈ ነው:: ይሄን ስትፅፍ ላይፕዚግ ነበርኩ:: ግጥሙን ስጨርስ የሆነ ነገር ተሰማኝ:: ምናልባት ሐዘን ምናልባት ሐዘንና መገረም:: ምናልባት ሐዘን፣ መገረምና ቀሽምነት:: ***ይሄ ሁሉ እሟ ትርፉ ለምንድነው? አንተ እኔን ካልሳምከኝ? አብረን ካልታየርነው***......የሀበሻ ሴት ይሄን ቃል በግጥም አስፍራ አንብቤ አላውቅም:: ከንፈራቸው እስኪገነጠል ይሳማሉ ግን 'ተሳምኩ' ብለው አይፅፉም:: *ለመሆኑ ሴት በሐፉ አለ እንዴ?* ወረቀቱን መፅሐፉ ውስጥ፣ መፅሃፉን ደሞ እነበረበት የመደርደሪያ እርከን ላይ መልሼ ወዲያ ወዲህ እያልኩ አሰብኩ:: ምናልባት ፀናዕል አድማሴ ናት:: እኔን አሜሪካ መጥራቷ ከባዶ መጣ? የሁለታችን መመሳሰል በጠማማ ልምድ ተጠብሰን መጠየማችን ነው:: ከተለያየ አቅጣጫ መራራቅን መለያየትን አይተናል:: ያለፈ አፅም እየቆፈርኩና እያወጣሁ ማላዘን የለብኝም:: ግጥሙ ራሱ እዚህ ብቻዬን ሳሎን ውስጥ መብሰልሰልና መተከዜን አይወድም:: ቶሎ ቶሎ ልብሴን ለባብሼ ከአፓርትመንቱ ወጣሁ::

ባሉኖቹን ወደ ያዘው ዛፍ ስሄድ ባሉኖቹ ከቅርንጫፎቹ ተላቀው ወደ ሰማይ ጉዞ ጀምረዋል:: ወደ አንድ ሕንፃ ጀርባ በቀስታ እየተመሙ ሲያልፉ አየሁዋቸው:: የሚሄዱት ወደ ደቡብ ነው::

*የት አካባቢ ደርሳ ይሆን?* በሄደችበት አቅጣጫ መራመድ ጀመርኩ:: የሰው ብዛት ቀለል ሲል እየፈጠንኩ፣ መንገድ ሲዘጋብኝ በፍጥነት እየተራመድኩ አስር ደቂቃዎች ያህል ሄድኩ:: ቢያልበኝም አልደከመኝም:: ከሚሉስ ጋር የምሰራው ስፖርት ሳይጠቅመኝ አልቀረም:: ከሩቅ ብቅ ጥልቅ ስትል አየሁዋት:: የአለችበትን የአቅጣጫ መስመር ቀና እያልኩ እያየሁ ፍጥነቴን ጨምሬ መሮጥ ጀመርኩ......ከሁዋላዋ ስደርስ ቆም አልኩና ጎበጥ ብዬ ከድካሜ አረፍኩ......ልቤን ሲደልቅ እሰማዋለሁ:: የሚበርም ይመስላል......ደረቴ ውስጥ እንደ ቢራቢሮ ከደረት አጥንቶቼ ጋር እየተጋጨ......ከጎን አጥንቴ እየተላተመ......ላባው ጉበቴ ላይ እንደ ጥጥ በረዶ ሲቦን......ቅንቅኑ ጣፊያዬ ላይ ሲረግፍ......ዊን ቀና ብዬ አየሁዋት:: መንገድዋን ቀጥላለች:: ትንፋሼ ሲመለስ፣ በፍጥነት እየተራመድኩ ከሁዋላዋ ደረስኩባትና ጠራሁዋት:: ዞር አለች:: ፀጉርዋን ወደ ጀርባዋ እየመለሰች 'ምነው?' አይነት አየችኝ......

ተርዕቻችን በሙከ። ተቀ-ር ፊር
ደሞገሱ-

# ተባረኪ፡ 'ሁለት ፍቅር ያመናቅር'



# በመጀመሪያ መተሳሰብ ነበር

'ትደነቂያለሽ' ከተባለች እናቴ (ትደነቂያለሽ ሳህለ ማርያም)፣ ረኸርም፣ ደልዳላ፣ የሰፈር ሰዎች ልካቸውን ስትነግራቸው 'ሙጢ'፣ በግልፅነቷ ስትመቻቸው ደሞ 'ሃይለኛ' ከሚሏት እናቴ ጋር ነበር የምኖረው:: ልጅ እያለሁ ቁጣ የተቀላቀለበት ግልፅነቷ ስለሚያስፈራኝ እሸሻት ነበር:: ምናልባት ጎረቤቶቻችን የሚያሟት ነገር በጆሮዬ እየገባ እነሱን ተከትዬ ይሆናል:: *ብዙሃን ይመውኡ* ነው አይደለ:: 'የሚመች ወሬ ከእናት ያርቃል' ቢሉም ተረቱን መፍሪያ ልብና እናቴ ብትሆንም ለአንድ ሰው የማዳላበት አንጀቱ አልነበረኝም::

ትደነቅ/ትደነቂያለሽ የተወለደችው ሐረርጌ ነው:: እናቷ የጅጅጋ ሶማሌ ናት:: አባቷ ጋሼ ደግሰው የተባሉ ሰውዬ ነበሩ (እሷ 'ጋሼ' ነበር የምትላቸው):: የሚኖሩት ጅቡቲ ነው:: መልካቸውን በዐይነስጋ ሳይሆን በፎቶ አይቼአለሁ፣ የፃፉአቸውን ጥቂት ደብዳቤዎቻቸውን አንብቤአለሁ:: ጋሼ ከእናቴ ከትደነቂያለሽ ሌላ ከሌሎች ሴቶች የወለዷቸው አምስት ልጆች አሏቸው:: ልጅ እያለሁ 'ሁሉንም አስተዋውቃችሁዋለሁ' እያሉ ቢፅፉልንም እሳቸውንም ይሁን ሌሎች የወለዷቸውን ዘመዶቼን በአካል አይቼአቸው አላውቅም:: ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ያጠናቀቀችው ናዝሬት ከተማ የሆነ የሚሺኖች አዳሪ ትምህርት ቤት ነው:: አንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ ገንዘብ ክፍል ትሰራለች:: ብዙ ጊዜ ኒያላና አንበሳ ይምታቱብኝ ነበር:: ልጅ እያለሁ ሁልጊዜ እየተሳሳትኩ 'እማማ ኒያላ ኩባንያ ነው የምትሰራው' ብዬ ስናገር ስትሰማ፣

'ፍየልና አንበሳ ምናቸው ያምታታል?......እሱስ ምን ታደርጊ አንቺ፣ እርሻ ሚኒስቴር የማይደፍረውን ሁሉን ነገር በእንስሳ እየጠሩ' ትል ነበር::

ወላጅ አባቴ ዘርአይ ከእናቴ ተለያይቶ ደብረዘይት ከተማ የፈረንጅ ሬስቶራንት ከፍቶ 'አብረኸት' ከምትባል ሚስቱ ጋር (እናቴ እንደምትለው 'የአገሩ ልጅ') ይኖራል:: እስከ አዲስአባ የተነገረለት ባዛኛ ይሰራ ነበር:: ሲናፍቀኝ ደብረዘይት ልጠይቀው እወርዳለሁ:: እሱ ?

ስሄድ እማማ ትበሳጫለች:: ሉንቺና ላይ በጫንችኝ ቁጥር: 'አሁን ደብረዘይት ከሸሮሜዳ በምን ትበልጣለች? በጀት ለመደንቆር ካልሆነ? ግድ የለም፣ ለእሱ ቆሪጥ አለው፣ ለእኔም ማርያም አለች' ትላለች::

ከሰለታት አንድ አመት፣ በሕዳር ወር መጀመሪያ ላይ ('ሕዳር ሲታጠን አስመራ መንገድን ለቅቄ እዚህ ገባሁ' ትላለች ሰው 'መቼ ገባሽ እዚህ ትደነቅ?' ብሎ ሲጠይቃት) እማማና እኔ የባምቢስ መኖሪያችንን ለቀን ወደ ሰሜን አዲስአባ፣ ወደ ሸሮሜዳ ወጣን:: እማማ መኖሪያችንን ወደዚህ ሰፈር ለምን እንደለወጠች በደንብ አይገባኝም:: የሸሮሜዳን ጭቃ፣ ጎርፍ፣ አስፋልት የለሽነት፣ ኮረኮንች፣ አቧራ፣ የከብቱን ጋጋታ፣ የተቆለለውን የፋንድያ፣ የተዘፈዘፈውን የእበት ብዛት ላየ 'ከተማ ውስጥ እየኖርኩ ነው' ብሎ ቢናገር አያምርበትም:: ባምቢስ ስንኖር ብዙ ጊዜ ቅዳሜና እሁድ በአባባና በእማማ፣ (ገና አልተለያዩም ነበርና) እየተጎተትኩ ጄላቶና ኬክ፣ ሃምበርገርና ኮካ ከምበላና ከምጠጣባቸው ቦሌ፣ አውሮራና ስታዲዮም እርቄ የሱሉልታን ጢስ የጠጣ ግት ከምትጠባ 'ሸሮሜዳ' የተባለች ገበሬ ማህበር መስፈሬ እስክለምደው መዋረድ መሰለኝ::

እማማ አዲሱን ቤት በሶስት ወሮች አሰርታ ጨርሳ የገባን ዕለት ማታ፣ ጎንዋ አስተኝታ እንቅልፍ እንዲወስደኝ ስታባብለኝ፣ እንዲህ ስትል ሰማሁዋት: *የዚህ ሰፈር ሰላምና ፀጥታ ማማሩ::* ይህቺ አዲስ አለሜ: ሸሮሜዳ የምትባል እንጦጦ የተራራ ሰንሰለት መንበር ስር ያለች ቦታ:: በግብርና መተት የተያዘች በጠጥ:: ከተማ ነኝ ልትል ነጋ ጠባ የምትለፋ:: *ሰላም ማን አጣ የትስ?*

በአባቴ ደስ ይለኝ ነበር:: ደስ ማለት ብቻ ሳይሆን፣ እኮራለሁ:: አራት ምክንያቶች አሉኝ:: *አንደኛ*: የፈረንጅ ሬስቶራንት አለው:: *ሁለተኛ*: ሩቅ ቦታ ማለት ከዚህ ከሸሮሜዳ እርቆ ይኖራል:: እርቆ የሚኖረው ሊነግድ ነው:: አባቴ ሐይለኛ ነጋዴ እንደሆነ እሰማለሁ:: እናቴም ትላለች: 'ከእኔ ይልቅ ንግድ፣ ገንዘብና አካለጉዛይን ነው የሚወደው፣ እንዲህ የሚያብሰከስከውን አገር ባየሁለት፣ ለመሆኑ ከአካለጉዛይ ሰማይ ስኳር ይዘንባል አሉ?' አዲስአባ ሲመጣ እግሩ እንደጣለው ሁሉ ሸሮሜዳ ሳያስጠነቅቅ ብቅ ይላል:: እኔ በናፍቆት በላዩ ላይ እንደ ኳስ ስንከባለል፣ እናቴን እንድትቆይና እንዲጫወቱ ይለማመጣታል:: 'የፈለከው ገብቶኛል:: ከምትሄዱበት ስትመለሱ ሮዛ ጋ ነኝ ጥራኝ' ብላ ትታን ትሄዳለች::

*ሶስተኛ*: አባቴን ዘርዐይን ከእማማ አስበልጬ እንድወደው ያደረገኝ ከረሜላውን፣ ብስኩቱን፣ አሻንጉሊቱንና የሚያማምር ቁሳቁሱን ሁሉ እሱ ብቻ ስለሚገዛልኝ ነው:: አባቴ ለምን እንዲህ እንደሚያደርግልኝ ራሴን ጠይቄ አላውቅም:: በተጨማሪም ቆሻሻ ከሆኑ ሰዎችና ቦታዎች ያርቀኛል:: ስለ ወደደኝ ካልሆነ ሌላ ምን መልስ ይኖራል?

እናቴ 'ከዘመዶቼ ሁሉ እወዳታለሁ' የምትላትን 'ማተቤ' የተባለች የጎሎ ሰፈር ሰዎች 'ማልደያ' እያሉ የሚጠሯት እህቷን ማለት አክስቴን ዘርአይ እንድቀርባት በፍፁም አይፈልግም:: (ማተቤ ቤቷ እዛ ቆሻሻው ጎላ ሰፈር ከቶታል ነዳጅ ማደያው ወረድ ብሎ ነበር:: ቤቱን እኔ ከመወለዱ በፊት ከደብረብርሃን እንደመጣች ከዓላዛር አያት ከእትዬ እናኑ ተከራይታው ትኖርበታለች:: 67 ላይ *የከተማና ትርፍ ቤት* አዋጅ ሲታወጅ ቀበሌ ይወርሰዋል:: እሷም ሳትለቀው እዛው አለች) እማማ 'ተባረኪን ማተቤ ጋ ልውሰዳት አንተም ደብረዘይትህ ተመለስ' ስትል አባቴ 'እቆያለሁ......እቆያለሁ' ይላትና ከእሷ ሽሽት አድርጎ እየጎተተ ወሰደ:

«ከእኔ ጋር ሁኚ:: አይስክሬም ልግዛልሽ? ወይስ እዛ ቆሻሻ ቦታ መሄድ ይሻልሻል?» ይለኛል:: ልጅ ነኝና አይስክሬም እመርጣለሁ:: ሃይጂንና የሚጣፍጥ ነገር አይበልጥም? እማማ ማተቤ ጋ መሄድ አለመፈለጌን ስነግራት: 'ወደዛ ወስደህ ይህቺን ልጅ ምን ቀባጠርክላት?' ትለዋለች:: ፊቴን አይታ በፊቴ ሚስጢር መደበቅ አልችልምና ራሷን በሐዘን ነቅንቃ፣ ብቻዋን ማተቤ ጋ ትሄዳለች:: ማተቤ 'የፈለገው ይምጣ' ብላ የዘርዐይን ግልምጫ ችላ ለገና ወይም ለሆነ በአል ከነልጆቿ ስትመጣ፣ ከአባቴ ጋር ከተገጣጠሙ: 'ቴቢዬ ነይ እዚህ እውጭ እናውራ' ብሎ እጄን ይዞ ግቢው ውስጥ ወዲያ ወዲህ እየተመላለስን:

'እነዚህ ደደቦች መጡ፤ አብረሻቸው ስትጫወቺ እንዳላይሽ፤ ይሸታሉ ደሞ (አነፈንፋለሁ እውነት መስሎኝ):: ተጠንቀቂ፤ የነገርኩሽን ለእናትሽ እንዳትነግሪ' ይለኛል:: ለጥቂት ጊዜ ነፋስ እንደሚቀበል በስለቱኝ የሸሮሜዳ የአስፋልት ጠርዞች ላይ (ድንጋዮቹን መቁጠር እችላለሁ) ወዲያ ወዲህ ያንሸራሸረኛል:: ዋሕድ ካለም ሸንኮራ ይገዛልኝና ከእኔ ጋር እንዳልወጣ ሁሉ ከዋሕድ ጋር ቆሞ፣ ረዥም ወሬውን ያወራል (እጁን ይገፌ ወደ ቤት እንድንሄድ ብጎትተው እንኳን):: አክስቴ ከቤት ስትወጣ ያይና ከእርቀት ማልደያን 'ምን እዚህ ወሬ ይገፌ ሳንጫወት......በይ ደህና እንገናኝ' ይልና እየጎተተኝ ቤት እንመለሳለን:: አንዳንዴ ያላየ መስሎ ከዋሕድ ጋር ወሬውን ሲቀጥል ማልደያ ትጠራኛለች(ይግባት አይግባት እንጃ):: ልትስናበተኝ ስታጎነብስ (በጣም ረዥም ሴትዮ ናት) ጉንጬን እንድትነካብኝ ስለማልፈልግ አንገቴን እሰብራለሁ:: 'አደግሽ በቃ አልሳምም አልሽ' ትልና እናቴን ትስመኛለች:: ፀጉሬ ተመልጦ እዛው የሚወድቅ ይመስለኛል::

አንድ ቀን ማተቤ ጋ ለመሄድ እየለበሰችና እያለበሰችኝ ስንዘገጃጅ 'አብሬሽ አልሄድም' ብዬ ምርር ብዬ ሳለቅስባት፣ በአስመረረኝ ቁንጠጣዋ አስፈራርታ ምክንያቴን ስትጠይቀኝ፣ ከማተቤና ከልጆቿ ጋር መጫወት

የማልፈልግበት ምክንያት አባቴ 'ቆሻሻ ናቸው' ስላለኝ ነው ብዬ ነገርኳት:: ቀን ጠብቃ ሊጠይቀኝ ሲመጣ እኔ ባለሁበት:

«ዘመዶቼን ንቀህ፣ የምወዳት እህቴንና ልጆቿን ንቀህ ለምን ከእኔ ጋር ኖርክ? ለምን ከእኔ ወለድክ?» አተኩሮ እያየት አልመለሰላትም::

*አራተኛ:* ለአባቴ እንዳዳላ የሚገፋፋኝ የእሷ የእማማ ፀባይ ነው:: ብዙ ጊዜ እናቴ በእኔ ድርጊት አለመስማማቷን የምትገልፀው መጀመሪያ በእርግማንና በቁጣ (እነዚህ አይነጣጠሉም) ነው:: 'ብዙ ጊዜ እናቶች ልጆቻቸውን ይከላከላሉ፣ አባቶች ግን ይማታሉ' ሲባል እሰማለሁ:: በእናቴ ሁኔታ (የአባትነትና እናትነትን ሃላፊነት ደርባ ለያዘች) አዳጋች አባባል ሊሆን ይችላል:: እናቴ ትደነቂያለሽ የእርግማንዋ መብረቅ ያላስተካከለኝ ከመሰላት አካሌ ላይ ቀጥታ ጥቃት ትፈፅማለች:: ሁለት ማጥቂያ መሳሪያዎች ነበሯት: በወጥ ትኩሳትና በኑግ ዘይት የጠቆረ ማማሰያና እንደ ዘመሚት ጭኔ ላይ የምትተክል ቁንጠጣ(እጇን ጭኖቼ መሃል አስገብታ በአውራ ጣቷና በአመልካች ጣቷ ጭኔን፣ ጭኔ ካላጋጠማት ዳቦዬን ትቆነጥጠኛለች)::

## የቀመስሽ አትጠፊም......

እናቴን እወዳታለሁ:: ለምን? በቃ እናቴ ናት:: ደሞ እፈራታለሁ:: ለምን? አምላክ እንዳዘዛት ወይም ሃይማኖቷ እንደሆነ ሁሉ የምጠላቸውን ነገሮች ሁሉ ታስደርገኛለች:

*አንደኛ:* ድንች ወጥ አልወድም: እሱን ታበላኛለች:: 'ጥጋበኛ፣ ይሄን ያጣ አለ፣ አትሞላቀቂ'

*ሁለተኛ:* እጇ ስጠላ:: ይሄንንም ከመላዕክት ጡት እንደታለበ የመለኮት ወተት ታጠጣኛለች:: 'እያየሁሽ ትጠጪታለሽ፣ እየደፉ ጠጣሁ የለም፣ አለበለዚያ አጮልሻለሁ'

*ሶስተኛ:* ትምህርት ቤት ያደከመኛልና አርፍጄ መተኛት እወዳለሁ: ከጠዋቱ አንድ ሰአት ላይ መኝታ ቤቴ መጥታ ትቀሰቅሰኛለች:: የምትቀሰቅሰኝ ደሞ በእርግማን ድርሰት ነው: 'አሁን ስምንት አለፈሽ: ትልቅ ልጅ ነሽ:: አንቺን ከአልጋ ሳስነሳ የራሴ እንሰኝ? አርፈሽ ተማሪ:: ሌላ ምን ስትሰሪ ነው:: ማታ ቶሎ አልተኛም ትያለሽ፣ ጠዋት እንደ ግንድ ትጋደሚያለሽ:: ቂጣም:: ከአሁኑ ቂጥ አውጥታ ምን ታደርግ?' ወዘተ......ነፍስ አውቄ በራሴ ከአልጋዬ መነሳት እስከችልና እስከለምድ ድረስ የተረተረቻቸው እርግማኖች ተፅፈው ቢሰበሰቡና ቢጠረዙ 500 ገፅ የሚሆን *የትደነቂያለሽ ራዕይ ለሽሮሜዳ ጨጨዎች* የተባለ ሌላ የአዲስ ኪዳን ምዕራፍ ይወጣዋል:: መልስ ከሰጠሁዋት የእርግማን ገመዱ አዲስ ቀስቃሽ ጉዳይ ያጋጥመውና ያልጠበቅሁት አይነት ይረዝማል፣ ቋጠሮውም

ይጠብቃል። ወገቧን ይዛ፣ አልጋዩ ደርሀ ቆማ ቁጭት፣ ስድብ፣ ተረብ፣ ማስጠንቀቂያና ሐዘን የተቀላቀለበት ንግግሯን ታነበንባለች። የምትደመድመው አገሬቷን፣ የማላውቃቸው ዜጎችን፣ እግዚአብሄርን፣ እኔን፣ አባቴንና ራሷን አማ'ራ' ነው።

ሐይለኛነቷ (ለምን 'ሃይለኛነት' ይሉታል?) የታወቀ ስለሆነ ሳጠፋ ያገኘኝና እንድቀጣ የፈለገ ማድረግ ያለበት እኔ ላይ 'ጠብቂ' ብሎ ገቶ ለእናቴ ጥፋቴን መንገር ነው። (እኔ ዓላዛር ማማሰያውን 'የትደነቂያለሽ ሚሳይል'፣ ቁንጠጣውን 'ድምፅ የሌለው መሳሪያ' ይሉት ነበር) ብዙ ጊዜ እናቴ እንደዚያ የምትበድለኝ አባቴ ስለሌለ ይመስለኝ ነበር። ተቆንጥጬ ሳለቅስ በአእምሮዬ የሚመጣው ቀጭኑ፣ ሲያቅፈኝ እንደ አሊቭ ዘይትና ትኩስ ሻይ ውስጥ እንደተነከረ ግሊሲሪ የሚሸተኝ አባቴ ነው። እየተቆነጠጥኩ ወደ በማማሰያ እየተከካሁ እያለሁ የደብረ ዘይት ፀሐይና ቀይና ነጭ ሰንበር ባለው ጨርቅ የተሸፈኑት የሬስቶራንቱ ጠረጴዛዎች ጋ አስቀምጦ ኩተሌት እየቆረጠ የሚያበላኝ አባቴ ውል ይለኛል። በዛን ጊዜ 'እናትሽን ትወጂያታለሽ?' ተብዬ ብጠየቅ መልስ ለመስጠት ለማሰብ ቆም ማለቴ አይቀርም።

በከፊል የማይገባኝና ሙሉ በሙሉ የሚያስፈራኝ የማስገደጃ ጥበቧና የእርግማን ቋንቋዋ ሲበዛብኝ 'አባባ ጋ ልሂድ' እላታለሁ። ወደ ደብረዘይት መሄዴን በእምቢታ ከደመደመችው፣ አባቴ በትልቅ አራት ማዕዘን ሲራሚክ ድስት ለሳምንት በልቼ የማልጨርሰው ወርቅ የመሰለ ላዛኛ ይዞልኝ ይመጣል። (እናቴ 'በይ ተይኝ ይሄን ልፋጭ ነገር ምን እንዳስገባበትም አይታወቅ። በእሱ ቀማኛ ሆነሽ እንዳትወጪ። የዛ ሬስቶራንት ገንዘብ ማግሹ የራሴ ነው' ትላለች)። 'ዐይኑን አላይም' ብላ ወደ ምትሄድበት ትሄዳለች። አንዳንዴ በነገሯ ስታደክመው መሰለኝ፣ ከእሷ አርቆ ታች ፒያሳ ክሪያዚስ ይወስደኛል። እዛ የምፈልገውን አብልቶኝ ገብረተንሳይ ኬክ ቤት ወስዶ ባቅላቫ ይገዛልኛል።

እንዲህ ሁሉ ሲሆን ስለ አባቴና እናቴ የልጅነት ወዳጅነት ብዙ የማውቀው ነገር የለም። ትምህርት ቤት እንደተዋወቁ አንዳንዴ በጨዋታ መሃል እንደ ወሸመጥ ገብቶ ሲወራ ወይም ስታወራ እሰማለሁ።

እዛ ሸሮሜዳ የተባለ ሰፈር ስንገባ (ስሙ አያስጠላም?) ሰባት አመቴ ነበር። ወደ ሸሮሜዳ ያስደዳት፣ እንቅልፍ የነሳት 'ያ ቅዠት' እያለች የምታወራው ሕልምዋ ነበር። የቅዠቷን ዝርዝር ብረሳም ስታወራ እንደሰማሁት ዋናው ዋናው እንዲህ ነው:

ቤታችን ከቁርጡማ ወንዝ አጠገብ ነበር። እና ሁልጊዜ እኩለ ሌሊት ሲሆን ከእንቅልፏ የባነነች ይመስላታል። ትንቃ አትንቃ እርግጠኛ አይደለችም። (በእሷ እምነት በዛ ሰአት ብቻ የሚቀሰቅሳት ምናምንቴው

ነው::) 'እንደባነነች' ሳትና ለቅሶ የተቀላቀለበት ድምፅ ከቁርጡሜ ወንዝ ሲመጣ ትሰማለች:: ይሄ ድምፅ እተኛችበት ድረስ እየተራመደ መጥቶ እምቢ ብላ ብትታገልም ከአልጋዋ እጇን እየጎተተ ያወጣትና ወንዝ ዳር ወስዶ አንድ ሰውዬ ወይም ፍጡር ፊት ያቆማታል:: ሰውዬው ወይም ፍጡሩ ጥቁር፣ ረዥም፣ አጥንታም፣ የገላው ቆዳ አመድ የመሰለ፣ ጀርባው ጎባጣ፣ የታችኛው ጥርሶቹ ሰልፍ ከላይኛው ጥርሶቹ ድርድር ስር የተወሸቁ አስፈሪ ፍጡር ነው:: ይሄ ቅዠት በየቀኑ ስለሚመጣባት መተኛት አልቻለችም:: ለነፍስ አባቷ ነግራ ቤቷን፣ እራሷንና ዘርዐይን ጠበል ብታስረጭና ጠበሉን በጠርሙስ እየሞላች ቤቷ ዙሪያ ግድግዳና አጥር ላይ ብትስቅል የሚተዋት አልሆነም:: አዋቂ እንደ መከራት(ቄስ ይሁን ኮከብ ቆጣሪ እንጃ) በውርስ ያገኘችውን ይሄን የመሃል ከተማ ቤቷን ዶክተር አባይነህ ለተባሉ ሰውዬ ሽጣ ሽሮሜዳ መጣች:: ያ ቅዠት ግን የተዋት አሁን አሁን እንደምትለው ከቁርጡሜ ስለሸሸች ሳይሆን ከአባቴ ከተለያየች በሁዋላ እንደሆነ እየሳቀች ትናገራለች:: ዶክተር አባይነህ እዛ ቤት ከገቡ ጀምሮ ይቃዡ እንደሆነ ደጋግማ ጠይቃቸው ሳትና ለቅሶ ከወንዙ እንደማይሰሙ፣ ወደ ወንዙ ራቁታቸውን ጎትቶ የወሰዳቸው ድምፅ፣ ራቁታቸውንም አቁሞ የሚያያቸው ሰይጣን እንዳሌለና በዚህ አይነት ነገርም እንደማያምኑ ነገሯት::

እናቴ ይሄን የሚያምር ቤት የሰራችው የአባቷንና የእናቷን ቤት ሽጣና ከዛ ባገኘችው ገንዘብ ላይ ደሞ ከታላቅ ወንድሟ በኑዛዜ ያገኘችውን ጨምራ ነው:: ከአባቴ የተፋታችው በዚህ ሳይስማሙ ስለቀሩ ነው:: አልፎ አልፎ እንደምትለው አባቴ 'ዘሩ' የፈለገው ገንዘቧን ወስዶ ሬስቶራንት አቋቁሞ የፈረንጅ ምግብ እየሸጠ መክበር ነው:: እሷ ግን ፈቃደኛ አልሆነችም::

አዲሱ ቤታችን ተሰርቶ ከማለቁ በፊት ሽሮሜዳ የተባለው ቦታ የሄድኩት ሁለት ጊዜ ቢሆን ነው:: ያን ጊዜ እናቴ ከአናጢዎች፣ ከአቶ ብርሃን ወይም ከቄስ ታዚና ጋር ቆማ ስታወራ እስኪሰለቸኝ የማየው እየተጯጯሁ ኳስ የሚያለፉትን ዓላዛር፣ ቸርነትን፣ እዝራንና ብዙ የዛ ሰፈር ልጆችን ነበር:: አዲስና ሴት ልጅ ስለሆንኩ ከእነሱ ጋር በቶሎ መግባባት አልቻልኩም::

አንድ ጊዜ እናቴ እግር ስር ቆሜ ከእኛ ግቢ ጀርባ ያለ ቪላ ቤት ከሚያሰራው ሰይፌ ከተባለ ሰውዬ ጋር እናቴ ቆማ ስታወራ፣ ልጆቹ የሚጫወቱባት ነጭና ጥቁር የቆዳ ኳስ እየተንከባለለች መጥታ ገጥሚ የቆምኳቸው እግሮቼ ስር ቆመች:: ልጆቹ 'ምቺ.እት!' ብለው ሲጮሁ በፍርሃት ከኳሷ ሸሽቼ ወደ እናቴ ተጠጋሁ::

'ምቺላቸው እንጂ? የምን ማፈር ነው? የሰፈርሽ ልጆች እኮ ናቸው' ቢሉኝም፣ እየተቁለጨለጭኩ በዝምታ እየሁዋቸው:: ዓላዛር የተባለው

ምናልባት 9 ወይም 10 የሚሆነው ልጅ ወደ እኔ እያለከለከ መጣ:: በላብ የረጠበ ነጭ ካናቴራ ለብሷል:: የገፁ ቆዳ ጥሩ ሆኖ የበሰለ ነጭ የስንዴ ዳቦ ይመስላል:: እያየሁት ሳላውቀው ፈገግ አልኩ:: ፈገግታዬን ተማምኖ መሰለኝ ቀረበኝና እጁን ዘረጋ::

‘ዓላዛር እባላለሁ’ አለኝ *አበዛኸው* አይነት በማፈር ፊቴን እናቴ ቀሚስ ውስጥ ደበቅሁ:: እማማና ሰይፉ ሳቁብኝ:: ዓላዛር ትንሽ ተለማምጦኝ (ይመስለኛል፣ ይሄ መለማመጡ ትዝ ባይለኝም) በእምቢታዬ እየሳቀ ወደ ጨዋታው መመለስ ጀመረ:: ፊቱን እንዳዞረ ከእማማ ቀሚስ ወጣ ብዬ አየሁት:: ከጀርባው ያየሁት በትንሹ ሸፈፍ ያለ አረማመዱ፣ ከገላው የተጣበቀው በላብ የረጠበ ካናቴራው፣ ገመዱ ተፈቶ የሚጎተት ጥቁር ስኒከር ጫማውን ነው:: ዓላዛር ብርሃነ መስቀል የተባለውን መልከመልካም የተዋወቅሁት እንዲህ ነበር:: አንዳንዴ ትንሽ የመሰለው የአልዩ ሸፋፋ አካሄድ ዛሬ ድረስ ትዝ ይለኛል:: አንጀቴን ይበላኛል:: ‘ሸፋፋ እንዴት አንጀት ይበላል?’ አልባል

ቤታችን ማዕዘኖቹ በሸክላ፣ የቀረው በብሎኬት የተሰራ፣ ሶስት መኝታ ቤቶች፣ አንድ ሳሎን፣ አንድ ምግብ ቤት፣ አንድ ማድቤት እና ከጀርባ ደሞ ሶስት ትናንሽ ክፍሎች የነበሩት ሰርቪስ ቤት ያለው ትልቅ ቤት ነው:: ዙሪያውን ደሞ አትክልት መትከያ ሰፊ ቦታ ነበር:: እቃችንን እንዳስገባን ግቢው በቆርቆሮ ታጠረ:: ያ የታጠረበት ቆርቆሮ ከፊሉ በአፈር ተበልቶ፣ ዝጎና ተበሳስቶ ዛሬ ድረስ አለ::

ከቤታችን በስተግራ የተማም አባት አቶ መሐመድ ባለሱቁ፣ በስተቀኝ ደሞ የገርማሜ አጎት ይኖራሉ:: ከቤታችን ፊት ለፊት በደረቀ ሲሚንቶና አፈር የተሸፈኑ ልጃገረዶች ብዙ ጊዜ ሰኞ ማክሰኞና ገመድ ዝላይ የምንጫወትበት ሜዳማ ቦታ አለ:: ከዚህ አለፍ ብሎ በቅርብ ክሊኒክ የተሰራበት ድሮ ባዶ የነበረ ድንጋያማ ቦታ ነው:: ከዚህ ፈቀቅ ብሎ የታዚና ሆቴል ነው:: ከሆቴሉ አለፍ ብሎ ደሞ የሰፈር ጎረምሶች የሚያዘወትሯት አንዲት ደቃቃ ድልድይ አለች:: ከእዛ ተሻግሮ ግራና ቀኝ ብዙ መኖርያ ቤቶች አሉ:: ቤቴ በረንዳ ላይ ቆሜ መንገዱን ተሻግሮ፣ ከመንገዱ ፈቀቅ ብሎ የተሰራውን የዓላዛርን ቤት ማየት እችላለሁ:: ከነዓላዛር ቤት አልፎ እወዲያ አንድ ኮረኮንች መንገድ አለ:: ኮረኮንቹን ተከትለው ሲሄዱ፣ ብዙ መኖሪያ ቤቶች፣ ጉርጉሱም ሆቴልና አንደኛ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ የተማርኩበት *የንጋት ኮከብ ትምህርት ቤት* አሉ:: በእነዚህ መሃል ከመጫወቻችንና ከክሊኒኩ ጎን ወደ ስድስት ኪሎ የሚወርደውና ወደ ጎጃም የሚወስደው ብቸኛው የአስፋልት መንገድ ነው::

ሽሮሜዳ ስገባ ለመጀመሪያ ቀን የጅብ ጩኸት ስሰማ ቁጥራቸው ትዝ ለማይሉኝ ቀኖች እውጭ መውጣት ፈራሁ:: ምሳ ለመብላት ከትምህርት ቤት ስመለስ ወና ቤታችን ገብቼ እናቴ ያስቀመጠችልኝን የተገኘውን

ምግብ ስበላ ጅቦች ድምፃቸውን አጥፍተው ተከትለውኝ የመጡ እየመሰለኝ እፈራ ነበር:: አንዳንዴም ጠብቀው የሚነክሱኝ እየመሰለኝ በባዶ ሜዳ ወደ ምሄድበት ልቤ እስኪፈርስ እሮጣለሁ::

ቤቱ ተሰርቶ አልቆ የገባን ሰሞን እናቴ ያለችኝን አልረሳም:

'አሁን እኔና አንቺ ብቻችንን ነን፣ ወደ ፊት የሚሆነው አይታወቅም፣ ማስብ አለብሽ:: ትምህርትሽን በደንብ ትከታተያለሽ፣ ይሄን ጓሮ መቆፈር ትለምጂያለሽ፣ ጎበዝ ሁኚ'

ይሄን ካለችኝ በሁዋላ (ቃሏን ለመጠበቅ ይሁን እኔን ስነስርአት ልታስተምር ወይ ሁለቱንም) የሰርቪሱ ቤት አንዷ ክፍል ቀስ በቀስ በዶማ፣ በመኮትኮቻ፣ በአካፋና በመሳሰሉት መሳሪያዎች መሞላት ጀመረች::

ከዕለታት አንድ ቀን የታዚና ሆቴል ባለቤት ልጅ አዝራ፣ 'ቤቴን የማሳምርበት አትክልት ባገኝ' እያለች እናቴ ስታወራ ሰምቶ ከእንጦጦ ብዙ አይነት የዱር ተክሎች ይዞላት መጣ:: ካመጣቸው ሁሉ የጸደቁት በረንዳችን ስር የተተከለችው ደካማ የመሰለች ሐረግና ሊጠወልግ ደርሶ ከሚጣል ብለን የተከልነው የሰንደል ዛፍ ነበሩ:: የሰንደል ዛፉን የሰንደል ዛፍ መሆኑን ያወቅሁት እጅግ ከርሞ ነው:: ዛሬ ድረስ ነጫጭ አበቦቹንና ከመሃላቸው በነሲብና በድንገት የተረጨ የሚመስለውን ሐምራዊ ቀለም አልረሳም::

ደን እየሄዱ ከሚመጡ ልጆች ጋር ሽርክና ለመፍጠርና የምሰራውም ስለሌለኝ አንድ አሮጌ የፎቶ አልበም ወስጄ የሚያመጡልኝን ቅጠሎች እየቀነጠስኩ በመከተትና በከባድ እቃ በመተምተም፣ ወይም ጨርቅ መሃል አስተኝቼ በካውያ በመተኮስ በሕይወት ያሉ የመሰሉ የቅጠል ሐውልቶችን መስራት ጀመርኩ:: ቆይቶ ይሄን ያዩ የጓደኛዬ የፀናዕል አባት በአንዱ የልደት ቀኔ ትንሽዬ ማይክሮስኮፕ ገዙልኝና ቅጠል በጣሽነቴ ባሰብኝ:: ትልቅ ሆኜ ነገር አለሙን እስካቆም የሶስት ቅፅ ተክሎች ቅጠል ሰብስቤ ነበር:: ሁለቱ በስድሳ ዘጠኝ አመተምሕረት በአሰሳ ሰሞን ተሰርቀውብኛል፣ ሶስተኛው እስከ አሁን ቢኖርም ገልጬ የማየው ባር ባር እያለኝ ነው:: ሁለት የሰንደል ቅጠሎች ገፅ አራት ላይ ነበሩ::

እማማ ቅዳሜ ቅዳሜ የሚበላ አስቀምጣልኝ፣ ለሽንኩራ የሚሆን ሳንቲም ሰጥታኝ ወደምትሄድበት ትሄዳለች:: ብዙ ጊዜ የምትወጣው ከአቶ አባይነህ ጋር ነው:: እኚህ አባይነህ ከባምቢስ ሽሮሜዳ ድረስ በአሮጌ ሲትሮይን መኪናቸው ይመጡና፣ እሱን ከግቢ ውጭ አቁመው እናቴ እስክትለባብስ እጃቸውን እያሻሹ ሶፋ ላይ በዝምታ ይቀመጣሉ:: ለግማሽ ሰአት ያህል ጠብቀዋት ከመኝታ ቤት ትወጣለች:: 'ጨርሼአለሁ' ስትላቸው፣ ቀደም ብለው ሄደው የመኪናቸውን በር ከፍተው ያስገቧትና

ወደሚሄዱበት ይሄዳሉ:: አባይነህን ደግሜ የማያቸው ምናልባት ከሳምንት ወይም ከሁለት ሳምንታት በኋላ ነው:: በመጀመሪያ ሰሞን ባይመጡ እወድ ነበር:: እናቴ ግን እሳቸው ሲደውሉና ስልክ አንስታ ስታዋራቸው እንዴት እንደሚያቁነጠንጣት ላይ እረሳሳታለሁ:: የሰማሁዋት ይመስለኛል፣ ቀኝ እጅዋን ቀኝ ጡቷ ላይ ጣል አድርጋ፣ በግራ እጇ ስልኳን ጆሮዋ ላይ ደግና፣ በተመሰጠ ፊት 'ስኳሬ' ስትል:: 'አባይ ወለላዬ' ስትል፣ ትርጉሙ ባይገባኝም የሆነ ትክክለኛ ነገር እንደተናገረች፣ አባይም የሆነ ትክክለኛ ሰውዬ የሆኑ ይመስለኝ ነበር:: ብቻዬን ትተውኝ በመሄዳቸው ቅር እንዳይለኝ ብለው፣ ወይ እናቴን ሳላለቅስ ስለለቀቅሁላቸው እንደ ውለታ መሰለኝ ሎሊ ፖፕ ከረሜላ ያመጡልኝ ነበር::

እነሱ ከሄዱ በሁዋላ እኔ ከሰፈራችን ነጋዴ ከዋሕድ የምፈልገውን ያህል ሸንኮራ ገዝቼ፣ ልጆችን በሸንኮራው ስደልልና ሳፎካክር፣ ለጋስ ስሆንና ስነፍግ ቀኑ ሳላስበው ያልፋል::

ሸንኮራ ሻጩ ዋሕድ ሰፈር ስገባ ጀምሮ የማውቀው ነጋዴ ነው:: መንገድ ዳር ካሉ ድንጋዮች እንዱን ጠፍጠፍ ያለውን መርጦ ሙሉ ቀን እዛ ሲቀመጥና ከዚያ ሲነሳ፣ እዛ ጎን እየተመላለሰ ግስላውን ሲያጤስ ይውላል:: ቀትር ሆኖ እናቱን ፀሐይ ብትነድለውም ያንን በዘፈን ዣንጥላ እያበረደ እስኪመሽ፣ ዐይን እስኪይዝ ይቆያል:: ***የዚህ ሰፈር ሰዎች ምግብ አያምራቸው፣ እጅሬ ሸንኮራ ገብቶ ከቤታቸው::*** (በ ***አመልሽ ወርቅ ነው፣ ለአንጥረኛ ልስጠው፤ ሁሉም አሰርቶ አፍ አፉ ላይ ያርገው*** በተባለው ዘፈን ዜማ)

እማማ ከሄደችበት ተመልሳ ገና እግሮችዋ በረንዳ ሲረግጡ:

«አንቺ! ቤቱን በዚህ በሸንኮራ ልጣጭ አበላሸሸው!» ትላለች:: ዋሕድን ትረግማለች:: ሳንቲም ሰጥታ ገዝተሽ ብዬ እንዳላለችኝ ያደርጋታል:: ይሄ አቋሟ ራስ ምታት ይሆንብኝ ነበር:: በሰፈራችን ያሉ የተለያዩ እናቶች ንጭንጫቸው ከአንድ ኩሬ የተቀዳ ነው:: ልጅ የወለዱ ብዙዎቹ የሰፈሩ ሴቶች በዚህ አይነት ነጨናጫነት የተካኑ ነበሩ:: ይሄ የጋራ በየቤቱ የሚያጋጥመኝ ፀባይ እናቴን የተለየች ሐጢያተኛ አድርጌ እንዳላያት፣ በተጨማሪም ነገሯን ችላ እንድለው ወይም እንድንቀው አድርጎኛል:: በእናቷ ንጭንጭ ያልተነጩች ልጃገረድ እዛ ያለች አይመስለኝም::

ሰፈሩንና ልጆቹን ለመልመድ ጊዜ አልወሰደብኝም:: የተላመዱ ነባር ልጆች ተጠራርተው አጋም ለቀማ እንጦጦ ሲወጡ እነሱን ተከትዬ እንድሄድ እናቴ አትፈቅድልኝም:: ታዲያ ከታች ሆኜ የእንጦጦን ወገብ፣ ደረትና ደኑን እያየሁ እመሰጣለሁ:: ይሄ አካላዊና መንፈሳዊ እርቀት አንዳንድ የማልረሳው ቁም ነገር ያሳየኛል:: መንገድ ሊሰራ ገደል ሲናድ፣

አልፈርስም ብሎ አምዖ የቀረ ከእንጦጦ ተራራ ደረት ላይ ምናልባት አንድ ሃያ ሜትር ያህል አሞጥሙጦ የወጣ ትልቅ የድንጋይ ምላስ አለ (በቅፅል አሞራው የምንለው):: ካየሁት ቀን ጀምሮ ታዲያ እዛ የድንጋይ ምላስ ላይ ወጥቼ አዲስ አባን ወደ ታች ማየት እመኝ ነበር:: አንዳንዴ እናቴ ከዓላዛር እናት ከሮዛ ጋር እኔንና ዓላዛርን ከመኪና ሁዋላ ጭነውን ደብረ ሊባኖስ ሄደን ስንመለስ ሁልጊዜ እንጦጦ እስክንደርስ አልተኛም:: 'እዛ ድንጋይ ጋ ውሰዱኝ' እላለሁ:: 'ማለፊያ መንገድ የለም' ይሉኛል:: ስንፍናቸውና ንፉግነታቸው እንደሆነ አሳምሬ አምናለሁ::

ወዳጆቼ በደን የፍራፍሬ ወለላ ሰክረው ከእንጦጦ እያሽካኩ ከሄዱበት ሲመለሱ ልቤ በቅናት ትፈርሳለች:: እናቴ እንዳልሄድ የምትፈልግበት ምክንያት የገባኝ በኋላ ነው:: ተራራ ወጥተን መልቀም ያልቻልን፣ ያልተፈቀደልን ልጃገረዶች የሄዱት ሲመለሱ እንጠብቃለን:: ለቅመው ካመጡት ይሰጡናል:: ከሁሉም የበለጠ የሚያቀርበኝ 'ቸርነት' የሚባል ልጅ ነበር:: ለቅሞ ያመጣውን ሳልለምነውና ሳይሰስት ይሰጠኛል:: ይሄንን ከሌሎች ልጃገረዶች ጋር እንቀራመታለን:: ሴቶቹ እኔን ሲጠቀሙብኝ፣ እኔ ቸርነትን መጠቀሚ እንደ ደንብ ሆነ:: ከሁሉ ወንዶች ልጆች ግን የምወደው ዓላዛርን ነበር:: ቅላቱ ሊሆን ይችላል:: ዓላዛር ጨዋታ ያለበት የትም ቦታ ይገኛል:: የልደት ቀን ሲከበር ተሰባስበን የምንገናኝበት ቦታ ግን መደብ ምርጫ ሆኖ ሳይሆን አይቀርም፣ ቸርነት ፀናዕል ቤት አይመጣም:: ቸርነት ማራኪ ደግነት ቢኖረውም ከዓላዛር በስተቀር የሚያቀርቡት ብዙ ልጆች አልነበሩም:: ይሄ በጣም ባይሆንም እኔንም እንደሚመለከተኝ ገባኝ:: እንደ ዓላዛርና እንደ ሌሎቹ ሃብታም አይደለሁም:: ቤቴ የሚያምር ቢሆን እንኳን የምበላው የምለብሰው እንደ ደሃ ነው::

አንድ ሰሞን እናቴ ለወር ያህል ታማ ችግር ውስጥ ገባን:: 'በሽታው እረፍት ይፈልጋል' ተብላ ቤት ስትሆን ስራዋን ስላቆመች ገንዘብ አልነበረንም:: ያስቀመጠቻትን ብር ልትጨርስ ስትል አባቴ መጥቶ እንዲወስደኝ ስልክ ደወለችለት:: እሱ ግን አልመጣም:: የተለመደ የምፈራውን ንጭንጭዋን ሊሸሽ መስሎኝ ነበር:: ለምን እንዳልመጣ እንድትነግረኝ ስነዘንዛት::

'ችግሬን ባልነግረው ኖሮ ይመጣ ነበር:: አንቺን አብልቼ ማሳደር እንደማልችል ለአንቺም ለአለምም ሊያሳይ ነው' አለችኝ:: ያለችኝ ሙሉ ለሙሉ ባይገባኝም፣ የተለመደ እሱን ማጣጣያ ቴክኒክ መስሎኝ አላመንኩአትም:: ማታ ላይ የዓላዛር እናት እትዬ ሮዛ፣ በበነጋታው ደሞ ሰይፈ፣ ከትምህርት ቤቱ ጀርባ ያሉ ከእናቴ ጋር ብዙ ጊዜ ቤት እየመጡ ቡና የሚጠጡ አንድ 'ሮባ' የተባሉ ስውዬና ዶክተር አባይነህ ረድተውን 'መንገድ ከመውደቅ' ወይም 'ቤቱን ሸጠን ከመሄድ' (እናቴ እንደምትለኝ)፡ ዳንን:: ያን ሰሞን ብቻችንን ስንሆን ደጋግማ አነስ ያለ

ቤት ገዝታ የሚከራይ ቤት መስራት እንደሚያስፈልጋት ዕንባ እየተናነቃት ስትናገር ሰማኋት:: 'ሰዎቹን ለምጄአለሁ፣ ሰፈሩን ለምደሻል፡ አሁን ተነስቼ ብሄድ አንቺም ትንከራተቺብኛለሽ' የብዙ ጊዜ ልፋቷ እኔን ያለ ዘርአይ እርዳታ ማሳደግ እንደምትችል ትልቅና ትንሽ ፈተናዋን ማለፍ የነበረ ይመስለኛል::

ከፍ ስል የእማማ ቁንጠጣዋና የማማስያው ቅጣት አቆመ:: ግን በሁለት መልክ ከአፏ በርታ አለች:: *ንጭንጭና መሳም*:: ንጭንጭዋ የበዛብኝ ሰሞን ልክ እንደተደበደብኩ ሁሉ ልቤ ውስጥ ቶሎ የሚመጣው አባቴ ነው:: ለብቻዬ ለመጀመሪያ ጊዜ እሱ ጋ መሄድ ስጀመር እናቴ የቤት ስልክ አስገባች:: አርብ ደብረዘይት ሄጄ እሁድ ማታ አዲስአባ ስመለስ ናዝሬት አውቶቡስ ተራ ለአንድ ሰአት ጠብቃኝ ገና ከተሳፈርኩበት መኪና ስወርድ ስታየኝ ፊቷ በዕንባዋ ታጠበ:: እንደምትወደኝ የገባኝ ያኔ ነው:: ያ ቁጣዋ፣ እነዛ ቆንጣጭ ጣቶቿ፣ ያ ልብ የሚሰብር የእርግማን አማርኛዋ ፈርሶ 'ሴቶች ይሆናሉ' እንደሚባሉት ሆነች::

ያን ዕለት ማታ እናቴ፣ ሮዛና የማላስታውሳቸው ሰዎች ሳሎን ተቀምጠን ለእኔ የሞቀ እጇ ሰጥታኝ በሃሳብ ሰምጣ ባዶ አየር ላይ አፍጣ አይቼአታለሁ:: ያን እጇና ያን በእጇ የተኳለ መደ'በሯን አልረሳባትም::

«አይዞሽ ትደነቅ፡ ጎበዝ እናት ነሽ:: አታስቢ፣ ደሞ አድጋለች:: ደብረዘይት ብቻዋን ደርሳ መጣች እኮ» አሏት እትዬ ሮዛ

«ለልጄ እንጀራ አባት አልሰጣትም:: ያ ከርፋፋ ዘሩ እኔን ቢክደኝም እሷን አልካደም:: ወጣት ስላገባ የሚረባ ሴት ያገኘ መሰለው:: እኔ ልጅት ማር ነኝ:: የቀመሰኝ ይናገረው» አለች::

«አንቺ ደሞ ልጅ ፊት እንዲህ ይባላል?» አሉ አንዷ

«ምን ይገባታል? አታዳንቁ»

«እንዳንቺ ግልፅነት ቢቻል» አለች የዓላዛር እናት ሮዛ

«የተመቸሽ:: የተመቸው ግልፅ አይሆንም»

«ዘርዐይን አሁንም ትወጂዋለሽ?» አሉ አንዷ

«ለምን አልወደውም? የልጃገረድነቴ እኮ ነው:: ሲያጥብል ሲችልበት፣ *'የሐረር መንደሪን ብርቱካን ቀምሼ፣ ተመለስስ ቢሉኝ መቼ ተመልሼ'* ይለኝ ነበር:: አሁንም እኮ ያቺን ነገር ይፈልጋል፡ እንዴ! እኔ ልጅት መጫወቻ ነኝ?»

ታዲያ እኔ ከነዓላዛርና ከነቸርነት ጋር እየዋልኩ በትንሹም ቢሆን ይህቺ ይህቺ እንዴት አትገባኝም?

አንዳንድ ቀን ጠዋት ላይ ከቤተክርስቲያን ስትመለስ ወደ ተኛሁበት መጥታ፣ በእንጦጦ ብርድ የቀዘቀዘ ነጠላዋን እንኳን ከላይዋ ሳታወርድ

ፊቴን በጠመ አፏ ትጨመጭመኛለች:: የአገራችን እናቶች ለልጆቻቸው ያላቸው ተዓራሪ አቋም ያኔ ታየኝ:: ሁሉ እናቶች ይራገማሉ:: ሁሉ እናቶች ይሳደባሉ፣ ይቆናጠጣሉ:: ሁሉ እናቶች እንቅፋት መቶን ስንደማ እንደ ሞትን ሁሉ መርዶ ይጠራራሉ፣ ድንኳን ሊተክሉ ይደርሳሉ:: በጣም ከመውደዳቸው የተነሳ የሚሰሩት እየጠፋቸው ነው? ፍፁም እንድንሆን ስለሚፈልጉ ግን መሆን አለመቻላችን እያበሳጫቸው ነው? ብዙዎቹ እናቶች እንደ ዘመኑ ተጣብሰው ሳይሆን በሰው አገናኝነት፣ በዘመድ አዝማድ ስላይነትና መሪነት እየተጋቡ በኋላ የተገባላቸው ቃልኪዳን ስንካላ መሆኑን ተረድተው ምሬታቸውን እየተወጡብን ነው? ሲመቱን ባላቸውን እየመቱ ነው? መመለስ አልችልም::

እንጻልኩት ዕድሜዬ ከፍ ሲል፣ የእናቴ የቁጥጥር ገመድ ሲበጠስ፣ ወይም የመዋሸት ድፍረት ሳገኝ፣ ከዓላዛር፣ ከማሚ፣ ከወለተ መስቀል፣ ከቸርነትና ከሌሎች ልጆች ጋር አብሬ ወደ እንጠጠ ተራራ መሄድ ጀመርኩ:: የመጀመሪያው ጉዞዬ 'አሞራው' ወደ ተባለው አለት ነበር:: በጀርባው ዞረን ልጆች 'ተይ ተይ አንሸራቶሽ ብትወድቂስ' እያሉኝ እላዩ ላይ ወጥቼ ጠንካራ ምድራዊ ጥቁረቱ ላይ ተኛሁ:: ትኩሳቱ ገና ከምጣዱ እንደወጣ ህብስት ጣፈጠኝ:: የናቅሁዋትን ሽሮሜዳና ሰዎቹን እዛ ላይ ሆኜ በአንድ ትኩረት ዘግኜ ሳያቸው አሳዘኑኝ:: ዛሬ ራሴን በምናቤ አየዋለሁ ከሐምራዊ ቀለም እንደተሰራ መስቀል (እናቴ ሁልጊዜ ሃምራዊ ቀለም ያለው ቀሚስ ታሰፋልኝ ነበር) እጆቼን ግራና ቀኝ ዘርግቼ ......ዓይኖቼን ከድኜ.....ዙሪያዬን የዝንብ፣ የንብና የሌሎች ነፍሳት ዛዛታ ......እዛ እዛ ታች፣ አምጣ ያመጣችኝ እማማ አዲስ አባ......ዜጎቿ ላይና ታች እየዳከሩ......እየወጡና እየወረዱ......የቀዝቃዛ አየር ጠረን ከእንጠጠ ማርያምም ከዛ ከየረርም ከዛ ከአቃቂም ከዛ ከሱሉልታም ከማያየኝ ከማላየው የሚፋጅ የውስጥ ሱሪዬን ስሞ ሲያልፍ......በፍቅሩ የመረዘኝ......የዚህቺ እንጠጠ አልባብ ወንድ በማያውቅ ማሕፀኔ ሲጎሰጎስ ......ያ የእንጠጠ ፍቅር ዘለሰኛ ቢሆን ነፋሷም ትዝታ ቢሆን የደኑ ፍቅር ባቲ ቢሆን ማንን አረግዝ ነበር?......በፍስሐ በሚፈራገጡ እግሮቼ የመታሁዋቸው ድንጋዮች ናዳ ሆነው ታች ከሰላሌ ተንሮ የመጣ የገበሬ ነጋዴ ረብሸዋል......ብስቅ ሰዎቹን መናቄ አልነበረም......ኩሽትን አሁን ወልደናት፣ በእሷ ሰበብ ተበሳጭተን፣ በእሷ ሰበብ ተሰዳድበን ደም አሁን ስንረሳት:: እንዲህ ነው:: ልብ ያላሉት ፍቅር እንዲህ ነው:: ብቅ ጥልቅ እያለ፣ እያጫወተ፣ መጣ ቀረ እያሰኘ፣ እያዘናጋ:: እሱም ከውስጣችን ወጥቶ ፊታችን ላይ ሲፈነዳ የሚተርፍ የለም:: የማየው የክረምት ጉም ከታች እስከላይ ለመስከረም የሚዘረጋው የአደይ ምንጣፍና የሚሊዮን አዋፋት ዝማሬ ምናምን ነው፣ ከተማና ገጠር ተዳቅለው ነው፣ ደሞም ዓላዛር ብርሃነመስቀል ነው......

ሁልጊዜ የከደንኩዋቸውን አይኖቼን ገልጬ ወደ ጎን ዞር ስል፣ ዓላዛር ጎኔ አለ (እንዴት ሊሆን ቻለ?)። ወደ ታች በማገዶ የእንጨት ጪስ የታጠነች አዲስ አባን እያየ 'ከተሰጣሽ አንድ ሰዓት ሊሆንሽ ነው' እያለኝ......አንድ እግሬን አጥፌ የእሱ የወዳጄ የዓላዛርን የዓላዛርዬን፣ የአዝዬን (ለብቻዬ ስሆን ድምጼን ደብቄ 'አፈር ልሁንልህ' የምለው) ......የላበው እጄን በሚሞቅ እጁ ይዞ በቀስታ እየነካካ ልዩ ነገር እንደሚያገኝበት ሁሉ እሱን በአትኩሮትም እየዳበሰ......

## ፍቅር ያዘኝ ለምጄ[94]

የምንማረክበት አንድ ነገር ልባችን ውስጥ ሳናስበው ከፍቶ ይገባና (ወይስ ከፍቼ አስገባሁት) እንደ ቤቱ ተመቻችቶ ይቀመጣል:: ልባችን ምንም እንዳላየ ሁሉ ይቆለፋል:: ደሞ ሌላ የሚማርከንን ጉዳይ (ማን እንደ ከፈተው አይታወቅም) ልባችን እሱን ያስገባውና ይከደናል:: ይሄ እየከፈቱ ማስገባት ይቀጥልና ውስጣችን በሚማርኩን ነገሮች ሞልቶ ይወጠራል:: በዚህ መሃል አንዲት ትንሽ የረቀቀች ስሜት ስትወጋን ፈንድተን የገባው ሁሉ እየፈሰሰ ይወጣል፣ በዙሪያችን ይንዘረፈፋል:: በኖህ ውሃ እንደ መጠረግ ነው::

ዕድሜዬ አስራ ሶስት መሰለኝ:: አንድ ዕለት ከመንገድ ውጭ ቤት ሲሰራ ሲሚንቶ የተቦካበት ነጭ አስፋልት የመሰለ ሰፊ ቦታ ላይ በቾክ ሰኞ ማክሰኞ ሰርተን ከጓደኞቼ ከወለተ መስቀል፣ ከሰላም፣ ከፀናዕልና ከማሚ ጋር እንጫወታለን:: ዓላዛር ከሜዳ ኳስ በክንዱ አቅፎ ይዞ ሲመጣ ሳየው ፈዝዤ ቀረሁ:: ከወገቡ በላይ ራቁቱን ነው:: ሸሚዙን ወገቡ ላይ አስሯል:: ፀጉሩ በላብ እርሶ አፍሮው ረጥቦ ግንባሩና ማጅራቱ ላይ ወድቋል:: ሽንጡ የሚሰበር ይመስላል:: በግራ እግሬ እንደ ቆምኩ እያየሁት ፈዝዤ ቀረሁ:: የሆነ የሚያስፈራ ላወራው የማልደፍረው ሚስጢራዊ ስሜት ነገር የሰራ ገላዬን ወረረኝ:: ያን ሰከንድ ሰዎች ጎኔን እየጎነታተሉ ስሜን ቢጠይቁኝ የምስማቸው፣ ብስማቸው የሚገባኝ አይመስለኝም::

«ምነው?» አለች ማሚ:: ያኔ ‘ጨዋታውን ቀጥዪ’ ማለቷ ይመስለኝ ነበር:: ምንም ሳልመልስ ሁሉንም እዛው ትቼአቸው በሩጫ ቤቴ ገባሁና አልጋ ላይ በሆዴ ተደፋሁ:: ማሚ ተከትላኝ መጣች::

«አመመኝ መሰለኝ» አልኳት እየተኮላተፍኩ::

የሆንኩትን ነገር ስም ልሰጠው አልቻልኩም:: ቁና ቁና እተነፍሳለሁ:: ያን ቀን ያጋጠመኝ እጅግ ገናና የሆነ፣ ለሰባሰገል ብቻ የሚከሰት ዓይነት ሚስጢር ነበር:: ማሚ የምጠጣው ውሃ ልታመጣ ብርጭቆ ፍለጋ ከክፍሌ

[94] ከሆነ ዘፈን

እንደወጣች፣ እንቅልፍ ጠርጎ ወሰደኝ:: እናቴ ራቴን እንድበላ ስትቀሰቅሰኝ ጨልሞ ነበር:: በማላውቀው ምክንያት የእናቴን አይኖች ማየት ፈራሁ::

በተለይ ከዛን ቀን ጀምሮ አብሬው እንዳላደግሁ ሁሉ የዓላዛር ስም ራሱ አስፈራኝ:: ስሙን ሲጠሩት እና 'አቤት' ሲል ስሰማው ልቤ ትር ትር ትር:: በወሬ እንዳልተላፋሁት እጅ ለእጅ እንዳልተጓተትኩት፣ ገና ሳየው ብረሪ ብረሪ ይለኛል:: አብሬው መሆን እየፈለኩ ግን እሸሸዋለሁ:: እዛ የተሰበሰብነውን ልጃገረዶች ሊያጫውተን ወይም ሊተርበን ወይ ሊቃለደን ሲመጣ ንግግሬ ይልፈሰፈሳል:: እግሮቼ ይደክማሉ:: ደረቱ ላይ ሆነሽ አልቅሽ አልቅሽ ይለኛል::

ቤቶቻችን ትይዩ ስለነበሩ እኔ ግቢ በረንዳ ላይ ከቆምኩ እሱን በረንዳ ላይ ቆሞ ወይም ጠዋት ጠዋት መስኮት ከከፈተ፣ መኝታ ቤቱ ውስጥ ወዲያና ወዲህ ሲል አየዋለሁ:: ቀና ብዬ የቤቱን በረንዳ ሳይ እሱ ካሌለ ሁሉ ነገር ባዶ ይሆንብኛል:: ተገናኝተን 'ሰላም' ብሎኝ መልሼ 'ሰላም' ለማለት ከዘገየሁ 'ምናባቷ ትኮራለች' ብሎ ሊያሯሩጠኝ ሲመጣ ፈዝዤ እጠብቀዋለሁ:: በተደጋጋሚ አይኖቹ የሚያርፉበትን የገላዬን ክፍል አይቼ እንዲደሰት ጭኖቼን መግለጥ የጀመርኩት ያኔ ነው:: ከቤት ሆኜ (በረንዳ ላይ መንገድ መንገድ እያየሁ እጠብቀዋለሁ) ካየሁት፣ ቶሎ እወጣና እውጭ የማይሆን ጨዋታ ብቻዬንም ቢሆን እጫወታለሁ:: ካለሰኘኝም ቤቴ አጥር ጎን ፀሐይ ውስጥ ጭኖቼ እንዲታዩ ቀሚሴን ትንሽ ወደ ላይ ሰብስቤ እቀመጣለሁ:: ይሄ ስራዬ በኋላ ለራሴ ቢያሳፍረኝም፣ የእሱን አትኩሮት ለመሳብ ደጋግሜ ማድረጌን አልተውኩም:: እማማ ከጉልበቴ ዝቅ የሚል ቀሚስ ስትገዛ ወይም ስታሰፋልኝ፣ መጀመሪያ የማደርገው ነገር እዛ መንገድ ዳር፣ ሱቅ ጥላ ስር ልብስ እየጣፈ የሚተዳደረው ዋሴ ጋ ሄጄ አሳጥሬ ማስቀምቀም ነው:: በሌላ ቀን ስታየኝ 'እንዴ? ይሄ ቀሚስ እንዲህ አጭር ነው?' ብላ ለማርዘም ጎተት ጎተት ታደርገዋለች:: 'ሲታጠብ የሚያጥር ጨርቅ ነው እኮ' እላታለሁ:: እማማ ድምፅዋን ከፍ አድርጋ ፋብሪካዎችንና ነጋዴዎችን ትራገማለች:: በእንድ በማይረባ ቀሚስ ነጋዴና ሳይንስ እንድትጠላ አደርጋታለሁ:: ከዚህ የተማርኩት አንድ ነገር ልብን ስለ መደበቅ ነው:: መታመንን (ለእማማ ከእኔ የስጋዋ ቅንጣቢ የደምዋ ፍሳሽ የበለጠ ማን ይቀርባታል?) ተጠቅሞ በውሸት ልቦናን ማሸፈት ነው:: (እሷን በሀሰት ማደናገር የፈለገ የሚጠበቅበት እኔን ብቻ አሳምኖ መጋለብ ነው)

ብዙ ሴቶች ጨዋ አይደለንም፡ እንደሚወራልን ማለቴ ነው:: 'ጨዋነት' ምንድነው አልባልና:: ቢሆን ኖሮ ትናንት አይኖቿን የደፋችው ልጅ፣ በምን ጥበቧና የት በደበቀችው ችሎታዋ ነው ከሁለት አመታት በሁዋላ አንድ ልጅዋን ተንጋላ፣ ሁለተኛውን አጎንብሳ፣ ሶስተኛውን ዘፍ ላይ ሆና የምትገላገለው? ግብዝነትንና ማስመሰልን ገና በኮረዳነታችን ነው

የምንለማመደው:: ውስጥ ለውስጥ በቅርብ ካሉት ጓደኞቻችን ሚስጢር ደብቀን ራሳችን ብቻ የምናስባቸውና የምናደርጋቸው ብዙ ትንንሽ ነገሮች አሉ:: እንዲህ በቀሚሴና በጭኔ ጨዋታ እየሰራሁ ጎበዝ ተማሪ ብቻ ሳይሆን 'ጨዋ ናት' እባል ነበር:: እንደሚመስለኝ አጋልጠ የሚያወጣ ማህበራዊ ኑሮ ስለሌለን ይሆናል:: የሚያገናኙን ክለቦች የሉንም:: ከትምህርት ውጭ ሌላ ኮስታራ ነገር አናወራም:: በሚያስጨንቀን ትንሽም ይሁን ትልቅ ነገር እየተብሰለሰልን ከሆዳችን ወይም ከልባችን (በትክክል የት እንደሚቀመጥ እንጃ) አናወጣውም:: ቱጭ ብለን የምናወራው ስለሌላ ሰው ነው:: ብናወራ ሃሜት ነው:: የእኛ ጉዳይ የሚነሳው በሌሎች አፍ ነው:: በሌላ ሰው አፍ መነሳት ነው አይደል ሃሜት የሚባለው? ያ እንዳይሆንና እንዳልታማ መረጃዬን አፍኜ ይዤ ነበር:: ለማሜ (ከሁሉ ጓደኞቼ ለማቀርባት) እንኳን የተሰማኝን አልነገርኳትም:: ማሜ አምልጧት ለእናቴና ለሌሎች ልጆች ብታወራብኝስ? አንዳንድ ሰው ማውራት ባይፈልግም ያመልጠዋል አይደል? እንደዛ ናት ማምሽ:: ስንሰድባት 'አንቺ ቦርቃቃ' ብለን ነው::

አንድ ዕለት አባቴን ለማየት ደብረዘይት ስወርድ ለመጀመሪያ ቅር ሲለኝ ማን ትዝ አለኝ? ዓላዛር:: ግን አቃቂ ስደርስ ነው የተገለጠልኝ:: ለመመለስ እያሰብኩ፣ ሳላቋርጥ ወደ ሸሮሜዳ ስለመመለስ እያሰብኩ ደብረዘይት ገባሁ:: በዛ ወቅት የምፈልገው ከዓላዛር ጋ መሆን ነበር:: ምን ሊያደርግልኝ?

አንድ ጊዜ በትንንሹ ነገር እናቴን ተቀይሜ 'ደብረዘይት እሄዳለሁ' 'ደብረዘይት እሄዳለሁ ስል'፣ ዓላዛር ደሞ እየተንሰፈሰፍኩለት (በድብቅ ቢሆንም) አልገባው ሲል ('ተይ ቅሪ' እንኳን አይለኝም?) ተበሳጨሁና ተነስቼ ሄድኩ:: ቀኑ ፀሐያማ በሚሊዮን ብር የሚገዛ ውበት ነበረው:: ቀዝቃዛ አየር ከእንጦጦ እየወረደ ይሰማኛል፣ እግሮቼ መሃል ቀሚሴን እየገለበ እንደ ባሌ ሲንፈራፈር:: ለገሃር ከታክሲ ወርጄ ገና ወደ ደብረዘይት የሚወስደውን የሉንቺና አስተናጋጅ ሳይ ተመልሶ ሳይከደን አይነት ልቤ ለሁለት ተከፈለ......ተከዝኩ:: ይሄ ሉንቺና ተሳፍሮ ትከዛ አራግፌ ልጥለው ያልቻልኩት ፀባዬ ሆነ:: መብሰልም ይመስላል:: ማፍቀር በሆነ መልክ ማወቅ ሆኖ ያስረጃል መሰለኝ:: በዛ የሞቀ ጉዞ ፊቴን መስኮት ላይ ደግፌ ያማስበው ብዙ ነገር ነው፡ አባቴ ከእናቴ ጋር ሲሆን አስባለሁ......ብዙ እመኛለሁ፡ አብረን ሳሎን ተሰብስበን ራት ስንበላ......(የአባቴ ፓስታና የፓስታ ወጥ) የምወደው የእማማ የሚያምር የተቆራረሰ ፀሐይ የመሰለ ሃምባሻና ጠይም እንጀራ ጠረጴዛውን ሞልቶት......ከአባቴ ጋር ቤታችን ግቢ ከጀርባ ቮሊቮል አብረን ስንጫወት......አውቶቡስ መስኮት ላይ አንገቴን እስኪያመኝ ተለጥፌ ብዙ ብዙ አስባለሁ፡ እዛ ሜዳ ላይ ጨርቅ ኳስ ከሚጫወቱት ልጆች ስንቶቹ አባት የላቸውም? እዛ ያቺ ሴት ትልቅ ያበጠ አንሶላ በዕቃ ሞልታ ከአህያ ኋላ የምትከተለውን

ማነው 'እንዲህ አድርጊ' ያላት? እዛ ቀንበር የተሸከመ በሬ የሚገፋ ገበሬ ማን አባቱ አዘዘው እንዲያ ጅማቱ እስኪወጠር መማሰን? ለምን ይለፋሉ? ወይስ መልፋት ፈልገዋል? ወይስ አባት የላቸውም? ያቺ ፓፓያ የምትሸጥ ልጅ ብብቷ ስር ከእኔ የሚያምር የጡቷን ደርዝ አያለሁ፣ ለምን ወንዱ ሳቢነቷን ዐይኖቿ የማያውቁ ይመስላሉ? የወለዳት አላለበሳትም? ግራ ጆሮውን ለመንገድ እያሳየ አሽብርኮ የሚፀዳዳው ውሻ እንደ እኔ አባት የለውም?

የአባቴ ሁለተኛ ሚስቱ አብረኸት የምትባል ከእናቴ ልጅ የሆነች ሁልጊዜ እኔን ስታይ የምትፍለቀለቅ፣ ያለትግርኛ የማትናገር ደግ ሴት ነበረች:: ለምን ትፍለቀለቅ እንደ ነበር፣ ምንና ምኔ ያፍለቀልቃት እንደ ነበር ግን እስከ ዛሬ አላውቅም:: ቤቱ የእሷ፣ ሬስቶራንቱ የአባቴ ነው:: ግራና ቀኝ ሆነው በትግርኛ ሲነጋገሩ ከመሃል እሱ በአማርኛ እሷ በትግርኛ እየመለሰች ይቆያሉ:: ስታናግረው እሷ እመቤቱ፣ እሱ ምንዝር እንዲመስልላት ትፈልጋለች:: አብረኸት ከእናቴ የተሻለ አለባበስና ዘመናዊነት አላት:: ግን አያምርባትም:: ልቅም ብላ ያማረች ቆንጆ ብትሆንም ደም የላትም:: ሳያት አታስደስተኝም:: ምናልባት ለእሷም አላስደስታትም ነበር::

ብዙ ሰው በማወቅ፣ ብዙ ልጆች በማወቅ፣ ያጋጠመኝን ሰው ሰላም በማለት የደብረዘይት ሰው ለመሆን ጣርኩ:: አልቻልኩም:: መሰላቸትና ብዙም ልብ የማልለው ስሜቴ ወደ ወንዶች ይገፋፋኛል:: አንድ ቀን 'በረከት ነጋሚ' የሚባል የአየር ወለድ ኮሎኔል ልጅ ለብቻዬ ራስ ሆቴል ተቀምጬ ፋንታ ስጠጣ እያለሁ ተዋወቅሁት:: ያን ጊዜ የስድሳ ስድስት ንቅናቄ ተጀምሮ ትምህርት ቤት ተዘግቶ አባቴ ጋ ነበርኩ፤ ምናልባት ፋሲካ ነበር:: ቀኑና የቀኑ ፀባይ በትክክል ትዝ አይለኝም:: አባቱ ሲያወሩ እየሰማ ነው መሰለኝ በረከት ስለ ፖለቲካ ብዙ ያውቃል:: ምናልባት ይሄ ችሎታው መስጦኛል:: ስለ ቆሪጥና ስለ ሐይለስላሴ የማያውቀው ነገር አልነበረም:: ይሄም ተረቱ ልቤን አላልቶታል:: በአጭር ጊዜ ውስጥ ልጁ፣ አገሪቷ፣ ደብረዘይትና ሰዎቹ ሲደራረቡ ሚስጢራቸው ሰፍቶብኝ መሰለኝ ተማረኩለት:: ያሰበውን አስቦአልና ነጋ ጠባ ቤቴ እየተመላለሰ መግቢያ መውጫ አሳጣኝ:: አብረኸት ደሞ 'ያ የኮሎኔሉ ልጅ ፈልጎሽ ነበር' 'ያ የኮሎኔሉ ልጅ ይጠራሻል' እያለች ያልተከፈላት አቃጣሪ ሆነች:: (የልጁን ስም ብታውቀውም ስሙን አትጠራም) ልጁ ሊጠብሰኝ እንደሚፈልግ እያወቅሁ ያላወቀ መስዬ ተጠበስኩለት:: ሲያባብለኝ የተባበልኩ መሰልኩ:: በወር ከአምስት ቀን ውስጥ የምትጠልቅ ፀሐይ እያሳየ ሳመኝ:: በሚቀጥለው ሳምንት ላይ ሴት ስሆን በረከትን ላየው አልፈለግሁም:: ያውም ከአዲስ አባ ደብረዘይት መሄዱን ልቻልበት እንጂ. ገና አስራ አምስት እንኳን ያልሞላኝ ልጃገረድ ነበርኩ (ዛሬስ ልጅ አልባልምና ነው):: ክብርናዬን ካጣሁ በሁዋላ ልገልፀው በማልችል መልክ ደብረዘይት ከበደችኝ:: በረከት ሊያናግረኝ ቤታችን ደጃፍ መጥቶ ሲዘፈዝፍ፣ ከቤቱ

በሌቶ መጥቶ ሲያየኝ ወይም ሲጠይቀኝ ሬስቶራንታችን ምግብ ሲያዝ፣ ዘግቼው ክፍሌ ገብቼ የእውነት አለቀስኩ፡፡ አንድ እሁድ ዕለት ለእሱም ሳልነግረው፣ አባቴንም እንደቀድሞው በስርአቱ ሳልሰናበት በጠዋት አዲስ አባ ለመሄድ ተነሳሁ......

......በተከፈተ የአውቶቡስ መስኮት የአዲስአባ ጠረን በአፍንጫዬ ሲገባ፣ ከተማዬን የከዳሁዋት መሰለኝ፡፡ አጥብታኝ፣ አጠጥታኝ፣ አብልታኝ፣ ፀጉሬን አበጥራ፣ እግሮቼን አጥባ፣ ጠዋት ስማ፣ ማታ ነጅሳ፣ ግን ገላዬን ቆላ ጥዬባት መጣሁ......ቆሬጥ እግር ስር ዝቋላ ደብር ዳር አረንጉዋዴ ሐይቅ እያየሁ......የምወረውረው ድንጋይ ውሃ እስኪመታ በቆጠርኩት የጊዜ ስፋት......

......መርካቶ ሱቅ በደረቴ መካከያ፣ ሊስትሮ ከነሳጥኑ ከሚሰፍርበት ድንጋይ ላይ ራሴን ይዤ ተቀመጥኩ፡፡ እዛ ሽሮሜዳ ስመለስ ኦሪጅናል ሳልሆን ተሰብሬ ነው፡፡ አልቦናዬ ያስገባሁትና የምወደው ዓላዛር በሆነ መልክ እንደምጠፋበት አወቅሁ፡፡ መደቤ የቀለለ መሰለኝ፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ወዶኝ 'ሳሚኝ' ቢለኝ የቱን ያልተለከፈ ከንፈር እሰጠዋለሁ? እና ሌላ ሌላ ቢለኝ ምን እመልስለታለሁ? ሁሉም በደብተሩ የገፈኝ ጨዋ የሆንኩት ልጅ፣ እና የምባለው ልጅ የሆነ ነገር ጎሎኝ ሰፈሬ ስገባ ተዘራፊነቴ ግንባሬ ላይ በጉራጊኛ ይሁን በወላይትኛ ተፅፎ ቢነበብስ? የጥፋቴ ልቀት ገብቶኝ መቀመጥ እስኪያቅተኝ ልቤ በፍርሃት ተንዘረዘረች፡፡ ቤት እንደገባሁ እናቴን እንኳን በደንብ ሰላም ሳልል፣ ሁለት የውስጥ ሱሪዎች ለብሼ፣ እንደ በረደኝ ሁሉ ፒጃማዬ ላይ ሹራብ ደርቤ፣ ዓይኖቼን እያቁለጨለጭኩ አንሶላዎች መሃል ተቀረቀርኩ፡፡

«ምን ልሁን ነው? እ? ጥጋብ፡፡ ምን ያየሽው አለ እዚያ፡፡ እ? እንደ እሱ ሃብታም ባልሆን አሳጎልብሽ፡፡ እኔ ዓላዛር አንቺን ፍለጋ እስሬ ሲመላለሱ?» አለች እናቴ፡፡

እኔም ልሁን ማንም ጠልቶ ሊገባን በማይችል መልክ ብቸኝነት የመሰለ ነገር ተሰማኝ፡፡ በሁለተኛው ቀን (አልረሳውም ቀኑን) እሁድ ጠዋት ዓላዛር ከአልጋው ሳይወጣ፣ ቁርሱንም ሳይበላ፣ ያፈለገው ይሁን ብዬ ባልተለመደ ንጋት ላይ ቤቱ ሄድኩ፡፡ ሌላ እንዳይመስልብኝ እንደሚያነብ መጽሐፍ ያዝኩ፡፡ ቤቱ ሄድኩና ጎኑ ወደቅሁ፡፡ አፌ ላይ እነዚህ ጠያቂ ቃላት፡ 'ለምን አትስመኝም?!' ሊወጡ ይንሰፈሰፉ ነበር፡፡ ያኔ ለመጀመሪያም ለመጨረሻም የመፈራራታችንና የመተፋፈራችን መጋረጃ ተቀደደ፡፡ ስንተቃቀፍ ሩቅ ተጉዞ እንደ መጣ ሁሉ......ታጅራ እርቀት ያህል ሄዶ እዛም ደርሶ እንደ ተመለሰ መንገድ እንዳደከመው ነፍስ፣ ወይም መልካም ሕልም ለማለም እንደ ጀመረ......ዓላዛር አንገቴ ላይ እንደ ቆዳ ተለጥፎ ትንፋሹ እየፈጀኝ......ይኼ የእኔ ዳሉል......ይሄንንም ተከትሎ የዕንባ ኳስ ከግራ ዐይኑ ቀኝ ጉንጩ ላይ ሲያርፍ......(አልረሳም፡፡ እስከ ዛሬ ያቺ ነጠላ የዕንባ ጠብታ እኩያ

የላትም:: የሚኖራትም አይመስለኝም) ሁለመናዬ እንደ ታላቅ......እነ ማርያም እንደማየው የብራና መጽሐፍ ተከፈተ......(ፍቅር ቀላል ነገር አይደለችም)......

ብዙ ጊዜ ያነበብኩዋቸው ደራሲዎች ስለፍቅር ይፅፋሉ እንጂ ዘርዘር አድርገው ያን ፍቅር ስለሚያጅበው ዕንባ አያብራሩም:: ስለሚያምር ዐይን ይናገሩና፣ ስለፍቅር ይናገሩና 'አለቀሰ' ወይም 'አለቀሰች' ሲሉ ለብቻ ቃሉን እንጂ በዝርዝር 'ይሄውላችሁ' አይሉንም:: ስለ አንድ ነጠላ ዕንባ በብዕራቸው አይነግሩንም:: ካልጎረፈ አይፅፉትም:: የሚነግሩን ለቅሶ መሃረብ የሚያረጥብ ሲሆን ብቻ ነው:: እኔ ግን አውቃለሁ:: እንዳየሁት ያቺ ዕንባ ወይም ያ ዕንባ (ከወንድ ዐይን ስለወጣ ተባዕት ላደርገው) ከዐይን ሲወጣ አይፈጥንም:: እንደ ሚሮን ነው:: በጉንጭ ላይ አይፈስም:: ከታችኛው ሽፋሽፍት ላይ በሙጫ እንደተያያዘ ሁሉ ባላ ባልቾ የሽፋል ክንፎች ላይ ይቀመጣል:: እንደ ዕንቁ እየፈለቀ እዛ ይቆያል:: ብርሃን ያወጣል:: የሚጠብቀው የምትጠጣው ፍቅረኛ ነው:: በመሳሳም ሂደት ዐይን ሲከደን፣ የላይኛው ሽፋሽፍት ታችኛው ላይ ቀስ ብሎ ሲያርፍ ዕንባ ቦታ ይለቃል:: አዚዬን የሆነው እንዲህ ነው:: ለመጀመሪያ ራቁታችንን ስንወድቅ ከንፈሮቼ ያጠመዱት ዕንባውን ነው:: ሆዴ ውስጥ እስከዛሬ ድረስ ያ ዕንባ አለ:: ከገባ በኋላ ወደ ታች አልዘለቀም:: በግራ ጎኔ፣ በልቤና በጡቴ አካያ እንደ ሩቢ እያበራ ተቀምጧል:: (የሚወዱት ሰው ዕንባ ሆድ ሲገባ ቀለሙ ቀይ ይሆናል:: ማርያምን)

ሲመስለኝ ወደ መዋደድ አውራጃ መግባታችንን ሁለታችንም አላወቅነውም:: 'የፍቅር አውቶቡስ ጎማው ረቂቅ ነው' አሉ:: ከት/ቤት ሲመጣ ቤቱ ደብተሩን ወርውሮ እግሩ እኔ ጋ ሆነ:: የእኔም እግር ሁልጊዜ ወደ እሱ ቤት:: ለዘለለት ቅዳሜ ቅዳሜ ከእናቴ ጋር መርካቶ ገበያ ደርሼ ስመለስ ሳንቲሞች ሸውጄ፣ እናቴ ትንሽ ሳለሁ ታደርግልኝ እንደነበረው የሚወደውን ነገር ገዝቼለት እመጣለሁ:: አንዳንዴ ካልሲ፣ ቆንጆ እርሳስ፣ የሚያምር ስክሪፕቶ፣ ቆንጆ ማበጠሪያ(አቤት ፀጉሩ ሲያምር የነበረው!) አንዳንዴ ላበሸቀው ሽምብራ ዱቤ ወይም አልቲት ወይም ድንገተኛ መድሃኒት ይገዤለት እመጣለሁ:: የያዝኩትን እቃ ገዝቼ እተቀመጠበት ወይ እተኛበት ሄጄ በጆርባዬ ደብቄ 'ምን ይገኝ እለሁ?' ብዬ ስጠይቀውና መገመት ሳይችል ሲቀር አቤት ደስ ሲለኝ:: ሚዶ ከሆነ ወይም ቡሩሽ እሱ እቃውን ሳይነካው በፊት ከሁዋላው እቀመጥና አፍሮውን እከመክምለታለሁ:: 'አትታጠበውም እንዴ?' እያልኩ:: እሱም ሳይገባው፣ ሌላ ሰውም ሳያየኝ ፊቴን ወደ አፍሮው አስጠጋና ጎምዛዛ የላቡን ጠረን እሸታለሁ:: ቢሆን እዚያው የእናቱ ነዶ ውስጥ ሩብ ሰዓት ታፍኜ መቆየት እመኛለሁ:: ብዙ ጊዜ እላይ ሰፈር ያለው ኳስ ሜዳ እሱ ሲጫወት ለማየት እሄድ ነበር:: ላብ የፈሰሰበት ቅላቱን ሳይ እርበተበታለሁ:: መርበትበት ብቻ ሳይሆን፣ የሚጫወትበት ሳር ላይ በጀርባው አጋድሜ መንጋጋዬን እስኪደክመኝ

ሁለመናውን መንከስ ወላ ንክስክስ ማድረግ። ይሄን ሳስብ ልክ ምግብ እንዳሰኘኝ ሁሉ አፌ ውሃ ይሞላል።

አብረን ብዙ ጊዜ በመታየታችን ልጆች ሊያበሽቁት 'ስሚ ዓሌክስ ሚስትሽ መጣች!!' ይሉታል። ኳሱን ችላ ብሎ እቆመበት ወገቡን ይይዝና በሃይል እየተነፈሰ እጄን ለሰላምታ ያነሳልኛል። አይ ሸንጥ። አንዳንዴ ጨዋታ ለማየት እየደጋገምኩ ወደ ሜዳ መሄዴ ለራሴ ያሳፍረኝና የቤቴን መስኮት ከፍቼ ጨዋታ ጨርሶ እስኪመጣ እጠብ ቀዋለሁ። ቤቱ እንደ ገባ ሮጬ ወጥቼ 'ሚዞ ሻወር'[95] ወደ ሚወስድበት ወደ ጓሮ አልፍና ከወገቡ በላይ ሲታጠብ 'ላፍስልህ' ብዬ በአትክልት ማጠጫ ጎማ ውሃ አፈስለታለሁ። ሉጫ ፀጉሩ 'ርሶ እናቱ ላይ ተፈታትሎ ሳይ ልቤ ይሸበራል፣ ለዘለዓለምም ላንቆረቁርለት እፈልጋለሁ።

**አንተ ሴት ብትሆን**

**በዚህ በዚህ ስሜት ብታልፍ ይገባሃል?**

**ከገባህ ታድለሃል።**

**ካልገባህ ይሄው ከእኔ ተማረው**

አሌክስ ሁለመናው ይፋጃል......እየነከሰ ሲስመኝ እየሳመ ሲነክሰኝ...... የትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ......ሲያለከልክ ሲያምር። የዚህ ልጅ ስሙ ከአፌ ስንቴ እንደ ምርጥ ቃል ወጣ? እኔ ቀድሜ ነቅቼ ከላይ እስከታች ሳላፍር እንዲህ እያየሁት......ባየው ባየው......ባልበረደ ፍትወቴ ውጩው ልሞት ......በቀስታ ደሞ የለበሰውን ብርድ ልብስ እንዲህ ገልቤ ነጭ አንሶላ ላይ እንደ በሰለ ፓስታ እርካታ አሳልቶት......በፍስሐ የሚያናውዝ ልጅነቱ...... አጥንታም ደረቱን ተደግፌ የምንተፍረቴን......ስኳር እንደ ነካ የቡና ሲኒ የላሰኩት ግንባሩ......እንዳልቀሰቅሰው በቀስታ ስስመው......ያዘነበለ፣ ሐዘን የገባው ቡችላ የመሰለ ወንድነቱን......በእንግዳነቱና በጉጉት በጣቴ ልነካው እየፈለኩ ግን ፈርቼ ሳፈጥ......ውስጤ ሆኖም ያደረገኝን ሳስብ......ቅንድ ቡንም በቀስታ በትንሽ ጣቴ እያበጠርኩ......የመሃል ጣቱ ዙርያ ሴትነቴ እንደ ቀለበት......ከእሱ ጋ አምሽቼ ስተኛ የሚወስደኝ ጥልቀቱ የሚያስ- ገርም ድንቅ እንቅልፍ፣ ወገቤ ላይ የሚቀረው የጥፍሮቹ ዳና...... አንዳንዴም ሰባኘን አልጋዬ ላይ በጀርባዬ ተኝቼ ሁለመናዬ እንደ አዲስ ሲፈልገውና ወሲብ አለመጥገብ ሐጢያት መስሎኝ ስር በደበድ......

ወላጅ አባቴ በእናቴ አሳቦም ይሁን አስመርራው ሸሽቶኝ ቢሄድም ይሄ ዓላዛር የተባለ የሽሮሜዳ ሸንከራ እግሮቼን ተከትሎ ወደ ምሄድበት ሄደ፣

[95] ከወገብ በላይ መታጠብ

አረፍኩበት አረፈ፣ ሳቄን ሳቀ:: አባቴ ወደ ቆላ ቢኮበልልም ዓላዛር እጄን ያዘኝ:: ዘመናይ ለዘመናይ:: እዚህች ደጋና ወይና ደጋ ሰላሚን አገኘኋት፣ እዚዬ በቁጭት የተጨበጠች ግራ እጄን ከፍቶ ግራ መዳፌ መሃል ትር ትር የምትል በፍጥነት የምትመታ ልቡን፣ ቀኝ መዳፌ መሃልም ማር ማር የምትል መሳሙን አስቀመጠ......

ይሄን ይሄን ፍቅር ስንጀምር ብዙ እንደ ደመራ የሚንቦገቦጉ ለአለምና ለሕዋው የተገለጡ ምስክሮች አሉ......

ምስክሬ ነው: የከንፈሮቼን ንቅናቄ መሐላዬን ያነበበ ዕርግብ ይሁን ንስር ሽሮሜዳን ከተወለደ ጀምሮ ገና ከዕንቁላልነቱ ያነበበ:: ዕውነቴን እንደ ነበር:: ምስክሬ ነው ያ በራሪ......

ምስክሬ ነው: የነፈሰብኝ የተነፈስኩት የነካኝ የነካሁት የዘፈንኩበት(*ከቶ ሳላውቅ ይዞኛል ፍቅር ከእሷ ጠምዶኛል* የተባለ ጊዜ) አደግሁ ብዬ አፍሮዬን ስከመክም......እዚህ እዚያ የትም ያወረደችው የእናቴ ቀጭን ሁሉን ያስመረረ የንጭንጯ ዶፍ (‘አንቺ ከዛ ልጅ ምን አለሽ?’)......እሱም ምስክሬ ነው......

ምስክሬ ነው: የእንጦጦ ወጣ ገባ ተሰነካክዬ የወደቅሁበት፣ እየሳቅሁ የተነሳሁበት፣ ብሳና ዛፍ ጥላ ስር አቅፎ የጣለኝ......በእቅፉ መግቢያ መውጫ ያጣሁበት......ምስክሬ ነው ወጣ ገባው......ብሳናውም......

ምስክሬ ነው: እንጨት በአጋሰስ የጫነ ገበሬ ፊቱን ወደ ማርያም አዙሮ ለእኛ ብልግና የፀለየበት......ወይ የረገመበት......ወፍራም ድምፁ እንደ ነፋስ በየቅጠሉ ሳንባ የገባው......ቃሉ ምስክሬ ነው......

ምስክሬ ነው:......የረጠበ ሳር ላይ ተቀምጠን......ደሞ ደረቱ ላይ ሆኜ ልቡ ስትመታ......ለዘላለም ለመስለ ጊዜ የሰማሁዋቸው ድም ድም ድም ......ምስክሬ ናቸው አስር ሆኑ ሃያ......

ምስክሬ ናቸው በልጅነታችን እሳት እንደ ኮሬብ ቅጠል የነደዱት የእንጦጦ ቁጥቋጦዎች......

ምስክሬ ነው ሲኒማ አምፒር ክብር ትሪቡን በሲጋራ ጢስ መሃል ተቃቅፈን አሚትባህና ራጅ ካፑር(አቤት የሕንድ ፊልም ስወድ የነበረው!) ዕጌሬዳዎች መሃል ቆንጆ ሲያባርሩ ጭኖቼ መሃል እጁን ሰዶ ቂጤማ ሲፈትል......*በማርያም ተወኝ* እያልኩት......ምስክሬ ነው ሳሩ......

ምስክሬ ነው የማርገዝ ፍርሃትና የሚከተለው ውርደቱ ጠዋት ማታ እንደ ፍልስፍና ሃሳብ ሲዘነትረኝ: ሴት ነኝና፣ በዚህ ህብረተሰብ ሂሳብ (በየትኛውስ ቢሆን) ገላዬ የራሴም ቢሆን ከፍርድ መቅረቡ እያስፈራኝ፣ ቡና ማጣጫ ፖለቲካ መሆኔ እያስጋኝ......ከ ‘የምትረባ’ ወደ ‘የማትረባ

ስሜ በቅፅበት ሲደራጅብኝ እያሰብኩ መብሰልሰሌ……ይሄ ይሄ……ፍርሃቴ ምስክሬ ነው::

አተኩረው ካሰቡት የማንም ፍቅር ገጋ አያጣውም:: 'ለምን ገጋው?' የሚል 'ለምን ወላላው?' ማለት አለበት?……ወግ ለማሳመር ወይ ለማሳጠር (የቱን ልበል?)……ጥንቅሽ ልጠን ስንበላ ልጣጩ ቆዳችንን ይቀደዋል:: አጋም ስንሰበስብ ጋሬጣ ይወጋናል:: ደስታ ይሄን ማቻቻል ቢሆንም እንደ ዘመኑና እንደ ሰዉ ፀባይ ይለያያል:: ለአንድ እፍኝ አጋም፣ ለአንዲት ዕጌሬዳ አበባ፣ ለአንድ መለሎታ አገዳ ክንዴን አላጣም:: ሕይወታችን በምርጫ ሂሳብ በማይታይና በማይዳሰስ በማይገባን የሆሄና የአሃዝ ቀመር የተሞላ ነው:: 'ቀውስ' የሚባለው እንግዳ ቀመር የምርጫ ስልታችን ውስጥ (በግዴታ ወይም ተሳስተን) ሲገባ ነው:: 'ግራ መጋባት' ይሉታል:: ቀውስ ማለት የምናውቀው የምንንደባለልበት የሰፈራችን ቀዝቃዛ የደጋ መስክ ላይ ወባ መርዟን ይዛ ስትገባ ማለት ነው::

## ዓላዛርና ማርክስ

ፖለቲካ ለአገር ማሰብ ነው:: ፖለቲካ መታደል ከተጨመረበት ለአገርና ውስጥዋ ለሚኖረው ለሕዝብ መልካም ለመስራት መጣር ነው:: 'ከራስ በላይ ነፋስ' በሚባለው ነገር አላምንም:: ከራስ በላይ ቤተሰብ፣ ዘመድ፣ ሰፈር፣ ወረዳ፣ አውራጃ ክፍለሃገርና አገር አሉ:: የቻለበትም አህጉርና አለምን በልቦናው ይከታል:: የአገራችን አንድ የሚታይ ማንም የሚያወራባት ፀባይዋ በደሃና በተራራ የተሞላች መሆኗ ነው:: አንድ ሰው በአገሩ ደሃ መሆን የለበትም:: ቢያንስ መሰረታዊ ፍላጎቶቹና መብቶቹ መጠ'በቅ አለባቸው:: የድሆች መናጢነት የሚመጣው ሰነፍ ስለሆኑ አይደለም:: የለፋበት ውጤት በጥቂት ማን አለብኝ ባዮች ስለሚዘረፍ ነው:: እነዚህም ዘራፊዎች ዝርፊያቸውን ያለሃሳብ ለማካሄድ ማስፈራ-ራትንና ራሳቸው ያወጡትን ሕግ ይጠቀማሉ:: ድሆች ወይም ጭቁኖች መብታቸውን ለማስከበር የሚነሱት ከወደቁበት የደሃነት አዘቅጥ ለመውጣት እንጂ በሃብታሞቹ ቀንተው አይደለም:: ወይም በረብሻ ሃራራ ስላደጉ አይደለም:: የሰዎችን የዜግነትና ሰብአዊ ክብር ካመግፈፍ የበለጠ ሌላ በጥባጭነት አለ? እንደማንም ማሰቢያ አእምሮ እንዳለው ፍጡር የአካባቢዬ ሁኔታ ሲለወጥ መለወጥ አለብኝ:: ይሄ ደንብ ነው::

ስድሳ ሰባት አመተምሕረት መጨረሻ ላይ ሚኒሊክ ትምህርት ቤት የማውቀው ልጅ አንድ ጥናት ክበብ አስገብቶኝ ማርክሲስት ፍልስፍና ስማር፣ የግል ሕይወቴ ቅርፅ ብቻ ሳይሆን ማራኪ ትርጉም አገኘ:: ማርክሲዝምን እንደ አላሌሆይ ወይ እንደ ሆያ ሆዬ የሚዘፍኑ ልጆች አጋጠሙኝ:: ተፍካካሪ ነኝና የፍልስፍና መሰረታዊያኑን በአጭር ጊዜ መረዳት አላቃተኝም:: ከሁሉ የሳበኝ ዲያሌክቲካልና ሂስቶሪካል ማቴሪያሊዝም ነበር:: እነዚህ ሁለቱን በመጠኑ ስረዳ በምኖርበት አለም ላይ ያሉ ተፈጥሮአዊም ሆኑ ማህበራዊ እውነታዎች በሚገርም መልክ ለማንዛቤዬ ተከፈቱ:: በተወሰኑ ሕጎች ማለት በተቃርኖ ሕግ፣ በሻሪ ሻሪ ሕግ......ወዘተ የተወሳሰቡ ማሕበራዊ ጉዳዮች ሲተነተኑ የአሰራራቸው ሚስጢር ግልፅ ሆነልኝ:: አንድ ወጥና ውስብስብ የሚመስለው ሕብረተሰብ እድገቱና ጉዞው በአምስት ቦታ ሲከፋፈል ቀላልነቱ መሰጠኝ:: የሆነ ነገር በራልኝ:: እንዲህ ተበታትኖ የማየው አለም ረድፍ ረድፍ፣ ቦታ ቦታ ያዘ::

የማያቸውን ሰዎች በቀላሉ የት የማህበረሰብ ክፍል እንዳሉ በመገመት ፈጣን ፍርድ መስጠት ቻልኩ። ግለሰቦች ሳይቀሩ ሰፍራ ሰፍራቸውን ያዙ። ታክሲ ነጂው ንኡስ ከበርቴ ነው። ምሁሩ እንደ ዓላዛርና ፀናዕል አባት ያሉት አቀባባይ ከበርቴ ናቸው። የፀናዕልን እናት የመሰሉት ደሞ ፊውዳል ናቸው። በምድር ላይ ሌሎች ፍልስፍናዎች ቢኖሩም፣ ማርክሲዝምን ሊቋቋሙ የማይችሉ መሆኑ በደመ ነፍስ ገባኝ። እነዚህን የያዘ ሁሉን የያዘ ይመስላል።

'ፍቅር ምንድነው?' ለሚለው ጥያቄ ያገኘሁት መልስ አጭርና የማያሻማ ነበር። በመደብ በተከፋፈለ ሕብረተሰብ፣ ለጥቅም በሚነታረ ኩበት አለም ላይ፣ በስስትና በስግብግብነት ጦርነት የሚወጡ ህዝቦች ፍቅርን ሊያውቁ አይቻላቸውም። ፍቅር ትክክል የሚሆነው በሶሻሊዝም ነው። ማርክስ ፈረንጅ ሳይሆን የእዝራን አባት መሰለኝ ወይም ሰይፈን-- ጎረቤቴ፣ ሳጠፋ እጄን ይዞ የሚመክረኝና የሚያበረታታኝ፣ ሲጨልምብኝ 'ይሄው መንገዱ' የሚለኝ፤ ለእኔ፣ ለደሃዋና ለአገሬ ያሰበ ወዳጄ። በመጠኑ የእኔ ስንፍና ቢኖርበትም ቤተክርስቲያንን ናቅሁ። ቄስና ፓስተር የሕልም ቸርቻሪዎች ሆኑብኝ። ነፃነትን ከሰማይ አልጠብቅም። ነፃነት ዝናብ አይደለም። ነፃነት በሆያ ሆዬ እንደ ጥቢኛ አይገኝም። በትግል ነው። አዲስ ሰው ሆንኩ።

በሙሉ ልቤ አንድን ነገር ለመፈፀም የተነሳሳሁት ያኔ ይመስለኛል። የሰራ ገላዬን በጨርቅ ሰወርኩ። ለመጀመሪያ ጊዜ ሱሪ ለበስኩ። በወገቤና በቂጤ መሃል ልዩነት እስኪጠፋ አሰፋሁት። ፀጉሬን አሳጠርኩ። በዚህ በመጀመሪያ ያኮረፈኝ ዓላዛር ነው። መማሬ ደበረኝ። 'ከትግል በሁዋላ ትምህርት' እያልኩ አራት ኪሎ ሚኒሊክ ነጭናጫው ሸገኔ ጋ መመላለስና መልከስከስ አስጠላኝ። ግን ሌላ አማራጭ አልነበረኝም። 'ጊዜው ያስፈራል' 'መማር አልችልም' 'መማር አትበይው' እያልኩ ባስፈራራና ባጥላላ፣ 'ድሮም እንደዛ ነው። በሃይለስላሴ ጊዜ ሲረበሽ ነው የኖረው። ይልቁን አርፈሽ አፍሽን ዘግተሽ ተማሪ። የምን ጥጋብ ነው' ትለኛለች እማማ። ግን በመልካም አስተዳደር እጦት ሕዝብ ሲያከና ሲሰቃይ እግር ዘርግቶ ለግል ምቾት መማስንን እንደ ወንጀል ቆጠርኩት።

ራሱን በድርቅና 'ጊዜያዊ' ብሎ አገር ሊያጠፋ የሚርመጠመጠው የምርጥ መኮንኖች መንግስት በትንታኔ ብቻ ሳይሆን በስሜቴም ትክክል እንዳልሆነ አውቄአለሁ። ገደብ የሌለው ዲሞክራሲ ሰፍኖ ሕዝቡ የራሱን ሕዝባዊ መንግስት ካላቋቋመ መታገል እንዳለብኝም አምናለሁ። ይሄ ውሳኔዬ ለራሴ ጥቅም አይደለም። ለሕዝብና ለአገር ሲታገሉ እንዲህ ነው። ደሞ ለፋሺሽቶች ጊዜ መስጠት ሞኝነት ነው። ***እዋጋለሁኝ ለመብቴ፣ ትግል ነው ሕይወቴ......***

በእድገት በህብረት ዘመቻ ተማሮ ወይም በራሱ ፈቃድ ትቶ ወይም እንዲተው ተቀስቅሶ የተመለሰ ወጣት አዲስአባን ሞላት:: የማይመለከተኝ ቢሆንም 'ከትምህርት በፊት ዳቦ' በሚል መፈክር ሥር ተሰባስበን በየመስሪያ ቤቱ እየዞርን ደርግን ትንፋሽ አሳጣነው:: አንዳንድ ጊዜ እስከ ሺህ የሚደርስ ከዘመቻ የተመለሰ ወጣት፣ ሲቪውን ይዞ ከመስሪያ ቤት መስሪያ ቤት ይንጠራወዛል:: ከፋብሪካ ወደ ፋብሪካ፣ ከማህበራዊ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ወደ ዋና ዋና የመንግስት ቢሮዎች በኮሚቴ እየዘመትን 'በመጀመሪያ ዳቦ' እያልን ፋሺሽቶችን ሰላም ነፈግናቸው:: ስልጣን ከያዘ አንድ አመት የሆነው መንግስት አቅም ኖሮት ያን ሁሉ ሰው ስራ ያስይዛል ብለን ሳይሆን ክፉና ለአገሪቷ የማያስብ አምባገነን አድርገን ለሕዝቡ ማጋለጥ ነበር:: 'ከተማ ልማት እንሂድ' ስንል ማን እየመራው እንኩዋን ሳያውቅ ዘማቹ በዝናብና በፀሐይ ሲንከራተት ሳይ ወጣት ማደራጀት ቀላል እንደሆነና፣ ለውጥ ፈላጊነቱንም ተጠቅሞ ወደ ተፈለገው አቅጣጫ ማዞር እንደሚቻል ዕውቀት አገኘሁ:: በቀላል መቀስቀሻዎች ወፋፍራም አድማ ማስራት፣ አድማውም እርፍና ተደርጎ እንዲቆጠር ማድረግ እንደሚቻል ተረዳሁ:: አሳፋሪ ቢመስልም ወጣቱና ይሄ ትውልድ በመሀይም ወታደሮች ከመገዛት ይልቅ ለለውጥ ታጥቆ መነሳት አስፈላጊ እንደሆነ መረዳት አለበት:: ሰልፍ ላይ ድንገት ዘማች እንዳልነበርኩ የሚያውቁኝ ሲያዩኝ ሰው ተከትዬ እንደመጣሁ እነግራቸዋለሁ:: ብዙዎቹ የማያውቁኝ የአዲስ አባ ዘማች የነበርኩ ይመስላቸዋል:: ማንነትን መደበቅ ደሞ የትግሉ ሌላው ዕውቀት ነው::

•

ዓላዛርን በተለያየ ቴክኒክ አንድ ሁለት ሶስቴ ድርጅቴ ውስጥ ሳስገባው ቢያንስ አነካክቼ ጣዕሙን እንዲያይ ሞከርኩ:: ፍላጎቱ እንዳሌለው ብጠራጠርም፣ በሆዴ ለመጨረሻ ብዬ እኔ የምሳተፍበትን የቲያትር ዝግጅት እንዲያይ ቀበሌ ጋበዝኩት:: 'ስለምን ፃፍሽ?' ሲለኝ 'በቃ በአገሪቷ ውስጥ ስላለው ሁኔታ' አልኩት:: ምንም ሳይከራከረኝ ተከተለኝ:: የመመልመሉ አጋጣሚ እንዲሰፋ ቲያትሩ የሚታይበት አዳራሽ ከመግባታችን በፊት ከብዙ አረፍ ልጆች ጋር አስተዋወቅሁት:: ቲያትሬን ስሰራ በቃሌ ከያዝኳቸው ቃላት ጋር ዓላዛር ነበር:: ጥሩ የተጫወትኩት እሱን ለመሳብ ነበር:: እሱ እንዲያደንቀኝና እንዲያደንቀን ነበር:: ቲያትሩ አልቆ ከአዳራሽ ስንወጣ ካስተዋወቅሁት ሰዎች አንዱ ከታች ከስድስት ኪሎ የመጣ፣ ዓላዛርም በትንሹ የሚያውቀው ስለሞን የተባለ ልጅ፣ ግራና ቀኝ እያሂሂረ፣ እያሳሳቀና በሃሳብ እየነካካ ለድርጅት ይመጥን ወይ አይመጥን እንደሆነ ሲፈትሸው ቆየ:: ዓላዛር በመስለል ላይ እንዳለ አልገባውምና ደሞ ማድየለውምና እኔ የደረስኩትን፣ ከልቤ የተሳተፍኩበትንና የምኮራበትን ቲያትር እያጣጣለ ተቸ::

ልጁ የሰማውን ሰምቶ መጥቶ የእፍቃሪዬን አቋም ሲነግረኝ ቅር አለኝ:: ዓላዛር ከፋም ለማም ሁልጊዜ ከጎኔ የሚሆን ይመስለኝ ነበር:: በደንብ ለማያውቀው ባዕድ ሰው ልፋቴን ማጣጣሉ ከነከነኝ:: እንደበደለኝ አልገ ባውም:: በቀላሉ ዓላዛር ከሃዲ ነው:: በሕግ ባይጠየቅም በሕሊናው ይጠየቃል:: የሰለለው ልጅ ስሜቴ ስለገባው ዓላዛርን ለማበሳጨት ጎረምሶችን በላዬ ላይ እንደ ጅራፍ ለቀቀ:: ጎረምሶቹ የከበቡኝ ለስራዬ የተለየ አድናቆት ኖሮአቸው ሳይሆን ዓላዛርን ሊያገሉት እንደሆነ የመረዳት ብሩህነቱ አልነበረኝም:: በዚያን ጊዜ ምንም ባደርግ የሚከላከሉኝ፣ ጎኔ የሚቆሙ ሰዎች እንዳሉ ማወቅ የሆነ የደህንነትና ትክክል የመሆን ስሜት ይሰጣል:: ሁኔታው ከድርጅት ስራ አልፎ የልጁ የግል ከፋት ይመስላል:: ቢገባኝም ምንም ማድረግ አልቻልኩም:: ትንሽም ደስ ሳይለኝ ይቀራል? ትግል የተባለው ጉዳይ ሲቆይ (እንዴት እንደሆን እንጃ) የዚህ አይነት ስራ ይሆናል:: መታገል ሽር መግመድ ይሆናል:: እዚህ ግቢ በማትባል የሰፈር ስለላ 'እኔና' 'እሱ' ይፈጠራሉ:: በታላላቅ መጽሐፍት የተመዘገበው ቲዎሪ እድራጊው ጋ ሲመጣ እን እማማ ቡና ሲጠጡ የሚያደርጉትን ይመስላል:: ከዛ ሲራ የሚቀጥለው መባጠስ የዕናትና የቆራጥነት መለኪያ ይሆናል:: ይሄ ሲበስል ደሞ የአርበኛነትና የመስዋዕትነት:: ዓላዛር ከአዳራሽ ውጭ ቆሞ አብሬው ቤት እንድንሄድ ይጠብቀኛል:: ወደ እሱ ለመሄድ መንገድ ስጀምር እየተንጋጉ መንገዱን ዘግተው የሚያደንቁኝ አዳስ ልጆች በዙ (የድርጅቴን የዚህ አይነት ትብብር አደንቅ ነበር:: ማን እንዳሰለጠናቸው አላውቅም:: አንዳንዴ ብልጠቱ እኔንም ይከብደኛል):: በእጅ ጥቅሻና በአፍ እሱን 'መጣሁ!' እያልኩት የሚያስለችና የሚያናድድ ያህል ጊዜ አስጠበቅሁት:: ቅር ብሎኛል:: ግን ደሞ ከሰዎች መግባባትና ለድርጅቴ ትንሽም ብትሆን አስተዋፅዖ ማበርከት አለብኝ:: ዓላዛር እጆቹን ሱሪ ኪሶቹ ከቶ ግድግዳ ተደግፎ ቆሞ በመበሳጨት:

«ምን መሆንሽ ነው አስቆምሽኝ?!» አለ::

ጎኔ የነበሩት ልጆች ዞር ብለው ምድር ላይ ያልተፈጠረ፣ ከተፈጠረም እዛ አካባቢ መገኘት እንደማይገባው ፍጡር አይተውት ከእኔ ጋር ወሬአቸውን ቀጠሉ: *'በተለይ የድራማው አጨራረስ የላብ አደሩንና የአርሶ አደሩን ተስፋ......*

ሲሰለቸው:

«ቤት ነኝ እጠብቅሻለሁ!» ብሎኝ ሄደ

አዎ አንጀቴ ተላወሰ:: እሱ ባደረገው ስለት ባዕዳን ፊት ዝቅ አደረኩት:: ትቼአቸው ብሄድ ለወንድ ቦታ መስጠቴ ስለሆን (በውስጠት አዋቂ ለሴክስ ይሆናል) ደካማ ያስመስለኛል:: (ዓላዛር ዝም ብሎ ወንድ አልነበረም:: ፍቅረኛዬ ነው:: ግን ከውጭ ለሚያዩት አይኖች ዝም ብሎ

ከሌላው ያልተለየ ወንድ ነው) ግን ትግል ነው:: ባላጋራ ላይ የባሩድ ባይሆንም የስሜት ጥይት ይተኮሳል:: አዝዬን እያቆላመጥኩት ደረቱ ላይ ነበር የመታሁት::

አርፍጄ ቤቱ ስሄድ፣ አልጋው ላይ ተጋድሞ ሙዚቃ ሲያዳምጥ አገኘሁት:: የበደልኩትን ሁሉ የረሳልኝ ለማስመሰል ጎኑ ሆኜ ራሱን እየዳበስኩት:

«ለምን አስቆምሽኝ? ያ ሁሉ ጎረምሳ የተሰበሰበው እኔን ለማስቀናት ነው?» አለኝ የማይዳብሰውን እጄን ጎትቶ እየሳመ:: እንደ ቀልድ አድርጎ እውነቱን ሲናገር መሰለኝ::

«ስራዬ ደስ ብሎአቸው ነዋ:: አንተ ደስ አይልህም?»

«ሁሉ ነገር ደብሮኛል:: መዶሻ፣ ማጭድ፣ ኢንተርናሲዮናል ምናምን፣ ትርጉሙም አልገባኝም:: 'ላብ አደር ያሸንፋል' ለማለት ነው? *ሁ ኬርስ*[96]:: አርት የለውም» አለ::

ሁሉን ነገሩን ቀድሜ ስለሰማሁ አልገረመኝም:: ብዙ ጎተተኝ:: ክፍሉን ቆለፍን:: በስስት ከላዬ ሆኖ ሲያለከልክ ለመጀመሪያ ጊዜ ገለል ብዬ አየሁት:: ገለል ብዬ አላውቅም:: ገላችን ሲነካካ ገለል ማለት አልችልበትም:: ተያይዘን ፍስሐ ባሕር ውስጥ እንገባለን እንጂ እንዲህ ቆሜ ሲወድቅ አላየውም:: ያን ቀን አየሁት:: ለእኔ ገላ የነበረው ስስት ስግብግብነት መሰለኝ፣ አፍረተ ቢስ ስድነት መሰለኝ:: ሁሉን አድርጎ እየተንቀጠቀጠ በጀርባው ሲገለበጥ ሁለመናዬ እንጨት ነበር:: የዓላዛርን የልቡና ጎፍረት አየሁ:: ትንሽነቱንም አየሁ:: ወደ ታላቅ ነገር እንደማይሄድ ከወንድነቱ አቋቋም አየሁ:: 'የመደብ ጀርባው'፣ 'የመደብ ጀርባዋ' የተባሉት ፅንሰ ሃሳቦች ትዝ አሉኝ:: እንዳላስቀይመው ግን አልነገርኩትም:: ግን ነው? ስለ መደብ ጀርባ እያሰብኩ *ግን እንዲህ ነው ጥያቄና መልሱ?* እላለሁ:: ስላስቆየሁትና እኔን ብሎ መጥቶ ስለጠፋሁበት የመናደዱን ምንጭ የምገልፅበት ፅንሰ-ሃሳብ ያስፈልገኛል:: መግለፅም ነበረብኝ:: ከበላሁትና ከጠጣሁት ትምህርት ይሄ 'የመደብ ጀርባ' ይባላል:: *ክላስ ባክ ግራውንድ*: በእንግሊዘኛ ሲባል የበለጠ እውነትነቱ ወጥቶ ጉቾ ይላል::

*

......1968 ማለቂያ አካባቢ ማታ ላይ እናቱ ኡኡ ሲሉ ሰማሁ:: እናቱ እትዬ ሮዛ ሲጮሁ ወይም ከፍ አድርገው ሲያለቅሱ ሰምቼ አላውቅም:: እናቱ ዝምተኛ፣ ድምፃቸው ከአራት ሜትር እርቆ የማይሰማ ነበሩ:: የጄሲ ፔኒ ወይ የሲርስ ሽብሽብ ቀሚሳቸውን፣ ማክሲ ወይም ሚዲ ፒሊሲያቸውን ለብሰው በቀስታ የሚራመዱ ገፃቸው እጅግ የሚያምር

[96] ማን ግድ አለው? ( who cares?)

ተጫጫ ሲት ነበሩ:: ከሁዋላቸው አየሩን የሚወር ትተውት በሚሄዱት የሽቶአቸው መልካም ጠረን ማንም ያውቃቸዋል::

ለትሰውን እንደ ሰማሁ ከቤት ወጣሁ:: በመንገድ ላይ የሆነውን ያዩ ሰዎች ጓላዛር ታፍሶ እንደሄደ ነገሩኝ:: የተገደለ መሰለኝ:: እናቴና ሰይፊ ሊይዙኝ ሲታገሉ እያፈተለክሁ ‘ጓላዛርዬን ሊገሉብኝ ነው’ እያልኩ ከዚያች ቤቴ እሱ ቤት መድረስ አቅቶኝ እግሮቼ እየተሳሰሩ አደናቅፎኝ በጎኔ የሆነ ድንጋይ ላይ ወድቄ ተቀጥቅጬ ዛሬ ድረስ አጉዋጉል በሆነ አቅጣጫ ሰቀመጥ ያመኛል::

በሳምንቱ ታፍኖ ከታገተበት እንደ ተለቀቀ ሞግዚቴ ፀሐይ መኝታ ቤቴ ድረስ መጥታ ስትነግረኝ በድንጋጤ ከተቀመጥኩበት መነሳት አልቻልኩም:: ከእኔ ቁጥጥር ውጭ ሰንባ ይወርደኛል......እተቀመጥኩበት ሽንቴን ጭር ጭር አደረግሁ:: ስሽና ይታወቀኛል፡ ግን እንዴት ላቁመው? በልቤ ‘ተዋረድኩ’ እላለሁ:: በዚያች ቅንሽ ደቂቃ ተረት መተረቻ ነገር እየሰራሁ እንደሆንኩ ቢገባኝም ከአቅሜ በላይ ነበር:: ሁሉ ሁሉ ነገር ቢከብደኝ ከወንበር ላይ ወደ ወለል ተንሸራትቼ ወርጄ የቤቴን የሸክላ ካሬ እያየሁ ወጸጄ መጥቶልኝ ነበርና......በደስታ አለቀስኩ:: እንደ አሮጊት እየተራመድኩ ወይም ወደሚሰቀልበት እንደሚነዳ ተስፋ እንደቆረጠ ሞት እንደተፈረደበት እስረኛ እየተጎተትኩ፣ እነበረበት ስገባ ከሰፈር ጎረምሳዎች መሃል ተነስቶ ሲያቅፈኝ፣ ደሉኝታዬን ሁሉ ጥዬ ትከሻው ላይ ተንሰቅስቄ አለቀስኩ:: ዛሬ ድረስ ጠረኑ ትዝ ይለኛል፡ ሁለመናው እንደትኩስ ሻይ ይሸት ነበር:: ሰው ባይኖር ሳልጨልጠው ሳልጠጣው እቀራለሁ? ጓደኞቻችን ቸርነት፣ ተስፋዬ፣ ልዑል፣ ገርማሜ፣ ዕገሬዳና እህቷ ወዘተ......እንገታቸውን ሰብረው አጸመጡኝና ቦታ ለቀውልኝ ተቀመጥኩ:: መሽቶ አንዳንዶቹ ጓደኞቻችን ወደ የቤታቸው ሲሄዱ አብሬው እቆይ እንደሆን ጠየቀኝ:: አብሬው ሆኜ ምን አደረግሁ?

እሱ እንቅልፍ ሲወስደው እኔ ጎኑ ተቀምጬ የሚንሸራተት ጋቢውን አለበስኩት......እንዳልቀሰቅሰው እያልኩ በቀስታ የፀጉሩን ጫፍ ነካሁ......ደሞ ማንም እንደማያየኝ ለማረጋገጥ ተገላምጬ ወደ ፊቱ ተጠግቼ የሚተነፍሰውን ተነፈስኩ......ሲገላበጥ የሚያሰማውን ድምፅ እንደ ብራንዳ ሊ when you whisper sweet nothings in my ear[97] ዓይነት ሙዚቃ አዳመጥኩ......ቅር ያለው የመሰለው አዘንተኛ ፊቱን እያየሁ፣ በደህና ስለመጣልኝ እግዜርን አመሰገንኩ (ኮሚኒስትነቴን ረስቼአለሁ) ሲንጠራራና ሲገላበጥ ሊሞት የሚያቃስት እየመሰለኝ እየተደናገጥኩ......መንጋቱ አይቀር ነጋ:: ጠዋት ከተኛሁበት ተነሳሁና ወደ ውጭ ወጥቼ ተታጥቤ ስመለስ ከነጋቢዬ ወደ ራሱ ስቦ አንገቴ ላይ ሳመኝ:: I

[97] የሚያማምር ነገር በጆሮዬ ሹክ በለኝ

missed you[98] የኔ ጌታ I missed you የኔ ጌታ ምን እንዳደረ-ግን በትክክል ትዝ አይለኝም:: ስባንን ወለል ላይ አልጋ ተደግፌ ራቁቴን ተቀምጬአለሁ:: የመኝታቤቱ ጣውላ ይጎራብጠኛል፣ መናገር አያስኘኝም:: ስጋና አጥንቴ ወደ ዕንባ ሳይሟሟ አልቀረም:: እየተንቡዋቸሁ አልጋ ላይ እንደ ሞሳ ወጣሁና እናቴን ሆዱ ላይ አድርጌ ተኛሁ was that love?[99] ወይስ madness?[100]

ከጥቂት ቀኖች በሁዋላ ይሄ ያሳለፈውን፣ ማለት፣ ደርግ ያሳየውን አበሳ ቂም አድርጎ ድርጅቴ ገብቶ እንዲታገል በቀጥታና በተዘዋዋሪ ስገፋፋው፣ እጆቹን በመሰላቸት ያነሳል:: እንደ እናቱ:: እናቱ እንደዛ ናቸው:: እሳቸው ክርክር ቶሎ ያደክማቸዋልና ቆመው እንደሆነ ፊታቸውን አዙረው እጆቻቸውን ወደ ላይ አንስተው ወደ ሚሄዱበት ይሄዳሉ:: ከተቀመጡም ፊታቸውን ባጋጠማቸው አቅጣጫ አዙረው የፈረደበት እጃቸውን አንስተው መሬት መሬት ያያሉ:: ይሄ የአህያነቱ ምስክር ነው:: የሆነ ከትርጉም ውጭ ያለ፣ ሊገለፅ የማይችል በቅቧቃነት ሆነብኝ:: ፈሪነቱ አሳፈረኝ:: በልቤ እንደዛ አልኩት:: መቼም ፈሪ አይደለም ከተባለ ደደብ ነው:: ከአንዱ አያመልጥም:: እነዚህ ሁለቱ ባይሆኑ ከግል ስሜቱ መውጣት የከበደው ራስ ወዳድ ነው:: ሲያሳፍረኝና ሲያበሳጨኝ ቆይቶ ሌላ የሚገርም ከእሱ የማይጠበቅ ነገር ይዞ ብቅ አለ::

### 'ምን?' አትይኝም

ለመሆኑ የቅናት መነሻዋ ምንድነው? ከየት ትመጣለች? የመቅናት ትክክለኛ አለው? ማን በማን መቀናናት እንደሚገባው ያልተፃፈ ፍቅረኞች በዝምታቸው ብቻ የሚያውቁት ሕግ አለ? አንድ ቀን በልቡ ይዞት የከረመውን ያስደነገጠኝን እንግዳ ጥያቄ ጠየቀኝ::

«የመጀመሪያሽ ማነው?»

«ምነው ዛሬ ጠየቅኸኝ?» አልኩት

«አውርተሽኝ አታውቂም»

«ይሄን ያህል ቅሲፋዬ ነው? ምን ያስወራል?» አልኩት

ወይስ ሊያሾግፈው ያልቻለ የፊውዳል ባህል? የትኛውንም አላልኩትም:: አንጀቱ አልነበረኝም:: የምርጥ መኮንኖችን መንግስት በምስድብበት ቃል ዓላዛርን መጥራት አልፈለኩም:: ቢነዘንዘኝ አሁንም አሁንም ቢነዘንዘኝ:

---

[98] ጠፋህብኝ

[99] ፍቅር ነው?

[100] ዕብደት?

«ደብረዘይት አባቴ ጋ ስሄድ የማውቀው ልጅ ነበር:: የአባቴ ጎረቤት(ፈጠራ)፣ ተሳሳትኩ (ትንሽ ደስ ሳይለኝ ይቀራል?) እኔ ረስቼዋለሁ(አልረሳሁትም):: የምልህ እንዴት እንደሆነ ትዝም አይለኝ (በዝርዝር ትዝ ይለኛል፤ ግን ልረሳ እፈልጋለሁ፣ ሳልናገረውም እፈልጋለሁ)» ብለው

«እምልሽ ምን ያህል ብትወጂው ነው? ማለት ልጁን ወይም ሰውዬውን» አለኝ::

«ልጅ ነው:: ሰውዬ አይደለም:: ስታስበው እሱን የምወድ ይመስልሃል ወይስ አንተን?» (ከፋት አይደለም? እኔን ከ 'ሰውዬ' ማያያዙ?)

«ምን አውቃለሁ? የተጨነቅሽለት ትመስያለሽ» አለኝ::

«ምን?» ተናድጄአለሁ::

«ምን አውቃለሁ?» አለ ትከሻውን እየነቀነቀ::

ራሴን በፀፀት ነቀነቅሁ:: እስኪ ካላጣው ነገር መርጦ 'እንትን' ተነጠቅሁ ይላል? አጥንታም ደረቱ አማሉኝ የለ:: ቧንቧ ከፍቶ ሜዞ ሻወር ሲወስድ ስራ ፈትቼ ቆሜ ያየሁት እኔ አይደለሁ? ሲስመኝ ትንፋሽ አጥሮኝ አላቃተትኩም? ዞማ አናቱን በሁለት እጆቼ ይዤ ጢም ያኮረኮረ ፊቱን አላስኩለትም? 'ምን አደረግሽ አሁን?' ቢባል ያደረገኝን ሳላውቅ:: ያ ሁሉ ስለዓላዛር ያለምኩት በአንድ የደብረዘይት ቀልቃላ ሲፈርስ የሚያስገርም ነገር አለው:: ያን ገጠመኝ እያሰብኩ በሚገባ አልመለስኩለትም:: ለምሳሌ በጥፊ ባጮለው:: በጆሮህ ልንገርህ ብዬ ጠጋ ቢል ብወለውለው::

ይሄን ካለኝ ጀምሮ ትንሽም ሳያፍር፣ ከስብሰባ በምሽት ወደ ሰፈር ስመጣ ጨለማ ውስጥ እንደ አውሬ በኩርፊያ ተኮፍሶ አገኘዋለሁ:: በጀት ፍጥነት ከሰፈራችን ትምህርት ቤቴ ድረስ ይመጣል (ምናልባት ፎርፌ ሳይሰጥ አይቀርም፣ ባይነግረኝ እንጂ):: ከክፍል ስወጣ ከሰው እንዳልገናኝ ነው መሰለኝ ወይ ካፌ ውስጥ ደባሪ የምዕራብ ልብወለድ መፅሐፍ እያነበበ ይጠብቀኛል:: ብዙ ጊዜ በተማሪ ትርምስ ተከልዬ ወይም ትምህርት ቤት ግቢ ወደ ሁዋላ እቀርና ጠፍቼበት ሳያገኘኝ ይሄዳል:: ከአፉ ሲወጡ የምሰማቸው የቅፍኝ ቃላትና ግንባሩ ላይ በላብ የሚፃፈው ኮስታራነት ሰላም ነሳኝ:: አንድ ቀን እሱ፣ አማንና እኔ አራት ኪሎ ባጋጣሚ ተገናኝተን ቱሪስት ሆቴል ኮካ ልንጠጣ ገባን:: በማውቀው ምክንያት በሃሳብና በጨዋታ ከአማን ጋር እንቀራረባለን:: አንድ ሁለት ሰአት ቆይተን ከሆቴል ስንወጣ አማን 'ለብቻሽ ላነጋግርሽ' አለኝ:: አስፈላጊ አልነበረም:: ግን ምን አለበት? ለአንድ አምስት ደቂቃ አማን የረባ ያልረባ ሲያወራኝ ቆየና እኔንም አሌክስንም ተሰናብቶን ሄደ:: ገና እሱን 'ደህና ዋል ብዬ' ፊቴን ወደ ዓላዛር ሳዞር ገፁ ተለዋውጦ ለምቦጩን

ሲጥል አየሁት:: አለዋወጡ የሚያስፈራ ነገር አለው:: ዓላዛር ማኩረፊያ ለምቦጭ የለውም:: የሚያምር አፍ አለው፣ ልጣልህ ቢለው እንኳን አይወድቅም:: በዝምታ እየተራመድን አምስት ኪሎ ሙዚዬም ጋ ስንደርስ (ቦታውን አልረሳውም):

«አማን እንዴት ነው የሚያይሽ?» አለ ኮስተር ብሎ:: ቢኮሳተርም የፍርሃት ቅላፄ ድምፁ ውስጥ አለ::

«ጉዋደኛችን አይደለም እንዴ?» አልኩት መረር አድርጌ

«አስተያየቱ ማለቴ ነው»

«ምን ብሎ?»

«ዐይኑ......ስትጨባበጡ......ወላ ምናምን»

«ምንድነው ምናምን ብሎ ነገር? እኔ ዓይኑን አዛለሁ እንዴ? አልጨባበጥ እንዴ? እሱን ጠይቀው ከፈለክ:: እንዲህ አይነት ነህ እንዴ?»

«ፊት ለምን ታሳይዋለሽ?»

«ሰላም አልበለው?»

አማንን የማደንቀውና በትግል መስክ ላይ አብሬው ለመሞት የተዘጋጀሁ ልጅ ብሆንም፣ በሌላ በሌላ ጉዳይ በሃሳቤ አይመጣም:: ደብረዘይት ከተማ ላይ ለመጀመሪያ ከተሳሳትኩ በኋላ በፍፁም ጠንቃቃ ነበርኩ:: ማንንም ከመስመር አላሳልፍም:: ችግሩ ዓላዛር ከታሪክ ውጭ ሆኖ ነው የሚያየኝ:: እኔ ደሞ ታሪክ ልሰራ እየለፋሁ ነው:: ጊዜዬን ለጭቁን ሕዝቦች ነፃ መውጣት መስጠት ነበረብኝ:: ለምወደው ድርጅቴ መስጠት ነበረብኝ:: ሰዎች እንደ እቃ በመታፈስ፣ በመታሰርና በመሞት መስዋዕትነት ሲከፍሉ እኔ ለጥቂት ወሮችና ቀኖች ቦይ ፍሬንዴ ቢቀርብኝ ምን እጎዳለሁ? ስንት ሴት ጓዶች አሉኝ፣ ያለ ወንድ ወዳጅ ስጋና ነፍሳቸውን ለትግል ሰጥተው የሚያስቀና መስዋዕትነት የሚከፍሉ? ስንት ከእኔ የባሱ የደሃ ልጆች እንደእኔ መርጠው ሳይበሉ፣ እንደ እኔ በሚመች አልጋ ተኝተው ሳያድሩ፣ እንደ እኔ በየቲያትር ቤቱ ማደንዘዣ የኢምፔሪያሊዝም ሲኒማ ሳያዩ፣ ደስታቸው ደርጅታቸውን ማገልገል ብቻ የሆነ? አይስከሬም እዚህች አዲስ አባ እየኖሩ ቀምሰው የማያውቁ ስንት ቆንጆ ልጃገረዶች ለል ብ አደሩ ትግል እየተፋለሙ፣ እየተሰቃዩና እየተሳደዱ ይኖራሉ?

*

መጋቢት ወር 1969 ውስጥ ወጣት ሊጋችን በአዲስአበባ ከተማ በየዞኑ ሰላማዊ ሰልፍ እንዲደረግ ውሳኔ አስተላለፈና ለደህንነቴ እንዲያመቸኝ ከሰፈሬ ውጭ ለመሳተፍ ቡልጋርያ አካባቢ 'ሶፎልያ' የምትባል አንዲት ጓደኛዬ ጋ ሄድኩ:: ከዛ ቀደም ብዬ ድንገት ሰላማዊ ሰልፉ ላይ ችግር

ቢያጋጥመኝ መስቀል ተራራ ጀርባ ያለ አንድ ቤት እንድመጣ አማን ነግሮኝ ቦታውን አብረን ሄደን አሳየኝ:: ሰላማዊ ሰልፉን ማድረጉ ትንሽ ቅር ቢለኝም (ፈሪው ወዳጄ ዓላዛር በልቡ ጥርጣሬ አስገብቶ ሳይሆን ይቀራል?) ለአማን ልነግረው ግን አልደፈርኩም:: ግን ደሞ የጠላቴን ዐይን እያየሁ ግንባሩ ላይ መጮህ እፈልጋለሁ......

......ሰላማዊ ሰልፉ ሲጦፍ፣ ጓዶች ላይ ሲተኮስና ሲገደሉ፣ እኔም ከዚያ ሰቆቃ በተቻለኝ አቅም ሸሽ አንድ መብራት የሌለበት የማላውቀው መንገድ ውስጥ ብቻዬን ተሰነቀርኩ:: አማን ያሳየኝ ቤት መሄድ አልቻልኩም:: ወደማውቀው አቅጣጫ ወደ ቦሌ መንገድ ማዝገም ጀመ-ርኩ:: ቦሌ መንገድ ልደርስ ትንሽ ሲቀረኝ ቮልሶችና ጂፖች ሲሯሯጡ አየሁ:: የት እንደ አለሁ በቀላሉ ማወቅ ስለቻልኩ ካርታዬን በአእምሮዬ እያወጣሁ እያወረድኩ ወደ ኋላ ተመለስኩ::

በዛን ወቅት ራሴን ከማዳን ዕቅድ ጋር ደርቤ የማስበው እናቴን ነበር:: ከተማው እንዲህ በተኩስና በጫጫታ ሲታመስ 'ልጄ የት ናት?' ብላ መጠየቋ አይቀርም:: እዬዬዋን እንደምትለቀው አውቃለሁ:: በቶሎ ስልክ አግኝቼ መደወል አለብኝ:: መቶ በመቶ እርግጠኛ ባልሆንም አማን ወደ አሳየኝ ቤት አካባቢ ስደርስ አጥር ላይ ከተሰቀለች ደብዛዛ አምፖል ስር አንድ ሰው አጨበጨበና ጠራኝ:: ያየኛል እንጂ አላየውም:: ቁና ቁና እየተነፈስኩ ስጠጋው፣ ከአማን ጋር አንዳንዴ የማገኘው 'ሳምሶን' የተባለ ልጅ ነው:: በሹክሹክታ ሰላም ተባባልን:: 'በዚህ ነይ' አለና አጠገቡ የነበረ በጨለማው የማይታይ በር (በፀሐይ እንዳየሁት ቡና ቀለም የተቀባ ነበር) ከፍቶ ገባ:: ተከተልኩት:: ግቢው ውስጥ ሶስት ጎረምሶች ጨለማ ውስጥ በዝምታ ተቀምጠዋል:: ሳምሶን እጄን እየጎተተ ወስዶ ሳሎን ሲያስገባኝ ሁለት ወጣት ሴቶችና ሁለት ወንዶች አገኘሁ:: ሁለቱን በዐይን አውቃቸዋለሁ:: ሰላምታ ለማለት ጊዜ አልነበረኝም:: ልጁ እጄን እየጎተተ ወደ ውስጥ ወሰደኝ:: አንድ ክፍል በር ጋ አማንን ግድግዳ ተደግፎ ቆሞ አየሁት:: እንዳየኝ በእጁ እየጠራኝ ወደ ጀርባ አለፈ:: ተከተልኩት:: ይሄ አጠራሩ የሁልጊዜ ልማዱ ነበር:: እንዲህ አይነት የልጅነት ልማዶች አስጨናቂ በሆነ ወቅትም አይጠፉም እያልኩ አሰብኩ:: ይሄ ልማዱ ያለንበትን ሁኔታ ቀላል፣ የተለመደና የየቀኑ ስራ አስመሰለው:: ያፅናናል:: በጀርባ ስንወጣ ፀጥታ ነበር:: የሚቆላ ቡና ይሸታል:: ለአፍታ ሰፈር እቤቴ ያለሁ መሰለኝ:: አማን ዞር ብሎ ትከሻዬ ላይ ያዘኝና:

«ለመሆኑ ደህና ነሽ? አስቤ ነበር» አለ በጭንቀት ድምፅ::

«ደህና ነኝ:: ስማ አማን! ለእናቴ ልደውልላት» አልኩት

ትከሻዬን ለቆ ወደ ኋላ ተመለሰና ለአንዲት ሴት የሆነ ነገር በትግርኛ አወራት

«ብዙ አይቆይ እ?» ስትል ሰማኋት

እኔ ስልክ ለማውራት አንድ ክፍል ስገባ ከሳሎን የሆነ ፈንክ ሙዚቃ ተለቀቀ::

«ከፍ አድርጉት!» አለ አንዱ

«ሬድዮ ብታደርጉ አይሻልም እንዴ?» አለ አንዱ

«ከፈቱአ» አለች አንዷ

«ይሻላል» መለሰ የመጀመሪያው ድምፅ

ስልክ መታሁ......

«ፓርቲ እያደረግሽ ነው እዛ? እኔ ደሞ እንዴት ልሁን፣ ወታደር የጨረሰሽ መሰለኝ» አለች እናቴ በቁጣ:: ስለ ዓላዛር ልጠይቃት አሰብኩና ሰፍሳፋ እንዳያስመስለኝ ተውኩት:: ለእናቴ ሰው በመኪና እንደሚያደርሰኝ ነግሬአት ስልኩን ዘግቼ እዛው ክፍል በሃሳብ ስምጭ እንደተቀመጥኩ፣ አማን መጣና ጎኔ ተቀመጠ:: እንደ ጨዋታ እያለ ጀርባዬን ሲያሻሽኝ፣ የሮጥኩት ሩጫ ያደከማቸው እግሮቼ፣ በመፈክር ጩኸት የተቃጠሉት እንጥሎቼና የደከማቸው ጡንቻዎቼ መረጋጋት ፈለጉና ለማረፍ አማንን ተደገፍኩት:: አንድ ልጅ ያለንበት ክፍል መጥቶ:

«ሁለት ሰዎች ብቻ ይውጡ!» አለ

በተራ በተራ ወደ የቤታችን እየተለቀቅን ነው::

«አንዷን ልጅ ከጎኔ መቷት፣ ምን ሆና ይሆን?» አለ አማን

«ሁለት ልጆች አጠገቤ ወድቀዋል:: ምን እንደሆኑ እንጃ:: ምናልባት ሳይበልጥ አይቀርም» አለ ልጁ:: ገፁ ላይ ጥልቅ ፍርሃት ይነበባል:: ይሄን ተናግሮ የእኔ ተራ እንዳልሆነ ሲገባው ከክፍሉ ወጣ::

ከሁሉ ለመሸሽ የምችል አይነት ወደ አማን ደረት ተጣበቅሁ:: አማን ጓደኛዬ ነው፣ ጓደኛዬ ነበር፣ እና ምን አለበት? አይኖቼን ገርበብ አድርጌ ዓላዛርን አሰባለሁ:: ዓላዛር አይኖቹን ጨፍኖ እየተልቆሰቆሰ ሲያቅፈኝ:: በፀሐያማ ቀን በቀስታ ታከኝ ሲቆም:: በሃሳቤ እዛና እዛ ስቀባዠር አማን እናቴን ሲስመኝ ሰማሁት፤ ዓላዛርን ማለም አቆምኩ:: ግራ በመጋባት መልክ ቀና ብዬ አማንን አየሁት:: ቀና ብዬ እያየሁት ሳለሁ ሳልጠብቀው አፌ ላይ ሙሉ በሙሉ ሳመኝ::

በፍጥነት ከእቅፉ ተላቀቅሁና ከተቀመጥኩበት ተነስቼ ቆም ብዬ ጃኬቴንና ሱሪዬን አስተካከልኩ::

«የት ነው?» አለኝ

«ቤት ለመሄድ ነበር» ተራዬ እንዳልሆነ አውቃለሁ

«መኪና የለም:: ትንሽ ረጋ በይ:: ተራሽ ገና ነው»

የምመልሰው አልነበረኝም፡፡ ያደረገው ነገር እንዳልተስማማኝ ሁለታችንም ይገባናል፡፡ ያልተስማማኝ በሁለት አቅጣጫ ነው፡፡ አንድ ቢያምርም ባያምርም ገና የጓደኛው ፍቅረኛ ነኝ፡፡ ሁለት በዚህ አይነት የጭንቅ ጊዜ እንዲህ ማሰቡ የሚያሳፍር ነገር አለው፡፡ ባለጌ ቢሆንም ባለጌ መሆን አልፈለኩም፡፡ ከንፈሮቼ ደረቅ ቢሆኑም እንዲገባው ብቻ አፌን ጠረኩ፡፡

«ቁጭ በይ ነይ፡፡ ይቅርታ»

በዐይኔ ቂጥ አየሁት፡፡ ከአማን በጣም ልጅ ነኝ፡፡ ግን ፈርቶኛል፡፡ ዓላዛርን እንደምወደው ያውቃል፡፡ ምናልባት ተዋረድ ሳያወጣ አልቀረም፡፡ መጀመሪያ ኢሕአፓን ትወዳለች ከዛ ዓላዛርን ከዛ......ግን ዓላዛር የነካውን ገላዬን ማንም አይነካም፡፡ ታጋይ ወንድሜን ሳላስከፋ፣ ዓላዛርንም ሳልከድ ጎኑ ሄጄ ተቀመጥኩና እጄን ሰጠሁት፡፡ እጁን በእጄ ይገፔ በቀረው ገላዬ ሳልነካው ተቀመጥኩ፡፡ አማን አንድ ሁለቴ ዓላዛር ለተቀደሰ ትግል መታጨት ሊገባው የማይችል ግድ የለሽ እንደሆነ በቀልድ አስመስሎ የነገረኝ ትዝ አለኝ፡፡ እሱ ምኞት ውስጥ ባልሳተፍም እኔን መመኘቱ ከዓላዛር ጋር ያለኝ ነገር ፍፁም እንደልሆነ ገምቶ ያደረገው መስሎኝ አሳሰበኝ፡፡ አማንና ዓላዛር ማርክስና አብዮት ከመምጣታቸው በፊት በግድ-የለሽነታቸው ይተናነሱ ነበር እንዴ? አብረው ከተንዘላዘሉ በኋላ 'የለሁበትም' ብሎ ማማት ምን ማለት ነው? ግን አላልኩትም፡፡ ቢሆንም አማን የዘመኑ ትክክለኛ ሰው ነው፡፡

«ቴቢ የዋህ ነሽ» አለ አማን፡፡ ቀና ብዬ አየሁት፡፡ አይኖቹን ከዐይኖቼ መለሰ

«ለምን?» አልኩት

«በአሁኑ ሰአት ዓላዛር ይሄኔ አልማዝ ጋ ነው» አለ

«ምን? የማን አልማዝ?» አልኩት

«የሰፈራችሁ አልማዝ»

«አልማዝ የምትባል አላውቅም»

«የጉርጉሱም ቡና ቤት ባለቤቷ»

«መስከር ከጀመረ ቆየ»

«መስከር ሳይሆን ሌላ......» አለ

ቀና ብዬ አየሁት፡፡

በብስጭትና በፈገግታ ያየኛል፡፡ ብስጭቱ ለምን? ፈገግታው ለምን? ለእኔ ተቆጭቶ? ጓደኛው ባለጌ በመሆኑ ተበሳጭቶ? እንዴት ሁለቱ ተፃራሪ ነገሮች ተቃቅፈው ፊቱ ላይ ቁጭ አሉ? መከላከል ነበረብኝ፡፡

«አያደርገውም» አልኩ:: ቋቅ ሊለኝ የጀመረ መሰለኝ::

እንዴት ነው መሆኑን ሳላረጋግጥ ቋቅ የሚለኝ? የሚያስጠላ ወሬ የሚያወራው ሰው፣ ከሚያስጠላው ነገር በምን ይለያል? አማን ያመንኩት መስለው መሰለኝ ፈገግ ብሎ አየኝ:: በትክክል እንዲገባው፣ በግራ እጄ ወደ ደረቴ እየጠቀስኩ:

«በሁለመናዬ ዓላዛር ነው:: ከዛች አይነት አሮጊት ጋር እንዲህ አይነት ነገር አያደርግም:: አይልከሰከስም:: ከእኔ ያማረች ቢፈልግ በደቂቃ ያገኛል:: ሂ ኢዝ ኤቭሪቲንግ ፎር ሚ»[101]

ይሄን እያልኩ ግን የአማንን የተረጋጋ ሳቅ፣ ('መስሎሻል' የሚል የመሰለውን) ሳይርበተበት የተናገረው መረጃ እውነት መስሎኝ ከውስጥ ሁለመናዬ ተቃጠለ:: እውነት መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ እንኳን በማልችልበት ሁኔታ አማን የተናገረው በአንጀቴ የሆነ እጥፋቱ መሃል ገብቶ ቁጭ አለ......ደመነፍስ የመሰለ ነገር:: ፈራሁ:: ለአማን ከዛ በላይ አልነገርኩትም:: 'አትዋሽ' ብዬ ከጎኔ አላባረርኩትም:: ፈዝዤ ተጎለትኩ:: የያዘውን እጄን ደሞ አለቀቀም:: ይሄ የሰማሁት ወሬና በምሽቱ ያጋጠሙኝ መንገላታት ተደምሮ የምሰራው ጠፋኝ:: ከሁሉ ከሁሉ መጀመሪያ ቤቴ መሄድ ፈለኩ:: ዓላዛርን ለማየት:: ስለ አልማዝ ልጠይቀው አይደለም:: ዓላዛር ጤና እንደሆነ ለመመልከት:: እጆቹን፣ ፊቱን፣ ደረቱን ነካክቼ፣ ድምፁን ሰምቼ ፊትሼ እዚህ ምድር ላይ በሰላም እንዳለ ለማረጋገጥ::

ማታ አራት ሰአት ላይ ተራዬን ጠብቄ በተመደበችልኝ የቤት መኪና ከምሽቱ አምስት ሰአት ሽሮሜዳ ገባሁ:: የአጥር በር እያንኳኳሁ ቀና ብዬ ወደ ዓላዛር ቤት አየሁ:: ፀጥታ ነው:: እናቴ በር ስትከፍትልኝ እያለቀሰች ነበር::

«ከእኔ ለቅሶ ይልቅ የማንም ባእድ ቤት በለጠብሽ አይደል?» እያለች:: ገብቼ ገና ጀርባዬ አልጋ ሲነካ እንቅልፍ ጠርጎ ወሰደኝ::

ስባንን ከጠዋቱ ሶስት ሰአት ነበር:: ከአልጋ ተነስቼ ፊቴን ለመታጠብ ሳንጎዳጉድ፣ ዓላዛርን ከልቤ ውስጥ ባላወጣውም ዓላዛርን በመርሳት ላይ ያለሁ መሰለኝ:: እንዴት ነው እየወደዱ መርሳት? ዓላዛር ከሴትነቴ የተቆላለፈ ማንነቴ አይደለም እንዴ? የሆነ ባዶነት ተሰማኝ:: ይሄ እንዴት ሊሆን እንደሚችል እንጃ:: ወይስ ትውስታው ነው ፍቅር የመሰለኝ? ማፍቀሬ ትውስታ ሆኖ? ሳንራራቅ መራራቅ:: የሆነ የሚያስፈራ ነገር አለው:: የሰላማዊ ሰልፉ ማታ በመሸሽ ላይ እያለሁ፣ ትዝ ያሉኝ ብቸኛዋ እናቴና ዓላዛር ነበሩ:: በኮረኮንች ላይ እየተወለካከፍኩ ስሮጥ የከበበኝ ጨለማ መሃል የታወሱኝ እማማና ዓላዛር ነበሩ:: ፍቅር ከዋናው አላማዬ

[101] ሁሉን ነገር ነው ለእኔ እሱ (his is everything for me)

በላይ የሚንሳፈፍ መለኮታዊ ጉድ የለውም? አልጋዬ ላይ በውስጥ ልብስ ተቀምጬ ትናንት ያሳለፍኩትን ደጋግሜ አሰብኩ። መኝታቤቴን ልክ ሞቼ እንደተነሳሁ ሁሉ ዙሪያዋን እንደሰው አየሁዋት። እዛ ጋ ያለችዋን ጥቂት መፃህፍት የተሸከመች መደርደሪያ፣ እዛ ጋ ያለችዋን ዓላዛር ድሮ ቀድሞ ለአንድ የልደት ቀኔ የሰጠኝ አሻንጉሊት፣ ልብሶቼን የያዘው ቢጫ ኮመዲና፣ ኮመዲናው ላይ ግራና ቀኝ ተካፋች በሮቹ ላይ የተለጠፉት ከካሌንደር ላይ የገነጠልኩዋቸው የሰሜን ቀበሮ ስዕልና ጉም ውስጥ የተኙ የሰሜን ተራሮች፣ *አሲምባ እንዛን ይመስል ይሆን?*፣ ከጥልፍ ጨርቅ የተሰሩ ጥንድ መጋረጃዎች፣ ግድግዳ ላይ የተሰቀሉ የእማማና የአባባ ፎቶዎች፣ ፒያሳ ስቲዲ የተነሳሁት ትልቅ ጉርድ ፎቶ (የዚህ ትንሹ የስምንተኛ ሚኒስትሪ ፎቶዬ ነበር)፣ ሁልጊዜ የማይለወጠው የክፍሌ የሳሙና፣ የጨርቃ ጨርቅና የቀዝቃዛ አየር ጠረኗ፣ የረጋው ፀጥታዋ-......እጄን ባነሳ የሚበጠበጥ የመሰለ። ምናልባትም ገነት እዚህ ናት። ገነት ምናልባት ይህቺ ናት። አእምሮዬ ግን በፍጫ የተሞላ ነው። አእምሮዬ ውስጥ ላምነው ያልፈለኩት ፍርሃት አለ። 'ፈሪ' መባል ግን አልፈልግም። ልተፋው እንዳልፈለኩት ምራቅ ሰው ፊት ስሆን እውጠዋለሁ። የአማን ነገር ይከነክነኛል። የአማን ከንፈር ያሳክከኛል። በእጄ አፌን ጠረግሁ። ውስጥ ሱሪዬን ከወገቡ ሰፋ አድርጌ ወደ ታች አየሁ። የማየው ጨለም ያለ ቦታ ነው። እዛ ምንም እያየሁ በየጎዳናው እያወኩ፣ መንገደኛ ሲረብሹ፣ እየተላፉና እየተንጓጀሱ ሰው ሲያደነቁሩ የነበሩ ወዳጆችን ይህቺ እዚህ ጨለማ ውስጥ የተደበቀች ነገር እንዴት ልታከዳዳቸው እንደቻለች ማሰቡ ከበደኝ። የቀመሰኝ ዓላዛር ባልቀመሰኝ አማን ሲቀናበት። የሚያስቅ፣ የሚያስገርም፣ ግራ የሚያጋባ ነገር አለው። ምናልባት እንደ ሃይማኖት ነኝ። ገላዬ የሆነ ደጀሰላም ነው። ወይም የሆነ መቅደስ። ወንዶች ሁሉ ሊሳለሚት የሚፈልጓት (አይቼአለሁ የብዙዎቹ አይኖች ገላዬ ላይ ሲፈራገጡ......*ይባላል?*) ባይቀናንም ስለት መሳላችን አይቀርም። ፀሎታችን ባይመለስም፣ እሁድ እሁድ ማርያምን እንሳለ ማለን። ልብሴን አስተካክዬ፣ የተበታተነ ፀጉሬን ጎነጎንኩና ከአልጋ ወጣሁ። የወለሉ ሲሚንቶ ብርዱ እግሬን የውጋት ያህል ይቆረጥመኛል። ቶሎ ብዬ ነጠላ ጫማዬን አደረኩ። ተረጋግቼ ፒጃማዬን አውልቄ፣ ውስጥ ሱሪዎቼን ለውጬና ቀሚሴን ደርቤ ከመኝታ ቤቴ ወጣሁ።

እማማ ነጠላዋን ዘቅዝቃ ተቀምጣ አገኘሁዋት።

«ደህና አደርሽ አንቺ ዱርዬ፣ ያቺ ጓደኛሽ ጋ ነበርሽ? ለምን እሷ አትመጣም አንዳንዴ? ከተማ ተረብሾ እንዴት አስቻለሽ ማርፈድ?» አለችኝ።

«ለዛ ነው የዘገየሁት እማ። ጎረቤት መኪና ለምነን ነው የመጣሁት»

«እዚህ ተኩሱ ጦፎ ነበር......መች ተኛ ሰፈሩ»

«ምን ሆነ?»

«ልጂ ምን ይወራል……»

ዓይኖቿ ቀልተዋል:: ልብ አላልኩም ነበር::

«የሃምሳ አለቃ ጥላሁን ልጅ ደበበ ተገደለ:: ያን የመሰለ ልጅ……ታዚና ፊት ለፊት ተጥሎ ተገኘ»

በድንጋጤ እቆምኩበት ደረቅሁ::

«ከዛሬ ጀምሮ ሳይመሽ ቤት እንድትመጪ……ወደ ስድስት ኪሎ ማአት ወጣት አለቀ አሉ አያድርስ:: ነገርኩሽ ንቅንቅ እንዳትይ» ከተቀመጠችበት ተነስታ ነጠላዋን እያመቻቸች ስትወጣ:

«እናቱን ልያት:: የደሃ ልጅ……ደርሶልኝ ይጦረኛል ስትል……ደሞ ዓላዛር አስቦ በጠዋት መጥቶ ጠይቆሽ ሄደ»

እንዲህ ስትለኝ፣ የደበበ መስዋዕትነትና የዓላዛር እኔን ለማየት መምጣት በግብ በመራራቃቸው መሰለኝ ተደበርኩ:: አማን በአእምሮዬ መጣ:: ዓላዛር ያለጥርጥር የሆነ ሴታ ሴት መሰለኝ:: የሆነ ያልወለደኝ እማማ:: ጡት ባያጠባኝም ያሳደገኝ ምንትስ:: ያን የሚወደኝንና የምወደውን ልጅ ስሮጥና ስሸሽ አስታውሼው፣ ስረጋጋ፣ በዝምታ በልቤ እንዲህ አልኩት: *ማዘሬ*[102] *ነህ ምንድነህ?*

---

[102] እናቴ

## እስኪ መቅደስ እናርክስ

አጋጣሚው ፈቅዶ ከዓላዛር ጋር ከተገናኘን ቀዳዳ ፈልጎ ወይም ፈጥሮ ይጨቃጨቀኛል:: ሁለት ስነ ስርአቶች ነበሩን:: አንደኛው እንጠጣ ደን ስንገባ ከመሳሳምና ከመላፋት ሌላ ስድ ነገር እናደርግም:: ሁለተኛው እኔ መኝታ ቤት አንገባም:: ለመጀመሪያ ጊዜ ከቁጥጥር ውጭ ቤቴ ሳሎን የሆነው ከሆነ በሁዋላ እቤቴ ሊጫወት ሲመጣ በፍፁም ወደዛ አይነት ድርጊት ብንፈልግ እንኳን አንገባም:: አንድ ቀን በሆነ አጋጣሚ ተገናኘንና ወደ እንጠጣ ወጥተን ትንሽ እንድንሸራሸር ጠየቀኝ:: ድሮ (ምን ሳድርግ 'ድሮ' ልበል እንጂ) እንዲህ ሲለኝ የማያሳክከኝ ቦታ አልነበረም:: በቸልታ፣ እኔም ትንሽ ተደብሬ ስለነበር (ፖለቲካው ያሳስባል) 'አሞራው' የምንለው ቦታ ወጥተን በዝምታ ተቀምጠን የምናስበውን ስናስብና ልቤ ያልገባ የማይመስጠኝ ወሬ ስናወራ ቆየን:: ሙሉ በሙሉ ልገልፀው የማልችለው እየደጋገመ የሚነጣጥለን ሁኔታ መሃላችን ገብቷል:: እሱ የተለያየ ቀለም የሚቀባው የቅናት ንዝነዛና አማን የነገረኝ ወሬ ይጎራብጡኛል:: ከመሬት እየተነሳ እምነቴንና አላማዬን ይጋፋል:

'መቼ ነው አገሩ ዲሞክራሲ በዲሞክራሲ የሚሆነው? አማን አያውቅም?'

'ይሄ ኮሚኒዝም በበቅሎ ነው የሚመጣው አልደርስ አለ'

'ብታሸንፉ እንቺ ያው ደብረዘይትን ስለምታውቂ በጀት በኤፍ ፋይቭ ምናምን ታስተዳድሪያለሽ ሃሃሃሃሀ'

እንዲህ የመሳቢያ ነገር ማለት አበዛ:: ምንም ሳልመልስለት እየሰማሁ እተክዛለሁ:: ስተክዝ ስለ አልማዝ ስለ ጉርጉሱም ማሰብ እጀምርና መሆን እንደሚችል እጠራጠራለሁ:: ጥርጣሬውን ሳመነኝርክ የአማንን ወሬ ለማመን ዳር ዳር እላለሁ::

ጣጣ::

የእኔ እህት

እንኪ ጣጣ

ለዲሞክራሲ የማደርገው ትግሌን ከመባለግ ጋር በማዛነቅ አስከፋኝ:: አማን የነገረኝን ወሬ ስላላመንኩ፣ የአልማዝን ነገር ሳነሳበት አልፈለኩም:: የአማንን ወሬ ባምን ማስረጃዬ ወሬ ሊሆንብኝ ነው:: ግን ልቤ እመኝው እመኝው ይለኛል:: ዓላዛር እንዳልተመቸኝ ሲገባው ልክ እኔ ጥፋተኛ እንደሆንኩ ሁሉ አኩርፎኝ ተቀመጠ:: ጩኸቴን መቀማት አይነት:: አጠገባችን የነበረ ለጋ ብርማ የባሕር ዛፍ ቅጠል በጥሶ በፊት ጥርሱ እየነከሰና እየተፋ እንደማያውቀኝ ሁሉ ሲያየኝ ቆየና:

«ትደነቂያለሽ የለችም አይደለ? ለምን እናንተ ቤት አንሄድም? ሻይ እንጠጣ» አለ

ከአፉ ላይ የቅጠሉን ዱቄት በማባበል ጠረግሁለት:: የጠረኩለት ንዝንዙን እንዲረሳልኝ ነበር:: ድለላ ነው:: ዓላዛርን ደልዬው አላውቅም:: መደለል መዋሸት ነው:: 'ሻይ እፈልጋለሁ' ይበል እንጂ ሻይ አላሰኘውም:: እንዳላሰኘው ባውቅም 'አላሰኘህም' አላልኩትም:: ሻይ ካሰኘው ቤቴ መምጣት የለበትም:: ከአስተያየቱ ምን ለማድረግ እንደፈለገ ጠር-ጥሬአለሁ:: ልሰራው የማልሻውን፣ የተስማማንበትን ትክክል ያልሆነ ነገር እንዳደርግ እየገፋፋኝ እንደሆነ በደመነፍስ ጠርጥሬአለሁ:: ሳይጠጋኝ እጄን እንኩዋን ሳይዝ እንዲሁ ጎን ለጎን እየተያየን ቤቴ ደረስን:: 'ያዘኝ' አላልኩትም:: በመጠኑ መኩራት፣ (ቢገባውም ባይገባውም) ማኩረፍ ነበረብኝ (ጎኔ ካለ እጁን ካልያዝኩት እጄን ይበላኛል):: 'እንዴት ነው ደሞ እያኮረፉ ለሻይ መሄድ? ለሌላም መሄድ?' ቢባል የምመልሰው የለኝም::

ቤት እንደ ደረስን በየክፍሉ እየሄድኩ እናቴን እየጠራሁ አለመኖሯን ካረጋገጥኩ በሁዋላ ሻይ ጣድኩ:: ወደ መኝታ ቤቴ ሄዶ ሳይገባ በሩ ጋ ቆሞ ሁለመናዋን አጠና:: ግድግዳ ላይ የእናቴና የአባቴ የሰርግ ፎቶ አለ:: የሚጠና ነገር ባይኖረውም በጉጉት አየው:: ክፍሌን፣ እማማና አባባን ያማያውቃቸው ይመስላል:: እኔ ግድግዳ ላይ አይዛክ ሄይስ ወይም ሬይ ቻርለስ የለም:: ቢጂስ፣ አባ፣ ምናምን ሌላም ዘፋኝ:: እንደ እሱ ክፍል አይሰፋም:: እንደሱ ክፍል በየቦታው ካሴት አልተዘረገፈም:: አልፎው ሄጄ አልጋ ላይ ላለመሆን የማይመቸኝን አንድ የእንጨት ወንበር ስቤ ተቀመጥኩ:: አልፎኝ ሄዶ መስኮቱ ጋ ቆሞ ወደ ላይ አየ:

«አንቺ የሰይፉ ቤት ከዚህ በደንብ ይታያል?»

ድሮም እንደሚታይ ያውቃል::

መጋረጃውን ጋረደ:: አንገቴን ሰበርኩ:: እናቴ ሳንሰማት ገብታ ሳሎን ያለች ይመስለኛል:: ከሁዋላው አየዋለሁ:: አፍሮውን፣ ወገቡን፣ እጆቹን ኪሱ ከቶ ቸል ያለ የመሰለ አቋቋሙን::

«ሻይውን ልየውና ልምጣ»

ልነሳ ስል እጄን ያዘኝና ሊስመኝ ታገለኝ:: እናቴ ባሉን ያለች ይመስለኛል::

«ብርጭቆ አሰናድቼ መጣሁ» አልኩና ነጥቄው ወጣሁ::

ጀበና አለቃልቄ እየጣድኩ ይሄ የሚያስፈራኝ ጊዜ በፍጥነት እዛው እንደቆምኩ ቢያልፍ፣ እናቴ ቶሎ ከሄደችበት እንድትመጣ ተመኘሁ:: ወገቡን አስባለሁ ግን:: ወገቡ እላዬ ላይ እንደ ሰማይ ሲቀነፍ:: ወገቡን፣ ትግሌን:: ወገቡን፣ ትግሌን፣ ጀበናዬን......

«ቴቢ!!!»

ተጣራ::

እናቴ የአጥሩን በር ገፍታ የገባች ይመስለኛል:: የቤቱን በር ከፍቼ ግራና ቀኝ አየሁ:: የግቢው ፊት ለፊት እንደተኛ አራስ ልጅ ፀጥ ያለ ነው:: ወደ ዓላዛር ሄድኩ:: አልጋ ላይ በጀርባው ተጋድሞአል:: ካናቴራው ወደ ደረቱ ተሰብስቦ እምብርቱን አያለሁ:: ያልበላ የመሰለ አንጀቱን አያለሁ:: ሳልጠጋው በር አጠገብ ግድግዳ ተደግፌ ቆምኩ:: ሆዴ ይተራመሳል:: ውስጤ መናድ ጀምሯል:: ያየኛል:: ግንባሩ ይኮሳተራል:: ግንባሩ ይፈታል:: ዓይኖቹን ጨፍኖ የሚያልም የሚስለመለም ይመስላል:: ፊቱ ላይ አያለሁ በራሱ አእምሮ የፈጠረውን የቅናት ታሪክና የአጀማመሬን ስህተት ሊረሳው እንዳልቻለ ወይም እንደማይችል::

«ለምን ቆምሽ?»

«ሻይው እንዳይገነፍል እየጠበቅሁ ነው»

እናቴ ከግቢ እውጭ ከሆነ ሰው ጋር ወሬ ይዛለች ይሄኔ:: ከተጋደመበት መጥቶ እቆምኩበት አቀፈኝ:: በዐይነሕሊናዬ በር በር አያለሁ:: ምንአለበት ዛሬ ብትተወኝ......በተጋረደው መጋረጃ የዛፍ ጥላ አያለሁ: እዛና እዛ ይላል: እጮልቆ ሊያየኝ የሚለፋ::

የመኝታ ቤቱ ድባብ፣ የአልጋው ምቹነት፣ የእሱ ልጅ መልከመልካምነት፣ የእኔ በጭንቀት መወጠርና ይሄን ውጥረት ለመተን-ፈስ ማሰብ ሲጠረቃቀሙ እንደማልተወው ገባኝ:: የእሱንም የእኔንም ግፊት ለማክሸፍ ግን እለፋለሁ::

እየሳመ ወስዶ (እኔም መልሼ እየሳምኩት) አልጋ ዳር አስቀመጠኝ:: ልከላከልበት ያነሳሁት እጄን ደከመው::

«ሻይው እንዳይገነፍል»

«አሁን አይደለም የጣድሽው?»

ትከሻዬን አቅፎ ወደ እሱ ሳበኝና በቀስታ ሳመኝ:: ዓይኖቼን ጨፈንኩ......

ጠባብ አልጋዬ ላይ በጀርባዬ ነበርኩ፣ በሚከፈቱ በሚከደኑ ዓይኖቼ በር በር እያየሁ:: የሹራቤን የደረት ቁልፍ ሲፈታ ዝም አልኩት (ተስፋ መቁረጥ ሲደመር መፈለግ):: ከንፈሮቹ የተጋጠሙበት ቦታ አፍርንጅ ይመስላል:: አይኖቹ ሰንባ ያቀረሩ ይመስላሉ:: ጎንበስ ብሎ ጡቶቼ መሃል ሳመኝ:: ከዚህ ያማረ ድርጊት ጀርባ ንጼቴ አፈር እየማሰች ታስባለች:: ባልገባኝ ምክንያት ማልቀስ እፈልጋለሁ:: 'አልፈልግም' ልለው እፈልጋለሁ:: ፊቴ የአበባና የወፍ ስዕል የተጠለፈባት ትራሴ ውስጥ በተስፋ መቁረጥ ተቀበረ:: የውስጥ ሱሪዎቼ ወልቀው ጎኔ እንደ ተጨባበጡ ወረቀቶች:: መደፈን በጀመሩ ጆሮዎቼ የእናቴን ኮቴ ልሰማ እለፋለሁ......እያየሁ......እየታወርኩ......እየሰማሁ......እየደነቆርሁ......እያየ ሁ......እየደነቆርኩ......እየሰማሁ...... ደሞ......ማርያም ለምን መውደድን ፈጠርሽ? እያልኩ......በተከፈተ መስኮት ያ ደርዙ በእናቴ ሙያ የከበረ መጋረጃ እየተነሳና እየወደቀ......ዓላዛር እፈጠረው ባሕር እንዳልሰምጥ አንገቱ ላይ ተጠምጥሜ ......

«አንቺ ልበ ቢስ ጀበና ጥደሽ ተኛሽ!!»

መነሳት አልቻልኩም:: ለመነሳት እጥራለሁ......የምለብሰው ነገር ፍለጋ በነሲብ ባበደ፣ በደከመ እጄ ስፈልግ፣ ዓላዛር ከላዬ እየቃሰተ ተነሳና ወደ ጎን ተገልብጦ በአልጋና በግድግዳ መሃል ወደቀ:: እንደ ምንም ነጠላ በላዬ በችኮላ ደርቤ እየሮጥኩ ሄጄ የመኝታ ቤቱን በር ልዘጋ ስል ከእናቴ ጋር ተገጣጠምን......

«ቀን በቀን ተኝተሻል? እንቅልፋም!:: ራቁትሽን ደሞ ከመቼ? ቢጃማሽ የት ጠፋ?» በሩን ቶሎ መለስኩት

እግሮቼ ይንቀጠቀጣሉ:: በአእምሮዬ ከዳር እዳር የዓላዛር......ለስላሳ ቅላት......የዘጋሁትን በር እንዳልወድቅ ለአፍታ ተደግፌ ቁና ቁና እየተነ ፈስኩ ቆምኩ......ቶሎ ወደ ወለሉ ሽርተት ብዬ ተቀምጬ የተዘረጋጋው የተተራመሰው አለም ተጣጥፎ በእጄ እስኪገባ ጠበቅሁ::

'እንቅልፋም!' ቃሉ የሚያስቅ ነገር አለው:: ካለው ከሚሆነው ነገር ጋር አልገጥም በማለቱ መሰለኝ:: ተዋረድኩም እላለሁ::

«ጀበናውን አውጭልኝ ፔቱ ሳይቃጠል!!»

እየተበሳጨሁ እልጋዬ ላይ በሆዴ ወደቅሁ:: ዓላዛር ፀጥታውን ካጠና በሁዋላ ከአልጋው ስር ብቅ አለ:: በተስፋ መቁረጥ ፊቴን ብርድ ልብስ ውስጥ ቀበርኩ:: ዓላዛር መጥቶ እላዬ ላይ ተጋደመ......በጥርጣሬ ወደ በሩ እየሁ:: ተቆልፎአል:: ያልበረደች ስሜቴ እንዲህ ከርቀት ስትብለጨለጭ እሰማታለሁ......ትኩስ ሆዱ ጀርባዬ ላይ:: ሁሉ ማለቅ የለበትምና......

«ተነሳልኝ»

«እምቢ.»

«ጎዳኸኝ:: ላንተ ነው እንዲህ የማደርገው:: እወድሃለሁ:: አሁን በመስኮት ወጥተህ ሂድ:: እንዳንተ የምወደው የለም በቃ እሺ?......»

ያልበረደ እፍረቱን አያለሁ:: በማፈር አይኖቼን ጨፈንኩ:: ያ ነገር ውስጤ እንደነበረ ማሰብ አልፈለኩም:: እያጉረመረመ ልብሱን ለባብሶ በመስኮት ወጣ:: አወጣጡን አልረሳም:: ከመሃል አቋርጦ ሰውነታን ተቀብሎ ያለ እኔ እምቢታ ትቶኝ አለመሂዱ ስር ከሰደደ ደካማነቱ የመጣ መሰለኝ:: ማሕፀኔ ቢነድም በዲሲፕሊኔ የበላይነት ተሰማኝ:: ከእሱ ቆራጥ ነበርኩ:: ግን አይቼው በማላውቅ መልክ አዝኖ ነበር:: ደስታውን (ደስታችንን?) በወግ መነጠቁ ይሆናል:: እዛች ክፍል ውስጥ የማይነገር ብዙ ሃጢያት አስቤአለሁ:; ብዙ አልሜአለሁ:: ግዙፍ ሆነው ቢከሰቱ በሙሉ የዓላዛር ራቁትነት ናቸው:: ክፍሉም አይበቃቸው:: ከተደሰት- ኩበት ጊዜ ሁሉ ጎልቶ የሚታየኝ ይሄ አወጣጡ ነው:: እንድሰማው ያልፈለገው ከጉሮሮው የወጣው ቃሉ ነው:: ምን ነበር? ምንድን ነበር ያጉረመረመው?

ከዚህ ቀን በሁዋላ የተገናኘነው ለደቂቃዎች ያህል ሁለት ሶስቴ ቢሆን ነው:: ይሄንን ቀን ሳስበው 'ቆራጥ ነሽ' ብዬ ራሴን የማዳንቅበት አዲስ ፍቺ ሳልሰጠው አልቀረሁም:: ወደ ሁዋላ ሲታይ ያለፈው ሁሉ አዲስ ቋንቋ ይሆናል፣ በዛሬ እንደበት አዲስ ትርጉም ያበጃል:: እዛው ጎኑ እያለሁ (ዘራፍ ጎረቤቱ!) ግን፣ እዛው እያሰብኩት (ሁለተኛ ዘራፍ ጎረቤቱ!) ትዝታው ይወረኛል:: እንዴት እዚህ እያለ ትዝታው ይበላኛል? ይመዘምዘኛል?

## መለያየት ምንድነው?

የፖለቲካ ጉዞዬ መደነቃቀፍ ሲጀምር፣ ደረተ ሰፊው ድርጅታችንም ጡንቻው እንደ ኮረት ሲናድ፣ ሃሳብ ጠዋትና ማታ ሲዘቅዘኝ፣ ትንፋሼን ከድል አድራጊው ሕልሜ እየተበደርኩ መልካም የድል ጊዜ እንዲመጣ እየተመኘሁ ቀኖችን ሳሳልፍ፣ በእግዜር ማመን ያቆምኩት ልጅ ቅድስት ስላሴና ቅድስት ማርያም እየገባሁ ድንጋይ ላይ ስነጠፍ፣ ዛፍ ጥላ ስር ቆሜ ስተክዝ፣ የማውቃቸውም የማላውቃቸውም ጓዶቼ ሲሙቱና ሲታሰሩ፣ ከትምህርት ቤት እንዳልያዝ ፈርቼ በየስፈሩ ስስነቀርና ስሰወር፣ ለድርጅቴ ያለምኩት ተስፋ ቅዠት ሲሆን፣ የምበላውንና የምጠጣውን በግድ ስውጥ፣ በ69 አም ክረምት ውስጥ፣ እማማ ሊያስቀኝ ትንሽ የቀረው አንድ እንግዳ ጨዋታ አመጣች:: ከአለሁበት አደጋ በንፅፅር ሲታይ 'አላሌሆይ አላሌሆይ' ይመስላል:: ዐይኖቿን ጠበብ አድርጋ፣ (እማማ አይኖቿን ካጠበበች ነገር አመጣች ማለት ነው) ግንባሯን ከስክሳ:

«ለመሆኑ ታውቂያለሽ? ወይስ ስትታበዪ ነው?»

«ምኑን?» አልኩዋት

«ዓላዛር ለትምህርት ወደ ውጭ ሊሄድ እንደሆነ አልሰማሽም?»

ደነገጥኩ:: ድንጋጤዬን አይታ:

«የዕውነት አታውቂም?» የበለጠ አይኖቿን አጠበበች

«አሁን ነገርሽኝ»

«ይሄን ነገር አላምንም» አለች ራሷን እየነቀነቀች:: ዓይኖቿ ወደ ነባር ይዞታቸው ተመለሱ

«ለምን አታምኚም? በቃ እኔ ነኝ የማልታመነው? ካልነገረኝስ? ልጅሽን አታምኚም?»

«ባልወልደውም እኮ ልጄ ነው:: ምን ተፈጠረ? የዛሬ ዘመን ልጅ:: ምን ሆናችሁ ደሞ እናንተ?» ወገቧን ይዛ አተኩራ አየችኝ

«ንገሪኛ እኔ አልታመንም አይደለ? ወይ እሱን ጠይቂው:: እዛ......» ምናምን አልኩ

«ምነው እንዲህ እንዲህ አደረገሽ? በምን ተጣላችሁ ደሞ? ደርግና ኢህአፓ ሆናችሁ?»

«እኔ ምን አውቃለሁ? አልተጣላንም ደሞ:: እንዴ? ጠንቋይ ነኝ ምንድነኝ ሳይነግረኝ የማውቀው? ደሞ አገሩን ትቶ የት ነው የሚሄደው?»

«ነገ ነው ሚሄደው»

«ምን? መቼ?»

«ነገ! ለማንኛውም 'ደህና ግባ' በይው»

«ነገ? አልልም:: ለምን አይነግረኝም:: ምን ያስደብቃል?»

«እኔ አላውቅም:: ሄደሽ ግን 'ደህና ግባ' በይው:: ሰው ምን ይላል? ሌላ ይመስላል»

«ምን ሌላ? የፈለጉትን ይበሉ»

«በይ እንግዲህ ነገርኩሽ:: አታናግሪኝ:: የአገሩ ስም ጠፋኝ ብቻ ሄደሽ ካላልሽው እዚህ አትገቢያትም......አሁን ያለ እሱ ሮዛ ትተኛለች? ምን ብሎ እንቅልፍ ይወስዳታል?»

«አልሄድም:: ይሄኔ ሶሻሊስት አገር ይሆናል:: ደባሪ አገር»

«የትም ይሁን:: ምን ሆነች ልጅቷ? እንዳላጣፋሽ:: ደሞ ሶሻሊዝም ሶሻሊዝም ስትይ አልነበረም? ቀይ መጽሐፍ ስትገለብጪ አይደለም የምትውይው? የማይወጣው እንከዋን ዓላዛር ነው:: ወይስ አንቺ ደስ ካላለሽ ትክክል አይደለም? ነገርኩ በኋላ እከካሻለሁ ሳታይው ብትመጪ:: መግቢያሽን ፈልጊ»

ከዛ አላወራችም:: ግን ከአይኗ አለየችኝም:: የእሷም ክትትልና እኔም የወሬ ጉጉቴ አላስችል ብሎኝ ከሰአት ላይ ወደ ዘጠኝ ሰአት ቤቱ ሄድኩ:: ፀሐይ በሩን ከፈተችልኝ:: ካየኋት ብዙ ጊዜዬ ስለሆነ ተሳሳምንና ገባሁ:: ሮዛ ሳሎኗ ሶፋ ምሃል ቲቂምጣ ድንቿ ትልጣለች:: ገና ኮቴዬን ስትሰማ ቀና ብላ አይታኝ ቢላዋን መክተፊያ ላይ ወርወር አድርጋ:

«ቴቢዬ!» ብላ ከተቀመጠችበት ልትነሳ ስትሞክር ቶሎ ብዬ አጠገቧ ሄጄ ቁጭ አልኩ:: ሮዛ መልከመልካም ብቻ ሳትሆን የሚጠላ ነገር ቢታሰስ የማይገኝባት ሴትዮ ናት:: የማይገባት የምትመስል ግን የምትሰራው ስራ ሁሉ በፍፁም የገባው አይነት ናት:: ዓላዛር እንደሚሄድ ያመንኩት በአይኖቿና በከንፈሮቿ ነው:: አይኖቿ ቀልተዋል:: ከንፈሮቿ ዱቄት መስለው አብጠዋል:: ጠጋ ብዬ አቀፍኳት:: ጎንበስ ብላ ወለል ወለል እያየች:

«አንድ ዐይን ነበረኝ ሊሄድብኝ ነው» አለችና መናፈጥ ጀመረች

ቀና ብላ አየችኝ:: ቡናማ አይኖቿ ዕንባ ውስጥ ይዋኛሉ::

«ምን እናድርግ? ስላም ጠፋ»

ምናልባት አብሬአት እንዳለቅስ ትጠብቅ ይሆናል:: ይሄን ማድረግ ስለማልችል እሷ እንዳትጨነቅ ያዘንኩላት መስዬ ጠበቅ አድርጊ አቀፍኳትና ቶሎ አርዕስት ለወጥኩ:

«ለመሆኑ አለ?» አልኳት:: እንዳልነገረኝ ልነግራት አልፈለኩም:: አንደኛ ለእሷ ጥሩ አይደለም:: ሁለተኛ ስለዘጋኝ ቅር ብሎኛል:: ወይም አሳፍሮኛል:: ሁለቱም እየተቀያየረ ይሰማኛል::

«ከብርሃን ጋር እቃ ሊገዙ ወጥተዋል» አለች በሰለለ ድምፅ

«ምንም አይሆን አይዞሽ» አልኳት እኔም ድምፄን አሰልዬ

«እንዳልነገረሽ አውቃለሁ:: እናኑ ትሙት ትክክል አይደለም......አንድ ነገር እንዳይሆንብኝ ነው የምፈልገው:: አንድ ልጅ ቢኖረኝ እሱም......ሻይ ይፍላልሽ? ወይስ ማታ ትመጪያለሽ? ፓርቲ አደርጋለሁ ሲለኝ ነበር:: ለመሆኑ እናንተ ምን ሆናችሁ? አላይሽም:: በደህና ዝም ብሎ መራራቅ አለ?»

«ኸረ አልተራራቅንም:: አንዳንዴ አይመችም»

«አንዳንዴ? እንጃ ይሄ 'አንዳንዴ':: ቡና ይፍላ ዝም ብለን በደረቁ ከምንቀመጥ:: አንቺን ሳይ ቀለል አለኝ:: ፀሐይማ ታብስብሻለሽ:: ሳትታመም አትቀርም:: እሷንም መጠበቅ አለብኝ:: ውሽቴን መስሎሻል:: ፀሐይ! ፀሐይ!» አንጋጣ ፀሐይን ጠራቻት::

«ወዬ!»

«ወዬ' ብቻ አትልም እኮ:: ይሄኔ እርግማኗ አያድርስ ነው:: ድምፅዋን ዝቅ አድርጋ፣ የማትለው የለም» ሮዛ ከተቀመጠችበት ልትነሳ ስትል:

«እኔ ራሴ ልሂድ፣ አንቺ ቆዪ»

«ተይ እኔ እሄዳለሁ፣ እሷ ሁለመናዋ ጠሟል»

«ቁጭ በይ»

ቀድማ ሳትነሳብኝ ቶሎ ብዬ ወደ ጓዳ ሄድኩ:: ፀሐይን ማድቤት እያንጎዳጎደች ስትናፈጥ አገኘኋት::

«ምን ሆንሽ?»

«ምን ሆንሽ ትያለሽ? ያሳደኩት ልጄ የትም ሲሄድ? እሱን ብዬ ነው ጠዋት የምነሳው እኮ» አለች፣ በወፈረ ድምፅ::

«አንቺ ደሞ አበዛሽው ይልቁን ቡና አፍይልን:: ሊማር ነው የሚሄደው ለጦርነት አይደለም»

«ራስሽ አፍዪ!» አለች አይኖቿን ፈጠጥ አድርጋ

«እንዴ ምነው ፀሐይ ቀስ:: ምንሽ ነው?»

«ምን? ምን?»

«በቃ ተይው»

«ከቦተሊካና ከዓላዛር ማን ይበልጣል? ጥያቄ ልጠይቅሽ»

«ምን የምታውቂው ነገር አለ? አፍሽን ያገር»

«አልይዝም:: ደሞ በአፌ ምን አገባሽ?»

ቡና የመጠጣት ፍላጎቴ ሞተ:: ወደ ሳሎን ተመልሼ መጣሁ::

«ሮዛዬ ልሂድ ቀጠሮ ነበረኝ ረስቼ ነው:: አሁን ትዝ አለኝ:: ማታ እመጣለሁ»

ሮዛ ቢላዋን ይዛ አተኩራ አየችኝ:: መሄዴን አልወደደችም:: ጎንበስ ብዬ ሳምኩዋትና_ ቶሎ ቶሎ እየተራመድኩ ስወጣ፣ ጉንጭዋ እንዴት እንደሚለሰልስ እያሰብኩ ነበር:: ደረጃ መውረድ ስጀምር በሚያሳዝን አንደበት፣

«ፀሐይ ነጀሰችሽ?......አይ አይ» አለች ለእኔ ሳይሆን **ለጊዜ** የተናገረችው ይመስላል:: **ጊዜ** የሚባል ልዕለ ፍጡር ቢኖርና ሰምቶ የሚታዘብ፣ ታዝቦም መፍትሄ የሚሰጥ:: ድምፅዋ ውስጥ ያለ ነገር ነው:: በትክክል መስየም የሚከብድ:: እንዳልሰማሁዋት ሁሉ ደረጃ መውረዴን፣ ከግቢው መውጣቴን ቀጠልኩ:: ያልሰማሁ ሊመስላት ይችላል:: ባልሰማ ግድ ይሰጣታል? ብቻ በሁለት ማሚቶ ቃላት ሁሉን ነገር ሰብስባ ሁላችንንም የከሰሰችን መሰለኝ::

ቤት ሳልገባ በዛው ወደ ምሄድበት ሄጄ፣ ማታ ከምሽቱ ሁለት ሰአት ሰፈር ተመለስኩ:: እማማ የግቢ በር እየከፈተች፣ 'ደህና ዋልሽ?' እንኳን ሳትለኝ:

«ተሰናበትሽው?» አለች

«ደክሞኛል፣ አረፍ ብዬ እሄዳለሁ»

«በይ በዛው ደርሰሽ ነይ፤ አትገቢያትም» አለች

«ደክሞኛል ምን መሆንሽ ነው?»

«በይ ሂጂ ምን ደክሞኛል ነው? ቤቱ ትውዪ አልነበረም? ደሞ ሮዛን ሳታጫውቺያት ምን ቆርጦሽ ነው 'ጉዳይ አለኝ' ብለሽ የሄድሽው? የምን ጉዳይ ነው? ከቴም ባለጉዳይ:: ከሮዛ የሚበልጥ ማነው?»

«ፀሐይ ደብራኝ ነው! እማ ደክሞኛል ልረፍበት!፣ ውሃ ጠምቶኛል!»

«እዛ ጠጪ:: እዛ ገፈርሳ የለም እሱ እንዴ?»

«እያስገደደኝ ነው እኮ»

«እኮ ደርሰሽ ነይ፣ ከአገር ሊሄድ ነው......ከአንቺ መጨቃጨቅ መቃጠል ነው:: ቦሌ ሄደሽ መሸኘት ነበረብሽ:: ሰው ይሰማል አታስጨሂኝ፣ ካላየሽው እዚህ አታድሪያትም»

ልከራከራት አልቻልኩም፣ ቁጣዋን አሸንፌ ማለፍ አልችልም:: እንደውም 'የምታደርጊውን አያለሁ' ብላ በሌሊት ተነስተሽ ሸኚው ብትለኝስ:: ቶሎ ወጥቼ ወደ ዓላዛር ቤት ሄድኩ:: የአጥሩ በር ተገርብቷል:: የቤቱን ደረጃ እንደወጣሁ በር ከውስጥ ተከፈተ:: ቸርነት እየተጎማለለ ወጣ:: ጥቁር ኮት ለብሷል::

«ሂሂሂ ማዶና ሳታ የጠፋችው!!» ሁልጊዜ ሲገረም 'ማዶና ሳታ' ይል ነበር:: ምን ማለት ነው?

ከእሱ ኋላ ዓላዛር ፊቱን አጥቁሮ ይከተለዋል:: ጃኬት አልደረበም:: ሁልጊዜ በካናቴራ ወይ በሸሚዝ ነው::

«ምነው ተዘፍዝፈን ስንጠብቅሽ ትመጪያለሽ ተብሎ?» አለ ቀጠለና::

ምንም ሳልመልስ ከሁለቱም ጋር ጉንጭ ለጉንጭ ተሳሳምኩ::

«በሉ ሸኙኝ:: ብዙ ቆየሁ:: ማዘርን አሚታል እንክብካቤ ትፈልጋለች» አለ ቸርነት

ሶስታችንም ተከታትለን ከግቢው ወጣን:: ቸርነት ከተናገራቸው 8 ቃላት በኋላ መንገድ እስክንገባ ድረስ ፀጥታ ነበር:: ያቺ ወደ ውጭ የወጣንባትን ጊዜ እንደ መንፈስ ወፌላላ አስታውሳታለሁ:: እንዲህ በቅዝቃዜ የተከበበ መከታተል ያሳለፍን አይመስለኝም:: የማልረሳው የሚያስጨንቅ ፀጥታና ሰልፍ ነው:: አንዳንድ ፀጥታዎችን ለመግለፅ ቃል ያጥራል:: ያን ማፍረሺያ፣ ያን ከመሃላችን የተጋደመ ነገር ገለል ማድረጊያ ጥበብ ያጥራል:: መከታተሎች ተራ ጥበቃ መሆን አቁመው የሆነ የእንጓና የፀጥታ አገዳ ዱሆናሉ:: እንጓው ድብርት ነው:: ፀጥታው ዱካክ ነው:: ዘመን ዘሞን አለ ቢያምጡ እንኳን ሳቅ የማይወለድበት:: በጥርጣሬ፣ በመግደርደርና በአለመመቸት ፍልስፍና የታጠረ:: እኔ፣ ቸርነትና ዓላዛር የአግድም ሰልፍ ገብተናል:: ቀላል መስመር ነው:: ቀላል እርቀት ግን አይደለም:: ጨለማውና ጠማማ ዐይነአፋርነት የፈጠሩት እንዲመስል እንሞክራለን እንጂ አልነበረም:: ከአስፋልቱ ወጥተን ኮረኮንች ስንገባ:

«ወንድማችን ካልጠፋ አገር ኢስት ጀርመኒ ይሄዳል» አለ እየሳቀ ቸርነት

ዞር ብዬ ዓላዛርን አያሁት::

«ምን አለበት? ከእኛ ይሻላሉ፣ የሀበሻ ጉራ አይቻልም እንጂ.» አለ ዓላዛር

«በዛው እንግሊዝ ወይ አሜሪካ መርሺ ከቻልሽ» አለ ቸርነት

«እኔ ሰው ነው የምፈልገው አገር አይደለም:: ፋክ አገሮችን» አለ ዓላዛር

«አቦ ሃሃሃሃሃሃሃ ደሞ ደብዳቤ መፃፍ እንዳታቆም:: ለእኛ ባይሆን ለፅጌ»

ቸርነት የዓላዛርን እናት ስም ተርጉሞ ነው የሚጠራት:: 'ሮዛ' አይላትም:: ዓላዛር ወደ እኔ ዞሮ መጣ:: እጄን ያዘኝ:: ቀላል ማታ ነው፣ ነፋስና ቅዝቃዜ ነው፣ ኮረኮንች ሊሸውድ የሚጥር ግን ያልቻለበት ኮቴ-ያችን፣ ነፋስ የሚያንኳትተው የቅጠላቅጠል ዳና ነው:: ከባቢያችን ሁሉ ቀላል ነው:: ምቾቱ ማር የተሰነገበት እርጎ:: ግን ከባድ ነበር: ለስላሳ ጨርቆች ነን በማይሆን ክር የተሰፋን:: ክሩ የነተበ:: ክሩ ነኝ:: ዘመናችን ሰፊው ነው:: ዋናውን ሽሽቴን ለማዘናጋት የዓላዛርን እጅ ጨምድጄ ያዝኩት:: የጣቶቹ አጥንቶች እንደ ጨፈቃ ችቦ መዳፌ ላይ ይሰሙኛል:: የሚመች ሙቀት ኪሱ ከቆየ ገላው ወደ ገላዬ ወሰድኩ:: ክንዴ ላይ እንጂ ልቤ ላይ ክብደት አልነበረውም:: ለመስዋዕትነት የቀረበ እንደእኔ ያለች ወጣት የወዳጅዋን እጅ አጥብቃ የመያዝ ወንጀል አትሰራም:: የልብ መከፈል አጥፊና አልሚ ትርጉም አለው:: ቸርነት ዞር ብሎ አይቶን:

«በጣም ያምርባችኋል» አለ በተቆጠበ ፈገግታ:: በአይኖቹ የሚያየው የአራት ነጥብ ዱካውን ነው:: ይኼ የሚያየውን አጨራረስ ሊጋፋ መሰለኝ ከተረበሽነው ከሁለታችን ቀድሞ እንዲህ የሚለው:: ሁላችንም ይገባናል::

«እጅ ለእጅ መያያዝ የሚያምርባቸው አሉ:: የዕውነት:: ምን እንደሚመስለኝ ታውቃላችሁ? ከአምስት አመት በኋላ ወይም አራት እንጃ ሚዜአችሁ የምሆን:: አይ ዊል ዳንስ ላይክ[103] ምናምን ፌስታክ[104] ነው የምሰራው:: ሃሃሃሃ» አለ:: ፈገግ ፈገግ ብልም ቸርነትን ትንሽ እንደ ቲያትረኛ አየዋለሁ:: የሚወዱን ፍቅር ሲመኙልን በጥርጣሬና በቸልታ ማዳመጥ የሰለጠንኩበት ዘመን ነው:: ፈገግ ማለቴ ለአብሮአደግነት ወዳጅነታችን ነው:: ይሉኝታ ነው::

ከእኛ መልስ ቢያጣም፣ ሲቀልድና ሲያፌዝ ቆይቶ 'ጊዜ ዘራፊ አይደለሁም እናንተ ተላላሱ' ብሎን እንድንመለስ ወተወተንና ከዓላዛር

---

[103] I will Dance like.........

[104] ሙዚቃዊ ፊልም( musical film)

ጋር ሊላቀሱ እስኪደርሱ ተሳሳሙ:: ዓላዛር ከቸርነት ጋር ሲሳሳም እጅ ለእጅ መያያዛችን የቆመ ቢመስለኝም፣ ስንመለስ ግን ባላስታወስኩት ሰበብ ተያያዝን:: የተያያዝነው ምናልባት በድሮው ልማድ ግፊት ነው:: ማለት የድሮ ልማዳችን ወደ ሁለተኛ ተፈጥሮ፣ ወደ ደመነፍስነት ተለውጦ::

«እንዴት ነው ትምህርት?» አለ ከዝምተኛ ጉዞ በኋላ:: ቤቱ ግቢ በር ስንደርስ:: ጆብ ሲጮህ እንሰማለን:: የማላውቀው ድምፅ መሰለኝ:: አሁን አሁን እንደ ሌላ አውራጃ ዜጋ የውሸት የምፈራበት፣ ሆን ብዬ ለመታቀፍ ወደ እሱ ጉያ የምገባበት ጊዜ አይደለም:: ያቺ ብልጠት ያለፈባት የልጅነት ጊዜ ናት:: ኅሑ ፅዮን ጆብ ሲጮህ እዚህ 'እቀፈኝ' እለው ነበር:: የብብቱ መልካም ወንዳታ ጣዕም እንደ ጤና አዳም ናፍቆኝ::

«ምንም አይል» አልኩት::

«የእውነት?»

«ወጣቱ እየታደነና እየተገደለ መማርን ከሁሉ የበለጠ ቁም ነገር አላደርገውም» አልኩት

አተኩሮ አየኝ:: ፈገግ አለ ልበል? በር በግራ እጁ ገፋና እንድቀድመው መራኝ:: አሰባለሁ *ከዚሁ ልሂድ? ከአሁን በኋላ...*

«ፋዘር ገና አልገባም»

«ስንት ሰአት ነው የምትሄደው?»

«ጠዋት ከአንድ ሰአት በፊት፣ እራት በልተሻል?»

«ደክሞኛል ካልክስ......» ልናገር የፈለኩትን አልጨረስኩትም:: 'ደክሞኛል፣ ሂጂ ልተኛ' ለማለት አልቻልኩም:: ይሉኝታ ይሆናል? አንድ የለመድነውን ነገር ፊት ለፊታችን ስናይ ከእሱ ጋር ስናደርግ የነበረው ልማድ ሳናውቀው አመራሩን ይወስድና 'የመጣልንን' (የለመድነውን) እንናገራለን:: እንደዛም ይሆናል::

«እሪፍ ክትፎ አለ:: ማም[105] ናት የሰራችው:: እሪፍ ቀይ ወጥ አለ:: እዝራ ጠብቆሽ ጠ<sup></sup>ብቆሽ ሂጂ:: ሲያሰቅኝ ነበር:: ታውቂዋለሽ እሱን»

[redacted] ተነቃቃ:: ስሜቴን እየጠበቀ ነበር? ሳልደብረው ዛሬን አታልዬው ለመሰናበት ወሰንኩ::

'ጊዜው አይመችም:: አብዮት ጠባቂ ያገኘውን ይደፋል:: ሰው እየተባላ ነው' ብለውስ? ተከታትለን ቤት ውስጥ ገባን:: ሮዛ አልነበረችም:: ፀሐይ ስታየኝ:

105 እናቴ (mam)

«ጊዜ አገኘሽ? የምትመጪ አልመሰለኝም» አለች እንደማሽሟጠጥ

«ምን መሆኗ ነው?» አለ ዓላዛር በቁጣ

«አትነጅሺኝ አንቺ» አልኳት:: እየተፈናጠረች ከሳሎን ወጣች:: ሳሎን እንደተቀመጥን ሮዛ ገባችና ሰላም ብላኝ ሊሊት እንደምትነሳ አሁን መተኛት እንዳለባት ነገረችን:: ዓላዛርን ማንባሩ ላይ፣ እኔን ጉንጬን እንደጨዋታ ጎንትላ ወደ መኝታ ቤት ሄደች::

«ምን እንብላ?» አለኝ

«ለእኔ ብለህ ነው ወይስ አልበላህም?»

«አላሰኘኝም ነበር»

አባባሉ አልመሰጠኝም:: ከተናገረ በኋላ አተኩሮ አየኝ:: 'አንቺ ስላሌለሽ ነው ያልበላሁት' ብሎ የእሱን የመራብ ሃላፊነት እኔ ላይ ሊጥል የሚጥር ይመስላል::

«ለምን ክፍሌ አንሄድም:: ፀሐይ ራት ታምጣልን ሙዚቃ እየሰማን እንበላለን» አለ

«ያቺን ጥጋበኛ ልክዋን ነግሬት መጣሁ:: ምን ትፈልጋለህ?» አልኩት

«ቀይ ወጥ:: የተገኘውን ብቻ:: ሙዚቃውን ልምረጥ? ማንን ትፈል-ጊያለሽ?»

«ደስ ያለህን» የዘፈንና የዘፋኝ ስም ማሰብ አልፈለኩም:: ትቼው ሄድኩ::

ፀሐይ ማድቤት ውስጥ ምድጃ አጠገብ ቆማ እያንጎራጎረች የምትሰራውን ትሰራለች:: ዳናዬን ስትሰማ ዞር አለችና:

«ምን ፈለግሽ?» አለች

«አንቺ ለምን ጠመድሽኝ? ቀይ ወጥ እንፈልጋለን:: እሱም እኔም ራት አልበላንም»

ለምን እንደጠመደችኝ ባውቅም ማደናገር ነበረብኝ:: በሰላም ተሰናብቼው መሂድ ነው የፈለኩት:: ምንም ሳትናገር ከላይ እስከታች ገላምጣኝ:

«እንደሚወድሽ ታውቂያለሽ?» አለች በግራ እጇ ወገቧን ይዛ:: በቀኝ እጇ የያዘችው ማማሰያ የሰበሰበውን ሊጥ ወለል ላይ እያንጠባጠበ:: ዝቅ ብላ አይታው ምንም ሳታደርግ መልሴን ጠበቀች::

«እና? ይልቁን ራታችንን አምጪው እሱ መኝታ ቤት ነን» አልኩና መለስ አልኩ:: የሆነ ነገር ጀርባዬን መታኝ:: ምን እንደሆነ ለማየት ዞር ስል ማማሰያዋን ቀጥላለች::

የዓላዛር መኝታ ቤት በማርቪን ጌይ አይ ወንት ዩ ዘ ራይት ዌይ በት አይ ወነት ዩ ዘ ራይት ዌይ[106] ዘፈን ደምቃ ደረስኩ:: ትዝታ ሊያመጣ እንዳሰበ ይገባኛል:: ነው? የወንት[107] መዓት ግቡ ምንድነው? ገና እንደ ገባሁ እጁን ግራና ቀኝ ዘርግቶ 'እንደንስ' አለኝ:: አልፈለኩም:: እጆቹን እንደያዝኩ በሩን በእግሩ መቶ ዘጋና መነቃነቅ ጀመርን:: ሙዚቃው እንዳጋመሰ በር ተንኳኳ:: ሁለታችንም በአንድ ላይ 'ግቢ!' አልን:: ፀሐይ በር ከፍታ ትሪና ወጥ ያለበት ሳህን ይዛ አልፋን ሄዳ ማንበቢያ ጠረጴዛ ላይ አስቀምጣ ስትወጣ፣ ዓላዛርን ጀርባው ላይ በጥፊ መታችው:: በር እንደተዘጋ ምንም ሳንናገር መደነስ ቀጠልን::

«ራበኝ» አልኩት::

መደነሱን አቁሞ እጄን ይዞ ወደ ጠረጴዛው ወሰደኝ:: አንድ ወንበር ብቻ ስላለ፣ እሱ ቆመና እንድቀመጥ ጋበዘኝ:: እርቦኝ ስለነበር ከእሱ በእጥፍ ፍጥነት መብላት ጀመርኩ:: ሲያየኝ ቆየና:

«የሚጠጣ ላምጣ......ምን ላምጣ?»

«ውሃ»

«ቢራ አለ»

«አልፈልግም»

ከቆመበት ሄደ:: ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ በጠርሙስ ውሃ ይዞ መጣ::

«አትበላም?» አልኩት

«በቃኝ» አለና የታጠበ እጁን ወደ ላይ ሰቅሎ አሳየኝና ከጀርባዬ መጥቶ ቆመ:: መሃል አናቴ ላይ ሳመኝ:: እጁን ትከሻዬ ላይ ሲያስቀምጥ በጉንጬ ነካሁት:: ፊቴን ይዞ አዞረኝና በጉርሻ የሞላ አፌን ከነወጡ ሳመው::

«ተው ትን ይለኛል» አልኩት:: ወጥ ባልነካ ግራ እጄ ራቅ እንዲልልኝ ገፋሁት:: እየሳቀ ሙዚቃ ለወጠና ትቶኝ አልጋው ላይ ተጋደመ:: ነጫጭ መስመሮች ያሉት ቲሸርት ለብሷል:: የቲሸርቱን ቀለም ልብ ያልኩት አሁን ነው:: የጎድን አጥንቶቹ በነዛ መስመሮች ላይ ሲንበሮች ሆነው ይታያሉ:: የበለጠ ክሳ? ወይስ የካናቴራው አቀላለም ነው?

«መቼ ነው የምትወፍረው?»

«በእያቴ ነው የወጣሁት፣ አልወፍርም»

---

[106] በትክክለኛው መንገድ እፈልግሻለሁ እፈልግሻለሁ አንቺም እንድትፈልጊኝ እፈልጋለሁ ( I want you the right way, I want you but I want you to want me.......)

[107] 'የመፈለግ'

«እያቴ ስትል......»

«ሰብለ:: ሰብለ መሸሻ» አለ ወደ ግድግዳው እያሳየኝ

«ማን አለህ? አላየሃቸውም»

«እናኑም እማማም ያውቋታል»

«እና አትወፍርም?»

«ምን ያደርግልኛል? አቆርቋዥ መምሰል»

ወደ ቴፑ ሄደና ማርቪን ጌይን አውጥቶ የማንሃታንን ካሴት አስገባ:: ከሙዚቃው ሙዚቃው፣ ከውዝዋዜው ውዝዋዜው::

«ሂሂ ቀልደህ ሞተሃል:: በቃኝ በጣም ቶሎ ቶሎ በላሁ:: ልታጠብ»

ተነስቼ ወደ በሩ ስሄድ ከመሀል መንገድ አቆመና ክንዴን ያዘኝ::

«በዚህች እንደንስ»

«በቃ በእናትህ......ደሞ ልታጠብ»

በዛው ወጥቼ የምቀር መስሎታል:: ያሰብኩትም እንደዛ ነበር:: አስተያየቱን፣ የሙዚቃውን መልዕክትና የሙዚቃውን ቀስስተኛነት አልወደድኩትም:: የማንሃታንስ *ኪስ ኤንድ ሰይ ጉድባይ*[108] ነው:: እንዳቀደው ይገባኛል:: ገና አቤቱታዬን መዘርዘር ስጀመር አንገቴ ላይ በሁለት እጆቹ ይዞ ጎትቶ ሳመኝ:: የዓላዛር አፍና ትንፋሽ የምወደው አጥንታም ሰፊ ደረቱ፣ ሙዚቃው ምኑ ተሰባስበው ከበዱኝና ዞር አለብኝ:: መልሼ ሳምኩት፣ ግን ቶሎ ባነንኩ::

«ልሂድ ተወኝ፣ ሰላም ልልህ ነው፣ ለሌላ ነገር አልመጣሁም» አልኩት

«እኔ ነኝ የምወስነው» አለ አንገቴን እየነከሰና የመሳሰለ ነገር እያደረገ:: ወጥ ባልነካ እጄ ዞር አድርጌው ላልፍ ስል ወደ አልጋው እየገፋፋ ወሰደኝ:: ፊት ለፊቴ እንደቆመ የሱሪዬውን ዚፕ ፈታ::

«እንዴ?! ከእሱ ሌላ አታውቅም?» አልኩት እንዲያፍር::

አልሰማኝም:: ትንሽ ገፋኝ:: መሄጃ ስለሌለኝ አልጋው ጠርዝ ተቀመጥኩ:

«አይሆንም ፔሬድ ላይ ነኝ»

ከተቀመጥኩበት ልነሳ ስል፣ በእኔና በእሱ መሃል ያለው ቦታ በመጥበቡ፣ ተመልሼ አልጋው ላይ ተቀመጥኩ::

«ምን ታውቂያለሽ ስለ ፔሬድ» አለና ትከሻዬን ግራና ቀኝ ይዞ ወደ አልጋው እስክንጋለል ገፋኝ:: ቀሚሴን ወደ ላይ ሊገፍ ይለፋል:: እታገላለሁ::

[108] The manahattans *kiss and say goodbye* (1976)

«ምን ሆንክ?» ወጥ በነካ እጇ ካኔቴራውን ጨመደደችኝ:: ግድ አልሰጠውም::

«ምንም:: አንቺ ነሽ:: ብፈልግ ያጣሁሽ:: ምን ሆንሽ? ከእኔ ሌላ የምትወጂው ያለ አይመስለኝም ነበር»

«ምን ማለትህ ነው?»

«አዎ:: ምን ማለቴ እንደ ሆነ ይገባሻል:: ራቅሽኝ:: ለምን?» ድምፁ ወፈረብኝ:: ዓላዛርን ሲቆጣ ስለማላውቀው ዞር አለብኝ:: ሌላ ቦታ ያለሁ ሁሉ መሰለኝ::

«እንደዚህ ነህ እንዴ?»

«ምን ማለት ነው?»

ራሴን አላቅቄ ልነሳ ስል ወደ አልጋው መልሶ ገፋኝ:: እሱ ይገለባል፣ እኔ ለማስተካከል እለፋለሁ:: የውስጥ ሱሪዬን ታግሎ አወለቀ:: የነቀለው እስኪመስል:: ሌላ ሰው እንዳይሰማን እያንሾካሾክን የ'አታደርግም' የ'አደርጋለሁ' ትግላችን ከባድ ሆነ:: እላዬ ላይ ተጋደመ:: እጆቼን ግራና ቀኝ መስቀልኛ ወጥሮ ያዛቸው:: መንቃነቂያ አልነበረኝም:: ብጮህ ደስ ይለኛል፣ ግን ሰው ሊሰማ ነው::

«አንቺ ስወድሽ ትጠሚያለሽ:: ለምን?»

ላቆመውም አልቻልኩም:: [redacted]ዛ ጠንካራ አይመስለኝም ነበር:: ከንፈሮቼን ነክሶ ያዘኝ:: መናገር አልቻልኩም:: ትንፋሽ አጠረኝ:: ትኩረቴ ወደ አፌ ሲመጣ.......................

ቤት ገብቼ [redacted]ሴን አውልቄ ተጣጥቤ ስመለስ፣ ያወለቅሁትን ከጣልኩበት ስሰበስብ ሹራቤ ጀርባ ላይ የደረቁ የሙቅ ፍንጣቂዎች ተለጥፈው አገኘሁ:: ምናባቷን

......እንደ ፍቅረኛ ሳይሆን እንደ ጠላት በመድፈር ነው የተሰናበተኝ ......ነገር ሳብሰለስል እኩለ [redacted] ላይ እንቅልፍ ወሰደኝ::

ከ66 ጀምሮ እስከ አሁን ያለው ጊዜዬ ስም ብሌለው፣ ሕድራሻው የትም በሆነ፣ ገላው በማይክለት፣ በማላውቀው ሰው የተደረሰ ነው:: መደፈር እንደ ዕሑፍ አይደረስም? ከተለያየ ስፍራ......ከተለያየ አቅጣጫ......በተለያዩ ሰዎች......በተለያዩ ድርጅቶች......በተለያዩ አምላኮች...... በሚለዋወጥ ፀባይ......በመሳሰለ በመሳሰለ በመሳሰለ......

## የማያደፈርሰንስ የለም……

የዓላዛር እግሮች ገና አዲስአባን ሲለቁ፣ 'ደካሞች' ስንላቸው የነበሩ፣ 'መሀይም' ብለን የናቅናቸው ሊወድቁ የደረሱት ፋሽሽቶች ለሶስተኛ አሰሳ እያጉዋሩ ተነሱ (እሱ እስኪወጣላቸው ነበር የሚጠብቁት?)፡፡ ድንጋይ የመሰሉ ዲሞትፈር ተሸካሚዎች ድንጋይ መወርወር ጀመሩ፡፡ እስር ያልገባሁት የሕዋሴ ሰው እኔ ብቻ ነበርኩ፡፡ እንኩዋን በቂ መሸሸጊያ ሳይኖረኝ ይቅርና አገሩ ጠቅላላ መሸሸጊያ ቢሆነኝ ማምለጥ የምችል አልመሰለኝም፡፡ ስራዬ ለመታሰር ቁጭ ብዬ መጠበቅ ነው፡፡ ታዲያ ከተወረወረብን የሳተን ጥቂት ነን፡፡

አንድ እሁድ ከሰአት በሁዋላ እናቴ ቡና ልትጠጣ ገርማሜ እጎት ቤት ሄዳለች፡፡ ቤት ሳሎን ሶፋ ላይ ተንጋልዬ በዝናብ ልጋግ ኮርኒስ ላይ የተሰራ ካርታ እያነበብኩ ስጨነቅ የውጭ በር ተንኩዋኳ፡፡ የተለየ አይነት መንኳኳት ነው፡፡ መንኳኳቶች ሁሉ ተለቅመው አሰልፌ ብሰማቸው ይሄኛው ልዩ መሆኑን ማወቅ እችላለሁ፡፡ በር እየተኮረኮመ ግን በር አይመስልም፡፡ በእጅ እየተኮረኮመ በእጅ የሚኮረኮም አይመስልም፡፡ ድምፁ ለእኔ ብቻ የተላከ ይመስላል፡ ከእኔ አልፎ ወደ ጆሮባዬ የማይሄድ ……ወደ ማድቤት የማያልፍ……መኝታ ቤት ሰው ቢኖር የማይሰማው…… ድምፁ ሞገድ ላይ አድራሻዬ የተፃፈበት ወረቀት የሚውለበለብ……እኔ ልቦና ብቻ ሶቶ የሚገባ……ለጎረቤት የማይደመጥ፡፡ በሩን እያየሁ በልቤ አሳሪዎቼ እንደሆኑ ገባኝ፡፡ ሃሞቴን እያዝረበረብኩ ተነስቼ ስከፍት፣ ፊት ለፊቴ ዲሞትፈሩንም በጀርባቸው አዟያ ዋገተረ ወንድወሰን የተባለ የሰፈሬ አብዮት ጠባቂና ከእነሱ ሁዋላ የራሴ ድርጅት አባል እንደሆኑ የምጠረጥራቸው ሁለት ልጆች ቆመዋል፡፡ አንደኛው ልጅ ልክ ጠላቱ እንደሆንኩ ሁሉ አፍጦና አግጦ ሽጉጡን እያሳየኝ፡

«ጣጣ ሳታበዢ ተከተይን!» አለኝ

ወደ ሁዋላ ልሮጥ ሞከርኩ፡፡ ገላዬ ከብዶኝ መሮጥ አልቻልኩም፡፡ መሮጥ እንደማልችል ያወቅሁት ያኔ ነው፡፡ ያ ገላ በዝናው ዐይን እንዳልጎለጎለ፣ ያጣላኝ፣ ያቀያየመኝ፣ ያስጠቀሰኝ፣ የኮራሁበት፣ ያኮራኝ፣

ያ የሱፍ አበባ የመሰለ ቂጥ የበቀለበት መዋቅሬ ለመጀመሪያ የራሴ አልመስል አለኝ:: ምናልባት በጥቂት አመታት አርጅቼአለሁ:: ምናልባት ስፈጠር ለሀይኑካ እንጂ ለአትሌትነት አልተሰራሁም:: በገላዬ የፈለኩትን አለማድረጌ ዕንባዬን አመጣው:: በንዴት ተነጫነጭኩ::

«ወደ የት!!? ወደ የት?!!» አለ አንዱ እየሳቀ

ጀርባዬን ሰጥቼአቸው ቆምኩ:: ማልቀስ መጮህ አላሰብኩም:: እራቱም ይስቃሉ:: መሮጥ ባለመቻሌ በጣም የናቁኝ መሰለኝ:: ዞር አልኩ:: ጎንበስ አልኩና ድንጋይ ፈለኩ:: ያጋጠመኝን አንዱን አነሳሁና ዕንባ እየተናነቀኝ ወረወርኩ:: የአጥር ቆርቆሮ መታሁ:: በትክክል የምሰራውን አላውቅም:: ሰዎቹ የገባቸው ይመስለኛል:: እናቴ ማወቋ ይቀር ይመስል ከዚህ ጭንቀትና ውርደት እሷ ሳትሰማና ሳታየኝ እንዲገላግሉኝ ፈለኩ::

ሌላ ድንጋይ ለመፈለግ ጎበጥ ጎበጥ ስል አብዮት ጠባቂው ከጀርባ መጥቶ ጉንጉኔን ጨምድዶ ያዘና ቀና አደረገኝ::

እናቴ እንድትመጣና በጨኸቷ ሰፈሩን እንድታምስልኝ ተመኘሁ:: እየተነዳሁ ሄጄ መኪና ጀርባ ስወረወር አስቸጋሪ እንዳልሆንኩ ገባኝ:: ከቤት ስወሰድ ያዩ እማማ ቡና የምትጠጣበት ቤት ሄደው ለእናቴ ሊግሯት ሲሯሯጡ እኔ ላንድሮቨር ውስጥ ሆኜ ጉዞ ጀምሬአለሁ:: የምጎተት፣ የምገፋ፣ የምሰደብ፣ የምጠፋና ምንም ነበርኩ:: አንድ ኡዚ ፊት ቆራጥነት ባዶ ናት:: ድርጅታችን ጠቅላላ ስለተንበረከከ እኔ አይነቶቹ አስጊ አልነበርንም:: በገንዘብ መጠን ብቻ ሳይሆን በአሟሟት የበላይና የበታች ተዋረድ አለ:: በሚገርም መልክ ከላይ ካሉት ሚስጥራቸው በግድ ከሚገኝ አመራሮች የበለጠ ለሞት የተጠጋሁ ነበርኩ:: ምክንያቱም በቀላሉ ተጋላጭ ነኝ:: እዚህ እዛ እዛ ስል ታይቼለሁ:: ባልተደበቅንበት በጥናት ክበብ ዘመን ከጠላቶቼ ጋር ፊት ለፊት ተገለማምጠናል:: በሆነ መልክ የእውነት ህቡዕ አልነበርኩም:: እንዴት ነው ሲተያዩ ኖሮ 'ህቡዕ ገባሁ' ማለት? የመታሰሬ ነገር አስገራሚ አይሆንም:: ታች አረንጓዴ ሆቴል እያለሁ የእማማ መሆን አለበት የሴት ኡኡታ ሰማሁ:: ካደኩ ጀምሮ በማውቀው መረጃ ላይ ብመረኮዝ ይሄ የእማማ ጨኸት የመጀመሪያዋ ነው:: የጉሮሮዋ ድንግል ያኔ ነው የተገሰሰው:: ሌሎች ቡና የምታጣጣቸው ሴቶች የት ሄዱ?

በነፃ እርምጃ ሰሞን ቢሆን ኖሮ በሽሮሜዳና በአፍንጮ በር መሃል አንዱ ቦይ ውስጥ ወድቄ እቀር ነበር:: ቀሽምነት ነፍስን ያድናታል:: አፈርኩም ተፅናናሁም:: በራሴው ድርጅት ተጋልጬ በራሴው ድርጅት አባል በነበረ ሰው ለመገረፍ የተዘጋጀሁ ነበርኩ:: ይሄ ውስጤን ሰበረው::

የታሰርኩበት ቤት ሰፊ ግቢ ያለው በትርፍ ቤቶች አዋጅ ተወርሶ ከግል ወደ መንግስት የዞረ ሁሉ ነገሩ በድንጋይ የተገነባ ግሪኮች

አርመኖች ወይም የጣሊያኖች የሰሩት የድሮ ቪላ ነው። ይሄ ቤት አስደንግጦኛል። ይሄ ቤት ድሮ እትዬ እናኑ ይኖሩበት የነበረ ነው። (እትዬ ሮዛ የታሰርኩበትን ቦታ እንዳየች አፏን በእጇ ይዛ ሳታነሳው አንድ ቀን ያህል ቆየች አሉ። እንድ ሁለቴ እንስታ 'እርግማን ነው ምንድነው?' አለች አሉ። *ታሪክ ነው የእኔ እናት*......) ይሄን ቤት እንደማውቀው ለማንም አብሮኝ ታሳሪ አልተናገርኩም። ባንዶች እስር ቤት ቢያደርጉትም፣ ልክ እኔ የማውቃቸው ሰዎችና ዘመዶች ማሰሪያ እንዳደረግነው ሁሉ አፈርኩ። ቤቱ አራት ክፍሎችና ከጀርባ አንድ ትልቅ ባለ ሶስት ክፍል ሰርቪስ ቤት አለው። ክፍሎቹ ሁሉ የተለያየ ጠረን አላቸው። እነዚህ ሁሉ ግን ተሰባጥረው የሚሰማው ግን የእምግ ሽታ ነው። ሴቶች የታጎርነው የቤቱ *መመግቢያ* ክፍል ውስጥ ነው። በትንሹ እንደ ምግብ ምግብ ይላል። የዋናውን ቤት ደጃፍ አለፍ እንዳሉ በስተቀኝ በኩል ውሃው የማይመጣ መታጠቢያ ቤት አለ። በስተመጨረሻ ያለው ክፍል ከዋናው ቤት ውስጥ ያለ ግን በአሰራሩ ፀባይ ደሞ የተገለለ ነው። መዝጊያው ከውጭ የቦንዳና የአጣና መቀርቀሪያ አለው። ገና ክፍሉ ሲገቡ ምላስ ላይ የሚሰማ መራራ የሽንትና የላብ ሽታ ይሸታል። ከክፍሉ ግራ ጥግ የተላላጠ ነጭ የዛገ ስሃንና የተበጣጠሰ፣ የቆሸሸ፣ ልባስ የሌለው መላጣ ፍራሽ አለ። ግድግዳው በፅሑፎች ተሞልቷል። እንደ ጨፈቃ የቆሙ፣ ወገባቸው ላይ ማገር የተሰመረባቸው ቀን መቁጠሪያ ጭረቶች ከርብርብ ሽክላዎች በተሰሩት አራቱም ግድግዳዎች ላይ አሉ። አንዱ ጥግ በእንግሊዘኛ በትልቁ hoping is hopeless ተብሎ ተፅፏል። ጣሪያው ኮርኒስ የለውም፡ ከመሃሉ በበራሪ ዓይነምድርና በሸረሪት ድር የተሸፈነች ቢጫ ቀለም ያላት በወፍራም ገመድ የተንጠለጠለች አምፖል አለች። አምፖሏ ሁልጊዜ በቀስታ ትነቃነቃለች። በጉድፍና በሸረሪት ድር ስለተከበበች ባትበራ ድንጋይ ትሁን ኳስ መለየት ይከብዳል። በጣርያውና በግድግዳው መገናኛ ቀጭን ክፍተት አለ። በዛ ክፍተት የሚገባው የሚያስፈራ ፀጥታና አምፖሏን የሚያነቃንቀው አየር ነው። በማልረሳው መልክ ትዝ የሚለኝ መብረዱ ነው።

የተደራጀሁበት ሕዋሴ ጠቅላላ ቢጠፋም በበቀል ቅጣት እንዴ ተገርፌ ነበር። ስገለበጥ በህመሜ መሃል እሱንና ጠቅላላ የተፈጠርኩበትን አለም በጥላቻ አይቼአለሁ። እንደገናም ከመገረፍ ሳርፍ ያ ክፍተት አሾልኮ ባስገባው ቀዝቃዛ አየር አብርዶልኛል። በዚህም ሰበብ እንደ ወዳጅ አይቼዋለሁ። ***ሆፕ ኢዝ ሆፕለስ*** የሚሉትን ቃላቶች ወንበር ላይ እንደተቀመጥኩ እንዳነበብኩአቸው (ገራፊዎቼ ተስፋ እንዳይኖረኝ የፃፉት መሰለኝ) ሁሉ፣ ተዘቅዝቄም እያነበብኳቸው ገራፊዎቼ ያጎረሱኝን ጨርቅ ነክሼ አንዱ ጭኔን ሲዳብስ ምራቅ ባቋረ ጉሮሮዬ ጮሄበታለሁ። ሆፕ

hoping is hopeless

ኢዝ ሆፕ ለስ ሌላ ትርጉም የለውም። ከዚህ ግርፋት ያገኘሁት ሲመስለኝ ከወር በሁዋላ የዳኑ ጥቂት

ሰንበሮችና አልጠፉ ያለኝ የአፍ መስፋት ስሜቶች ናቸው:: በትክክል ቀይ ሽብር የተፋፋመው ጭኔና አፌ ላይ ይመስለኛል:: ዛሬ ድረስ በጨርቅ የተወጠረው አፌ ተመልሶ የጠበበ አይመስለኝም:: የሆነ ደባሪ ገራፊ ደም በነካቸው የሞቁ ጣቶቹ የነካው ከግራ ጭኔ ውስጥ ያለች ቦታ ዛሬ ድረስ ያለች ይመስለኛል:: ዛሬ ድረስ በጣም የምታጠበው ያቺን ቦታ ነው:: አንዳንዴ በጣም ስለምፍቃት እንደተነከስኩት ያህል ትቀላለች:: ግን ሁሉ አልፎ ግድግዳ ተደግፌ ጋቢዬን ተከናንቤ በግድግዳና በጣሪያ መሃል ያለ ክፍት ቦታ ለምን እንደጠላሁና እንደወደድኩ አስባለሁ:: *አለምን እያሳየ ስላልሰጠኝ ነው? እንቁልልጭ አናዶኝ ነው?*

እኔ በገባሁ በሳምንቱ መደ'ብደቢያና መደብደቢያ የነበረው መታጠቢያ ቤት በእስረኞች ተጠርጎ ወደ መኝታ ቤት ተለወጠ:: ሁለተኛውን ክፍል እንድናፀዳ ስድስት ሴቶች ታዘዝን:: ግድግዳው በስቃይ፣ በደምና በጩኸት ጠቁሯል:: በዚህ የተነሳ መሰለኝ የሕንፃው ጠረን የመኖሪያ ቤት መሆኑ አቁሞ የሚሸተው እንደ በሰበሰ ክርታስ ነው:: በላባችን አጥበን ዕንባችንን ቀባነው:: እኛ ካፀዳነው በሁዋላ ከሌላ ክፍተኛ የመጡ፣ ወደ አብዮቱ የገቡ ወይም በአብዮቱ የነቁ አዲስ ልጆች ገቡበት:: የትግል አጋሮቹ የተገረፉበት መሬት ላይ መተኛት፣ መተኛትንም ማወቅ ደባሪ ነገር አለው::

የታሰርንበት ግቢ ውብ ነው:: ከሚቀረኑት ክፍሎች በጎሕ ወጥቶ ግቢው ውስጥ ተቀምጦ የከበቡትን ዛፎች ድምፅ ለመስማት፣ ነፋሱን ለመተንፈስ የማይቸኩል የለም:: በተለይ ሴቶች ጋቢያችንን ተከናንበን (ለምን ጋቢ መከናነብ እንደምንወድ እስከዛሬ አይገባኝም) በረንዳ ላይ ጭር እንዳሉ ዶሮዎች ተኮፍሰን ታች ሳር ላይ ፀሐይ ለመሞቅና ለማውጋት በየቦታው ከተዘረሩት ወንዶች ጋር እኔ ባላደርገውም እናስካካለን:: እኔ መቀመጥ የምወደው ከውሃ ልኩ ታች ነው:: በማላውቀው ምክንያት ቂጤ ያን ሰሞን ትኩሳታም ነበር:: ጋቢዬን ብከናነብም ከስር ሆን ብዬ ቀሚሴን እገልብና ሳሩ ላይ እቀመጣለሁ:: ጤዛ ቢኖርም ግድ የለኝም:: የሳሩ ቅዝቃዜ ሲነካኝ የቂጤ ፍም ቸስ ይላል:: የተደበረ ገላዬ ይረጋል:: ወሬ ስለሚያስጠላኝ ብዙ ጊዜዬን የማሳልፈው ከአንደኛው ደረጃ ዝቅ ወዳለው ደረጃ ለሚመሳለሱ ጉንዳኖች ሳር እየበጠስኩ ሳቀብል ነው:: አንድ ጊዜ የሰው ጥፍር ተሸክሞ የሚሄድ ጉንዳን አጋጠመኝ:: ጉንዳኑን በመዳፌ ከጉዞው አቆምኩትና ሸክሙን አስጥዬ አንስቼ ጥፍር መሆኑን ካረጋገጥኩ በሁዋላ እንደቀፈፈኝ መንገዱ ላይ መልሼ አስቀመጥኩለት:: ሌላ ቀልቃላ ይዞት ሄደ::

ወንዶች ብዙ ጊዜ የሚቀመጡት በስተቀኛችን ካለ ትልቅ ዋርካ ስር ነው:: 'ቬትናም' ይሉታል በቅፅል:: እዛ አካባቢ ሁልጊዜ ሲጋራ እንደጤሰ ነው:: እዛ ተሰብስበው የተረጋጋ በመሰለ ገፅ ወንዶች

ትንባሆአቸውን ሲያቀጣጥሉ፣ አንድ ማድቤት ሳይሆን አራት አምስት ያህል ያሉ ይመስላል:: ግቢው ውስጥ ቮሊቮል ጨዋታ ተጀምሯል:: ሁለቱ የሴል ጓዶቼ እዚህ ታስረዋል:: ሁለቱም ሲጋራ እንደሚያጨሱ አላውቅም ነበር:: አንደኛውን ልጆች ከበውት ቀልድ ይተረትራል:: ቀልደኛ መሆኑን አላውቅም ነበር:: በእርግጥ አንተዋወቅም:: እማን እንደታሰረ ተነግሮኛል:: ከዛ ምን እንደደረሰበት አላውቅም:: ጋቢ የተከናነቡን ሴቶች፣ ቁልፉ የረገፈ ሸሚዝ የለበሱ ወንዶች፣ ልጅነታችን፣ ሳቃችን፣ ዝምታችን፣ ሹክሹክታችንና ደህና ምግብ ሲመጣ ሽሚያችን፣ እዛው በዛው ፍቅር ሲጀመር፣ ይሄ ሁሉ ከጥቂት ወራት በፊት መንግስት ለመገልበጥ የተባበርን አይመስልም:: ያንንም ለመዘንጋት የምንማስን ይመስላል:: እኔ ልረሳ አልቻልኩም:: ቶሎ መሳቅ አልችልም:: ሲጠሩኝ ቶሎ አልሰማም:: የመጨረሻዋ ተጋላጭ ስለነበርኩ ባለመታሸቴ፣ በደንብ ተገርፌ ጉብዝናዬን ባለማሳየቴ ቅር ይለኛል:: አስቸጋሪ ታጋይ መሆኔን ማረጋገጫዬን የተነጠቅሁ መሰለኝ:: መሸበርን ለግሌ በትንሹም ይሁን ፈለኳት::

መታሰሬን የሰሙ እኔን ይሁን እማማን የሚወዱ ወይም በባህል 'የታሰረ ይጠየቃል'ና የምግብ ስንቅ ይዘው ወደ ታሰርኩበት ቦታ ተንጋጉ:: እማማ አዲስ ጋቢ፣ ሮዛም ሌላ አንድ ጋቢ አመጡልኝ:: ብቻ ሶስት ጋቢዎች ነበሩኝ:: ሮዛ አዲስ ነጠላ ጫማና የዓላዛርን ስሊፒንግ ባግ አመጣችልኝ:: እሱ ውስጥ ገብቼ ያለቀስኩትን ማልቀስ እኔ ነኝ የማውቀው:: እማማ መዓት ሞዴስ፣ ቫዝሊን፣ ሚዶ፣ ጋሼ ሰይፈ የሰጣትን የእንግሊዘኛ ልብወለዶች ወዘተ አመጣች:: እዛ በነበርኩባቸው ቀኖች ምግብ የሚመጣልኝ በየቀኑ ነበር:: ብዙ ጊዜ የሚመጡባቸው ዕቃዎች ሁለመናቸው የሞቀ ወይም ለስ ያለ ነው:: የሚመጡልኝ የምግብ አይነቶች በአጠቃላይ በአራት ይመደባሉ::

አንደኛው የአባቴ ቺዝ፣ ሞርቴዴላ፣ በኦሊቭ ኦይል የተጠበሰ ፓስታ፣ ቀዝቃዛ አሮስቶ እና ሌላም:: ሁለተኛው የእማማ እንጀራ ክክ በስጋ፣ ድንች በስጋ፣ ድንች በካሮት ምናምን:: ሶስተኛው የሰፈር የዘመድና የወዳጅ በተለይ የፀሐይ አልጫና በሶ፣ በመጨረሻ የማልደያ ቀይ ሽሮ፣ አልጫ ሽሮ፣ ሽሮ ፀቅፁ፣ ትንሽ ክክ ያለበት ሽሮ፣ ስጋ እዛ እዛ ያለበት ክክና ድንች::

በጋራ ስለታሰርን 'በጋራ እንብላ' ስለሚባል ብዙዎቹ ለአባቴ ምግብ ይሻሙ ነበር:: 'አብረው ይበላሉ፣ ይደጋገፋሉ፡ ይዋደዳሉ' ይባላልና ይሄን የሽሚያ ቄንጥ የታዘበ የለም:: ቢታዘቡም ስቀው ያልፋሉ:: እኔ ስቄ አላለፍኩም:: ምክንያቱም ከምግቡ ሁሉ ሳይበላ የሚቀረው ማልደያ ያመጣችው ብቻ ነበር:: መቅረት ብቻ ሳይሆን እጅ እጅ ስለሚል ሲነጋ ለውሾች ይጣላል:: አዲስ የተሻለ ምግብ ይመጣና ተመሳሳይ ሽሚያ ይቀጥላል:: በዚህ ለማልደያ አዘንኩ:: እንደገና ከእኩልነት ጡሩንባ ጀርባ

ትንሽ ብንገልብ ሆዳም ቁጭ እንዳለ ተረዳሁ:: በዚህ ራሴንም አብዮተኞችንም ገመትኩ:: ግን ትዝብት ጋ ነው ያቆምኩት:: ትዝብት ጋ ማቆም የፈሪ ነው:: ገፋ አድርጌ ማጤን ነበረብኝ:: ገፋ አድርጌ የዛን ሁሉ ሰው መስዋዕትነት መነሻውንና መድረሻውን አልገመገምኩም:: እኔንም እንደሚጨምረኝ ገብቶኝ ይሆናል:: ማልደያ ሲደላት ብቻ የምትበላው ግን ለእኔ በየቀኑ የምታመጣው ምግቧ ለእሷ ለጭቁኗ እንታገላለን በሚሉ አብዮታውያን በድብቅ ቢገለልም፣ ከመውደድ ሌላ ሽፍጥ አይገባትምና ደሞም አታውቅምና በእድፍ ቡላ የሆነ ጋቢዋን ለብሳ ለስአታት የታሰርኩበት ቤት ደጃፍ ላይ ትቆማለች:: ተነግሮኝ ወጥቼ እንድትሄድ እለማመጣታለሁ:: በአጥሩ በር የብረት ፍርግርግ መሃል እጇን ይዛ ጣቶቼን ትስማለች:: እንድትሄድልኝ እለምናታለሁ:: ስትሄድም በትክክል መሄድ አይባልም::

እንዲህ አይነቱ ዘመዶቻችን የሚያደርጉልን እንክብካቤ በመጠኑ የገባንበትን ፖለቲካ ትክክለኛነት የመሰከረና የተደነቀ ሳያደርግልን አልቀረም:: 'የታሰረ ይጠየቃል' ብሎ ክርስቲያን ቢተነትንም አዙሬ የመበደሌ መለኪያ አደረኩት:: ብበድልም የእስር ቤት ስንቅና ትጥቅ፣ ሳይለፉ መጥገብ፣ የዘመዶቻችን ሰንባ፣ በዳይነቴን ሰረዘልኝ:: ቢያንስ ከለለልኝ::

ማታም ይሁን ቀን ትንሽ ካናወዘኝ ጥልቅና ትርጉሙን የማላውቀው ቅዠት እያነሳ ይጥለኛል:: ባላለቅስም አይኖቼ ያበጡ ናቸው:: ብተኛም አልተኛሁም:: ደም የደረቀበት ስፖንጅ ወለል ላይ ስጋደም ከውጭ ትቼው የመጣሁት ምኞት ይናፍቀኛል:: ከቤትና ከዘመድ የሚመጣልኝ ምግብ፣ እዝራ የሚልክልኝ ሳንቡሳ፣ ሮዛ የምትሰራልኝ በስጎ የረሰረሰ ፓስታ አያምሩኝም:: ከማየው፣ ከምነካውና እዚህ ካለው ማዕናኛ ይልቅ በሃሳቤ ያሉት የሽሮሚዳ ንፁህ አየር፣ የዋሕድ ሸንኮራ፣ የአባባ ፐሪም፣ የአብረኸት ሳቅ፣ የሮዛ ጉንጉን፣ በባዶ እግሬ የምጫወትበት በዝናብ የተበጠበጠ ያቋረ ውሃና ቀዝቃዛው ክረምት፣ እጆቼ መሃል መዳፌ ላይ የሚፈነዱ ያሞቀሞቁ ቀጋዎች ናቸው:: በመጀመሪያ ቀን የተገረፍኩዋቸው ውስጥ እግሮቼ ወደነዚህ እንዳልሄድ ማዘግያ መሰሉኝ:: የሚሰማኝ ህመም አንዳንዴ ሕልሜን ያቆመቀል:: በእንቅልፍ ትመስሎ ሞት እንዲወስደኝ ያሰብኩበት ጊዜ አለ--በተኛሁበት ብቀር:: ሁልጊዜ ሌሊት ካድሬዎችና አብዮት ጠባቂዎች በረንዳ ላይና ግቢ ውስጥ ስክረው ሲሳሳቁ እሰማለሁ:: ሁልጊዜ እንደዛ ነው:: 'አልኮል የተፈለሰፈው በዛ ሰሞን ነው እንዴ?' ያሰኛል:: ከመሀል ፀጥታ ይሰፍናል:: ፀጥታው ካድሬዎች ሴራ ሊፈትሉ ሲዘጋጁ፣ ጆሮ እየተቀዋወሱ ሌላ ያልተነገረን አይነት መከራ ሊያመጡ ያደፈጡ ይመስለኛል:: ከመሃል አንዳችን እንድንጠ'ራ ስጠብቅ ትርጉም የለሽ ሳቅና አስፈሪ የወንድ ድምፆች እሰማለሁ::

ትናንት በቸልታና በንቀት ያለፍኩዋቸው በልጅነቴ የማውቃቸው ምስሎች ቀን ብቻ ሳይሆን ማታም ይመጣሉ:: ሰይጣን ከነፍሴ ጋር እንቁልልጭ የያዘ ይመስለኛል:: ለምን ያኔ ቸል ያልኩዋቸው ያጓጉኛል? አንዳንዴ ፈረንጅ አገር እሄዳለሁ::: በማላውቀው ትልቅ ፎቃም ከተማ ውስጥ ዓላዛርን እፈልገዋለሁ:: ፈጣን ባቡሮች በሚንካኩበት፣ ባዕድ ቋንቋ በሚተረትሩ ሰዎች መሃል፣ በትርምሱ፣ የሆነ አደባባይ ጥግ ዋሕድ ሸንኮራ ሲሸጥ አገኘዋለሁ:: አያውቀኝም:: ማን እንደሆንኩ ብነግረው አያውቀኝም:: ባዶ ቤት ገብቼ አኩርፌ እቀመጣለሁ:: ዓላዛርን እንደምጠብቅ ትዝ ይለኛል:: የምጠብቀው ዓላዛርን ነው:: ደሞ አልጠብቀውም:: አለሁበት ክፍል ውስጥ ለሁለት ቀኖች በወፌ ያገላበጠኝ ካድሬ በግ እየጎተተ ይገባል::: ከክፍሉ እየሮጥኩ እወጣለሁ:: 'በረት ውስጥ ምን ትሰሪያለሽ?' ይለኛል:: ወደ ውጭ እየሮጥኩ ስወጣ ደብረዘይት ከተማ ነው፣ መንገዶቹ በጋሪ ሞልተዋል:: አየሩ ሸቶ ሸቶ ይሸታል:: 'ምናልባት አብረኸት በዛ አልፋለች' የምባንነው ያኔ ነው:: ለምን አየሩ ሸቶ ሸቶ እንደሚል እየተመራመርኩ እባንናለሁ:: ሰባንን ያጥወለውለኛል:: እንደምንም አድርጌ ከሆዴ ሊወጣ የሚዳዳውን ምናምን እውጠዋለሁ::

ከጥቂት ቀኖች በሁዋላ በጠዋት በጠዋት ያስታውከኝ ጀመር:: ቀላል ትውከት አልነበረም:: ከጭንቀት የመጣ የሆድ ሁከት እየመሰለኝ ዝም አልኩት:: አብረውኝ ከታሰሩት ያልተኙ ከሆኑ ሳስታውክ ሊደግፉኝ እደጅ አብረውኝ ይወጣሉ:: ደጋግሜ መታመሜን በመናገሬ ከአንድ አብዮት ጠባቂ ጋር ሌሎች ስድስት ሴቶችና አንድ ወንድ ልጅ ለተለያየ አይነት ሕክምና ቀሐሥ ሆስፒታል ተላክን:: ከደምና ሽንት ምርመራ በሁዋላ 'ፀንሰሻል' ተብሎ ሲነገረኝ እጢዬ ዱብ አለ:: ከሆስፒታል ወደ እስር ቤት ያለ ድምፅ በውስጤ እያለቀስኩ ሄድኩ:: በአእምሮዬ የመጣችው የብርሃንና ሰላሟ ዳሮ ነበረች:: የመገዳደሉ ነገር የቀዘቀዘ ቢሆንም፣ በፍርሃት ብቻ እንቅልፍ አልወሰድ አለኝ:: ሲያቀብጠኝ ነግሬ፣ ያውም ቃል አስገብቼ፣ አብረውኝ ሆስፒታል የሄዱት ልጆች እርጉዝ እንደሆንኩ አወሩ:: እንዲህ አይነት ወሬ በዛ ጊዜ ሲመጣባቸው ብዙ ልጆች በሆነ ካድሬ ተደፍራ ነው ብለው አመኑ::

መፅነሴን ባወቅሁ በሶስተኛው ቀን መሰለኝ አንድ ጠዋት ላይ አዲስ ካድሬ እንደ ተመደበ ተወራ:: ገና በገባ በአምስት ደቂቃ ውስጥ ሁሉን እስረኛ ሰብስቦ ይህቺን አጭር ጉዳይ ተናገረ:

«ሙላት ተመስገን እባላለሁ፣ ጓድ ሙላት ማለት ትችላላችሁ:: የዚህ ካምፕ ፈላጭ ቆራጭ ነኝ:: ስቀልድ ነው:: ምንም አትፍሩ:: ሁሉ ነገር በስርአት እየተካሄደ ነው:: አንዳንድ አስቸኳይ ውሳኔ የሚያስፈልጋቸው ነገሮች ስላሉ አብረን እንፈታቸዋለን:: አንድ ነገር ደሞ፣ ፈቃድ ስጠኝ

እያላችሁ አትጨቅጨቁኝ:: እስር ቤት መሆኑን ትረሳላችሁ:: አንዳንድ ሰዎችን ማነጋገር እፈልጋለሁ:: ከአንድ አምስት ደቂቃ በሁዋላ ስማችሁን እንጠራለን:: በሉ ሽርክ እንሁን ጓዶች»

ይሄን ተናግሮ ከሄደ ከጥቂት ደቂቃዎች በሁዋላ ወደ ቢሮው ተጠራሁ::

ጋቢዬን እንደተከናነብኩ ሄድኩ:: ሳልፍ በመስኮት መስታወት ውስጥ ራሴን ለአፍታ አየሁት:: ሳይበርደኝ የበረደኝ፣ ሳላረጅ ያረጀሁ እመስላለሁ:: አይኖቼን ቶሎ ዞር አድርጌ በፍርሃት ጎበጥ ብዬ ቢሮው ገባሁ:: ጓዱ ገና እንዳየኝ ቆጣ ብሎ:

«ዝጊው!» አለኝ በሩን እያየ:: በሩን ዘግቼ ስመለስ እንድቀመጥ ወንበር በእጁ አሳየኝና ኑዛዜዬ የተቀመጠበትን ፋይል እንዳላነበበው ሁሉ በዝምታ ሲያገላብጥ ቆይቶ:

«ከማን ነው ያረገዝሽው?» አለኝ

«ከቦይ ፍሬንዴ» አልኩት

«ማነው ስሙ?»

ልመልስ አልፈለኩም::

«ስሙ ምን ያደርግልሃል?»

«አይዞሽ» አለና ቀና ብሎ አየኝ

«ዓላዛር ይባላል»

«አገር ውስጥ አለ?»

«አልገባኝም»

«ተፈሪ መኮንን ተማሪ ነው አይደል:: ጀርመን ስኩል ነበር ወደ እዛ ቀየረ»

ዞር አለብኝ:: ሁኔታዬን አይቶ ፈገግ አለና:

«አለዓዛርን አውቀዋለሁ»

ምንም መናገር አልቻልኩም::

«የተፈሪ መኮንን ተማሪ ነበርኩ:: 12 ዲ ክላስሜቴ ነበር:: 'ሙላት ተመስገን' ብትይው ያውቃል:: ያኔ 'ሙላት ጆሊው' ነበር የምባለው ሂሂሂ፣ አፍሮዬ ጎጆ ቤት ነበር የሚያክለው:: አይ ጊዜ......እና 'ጓድ' አትበይኝ:: ሰው ባለበት ብቻ:: ስለአንቺ የተሟላ ሪፖርት ደርሶኛል፣ መደፈር ደርሶብሽ ቢሆን ኖሮ እጃችን ደም ይነካ ነበር:: ቶሎ ትወጪያለሽ:: አማንን ታውቂዋለሽ አይደል? አማን ለሕክምና ወደ ሆስፒታል ሲሄድ ከጠባቂው ወታደር ጋር ተያይዘው ጠፍተዋል::

ምናልባት ጅቡቲ ነው:: አትፍሪ አይዞሽ:: ዘመዶችሽም ከሚገናኙት እየተገናኙ ነው»

ሲጋራውን ለኮሰ:: «የዚያ አይነት ሰዎች ያኮራሉ:: እኔ ዘመድ አልነበረኝም:: አባቴም እናቴም 'እንዴ አስጠንቅቀንሃል' ብለው ዞር ብሎ ያየኝ የለም:: ግን አንድ ቅር ያለኝ ነገር አለ:: አባትሽ አንቺን ይውደድ ደርግን ይጥላ እርግጠኛ አይደለሁም:: ቢሆንም ለፍተውልሻል:: ከገንጣዮች፣ ከፊውዳሎችና ከወራሪዎች ጋር የሚያሴር ድርጅት አጋልጬና ሃሳቤን ለውጬ ራሴን ማደስ ነበረብኝ:: የደርግን ሰዎች ለመግደል የሚፈጥኑ ስኳዶች እንዴት እኛን ለማዳን አልቻሉም? እንዴት ዘገዩ? የት ነበሩ? ፓትሲ መሆን አልፈልግም:: 'ፓትሲ' ታውቂያለሽ? ፓትሲ ማለት አንቺ ጠመንጃ ትይዢአለሽ ገዳዩ ሌላ ሰው ነው:: ፖሊስ ከነጠመንጃሽ አንቺን ይይዛል፣ ገዳይ ተገኘ ማለት ነው:: በዋናው ገዳይ ምትክ 'ገዳይ' ተብለሽ ትገደያለሽ:: ያ ዋናው ገዳይ የት አለ? ለምን መልኩን አናይም? ለምን ሙሉ ስሙ ከነአባቱ አይነግረንም? አንቺን እንደዚህ የማወራሽ ዓላዛርን ስለማምነው ነው:: ከሚኒሊክ በፊትም አውቀዋለሁ:: ከእዝራ ጋር ወወክማ ይመጡ ነበር:: ዘውገ፣ ነፀረ ምናምን የሚባሉ ልጆች ነበሩ:: እስከቅርብ አራት ኪሎ አየው ነበር:: እንድትጎጂ አልፈልግም:: አዲስ ፍትህ ያለው ስርአት መገንባት ባልችል፣ የዓላዛር ልጅ በሰላምና በጤና ተወልዶ ማየት ደስ ይለኛል:: ለልጁ ነው:: በሌሎች ሂሳብ መቀጣት ነበረብሽ:: ግን ልጁ አይቀጣም:: ትክክል የነበርሽ አይምሰልሽ»

«እሺ» አልኩ አንገቴን ሰብሬ

«እዚህ ስናየው ሁሉ ቀላል ይመስላል:: መባላት አለ:: ሁላችንም እየተጠባበቅን ነው:: ወጣቱን በሙሉ ለመጨረስ የሚፈልጉ አሉ:: ደም የሚወዱ አሉ:: እኔ አንቺን ስከላከል አንቺ እኔን መደገፍ አለብሽ:: ለአንቺ ለተራዋ የፓርቲ እጩ ማን ግድ አለው? ምንም አይደለሽም:: ይሄን በልቦናሽ ያዢ:: ልጎዳሽ አይደለም:: የግጭት ኤክስፐርቶች አሉ፣ እያንዳንድዋን አለመግባባት ሞት ሊያደርጉ የሚፈልጉ:: ከዚህ ጣጣ ከወጣሽ በሁዋላ የራስሽ ጉዳይ ነው:: አሁን ውይይት ሲደረግ ተደብረሽ ዝም አትበይ:: ውይይቱ ላይ በርታ በይ:: ስለ አብዮቱ ትክክለኛነት ሃሳብ ስጪ:: ማንስ ድርጅት ትክክል ሆነ አልሆነ ለአንቺ አሁን ምንም አይደለም:: ሁሉ ነገር ስለፈረሰ የምንከላከለውና የሚከላከለን የለም:: ድሮም አልነበረም:: የአብዮታዊ ዘፈን ብትለማመጂና ስብሰባ ማሳረጊያ ላይ ብታቀነቅኚ ለአንቺም ለልጅሽም ጥሩ ነው:: አሁን ወደ ቲያትር ተሸጋግረናል:: ገባሽ?»

«የሚያምር ድምፅ ያስፈልጋል:: ደሞ......» አልኩት፣ ስዘምር እያሰብኩ ሳቄ መጣ::

«ገባኝ:: ድምፃዊ ሁኚ ያለሽ አለ? ራስሽን አድነሽ የሌላ መወጣጫ ሳትሆኚ ማምለጥ ነው:: አራዳ መሆን ያስፈልጋል:: ለንቃት የሚሆን ምዕራፍ የማያስቸግርሽን ትመርጪያለሽ:: 'እርጉዝ ስለሆነች ብቻ ሳይሆን፣ ወደ አብዮቱ ስለተመለሰች ተለቃለች' ይባላል:: ነጥቦቼን እሰጥሻለሁ:: ለእኔ አይደለም፣ ለልጅሽ ነው:: የምትችይውን ገለፃ ታደርጊያለሽ:: የውሸት ፈጠን ፈጠን በይ:: አስፈላጊው እውነት አይደለም፣ መታየት ነው:: አሁን የመታየት ጊዜ ነው:: ስለ አብዮታዊ ባህል የሆነ የውይይት ሃሳብ ሲነሳ 'እኔ ሃሳብ አለኝ' ብለሽ እጅሽን አውጪ:: ከአሁን ሁኔታ አንዳንድ ነገር መተንበይ ቢቻልም፣ የሚሆነው አይታወቅም:: እርጉዝ እንደሆንሽ ሁሉ ሰምቷል:: ዳሮ ነጋሽና ግርማ ከበደ ምናምን ብለን ነገሩን አስፈሪ አድርገነዋል:: ወደ ላይ ደርሷል ያንቺ ሁኔታ:: ስለ ዓላዛር ምናምን አያውቁም፣ መጠየቂያ ጊዜ የላቸውም:: ፍርሃት፣ ትርምስና ጦርነት ነው:: የአንቺን ማርገዝ 'ደግ' ለመባል ሊጠቀሙበት የሚፈልጉ ይኖራሉ:: ምን ቸገረን እንለቅላቸዋለን:: ዕድል ጠቃሚ ነው አንዳንዴ:: ለመሆኑ ዓላዛር እንዴት ነው?»

«ምስራቅ ጀርመን ሄዷል»

«መቼ?» ሂሳብ እያሰላ ነበር፣ ማርገዜን ሊያረጋግጥ መሰለኝ::

«ወር ይሆነዋል ከሄደ»

«በመጀመሪያ እንደመጣሽ ስለደረሰብሽ ግርፊያ ሰምቼአለሁ:: ከአሁን በሁዋላ ምንም አትሆኚም:: ግን እንዳልኩሽ ታደርጊያለሽ»

«ዓላዛርን በደንብ ታውቀው ነበር?»

«ክላስሜቴ ነበር:: ትግል ከገባሁ በሁዋላ ብዙ አላገኘሁትም:: እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ አንዳንዴ እዚህ አራት ኪሎ አገኘው ነበር:: 'ጓደኞቹን እጠብቃለሁ' ይለኛል:: ቁንጥንጥ ስለሆንኩ ብዙ መቀመጥ አልወድም:: አንድ ሁለቴ ከእርቀት አይቼሻለሁ:: ስላላየሽኝ ትዝ አልልሽም»

«እሱ ከብዙ ሰው ስለሚተዋወቅ......ሰላም የሚለውን ሁሉ ሰላም ማለት ይደክመኛል»

«ሃሃሃሃ......አይቼሻለሁ ግን ለመተዋወቅ ጥሩ አጋጣሚ አልነበረም:: እሱ አስፈላጊ አይደለም አሁን:: አይደለ? ብዙ እናውራ:: እንገናኛለን»

ፋይሌን አጣጥፎ ወደ ጎን ገፋና እየሳቀ አየኝ:: ምን እንደምል አላወቅሁም:: አይኖቼን ላለማየት ከእሱ ሁዋላ ያለው ግድግዳ ላይ አፈጠጥኩ:: በእርጅና ቡናማ የሆነ መደርደሪያ አለ:: መደርደሪያው ላይ በጣም የሚያማምሩ ቅሎች አሉ:: እላያቸው ላይ የተሰራው ንድፍ ብቻ ሳይሆን እንዳይከነበሉ የተሰሩበት የመዳብ መቀመጫ ያበራል:: ወደ

ሙላት ዞር አልኩ:: እስከ ዛሬ ስኖር እንደዛ ቁጡ የሆኑ አይኖች አላየሁም:: *ምን መጥፎ ነገር ተናገርኩ?* ብዬ አሰብኩ:: ወደ ሁዋላው ትንሽ ለጠጥ ብሎ ግድግዳውን አየና:

«ደስ ይላሉ አይደለ? እዚህ ከጆርባ በቀረጢት ተከተው ተጥለው ነበር:: መጠጫ ትፈልጊ እንደሆነ ውሰጂ:: ሰዎች እየሰከሩ እየሰበሩ ሳይጨርሱት:: መቼ እለት ጓድ ዘለቀ ገርባ አንድ ምን የመሰለ ቅል ሰበረ»

«የምር ልውሰድ?»

«አዎ:: የትኛውን ትፈልጊያለሽ?»

«ያን የብረት እንትን ያለውን»

«ተንኮለኛ! ደህናዋን *መረጥሽ*»

ከተቀመጠበት ተነስቶ በሁለት መዳፍ እፍኝ መያዝ የምትችል መንበርዋ በመዳብ አምባር የተጠረዘ አንድ ቅል አወረደልኝና ፈገግ ብሎ ሰጠኝ:: ፈገግ ቢልም የአይኖቹ ሁኔታ አልተለወጠም:: አመሰገንኩትና ቅሌን በጉያዬ ይዤ ቶሎ ወጣሁ::

«ቻው»

«ቻው»

እውጭ እንደሆንኩ ሙላትን ከክንብንቤ ሳልወጣ ሳዋራው እንደቆየሁ ገባኝ:: ፈሪ መባል ባልፈልግም ፈርቼ ነበር:: ሙላት በመኖሩ የታደልኩ ቢመስለኝም፣ የተናገረውን ባምነውም፣ ከማበራታቻው ይልቅ ከህሊናዬ ተጣብቆ የቀረው የነገሮች መተንበይ አለመቻልና መጨረሻ ላይ ያየሁዋቸው በቁጣ የተቀነበቡት ጥቋቁር አይኖቹ ናቸው:: መተኛ ቦታዬ ተመልሼ ስቀመጥ የመኖርና የመውለድ ተስፋ የተሰጠኝ ልጅ አልመሰልም:: ቅልዋን እያገላበጥኩ ሳይ ሊጠፋ በደረሰ ፍቂያ ብረቱ ቂጥ ላይ ይሄ ተፅፎ አነበብኩ:

***ሸሽተሽ ተአራዳው ብትገቢ እሞጆ***
***ተዓይን አይሸሸግም ተራራና ቆንጆ***

ያጋጠመኝን ለሙላት ላሳየው አልፈለኩም:: በትክክል ደግሜ እሱ ጋ መሄድ፣ እነዛን አይኖቹን ማየት አልደፈርኩም::

ሁኔታዬን መለወጥ ጀመርኩ:: ሬድዮ እየሰማሁ መፈከር ተለማመድኩ:: ግቢው ውስጥ ባለው ቮሊቦል ጨዋታ አንደኛዋ ነበርኩ:: ቅጠል በጥሰው ጢብጢብ የሚጫወቱ ወንዶችን አፈርድሜ አስበላሁ:: የሽሮሜዳ ስፖርት መሆኑን አያውቁም:: የምወደድ ልጅ ነበርኩ::

በቮሊቮል ተከልሎ ሌላ ነገር የሚሞክር ወንድ በተረብ ይቀጣል:: ከውይይት በሁዋላ የማስማው መፈከር ውብ ነበር::

ሌላም ተግራሪ ስሜት አይጠፋም......

......ከዚህ ሁሉ ሳርፍ፣ ብቻዬን ስሆን......መሞቴ በዕጣ በሚወሰንበት ጊዜ......ፊቴን የእጄ መዳፎች ላይ አስቀምጬ አየርና መሬት ማየት፣ በልቦናዬ ጆሮም የጀርባ ቀስሌን ማዳመጥ ነበር ትልቁ ስራዬ:: እናም አስባለሁ:: አስባለሁ ዝም ብዬ አስባለሁ......ምንም ከአላማዬ ስነስርአትና ካለሁበት ሁኔታ ባይጣጣምም፣ ለማንም ባልናገረውም (አልናገረውምና)፣ ከምሰበሰብበት ጠረጴዛ ዙሪያ ድሮ ስጀምረው ፖለቲካውን 'ቻው' ብዬ ተነስቼ ብቀር:: *ፖለቲካ ውስጥ ባልገባ ኖሮ?* ለአገሬ የተሻለኝን አደረግሁ ብልም፣ ለራሴና ለጉዋዶቼ ብናገርም፣ ከውስጥ ግን 'ባይሆን ኖሮ' ጥርጣሬ ገባችኝ::

በዘመድና በሰብአዊነት ግፊት የሶስት ወር እርጉዝ እንደሆንኩ ተፈታሁ:: የእስር ቤት ጓደኞቼ ይቀልዱ ነበር፡ *ሽረ እኛንም የሚያስረግዘን ፈልጉ::*

ከእስር ከተፈታሁ በሁለተኛው ቀኔ፣ ማረፊያ ጊዜ እንኩዋን ሳትሰጠኝ እማማ በጠዋት ክፍሌ መጥታ፣ ገና እንኩዋን ከአልጋዬ ሳልወጣ፡

«ማንም ያውቃል አሁን:: ልጁ የማነው?» አለችኝ:: ወገቧን ይዛ ጥርሶቿን ነክሳ::

«የዓላዛር»

«ይሄ ልጅ የማንም ካድሬ ከሆነ፣ ባልቻ ሂደን እኔ ፈርሜ ታስወጪያታለሽ:: የዓላዛር ከሆነ ምንም አይደል:: ልክ አይደለም፣ ግን ምንም አይደል:: የተዘባረቀ ነገር»

አልመለስኩላትም:: ዝምታዬን ስታዳምጥ ቆይታ አመልካች ጣትዋን እየነቀነቀች፡

«ዕውነቷን! ዕውነቷን ታወጪያታለሽ!» አለች::

ያልኩዋትን እንደሰማች ተንቀልቅላ ሂዳ 'የፀነሰችው ከዓላዛር ነው' ብላ ለአባቱ ለዓላዛር አባት ነግራው ተጣሉ::

'ልጅሽ የት እንደምትውል ይታወቃል? አፍንጫሽ ስር ፖለቲካ ስትሰራ ምን ታደርግ እንደነበረ እንኳን አታውቂም' አለኝ ምናባቱን እሱ ደህና ሰው ሆኖ ሙቶ ልጄን 'ዱርዬ' አለ ብላ፣ እንደገና ተመልሳ የነገርኩዋትን ሁሉ በእሱ የግምት ግፊት ተጠራጥራ፡

«እውነትሽን ነው አንቺ የዓላዛር ልጅ ነው?»

«ካመንሽ እመኚ፣ ካላምንሽ ተይው» አልኩዋት::

«ምን ይህቺ የዞረባት። እኔ እኮ ነኝ አሳዳጊ......አንቺ ገና ጡት ትናንት ወዲያ የጣልሽ ፍየል......»

አልመለስኩላትም። እንዲህ እንዲህ አይነት ነገሮችን በሚመለከት ለብቻዬ መሆንን መለማመድ ጀመርኩ።

በስንቶቻችን መሃል ሽብልቅ ገባ? በእኔና በዓላዛር፣ በእኔና በእማማ፣ በእማማና በዓላዛር ቤተሰብ። አስገራሚ ነው። ሳስበው ለዓላዛር ያሳየሁት የመጨረሻው ቀን ንፍገቴ ያሳለፍኩትን ልጅነቴን ባዶ ያደረገ፤ ያን ሁሉ ጨዋታ ያን ሁሉ ቀልድ ያን ሁሉ 'አንተ ትብስ አንቺ ትብስ' እንዲህ ዝም ብሎ ሜዳ ያስቀረ መሰለኝ። አንዳንዴ *ለምን በፈቃዴ አልሰጠሁትም? ምን እጎዳ ነበር?* እያልኩ ጥያቄ አስባለሁ። (ከሚያፈቅሩት ጓደኛ ጋ በጥልቅ መዋሰብን እንደ ስህተት እንድገነዘብ ያደረገኝ በየዋህነት በልቤ የከተትኩት የትግል ስነስርአት-(በግልፅ ባይነገረኝም)-ባይኖር ኖሮ እላለሁ) ከእሱ ሌላ ማንንም ወንድ አለማወቁ የሚታወቀው *በእኔ ብቻ* ነው። የእኔ ምስክር *እኔ ብቻ* ነኝ። መንገድ ላይ ገትሬ ትዝብት ውስጥ ከትቼዋለሁ። ለምን እያለ እንዳሴለ አደረኩት? ዐይን አስገብቼዋለሁ። 'ለምን?' ተመልካች 'ለምን?' ብሎ ይጠይቃል። ስለዘጋሁት እንደሆነ ያምናል። ታዲያ ከዘጋሁት እንዴት ከእሱ አረግዛለሁ? 'ከማንም ካድሬ ቀፍድዳ *አይ ላቭ ሂም*[109] የእሱ ልጅ ነው ትላለች' እንደሚሉኝ አውቃለሁ። ብርሃን ቢጠራጠረኝ አይገርመኝም። ግን በብርሃን አባባል ተበሳጨሁ። ሰው እውነቱን የሚናገረው ሲደላው ነው። እናቴም ጠመም ባለ መንገድ ብርሃንን አምታ ስትበሳጭ 'እረፊ' አላልኩዋትም።

ግን አሁንም እንደ ዓላዛር የማስበው ማንም የለም። አላምር ይላል። ምንም አላምር ይላል። ቢናገሩት አላምር ይላል። ጭንቅላቴ የትዝታ አደባባይ ነው: ቦታ፣ ዘመንና እሱ ትዝ ይሉኛል......ሰኞ ማክሰኞ የተጫወትኩበት ቤቴ ፊት ለፊት ያለው በጫማና በእግር የተገጠበ ሳርና ሲሚንቶ፣ የስድስት ኪሎ ሰፈ አስፋልት፣ ወሬናውና ሳቁ፣ ቤታቸው ጓሮ ካሉት የብርቱካን ዛፎች ጥላ ስር፣ የሎሚናት ጭማቂ እየሰራን ስንጠጣና በጥጋብ በእሱ ስንራጭ፣ እናቱም እንደ መስታወት የጠራ ፊታቸውን ወደ አፌ አስጠግተው እንድስመው ሲሰጡኝ--የሽቶአቸው ጣዕም፣ እሱ ዛፍ ላይ እየወጣ ሲጠፋብኝ--ሳልጠብቀው ከሁዋላዬ ዘሎ ወርዶ ሲያስደነግጠኝ፣ ሰፈሬን እንደ ወረቀት ቀደው የሚያልፉት በዮች፣ መጠውለግ የጀመሩት ነፋስ የሚያነቃንቃቸው ባሕርዛፎች ('መጣሁ!' ብዬ ብጮህ ይሰሙኛል?) ከታዚና ሆቴል የሚመጣው የአማርኛ ሙዚቃ......በሰው ላብ መጥቆር የጀመሩ የበረንዳዎቹ አራት ማዕዘን የዕድ ምሰሶዎች......በህቡዕ የምናልፍ በት የስርቆሹ በር ዝገቱ፣ ከዓላዛር ጋር አልጋ ውስጥ ገብተን የምን ሰማቸው ድምፆች......መጀመሪያ ከእሱ ጋር መኝታ ቤቱ ያደረግነው

[109] እወደዋለሁ(I love him)

የሚጥመው ነገር ሁሉ......ጨው ጨው የሚለኝ የገፁ ላብ (አሁንም ምላሴ ላይ ይሰማኛል)......ምሳ ሲበላ ደርሼ እንደሆነ አፌ የሚፈነዳ እስኪመስለኝ ሲያጎርሰኝ......ከእኔ ተርፎ ሊንጠባጠብ የተንጠለጠለውን እንደ ቡችላ ተንጠራርቶ በአፉ ሲለቅም......ተዝናንቶ የሚተነፍስ ፊቱ ጎፈሬዬ ውስጥ ሲጠፋ......አጥብቆ አቅፎ ወደ ደረቱ ሲስበኝ......ከፖለቲካ ለመራቅ የሚጠቀምበት የማሾፊያ ጥበቡ--'ምን ይፈልጋሉ ከእኔ? ፋራ አረጉኝ' ሲል......ጉዋደኞቹን በሰፈራችን ጨለማ ሲጣራ--እናቴ 'ይሄ ልጅ ቀስ አይልም? አደነቆረን እኮ፣ አናርኪስት ቢባል እሱ' ስትል......ሁሉ ሰዎች እንደማያውቁ እየተጠቃቀሱብን በአጠገባችን ሲያልፉ......እናቴም እናቱም አባቱም፣ ኤንሪኮ ለስላሳ ኬክ ስበላ ኩርማኑ ተሰብሮ ደረቴ ላይ ቢወድቅ ተስፋዬን (ዛሬ 'ክሬዚ' የተባለው) 'ጠብቀን መጣን' ብለን ሄደን ሽንት ቤት ተከታትለን ገብተን ልብሴን አብሮኝ እየጠረገ ደሞ እየኮረኮረኝ ስስቅ ባለቤቱ መጥተው ገላምጠው ሲያስወጡን......ትንንሽ ነገሩና ሌላ የማያውቀው ፀባዩ እየናፈቀ ያብሰለስለኛል:: የእውነት የቆዳው ንኪ እንደ እንጀራ ይርበኛል:: የእውነት ራስሽን ቧጭሪ ቧጭሪ ይለኛል:: አንዳንዴ እንዳላበኝ ሁሉ አንገቴን አካለሁ::

ምስሎቹ እየተደጋገሙ ይመጣሉ:: ከልቤ ስር ያቆስሉኛል:: ከላይ እስከታች ከተዘረጋው ደም ስሬ ውስጥ ጎምዛዛነት እንደ አረቄ ይጠነሰሳል:: እሱን መልሼ እጠጣለሁ:: እና: እስባለሁ:: ዝም ብሎ ማሰብ:: የትም አይደርስም ግን እስባለሁ:: እሱ ልጅ ሁለመናው እዚህ ነው:: የምዳሰሰው ያህል:: የምጨብጠው ያህል:: በየሰከንዱ ዕንባ በአይኖቼ ይከተራል:: ለመኖር ያቀደ የዕንባ ፍጡር እወልዳለሁ:: ሳንባ ያለው ዕንባ ነው:: ኩላሊት ያለው ዕንባ ነው:: ጣፊያም ጉበትም አለው:: የእግርና የእጅም ባለቤት ነው:: ትዝታ የተባለ ብልትም አለው:: ወደ ጉንጬ ወርዶ እንዳያሳጣኝ ቅልጥሞቹ ተሰብረው ሽፋሽፍቶቼ ድልድይ ላይ እየተነፈሰ ይቆለላል:: ዓላዛርን ይሄኔ ባገኘው ስጋውን እበላለሁ፣ አጥንቱን እቆረጥማለሁ፣ ደሙን እጠጣለሁ:: በዘሩ እታጠባለሁ:: የትም አይሄድም:: እንደዛ ይመስለኛል:: ዝም ብሎ እንደዛ ይመስለኛል::

## ወይ እሩቅ አይደለህ አልተሰወርክ ከዓይኔ[110]

ሰፈር መቀመጥ አልፈለኩም:: ደብረዘይት ምናልባት በረከት ነጋሚ ቢኖር (ሲለፈልፍ የተማረረ ካልገደለው) እንዳላየው በሚል መሄድ አልፈለኩም:: ቀድሞ የሚሰማኝ ሐይል ውስጤ አልነበረም:: አቅም የሰጠኝ ድርጅቴ ስላልነበረ ነው? አዲስ አባ ብቻ ሳትሆን ሸሮሜዳም የአቅሚቲ ሰፋችብኝ:: የማየው ፊት ሁሉ እንግዳ ሆነብኝ:: በጥርጣሬ የሚያየኝን ወይም የሚያየኝ የመሰለኝን ሰው ለድርጅቴ ነግሬ ስሙን ማጥፋት፣ ወይ መልሼ መገላመጥ አልችልም:: የማስፈራራት ችሎታዬ የለም:: ደፋር ያደረገኝ መሠረተ ልማት አልነበረም::

ከእስር ቤት ስወጣ ያላደረግሁትን 'አደረገች' ተብሎ እንደ ተወራብኝ ሰምቼአለሁ:: ያልሰራሁት 'ተሰራ' ተብሎአል:: ሰው ያመነው ብቻ አይደል ዕውነት:: የግርማቸውን አባት በመግደል ሴራ የሸሮሚዳ ኢሕአፓዎች አሉበት ተብሎ ያላመነ ሰው ጥቂት ነው:: ብዙ ወሬ እስር ቤት እያለሁ በእኔ ላይ ባይሆንም፣ በነበርኩበት ድርጅት ላይ ተነዝቷል ......ይመለከተኛል:: የወሬን ጉልበት ስለሰራሁበት አውቃለሁ......ከእልፍ ሰራዊት እንደሚበልጥ አውቃለሁ:: በሰፈርኩት ቁና እየተሰፈርኩ ነው......

በዚህ በዚህ ምክንያት ከግቢዬ ወጥቼ ያደግሁባትን ሸሮሚዳ ደፍሬ ማየት፣ ሰፈር መቀመጥ አልቻልኩም:: ይሄ እጄ በአገሬ ፖለቲካ ውስጥ በደምም ይሁን በንፍጥ ተነክሮአል:: በፖለቲካ ንፁሕ ድርጊት የለም:: እንኳን የቀለጠ የትግል መንገድ ላይ ቀርቶ ደብረ ሊባኖስም ሳንክ አይጠፋም::

ግንቦት ልደታ ፳፻፲ ዓ.ም. ላይ የካቲት አስራ ሁለት ሆስፒታል ሴት ልጅ ተገላገልኩ:: ልጄን ስገላገል አጠገቤ የነበሩት እናቴ፣ ሮዛና አባቴ ነበሩ:: ሁሉም የመጡት መገላገሌን ሊያዩ ሳይሆን የምገላገለው ማንን እንደሚመስል ሊያጣሩ መሰለኝ:: እንዲህ በዝምታ መጠ'ርጠ'ር እንጀት አይበላም? ምጤ ሲጠናቀቅና የሕፃንዋን ድምፅ ስሰማ አለቀስኩ:: ሴት ብወልድም ዓላዛርን መምሰሏን ያወቅሁት ሮዛ መጥታ የላበው ግንባሬን

[110] ከአስቴር አወቀ ዘፈን

ስማ አይኖቿ ሰንባ አትረው፡ 'ስትበረቺ እንጫወታለን' ስትለኝ ነው። ሁሉም እየተያዩ ለመሳሳት ሞከሩ። ምናልባት እኔን በመጠራጠራቸው አፍረው ይሆናል። ድል ያደረኩ አልመሰለኝም። ልጅቷ እማማን ብትመስል ኖሮስ? ማተቤን ብትመስል ኖሮስ? ላልታመን ነበር ማለት ነው? የማልናገረውን፣ ሁሉም የማላውቃቸው እንግዳ ሰዎች መሰሉኝ። እስከዛሬ ያልተናገርኩትን ቂም ያዝኩባቸው።

የልጄን ስም *ምስክር* አልኳት። በአለም ላይ ከተፈጠሩት ውብ ነገሮች አንዷ ናት። በቀስም የምትመጠጥ መረቅ ነገር። ስትወለድ በቡናማ ሉጫ ፀጉር ተሸፍና ነበር። ፀጉሯን ብቻ ያየ ዝም ብሎ እሱን ያየ የዓላዛር ልጅ እንደሆነች ማወቅ ይችላል። ወልደሽ የተኛሽበት አልጋ ጋ ተጠግቶ ግንባርሽን እየዳበሰ የሚያባብል ባል ትፈልጊያለሽ? ሙዝ፣ ብርቱካን፣ ማንጎ፣ ሌላም ሌላም ፍራፍሬ እያቀያየረ ጠዋት ማታ የሚያመጣ ባል ትፈልጊያለሽ? ብዙ ሳይናገር ሳይፎክር ሳይጎርር 'ደህና እደሪልኝ' ብሎ የሚሄድስ? አብሮአሽ ተቀምጦ የተወለደለትን ሞሳ እያጫወተ ገንፎ የሚሻማሽ?

ሱሚ ነው ቴቢ።

የቀረኝ ምስክር ልጄ ናት እንጂ እኔ አይደለሁም። መታመኛ ካርዴን ተጫውቼበት ጨርሼአለሁ።

ደብዳቤ ያኔውኑ ለዓላዛር እንደተፃፈለት ተነገረኝ። 'አቤት! ይደሰታል' ተብሎ። ልባቸው የመደሰቱን ነገር ሳይጠረጥር አይቀርም። ዓላዛር መልስ አልፃፈም። ቢፅፍም ስለ ልጁ አንዲት ቃል አልወጣውም። ያዋረድኩትን ይረሳል? ቀኑ እየረዘመ ሲሄድ እናቱም እማማም እዝራም ሰላፈሩ፡

'አንቺ ለምን አልፃፍሽም ብሎ ይሆናል። በእግዚአብሄር ፃፊ' አሉኝና፣ እነሱ ባሉበት አስክሪፕቶ ተሰጥቶኝ እማ ፖስታ ቤት ከታው መልሱ ተጠበቀ። ደሞ ለማንም ሳልነገር ተደብቄ የስድስት ወር ልጄን ፎቶ አድርጌ ለመጨረሻ ፃፍኩለት። አመት አልፎ ለሌሎች በሚፅፈው ደብዳቤ እንኳን ስሜን አላነሳም። ለሶስት ወር ያህል 'የሶሻሊስት አገር ፖስታ ቤቶች ደካማ ናቸው' እያሉ ራሳቸውንም እየደለሉ ጠበቁት። እንደተፈጠርኩ ትዝ ያለው እንኩዋን አይመስለኝም። እናቴ የሆነውን ታዝባ ከንፈሮቿን እየመጠጠች፡

«ምን አደረግነው? ምን አደረግሽው? ለአንቺ ብቻ አይምሰልሽ ለሮዛ ሲፅፍ የአባቱን ስም እንኩዋን አያነሳም። የእኛማ የእኛ ነው። እናንተ ሁለታችሁ ከመጀመሪያው ስትሰሩ እህትና ወንድም ናችሁ። በልቤ ዐይን ይከላላቸው እል ነበር። ያላላችሁ ማነው? ስታምሩ የነበረው። አሁን ማን ያምናል እንዲህ ተራራቃችሁ ሲባል። አይታመንም። ለምን ቢባል ምኑ ያው ሰይጣን ነው እንጂ ሌላ ምንድነው። ደማችሁ ባይገናኝም አብራችሁ

አድጋችሁ፣ አብራችሁ በልታችሁና ጠጥታችሁ ተጫውታችሁ......አየሽ እንደ እህትና ወንድም ሆናችሁዋል:: ሌላ ሌላ ነገር ከማሰባችሁ በፊት ወንድምና እህት ሆናችሁዋል:: ወንድ አይገባውም:: ይልቁንስ ትምህር-ትሽን ጠበቅ አድርጊ»

ለአንድ አመት ያህል ልጄን ሳሳድግ ቆየሁና ትምህርቴን ለመከታተል 1972 መስከረም አዋሳ እርሻ ኮሌጅ ሄድኩ:: ሽርሚዳን ለዘላለም የምለያት ስለመሰለኝ ወደ ጓሮ ሄጄ ልጅ እያለን አዝራ የተከላቸው ዛፎች ስር ትንሽ አለቀስኩ:: ብዙ ሳይሆን ትንሽ:: ዓላዛር ናፈቀኝ:: አቅፈው መደንስ ፈለግሁ፣ የእሱ እጅ እንዲነካኝ ፈለግሁ፣ ቀሚሴን በቀስታ እንስቶ ሲትንቴን እንዲኮረኩረኝ ፈለግሁ፣ ጡቶቼን እንደ ምስክር እንዲጠባልኝ ፈለግሁ......ቂልነትና ፖለቲካ ከአፌ አስፈንጥሮ የደፋው እሱ መረቅ......

በጭንቀትና (በዚህች ዕድሜዬ ብዙ አሳልፌ የለ) በበቀል ሳይሆን አይቀርም (ምን ልበቀል እንደሆን አይገባኝም:: በቀል እንደሆነ ግን ይገባኛል) የአዋሳ ካምፓስ ዱርዬ ሆንኩ:: ከሊክቸረር ጀምሮ በፍሬሽ ማን አድርጎ፣ ገና ገበሬ ገበሬ በሚል ጎረምሳ በኩል፣ መንግሥት ሆቴል በግ ጥብሱን በልቶ በቁንጣን ሆዱን እስኪሚያሽ፣ አዲስ ከኢሕአፓ ወደ አብዮቱ የገባ፣ ደርግን አብሮኝ የሚያማ የኢሠፓኮ ወንዳወንድ ድረስ:: ትናንት የታገልኳቸውን የአብዮቱ ባለስልጣኖች እልጋ ላይ ለመጣል (በወረቀትና በእሲምባ ካልተቻለ) ገልቤ ትንሽዋ ከተማ ወጣሁ:: እጠጣለሁ እዳራለሁ:: ያ እንገቱ ላይ ጠባሳ ያለበትን ልጅ ሲነጋ ሳየው አብሬው የነበርኩ አይመስለኝም:: ያ ቦርጫም ሰውዬ ምናልባት ዕድሜው እርባ የሚሆን እምብርቱ ከፊት ለፊቱ የተንጠለጠለ፣ ብልቱ የጊኛ የመሰለ፣ ከሶስት ልጆቹ ትልቅዋ ኮተቤ መምህራን ማሰልጠኛ የምትማር እሱ ያወጣሁት ነው:: ያ የመንገዱን ጠርዝ በከዘራው እየደበደበ የሚያልፍ ዕውር ልጅ ጥርሱን ዓይቶ ማዕዱት ያልቻለ፣ በክፊል በሽግን የተሸፈነ አንድ ሁለት ቀን ሰሞኛል:: ወንዶች 'ቴብሽ' ቢለው ቢጠሩኝ ስለ ሰጠሁዋቸው፣ የመስጠት ተስፋ ስለምሰጣቸውም ነበር:: ያቺ ልጅ አፏን ወደ ወዳጆቿ ጆሮ ጠጋ አድርጋ የምታማው እኔን ነው:: ልደንስ እያልኩ የአባን mama mia ወይ የአርቺን sugar sugar honey honey ወይ የቢሊ ጄልን only the good die young (ይሄ ዘፈን ስለ ራሴ ሕይወት የሚናገር ይመስለኝ ነበር፤ በተለይ የወጣቱን) የሙንጎ ሬይን in the summer time (አዋሳ ሁልጊዜ በጋ አይደለ እንዴ?) እያንጎራጎርኩ ሌላ ትዝ ስለማይለኝ ወይም......በሰከረ ልቦና ከዓላዛር ጋር ብቻ ማድረግ የምመኘውን ከማንም ለፍዳዳ ጋር......

በዚህ የተተበተበ ሕይወቴ ወስጥ የዓላዛር እናት ሞታ እንኳዋን ቀብር ሳልደርስ ቀረሁ:: ሰበብ ሆኖም ወደ ብዙ ነገር እንደሚተረጎም ይገባኛል:: ዋናው የጋራ አካፋይ ለእኔ የሚለጠፍልኝ ስድብ *የዞረባት* ይሆናል:: በእርግጥ በመቅረቴ ቅር አላለኝም:: በመርሳት ሂደት ላይ ነበርኩ::

ውስጤ በብርና በወርቅ የተጻፈው የዓላዛር ስም በነዚህ ወንዶች ላጺስ እየተፋቀ የሚጠፋ መስለኝ ነበር:: (ወይስ የተከተበው በጠባሳ ነው?) አንዳንዴ ተመርጦ ሳይሆን የዘመን ጉድፍ የጠራውንም ተሸክሞ ይዞ ወደ ሚሄድበት ይጠረጋል:: ከወንዶች የማገኘው የማዘንጊያ ኪኒን በሚያማምሩ እናቶች ሞት አይረክስም:: የልግመት ስልጣንም ነው:: ከወር በሁዋላ ስፈር ስሄድ ይህቺን 'ምን ቢያደርጓት ይሻላል? ሰው ሲበላሽ ቅራሪ የለውም' 'ፖለቲካ ያጠዛት' ብቻ ነው ያሉኝ:: ቢራ አለው ሲቀል:: ውስኪ አለው ሲቀል፣ ብዙ ወዳጅ አላቸው እንኚህ ቢቀሉ:: ወጣት ከቀለለች ግን……

ምሁር ነን ባዮች ከእኔ ይዞታ ተነስተው የአገሬን ሴቶች ሁሉ ሰደቡ: 'ይህቺ ልጅ አሁን ምን ጎሎባት ነው እንዲህ የምትሆነው?' ይሉኛል (እያወጡኝም):: ሴቶችም እንደ እኔ እየዞሩ ከእኔ አብዝተው የሚደረጉ ቢሆኑ እንኳን 'ሴት አሰዳቢ' አሉኝ:: ታዲያ ያሙኝ ነበር……ታማኛለች.. ከውሽማ የተወለደች፣ ሶስት ጉልቻ ሕልምዋ……ዲፕሎማ ዲግሪ ፍፁም ሕልምዋ……ቢያንስ በትንሽ ጨኸቴ ከአንድ ወታደር ጭንቅላት ላይ የብረት ቆብ ሳልጥል አልቀርም……ከዓላዛር ጋር በፍቅር ስንቀጣጠል ታዚና ቤት እንሄድ ነበር:: የሴተኛ አዳሪዎች መውደቂያ ስትሪት ገርልስ የሚያርፉበት የነበረ……የአዋሳው ጊዜ ቤሰኛነቴ ሲያንገላታኝ፣ እነዚያ ዓይነት ሰዎች ከተኙበት ቦታ የሆነ ዓይነት ቫይረስ ሳይጋባብኝ አልቀረም ያልኩበት ጊዜ አለ:: ከብርድልብሱና ከአንሶላው ላይ ባለጌዎች የተውት ተባይ (ከዓላዛር ምን ይወጣል? መረቅ እንጂ) በሚታከከኝ ጨርቅ ውስጤ ገብቶ:: ማን ያውቃል?

ከዕለታት አንድ ቀን ፈተና አልቆ ልዝናና ብዬ ከአንዱ ወርቅነህ ከተባለ ባለስልጣን ጋር አደርኩ:: የወደድኩት ደርግ ውስጥ ሆኖ ደርግን ስለሚሰድብ ነው:: ስድብ ብቻ ሳይሆን ካሽም ነበረው:: ሁሉ ታዛዥ ነው:: ደብረዘይት አብረኸት ቤት ተዋውቀን፣ በመኪና ናዝሬት ውለንና አድረን አዋሳ ስንመለስ የሆነ ነው:: ጊዜውን አልረሳውም:: ሁለመናዬ በአልኮል ጦዞ በሆዴ ወድቄ ጀርባዬ ላይ ሲዳክር፣ ፊት ለፊቴ ያለው ትራስ ደብዛዛ ቀይ መሆኑን አየሁ:: የዓላዛር የድሮ ሸሚዝ ትዝ አለኝ:: ኮሌታው ትልቅ የሆነ እጀታውን እየጠቀለለ የሚለብሰው:: እሱ ክንድ ላይ ሆኜ ይሄ የሸሚዙ እጥፋት ሲጎራብጠኝ፣ ጎንበስ ብሎ ከንፈሮቼን በአፉ ሙሉ ሲይዛቸው:: ልክ አሁን እንደሆነ ሁሉ በዐይነሕሊናዬ አለፈ:: ከዚያ ቀና ሳልልም ትራሱን አፍጥጬ እያየሁ 'አትንካኝ!' ብዬ ጮህኩ:: ሰውዬው ግራ ገብቶት: 'ምን ሆንሽ? ደሞ' አለ በወሲብ ስራው የሚብለጨለጭ ግንባሩን እያከከ:: 'አትንካኝ! ተነስልኝ!' አልኩት:: እጅሪ በሙቅ እንደተለጠፈ ሁሉ ሊላቀቀኝ አልፈለገም:: ዞር ብዬ በድጋሚ እንደ ዕብድ ጮህኩበት:: በጥፊ ሊመታኝ እጁን አነሳ::

«እንዴ! እኔ ተባረኪ ሽርሙጣ አደረግሽኝ?» አልኩና ተፈራገጥኩበት:: ከተላቀቅን በሁዋላ አልጋ ዳር ቆሞ እፍረቱን እየሸፈነ:

«ታዲያ ምንድን ነሽ? እ እ እ እ አንቺን ያላደረገ እስኪ ይፈለግ:: ግመል ነው ያላደረገሽ:: ሽርሙጣ»

እዚሁ በዚሁ ሰደበኝ:: በሰከንድ ውስጥ እጅግ ተደበርኩ:: ቃላት ከሚገልፁት በላይ:: ከዚያን ቀን በሁዋላ የመንቀልቀል ፍላጎቴ ጠፋ:: እውስጤ የሆነ ጥቁር ቀዳዳ የተፈጠረ መሰለኝ:: መሃሉ የሚሽከረከር ብርድ ነው:: ለጥቂት ወራት ወንድ አስጠላኝ:: ሰዎች፣ እነዛ የዞረባቸው ሰዎች ብልግናዬን ማቆሜን ሲያዩ 'ወጠላት ነው' አሉኝ:: የእኛ ሰው:: ዘባራቂው ወገኔ:: ያደኩበትና ያሳደገኝ ነውና አላሳሰበኝም:: ባገራችን እንዲህ ነው: ሲባልጉ መከራ:: ሳይባልጉ መከራ:: ብልጠት ይበሉት ምን አይታወቅም::

•

ተስፋ መቁረጥ ጠቅላላ የእኔን ሰማይና መሬት የሞላት ግዙፍ ነገር ነበር:: ውስጤንም የዋጠ:: መጨረሻ አመት ላይ እዚሁ አዋላ የሚያስተምር ፋሲል ሞሲሳ ከተባለ ሰውዬ ጋር ተዋወቅሁ:: በደርግ ለሁለት አመታት ከርቸሌ ታስሮ የወጣ መሆኑን ሳውቅ አመንኩት:: ሌላ መተማመኛ መንገድ አልነበረኝም:: ስም ልስጠው በከበደኝ አይነት ብስጭትና ተስፋ መቁረጥ እየነደድኩ ስለሆነ እንዲያበርድልኝ ብዬ እሱን ተጠለልኩት:: እውስጤ ያለውን ቀዝቃዛ ቀዳዳ እንዲደፍንልኝ ስርስሩን ሄድኩ:: ቅን ጎልማሳ ነበር:: ሌሎች ወንዶችን ጠቅላላ ረስቼ ከፋሲል ጋር በስርአት መውጣት ጀመርኩ:: ከእሱ ጋር ካልሆንኩ ደብረዘይት ወጥቼ የሚጠጣ ይገኔ መኝታ ክፍሌ ገብቼ ለብቻዬ እስክራለሁ::

እንጀራ እናቴ ደሞ ታስሬ ከተፈታሁ በኋላ ከማንም የበለጠ ትንከባከበኛለች:: በእሷ አይነት ሰዎች ለመወደድ በደርግ መታሰር ሳይኖርብን አይቀርም::

አንድ ማታ በቢራ ሞቅ ብሎኝ መኝታ ክፍሌ ገብቼ የሆነ ልብወለድ እያነበብኩ ሳለሁ ክፍሌ ገባችና ማራኪ ልጃገረድ የሚያስመስላትን ፈገግታዋን ተቀብብታ፡

«የእኔ ቆንጆ ነይ እስኪ» ብላ ጀርባዬን እየደባበሰች በዋናው ቤትና በሬስቶራንቱ መሃል ያለ ባዶ ቦታ ወሰደችኝ::

«ምነው?» አልኳት ብቻችንን እንደሆንን

«ብዙ አትጠጪ»

«አልጠጣሁም:: ስስት ምናምን ነው፣ ደሞ ቴስት አለኝ ስኖ»

«ያ ነጭ ሽሚዝ ያደረገው ሰውዬ ይታይሻል?» በመስታወት መስኮት ጎንበስ ቀና እያለች::

«እና ምን ይጠበስ ለወታደር»

«ቅድም አይቶሽ የሚያወራው ስለአንቺ ነው፣ ሊገለኝ ነው ልተዋወቃት እያለ»

«እና? ፋሲል በዚህ ሲያልፍ ቢያየኝስ»

«ሌላ ነገር አይደለም፣ ተሻረኪው»

«ለምን?»

«ስልጣን አለው፣ እዛ ላይ ነው» እጆቿን ከአናቷ በላይ አንስታ

«ቢኖረው ምን አገባኝ!»

«አይ አንቺ»

«ምን? እያቃጠርሽኝ ነው ለእሱ?»

(ወርቅነህ ለተባለው የአየር ሃይል መኮንን ያቃጠረችኝም እሷ ናት)

«ምነው አንቺ:: እናትሽ ነኝ»

«ስታስር ብዙ ጥሩ ነገር አድርገሽልኛል:: አልረሳም:: አክስቴ ማተብም አድርጋለች (የማትወዳትን ሴትዮ ጠርቼ):: ደሃ ናት ያውም»

በኤርትራኛዋ የማይገባኝን ነገር ለፈለፈች::

አንዳንዴ የምትሰራው ነገር አፍ ያካፍታል:: ግን ዝም እላታለሁ:: ልክ የፖለቲካው ሆሆ ሲያልቅ የታዘብኩት ነገር ሌላው ዕውነት እየተዘነጋ ፖለቲካው መክረሩ ነው:: እንዴት ነው ፖለቲካው አልቆ ፖለቲካ የሚጀምረው? ነገረኛ መሬት እንዲህ መሰለኝ:: እያለቀ አያልቅም:: ዘንቦም አይረጥብም:: ሁሉ ደርግን ይሰድብና ቅዱስ ይመስላል:: ልክ አለ አይደለ ገነት ስንደርስ የሚቀርብልን ፈተና አንድና አንድ ይመስላል:: ሚካኤል ወይም የሆነ ተረኛ መልአክ ጥያቄ ይጠይቃል: 'አንቺ ሰርቀሻል?' 'አዎ' 'አመንዝረሻል?' 'አዎ' 'እንጀራ ልጅሽን አቃጥረሻል? ያውም ለምትጠይው ሰው?' 'አዎ' 'ደርግን ሰድበሻል? 'አዎ' 'አራተኛው ሖዎ ከሆነ ግድየለም የሌሎቹ መልስ አያሳስብም:: ገነት አንደኛ ፎቅ አስገባት'

ሺት!! በአገራችን ያኔ ሲነቃ እንዲህ ነው::

እዝራ ድሮ ይሄ ቀልድ ነበረው:

ከሽሮሜዳ ሰው ሞቶ ሲሄድ ገብሬል:

«የሽሮሜዳ ዜጋ ናት?» ብሎ ይጠይቃል

«አዎ»

«ስራ የፈታች:: ከገነት ገነት ትለውጣለች? ተመለሺ በላት እዛው ሽሮሜዳ:: እዚህ ቦታ የለንም»

መስሎታል:: እግዜር እንደሰራት ያለች መስሎታል:: የት ነበር? ይሄን ሁሉ ዘመን የት ነበር?

ወደ ፋሲል ቀላል ትህትና ተጠጋሁ:: በመጠኑ የተረጋጋ ሕይወት ጀመርኩ:: የኮሌጅ የመጨረሻዬ አምስት ወራት ሰላምና ምቾት ነበረባቸው::

[illegible]

ተርቦቻችን በመከ፣ ተቁር ፈር ደምቁሉ።

[illegible]

## መዋዕለ አዋሳ



ተርፎቻችን በመኪ. ተቀ.ር ፊር ይሞላሉ·

......ከአዋሳ እርሻ ኮሌጅ በዲፕሎማ ከተመረቅሁ በሁዋላ እዛው ከተማ 75 አመተምሕረት ላይ በማውቀው ሰው እርዳታ ግብርና ሚኒስቴር ተቀጠርኩ:: 'አዲስአባ እንመድብሽ' ቢሉኝም አልሄድም ነበር:: አዲስአባን ጠላሁዋት:: በ*ቦዲ ሚሞሪ* (የገላ ትውስታ ወይም የገላ ትዝታ) ይመስለኛል:: ቦዲ ሚሞሪ (Body Memory) በአንጎል ውስጥ ብቻ ሳይሆን በሌላ የአካል ክፍል ውስጥም (በጡንቻ፣ በልፋጭ፣ በሞራ፣ በጉበት፣ በሳንባ ወዘተ) ትውስታ ሲከማች ማለት ነው:: የፖለቲካ ጉዳዬ ከሽሮሚዳው ዓላዛር ጋር ተደርቦ አዲስአባን ስጠላ ትንሽ ልክ አይደለም:: ባቡር ጣቢያ ምን አደረገኝ? በቅሎ ቤትና መካኒሳ ምን አደረጉኝ? እናቴ ለምን አዲስአባ እንደማልመጣ ስትጠይቀኝ '*እማማ ሙቾ መንግስት* በእጣ ልመድብ እያለ አዋሳ ደረሰኝ፤ ገንዘብ ከፍዬ እንኳን የሚለውጠኝ አላገኘሁም:: ምስክር ካስቸገረችሽ በደንብ ስቋቋም እወስዳታለሁ' አልኳት:: እማማ 'ኸረ ለልጅቷ አይደለም፤ በሰራተኛ ከምታድግ ከእኔ ጋ ትሆናለች:: ይሄን ደርግ የተባለ በጥባጭ ማን ላከብን እመቤቴ' ምናምን ምናምን:: በልቤ *የፈለግሽውን በይ* እላለሁ:: የአገራችን ምስክር መሐላ ነው:: እንዋሸና እንምላለን:: የማንምልበት የለም:: ልብ ያልኩት እንዲህ ስገባበት ነው:: በእግዚአብሄር እንምላለን፣ በሃይሥላሤ እንምላለን (ከንጉሡነገሥቱ የሚቀረው ጢማቸው ነው፣ እና ቀን ጠብቀንም ከተመቸን በጢማቸውም እንምላለን)፣ በመላዕክት፣ በአባት፣ በእናት፣ በምንወደው ሰው፣ በደርጉ፣ በልባችን፣ በሳንባችን፣ በባላችንና በሚስታችን እንምላለን:: በዚህ በዚህ ተለማምጄ ምናልባት በፋሲል እምላለሁ በፋሲል ፔርሙስም እምላለሁ::

ወደ አዋሳ ለመሄድ አንዳንድ እቃዎቼን በሻንጣ ስከት ያገኘሁዋቸውን የማርክሲስት መጽሐፍት፣ሊማድቤት... እሳት ወረወርኩ:: እሸር ቤት ሙላት የሰጠኝን ያማረኝ ቅል እንዳትሰበርብኝ በጥንቃቄ በወረቀትና በላስቲክ ጠቅልዬ በልብሶቼ መሃል ወሸቅሁዋት:: ድሮ አበባና ተክሎችን ከሰበሰብኩባቸው ሶስት አልበሞቼ አንዱን ብቻ አገኘሁ:: ታስሬ ከተወሰድኩ በሁዋላ በበነጋታው ፈታሾች እኔን የሚወነጅሉበት ፀረአብዮት ወረቀት ሊያገኙ ሲበረብሩ እንደነበር ተነግሮኛል:: የቀሩትን በርባሪዎቹ እንደወሰዱአቸው አውቃለሁ:: ቢያበሳጭም ምን ይደረጋል? ቀኑ ሲያልፍ 'ምን አውቃለሁ የሆነ ወረቀት ሰብስበው ሂዱ' አለች እማማ:: አላለፈም:: በልጅነቴ የለፋሁበት ሲጠፋ ሐዘን አይገባኝም አሉ? ሐዘን ከለ

የአልበሞቼ ትዝታ እለ ማለት ነው:: ሁሉም አልበሞቼ ገና እኔ ውስጥ አሉ:: ትንሽ ተቀምጬ ከትውስታዬ ሊጠፉ የጀመሩ አትክልቶችን እየገለጥኩ አየሁ:: የመፅሐፉ ጠረን መስከረም ወር ውስጥ እንደሚያጋጥም የእንጠጦ ሽለቆ ነው:: መጨረሻው ገፅ ላይ አንድ ጠጅ ሳር አገኘሁ:: ገና በጣቴ ስነካው ፈራረሰ:: መደርደሪያዬ ላይ ደሞ ምናልባት ከሰባት አመታት በፊት ዓላዛር ለልደት ቀኔ የሰጠኝን አንድ ዳልሚሽያን የውሻ አሻንጉሊት አገኘሁ:: ወደ ግድግዳ ገፋ ተደርጋለች:: አቧራ ለብሳለች:: በአዲስነቷ በጥቁር ነጠብጣቦች የተሸፈነች በረዶ ነጭ ነበረች:: አይኖቿ ጥቁር ሆነው ዙሪያቸውን አረንጓዴ ናቸው:: አፍንጫዋ ጥቁር ነው:: ጅራተ ጎዳ ናት:: አልጋዬ ላይ በጀርባዬ ስሆን ሳታቋርጥ ታየኝ ነበር:: አስተያየቷ ያባባል:: ቆሻሻዋን አራግፌ ሻንጣዬ ውስጥ ከተትኳት::

አቶ አባይ 'አዋሳ አደርሳታለሁ' ስላሉ ሳሎን ተቀምጬ እሳቸውን ስጠብቅ ቆይቼ፣ ስልችቶኝ መኝታ ቤት ስገባ፣ እማማ ሻንጣዬን ስትበረብር አገኘሁዋት:: በቀኝ እጅዋ ዳልሚሽያን አሻንጉሊቷን ይዛለች:: ቀና ብላ በማዘን አየችኝና ምንም ሳትናገር እነበረችበት አመቻችታ አስቀመጠቻት:: አፍሬ ወደ ሳሎን ተመለስኩ:: አለሁበት መጥታ ምንም ነገር እንዳልሆነ:

«አባይ የት ጠፋ? እያረጀ ሲሄድ ቀጠሮ መርሳት ጀመረ?» አለች:: አልመለስኩላትም::

አጠገቧ እግሮቿ ስር በጉዞዬ አውቶቡስ ውስጥ የምበላቸው ብርቱካኖችና ሙዞች ተደጋግፈው ተቀምጠዋል:: ብርቱካኑ ቅጠልያ ቀለሙ አልተወውም:: ሎሚ አስተኔ ቆምጣጣ ሳይሆን አይቀርም:: ፍራፍሬ ኮርፖሬሽን በየመንገዱ ድንኩዋን ተክሎ ኪሎውን በሁለት ብር ካምሳ ከሚሸጠው እማማ ገዝታ ነው:: ከነዚህ ጎን ደሞ ገና አረንጓዴነቱ ያለቀቀው ጥሬ ሙዝ አለ:: እማማ ከመስሪያቤቷ ስትወጣ የስራ ጓደኛዋ 'ልጅሽን ደህና ግቢ በይልኝ' ብላ የላከችልኝ ነው:: ከሴትዮዋ አልቀራረብም:: ሙዞቹ ጥሬ ከመሆናቸው የተነሳ እያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ጠንካራ ሰረሰሮች አሉዋቸው:: ስድስቱም አንድ እንጓ ላይ እንደ ደራጎን ጥርስ ተደርድረዋል:: እማማ የላስቲክ ቀረጢቱን በእግሯ እየነካካች ታስባለች:: ስለ እኔ ጉዞና ሰፈር ስለመቀየር ይሁን ስለ አባይ እንጃ:: እኔ መሄዴ ነው:: እማማ ብቻዋን መኖር የምትችል አይመስለኝም:: ከአባይ ጋር ለምን እንደማይጋቡ አይገባኝም:: አሻንጉሊቴን ባታይብኝ ኖሮ ትዳር ስለ መመሥረት እጠይቃት ነበር:: ግን:

'እንቺስ አሻንጉሊት ከመሰብሰብ ዓላዛርን ጠበቅ አታደርጊም ነበር' ብትለኝስ ብዬ ተውኩት:: በየቀኑ በደም ስሬ በልቦናዬ ደካማ የሚያደርገኝን ነገር የምሰበስብ ይመስለኛል::

«ምናለበት አዲስአባ ብትሆኚ ኖሮ፣ እኔም ብቻዬን አንቺም ብቻሽን» አለች እማማ

ልጄን ስሜ ስሜ ስሜ ስሜ ሄድኩ። አባይ ለእኔም ለእማማም መለያየታችንን አክርረን እንዳናየው ሞራል ሲሰጡን በልቤ አልገባም። እዛው እተማርኩበት ከተማ በመመደቤ ግን ከአስተማሪዬና ከወዳጄ ከፋሲል ጋር የነበረኝ ግኑኝነት ጠበቀ። ከተማዋም ለእኔ እንግዳ አልነበረችም። ቡናና ቢራ የጠጣሁባቸው ቦታዎች አሉ። የባለኩባቸው ቦታዎች አሉ። ያባለጉኝ ጥቂት ሰዎች አሉ። ሁለመናዬን ግን ያላዩ። በአንድ ጎኔ ብቻ የሚያውቁኝ። በሆነ መልክ ለአዋሳም አዲስ ነኝ።

«ያ ሰው በጣም ያይሻል» ሲለኝ ፋሲል

«ውሃቸውን አጥርተው ያልጠጡት ሴት ቂጥ ላይ አፍጠው ስለሚውሉ ነው» እለዋለሁ

«አይ የአንቺ ተረብ» ይላል

የማውቃትና የማላውቃት አዋሳ። የማታውቀኝ ደሞ ግን የምታውቀኝ አዋሳ። ማምለጥ ካልቻልኩ ብዋሽ ምን አለበት?

•

•

•

ጥሩ ሰው ቢሆንም፣ የፋሲል መሠረተ ጠባዩ ያሰለቻል። አዎ...... የምወደው ሰው ያሰለቸኛል። ተራቀቅሁ ሲል፣ ቁም ነገር ሲጫወት የሚያወራው የፖለቲካ ሻሜት[111] ነው። ትዕንግርትና ታሪክ አመጣሁ ብሎ ማውራት ሲጀምር በልቤ 'ባትናገረው' እላለሁ። የፋሲል ትንግርት ወንድነቱ ነው። የእግሩ መሃል መድፍ ነው። ያገናኘን ከአንድ ብሄረሰብ መመንጨታችንም ነው። ***ደርግ ያሰረው***። ይሄም ትንግርተኛ ብሄረሰብ ነው። በመወለድ ላይ ያለ አዲስ ጎሳ ነው።

«እኔ እንደዛ ያደረገኝን ደርግ፣ እንደዛ ያሰቃየኝን መንግሥት ይቅር አልለውም» ይለኛል

ለሁለት አመታት ከርቸሌ መታሰሩን የፈለገውን አይነት ትችት መሰንዘሪያ ዋስትና አድርጎታል። አልፈርድርበትም። ከቀለሜዋ ሕይወቱ አላቆ መንግስት ግልበጣ ያሳተፈውን ድርጅት ለምን ይረሳል? በገጠር ሕይወቱ ኩራዝ መብራት ስር ከሚያደርገው ደባሪ ቀለም ሽምደዳ ተላቆ በአድሬናሊን የተሞላች የወጣትነቱን ጊዜ ሊዘነጋ ነው? የሕይወቱ ዋና

[111] የትም የማይደርስ ሐሜት

ጀብድ ነው:: ድብብቆሽ ጨዋታው፣ አደጋውን ፈልስፎ የፈለሰፉትን አደጋ ማምለጥ አይጥምም?

ሁሉ እንደዛ ይመስለኛል አንዳንዴ ሳስበው:: አማንን ሩካቤ ስጋ እምቢ ብለውም ባማረ መልክ በፖለቲካ ተራክበናል:: እኔ እንደማልረሳው እሱም አይረሳኝም:: በማንም እምባገነንና ዘባራቂ አፍ 'የአገር አንድነት ተፃረራችሁ' ተብሎ መተ'ረብና መሳደድ ከዚህ ሚስጢራዊ ውበት ጋር ሲነፃፀር ባዶ ነው:: ብዙው ወጣት ከጢብ ጢብ ጨዋታውና በሽሮና በክክ ከጦዘ አሰልቺ ኑሮው ተላቆ ትልቅ ተዋናይ ሆኖ ቲያትር የሰራበት ነው:: ቢፈርስም ባይፈርስም የዚህ ትዕይንት አካል መሆን ራሱ ናፍቆት አለው:: ይሄ የሚጣፍጥ ስሜቴ ነቃፊ እንዳያመጣ ደርግ እስከ ዘላለም መጠላት አለበት:: ጁንታው ከአካሉ እስከ እምነቱ መሽሚጠጥ አለበት:: ከመልኩ እስከ ቋንቋው መሰደብ አለበት:: ካልሆነ ሚስጢራዊው ደስታዬ ይባክናል:: ኮሚኒስት ነኝ ብልም፣ ደሃ ገበሬ ሲያስገርፉ ከነበሩ ባላምባራስ ጋር አብሬ መንግስቱ ለምቦጭ ላይ ማላገጥ አለብኝ:: የፋቢሌ ስሜት መቶ በመቶ ባይሆንም ይገባኛል:: ለምን አማን ይናፍቀኛል? ነፍሳችን በዚህ በዚህ ቢያያዝ አይደለ? 'በወጣትነትሽ ምን ሰራሽ?' ቢባል የሚነገር ነው:: ሊያሽማቅቁን የሚታትሩት የተሰራ ያሌላቸው ምናምኖች ናቸው፡ ያኔ 'ሰክረን ስንረብሽ' እንደሚሉ ጉርምስናቸውን እንደሚያስታውሱ ነልማሳ ብኩኖች:: የሆኑ ዓላዛርእውያን:: 'አርፈን እንማር' የሚሉ ፈሪዎችና ሕልም የለሾች::

•

•

•

እንግዲህ ሲመስለኝ ነው:: በትክክል አብዮተኛ አይደለሁም:: ዓላዛር ውስጥ ሱሪውን ሲያወልቅ አስባለሁ:: ግን አፌን ከፍቼ አንድም ቀን 'ዓላዛርዬ ውስጥ ሱሪህን ስታወልቅ ልይህ' አላልኩትም:: ዓላዛር ከንፈረ ሎሚ ነው:: ግን 'ዓላዛርዬ አፍህን ልምጠጠው ሎሚ ሎሚ ይለኛል' አላልኩትም:: ዓላዛር ማጅራቱ ያምራል ዞማው የተኛበት:: ሲያንቀላፋ ነካክቼ ሳምኩለት እንጂ 'የማጅራትህን ዞማ ሳየው ሁለመናዬን ይበላኛል' አላልኩትም:: አብዮተኛ አይደለሁም:: መናፍቅ ነኝ:: ከጀርባዬ ተኝቼ እሱ እያወራኝ ከሆነ አመት በሁዋላ ቬሎ ለብሼ፣ አምስት ስድስት ሚዜ ተከትሉኝ፣ ዙሪያዬን አደይና ዕጊሬዳ እየዘነበ ሚስቱ ሆኜ ሲስመኝ፣ በዚህ የቀን ሕልም ደስታ እንደተመዘመዝኩ መቼ ነገርኩት? 15 ልጆች ስወልድለት ሁሉም እሱን የመሰሉ፣ ከነዚህም ከፊሎቹ በምርቃት ስለተፀነሱ፣ ነጫጭ ክንፎች አብቅለው የአዲስአባን ሰማይ በበረራ የሚያካልሉ:: አንድዋ ልጁ ስሟ ምስራቅ ነው:: እንዲህ ማሰቤን መቼ ነገርኩት? እንዲህም አስቤ ዕንባ ዕንባ እንዳለኝ መች አወራሁት? በትክክል አብዮተኛ አይደለሁም:: ደርግን ለመስደብ በደፈርኩበት አፌ ማፍቀሬን፣

ፍቅሬን፣ ሂደቱን እና ሕልሜን ደፍሬ አልተናገርኩም:: ምክንያቱም እሱን የሚያወድስ ድርጅት አላዘጋጀኝም:: ደርግን ለመታገል አጄቢ አለኝ:: ዓላዛርን ለማሞገስ ግን ብቻዬን ነኝ:: ይሄን እርቀት ዛሬ በስሜቴ ስለካው፣ በእኩለ ሌሊት ነቅቼ ሽንቴን እየሸናሁ በልቤ ሳጸምጠው፣ እየበላሁ እየጠጣሁ ሳስበው እንዴት ሆነ? ብዬ ራሴን ስጠይቅ:

**ምንም ምንም አጥርቼ መመለስ አልቻልኩም እማማ::**

**ምንም ምንም ደፍሬ መመለስ አልቻልኩም አባባ::**

•

•

•

መቃጥን ላይ አጎነብሰው፣ ጥጋብን ወደ ከተማዋ ሊያመጡ አሳ አጥማጆች የቱም እንቅልፍ ይዘዋል:: በዘመናት ውሃ ያልታጠበ የላባ ካባውን የለበሰ መረቡ አሞራ ከፈላሚንጎዎች አሳ ይሻማል:: ከሽመላዎች አሳ ይሻማል:: ቦታው ከትንሽ ትርምስ በሁዋላ ይፀዳል:: ሃይቁ እንደ ሞላ ልጅ ቆዳ ይለሰልሳል:: ይሄን ሁሉ እንደ ትልቅ እውቀት አያለሁ:: ሚስጢር እንደሆነ ሁሉ ግን ለማንም አልነግርም:: ነፃነትን የተናገረላት ብቻ ሳይሆን፣ በልቡ የተመኛትም ጠፊ ነው እንዲል ዘመኑ::

•

•

•

ፋሲል በቀን ውስጥ ሁለት ሶስቴ ስለመኪናና ስለ ንፁሕ ቤት ሳያወራ አይቀርም:: ቸንጥላ በሚያስንቅ የተንቸረገገ አፍሮው ውስጥ ነፋስ ሲያልፍ ሁሉ ይሄን ንግግር የሰማሁት ይመስለኛል: 'ዛሬ መኪናዬን ቴቢሽ ናት የምትነዳው': ብሎ ማውራቱ ያዝናናዋል:: እና ለሕዝብ የታገለበት ስሜቱ ከዚህ አማርኛው ጋ አልጣጣም ይለኛል:: ፋሲል በእምነቱና በቁስ ፍላጎቱ ሞቅ እያለ ሲመጣብኝ ሁሉን የሚያዛምድ ነገር ማሰቤ አልቀረም.......

አብዮተኛው ውስጥ ብርዝዋ አለ::

ብርዝዋው ውስጥ ፊውዳል አለ

ፊውዳሉ ውስጥ ገበሬ አለ

ገበሬው ውስጥ እረኛ አለ

እረኛው ውስጥ ላም አለ

ላሟ ውስጥ ሳር አለ

ሳሩ ውስጥ አፈር አለ


ሊሊ.ታችን ተቆፍሮ ቢ.ታይ ሁላችንም የምናልመው በእርግጥ አፈር ነው:: ታላቅ የሚመስለው፣ የረቀቀ የመሰለው ዕንስ ሃሳብ ሁሉ በምላስ ሙጫ የቆመ የአረፋ እንክብል ነው::

•

•

•

ክረምቱ ያምራል:: የእውነት:: ውስጤ ነው ቅር የሚለው:: ውጩ እርጥብ ቢ.ሆንም ውስጤ ደረቅ ነው:: ይታወቀኛል:: ፈጣን ዝናብ ጥሎ ከቤቴ ደጃፍ እስከ አጥሩ በር በአንድ ጊዜ ጭቃ ሆኗል:: ድንጋይ እንዲ.ያስነጥፉበት ቀበሌውን ብንነግርም ልብ ያለን የለም:: ደሞ በዚ.ህ እርጥብ ቀን ከጎረቤቶቻችን ከጎረቤቶቻችን ጎረቤቶች እንዲሀም እያለ ከይርጋለም ሊ.ሆን ይችላል ዶሮዎች እዛ መጥተው ተሰብስበዋል:: የሆነ ነገር ይለቅማሉ:: ቤት ስራ የሚረዱኝን አሮጊት ዶሮዎቹን ምን እንደሰበሰባቸው ስጠይቃቸው ለቡና ቁርስ የገዙት ሽምብራ ግማሹ እዛ ጭቃ ውስጥ እንደፈሰሰባቸው ነገሩኝ:: በውሃ ተነክሮና ለስልሶ የተቀቀለ የሽምብራ ንፍሮ እወዳለሁ:: ፋሲ.ልም እንደ እኔ ነው:: ፋሲል እንደውም ያደገው በሽምብራ፣ በወንዝ ውሃና በአየር ነው:: ቢሆንም እናትን አይረግሙም:: ብረግማቸው ደስ ይለኛል: *ያፍስዎት የሚያፌስ*:: ሂሂሂ:: ዶሮዎቹን ላባርር ስጠጋቸው መጥማጥ እንደመጣባቸው ሁሉ እያሽካኩ ግራና ቀኝ ተበታተኑ:: አሮጊቷ እንዳሉኝ መዓት የፈሰሰ ሽንብራ አለ:: ለመጀመሪያ ጊዜ የዶሮ እግር ምን እንደሚመስል ጭቃ ውስጥ ታትሞ አየሁ:: የሚያምነኝ ግን የለም:: ሳየው ብኖርም ልብ ያልኩት ግን አሁን ነው:: አጠገባችን ሆኖ የምንስተው ስንት ነገር አለ? መዓት ቢሆኑም የዶሮ እግሮች መሆናቸው አልጠፋኝም:: እንደገና ትዝ ያለኝ ፀሐይ ጀርባዬ ላይ የረጨችው ሊ.ጥ ነው:: ለምን ይሄ ምስል ያን አስታወሰኝ? አጋጣሚ ነው? ወይስ የሕይወቴ ዜማ ያልጣለው አንድ ያልተለወጠ ኖታ ነው?



ሃያ ሰላሳ የሚሆኑ ማህተሞች የእግር መንገዱ ጭቃ ላይ ለብቻቸውም ተደራርበውም ተስለዋል:: የተጨፈላለቁ ቢ.ጫ፣ ጥቁርና

ነጫጭ ሽንብራዎች ኮከብ መስለው ፈሰዋል:: መኖር የሚከብደው ከሰው ጋር ብቻ አይደለም ከዶሮም ጋር ነው:: አሁን ከጎረቤቶቼ መጣላት ብፈልግ በዶሮአችሁን ሰብስቡ ሰበብ አምባጓሮ መቀስቀስ እችላለሁ:: ዋናው እውነት መሆኑ አይደለም:: ደፍሮ የመዘባረቅ ነው:: ፋቢል ጎበዝ ሆኖ የተማረው ከሽንብራ ተቀያይሞ ነው:: *መማር እወዳለሁ* ቢልም የተማረው በትክክል ሽምብራ በዞረበት ላይዞር ነው:: ዶሮ አራት የእግር ጣቶች ወይም ጥፍሮች እንዳላት አላውቅም ነበር:: ቀዳሚ ማመሳከሪያ ዕውቀት እንዳለኝና እንደተሳሳትኩ ሁሉ ደጋግሜ ቆጠርኩ:: ይሄን ማወቅ ዕውቀት ነው:: ዶሮ ወጥ ከእማማ ጋር ሰርቼአለሁ:: ላባ በፈላ ውሃ ገፍፌአለሁ:: ብልት በል'ቼአለሁ:: ምድጃ ዳር ለስአታት ተጎልቼ ሽንኩርት አቁላልቼአለሁ:: ዶሮ አራት ጣት/ጥፍር እንዳላት አላውቅም:: (ከሰማይ በታች ሁሉ ነገር እየቀረቡ ሲያዩት አዲስ ነው:: ልመርምርህ ካሉት መቆሚያ የለውም:: ያየነውን ነገር ያወቅነው ይመስለናል:: የባሌን ፊት አላውቀውም:: ዳብሼዋለሁ፣ ስሜዋለሁ፣ ጠዋት ማታ አይቼዋለሁ፣ በጢምና ያለጢም አይቼዋለሁ:: የፋቢል ፊት በየቀኑ ይለዋወጣል:: የእማማንም አላውቀውም:: ለመሆኑ ፀጉሯ ቁጥሩ እንዳለፈው አመት ነው? ልጄንም አላውቃትም:: በሕልምዋ ትናንት ምን አየች? ማለት ሰዎች ሁሉ በሆነ ስልት ደንቆሮ ናቸው:: ሰው ስለራሱም ደንቆሮ ነው:: እንኩዋን በአመት አራት አምስቴ የሰራሁዋትን ዶሮ የሚያረባትም ገበሬ አያውቃትም) ለምን አምስት ጣቶች የላቸውም? የዶሮዎቹ የጣቶቻቸው ጂኦሜትሪ መሰጠኝ:: ለምን ጣቶቻቸው በተርታ ተሰልፈው አልተፈጠሩም? ለምን ጣቶቻቸው ጫፋቸው ሾል ሾል ያለ ሆነ? መሾል ግዴታቸው ነው? ሶስቱ ወደ ፊት ሲዘረጉ አንዱ ወደ ሁዋላ ለምን አፈነገጠ? ሲጀመር ከተዋሃዱበት ማዕከል በተለያየ አቅጣጫ የተበታተኑ መሰለኝ:: ማዕከሉ መሰብሰቢያ ሳይሆን መበተኛ ነው:: *ታዲያ ስለ ዶሮ አውቃለሁ* ማለት እችላለሁ? ሳስበው አለም እንደዛ ነው:: አለም ሲተራመስ የማየው በትንሹ በታመነበት ዕውነት ነው:: አሮጊቷ 'ግማሹን ሽምብራ ደፋሁት' ሲሉ ምን ያህል ዕውነታቸውን ነው? የዕውነት ግማሽ ነው? እንዴት ሳላመነታ ላምናቸው እችላለሁ?

***ዝናብና አብሮ አደጎቼ:*** ቀና ብዬ እየሁ:: [redacted] ደግሞ ሊመጣ ያስባል:: ማሰብ ይችላል ዝናብ? እኔ ነኝ የማስብለት? ትዝ ትለኛለች ማሜ እንደዛ ማለት ትወድ ነበር:: *አንቺ ማሰብ ማሰብ ማሰብ አይደብርም?* ማሜ ቅዳሜ ከሰአት ከግርማቸው ጋር ላለባት ቀጠሮ ጠዋት ላይ ፀጉሯን ትታጠባለች:: የሆነች የጎረቤት ጩጩ ልጅ ነበረች የምታስታጥባት:: ውሃ እየፈሰሰባት ማውራት እንኩዋን አታቆምም::

ሳውራበት ባክሽ የምዋኝ መሰለሽ ምናምን ትለኛለች:: ማሚ የሃበሻ እስላም አግብታ ጂዳ እንደሄደች ሰማሁ:: ሰውዬው የሰፈር ሰው ነው ቢሉኝም አላወቅሁትም:: እንዴት ነው ማሚ ወግ አጥባቂ አለም ውስጥ የምትኖረው? በእሷ ሲገርመኝ የሰዎች ቅናት:: ማሚ ማር......ማሚ የዋህ......ማሚ ደስተኛ......ማሚ ለስላሳ......ማሚ ብዙ ነገር ነበረች:: ግን አያስቀናም:: የጓጎለ ሸሮ አንተርሶ ደሃ ወገኔ ቢያደርገኝ ይሻለኛል ወደ ማልተነፍስበት ገንዘባም አገር ከመሰደድ:: በልቼ ማደር ከቻልኩ ለገላ ለምቾት አገሬን አልተውም:: ግድ የለም፣ አመድ ላይ ተኝቼ አመድ የመሰለ ልጅ እወልዳለሁ:: ግድ የለም ደርግ እያስረ ይፍታኝ:: እየፈታ ይስረኝ:: ሰይፍ መዝገቤ ፋሺሽቶችን ተዋግቼ ነፃነቴን እነጥቃለሁ እንጂ ወደ ሚንቀኝ አላቀናም:: ግን ያቺ እህቴ በዚህ የተሸወደችው ብትመረር አይደል? ግን ምን አስመረራት? በምናውቀው ዳቦ ውስጥ የማናውቀው ልብ አለ:: አሁን ሲያዩኝ 'እንዲህ' ነኝ፣ ገልጠው ቢያዩኝ 'እንዲያ' ነኝ:: ዛሬን የምኖራት እየተገላበጥኩ ነው: በእንዲህ በእንዲያ::

ፀናዕል ተክለማርያም ዩኬ ገባች አሉ:: ፒያኖ ጨዋታዋ ትዝ ይለኛል:: ቤቷ ላያት ስሄድ ከሳሎናቸው መስኮት ቤቶቨን ምናምን ይቀበለኛል:: ልጫወት እንደመጣሁ ብታውቅም፣ ዞር ብላም ሳታየኝ የጀመረችውን ትጨርሳለች:: ከሁዋላዋ ተቀምጬ እጠብቃታለሁ:: አንገቷ የሚያስቀና እርዝመት ነበረው:: ቀይ ስለነበረች እዛ ላይ ያለው የወርቅ ሃብል ስትነቃነቅ ካልሆነ አይታይም:: ለምን ዓላዛርን እየፈለገችው አልፈለጋትም? ለምን ከእኔ አዳረቀው? ፍቅር በምናየው መረጃ የማይደርስባት ሞላጫ ነገር ናት:: ፍቅርም በልቧ ሚስጢር አላት:: የምር:: በእንዲያ በእንዲህ::

ወለተመስቀል ፍፁም አለማያ ናት:: አግሮ ኢኮኖሚክስ እያጠናች ነው:: የምስክርን ፀጉር ስጎነጉን የወለተ መስቀል ዞማ ትዝ ይለኛል:: ስለ እሷ ውብ ዞማ እዚህ ጽዋሳ እንዳለች ሁሉ የፀጉር ነገር ሲወራ ስሟን አነሳለሁ:: ሰፈር በሄደች ቁጥር እማማን ታያለች:: እማማን ባየች ቁጥር ቴቢዬ እንደናፈቀችኝ ትላለች:: እኳ እንደዛ ነው:: ወልዬንም የማይናፍቃት የለም:: ወሬውን እማማ ታመጣልኛለች::

እኔ እያለሁም የለሁም:: እነዚህን ብቻ ሳይሆን በየቦታው የተበተኑ የሰፈር ልጆችን ሳልጠጋቸው አስባቸዋለሁ:: ሳስባቸው ግን በልጅነት ቀለም ነው:: ሰፈር ስሄድ ድምጼን አጥፍቼ በጨለማ ገብቼ በጨለማ ወደ አዋሳ እመለሳለሁ:: ወላጆቻቸውን እንኳን አልጠይቅም:: የተለወጠ ነገር ፈርቼአለሁ:: ስለእነሱ ሳወራ ስለጥበት ሳወራ ነው:: ተነጣጥለን እንዲህ ስንኖር ኖርን ይባላል? እንዲህ ስሜቴን የሚነዳው ሾፌር ምንድነው? እንኩዋን ከአያቶቻችን የታሪክ ቡሉኮ ወስጄ ልከናነብ ይቅርና፣ የሰፈሬም ዳንቴል ተበጣጥሷል:: አንድ እጄ ጀርመን፣ አንዱ እንግሊዝ፣ አንድ

እግሬ አዋሳ፣ ሌላው እግሬ ሳውዲ፣ ፀጉሯ አለማያ:: ሙሉ ገላ አይደለሁም:: ሰው የሚከብደው ከሌላ ቢያንስ አብሮት ከኖረ ሰው ጋር ሲመዘን ነው:: የቀረኝ ርዕዮተ አለም ያለፈውን ማስታወስ ብቻ ነው:: ቀላል ሚዛን ነኝ:: በፈቃዴ ይሁን በታሪክ አጋጣሚ (የቱ እንደሆነ ይዞርብኛል) ካሳደገኝ ደም ስር ተለያይቼአለሁ::

•

•

•

ሙላት የሰጠኝን ቅል ሳሎን መደርደሪያ ላይ አስቀመጥኳት:: ቆይቶ ቆይቶ ፋሲል ጠየቀኝ:

«ያንን ያገኘሽው እዚህ አዋሳ ነው?»

ስለ ሙላት ነገርኩት:: ልጁ ዓላዛርን እንደሚያውቀው ነገርኩት:: ዝርዝር ምናምን አላነሳሁም:: የድርጅታችን ሰው እንደነበርና እንክብካቤ እንዳደረገልኝ አወራሁት:: ማታ ነበር:: ሶፋ ላይ ተደጋግፈን ተቀምጠናል:: የበላንበት እቃ እዛ እዛ ነው:: ሆዴ ስለሞላ መነሳት አልፈለኩም:: ጠንካራ የቅቅል ጠረን ከበላንበት ትሪ ላይ ይሰማኛል:: አጥንቶች በቅባት የሚፈልቀው ትሪ ላይ እዛ እዛ ወዳድቀዋል:: ፋሲል አጥንት አይቆረጥምም:: ከአጥንቶቹ ሁለቱ ወገባቸው ተሰብሮ መቅኒያቸው ወጥቶ ድንክ ዋሽንቶች መስለዋል:: እነዛ የእኔ አጥንቶች ናቸው::

«እንዴት አላውቀውም ሙላትን?» አለኝ

ብዙ ወደ ደርግ የገቡ የድርጅቱን ሰዎች ቢያንስ በወሬ ያውቃል

«የተፈሪ መኮንን ተማሪ ነበር»

ማውራት አልፈለኩም:: ከሁኔታዬ የጠረጠረው ነገር ነበርና

«ዓላዛርን አሁንም ታስቢዋለሽ?» አለኝ ኮስተር ብሎ

«ምን?» አልኩ ዞር ብዬ:: ድንጋጤዬ ቁጣ ይመስላል::

«ተይው በቃ» አለ

«ከወደድኩ ወደድኩ፣ ካልወደድኩ አልወድም:: ዓላዛርን ማስታወሻ እቃ መሰለህ?»

«እም መሰለኝ:: ይቅርታ:: እንደምትወጂኝ አውቃለሁ:: ትዳርሽን ትወጂያለሽ:: ጥሩ ጎጂት[112] ነሽ»

ወጥ የነካ እጄን አንከርፌ አንገቱን አቀፍኩትና አይኖቹን አተኩሬ እያየሁት:

---

[112] ለጎጆዋ፣ ለትዳርዋ የምታስብ ሴት

«ፋሲልዬ አንተን ብቻ ነው የምወድህ:: ከወደድኩ ደሞ እወዳለሁ» ድምፄ ደከመ:: በትባት የሚያዳልጥ አፌን አፍንጫው ላይ አስቀመጥኩ:: ከዛ ሳምኩት::

«በሁሉ ነገር እወድሃለሁ:: አንኳልህን:: ስታቅፈኝም»

እውነት ሁሉ ይውጣ አይባልም:: እውነት ሁሉ አንዴ ተዘክዝኮ ከወጣ ዛሬንም ነገንም አንኖራትም::

«እ......አሁን እዚህ አስኘኸኝ ምናባክን:: ለምን ትማርከኛለህ?»

«አይመችም:: ወጥ በወጥ ነን»

«ሂድዛ»

እንደምወደው ልነግረው እጆቼን በጨርቅ ጠርጌ አልጋ ላይ በሆዴ እወድቃለሁ:: ቂጤ ላይ ብርድ ይወርዳል::

«እወድሃለሁ! እወድሃለሁ! ፋሲል! ፋሲልነት! ፋሲልነት!»

ባሌን በጀርባዬ እንደ እንቀልባ እለብሰዋለሁ:: ተጸክሞ ሲተኛ ቅንቅኔን ለማራገፍ ወደ ውጭ እወጣለሁ:: እንደ ቀጠርኩዋቸው ሁሉ ያን ጊዜ ከደጅ የሚቀበሉኝ የከተማው እንቁራሪቶች ናቸው:: ካካታቸው ሃይለኛ ነው:: ከቤቴ ስብሳብ ፈቀቅ ብዬ እንደ ሳም ሳንፎለፉል ወደ ተቀመጥኩበት የጨለማ ድምፆች እሰማለሁ:: እንዲህ ተቀምጦ ጨለማንና ተፈጥሮን ማዳመጥ እውነትንና ፍቅርን መልቀሚያ ነው:: እውነትን መቼም አልናገራት:: እየረሳሁዋት እየሸሸሁዋት ጥፋቴም እንዱ ዕድለቢስ ላይ በ*ብዙሃን ይመውሉ* ስልት ተሳብቃ ማምለጫ ጊዜ ይኖረኛል:: ፍቅርን እነጥቃለሁ:: እዛና እዛ ተደብቆ ከግቢ ግቢ የሚሾልከው ውሻ ከእኔ በምን ይለያል? ሌሊት ከእንቅልፉ ተነስቶ ቤቱ አጥር ላይ በሸንቱ ቅጠል የሚገርፍ አባ ወራ:: ፈኛው ምን ቢያክል ነው? ሽንቶ ሲጨርስ ይስላል:: ሳል ፀጥ ባለ ሌሊት ያምራል:: ሳል ውብ መሆኑን ያየሁት ያን ሰሞን ነው:: በጨለማ *ውስጥ* ማንነቱን ሳይደብቅ እየዋኘ ይመጣል:: እኔ ተባረኪ ከሳል እንሳለሁ?

•

•

•

ፋሲል አንዳንድ ጠዋት ከአልጋው ሳይወጣ ብርድልብሱን ብቻ ይገልብና እግሩን ያየዋል::

«ምነው?»

«ጠዘጠዘኝ» ግራ እግሩ እስከ ባቱ ጠባሳ ነው::

«እንዲህ ያደረገኝ ፋሺሽት ሳይጠፋ እግዜር አይግደለኝ»

ለዚህ አባባሉ ምስክር እየቆጠረኝ ይመስለኛል:: አውቃለሁ. ብዙዎቻችን አለማችን ጠባሳችን ጋ ነው:: የድብደባ ዝናብ የጠጣ ጀርባችን ላይ ነው:: ከባላቤቱ የበለጠ ውጋትን ማን ማወቅ ይቻለዋል? ከባለቤቱ ያወቀ ባንዳ ነው::

•

•

•

ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ሐይቅ ማየት ወድጄአለሁ:: ዝም ብሎ የትም የማይሄድ ሰፊ የቆመ ውሃ ማየት:: አዋሳ ከተማ የሰጠችኝ አንዱ ሱስ ነው:: ከዛ እሱ ሲሰለቸኝ ዝም ብዬ ሰማይና ተራራ የተገናኙበት አድማስ ማየት:: ምስክርን እየጎተትኩ በእግሬ አሞራ ገደል እሄዳለሁ:: በቢጫ አፈር ላይ የእኔና የልጇ ኮቴ ስንሄድም ብቻውን ነው፤ ስንመጣም:: ከመሃል እሷ ይደክማታል:: መታቀፍ ትፈልጋለች:: የማታየውን የምትወድ ናት:: 'እማማ ሃይኩ ውስጥ ምን አለ?' 'አሳ' 'እማማ እዛ ሃይኩ ውስጥ ብገባ ምን እሆናለሁ?' 'አባ ኮዳ ይውጥሻል' 'እማማ አባባ እሳ ተደብኮ ቢሆንስ?' 'እሱ እዚህ አገር የለም' 'ጀርመን' የሚለውን ቃል እጠላለሁ:: 'አውከሽ ነው እንጂ እሳ ነው' 'ዝም በይ......ለፍላፊ'

በኮሮሶ ጥብስ የወዛ አፏን አንጋጣ ጥረጊልኝ ትለኛለች:: ዐይኔ ውሃዋ ውስጥ ዓላዛር ተደብቆ ያየኛል:: በከንፈሮቿ ተደብቆ ያየኛል:: ቅላትዋ ሆኖ ያየኛል:: በዞማዋ ልፍስፍስ ውስጥ ተደብቆ ያየኛል:: ጉንጮቿ ሰርጓዳ ተቀምጦ ያየኛል:: ልስማት እፈልግና እሱን የሳምኩ ይመስለኛል:: ፋሲልን መክዳት አልፈልግም:: ትንሽ የመሰሉት ነገሮች ሁሉ ከበዱኝ::

«እማማ ስትስሚኝ ለምን ዐይንሽን ትቸፍኚያለሽ?»

«እኔ?»

«ፋሲል አይቶሻል» (አባዬ አትለውም)

«ወሬኛ»

«እማ ሌላ አሳ እፈልጋለሁ»

«አይበቃሽም? ጸጦ ኾጳ ሆንሽ ኺፁጓስ»

ቆዳቸው የደረቀ ሳር የመሰለ የሜዳ ፍየሎች፣ አንገታቸውን ቀስረው አተኩረው ከሩቅ ያዩናል::

•

•

•

ጉች: (ከግሌ መዝገበ ቃላት) ከራሳችንን የልብ ምት ሸሽተን የሌሎችን ማዳመጥ:: ድርጊቱ *መጎቸቸ* ይባላል:: ወንዱ ጉቻ ሴቷ

**ጉቺት** ይባላሉ:: ከማሕበራዊ ማዕበል ተርፎ ስለመጣ ቁና ቁና እየተነፈሰ ከሁሉ ተገልሎ ተቀምጧል:: ያጠገገ ቁስለኛ፣ ያልፈራ ፈሪ ነው:: በሁለቱም ስፍራ ተመቻችቶአል:: በዚህ ቢይዙት በዛ ያመልጣል:: የቅርብና የሩቅ ውጤት አለው:: የቅርብ ውጤቱ *መስዋዕትነት* ነው:: የሩቅ ውጤቱ *ቂጭት* ነው:: ጉቾ ና ጉቺት በባህርያቸው ከቅርብ ውጤት የተጣበቁ ናቸው:: እውነተኛነቱን የሚለኩት በመስቃየታቸውና በመሞታቸው ብቻ ነው:: ካልተሰቃየህ እንዴት እውነተኛ መሆንህ ይረጋገጣል? ፋሲል በትክክል በቅርብ ውጤቱ ይኮራል:: እኔ በስማዕትነትና በቁጭት መሃል ነኝ:: መሃል ሰፋሪ ነኝ:: ደልዳላ ቂጤን ደልዳላ አጥር ላይ አስቀምጬአለሁ:: መስዋዕት መሆኔን ከተጠራጠርኩ ጥሬ-ጉቺት ነኝ:: እማማና አባባ ትዳር ሲመሠርቱ በዘመድ ተፈቅዶላቸው ነው:: የተዋደዱት እነሱ:: የሚጋቡት እነሱ:: የሚወልዱት እነሱ:: የፈቀደላቸው ግን ሌላ ሰው:: ትዳራቸው የጣልቃ ገብነት ውጤት ነው:: ስለማህበራዊ ለውጥ ብሰብክ፣ ሺህ ጊዜ ቀይ ቀለም ውስጥ ብነከር፣ ከእማማ የተለየሁ አይደለሁም:: ድርጅቴ ዘመዴ ነው:: እየዳረ የሚያፋታኝ:: የምጠላውና የምወደውን የሚነግረኝ:: እማማ እኔን ምን ለየን? ከእማማም እብሳለሁ:: መባሴ ያለው በ'አውቃለሁ' ጉራዬ ነው:: 'ማህበራዊ አለመታደል' ሲሉ በእጭሩ ይሄው::

አንድ መዝገበ ቃላት 'ጉች' ማለት 'የእህል ክምር ነው' ይላል:: 'ጉቾ' ማለት 'የተጎቾ ክምር' ነው ይላል:: ክምር መሬትን የለቀቀ ግን ገና ወደ ሰው አፍ ያልገባ መብል አይደለ? የራሱ ማንነት ስላለው ነው ስም የሰጡት:: ከነበሩበት አፈር ተላቆ ሰው አፍ ሳይደርሱ መሃል ሜዳ ላይ ተንሳፎ መቀመጥ? 'ጉች አለ' 'አጎቻቸት' እያለ ይራባል፣ ይመስለኛል ባላነበውም:: ጤፍ ይሁን ስንዴ ክምር ናቸው:: ለምን 'ሴቴ ጉች' የለም? ('ጉቺት' ልንለው) አላረምንም? ባላችን ገበሬውን አላስደሰትንም? ወይስ ለምሳው የቋጠርንለት ቂጣ ወርዶ ጠበበ? ከዚህ የበለጠ ብቸኝነት ምንድነው? መኖሪያ ጎጆዎቻችን የእህል ክምር ይመስላሉ:: አጠራራቸው ከጉች ቢመሳሰል እኔ ያደረኩት አይደለም::

•

ጥርቦቻችን በመኪ• ጥቁር ፈር
ይሞላሉ

•

ዓሌክስን የማላውቀው ጀርመን የተባለ አገር ዶሮ ከመሰለች የፈረንጅ ሴት ጋር በሃሳቤ አገናኘውና አንጀቴ ሊቆረጥ ይደርሳል:: ደረቱ ጋ ከትክሻው ዝቅ ብሎ ቀይ ቆዳው ላይ የፈሰሱት ስሊጥ የመሰሉት ነጠብጣቦች

……ለማይሆኑ ሰዎች ያደረኩትን ምነው ባደረኩለት?……

ለምን ሰዎች ቅናትን ክፉ አድርገን ተረዳነው? እዛ አልጋው ግርጌ የወደቀው ተራው የካናቴራው ጨርቅ አስተጣጠፍ የዓላዛር በመሆኑ ብቻ ውድ አይሆንም? ዕንብርቱ ሰርጓዳ የሚሰበሰቡት ደቃቃ ጥጦች አንጀቴን እንደሚበሉት ለምን ካድኩ? ብቀናስ ቢቀናስ ምን ክፋት ነበረው? ግን የምቀናበትን ለራሴ ላደርግ አልቻልኩም:: ልብ የሚፈልገውን አለማወቅ እንዴት ሆነ?......አለማድረግስ እንዴት ተቻለ?

•

•

•

እንደ ባሌ እንደ ፋሲል የመነሻቴ ቁስል ከውጭ አይታይም:: በልቦናዬ ልቦና የተሸሸገ ነው:: አድማሴ ኮሚኒዝም ነበር አሉ ሲሰብኩኝ:: አሁን አሁን እንደምትጠልቅ ፀሐይ የቀላ የሆድ ቁስል ነው:: በኃሕ የሆነ ጥቁር ድንጋይ ላይ ጋቢዬን ተከናንቤ አዋሳ ሐይቅ ዳር ቁጢጥ አልኩ:: ከአመዳሙ የአካባቢዬ ግት የወፍ ጫጫታ ይታለባል:: ሁሉ ነገር ገና በቀለም አልተነከረም:: እንዲህ እንዲሆን እፈልጋለሁ:: ባዶ አየር ላይ አፍጥጬ የማስበው ባዶ ነገር ነው:: ወሳኝ ነገር ሁሉ አሁን የለም:: የሚያስጨንቀኝ ነገር ሁሉ አልጋዬ ላይ ነው:: ተመልሼ መተኛት እፈራለሁ:: ሁለመናዬን ደሞ ከብዶኛል:: ሁለመናዬ በኮምጣጤ የተሞላ ነው: ይሄ መሞላትና ባዶ መሆን እንዴት እንደተያያዙብኝ ሳስብ ከሁዋላዬ ኮቴ ሰማሁ:: እንዳልተደበርኩ ሁሉ ደንግጬ ዞር አልኩ:: ፋሲል ጋቢ ተከናንቦ ፒጃማውን ሳያወልቅ በሸበጥ ተከትሎኝ መጥቷል:: ለምን እንደመጣ አውቃለሁ::

«ምን ልሁን ብለሽ ነው በሌሊት እዚህ?»

አልመለስኩለትም:: እንደማልመልስለት ያውቃል:: የለበሰው ጋቢ ልዩ ሙቀት ያለው መሰለኝ:: በዛን ደቂቃ በረደኝ:: እንዲይዘኝ ፈለኩ:: ከተቀመጥኩበት ስነሳ ከሁዋላዬ መጥቶ አቀፈኝ::

«በደንብ እቀፈኝ በማርያም» አልኩት:: ላለቀስ እፈልጋለሁ:: ምክንያቱን መንገር ስለማልችል ግን ዋጥኩት

«ከዚህ በላይ? ደኸው»

«በጣም! በጣም!»

ደረቱን ደርምሼ መግባት ፈለኩ:: ስጋውን አጥንቱን መሆን:: መድረሻዬን ባላውቅም መሸሽ::

«ምን ሆንሽ?»

«እንጃ»

«እም......እንጃ?»

አልገባውም:: ለእሱ ቀላል ነው:: የሚጠላውን ጠልቶ ተመቻችቷል:: የተዋጣለት ጉቾ ነው::

ራሴ ያስጠላኛል (በደካማነቴ)

ደርግ ያስጠላኛል (ስላሰረኝ)

እማማ ታስጠላኛለች (ሁሉን ነገር ስለምታቃልልብኝ)

ፋሲልን ብወደውም ትንሽ አንዳንዴ እንዲህ እጠላዋለሁ (ሳይገባው የገባው ስለሚመስል……ደሞ ትንሽ እንደሚያናድደኝ ስለማያውቅ)

«ነይ እንቀመጥ እዚህ ድንጋይ ላይ ጠፍጠፍ ያለው ላይ» እንደተቀመጥን፣ የሰፈረብኝ ክፈሉ ድብርት ሲነሳልኝ ተሰማኝ:: ክፈሉ ግን አእምሮዬ ነርቭ ውስጥ እንደ እንክብክብ ምሶ ተደበቀ::

«ሞቆሃል?»

«አዎ»

«ሞቆሃል?»

«በደንብ»

በጋቢው ስር ዳብሼ ፒጃማውን ፈልፍዬ ወንድነቱን ያዝኩት:: የተደበቀውን ድብርት ለማውጣት ፋሲል እንዲረዳኝ እንዲገባው አንገቱን ሳምኩት::

«ፋስሽ» አልኩት እንደ መለመን

«ቤት እንሂድ» አለኝ

«እዚህ ነው የምፈልገው»

«ብርድ ነው»

አውቃለሁ ሁለተኛው ልጁ እሳ እሳ እንደሚሸት:: እንደ ተወለደ ወደ ሐይቁ ብወረውረው፣ እሶች በቅዳሴ ይቀበሉታል:: የዛን ለት ጎህ ጥቁር ድንጋይ ላይ ስልት ባለው መንገድ የሚነቃነቅ ጉም የመሰለ ጋቢ ስር ሽል ሲቀምሙ ነበር የዚህች ከተማ ልጆች::

•

•

•

የአዋላ ኗሪ ስሆን በእርግጥ የመጣሁበትን ጎዳና አቅጄ ነው? እንደ እናቴ አዳናቂነትና ፕሮፓጋንዳ ሐረር ወይም ድሬዳዋ መስፈር ነበረብኝ:: ለመሆኑ ሽሮሜዳ ልኖር መሄዴ ዕጣ አይደለም? የእግዜር እቅድ አይደለም? ዓላዛር ሽሮሜዳ መወለዱን እሱ አቅዷል? እኔና እሱ እዛ

መገናኘታችን ዕጣ አይደለ? ስሜ *በቃለች* ስሙ *በቃለ* አለመሆኑ ዕጣ አይደለ? ከዛ ሁሉ ልጅ እሱን ስወድ፣ የእግዜር ቀመር አይደለ:: ታዲያ ክርሞ በፖለቲካ ተሰቅዘ እሱን ስረሳው በሰው ስራ እግዜር ተረታ ማለት አይደለም? የሰው ስራ ከእግዜር ስራ ሲገን አያስተዛዝብም? እንዴት ነው ዕጣን የጥቂት አመታት ስሌት የበለጣት? አመክንዮ እንዴት ቢንሰራፋ ነው የእግዜርን ግርማ የጋረደው?

•

•

•

የታሪኬን ነፍስ ፍለጋ እማስናለሁ:: እየሸሸሁም አስባለሁ፣ እያሰብኩም እደበራለሁ......የአባብ መርዝ መርዝ መሆኑን አቁሞ መድሃኒት የሚሆነው መቼ ነው? ፀጉሬ ምን ያህል ቢያድግ ነው ጎፈሬ ተብሎ የሚሰየመው? ያ ሽግግር፣ ያ ፀጉሬ ጎፈሬ የሚባልበት፣ መርዙ መድሃኒት የሚሆንበት መደ'በሬ ሽፍትነት የሚሆነው መቼ ነው? ሽሹቴስ ዘራፍ የሚሆነው? ......ያ ቦታ የት ጋ ነው?

ሰያሚው ማን ነው? ታሪክ እንደ ግለሰብና እንደ ቡድን ተነጥሎ የሚጠራበት ነፍስ አለው? 'እሬት' ሲባል መራራነት፣ 'ማር' ሲባል ጣፋጭነት ትዝ እንደሚለን:: በዛን ሰሞን የተነፈስኩትን አየር ብተነትነው ንጥረ ነገሮቹ ፍፁም የእኔ ናቸው? ይሄን ቅልቅል ሁሉን አወቅ ሆኜ ዘርዝሬ መመደብ እችላለሁ?

•

•

•

***ትርፉ ምንድነው?*** ከእናቴ ነፃነቴን የማገኘው በመዋሸት ነበር:: ፖለቲካ ገብቼ እስክታሰር የፖለቲካ እንቅስቃሴ እንደማደርግ አታውቅም:: ልትጠረጥር አትችልም:: ከዓላዛር ጋር ስንሆን የሚረብሻት ሞጥማጣነቴ እንጂ ሌላ ነገር ታደርጋለች ብላ አትጠረጥረኝም:: ምክንያቱም ገና ልጅ ነኝ:: እሷ እያለች እንንካካም:: አሉባልተኞች በሽሙጥ ሲያሙ ስትሰማ 'ይሄኔ ቀንተሽ ነው አዳሜ' ትላለች እንጂ በሌላ ነገር አልጠረጠረችኝም:: ምክንያቱም ዋሽቼአታለሁ:: ዓላዛር ወንድሜ አይደለም እንዴ? አልጫወት እንዴ? ሌላም ብዙ ውሸት:: ዓላዛር ክንድ ላይ ሳርፍ ጥሩ ቲያትረኛ ሆኛለሁ:: ሰዎች አፌ ላይ ልጥ ያዩ ይመስላቸዋል እንጂ ልቤ ውስጥ የተኛው እባብ ነው:: በፖለቲካ ሕቡዕ ስገባ ዋናውን ፍላጎቴን የመደበቅ ችሎታዬ ቀልጣፋ ሆነ፣ እማማ ላይ የተለማመድኩት ቲያትረኛነቴ ጠቀመኝ:: ሁለተኛ ዲግሪዬ ነው:: ፋቢል

ሲጠናቀቅ ያኔውኑ ከአልጋ ተነስቼ መታጠብ እችላለሁ:: ቲያትር እንዳይመስልብኝ፣ ስሜት የለሽ እንዳያስመስለኝ ግን አላደርገውም:: አስጠግቼ አቅፌውና ስለ እዋሳ ሐይቅ አስባለሁ:: የዚህ ሁሉ ቲያትር በእርግጥ ትርፉ ምንድነው?

•

•

•

አንድ ቀን ሙዚቃ እየሰማሁ፣ እሱንም ተከትዬ እያንጎራጎርኩ ጊዜው ደርሶ እራት ሳደርስ ወዲያ ወዲህ ስል ፋሲል የተጠረዘ ነገር አምጥቶ ፊቴ ላይ ዘጭ አደረገ:: ፈገግታው ልዩ ነበር: ወፍራም ፊቱ ላይ አንድ ትልቅ ቀዳዳ ተከፈተ::

«ምንድነው?» አልኩት

«ለትዝታ:: ልሳናችን»

«የምን ልሳን?»

«እጁው»

እርጥብ እጄን በቀሚሴ ጠርጌ ፋይሉን አነሳሁና ገለጥኩት:: ደነገጥኩ::

«የት አገኘሽው?»

«ሺፈራው አዋሰኝ:: ከሁለቱ በስተቀር ሁሉም እትሞች አሉ»

ቃሉ ራሱ ደስ ይላል:: *ዲሞክራሲያ*: የተፃፈበት ቀይ ገርዳፋ ቀለምና የቀለሙ ጥልቀት ልብ ይገባል:: ፓምፍሌቶቹ በጥንቃቄ ተጠርዘዋል:: የልሳኑ በቀይ አጀማመር፣ የአተያየቡ ስለት በትውስታው ናጠኝ:: ከመጀመሪያ ጀምሬ ቶሎ ቶሎ እየገለጥኩ አየሁት:: ማድ ቤቱን አዘገጃጀቴ ሳነብ ተቀመጥኩ:: ከድስቴ አልራቅሁም:: ደሞ ፋሲል እኔ ካልሰራሁለት አይበላም:: ገልጬ ገልጬ ወደ ቅፅ አራት ሄድኩ:: ወደ አጨራረሱ:: ገና ማንበብ ስጀምር ምስክር እያለቀሰች አለፁበት መጣች:: እኗን ለማባበል ከተቀመጥኩበት ተነሳሁ:: ሳባብላት አትሰማኝም:: ሳባብላት ደስ ይላታል:: ስለማመጣት ትክክል የሆነች ይመስላታል:: ይሄ ውኸንብሯ እንዲተዋት ቆነጠጥኩዋት:: ትንሽ እንዲህ ስትቀምስ አፏን ትይዛለች:: አንዳንዴ ነገር ስታበዛብኝ፣ ሰላሜን ስታደፈርስ ከሩቅ ሳልቀርባት አመልካች ጣቴንና አውራ ጣቴን አጋጥሜ አሳያታለሁ:: እጆቿን እግሮቿ መሃል አድርጋ እየተቁለጨለጨች በዝምታ ትቀመጣለች:: ይሄ ለእኔ ማባበል ነው:: እኗን አባብዬ ስመለስ ወጡ መገንፈል ጀምሯል::

እንዲህ እንዲህ ትሰራኛለች:: ምስክር ብታምርም ሚጢጢ ቢች[113] ናት:: የፈሰሰ ሳፍስ፣ እሷን ሳስተካክል ማንበቤን መቀጠል ረሳሁ:: ማታ ልተኛ ስል አነበዋለሁ ብዬ ፋይሉን አንስቼ ትራሴ ስር አስቀመጥኩት:: ለመተኛት ብርድልብስ ስለብስ ረሳሁት::

•

•

•

ሲስመው ካስጮኸው መቃጦኑ የተለያየ፣ ውሃው ከላዩ ያልጠፈፈ ቴላፒያ ወደ ጳርቻ ሲወረወር፣ ብሌኖቹ ሰማይና ምድርን በትዝብት ያያሉ:: የአሳ ወጋሪ ፌሽታ፣ የሰው ዕጣ ትዝ ይለኛል......

•

•

•

መብት አለኝ ለመሆኑ የራሴን ቁርጠት የሕዝብ ነው ብዬ መለደፍ? መለጠፍ? ማን ነኝ በፈራጅነት የመደበኝ? የዛንም የዚህንም የስሜት አብራክ የመፈተሽ አቅሙ አለኝ? በእያንዳንዱ ነገር እያንዳንዱን ዜጋ መሞገት እችላለሁ? በሁሉ ልክ ነኝ ማን አለ? ቆሜ እሄዳለሁ:: በሚያስቀው እስቃለሁ:: እንዲህ እንዲህ እንዲህ ነው ለማለት የሚችለው የእኔ እንደበት፣ የእኔ ጉዳይ ብቻ ሲሆን መሰለኝ::

እንደማታውቂኝ ሁሉ አላውቅሽም

ቦታ ብንለዋወጥ ቅጥፈት አይሆንብንም?

ወይ ብልጠት::

ብሳናው ሸንኮራ አገዳ ሆኖ የሚሉሽ እንዲህ ሲሆን መሰለኝ

•

•

ጥርሶቻችን በመከ. ጥቁር ፈር ይሞላሉ.

•

'ከሁሉም በላይ ፍጅቱን ለማስፋፋት ሕዝቦችን እርስ በእርሱ እያጣላ ነው:: በጉርጉሱም በጋራሙለታና በሀብሮ አውራጃዎች ሕዝባዊ ጦር ብሎ ያሰለፈው በፊት ኦሮሞዎችን ይበዘብዙ የነበሩ ነፍጠኞችን ነው...... ቅፅ 4......ቁ......'

---

[113] ጨቅጫቃ ( bitch)

«ፋሲልዬ! ፋሲል! ነፍጠኛ ምንድነው?»

«አይሰማኝም! ምን አልሽ!?»

ተወው:: ከእኔ አምስት ኪሎሜትር እርቀት ላይ ያለ ይመስላል:: አንዱ ጆሮው ሕመምተኛ መሆኑን እረሳለሁ:: በቀኙ በኩል ተቀምጬ ማውራት መለማመድ አለብኝ:: ደህናው ጆሮ ደሞ የሚሰማው ድምፅ፣ ውስጥ ልብሴ ሲገፈፍ ብቻ ነው::

•

•

•

የአሳ ሾርባ የምስክር ቀሚስ ላይ ከደረቱ እስከ ጉልበቱ ድረስ:: ጠዋት ማታ:: ካልተቀቀለ አጥንቱ አይደክምም:: ካልተቀቀለ የደከመው አጥንት አይመር'ቅም:: ምስክር አዋሳ ሃይቅ ጠቅላላ የአሳ መረቅ ይመስላታል:: በሆነ መልክ ልክ ናት:: የነዛ ተራሮች ጎርበጥባጣ የጎድንና የሰረሰር ምሳሌ ሳይሆን አይቀርም:: በእቋሪ ውሃ ስትጫወት ቆይታ ሲደክማት 'እዘይኝ' ትላለች:: አዝያት እመለሳለሁ:: ጀርባዬ ላይ ሆና ከዕንቅልፏ እየታገለች: 'ሐይኩ መረክ አደለ?' ትላለች:: ዝጊ......ችጋራም::

•

•

•

የተጎዳሁበት አላማ በጊዜ ተገምግሞ ቢጣጣልስ? ማለት በጊዜ ቅርበትና እርቀት ግምገማ ሊሻር አይችልም? ልጄ ነገ አድጋ፣ አፏን ፈታ፣ ድፍረትና ብልጠት ኖሯት 'ከአባቴ ምን ለያያችሁ?' ብትለኝ ምን ልመልስላት ነው? ደካማነቴን ልንግራት? ቂልነቴን ልንግራት? የጊዜ ዕርቀት አዲስ እውቀት ሰጥቷት፣ እንደ እኔ ሳትደበቅ ያጠናችው ያብሰለሰላት እውነት ሌላ ጉዳይ ቢተርካትስ? ዛሬን ሳይሆን የወደፊት መገለቤን እፈራለሁ:: እንዲህ ብጠረጥር ልክ ነኝ?

•

•

•

**ሴት ነኝ--እንደ አንቺ::**

**ምስክርን ያጠቡት ጡቶቼ እነኚሁና--**

**ቅድመ-ዘልዛላ**

እበላለሁ፣ እጠጣለሁ፣ እሰራለሁ፣ የቀበሌ መታወቂያ አለኝ--ይሄ እንግዲህ ዜግነቴ ነው::

ኮሌጃችን አብረን ገብተናል::

ጫማ ገበያ ከአንቺ ተሻምቼ እገዛለሁ

ወፍጮ ቤት የሽሮ እህል እንደ አንቺው አስፈጫለሁ

ሚጥሚጣ እተመትማለሁ

'ያማረች' የሚሉኝ 'የምታምር' የሚሉኝ 'ባለሙያ' የሚሉኝ፡ ግን ባሳለፍኩት ነገር የተለየሁ ነኝ:: ወደ ታሪክ እየደነስኩ ገብቼ እየጮህኩ የወጣሁ:: እርስዎ እንደ ታዛቢ ክቡር ትሪቡን ተቀምጠው

ሲያጨበጭቡ::

ለማን አጨበጨቡ?

ግን 'የተለየሁ ነኝ' ብል፡ ከዓሳ አጥማጅ ሕይወት፣ ከእትዬ በቀለች ሕይወት፣ ከነርሷ ሕይወት፣ ከእረኛው ሕይወት፣ ከዘበኛው ሕይወት፣ ከኩሊው ሕይወት፣ ከዶክተሩ ሕይወት፣ ከሰአሊው ሕይወት በምን ይለያል? ሁሉ የተለዩ አይደሉ?

•

•

•

'የኢትዮጵያ ታሪክ ሂደቱ የገፋበት ጊዜ መቶ አመት እንኳዋን እንዳልሞላው......ቅፅ 4......ቁ 9 ገፅ 8......'

«ምነው? ገፋኸኝ»

«በእናትሽ ነገ እንብቢ እንቅልፍ ልተኛ አልቻልኩም»

«መቼ ላንብብ?»

«ለምርት ዘመቻው እንደ አንቺ ማን ይሰራልና:: ደስ ያለሽ ጊዜ አንብቢ:: አሁን ተኚ:: ቢሮሽ ብታነቢው ማንም አያይሽም ሃሃ»

«ተው በእናትህ:: የመጨረሻ እትሞችን እኮ አላነበብኩም:: አንዳንድ የማይገቡኝ ነገሮች አሉ»

«ተኚ አሁን፣ ስብሰባ አለብኝ በጠዋት:: ለቀይ ኮከብ ጥሪ ሰዎች ስለሄዱ ስራ ጨምረውብኛል:: ደክሞኛል የእኔ እመቤት»

«ምናባቱን ይሂውልህ:: ደስ አለህ?»

•

•

•

ጉዞዬ የቁልቁለት ነው:: ይሄ ይሄ ሁሉ ያልተመኘሁት፣ ያላቀድኩት አመጣጥና አጨራረስ ነው:: ደሞም አያልቅምና በግድ እኖራታለሁ:: ለእኔ ለባለቁስሏ ብቻ የሚገባኝ ሁለት አይነት አወዳደቅ አለ፡

ሀ/ከሌላ ጋር እራሴን አወዳድሬ ማነሴን የማይበት (ከብዙዎቹ የአገሬ ሰዎች በተሻለ ክብርና የኢኮኖሚ ደረጃ እኖራለሁ)

ለ/ከወደቀው የግል ህልሜ ጋር አወዳድሬ ዛሬን ሳነፃፅር (ይሄን እኔ ብቻ ነኝ የማየው:: የሚገባኝም እኔ ብቻ ነኝ:: 'ይገባኛል' የሚለውን ማንም ጉረኛ 'ዞር በል' እለዋለሁ::)

ሁለተኛው ከመጀመሪያው የበለጠ በስሜት እንጂ በመረጃ አይደረስበትም:: 'ይብራራ' ብባል ማብራራት ይከብደኛል:: መረጃዬ ደመነፍሴ ውስጥ ነው:: ደሜ ውስጥ እንኳን አይደለም:: ቢበጡኝ አይገኝም:: ከደሜ ጋር ተደባልቆ እንደ አየር ይነፍሳል::

•

•

•

1976 መስከረም ውስጥ ፀነስኩ:: ታህሳስ ላይ ገናን አስታከን ከፋቢል ጋር በትንሽ ድግስ ተጋባን:: ግንቦት ከባድ ምጥ ጀመረኝ:: ቤት ማንም አልነበረም:: ውስጤ የተሰበሰበው የስጋና የደም ውጋት ብቻ አይደለም:: የማማጥና የመውለድ ብቻ አልነበረም:: ለምን ጠለቀ? ለምን ሰፋ? ከሁለመናዬ ተጠራርቶ የተጠራቀመ የፀነነ ነገር ነበር የማሕፀኔን ደጃፍ የሚያምሰው:: አውዱ ሁሉ ነው:: ማማጥን እንዳላወቅሁዋት:: የአለም መሰለኝ ሕመሙ (የተራራዎቹ፣ የሜዳው፣ የአዋሳ ፍካት፣ የእማማ ንዝንዝ፣ የዓላዛር ትዝታ፣ እንጦጦ ማርያም፣ የአዲስአበባበ ዶፍ፣ የእስር ቤት ለቅሶ፣ የአብዮት አደባባይ መፈክሮች፣ ዘመኑ ዘመኑና ዘመኑ):: ጩኸቴ አፌን ለቆ ሲወጣ 'ናልኝ' ያልኩት 'ዓላዛር!'ን ነበር:: ቀጫጫ ክንዱ ትዝ አለኝ:: አቤት እሱን ተደግፌ መውለድ እንደተመኘሁ:: የጡቱን ጫፍ እንደ ሞላ ነክሼ፣ የሚያምረው የሆዱን ስሌዳ እየቧጠጥኩ:: አቤት እሱ ግንባሬን እየሳመኝ ባምጥ:: የጮህኩትን ስሰማ በድንጋጤ ሕመሜን ረሳሁ:: ግራና ቀኝ እንደ ሌባ ተገላመጥኩ......

ምስክር ምጥ አልነበራትም:: 'ሾልካ ወጣች' አሉዋት:: የቀላል አፍቃሪ ልጅ ነበረች:: በዘበዛ ከማያበዛ ፍስ ያልተበጀች:: ጣጣ ካልፀረሰበት እንቁላል ያልተቀመመች......

......ሐኪም ቤት በጀርባዬ ሆኜ......

«ፋሲል ናልኝ» አልኩት::

ጎንበስ ብሎ በላብ የሚያዳልጥ ግንባሬን እየሳመ:

«አይዞሽ የእኔ እመቤት» አለኝ::

«አፈር ስሆን አትሂድ» ('አፈር ስሆን' የሚለውን ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ ተጠቀምኩ)

ወንበር ስቦ ጎኔ ተቀመጠ::

«ፋሲል ምን ሳስብ ነበር መሰለህ?»

«ምን?»

«የምስክር የአባቷ ስም በአንተ ይሁን»

«ምን አሳሰበሽ እንዲህ ያለ ነገር:: ጊዜው አይደለም:: ሌላ ጊዜ እናወራለን:: አሁን አሞሻል»

እራሴን ለመደለል መሞከሬ ነው::

«ደህና ነኝ»

«ልንገርሽ? ልክ አይደለም:: እንዳለ ይሁን ምን ያሳስባል?»

የነቃብኝ መሰለኝ::

አይኖቼን ስጨፍን አዞረኝ:: እጄን ሰጠሁት:: ጨበጥ ጨበጥ አደረገኝ::

......ፋሲል ልጁን 'ሳሙኤል' አለው::

በቀይ ሽብር ሰሞን ዓላዛር የታሰረ ጊዜ ወደ ቤቱ ስሮጥ ተደናቅፌ ወድቄ የተቀጠቀጠው ጀርባዬ እየተጠነቀቅሁ ካልሆነ አንጉል አቀማመጥ ስቀመጥ ያመኛል:: ሳሙኤልን ከወለድኩ በሁዋላ በረታብኝ:: ይሄው ትናንት እዚህ ሞቅ ብሏት አልጠፋ ብላ::

•

•

•

ያለፈውን ሳሳስብ የዋልኩበት ጊዜ ስለሌለ በትክክል ዛሬን እየኖርኳት አይደለም:: ሁለመናዬ ገና ቁስል ነው:: ብልጥ እንስሳ ነኝና ለማንም ደሞ አላወራውም:: ምስክር ከአልጋዬ ግርጌ ቆማ 'ወንድሜን ልየው' እያለች ስታስጨንቀኝ ቆይታ ወለል ላይ ትጫወታለች:: ለመጀመሪያ ጊዜ በትክክል፣ ያለ የሁዋልዮሽ ጉዞ ጡቶቼ እንደወደቁ አየሁ:: እንዲህ ግዙፍ አይመስሉኝም ነበር:: ምስክር እንዳታየኝ አድርጌ አንዱ ጡቴን በወተቱ የከበደውን፣ በግራ እጄ እንደ ኮሮጆ ያዝኩት:: በላዩ የወጡትን ሽንተረሮች እንደ ተመራማሪ አየሁ:: ልጅ እያለሁ

ምኞቴ፡ ከአንድ ልጅ ጋር ተፋትሬ፣ ከዛው ልጅ ጋር ተጋብቼ፣ መዓት ልጆች መውለድ ጻናው የለም:: ሁሉ ያለምኩዋቸው አሉ:: ግን ሁሉም ባልተጠበቀ ባቡር መንገድ ነው የመጡት:: በቀላሉ እዚህ አልጋ ላይ በዚህ ሰአት ሁለተኛ ልጄን ከሁለተኛ ወንድ እንደምወልድ በህልሜም አልነበረም:: አሪጂናሌ አይደለሁም:: ይሄ ስለ አውድ አያቃጥርም? ስለ አገሬ? ስለ ኖርኩበት መስከ?

**ስለ አንቺ? ስለ አንተ?**

•

•

•

ሁሉ ነገር አያልፍም:: ለምን ያልፋል? ልቦናችን ሲፈጠር ስስታም የተጣመረ ብዕርና ብራና ነው:: ከታሪኬ ብሸሽም ይፅፋል::

•

•

•

ዓላዛር ሁለመናዬን አንብቦ የጨረሰ ይመስለኛል:: እንቅልፍ የወሰደኝ መስሎት ብርድ ልብስ ገፎ ጀርባዬን ዳብሶኛል:: ግንባሬና ማጅራቴ ላይ አሁንም አሁንም ስሞኛል:: ግራና ቀኝ ጭኖቼን ከውስጥ ነክሶኛል:: በሚጣፍጥ የልጅነት እብደት፣ ሁሉ ነገር ብርቅ በሚመስልበት ጊዜ በጋራ እርጥበታችን የሚንጣጣ ጠባብ አልጋ ላይ ተተራምሰናል:: አንገቴን ስሞኛል (አንገቴን መሳም ሲወድ፣ አንዳንዴ እዛ ጋ ያሳክከኛል:: ማርያምን:: ከሰው ጋር ብሆንም አይኖቼን ጨፍኜ በእጄ ቦታውን እዳብሳለሁ)፣ ጣቶቼን እያገላበጠ በጉንጩ ዳብሷቸዋል:: ያኔ በሰመመን ስስነጠቅ በልቤ *'ዓላዛር እወድሻለሁ በለኝ...... በለኝ......'* እል ነበር:: ለምን አላለኝም? የእውነት አላለኝም::

**ሰው ቤትዎ ተጋብዞ ተዝናንቶም ሲወጣ**

**ላደረጉት ትህትና ሳያመሰግንዎት**

**በዝምታ በር መልሶ ቢሄድ**

**ቅር አይልዎትም?**

**ደሞስ ያማሩ ሁኔታዎች**

**ሲገኑ**

**የሆነ ተናግረው የማያውቁትን አዲስ ቃል**

**እንዲጠቀሙ ይገፋፋዎት የለም?**

ዓላዛር አልወጣውም፡፡ ያኔ እንዲል ይገባው ነበር፡፡ ያኔ ልብ አላልኩም፤ እነዛን ቃላት አለማለቱን፡፡ ለምን የልቡን እውነትና እምልክ በእንደበቱ አልኩዋለውም?

ሃርአምባና ቆቦ ነበርን፡፡ ምናልባት፡፡

ዓላዛር ቆቅ እዚያ ገደል ስር ወረባቦ......

እኔ ተባረኪ ደነዝ እረኛ ዘንጌን የምወረውረው ወደ ቆቦ......

•

•

•

> ‘ኢምፔሪያሊስቶች ሆኑ ሚኒሊክ ከዚያም ዘውዲቱም ኃይለስላሴ እንዴ በስምምነት እንዴ በጦር ሃይል፣ እያሉ ቅኝ ግዛት ሲያማርጡ ሲያስፋፉ እንዲያም ቢል በአካባቢው ነዋሪ የሆኑ ሕዝቦችን ሕልውና ተገንዝበው......ቅፅ 4 ቁ 9’

«አንቺ አትመጪም!»

«ምነው?!»

«እየጠበቅሁሽ ነው!»

«ለምን?!»

«ለምን ትላለች? ጀርባዬን እሺኝ ብዬሽ አልነበረም!»

«አሁን አልመሰለኝማ! ትንሽ ላንብብ፡፡ የተወሳሰበ ነገር አለ እዚህ ያልገባኝ......»

«የዞረባት፣ በደንብ አትሰሚም፣ በእናትሽ ብርድ ሞትኩ ነይ! እቶ ባቶ ጋ ኮፒ አደርገዋለሁ፣ ኦሪጂናሉን እንድታዪው ነበር ያመጣሁት»

ፋይሉን አልጋዬ ትራስ መልሼ በውስጥ ልብስ መታጠቢያ ቤት ገባሁ፡፡ ፋሲል የሚፈስ ውሃ ስር ጀርባ ማከኪያ ስፖንጁን ይዞ ቆሞአል፡፡ ገና ስጠጋው ውስጥ ልብሴን ይዞ ወደ ሻወሩ ጎተተኝ፡፡ ብጮህም አለቀቀኝም፡፡

«አይሆንም! እምቢ አይሆንም!» እለዋለሁ፡፡

ፋሲል አይሰማም፡፡

•

•

•

የታባ ጉዞ አትጣጫው አይለይም:: ወደ ፊት ነው የሄድኩት ወደ ሁዋላ? እንደገና መውደድ? እንደገና መወለድ? ብቅ ጥልቅ የበዛበት ያውጎዳና? አዲስ የሚመስለው የሚመስለኝ የውጋቱ ክብደት ነው ቅለት? የጥራት ለውጥ የሚመስለው የቦታ ልውውጥ ነው? 'ሀ' እና 'ለ' ወደ 'ለ' እና 'ሀ' ቢሽጋሽጉ ተለወጡ ነው? ('ሀ' ም ደጋ 'ለ' ም ደጋ፣ ደጋ ለደጋ ተስማምተው ነጋ) ትናንት አርባ ኪሎ የምመዝነው ዛሬ ስማንያ ብሆን ልብ እሞላለሁ? ሕሊና? ቦታ እሞላለሁ አፍ?

•

•

•

ከፋሲል ጋር ብንስናኝም፣ ባገናኘን ስፈት መሃል አሮጊ አየር ይገባል:: ሲነፍስ የማዳምጠው እኔ ብቻ ነኝ:: 'ሰማህ? ፋሲልዬ ሰማህ?' እለዋለሁ:: ምንም:: ፋሲል ውስጤ ገብቶ ሲናጥ አንዳንዴ የማስታውሰው አየር ነው:: 'ሚስቴ በሁሉ ነገር ጎበዝ ናት' ቢልም፣ መሆን እንዳቆምኩ አያውቅም:: እላዩ ላይ ሆኜ ስነቃነቅ በተጨፈነ ዐይኔ የማየው ጥቁር አየር ነው:: ስገልጥ ፋሲልን ነው:: 'አየህ አየሩን? አየህ?' የፋሲል ልቡ ማሕፀኔ ውስጥ ነው:: በአዋሳ ስታታ በሲዳሞ ሰርታታ ነፋስ ቢጃማዬን እየገለበው ከልቤ ያላጣጣምኩት ዘመን (የተረገመ ትውልድ ልጅነቱን አያጣጥምም) አልፎኝ ይሄዳል:: ሁሉም ልክ ነው:: ሁሉም ልክ አይደለም:: ልክ ያልሆነው ውስጥ ልኩ አለ:: ልኩ ውስጥ ልክ ያልሆነው አለ:: ተፃራሪዎች ተቃቅፈው ይመጣሉ:: ይሄ መቃጠል ይባላል::

የፋሲል ዘር ጭኖቼ ላይ ይረግፋል::

•

•

•

ዓላዛር እኔን 'ጠፋሽ' እያለ ለራሱና ለሚያውቀን ሲያማኝ፣ ሲያሳጣኝ፣ እኔ በታሪክ ግዳጅ ሊጭቁን ሕዝቦች ስታገል አጠገቤ ነበር? ስጎዳ እዛ ነበር? እሱስ አልጠፋም? ምናልባት አማን እንዳለኝ አሮጊት ነጣላ ስር፣ ዱርዬዎች ጉያ በእንስሳዊ ሕይወት ተለክፎ:: እዚህች አገር ላይ ኖሬ ለዚህች አገር አሰብኩ ስል እሱ አብሮኝ ላስብ አለ? የእሱ ፅናት በልቶ መተኛት ነው:: ፅናቴ ለፍትህ ነው::

ግን ደሞ ለአገሬ ማሰብ ማለት፣ ተማሪ ስለሆንኩ፣ ጥሩ መማር፣ በሙያዬ ሰበስል ክብልግና ተቆጥቤ ሰው ከሰው ሳልመርጥ በስራዬ ማገልገል አይደለም? ችግር ቆስቁሼ በግድ መፅናት ለመፅናት? ሃይለስላሴ

ያስተማሩት ያ ሁሉ ያ ሁሉ ቢሮክራሲ ውስጥ የገባው ምሁር ምን ያህል የተቀደሰ ነገር ሲያደርግ ነበር? ከረፈደ በሁዋላ ለምን እሳቸው ላይ ሁሉን ነገር አሳበበ?

•

•

•

ዋቢ ሸበሌ ሆቴል ዛፎች ጥላ ስር ለስ ካለ ኮካ ጋር:: ምስክር ኳስዋን ወደ አንድ ትልቅ ዛፍ እየደጋገመች ትወረውራለች:: ትወረውራለች:: ትስታለች:: ትወረውራለች:: ፋሲል መነፅሩን አሁንም አሁንም እያስተካከለ ያነባል:: ሳሙኤል ጭኔ ላይ ተቀምጦ ማንጎ ይመጣል:: የፋሲል ኮፒ ነው:: ለምቦጫም ወንዳወንድ:: ከአሁኑ ጡንቻ ሊያወጣ ምንም አልቀረው:: ፋሲል ቀና ብሎ እያየኝ ፈገግ ይላል:: ፋሲል ፈገግ ሲል የሚያምር የዘጠኝ አመት ጉብል ይመስላል:: አንጀቴን ይበላዋል፣ ያሳዝነኛል:: ትናንትን የምናየው ከተለያየ አቅጣጫ እንደሆነ ይገባኛል:: አይገባውም:: እጁን እይዘዋለሁ:: 'ምነው?' አለኝ:: 'ምንም':: የሚያልፉ ጋሪዎች እርግማንና ምርቃት የጠጡ:: ፀሐይን ተከትለው ወደ ምሽቱ ይሄዳሉ:: መድረሻቸው እዚህ ሳይሆን ሞጆ ይመስላል::

'እቤት እንሂድ? ደበረሽ? አንዳንዴ እንዲህ ያደርግሻል'

'ዝም ብሎ ነው'

አለም ተባብራ ታሪክን ጨለማ ውስጥ ብትቀብረው ደስ ይለኛል:: እልቤ የተቸነከረውን ጉዳይ ከጋሪው ጀርባ ወይ ከሾፌሩ ጎን ባስቀምጠው:: ይዞልኝ ቢሄድ::

•

•

•

**'የሱማሌ ሕዝቦች ሳያውቁና ሳይፈቅዱ በሚኒሊክና በኢምፔሪያሊስቶች ደባ በኢትዮጵያ ግዛት ስር ውለዋል::ይህን እብሪት በመቃወም ሱማሌዎች በተደጋጋሚ እርምጃዎችን ወስደናል ቅፅ 4 ቁ 9 ገፅ 9'**

ትንሽ በዚህ አባባል ግራ ገባኝ:: *ማነው እርምጃ የወሰደው?* ፋሲል ያውቃል ይሆን:: *እጠይቀዋለሁ......*

ፊልድ ሁለት ሳምንት ቆይቼ እረፍት ላይ ነኝ:: መስከ ስራ እየወደድኩ ነው:: የማድቤት ስራ በትክክልና በስሜት ማቀናጀት አልቻልኩም:: ሽንኩርት መክተፍ ይደብረኛል:: ተራራ መውጣት፣ ገበሬ ማህበር ሄዶ ከገበሬ ሴቶች ጋር መጻረት፣ የተበላሸ መኪና ሲቀየር ኮባ ስር ተቀምጦ መጠበቅ ተመቸኝ:: ትክክል ነው? እላለሁ ራሴን:: ወደ ቤት ስመጣ በተለይ ሳሚን ሳየው እቅለበለባለሁ:: የሚረዱኝ ተመላላሽ አሮጊት ሰራተኛ ቢኖሩም፣ እኔ ሳምንት ሁለት ሳምንት ከርሚ ስመጣ ፋሲል ሲትዮዋን ማየት አይፈልግም:: የእኔን ወጥ ያውቀዋል:: አልጫ ይወዳል፡ እኔ ልስራው ሲትዮዋ እንዴ ጎርሶ ያውቀዋል:: እንደ ልማዴ ምግቡን ሰርቼለት፣ ልጆቹን እራት አብልቼና አስተኝቼ ተጣጥቢ ጠበቅሁት:: ገና ቤት እግሩ እንደገባ፡

«ምን እያደረግሽ ነው? ጥሩ ወሬ አምጥቼለሁ» አለ

«ልጠይቅህ አንድ ነገር......መጀመሪያ ተቀመጥ......ከየት አገኘሽው ሳምሶናይቱን?»

«ደሳለኝ ኢንግላንድ ሄዶ አልነበረም? አመጣልኝ......ልንገርሽ አሪፍ ወሬ»

«ምን?»

«ምን ይመስልሻል?»

«እንዴት አውቃለሁ አንተ ንገረኝ:: ልንገርሽ ብለህ የለ? ባውቀው ለምን ትነግረኛለህ?»

«ፋኦ[114] የሁለት ሚሊዮን ዶላር ፕሮጄክት ሲዳሞ ውስጥ ሊሰራ ነው:: ግሩፕ ሊደር[115] ማን መሰለሽ? እኔ:: ጥሩ ገንዘብ አለው:: የዚህን ቤት እዳ እንከፍላለን»

«ደስ ሲል»

«ምነው አታቅፊኝም? አልሳምም?»

«የሆነ ነገር እያሰብኩ ነበረ......የሆነ ነገር ልጠይቅህ ብዬ ረሳሁት......»

«እራት በሏቼአለሁ:: ጥሩ ቅቅል ጋበዘኝ የስንዱ ባል»

ልብሱን እያወለቀ ወደ መኝታ ቤት የተለመደ መንገዱን ጀመረ:: ከፊልድ ስመጣ ያኔውኑ በናካቤ ካላገኘኝ ይደበራል:: እኔም እደበራለሁ:: እንደ ሞሳ ጡት ሲወድ:: አንዳንዴ 'ቱቱ ቱቱ' እያለ ፍንጫቸው እስኪቃጠል ይመጠምጠኛል:: ምናባቱን::

---

114 አለም አቀፍ የምግብ ድርጅት ( FAO)

115 የቡድን መሪ ( Group leader)

«ጠብቀኝ አሮጊቷን ልሸኛቸው»

ሴትዮዋን ቤታቸው እንዲሄዱ ነግሬ ገና ከሳሎን ጉርድ ቀሚሴን አውልቄ ገባሁ:: አልጋ ላይ ራቁቴን እግሮቹን ግራና ቀኝ ዘርግቶ በጀርባው ተንጋሎአል:: ፋሲልን ማቀፍ የከሰል ፍም ሲነድበት የቆየ ጀበና ማቀፍ ነው:: ውስጤ እየገባ የሚወጣው ክጻኑ ያልተከፈተ ፔርሙዝ ነው:: ፋሲል የሚሰጠኝ ስጦታ ፍፁም የሆነች ዛሬን ነው:: የማላስበው እንዲህ ሲሆን ነው:: አእምሮዬ ወደፊትም ወደ ሁዋላም አይሄድም::

•

•

•

ሳሙኤልን እያጠባሁ ሶፋ ላይ ተጋድሜአለሁ:: ምስክር ፊት ለፊቴ ቆማ ፋሲል ለፋሲካ የገዛላትን ቀሚስ ልታሳየኝ ትሽከረከራለች:: 'እንዳትወድቂና እንዳታለቅሺ' እላታለሁ:: ፋሲል ስብሰባ ስላለበት ገና ምሳውን በልቶ እንደተነሳ ሊወጣ እዛና እዛ ይላል:: ባይናገራትም ምስክር እንዳትወድቅ ይጠብቃል:: ሳሚ 'ጡት ካልሰጠሽኝ' እያለ ቀሚሴን ይጎትታል:: እነፍገዋለሁ፣ ከባድ ጠቢ ነው:: የጡቴን ጫፍ ሳያቋርጥ ይለበልበኛል::

«ምናልባት ከስብሰባ በሁዋላ ትንሽ ለቢራ እቆያለሁ» አለ ፋሲል ቆለፊቱን እየዳበሰ

«እንዳታድር እንጂ ምንም አይደል»

«ባድር ምን ታደርጊያለሽ?»

አልመለስኩለትም:: የዚህ አይነት ቀልድ ይወዳል:: ቀልድ አይገባኝም ወይም ቀልድ ከተፈጠረበት ቦታ እሱ ባሌ አልነበረም::

«የምን ስብሰባ ነው? አለህበት መጥቼ በጥፊ አጮልሃለሁ» በፔርሙሴ እቀናለሁ::

«ስወድሽ......ከሚኒስቴር መስሪያ ቤት መዓት የፓርቲ ምስረታ ምናምን ተብሎ......ከነዚህ ሰዎች እግዜር መቼ እንደሚገላግለን»

«ከእነሱ ጋር ነው ቢራ?»

«ከስብሰባ በሁዋላ የምንግባባ ሰዎች እንሰባሰባለን:: የሚብጠለጠል ይብጠለጠላል»

«ለሃሜት? ቴስት ማረም የለብህም? ራስህን ጠብቅ»

«የተማሪዎች ነገር ይቆያል:: ተሜ ምን ይሆናል መሰለሽ? ቂል አይደለሁም:: እኬ?»

«እማማ እዩ» አለች ምስክር:

«አርፌሽ ከረሜላሽን ብዩ:: ያን ነገር ከጠዋት ጀምራ ስትጠይቀኝ:: ልትገለኝ ነው»

ፊት ለፊቴ አኩርፋ ተቀመጠች

«እናትሽን ስሚያት»

ቀና ብላ አየችውና:

«አባቴ መቼ ነው የሚመጣው?» አለች:: ትንሽ ደስ ካላላት እንዲህ ትጠይቃለች:: 'አባባ ጋ እሄዳለሁ' ትላለች:: የመጨረሻ ነገረኛ::

«ይሄው እሱ እዚህ አጠገብሽ» አልኩዋት

ፋሲል ዞር ብሎ አየኝ:: እሷን አይቶ ፈገግ አለ:: ምስክር ትኩር ብላ አይታው:

«እነ ምርቃት 'ፋሲል አባትሽ አይደለም' ይሉኛል»

«አባትሽ ነው»

«አባቴ ከሆነ ለምን የአባቴ ስም 'ዓላዛር' ሆነ?»

«የመዝገብ ቤት ስህተት፣ ይህቺ አሁን ሰባት አመቷ ነው? በሪኢንካርኔሽን የማምነው እንዲህ አይነት ሲያጋጥመኝ ነው»

ፋሲል አተኩሮ አየኝና:

«ጊዜው የደረሰ አይመስልሽም?» አለኝ

«ሰማሽ መሲዬ» አለ ፋሲል ወደ እሷ እየሄደ:: ፊት ለፊቷ ቁጢጥ ብሎ:

«አባትሽ አይመጣም»

«ለምን?»

«አባትሽ ደርግ እያለ አይመጣም»

«ለምን?»

«አባትሽ ጥሩ ነው፤ ደርግ መጥፎ ነው»

«እንዴት?

«በቃ ይጎዳዋል እና አይመጣም»

«ለምን?»

«አለ አይደለ» ፋሲል ዞር ብሎ አየኝ

«ምን ይመለሳል ለዚህ ጥያቄ? ሺ ኢዝ ትዊስትድ[116]»

«ለምን?» አለች ደግማ

«ደርግ ሊያስረው መጥፎ ነገር ሊያደርገው ይችላል:: ወታደር መጥፎ ነው»

«አው ቃለሁ»

«እንዴት አወቅሽ?»

«ቴቢዬ ነግራኛለች»

«አዎ:: ከረሜላሽን ጨርሺና ዛሬ በሙሉ እረፍት ነሽ ከፈለግሽ ቪዲዮ እዪ፣ ከፈለግሽ ልጆችን ጠርተሽ ተጫወቺ፣ ወይም ደስ ያለሽን አድርጊ»

ባይሉጂ ላይ የተማርኩት የቦልድዊን ኢፌክት መሠረተ ድንጋይ እየተጣለ ነው:: አንድ ፍጡር፣ ተክል ይሁን እንስሳ አንድ ፀባዩን በአካባቢ ሁኔታ ተገዶ ደጋግሞ ቢሰራው፣ ከእሱ ቀጥሎ የሚመጣው፣ ወደፊት የሚወልደው ፍጡር ጂን ውስጥ ያ ባህርይ ይታተምና ተፈጥሮአዊ ይሆናል?

ማን ግድ አለው::

•

•

•

ለመጀመሪያዎቹ ሁለት አሰሳዎች አክስቴ ማልደያ ቤት አድር ነበር:: እሷ ጋ የመጣሁት ስለናፈቀችኝ ይመስላታል:: ማታ 'ምን ላድርግልሽ የእኔ እመቤት' ትለኛለች:: እንዲህ ስትለኝ ባትለኝ እወዳለሁ:: የሚያስጨንቀኝ ስተኛ የሚወረኝ ቁንጫ እንደሆነ አታውቅም:: ብወዳት እንኳን ቤቷ ማደሪያ አይደለም:: አሁን ዛሬ ሂጂ እንዲህ ላወራት እችላለሁ?:

'ስሚ ማልደያ፣ ቤትሽ አድር የነበረው ልጆችሽ ናፍቀውኝ አይደለም:: የቤትሽ ቁንጫም አያስተኛኝም ነበር:: የማድረው ድንገት ፍተሻ ቢኖር እንዳልታሰር ነው:: ገባሽ?'

ምን ትለኛለች?

በጠዋት ተነስቼ ጎረቤቶቼ ድንገት ካዩኝ በኩራት:

---

116 ጠማማ ናት (She is twisted)

'የእህቴ ልጅ እኮ ናት' የምትለውን ትላለች?

እስር ቤት መጥታ እጄን ይዛ ታለቅስ እንደነበረው እጅዋን ይዤ የመናገር የመናዘዝ ድፍረቱ አለኝ? እራሴንም እሷንና ልጆቿን አደጋ ውስጥ እንደከተትኩ ቢገባትና ፀባይዋን ብትለውጥ እቀየማታለሁ? 'ይሄ ሕዝብ ሲታገሉለት አይገባውም' እላለሁ? የአጥፊው ፖለቲካዬ መሳሪያ ደሞ ያው ባህል የሰራው ነባሩ መግባባትና መተሳሰብ ነው። የሚዋኝበትን ባህር የሚመርዝ አሳ እኔ ብቻ ነኝ። የቀረበለትን መረቅ በውሃ የሚከልስ። ከዛ ነቅተውብኝ ጠንቀቅ ሲሉ 'የእኛ ሰው ክፉ ተጠራጣሪ ነው' እላለሁ። ብልጥ ነኝ? ወይስ ክፉ?

•

•

•

ከአሞራ ገደልና ከሌሎችም ከሚታዩኝና ከማይታዩኝ አፅናፍት ወደ ሃይቁ የሚተርበው ውሃ ስውር ነው። ሃይቁ አይጎልም። ስጦታው አሁንም ስፊ ነው። ይሄ ስጦታው ብድር ቢሆን ምን ልንከፍለው ነው? አሶች የሃይቁን ጠለል ፈንጣጣ የወጣበት ያስመስሉታል። በዛ ቀዝቃዛ ጠዋት ባላጠምድም አያለሁ። ማታ ማታ እና ለምሳም በሞቱበት ሳህን ላይ የማየው ዛሬን ማለፍ የከበደውን ነፃነታቸውን ነው።

ጎመኔ የታለ?

•

•

•

እሁድ ጠዋት ከቤተክርስቲያን ምስክርንና ሳሚን ከሰራተኛዬ ጋር ፍልሰታ አቁርቤ ተመልሼአለሁ። ፋሲል ከእንቅልፉ አልተነሳም። ከአልጋው ውጭ ተኝቷል። ይሄ ልማድ አለው፡ ወደ አስራ ሁለት ሰአት አካባቢ ይነሳና ሽንቱን ሽንቶ ወደ አልጋ ሲመለስ እውስጥ አይተኛም። የተኛበት ክፍል የአደረ መጥፎ ጠረን ስላለው፣ እንዲነፍስበት መስኮት በትንሹ ከፈትኩ። ወርቃማ የጠዋት ፀሐይ ብርሃን ከጉልበቱ በታች አረፈበት። ሁለቱም የፋሲል እግሮች ከባቱ ጀምሮ በጠባሳ ተሸፍነዋል። ጠባሳው ከቆዳው ይቀላል። ከጠባሳው መሃል አልፎ አልፎ ጠያይም ደሴቶች አሉ። የአንዱ አውራ ጣት ጥፍሩ ዱልዱም ነው። ይሄን በጠባሳ የተሸፈነ እግሩንና የሚያስፈራራ ዱልዱሙን እያየሁ አልጋ ዳር ተቀመጥኩ። ይሄ ጠባሳና ዱልዱም የፋሲል ካርታ ነው። የፋሲል ካርታ የኢትዮጵያ ካርታ አይደለም። ገና እዚህ አገር አልገባም። ወደዚህች አገር የሚገባው በዚህ ካርታ እየተመራ ነው። ሱሪው ወደ ላይ ተሰብስቦ ጠባሳው እንዳይታይ ብዙ ጊዜ የትኛውንም እግሩን ጉልበቱ ላይ አጥፎ

አይቀመጥም:: ሲነተቱ ጉልበቱ የሚደርሱ ካልሲዎች ማድረግ የሚወደው ይሄን ለመሸፈን ነው:: እንዴት በአንድ ጊዜ ሰው በጠባሳው ይኮራል? በጠባሳውም ያፍራል? እንዴት በአንድ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ ሆኖ ወደ ኢትዮጵያ ይጓዛል?

እግሮቼ ቂም ናቸው:: የባሌ ካርታ በቂም ቀለም የተነደፈ ነው:: ቢድንም አልዳነም:: እኔ አልጋው ዳር ከሕይወቱ ዳርቻ የተጎለትኩ ኮረብታ፣ ካርታ እያየ ቀና ብሎ የሚያጤነኝ ንባቡን መቆጣጠሪያ ታቦር ነኝ:: ፋሲል ውስጤ ጠባሳ እንዳለ አያውቅም:: ቢያወራም ምን እንደሚመስል አያውቅም:: እውስጤ ዓላዛር የተባለ ጠባሳ እንዳለ አይገባውም:: ዓላዛር ምስክርን የወለድኩለት መረጃ ብቻ ሳይሆን ጠባሳ እንደሆነ አልተረዳም::

እግሮቼን ልዳብሳቸው ፈለኩ፣ ግን መቀስቀስ ሊሆንብኝ ነው:: በቀስታ አንሶላ አልብሼአቸው ወጣሁ::

•

•

•

ምስክር ባታም ሩጫ ወዳጅ ናት:: መንቀልቀል ትወዳለች:: ከዛ እዛ ስትል:: ነገረ ንቅናቄዋ እንደ ጥንቸል ነው:: ላስቆማት ብል አልችላትም:: ስትሮጥ ፀጉሯ እየተፈረፈረ ወደ መሬት ሊወድቅ የሚያሽቃብጥ ይመስላል:: አንዳንዴ ንዝንዝዋ ሲጠፋ እየሳምኩዋት አብሬ ብበር ደስ ይለኛል:: አፌን ጉንጭዋ ላይ አድርጌ ብንቀለቀል......

......አብዮት ጠባቂዎች በቁጥጥር ስር ሊያውሉኝ ሲሉ ያደረኩት የሩጫ ሙከራ ትዝ አለኝ:: አሁን ሳቅሁ:: እማምላክን ሳቅሁ:: ግን ደሞም አሰብኩ:: በእርግጥ ተዋጊ ነበርኩ? ወይስ ለመስዋዕትነት የምዘጋጅ በመስባት ላይ የነበርኩ ላም? ግራ ያጋባል:: በሩጫ አገር፣ ሯጭ አይደለሁም......

......ቁጢጥ ብዬ እጠራታለሁ:: መቼ እንደምቆነጥጣትና እንደማልቆነጥጣት ይገባታል:: ይሄ ዕውቀቷ ያሳዝነኛል:: ተንደረድራ መጥታ ተላትማ ሲታቀፉኝ፣ I want to cry[117]::

•

•

•

ከዓላዛር ጋር ስንተኛው የፍቅር ምዕራፍ ላይ ነበርን? እንዴት ነው የሚሰላው? ሂሳብ አለው? ደንብ አለው ከጥንት ዘመን ተረፉ

[117] ማልቀስ እፈልጋለሁ

የተላለፈልን? ከዕውን ሕይወት ይሁን ከልብ ወለድ ተጠረቃቅሞ የተበጀ ማብራሪያ ስለት?

አብረን አድረን በጠዋት ሳልቀሰቅሰው......

ቀስቅሼው በሞቀ ውሃ ፊቱን እንደ ልጅ አጥቤ

በፎጣ ሳላደርቀው......(መጀመሪያ በመዳፌ እልግለታለሁ)

ወንበር ላይ ሳላስቀምጠው......

አስቀምጬ እስኪጠግብ ሳላጎርሰው......

አብልቼ ልብሱን አልብሼ ስራው ሳልሸኘው......

አራት አምስቴ ከቢሮዬ ቢሮው እየደወልኩ በስሜቴና በጆሮዬ ትንፋሹን ሳልሰማው......

ቁልምጫውንም እንደ ምሳዬ ሳልበላው......

ምሽት እምስራበት ቦታ መጥቶ ቆሞ ወዲያ ወዲህ እያለ ፀጉሩን እየዳበሰ ሳይጠብቀኝ......

በሰፊው ከተማ እዛ እዛ እዛና እዛ በእግር ሳያዞረኝ......

ገላዬን እጠበኝ ብዬው ውሃ ውስጥ ሳልንጋለል......በዋናዬ መሃል ጣቱን እንደ ከረሜላ ሳልጠባ......

ጭር ባለ ሌሊት ቀስቅሼው 'አዝዬ ናፈቅኸኝ' ሳልለው......

ማለት እችላለሁ ፍቅር አለቀ?

ፍቅር ተጠናቀቀ?

ፍቅር ላመ ደቀቀ?

•

•

•

ፊንዛ ፈርኩስ ፈኝዞ እዛት...በ...አዋሳ በእሳቶስብ ትፈልቃለች:: አፈን ከቅባቱ አፀዳለሁ:: ካርፍም ሽመላና ቁርዬ እቆጥራለሁ:: የቅዳሚና የእሁድ ሂሳቤ ናቸው:: ሳልፍ ዋቢ ሸበሌ ሆቴልን አያለሁ:: በፋልቱነት ዘመኔ የወደቅሁባቸውን አልጋዎች በሃሳቤ እጠራለሁ:: አንዱም ትዝ አይሉኝ:: ሰበቡን ግን ከቶ አልረሳም::

•

•

•

የግሪኩን ምፀተኛ ፈላስፋ ዲዮጋንን አንዱ እንዲህ ብሎ ጠየቀው:

«በሕይወትና በመሞት መሃል ልዩነቱ ምንድነው?»

«ምንም ልዩነት የለውም»

«ታዲያ ለምን በሕይወት አለህ አንተ? ለምን ራስህን አትገልም?»

«ምክንያቱም......ምንም ልዩነት የለውም»

•

•

•

የጎረቤቴ ዶሮዎች ሳያቋርጡ ይራባ'ሉ:: አጥር ሰብረው ይገባሉ:: ጠዋት ማታ ጓሮዬ በነዚህ ሻሻቴዎች ይወረራል:: ምስክር እነዚህን ታባርራለች:: አንዱንም ጫጩት ይዛ አታውቅም፣ ግን ልትይዝ እዛ እዛ ትሮጣለች:: ላባ የለበሱ ሕልሞች ናቸው:: ታሳዝነኛለች:: አይኖቿ ውስጥ ቆራጥነት አያለሁ:: ዶሮ ማባረር ቁርጠኛነት ያስፈልገዋል? ያ ሁሉ ትኩረት ያስፈልገዋል? ጥሬ ተበትኖላቸው ለሚያዙ ነገሮች ልጄ ለምን ልብ የሚያቆስል ሩጫ ትሩጥ? *'እረፊ አንቺ! አደናቅፎሽ ብትወድቂስ?!!'*

•

•

•

ጠዋት ላይ ሸንቴን ሸንቼ ገላዬን ታጥቤ ወደ አልጋዬ ተመለስኩና የደበቅሁትን *ዲሞክራሲያ* ለማንበብ ትራሴን ሳነሳ የለም:: ፋሲል ብርድ ልብስ ውስጥ ይንጠራራል:: የነቃ መሰለኝ:

«ፋሲል የት አደረከው?» አልኩት::

አልመለሰም:: እየለገመ መሰለኝ ደገምኩት:

«ምን?»

«ዲሞክራሲያውን»

«መለስኩት ለባለቤቱ:: እዚህ ትራስ ስር መደበቅሽ ነው? የኖርሽው ነው:: ኮፒ አደርገዋለሁ፣ ኮፒ ማሽን ደሞ ተበላሸ:: የዚህ አገር ነገር:: ደሞ ምን እንደተመራማሪ ታነቢያለሽ»

«ልክ አይደለህም»

«ተኚ ይልቁን:: ነይ»

በእጁ እየዳበሰ አንገቴ ላይ ይዞ ወደ አሊጋው ሳበኝ:: እምቢ አይነት አላቀቅሁት:: ከተከናነበበት ብቅ ብሎ አየኝ::

«በሌሊት ምን ብለሽ ትታጠቢያለሽ? አይበርድሽም? እስኪ ነይ ፀጉርሽን ላሽተው» ጎንበስ ብዬ አናቴን ወደ ፊቱ አስጠጋሁ

«ፓልሞሊቭ......» አለና ወደ ጎን አየ:: ቀኝ እግሬን አጥፌአለሁ፣ ግራ እግሬን ዘርግቼአለሁ:: ከላይ ያለውን አንዱን እግሬን አተኩሮ አየና:

«ለምንድነው ጭንሽን እስኪላጥ የምታጥቢው?» አለኝ

አሰብኩና:

«በቃ ሴንሲቲቭ ነው:: ትንሽ ሳሸው እንደዚህ ይሆናል»

«በግድ ከንፁሕ በላይ ሁን ስትዪው ምን ያድርግ? ነይ.....»

የሚሞቅ እቅፉ ውስጥ ጎስጉሼ ገባሁ:: እጁን እግሬ መሃል ሰደደ:: ቀኙን እግሬን በቀስታ አነሳሁለት:: የሚሸት የጠዋት አፉን በጉጉት ሳምኩት:: የኖርኩትን ለምን አያለሁ? የኖርኩት ምኑ ይነበባል? መኖር አይበልጥም? ሕይወቱ ነው ወይስ ድርሰቱ ዋናው?

•

•

•

እማማ ልታየኝ መጥታ ነበር:: ቢያንስ በየወሩ ብቅ ብዬ ልይሽ ብላ ትመጣለች:: በዚህ ቀን ግን እንደለመደችው አታወራም:: ለአስራ አምስት ደቂቃ ያህል ዝም ብላ ስታየኝ ቆይታ የአፏን ደርዝ በአመልካች ጣትዋና በአውራጣቷ አበሰች:: እማማ እንዲህ ስታደርግ ነገር አስባለች ማለት ነው:: እንዲህ ሲሆን ደስ አላላትም ማለት ነው::

«ምን ሆንሽ?» አልኩዋት::

«እም እህ»

«አይ በቃ ደምበኛ አሮጊት ሆንሽ አሁንስ»

ነካክቼ ላናግራት......

ማሰቧ አይቀርም: *በስርአት ሳታገቢ ማቲ ፈለፈልሽ......ምንም የማይጎላት ልጄን ለምን እግዚአብሄር እንደጎደለባት ቅሪ አጣማለብኝ* እያለች:: አሁን በእግዚአብሄር ሁለት ሕፃናት እንዴት ቢቆጠሩ ነው ማቲ የሚሆኑት? እማማ የዚህ አገር ፖለቲከኛ አይነት ናት:: ወይስ እኛ ነን የእማማ አይነት የሆንነው? ይሄ ግምቴ ትክክል ቢሆንም *እም እም እህ እህ* ስታበዛብኝ አየሁዋት......አየችኝ......

«ምን?»

«አልሰማሽም?»

«ምን?»

«ስለዓላዛር»

«ምን ሆነ?»

«ምንም ይሆናል እሱ፣ አይ ቂሌ»

«ምንድነው?»

«አሜሪካ ሄደ»

«አሜሪካ ሄደ? ለምን?»

«እኔ ምን አውቃለሁ? ፀናፅልን ጠይቂአት»

«ፀናፅል?»

«እሷ ጋ ነው አሉ የሄደው»

«ምን? እንዴት?»

«ብልጦቹ የፈረንጅ አገር ያማርጣሉ፣ ቂሌ እስር ትቀምሳለች: ዲ.ቃላ ትቀፈቅፋለች»

«ምን ማለትሽ ነው? ደሞ ይሄም ብልጥነት አለበት?» እንዲህ እያልኩ ልቤ ሌላ ጋ ነው::

«ይገባኛል»

*አይገባሽም* ልላት ፈለኩ

«ይገባኛል ደብቀውኝ ከፀሐይ ነው የሰማሁት:: የፀናፅል ቤተሰቦች አይነግሩኝም? ምን ያሳፍራል? ምን ያስኮራል? ዓላዛር ማን ሆኖ ነው? አናውቀውም? ወንድ ጠፋ አሉ በአገር? ፀሐይን 'ለምን አልነገርሽኝም ቀደም ብለሽ' ስላት፣ 'ቀረ ቢሉኝ ምኑን ላውራው፣ የምገባበት ጠፋኝ' አለችኝ:: አሁን ኢዝራ ሳይሰማ ቀርቶ ነው? የሚያይዘኝ»

እንዴት ይሄ ተራ የመሰለው ነገር ሰፋ? እማማ በየትም በየትም አድርጋ ጠቅላላ ሰፈሩን እዚህ ጉዳይ ውስጥ ከተተችው:: ማውራት እንድታቆም እፈልጋለሁ:: ደሞ በሆነ መልክ የተከዳሁ መሰለኝ:: የተበለጥኩም መሰለኝ:: ውስጤ በንዴት ይቀጣጠላል:: እንደእሷ መናገር ግን አልፈለኩም......እኔስ አሁን ባለትዳር አይደለሁም? የእኔ ስራ በምን ሊመደብ ነው? እኔ ፋሲልን ሳገባ እነ ብርሃንን ማን አማከራቸው?

እማማን እንዲህ ልላት ፈልጌ......መከፋቴን የተቀበልኩ እንዲያስመስልብኝ አልፈለኩም......ለትንሽ ጊዜም ቢሆን ከእናቴ ጋር ለራሴ ማዳላት አለብኝ::

«እግዜር ልብሽን አይቶ ፋሲልን የመሰለ ልጅ ሰጥቶሻል፣ ምን ይጎለዋል? ያ ብርሃን የዱርዬ ዱርዬ እሱ ነው 'አትንገሯት' እያለ:: ሮዛ ብትኖር ነፍስዋን ይማር አታደርገውም:: አይወጣትም:: ሮዛ የፈራችው አልቀረም:: ልብዋ ንፁህ አይደለ፣ ይታያታል:: ያው መሰደድ ከመጥፋት ምን ይለያል? ምን ጎደለበት? ልጄን ልይ አይልም? በአባቱ የወጣ...... ባህርይም እንደ ደረት ሰፋት በደም ይወረሳል......ምን ያደርጋል ቢያወሩት»

ፀናፅል ለአስርና ለምናምን አመታት እሱን ለማግኘት ስታሴር የቆየች መሰለኝ:: ልጅነቴ ሲታወሰኝ እሷን መናፈቄ አበሳጨኝ:: ግራ አይነት ቅናት ተሰማኝ:: የዓላዛር ገላና አሳሳቅ፣ ሲያደርገኝ የምሆነው ነገር ውል ብሎኝ አንጀቴ ተቋጠረ:: ለእማማ ምን እንደምላት አላውቅም::

«አንድ ነገር በይ» አለች::

አፏን ጠራርጋ ወገቧን ይዛ ከተቀመጠችበት ተነሳች:: ተንጎራደደች::

«አገር መከዳት ከመቼ ከመቼ......እናኑ አላሳደጉትም? ይሄ ከሃዲ ነው......በሁ......ልጄን ልይ......አይመጣም......አይመጣም? እኛ አላሳደግ ነውም?......አላ......አላጠጣነውም? ፖለቲካ......የለበት:: ምን የለበት...... ልጅ:: አይ......ልጅ» ስትንጎራደድ አያታለሁ እንጂ የምትናገረውን በደንብ አልሰማትም:: ኩርማኑን መስማቴን እንጃ:: የዓላዛር ቅላት ሆዷ ላይ እንደተንበለበለ ነው::

አንድ እጅዋን እሳት እንደነካው ሁሉ አርገበገበች:: ስትንጎራደድ እንደሌላ ሰው አያታለሁ:: መንጎራደድዋን አቁማ ተቀመጠች:: *ምን ልበላት?*

«ሰፈር ስትመጪ......አታነሺም:: ስሙን......ብለሽ ስሙን እንዳ......:: ገባሽ? ደሞ ገና ከልጅነቱ ከአልሀ...ኮጋር አሸሼ ዴል እጸደነበር ሰማሁ:: እድሜ የማያስ...የለ:: ከሆነች......ጠንቋይ ጋር:: አስደግማበት ይሆናል:: ቤተሰቡን......የትም ሜዳ:: ታውቂ ነበር ጠንቋይ መሆኗን? በእንጀራ ነው አሉ የምትጠነቁለው ደሞ:: እንጀራዋን የሚዘጋ ይዝጋውና»

በትክክል ብሰማትም ነገሩ ስለከበደኝና ስላሳፈረኝ አልመለስኩላትም::

«የምነግርሽን አትሰሚም»

*ምን ነግራኝ ነበር?* የሰራሁት ስህተት ሁሉ እሷ እየጠቀሰች እንዳልሰራ የነገረችኝ ነው:: ባይሆንም 'ነግሬሻለሁ' ማለት ትችላለች::

አፏን መያዝ፣ ውሳኔዋን ከልብዋ መፋቅ አይቻልም: ከፋሲል ብለያይ ባትልም 'ተይ ብዬሽ ነበር ልጅ ወልዶ ሌላ ወንድ ጋ መግባት አይሆንም ብዬሽ ነበር' ልትል ነው':: ተራው ሰው እንደ ፖለቲከኞች ያሌለውን እውነት ከሬሳችን ላይ፣ ከመውደቃችን ላይ ይለቅማል:: ዓላዛር በሁለት እጆቹ እናቴን ግራና ቀኝ ይዞ እየገባ ይወጣል......

«......መሲ?»

*ሁለመናው እንደ እባብ ነው......*

«እ»

*እንገቴን ይነክሰኛል......*

«......ደህና ነው ሳሙኤል?»

*አገጬን ይነክሰኛል......*

«እ»

*አፌን ይነክሰኛል......*

«ምንድነው እ እ ምን ሆንሽ?»

......አፌ በትዝታው መረቅ ይሞላል......

......እማማ በሄደች በበነጋታው ገላዬን እየታጠብኩ ምንም ብተነትን ተንትኜ ደመደምኩ ብልም፣ ዓላዛር አሜሪካ ቢሻገርም፣ ሽሮሜዳን ቢተዋትም እንደአልሄደም ገባኝ:: እዚህ ባይኖርም ይሄው በተለወጠ የግጭት መስክ ላይ አለ:: የቦታ አያያዝ ነው:: ትንሽ ስደበር ከዓላዛር ጋር ያሳለፍኩዋቸው የልጅነቴ የቅመም ቀኖች ምላሴ ላይ ጣዕማቸው ይሰማኛል:: ይሄው ሆዴ ላይ ስድስት ጅብ የሚመልስ ስብ ይገኔ የለ? ይሄ ስብ የተጋረደበትን ቆዳ ዓላዛር ሲያቅፈው አልነበረም? ዓላዛርን ከዚህ ስብ ከዚህ ወገቤ የሚለየው ምንድነው? እኔን እማማም ማናችንም ስልጣን የለንም:: ማነው ያቀደው? ታሪክ የሚባል ፍጡር ብቻውን ምድር ላይ የለም:: የሰው ስራ ነው:: አንድ ሰው ከሆነ፣ ያ ሰው ማነው? ብዙ ከሆኑ እነማን ናቸው?

•

•

ተርታ ጊዜ:: ተርታ ሴት ነኝ? ተርታ ትሑት ሚስት ነኝ? ምስክሮን ግቢያችን ውስጥ ቅልልቦሽ አጫውታታለሁ:: ተንፈራጣ ከተቀመጠችበት ቀና ብላ ስታየኝ አይኖቿ የዓላዛር ናቸው:: እንዳጠፋሁ ሁሉ ግንባሬ ይታጠፋል:: አይኖቼን ለአፍታ እጨፍንና ያላለቁብኝን የሽሮሜዳ አረንጉዋዴ ዘመናት አስባለሁ::

«ደህና ነሽ ማሚ?»

«ደህና ነኝ»

«ታዲያ ጀምሪአ»

«ምኑን?»

•

•

•

ታቦር ተራራን ማየት ሱስ ሆኖብኛል:: የሆነ ጡት ነው:: በትንሹ የእኔን የልጅነቴን ይመስላል:: እዛ ፍንጩ አፌን ብለጉም፣ ወደ ሆዴ የሚገባው የአዋሳ ሃይቅና ውስጡ የሚንሸራሸሩ ጥሬ አሶች ናቸው:: የምትጋራኝ ምስክር ናት::

'ታቦር አያምርም?' እላታለሁ

ቀና ብላ አተኩራ ታያለች:: ምንም አትናገርም

ስታበሳጪ

•

•

•

ልጆች ነን፣ ጡት የጣልነው ትናንት፡ አፎቻችንም በመጨረሻው ጥቢ ሙሉ ናቸው:: ከንፈሮቻችን ላይ ያለው የወተት እንጥፍጣፊ ገና አልደረቀም:: ይሄንን እንረሳለን:: የበሰልን እንመስላለን:: ፍቅረኞች ጠዋት ማታ ሳያርፉ የተጣጣሉበትን ጊዜ ይደምራሉ:: መበ'ደላቸውን ይፅፋሉ:: ልብ አካውንት አለው:: ፖለቲካ ባለ ላጲስ ቆብ እርሳስ ነው:: እየፃፈ ይሰርዛል፣ እየሰረዘ ይፅፋል:: ፖለቲካ አፍረተቢስ አራሚ ነው:: የአፍቃሪዎች ልቦና ከቅዱስ መፅሃፍ ይረቃል:: ተደብቀን በእሱ እናምናለን::

•

•

•

ፋሲል እቃ ሲፈልግ የእኔን ዳልሚሽያን አሻንጉሊት አግኝቶ ለምስክር አመጣላት:: ትንሽ ደነገጥኩ:: አሻንጉሊቱን ወረወረችው:: 'ነይ ነይ እንዴ?' አልኩና በቁጣ ከወደቀበት አንስቼ ሳምኩና ሰጠሁዋት:: ቀና ብዬ ፋሲልን ማየት አልደፈርኩም:: ምስክር እንደገና ወረወረችው:: የውሸቴን እየሳቅሁ ወደ ውጭ ወጣሁ......ለብቻዬ ብስጭት አልኩ...... የምቆይበት ቆይቼ ስመለስ ምስክር አሻንጉሊቱን አቅፋ ተኝታ

አገኘሁዋት:: ፋሲል ቅን ነው:: ቅን መሆኑን አያውቅም:: አንዳንዴ ብሩህ ነው:: አንዳንዴ ጅል ነው:: በየትኛው ጎኑ ፖለቲካ እንደገባ እንጃ:: ለራሴ ስራ ፈጥሬ ፀጥ ባለ ቤት ውስጥ ደፋ ቀና እያልኩ እቃ ሳዘገጃጅና ሳፀዳዳ ከሶፋ ስር ሙዝ አገኘሁ:: ጎትቼ ባወጣሁበት መጥረጊያ አገላብጬ በእጄ ሳልነካ አየሁት:: ጥቁር ሆኗል:: ተኮማትሯል:: እዚህ ቤት ሙዝ መቼ እንዳመጣን ጊዜውን ለመገመት ሳስብ ሞከርኩ:: ትዝ አላለኝም:: ከወለል ላይ አነሳሁና አየሁት:: ለጣቶቼ ቀዝቃዛ ነው:: ሁለቱም ጫፎቹ ላይ እሳት እንደነካው ላስቲክ ተኮማትሯል:: ግማሹ ሞቅሙቋል:: በጣቴ ነካካሁና ከአናቱ ከለሰላሳው በኩል ለመላጥ ስሞክር ደስ የማይል ጠረን ሸተተኝ:: ይገፔ ወጣሁና አበባ መሃል ወረወርኩት:: መሬት ሳይነካ የሆነ ቅርንጫፍ ላይ ግራና ቀኝ እንደ እግር ተዘርግቶ ቀረ:: በር ላይ እንደቆምኩ ለደቂቃዎች አየሁት:: ያልሆነ ታሪክ አላምጦ የሚጥለንም እንደዛ ነው::

•

•

•

ግን ለመሆኑ 'ግድየለሽ' ማለት ከመቼ ወዲህ ነው ትርጉሙ የፖለቲካ ድርጊት ውስጥ ካለመግባት ጋር ብቻ የተስተካከለው? የትኛው መዝገበ ቃላት ነው ከርክሞ ያበጀው? እነማን ብልጦች ናቸው ትርጉሙን የቀመሙት? አስባለሁ አስባለሁ አስባለሁ አስባለሁ አስባለሁ የእውነት አስባለሁ:: እንዲህ ለምን ድሮ አላሰብኩም? ይሄን ባስብ ኖሮ የሚያዳምጠኝ ማነው? 'እህ' የሚለኝ እንደበት የማን ነበር?

•

•

•

ምስክር ስምንተኛ አመት የልደት በአልዋን ስታከብር በተገዙላት ስምንት ባሉኖች ትጫወታለች:: ቀለማቸው ሰማያዊ ቀይና ቢጫ ነው:: ባሉኖች አንድ ላይ እንደታሰሩ ከእጇ አምልጠው ወደ ሰማይ መውጣት ጀመሩ:: ዛፍና ቤት እላቆምቸውም ምስክር ቋለቅሳለች ደሞ ከመሃል ትስቃለች:: አሞሮች ባሉኖቹ ዙሪያ ይበራሉ:: በክንፋቸው ይመቷቸዋል:: ባሉኖቹ በትዕግስት ሰማይ እየቀደዱ ተነቃናቂ ስምንት ጥቁር ነጥቦች ሆነው ከአይናችን ተሰወሩ:: ማልቀስ ያቆመችው ምስክር ማልቀስ ጀመረች:: ፋሲል እየሳቀ ሌላ ሊገዛላት ወጣ::

# ክፍል ፲

ትርሶቻችን በሙከ። ተቀ።ር ፊር
ይምቀሉ።

# ጥብስና ጠበል



«......ሽሮሜዳ አማረም አላማረም ማንም በልቶ ጠግቦ የሚያድርባት ሰፍራ ናት:: ልጆቻችን የረጉ፣ በሳቅ በጨዋታ ነፍሳቸው የቀለለችና የተኳለች ናት:: እያድርገውና ቢያደናቅፋቸው መሬት አይነኩም:: መሬት ነክተው እንዳይጎዱ ከሚንሳፈፉበት አየር ላይ በወገናቸው በፍጥነት ይለቀማሉ:: እዬ እግሮቼንና ክንዶቼን:: ሺህ ጊዜ አደናቅፎኛል፣ ሺህ ጊዜም ወድቄአለሁ:: ምንም ጠባሳ ግን የለብኝም:: እዳሪያችን ድስት፣ መሶብና ማዕድ ነው:: የሰውን ተውኝና ባለቤት የሌላቸው ለቅልውጥ የመጡ የሌላ ሰፈር ውሾች እንኳዋን እዛ እዛ ብለው ቀራርመው የሚመሰጡበት ቁራጭ ስጋ፣ መቅኒ የለጎመ አጥንት አያጡም:: ንቦቻችን ፍጡር ናቸውና ክብር አላቸው:: ይሄም ንቁ አድርጎአቸዋል:: ጌጥ ስለሚወዱና ኪነጥበብ ስለሚያደንቁ በዐይን ማየት የሚያዳግት ቁንዳላቸውን ለማበጠሪያ ክንፎቻቸው ሽር ከሰንደል እንጨት የተበጀች ደቃቃ ሚዶ ይዘው ይበራሉ:: ከዛም አልፎ አይኖቻቸውንም ይኳላሉ:: በየቦታው ሲንዛዙ ወለላ ማጠራቀሚያ ወርቅማ ሙዳዮች በጀርባቸው አዝለው ነው:: ጣፋጭነታችን በእንደበታችን፣ በዘፈናችንና በሽፋኑን ቆዳችን ላይ አለ:: ልብሶቻችን ለአንድ ሰአት ያህል እውጭ ቢሰጡ፣ ከላያቸው የሚወርደው ዮጵ የመሰለ ማር ነው:: ጥርሶቻችን ነጫጮች ናቸው:: እኔን እዩ (እኝ):: ከብቶቻችን የሚግጡት የባቄላና የአተር ደን ነው:: (እለነገር 'ሽሮሜዳ' ተባለ መሰላችሁ?) ቅቤያችን ያለ አላቢ ከላሞቻችን ግት በራሱ ፈቃድ እየተንዠረዠረ ይወጣል:: ጆምበር ስታዘቀዝቅ፣ ብዙ 'እምቧ' ብትሰሙ የሰፈራችን ጥገቶች 'ወተታችንን ዋባዱ' እያሉ ሲለማመጡኝ ነው:: ሊታሪክ የሚቋምጥ አንድ ነገር እንካችሁ: በዚህች አለም ላይ ሽሮሜዳ ብቻ ናት የሚያቀነቅኑ ላሞች ያሉባት:: ይሄ ቀጥሎ የምትሰሙትን 'እምቧ በይ ላሚቱ' የተባለውን የሙሉቀን ታፈሰን ዘፈን በመጀመሪያ ያንጎራጎረችው 'ቡራቡሬት' የተባለች የሽሮሜዳ ላም ናት......» (*አንድ የሽሮሜዳ ወጣት ስለ ሽሮሜዳ ሰፈር በኢትዮጵያ ሬድዮ መዝናኛ ፕሮግራም ላይ ካነበበው የተቀነጨበ 1963 ዓ.ም*)

# ተናገራ ታዚና ተናገራ

እኔ እዝራ ወልደ ሲራክ.....ወልደ ታዚና......

የሚረባ ታሪክ ያላቸው ጥቂት ናቸው ቢሉንም፣ ከፋም ለማም ያሳለፍነውን ከመናገር እንቆጠብም:: ማን የማን ጌታ ሆኖ ነው በማንስ ዕውቀት ተሹሞ የረባ ያልረባ ብሎ በማላውቀው ሜትር ለክቶ የሚፈርጀኝ? ከዕለታት አንድ ቀን በሕይወታችን፣ ከለመድነው ወደ አለመድነው፣ ከምናውቀው ወደ ማናውቀው፣ በትንሹ ከተረዳነው ምኑንም ወደ አልተረዳነው የሚነዳን አጋጣሚ ይመጣል:: ይሄን የሽግግር ልምድ ለወገናችን ለማጋራት ከዕለታት አንድ ቀን ልብ እንገዛና የታሰረው የእንደበታችንን ቅስም (ማን እንዳበተው አናውቅም፣ ብናውቅም በእርግጥ አናውቅም፣ በእርግጥ ብናውቅም አንናገረውም) ከታሰረበት ፈተን ለሰሚ ጆሮ እንለቀዋለን:: ከዕለታት አንድ ቀን እያንጻንጻችን ተረትና ታሪክ እንወልዳለን:: እኔም ያ ከዕለታት አንድ ቀን የደረሰ መስሎኛልና፣ ዘርዓ ያዕቆብ ፈላስፋው በሃሰሳውና በሃተታው 'አፍን ከመክፈት ይልቅ መስማት ደግ ነው' ቢልም፣ እናንት ሆቴሌ መጥታችሁ እስከ አንገታችሁ ድረስ በጎረድ ጎረድ የምሞላችሁ ዜጎቼ ሆይ! ከአይኖቻችሁም ውስጥ የመደበርን ዕንባ አድርቄ ለጋ ደስታ የማርከፈክፍባችሁ ውድ ታዳሚዎቼ ሆይ! ታሪኬን እዝዝዝዝዝ ልበላችሁ እንደ ሕንዝዛ፣ መስማት በተሳናቸው ጆሮዎቻችሁ::

ይሄው የአገሬ ተጋሪምሮችና አዋቂዎች በፊልት[118] ባሕሩ ላይ የመልካም ጨዋታ ሐመር ቀዝፍችሁ:: ኮረዶችና ወይዛዝርትም በሁዳዴና በፍስክ

---

[118] ፊልቴር ሲቆላመጥ:: ይሄንንም ተከትሎ ፊልቱ: የማይጨነቅ ዘናጭ ልጅ:: ይሄን ቃል የእንግሊዘኛው 'ኩል' ይተረጉመዋል:: አፈላለት: አዘናን፤ መፈለት: መዝናናት ተብለው ይተረጎማሉ:: ምሳሌ: «አገራችን በዚህ ፈታኝ ወቅት ላይ ሆና አለም ሰላም እንደ ሆነ ሁሉ በየመሸታ ቤቶች መፈለት በታሪክ ተወቃሽ ያደርጋል......» በአአ ከተማ ማዘጋጃ ቤት አንድ ባህላዊ ስብሰባ ላይ በአንድ ባለስልጣን መድረክ ላይ በንባብ የተነገረ:: 1976 ዓም

አላፊ ደስታ ልትሰበስቡ በሆቴሌ ወንበሮች ላይ ሻሞ ተደረደራችሁ:: ከወገናችሁ የበለጠ ስለምን የከብት ስጋ ትወዳላችሁ? እሳት ያለሰለሰው፣ ድልህ የኳለና ያከሳተረው ያማረ የሽንጥ ኳስ በጉንጫችሁ ቋጥራችሁ በአሽሙር ስትከዳዱ ሰማሁ:: ባሎቻችሁንና ወዳጆቻችሁንም በማያስተዛዝብ *የረሻት ይሉኝታ*[119] አቃለላችሁ:: ስለ እናንተ እኔ ተንቀጠቀጥኩ:: በልታችሁ እንደማታውቁ የእህልም ዘር በዓይናችሁ ዞሮ እንደማያውቅ አሳላፊዎቼን በልምምጥ ስትጠብቁ፣ ትሪው ፈጥኖ እንዲመጣላችሁ ስትቁለጨለጩ፣ መቆጣጠሪያ ማማዬ ላይ ቆሜ ሳያችሁ ከአንጀቴ አዘንኩ:: የተማራችሁትም ያልተማራችሁትም *በሐሲር*[120] ጎዳና ሰከም ሰከም ስትሉ እንደ አንድ ዜጋ ወንድማችሁ ታዘብኳችሁ:: ጣቢታ አቅፎ በያዘ የአፋችሁ የቅልምጫ ዜማ የቤቴን አዋይ አደነቆራችሁ:: በለጋ ጆሮዎቻችሁ የሰበሰባችሁትን የገባችሁንና ያልገባችሁን ቀልድ በፋፋና በለሰለሱ ከንፈሮቻችሁ አራባችሁ:: መሰሎቻችሁን ለሳቅ፣ ለባልትና ለከንቱነት ጋበዛችሁ:: እኔም አልኩ: *ሰው ነህና በልተህና አሹፈህ ትሞታለህ:*

እንዲህ ስታደርጉ ከፋኝን? አልከፋኝም:: የጠበቅሁት፣ መሆን ግን የማይገባው ሁኔታ ሲሆን እንዴትስ ብዬ ልከፋ? ለምን እከፋለሁ? ለምንስ ቅር ይለኛል? ትናንት የተናቅሁና የማያልፍለት ፋንታሮት ጎረምሳ ዛሬ ሰው በአድናቆትና በአክብሮት ቀና ብሎ የሚያየኝ ዲታ ሆኛለሁ:: በዝቅተኛነት ስሜትና በመንቀጥቀጥ እያቸው የነበሩ ሰዎች ዛሬ ሐብት ሳፈራ ሁለመናቸውን አቀለሉልኝ:: ይከብዱኝ የነበሩ ምሁራንና ቀለጤዎች ትንሽ ሆኑ:: ሁሉ ሰው የሚያልመው (የሚያታልለት፣ የሚያስርለት፣ የሚገልለትና የሚያቃጥርለት) ለእኔ እውነት ሆኖአል::

ሳምንት የከረመ ቀይ ወጥና ጥርስ የሚነቅል ግንትር የበሬ ጥብስ ትሸጥ የነበረችው የአባቴ ታዚና ሆቴል ባልጠበቅሁት ፍጥነት ዝናዋ ተስፋፍቶ፣ ስሟ ዛሬ በአዲስ አባ ቀልባጣ ኑዋሪዎችና ቱሪስቶች አፍ እንደ ማር ከረሜላ የሚመጠጥ ቃል ሆኖአል:: 'ሰላምታ' በተባለው የቱሪዝም መፅሄት ጀርባ ላይና 'ሎንሊ ፕላኔት' በተባለው አለም አቀፍ የቱሪስት መሪ መፅሄት የእኔ ጉርድ ፎቶግራፍና የሆቴሌ ፎቶ በየጊዜው ወጥቷል:: መውጣቱ ብቻ ሳይሆን አንዳንድ ነገሮችም በአድናቆት

[119] የወሲብ ይሉኝታ:: ወሲብ ሳደረጉት ሰው ማዳላት:: በአራዳ አዝማሪ ተረትና ምሳሌ ይሄ ይባላል:
*«እኔስ መስሎኝ ነበር የተዋደዳችሁ*
*በረሻት ይሉኝታ እውነትን ስታችሁ»*
[120] ውድቀት (decadence) ቃሉ ግዕዝ ነው::

ተፅፈውላታል:: እኛ የእኛን እናምንምና በፈረንጅ አፍ ከተፃፉት ጥቂቶቹን 'እነሆ!' ልበላችሁ:......

*«......ታዚና በዛች ታሪካዊ አገር [ኢትዮጵያ] ተወዳዳሪ የማይገኝለት ከጥብስ ዓይነቶች በአንዱ---በጎረድ ጎረድ ስፔሻላይዝ ያደረገ ሆቴል ነው:: የታዚና ሆቴል ባለቤት አዝራ ታዚና በአገሪቷ የመጀመሪያውን የምግብ አሰራር መጽሐፍ (ጥብስ፣ ጥብስ እንደገና ጥብስ 1975 አአ ቦሌ ማተሚያ ቤት) ጥብስን በተመለከተ የፃፈ ሰው ነው:: ሽሮሜዳ በእንጦጦ ጎዳና ላይ ትልቁን ድልድይ እንዳለፉ በስተቀኝ በኩል ከቀበሌው [ከኮሚኒቲው] ፅ/ቤት አጠገብ ይገኛል:: ሬስቶራንቱ ሰባት የመብያ ክፍሎች ሲኖሩት፣ በመጀመሪያ ሆቴሉ ሲገቡ የሚያጋጥምዎት ትልቁና በአንድ ጊዜ ስድሳ ሰዎች ማስተናገድ የሚችለው 'ቆቃ' የተባለው አዳራሽ ነው:: በአዲስ አበባ ሆቴሎች ብዙም ያልተለመዱ ሴቶችና ወንዶችን የሚያገለግሉ በጠቅላላው ስድስት የመፀዳጃ ቤቶች ሲኖሩት፣ ወደ ሰላሳ የቤት መኪናዎች ማቆም የሚያስችል ስፍራ አለው:: ተመጋቢ በሚበዛበት እሁድና ቅዳሜ፣ ቦታ በመጥበቡ ብዙ ደንበኞች መኪናቸውን መንገድ ዳር እያቆሙ ሲገቡ አይተናል:: አዝራ በጣም ጠንካራ ሰራተኛና ሆቴሉ በቆመበት አካባቢ ባሉ ኑዋሪዎች የሚወደድ ነው::*

*......በመፅሐፉ ውስጥ አቶ አዝራ እንዲህ ይላል:*

*«በእኔ እምነት ስልጣኔና የሥጋ ፍቅር የሚገናኙት ጎረድ ጎረድ ጥብስ ላይ ነው:: ወደ ጥሬው የቀረበ ግን ለኮሶ የማያጋልጥ:: ወደ ጥብሱ የተጠጋ ግን በለጋነቱ የተመሰጠ እሱ መልካም ነገር ነው:: ከምግቦች የላም፣ የጥጃና የበሬ ጥብስ፣ ከጠረኖች የጥብስ ጠረን፣ ለምላስም የጥብስ ጣዕም፣ ተስተካካይ የሌላቸው መሆኑ እንድ ሌሊት ተከሰተልኝ»*

ይሄ ሁሉ ዕውነት ነውን? ዕውነት ዕውነት እላችሁዋለሁ ሁሉም ዕውነት አይደለም:: ብዙው ለመደለያ የወጣ ደምበኛና ሆዳም መሳብያ *ወሬ*[121] ነው:: ሰው ንግድ ሲሰራ ወይም በንግድ ስራ ሲተዳደር የሚሸጠው ዕቃ፣ የሚገዛው ደሞ የሰውን ልቡና ነው:: ደንበኛ እንዲበረክት የሰዎች ልቦና በተወሰነ ደረጃ በቅጥፈት መሞላት አለበት:: መጽሐፉ ሲራክ በምዕራፍ ሰባት "የአገርህንም ሰው አትበድል፣ ራስህንም በወገኖችህ መሃል 'አታስት' ቢለኝም፣ ጥሩ በሆነ ምክንያት ላዳምጠው አልቻልኩም:: በዚህች ትንሽ ዕድሜዬ ወዲያ ወዲህ ስል እንዳየሁትና እንደምመሰከረው ከመካሪያችንና ከእሱም ምክር ይልቅ ጠባያችን ሃያል ነው:: የገነነ ቅጥፈትና የሆረበት ተረት እንወዳለን፣ በቀላሉም እናምናለን:: ብዋሻችሁ ወድጄ አይደለም፣ እናንተን በባህርያችሁ ለማገልገል ስል ብቻ *ከስህተታችሁ ልስተካከል ነው::*

[121] ሆን ተብሎ ለማሳሳት በትክክል ያልቀረበ መረጃ

ሆቴል ስራ የጀመርኩት እንደ አባቴ አባባል 'ጥሩ ስነምግባርና ኩሽት አለው' ተብዬ ነው:: እኔ ስገምት ግን እሱ አጋኖና አሳስቶ የሚያየው ስነምግባሬና ኩሽቴ ከሆቴል ስራ አልፎ የትም ስለማያደርሰኝ ስለተረዳ ነበር:: ዕድሜዬ አራት ሲሆን መንግሥት ትምህርት ቤት ስለሚጠላ እዚሁ እንጦጦ ደብረ ሐይል ቅዱስ ራጉኤል የቤተክህነት ትምህርት እንድማር አስገባኝ:: ወደ ደጀሰላም ይወረውሩንና በአለማዊ ስራ እንድንካን ይጠብቃሉ:: ስጋ ባለበት አገር የሚመጥነው ቢላ መዘጋጀት አለበት:: የዕድሜ እኩያዎቼ መንግሥት ትምህርት ቤት ሲገቡና በዓለማዊው ትምህርት እየተሻሻሉ ሲሄዱ እኔ ዲያቆን ሆንኩ:: ቆይቶ ዘመናዊ ትምህርት ገብቼ በብሩህነቴ እርዳታ በፍጥነት ብገሰግስም ተዘባርቆብኝ ብዙ አልዘለቅሁም:: በደጀሰላም ከሥነሥርዐቴ ይልቅ በምዕመናን የሚወራለት እጅግ የሚያምር ድምጼ ነው:: አንዳንድ ሰዎችም 'ከለልቴው እዝራ' ብለው ቀዕለው ይጠሩኝ ነበር:: ይሄም ስያሜ እያስደሰተኝና እየገፋፋኝ ሳይሆን አይቀርም አስራ ስምንት ዓመቴ እስኪሆን ድረስ መጀመሪያ ራጉኤልን፣ ቀጥዬ ኪዳነ ምሕረትን አገለገልኩ:: ከዚህም ጋር ሲመቸኝ ሙያ አይጎዳምና አቶ አበበ ወልደ ጊዮርጊስ አስተዳዳሪ ለነበሩ ጊዜ ሚኒሊክ ኪነጥበብ ለአጭር ጊዜ ስዕል ተማርኩ:: ግን አልወደድኩትም:: ስዕል፣ ኪነት ምንትስ የተባለ ነገር ምንም የረባ እንጀራ እንደማያበላ ያኔም ተረድቼአለሁ:: ለሁሉ ሙግት ደጋፊ ማስረጃ ማቅረብ ግድ ይላልና ማስረጃዬ እነሆ:: ያን ጊዜ ስዕል ት/ቤት ስመላለስ አንድ ቢሮ ውስጥ 'ከበደ ሚካኤል' የተባለ ደራሲ ተቀምጦ ሲፅፍ አየው ነበር:: ለመሆኑ ያ ሰውዬ የት ደረሰ? ከበደ ሚካኤል እዛ ተጎልቶ ሲማስን ነበር:: የት ነው አሁን?

አባቴ ወራሽ አልነበረውም፤ ግን በእሱ ሃሳብ ከዓለም አደናቃፊ ድርጊቶች መቆጠቤ ስላስተማመነው አብሬው ሆቴሉን እንዳስተዳድር ጠየቀኝ/አዘዘኝ/ጠራኝ::

## ደስ ያለዎትን ቃል ምረጡ::

አባቴ ቄስ ቋዜማ ዘመናይነትን እያማረረ አንገቱን ለአመል ሰብሮ የሚሸሽ፣ ቁጡ፣ ተቺ፣ ግን ሥነሥርዐት አክባሪ ሰው ነበር:: ከቅዱሳን ገድል ይልቅ ነጋ ጠባ አባቱ የነገሩትን እሱ ግን ስለአላየው እተጌ ጣይቱ እንጦጦ ማርያም ስለአዘጋጁት ግብር ያወጋልኝ ነበር::

«ነበርክ?» እለዋለሁ መደጋገሙ ሲሰለቸኝ::

«ባልኖርስ? ከአሕዛብ ጋር እየዋልክ እነሱ የሚያስቡትን ጥርጣሬ ነው የምትነግረኝ:: ያንተ ሃሳብ አይደለም አውቃለሁ» ይለኛል:: ከአባቴ ጋር መከራከር አይቻልም:: ለፍልፌ ካለመታመን ይልቅ አንገቴን ሰብሬ

ብታመን ሳይሻል ይቀራል? ታዲያ የትም ለማይዘልቅ ነገር ምን ያናግረኛል? ለምንስ ጉልበቴን በጭቅጭቅ እጨርሳለሁ?

አዎ፣ አእምሮው ብሩህ ቢሆንም፣ ግን አንዳንዴ ትንሽ ቂልነት የሚያጣ ሰው ነበር:: አልፎ አልፎ እንደ አለማዊ መኖር ይጀምርና ከመሃል ያደገበት፣ የጎለመሰበት፣ የሸመገለበት መንፈሳዊነቱ እየገረመመ ያቆመዋል:: ዘልቆ ሊሰለጥን አልቻለም:: በንግዱ ከልክ ያለፈ ሃብታም ቢሆን፣ ሐጢያተኛ ተብሎ እንዳይታማ ይፈራል:: ድንገት ብልጠት ከተጠናወተውና ሰው ካታለለ:

«መሸበት ስጀምር ይሄ ይምጣብኝ?» ይልና መዝሙረ ዳዊቱ ላይ ለንዝዜ ይደፋል::

አባቴ ቁመቱ አጭርና የንጉሰነገስት ሐይለስላሴ አይነት ጎፈሬ ነበረው:: ጢሙ አገጩ ላይ የበቀለ ሶስተኛ እጅ ይመስላል:: ሲያወራ ሳያቋርጥ ስለሚልገው ይሾላል:: እያደግሁ ስሄድ በጢሙ ሳይሆን በጢሙ ሹልነት አፍር ነበር:: ያውም እኔን የመሰለ በራሱ ማፈር የሚገባው ጎባጣ:: የሚወደው መጠጥ ጠጅ፣ የሚወዳቸው ፍጡራን ላምና ንብ ነበሩ:: ንብ ሞታ ካጋጠመው ከወደቀችበት ለቅሞ የሆነ ነገር ያጉተመትማል፣ ፍታትም ይሆናል:: ሬሳዋን ሰው እንዳይረግጠው አፈር ምሶ የሆነ ዛፍ ጥላ ስር እንደ ሰው ይቀብራታል:: ላም ባያረባም ላም ያለበት በረት ሲደርስ አይኖቹን ጨፍኖ በእበትና በኩበት ጠረን ይመሰጣል:: ምንም ባይበላ ወተት ወይም እርጎ ካገኘ ግድ የለውም:: ትንሽ ያበዛው ከመሰለኝ ይሄንንም ሃሳቤን ገጼ ላይ ካነበበ 'አንድ አገር ሲያምርበት፣ አንድ ስፍራ መልካም ሲሆን 'ማርና ወተት ያፈሳል' ሲባል አልሰማህም?' ብሎ ይስቃል::

ሁነኛ ሰው ነው ስለሚባል አባቴ ጋ ለምክር የሚመጡ ብዙ ሰዎች ነበሩ:: ከሚስቶቻቸው የተጣሉ፣ ልጆቻቸው ያስቸገሯቸው፣ ወዘተ:: ጥሬ መካሪና አንደበተ ትብ ነበር:: ለብቻችን ስንሆን:

'አንተ ጣፎንጋ መልኬ ባይደርስህ እስኪ ከአንጎሌ ትንሽ ውሰድ' ይለኛል::

አንድ ነገር ሊናገር ሲፈልግ በዙርያ ጥምጥም ነው:: ረዥም ክብ ሰርቶ 'የት መሄዱ ነው?' እየተባለ እየተጠረጠረ፣ ታሪክ ጠቅሶ፣ ተረት ተርቶ፣ ዞሮ ቁጭ ያደርጋል:: እሱ ደግሞ ወይም ነቅፎ የተናገረው በሲሚንቶ የተመረገ እውነት ይሆናል:: የሚያስፈራ ትባት አለው:: አንዳንዴ እንዴት ብሎ በታምራት አምኖ ቄስ ሊሆን እንደቻለ ይገርመኛል:: እንኮበር፣ ዲማና ጎንደር ስለተማረ አይመስለኝም:: የተፈጥሮ ብሩሕነት ነበረው:: ለአንድ ጉዳይ ሁለት ሶስት ምሳሌ ያመጣል:: የፈላሰስፋው ወልደ ሕይወት ተረቶች ምሳሉ ጉያ ይዞአቸው የሚዞር የአንደበቱ ስረስር ናቸው::

አንዳንዴ በማይገባኝ ምክንያት ይደበርና ዝም ይላል:: 'ውሃ አቀብለኝ' ብሎ ለመናገር ይከብደዋል:: ግንባሩን ይከሰክሳል:: ትልቅ የብራና መጽሐፍ በምጥ ከሳጥኑ አውጥቶ እንዳነብለት ጭኔ ላይ በዝምታ በቀስታ ያስቀምጣል:: እሱ እዛ በርጩማ ላይ ቀጥ ብሎ ጋቢውን ተከናንቦ ፊቱን ብቻ እያሳየ ይጎለታል:: ጎኑ አጎዛ የለበሰ ድኳዬን (አጎዛ ካላነጠፍኩ ጀሮው ክፍት አይሆንም ቄሱ) አመቻችና 'አቁም' እስከሚለኝ አነብለታለሁ:: ስህተቴ ካስመረረው ያርመኛል:: ንባቤ መሃል ከንፈሩን ይመጣል:: ካነበብኩለት ቀን ጀምሮ ለሁለት ቀኖች ያህል ዝም ይላል::

'የቃሉ ክብር ይሄን አፌን ይዘጋልኛል፣ ካንቀለቀለህ ቅዱስ ቃሉን አንብብ' ይላል:: አንቀልቀሎት ነው ያስነበበኝ? ወይስ ሲያሽሙዋጥጠኝ ነበር?

ትዝ ይለኛል አንድ ማታ፣ አጠገቡ አስቀምጦኝ ከማልደያ ቤት በማንቆርቆርያ ገዝቼ ያመጣሁለትን ቀዝቃዛ ጠላ እየጠጣ (ደብቶ ስለሚያስተኛው መሰለኝ፣ አልጋው ላይ ተጋድሞ የሚጠጣው) ጠረጴዛ ላይ የተዘረገፉትን የሆቴሉን ቁልፎች እያሳየኝ:

«ስማ አንተ ደንባዛ:: ያ ሁቴል ያንተ ነው:: እኔ ብጥር ብጥር ላሻሽለው አልቻልኩም:: አልሆን አለኝ:: ያው መሬቱ አለ:: ሰፊ ነው:: ቤቱ አለ:: ለመጀመር በቂ ነው:: ጎበዝ ከሆንክ ምን የመሰለ የተስፋፋ አድርገህ መስራት ትችላለህ፣ ታድግበታለህ:: ብዙ የማላውቀው ነገር አለ:: አዎ ብዙ የማላውቀው ነገር ቢኖርም፣ የማውቀውን አውቃለሁ:: የገባኝንም ዕውነት እነግርሃለሁ:: አባት ሌላ ማድረግ የሚችለው ነገር ምንድነው? አንድ ወጣት ዕውነትን ካስተማሩት እውነተኛ ይሆናል:: ውሸትም ካስተማሩት ውሸታም ይሆናል:: ከባድ አይደለም:: ውሸታም ልጅ ከቤተሰቡና አብረውት ከሚኖሩት በዕድሜ ከሚበልጡት የተማረው ነው:: ተረት ልንገርህ:: አንድ አባትና ልጅ ጎጆአቸው ፊት ለፊት ቆመዋል:: አባትዬው የታወቀ ውሸታም ነው:: ይበላዋል፣ ውሸት ካልተናገረ አይውልም:: ልጁን እንዲህ አለው: 'ስማ ልጄ እዛ ሰማይ ላይ ምን ይታይሃል?' ልጁ ቀና ብሎ ወደ ሰማይ አየና 'ደመና አያለሁ፣ አዎ ወፍም አለ' አለው:: 'ሌላ ምንም አይታይህም ልጄ?' 'ምንም አይታየኝም አባባ' አባቱ ቆጣ ይልና 'እግዚአብሄር ጤፍ ሲያበራይ እያለሁ' አለው:: ልጁ ግራ ገባው:: አባትዬው ቀጠለና: 'እንዴት አይታይህም:: በጥቋቁር በሬዎች ነው ደሞ የሚያበራየው' ልጁ ከአባቱ ጭቅጭቅ ለመገላገል 'አባባ ካልክስ ዕብቁ በዐይኔ ገባ' አለው:: አለም ትልቅ አስተማሪ ናትና አንዳንድ ነገር በእውነት አውቃለሁ:: የማውቀውንም ዕውነት እናገራለሁ:: የሰማኝም ያን ዕውነት ይናገራል:: ውሸትም እንዲሁ እንደ ዕውነት፣ እንደ ሃብትና እንደ በሽታ ከሰው ወደ ሰው ይተላለፋል:: እንዲህ ስልህ ገና በማሕፀን እያለ የተረገመ ወይም የተመረቀ የለም ማለቴ አይደለም:: እግዜር አሳምሮ የሰራው አለ:: የረገመውም አለ::

«ሰማኸኝ? እተጌ ጣይቱ ከአድዋ ጦርነት በኋላ የንግሥና በዓላቸውን ምክንያት በማድረግ ግብር አስገብተው ነበር:: የዚያ ዓይነት ግብር ታይቶ አይታወቅም ነው የሚባለው:: እና በዚያ ግብር የታረደው ከብት ብዛት ስድስት ሺ.ህ ይደርሳል ይባላል:: ጠላና ጠጁ በቦንባ በቀርከሃ አሸንዳ ሆኖ እንደ ገፈርሳ ውሃ ነበር የሚቀዳው:: የምግቡ ጠረን ማንም የሚያወራለት ነበር፤ በእንጦጦ ዙሪያ እንደ መቀነት ተጠምጥሞ ልብ ይሰውር ነበር አሉ:: እንግዲህ አባቴ እዛው ደብር ነበር የሚማረው:: ልጅ ስለሆነ ድግሱ መግባት አልቻለም:: አሁን ነው እንጂ እንጦጦ እንዲህ እንደው ባዶ ተራራ አልነበረችም:: ጥንትም ከተማ ነበረባት:: 'እንዶጥናህ' የተባለ:: አጤ ይኩኖ አምላክ ነው የሰሩአት:: በኋላ ግራኝ ያጠፉታል:: እና ሚኒሊክ ትንቢት አንብበው ነው አሉ እንጦጦን ከተማ ለማድረግ የመረጡት:: የድግሱን ነገር ሳልረሳ......በአራተኛው ቀን ነው አሉ ንግስቲቱ 'መኳንንቱን በአለፈው የሶስት ቀን ግብዣ አሰላቸነው' ብለው፣ የተለየ ምግብ ለማዘጋጀት አቀዱ:: ለዚህ ልዩ ምግብ የሚሆኑ አምስት ጥሩ ላሞች ታረዱ:: እና እንግዲህ የግብር ቦታው ሁለት መግቢያ ነበረው:: አባቴ በአንዱ ደጃፍ በድፍረት ተደብቆ ይገባል:: እውስጥ ገብቶ የሚያደርገው ጠፍቶት ፈዞ እንደ ቆመ፣ ተበልቶ ሊያልቅ ሲል ነበረና አንዲት ሴትዮ ወዲያ ወዲህ ሲቁለጨለጭ አይተውት ጠርተው መልካም ዳረጎት ከዚያ ከተራረፈው እንጀራና ለምለም ጥብስ ያጎርሱታል:: እሱን በአፉ ይዞ በእጁ ደግፎ እድንኳኑ ደጃፍ ሆኖ ሲበላ ልቡ ተሰወረ:: ሁለት ነገር አልረሳም አለኝ:: አንደኛው የዚያ ምግብ ጣፋጭነት፣ ሁለተኛ ያጎረሱኝ ሴትዮ ጣቶች:: 'ምክንያቱስ?' በል አንደኛ የዚያ ዓይነት ጥብስ እስከ ዛሬ አልበላም:: ማንም የሚለው ነው:: እስከዛሬ ያን ዓይነት ጥብስ ከጥቂት መኳንንቶች በስተቀር በማንም አልተበላም:: ሁለተኛ በሁዋላ ያዩ ሲነግሩት ሴትዮዋ ለካስ ጣይቱ ናቸው:: ንግሥቲት ራሳቸው:: እነዚያ ጣቶች በስራ ብዛት በመገርደፋቸው የስራ ቤት ጣቶች ናቸው:: ከአውራጣታቸው እና ከመዳፋቸው መገናኛ ላይ ስለት ቆርጦአቸው ጠባሳው አለ:: አንባር መዋያቸው ላይ ትልቅ ማርያም የሳመችው ምልክት አለ:: መልከ መልካም አይደሉም ግን እንደው ጠጋ ብለው ሲያዩአቸው ግርማ አላቸው:: ሲነግረኝ 'ይሄንን ታሪክ የሚያምነኝ የለም' እያለ ነው:: የሚያምነው የለም:: 'አንደኛ፣ ንግሥቲቱ የሚቀመጡበትን የተመቸ ቦታ ትተው አንድ ኡሪ እየተናፈጠ እቆመበት ማድ ቤት ስር ምን አመጣቸው? እንግዲህ ልትሸነግለን ያላየኸውን አየሁ በማለት ለጉራ የተናገርከው ነው እንጂ እዛ በመጀመሪያ የሚያስገባህ የለም:: ሁለተኛ፣ አንተን ከቁም ነገር ቆጥሮ እጅህን ጎትቶ አስገብቶ የሚያስጎርስ ምንም ምክንያት አለ? ሶስተኛ፣ 'ንጉስ ግብር ባልጠ'ራም እገባለሁ ደፋር ነኝ' ለማለት ከሆነ ለደፋርነት ለደፋርነቱ አራዳ ለአራዳ ከመልከስከስ፣ ለምን ማይጨው አልዘመትክም?' ይሉታል:: በእርግጥ ያልዘመተው ፈሪ ሆኖ

ሳይሆን ሚስቱ አራስ ስለነበረችና (የእኔን ታናሽ ወልዳ) አጠገቧ ማንም ዘመድ ስላልነበራቸው ሊጠብቃት ግድ ሆኖበት እንደሆነ ማንም ያውቃል:: ታዲያ ሊሞት ሲል እንደአደራ እንዲህ አለኝ: 'በየትም በየትም ብለህ የእተጌ ጥብስ እንዴት እንደ ተሰራ ከአዋቂ፣ ከነበረ ካየ ሰው ጠይቀህ፣ ከተቻለ መጽሐፍም መርምረህ ሁቴል ቤት ክፈት'

እስኪሞት ስለዚህ ነገር የሚያብራራለት ስላጣ 'ማን ይናገር የጠበሰ' ይል ነበር::

«አባቴ የጥብሱን አሰራር አንዳንድ ዋና ዋና ነገሮች ተፈላስሞ ቢደርስበትም የሁሉን ቅመም ዝርዝር ሊያገኘው ግን አልቻለም:: ተስፋ ቆርጦ ተወው:: እኔም እሱን ለመምሰል ቅስናዬን ችላ ብዬ ሆቴል ከፍቼ ብሞክር ይሄው እንደምታየው አልቻልኩም:: ስለዚህ ጊዜው የዕውቀት ስለሆነ፣ አንተ አንድ ልጄ በተቻለህ አቅም ይሄንን ለማድረግ ብትሞክር የእኔም ይሁን የአያትህ ነፍስ ከመቃብር ወዲያ እረፍት ታገኛለች:: አያትህ ጥሩ ነጋዴ ነበር ግን ለምርምር እያለ በድብቅ ጥብስ እየጠበሰ ሲበላና፣ (አልሆን ሲለው ለውሻ ሲጥል) በከተማ እየዞረ ጥብስ ሲያሳድድና ለጥብስ ጥራኑን ሲያጥብና ጥራኑን ሲረብሽ ነው የኖረው:: መቼም ለዚህ ለዚህ ፍተሻው ወደ ሁቴል በሄደ ቁጥር ማወራረጃ መቀማመሱ አልቀረም:: በዚያው ሰካራም ሆነ:: እንደምታየው እኔም ሰካራም ባልሆንም ከእሱ አልተሻልኩም:: አያትህ ያላጠናቀቀውን የንግሥት ጥብስ ፍለጋ በሁቴሌም በየትም በየትም ብል አደራ እንዳለኝና እኔም እንደተመኘሁት አልቀናኝም:: እንደምታየው ሳይሳካልኝ ማለፌ ነው:: እና ልጄ አትርሳ ሁቴሉ አለ:: ብትሰንፍ እንኩዋን መልካም የሚያሳድር ገቢ አለው:: ማሴጥህ ካላበላሸህ ጥሩ ከተሜ ሆነሃል:: ያ የአያትህንና የእኔን ሕልም እንደምንም ብለህ ስራ ላይ አውል:: እሱን ብቻ አድርግ:: ሌላ አልጠይቅህም:: ያ ጥበብ መከሰት አለበት:: ካሌለ ታዲያ ንግስቲቱ እንዴት አገኙት? ላሞቹ ከሰማይ አልወረዱ፣ ቅመሙ ከኢዮር አልመጣ:: ግን ቶሎ አልሆነም ብለህ ተስፋ አትቁረጥ:: ፅናት ያስፈልጋል:: ሁልጊዜም:: መጽሐፈ መክብብ እንዲህ ይላል: 'የአንድ ነገር ፍጻሜ ከጅማሬው ይሻላል፣ ትዕግስተኛም ከትዕቢተኛ ይሻላል'::

«አንዳንዴ ቂልነት፣ ብልጠት ሆኖ፣ ኩሸት መስሎ የሚጠናወተው ሺዎችን ኸረ ሚሊዮኖችን ነው:: ሁቴሏን በትዕቢትህ እንዳትንቃት:: በቀጥታ ቀርቶ በእጅ አዙር እንዳትንቃት:: መጥፋት ራስን ከመናቅ ይጀምራል:: 'መሃል ከተማ ይሻላል' ብለህ ሽጠኻት እንዳትሄድ:: ሸሮሜዳ ቀላል ቦታ አይደለችም:: ለመስፋት የተመቸች ናት:: ልንገርህማ ታሪክ:: ታሪክ መቼም ትወዳለህ:: ታሪክ ነው የምትወደው ወሬ ነው?

'ማን ያውራ የነበረ' ይባላል:: ኩሬው ውስጥ የነበረ ያወራል፣ ከኩሬው ዳር የነበረም ያወራል፣ ኩሬውን በፎቶ ያየም ያወራል፣ ስለኩሬው ከታሪክ የሰማም ያወራል፣ በፍርድ የሰለጠነም ስለኩሬው ያወራል፣ መልካም

አእምሮ ያለውም በዕዳት ስለኩሬው ይገምታል:: እውነት ግን ሁልጊዜም የእግዚአብሄር ናት:: በሁሉም ስልት ኖረዋል የተባሉት እናኑ የብርሃን መስቀል ዘመድ፣ የሮዛ አያት ስትናገር የሰማኋት ነው:: ይሄ የሽሮሜዳ መሬቱ ሁሉ የእሷ ነበር:: ከንግሥት ዘውዲቱ የተሰጣት:: ሴትዮዋ ፊደል አትለይም:: ከአፏ የሚወጣው ግን መጽሐፍ ምሳሌ ማለት ነው:: ታሪኳ ሰማይ ቤት የመሄድ፣ ሰይጣን የማባረር ገድል አይነት አይደለም:: ሰማኝ:: ከቤተክርስቲያን ከወጣሁ በኋላ ያየሁት ነገር ቢኖር ክንፍ ባይኖራቸውም ከሚካኤል የሚተካከሉ ሰዎች በየቦታው መኖራቸውን ነው:: ስለ ሚካኤል ሳነብ ስለ ሰዎች የማነብ አይመስለኝም ነበር:: ሰው ሰዉን ከአደጋ፣ ከሰይጣናዊ ሃሳብና ድርጊት ሲያድን ያው ሚካኤል ሆነ አይደል? አንተን ደጀሰላም ያስገባሁት ላካክስ ሳይሆን ይቀራል? (ካስከፋሁህ ይቅርታ አድርግልኝ ልጄ) የእናኑ ጎረቤት ናት ሰንኬት የምትባል ወዳጄ ነበረች:: እሷ ወዳጄ ስትነግረኝ ይህቺ እናኑ በጣሊያን ጊዜ ብዙ አርበኛ እየደበቀች አድናለች:: ጣሊያን ሲወጣ ለድግስ የመጣው አርበኛ እነገረሱ አልቀሩም፣ ጎላ ሚካኤልን በጠላቸው በጠበጡ፣ ፌሽታው ሌላ ነበር:: አርበኛ መሆንዋን የሰማሁት ከሰው ነው:: እሷ አንዲት ቃል አትናገርም::......ረሳሁት የተነሳንበትን......ሽሮሜዳን እንዳትተዋት ልልህ ነው:: ለምን መሰለህ? እሷ እናኑ ያወጋችንን እነግርሃለሁ:: ቦታውን ለመሸጥ ፈልጋ እንዴት ሸነሸነችው መሰለህ? ድሮ የነበረውን የእግር መንገድ ተከትላ:: ድሮ ሰው ሲጓዝ ያወጣው የእግር መንገድ፣ የከብት መንገድ አለ አይደለ? 'እሱ አስፋልት ይሁን፣ ድንጋይ ይነጠፍበት:: ሰው ይጓዝበት' አለች:: ዛሬ ሽሮሜዳን እዛ እዛ የቆራረጣት መንገድ ሁሉ የጥንቱ እግር መንገድ ነው:: አስፋልቱም የጥንቱ እግር መንገድ ነው:: እሷ እንደምትለውማ 'የእግር መንገድ እንደ ሐውልት እንደ መጣፍ ታሪክ አለው:: አባቶችህና እናቶችህ በሰሩት፣ ስንት አዋቂ በሄደበት መንገድ ብትሄድ ምን ብሎ ይጎዳሃል? እንዲህ ስትል ሳቅሁባት:: ፊደል ሳትቆጥር መጣፍ ሳታነብ ከእኔ ብሩህ በመሆኗ መሰለኝ፣ እንጂ ሴት አደለች? አዋቂ ማለት አየህ ካየው ከመረመረው ተስማሚና ጤነኛ የሆነ ነገር ጨምቆ ሲያወጣ ነው:: የጨመቀውንም መልካም ጨዋ ጉዳይ ሲሰራበት ነው:: እና እናኑ 'አጓጉል ጀምረህ አጓጉል ተጉዘህ ወደ ኋላ ከመመለስ በታወቀው ሂድ መጀመሪያ:: ሺህ ሰዎች በሕይወታቸውና በኑሮአቸው የመረጡትን መንገድ አንድ ፈረንጅ አገር ተማረ የተባለ መሐንዲስ ሊያሻሽል አይችልም' ትላለች:: እንደሚባለው ጣይቱ ከፍልውሃ እንጦጦ ማርያምን ሊሳለሙ ሲወጡ የሄዱበት መንገድ ዛሬም አለ:: መቼም አዲስአባን ሊቆረቁሩ ሲያስቡ......በዚህ በኩል በእግር እየሄዱ፣ በበቅሎ እየሰገሩ ነው:: በሰይፈ ቤት በኩል የእንዳልካቸውን ቤት ታኮ ከእኛ ሁቴል በላይ ወደ ዳገቱ የሚወስደው ቀጭን የአስፋልት መንገድ ድሮ የእግር መንገድ እያለ እሳቸው ወደ ፍልውሃ ይወርዱና ይወጡበት ነበር:: መሃል ሰፈር ከብርሃን መስቀል ቤት ጀርባ ያለው ቦኖ ሚኒሊክ

ድሮ አድዋ ድል አድርገው ሲመጡ ግቢ ተመግባታቸው በፊት አርፈው የአላማ ሰንደቅ የተከሉበት ነው:: በወሬ መሃል እናኑ ስታወራ እንደምትለው አንድ ወደላ ነው ‘ፈረንጂ ማል በርባዳ!’ ብሎ ጮሆ ባንዲራውን የተከለው:: የዛሬው ቦኖ የተቆፈረው በዛች ቀዳዳ ነው:: እንድ ክንድ ብቻ እንደተማሰ ውሃ ቡግ አለ:: ምን የመሰለ ውሃ:: ከፊሉ እሱ የኪዳነ ምሕረት ጠበል ነው ዛሬ:: አሁን አሁን ደረቀ እንጂ ግራዚያኒ የሚባለው ሰው በታኒካ እያስጫነ ከዛ ይጠጣ ነበር:: ያን የሚጭኑት አስካሪስ የነበሩትን ሁለቱን በዐይን አውቃቸዋለሁ:: አንዱ መርካቶ ጫማ ሱቅ አለው:: አንዱ ምን የመሰለ የጣልያን ምግብ ቤት እዛ ቢያሳ አለው:: የሁለተኛው ወንድም እዚህ ታች አሜሪካን ኤምባሲ አካባቢ ይኖራል:: ታንተ ዝቅ ያለ ዕድሜ ያለው ልጅ አድርሷል:: ሰውዬው አንዳንዴ ብርሃን መስቀል ቤት ይመጣ ነበር:: መረሳ የሚባል:: ሰላምተኛ ሰው ነው:: የልቡን ነገር እግዜር ይወቅ:: ይሄን ሁሉ እምልህ ሽሮሜዳን ንቀህ ሁቴሏን እንዳትሸጥ ለማለት ነው:: ይህቺ እናኑ መቼም ብሩህ ሴት ብትሆንም ሁሉ ነገር ልክ ናት ማለት አይደለም:: አንዳንዴ ጤነኛ ያልሆነ ነገር ታወራ ነበር:: እንዲህ አይነት ሰዎች በየቦታው አሉ:: አወቅን አወቅን ብለው የማያጥቡት ነገር የለም:: ቅድም ስለ ጣይቱ ጥብስ ነግሬህ ነበር:: ይህቺ እናኑ የያን ጊዜ አለሙን ያስገረመው ወጥ የተሰራው ከዱባ ነው አለችኝ:: አንድ ሰው ምንም ቁም ነገረኛ ቢሆን ከመቶ መቶ የተተካከለ ነገር ይናገራል ብሎ ማመን ይቸግራል:: ዱባ ምን አለው? ቢሆን እንኳ በዱባው ሌላ ነገር ቢከቱበት እንጂ፣ ‘በጨው ደንደስ በርበሬ ተወደስ’ እንደሚሉት፣ ምንም የረባ ነገር የለውም:: እናልህ ያ አባቴ ያደነቀውን የበላውን የጥጃ ጥብስ ማንም መኳንንት በለመደ ምላሱ ያጣጣመውንና ያረጋገጠውን ‘ዱባ’ ነው አለች:: ሰው መቼም ይሳሳታል:: ሲሳሳትም ይታረማል:: ‘አይ ተይ’ ስላት፣ አልረሳውም ያለችኝን: ‘የብብታችሁን ጠጉር ነጭተው የጎሽ ነው ቢሏችሁ ታምናላችሁ:: ሰነፍ ሁሳ’ አለችኝ:: ካዳመጧት እሷ የማይወራም ታወራለች:: ‘እተጌ ጣይቱ አልሞቱም’ ትላለች:: አልቅሰን ቀብረን:: እዛ ቤተ መንግስት እሳቸው ስራ ቤት ስለኖረች ያወቀች መስሏትም ይሆናል ......ሰው በአንዱ ተሳስቷል ተብሎ የተናገረው ሌላው ትክክል ጉዳይ አይካድም:: ዋናው መመራመርና መጠየቅ ነው:: ሰማኸኝ አይደል? መመራመርና መጠየቅ......

«መቼም ደሞ ሰው ምድር ላይ ሲኖር መዋሸቱና ማታለሉ የማይቀር ነው:: ሰው ነዋ:: ይሄ አሁን የምጀምርልህ የእናኑ ነገር አይደለም:: ሌላ ጨዋታ ነው:: እናልህ እዚህ ማርያም ለማስቀደስ አንድ ባውሎስ የተባለ ግሪክ ይመጣ ነበር:: አንድ ነው ሐይማኖታችን:: ስለት ተስሎ ይደርስለታልና እዛ ሲመጣ ተዋወቅሁት:: ወዳጅ ሆነን እዚህ ታዚና እንገናኛለን፤ አንተ ገና ድክድክ ትላለህ፣ ደስ ያለውን ምግብ በእውቅ አሰራለታለሁ:: ሳይፀልይ አይበላም ነበር:: የወደድኩትም በዛ ነው::

እንደው ሁሉን ሲቀምስ፣ ቢቸኩል እንኳን አማትቦ ነው:: አንዳንዴ ይመጣል ያገሩን አረቄ ይዞ:: አይ ታዲያ ስንጫወት ማምሸት ነው:: እንግዲህ ደህና ጨዋታ መሃል ሰይጣን ጥልቅ ይላል አይደል:: እንደ ጨዋታ የሐጢያት መግነጢስ የለም:: ባውሎስ 'ጥንቆላ ላሳይህ' አለኝ:: ነገር መጣ አልኩ:: እኔ ያቺን የአገሬን ጥንቆላ እንኳን አልሞከርኩም:: ያልሞከርኩት ሐጢያት እሱ ነው:: ራሴን ለመከላከል መፍትሄ ስራይ እንኳን አልሰራሁም:: ለልጅ ነው መናዘዝ ዋና ነገር:: ስንት የማውቃቸው ከብረዋል በጥንቆላ:: እንዳልኩህ ማታ ላይ ይሄ ግሪክ ይመጣል፣ እላይ አሁን ሰይፉ ከሚኖርበት ደሞ ቀኝ ጌታ ዮፍታሄ ነበር እሱም ይመጣል፣ እንደው ሆቴል ያደረ መንገደኛ ይመጣል፣ ሰው አይመራርጥም መጫወት ነው:: ያን ሐጢያት ተማርኩ:: 'ምን?' በለኝ:: ጥንቆላ አይደለም:: ብልጠት ነው፣ ሙያ ነው:: ታዲያ ባውሎስ:

'አንተን ሰይጣን እንዲጠራህ አደርጋለሁ' አለኝ::

'አይ ባውሎስ አታደርገውም፣ አንተ ዘርህ ሃይማኖተኛ ነው፣ ያላየሁብህን ነገር ከመቸ' አልኩት

'አይ እንግዲህ አታውቀኝም' አለና አደረገው:: ከጨለማ ከእዳሪ የሆነ ድምጥ 'ቄስ ታዚና' ብሎ ሲጠራኝ ሰማሁት:: እዛ የተቀመጠው ሰው ሁሉ ሰማ:: ደነገጥን::

'አይ አስብለው እንደገና: ማን ይፈራል የማርያም አሽከር' አልኩ:: በሴት ድምፅ 'አንተ ቄስ አርፈህ ጠጣ' ሲል ሰማነው ሁላችን:: 'አይ' አልኩት ያን ግሪክ 'ውጣልኝ':: ከት ብሎ ሳቀ:: ለካስ ጥበብ ነው ነገሩ::

'ጠብህ ሳይበዛ አንተ ጅል ላፍታታልህ' አለና ብልሃቱን አብራራልኝ:: ለካስ ***ቶትኮኝ የለሽ*** ነው:: 'አትኩኝ የለሽ' ማለት እንግዲህ ምንድነው? አንተ እዚህ ትሆንና እንደው በጥበብ ድምጥሕ ከሌላ ቦታ የመጣ ማስመሰል ነው:: እዚህ ሆነህ ተደጅ የመጣ ማስመሰል......እንደዛ:: 'አስለምደኝ' አልኩት: 'እምቢ' አለ:: 'ምነው? ምን ቆርጦህ ጥበብ ላላስተምር ትለኝ' ስለው:: 'አንተ ተንኮል አለችብህ፣ አእምሮህ ብሩህ ነው:: እና ይሄን ነገር ተለመድክ ሰው ትበድላለህ' አለኝ:: 'አይ አላወቅኽኝም እሳ' ብዬ ጠዋት ማታ ስጎተጉተው ተዋዋልንና በየጊዜው እየመጣ አፍ ገጥሞ መናገር አስተማረኝ:: አፌን ገጥሜ ድምጤን እሻግሬ መወርወር ተማርኩ:: ታዲያ ባውሎስ እንደተነበየው በደንብ መቻሌን ካወቅሁ በኋላ ለክፉት አደረግሁት:: ሴት ቆንጆዎች ባሉበት እየሄድኩ ስራዬ ከእኔ እንዲተኙ መንገር ሆነ:: ቆንጆ አታልፈኝም ሆነ:: ከእዝጌር ወይ ከሰይጣን የተኙ ሳይመስላቸው አይቀርም:: ግብር ውሃ ስትወጣ ብቻዋን ካገኘኋት በቃ አለቀላት:: 'አንድ ሳር ባርኔጣ ያደረገ ልጅ እግር፣ ፊተ ስልካካ በበርሽ ነገ ልክ አስር ሰአት ላይ ያልፋል:: እግዜር የላከው ነውና አስተናግጂው' እላታለሁ:: በዛ ሰአት እኔ ሽቅርቅር ብዬ

በቤቷ ማለፍ ነው:: 'አንተ ሰውዬ አንድ ነገር ልጠይቅህ ና እስኪ' እባላለሁ በሴቷ:: ምን ያህል ዲቃላ ወልጄ ይሆን? ስንት ትዳር ፈርሶ ይሆን? እንጃ ልጄ:: እንዲህ እንደነገርኩህ ያሰብኩት ዋናው የጥብሱ ነገር ያልሆነልኝ አእምሮዬ በዚህ ተዘግቶ መሰለኝ:: መከየንና ክፋት አብረው አያድሩም:: ያንተ በእግዜር ሕግና ትዛዝ መሰማራት ምናልባት ከእሳት ቢያድነኝ:: አትበድል ሰው:: 'የልጅ አመሳሶ የለውም' ይባላል:: አለው እዝራ:: ልጅ በልቡና በአእምሮው በራሱ ትክክል ሃሳብ ካላደረ መናኛ መርዝ ይሆናል:: በአእምሮህ እደር:: ታዲያልህ ስፈራ ስቸር ቆይቼ አንድ ቀን ስለ እኔ የፈረደው በሞላ ትክክል እንደሆነ ለባውሎስ ነግሬው ይቅርታ ጠየቅሁት:: ከዚህ ከልቤ ሁሉን ይቅርታ እጠይቃለሁ:: ላንተ ይሄን እውቀት ያላስተማርኩህ ትንሽ ተንኮል ስላለችብህ ነው:: ሁቴል አወርስሃለሁ:: ቤቴን አወርስሃለሁ:: ቃሌንም አወርስሃለሁ:: መልካም ምክር ሃብት ነው::

«ሌላ የምነግርህ ነገር ቢኖር እድሜህ ሳይገፋ ሚስት አግብተህ ልጅ መውለድ እንዳለብህ ነው:: ይሄን ሁሉ ለማን ትተህ ትሄዳለህ? ዘር ጥሩ ነው:: ሁሉ ሰው በእግዜር ዐይን እኩል እንደሆነ ማንም ይነግርሃል:: ልክ አይደለም:: በሰውም ይሁን በእግዜር ዐይን ሰዎች ሁሉ እኩል አይደሉም:: ማባበያ ነው:: ከአፈር ብንፈጠርም ሲመስለኝ ከተለያየ አይነት አፈር ነው:: ሚስት ስታገባ ወንድ የማታውቅ አግባ:: ሃብት ይኑራት አይኑራት አይደለም:: መጠንቀቅ ያለብህ ለትዳር ድፍን ሴትን የመሰለ የለም:: ለምን?' በለኝ 'ለምን?' ማለት ጥሩ ነው:: ድፍን ሴት ማለት ላይና ታቿ ልክ እንደ ሸንኮራ አገዳ የተዘጋ ነው:: ውስጧ ማንም ያልነካው መረቅ ነው:: በማሕፀንዋ ያለው አየር ክፋት ያልገባው ነው:: ምድርና ሰማይ ሲፈጠር አዳምን ያቆመው፣ ከእግዜር ጋር አብሮ የማገው አየር እዛ ነው ያለው:: ዮሐንስ አፈወርቅ: 'የሃጢያት ምንፃፍ የማታውቅ ነውር የሌለባት ድንግል ሴት ክብር ናት:: እንዲህ ያለችቱ ሴት ነፍሳት በጸጋና በክብር በተገኙበት ጊዜ ዋጋዋን ታገኛለች' ይላል:: በዘመኑ እኮ የበኩር ልጅ እየጠፋ ነው:: ለምን ሀሞተ ቢስ ሆነ ዘመኑ? ለምን ደደብነት ይነካካዋል? ለምን ጅል እየበዛ ሄደ? ለምን ፈሪ ተትረፈረፈ? ሀሞት ቢኖረው አእምሮ፣ አእምሮ ቢኖረው ሃሞት ለምን ሙሉውን አጣ? የበኩር ልጅ ስላልሆነ ነው:: ቤቶቹ ዘመናዊ ትምህርት ለመማር ሲሉ ትዳር ለመመሥረት ሲዘነቁ ዕድሜያቸው ሲገፋ አያስቻላቸውምና ከወንድ ይገናኛሉ:: ይሳሳታሉ፣ ከዚያ በተገኘው በዘመኑ ወይ በባህል መድሃኒት ያስወርዳሉ:: እንዲህ ካልሆነም ዘግይተው ያገባሉ:: ትዳር ሲይዙም ማህፀናቸው ደንግጧልና እንደ ልጃገረድ ዘር አይቀበልም:: ይሰንፋል:: የበኩር ልጅ መጀመሪያ የተወለደ ወይም የተወለደች ማለት አይደለም:: ቁጥር አይደለም:: ያለ ድንግልና መበ'ከር የለም:: የዛች አይነት ሴትና ትንሽ ሃብት ደስታ ነው:: ልጆችህ ጠንካራ ይሆናሉ:: ከግዜር ጋር:: ፍቅር የሁዋላ ጉዳይ ነው:: ሲለማመዱ፣ ሲተሳሰቡ:: ከሌላ ወንድ ጀምራ

የመጣች ሴት አትሆንህም፣ ትዝታዋ ባልሆነ ጊዜ እየተነሳ ይረብሽሃል:: ባኋ የሞተባት እማ ይብስባታል:: ባትችልበትና ባይሆንልህ ባኋ የስቃያትን ምረጥ:: ትዝታዋን ትፈራለች:: እመርቅሃለሁ 'የበኩር ልጅ ይስጥህ' ብዬ:: ሌላም ሌላ ጉዳይ አለው እሱስ:: ሌላው ልጂ የራስህ አብራክ ሲጣፍጥህ ነው:: ሰማህ? ሰማህ እዝራ? 'ማስተዋል የጎደለውን ወጣት ብስለት ከሌላቸው መሃል አገኘሁት' ይላል ምሳሌ:: ሰማህ እዝራ?»

'ምርቃቱ ትደርስልህ ዘንድ ቢጠራህ 'አቤት!' ቢልክህ 'ወዴት?' ብለህ አባትህን አክብረው' ይላል ሲራክ በምዕራፍ ሶስት:: እኔ ልጁ እዝራ ይሄን ምክሩንና ታሪኩን እንደፈንጠዝያና የራሱን ፍርሃት መግለጫ እንጂ ከቁም ነገር አልቆጠርኩትም:: የትውልዴ አንዱ መስመር ኑፋቄ ነው:: ማፈር ቢገባኝም አላፈርኩም:: የማዳምጠው በከፊል የንቀት ፈገግታ ነበር:: ለመሆኑ እናቴን ያገኛት በዚህ በአትኮኝ የለሽ ጥበብ ጠምዷት ነው ወይስ በእርግጥ ወዳው ነው? እኔ የተወለድኩት በተንኮል ቅንብር ነው? ባልጠይቀውም በልቤ ግን አስሳለሁ::

ከሰፈሬ መሃል ቆሜ ቀና ስል የማየው ኮረብታ፣ ጅብ፣ ዛፍ፣ ገደል፣ ደን፣ ጠጣ፣ ቀበሮ፣ ሚዳቋ፣ እንቆቆ፣ የዶጋ አባሎ፣ ግራር፣ ምንትስ ነው:: ዝነኛዋን የታወቁ ሰዎች መፍለቂያ የሆነችዋን የአያቴን እንጦጦን አልነበረም:: በኩርንቷን ፊንፌኔ በሞቀ ውሃ የነጠቀቻትን ኮረብታ አይደለም:: ጊዜው የተለወጠ ነው:: አባቴም ያምናል:: ታዲያ ለምን በእሱ የትዝታ ዝገት እሰለጥናለሁ? ብፈልግስ በዚህ ዘመን ይቻላል? አብዮት ፈንድቶ ብዙ ነገር ሲወራና አገሩ በዘረፋ አዋጅ ሲጥለቀለቅ አባቴ ቄስ ታዚና ምንም አልተጨነቀም:: አንድ ማታ ከዚያው የሆቴላችን መውጫ ላይ የዕዳት ሰራተኞችን ሙርይ የሳተው አይበሮ[122] ሞራ አንሸራቶት ሲሚንቶ ላይ ወድቆ ምኑ ላይ እንደተጎዳ እንኳን በትክክል ሳይታወቅ በሶስተኛው ቀን ሌሊት አልጋው ላይ ሞቶ ተገኘ::

አባቴ ቄስ ታዚና ፍስሐፅዮን፣ ብዙ ወዳጆቼ በተበታተኑብኝ አብዮታዊ በተባለው ዘመን ሕይወቱ አለፈ:: እንደ እሱ ሃይለኛ አእምሮ የነበራቸው ጥቂት ነበሩ:: እንደ አልባሌ ነጋዴ፣ ውሐ ውሐ በሚሸት አቡጀዲ ተጠቅሎ ሲያልፍ እንደማንኛውም ሰው ታዘነለት:: እንደ ማንኛውም ሰው ተለቀሰለት:: እየተቆጣ ቢያስከፋኝም፣ እንደበቀርቱ ዕንቁ ትዝ ሲለኝ፣ የተናገረው ሁሉ ጸልፍ ሳይል ተፈፅሞ ሳይ፣ ምክሩን ያንጓጠጥኩበትን የልጅነቴን ጊዜ፣ ደደብነቴን ሰደብኩ:: እሱ የሞተ ዕለት እድርተኛ ከመጥራቴ በፊት፣ ለጥቂት ሰአታት አጠገቡ ተቀምጬ የትኩስ ሬሳውን ግንባር እየሳምኩ፣ ጭል ያለ ፊቱን እያየሁ አለቀስኩለት::

ከአባቴ ጋር ሆቴል ውስጥ እየሰራሁ ሳላቀዋርጥ ለፆምና ለሰንበት ለቤተክርስቲያን ከእኔ የሚጠበቀውን አገልግሎት እሰጥ ነበር:: በሞት

[122] የስጋ ቁራጭ

ሲለየኝ ግን ስራ ስለበዛብኝ ሆቴሉ ላይ አተኮርኩ:: የመከረኝን ብዙዉን በኩሽቴ አላጠፋሁትም:: ምን ጠንካራ እንዳረገኝ እስከዛሬ አላውቅም:: ብቻዬን መሆኔ ይሁን፣ ወይ በዚያን ጊዜ በረባው ባልረባው ያልተከረከመ የልጅነት ተስፋ ውስጤ ስለነበር፣ ወይ የምሰማውና የዘመርኩት የእግዜር ቃል በቀጥታ ወደ ሰውነት ይተረጎማል ብዬ ስለማምን ይሁን እንጃ::

እኔ እዝራ ታዚና ከአስርቱ ቃላተ ኦሪት እስከ ሐዲስ መንፈሳዊ ያሉትን ዋና ዋና ትምህርቶችንና ሕግጋትን በነቂስ እከተላቸው እንደ ነበር አብሮኝ የኖረ ሁሉ ይመሰክራል:: ግን እንደማንኛውም ዓይነት ልምድ (ግልፁኑ እንደ ስጋዊ ልበለው) ይሄ አቋዋሜና ሰምነቴ የአባቴ የሙት አመት ዕለት በ1971 ኦም ግንቦት 14 እሁድ ጥያቄ ውስጥ ገባ ወይም ልዩ ራዕይ በመሰለ አጋጣሚ ተፈተነ:: ከዚህ በሁዋላ ሰይጣን በልቦናዬ አደረ......‘እንዴት?’ በሉ:: ለሁሉም ነገር ‘እንዴት?’ ማለት ደግ ነው::

## ‘እንዴት?’ ማለት ልመድ

## ‘እንዴት?’ ማለት አባትህን ገደለ?

## ከመዝ ውዕቱ ራዕያ[123]

በዛ የአባቴ ሙት አመት ምሽት ከአጎቴ ጋር እቤት እንደተቀመጥን 'ወንድ ወሰን ሞጆ' የተባለ ረዥም ጎልማሳ ሰውዬ፣ ለሆቴላችን እንጨት ያመጣልን የነበረ የሰፈራችን እንጨት ነጋዴ፣ በሁዋላ አብዮት ጠባቂ የሆነ፣ የጠላ ሻጯ የማልደያ ባል፣ እንጀራ በትሪ (እሱ የተሸከመው) ወጥ በጎድጉዋዳ ሳህን (ልጁ የተሸከመችው) ይዞ መጣ:: ከተቀመጥኩበት ተነስቼ ሰላምታ ሰጠሁዋቸውና እሱ የያዘውን ትሪ ተቀብዬ ወደ ጉዋዳ ስገባ፣ ልጅቷ ሰሃንዋን ይዛ ተከተለችኝ:: ትሪውን አስቀምጬ ልጅቷ የያዘችውን ጎድጉዋዳ ሳህን ከእጆቿ ስቀበል ፊቷን አየሁት:: አይኖቼ ከአይኖቿ ላይ መነሳት ተሳናቸው፣ እግሮቼ ተሳሰሩ:: የዓይኖቿን ጥቁርና ነጭ የመሽኮርመም ሽፋሽፍት በከፊል የከለላቸው ነበሩ:: እድሜዋ አስራስድስት ይሞላ ይሆን? ወደ ሳሎን ተመልሰን አገልጋያችን ራት እስከታመጣልን ስንጠብቅ፣ አባቴ ይወደው የነበረው ነጠላ ሶፋ ላይ ተቀምጣ ነበር:: ጎዳ ኩታ ተከናንባለች:: ኩታው ያረፈባቸው ያኮረኮሩ ጡቶቿ የሚያምር ረቂቅ ዲብ ሰርተዋል:: ያነባበረቻቸው ባቶቿ ተስተካክለው የተሰሩ ነበሩ:: ገፅዋ ብዙ ብዙ አለማዊ ነገር አሳሰበኝ:: ከበሉና ከጠጡ በሁዋላ አባቷ: 'በይ ማከዳ እንሂድ' ብሎ ተናገረ:: ……በዚያች ትንሽ ሳሎናችን ቆማ ስትራመድ……የስጋ ፍላጎቴ በደም ስሬ እሳት ለቀቀ:: አባቷና አጎቴ ከገቢ መለዋወጥ ያወቁብኝ መስሎኝ ተንቀጠቀጥኩ::

ከዛ ቀን ሰአት ደቂቃና ሰኮንድ ጀምሮ ማከዳን ከሕሊናዬ ልሰርዛት አቅሙ አልነበረኝም:: በመንገድ ሳገኛት የሚንቀጠቀጥ የቦቅቧቃ ሰላምታ ከማቅረብ በስተቀር ላናግራት እየፈራሁና እያፈርኩ ሳልፋት ቆየሁ:: መጽሐፍ ሲራክ 'ከመልከመልካም ሴት ዐይንህን መልስ' ቢልም፣ ገና ከሩቅ ሳያት ሰፈሯ ሌላ ቦታ እንዲሆን እመኛለሁ:: ባልወለድ ኖሮ ብዬ እፀልያለሁ:: ሰላምታ ሰጥታኝ ስታልፍ፣ ራሴን ልስት ትንሽ ይቀረኛል:: በአጋጣሚ ከተሳለፍን መኖሬና አለመኖሬ ትዝ ባይላትም እንኳን እኔን

[123] ራዕዩም እንደዚህ ነው (ግዕዝ)

አሳስቶ ለማጥፋት ሰይጣን እንደላካት አምኜ ሁለመናዬ በፍርሃት ይርዳል:: በሕልሜም በዕውኔም ያልጠበቅሁት እንቅፋት ላይ ወደቅሁ:: በልቤ እንደ አንድ ወንድ ለዚህ አይነት ጉዳይ አለመዘጋጀቴ ራሴን አሳዘነኝ:: በዝግታ ሰው ሳይሰማ በሚስጥር ብጠየቅ እል ነበር: *አነ አፍቀራ ከመ እም*[124]::

ከዕለታት አንድ ቀን ለሁለት እንግዶች የታዘዘ ምግብ ሰርቼ መብያ አዳራሽ ስመጣ፣ ያቺ ማክዳ የተባለች ልጅ ከአንድ ሱፍ ከለበሰ ሽቅርቅር ጎልማሳ ጋር ተቀምጣ አየሁዋት:: በድንጋጤ ተረብሼ፣ ከያዝኩት ትሪ ላይ ተስተካክለው የተቀመጡት ሙሉ አንድ ቀይ ወጥና አምቦ ውሃ ተንሸራተው ወደቁ:: ልቦናዬ በእሷ ትዕይንት ተዘርፎ እንዲህ እንደማደርግ የሚጠረጥር ሰው አይኖርም:: *ይሄ የአጋንንት ስራ ነው* አልኩ:: ሁሉን ነገር ከወለል ላይ አፀዳድቼ አሳላፊ ቶሎ ሌላ ምግብ እንዲሰራላቸው ነግሬ የማክዳንና የወዳጇን ስሜት ለመሰለል ከማድቤት ስመለስ ቦታቸው ላይ አልነበሩም:: ምግብ ቤቱ መሃል ቆሜ በድንጋጤ ማለክለክ ጀመርኩ:: ራሴን ከመ ምንትኒ[125] ተቆጣጥሬ ወደ ጉዋዳ ስመለስ በማድቤት መስኮት፣ ልጅና ማክዳ እጅ ለእጅ ተያይዘው ወደ መኝታ ክፍል ሲሄዱ አየሁ:: መጮህ ቃጣኝ:: ያዘዙትን ማዕድ ለሁለተኛ ጊዜ ይዤ ወደ ተከራዩት ክፍል ስሄድ፣ በሩ ተዘግቶ መስኮት ግን በመጋረጃ እንደነገሩ ተጋርዶ ደረስኩ (የማይረባ፣ በታጠበ ቁጥር ሴንቲ ሜትር በሴንቲሜትር እያጠረ የደሃ ሴት የስራ ቀሚስ የመሰለ):: ሁለመናዬ በቅናት ይተራመሳል:: በሩ ከመድረሴ በፊት በቅድሚያ በተከፈተው መስኮት መጋረጃውን በትንሹ ገለል አድርጌ(አጥብቆ ጠያቂ የእናቱን ሞት ይረዳል) ወደ ውስጥ አየሁ:: «በስመአብ!» አልኩና ጮህኩ:: የያዝኩት ትሪ ዘሎ ከእጄ ሊወጣ ትንሽ ነበር የቀረው(ጉድ ያልሆንኩት ከቀድሞው ስህተቴ ተምሬ መሰለኝ):: ከመኝታ ቤቱ የልጁ አላጋጭ ሳቅ እየተንከለከለ ተከተለኝ:: ትሪውን በረንዳ ወለል ላይ አስቀምጬ፣ አንድ ሰራተኛዬን ጠራሁና ምግቡን እንዲሰጣቸው አዘዝኩት:: ማድቤት ገብቼ በአእምሮዬ የሰረፀውን የማክዳን ራቁት ገላ ምስል በስየታና በሃጢያተኛነት ሳብሰለስል፣ አንድም ደህና ስራ ሳልሰራ ቀኑ እንደ ቀንድ አውጣ እየተጎተተ መሸ:: ይሄን ጭንቀቴን የተረዳው ወዳጄና ረዳቴ ጌታቸው: «የሐጢያት ስራ የትም አለ እዝራ:: ብዙ ብዙ ነገር አለ:: ወጣቶች ስነስርዓት ማክበር ካቆሙ ከርሞአል እኮ»

ጌታቸው ሚስጥረኛዬ ነው:: ጌታቸው እንደ ወንድሜ ነው:: ጌታቸው ከገጠር እዚህ ኪዳነምሕረት ሊቀድስ የመጣ ልጅ ነበር:: እዛ በሽኩቻ ጨዋታ ተለማምደን ወዳጅ ሆንን:: አባቴ ከሞተ በኋላ ለኪራይ

[124] እንደ እናት እወዳታለሁ

[125] እንደ ምንም(ግዕዝ)

እንዳይከፍል ቤቴ አመጣሁት:: በሽኩቻ ጨዋታ ዛሬ እሱና እኔ በመገረም የምናነሳው፣ አንድ ጊዜ እንኳን አሸንፎኝ አለማወቁ ነው:: መርፌ፣ መቀስ፣ ሰይፍ፣ መዶሻ:: እንዴ እንኳን አሸንፎኝ አያውቅም:: በዚህ ምክንያት አሩቱ ሁሉ በእኔ የበላይነት የሚፈፀም መሆኑን ሳይገምትና ሳያምን አልቀረም:: ታዲያ መደንገጤን ሲያጤን ዲያቆንነቴ ያን ማየት የጠላ መሰለው:: ልቤ ግን በቅናት፣ በሐጢያትና *በትኩነት*[126] ተሞላች:: እና ከዚያ ነው የጀመረኝ በጥብስ ፍቅር መለከፍ:: እንዴት? እንዴት? ሳያቋርጡ 'እንዴት?' ማለት ደግ ነው:

## አትስነፌ

አንድ ማታ አራት ሰአት ተኩል አካባቢ ዘግይተው የመጡ ሰዎች ለማስተናገድ ስጋ ቆራርጬ መጥበስ ጀምሬአለሁ:: ያን ጊዜ ገና የማስፋፋት ምኞቱ አለ እንጂ ሆቴሌ የዛሬውን አይነት ጎረድ ጎረድ ጥብስ መስራት አልጀመረችም:: በሃሳብ ሰምጬ፣ ስጋውን መጥበሻ ላይ ሳንጉዋልል፣ ከመሃል በድንጋጤ ባነንኩ:: የስጋው ክትፋት አስደነገጠኝ:: የጥብሱ ጠይም አስደነገጠኝ:: ይሄ ጥብስ ሳያቋዋርጥ አእምሮዬ ውስጥ እንደ ደም የሚመሳለሰውን የምሽት እግረ--ፀሐይ ያረፈበትን የማክዳን ገላ ይመስላል:: ማክዳ ጠይም ናት:: በጣም የሚገርም አንጀት የምታምስ ጠይም ናት:: መጥበሻውን ከእሳት ላይ አንስቼ ስጋውን አተኩሬ አየሁ:: ጨው በላዩ ነሰነስኩና አንድ ፍሬ አንስቼ በላሁ:: በዐይነ ሕሊናዬ እዚያች ማክዳና አባላጊዋ የገቡበት መኝታ ቤት መስኮት ፊት ቆሜአለሁ:: እሷ በጀርባዋ ተንጋላ ቢጫ የአስራ ሁለት ሰዓት የፀሐይ ብርሃን ከእግሯ እስከ ውስጥ ሱሪዋ ድረስ ይፈሳል:: ጠይም ቆዳዋ ልዩ ምትሃት እያወገገ አየዋለሁ:: በግራ ጭንዋ ውስጥ የብር አምባር ያደረገ እጅ ወደ ላይ እየወጣ ይመለሳል:: የዚህ እጅ ባለቤት ያንን የመሰለ ገላዋን አያየውም:: ይሄ እጅ ውበትን ሳይሆን የሚገባበትን ጉድጉዋድ ይሻል እንጂ:: ጥብሱን እያላመጥኩ መዋጥ አልቻልኩም:: ወደ ማክዳ ራቀትነት እየዳህኩ ነበር:: በሐጢያት ተለጉሜ ነበር:: በአፌ የያዝኩትን ጥብስ ዋጥኩና ቤቴ ገብቼ ዘግቼ ተቀመጥኩ::

ሲነጋ፣ አልጋው ላይ ሪቂቴን ቀቅምጬ እንዲህ አልኩ: *የሚያምር የሚስብ የሚያስጎመጅ የስጋ ጥብስ የማክዳን የቆዳ ቀለም መምሰል አለበት*:: የጥብስ ቀለም እንደ ማክዳ ጭን ጠይም ከሆነ የሚጠላው የለም፣ የሚንቀው የለም:: ቀኑ *መጋቢት 23 እሁድ 1973* ነበር:: አልጋ ላይ እንደ ተቀመጥኩ እጆቼን እንደ ፀላይ አጣምሬ የለመድኩትን

---

[126] ሌሎች ሰዎች የሚሰሩትን መልካም መካሪ መስሎ በማጣጣልና በመተቸት የራስ ተራ ሲደርስ ግን ቀድመው የተቹትን የሌሎችን ድርጊት በድብቅና ካልተቻለ በግልፅ መስራት::

አቡነዘበሰማያት አድርጌ ለመደምደሚያ ከ'አሜኔ' አስከትዬ እንዲህ አልኩ: ***አንሰ ገብሩ ለማክዳ***[127] ይሄ አንሰ ገብሩ ለማክዳ 'አብዮታዊት እናት አገር' ወይም 'ታጋይ ይሞታል ትግል አይሞትም' እንደሚሉአቸው ዓይነት መፈክሮች ነው::

ከዚያን ቀን በሁዋላ የታዚና ሆቴል አዲስ ሕይወት ተጀመረ:: በሃሳቢ ሳወጣና ሳወርድ ቆይቼ ቤት ፍራሽ ስር የተቀበረውንና ባንክ የተከመረውን የአባቴን ገንዘብ ሁሉ ሰባስቤ አዲስ አይነት ሆቴልና የምግብ አዘገጃጀት ጥበብ ለመጀመር ዕቅድ ዘረጋሁ:: አባቴ በሕይወት እያለ ሆቴላችን ከጀርባው አስር የሚደርሱ መኝታ ቤቶች ነበሩት:: እነዚህን አልቤርጎዎች ወደ መኪና ማቆሚያና ወደ መብያ በረት ለወጥኳቸው:: ለክፍሎቹ ጋሞ(ጥቂት ጊዜ የአሶ ስጋ ይሸጥበት የነበረ)፣ አዋሳ(የዓሣ ጎረድ ጎረድ ይሸጥበት የነበረ)፣ ሻሸመኔ(እናቴ እዛ ነው የተወለደችው)፣ አረና(አያቴ የተወለዱት እዚያ ነው)፣ ደጋ ዳሞት(ፊልተሬን የማልሰው ማር የማስመጣው ከዚያ ነው)፣ በቾ(የእንጀራዬ ጤፍ የሚጫነው ከዚያ ስለ ነበር) እና ዋናው ትልቁ አዳራሽ ቆቃ (ሁሉ ያለ አዲስአባ እሳት አይበስልምና፣ አያምርምና) የተባሉ ስሞች አወጣሁላቸው:: በጀርባ በኩል ከመኪናው ማቆሚያ አለፍ ብሎ ያለውን ረባዳ ቦታ ዕርጥበቱና ዋልካነቱ ሕንፃ ለመስሪያ ስላልተመቸ ዝንጥላ ዘርግቼ ደንበኞቼን ማስተናገጃ አመቻቸሁት:: ስፍራው ዘባጣ ስለሆነ ድስት ይመስላል:: ('ድስቱ ጋ ማነው የታዘዘው? ፍቅረኞቹ ተናደዋል አንድ ነገር አድርጉ!' እንላለን:: ለደንበኞቻችን ያለማመድናቸው ግን 'ሚኒ ጋርደን' ብለን ነው:: (ደካማ ሰዎች ስለሆንን ምንም አይነት መርዝ በፈረንጅኛ ከተበጠበጠ ከወተት አስቀድመን እንደምንጠጣው የሕይወታችን ድርሳን ውስጥ ተመዝግቧል:: ከአዋቂዎቻችንም አንደበት እንደ ቅዱስ ቃል ይፈሳል:: ይህቺ የ3000 አመታት ታሪክ ምናምን የምትለዋ ነገር ለእኛ አይነት ጉረኞች አትሰራም:: (ወእሆ/ ወይ እግዚአብሄር ሆይ) ብዙዎቻችን እንደ ጨርቅ ብንጠመዘዝ ከውስጣችን ተንጠባጥቦ የሚወጣው ፈረንጅና ፈረንጅ ነኬዎች በምላሳቸው፣ በድርሳኖቻቸውና በማባበያ ሙርጣቸው በአንጎላችን ማሕፀን የዘሩት ባርነታችን ነው) ጋርደኑ ከስሩ ሰባት ያህል ትናንሽ ጠረጴዛዎች የሚያዘረጋ ዝልል ነው:: እኔም አንዳንዴ ሰደንበኞች ካልተያዘች ቤት ውስጥ መቀመጥ ሲሰለቸኝ ወደ ሚኒ ጋርደኗ እሄዳለሁ:: ወደ ረባዳዋ በቀስታ ስወርድ ንፁሕ ድንቅ የደጋ ዓይነት የአየር ፀባይ ያጋጥመኛል:: ይሄ ግልፅና አስገራሚ በትንሽ ሜትሮች ዕርቀት ውስጥ የሚከሰት ለውጥ ሁልጊዜ እንዳስገረመኝ ነው:: ክረምት ክረምት የዚህን ቦታ ፈሳሽ በቦይ እየመራሁ አወጣዋለሁ እንጂ እስከ ጥቅምት ግማሽ ድረስ በውሃ ይሞላል፣ በድንክ እንግጫ ይደፈናል:: ከስር የሳሩ አረንጉዋዴ፣ ያነጠፍኩት ቀይ

---

[127] እኔ የማክዳ ባርያ እንጂ (ግዕዝ)

አሸዋና ከላይ የሆቴሌን ቢጫ ቀለም የተነከሩ በቀይ ቀለም 'ታዚና' የሚል የተፃፈባቸው ትንንሽ ድንኳን የሚያክሉ ዣንጥላዎች ሲዘረጉ ቦታው ያምራል:: አንዳንዶች እንደሚሉት: 'ፈረንጅ አገር ያለን ይመስለናል':: እዛ ሄዶ የሚቀመጥ ሰው ከሚያጋጥመው ፀጥታ ጥልቀት የተነሳ ከአዲስ አባ የተገለለ ሊመስለው ይችላል:: ይሄን ገለሌነት የበለጠ ለማጠናከር፣ የረባዳዋን ጠንፍ ሶስት ጫማ እርዝመት ባለው የሽክላ ግንብ አጥሬዋለሁ:: ይሄ ግንብ ሰውና አየር የሚያስገቡ አራት ትናንሽና ትላልቅ ክፍተቶች አሉት:: ከወዲያ በኩል ዋናው የሆቴሉ ሕንፃ ግድግዳ ላይ ወደ ረባዳዋ አቅጣጫ የጊዜውን ምርጥ የተባሉ ዘፈኖች ሳያቋርጥ የሚያፈስ ትልቅ ስፒከር ተሰቅሏል:: ከዳገት ላይ ሆኖ (ከጋርደኑ ወዲያ ማለት ነው) ሆቴሌ ሲታይ ትልቅ መርከብ ይመስላል:: ያየ ሁሉ የሚለው ነው:: ይሄ ቦታ የሚፈልጉትን መጠጥ ይሁን ምግብ አዝዘው ብቻቸውን ለመሆን ለሚሹ ፍቅረኞችና ሚስጢረኞች የተደላደለ ስለሆነ በእነሱና በሚመስሉት ይዘወተራል::

ማዕድ ማቅረቢያ ሰደቃዎቼ የመጡት ከባህር ዳር ነው:: ከፍታቸው ከወገብ ዝቅ የሚል፣ እንደ ቀስተደመና የተዝጎረጎሩ፣ የአገሬ ባንዲራዎች እንደ መቀነት ዙሪያቸውን የተሰራባቸው ናቸው:: የሚለብሱት አረንጓዴ ጨርቅ ቅጠልያ ቀለም የተነከረ ሸማ ነው:: ደርዙም እንደታቦት ዣንጥላ የወርቅ ዘርፍ የመሰለ ነገር አለው:: የሆቴሌ መቀመጫዎች በሙሉ ባሕላችንን መሠረት ያደረጉ ናቸው:: የኩርሲዎቼ እንጨት ጥቁር እስኪሆን በዘይት የተወለወለ ነው:: ይሄንን ያደረገልኝ ዐይነ ስውር በቅርብ ሕይወቱ ባልታወቀ ምክንያት ስላለፈ ስማቸውን 'ልዋጥህ' ብዬዋለሁ:: የልጁ ስም 'ልዋጥህ አማርከኝ' የተባለ ነው:: ኩርሲው ጎራብጠኝ ለሚል ጥጋበኛ ትናንሽ ትራሶች አዘጋጅቻለሁ:: ትራሶቹ ላይ ከፊት ለፊት ከብራና ስዕል ላይ የገለበጥኩት እልጋ ላይ የተኙ ሰለሞንና ሳባ፣ ሲገለብጡት ደሞ ጡጦ የሚጠባ ሚኒሊክ ቀዳማዊ አሉባቸው:: ደንበኞቼ ይስቃሉ:: ሳቅም ይሸጣል ጃን::

በተጨማሪ የሆቴሌን ውስጥ የትም በማይገኙ የባህል ዕቃዎች አስጌጥኩት:: ለምሳሌ ማሞ ወልዴ በ1960አም ኦሎምፒክስ በሜክሲኮ ከተማ 10000 ሜትር ሲሮጥ የለበሳት ቢጫ ቁምጣ (ቤቱ ድረስ ወስዶ አስተዋውቆ ለእኔ እንዲሰጠኝ ላግባባው ለአቶ ሱራፌል ዳኜ ምስጋና አቀርባለሁ)፣ ዝነኛው ብስክሌተኛችን ገረመው ደንበባ ለመጀመሪያ በኦሎምፒክ ሲሳተፍ የነዳት ብስክሌት የሁዋላ ጎማና(ሆቴሉ ደጃፍ ደንበኞቼ መግቢያ በር ከፍ ብሎ ግድግዳ ላይ ሰቅዬዋለሁ) የተወዳዳሪዎቹ ፎቶ (ፎቶውን ከአትሌቲክስ ፌዴሬሽን፣ ጎማውን ገረመው ራሱ ከተዋውቅሁት በሁዋላ ታሪኩን ሲናገር ሰምቼ ለዘላለም ሆቴሌ ስራ ካላቆምኩ በነፃ እንዲበላ ቃል ገብቼለት ስጦታ የሰጠኝ---ከዚያ በሁዋላ ገረመውን ሆቴሌ ያየሁት ሶስት ቀኖች ብቻ ነበር):: በተጨማሪም

በጣሊያን ጊዜ ለመጀመሪያ ኢትዮጵያን ወክሎ በብስክሌት እሽቅድድም ተወዳዳሪ የነበረው ጀግናው የቸሃ ተወላጅ ካሳ ፈዲል ፋሺሽቶችን አሸንፎ ሲገባ (ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከባሪያዎቹ ጋር ማንም ጣሊያናዊ ውድድር እንዳያደርግ ተከለከለ ይላሉ) ደጋፊዎቹ የዘፈኑለት ዘፈን የተቀዳበት ከኢትዮጵያ ሬድዮ ሙዚቃ ላይብረሪ ትንሽ ጉቦ ከፍዬ ያገኘሁት ሸክላ አለ:: (በዚህ ኤልፒ ላይ 'ከዘማሪዎቹ ድምፅ ጎላ ብሎ የሚሰማው የይድነቃቸው ተሰማ ነው' ብሎ የነገረኝ ሰው አለ:: ሸክላው በማርጀቱ ዘፈኑ ውስጥ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ እየተደጋገመ የሚሰማው ስንኝ ይሄ ብቻ ነው: *ሰሙ ካሣ ፈዲል ሰራው ረዳሌ፣ ሄዳችሁ ጠይቁት ቪያ ትሪፖሌ*) በደንበኞቼ ተወዳጅ ከሆኑ የሆቴሌ ዕቃዎች ጥቀቶቹ ናቸው::

እንደገናም አንዲት የጨንቻ ባላባት ሚስት ለንጉሠነገሥት ሚኒሊክ ፈትለው የሰጡአቸውን ማርያም ሲያስቀድሱ የሚለብሱትን ጋቢ አንድ ሰው ሊሸጥልኝ ቃል ገብቶ አንዱ ግድግዳዬ ላይ እንደ ስዕል ልዘረጋው ስፊ ቦታ ትቼለታለሁ:: (ቃል ከተገባልኝ ስለከረመ ተስፋ እየቆረጥኩ ነው)

ከሁሉም የበለጠ እኔንም ይሁን ደንበኞቼን የሚስቡን ከዋናው በር በስተግራ ጎን ለጎን በአለው ዘለንጋ[128] ውስጥ የተደረደሩት ዕቃዎች ናቸው:: ራሴ የፃፍኩትና ራሴ ያሳተምኩት ስለ ጥብስ የምታወራዋ ባለ ሰባ ገፅ ትንሽ መጽሐፍ፣ ደረታቸውና ጀርባቸው ላይ የሆቴሌ ስም የተፃፈባቸው ለሽያጭ የቀረቡ የተለያዩ ቀለማት ያላቸው ካናቴራዎች፣ ፊልተሮቼ የሚቀርቡባቸው የሚያማምሩ ጥቂት ቀለማም ማሰሮዎች፣ ቤቴን ሳዘገጃጅ ያገኘሁት በ1901 ዓም የታታመ 'ጦቢያ' የተባለ አባቴ ለረዥም ጊዜ ጠብቆ ያቆየው ሌብወለድ መጽሐፍ አንደኛ እትም፣ አሰፋ አባተ የተጫወተበት ክራርና ሐታዝ የተባለ የአክሱም ንጉሥ ያሰራው የነሐስ ገንዘብ ኮፒ (የሐታዝ የወርቅ ገንዘብ ወይም ሳንቲም ኦሪጂናሉ ጥቂት ሳንቲሜትሮች ስፋት ያለው ሲሆን እኔ የሰቀልኩት ግን አንድ ሜትር ስፋት ያለው ብረት ነው:: ይኼን የቅርፅ ለውጥ በትብብር የሰሩት አንድ ጋራዥ ያለው 'ገብሬ' የተባለ ጉዋደኛዬና ሰዓሊ 'እንዳርጋቸው ማንችሎት' ናቸው) ደንበኞችን የሚያስደስታቸው እዛ ላይ ያለው ፅሁፍ ነበር:: እንዲህ ይላል:

ጥርሶቻችን በመከ፡ ጥቁር ፈር
ይሞላሉ ፍሥሐ ወሠላም ለሕዝብ

ጥቂት ጊዜ ስዕል ተምሬ ስለነበር ለማውራትና መሀይም እንዳልሆንኩ አንዳንዴ ለመጎረር(ጉራ ለመንፋት)፣ የሆቴሌንም ባህላዊ ውበት ለመጠበቅ፣ የበላቸው ይመርና የታደጌ ዴፌርሳን ባሕላዊ ስዕሎች በዋናው

[128] (መስታወት የጋረደው መደርደሪያ)

ቆቃ አጸራሽና በሁለቱ ትንንሽ አጸራሾች ውስጥ በዕውቅ በተሰሩ የእንጨት ውሊያኖች በስርዓት ሰቅዬአለሁ:: የተመኘሁትን ያህል ያልተዋጣልኝ ቢኖር ጥብሴንና ፊልቴሬን በቀጥታ የሚመለከት የሚያረካ ሱቬኒር መሰብሰብ አለመቻሌ ነው:: የለኝም ማለቴ እንኳ አይደለም:: አንድ ቤቴ እየደጋገመ የሚመጣ ድሮ የአገር ፍቅር ማሲንቆና ክራር ተጫዋች የነበረ ሰላምተኛዬ:

«የድሮ ጋዜጣ አለኝ:: እዛ ጋዜጣ ላይ የሒሩት በቀለ ቃለ መጠይቅ ይገኝበታል:: እና ቃለ መጠይቁ ላይ ጋዜጠኛ አሳምነው ገብረወልድ 'ምን መጠጥ ትወጂያለሽ?' ብሎ ሒሩትን ይጠይቃታል:: ምን ትመልስለታለች መሰለህ? 'ጥሩ ፊልቴር'» አለኝ:: ይኼን ስሰማ አላመንኩም:: ከሶስት ቀኖች በሁዋላ ሰውዬው ጋዜጣውን ሲያመጣልኝ ምን አገኛለሁ? የሒሩት በቀለን ትልቅ ፎቶ:: እዚህ ፎቶ ላይ ዓይነ መልካሟ ሒሩት ቢፌ ተደግፋ ተሽኮርምማ የተነሳችው ፎቶ ብቻ ሳይሆን ከስር ይሄ ተፅፎአል: *'የምወደው መጠጥ ጥሩ ፊልተር ነው'* ከሁለት ቀኖች በሁዋላ በሆቴሌ አንዱ ግድግዳ ላይ የሒሩት በቀለን የጋዜጣ ላይ ፎቶ አሳድጌ በጠንካራ ወረቀት ላይ ለስኜ ሰቀልኩት:: 'እንዴት አንድ ዲያቆን እጣነ ሞገርና ሰለስተን፣ አኮቴትና ሚስጥርን የሚዘምር እዚህች ሴት ጉዳይ ምን ዶለው?' አልባልና ቀድሞም ቢሆን የሒሩት እንጉርጉሮዎች 'ደስ በሚል የደስታ መዐዛ ያውዱኝ ነበር' የሚል መልስ እሰጣለሁ::

በመጨረሻ ሊወራለት የሚገባው በቸልታ የማይዘለለው የሆቴሌ አርማ ነው:: የሆቴሉ መግቢያ ላይ እና በመጠጫ ጠርሙሶችና ብርጭቆዎች ወገብ ላይ በከንፈሩ የቆመ ብርቱካንማ ቀለም ያለው ሰፌድ አለ:: እዚህ ሰፌድ ዙርያ፣ በወርቅ ቀለም የቁም ዕፈት 'ታዚና ሆቴል' የሚል ንባብ አለ:: ይሄ አርማ የምኞት፣ የደስታ፣ ሳይቆስሉ፣ ሳይደሙና ሳይነዛነዙ የአገርን ባህል መውደድ እንደሚቻል የሚያሳይ ምልክት ነው::

ሆቴሌን በአዲስ መልክ እያደረጀሁ፣ እያስጌጥኩ፣ እየወጣሁና እየወረድኩ ስለ እሷ ስለ ማክዳ ማሰቤ አልቀረም:: አልቤርጎዎቹን ወደ መብያ ቦታ ብለውጣቸውም ማክዳ ምሳዋን ወይም ራቷን ለመብላት በተለያዩ ሰዎች እየተቀያየረች ስትመጣ በዓይኔ በብሌኖቹ ማየቴ አልቀረም:: እነዚህ ሰዎች የሚበላና የሚጠጣ ከጋበዝዋት በሁዋላ ወደ ከተማችን ጉራንጉር ለአሰኛቸው የሐጢያት ስራ ሊወጡ ሲሰናዱ፣ (ሁልጊዜ እንደዛ ይመስለኛል) ቀደም ብዬ ወደ መኪና ማቆሚያው ቦታ ሄጄ ጨለማ ተከናንቤ (የሚመቸኝ እንደዚህ ነው) እያብሰለሰልኩና አንጀቴ እየተቃጠለ አጤናታለሁ(በቸልታ እንደማይመለከተው ሰው):: ስትራመድ አባላጊዎቿ የሚገዙላት ቀሚሷ ገላዋ ላይ እንደ አበባ ሲሰራው፣ በሽኩርኩር ቂጥዋ ሰማይና ምድርን እያንቀላለጠች ወደ ጨለማ ውስጥ ስትሰረግ፣ በቡራቡሬው የሽሮሜዳ የምሽት ውጋጋን ውስጥ ጥርሷ

አፏ መሃል ጠመኔ የመሰለ ብርሃን ሲቀድ፣ እዚህ ልቤ ስር እዚህ ጋ በሚነሳ ውጋት እቆምኩበት እጠመዳለሁ::

ቢያስጠላኝም ቢያስከፋኝም የመቀበል ነገር ቢያብሰለስለኝም ሰዎች ጉስሚት[129] ናት አሉኝ:: ቅዳሜ ቅዳሜ በተለይ መሸት ብሎ ዐይን ሲይዝ፣ ከተለያዩ ሰዎች ጋር ጥብሴን በልታና ጠላዬን ጠጥታ ከጨረሰች በኋላ ባለአልቤርጎ ሆቴሎች---ናዝሬት ሆቴል፣ ተራራ ሆቴል፣ አባይ ሆቴል፣ መናኸሪያ ማረፊያ ቤት ወዘተ መቀናዘሪያዋ እንደሆነ አወሩኝ:: እንዴ-ምወዳት አያውቁምና ብጥል/እላቂ ናት አሉኝ:: ይህቺ ልጅ ስለምንድነው የፈለገችው ሊወዳትና ቁም ነገር ሊያደርሳት ሲችል ከማንም ወጠጤና በእድሜው ከሚያስከነዳት ጐልማሳ ጋር ያለ ዕፍረት እየተመላለሰች ራሷን የምታበለሻሸው? ጭኖቿን ያየሁ ዕለት ያየሁት ቅንዝርነትን ብቻ አልነበረም:: ለምለም መስከና ገርነትንም ነበር:: እንደዛ አይኖቼን እንደ መድሃኒተኛ እጆች የዳበሰኝ አፍዝ አደንግዝ ገላ ዘንካታነቱ እንዴት በየቦታው ይወድቃል? እንዴትስ ስጋና ነፍሴን ቀስቅሶ ያቁነጠነጠኝ ውበቷ እንዲህ በፋልቱነቷ ይረክሳል? ምነው አገሬን መሰልሽኝ? *ውበት ሐሰት ነው ደም ግባትም ከንቱ ነው*[130] አልኩ:: ***የፈረንጅ አረቄ መስቲካ ነሽ አሉ፣ እስኪ እንደ ቅራሪ አትስጪው ለሁሉ እለ አዝማሪ::***

እሷን በቀጥታ ማዋራት ቢያሳፍረኝና ቢከብደኝ አባቷን ወንድ ወሰንን ለመሻረክ ጥረት ማድረግ ጀምሬ ነበር---'የጨነቀው እርጉዝ ያገባል' እንዲሉ:: ወላጅ አባቷ፣ አባቷ መሆን ያማረረው ሰው ሆኖ 'የዘመኑ ልጆች እንኳን በምክር በቁጣና በታንክ ተገደው መልካም ነገር እንደማይሰሙ፣ መንገዳቸው ሁሉ በሴሰኛነት በአናርኪስትነትና በመሳሰሉት የብልግና ዝርያዎች የታጠረ አሳፋሪ' እንደሆነ አወራልኝ (አስገራሚ አባት):: ቤቴ እንኳን አምጥቼ ጋብዤ ወደ እሷ የሚወስደኝ ድልድይ እንዳላደርገው አብረውት ተቀምጠው ቁም ነገር ሊያወሩት የማይቻል ወሬኛ ሰው ሆኖ አገኘሁት:: ከመሃልም ልጅቷ ራሷ ፈልጋ እኔ እንደወደድኳት ገብቶአት ወይም ተረድታ ካልመጣች በተቀር የልፋቴ መጨረሻ የበለጠ ልፋትን፣ ሲያልፍም ውርደትን ያዘግነኝ እንደሆን እንጂ ሌላ አያመጣም ብዬ እንዲህ የመቅረቡን ዕቅዴን ተውኩት::

ማክዳን በቀጥታ የማናገር አቅም ያሳነሰኝ ከሃይማኖት ትምህርቴ የመጣ ዐይነአፋርነቴ ብቻ አልነበረም:: እስከ አሁን ያላወራሁትና ላወራው ብልም ራሴን የሚያስጨንቀኝና የሚያሳፍረኝ ሌሎች ምክንያቶችም አሉ:: አንደኛው ምክንያት ጥርሶቼ ሊፀዳ በማይችል እርጉም ልማም

[129] ተሽኮርማሚ ግን ሂያጅ ሴት

[130] ከመዝሙረ ዳዊት፡ ምዕራፍ 31 ቁ:10

መሸፈናቸው ነበር:: የፊት ጥርስ የምትባል ትንሽ ነገር ባለማግጧ በእግዜር የምታምነው ትንሽ ነፍሴ በሽሙጥና በሿሌት ነዳለች:: ከልጅነቴ ጀምሬ ከማውቃቸው ቸርነት፣ ዓላዛርና አንድ ሁለት ልጆች በተቀር ይሄን የሚያሳፍረኝን የተፈጥሮ ነገር በአግቦ እያነሱ ያልጎዱኝ ሰዎች፣ ለግላጋ ዘበሬታዬ መሃል የነገር ውሻል እየከተተ ያልነከሱኝ ጥቂት ነበሩ (ምን ይጠቅማቸዋል?):: ገላዬ ትኩስ በሆነ ዘመን ወንድ ወጣቶች ከሚያምሩና ከሚያስቀይሙ (የፈለጋቸው ዓይነት ይሁኑ) ፀጉራቸው ከተተኮስ ልጃገረዶች ጋር (የተተኮሰ ፀጉር ስወድ) የመጀመሪያው የአገራችንን ፊልም የኢሳላ ኢብሳን 'ሂሩት አባቷ ማነው?'ን ለማየት እጅ ለእጅ ተያይዘው ሲኒማ ቤት ሲገቡ እኔ ብቻ ነበርኩ ከዛ ሁሉ ወጣት ለብቻዬ ጎናቸው ቁጭ ብዬ ምራቅ የነካው ከንፈር እየናፈቀኝ የቀረው:: ቀላል ያልሆነ ድብት የተደበትኩት:: ዓላዛር ያለኝ ግን ትዝ ይለኛል:

«እዝራ ጂሚ ('ጂሚ' ማለት ይወድ ነበር:: ዲያቆን ሆኖ 'ጂሚ' መባል ትንሽ ግራ ቢሆንም) ዘፋኝ መሆን ትቺያለሽ:: ዘፋኝ ስትሆኚ ደሞ ደናው ይመጣል:: ደና ካሽ ሲያይ አፈር ድሜ ነው የሚበላው:: ጥርስሽ አዎ ይደብራል ግን ድምፅሽ የአማልክት ነው:: ጥላሁን ገሠሠ አለማየሁ ምናምን ምን አላቸው:: አንቺ ብቻ አትሳቂ ጀስት ዝፈኚ.»

ስድብ ነበር? ያለፍኩበትን ላላወቀ ይመስላል:: በአብዛኛው ትክክል ነበር:: ስድብ ሳይሆን እንዳልፈራ ምክር ነበር:: ለምን 'በአብዛኛው' አልኩ? ከዓላዛር አስተያየት የጎደለው አእምሮዬ ብሩህ መሆኑን አለመጥቀሱ ነበር:: የወንድሜ ወግ ግን በአብዛኛው የዘመኑ እውነት የሰፈረበት ነው:: 'ከፍትፍቱ ፊቱ' እንጂ፣ 'ከፍትፍቱ አንጎሉ' የሚል አባባል የለንም:: በጣም ከሳቅሁ ይኼ የተፈጥሮ ጉድለቴን ለመጋረድ በልማድ ቶሎ አፌን እጋርድ ስለነበር እጄን ከአፌ ላይ ከልቶ ነው:

«እዝራ ጂሚ......»ያለኝ

ይኼ ብቻ? ይኼ ጉዳይ ብቻ? አይደለም:: በልጅነቴ የት ይደርሳል የተባልኩ መለሎ መፃጉዕ ያስመሰለኝ ጎባጣ ሆንኩ:: ይኼም ገላማጭና ታዛቢ የሰው ዓይኖች ሰቦበኛል::

አራዳ ተወልጄ አራዳ ባድግም፣ በዚያች በራጉኤል መቅደስ አንዳንድ ታምራትን አይቼአለሁና፣ ባላይም ሰምቼአለሁና፣ ባላይም ባልሰማም አምናለሁና ('ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው') የእኔ ጎብታም መሆን ራሱ አንድ ተአምር ነውና፣ ተማርን ተመራመርን የሚሉት በክፉም በደጉም ሲሞቱ፣ ሲሰደዱና ሲደኸዩ (ይኸም አስገራሚ ነገር አለውና) እኔ ግን ፍቅር ቢይዘኝና በዚህም ምክንያት ልቤ ተነክቶ፣ አንጀቴ ተላውሶ፣ ጉበቴ ተመስጦ፣ ኩላሊቴ ተንዘርዝሮ፣ ያሬዳዊ ዜማ ማንቀርቀር በለመደ

ድምፄ አንሶላዬን ለእንቅልፍ እላዬ ላይ ከመጣሌ በፊት በዓለማዊ እንጉርጉሮ ከሜሪ አርምዴ በኮረጅኩት እንዲህ ብል:

*እዝራ ከመምንት አለህ?*
*እኔ እንዳለሁ አለሁ*
*የፍቅር አጋሰስ መጋዣ ሆኛለሁ*

እሱም የሚገርም ታምር ይሆናል? ወተት ሲጠቁር ብቻ ነው ተአምር ወይ በሬ ፀንሶ ሲወልድ?

በዚያን ወቅት ወዳጅ አልነበረኝም? እንግዳ በሆነ መልክ ማውራት በማይመች ስልት ነበረኝ:: ግን በአደባባይ ያውም ለዓላዛር አይነት ሰው የሚወራ አልነበረም:: ጊዜው ሲደርስ መናገሬ አይቀርም:: በመጀመሪያ ግን......

# ስለ ጥብሱ ሀ ልበል
## ወይም ስለ ኮሻሻ[131] መሞት

'አንተ እግዚአብሄርን ከማገልገልና እሱ የሰጠህን የመዘመር ችሮታ እዛ ታምረኛው ራጉኤል፣ ከግቢው ውጭ እንደ ጠዋት አክታ ጥለኸው፣ ነፍስን ማጣጣያ ይኼን የሆድ አራሙቻ ኢንዱስትሪ ጀመርክ? እንዴት ይኼን አደረግህ?' እንዳልባል ልዑጥ[132] ተረት ፈጥሬአለሁ:: ታዚና እንደ ሰማችሁትና እንደምታውቁት አዲስአባ ሁላ የሚዝራገድበት፣ የሚጣላበት፣ የሚዋደድበት፣ የሚሰባበክበት፣ የሚለያይበት፣ የሚኮራረፍበት የመሳሰለ) የሆድ ቤት ብቻ ሳይሆን ከስሩ ሲገለጥ ብዙ ሚስጥር የያዘ ነው::

«ጥብሱ እንዴት እንዲህ አማረልህ?» ሲሉኝ......

የምነግራቸው አእምሮዬ ውስጥ ገናና ስለሆነው የማክዳ የጭን ቀለምና ከእሱ ጋር የተያያዘውን መቅኖ ቢስነቴን አይደለም:: የየካቲት መፅሔት የባህል ክፍል ባለሟሎች ላቀረቡልኝ ጥያቄ የመለስኩላቸው ጉዳይ ከላይ እስከታች ልዑጥ ነው:: ጠቅላላ የአዲስ አበባ ከተማ በሚያየውም ቴሌቭዥን ቀርቤ ስለታዚና የጥብስ ትዕንግርት ሲጠይቁኝ፣ መሸምደድ ቄስ ት/ቤት ለምጄአለሁና አንዲት ሆሄ ሳላሳስት የመለስኩላቸውም ከዚህ በታች ያለውን ለመፅሔቱ ጋዜጠኛ የተናገርኩትን 'ታሪኬን' ነው......ሲራክ: *ዋጋህ እንዳይጠፋብህ ለሰው ሁሉ የልብህን ሚስጢር አትግለጥ* (ምዕ 8) ይላልና......

ብዙ ጊዜ የእንስሳት ስጋ 75 ከመቶ ውሃ፣ 20 ከመቶ ፕሮቲን፣ 5 ከመቶ ስብና ካርቦ ሃይድሬት ነው:: ይሄ ሳይንስ ነው:: ስጋን በማጉያ መነፅር ወይም ማይክሮስኮፕ ቀረብ ብለን ካየነው ቃጫ ከመሰሉ ጭረቶች

---

[131] ደረቅ ጥብስ

[132]ተቀባይነት የሚያጣውን ዋናውን ታሪክ የሚሸፍን ከላይ ያለ በብዙ ሰዎች አይን ተቀባይነት የሚያገኝ ቆዳ ታሪክ:: ልዑጥ የተደራረበ ሊሆን ይችላል:: ልዑጥ ታሪኮች እንደ ሽንኩርት ሊዋቀሩ ይችላሉ:: እውነቱ እስኪደረስ ያሉት መሸፈኛ ክርታሶች በየደረጃው ብዙ አይነት እምነቶች፣ አመለካከቶችና ከዚህም ጋር ተያይዞ ግጭቶች ይፈጥራሉ::

የተሰራ ነው:: ጡንቻ ለእንስሳው አጥንቶቹን በማያያዝ ለገላ ንቅናቄ ይጠቅመዋል:: ቀላል ለመሰሉ ግን አስፈላጊ ለሆኑ ድርጊቶችም ለምሳሌ ወፎች ቆዳው ላይ ሲያርፉ ቆዳውን በማንቀጥቀጥ ለማባረር ያግዘዋል:: የበሬ ስጋ *ዚንክ* የተባለ ለምለምነት የሚሰጠው በላተኛ ምላስ ላይ ያሉትንም የጣዕም ዕባጮች ወይም ሽፍታዎች የሚያነቃ ንጥረ ነገር አለው:: ምላሳችን ላይ ቀረብ ብለን ብናይ ደቃቃ ሽፍታዎች እንዳሉ እንገነዘባለን:: የስጋ ቅላት ደም የሚመጣው *ማይገሎቢን* በተባለ ጡንቻዎች ውስጥ ባለ ንጥረ ነገር መንስዔ ነው:: ሌላው ስጋ ውስጥ ያለው ጠቃሚ ቅመም *ፎስፎረስ* ነው፡ በእንግሊዘኛ ምሕፃር ፒኤች (Ph) ይባላል:: የፒኤች ከስጋው ውስጥ በፍጥነት መጥፋት የስጋውን ቅላት አመንምኖ የገረጣ ያደርገዋል:: ስጋ ጡንቻ ነው ብዬአለሁ:: ይሄ ጡንቻ ግን ስጋ የሚሆነው ከውስጡ ያለው አክሲጅን ሲወጣ ነው:: በጥሬ ስጋ ውስጥ ያሉት ፕሮቲኖች እሳት ሲመታቸው ከተያያዙበት ይላቀቃሉ:: በመሠረቱ የስጋ ጣፋጭነት የሚከሰተው እነዚህን በመቆጣጠር ስልት ነው:: የነዚህን አለዋወጥ በመገንዘብ ነው:: በተጨማሪም ለስጋ ጣዕም የስብ አስተዋጽዖ ከፍተኛ ነው:: ከብቶች የሚግጡት የሳር ዓይነትም የስጋቸውን ጥራትና ደረጃ ይወስነዋል::

ለደንበኞቼ የማቀርባቸው የስጋ አይነቶች የጥጃ፣ የላምና የበሬ ነው:: ለአጭር ጊዜ የሚዳቋና የድኩላ ስጋ ሞክሬ ከደንና ከዱር አራዊት ሚኒስቴር ማስጠንቀቂያ ስለደረሰኝ አቁሜዋለሁ:: በሬዎች፣ ላሞችና ጥጆች አዲስ አባ ለእርድ ሲመጡ፣ መነሻቸውና የተላለፉበት አድራሻ በቅብብሎሽ (በገዥና በነጋዴ መሃል ባለው) ስለሚወናበድና ስለሚጠፋ ብዙ ጊዜ ከብቶች የምገዛው ራሴ በየገጠሩ እየተዘዋወርኩ ነው:: ከገዛሁዋቸው በሁዋላ ኮንትራት በቀጠርኩት ነጋዴ ወደ አዲስአባ ሲነዱ ከሌሎች እንዳይደባለቁና፣ ተደባልቀውም እንኳን ቢሆን መርጦ ለማውጣት እንዳያምታቱ፣ በቆዳቸው ላይ በትልልቁ ፊደላት 'ታዚና' ብዬ አፅፍባቸዋለሁ:: በነገራችን ላይ ከብቶቼን ከየት ክፍለ ሐገር ወይም ገጠር እንደማስጭን ለማንም አልናገርም:: ከብቶች ከገጠር ተነድተው ከመጡ በሁዋላ አቧሬ ባሰራሁት የከብቶች ማረፊያ ግቢ ውስጥ ለሳምንት የተቀመመ የሳር ድርቆሽና እህል እየተመገቡ (የንግድ ሚስጢሬ ስለሆነ ስለነዚህ የተፈጥሮ ቅመማት አልናገርም፡ በአጭሩ ከዱር በገበሬዎች እንደሚታጨዱ ሳልጠቁም አላልፍም)፣ አሞሌ እየላሱ ይቆያሉ:: ከብቶቹ ከታረዱ በሁዋላ የስጋ አበላለቱ ቀይ ከነጭ እየሆነ ነው:: ሲዘለዘሉም በብዛት በአንዳንድ ክንድ ዕርዝመት ነው:: በዚህ ዕርዝመት ውስጥ ቢያንስ አንድ የስብ ሰንበር አይጠፋም::

ማድ ቤቴ ሶስት ክፍሎች አሉት:: አንደኛው ስጋ ማጎሪያና መምረጫ ሁለተኛው መዘልዘያ ሶስተኛው መጥበሻ ናቸው:: በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ እነዚህን ክንዋኔዎች የምቆጣጠረው እኔ ነኝ:: እኔ ካሌለሁ

ጌታቸው ዘኅላ ሰፈር ይተካኛል:: ጌታቸው ስለታዚና ከእኔ እኩል የውቃል ብል አልዋሽሁም::

የታዚና ጥብስ ፍፁም ደረቅ አይደለም:: ፍፁም ደረቅ መሆን የለበትም:: በችኮላ በይድረስ ይድረስ ጥብሱ አይቀመርም:: አንድ ትዕዛዝ ብዙ ጊዜ የሚሰራው አንድ ክንድ እርዝመትና የደህና ሰው አውራጣት ስፋት ካለው የተዘለዘለ ስጋ ነው:: መጥበሻዎቼ ከዚህ ለማያንስ ከዚህም ለማይበዛ የስጋ ስፍር የሚመቹ ናቸው:: መጥበሻዎቹ የተንተረከከ ከሰል ላይ በቀስታ ይቀመጣሉ:: ስጋው እየተነቻቻ ይጠበሳል:: መገልበጥ ያለበት *በሃያ* ነው:: *በሃያ* ማለት በየሃያው ሰከንድ ነው:: ጠባሹ ፊት ለፊት ግድግዳ ላይ የሚሞሉ የግድግዳ ሰዓቶች አሉ:: በየሃያ ደቂቃ ያቃጭላሉ:: ሲያቃጭሉ ጥብሱ ይገለበጣል:: ስጋው ውስጥ ያለው ፈሳሽ በሙሉ መውጣት የለበትም:: ከዚያ ከአስራ ሁለት ቅመማት የተነጠረ ቅቤ በላዩ ይጣልበታል:: ቅቤው ስጋው ውስጥ በቀስታ እንዲሰረግ ከተደረገ በሁዋላ ጥብሱ ተጠቅሎ ነጭ የገድጉዋዳ ሳህን ላይ ጥብሱ እየተጠቀለለ ይቀመጥና፣ የሰሃኑ ቂጥ አጮልቆ በሚታይበት ጎድጉዋዳው መሃል ደንበኞችን ከመረጣቸው ስመጥር የድልህ አይነቶች አንዱ ይፈሳል:: መሰረታቸው በርበሬ የሆነ ሶስት አይነት ድልሆች አሉኝ:: ድልሆቹ ከተለያዩ እንስሳት የተለቀሙ የሃሞት ፈሳሾች ይገባባቸዋል:: ዝርዝራቸው የንግድ ሚስጢሬ ስለ ሆነ ከመደበቅ አላመነታም:: የድልሆቹን ውፍረትና ቅጥነት የምቆጣጠረው እኔ ነኝ:: ሆቴሌ ማንም ሲገባ እንዲያሸትና ነጥሎ እንዲቀምስ የምፈልገው እነዚህን አስደሳች ነገሮች ነው::

በመጨረሻ የዝቡቅቡቅ እንጀራ ጥቅሎች ዙሪያውን እናስቀምጣለን:: ጥብሱ ለዐይን አልባሌ አይመስልም:: እንደበላተኞቼና እንደእኔ የበለጠው ትንግርት የሚመጣው አፍ ውስጥ ከገባ በሁዋላ ነው:: አፍ ውስጥ እንደ ፍቅረኛ ከናፍርት ያደርገዋል፣ ለጥርስም ሽርክ ነው:: ጥበቤን ከዚህ የበለጠ ለመግለፅ አልሻም:: አጉል ሚስጥረኛነት አይደለም:: የትም ዓለም ያልተሰራ የስጋ አጠባበስ ዘይቤ ቢደበቅ ምን አለበት? ራሱ ቴክኖሎጂ እኮ ነው::

ለውጦች በሁለት ዓይነት መንገድ ይከሰታሉ:: አንደኛው በአብዮታዊ ፍጥነትና ቀውስ ነው:: በችኩልነት ነው:: ሁለተኛው ደሞ በዝግመተ-ለውጥ ነው:: አንድ ዝርያ ከሌላ ዝርያ በዝግመት ሂደት ተለውጦ 'ልዩ' ሲሆን 'ፋይሌቲክ ለውጥ' ይባላል:: ዝልዝል ጥብስም/ጎረድ ጎረድ/ ይሁን ፊልቴር የፋይሌቲክ ለውጥ ውጤቶች ናቸው:: ስለ ፊልተሩ መናገር አልፈለግሁም::

# የፊልቴር አኮቴት

ውሃና አፈር አይነጣጠሉም:: ውሃ ጉም ወይ ደመና ሆኖ ቢንጠለጠል፣ ከምድር ጋር ያለው ፍቅሩ አያስችለውምና ማይ ሆኖ መውረዱ አይቀርም:: እንግዲህ ይሄ 'ዝናብ' የምንለው ነው:: ያ ፉዋፉዋቴ ያማረው የተሸከመችው መሬት ልቀፈው ብላ ስለፈረሰች አይደለ? አባይን እስከ ምስር አዝላ በግርማ የሞላችው የተከፈለች መሬት አይደለች:: ሰዎች ሆቴሌ መጥተው እንጀራ (ምሳሌነቱ አፈርና ምድር ቢሆን) ለመብላት ሲያዙ የሚጠጡት ያስፈልጋቸዋል ማለት ነው:: አያከራክርም:: ይሄን የግዴታ ፍላጎት ለማሙዋላት ሆቴሌ እንዲሸጥ ያደረግሁት ፊልቴር ነው:: አዎ ፊልቴር::

ማብራራቴን እንዲህ በነገር ብጀምርስ?

ዛሬ ስለጠን የሚሉ የአገራችን ሰዎች በአምስት ተከፍለዋል:: (የሆነ ነጭናጫ ቁጥሩን ሊያርመኝ ይችላል---አስፈላጊ አይደለም እንጂ) አንዱ የምስራቅ ስልጡን ነኝ የሚል፣ ሁለተኛው የምዕራብ ስልጡን ነኝ የሚል፣ ሶስተኛው የአበሻ ስልጡን ነኝ የሚል፣ አራተኛው የአረብ ስልጡን ነኝ የሚልና አምስተኛው ደሞ የዞረበት:: እኔ ግን ፍልስፍና የማላውቅ ብስከሌት ጠጋኝ፣ ጥብስ ጠባሽና እና ዐይነአፋር ቀዳሽ በአንድ ነገር አምናለሁ:: ማንም ሰው ዘመነ አልዘመነ፣ መሰረቀ መረበ፣ አረበ አላረበ፣ ዞረበት አልዞረበት ጥማትን እንደሚጠማ:: ከላይ የጠቀስኳቸው የአምስቱ መናከሻ ተከታዮች መታወቂያ ላይ ምን እንዳለ አውቃለሁ:: የሁሉም ፓስፖርት 'ኢትዮጵያዊ' ይላል:: ስለዚህ ውድ ባልሆነ ገንዘብ(ውድ ነው እያሉ የሚነጫነጩ አሉ) 'የታዚና ጠበል' የተባለውን ፊሊቴር ከጥብሶቼ ጋር መሸጥ ጀመርኩ:: ግን በየመንገዱ ዳር ከሚገኘው ተራ አይነት ሸሎና ሸኮቴ አልነበረም:: ልዩ ነው::

'አፉንም ከፍቶ እንዲህ አላቸው' መባሉ ካልቀረ ዘርዘር አድርጌ ልናገር......

አንድ ቀን ማታ ቁጥራቸው ሃያ ሰባት ለሚደርስ የክፍለ ሐገር አውቶቡስ ሾፌሮችና ገጠር ተመላልሰው ለሚሰሩ ሰዎች በራሴ ሂሳብ

የእራት ግብዣ አደረግሁ:: ከድግሱ በሁዋላ ቸርነት ወዳጄ፣ አፊ ማር፣ ቀልደኛው፣ እዚህ ሆኖ እዚህ ያሉ ወዳጆቹን ናፋቂ፣ ሞጥሙዋጣው ('አውርቶ አደር' ብለን የምንቀልድበት) እንደ ተመካከርነው ሞቅ ካለ ጨዋታ መሃል ብድግ ብሎ በከፍተኛ ድምፅ እንዲህ አለ:

«ብዙ ጊዜ ሰዎች የአገራቸውን የመብልና የመጠጥ ሙያ ሲንቁ እንሰማለን:: ሲያደርጉትም እናያለን:: እነዚህን በቀላሉ 'ደካሞች' እንላቸዋለን:: ብዙ ጊዜ ሰዎች ተምሮአል ምናምን በሚል ሰበብ ከመሬት ተነስተው የረባ ነገር ባይሰራም ዶክተር ምናምን ያመሰግናሉ:: የሚገርመው በአገራችን ረሃብ የገባው 'ዶክተር' የተባለ መጠሪያ መስማት ስንጀምር ነው(ሳቅ):: ዶክተር ደሞ ለሁሉም ችግር መልስ አይሆንም:: ብቻውንም የሚሰራው ተአምር የለም:: ሐኪሙ ዶክተር ያከመውን በሽተኛ ተንከባክበን ሞጆ አጎቱ ጋ ወይም እናቱ ጋ ሐረር በአውቶቡሳችን ጭነን ካላደረስነውና ትኅሽ በርጫ ካላደረገ ምን ጥቅም አለው? (ሳቅ) ዛሬ በቡጡሌ የታሸገ እናቶቻችን ከሚጠምቁት ጠላ መብለጡ የሚያጠራጥር 'ቢራ' የተባለ ነገር በከተማችን ይጠጣል:: ለዚህ መጠጥ የማይሻማ የለም:: የዚህን ሽሚያ ፍላጎት ለማርካት የአስመራና የአዲስአባ ትልልቅ ፋብሪካዎች በከፍተኛ ቁጥር በየቀኑ ያመርቱታል:: ግን ቢራዎች በሙሉ ትክክለኛ ናቸው? ትክክለኛ መሆናቸውን ማን አረጋገጠ? ማነው በመጀመሪያ የፈለሰፋቸው? እስከ ዛሬ ያልገባን ዓይነት በሽታ ያመጡብን እንደሆነ ጠርጥረናል? ብዙ እንጠይቃለን:: እኔ በተደጋጋሚ ክፍለ ሐገር ሄጃለሁ:: በትንንሽ ከተሞች አድሬአለሁ(ይሄ በሙሉ የቸርነት ውሸት ነው:: ከአዲስ አባ ወጥቶ አያውቅም) ከምንም አይነት ቢራ የበለጠ ጣት የሚያስቆረጥም ጠላና ፊልቴር ጠጥቼአለሁ እና......»

......እንዳዛ የተደሰቱ ሾፌሮች፣ ቀያሾችና የግብርና ሚኒስቴር ሰራተኞች አላየሁም:: እያንዳንዱ ሾፌር በተሰጠው ወረቀት ላይ ልምዱን ተመርኩዞ ለእነዚህ ቀላል ግን መሰረታዊ ጥያቄዎች የተሙዋላ መልስ እንዲሰጠን ጠየቅን---

*የፊልቴሩ ቤት ስም/የምግብ ቤቱ ስም--------------------*

*ያለበት ከተማ---------------------------*

*የቤቱ ባለቤት---------------------------*

*የጠማቂዎቹ ስም---------------------------*

*ከላይ የተዘረዘሩትን መረጃዎች አቅራቢ-------------------------*

*የፊልቴሩ ደረጃ (ከአንደኛ እስከ አምስተኛ)-------------------*

*የፊልቴሩ የተለየ መልካም ጎን---------------------------*

እነዚህን መረጃዎች ሰብስቤ በሶስት ወር ውስጥ ተወዳዳሪ የሌለው ፈልቴር እዚህ ቤቴ ማስጠመቅ ጀመርኩ:: የመጀመሪያው ፈልቴር ጥብሱ *ከተፈለሰፈ ከሶስት ወራት በሁዋላ በጥር አስራ ሰባት ቀን 1974* አም ለደንበኞቼ ቀረበ (በአመቱ በአምስተኛው ወር፣ በወሩ በአስራ ሰባተኛው ቀን[133])::

ስለንዳቸው እንዲህ ነው: ፈልቴሮቹ ነጭና ጥቁር ሲሆኑ: እነዚህም ማር ወይም ስኳር የላሰ ነጭና፣ ማር ወይም ስኳር የላሰ ጥቁር ሊሆኑ ይችላሉ:: የሚቀርቡት እንደ ቅል አንገት ባላት መስቴ በምትባል ሸክላ እቃ፣ በቢራ ቡጡሌ እና በአምቦ ውሃ ጠርሙሶች ነው:: እላያቸውም ላይ በከፊል ወገባቸውን የሸፈነ የሆቴሌ ስም የተፃፈበት ወረቀት ተለጥፏል:: ገና ሲያዩዋቸው በውበታቸው፣ ሲነኳቸው በቅዝቃዜአቸው፣ ማራኪ መልዕክት ለወስፋታችን ይደውላሉ:: ጠርሙስ ውስጥ ሲታዩ ጥቁሩ በጥቁርነቱ ጨለማ የሚያስንቅ፣ ነጩም የሱፍ መረቅ የመሰለ ጥም የሚቀሰቅስ የጋራ ግርማ አላቸው:: የፈልቴሩ ክፍል ሃላፊዎች ሁለት ሴቶች ሲሆኑ፣ በሾፌሮቹና በቀያሾቹ ምርጫ ከየአገሩ ተመልምለው የመጡ ናቸው:: የራሳቸውንና የታዚናን ፈንጣራ ፈልቴር በአስገራሚ ጥበብ ይጠምቃሉ:: በዕድሜአቸው ወጣት ሲሆኑ የመጡት ወይዘሮ ታንጉት ከጎጃም (ደምበጫ)፣ እና ወይዘሪት ጥሩወርቅ ከሸዋ (አላባ ቁሊቶ) ነው:: ፈልተሮቼ በነጭ ጠርሙስ ከምግብ ጋር አብረው ይቀርባሉ:: እነሱን በብዛት የጠጣ መስከሩ የተረጋገጠ ቢሆንም፣ ሰራተኞቼ ይሄን ዓይነት ስህተት እንዳይከሰት ይከታተላሉ:: ስለፈልቴሩ ፍቅሩን የገለፀ አንድ ምግብ ድርጅት የሚሰራ የፋፋ ቀማሚና የስነ-ምግብ ተመራማሪ እንዲህ ብሎአል:

*«......የጠጣሁት ጥቁር ፈልቴሩን ነበር:: ከሚያምረው ጠርሙስ ወደ ብርጭቆው ቀዳሁና ገና ከመጠጣቴ በፊት ጠረኑን በታደሉት አፍንጮቼ ስነፈጥኩ:: መዓዛው (የማሽተቱ ድርጊት ደስ የሚል ሙዚቃ እንደ ማዳመጥ የሚቆጠር ነው) በታላቅ መጠበብ የተሰራና በአሁን ጊዜ በማሺን ውጤቶች ከተፈበረኩ ማንኛውም ዓይነት መጠጦች የላቀ ነበር:: ያጋጠሙኝ ተፈራራቂ ጠረኖች ገና መሰየም ስላለባቸው በስም ልጠራቸው ይከብደኛል:: ያልጠበቅሁት ጥፃት በሁለማናዬ ተነሳስ (እስታውሱ የመጀመሪያ ጊዜዬ ነው) የፈልቴሩ ጠብታ ከንፈሮቼን ሲነካኝ ቅዝቃዜው ከሰለጠኑት የአውሮፓ አገሮችና ከተሞች ጋር አገናኘኝ ብል አልዋሸሁም:: በእኔ በእኔ ሁለተኛ ዲግሪዬን ያገኘሁበት ሎንዶንንና ለአጭር ጊዜ ዘመድ ጥየቃ የቆየሁባትን የአሜሪካንዋን ውብ ከተማ ሲያትል ያስታውሰኛል:: የዚህ ፈልቴር አስገራሚ ጠባዩ አፋችን ውስጥ ከያዝነው ጀምሮ ጠጥተን ጨርሰን እስከምንነሳ የተለያየ ጣዕም መፈልቀቁ ነው(ሌላ ቃል ስላላገኘሁ*

[133] ዘፍጥረት በዚህ ወር ላይ 'የሰማይ ቀላያት ተከፈቱ' ይላል(7-11)

*ይሄን እንድጠቀም ይፈቀድልኝ) ቢያንስ ስድስት ዓይነት ጣዕም ቁጥሬአለሁ:: ይሄን ዓይነት ከአንድ ጣዕም ወደ ሌላ ጣዕም ልባችን እስኪጠፋ ድረስ የሚያንሸራሽሩን ምን ዓይነት ጥበብ ተጠቅመው እንደሆነ ብጠይቃቸው የምግብ ቤቱ ባለቤት አቶ አዝራም ሆነ ሙያተኞቹ ጥሩወርቅና ጉዋደኛዋ ታንጉት ሊነግሩኝ ፈቃደኛ አልሆኑም:: በዚህም አላኮረፍኩም:: ዋናው የምላቸው ፊልተራችሁን አታስቀሩብን ነው:: ከተጠጣ በሁዋላ (ሁሉንም ከጠርሙሳችሁ አንጠፍጥፋችሁ መጠጣታችሁ እንደማይቀር እምልላችሁዋለሁ) በሰራ ገላ ተስተካክሎ ይሰማል:: ሆድ አይቆርጥ አይፈልጥ:: አንድ የታዘብኩት ነገር እዛ ቤት ውስጥ ሰው ሁሉ ፊልቴሩን እየጠጣ ብዙ ሰካራም አለመኖሩ ነው:: ከቅመሙ ይሆን? ደምም ከራስ ምታት ይፈውሳል እንጂ ራስ ምታት አይሆን:: ለማንኛውም ዓለም ከመጥፋቷ በፊት ሂዱና ይሄን ፈሳሽ ሞክሩት»*[134]

ከሆነው በላይ አናጋነውና በአጠረ አማርኛ፣ ፊልቴር የነጠረ ጠላ ነው:: የጠላ ከፍተኛ ደረጃ ፊልቴር ነው:: የሚንቁት ካሉ ከጥንት መፃህፍት ያገኘሁትን አንዳንድ ዕውቀት ላካፍላቸው::

ፊልቴር በቀጥታ ከእህል የሚሰራ ሰው ሰራሽ ቅመምና እንደ ዘመኑ ቢራና ወይን ኬሚካል የማይገባበት መጠጥ ነው:: ከምግብ የሚስተካከል ጠቃሚነቱን ትቼ፣ የፊልቴር ስራ ቴክኖሎጂ ከማንኛውም ዓይነት አልኮል የማምረት ስራዎች የተለየ ነው ብል ማጋነኔ አይደለም:: ሕልውናውና አሰራሩ ከስንት ሺህ አመታት በፊት ጀምሮ ያለ ነው:: የተለወጠ አንድም ነገር የለውም:: ጥንት የፈርኦን ምስራውያን ልክ እንደኛው ጠላቸውን የሚሰሩት በቂጣ ወይም በጥቢኛ ነበር:: የእኛዎቹ አይሁኑ እንጂ፣ ታላላቅ የባዕድ ታሪክ ፀሐፊዎች በብዕራቸውና በእንደበታቸው መስክረውታል:: በድሮ ጊዜ ጠላ በማንኛውም ዓይነት ሰዎች የሚጠጣ ዕድሜ፣ መደብና ዕውቀት የማይለይ መጠጥ ነበር:: ለምን? ቢሉ......መልሱ: ለጤንነት ይበጃልና ነው:: የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሳይኖር ጠላ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ነበር:: ዛሬ ዛሬ የደሃ መጠጥ ተደርጎ የሚቆጠረውን፣ ለምን የጥንት ነገስታትና መኳንንቶች ይጨልጡት እንደ ነበረ መጥቀስ ብቻም ሳይሆን መመርመርም ያስፈልጋል:: ለምን ፈርኦኖች፣ ካህናት፣ እተጌዎችና አፄዎች ይጠጡታል? 'አፌ ታሪክ ናቸው' እየተባለና ይኼም እንደ በቂ ምክንያት ተቆጥሮ ስንት ዕውነቶች ይዘለላሉ? 'ንግስት ሳባ ዕንቁና የከበረ ድንጋይ ለሰለሞን ወሰደች' ከምንል ለምን 'ጠላ ወሰደችለት' አንልም? መቼም ሰውዬው ሴሰኛ ከሆነ ሰካራምነት አያጣውም:: ጠላ ርካሽና ክብር ስላሌለው ነው? በዕርግጥ ሳባ በረሐ አቋርጣ ጠቢቡ ጋ ስትሄድ የለመደችውንና የምትወደውን ጠላ አክሱም ረስታው አይደለም:: ዝንጉ

---

[134] አበበ ማሞ ጠላና ስልጣኔ አዲስ ዘመን ጋዜጣ 1978

ልጅም አልነበረችም:: እንደውም ወደ ኢየሩሳሌም አብሯት ከሚሄዱት ቆሶች ሁሉ ከማርና ከነጠረ ቅቤ እኩል ክብር ያለው የጠላ ድፍድፍ በብዙ ግመሎች ላይ አስጭና ነበር:: ለዚህ ምስክሬ ታሪክ እንጂ አፈ ታሪክ አይደለም:: ያቺ ንግስት ይሄን ያደረገችው የመስከር ሱስ ኖሮባት ሳይሆን፣ ለጤንነትዋ ስትል ነበር:: ሰለሞን ጋ ስትሄድ አስቸጋሪ ጉዞ ስለሆነ በመንገድ ላይ አርባ አራት ጊዜ ጭኗ ይቆስላል:: ይኼ በመጽሐፍት ተጠቅሶአል:: አርባ አራት ጊዜ::(ይሄን የጠቀስኩለት አንዱ ቀልደኛ፣ 'ሰለሞን ይህቺን ጠባሳም ምን ብሎ ወደዳት?' ብሎኛል:: ምን ልበል? 'ሴሰኛ ሴት እንጂ ጠባሳ ሴት የለችም' አልኩት::) የበረሀ ጉዞ መጥፎ ነው:: እንዲህ ዓይነት ችግር እንዳለ ስለሚገባቸው ደንገጡሮቿ በማሰሮ በማሰሮ የጠላ ድፍድፍ ይዘው ነበር:: ጭኖቿ በተላጡ ቁጥር ይሄ ድፍድፍ በማንኪያ እየተለካ ቁስሏ ላይ እየተመረገና በንፁህ ጨርቅ እየተጠቀለለ ደጋግሞ ፈወሳት:: ምክንያቱ ምንድነው? ጥሩ ጠላ አንቲባዮቲክ የሚባል ንጥረነገር እንዳለው ስንቶች ያውቃሉ? አንቲባዮቲክ ዛሬ ለቂጥኝና ለመሳሰለው ኢንፌክሽን መዳኛ ነው:: ከዛም አልፎ የጥንት ኢትዮጵያውያን የድድ በሽታን በእሱ ይፈውሱ አልነበረም?

**ጥርስህ እየደማ የሚያስቸግርህ ከሆነ**

**ከመተኛትህ በፊት**

**ወይም**

**ከአልጋህ እንዳትነሳህ**

**በጠዋት ጠላ ለጋ'::**

**ይሄን ከምን እንደተቀመመ የማታውቀውን ሳሙናና የሲንጋፖር የላስቲክ ብሩሽ ከምታንጋጋ::**

መልካም ፊልቴር ሊሰ'ራ የሚችለው የጥንቱ መስሪያ መንገድ የተገለጠለት ብቻ እንደሆነ አምናለሁ:: እነዚህ መንገዶች ደሞ ሳይበረዙ ያሉት በአገራችን የገጠሩ ክፍል ነው:: ታንጉትንና ጥሩወርቅ ተርታ ሴቶች ተብለው የሚናቁ ፊልተሬን አሳምረው የሰሩበት ምክንያቱ ይሄ ነው:: *አንድ ነገር ሲስተካከል ልጁ ድሮ የነበረው ይመስላል (በቁስ ታሪኳ)*:: አባቶቻችን እንደ አሁኑ ጊዜ ሞተር ባይኖራቸውም፣ ብልሃታቸው ግን መስተፋቅር ነበር::

**መስተ ጠላ በለው**

ታንጉትና ጥሩወርቅ ይሄን ጠላ ጠመቃ ከማን ተማሩት? የ ዕውቀታቸው ከየት መጣ? እናታቸው ማን ነበረች? የእናታቸው እናትስ? እንዲህ እያልን ስንሄድ ማን ጋ እናርፋለን? አናውቅም:: የምናውቀው የጠላ ስራ ጥበባችን ብዙ ዘመን እንዳደረገ ነው::

አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ሰዎች እየበሉ እየጠጡ ወይም እየጠጡ እየበሉ፣ የሚገርመው ደሞ በልተውና ጠጥተው ከጨረሱ በሁዋላ፣ ቀፊታቸውን እያሹ፣ 'ምንድን ነው እባካችሁ የሚያበላንና የሚያጠጣን? እንዳያመን' ይላሉ:: ከበሉና ከጠጡ በሁዋላ፣ ከጠገቡ በሁዋላ፣ ለምንድነው ክፉ የሚናገሩት? ሲጀመር ለምን መጡ? በተደጋጋሚ እንደዛ ዓይነት ጠማማ ሰዎች ያጋጥሙኛል:: *ተሴዎች*[135] እላቸዋለሁ:: ተሴዎች በክፋት የሚወከሉ ሰዎች ናቸው:: ትንሽ መልካም ነገር ባለበት ቦታ መርዝ፣ ጥርጣሬና አለመተማመን በቧልት፣ በጨዋታና በቀልድ እያስመሰሉ እንዲሰርፅ ያደርጋሉ:: ሰይጣን በዐይን የማይታይ በእጅ የማይዳሰስ የዚህ አይነት ክፉነት አለቃ ነው:: ታዲያ እሱ ካልታየ ለምን አዳምና ሄዋን ተሳሳቱ? በእባብ:: እባብ *ተሴ* ይባላል:: እባብ ብቻውን ቢሆን በዱላ ይመለሳል:: እባብ አደገኛ የሚሆነው በሰይጣን በመታዘዙ ነው:: ለሰይጣን ሽፋን መሆኑ ነው:: ሰይጣን *አሴድ*[136] ይባላል:: አሴድ ተሴዋን ወይም እባቧን የሚያዝ ነው:: ቃሉ ከየት እንደመጣ እንጃ:: አንድ ቃዲ ነው ያወራኝ::

ፊልቴራችንን እንድናላግጥበት በለሆሳስ ያስተማረን ፈረንጅ በወርቅ መሳ ለመሳ ሰፍሮ የሚገዛው ነው:: እኛ ግን ልባችን ቀሊል ነውና እንኩዋን በትክክሉ ያልቀመሱትን ፊልተራችንን ይቅርና የሚወዱት ቡናችንን ስህተት ፈልገውለትና ፈጥረውለት ቢያጥላሉብን አብረን እናጥላላለን:: ሲያሞግሱልን ደሞ ሆዳችን እስኪወጠር ስሙን ለውጠን እንጠጣለን:: 'አቦል ቡና በወተት' ከሚሉን 'ማኪያቶ' ቢሉን እንመርጣለን:: እዝራ ወልደ ሲራክ እንዲህ ይላል: ***ፊልቴርን ያላወቅሃት አገርህን አታውቃትም::***

'ይሄ ደብተራ ምን ያወራል?' የሚለኝን አላዳምጠውም:: ጎበዝ ብሩህ ወጣት ይህቺን የተናገርኳትን ሳይንቅ መዝግቦ ይፈትሻል:: ያጠናል ይመረምራል:: እውነትን የሚያቆማት ጥቂት ነው:: ከሩቅም ይሁን ከቅርብ እውነት መኖሯ አይቀርም:: አፋችን ላይም ይሁን ሆዳችን ውስጥ እውነት ሁሌ አለች::

★

የተደረገን እያዳነቅንም ቢሆን ማድረግ እንዳልተደረገ ይቆጠራል:: የተዋጣለትን ሰውና አገር ፈልጎ እሱን መምሰል ብዙ ጊዜ ያየነው የፀባያችን አንዱ ጎኑ ነው:: በቋንቋችን መቀኘትና በአዲስ አባባል

---

[135] በሚስጢር ሰው የሚያሳድዱ

[136] ቃሉ ከውነተኛ ገጠመኝ የተቀዳ ነው:: አንድ ሰው ሌላውን: 'የተስማማህ ትመስላለህ' ሲለው 'ምኑን ተስማማኝ ውስጤ ተቦጥቡጦ አልቋል: ውስጤ በአሲድ ተበልቶአል' ይለዋል:: አሲድ= አሴድ:: አሲድ ማለት በቀጥታ ትርጉሙ 'ምቀኛ' ማለት ነው::

ማስደነቅ እንደምንደፍር አዲስ አካላዊ ነገር አስሶ የማግኘት ጀብድ የለንም:: በየቀኑ መደናቀፍን የምንፈራ እኛ እግረኞች:: ፊልተሬ የተለመደ የጌሾ መራራ እንዲኖረው ባህሉ ቢሆንም፣ እሱን ለመጠጣት ለሚቸገሩ፣ በተፈጥሮአቸው ለማይወዱ፣ ወይም ያምርብናል ብለው ሁዋላ ቀር ላለመምሰል የሚጣፍጥ ጠላ ለሚፈልጉ ወይዘሮዎች፣ ወይዛዝርትና ሃሞተ ቢስ ወንዶች እነሆ እንዲህ አደረኩ::

ከሃሌው ልምጣ: *ከስኳር*::

ስኳርን እንዴት እንደተጠቀምኩበት ከማውሳቴ በፊት በመጠኑ ስኳር ራሱ ምን እንደሆነ ልናገር:: በአጭሩ ስኳር የሸንኮራ አገዳ ተክል መረቅ ነው:: ስለዚህ በትንሹ ስለ ስኳር ለማወቅ በትንሹ ስለሸንኮራ አገዳ ማወቅ ነው እላለሁ:: ይሄን ለእናንተ የማካፍላችሁን ሳይንሳዊ እውቀቴን (የስጋውንም ጨምሮ) ብታምኑም ባታምኑም የሰበሰብኩት ከብሪቲሽ ካውንስል ቤተ መፃሕፍት ቤትና (ኤንሳክሎፔድያ ብሪታኒካ) ይመስገን ከሰንጋ ተራው ወመዘክር ቤተ መፃህፍት ነው:: በድጋሚ እላለሁ እዚህ መጥታችሁ ሆዳችሁን ከምትሞሉ ምሁራን 'ኢንሳይክሎፔዲያ ሃበሺካ' ወይም 'ኢንሳይክሎፔድያ ኢትዮፒካ' የሚባል እስከምታበጁልን እንደእኔ ቢጤ እንዲህ እየዞርን የረባውንም ያልረባውንም እንቃርማለን:: እስኪ ከሆዳችሁ ታገስ፣ ከብዕራችሁ በርቾስ በሉ:: መለካከፍ አይበሉአችሁ እንጂ፣ ማወቅ መቼም ደመኛችሁ ነው::

ሸንኮራ 37 አይነት ዝርያዎች እንዳሉት ይታመናል:: የሚቆጠረው እንደ ጣፋጭ ሳር ነው:: ጎሳው andropogoneae ንኡስ ጎሳው saccharum ይባላል:: ዘሩ የተገኘው ከኒው ጊኒ ነው (ይሄን ተገኘ የተባለበትን ቦታ አድምቄ ማመን አልችልም):: ብዙ ጊዜ እርዝመቱ ከሁለት እስከ ስድስት ሜትር ይደርሳል:: ከሸንኮራ የሚገኘው ዋናው ንጥረ ነገር *ሱክሮስ* የተባለው የአገዳው መረቅ ነው:: በአለም ላይ ያለው ስኳር 80 በመቶ፣ በእኛ አገር ደሞ መቶ በመቶ የሚገኘው ከሸንኮራ አገዳ ነው:: ይህቺ ከደብረዘይት ወዲያ ከናዝሬት ግድም ያለችው *ወንጂ* የተባለችው ወረዳ ቀላል እንዳትመስላችሁ:: ሸንኮራ አገዳ ሌላ ብዙ ብዙ ጥቅም አለው:: ቅርፊቱ ማገዶ ይሆናል፣ ለቤት ስራ፣ ያገለግላል:: ስኳሩን ለማውጣት ሲባል የሚቀረው ሞላሰስ የተባለው ጥቁር ፈሳሽ ደሞ ለመንገድ ስራ ዋቤነት አለው::

ከሸንኮራ አገዳ መረቅ ወይም ጭማቂ ወይም ሞላሰስ ረም የተባለ መጠጥ ይሰራል:: የወዳጄ የዓሳዛር አባት ብርሃን ሁልጊዜ የሚጠጣው ረም ነው:: አንዳንዴ የበአል ቀን ሲሆን ብርሃንን ከሚጠጣው ባካርዲ ትንሽ እንዲሰጠኝ እጠይቀዋለሁ:: ብርሃን ረሙን ከሚሻሙት ሚስቱን ቢቀሙት ሳይቀለው አይቀርም:: ወጣትነቴን መንፈጊያ ሰበብ አድርጎ ('ለልጅ አልኮል ጥሩ አይደለም') ቆንጥሮ ይሰጠኛል:: አባቴ አንዳንዴ በሆነ ነገር

ከደከምኩበት፣ ያለሁበትን ትውልድ ጠቅለሉ 'ምን እናንተ የሻይ ልጆች' ብሎ ይተርበኝ ነበር:: 'የሻይ ልጆች' ሲል ስኳር ሊል አስቦ እንደበቱ የሳተ ይመስለኛል:: አገራችን የማር አገር ናትና ለምን ሻይ በማር፣ ቡናስ በማር ለምን አለመድንም? ሌላ የመምሰል አባዜ ካልሆነ? ታዲያ በዚህ በዚህ ነገር እየተለመደ የመጣውን ይሄን ስኳር አንድ ነገር እንዳደርገው የሚገፋፋ ሃሳብ ሞላኝ:: ለምን ስኳርን ፊልቴር ለመስሪያ አልጠቀምበትም?

ሰፈራችን ውስጥ ዋናው መንገድ የቦይ ፈረድ ዳር ዳር እየተቀመጠና እየተነሳ፣ ወዲያ ወዲህ እያለ፣ እየዘፈነና እያንጎራጎረ ትዝ ከሚለኝ ጀምሮ ሸንኮራ የሚሸጥ 'ዋሕድ' የተባለ ሰውዬ አለ:: ለአንድ ቀን እንኳን 'መነገጃ ቦታዬን ልለውጥ' ብሎ ወደ ስድስት ኪሎ ወይም አራት ኪሎ ሸርተት ያለበት ጊዜ ትዝ አይለኝም:: ለጥምቀት በአል ብቻ ጃንሜዳ እንደሚሄድ አውቃለሁ:: ነጋዴነት ማትረፍ አላማው ነውና ግራ ቢገባኝ አንድ ጊዜ እንደ ጨዋታ አድርጌ 'ለምን ሌላ ሰው ያለበት ወይም የበዛበት አካባቢ ሄዶ ሸንኮራውን እንደማይሸጥ' ስጠይቀው እንዲህ ብሎ መለሰልኝ:

'ለኑሮዬ የሚበቃኝን እዚህ እሰራለሁ: እንደውም ይተርፈኛል:: ስለምን ለጥቂት ሳንቲም ብዬ ያልለመድኩትና ያልለመደኝ ቦታ ልሂድ? ገንዘቤን የምሰበስበው በልቤ ነው፣ በኪሴ አይደለም:: ብዙ ሰው ያለበት አካባቢ ዱርዬ፣ ስለጠንኩ ባይ ንቀተኛ፣ ተሳዳቢና ዘራፊ ነው ያለው:: እዚህ ገና ልጅ ልጅ የሚሉ ሕፃናት አሉ:: እድሜአቸው አስር እስኪደርስ የሚኮላተፉ ውጫጫት እንደ አፈር ናቸው:: እነሱን አሳድጋለሁ'

አዎ አስገራሚ እምነት ቢሆንም፣ እኔ ግን ከሸንኮራ ሽቀላው የበለጠ ከተለያዩ የሰፈሩ ሰዎች ጋር ቆሞ ማውራቱ ያስደሰተው መሰለኝ:: ዋሕድ በእርግጥ እዛ ሰፈር የሚኖረውን ነባር ይቅርና አዲስ ገቢዎችን ያውቃል:: ግራና ቀኝ የሚተላለፉትን ሰዎች እያየ ስሙ/ስሟ ማን እንደሆነ፣ የት እንደሚሰራ፣ የትምህርት ደረጃውን፣ ስንት ልጆች እንዳሉት፣ የልጆቹን እድሜ፣ ባለቤቱን፣ የባለቤቱን መልክና ቁመና፣ ባለቤቷ የት ይሰራ እንደሆነ፣ እሷ የት እንደምትሰራ፣ የትምህርት ደረጃቸውን፣ ማን በምን እንደታመመ፣ የትኛው ልጅ ልጆችን መልከፍ እንደሚወድ፣ ማን ከቤት ወጥቶ እንደተመለሰና እንዳልተመለሰ፣ ማ ልጅ የት ቦታ መጫወት እንደሚወድ፣ ማን ከማን እንደሚቀራረብ፣ የተከራረፉ እነማን እንደሆኑ፣ ማን ሃሜተኛ እንደሆነ፣ ማን ከማን እንደሚዋደድ፣ ማን ፎረፎራም እንደሆነ፣ ማን ምን እንደዋሸ፣ ማን ምን እንዳስወራ፣ ማን እከካም እንደሆነ፣ ማን ጥርሳም እንደሆነ፣ የማን ጥርስ እንደሚነቃነቅ፣ ማን እንዳወለቀ፣ ማን ድምፀ መልካም እንደሆነ፣ ማን ጎበዝ ተማሪ እንደሆነ፣ ማን ሰነፍ ተማሪ እንደሆነ፣ ማን ከማን እንደሚውል፣ ማን ቀልድ እንደሚወድ፣ ማን ቀጫጫ እንደሆነ፣ ማን ወፍራም እንደሆነ፣ ማን

እየወፈረ ማን እየከሳ እንደሆነ፣ ወዘተ.....በቀላሉ መንገር ይችላል:: አንዳንዴ የሰፈር ወሬ ስፈልግ ከእሱ ሽንኮራ እየገዛሁ እየበላሁ አዋራዋለሁ:: የሚሸጣቸው ሸንኮራዎች ሁልጊዜ የሚጣፍጡ፣ ተባይ ያልቦረቦራቸው ረዣዥም መለሎታ ያላቸው ናቸው::

አንድ ቀን በጨዋታ መሃል ስለዓላዛር ወሬ ተነሳና ጀርመን ከሄደ አንድም ደብዳቤ እንዳልፃፈ፣ ከእሱ ያልተጠበቀ ነገር እንደሚያደርግ ስነግረው ሳል ሳለና በጎሪጥ አየኝ:: ሳሉ 'ወሬ አለኝ' ማለት ሲሆን፣ የጎሪጥ አስተያየቱ ደሞ 'ወሬውን ላትወደው ትችላለህ' ማለቱ እንደሆነ ይገባኛል:: 'ምን አለ የምታወራው?' አልኩት:: በመጀመሪያ አጠቃላይ ወጣቶችን አወገዘና ቀጥሎ የፈረንጅ አገር ስለሚመች ሀበሾች ወይም የዘመኑ ሰዶች ወላጆቻቸውን ቢረሱ የሚገርም እንዳልሆነ አወራኝ:: አሁንም የቀረው ነገር እንዳለ ገብቶኝ 'የሆነ ነገር ልትናገር አስበህ ነበር አምጣው' አልኩት:: 'ካልተቀየምክ እነግርሃለሁ:: ግን የምታውቅ መሰለኝ' አለና ዓላዛርና አልማዝ ወዳጅ እንደ ነበሩ ቀስ ብሎ እየተገላመጠ በሚንገዳገድ አንደበት ነገረኝ:: በመጀመሪያ በአጠገባችን የሚያልፍ ሰው አልነበረም:: ተገላምጦ ምን አናገረው? ለመሆኑ ዓላዛርና አልማዝ እንዴት ወዳጅ ሊሆኑ ይችላሉ? ግራ ገብቶኝ አተኩሬ ሳየው እየተደናበረ: 'ያለፈ ነው፣ ተገላግሏል:: አንድ ነገር አስደግማበት እንጂ ተባረኪን የመሰለች ሸንኩርት ትቶ እዛች ጋ ማን ይሄዳል?' አለና ያስደነገጠኝን ወሬ አዝናኝ ሊያደርገው መሰለኝ ሳቅ ሳቅ አለ:: ዓላዛር ስለምን ይሄንን ይደብቀኛል? የገረመኝ ያስጀመረችው አልማዝ ናት ሲለኝ ነው:: ጊዜውን ጠየቅሁት:: 'ቆየ' አለ:: እንደቀላል ነገር:: ልቤ ከፋው:: ዓላዛር ከጓደኞቹ ከአማንና ከልዑል ጋር እዛ ይመላለስ ነበርና በመጠጥ ብቻ ብጠረጥረውም፣ ሰክሮ ተሳስቶ ሊያደርገው እንደሚችልና ዋሕድም በግሉ ከዓላዛር ምንም የሚያጣላ ጉዳይ እንደሌለው አምኜ በወንድሜ በዓላዛር ላይ ባለፈ ጉዳይ ቂም ያዝኩበት:: ዋሕድን 'ወሬኛ ነህ' ብዬ አብጠልጥዬ ብናገረውም፣ የተባረኪን ቤት እያየሁ ተከዝኩ:: አሁኑኑ እቃዋ ደውዬ ዓላዛርንና እሷን ያጣላቸው ጉዳይ ምን እንደሆነ እንደገባኝ ልንግራት አሰብኩ::

ይሄን ባወራኝ በወሩ መሰለኝ እርግጠኛ አይደለሁም፣ አስቤዛ ለመግዛት መርካቶ ወጥቼ ወዲያ ወዲህ ስንከራተት አንድ ድሮ ወወክማ አብረን እንሞላፈጥ የነበረ የማውቀው ሰው አገኘሁ:: አንድ አንድ ስንል 'ለስራህ የሚያስፈልግህ ከሆነ እዚህ የኖረ የአርመን ሰው ለአንዱ ልብስ መጭ መቂያ ማሺን ትቶለት ከአገር ስለወጣ እየውና ግዛው' አለኝ:: ባለ ሆቴል እንደሆንኩ ስለሚያውቅ ልብስ መጭመቂያ ያለኝ፣ ቢኖረኝም ተጨማሪ የሚያስፈልገኝ መስሎታል:: ግን አንሶላዎቼ በእጅ ታጥበው በነፋስ የሚደርቁ እንደሆኑ አያውቅም::

ባልፈልግም፣ ወይም ባያስፈልገኝም የሚሆነው አይታወቅምና ሃሳቡ አጉዋጉቶኝ እቃውን ለማየት ወደ አዲስ ከተማ ትምህርት ቤት ጀርባ ሄድን:: ጉራንጉር ሰፈር ውስጥ ይዞኝ ገባና ይሄን ማሺን፣ በትክክል ማሺን ያልሆነ መሳሪያ አሳየኝ:: ዕቃውን በሚመለከት የመጀመሪያው ጥያቄ 'ይሄ ማሺን የተባለው ነገር ይሰራል ወይ?' ነው:: አዎ ማሺኑ ይሰራል:: እያንዳንዳቸው አንድ ሜትር ተኩል ስፋት ያላቸው ሁለት ከባድና ሸጣጣ የእንጨት ከበሮዎች ላይና ታች ሆነው ተዛዝለው ተሰርተዋል:: ከቀኝ በኩል እነዚህን ማሽከርከሪያ የብረት እጀታ አለ:: ከግራ በኩል ደሞ ቱቦዎቹን በተለያየ ከፍታ ለማራራቅና ለማጠጋጋት ደረጃ የወጣለት ጥርስና የእነሱን እርቀት መመጠኛ ማዞሪያ አለ:: ከታች ያለው ቱቦ የማይሽከረከር ግትር ነው:: ለመጭመቅ ሲፈለግ በመጀመሪያ ልብሱን ወይንም እርጥቡን ጨርቅ በቱቦዎቹ መሃል ከጫፉ በደንብ ተጣብቆ እንዲያዝ ካደረጉ በሁዋላ የግራ እጀታውን በማዞር ትክክለኛውን ከፍታ መምረጥ ነው:: ከዛ በሁዋላ የቀኙን እጀታ በማዞር ጨርቁ በቀስታ እየተጨመቀ ከሁዋላ ወደ ፊት ወይም ከአንድ ጎን ወደ ሌላ ጎን በቀስታ እየተመዘዘ ሲወጣ ማየት ነው:: ማሺኑ ለልብስ መጭመቂያ ተብሎ የተሰራ ቢሆንም፣ ሳልሞክረው ብገዛው ያከስረኛል ብዬ ፈርቼ ለሰውዬው ቃብድ ሰጠሁትና ለፍተሻ ወደ ሰፈሬ ጭኜ አመጣሁት:: ያኔው ዕለት ፈትሼው የሚሰራ መሆኑን አወቅሁ:: ለብዙ ጊዜ በተለይ ለክረምት ጥሩ ተገለገልኩበት:: ከመሃል ምግብ ቤቴን ሳስፋፋና መኝታ ቤቶቹ ሲዘጉ አሮጌ ዕቃ ማጎሪያ መጋዘን ውስጥ ወርውሬ ረሳሁት::

አንድ ቀን ትንሽ ስራ ፈትቼ ሆቴሌ በረንዳ ላይ ተቀምጬ መንገደኛ እያየሁ ሳለሁ፣ የዋሕድ ጥላሞት በምሽቱ ፀሐይ እረዝሞ ሆቴሌ ደጃፍ ላይ እንደተኛ ልብ አልኩ:: ሌላ ሌላ ነገር እያሰብኩ ዋሕድንና የዋሕድን ጥላሞት ሳይ ቆየሁ:: ከዛ አንዲት እድሜዋ አስራ ሁለት የሚሆን ልጅ መጥታ ከእሱ ሸንኮራ ገዝታ ወደ ላይ ዳገቱን ስትወጣ፣ ከምታኝከው ሸንኮራ የወለላ ኳሶች ሲፈናጠሩ፣ ይሄንንም ወለላ ከከንፈሮቿ ላይ ለመጥረግ ቆም ስትል፣ ጭማቂው ለብቻው ሲፈልቅ፣ ልቦናዬ ልጅትዋንና ዋሕድን ረስቶ 'ጭማቂ' የተባለው ቃል ላይ አተኮረ:: ልጅቷ በተመስጦ ሸንኮራ ለመግሞጥ እንደገና አፏን ስትከፍት የልብስ መጭመቂያው ማሺን ትዝ አለኝ:: ከተቀመጥኩበት ቶሎ ተነስቼ እቃውን ያስቀመጥኩበት ክፍል ሄጄ ጎትቼ አወጣሁትና ዋሕድን ያኔውኑ ጠራሁት:: ሸንኮራውን መንገድ ዳር አጋድሞ (ማንም እንደማይወስድበት ስለሚያውቅ):

«ምነው ፈለከኝ?!» እያለ መጣ

«በጀርባ ና አንድ የማሳይህ ነገር አለ» አልኩት:::

እየመራሁ ወደ ጀርባ ወሰድኩትና ማሺኑ ጋ አቆምኩት::

«ልብስ እጠብ እንዳትለኝ» አለ

«አይ ይሄንን ለሌላ ነገር ለመጠቀም እንድንችል ገብቶኝ እንድንፈትሸው ነው»

«ለምን ጉዳይ?»

«ሽንኩራ መጭመቅ እንችል እንደሆነ»

«ንግዴን ልትወስድ ነው?»

«ሃሳቤ እንዲህ ነው:: አልወስድብህም:: ምን ሃሳብ መጣልኝ መሰለህ:: አንተ ለእኔ ወለላ ጭማቂ ትሰጣለህ:: እኔ በጭማቂው የምሰራበትን እሰራለሁ:: መጀመሪያ ይሄ ማሺን ሽንኩራ ይጨምቅ እንደሆነ እንየው»

«ሽንኩራ ላምጣ» አለ ምንም ሳይከራከር

«ሁለት ሙሉ አገዳ አምጣ እከፍልሃለሁ»

ዋሕድ ከጥቂት ደቂቃዎች በሁዋላ ሁለት የሽንኩራ ዘንጎች በትከሻው ተሸክሞ እየሮጠ መጣ:: ማሺኑን እንደሚመች አድርጌ አዘጋጀሁና ሽንኩራዎቹን በአጭሩ ቆራርጠን በቁመታቸው ሰንጥቀን ሁለቱ የእንጨት ከበሮዎች መሃል አስገባን:: ማሽከርከር ስጀምር ውሃ የመሰለ መረቅ እየተንዠረዠረ መውጣት ጀመረ:: ሁለተኛውን ሽንኩራ ማበላሸት አልፈለኩም:: ዋሕድ ምን እንደምናገር ጠበቀኝ:

«ይሄን መረቅ የሚይዝልን ጣሳ ወይም ድስት ብቻ የሆነ ነገር እሰራለሁ፣ ሞዲፊክ አደርገዋለሁ:: ሽንኩራ ጭማቂ ትሰራልኛለህ»

«ለምን?»

«ነገርኩህ:: ንግድህ አይሄድብህም:: ሌላ ስራ ነው የምሰጥህ:: የምትወደውን ሰፈር ለቀህ አትሄድም:: አንተም መንገድ ዳር አትቆምም»

ከዚህ የበለጠ ማብራሪያ ሳይጠይቀኝ፣ ስላመነኝ ብቻ ፈቃደኛ እንደሆነ ነገረኝ:: ከዚህ በሁዋላ የቀረኝ ጥናቴንና የጥናቴን ውጤት አስተካክዬ ንግዴን ስልት ማስያዝ ነበር::

እነሆ እላችሁዋለሁ፣ ብዙ ደንበኞቼ 'ካልቀመስን ሞተን እንገኛለን' የሚሉለት ፊልተሬ በቴክኖሎጂ፣ በአጋጣሚና በፈቃደኝነት ስብጥር አንድ ቀትር ላይ ተፀንሶና ተወልዶ መጀመሪያ ሽሮሜዳን ቀጥሎ አዲስአባን በጣፋጭ እስማቱ ያዘ::

*

እዚህች ቦታ ላይ ይሄን ብልህነቴን በጥቂት ገፆችና በጥቂት ቃላት ስናዘዘው ሁሉን ነገር ቀላል አስመስዬ ነው::

ቀላል ቢሆኑ ኖሮ

እስከዛሬ

እንዴት እርስዎ

ልትሰሩት አልቻላችሁም?

በየሱቁ ለስኳር ከመደርደር እንዲህ ማሰብ ይሻል አልነበረም?

ስንቴ ነው ደጋግመው

በነጋዴ የስኳር ዋጋ የተነጀሱት?

እዩ! አንጀትዎ የተሰቀለበትን ኅለኅታ

(ወእሆ) መልካም ነገር ሁሉ ያልፋል:: ቢጠነቀቁ ባይጠነቀቁም፣ በ'ይታደሉታል እንጂ አይታገሉትም' ስልትም የሚለወጠው ይለወጣል:: መልካም ነገሮችም የራሳቸው ተሴ አላቸው:: ነገር በዝቶ እንቅፋት ከተደረደረ፣ መዝለል አቅቶኝ ብሰበር፣ ሰባሪው ከታየ ይበቃኛል:: ዮናስን እግዜር ለምን መረጠው? ፈቃደኛ ነበር? አልነበረም:: ቅዠት ሆና ብት-መጣም ዕርፈትን እንደ እንቅልፍ ጠጥቼአታለሁ፤ ብታደናቅፈኝም እንደ መንገድ ተጉገሬአታለሁ፣ ብታስነጥሰኝም እንደ አየር ተንፍሼአታለሁ:: ማን ይፈራል ዕርፈትን? ማን ይፈራል መንገድን? ማን ይፈራል አየርን? ማን ይፈራል ተሴን? ከተዋጣ ደግ፣ ካልተዋጣም......

የፈለገው ይመጣል እንጂ ተስፋ አልቆርጥም[137]:: ከጠላቶቻችንም እጅ አድኖናልና......እስመላለም ምረቱ[138]::

[137] ከዳዊት መዝሙር ምዕራፍ 135

[138] ዝኒ ከማሁ

## ማን ይፈራል ሂስ!

መግቢያ 1: 'ማን ይፈራል ሞት!' ይሉ ነበር ዘመናዮች:: እዛ ምን አደረሰ? ምን ይወስዳል እዚያ? የልባችን ነገር-አለሙ ተለውጦ ካልሆነ:: መጀመሪያውኑ ድመት የለም:: መጀመሪያውኑ አይጡ የለም:: መጀመሪያ ራሳቸውን በወሬ ወደ አይጥ ይለውጣሉ:: ከዛ ድመቱን በወሬ ይፈጥራሉ:: ከዛ ለድመቱ ጥሩ አፍንጫ ያበጁለታል:: ከዛ ባይፈልግም የሆኑትን አይጥ ወደ ፈጠሩት ድመት ወስደው እንዲያሸተው ያደርጋሉ:: ከዛ ይተርታሉ:: በሂስ የሚቀጣውን ለምን በሞት ልባከፈው? የነገር በዘበዛ በፀዳ አንደበት ይመለሳል:: የተሳሳተ ሁሉ በቋንቋ ይታረማል:: አንጉል የተቋጠረ ትብታብ በአማርኛ ጥበብ ይፈታል:: የተንከልን ገደል ሰዋሰው ይፈናጠጣታል:: ማን ይፈራል ሂስ......!

መግቢያ 2: ከአንዳንድ መሰረታዊ ነገሮች እንድነሳ ይፈቀደልኝ:: አሁን የምንኖረው ሕይወታችን ሙሉ በሙሉ ከዕውነት የተበጀ አይደለም:: ለምሳሌ አባቴ ቤቱንና ሌላም ሃብቱን ሲያወርሰኝ መቶ በመቶ በእኔ አምኖ አይደለም:: እንደኛ እሱ ራሱ ጠጥቶበትና ባልኀበት ሊጨርሰው ባለመቻሉ ሊሆን ይችላል:: ሁለተኛ ከእኔ ሌላ ሊያወርሳቸው የሚችሉ የቅርብ ዘመዶች ቢኖሩትም እንደሚጠላቸው በቂ ፍንጮች አይቼአለሁ:: ኩሸት እንደምወድና ባልተጠበቀ ወቅት ሆቴሉን አደጋ ላይ እንደምጥለው ይጠረጥራል:: አንዳንዴ ፊት ለፊት ማረጋገጫ ባላገኝም ራሴንም የሚጣላኝ ይመስለኛል:: 'ልጄ ረጋ ያለ፣ የሚያስብ፣ ጥርስ መልካም፣ አቋቋመ መልካም ቢሆንልኝ ኖሮ' ብሎ በመመኘት የእኔን ምድር ላይ መሆን ተቀናቅኖ ይሆናል:: በእሱ እጅ ባይሆንም፣ በድንገተኛ አደጋ እንድሞትም ሳይፀልይ አይቀርም:: አንዳንዴ ጆሮዬ ይገባል ቅር የሚያሰኝኝ ነገር ሲናገር:

'ሴት ብወልድ ይሻለኝ ነበር'

ለምን? ለምን እንዲህ አለ? ሴት ለመውለድ ፈልጎ ነበር? አይደለም:: በአጭሩ 'ይሄን አስቀያሚ እዝራ አልፈልግም' ማለቱ ነው:: ልጁ ባልሆን

መመኘቱ ነው:: ይሄ የግል ምኞቱ ነፃነቱ ነውና አልቀየመውም:: ግን ይሄ ማለት 'እወደዋለሁ' 'ሃብቴን ይውረስ' የሚለኝ አባቴ በመጠኑም ቢሆን በሚያሳዝን መልክ ውሸታም ነበር ማለት ነው:: ታዲያ ለምን አወረሰኝ? ብሩህ መሆን የሚያስፈልገው አሁን ነው:: ጉምና ጭስ ከመለየቱ:: ለምሳሌ ለልብስ መግዣ የሰጠኝን ገንዘብ ተቀብዬ አሮጌ ብስክሌት ገዝቼ በማከራየት ገንዘብ መሰብሰብ ስጀምር ተደንቆ አመስግኖኛል:: በአዋቂ አእምሮው የዘነጋው ኩሸትን ለመስራት አንጎል እንጂ ለዐይን ግቡ መሆን እንደማይጠቅም ነው:: በዚህ ስራዬ ልጁ በመሆኔ ወዶኛል:: አልተዘባረቀም? ለእኔ አልተዘባረቀም:: ሕይወት ነው:: ሶስት ወር ሲሞላ ሁለት አዳዲስ ብስክሌቶችና የብስክሌት መጠገኛ ጉረኖ ነበረኝ:: አመስግኖኝም ደባብሶኝም በልቡ 'ምናለበት ዐይነ ግቡ በሆነ' ማለቱ አይቀርም::

*

አንድ ሁለት አመታት ካለፉ በሁዋላ፣ ሐብታም መሆን ስጀምር አንዳንድ መሳደኞች በመበሳጨት---ጭንቅላታቸው ከጠማማ ብልጠት በስተቀር ሌላ ጤነኛ ጉዳይ ማሰብ የማይሆንለት---ሁልጊዜ የማይሳሳቱ፣ ቢሳሳቱ እንኳን ዞር አድርገው ሌላ ላይ የማላከክ ችሎታ ያላቸው፣ አዋቂ ነን ባይ *አፍገሬዎች*[139] እርስ በርሱ በተጣረሰ የወሌፌንድ *ወሬ*[140] ጠመዱኝ:: ከተራ ስልል ተነስተው የተለያየ ምክንያት እየፈለሰፉ የሆቴሌን መመሠረት፣ ማደግና ብርቱ መሆን ከግል ድብቅና ግልፅ ግምቶቻቸው ጋር አያይዘዋል:: መጠራጠራቸውን መብታቸው ነው ብዬ ብደግፈውም፣ በግልፅ ውይይት ሳይሆን በሃሜት መምጣታቸው፣ በአሉባልታ ልፋቴን መውረራቸው አስከፍቶኛል:: ሂስ አልፈራም:: ግን እንዲህ......

አውቃለሁ ይሄ አገር የስህተት አገር ነው:: አውቃለሁ ከዘጠና ዘጠኝ መልካም ነገሮች ቶሎ የሚታየን አንዱ ስህተት ነው:: አውቃለሁ የዚህ አገር ጠላቶች ያሉት እዚሁ ነው:: ትክክለኛ ቦታውም ወንዞቹና በረሃዎቹ አይደሉም፤ አንጎላችን ውስጥ ነው:: እዛም አብሮን እንደተወለደ ደም ይመላለሳል:: እውነት እውነት እላችሁዋለሁ መልአኩ ገብሬል ኢትዮጵያዊ ሆኖ ከሰማይ ቢመጣ በአንዲት ቀን ከክብሩ ይወርዳል:: እኛን የመሰሉ ቀልበቢሶች ይመደቡና በመጀመሪያ የክንፉን ላባዎች ብዛት ይቆጥሩና ጎዶሎ አሃዝ መሆኑን ይነግሩናል:: ይሄንንም (እንድናረጋግጥም ዕድል አይሰጡንም፤ ባይሆንም እናምናለን):: ከዛም 'እንዴት ጎዶሎ ያለው

[139] አፍገሬ--በአፉ አገሬ አገሬ የሚል

[140] ለማሳሳት ሆን ተብሎ በትክክል ያልቀረበ መረጃ:: መነሻው ማንም ሊሆን ይችላል:: ወዳጅም ጠላትም:: እንዴት ነው ወዳጅ መሆን የሚገባው ጠላት የሚሆነውን ዘመኑ ደደብ ከሆነ ሁሉ ይሆናል:: የማይሆነውም::

ላባ ያለው በራሪ ገብሬል ይሆናል?' ይሉናል:: እንዲህም አድርገው የገብሬላችንን ላባው ነጭተው ወደ ሞጆ እየነዱ ወስደው ተራ ገበሬ ያደርጉታል:: ወደ ደብረዘይት ስትሄዱ በመስኮት አንገታችሁን ወጣ ስታደርጉ ሞፈርና ቀንበር ተሸክሞ ከሩቅ የምታዩት አንድ አራሽ ምናልባት ገብሬል ነው::

እኔንና ልፋቴን በተመለከተ ከምላሰ--ሬቶች ከዐይነ--ቀያዮች የተረጨብኝ ሃሜቶች ከዚህ የሚከተሉት ናቸው (የእውነት ሆድ ምንስ ብትዝጎረጎር አስራ አንድ ትሆናለች?)

1/ 'እዝራ አሳሳቁ የሚያስፈራ መልከ ጥፉ ስለሆነ የዝቅተኛነት ስሜት አለበት:: ይህ የዝቅተኛነት ስሜቱን ለማጥፋትና *'ከማንም አላንስም'* ለማለት ልዩ ጥብስና ጠላ ፈለሰፍኩ አለ'

[ ከላይ ስለዚህ ነገር አንስቼ ወዳጆቼ እነ ዓላዛር በመልከ ጥፉነቴ ቀዳዳ ገብተው ጠባዬን ሊያበላሹ የሞከሩ ሰዎችን እንዴት ይከላከሉልኝ እንደነበረ በምሳሌ አብራርቼአለሁ:: ቢሆንም ይሄ የሆቴል ስራዬ የተጀመረውና የተስፋፋው በልጅነቴ የተቀበልኩትን የስድብ ብድር እንደ ምመልስበት *በቀሽንት*[141] አይደለም:: ይሄ ይሄ ዓይነት የዛገ ደካማ ጉዳይ ተንተርሶ ቂም መቋጠር የለብኝም:: እግዜር በሰራው ነገር ተበሳጭቼ ጎረቤቴን ለምን አስከፍላለሁ? መልኬን ያዲስአባ ሕዝብ መርጦ አልሰጠኝም:: ባኮርፍ እሱን አንድዬን ነው:: እሱንስ አኩርፌ የት ልደርስ? እንዲህ ያሉኝ ምን ያህል መልከመልካም ናቸው? ጥርሴ ቢንሻፈፍ እግርዎ ሽፋፋ አይደለ? ፀጉሬ ቢከረድድ እርስዎ መላጣ አይደሉ? እኔ ጎባጣ ብሆን እርስዎ ቦርጫም ነዎት ወይ ሲባጎ]

2/ 'እዝራ ገንዘብ ወዳጅ ነው:: ገንዘብ የሚያገኝበትን ምንም ነገር ያለፍርሃትና ያለ ሀፍረት ያደርጋል'

[እኔ ገንዘብን በራሱ አልወደውም:: ሲራክ 'ገንዘብህን በከንቱ አትበትን፣ ገንዘብም በቃኝ አትበል' ይላል:: ለመሆኑ ገንዘብ የማትወዱ ስንት ናችሁ? ብወድ ከፋት ያደርግብኛል? ገንዘብ የምወደው ሃሳቤን ስራ ላይ ያውልልኛል በማለት ብቻ ነው:: ነገ ብደኸይ አልገረምም፣ አላስብም፣ አልጨነቅም:: ነገ ብደኸይ ምላሳቸውን ለስድብ የሚያወጡብኝ እነዚሁ ተንኮለኞች ናቸው:: እንደውም ከአሁኑ መርጠው መርጠው ሞራሌን የሚያነኩቱ ስድቦች ሳያዘጋጁልኝ ይቀራሉ? 'እከካም' 'ዕድለቢስ' 'ምስኪን' የመሳሰለ? እነዚህ የጠለፋ ጥበባቸው ግቡ የት እንደሚደርስ የተረዱና በልምድም የዳበሩ ስም አጥፊዎች ናቸው:: ይልቁንስ እኔ እንደ እነሱ የማስብ እየመሰላቸው የአራዳ ቋንቋ ልጠቀምና 'የሚያነጅቡት':: መልካምነቴን (ባልገደድም ተገድጄአለሁና) በማስረጃ ልዘረዝረው::

---

[141] ተበዳይ ጊዜ ዞሮ በዳይ ሲሆን

ሰራተኞቼ በደንብ ይከፈላቸዋል:: ጠይቁአቸው:: አራት አሳላፊዎች፣ ሁለት እንጀራ ቤቶች፣ አራት የስጋ ቤት ሰራተኞች፣ ሁለት ጠላ ቤቶች፣ አንድ ድልህ ቤት፣ አንድ ዋሕድ፣ በመጨረሻ ሁሉን የሚያስተባብረው ጌታቸው፣ በጠቅላላ ቋሚ የሆኑ አስራ አምስት ሰራተኞች በስሬ ይተዳደራሉ:: ሲታመሙ የማሳክማቸው እኔ ነኝ:: ሰራተኞቻቸውን በመበደል ብልጥ እንደሚሆኑ ነጋዴዎች አይደለሁም:: ብልጥነቴ ያለው ሰራተኞቼ ሲቸግራቸው ለመርዳት በማሳየው ቅን ጉጉት ነው:: በግል ሊሸከሙት የማይቻላቸው ችግር ሲያጋጥማቸው ሳይፈሩ ይነግሩኛል:: እርስ በእርሳችን ከመተማመናችን የተነሳ ምግብ ቤቱ የሁላችን ይመስላል:: ማድ ቤት ለአንድ ሰአት የሚሆነውን ብታዩ 'የዚህ ቤት ባለቤት ማነው?' ትላላችሁ:: ለምሳሌ ዘመዶቻቸውን ለመጠየቅ ክፍለ ሀገር ሲሄዱ ለብርቱካንና ለጉዋደኛዋ ለትራንስፖርት እከፍልላቸዋለሁ:: ብዙዎቹ ሲታመሙ በራሴ ወጪ አስታክሜአለሁ:: አንድ አሳላፊዬ ትዳር ሲመሠርት ለድግስ የሚሆነውን በሬ በራሴ ወጪ ገዝቼለታለሁ:: የአንድዋ ሰራተኛዬ ሴት ልጃቸው አለማያ ኮሌጅ ስለምትማር የኪስ ገንዘብ በየወሩ እልክላታለሁ:: ይሄን ሁሉ በተጨባጭ ማረጋገጥ ይቻላል:: ምግብ ቤቱ ስራ ከጀመረ በኋላ የአባቴን ቤት አፍርሼ የሚመቸኝ ቪላ ሰርቼአለሁ:: መኪና ገዝቼአለሁ:: በቂ ገንዘብ ባንክ አለኝ:: ይሄ የቸርነት ነው:: ይሄ የገብጋባ አይደለም:: 'አትንገብገቡ ይንገበገቡባችኋል' ነው:: ገብጋባነት ድግስ እንደሚያንጨባርቅ ይገባኛል:: ታዲያ ወሬኞቹ ለምን ይሄን አይነት ቃለ አህስሮ ተጠቀሙ?]

3/ 'ሆቴሉ የእዝራ ስራ አይደለም:: እዝራ ያ ዲያቆን እንዲህ ዓይነት ቢዝነስ የመስራት ችሎታ የለውም:: ከጀርባው የሆነ ድርጅት ወይም ፈቱን ሊያሳይ ያልፈለገ ወይ ስሙ ሊጠራ የማይሻ ሃብታም አለ:: አንደኛው ወገን 'እዝራ ፀረ--አብዮት ስለሆነ ለፀረ--አብዮተኞች ገንዘብ እየሰራ ይረዳል' የሚል ሲሆን፣ ሌላው ደሞ 'ሰዎች በሆድና በመዝናናት እንዲዘናጉና ከትግል እንዲርቁ በደርግ ድጎማ ተደርጎለት ነው' ይላሉ::

[ይሄ ወሬቻ ከአንድ ዓይነት ፖለቲከኞች ወይም ሰዎች አፍ ይወለድ ወይ በሁለት ተፃራሪ ድርጅታዊ ሐይሎች ይነዛ እስከዛሬ እርግጠኛ አይደለሁም:: እንዲህ ኢደሉና ፀረ ኢብዮተኛ እየጠሉ፣ ግን ጥብሴን ሊበሉ ተሰልፈው ይመጣሉ:: እንደገናም ደርግን እየጠሉ ቤቴ ፊልቴር ሊጠጡ ይመጣሉ:: ያስገርማል? አያስገርመኝም:: ዋናው አላማቸው ማበለሻሸት ነውና የፈለጋቸውን ብልሃት ይጠቀማሉ:: የቻሉትን ተንኮል ይገምዳሉ...... ስለ እግዚአብሄር ክብር በአደባባይ ዘምሬአለሁ:: በሕይወቴ ነፍስ ሳውቅ የበደልኩት ሰው ትዝ አይለኝም:: በራሴ እላፍርም:: በኩሽቴ ያበሳጩ ሁትን በልቦናዬና በእግዚአብሄር በኩል ይቅርታ ጠይቄአለሁ:: በራሳቸው የሚያፍሩ ሃጢያት ያለባቸው ናቸው:: ሕቡዕ ነገር ሁሉ የተረገመ ነው:: መልካም ነገር ሁሉ መቅረዝ ላይ ይቀመጣል:: ጠማማ ነገር ሁሉ ጋን

ውስጥ ይደበቃል:: ስለዚህ የእኔ ነገሬ ሁሉ ግልጥልጥልጥ ነው:: ይኼን ቃለ አፍርሆ የሚያስቡት አንዳንዶች ካለ ሌላ ሰው ግፊትና ተራ የወሬ ነጻጅ ሊነቃነቁ የማይችሉ ሕልውናቸውን በብድር አሳብ፣ በሆደ ሆደና በጅም አሉባልታ የሚያስተዳድሩ ናቸው]

4/ 'እዝራ ቤተሰብ የለውም:: እንደምታውቁት ሚስት ድስት ልጅ የለውም:: ሚስቱ ድስቱ ልጁ ሆቴሉ ነው:: ይሄ ሆቴሉ ታዲያ የተሙቀላ ወንድነትና የቤተሰብነት ስሜት ይሰጠዋል'

[አባቴንና እናቴን መተካት የሚችል ምንም ሃብትና ስራ የለም:: የፍቅር እኩያ ምንድነው? ገንዘብ ሰውን እንጂ ራሱን ማገልገል የለበትም:: በቅዱስ መጽሐፍ እንድንሰራ ተደንግጎአል:: መብላትና መጠጣት ብሎም መኖር አለብኝ:: ይሄ መስራት ይጠይቃል:: 'አይ አለማወቅ' የሚባለው ይኼን ጊዜ ነው:: በተጨማሪም በልቤ እላለሁ *የማክዳን ነገር አልሰማችሁም*]

5/ 'የእዝራ ኮከቡ አፍዝ አደንግዝ አለው:: በዚህ የተፈጥሮ ችሎታው ብዙ ደንበኞችና ወዳጆች መሰብሰብ ችሏል'

[ኮከቤ ደለዊ ነፋስ ነው:: በጥር ወር ነው የተወለድኩት:: አውደ ነገስት በመተተኛነት አያማኝም:: እንደውም ቃሉ ራሱ 'ደለዊ' ማለት አደላዳይ ወይም ሐይለኛ ማለት ነው:: እንደውም መፅሐፉ 'በተወለደበት አገር ጠላት ይበዛበታል' ነው የሚለው:: በዚህ ፍቺ ከተመራሁ፣ እንዲህ በክፉ እንደቀፀሉኝ አንዳንዶቹ ወታደራዊ መንግስትን ተሳድቤ፣ ስለ ዲሞክራሲ ስለመሳሰለው ብዙም ስለማላውቀው ነገር ቀባጥሬ ወደ አሜሪካ መሰደድ ነበረብኝ:: ያኔ አማረልኝ ልባል ነው?]

6/ 'ምንም ኮስማና ቢሆንም፣ የሽሮሜዳ አካባቢ የመጀመሪያው ሆቴል ታዚና ነበር፣ ከመሃል ተፎካካሪ የሆነች 'አልማዜ' የምትባል ከባድ ነጋዴ አጣደፈችው:: በዚህ መነሾ ከዚህች አልማዝ ከተባለች ሰፈር 'አልማዜ' እያለ በቁልምጫ ከሚጠራት ታዋቂና ተወዳጅ ሴት ጋር ቀንቶባትና ተመቅኝቷት ሰላምታ መባባል አቁሟል:: ከርሞ ከርሞ 'ካንቺ አላንስም' ለማለት በፉክክር ጀምሮ በድንገት በጥብስ ቀናው:: እስከዛሬ ድረስ ከሴትዮዋ አልታረቀም። እስከዛሬ ቂም እንደያዘባት ነው'

[ይሄ ሁሉ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ቅጥፈት ነው:: ለመሆኑ አልማዝ የተባለችውን ሴት ማነው 'አልማዜ' ብሎ አቆላምጦ መጥራት የጀመረው? ስለምንስ? መቼም ማንንም 'አቆላምጥ' 'አታቆላምጥ' ብዬ መንገር መብት ባይኖረኝም ለራሴ ግን ወስኛለሁ:: ሳላቆላምጥ 'አልማዝ' ነው የምላት:: በዚህ ቀጥታ አጠራሬ ቅር ብሏት ደጋግማ ገላምጣኛለች:: እንዲህ የምልበት ምክንያት በንግድ ሰበብ ፉክክሯ አበሳጭቶኝ ተቀይሜአት ሳይሆን የሚቆላመጥ ነገር ስለሌላት ነው:: አንዳንድ ሰው 'ማነህና የወጣልህ አስቀያሚ ማቆላመጥ የሚገባውን ፀአዳና ውብ ፍጡር አላቆላምጥም

የምትል? ማንስ ይሰማሃል?' ሲለኝ ይችላል:: ከታዚና እጅግ ዘግይታ የመጣች ብትሆንም (1962 ላይ) አዲሱ ታዚና ሲከፈትና ሲረቅ ንግዷ የሚበላሽባት መስሏት ስትገላምጠኝ፣ ስሜን በተለያየ መልክ ስታጠፋና ባሌለሁበት ስትሰድበኝ እንደ ነበር ሰምቼአለሁ:: ግን ቆይቶ በእኔ ጥብስ የጠገቡ፣ በድልሄ የነደዱ፣ በፊልተሬ ሞቅ ያላቸው ወንዶች ሴት ፍለጋ ወደ እሷ ቤት እንደሚሄዱ ሲገባት መፍለቅለቅ ጀመረች:: እኔም ስሜቷን እየተከተልኩ ሳልለዋወጥ ያው በአልማዝ መጥራቴን ቀጠልኩ:: አንደኛው ያልገባኝ ነገር ሁልጊዜ መቆላመጧ ነው:: አዎ ቁንጅና አላት:: አዎ አቋቋም አላት:: ግን ምን ማለቱ ነው አልባልና ተጠግቼ ሳያት እቃ የጠፋው ሰው ትመስለኛለች:: አልማዝን ቀረብ ብዬ ሳያት እገረማለሁ:: ሰላምታ ከሰጠኋት በኋላ ራጉኤል ምስክሬ ነው 'አገኘሽው?' ማለት ይቃጣኛል:: ይሄ ሁኔታ ሚስጢር ስለሚሆንብኝ እንደ አንድ ኮስታራ ጉዳይ ጊዜ ሰጥቼው እያሰብኩ መገረሜን ለመቀነስ አንዳንድ የግምት ጥያቄዎች እጠይቃለሁ:: ፍልስፍናም እፈላሰፋለሁ:: ይሄ ይመስለኛል: በጨቅላነታችን ከእናታችን ማሕፀን ስንወጣ ቅቤ መዋጥ ይገባን ይሆናል:: ይሄ በአገራችን የተለመደ ባህል ነው:: እና አልማዝ ከእናቷ ማሕፀን ስትወጣ ቅቤ ለመቀበል አፏን ከፈተች:: በቅቤ ምትክ እስከ አንጀቷ የሰረበው ቀዝቃዛ አየር ነበር:: እናቷ ቅቤ ያልሰጠቻት ደሃ ሆና ሳይሆን ሲመስለኝ እሷም ስለ ጠፋባት ነገር ስታስብ ቅቤ ማዋጡን ረስታው ነው::

ታዲያ ከአልማዝ ጋር በመንገድ ላይ ስንተላለፍ (ምንም እንኳ ከመሃላችን መፎካከርና ጠብ ባይኖርም)፣ ውበቷ፣ ዘና ያለ አካሄዷ ይሰወርና እቃ የጠፋባት ትመስላለች:: ከቤቷ የጠፋባትን ዕቃ ለመፈለግ የወጣች ይመስለኛል:: ይሄ ከአንድ ሁኔታ ወደ ሌላ መቀያየሯ ሁሌ ይመስጠኝና በመገረም ሳያት አመለካከቴን አሳስታ ተርጉማ: 'በል አምጣው' የምትል ይመስለኛል:: ማለቴ ያ የጠፋባትን......ያን በጉሎ ቅጠል የተሸበለለ ለጋ ቅቤ::

አልማዝ 'ትጠንቁላለች' የሚባል ቀልድ የመሰለ ነገር ሰምቼአለሁ:: በቡና አተላ እንደሚጠነቆል ሁሉ እሷ በቀይ ወጥ መረቅ ትጠንቁላለች ብለውኛል:: ይሄ ሁሉ ለእኔ ጨዋታ ነው::

ልጎዳት ብፈልግ ብዙ ድክመቶች አላት፣ አራት አምስት ቦታ ተከርቸም ከፍታ በወጣት ሴቶች እንደምትነግድና ኮሚሽን እንደምትበላ አውቃለሁ:: ማረጋገጫም አለኝ:: የአልማዝ ነገር እንግዲህ ይሄ ነው::]

7/ 'እዝራ ከራጉኤል ሲያባርሯት 'ሆቴል' ብላ የራሷን ስጋና ወደሙ እዚህ ጀምራለች:: ከባለጌ ደብተራ ምን ይጠበቃል?' ይሉኛል::

[እንዲህ ሲሉኝ እስቃለሁ:: ከራጉኤል አልተባረርኩም:: በስራ ብዛት ምክንያት ከዛ መልቀቄ በአዋጅ ስለማይነገር፣ ይኼንንም ድንቁርና ታኮ ስም ለማጥፋት ቢመቻቸው፣ ላልገባው ይመስላል:: ባልስቅም አዝናለሁ::

ባደርገውስ ሐጢያት ነው ማን አለ? እኔን ለማሽሟጠጥ ተብሎ ፊልተሬ 'ጠበል' ተብሎ ቢቀጠልበት፣ አሳመረው እንጂ አልከፋኝም:: ስጋና ወደሙን የምናገኘው (ምሳሌው ከቤተክርስቲያን ተቀመመ እንጂ) ከመኖር ይመስለኛል:: ዋናው ጉዳይ ምርቃቱን ወደ ውስጥ ማስገባትና ከውሽልሽል ነገር ይልቅ መልካም ማሰብን መገንዘብ ነው::]

8/ 'እዝራ ከልጅነቱ በደጀሰላም ሲልከሰከስ የኖረ ከእግዚአብሄር ቃል ይልቅ ሁለመናው አካሉም ወደ ሰይጣን ስራ ያዘነበለ ስለሆነ በዛች ነገር ('ጥንቆላ' የሚለውን ቃል እንደተጠየፉት ሁሉ፣ ወይም ለአሽሙዋጣጭ አሳልፈው ሊሰጡኝ) እጁን ሳያስገባ አይቀርም:: ጠጋ ብለው ሲያዩትም ያስፈራል:: ይሄ ማስፈራራቱ ከመጥፎ መንፈስ ጋር ገና ከልጅነቱ ውል ማድረጉ ምልክት እንደሆነ የሚያውቁት ያውቃሉ:: ማረጋገጫውን የሚፈልግ የአይኖቹ ፀባይ ውስጥ ያገኘዋል'

[የሰከነ የስራ ውጤቴን 'የጥንቆላ ነው' ብለው የሚናገሩና የተናገሩ እነዚህ *ማሳፈሮዎች*[142] ሁሉ እነሱንም የሚያምኑ ደደቦች የስራ ውጤቴ የጥንቆላ ሳይሆን የአትኩሮትና የመረዳት መሆኑን እንዲያውቁ እፈልጋለሁ:: ከየት መጥቶ ወደ የት እንደሚሄድ ሊገነዘብ ባልቻለና ተጣልፎ በወደቀ ሕብረተሰብ መሃል መገንዘብ የተሳታቸው ችሎታዬ የት ቦታ እንዳለን ማወቄ ነው::

**ተግባባን?**

**ወይስ ተቀየማችሁ?**

ድክመቱንና ጥንካሬውን ከአፍንጫው ስር ለቅሜ ነው ያቀረብኩለት:: ጥንቆላ? እኔ እውነትን የምፈልገው ከማየው ነገር ስር ነው:: ምን? ማን? እነማን? ለማን? ከምን? እንደምን? እጠይቃለሁ:: መልሱም እግራችን ስር ነው:: ታዚና ምግብ ቤት በሕይወት የተረፈችው በዚህ ጥበቤ ብቻ ሳይሆን (ሃይማኖተኛ ነኝ ለማለት ሳይሆን) በእግዜር ፈቃድም ነው:: ***ሰምዐኒ ኢግዚኦ ፀሎትየ*** ብዬአለሁና:: ስራ፣ ጥዝጠዛንና እግዚአብሄርን ከያዝኩ ማን ሊችለኝ ነው? በእጭሩ ሁሉን የአቅሜን ካደረግሁ በሁዋላ መሳካት አለመሳካቱን ለእግዚአብሄር መተው እወዳለሁ:: ቅዱስ እስጢፋኖስ እግዜርን በናቁ ጉረኞችና ደካሞች በድንጋይ ሲወገር፣ ራሱን

---

[142] *ማሳፈሮ*---------*ማሳፈዎች* የሚያስተባብሩትና ያልገባው የዋህ

*«ማሳፈሮ ማሳፈሮ*

*ሰው ነህ ወይስ ዝንጀሮ»* እንዲል እረኛ

*ማሳፍ*———የራስን ስህተት በጥበብ ሌላ ላይ ማላከክና የብዙ ሰው ድጋፊም ማግኘት::

*ማሳፈ*———የማሳፍ ስራ የሚሰሩ ወንድና ሴት

ቀና አድርጎ ላምላኩ ፀለየ እንጂ እነዛን የከፋት ልጆች፣ እነዛን ጊንጦች መብረቅ ወርዶ እንዲጠርጋቸው አልተመኘም::]

9/ 'እንዴት እግዚአብሔርን ሲያገለግል የኖረ ልጅ፣ መልካም ነገርን ማስተማር ሲገባው በማታለል የተካነ ነጋዴ ሆነ? በዚህ በችግር ዘመን ሕዝቡ በረሃብ እየረገፈ ምን ልሁን ብሎ ምግብ ቤት ያቋቁማል? ለሕዝባችን አንድ እንጀራ እንዲሰጠው መፀለይ የለበትም ነበር? ይሉኝታም የለው? ምን ዘመን መጣን? ክርስቶስ 'ሃብታም ገነት ከሚገባ ይልቅ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ብትሾልክ ይቀላል' ያለውን ዘነጋው?'

[ነባር ባሕላዊ ማሳደጃ ሃሳብና ጥበብ አገኘን ለማለት ይሁን አላውቅም ከደጀሰላም ርቄ ሐብት በማፍራቴ የሚቀኑ ደብተራና ደብተራ አስተኔዎች ችሎታቸው ከእኔ ያልተባ ምላሳቸው ግን የሾለ '*ወብዐል በዘመነ ተፅናዕ*[143]' እያሉ ሊያጣጥሉኝና ሞራሌን ሊሰብሩ ሞክረዋል---ልክ እነሱ በልተው እንደማያድሩ:: እኔ የኢትዮጵያ ነጋዴ እንጂ የቅፍርናሆም ነጋዴ አይደለሁም:: የትኛው የተስፋፋ ንግድ ነው የሚያሳማን? የትኛውስ ስስቴ? ክርስቶስ ራሱ የነጋዴ አርቦሽ አለው አይደለም? መግደላዊት እግሩን የቀባችው ሽቶ ከሱቅ የተገዛ አይደለም? ሊያኮላሹን ሲፈልጉ ለአሰኛቸው ጊዜ መጽሐፍ ይጠቅሱብናል:: ዝናብ አሳድራለሁ አሉ እንዴ? ሕዝብን በድርቅ የመታው እግዜር ራሱ ሆኖ ለምን እኔ በአለአንድ ትንሽ ሆቴል ሰውዬ እታማለሁ? ሃሜቱንስ ያመናችሁት በእርግጥ አንጎል አላችሁ? ይሄን ይሄን ስሰማ ወንድሞቼና እህቶቼ ሆይ (ወእሆ)፣ ጡሩንባ አስነፍቼ መርዶ መቀመጥ ያምረኛል:: 'ለምን?' ቢሉ ይሄው እውነት በርካሽ የቅጥፈት ገመድ ተሰቅላ ስትሞት!!]

10/ 'ይሄ ሁሉ ሃብት እሱ የለፋበት አይደለም:: እንዴት እንዲህ እዚህ ግባ የማይባል ሰው በአጭር ጊዜ ሃብታም ይሆናል? አባቱ እግዜር የተጣላው አራጣ አበዳሪ ቄስ ነበር:: ቤቱን በሉ ሆቴሉን በሉ ጥሬ ገንዘቡን በሉ ምኑም በሉ በውርስ ያገኘው ነው' ይሉኛል::

[ትንሽ ለፍተን ገንዘብ ስናገኝ አጠገባችን እንኩዋን ያሉት እንዲህ ማለታቸው አይቀርም:: አባቴ አራጣ አበዳሪ አልነበረም:: ሕልሙ የከሸፈበት በዚህም የተበሳጨ እንደነበረ አውቃለሁ:: አዎ የአባቴ ገንዘብ ረድቶኛል:: ይሄ ማምታቸው እንጂ የገንዘቡን ብዛት አይተውት አይደለም:: ሃሳባቸው ግን የእኔን ጥረት ሁሉ የአባቴ በማድረግ እኔን ባዶ ለማስቀረት ነው:: ድንገት ንግዴ ቢበላሽብኝ እነዚህ ሰዎች ቀድመው አባቴን ከሆቴሌ ታሪክ ያወጡታል:: ያከሰረው ወንጀለኛ እኔ እሆንላቸዋለሁ:: ያለማረጋገጫ ሙታንን ማማት፣ ባሌሉበት ስማቸውን

---

[143] በችጋር ጊዜ መብል

ማጥፋት የአረመኔ ስራ ነው:: አዎ እነዚህ ሰዎች ይሄነት አያጣቸውም:: ለመሆኑ ይህቺ ምኑም የምትለው ቃል ለምን ገባች? አዎ እሳን የሚሞላት ሃብቱ ዛሬ የለም:: ግን ይህቺ ቃል ያን ወደፊት የሚመጣ ሃብት ተቀምጣ ትጠብቃለች:: ወደ ፊት አይሮፕላን ብገዛ እሱንም እንደወረስኩት ተደርጎ ይሞላባታል::]

11/ 'እዝራ ተወዳዳሪ የሌለው ገብጋባ ነው:: በሚያሳፍር መልክ ጠም እያደረ፣ ነፍስ ይማር እየለበሰ፣ የሰበሰበው ሃብት ነው:: ይሄን በስቃዩ ያገኘውን ሃብት ከሆቴሉ ያገኘው እንደመስልለትም ይለፋል:: አለማፈር ያደገበት ነው:: ምን ሙያ አለው? ወይስ አቡነዘበሰማያትን እየደገመ ጥብሱን ጠበሰ? ፊልቴሩን ጠመቀ?'

[ይሄ ከአስረኛው ሆሆታ በምን ይዛመዳል? እንዴት ሁለቱን እየሰሙ ሰዎች የቀረውን ማመን ቻሉ? 'አገር መጥፊያዋን ስትሻ የሀሰት አፍን ታሸታለች' ይላሉ:: 'ጠገብኩ' ብሎ መናገር ሁሉ የገብጋባነትና የሆዳ ምነት ምልክት ይመስላቸዋል:: ከልጅነቴ ጀምሮ ከቤቴ ስጋና ወተት የጠፋበት ጊዜ የለም:: እርጎማ ሁሌም አለ:: ጠዋት ቁርሴን የምበላው ሶስት እንቁላል ፈርፍሬ ነው:: አልኮል አልጠጣም:: ገብጋባ አይደለሁም ለማለት እንደ እነ አጅሬ መስከር አለብኝ? ልብሴ ዘናጭ ባይሆንም ፀአዳ ነው:: ትንባሆ አላጤስም:: ገብጋባ አይደለሁም ለማለት ሳንባዬን ላበላሽ? ቤቴ እንግዳ መጥቶ ቡናና ሻይ ሳይጠጣ፣ ከራበውም ሳይበላ አይሄድም:: እንግዲህ መሶብ ተሸክሜ በየሰፈሩ እየዞርኩ አላበላም]

•

ከማክዳ በፊት እጅግ የምወዳቸው ሶስት ነገሮች ቅዳሴ፣ ብስክሌትና ሶስተኛው......(ሶስተኛውን ወደ በሁዋላ እነሳዋለሁ) ነበሩ:: የቅዳሴው ነገር አንደኛ ነው:: ያን የረቀቀ ያሬድ ከእግዜር የተነጋገረበትን ዜማ ማን ሊጠላ ይችላል? ማንስ ልቡና ያለው ይንቀዋል? እሱንስ ተቀጥሬ ብሰራበት፣ ተምሬ በየደጀሰላሙ ከክህሎቴ የሚንፎለፎል ውበቱን ባንቆረቁረውና ምዕመናንን ባስደስት አያስመርቅም? የድምጼ ማማር ብቻ ሳይሆን ወደ ቤተክርስቲያን የምሄደውና ከቤተክርስቲያን የምመጣው በብስክሌት ነበር:: በዘናጭ ስፖርት ብስክሌት ላይ ተቀምጦ ያሬድን እያቀነቀን ፔዳል የሚያደርግ አያስገርምም? ኤልያስ በእሳት ሰረገላ እርጎ የለ እንዴ? እኔ ምድር ለምድር በብስክሌት ብንከባለል ምን አለበት? የብስክሌት ፍቅሬ እየጠና በመጨረሻ ከድሮው ሆቴል ጎን ትንሽ መጠለያ ሰርቼ የብስክሌት መጠገኛ ሱቅ ከፈትኩ:: ይሄ ስራዬ ከሰው ጋር የመቀራረብ፣ የንግድ፣ የገንዘብ ቁጠባና አወጣጥ ልምድ እንዲኖረኝ አስለጠነኝ:: የብስክሌቱ ነገር ከንግድ ቢላቀቅም አሁንም አንዳንዴ ስራዬ ጋብ ሲልልኝ በከተማ መሃል ርቅቅ ባለች ኮርስ እሽከረክራለሁ:: ሰዎችም

ይሉኛል: 'ምን የመሰለ መኪና አለህ:: ምን አይነት ኀብጋባነት ነው፣ ምን የሚሉት ዘዬ ነው በከተማ መሃል እንደ ዶሮ በሁለት ጎማ የምትንደፋደፈው?'

እኔም እላቸዋለሁ: 'እናንት ታካቾች የሰዎች ደስታ ይለያያል:: አንዱ በሊብነት፣ አንዱ በፖለቲካ፣ አንዱ በዝሙት፣ አንዷም በሆድ ይደሰታሉ:: እኔስ የሚያስደስተኝን መምረጥ የለብኝምን?'

መልሰው ይሉኛል:

'ሃብትህን በልተህ ሳትጨርሰው እንዳትሞት'

በልቤም እላለሁ: *ሁሉ የማከዳ ነው::*

*

(ወእሆ) ስለምን ይሄን ሁሉ ዘበዘብኩ? 'ይህቺ የጥብስ መቸርቸሪያ ፍንዱቅ ምን ያህል ወሳኝ ነገር ሆና ነው ብዙ ያወራህባት?' መባሌ አይቀርም:: 'ጭንቅ ያጨቃጭቅ' እንዲሉ ቢጨንቀኝ ነው:: 'ነገር ያናግራል' ቢባል ስህተት የለውም:: እኔ ያቺን ምግብ ቤት ማሻሻሌ ቀላል ጉዳይ ቢሆንም፣ ቀላል መሆኑን ባምንም፣ ተከትሏት የመጣው ጥምጠማ ግን ለትንሽነቷ የሚመጥን አልነበረም:: ይሄን ያልተገነዘበ እንዲገነዘብልኝ እሻለሁ:: እንኳን የሚያስብ ሰውና ደነዞችን የሚያስገርም ጎን እንዳለው እንዲታወቅም ስለምፈልግ ነው:: በአስራ አንድ ስልት ስነተረክ አንድ ጊዜ እንኳዋን እነዚህ የተቀጠፉም ያልተቀጠፉም ነትራኪዎች የሆቴሌን መፈጠር ከፍቅር ጋር አላያያዙትም:: ከሁሉ ከሁሉ ቅር ያለኝ በዚህ ነው:: የደረሰብኝ ነኝና መጠየቄ አልቀርም:: መጠየቅ ብቻ ሳይሆን *መመራመር* ነበረብኝ:: *መመራመር* ብቻ ሳይሆን መልሱን አገኘሁ::

በመልሴ ባትስማሙም *ወእሆ* ግድ የለኝም:: ቁም ነገር የሚሰሙ ከሆነ፣ በጴጥሮስ አፍ: 'ሕይወትን ሊወድ መልካሞችን ቀኖች ሊያይ የሚፈልግ ሰው ምላሱን ከክፉ፣ ከንፈሮቹንም ተንኮል ከመናገር ይከልክል' እላቸዋለሁ::

ስም አጥፊዎቹ በትክክል ከስያሜአቸው ጋር አድረዋል:: ብርድልብስ ተጋፈዋል:: ስምኝ ሰሪና እግዜር ያወጣዋል እንዲሉ:: ዋና አላማቸው ሞራሌን ለመስበር ስለሆነ የሰበሰቡት ግምት ሁሉ እኔን ማዋረጃ ሊሆን የሚችለውን ብቻ ነው:: ሁሉን ፍጡር ይግረመውና 'ፍቅር' የተባለው ቃል በሃሜትና በወሬ እንኳዋን እንዳይደርሰኝ ነው:: ከልብወለድ መሬታቸው ያሌለውን ምክንያት እየቆፈረ ያወጣው ዶማቸው መረሬ ሲምስ እንዴት አንድ ለወሬ የምትሆን ስለፍቅር የምትናገር ኳል ያጣል? ምን ያህል እንቅፋት መሆን ቢጣፍጣቸው ነው? ሰው መጣልስ ቢጎመጁ ነው? ቢሆንም ባይሆንም ይሄን ሆቴል እንዲህ ያዘመነው 'አንዷ የወደዳት

እንድትቀርበው ነው' የተባለ ግምት አልሰነዘሩም? በዚህ ሁሉ ዝባዝንኪ እንዴት አንዲት የአማረኛ ሃሜት እንኩዋን አይለጥፉብኝም? የአገራችን ሆድ ኸንጉርጉር ነው:: ይሄው:: ጥቁርና ነጭ ቡራቡሬዎች የወለዱን እኛ:: ደሞ የባሰብን አስገራሚ አስራ አንድ አይነት ውላጅ ቡራቡሬዎች:: የእናታችን ሆድ ምንም ቢኸጎረጎር የረባ ኸጉርጉር አለመሆኑ ምልክት ነው:: ወእሆ ይሄን እንደ ምሳሌ ውሰዱት:: የአገራችሁ ኢንዱስትሪ አቃቂ በስቃ አይደለም ያለው፣ እዚህ ነው:: የሚያሳዝነውም እንዲህ እንዲህ አስራ አንድ ጊዜ ማስነው[144] ዋናውን ምክንያት መጠርጠር እንኩዋን አለመቻላቸው ነው:: በዚህም 'ቋያ እንደ ከበበው፣ በእሳትም መሃል እንደማይቃጠል' ብሎ ሲራክ እንደመሰለው ሰው ሆንኩ::

ብዙ ደንባራዎችና መቀቴዎች[145] እንደሚሉት ስራዬን ሁሉ ያከናወንኩትና የማከናውነው ልዩ ሚስጢርና ችሎታ ኖሮኝ ሳይሆን ዕቅዴን የማወጣውና ስራ ላይ የማውለው ከማያቸው፣ በዝርዝር ከኖርኳቸው፣ ከነካሁዋቸው፣ ካሸተትኳቸው ነገሮች ነው:: እንደ አንዳንድ አዋቂ ነን ባዮች እና ተደላዮች ብልህነቱ አጠራጣሪ ከሆነ ጎረቤቴ፣ ማን እንደሆነ ከማያውቅ አብሮ አደጌ፣ ምን ዓይነት ሰው እንደሆነ ካልታወቀ ደራሲ ከፃፈው መጽሐፍ፣ ወይም ጋዜጣ፣ ወይም መፅሔት፣ ወይም ማን እንዳቁዋቁዋመው ከማላውቀው በጭፍን ከምታዘዘው የፖለቲካ ድርጅት አላማ አልዋስም:: የሌላ አካሄድ አልመኝም:: አለም እዚህ ጭንቅላቴ ውስጥ ናት:: ታዩኛላችሁ ደሞ አታዩኝም:: የኮክን ስጋ ቢቆፍሩ የሚያገኙት ወለላ ብቻ አይደለም:: ጠጠርም ነው:: ኮኩን ስወረውር እንዲበሉት ብቻ ማቀበሌ ላይሆን ይችላል፣ እንዲፈነክትዎትም ነው:: የሚወረወረው ቅኔ ነው::

**ግን ግንባርዎን ያለ ትርፍ ከሚፈነክቱ፣**

**አባጣዎን እያሹ**

**ከስጋው ሞንቸፍ**

**ቢያደርጉ አይሻልዎትም?**

ብዙውን ነገር እንዲህ በአጭር ታታ አድርጌ ሳወራው ያሳለፍኩት ችግር ይሄ ብቻ የሚመስላቸው አይጠፉም:: እሱ ብቻ ሳይሆን በየአይነቱ ቀለም አይቼአለሁ:: ችግርን ብቻ አይደለም ደስታንም እንደ ቆሎ ቅሜአለሁ፤ ፍሰሃ ደጋግማ የተባረከውን የቤቴን በር አንኳኩታለች:: ጣጣም በፈንታው የተለያየ ክብደት ባለው ኮቴው ወጥቶብኛል ወርዶብኛል፤ በአዲስአባም ራስ ወዳድ ጎዳናዎች ላይ እስኪሳቅብኝ ቼ ቼ

---

[144] (አስራ አንድ ጊዜ መማሰን) ከዚህ አጋጣሚ በሁዋላ በጣም ብዙ ከለፋሁ ወይም ሰው ሲለፋ ካየሁ 'አስራ አንድ ጊዜ ማሰንኩ ልረፍ':: 'አስራ አንድ ጊዜ ማሰንክ እረፍ' ማለት በከባድ መልፋትን የሚገልፅ ዘዬ ሆነ::

[145] የምቀኛ ተቺዎች (ስሩ ምቀኝነት የሆነ ትችት)

ብሎኛል:: አንዳንዴም የአለም ችሎታዋ መቅጣት ብቻ እስኪመስለኝ ተቆንጥጬአለሁ፣ እንዲህ ሲሆን እንደ ጌታዬ 'ተፈፀመ' አላልኩም:: የተሳሳትኩትን አረምኩ:: ከአሳሳቾችም ራቅሁ:: ጥንካሬዬንም አየሁ:: ስህተት የማይፈፅም የሰው ልጅ የለም:: ዛሬ የለበስነው ንጹህ ነገር ከትናንት ወዲያ ቆሸሾ ትናንት የታጠበ ቢሆን እኮ ነው:: 'ወእምሐበ ወረደ እንብዑ ሃረገ ንቅዓ ማይ ፀዓዳ'---ዕንባው ከፈሰሰበት ቦታ ዕሩ ውሐ ወጣ ይላል ገድለ-ተክለሃይማኖት......ታዲያ ቆሻሻው ወጥቶልን ነፍሳችን የምትፀዳው ሂስ ወይ ግለ ሒስ ስናደርግ ነው::

**ከሁሉ ከሁሉ ግን እልሃለሁ**

**ራስን ማጠብ ይመረጣል::**

## ተፃብኦ

እላይ ቃል ስለገባሁላችሁ ሳልጨርሰው ስላለፍኩት ('ሶስተኛውን ወደ በኋላ እነሳዋለሁ' ብዬ ያልኩዋችሁን) ታሪክ ልምጣ:: በሕይወቴ ላይ ለማንም ያላወራሁትን ከሁሉ ገኖ ጥልቅ ማህተሙን የተወው የሚቀጥለው ልምዴ ነው:: ደስታም አለው፣ ሐዘንም አለው::

በአፍላነቴ ጊዜ እንዲህ ሆነ፡ አንድ ቀን ከሰአት ላይ ዓላዛርን ልጠራው ቤቱ ሄድኩ:: ወደ እሱ መኝታ ቤት አርፌ እንደማለፍ እንደ ጨዋታ (ሌላም ጊዜ አድርጌዋለሁና) የብርሃንና የዕጌን (የአባትና የእናቱን) መኝታ ቤት በር ገርበብ ብሎ ነበርና ሳልገባ በቀስታ ገፋሁት:: እዛ ውስጥ ያየሁት ነገር እንደ እግዜር መልዕክት እንደ አዲስ ዘመን ራዕይ በአንጀቴ ገባ:: የዓላዛር እናት ሮዛ ውስጥ ልብሷን እየለበሰች ነበር:: ታጥባ መሰለኝ ሁለመናዋ እርጥብ ነው:: ቀይ ቆዳዋ ላይ የተለያየ መጠን ያላቸው ጨረሮች ካላዳረቀችው እርጥብ ገላዋ ላይ ይነሳሉ:: ከፍሉ በቅላትዋ ሰበብ የጠዋት ፀሐይ የገባችበት መስሏል:: በውሃ የታተተ ፀጉሯ አናቷና ጀርባዋ ላይ እንደ ረግረግ ቄጤማ ተኝቷል:: የቂጧ ዛላ ያሳዝናል:: ሆዷ ሉሕ ነው:: አንድ ጡቷ ወንድሜ ዓላዛርን ያጠባ (የታደለ) ገና ካልሸፈናት የውስጥ ልብሷ በር የተላጠ ብርቱካን መስሎ ይታያል:: ፊቷን ወደ እኔ ስላዞረች የአፍረቷን የተቆላዘመ ፀጉር አያለሁ:: በአለንጋ ጣቶቿ እንደ ቀላል ነገር ዳብሳ ከላዩ ውሃ አራገፈች:: በቀስታ እየተናገረች በቀስታ የምትራመደውን የአደባባይዋን ሮዛ አትመስልም:: ስለ ሴት ምንም የማላውቀው፣ ሴት ቀና ብዬ የማላየው፣ በሃይማኖቴ በእምነቴ ተሰብኬ ፍትወትን ችላ ብዬ የኖርኩ ጎረምሳ፣ ከውስጤ የሆነ ነገር ተፈቶ ሲለቀቅ ተሰማኝ:: ልቤ እዛ የሸከላ ወለል ላይ በፍትወት ተዘረረች:: ሮዛን ያየኋት ለጥቂት ሰከንዶች ቢሆንም ምስሏ እንደ ሕዋስ አእምሮዬ ስብ ላይ ታተመ:: በር እንደ ተከፈተ ሰምታ ጭንቅላቷ ልብሷ ውስጥ እንደሆነ 'ፀሐይ! ፀሐይ!?' ስትል እየሰማኋት ዓላዛርን መፈለግ አቋርጬ ቤቴ በቶሎ ሄድኩ:: ቤቴ ደርሼ እያለከለክሁ ስቀመጥ፣ የከፈትኩትን አፌን እንዳልዘጋሁ ታወቀኝ:: ያን ምሽት ብቻ ሳይሆን

ለሚቀጥሉት ሶስት ቀኖች እንደበቴ ቃል ማውጣት ከበደው:: ማንም ሊገምተው የማይችል ለራሲም የሚያስፈራኝ ስየታ አደረብኝ::

## እውነት እውነት እልሻለሁ

ራሴ ዞረ:: ከዛን ቀን ጀምሮ ለብዙ ሰዎች አባቴንም ጨምሮ ለመታዘዝ የማገነግነው ልጅ፣ ለፅጌ ባርያ ሆንኩ:: ምንም ያልገባቸው ሰዎች 'እሱ ሮዛ የምትለውን ይሰማል' ይሉኛል:: በትክክል የምሰማው ግን ያነሳሳኝን ውበቷን ነበር::

እንደ ውሃ የሚዋልል ለመሰለ ረዥም ቀሚሷ......

በነፋስ እንደሚገፋ ለጋ ደመና ለሚሰራው ዛላዋ......

ለአንገቷና ለቀሚሷ ክሳድ ውህደት......

ውሃ አረንጓዴ ቀለም ላለው ወገቧን ሰንጎ ለሚይዛት ሹራብ......

ለእጅ ጣቶቿ እርዝመትና ቅጥነት......

ደቃቃ ቀያይ ፈርጦች ላላቸው የጆሮ ሎቲዎቿ......

የሹራቧን እጅታዎች ስትሰበስብ ቀልተው ለሚታዩት ክንዶቿና ሰማያዊ ደም ስሮቿ......

ለመዳፏ ንጣትና በግድ ለሚታዩት ኸረቶቹ......

ከስታራም ይሁን ለስላሳ ጉዳይ ስትናገር ቤቴ ድረስ ተከትሎኝ ለሚመጣው ጆሮዎቼ ቅንፍ ውስጥ እንደ አበባ ወለላ ለሚተኛው፣ ለነፍሴ የሙዚቃ መረቅ ለሚሰራው ድምፅዋ......

በሆነ ቀን ታኮ ጫማ አድርጋ ነገረኛ የሸሮሜዳ ኮረኮንች ሲያንገዳግዳት፣ ለአፍታ አየር ውስጥ ደንግጦ መውደቂያ የጠፋው ለሚመስለው ክብ ቂጧ......የሚሰራውን እንደፈራ ሞላ ለሚንገላታው......

እናም በእጆቼ ሰብስቤና አርቅቄ እንደ ጥቢኛ ልበላት፣ እንደ ሸንኮራ ከነልብሷ ልመጣት ስንቴ ሰየሁ? እየተመኘሁ ሰየሁ?

ብዙ ጊዜ ሰዎች ያለሁበት አስቸጋሪ ሁኔታ የገባቸው እየመሰለኝ እፍራለሁ:: እግዜር እንደ ደቀ እስጢፋ፣ ጥበብ ቢያድለኝ ይገፔአት ለመጥፋት በምኖቴ ቦታ እመርጣለሁ:: አዋሳ ነው የምወስዳት? ሞጆ ነው የምወስዳት? ዝዋይ መሃል ደብቄ ነው አሳ እያበላሁ የማኖራት? እንደዛች እንደ ንጉስ ሚስት እንደ ሂሩት በድግምቴ አባይ በረሃ ነው ይገፔአት የምሄድ? ያኔ እንዲህ እንዲህ ሳልም ለራሴ ብቻ የሚገባኝ እርካታ ይሰጠኝ ነበር:: ከፅጌ ሌላ የታባ ስም አውጥቼላት ነበር: 'ሸንኮራ' 'ወደር የለሽ'፣ 'ትርንጎ'፣ 'ብርቱካን'፣ 'ማር ከረሜላ'፣ 'አቻም የለሽ'

አይደለም:: 'ዕፁብ' ነው:: ለ'ዕፁብ' ምን አቻ ትርጓሜ አለው? ዕፁብ **ወዕፁብ ውዕቱ/ እስመ ለዕፁብ ትርጓሜ አልቦቱ[146] እንደሚሉት::**

የፅጌ ነገር በዚህ ቢያቆም መልካም ነበር:: አልቆመም::

አንድ ሌሊት፣ እውነት የሚመስል ለረዥም ጊዜ የቆየ፣ እኔና ራጉኤል ብቻ እስከዛሬ የምናውቀው ሕልም አለምኩ:: በኅኸ ፅባሕ እሁድ ከእንጦጦ ዳገት ወደ ሽሮሜዳ አንዲት ሴት ነጠላ ተከናንባ ስትመጣ በመስኮት አያለሁ:: ይሄ መንገድ በጥቁር አረንጓዴው የእንጦጦ ተረተር ላይ ከቆቡ ጀምሮ ሽሮሜዳ እስከ ሰፈረበት አረሁ ድረስ የብር አለንጋ መስሎ እያብረቀረቀ ተኝቷል:: አልጋዬ ላይ የተንጋለልኩ ይመስለኛል:: መኝታ ቤቴ በእውን ደቡብ ትይዩ ስለሆነ የሚያሳየኝ የአዲስ አባን ማዕከል እንጂ እንጦጦን አልነበረም:: በዚህ ተገርሜ ሳለ በየት እንደሆነ እንጃ ሴትዮዋ 'ቤቶች!' ብላ አለሁበት ክፍል ትገባለች:: ፅጌ ነበረች:: አልጋዬ ግርጌ ቆማ ነጠላዋን ስትጥል ራቁቷን ናት:: ትራሴ ላይ የሚያምር አናቷ ተጋደመ::

ለሁለት ተከፍሎ በግራና ቀኝ ትከሻዋ ላይ አልፎ በደረቷ ላይ የዘመተ ፀጉሯን እየዳበስኩ፣ ሰልፋቸው ያማረ ፈገግ ባለች ቁጥር ልቤ የሚደክምላቸውን እነዚያን ጥርሶች እያየሁ፣ በዕለተ ደመና ብርሃን ያረፈባቸው የመሰሉ ጭኖቿን እያየሁ፣ ቢደመሩ የፊቷን ስፋት ግማሽ የሚሞሉትን አይኖቿን እያየሁ......በጤና አዳም የተከበበ የስኳር ጤዛ የተርከፈከፈበትን ሴትነቷን እያየሁ፣ ያላወቅሁትን እያሳወቀችኝ...... ስባንንና ስተኛ አደርኩ:: አለም በተኛበት ሌሊት ገላዋን ብርሃን ጎን ትታ በቀልቧ ተራከበችኝ:: ፀሐይ እመሰለ ደረቷ ላይ በቅዠቴ ደፋችኝ......ከዛ ቀን ጀምሮ ፍቅረኛዬ ሆነች::

በአስገራሚው የሕልም አለሜ ዛፍ ላይ ነበርን......ክፍክፋቱ ላይ እንደ ዝንጀሮ ተጎትተን ወጥተን ሰማይ እያየሁ እንደ ባሏ ያወቅኋት......መስክ ላይ ነበርን ሳቢሳዎች በሚንሸራሸሩበት፣ ላሞች በሞሉበት ፀሐይ የመታው ቀይነቷ ላይ ስንቴ የጎረምሳ ዘሬ ተደፋ......? በደረቅ የሽሮሜዳ ሌሊት ሁሉ ዜጋ በደነቆረብት? ስንቴ ዘፈንኩላት......? ስንቴ እንዲህ አልኳት......?:

**ዛሬ በምናቤ ትናንትና በሕልሜ**

**ታንኳ ተሰብሮብኝ ከባሕር ላይ ቆሜ**

**ታንኳውም አንቺ ነሽ ባሕሩም ዕንባዬ**

---

[146] ዕፁብ ዕፁብ ነው፣ ለዕፁብ ምን ትርጓሜ አለው?

ይሄ ቢያስደስተኝም እጅግ ረበሸኝ:: እንደ ልማዴ ፈጣሪ ሐጢያቴን ይቅር እንዲለኝ ነጋ ጠባ ተንበርክኬ እሷን እንዳያመጣብኝ የቆሰለ መትኔ እስኪረግብ ለአምላክ ፀለይኩ:: ለማርያም ደጋግሜ ተሳልኩ 'እባክሽ እንዳትመጣ ጎንሽ አስቀምጠሽ ተቆጪልኝ' ብዬ:: ግን አልሆነም:: እንደተፈረደብኝ ገባኝ:: እሱ እስኪምረኝ በትህትና ጠበቅኩ::

አንድ ዕለት ማክዳን ባየሁ በሳምንቱ መሰለኝ ከእስጢፋኖስ አስቀድሼ መጥቼ ደክሞኝ አልጋ ላይ እንዳረፍኩ እንቅልፍ ሳልጠብቀው ጣለኝና ሮዛን እንደ መጀመሪያው ዕለት ሆና በሕልሜ አየኋት:: ከእንጦጦ ተራራ ጀኖ ጥለቱ ድንቅ የሆነ እንደ መስታወት የሚፈልቅ ነጠላ ተከናንባ ትወርዳለች:: እኔ እንደዛው እንደለመድኩት በጀርባዬ አልጋዬ ላይ ነኝ:: በር ከፍታ ወደ እኔ ትመጣለች ብዬ ስጠብቃት መኝታ ቤቴ መስኮት አጠገብ ቆመችና አተኩራ አየችኝ:: ኩታዋን እንደተከናነበች ፊቷን ዞር አድርጋ መንገድዋን ልትቀጥል ስትል እየለመንኩ እጠራት ጀመር:: 'አፈር ስሆን!'(ልጅ እያለሁ ከአባቴ የኮረጅኩት መለመኛ ዘይቤ፡ 'ስሞትልሽ!':: እንዳሳዘንኳት ሁሉ መለስ ብላ የተኛሁበት መጣች:: ጎኔ እንድትተኛ በስርአት ብርድልብሱን ፈቀቅ አደረኩላት፣ ፈገግ እያልኩ ጋበዝኳት:: ነጠላዋን ሳታወርድ ጎኔ ጋደም አለች:: ራሷን ትራስ ላይ ከማስቀመጧ በፊት ቀኝ ክንዴን ያዘችኝና ለመጀመሪያ ጊዜ እንዳየችው ሁሉ በመሃል ጣቴ ላይ ያለውን ቀለበት አጠናችው:: ጎኔ ተጋድማ እጄን ወደ ላይ ስቅላ ቀለበቱን ስትዳብስ ቆየች:: ከአባቴ የወረስኩት ምሰዙን ሰሌዳ ላይ ጥቁር አንበሳ ያለበት የወርቅ ቀለበት ነበር:: እሱን እየዳበሰች እያለች የሆነ ነገር በመስኮት ውልብ ያለ መሰለኝ ዞር አልኩ:: ከተራራው ላይ እንደ ፏፏቴ የሚወርደው የእግር መንገድ ዐይኔን እስኪያመኝ ይፈልቅብኛል:: ሮዛን ለማየት ወደ ትራሱ ለመዞር ሳስብ ከጎኔ ተነስታ ከውጭ መስኮቱ ጋ ቆማ አየኋት:: የሆነ ነገር ቅር አለኝና እጄን ከፍ አድርጌ ሳየው ቀለበቴ ከጣቴ ላይ የለም:: የነበረበት ላይ የተሰነበረ አመዳም ቦታ አለ:: ዓይኖቼን ከቀለበቱ ዞር ሳደርግ፣ ሮዛ አልጋው ላይ የለችም:: ወደ መስኮቱ አየሁ:: ጀርባዋን ለእኔ ሰጥታ ኩረብታውን መውጣት ጀምራለች:: እንድትመጣልኝ ብጠራት አልሰማችኝም፣ ወይም ልትሰማኝ አልፈለገችም:: አንድ ጊዜ እንኳን ፊቷን ሳታዞር የእንጦጦን ዳገት እየወጣች የሚፈልቀውን መንገድ ተከትላ ጨለማ የመሰለው ደን ውስጥ ጠፋች......ከውስጤ የሆነ ነገር የጎደለ መሰለኝ በፍርሃት ባንንኩ:: ባልገባኝ ምክንያት አልጋዬ ውስጥ እንቀጠቀጥ ነበር:: ሁለመናዬ በላብ ተዘፍቋል፣ በደመ ነፍሴ ፍቅረኛዬ ተመልሳ እንደማትመጣ ገብቶኛል:: ከአልጋዬ ተነስቼ፣ እየተንገዳገድኩ እውጭ ወጣሁ:: ቀና ብዬ እንጦጦን አየሁ:: ፀሐይ ልትወጣ ጀምራለች:: ፊቴን ለመዳበስና አይኖቼን የበለጠ እንዲገለጡ ሳንቃቃ እጄን ሳነሳ ቀኝ ጣቴ ላይ የማደርገው ቀለበቴ እንደሌለ አየሁ:: ከላይ እስከታች በድንጋጤ ተመተርኩ:: ወደ ቤቴ ግድግዳ ተጠጋሁና ውሃ ልክ ላይ ተቀምጬ፣ በመተንፈስ ላይ ያለሁት

በሕልሜ ይሁን በእውኔ መወሰን ከበደኝ:: በግቢዬ ፊት ለፊት ለቀን ስራ የሚወጡ ሰዎች እየዘፈኑ ሲያልፉ ሰምቼ ነገሩ እውን እንደሆነ ተረዳሁ::

ቤቴ ገብቼ መኝታ ቤቴን ጨምሮ አራቱንም ክፍሎች ለግማሽ ሰአት ያህል ገለባብጬ ቀለበቴን ፈለግሁ:: አላገኘሁትም:: ከዛ ቀን ጀምሮ ግን ሮዛ ተመልሳ አልመጣችም:: ለሳምንት ያህል ሳይሆን አይቀርም ወሽባ ገባሁ:: የዚያው አመት ሚያዚያ ውስጥ እጅግ የምወዳት የጓደኛዬ እናት ሮዛ በልብ ድካም ከዚህ አለም በሞት ተለየች:: መሞቷን ስሰማ ውስጤ በሐዘን ፈረሰ፣ ነጋ ጠባ አነባሁ፣ ነጋ ጠባ ለመሆኑ 'ምኗ ነው?' እንዳልባል ቤቴ ዘግቼ እህህ አልኩ:: በዕንባ መታጠብ ግን በሕይወት ያሌለችውን በህልሜም የማትመጣውን ሮዛን ቀርቶ የእውኗን ማክዳን አልሰጠኝም:: (ለትንሽ መልካም ነገራችን ትንሽ የምንወደው አይሰጠንም? ምነው ጨከነ አጅሬ?)

*

አንድ ዕለት ስራ አድክሞኝ ከለመድኩት ሰአት ቀደም ብዬ ቤቴ ገብቼ ከሆቴሌ ያመጣሁትን ጥብስ በሻይ እያማግሁ ስበላ የግቢ በር ተንኳኳ:: ጉንጬን በጉርሻ አሳብጬ በማያጎርሰኝ ሌላ እጄ በር ከፈትኩ:: የዓላዛር ታላቅ እህት (እህቱ ባትሆንም እንደዛ ነበር የምንላት) ፀሐይ ነበረች::

«ታዲያስ ፀሐይ ምን እግር ጣለሽ?» አልኳት

«ላነጋግርህ ነበር፣ እንግባ» አለች

እጆቿን ጉያዋ ስለከተተች በጣም የበረዳት ትመስላለች:: ቀጭንና የማታረጅ ናት:: ዕድሜዋ አርባ ደርሶ ሃያ ትመስላለች:: ሮዛ መዓት ጊዜ ልታስተምራት ሞክራ አልሆነላትም:: እስከዛሬ ስሟን መፃፍ እንኳን አትችልም:: በሃሳብዋ የመጣውን የምታወራ፣ ሁልጊዜ ቀፈቷ እንደ ኮሮጆ ፊጦ የወጣ ነው:: 'ጥንቸል አርግዛለች' እንላት ነበር:: ግድ ሳይሰጣት ጠባብ ቦላሌ ሱሪ የምታደርግ ናት:: 'ኸረ በማርያም! እሱን አትልበሺ' ተብላ ስትነጨነጭ በላዩ ላይ ተራ ጉርድ ቀሚስ ለበሰች:: አሁን አሁን እሱ ለምዶባት ሱሪ በቀሚስ ነጣ የምትለብሰው:: ቁጡ ቢጤ ስለሆነች ከእሷ ጋር መነቃቸር 'አፍ መካፈት' ይባላል:: ቀፈቷን ማሳነስ አልቻለችም እንጂ ነገር መገለባበጥ ይሆንላታል:: የምትናገረውን ለመጀመሪያ ያጸመጠ 'ነካ ያደረጋት' ቢል አይገርመኝም:: ቅፅል ስሟ 'ተንፌ' ነው:: አልማዝን ባልታወቀ ምክንያት 'አንቺ ተነፊታ' ብላ ሰድባት ነው ስሙ የወጣላት:: ስለ 'መነፋት' የምታውቀው ነገር የለም:: ቃሉን የተጠቀመችው ግን ወገቧን ይዛ ነው:: ደጀሰላም የቀደሰ ሁሉ የሚጠነቁል እየመሰላት 'ትምህርት የሚገልጥ ድግምት አሰራልኝ' ብላኝ 'አላውቅም' ብዬአት እንደ ክፉት ቆጥራው አኩርፋኝ ነበር::

ፈገግ ብዬ (ኮስታራ ፊት አትወድም) ቀደም እንድትል ጠቀስኳትና ተከትዬአት ቤት ገባን::

«አንድ ነገር......» አለች ሳትቀመጥ

«ምን?»

«ሰው አይኖርም ብዬ ነው እንዲህ በሌሊት የመጣሁት፤ የወንደላጤ ነገር አይታወቅም:: ማን አለ?»

«እኔ ብቻ ነኝ»

ከጉያዋ ቀኝ እጇን አወጣችና ትንሽ የተጠቀለለ ጨርቅ ሰጠችኝ::

«ምንድነው?» አልኳት

«እረስቼው እስከዛሬ:: እቃ ሳሰናዳ አንድ ቦታ ተወሽቆ አገኘሁት»

«ምኑን?»

«እየው»

ጨርቁን እየፈታሁ:

«ሮዛ ከማረፏ በፊት ለእዝራ ስጪልኝ ብላኝ ነበር......»

......ጨርቁን ተርትሬ ስጨርስ እዛ ውስጥ የነበረው የጠፋው የጣቴ ቀለበት መሆኑን አየሁ:: ማመን ስላልቻልኩ አገላብጬ ከውስጥ የተፃፈውን አነበብኩ: 'ታዚና':: ምንም ሳልናገር አዞረኝና እንደ እውር ሶፋ በእጄ ዳብሼ ተቀመጥኩ::

«ደህና ነህ እዝራ?» አለች ፀሐይ ደንግጣ

በአወንታ ራሴን ነቀነቅሁ:: ግን ልክ አልነበርኩም::

«እቤት ሲጫወት ጥሎት ሳይሆን አይቀርም፣ ብላኝ በቃ......ልቤ በቃ......ታውቃለህ፣ ይቅርታ ስላዘገየሁብህ»

ለብቻዬ መሆን ፈለኩ:: ቀለበቱን በእጄ ጨብጬ ወዳጄን እመቤቴን በሕልሜ የፍስሐ መረቅ የምታጠጣኝን ሮዛን አሰብኳት::

«ውሃ ላምጣልህ?»

ፀሐይ ጓዳ ገብታ የማታውቅበትን ትፈልጋለች::

«ተይው!» አልኳት

የነገሩ ታምረኛነት ብቻ ሳይሆን ያደነዘዘኝ ሮዛ በሕልሟ በፈቃዷ ትመጣ እንደነበረ መረዳቴ ነው:: ከዛ ገና ከመንጋቱ ማዘን፣ መከፋት የጀመርኩት ሰውዬ ፈገግ አልኩ:: አልጋዬ ላይ ጋደም ብዬ በደስታ የባዘተች ነፍሴን አዳመጥኩዋት:: 'በዐይኑ ያየ አመነዘረ......በልቡም

የተመኘ አመነዘረ' የሚለውን ሸውዳ እንገናኝ ነበር:: 'ተይ' እና 'ተው' በማይባል አመል ብዙ ተሳስረን ነበር::

## ሊቅ ሆይ መጽሐፍህን አርም::

ቤቷ ስሄድ ከማንም ቀድማ 'ቀይ ወጥህ ቆይ ይሰራልህ' የምትለኝ የፍቅር አመልዋን እንዳውቅ እንዲገባኝ የምትሰራው ኪነት ነበር? ከመንገድ መንገድ ኮረኮንቹ ሲያስቸግራት ጭቃው ሲያበሳጫት ዕውነት ነበር ይሄስ? እስኪ ናና አሻግረኝ ስትለኝ? እጇን ይዛ የሚያልባት በእርግጥ በጎዳናው ወጣ ገባ አልቧት ነው? ወይስ ሕልማችን ትዝ ብሏት? አንዳንዴ ዞር ብዬ ሳያት ለምን ስታየኝ እይዛታለሁ? ቶሎስ ፊቷን ትሰብራለች? ለምን? ለምን ፊቷ ያኔውኑ የሐዘን ድባብ ያጠላበታል? ብርሃን እያሰቃያት ይመስለኝ ነበር:: ካልሆነስ? ወዳኝ ምናልባት በዕድሜና በሌላም መንገድ ስለማንመጣጠን፣ ከሥርአትና ከሕግ አምልጣ መምጫዋ ሕልሟ ብቻ ነበር? ማረጋገጥ ባልችልም ግን መሰለኝ:: እግዜር ፍቅርን ሲያመሳጥር እንዲህ ነው? እንዲህ እንዲከብደን አድርጎ ነው? የተወችኝስ ለማከዳ ቦታ ለመልቀቅ እንደሆነስ? ጤነኛ ፍቅር እንዲደርሰኝ ለምትነካዋ፣ ለምትጨበጠዋ ልትተወኝ? ይሄ ስራችንን አምላክ በሃጢያት ደረጃ መድቦ እንደማይቀጣን እገምታለሁ:: ቅጣት ካለው ለእኔ ብቻ ይስጠኝ:: የምር የእሷን ደምሮ ለእኔ ብቻ ይስጠኝ:: ይሄ ለዘላለም በፍቅረኞች የሚነገር የመዋደድ አትኮኝ የለሽ ነው::

# አትኮኝ የለሽ

ከሺህ ዘጠኝ መቶ ስድሳድስት ዓመተምሕረት በሁዋላ ብዙ ወጣቶች ከጥቂቶች በስተቀር ፖለቲካ ሽር ጉድ ውስጥ ገቡ:: በወቅቱ ስለ ፖለቲካ የማያስብ ፖለቲካ የማይናገር ወጣት ማግኘት ከባድ ነበር:: ከማውቃቸው አብሮ አደጎቼ እዚህ ነገር ውስጥ ያልገቡት ቸርነት፣ ዓላዛርና ግርማ ብቻ ነበሩ:: ግርማ ቆይቶ አባቱ መቶ አለቃ መክብብ በነጭ ሽብር ስለተገደሉበት፣ የአብዮት ካምፕ እተባለው ውስጥ ገባ (ይኼን መግባቱን ግርማ ያስታወቀው እኔ ሆቴል ስድስት ከፉብ ቢራ ጠጥቶ ሰክሮ፣ ብዙ ሰው ባልነበረበት አደባባይ ነው:: የተናገራቸውን የብልግና ቃላት ቀንሼ ይኼ ያለው ትዝ ይለኛል: 'ትፈልጊያለሽ አናርኪስትና ተገንጣይ ሁሉ አባቴን እንደደፉሽ እደፋሻለሁ:: ጆክ የለም:: አነጥፍሻለሁ:: አውቅሻለሁ ማን ማን እንደ ሆንሽ:: በሁዋላ 'ጨፍጫፊ' እንዳትይኝ:: እንደ ሊቫን ከሊፍ ሒሳብሽን እስጥሻለሁ:: ቪቫ መንጌ!':: ያድርገው አያድርገው የማውቀው ነገር የለም:: ይኼን በዚያን ዕለት በመናገሩ ሲነጋ ቅር ይበለው አይበለው አላውቅም) ወዳጁ ማሚ ኢሕአፓ ስለነበረች ተቀያይመው ተለያዩ:: (እነሱን ወጣቶች አብረው ያያቸው በአእምሮው የሚመጣው የበኩር ልጅነት ነው:: ረገ'ዥ'ሮሞች፣ ገላቸው በምኞት የሞላ፣ ሁልጊዜም የሚስቁ መልከመልካሞች ነበሩ:: የእነሱን መለያየት ያየ ሰው፣ በልቡ የሚያድረው ተስፋ መቁረጥ ነው) ያኔ ከዓላዛር ጋር ተቀምጠን የምናወራው ስለዚህ እንግዳ ክስተት(ይሄን ፖለቲካ የወለደውን አስተዳደጌ ያላስተማረኝን ቃል፡ በመጠቀሜ ራሴ፤ለራሴ ይቅርታ አደርጋለሁ) ነበር:: እንዴት ትናንትና 'ብስኩት ይከረሽም፣ ፓስቴ ይነጭ እና ቡና በወተት ሲልፍ የነበረው ወጣት በአጭር ጊዜ ለፖለቲካ ስራ፣ ያውም አደጋው ለበዛ አስፈላጊ ሆኖ የተገኘው? በተለያዩ ድርጅቶች ውስጥ በፖለቲካ የሚሳተፉ፣ ባላጋራ የሆኑት፣ ለባላጋራነት የሚፈላለጉት ወጣቶች እንደተለመደው ታዚና ሲመጡ ፀባያዬን ሳለውጥ፣ ሰው መርጬ ፊቴን ሳላጠቁር፣ ድሮ እንደማውቃቸው አጫውታቸዋለሁ፣ እቃለዳቸዋለሁ፣ እላፋቸዋለሁ::

በዚህ ጊዜ የተረዳሁት የሆቴሌ የገንዘብ ገቢ አስገራሚ በሆነ መልክ ማሽቆልቆል ነበር:: በቁጥር ተንጋግቶ መግባት ብቻ ሳይሆን በዚያን ጊዜ ብዙው ወጣት ራሱን ለፖለቲካ አሳልፎ በመስጠቱ በሌላ በሌላ ጉዳይ መነኩሴ ሆኖ ነበር:: ፀጉሩን የሚላጭ፣ ቀዳዳ የሚለብስ፣ ጥፍሩን የማይቆረጥ፣ ቡና ቤት ገብቶ መጠጣት ከዓላማው የሚያርቀው የሚመስለው በዛ:: ዓላዛር ይላል «ወላ ሌኒን ቅልጥ ያለ ክራቫት ያደርግ የለ»

የባሰ ተደመም ሲለኝ ነው መሰለኝ፣ አንድ የግርማቸውን አባት የገደለ ሰው 'ሆቴልህ አድሮ ነበርና፣ አንተና እዛ ተሰብስባችሁ ታወሩ የነበራችሁ ሽርጉዱ ውስጥ ሳትኖሩበት አትቀሩም' ብሎ ደርግ እኔና ዓላዛርን ከሳምንት በላይ አሰረን:: የታሰርኩ ሰሞን ጀርባዬ ላይ የተገረፍኩትና በዚያ ሰበብ የወጣብኝ ነጭ የጠባሳ ሪጋ ዛሬ ድረስ አለ::

ወጣቱ በአጭር ጊዜ ፖለቲካ ባሕር ውስጥ የጠለቀው ሲመስለኝ እንዲህ ነው:

አንድ ፍልስፍና ተቀባይነቱ አጠራጣሪ ሲሆን፣ ልዩ የሚያስመስለው አቀራረብ ወይም የሚሸፍነው ኪነት ይሰራለታል:: ያማረ መጎናፀፊያ ይሰፋለታል:: እንዲያብረቀረቅ ዕውነት ሳይመስል እንዲመስል የሚያብለጨልጩ ነገሮች ይሰቀሉበታል:: ፍልስፍና እንደ ጀሮ ሉቲ ይንጠለጠልበታል:: ሁሉ ነገር ካለቀ በሁዋላ (ነጭና ቀይ የሚሉት ሽብር) ታዲያ አብረቅራቂው ነገር ተገፈፈ፣ ከእሱ ስር የተደበቀው ዕውነት ያልሆነ ዕውነት-አስተኔ መሆኑ ተደረሰበት::

በፍጥነት ተሰባስቦ በፍጥነት ፖለቲከኛ የሆነው ወጣት በአንድ ወቅት በመጣበት ፍጥነት በፖለቲካ ሲበላና ከፖለቲካ ሲሸሽ፣ የተረፈው መሄጃ የሌለው፣ 'የመደብ ጀርባው' እየታየ ከእስር የተለቀቀ፣ በድፍረቱ የኮራ ግን ቀጣይ ድፍረቱን የፈራ፣ አስገራሚ ከሆነ ስነስርዓት ወጥቶ መጠጣትና መስከር የጀመረ ወጣት ታዚና ብቅ አለ:: ካህኑ ሳዶቅ ለወጣቱ ሚኒሊክ ኢየሩሳሌም ሄዶ እያለ የመከረው ምክር ትዝ አለኝ:: 'በአንድ መንገድ ወደ እነሱ ትሄዳለህ፣ በሰባት መንገድም ከእነሱ ትሸሻለህ'[147]:: በዛን ጊዜ ያየሁትን የሁለት አመታት ሩጫና ወጣ ገባ ሰብስቦ የሚገልፅ አንድ የመሪጌታ ዘጠልሰም ቅኔ ትዝ ይለኛል። ይሄ ቅኔ እንዲሁ ይሄዳል:

***ኢተመኑ ሕዝብ ዘወለድክሙ በተድላ***

***እስመ ለማርያም ድንግል ዘወለደቶ ቀተላ***[148]

---

[147] ክብረ ነገሥት ምዕራፍ 40

[148] ወገኖች(ሕዝብ) በደስታ የወለዳችሁትን አትመኑ ድንግል ማርያምን የወለደችው ገሎአታልና

ምንድን ነበር ያለኝ ያኔ ሁሉ ነገር ልቡን የመዘመዘውና ያዘነ አንዱ የሰፈሬ ደራሲና ገጣሚ (ስሙን መንገር አስፈላጊ አይደለም እንጂ፣ ምን ይታወቃል ቢነጀስስ?) ወዳጆቹን ከዚህም ከዚያም እያስታወሰ ባህርያቸውን ካብራራ በሁዋላ:

***የዋህነት እንደ ጥይት***

***ውዥንብር ኮልት ውስጥ***

***ተመቻችታ የተቀመጠችበት፣***

***ባዶ አየር ላይ ታልማ***

***ተተኩሳ የነደደችበት***

እኔ እንኩዋን ይሄ የየዋህነቷን ነገር ሳሳ እንዲያደርጋት ጠይቄው ነበር:: በተረት ሳንታተልኩት:: ተንኮለኛ ገደል በሬ ያሳልፋል ዝንጀሮ ይጠልፋል፣ ጅል ያመጣው ነገር ለሁሉ ይተርፋል:: ሊመታኝ ምንም አልቀረው:: የዋህ--ነገር ያልገባው ጅል፣ ጅል--ነገር የገባው የዋህ ነው ብዬ ላመልጥ ነበር:: ሰውዬው 'ቅኔ ልቀኝ' እያለ ቢውተረተርም ስረ መሠረቱ የስድሳ ስድስት ጠማማ ነውና: 'እንዲህ ካልክ ሆቴልህ ዝር አልልም' አለኝ:: ችሎታው መዛት ብቻ ሳይሆን እሱን የመሰሉ ከብቶችን ማሳደም ነውና፣ ኑፋቄ የለመደ አፌ ላይ መልካም የዝምታ መጋረጃ ጣል አደረኩበት:: እሱና የመሳሰሉት ከአፋቸው እውነት ባትወጣም፣ በተገኘው መልክ ማስፈራራት ግን ይችላሉ:: ምላሴን ካሰርኩለት በኋላና የሚጠላውን እንደጠላሁ ሲረዳ፣ ለእሱ ሰውዬ እንደ እኔ ጥሩ ሰው በምድር ቢፈለግ የማይገኝ አይነት ሆንኩ:: ጥሩነቴ ከየትኛው አቅጣጫ እንደተገመገመ አልገባኝም: ከኑፋቄዬ? ከነጋዴነቴ? ኑፋቄዬን ለሌሎች ሳልነግርና ወደ ሳላሰራጭ ወደ ሆዴ ስለዋጥኩት? ወዘተ......

ወደ ዋናው ጉዳዬ ልጠምዘዝ:: በወጣቶች ደጋግሞ መምጣት የሆቴሌ አልጋዎች ሽቦ መርገብ ጀመረ:: የበሮቹ ማጠፊያ ምስማር ላላ:: ተኩሰውም ያገኙ፣ ተኩሰውም የሳቱ፣ ተተኩሶባቸው ያመለጡ ግን የተበተኑ ጎረምሶችና ኮረዶች ብቅ አሉና ሆቴሌን በ 'እንዝናና' ናጧት:: 'የሚበላ ምግብ የለም? የሚጠጣ ቢራ የለም?' የሚል ወጣት በዛ:: አልኮል መጠጣት ያሳፍረው የነበረው ጉብል በአጭር ጊዜ ነፍሱ አርጅቶ ጂን መምጠጥ ጀመረ:: መገረሜን በሆዴ ይዤ ሽቀላዬን ሞቅ አደረኩ:: ጠዋት ላይ ከሆቴሌ ፊት ለፊት፣ ከመንገዱ ወዲህ ሁለት ሶስት ሰዎች ማስታወካቸውን የሚያሳዩ ምልክቶች ብቅ ብቅ ማለታቸው ደንብ ሆነ:: ፀጥታ ሰፍኖበት የነበረው ሰፈሬ ንጭንጭ ያለ ጩኸት ወረረው:: ሰዎች በአጠቃላይ 'አገር ተረጋጋ ንግድ ደህና ሆነ' ሲሉ እኔ ይሄን ጥያቄ ጠይቄ ግን ቀጠል አደረግሁበት:: ይሄ የወጣቱ የሽሽት ጉዞ ('ፖለቲካና ኮሬንቲን ከሩቅ' በምትለው ቀልደኛ በመሰለች መፈክር ታጅቦ) በትክክል

የት እንደሚያርፍ መገንዘብ ነበረብኝ:: ይሄ ሲሆን ግን ወደ ሁዋላ መለስ ብዬ በእነዚያ በሶስት ጣቶች እንኳን በማይቆጠሩ ዓመታት የሆቴሎች መዳከም ማንን አጠፋ? ብዬ መጠየቅ ነበረብኝ:: ማንን አጠፋ?

ከአብዮት በፊት በአዲስአባ አራዶች ተወዳጅ የሆኑት ሬስቶራንቶች የፈረንጅ ምግብ የሚሸጥባቸው ነበሩ:: የአብዮት ማዕበል አገሪቷን ሲንጥ ከሁሉም አቅጣጫ በሚመጡ ፖለቲከኞች ተንቀውና ፀረ-ኢምፔሪያሊስት በተባለው አቋዋም ተደናግጠው ፍርሃት አስበርግጎአቸው ጠፉ:: በ71 ዓም አካባቢ ቀውሱ መብረድ ሲጀምር፣ ይሄን የውጭ አገር የምግብ ስፍራ በባሕል ምግብ መሙላት የቀረው አማራጭ ነበር:: ይሄን የለውጥ ጎዳና ብዙዎች ተከትለዋል፣ ግን እንደ እኔ ሰፉና ገፉ አላደረጉትም:: የተከፈተውን ቦታ በተመሳሳይ ይዘት ሞሉት እንጂ የተለየ ጣዕም ይሁን ቄንጥ አልወለዱም:: ከላይ እንደጠቀስኩት የዝልዘል ጥብሴ ነገር በራዕይ ፈሰሰልኝና ወደእዛ በድፍረት አመራሁ:: ግን ይሄ ፈጠራዬ ተወዳጅ እንዲሆን መደረግ የሚገባቸው ውስብስብ ነገሮች ነበሩ:: ከነዚህ መሰራት ከሚገባቸው ነገሮች አንደኛውና መሰረታዊው ፕሮፓጋንዳ ነበረ:: ዝልዝል ጥብስና ፕሮፓጋንዳ ወይም ቀለል ሳድርገውና ጥብስና ማስታወቂያን ለመሆኑ ምን አገናኛቸው? ጥብስ ለመሆኑ ኮካኮላ ነው? ፋንታ ነው? ወይስ ሳባ ጠጅ? የሚል አይጠፋም::

የሰው ልጆች ፍላጎት በየጊዜው ይለዋወጣል፣ ይኼ እውነት ልዩ ምስክር መጥራት የሚያሻው አይደለም:: የፍላጎት መለዋወጥ ብቻ ሳይሆን ያ ፍላጎቱ የሚተከልባቸው ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ይለዋወጣሉ:: እነዚህን ሳይነጣጠሉ በድምር የመረዳት ኪነቱ ነው 'መረዳት' የሚሆነው:: ምግብ እንደማንኛውም ሰባዊ ድርጊት ባሕል ነው:: በአዲስነቱ እንደ ማንኛውም ዕውቀትና ባሕል መጀመሪያ መፈልሰፍ፣ ቀጥሎ በብዙዎች መኖሩ መታወቅ፣ ቀጥሎ ልማድ መሆን መቻል አለበት:: ይኼ ደሞ እንደ ሁኔታው በአጭር ጊዜ ወይ በረዥም ጊዜ ሊሆን የሚችል ነው:: ሰብአዊ ባሕርይ ስለሆነ የዕድገት መንገዱን ከሌሎች ሰብአዊ ድርጊቶች በመቅዳት መምራትና መቆጣጠር ይቻላል:: ቀደም ብዬ ያነሳሁት የፖለቲካው ነገር የሚመጣው እዚህ ላይ ነው::

ወጣቶች ፖለቲካ ውስጥ ተንቃግተው የገቡበት ሁኔታ ባብዛኛው በእኔና በሳል በሆኑ ሰዎች ግምት (ወይም በገባቸው ሰዎች ግምት) በአገራችን የሰፈነው ጭቆና አስከፊ ሆኖ መላወሻና መንቀሳቀሻ ጠፍቶአቸው ሳይሆን በረቀቀ ፕሮፓጋንዳ ግፊት መሆኑ ነው:: ፕሮፓጋንዳ አዲስ ፍጡር አይደለም፣ ድሮም ነበረ:: ዛሬ የፈረሰውን የሰለሞናውያን ስርወ መንግስት እዚህ ያደረሰው የአንድ ሰው ፕሮፓጋንዳ እንደ ሆነ ያውቃሉ? ታምሪን የተባለ ነጋዴ ለሳባ ስለ ሰለሞን ጥበብ ነጋ ጠባ ይነግራታል፣ በዚህ ምክንያት ሰለሞንን በአይኗ ሳታየው ወደደችው:: ክብረ ነገስት 'ከፍቅሯም ብዛት የተነሳ ታለቅስ ነበር፣

ለመንግስቱም(ለሰለሞን መንግስት) ልትገባ ፈልጋ ትሻ ነበር' ይላል:: ይኸማ ትሁን አትሁን ወይም የዞረባት ቁሊታም፣ እንርሳውና፣ መጀመሪያውኑ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዳ አርግዛ እንድትመጣ ቀስቃሽ ምክንያት የሆናት የነጋዴው የታምራን ጥዝጠዛ ነው:: ጥዝጠዛ ቀላል ጉዳይ አይደለም:: ይሄን ክብረነገስት ውስጥ ሳነብ እስቅና እገረም ነበር:: አንዳንዴ ነገር ነገር ነገር ሲለኝ ሰለሞን ብዙ ቁባትና ሚስት ሰላለው ሳባ በእነሱ ቀንታ እንደ ማንኛዋም ርካሽ ሴት ሻሞ ልትገባ ያሰበች ይመስለኛል እላለሁ:: የራጉኤሉ ቄስ ጎርጎርዮስ በዚህ አተረጓጎሜ ሰድቦኛል:: 'እርጉም' ብሎ::

ይሄ ከላይ ያነሳሁት ፕሮፓጋንዳ የሚደረግባቸውን አንዳንድ መሰረታዊ መንገዶች በምሳሌ ላስረዳ ይፈቀድልኝ:: ፖሊቲካ ከወዳጆቼ ቢለያየኝም ከርቀት ሆኜ ግን እጠይቃለሁ:: 'ለምን?' እላለሁ:: 'እንዴት ሊሆን ቻለ?' እላለሁ:: እንግሊዘኛ የማይችል በግዕዝ የሚጠነቁል ደብተራ የመጠየቅ መብት የለውም ማን አለ? ለምሳሌ በቀለም ትምህርቷ ጎበዝ የነበረችው 'ሳይንቲስት ትሆናለች' ብሎ ተማሪና አስተማሪ ተስፋ የጣለባት ተባረኪ ፖለቲከኛ መሆን ነበረባት? ቢያንስ ቢያንስ የዳሌዋን ስፋት ያየ፣ የቁመቷን መለሎነት ያየ፣ የጡቶቿን ዳብ ያየ፣ የእግሮቿን ጠብደልነት ያየ፣ ጠንካራ ልጆች የምትወልድ ሚስት ትሆን ነበር ብሎ መገመት ይችላል:: ታዲያ ከጎበዝ ተማሪነቷና ሚስት ሆና ልትወልድለት ከሚገባት ዓላዛር እርቃ ፖለቲካ ውስጥ መሰንቀር ይገባት ነበር? እኔ እንደምገምተው አይመስለኝም:: ግን ጥሩ የፕሮፓጋንዳ መሳሪያ ትሆናለች:: እንዴት?

አዲስ ኪዳንን ለመረዳት ብሉይን ማጥናት እንደሚያስፈልግ፣ ማርክሲስት ለመሆን ከእሱ ቀድሞ የነበረው ዕውቀት መረዳት የሚያስፈልግ ይመስለኛል:: በዚህ ፈርጅ ወጣቶች ከማርክስና ሌኒን በፊት የነበሩትን ፈላስፎች በቅርብ የማጥናት የመመርመርና የማወቅ ግዴታ የነበረባቸው ይመስለኛል:: እንግዲህ በቅርብ ከማውቃቸው እንደ ተባረኪ ካሉ ወጣቶች ይኼ ይኼን ያውቁ ነበር? ያውቃሉ ከተባሉ ገና ልጅ ነበሩና መቼ አንብበውት፣ አጥንተውትና ተረድተውት ነው? ይሄን ጥያቄ ብጠይቅ ስህተት ነኝ? ታዲያ ወጣት ያወቀ መስሎት ፖለቲካ ውስጥ ገብቶ እንዲማስንና እንዲነድ ለማድረግ አንድ ነገር መስራት አለበት:: የመጀመሪያው ብልጠት እንደ ተባረኪ ያሉ ብሩህ ወጣቶችን አስቀድሞ ድርጅት ውስጥ በማስገባት 'ጥራት' 'ምርጥ' ወጣቶች ያሉበት ድርጅት ነው አሰኝቶ ሁለት ስሜቶች (ተፃራሪና ግን ደሞ ተደጋጋፊ) በወጣቱ ልቦና መቀስቀስ ነው:: ስሜቶቹ እነዚህ ናቸው፡

*አንደኛ*፡ እንደ ተባረኪ ዓይነቶች ትዕቢት እንዲገባቸውና ተፈላጊ የሆኑ፣ ወይም የድርጅታቸው ነፍስ እንደሆኑ ሁሉ አድርጎ ማቅረብ

*ሁለተኛ*፡ ሌሎቹ 'ደደብ' የሆኑ ወጣቶች ከ'ብሩሃኑ' ጋር ከ'ቀልጣፎቹ' ጋር አንድ ድርጅት ውስጥ በመጠለላቸው ብሩህ ባይሆኑም እንደሆኑ እንዲሰማቸው የማድረግ ነው።

በዚህ ሁለቱም አይነቶች አንዱ በትዕቢት፣ ሌላው በመምሰል ይተሳሰራሉ። ስልቱ ሁለቱንም ተገናኝተው በማያወሩበት መልክ ማሞካሸት፣ የፖሊቲካ ስልጣንን ብቻ ነጋ ጠባ የውይይቶች ሁሉ ቁንጮ ማድረግና ፊጣንና አደገኛ ድርጊት ውስጥ ከቶ የማሰላሰያና የመቆዘሚያ ጊዜ ማሳጣት ነው። ግን ይሄ ዓይነት አሰራር እንዲቸግኝ፣ እንዲያብብና እንዲያፈራ ሕብረተሰባችን ውስጥ የሚተከልበት አፈር ያስፈልገዋል። ስለ ተባረኪ ሳነሳ ምናልባት ሁሉን ነገር የእሷ ወይም እሷን የመሰሉ ልጆች ሃላፊነት ለማድረግና ራሴንም ሆነ በግርግሩ ያልነበረውን ሌላውን ከሃላፊነት ነፃ ለማውጣት አይደለም። የተባረኪ አይነት ወጣቶች ከሰማይ አልወረዱም። ሁላችን የፈጠርናቸው የሚያደርጉትንም አይተን ትክክለኛ መንገዱን ያልጠቆምናቸው ናቸው። ባይሰሙን እንዲሰሙን አላሰለጥናቸውም። አብረን ሆሆ ስንል፣ አንገታችንን ደፍተን ያየነውን እንዳላየን አልፈን፣ እሷንና እሷን የመሰሉትን ማማት ጥሩ የአተቻቸት ዘይቤ አይደለም። የእኛን ሃጢያት የተሸከሙ ናቸው። የእኛን ቂልነት፣ የእኛን ድንቁርናና አለመረዳት በለጋ ጀርባቸው ያዘሉ ናቸው። እሷንና እነሱን የመሳሰሉትን የምጠቅሰው ለናሙና እንጂ ሐጢያታችንን የሚሸከሙ ኤስታሊ[149] ወይም ኖኖች ፍለጋ አይደለም። ኪዳነ ምሕረት ደጀሰላም ካሉት ከማውቃቸው ቀሳውስት የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ ያልገባን ጥቂት ነበርን። የዕድል ጉዳይ ሆኖ ነው እንጂ ይሄ ወላፍ/መንጠቆ በማንኛችንም አፍ ሊገባ የሚችል ነበር።

'በመጀመሪያ ቃል ነበር' የሚለው ዓረፍተ ነገር በሃይማኖት የሰብከት ወይም በዘመኑ አለማዊ አባባል የፕሮፓጋንዳ መጀመሪያ ነው። (ከዲቃላው ሚኒሊክ መወለድና ሰለሞናዊ በርወ መንግስት ከመፈጠሩ በፊት የታምሪን ቃል ነበር እንድንል) የኪነት መዝሙር የሚባለው ሁሉ በድብቅ ሆነ በማልዕ የሚዘመረው ዓለማዊ ቅዳሴ ነው። እኔ ደጀሰላም ሄጄ የአምላክን ቃል በዜማ ሳጅብ የእሱ የፈጣሪዬ ካድሬ መሆኔ ነው እኮ። ታዲያ ከነበረው ብዙ ኗኗቂናል?

ቸርነት ከሰውኛዎመግባባት ትልቅ ችሎታ አለው። ፍፁም እንግዳ ከሆነ ሰው ጋር በአስር ደቂቃ አብሮ አደግ መምሰል ይችላል። በወጣቶች የተወደደ ነው። የታሰሩ የሰፈር ልጆችን በየታሰሩበት ሄዶ ሳይደክም ሳይፈራ ደህንነታቸውን ይጠይቃል። ለስቃያቸው ይሰቃያል፣ በስቃያቸውም ይስቃል። በተረቡ በሳቅ የማያንፈቀፍቀው የለም። ኩሸት ተወልዶ ያደገው፣ ደግነትም፣ ቁም ነገረኛነትም፣ እንደ እሱ አባባል

---

[149] ኖን (Scapegoat)

ተጠራጣሪነትም ቸርነት ልብ ውስጥ ነው። በፖለቲካ ምክንያት ትተውት ከሄዱ በሁዋላ ተርፈው የተመለሱት ወጣቶች ታዚና ሲመጡ 'ቸሩ የታለች?' እያሉ ነበር። (በዛን ጊዜ ዓላዛር ከዚህ አገር ብጥብጥ ለመራቅ ምስራቅ ጀርመን ለትምህርት ሄዶ ነበር።) ይሄን የቸርነት የተግባቢነት ጥበብ 'ተባረኪ ብሩህ ናት' ብለው ሌላ ወጣት መሰብሰቢያ እንዳደረጉት ፖለቲከኞች እኔም መሰብሰቢያ አደረግሁት። ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ የታዘብኩት ሁኔታ ብቅ አለ። ሌላው ሌላው ቢቀር 'ስለ ዓለም አቀፍ ወዛደርነት' ሲያወራ የነበረው ወጣት ዜጋ ሁሉ አለም አቀፋዊ መሆኑን ትቶ ለስለስ ያለ ብሔረተኛነት ማሳየት ጀመረ። ግን ይሄ የብሄረተኛነት ፀባይ የተከሰተው (ትዝብቴ የተሳሳተ ሊሆን ይችላል) በአብዛኛው ሆድን ወይም የአበላል ባሕልን በተመለከተ ነበር። ታዲያ ይሄ ሁሉ ተጠራቅሞ ንግዴን የተሳካ አያደርገውም? ስለ አገሩ ግድ የማይሰጠው እንደውም ሊያጠፋት የሚያሴር የአገር ባሕል ቀሚስና ነጠላ ይሸጥ የለ? እንደዛ። አባቴ ስለ 'አትኮኝ የለሽ' ሲያወራኝ ፍልስፍናው በጥልቅ ገብቶኝ ነበር። 'አትኮኝ የለሽ' ማለት በመሠረቱ ራስን ከመልዕክቱ መነሻ መነጠል ማለት ነው። የእኔ አትኮኝ የለሽ በወዳጅነትና በትህትና የማስተናግዳቸው ወጣቶች ነበሩ። ልክ የአገራችን ፖለቲከኞች የባዕድ ***አትኮኝ የለሽ*** እንደሆኑት......

**የኮኩን ነገር አይርሱ።**

## ጥጡን ነድፌሽ ነድፌሽ በአልጋ ቆልለሻል
## ይሄን አመል ምለሽ ብትተይ ይሻልሻል

ቀለበቴን ፀሐይ ያመጣችልኝ ዕለት ሆቴሌ ስራ እየሰራሁ ታምራቱ አስደምሞኝ እንደ እብድ ከራሴ ጋር እያወራሁ ለስራ ወዲያ ወዲህ ስል አንዲት ልጅ ወይም ሰው ፊቴ ቆሞ ወይም ቆማ አየሁ::

«ምን ልታዘዝ?» አልኩ:: ልጅቷ በሚያምር ድምፅ:

«ጋሞ ክፍል አንድ እሳት በደንብ የገባው ጥብስ ከአንድ ፊልት ጋር:: ያለ ሽንኩርት ይጠበስ» አለች::

«ያለሽንኩርት?» ብዬ ዞር ስል ማከዳ መሆንዋን አየሁ::

ወደ ምትቀመጥበት መሄድ ጀምራለች:: ፊቴን ሳታየኝ ሳልበረግግ እንደልቤ ከሁዋላዋ አየሁዋት:: ከባቷ አልፎ የሚወርድ ካኪ የመሰለ ረጋ ሰራሽ ቀሚስ ለብሳለች:: ቀጥ ያለ አቋቋሟ ዘልዛላ ጨርቅ ውስጥ ጠፍቷል:: ነጭ ሻሽ ጠምጥማ ፀጉሯ አይታይም:: የአካሄድዋ እንቁልልጩ የለም:: ከእሷ ጋር በቀላሉ መናገር መቻሌ አስገረመኝ:: ድፍረቴ ከመጥፋቱ በፊት ለሌላ ሰው የተዘጋጀ ጥብስ አለችበት ክፍል ይዤ ገባሁ:: ግድግዳ ጥግ የሚያስብ መስላ ተቀምጣለች:: በሁለቱም ክርኖቿ ጠረጴዛ ተደግፋለች::

ጥብሱንና ጠበሉን ወስጄ ፊት ለፊቷ ሳስቀምጥላት:

«ውይ በምኔው ደረሰ?» አለች

ምን ልበል?

«ይሄን ነገር ስወድ» አለች ቀጥላ:: አንገቷን እስኪሰበር እየሰበቀች፣ ፊቷን በትንሹ ዘንበል አድርጋ በዐይኗ ቂጥ እያየችኝ::

«ላንቺ በተለይ የተሰራ ነው» አልኩና በፍርሃት ፈርጥጬ ወጣሁ::

ቢሮዬ ገብቼ የተናገርኩት ነገር ምን ያህል ፍላጎቴን እንደሚጠቁም ሳሰላስል፣ የማይረባ የትም የማይደርስ ነገር እንደተናገርኩና፣ ልፋቴ ሁሉ እንደከሰረ ገባኝ:: ውስጤ ከሞላው ወሬና ዓረፍተነገር ምንድነው በባዶ ሜዳ አንድ ሃረግ ተፍቼ የምሸሸው?

ደግሜ ልበለውና ምድር ላይ ያሉ የሃይማኖት ተቋዋሞች ሁሉ ሰመረ አልሰመረ የእግዜር ማስታወቂያና የስለላ ድርጅቶች ናቸው:: የሰዎች መናዘዝና ንስሐ መግባት ቀደም ሲል በቅርብ አገሪቷ ውስጥ ሲደረግ የነበረውን ማጋለጥና ንቃት አይመስልም? ነገሩን ነው የምለው:: ከላይ እስከታች ያለው የፖለቲካ ድርጅቶች አሰራር መለኮትና ነገረ-መለኮት የተዋቀሩበትን ስልት የያዘ አይመስልም? ይኼን ማመሳሰል ሳደርግ ግን ቅንጣት ያህል ሐጢያተኛነት አይሰማኝም:: ለምን? የጨነቀኝና የጠበበኝ አፍቃሪ መሆኔን እግዜር ራሱ ያውቃል:: በዕውነተኛ ስሜት የወደድኳትን ልጅ ድፍረት ሰጥቶ እንዳናግራት ያልገፋፋኝንና ያላበረታታኝን ፀሎቴን በምድራዊ ችሎታዬ ብተካው ስህተት ይኖረዋል? ሐብቴን ያገኘሁትስ በእሱ በአንደዬው ፈቃድ አይደል? የንዕዕር ጠቃሚነቱም ይኼ ነው:: ስለዚህ ከሩቅ ሆኜ ካድሬዬን አሳላፊ ወደ እኳ ልኬ በገንዘቤ የወደደ ሰው ማድረግ የሚገባውን ባደርግ አሳፋሪ ነው? እግዜር ሐብቴን የሰጠኝ እኮ ደስ እንዲለኝና ደስ እንዳሰኝበት ፈልጎ ነው:: በቀረኝ አማራጭ ልቀርባት ፈለግሁና አሳላፊ ጠርቼ ገንዘብ እንዳይቀበላት ሂሳብ የቤቱ እንደሆነ እንዲነግራት አዘዝኩ::

የመጋበዜ ተዕዕኖ ከርሞ ይመጣል ብዬ አስቤ ሌላ ሌላ ነገር ሳሰላስል፣ ከግማሽ ሰዓት በሁዋላ የቢሮዬ በር ተንኳኳና ማክዳ ከአናቷ ላይ ነጠላዋን አውርዳ ሰላምታ ሰጠችኝና ቢሮዬ ገባች::

«ጋሼ ዕዝራ በጣም አመሰግናለሁ» አለች

ከጠረጴዛ ስር እግሮቼ ተንቀጠቀጡ:: አፌ ተሳሰረ:: ምን ልናገር?

«የሚያምር ቢሮ አለህ» አለች

ሳቅ ሳቅ አልኩ::

*ምን ታደርጊ ሌላ ሌላ ጎበዝ ጋ እየሄድሽ* አልኩ---በልቤ:: *የማልረባ*::

«ደስ የሚል ቴፕ አለህ»

«ሰምቼበት አላውቅም፣ የሆቴሉን ነው የምሰማው:: ቤ ቤ ተሰብ ደህና ነው?» አልኩ ሳታየኝ

«ደህና ናቸው» አለችኝ

«ተተተቀመጪ እቴቁሚ»

ከእኔ ራቅ ያለው ወንበር ላይ ተቀመጠች::

«ምን ልታዘዝ?» አልኳት አምራ ከአፌ የወጣች ለስራዬ የምጠቀምባት አረፍተነገር ነበረች::

«ምንም»

«ፊልቴር ትጨምሪያለሽ?»

«አይ በቃኝ ያንንም አልጠጣሁት»

«ምነው? አንቺን ሰማሁ 'አልጨረስኩትም' የሚል:: ጭማቂ ላሰራልሽ»

«ግድ የለም ውሐ ካገኘሁ ይበቃኛል»

«ግድ የለም ጭማቂ»

ጭማቂው እስኪሰራ መቆየቷ አይቀርምና ምን ላወራት ነው? እንደ እኔ አይነት ቦቅቧቃ የሚያቆይ ነገር መጋበዝ የለበትም:: እነዛ ዓይኖች ፊት ለፊት ማን ችሎ ይቆማል? ይቀመጣልስ? እነዛ ከናፈርት ስር ማን ችሎ ሰይጣን የሚነዳው ገላን ሊቆጣጠር ይችላል? ቃጭል ደወልኩና አሳላፊው ሲመጣ ብርቱካን ጭማቂ አዘዘች:: እሱ እንደወጣ ለጥቂት ደቂቃዎች ዝም ብዬ ሳፈጥባት ቆየሁ:: ከተቀመጠችበት ተነስታ ቢሮዬ ግድግዳ ላይ የተሰቀሉትን ፎቶዎችና ስዕሎች ማየት ጀመረች:: ብስክሌት ላይ ተንፈራጥጬ የተነሳሁት የድሮ ፎቶ ላይ ዓይኖቿ አተኮሩና (በጥቁር ነጭ 'በዛብህ' የሚባል ጋዜጠኛ ያነሳኝ ስድስተኛ ወጥቼ ስቄ የተነሳሁት ፎቶ አለ:: ጥርሴ ለብቻው ተነሳ ብል ይሻላል)፣ ለወሬ መቀስቀሻ ሳይሆን አይቀርም:

«ብስክሌት ተወዳድረህ ታውቃለህ?» አለች ወደ ወንበሯ ለመቀመጥ እየተመለሰች::

«ሁለት ጊዜ»

«አሸነፍክ?»

«ተሸነፍኩ:: ግን ሁለቱንም ጊዜ ስድስተኛ ወጣሁ»

ትኩረቷን ከዚህ ለማሸሽ ሌላ ፎቶ ላሳያት አልኩና ከተቀመጥኩበት ተነሳሁ:: ከመሃል ለምን መድፈር እንደቻልኩ ገባኝ:: ስለ እሷ ማሰብ የለብኝም:: የምፈራት ሳስባት ነው:: ከጠረጴዛዬ የታች መሳቢያ አንድ ክላሴር አወጣሁና እሱን ገላልጬ ንግስት ጣይቱ ብስክሌት ላይ ተቀምጠው እየሳቁ የተነሱትን ፎቶግራፍ ሰጠሁዋት:: ተቀበለችና አየችው::

«ማን ናት?» አለች ፊቷ ላይ መገረም እየተሣፈ

የገረማት አንዲት ሹርባ የተሰሩ ሴት በረዥም ሱሪ ላይ ቀሚስ ደርበው ብስክሌት ሲጋልቡ በማየቷ ነው::

«እትጌ ጣይቱ...» ፊቷ ላይ አሁንም መገረም አለ::

«ጣይቱ የአፄ ሚኒሊክ ሚስት ነበሩ» አልኳት ቀጠልኩና::

«ንጉሡ? እኔ ደሞ የሆነች የባላገር ሴት ምናምን መሰላኛለች»

«አየሽ የመጀመሪያዋ ብስክሌት ጋላቢ ሴት ነበሩ»

«ንግስት አይመስሉም:: ምነው ደህና ልብስ ጠፋ ለንግስት የሚሆን?»

«ይሄ በዚያን ጊዜ ደህና ልብስ ነበር»

ፎቶውን በዝምታ ስታይ ቆየችና መለሰችልኝ:: ጭማቂው መጣላት:: ስለምን ስለማን ላውራ እያልኩ ማሰብ ጀመርኩ:: ዝምታው በበረታ ቁጥር፣ ከአንጎሌ ጨለማ ያ ያኔ ያየሁት ጭንዋ እየተከሰተ ረብሸኝ:: ሳታየኝ አያታለሁ:: ስታየኝ አላያትም:: አንድ አፍታ ውስጥ ጭማቂውን በቀስታ መጠጥ መጠጥ አድርጋ በትላልቅ 'ማከዳማ ዓይኖቿ' አየት አደረገችኝ:: ፊኛዬ ሊከዳኝ ሲያቆበቁብ ይታወቀኛል:

«ያ ጓደኛህ ማነው ይፅፍልሃል?» አለችኝ

«ማን?»

«ስሙ ማን ነበር?......የአቶ ብርሃን ልጅ»

«ዓላዛር......ብዙ አይፅፍም:: ታውቂዋለሽ እንዴ?»

«ስለታዚና ሲወራ ስለአንተ ይወራል፤ ከዛ ስለ እሱ ከዛ ደሞ ስለተባረኪ. ሂሂ»

«ምን ይወራል?»

«ምን ልበልህ በቃ ዝምብሎ ወሬ:: ደሞ ሲሄድ አይቼዋለሁ:: የሆነ ሌሊት ሻንጣ ምናምን ሲጭኑ አባቱ መኪና ላይ:: አንተ ነበርክ፣ ቆማችሁ ተቃቅፋችሁ ስታወሩ ነበር:: ከዛ ወደ ውጭ አገር ለትምህርት እንደሄደ ዋሕድ ሲያወራ ሰማሁ»

«አይተሻል እ? በጣም ወዳጄ ነበር:: ከልጅነት ጀምሮ:: ትንሽ ታላቁ ብሆንም:: ኩሽት ይወድ ነበር:: አንደኛ ግን እኔ ነበርኩ:: ሃሃሃ:: ይገርምሻል አንዴ ምን አደረገ መሰለሽ እዚህ እነ ተባረኪ ቤት አጠገብ......»

ስለ ዓላዛርና ስለሌሎች የሰፈር ልጆች፣ እሷ ሞሳ ሳለች ስለነበረው ጊዜ፣ ብዙ ወሬ አወራሁዋት......ጭማቂውን ጨርሳ ተሰናብታኝ ስትወጣ፣ መሸኘትም አፍሬ ወንበሬ ላይ እንደተተከልኩ ቆየሁ:: ሁሉን ያሳለፍ ኩትን ጠቅልዬ አሰብኩና በትክክል ባልተረዳሁት ምክንያት እተቀመ ጥኩበት እንደ ዳንስ የመሰለ ንቅናቄ አስነካሁ......

ግን ከዚህ አጋጣሚ በሁዋላ የተፈጠረው ሽርክና ከመረሳቱ በፊት እሷን መጋበዝ አልነበረብኝም? ማሊት 'እስኪ ብቅ በይና ዝልዝል ጥብስ ሞክሪ ስድስት እግር ያለው ልዩ በሬ አምጥቻለሁ' የመሰለ ማለት? ምን እንደሆነች አላውቅም እሷም ሆቴሌ ድሮ እንደምታደርገው መመላለስ አቆመች::

አንድ ቀን በማንኛችንም ሳይታቀድ (ሲቀናኝ ልበል) ከስድስት ኪሎ ዩንቨርሲቲ ከፍ ብሎ መንገድ ላይ ወደ ታች ወደ አደባባዩ ስትሄድ አገኘሁዋት:: አልዘነጠችም:: 'ሊፍት ልስጥሽ' ብላት 'አልሳፈርም' የምትለኝ መስሎኝ ፈራሁ:: ሳቆምላትና ስጋብዛት ሳታንገራግር እየሳቀች ገባች:

«የት እየሄድክ ነበር?» አለችና አተኩራ አየችኝ::

«ገበያ» አልኳት በጥርጣሬ፣ ክፉ ቃል ባይሆንም፣ ቃሉን ስምታ 'አሳስቸግርህ' የምትል መሰለኝ::

«እኔም፣ የጥፍር ቀለም ልገዛ» ሳቅ ብላ: «ግጥጥሙ አይገርምም?»

«መርካቶ ነው የምሄደው፣ እዛ ከሆነ ላደርስሽ»

«አዎን እዛ ነኝ»

«ብዙ መንገድ ይቀርሻል፤ እኔም መርካቶ ነኝ»

«እም......ጥሩ»

አፍታ በዝምታ እንደቆየን:

«አጋዛሃለሁ እንደውም» አለች ፈገግ ብላ፣ ፊት ፊት እንደ ሾፌር እያየች:: ወይም አይኖቼን ማየት እንዳፈረች:: መለስ አድርጋ ስለ መንገዱ፣ ስለመኪና መብዛት፣ ስለ እቃ መወደድ፣ ስለ ጥሩ ክትፎ ቤት እያወራች እኔም እያጀብኳት መርካቶ ደረስን::

ገበያ ውስጥ በሚያስቸኩለኝ በእኔ ጉዳይ ጥቂት አብረን ዞርን:: አካሄድዋና ሁኔታዋ ሁሉ ትንሽ ተለውጦብኛል:: ምናልባት ቀርቤ አዋርቼአት ስለማላውቅ ይሆን? 'ምን ሆንሽ?' ብዬ መጠየቅ ግን አልደፈርኩም:: 'ምን ሆንኩ?' ብትለኝስ? የቤተሰቧን የኢኮኖሚ ሁኔታ አውቃለሁ:: እና እዚህ ላይ ብልጠት አስፈላጊ ስለመሰለኝ:

«ስሚ ማክዳ ከአንድ ሰዓት በሁዋላ እንገናኝ......እ......እኔ በየቦታው እያዞርኩ አላድክምሽ......እ......አንቺ ቀለምሽን ግዢና እዚህ......እ...... ማርስ ሆቴል ጠብቂኝ»

ስለደከማት አላንገራገረችም:: ከመኪና እንደወረደች በር ሳትዘጋ ቀድሜ ቦርሳዬን ከኮቴ የውስጥ ደረት ኪስ በፍጥነት አውጥቼ ከፈትኩና እጄ ያወጣውን ብር ሳልቆጥር ሰጠሁዋት:: ከተቀበለችኝ በሁዋላ አየችውና ደነገጠች::

«የጥፍር ቀለም ነው የምገዛው እኮ መኪና አይደለም» አለች

«ግድ የለም ብዙ ግዢ» አልኩና ቶሎ ትቼአት ሄድኩ

አስር ጉዳዮቼ መፈፀም ቢገባኝም፣ እሷን ለማየት ተቻኩዬ አንድ ሶስቱን ብቻ አጠናቅቄ ወደ ማርስ ሆቴል ስመለስ፣ በሩ አጠገብ ከጥግ ቁጭ ብላ ፓፓያ ጭማቂ ስትጠጣ አገኘሁዋት፤ ጥፍሯን በገዛችው ቀለም ተቀብታ ጨርሳለች:: ሃሳቤ እንደደረስኩ ሌላ ቦታ ልወስዳት ነበር::

«ነይ እንሂድ» ስላት

«ተቀመጥ» አለችና ከጭኗ ላይ አንድ በካኪ ወረቀት የተጠቀለለ ነገር ጠረጴዛ ላይ ቁጭ አደረገች:: በቀስታ ወደ እኔ ገፋ አደረገችው::

«ከፈተው» አለች እየተሽከረመመች፡፡ እንደ ቆምኩ፡

«ምንድነው?» ብዬ ስገላልጠው ያማረ ክራቫት እውስጥ ቁጭ ብሏል፡፡ ግራ በመጋባት አየሁዋት፡፡

«ገዛሁልህ፡፡ ያው ያንተ ገንዘብ ነው፡፡ ደረት ነኝ አይደል?» አለች

ያን ዕለት ማታ አልጋ ላይ ይዤው ወጥቼ እሱን እየዳበስኩ ማክዳን ሳስባት ነበር፡፡ ከአባቴ ቀለበት በተቀር እስከ ዛሬ ድረስ እንደዛ የምወደው ዕቃ ምድር ላይ የለም፡፡ ለብቻው የሚቀምጥበት ትንሽ ሚጢጢ የእንጨት ሳጥን አሰርቼለታለሁ (የሚያምነኝ አይኖርም እንጂ)፡፡

አንድ ሁለት ሳምንት ያህል ጠፍታ ቢሮዬ በየጊዜው ብቅ ማለት ጀመረች፡፡ ከሽሮሜዳ አውጥቼ የመረጠችው ቦታ እጋብዛታለሁ፡፡ ከዓላዛርና ከሌሎች ጓደኞቼ ኑሮ ካለያየን በሁዋላ የረሳሁዋቸው ምግብ ቤቶችና ሬስቶራንቶች መሄድ ጀመርኩ፡፡ ትዝታ እያነሳሁ ለመጫወት ተመቸኝ፡፡ አልፎ አልፎ እሁድ ደብረዘይትና ናዝሬት ስወስዳት፣ በዛ ለጥ ያለ ፀጥታና ብቸኝነት ውስጥ በሚከት ባዶ ጎዳና ላይ እጄን ሰድጄ እንኳን አልዳበስኳትም፡፡ ያልደፈርኩበት ምክንያት ፍርሃቴ እንደሆነ የደረስኩበት አይመስለኝም፡፡ ከሕልም ወደ እውን አለም ሕልም መጣሁ፡፡

ያ ጊዜ ግን ይደርሳል፡፡ ያ የፈራሁት ጊዜ ከች ይላል፡፡ ምክንያቱም በወሬ በወሬ ማክዳ ወዲያ ወዲህ የማለት ፀባይዋን 'ትታለች' ይባላል፡፡ ጊዜው ቢዘገይም ይሄ ዲያቆን በትዕግስት ይጠብቃታል፡፡ ችኩል አይደለሁም፡፡ አፍስሼ መልቀም አልፈልግም፡፡ በዘመኑ ደሞ ድንገት ቢፈስብኝ፣ ሊለቅም የሚመጣው አሞራ እንደ አሸን ነው፡፡ ያቺን ልጅ አምላኬ የዕውን ለእኔ እንዲያደርጋት ፀለይኩ፡፡ *ለሁለመናዋም ፀለይኩላት፡* አይቼአቸው ለማላውቅ ግን ለምናፍቃቸው አጥባቶቿ፣ በሽሮሜዳ መንገዶች ወዲያ ወዲህ ስትል አንጀቴን ለበሉት ለመከየድኪ፣ ቢያቅፉኝ ለምናፍቃቸው እይኖቼን ለሚያጫውቱት ለዓዛብዓኪ፣ ብስማቸው የምመኝ በልጅነት ለተወጠሩት የሚጠጣ ወለላ ነገር በውስጣቸው ያለ ለሚመስል ለከናፍርኪ፣ የተነደፈ ጥጥ ለመሰሉት ጠዋት ማታ ለሚያባቡኝ ለአስናንኪ፡፡ ደሞ እኛ ሁሌም ስለምትገኝበት ህልሜ፣ ባትገኝበትም ተዘጋጅቶ ለሚጠብቃት የሕልሜ መድረክ፡፡ ለእሱም ፀለይኩ፡፡

*ስምአኒ እግዚኦ ፀሎትየ፡፡*

## የቱ ነው ሕልም?

*በመጀመሪያ:*

አንድ እሁድ ከሰአት በሁዋላ ትንሽ ራሴን አሞኝ ቤት ተኝቼ ቆየሁና ወደ ታዚና ለመመለስ ስለባብስ በጣም እንደራበኝ ልብ አልኩ:: ምሳዬን ለመብላት ዐዞ ልሰራ ሰናፍጭ ያስቀመጥኩበት ቦታ ጠፍቶኝ ወዲያ ወዲህ እያንጎዳጎድኩ እያለሁ የአጥር በር ተንኳኳ:: ፍለጋዬን አቋርጬ የቤት በር ስከፍት፣ ማክዳ ጀነሴን አልፋ መጥታ ፊት ለፊቴ በሩ ጋ ቆማለች:: ደነገጥኩ::

«ታዲያስ እዝራ» አለች ፈገግ ብላ:: ነጠላ ደርባለች:: ከስር ጥቁር ቀይ ቀሚስ ለብሳለች:: ተረከዘ አልባ ቆዳ ጫማ አድርጋለች:: ሁለመናዋን ከላይ እስከታች በፍጥነት አይቼ

«አልጠበቅሁም ትመጪያለሽ ብዬ» አልኩ::

«አስቸገርኩህ? ታዚና ላይህ ስመጣ ጌታቸው አሞታል ብሎኝ ልጠይቅህ ነበር......ምንህን አመመህ?»

«ትንሽ ራሴን:: ትናንት ማታ እስከ ሌሊቱ ስምንት ሰአት ስሰራ ነበር:: ቀንም አላረፍኩም»

«ድካም ነዋ ታዲያ......»

«ልክ ነሽ:: አሁን ትንሽ......ኸረ ግቢ እቴ እንዴ?» በሩን ሰፋ አድርጌ ከፈትኩላት::

ቶሎ ቀደም ብዬ ድሮ የተቀመጠችበትን ዛሬ ልብ የማትለውን፣ አርጅቶም ቢሆን ግርማው ያልጠፋ ሶፋ ላይ እንድታርፍ ጋበዝኳት::

«እዚህ ሁኚ:: ታውቂያለሽ የምበላው እያዘጋጀሁ ነበር እንኩዋን መጣሽ»

«አንተ ነህ የምትሰራው ምግብህን?»

«ታዲያስ:: ሰራተኛ አልፈልግም፣ ስጋ ደሞ ብዙ አልወድም፣ ዐዞ ትበያለሽ?»

«ምን?......እንዴት ዐዞ ይበ'ላል?»

«እንስሳ አይደለም:: እርጎ ነው:: አባቴ ነው መስራት ያስተማረኝ»

«ዐዞ ተባለ?»

«ነጭ ሽንኩርትና ሰናፍጭ ይገባበታል:: ከዛ በእንጀራ ወይም በዳቦ ይበላል:: ምረጪ በእንጀራ ይሻልሻል በዳቦ?»

«እንጀራ ይሁን፣ ልየው ደሞ»

«ነይ እዚህ ተመልከቺ እንዴት እንደምሰራ:: ቀላል ነው»

ወደ ማድቤት ወስጄ፣ ሰናፍጩን እንደምንም አግኝቼ ዐዞ እንዴት እንደሚሰራ ሳሳያት:

«ውይ! ይሄማ ቀላል ነው» እያለች የምንበላውን ተቀብላኝ በትሪ ይዛ እኔ ከሁዋላዋ እየተከተልኩዋት ሳሎን መጣን:: መብላት ስንጀምር፣ 'የዕውነት ለምን መጣች?' እያልኩ በልቤ መጠየቅ ጀመርኩ:: ይሄን ሳወጣና ሳወርድ የምበላው በትክክል ከጉሮሮዬ አልወርድ አለኝ::

«ጥሩ ቤት አለህ» አለች ቀና ብላ ዙሪያዋን አይታ

«አሁን አድሼው ነው:: ሊወድቅ ትንሽ ነበር የቀረው:: አንድ ክፍል ከጀርባ ጨመርኩበት:: ለአንድ ሰው ሰፊ ነው:: የሚከራይ ካገኘሽ ፈልጊ:: በቪላ ስም ነው የሚከራየው ሃሃሃ» አልኩ በቀልድ

«እውነት፣ አይጠፋም የሚከራይ:: ልየው?»

«እ......እ......አዎ እዪው» ያኔውኑ 'በቃኝ' ብላ ተነሳችና ወደ ጓዳ አለፈች::

«እጄን የት ልታጠብ?!»

«እ......እጅሽን ለመታጠብ እዛ ክፍል ግቢ» አልኩዋት:: ዞር ብላ አይታ የእጄን ጥቆማ ተከትላ ወደ አሳየሁዋት ክፍል ሄደች:: ጣቶቼ ላይ የቀረውን ዐዞ በእንጀራ ጠርጌ ተከተልኩዋት::

«አይታይም ከዚህ! መብራቱ የት ጋ ነው?!»

«መጣሁ!» አልኩና ራመድ ራመድ ብዬ አለችበት ክፍል ልገባ ስል ደረት ለደረት ተሳተምን:: ደንግጬ ላፈገፍግ ስል ቀኝ ትከሻዬና ክርኔ ላይ የበሩ ጠርዝ ተራ በተራ መታኝ:: መነቃነቅ አልቻልኩም:: ከዛ በሁዋላ ደመነፍሴ ተቆጣጠረኝ:: ከዛ የእንግዳ ክፍል በር ጀምሮ እስከ መኝታቤቴ ድረስ የሆነውን በቃላት መግለፅ የሚከብድ ነበር......

......እንደ ጥብስ መረቅ የጣፈጠች:: በውስጥ ሱሪ ብቻ ሆኜ መኝታ ቤቴ በር ጋ ቆሜአለሁ:: እንድታየኝ አልፈለኩም፣ ግን የትም ሳልሄድና ሳልደበቅ የሚያመልጠኝ ነገር እንዳለ ሁሉ......እልጋ ደርዝ ተቀምጬ ......እንደ ተኛች ቆሜ ......እንደ አባብ ቆዳ የሚፈልቅ ራቁት ጀርባዋን

አያለሁ......የዳሌዋን ከፍታ አያለሁ......ወገብ እንዴት እንዲህ ይሰወራል? የበላችው የት ይቀመጣል? የፀጉሯ እንጭርፍ ከሻሽዋ ወጥቶ ደንዳናው ትራሲ ላይ እንደመጣለት የተበተነ......ገላዋ በትንፋሽዋ በቀስታ ከፍ ዝቅ ይላል......የሆነ ነገር መናገር ያለብኝ ይመስለኛል......'ማክዳ' አልኳት...... ዞር ብላም ሳታየኝ......ሳትነቃነቅ በደከመ አፍ 'ወዬ' አለች......ከዚህ የበለጠ ምንም ቃል አልወጣኝም......የሚያምር 'ወዬ' ነው...... ከአየር ላይ ተቀልቦ እንደ ሞላ የሚሳም......ከእሱ ቀጥሎ ሌላ ቃል ብናገር ጣዕሙ የሚበላሽብኝ መሰለኝ......ሳያት ከረምኩ......አልጋውን ዞሬ ፊት ለፊቷ ቆምኩ......የአይኖቿ ኳሶች ከሽፋሽፍቷ ስር ሲነቃነቁ አያለሁ ......ዕልቅትዋ በሚያሳዝን መልክ ትንተከተካለች......ወደ ፊቷ ጠጋ ብዬ አሸተትኩዋት......ከአፍንጫዋ የሚፈልቀው ስንበብ እንደ ሰንቡላ አጠነኝ ......ብትሰማኝም ባትሰማኝም አልኩዋት......'ማክዳ' 'ማክዳ እወድሻለሁ፣ ሁልጊዜ እወድሻለሁ'......ከግማሽ ሰአት በፊት ወይ ከአንድ ሰአት በፊት የነበረው ከውስጤ የፈለቀው ደመነፍስ ከተደበቀበት ወጥቶ ወደ እሷ መልሶ እንዲወስደኝ ተመኘሁ......ሃጢያቴን ፈለኳት......ቁጢጥ ብዬ የተዘጉ አይኖቿን ሳያቸው ቆየሁና......ልብሴን ለመልበስ ሳሎን ስገባ እንደራበኝ ታወቀኝ:: እዛ ያገኘሁትን የተረፈንን ዐዞ በልቼ እጄን ታጥቤ ስመለስ ነቅታ መጣች......ልብሷን ሁሉ ለብሳለች::

«ቤቴ ልሂድ መሸ» አለች:: ያሳለፍነውን ያለፈች አትመስልም:: ወለል ወለል አየች:: የረጠበ እጄን በሱሪዬ እያዳረቅሁ ሳልከራከር:

«ልሸኝሽ:: ልልበስና» አልኩዋት::

«ግድ የለም እኔ ብቻዬን እሄዳለሁ» አለች:: ድምፅዋ ከማውቀው የለሰለሰና ያማረ ነው::

«እም......ግድ የለም እሸኝሻለሁ» አልኩዋት:: በዐይኗ ቂጥ ስትከታተለኝ በዐይኔ ቂጥ አያታለሁ:: መኝታ ቤት ከእሷ ጋር ባሳለፍኩት የቅንጥ ጊዜ ያወለቅሁት ጫማዬ ጠፍቶኝ ትንሽ ለፋሁ:: እንዱን ያለ ሚር ተጫምቼው ወጣሁ::

በዛ ምሽት......በሽሮሜዳ ከማክዳ ጋር ያደረኩት የእግር መንገድ ......ከልጅነቴ ጀምሬ የኖርኩዋቸው የደስታ ሰአቶችና ደቂቃዎች በዛ አፍታ ተሰብስበው የመጡ ያህል ተሰማኝ:: ተንኮለኞች የተፋቀሩትን ከፍቅር ሲያሸሹ ከዚህ አይነት ደስታ ነበር? በትክክል ሊገባኝ ያልቻለ ጥልቅ ነገር አጋጠመኝ:: መብራት በሌለበት ስልም የሽሮሜዳ መንገዶች ላይ እጄን ስትይዘኝ አየር ላይ የተቀመጥኩ መሰለኝ......በደም በአጥንት በስጋ በነርቭ የተሰራ ጥየራ ሆንኩ:: ምላሴ ሰማይን ቢያክል፣ የእንጦጦን ገመገም ከሸጎሌ እስከ የረር እንደ ማር እልሰው ነበር:: ላላለፍኩት ጉዳይ እንገር እንደሆንኩ ቢገባኝም......ሚስጥሩ ከሌሎች ነገሮች የሚያያዝ አልመሰለኝም:: እንዴት ስሜትና ፍቅር ሕፀፅ የለውም?

እኗን ከሸኘሁ በሁዋላ ለግማሽ ሰአት በዛው አካባቢ ወደ ላይ ወደ ዳገቱ ወጣሁ:: በልጅነቴ ሽርተቴ የምጫወትባት ዛሬ ልጆች የማይደርሱባት መፋለቂያ ስፍራ ላይ ለረዥም ጊዜ ኢነባቢ ሆንኩ:: ገብቼ የወጣሁበትን ወጥቼ የገባሁበትን እያሰብኩ ቆየሁ:: ጠጠር በትካዜ እያነሳሁ እየጣልኩ:: በጨለማ እየለቀምን የምንጫወትበት የድሮ ሚሕየት ሄደ? ሕልሜ ውስጥ የተቀመጥኩ መስሎኝ ደስ አለኝ:: ፍፁም መምሰሉ አስፈራኝ:: የዛ ማታ አጨራረስ በሚፈርሰው ስጋችን ሳይሆን በኪነት ለዘላለም እንዲኖር ፈለኩ:: ከሰው ልጅ ስጋ በልጦ እንዴት ኪነቱ ይረዝማል? የሰው ነፍሱ ኪነቱ ቢሆን ነው? አንድ አንጎራጓሪ ከመቶ ተራ ሰዎች ሊበልጥ ነው? ቤቴ ያደረግነው ሩካቤ ስጋ አልነበረም ዘግይቶ የሳበኝ:: በመጨረሻ ስሸኛት የሆነው ተራ ነገር ነው:: እንዴት ይሄ ተራ ነገር ዘላለም እንዲኖር ለትዝታ ልዑልነት እንዳጨሁት አይገባኝም:: *እንዲህ ነበር:* በየራሳችን በዝምታ እየባከንን ሳለ ተዘናግተን ቤቷን በትንሹ አልፈነው ሄድን:: የዚያ አካባቢ ቤቶች በረዥም ሰልፍ የተሰሩ ናቸው:: ከፊት ለፊታቸው ቦይ አለ:: ቦዩ ቱቦ ገብቶለታል:: የቦዩ ቱቦ ራሱ እንደ ድልድይ ያገለግላል:: መሻገሪያዋን በመሳቷ ትፈር እንጃ:: አውቃ ያደረገችው እንዲመስልላት ይሁን እንጃ፣ ወደ ሁዋላ መለስ ብላ በቀላሉ በቦዩ ላይ ተራምዳ መሄድ ስትችል፣ 'እዚህ ጋ ልዝለል' አይነት ተሰናብታኝ ቦዩን ዘለለች:: ይሄ ቀላል የመሰለ ድርጊት ዘላለማዊ እንዲሆን ፈለኩ:: የተኛ የመሰለ ቀኝ እግርዋ በአንዴ ነቅቶ ሲነሳ......ገና ተሻግሮ መሬት ከመንካቱ ጀርባዋ ለአመል ወደ ሁዋላ ሄዶ ሲመለስ......ወገቧ ሊደርስ ዳር ዳር የሚለው ነዶ ፀጉሯ ጀርባዋን ሲለቅ ......ቀኝ እጅዋ እጄን ሳይለቅ ትቶኝ ሊሄድ ጣቶቼ ላይ ሲንሸራተት...... የስፖርተኛ ያልሆነ ግን የመሰለ አበለቃቀጧ......ይሄ የእጆችዋ አዘረጋግ ......ልቦናዬ ሳይሻ እኗን በመልቀቄ ገጼ ላይ ሊኖር የሚችለው የ'አትሂጅብኝ' ቅሬታ......እነዚህ ቀላል የመሰሉ ነገሮች ተጠረቃቅመው ለዘላለም እንድንኖር ወደ ነጭ የዕብነበረድ ሐውልት እንድንቀየር ተመኘሁ::

ሲነጋ ያዩን ምን ይሉ ይሆን? ምን ይባል ይሆን?

(1978 አም)'የት ነው ሳፈርህ?'

'ሽሮ ሚዳ'

'ሽሮሚዳ የቱ ጋ?'

'ሐውልቶቹ ጋ'

'ማን ሰራው እባክህ ያንን ሐውልት ደሞ እዛ እከተማ ዳር?'

'እንጃ አፈወርቅ ተክሌ ይሆናል፣ እሱ ነው እንደዛ አይነት ነገር የሚችለው'

(1979 አም)'ኽረባክህ ይሄን የሚያደርግ ጎረምሳ ምናምን ነው፣ አወቅሁ አወቅሁ የሚል'

(1980 አም) 'ሐውልት ለነገሥታትና ለጀግኖች እንጂ ለተራ ሰዎች ምንድነው ይሄ ሁሉ ግን? ምን ማለት ነው?'

'ዘግታው ልትሄድ ስትል እየለመናት መሰለኝ'

(1985 አም) 'አብረው ውለው ሊለያዩ ሲሉ ይሆናል'

'ጓደኛው ናት እህቱ?'

(1995 አም) 'ሐውልት የሆኑት ተረግመው ነው ይባላል:: አያታቸው እንዲጋቡ አይፈቅዱም ነበር አሉ:: የሴትዮዋ አያት:: እዚህ ደብረዘይት ይሁን ሞጆ ነበር አሉ የሚኖሩት:: ከእሳቸው ሸሽተው ሲመጡ ከሩቅ ረገሟቸው:: አያድርስ ነው'

(2000 አም) 'ዘግታው ስትሄድ ነው እኮ:: ፊቱን ታየዋለህ ተደብሯል'

(2005 አም) 'ለመሆኑ ሐውልቱ ስም አለው? ማን ሳለው?'

(2006 አም) 'አሳዋቂ ይሆናል የቀረፃቸው:: ለምን ስም የለውም?'

(2007 አም) 'ነበር አሉ:: ልጆች አበላሽተውት ነው'

(2007 አም) 'ምን ነበር?'

(2010 አም) 'ስም አለው ሐውልቱ?'

'እንጃ አሁን አሁን ***አባሮ ገዳይ*** ይባላል መሰለኝ'

(2015 አም) 'ስም አለው ሐውልቱ?'

'ታዲያስ'

'ምን ይባላል?'

'እንጃ:: እረሳሁት'

(2020 አም) '***ተመለሽ ተመለሽ***

'ሐውልቱ ስም አለው:: ሰማሁ መሰለኝ:: እስኪ ላስታውስ:: ለምን አይኖረውም:: እንዲህ ለፍቶ ቀራፂው ስም ካልሰጠውማ፤ አዎ ትዝ አለኝ ***ልሄድበት አባክህ*** ይባላል'

'ግራ ስም ነው አቦ፣ ስም ጠፋ? ግን ጥሩ ስም ይመስላል'

ሁለተኛ:

'በሕልምና በእውን መሃል ወሰኑ የት ጋ ነው?' ብዬ ጠየቅሁ::

እያንዳንዳችን እዚህች ሽሮሚዳ የተባለች ድስት ውስጥ ስንገባ፣ በሕይወት ጎዳና ስንገባ ማለት ነው ምሳሌው:: ፈጥነንም ይሁን

ተንቀራፈን፣ ቢያምርብንም ባያምርብንም፣ ከራሳችን ስንጋጭ፣ ከእሱም ከእሷም ስንጋጭ፣ ስንዋደድና ስንጣላ፣ ስንስቅና ስናለቅስ፣ ሁሉም ያበጀን እንሆናለን:: ወርቅ ብሆን በእሳት ነጥሬ ነው፣ ፈንድሻ ብሆን ታርሼ ነው፣ አውጥ ብሆን በልጃገረድ ጣት ተለቅሜ ነው:: ውሃ ብሆን በቆንጆ ጀርባ በደበናንሳ ስራ ተጭኜ ነው:: ዝናብ የምሆነው ነፋስ ቢያመጣኝ ነው:: ወጥ ሆኜ ብጣፍጥ የአፋር አሸቦ ገብቶብኝ ነው:: ጎል የገባን ኳስ ብሆን የቻለበት እግር ቢመታኝ ነው:: ይሄ የሰውን አለም ጉዞ ነው::

እጄን አየር ውስጥ ብዘረጋ እምባር ከሰማይ ይመጣል? ቁናዬን ጠረጴዛ ላይ ባስቀምጥ አውጡ በራሱ ተንኳሎ ይገባል? ማስሮዬን እዳሪ ባቆም ወንዙ ወደ ጎጆዬ ፈስሶ እሱን ሸክላ ይሞላዋል? ወጤን እያማሰልኩ ጨው ብሻ እሱ እንደ በረድ ከቤቴ ጣሪያ ይዘንባል? ይሄ የሕልም አለም ጉዞ ነው::

## ራሴው መመለስ

## ብችልም ልጠይቃችሁ......

'ይሄን እስኪ እናጣጥል' ቢባል......ያጣጣሉት፣ ያጣጣሉትን ያመኑትም ከሃዲ አይሆኑም?

ሶስተኛ:

ከወር በሁዋላ እርግማን የመሰለ ፆር መታኝ::

[illegible]

# መዋዕለ ታዚና



*......ቁ: 1732 ፍትሃ ነገስት* እንዲህ ይላል:

> 'ዘማውያንን የራሳቸውን ፀጉር ይላጩአቸው:: አፍንጫቸውንም ይፎንኑአቸው:: በዚህም መንገድ እየተላላኩ የሚያቃጥሯቸውን ይግረፏቸው:: ይላጩአቸውም:: ስደትንም ይፍረዱባቸው:: ብዙ ዘመንም በስደት ይኑሩ'

እነጣጣሪ ካልሆንኩስ? የምፈልገውን ቅልጥም ካልመታሁስ?

•

•

•

*ከአንድ አፍ በረከትና መርገም ይወጣሉ (የያዕቆብ መልዕክት* 3:10): በጀርባዬ ሆኜ የታመመ አፍረቴን ይገፔ ስጫኑው የሚወጣው የመግል እርግማን ሕልም ይመስላል:: በሮዛ ተፃብዖና በዚህ ዕውነት መሃል ልዩነቱ ምንድነው? ይሄ በአባቴ የቋንቋ በቅሎ ተሳፍሮ የመጣ እርግማን ነው::

•

•

•

ስለ ዓላዛር ብዙ የትዝታ ጓዝ እጎትታለሁ:: ሆቴሌ ፊት ለፊት ወይም ዋናው መንገድ መሃል በብስክሌት ትሪክ ሲሰራ:: ስንጪጪህ:: የዋህነቱ:: እመቤት እናቱ:: የግርማቸው ጩኸት:: ደቤ ደማም:: ቸርነት ተረባም:: ገርማሜ ቅኔያም:: ዓላዛር በፖለቲካ ተጠዝጥዞ ልሰደድ እንደማይል አውቃለሁ:: ፖለቲከኞች ሊፒስቲክ የተቀቡ ለምቦጫሞች ናቸው:: ቆዳ ጫማ ያደረጉ ሽፋፎች ናቸው:: በነፍስ አብረውኝ የሚሄዱ ሰዎች ደም እንዲላቸው አስቤ አላውቅም:: አጠገቤ ያለውን ቢራ ተቀባብለን የጠጣን ልጅ የሚሞት አይመስለኝም:: ባለቅኔው እንደበተ አልቦ እንደሚሆን አልጠረጥርም:: የተቀመጡበት ቦታ የማናገኛቸው ብዙ ናቸው:: ከመሃል ማክዳን የመሰሉ ሊያስረሱን ሲገባቸው፣ በቀዝቃዛ የትካዜ ኩባ ሸምልለው ይመልሱናል::

•

•

•

ለማከዳ እኔ አልሻላትም? እኔ አላዋጣትም? ከእኔ ጋር ብትሆን ቢያንስ ቢያንስ ከደሃነቷ አትላቀቅም? ለአፍታ እንኳዋን ሂያጇነቷ ሐጢያት ብቻ እንጂ የሃይጂን ጉድለትም አይመስለኝም ነበር:: ምንድነው የሚፈታታን? ሸክላችንን የሚሰብር መዶሻ ውጠን የተወለድን ይመስለኛል:: በዚህ ጎዳና ላይ የሚመላለሰው ሁሉ መዶሻ የዋጠ ይሆናል:: የ ሆዱን የሚዳብሰው የዋጠውን መዶሻ ሲያመቻች ነው:: ነፃ የምወጣው በመሸሸ ብቻ ነው:: ተስፋዬ ገል ናት::

•

•

•

ዕድሌ ነው እንጂ፣
ዕድሌ ነው እንጂ፣
ሀብቴ መች አነሰኝ
ብርቱካን ሲታደል፣
ሎሚ የደረሰኝ
ሜሪ አርምዴ

✱

ዕድሌ ነው እንጂ
ዕድሌ ነው እንጂ
ሌላ ምን አነሰኝ
መረቁ ሲታደል
አጥንት የደረሰኝ
እዝራ ታዚና

•

•

የሰላም ንግግር ከአፋቸው አይወጣም:: ዳሩ ግን በምድሪቱ በፀጥታ በሚኖሩት ላይ ነገር ይሸርባሉ:: አፋቸውን አስፍተው ከፈቱብኝ:: 'እሰይ! እሰይ! በዐይናችን አየነው' አሉ መዝሙረ ዳዊት 35: 20-21:

እኔን ተታላይ የሚያደርግ የፈራሁት ሃሜት አልመጣብኝም:: በአባላጊነት መዝግበውኝ፣ በገንዘቤ ትዕቢት ማከዳን ተጫውቼባት

እንደጣልኩዋት ያወራሉ:: 'ገንዘብ እኮ ትቢተኛ ያደርጋል':: 'ገንዘብ የማይሰራው ነገር የለም':: 'ይሄም ድዳም ሰው ሆኖ በልጆች ይጫወታል':: 'ይሄ ጎባጣ ጉብጥብጥ የተጉበጠበጠ' ያልተባልኩት የለም:: አገሬ በተኳሽ ሙሉ ነው:: ግን እንስታለን:: ሳያጣሩ ወሬኞች ሳይማርኩ አርበኞች ናቸው:: ርዕዮተ አለም የላቸውም ቢኖራቸውም ወሬ ነው:: የለቃቀሙትን ወሬ ይገጣጥሙና 'አመለካከት' ይሉታል:: አመለካከት ያሉትን አጣጥበው ይኩሉና 'እሳት' ያደርጉታል:: ይኼው እየነደደብኝ ነው:: በየገደሉ ያሉት እኔን መሰል ዝንጀሮዎች ቂጣቸው የተመለጠው በዚህ ሰደድ ነው:: ራጉኤል ምስክሬ ይሆናል::

•

•

•

አውቃለሁ፣ ከአባቴ ቃል እጅግ በራቀና በሚያበክተኝ ረግረግ ውስጥ እስከ ወገቤ እንደገባሁ:: ሲራክም ብሎኝ ነበር *እርስትህን እንዳታጣ ለአመንዝራ ልብህን አትስጣት::* ማክዳ እንኳን እንዴ፣ ሺህ ጊዜ ድንግል ብትሆን ድንግል ልትሆን አትችልም:: አባቴ እንደ ምኞቱ ጠንካራ የበኩር ልጅ የለውም:: የልጅ ልጅም አይኖረውም:: በዚህ ተልካሻነቴ ብራባ ፈለፈላው በሙሉ ደደብ፣ ራስ ወዳድ፣ ሴሰኛ፣ እንቅፋት፣ ምቀኛ፣ በራሱ የማይተማመን፣ ነፈዝ፣ ቂል፣ እንደሚሆን አልጠራጠርም:: ዘር ማንዘሬ የሰጠኝን የጥራት ሕግ በግል ስሜቴ የለወጥኩ የዘመኑ ልጅ ሆኛለሁ:: አባቴን ድጋሚ የገደልኩት ይመስለኛል:: ለፍርድ እግዚአብሄር ፊት ሲቀርብ ጥንድ ሟች ሆኖ ነው:: እግዚአብሄርም ይለዋል 'ልጄ ታዚና ለምን ሁለቴ ሞትክ?'

ማረኝ::

•

•

•

በእኩለ ሌሊት መንገድ በችኮላ የሚያቋርጠው የእንጦጦ ጅብና ተሸሎክሉካ ወደ ዳገቱ የምታልፈው ጥንቸል:: መሃል መንገድ ቆመው በአፋቸው የገባ ሳር በዝግታ እያላመጡ ወደ ታች የሚያዩ ሚዳቆዎች:: አሳዳሪያቸው እኔ የሆንኩ መሰለኝ:: ለምን ወደ ታች ብቻ ያያሉ? ምነው እኔ ወዳለሁበት ይማትራሉ? እንደ እኔ የጎደለባቸው አይመስሉም::

•

•

•

***ቆፐርፐር ቆፐፐር ቆፐርፐር:*** መቼ ስለት ሶስት ሰዎች 'ከአዲስአባ ማዘጋጃ ቤት ነን ልናናግርህ እንፈልጋለን' ብለው በጊቾ እየተመሩ ቢሮዬ መጡ:: በስርአት ወንበር አዘጋጀሁላቸውና ተቀመጡ:: ግና ምን ልርዳችሁ ለማለት አፌን ሳልከፍት፣ ግርማ ሞገስ ያለው፣ ከላይ እስከታች ጫማው ሳይቀር ጥቁር የለበሰ፣ ዥጉርጉር ሸሚዝ ያደረገ፣ 'በቀለ' እባላለሁ ብሎ ራሱን አስተዋወቀኝና:

«መረጃ ስለደረሰን እሱን ለማረጋገጥ ነው:: ሆቴልህ ትክክለኛ ያልሆነ ምግብና መጠጥ ይሸጣል ስለተባለ ለመፌተሽ አስበናል» አለኝ::

ግራ ገባኝ::

«ምን?» አልኩ

ሁለተኛው ክራቫት ያደረገ፣ ቡላ ከፌይ ኮት የለበሰ፣ የነጭ ሸሚዙ ኮሌታ ተኩስ የተሳከረ፣ አፉ ዙሪያ መሸበት የጀመረ ሪዝ እንደመስኮት የደገነ (አፉ የእውነት መስኮት ይመስላል)፣ ራስ በራ፣ መልከመልካም፣ በሚሰራው ስራ በመደሰት ላይ ያለ ብቻ ሳይሆን ደስታው ሲቃ ያስያዘው የመሰለ፣ ጥፋት ባይኖርብኝም ጥፋቴን ለመናገር የቸኮለ፣ ልክ ቤቴ እንዳለ ሁሉ እየተዝናና:

«ፖሊስ ለማምጣት ከመገደዳችን በፊት፣ ከአሁን በሁዋላ ከዚህ እስከንወጣ ምንም አይነት ምግብ መሸጥ እንደማትችል እንድታውቅ እንፈልጋለን:: ማለት ምንም አትችልም፣ ሆቴሉ ይዘጋል:: ለተወሰኑ ቀኖች፣ ምናልባትም ለሳምንት ያህል ውሳኔ ትጠብቃለህ»

«አልገባኝም:: እናንተ ራሳችሁ መርምራችሁ ትወስናላችሁ እንጂ ወሬ ሰምታችሁ ነው? ደንበኞቼ ሕፃናት አይደሉም:: የሚወዱትን የሚስማማቸውን ያውቃሉ»

«አሂሂ......ነገርንህ:: ሰው ጠቆመም አልጠቆመም ከአሁን ጀምረህ ይሄን ተቋም ዝጋልን፣ እንስራበት»

«ማነው የሚፈትሸው?» አልኩ::

ጥቁር በጥቁር ወደ ለበሰው ሰውዬ በአገጩና በፊቱ አቅጣጫ እያሳየኝ:

«እሱ ጓድ»

«ምንድነው ወሬው? ላስረዳችሁ ይፈቀድልኛል? ወሬን ያው በወሬ ነውና ሃሃ»

«እየቀለድን አይደለም፣ አንተም ታውቃለህ:: የአዞ ስጋ ትሸጣለህ ይባላል»

ከት ብዬ ሳቅሁ:: ከእነሱ ወጣትና ስልጣን የሌለኝ ስለሆንኩ እንዳከብራቸው ጠብቀዋል መሰለኝ በትዝብት ዐይን ተያዩ

«ምን ያስቃል ጓድ?»

«አዎ የአሆ ስጋ ለመሸጥ ለመጀመሪያ ሁለት ወር ሞክሬ ገበያ አላገኘሁም:: የአሆ ስጋ በልጅነቴ በልቼአለሁ:: በጣም ጥሩ ነው:: አሳ መብላት በሉት:: እናቴ የጋሞ ሴት ናት:: ልጅ እያለሁ አርባ ምንጭ ወስዳኝ ነበር አንድ ጊዜ......እና ያ ስጋ ይናፍቀኛል»

«አዲስአባ የተለየ ነው»

«ሆድ አገሩ የትም ነው:: በነገራችን ላይ የአሆ ስጋ የሚበሉ ደንበኞች ነበሩኝ፣ ግን ለንግድ አላዋጣም:: ብዙ ደንበኛ ያስፈልጋል እንዲያዋጣ»

«አሁንም በድብቅ ትሸጣለህ ይላሉ»

«በድብቅ? በሚስጢር?»

«አዎ»

«በሚስጢር ከሆነ ሚስጢር ነውና እንዴት ጠቋሚዎች አወቁት?»

ሁለቱም ተያዩና፣ ቀልቃላው:

«እኛ ለክርክር አልመጣንም:: ዝጋና እንፈትሻለን»

«ምን ያህል ቀን ነው የምትዘጉት?»

«ሁለት ቀን:: ወይም ሶስት:: ወይም ሳምንት:: ከተገኘብህ ለዘላለም ይዘጋል»

«እስኪዘጋ ድረስ የምትጠጡት ወይም የሚበላ ትፈልጋላችሁ?»

ተያዩ:: ምንም መተያየት አልነበረባቸውም:: አይኖቻቸው ጥብስ መብላት እንደሚፈልጉ ይናገራሉ:: ከሽፋሽፍቶቻቸው ስር ቆሞ የሚጤስ በሬ አያለሁ:: የተሳሳትኩ ነጋዴ ሳይሆን የተሴረብኝ መሆኑን አወቅሁት:: መልስ ቶሎ ስላልሰጡኝ:

«መጀመሪያ ፊልቴር ይምጣላችሁና ከዛ በሁዋላ ምሳችሁን ወይም ራታችሁን ትበላላችሁ» አልኩ በመዝናናት:: እነሱ ተከትለውኝ ከቢሮ ወጥቼ ጌታቸውን ጠራሁት:: የየክፍሉን ሃላፊዎች እንዲያቀርብልኝ ነግሬ ኮሪዶር ላይ ሰበሰብኩና የማዘጋጃ ቤቶቹ ሰዎች እያዩና እየሰሙ ማድረግ የሚገባቸውን ነገር ነገርኩዋቸው:: ጌታቸው በር ላይ ቆሞ ገና የሚመጡ ደንበኞቻችንን 'ምግብ የለም' እያለ እንዲመልስ አዘዝኩ:: ሁለት የፊልቴር ጠርሙስ ይዤ ቢሮዬ ተመለስኩ:: ለእኔም ለእነሱም ፊልተሯን ቀዳሁና ወንበሬ ላይ ተቀመጥኩ::

«እንዳያችሁት እየተዘጋ ነው:: ከማማሽ ሰአት በሁዋላ ደንበኞች ሁሉ ይወጣሉ:: ከዛ......»

«አሁን እየተሰራ ማየት እንፈልጋለን:: ፊልቲሩ ይቆየን» አለ ቀልቀል ያለው::

«ደስ እንዳላችሁ» አልኩና ከራሴ ፊልቴር ተነሳሁ::

«አሳዩና»

በመደበር ብርጭቆዬን ይዤ ተነሳሁ:: በቀጥታ ማድቤት ወስድኩዋቸውና ከየሃላፊዎቹ ጋር አገናኘሁዋቸው:: ለሰዎቹ ሁሉን እንዲያሳዩ ነገርኩ:: ስጋ የሚቀመጥባቸውን ሶስቱን ፍሪጆች፣ የመጠጥ ማስቀመጫ ቦታውን፣ መጥበሻ ቦታውን፣ ቅቤና ቅመም የሚቀመጥበትን ሁሉን በየተራ እንዲያሳዩ ራሳቸው ሰዎቹ እየሰሙ ትዕዛዝ አስተላለፍኩ:: እነሱ ዞር ሲሉ፣ እንዱን ሰራተኛዬን ወደ ጎን ጠርቼ፡

«ለነገር ስለመጡ አንድ ነገር አበላሽተው በእኛ እንዳያሳብቡ ከጎናቸው ሳትለይ የሚሰሩትን እይ» አልኩትና በጥባጮቹ የሚያደርጉት ግድ እንደማይሰጠኝ ላሳያቸው ወደ ቢሮዬ ተመለስኩ:: እንደተቀመጥኩ ስልክ አነሳሁና ማዘጋጃ ቤት አብዱላሂ የተባለ ወዳጄ ጋ ደወልኩ:: አብዱላሂ ገና ድምፄን ሲሰማ በሳቅ ሞተ::

«ምን ያስቅሃል?» አልኩት ግራ ቢገባኝ

«መጡልህ አይደለ» አለ

«ታውቃለህ?»

«የትም አይደርሱም:: ተዋቸው:: የቸገረኝ ማን እንደጠቆመ ማወቅ ነው:: አንተ ጋ እንደሚመጡ ነግረውኝ ነው የሄዱት:: እንደማውቅህ አያውቁም»

«ሆቴሌን ዘጉብኝ አሁን»

«ቲያትር ነው:: ገፋ ካደረጉት እናስቆመዋለን:: ጥሩ ጠላት አለህ ማን»

«ወደ ላይ መደወል ያስፈልጋል?»

«ሲመለሱ የት ሄደው ምን እንዳደረጉ ከተናገሩ ወይም ሪፖርት ከፃፉ እነግራቸዋለሁ:: ከሕግ ውጭ ነው የሚሰሩት:: ማን እንደጠቆመ ላይነግሩኝ ይችላሉ:: አስብበት:: ዛሬ ባይችሉ ሌላ ጊዜ መጠምጠማቸው አይቀርም:: አንተ ልክ ሲሄዱልህ ስራህን ቀጥል፣ አትዘጋ»

«ስለአንተ ልንገራቸው?»

«እንደ እዛ አታድርግ:: ይምጡ:: እንደምንተዋወቅ ማወቅ የለባቸውም:: 'ስልክ ተደውሎ ነበር' እላቸዋለሁ:: መጀመሪያ በጎን

እንዲተዉ እነግራቸዋለሁ:: ካልገባቸው አብዮቱ ይጠቀሳል:: እነሱ አብዮቱን ጠቅሰው ሲያስበረግጉ አንተም ጠቅሰህ የበለጠ ታስበረግጋለህ:: ያሉበትን ስለሚያውቁ የበለጠ በርጋጊዎች ናቸው:: መስታወት ቤት ውስጥ ያሉት እነሱ ናቸው:: 'ነገር እያበላሻችሁ በአብዮቱ ለማመሃኘት ነው እንዴ?' ካልከው የሚገባበት ይጠፋዋል ሃሃሃ»

«ቀል'ድ»

«ቀላል ነው»

«ምን ልታዘዝ ታዲያ?»

«እሱ አሁን አያሳስብም:: ዝም ብለን እንያቸው የት እንደሚደርሱ:: ጨዋታ ነው ራሱ ሃሃሃ»

«ቀል'ድ»

«ታዚና ለዘላለም ትኑር ሃሃሃ......በል እባክህ የሆነ አጥፊ እዚህ እየጠበቀኝ ነው የምሄድበት አለ»

«ደህና ዋል»

«ቻው»

ጠላፄን እየጠጣሁ ሰዎቹን ጠበቅሁዋቸው:: የሚሰሩትን ለማየት መሄድ ፈልጌአለሁ......ግን የተዝናና መምሰል አለብኝ:: በዚህ መሃል ማክዳን አስታውሳለሁ:: እስዋን ማስታወሴ የበለጠ ያደማኛል:: ይሄ አጠገቤ እነዚህ ማዘጋጃ ቤቶች የሚያደርጉት ተራ ነገር ክብደት ያገኛል:: ክብደት የለውም ግን ከጠዋት እስከ ማታ ያለውን ጊዜ 'የአለመታደል ቀን' ብዬ ልሰይመው ትንሽ ይቀረኛል:: ከውጭ ያለው ቀላል ጉዳይ ውስጤ ካለው ጉዳይ ጋር ሲደመር ሕልውና ከባድ ይሆናል:: ማክዳ ብትኖር ምንም አይመስለኝም ነበር:: እንዲህ መቀመጤ ቲያትር አይሆንም ነበር:: እሷ ብትኖር እንዲህ መቀመጤ በቀጥታ 'ምናባታችሁን' የተባለ ትርጉም ይኖረው ነበር::

አንዱ ሰው በር በቀስታ ከፍቶ ገባና የውሽቱን ሳቀ::

«ጥሩ ሆቴል ነው አቦ ግን......» ትንሽ ቆየብኝ:: አተኩሬ አየሁት

«ንፅሕና ይጎለዋል»

«ምኑ?»

«ብዙ ቦታ»

«አዞ ተገኘ?» አልኩ ለማላገጥ እየሞከርኩ::

«አዞው እንኳዋን ሳይሆን ንፅሕናውም......»

«አዞ አላልከኝም?» አልኩት በማቋረጥ

«ጓድ ለአንተ ነው። በዚህ ጊዜ አረንጉዋዴ ዘመቻ ሲባል ሁሉን ያካትታል እኮ»

«ምን ምን?»

«የተሳሳተ አሰራር ሁሉ»

«ምንድነው የተሳሳትኩት?»

«ጭቅጭቅ ትወዳለህ?»

«ጥያቄ ነው የጠየቅሁት»

«ይዘጋና ከሁለት ቀን በሁዋላ እንመለሳለን። ንፁህ መሆን አለበት......ሁሉ በስርአት......»

«እሺ......በነገራችን ላይ ጠላውን ረሳችሁት»

«እንደ ጉቦ ይቆጠርብናል» አለ ቀልቃላ

«ሃሃሃሃሃሃሃሃ»

«ያስቃል?» አለ ታላቅ ስህተት እንደሰራሁ ሁሉ በተጋነነ ትኩረት

«ግድ የለም። ነገር እንደ አመለካከቱ ነው»

«ከነገ ወዲያ እንመጣለን»

«ጥሩ»

በሩን ራሱ ዘግቶ ሄደ። ደቂቃ ቆይቼ ከቢሮዬ ወጣሁና በረንዳ ላይ ቆምኩ። ከሆቴሌ ፊት ለፊት መኪናቸው ቆሟል።

«ምንድን ናቸው?» አለ ዋሕድ

«ዝምብለው ነው»

«ያስፈራሉ»

«ምናቸው ያስፈራል?»

«የመንግስት ነገር ናቸው አይደለም?»

«ከሰማይ ቢመጡም ስህተት አያገኙብኝም»

«ምን አሉ?»

«ሆቴሉ ቆሻሻ ነው»

«ስለዚህ ምን አሉ?» አለ ወደ ስኳሩ መጭመቂያ እያሳየ

«ስለዚህ አይደለም። ስለሆቴሉ በሙሉ ነው፣ ምነው ዋሕድ ምን አሳሰበህ? የትም አይደርሱም»

«የት ደወልክ?»

«ምን? ምን አገባህ?»

መኪናቸውን አስነስተው ሄዱ።

ከአንድ ሰአት በሁዋላ ሆቴሉን ለደንበኞቼ ከፈትኩ። ዋሕድ እየደጋገመ እስክሰላች ድረስ፡

«ኸረ ካዩ ለዘላለም ይዘጉብናል» ሲል አመሸ። በሚቀጥለው ቀንም ከንጋት ጀምሮ እስከምሽት ይሄን ፍርሃቱን በቃለ አጋኖ ደጋገመ። ሰዎቹ ግን በሶስተኛው ቀን አልመጡም። በአምስተኛውም። ተመልሰው አልመጡም።

•

•

•

ሁሉ ግቡ ገንዘብ ነው። ገነት የምንጠጣው (መግባታችን አይቀርም) ወተት ምድር ላይ በሰራነው ደግነት ልክ ነው። ከዚህ የበለጠ ልውውጥ አለ? ትህትና በወተት ይለወጣል። ደግነት በማር ተለዋጭ ነው። ቅንነት በማይቆም ሰላም......ወዘተ። አለም ከላይ እስከ ታች የቀለጠ ንግድ ነው።

•

•

•

'የሰራሁት ከባድ ሐጢያት አለ? ካለ በትክክል ጠቁመኝ። አለበለዚያ ተወኝ። ካልተውከኝ ብትኖር እንኳን እክድሃለሁ' ብዬ ላስፈራራው አምላኬን? መፍሪያ ልብ ካለው? የጩኸቴ ሞገድ ካልተሰማው፣ በልቤ የሚሰርበውን ካላየው ምን ላድርግ? ለምሳሌ። ምሳሌ በምሳሌ። እኔ ምሳሌ አይደለሁም? ምሳሌ ብሆንም እኔን ለመግለፅ ደባል ምሳሌ ሳያስፈልገኝ አይቀርም። በጨለማ የጠፋ ደብዛዛ ባትሪ፣ ሃይለኛ ብርሃን በሚበለጥጥ ሌላ ባትሪ ይገኛል አይነት። የዓላዛር ጀርመን መሆን፣ የእኔ ጥብስ ጠባሽ መሆን፣ ከማክዳ ተገናኝቼ መለያየቴ፣ የዋሕድ የእኔ ሽንኩራ ጨማቂ መሆን፣ የሚያገናኛቸው ነገር አለ? ከማየው ከሚታየኝ ስር ሁላችንንም ያያያዘን ሽቦ አለ? እኛ ሳናውቀው ልቦናዎቻችንና ሐሊናዎቻችን ስልክ እየተደዋወሉ ውጫዊ ድርጊታችንን የሚረብሹት? የሚያርቁት? ነፍስን የሚያሳይ ማሺን አለ? ይሄን ስጋ ሰባብሮ ውስጣችንን 'ይሄው' የሚለን ወፍጮ አለ? አላማዋን፣ እቅድዋን፣ ከሌላ ፍጡር የሚያገናኛትን ከጎንዋ ያጎጠጎጠውን ሽቦ? ይሄን ለመረዳት ማን አቅም አለው? ማክዳን አዎ አየሁዋት። ወደድኩዋትም። በአምሳልዋም ጥብስ ሰራሁ። ውስጥዋ ምን እንዳለ አውቃለሁ? አንተ ራጉኤል ታደገኝ።

ልብን ማንበብ ብችል እዚህ አልደርስም ነበር:: ለምን ልብ አንባቢ አላደረከኝም? ከአንተ አምሳልነት ለምን ይህቺን ትንሽ እንኩዋን አልሰጠኸኝም? ገብጋባ::

•

•

•

*ጠረጴዛ ታሪክ:* ሆቴሌ ሳይጣል የቀረ ከአረጁ ጠረጴዛዎቼ አንዱ ቢሮዬ ውስጥ አለ:: ድሮ ከወዳጆቼ ጋር ከበነው እየበላን እየጠጣን የምንጫወትበት:: 'መሞላፈጫ' እንለው ነበር:: ቢገጣጣብም እዚህ ነው:: አንዳንዴ ሳልፍ ሳገድም እዳብሰዋለሁ:: ጠረጴዛው ስፌሬ ነው:: ጠረጴዛው ልጅነቴ ነው:: ጠረጴዛዬ እንደ ሰው ነው::

•

•

•

አሁን የዚያች ሆቴል ሲሚንቶ ምን ጎድታው ነው አባቴ የሞተው? አይደለም:: የአባቱን ቃል መሸከም ስላልቻለ ነው:: ሲሚንቶ ላይ የወደቀው ሸክሙ ተጭኖት ነው:: እግዜር በጠራራ ፀሐይ በመብረቅ አይመታም:: እግዜር ደካማን ለመምቻ ተአምር አያስፈልገውም:: ትንሽ ሰበብ ይበቃዋል:: የሰበቡ ክህሎት አለው::

**በሌላ ይጎዳህና በአንተ ያስይመዋል::**

በትንታ ('ቀስ ብለህ አትጠጣም' ይባላል)፣ በእንቅፋት ('እያየህ አትራመድም' ይባላል)፣ በመጥፎ ልጅ ('በደንብ አያሳድጉና' ይባላል)፣ በባለጌ ሚስት ('ቸኩሎ አግብቶ' ይባላል)፣ በደሃነት ( 'ሰነፍ ቢጤ ነው' ይባላል)፣ የምኞትህን ባለማግኘት ('ደህና አይመኝም፣ ደህና እንዲያገኝ' ይባላል):: እግዜር የሚያስፈራው በግርማ ሞገሱ አይደለም (የት አየሁት?) ሰበብ በመፍጠር የማያልቅ ጥበቡ ነው::

•

•

ወደ ላይ አንጋጥጬ አይሮፕላን ሳይ ትዝ የሚለኝ እዚህ የሌለው ዓላዛር ነው:: የአገጩ ሰርጓዳ፣ የጥርሱ ማማር:: በካናቴራ ሆቴሌ ደጃፍ ላይ ቆሞ ወዲያ ወዲህ እያለ ሲታረብ:: ወጉና ሳቁ:: እናም ከዛ እናቱ:: ዓላዛርን ሳስብ ብዙ ያልተለወጠው የሰፈሬን መልክአምድር አያለሁ:: ደሞ የሚለወጥ ውስጤን:: ሳላየው የሚለወጠውም ሌላው......የሆነ ቦታ ጋ፣

የሆኑ ቦታዎች ጋ እኔን የሚበላ ለውጥ ያደባ ይሆናል……ወይም ባይገባኝ እንጂ እየቆረጠመኝ ነው:: እሱ ምንድነው?

•

•

•

ዋሕድ ስሙን አጠገቤ አንስቶት የማያውቀውን ወንድወሰንን ለምን እንደሆነ እንጃ ጠቅሶ 'ቤቱን እንደሚቀይር እሱንም ሸክም መርዳት እንዳለበት' ሲያማርር ሰማሁት:: ስለ ማክዳ ሊነግረኝ እንደፈለገ ቢገባኝም ስላላስቻለኝ 'ወደየት እንደለወጠ' ጠየቅሁት:: ከጠየቅሁት በሁዋላ መጠየቄ ቆጨኝ:: 'መሸከም እረዳዋለሁ' ብሎ ከተናገረ በሁዋላ ግን አልሄደም:: ማታ ላይ ስራውን አቁሞ ቤቱ ሊሄድ ሲል 'ለምን ወንድወሰንን ለመርዳት እንዳልሄደ' ስጠይቀው ስራ እንደበዛበትና የወንድወሰን እቃ ደሞ ቁጥሩ 'ትንሽ' እንደሆነ አልጋው እንኳዋን 'ሶስት እግር' እንዳለው እየሳቀ አወራ::

•

•

•

ውስጤ ያ አለ፣ ውስጤ ያቺ አለች:: ውስጤ ሁሉ አለ: *አምላኪውም የሚመለከውም*:: ልቤ ሆደ ሰፊ ነው፣ እንኳዋን ሰው የየረርን የተራራ ሰንሰለት የሚያጋድም:: ሙሉኩሌው እዚህች ውስጤ ያለጥሪ ተሰብስቧል:: ማን ጠራው?

**ሐጢያቴ ሐጢያትዎ**

**ፍርሃቴ ፍርሃትዎ::**

**ቢጎዱኝ የምትጎዱት ራስዎን ነው::**

**ትንሽ እስዎ እኔ ውስጥ አለ::**

**ገልበው እዩት**

**ይሄው አለ::**

ውስጤ አለ ማለት 'አውቀዋለሁ' ማለት አይደለም:: የሚገርመኝ ሁሉ ውስጤ ተሰብስቦ አጫውቶና አስቆ ሊያሳድረኝ የሚችል ንቃት ነጥሮ አለመውጣቱ ነው::

•

•

•

ለምን ማክዳ እንዲህ አደረገች? ማንም ያላደረገላትን አረዳሁዋት፣ ከትምህርቷ ሲያሸኗት ወደ ትምህርቷ መራሁዋት:: ለመሆኑ በበሽታው ባትታመም፣ ወይም ታማ ባታሳምመኝ ኖሮ እኔን ማታለሏን አውቅ ነበር? ያላመማት ሰው ሆነ ብሎ ከሆነስ? መቀቴዎች በወሬ የጀመሩትን ወደ ድርጊት ለመለወጥ እሷን ተጠቅመው እንደሆነስ? ከወረደብኝ የድብርት ካፊያ ምን ያህሉ እርጥበት ከእሷ ነው?

ስለቂም የማስብባቸው ስአታት የበዙ መሰለኝ:: አድርጌ የማላውቀውን ጠየቅሁ: *ቂም ምንድናት?* ቂም የፈረሰ እምነት የሚቀመጥባት ስፍራ ናት:: ሰው በሰው ላይ፣ ሰው በቤተዘመዱ ላይ፣ ሰው በሰፈሩ ላይ፣ ሰው በአገሩ ላይ ቂም ይይዛል:: የመልፈስፈስ መብት የለኝም? 'የሚያደርጉትን ያውቃሉና ይቅር አትበላቸው' ማለት አልችልም? ጅራፌን ገምጄ ብወጣ ሽሮሜዳን አቋሜ ብገረፍ ግድ የሚሰጠው አለ? ወንጭፌን ይዤ እንጦጦ ላይ ወጥቼ በምትጦዝ ቂሊ አዲስአባን ባደባያት የሚከፋው አለ? ስርዓቱ? ክፋት ከሁሉ ማሕፀን የምትማጥ ናት:: እንዲህ ባስብ ያስከስሰኛል? ክፋዎች የሚደበቁት ደጋጎች ካባ ስር ነው:: ወንጭፌ አይመርጥም::

**ወይ ካባዎን ዞር ያርጉልኝ ወይ ወግዱልኝ::**

ወንጭፌ ግንባር ጠምቶታል:: የቂም ቅኝ ግዛት ነኝ::

•

•

•

እንደምንም ብዬ ከራሴ ጠማማነት ታግዬ ለማክዳ የምትተኛበት አልጋ እንዲወስድላት ዋሕድን ጠየቅሁት:: እንዳጠፋሁ ሁሉ አተኩሮ አየኝ::

«ምነው?» አልኩት

«ምንም:: ዛሬ አይመቸኝም»

«ሲመችህ:: መቼ ይመችሃል?»

«ያው እሁድ ከሰአት»

«ስትሰጣት እኔ እንደላኩላት አትንገራት»

«ካልክኝ እሺ:: የታለ አልጋው?»

«ጥሩ አልጋ ነው:: የእንጨት ነው:: አሪጂናሌ:: ምንም ነገር አልሆነም:: የሆቴሉ ነበር:: አንድ ሰው የሚያስተኛ ነው:: መጋዘኑ ውስጥ አለልህ»

ያኮረፈ ይመስላል:: ግራ:: ግን ቢነግራትስ? በሁኔታዋ አዝኜ ሳይሆን፣ 'ነይልኝ' ለማለት የፈጠርኩት ብልጠት አይመስልብኝም?

•

•

•

በአገሩ ድርቅ እንደገባ ይወራል:: ወገን አገሩን ያማል:: ጥብሴን እየበላ:: የሆነ 'ሐይለስላሴን ያጋለጠ ጉድ ተደገመ' እያለ:: ሃይለስላሴን ድርቅ ይሄንንም ድርቅ:: ሁላችንም እንደምንወድቅ አያውቁም? የአንዱ መዋረድ ለአንዱ አይሰራም? ሃይለስላሴን የጣላቸው ድርቅ ሳይሆን ወሬና ጠመንጃ መሰለኝ::

ይሄው አዲስ ሽኩቻ ጨዋታ: ወሬ፣ ረሃብ፣ ጠመንጃ:: ሁሉንም ወሬ ያሸንፋል::

•

•

•

ያውና እዚያ ማዶ ፍሪዳ ተጥሏል

ቢላዋው ደንዞ ልብ አልቆርጥም ብሏል

•

•

•

በዚህ እሁድ ምሽት ክረምት ውስጥ ተባረኪን ከባልዋ ጋር አገኘሁዋት:: 'ፋሲል' እባላለሁ ብሎ ተዋወቀኝ:: ረዥም ግርማ ሞገስ ያለው ሰውዬ ነው:: ዕድሜው ከተባረኪ ከፍ ያለ እንደሆነ በግልፅ ይታያል:: ጥሩ ሰው ይመስላል:: መሴ (ምስክርን 'መሴ' ነው የምላት) ትልቅ ልጅ ሆናለች:: ፀጉሯ ጀርባዋ ላይ ነው:: ገና ስታየኝ እጅዋን ስቅላ እየሮጠች መጣች:: ታዚና እንዲመጡና ምሳ እንዲበሉ ጋበዝኩዋቸው:: እሷ እምቢ ስትለኝ 'መሴን አውሽኝ' አልኩዋት:: 'እማማን ትያትና ትመጣለች' አለች:: የምታሸሽኝ ስለዓላዛር እንዳላወራት ይመስለኛል:: ምን ልበላት? የዓላዛርን ስም አላነሳም? ብል ያምራል? እሱን የመሰለች ልጅ ይዛ ትዞር የለም እንዴ:: ዓላዛር ትንሽ ሴት ልጅ መስሎ ጎንዋ አይደለ ያለው? ፋሲል እንዴት ይሄን ፉክክር ይቋቋማል? ሶስት ሆነው ሲቀመጡ አየሩ ውስጥ ዓላዛር ይንሳፈፍ የለ እንዴ?

ምናልባት ተባረኪ በትክክል የማንም አይደለችም:: ፋሲልም እሷም በቀን ሕልም ነጋዴዎች የተሸወዱ ይሆናሉ:: የእሷ አይነት ልጃገረዶች

ሲመስለኝ በትክክል ተገላብጠው የተሳሙት በፖለቲካ ድርጅታቸው ነው:: ፍቅረኛ ደረት ላይ ይወድቅ የነበረው እውነተኛው የመጀመሪያው ዕንባቸው ያረፈው ድርጅታቸው ደረት ላይ ነው:: መዶሻና ማጭድ በተጠለፈበት ቀይ ጋቢ ተከልለው በድርጅታቸው ተወስበዋል:: በከተማው የሚያስሙት ቃተታ ሲታሰሩ የሚተነፍሱት ብቻ አልነበረም፣ ሲገረፉ ብቻ የሚወጣ አልነበረም፡ የድርጅታቸው አለቆች በጆሮአቸው ጣፋጭ ተምኔት እያስገቡ ሲወስቡአቸው ነው:: ተስተካካይ ጣዕም ያለው ነገር ከዚያ በፊት አላጋጠማቸውም:: ያን ማን ይረሳል? ሲያድ ባሬ የጅጅጋን በር ሲያንኳኳ፣ በዚህ የስሜት መረቅ ሰክረው ነበር:: የአገሬ ወታደሮች ከሐረር ሲሸሹ (ሲዋጋ: 'ለምን ትዋጋለህ?' ሲሸሽ: 'እዩት የፈሪ መዓት፣ ሲሸሽ' ግራና ቀኝ እያጮሉት) በኮቴአቸው ድብደባ ከሚነሳው አቧራ ስር የእነዚህ ኮሚኒስቶች ዳንስ ጦፎ፣ የድርጅታቸው የሕልም ሙርጥ እስከ ዕንብርታቸው ተቸንክሮ በፍስሐ ሲያምጡ ነበር:: ለአገሩ ወሰን የሚዋጋ ወጣት ጠፍቶ አባት አርበኞች ደግመው ደጋግመው ሊሞቱ ወደ ጨለንቆ ሲሄዱ፣ የሐረር ሴቶች ማሕፀናቸው እየተቀደደ ሽላቸው ሲጎተት፣ የእነዚህ ልጆች ብሌን በድርጅታቸው እጠፋሪስ ተበልጥጦ ማሕፀናቸውም ተምኔት ሲያላምጥ ነበር:: እኔ ምስኪኑ ለእናት አገር ጥሪ በየሳምንቱ ካሼን ስጠፈጥፍ፣ ከጀርባ ቆመው ጥብሴን እየበሉ አሽሙዋጠውኛል:: ከሮዛ ተዓብያ የበለጠ እውነትነት የሌለው፣ ማድረግ የማይችሉብትን ሁሉን እኩል ላድርግ ጣጣ:: ቢማሩ ባይማሩ በቁጭ በሉዎች የተፈነገሉ ቁጭ በሉዎች::

ተባረኪ እንደነገረችኝ ፋሲል የኮሌጅ አስተማሪ ነው:: ሳልጠይቃት የነገረችኝ 'ምንም ትተውን ቢሄዱ፣ እዚህ በትልቁ እንዘግናለን' ብላ ይሆን እንጃ:: ፋሲል መሴን:

«ከም ሂር[150] መስኪ» አላት:: ምላሱ እንደ ፈረንጅ የለሰለሰ ነው::

ካልሄድኩ ብላ አለቃቅሳ ተባረኪ ራሷ ከሩብ ሰአት በሁዋላ እኔ ጋ አመጣቻትና ወደ ባሏ ተመለሰች:: ለመሴ ቢሮዬ አስገብቼ ምግብ አዘዝኩላት:: የሸንኮራ ጁስ መጣላት:: እሱን እስክትበላ ከበፍቃዱ ግሮሰሪ ቼራሊያ ብስኩት ገዝቼ አስቀመጥኩ:: የምስራውን ጨርሼ ስመጣ፣ መብላቷን ጨርሳ ስታንጎዳጉድ አገኘሁዋት::

ገና ስታየኝ:

«አንድ ነገር ልጠይቅህ?» አለች

ብዙ ስጋ ስለበላች ደክሚታል:: ንግግሯ ውስጥ እንቅልፍ አለ::

---

[150] ነይ እዚህ (come here)

«ምን?»

«ለምን ጆርባህ እንደዚህ ሆነ?» አለችና እጅዋን ወደ ላይ ዘርግታ ጎበጥ አደረገችው? ሳቂ ሊመጣ ነበር:: የፊቷ ኮስታራ መሆን አስቆመኝ::

«እም......አታምኚም ብነግርሽ»

«አምናለሁ፣ ማመን አሪፍ ነኝ»

«ነው?»

መስኮት ከፈትኩና እንጦጦን አሳየሁዋት

«ያ ይታይሻል?»

«ምኑ?»

«ተራራው?»

«እህም»

«እሱን ከአዋሳ ተሸክሜ ያመጣሁት እኔ ነኝ:: በቃ ከዛ በሁዋላ ጆርባዬ ጎበጠ»

«ውይ! አላምንም!»

«አምናለሁ አላልሽም?»

«አዋሳ ያለው ተራራ ታቦር ነው፣ አላቅ መሰለህ?»

«ይሄ የታቦር ጓደኛ ነበር»

«ጓደኛ አለው? አላምንም»

«እመኚኝ:: አዲስአባ ተራራ ስላስፈለጋት ይዤ መጣሁ»

«አዲስአባ ትወድሃለች ማለት ነዋ»

«ታዲያስ»

«እኔም እወድሃለሁ»

«ለምን?»

«በቃ እንደዚሁ......እም......የሸንኮራ ጁስ ትገዛልኛለህ» አለች አናቷን እያከከች

«አንድ ነገር ላሳይሽ»

«ምን?»

እዛ እዛ በርብሬ የዓላዛር የልጅነት ፎቶዎች ያሉበትን አልበም እያወጣሁ ሁሉን ተራ በተራ አሳየሁዋት:: ስታይ ቆየችና፣ በፀጉሯ እየተጫወተች ጠበቅ ባለና ባዘነ ድምፅ:

«አባባ አይመጣም» አለች

«ለምን?»

«ወታደሮች እንትን......ይደበድቡታል»

«ማን አለ?»

«ፋሲል»

«ፋሲል? ለምን?»

«በቃ ክፉ ናቸዋ ወታደሮቹ»

«ሁሉም ክፉ ነው:: የማይመጣው ሲመስለኝ መሴ ብዙ ብዙ ነገር አለ:: አይገባሽም አሁን:: ስታድጊ ይገባሻል»

«አድጌአለሁ»

«ሁሉም እንደዛ ብሎ ነበር»

«ደከመኝ እዝራ»

«ቴቢ ጋ ልውሰድሽ»

«እሽኮኮ አትለኝም?»

«ሃሃ በይ ነይ»

•

•

•

ለሁሉም ጊዜ አለው:: ለመረዳት፣ ላለመረዳት፣ ለመሳሳት፣ ለመስተካከል፣ ቀና ለማለት፣ ለመጉበጥም፣ ስኳር ከሰማይ የሚረግፍበት ዘመን አለ፣ የመጥመቅ ጊዜ አለው፣ የመጠጣት ጊዜ አለው፣ ጠጥቶም የመሽናት፣ የመወለድ ጊዜ አለው፣ የማደግም ጊዜ አለው፣ የመጎርመስም ጊዜ አለው፣ ጎርምሶ የመውደድም፣ ብስክሌት የመጋለብ:: የጋለቡትንም የመስበር:: የሰበሩትንም የመጠገን:: የጠገኑትንም መልሶ የመጋለብ:: ጊዜ አለው በሬ የሚያርስበት:: ለስጋም ወደ ገበያ የሚነዳበት፣ ከገበያም ተወስዶ የሚታረድበት:: ጊዜ አለው ወደ ጥብስ የሚለወጥበት:: ጊዜ አለው ማዕዳችን ላይ የሚከነበልበት፣ ጥብስም የሚመለከበት:: ጊዜ አለው ዲያቆን መሆን፣ ጊዜ አለው ነጋዴም መሆን፣ ብተዛብኦ ማፍቀር እሱም አልፎ በቃን ሕልም መውደድ፣ ቀለበትን የማጣት እሱንም መልሶ የማግኘት፣ ጊዜ አለው ለማፍቀርም፣ ጊዜ አለው አፍቅሮ ለመለያየትም (አሌክስና ተባሪኪ ምሳሌ ይሆኖሙ) ጊዜ አለው ገመና ገመና ላይሆን:: ጊዜ አለው ግዙፉ አውድ ረቂቅ አውድ የሚሆንበት:: ለሁሉም ጊዜ አለው ይላል ይሄ እዝራ ታዚና......

•

•

•

*ትዝታ እያረጀም*......ሮዛን ዛሬም ሳስታውሳት ደግነቷና ክህደት የሌለበት፣ ክህደት የማይታሰብበት ንፁሕ የሌሊት ፍቅሯ ትዝ ሲለኝ በተምታታበት ስሜት ዕንባ በአይኖቼ ግጥም ይላል::

•

•

•

የማክዳ ሱካ ናፈቀኝ:: አልጋዬ ላይ ተኝታ እንቅልፍ ጥሎአት:: የተበታተነ ጎፈሬዋ ትራሴ ላይ እንደ ጥቁር ፀሐይ:: ወገብ ያላት አትመስልም:: ጡቶቿን ስበት አልደፈራቸውም:: አፏን በትንሹ ከፍታ ተኝታ:: ተጠግቼ ለስላሳ ሀሀሀ ሀሀሀ.......ሀሀሀሀሀሀ ዋን ማዳመጥ:: ቆዳዋ እንደ መስታወት ነው:: ወደዛ ሄጄ መልኬን አየሁበት:: መልከመልካም ነኝ:: እና አለች፡ 'ገብተህ ተኛ':: አልጋው ውስጥ እንዳለሁ 'ፊትህን አዙር' አለችኝ:: ሆዴን አቅፋ ጀርባዬን ተደግፋ ስንተኛ:: በዐይነ ሕሊናዬ ጠዋት ማታ እነቸለችላታለሁ:: ውስብስብ ምስልዋን በተዘበራረቀ ተራ እየገለጥኩ አያታለሁ—ሱካዋ እንዳሳደገኝ ድፎ ይናፍቀኛል::

•

•

•

*ፍልሰታና ነነዌ:* እንደ ድሮው በስራዬ ተፍ ተፍ ማለት ከብዶኛል:: ቶሎ ከውስጤ ይደክመኛል:: ቆሜም ይሁን ተቀምጬ ቁና ቁና እተነፍሳለሁ:: ጌታቸው ይሄን ሁኔታዬን እያየ ትዕግስቱ አልቆ አልፎ አልፎ ያደከመኝን ዘይቤ ይነግረኛል: *ከኮባ ዛፍ ሙዝ ትጠብቃለህ?* ከማክዳ ለምን እንደተለያየሁ *በዝርዝር* ስነግረው ራሱን በቀስታ ነቀነቀ:: ምንም አላለም:: ብቻ እናቱን ግራና ቀኝ ነቀነቀ:: ለምን ይነቀንቃል? ሆዴ ቡጭ ቡጭ ሲል አይሰማውም? አድማሴ ፈርሶ ገደል ዳር እንደቆምኩ እንዴት አይታዘብም?

ገብሬል ከሌለ ደጀሰላሙ ምን ይሰራል?

ማርያም ከሌለች ፍልሰታን ለምን እፆማለሁ?

ነነዌ ካሌለች በስሟ ለምን እራባለሁ?

•

•

•

ማክዳ ኢኤስኤል ሲ አልፋ ስድስት ኪሎ ዩንቨርሲቲ እንደገባች ዋሕድ ነገረኝ:: ዋሕድ ሲነግረኝ ግን አጣጥሎ ነው:: ለምን እንደዛ እንደሚያደርግ አልገባኝም::

«እንዴት አለፈች? ኮሌጅ ቀልድ ሆኗል ማለት ነው። ደርግ ኮሌጁን ገሎ ማንም የሚገባበት ሆነ እኮ! ይገርማል። ቂጥዋ እኮ ቢት አይቀመጥም። ቢነገራት አትሰማም። ያኔ አልጋውን ስወስድላት ጠዋት የወጣች ስትዞር ውላ ማታ ነው በአጋጣሚ ስለቆየሁ ያገኘሁዋት። ጅብ መጮህ ጀምሯል። የሚኖሩበት ሰፈር አየር ጤና ደግሞ ያው ሳታውት አትቀርም የጅብ አገር ነው። የሽቶዋ ጠረን ራስ ያዞራል። እናቷ ጠዋት ማታ እንዳስለቀሰች ነው። ከአንተ ጋር ሲያዩአት ወላጆቿ በቃ እንዴት ደስ ብሎአቸው ነበር መሰለህ? 'የጨዋ ልጅ፣ የቄስ ልጅ አገኘች...... ሆኖላት ፀባይዋን ብታሳምር' እያሉ። እንደውም ባሰባት። የሚገርመኝ ገንዘቡን የት እንደምታገኘው?» አለና ፈገግ አለ

«እንዴት ነው?» አልኩት

«ምኑ?»

«ልጅቷ የጓደኛህ ልጅ አይደለችም እንዴ?»

«እና?»

«ክፉ ትናገራለህ»

«ማንም የሚያውቀውን ነው የምነግርህ»

«ማታ መምጣቷን አንተ ብቻ ነህ የምታውቀው፣ ያለችበት ቦታ ባላገር ስለሆነ ብዙ ሰውም አያያትም። ስለዚህ ማንም አያውቅም። ተሳሳትኩ?»

«ሌላውን ጊዜ እንጃ፣ ያጋጠመኝ ግን እንደዛ ነው። ምን አስዋሸኝ። ልጄ ማለት እኮ ናት። ስለምታበሳጨኝ ነው፣ ቢነግሯት አትሰማም እኮ። እንጃ ደስ ይለኛል ጥሩ ቢገጥማት። መበሳጨት ብዙ ያናግራል ወንድሜ»

እንዲህ ብሎ እንገቱን ሰበረ። ከንፈሩን መጠጠ። ከንፈር መጠጣው የተናገረውን ለመሰረዝ ያደረገው አይደለም። አይስምርም። ግን ዩንቨርሲቲ በመግባቷ ልቤን ደስ ብሎታል።

«ስማ»

ቀና ብሎ አየኝ። የምተቸው መስሎት ተቁለጨለጨ።

«ትንሽ ገንዘብ ትሰጥልኛለህ ለማክዳ?»

«በደንብ እንጂ» ክፉ መናገሩን ሊያኪያኪስ ቸኮለ።

ፊቱ ግራና ቀኝ በፈገግታ ተበለቀጠ። ላምነው ከበደኝ ግን አማራጭ አልነበረኝም። አንድ መቶ ብር አወጣሁና ሰጠሁት። ብሩ ላይ እፍጦ ተቀበለኝ።

«እዚህ ሰፈር እንዲት ጓደኛ አለቻት አይደለም? ማን ነበር ስሟ?»

«ምን ታደርግልሃለች?»

«አንዳንድ ነገር ልጠይቃት» ለማክዳ ገንዘቡን ይሰጣት ወይ አይሰጣት እንደሆነ መቆጣጠር እንደምችል ሳሳየው ነበር::

«አይ የአይጥ ምስክር ድምቢጥ ነው እባክህ:: ሴቱ ተበሳሽቷል:: የእኛ ጊዜ መሰለህ?»

«የቱ ነው የእኛ ጊዜ?»

«አይ ካልገባህ......»

«ይገባኛል»

«እንደ ድሮው አይደለም:: ቤቷን አሳይሃለሁ ከፈለክ»

«ተወው»

«ሚስጢር ልንገርህ?»

«ስለማን?»

«ስለሁለቱ»

«ልስማዋ» አልኩት ፊቱን ሳላይ:: ብታናድደኝም ሲያሙብኝ አልወድም::

«ጓደኛዋ ናት ፈተና አግኝታ ያመጣችላት:: ይህቺ ጓደኛዋ ወዳጅ አላት ዩንቨርሲቲ ውስጥ የሚሰራ»

«ለማክዳ?»

«እ......በእግዚአብሄር ለማንም አትንገር:: መንግስት ከሰማ የሚሆነው አይታወቅም:: ግንቦት ውስጥ ያለፈው አመት በቀላሉ እንደምታልፍ ነግራኝ ነበር እየሳቀች:: ቀልዷን መስሎኝ ነበር:: ለማንም አትንገር በማርያም፣ በተክልዬ»

«ፈተና ተገኘ ሲባል ሰምቼአለሁ:: ውሸት ሊሆን ይችላል»

«ኸረ ውሸት አይደለም»

«በል ይልቁን ገንዘቡን እንዳትረሳ......»

•

•

•

***የባለጌዎች ኪነጥበብ:*** ዓላዛር ወደ አሜሪካ እንደተሻገረ ሰማሁ:: ያን ቀን ስራ አልሰራሁም፣ ያን ቀን አልተኛሁም:: ምክንያቱም ዓላዛር ሲሰደድ የተሰደደው አንድ ሰው ብቻ አይደለም:: አንድ ደርዘን ዜጋ ነው:: ዓላዛር ሲሰደድ የተሰደደ ጆሊ ጃክ አይደለም:: አንድ እናቱ

የምትወደው ወልድ ነው፣ ወዳጄም ነው፣ አንድ የሚያምር ዛላ ነው፣ አንድ ብሩህ ነው፣ አንድ የሰፈር ልጅ ነው፣ አንድ አፍቃሪ ነው፣ አንድ ደግ ነው፣ አንድ ቀልደኛ ነው፣ አንድ የዋሕ ነው፣ አንድ ጎበዝ ተማሪ ነው፣ አንድ ፍጥር የሚችል እግር ኳስ ተጫዋች ነው:: የተሰደደው በአንድ የተመሰለ አስራ ሁለት ሰብ ነው:: የተሰደዱት ደርዘን ልጆች ናቸው:: አስራ ሶስተኛ የለም እንዴ? አንድ 'ለምን ብዬ እሰደዳለሁ?' ብሎ የሚከራከር ተጠራጣሪ:: የተፃፈለት ቶማስ? (ዓላዛር አንዳንዴ ጨዋታ ላይ ያልሆነ የመሰለ ነገር አምጥቶ አላምን ስለው 'ቶመስሽ እንዴ?' እዝራ ይለኝ ነበር ሂሂሂሂ)

ወሬኞች 'ይሄ አገር የሚኖርበት አይደለም' ይላሉ:: ምን ማለት እንደሆነ አይገባኝም:: ዛሬን በትክክል ያልተረዳ ሰው፣ ነቢይ ለሚያስፈልገው የነገ ጉዳይ አዋቂ እንዴት መሆን ቻለ? በምን የመተንበይ ችሎታው ነው *ነገ ክፉ ነው* ብሎ የመሰደድ እቅድ የሚያወጣው? ታሪክ የሚፈጥረው? ዓላዛር የጎደለበት አልነበረም:: ከግል ታሪኩ ነጥሮ ያልወጣ እኔ የማላየው የሆነ ረቂቅ መንፈስ ይኖር ለስደት የሚመለምል? አገር የሚባሉት ሕዝብና መሬቷ ናቸው:: መሬቷን በጦር መውሰድ ካልቻልክ፣ ሰዎች እያዩ 'አሳዳጅ' ብለው እንዳይሰድቡህ የስደት ጦርነት ትከፍታለህ:: ስደት ሁሉን አቅፎ የያዘ ጥፋት ነው:: ከአገሩና ከሰው' ታርቀዋለህ:: ደም ለምን ይፋሰሳል? ከሩቅ ሾርባ እየቀቀልክ ጢሱን በፎጣ ታሰራጫለህ:: ወጣት ጠረን እያነፈነፈ ወደ ሾርባው ይሮጣል:: እዛ ሲደርስ ድስቱ ተነስቷል:: እንኩዋን ድስቱ እሳቱ የለም:: እንኩዋን እሳቱ ጉልቻው የለም:: እንኩዋን ጉልቻው፣ ጉልቻው የሚቀመጥበት መሬት የለም::

ከዚህ ከሽሮሜዳ ተነስቼ እዛ ሞጆ መድረሴ ሰላም መሆኑ ዲሞክራሲ አይደለም? በርበሬ ተምትሜ በልቼ በጣሳ ውሃ ብጉመጠመጥ ዲሞክራሲ አይደለም? ምንድነው ይሄ ቃል? እንደሚመስለኝ የኢትዮጵያ ጠላቶች ብልጥ ናቸው:: አገሬ በብልጥ ጠላት እየተመዘመዘች ነው:: ይሄን ብልጥነት ሊቋቋም የሚችል ብሩህነት የለንም:: ስራችን ጠላቶቻችን የሚሰጡንን ማሳበቢያ እንደ ማሚቶ መጮህ ነው: *እዚህ አገር የሚኖርበት አይደለም!* ዓላዛር እንዲህ የሚያደርግ አይመስለኝም ነበር::

ፀሐይ ቢሮዬ ድረስ መጥታ ዓላዛር ዋሽንግተን የተባለ አገር እንደገባ (እኔ *ባለገ ነው* ያምለው) ስትነግረኝ ለደቂቃዎች ፈዝዤ ቀረሁ::

ፀሐይ ሁለመናዋ ተለዋውጦአል:: ሰፋፊ አይኖቿ ውስጥ ያየሁት ሰንባ ብቻ ሳይሆን ጩኸት ነው:: ወደ ቢጫ የሚወስደው ቀላቷ ጠይም ሆኗል:: ሁለመናዋ ልክ አይደለም:: እንድትቀመጥ ስነግራት *ምኑን ተቀመጥኩት* አይነት እጆችዋን አራገበች:: በጥቂት አመታት ውስጥ እናኑን ሮዛን አሁን ደሞ ዓላዛርን:: እጆቿን ፊቷ ላይ አድርጋ የሚንቀጠቀጡ ጣቶቿን ለመቆጣጠር ቡጢ እየሰራች ትለቃቸዋለች:: ከላይዋ ላይ እተቀመጥኩበት የሚደርስ ደስ የማይል ጠረን ይሸተኛል::

«መቼ ሰማሽ?» አልኳት

«ከትናንት ወዲያ:: ዛሬ ብርሃን ደውሎ አረጋገጠ:: ደሞ ፀናዕል ጋ ነው የሄደው አሉ:: መጥቼ ብነግርህ ምን ያደርጋል:: ደሞ እግሬን አመመኝ»

«ምን ሆነ እግርሽ ደሞ?»

«በቃ የመቅረቱን ወሬ እንደሰማሁ ተሳሰረብኝ:: የብርሃን ንጭንጭስ»

ትክክለኛው የማውቀው ሊረብሽ የሚቃጣ ድምፅዋ የለም:: ወደ በግ ተለውጣለች::

«አሁን አታስቢ:: ደሞ የሚያውቀው ሰው ጋ ነው የሄደው:: አሁን ግቢና እረፊ:: አታስቢ:: ገላሽን ታጠቢ ደሞ:: ልብስሽን ለውጪ:: ይመጣል:: ጉርምስና ነው:: ጤና ካልሆንሽ እንዴት ታይዋለሽ»

እያታለልኩዋት እንደሆነ ይገባኛል:: ራሴንም እያታለልኩ እንደሆነ ይገባኛል:: በዝምታ እየተያየን ተቀመጥን::

«ራስሽን አትጣዪ:: ልጅ አይደለም:: ፀናዕል ደሞ ጥሩ ልጅ ናት:: ከብርሃን ጋር ምን ያገናኝሻል:: ምግቡን ስሪ ልብሱን እጠቢ:: ቤቱ የአንቺም ነው:: እሱም እኮ ተጎድቷል:: ከረበሸሽ እኔ ጋ ነይ:: ቤቴ ሰፊ ነው:: አውቃለሁ ብርሃንም ያለአንቺ አይንቃነቅም:: ጊዜውን በትዕግስት ማለፍ ነው:: አደለ?»

ተነሳሁና እቆመችበት ሄጄ አቀፍኳት:: አናቷን ትከሻዬ ጋ አድርጋ ማልቀስ ጀመረች:: ዕንባ የላትም:: ብዙ ጊዜ አቅፌአታለሁ:: የሮዛን ሽቶ ስለምትጠቀም ጠረንዋ የሚጥም ነበር:: አሁን ሁለመናዋ ይቀረናል:: ለቅሶዋ ጋብ ቢል በሰፊ ድለላ ቤቷ ገብታ እንድትተኛ ነገርኳት:: እየተናፈጠች ወጣች::

ዓላዛርን እንዳትቀር ብዬ ብቀልደውም፣ ይቀራል ብዬ አስቤ አልነበረም:: ሳወራው ጊዜ ለመፍጀ፣ ስፅፍለት ደሞ ወረቀት ለመሙያ ያወራሁት ካልሆነ:: አገር ደሞ በኩርፊያ አይለቀቅም:: በኩርፊያ ብዛትማ ቢሆን ስንቱ አገር ባዶ ይሆን ነበር:: ዩሰው ልጅ እንዲያ አይደለ? ማንም የትም ያለ ይኖራል፣ ያኮርፋል፣ ይናደዳል:: አያስደድም:: ስደት ቀጥታ ሞት ስላልሆነ ቀላል ይመስላል:: ቆሞ ሁሉን እያዩ፣ እየሰሙ፣ እያሸተቱ መሞት ነው:: ትንሽ ቆይቼ ዘከዝኬ እፅፍለታለሁ::

ከመሃል ደሞ እኔ የማላውቀው ያልነገረኝ ልክ እንደ አልማዝ አይነት ጉዳይ ከፀናዕል ጋር ቢኖረውስ? አልኩ::

ቢሆንስ እንዴት ወደ ዘረኛነት ይሄዳል? ከጆርጅ ቡሽ መንግስቱ አይሻለውም? ጆርጅ ቡሽን ማን መልካም ሰው ነው ብሎ መረጠለት?

ፀሐይ ከዛ ቀን ጀምሮ ባገኘችኝ ቁጥር ታለቅሳለች:: የግል ጉዳይዋ አደረገችው: 'አልወልደውም:: ግን እናቱ ነኝ:: እህቱ ነኝ:: አሳዳጊው ነኝ:: ይወደኝ ይመስለኝ ነበር' ትልና እዬዬዬዬ:: እሷን ማባበል ደከመኝ::

•
•
•

ዳገቱን ወደ ማርያም እየወጣሁ ነው:: ምናልባት ያልታደሉ እኚያ ንግሥት ጣይቱ በዚህ አልፈዋል:: ከተማቸው ግን ጨልማለች:: ነጋ ጠባ ነገረኞችና ወሬኞች እሳቸው በቀደዱት ጎዳና [redacted] አዋቂ ይመላለሳሉ:: የሚያውቁት ከኩበት ቢቀልም አንጀባቸው ከባድ ነው:: ደግመው ሰልሰው በአሉባልታ ወገሩኝ:: በአልተጠቀምኩበት አሙኝ:: እንደ ጣኦት የማያት ሰፈሬን ዐይኔ [redacted] አፈረሷት:: 'ሸወዳት' ይላሉ:: እንዴት ብዬ? ማከዳን ለመሸወድ አንጀቱ ከየት አለኝ? ልቡስ? ሁሉን አንጠርጥረው እንደሚያውቁ ሁሉ ተራ ድምጻሜ እየተቀባበሉ በማይደክመው ምላሳቸው ጠበሱኝ:: አልመክት፣ አላያቸው:: 'እንዲህ ይሉሃል' ሲሉኝ ይመጣሉ:: ራሳቸው ብለውኝም ይሆናል:: አብረው ሲሉ ቆይተው 'መዋረዱን ካልሰማው እንዲሰማ እስኪ እንንገረው' ብለው ይሆናል:: ያልገባኝ ስመስል በሽሙጥ ይጋረፋሉ:: ውሽታሞች ናቸውና በፊት ለፊት አይመጡም:: *'አገር አጥፊ' 'አባላጊ' 'ጥጋበኛ' 'ወራዳ' 'ያማናውቅሽ መሰለሽ' 'ጉደኛ' 'የአንዳንዱ [redacted] እኮ' 'አያፍርም?' 'ይሄ ሶሻሊዝም እያሉ ያላመጡብን ጉድ የለም' 'የጉድ አገር' 'ደም ሰው ነኝ ብሎ' 'እሱ ደም ሰው ነው?'* ብዙውን ለምን እንደተባልኩም አይገባኝም:: የማይገናኘውን እንዴት እንዳገናኙት እንጃ:: የማይገናኝ አገናኝተው ሲያወሯቸው ሳይተነትኑ የሚያራግቡትም ይገርማሉ:: የሆነ ሰው፣ ሁሉን ስድብ የሚያቀናብርላቸው ይመስላል:: ሳልወድ በግድ ቀድሞ ከተናገርኩዋቸው አስራ አንድ ጉዳዮች ጋር ማያያዝ ነበረብኝ:: ቢዝነሴን ለማዳከም የሰነዘሩት አስራ አንድ ምክንያት አልሰራ ሲላቸው ይሄን ከማከዱ የደረሰብኝን ጉዳይ ወደ ማይመለከተው አቅጣጫ እስከመጨረሻው በመለጠጥ አስራ ሁለተኛ ሊፈጥሩ መሰለኝ......

ከፊት ለፊቴ እንድ ቀጫጫ ልጅ ጎንበስ ብሎ አስፋልቱ ጠርዝ ላይ ጀርባቸው የተላጠ ሁለት የቁልቋል ቅጠሎች ያነጥፋል:: ከሁዋላው ሁለት ልጆች እየተንቆራጠጡ ይስቃሉ:: አንደኛው የቁልቁዋሉ ቅጠሎች ላይ ሁለት እግሮቹን ገጥሞ [redacted]ቆመ ሌላው ልጅ ከኋላው ገፋው:: የቆመው ልጅ ቁልቋሉ ላይ እንደሆነ መንሸራተት ጀመረ:: እኔ ጋ ከመድረሱ በፊት የቁልቁዋሉ ልፋጭ አለቀና መንሸራተቱ ቀርቶ ተደናቅፎ በአደገኛ ሁኔታ መውደቅ ጀመረ:: ከአስፋልቱ ወጥቼ ወደ ቀኝ ልታጠፍ ስል እየጮኸ በእኔ አቅጣጫ መጣ:: 'ጋሼ እዝራ!' 'ጋሼ እዝራ!' እያሉ ልጆቹ ይጮሃሉ:: ልጁ በግራ በኩል በወገቤ ከፍታ በአየር ላይ

እየተንሳፈፈ አለፈ:: ዞር ብዬም አላየሁ:: ከፈለገ በዚህ አይነት ስልት እየበረረ ለገሃር ደርሶ ከባቡር ቢጋጭ ግድ የለኝም፣ እዚሁ በአፍጢሙ ተደፍቶ አፈር ቢዝቅ፣ ግንባሩ በአለት ቢፈነከት ግድ የለኝም:: በአፍጢሙ ተተክሎ ሳር እንደ ከብት ቢግጥ ግድ የለኝም:: ገና መሬት ሳይነካም በአየር ላይ ፍሊት እንደመታው ዝንብ ቢፈነዳ ግድ የለኝም:: ከክሊኒኩ የብሎኬት ግድግዳ ጋር ተላትሞ አናቱ እንደ ሽልጦ ቢጠፈጠፍ ግድ የለኝም:: እንዲህ ሄዶ ቦይ ውስጥ ቢጠፋና እንደ መድፌ ተፈልጎ ባይገኝ ግድ የለኝም:: እንዲህ በአየር ላይ እያለ ሽንቱን ራሱ ላይ ቢነሰንስ ግድ የለኝም:: እንዲሁ እየበረረ በዛው ሃዲድ ተከትሎ ጅቡቲ ደርሶ የስደተኛነት ደብዳቤ ቢያስገባ ግድ የለኝም:: ባብኤል መንደብ መሃል ወድቆ የአሳ አጥንት በጉሮሮው ቢገባ ግድየለኝም:: በአየር ውስጥ እንደ አሞራ ላባ አብቅሎ እንዲህ እየበረረ ዕድሜውን ቢጨርስ ግድ የለኝም:: ለብዙ ነገር ግድ የለኝም:: እንኩዋን እኔ ታላቁ ፈጣሪ በበቀል ያምን የለ? ሳያፍር *የበቀል አምላክ ነኝ* ይል የለም? መዝሙረ ዳዊት በምዕራፍ ዘጠና አራት በቁጥር አንድ *እግዚአብሄር የበቀል አምላክ ነው፣ የበቀል አምላክ ተገለጠ* ይላል:: ይሄ የምናከብረውና የምንፈራው የምንወደው የበቀል አምላክ በአፉም በድርጊትም ይረግማል:: ድርጊቱ ቢያቅተኝ: አብሬው እላለሁ በአፌ: *ሞት ይምጣባቸው:: በሕይወት ሳሉ ወደ ሲኦል ይውረዱ* እላለሁ:: *ክፋት በማደሪያቸውና በመካከላቸው ነውና* ይገባቸዋል እላለሁ:: ለብዙ ነገር ግድ የለኝም:: ለማስረጃም ከራሱ ከቅዱስ መጽሐፍ የእርግማን ቅኔ እዋሳለሁ:: በዚህ የሚያማኝ ካለ *መጀመሪያ የሚያመልከውን መፅሐፉን ይማ::*

•

•

•

ቤቴ በነጠላ ጫማ እዛ እዛ ስልና ስጠጣ ከሌሊቱ ስምንት ሰአት ይሆናል:: ትናንት ከትናንት ወዲያም ስራ አልሄድኩም:: ጌታቸው ራቴን ጥብስ ልኮልኝ ከድልሁ በስተቀር ምንም አልበላሁም:: ትሪው የተከደነበት እፊያ ምን እንደነካው እንጃ፣ ተንሸራቶ ወለል ላይ ወደቀ:: በረገግኩ:: የእቃው መውደቅና እኔም መበርገጌ አስቆጣኝ:: በጥልቅ ከተቆጣሁ ብዙ ጊዜዬ ነው:: ለብቻዬ እየተነጫነጭኩ፡ ከዚህ ሰፈር ስለመሄድ አሰብኩ...... ከዚህ ከአዲስአባ......ኅፍሴ እስክትበረታ ከዚህ ጣጣ መውጣት......እያልኩ ዓላዛር ትዝ አለኝ:: 'መውጣት' የሚለው ቃል ኮርኩሮኝ ይሁን እንጃ...... ዓላዛር ቢኖር ለዚህ መልስ ነበረው:: ዓላዛር አሜሪካ ከፀናፅል ጋር ነው:: ድሮም *እሷ ትወድሃለች* እለው ነበር:: ለምን ሄደ ግን? ያልኩት ትዝ ይለው ይሆን?

•

•

•

*ስደትና ባልትና:* መቼ ዕለት ፀሐይን አግኝቼአት ለነዓላዛር በርበሬ ልትልክ እንደሆነ እያማረረች 'እንዴት ነው ሰው ወደ በርበሬው ይመጣል እንጂ በርበሬው ወደ ሰው ይሄዳል?' ብላ አለች:: ነገረኛ:: አባቱን ባይወደው እንኩዋን፣ የእናቱን መቃብር ለማየት አይመጣም? እንዲህ ስትል በርበሬና ሽሮ ለማዘጋጀት እንዳልፈለገች ይገባኛል:: የገረመኝ የእሱን 'ወደ አሜሪካ ማቀጣጠን' ወጣቶች በሙሉ መደገፋቸው ነው:: ለምን? ቸርነት እንኩዋን ሰገሩን ይወዳል የምለው 'አሪፍ አደረገ' አለኝ:: ለምን? አልኩት 'እንዴ እዚህ ይደበር እንዴ?' ምን ማለት ነው? ይሄ ምኑም የማይገባኝ ግልፅ ያልሆነ መልስ ነው:: ከፀሐይ በስተቀር 'እንኩዋን ቀረ' ያላለ የለም:: 'ለምን?' ስል 'ይሄ አገር ተበላሽቷል::' 'እንዴት?' ስል 'ምን ማለትህ ነው?' 'እያወቅህ ምን አውቀህ ትተኛለህ?' 'አላውቅም' 'እዝራ ምን ሆንክ? ሌላ ጨዋታ አምጣ:: ኢሡፓ ሆንሽ እንዴ?' አባባላቸው በሃሳብና በመረጃ ሊፈታ የማይችል፣ ብልጦች ያበጁት መንጋ የተሰባሰበበት ክርክር ነው::

ይሄ ሁሉ ምን ማለት ነው? ይሄ ሁሉ ደደብነት ብቻ አይደለም:: አሁን ሲገባኝ ገበያም ነው:: ከሆቴሌ ጀርባ ያለውን መጋዘን አፍርሼ በርበሬ ሽሮና ቆሎ መሳኪያ ቦታ ለማዘጋጀት ሁኔታውን ለማጥናት አንድ ማታ እርሳስና ደብተር ይዤ ተቀመጥኩ:: የሆነ የወንጀለኛነት ስሜት ተሰማኝ:: ለስደት ያጨበጨብኩ መሰለኝ:: *ቾግኝ ራሱን ከነባር አፈሩ ተነጫንጮ ከነቀለ እኔ ምን ቸገረኝ?* የሱቁን ስም 'እናኑ' (አባቴ ስለ እሳቸው ያወራ ስለነበር)፣ ወይ 'ጣይቱ' እለዋለሁ (ከሆቴሉ በላይ ባለው የእግር መንገድ እቴጌ ጣይቱ ማርያምን ለመሳለም በበቅሎ ይመላለሱበት ነበር):: 'ሮዛ' ለማለት አሰብኩና 'ልጁ የረሳትን እሱ ምን ገዶት በስሟ ሱቅ ከፈተ?' እንዳልባል ተውኩት:: እቅዴን ዘርዝሬ ከአዘጋጃጀሁ በሁዋላ በደንብ ተኛሁ:: የነቃሁት ጠዋት ሶስት ሰአት ላይ ነው::

•

•

•

*ንብ:* ከአንዲት ያልታደለች ንብ ጋር እንዲህ ተገጣጣጠምን:: *ፍፃው ምን ይሆን?*

አንድ ማታ ሰራተኞች ሁሉ ወደ ቤታቸው ሄደዋል:: እኩለ ሌሊት ሊሆን ጥቂት ደቂቃዎች ቀርተውታል:: ቤቴ ሂጄ ለመተኛት ከመቀመጫዬ መነሳት አለብኝ:: ከመቀመጫዬ መነሳት ደክሞኛል:: መብራት አጥፍቼ ጠረጴዛዬ ላይ ያለውን ሻማ ለኩሼ፣ በኸርጉርጉር ድባብ ውስጥ ለማረፍ እጥራለሁ:: እንዲያናውዘኝ የውሸቴን አይኖቼን ከድኜ ለዘላለም የማውቀውን የሆቴሌን ፀጥታ እያዳመጥኩ ራሴን አባብላለሁ:: እንዲህ እንዳለሁ በድንገት ብቅ ያለ ለሰከንድ የቆየ ድምፅ አባነነኝ::

አይኖቼን በቀስታ ገለጥኩ:: የማየው ፅጥታ ነው:: ግራና ቀኝ አይቼ መልሼ ልጨፈን ስል ድምፁን ደግሜ ሰማሁት:: ምን እንደሆነ አልጠፋኝም:: በተዝጎረጎረው አየር ውስጥ ሲነዛዛ ቆይቶ የሆነ ቦታ አረፈ:: ትክክለኛውን ቦታ ለማግኘት በማቀዴ ድካሜ ለአፍታ ራቀኝ:: ከተቀመጥኩበት ስማተር ከጥቂት ፍተሻ በሁዋላ በስተግራ ግድግዳ ላይ ለብስክሌት ውድድር ዕለት ስታድዮም አጠገብ የተነሳሁት ፎቶ የገባበት የእንጨት ቢጋር ጠርዝ ላይ ደቃቃ ጥንግ መስሎ ተቀምጦአል:: ድምፁ በእርግጥ ከእሱ እንደመጣ ለማረጋገጥ አይኖቼን ሳልነቀል በትዕግስት ጠበቅሁት:: ብዙ ሳይቆይ ንቡ ከኮርቻው ላይ ተነሳና መንዛዛት ጀመረ:: ድምፁን እሰማለሁ እንጂ ላየው አልቻልኩም:: ክፍሉ ውስጥ ሲዞር ቆይቶ ቀድሞ የተቀመጠበት ቦታ ምናልባት አንድ ሳንቲሜትር ፈቀቅ ብሎ አረፈ:: ሳቄ መጣ:: ከተቀመጥኩበት በቀስታ ተነሳሁ:: መብራት ሳበራ ብሞክር ዳናዬ የሚያስደነብረው ስለመሰለኝ ለአፍታ ቆሜ አየሁት:: ወንበሬ ላይ የማስቀምጠው ቂጤ የሚያርፍበት የተጠፈጠፈ ትራስ አነሳሁና ወደ ፎቶው አቅጣጫ ወረወርኩ:: ለምን እንደወረወርኩት እንጃ:: አንዳንድ ነገሮችን ያለምክንያት እንሰራለን:: ትራሱ ፎቶውን በስፋት መታውና ነጥሮ እንግዳ መቀበያው ወንበር እግር ስር ወደቀ:: ያኔውኑ የሻማው ብርሃን ጠፋ:: ቢሮዬ እንደዛ ጨለማ አይመስለኝም ነበር:: ከቆምኩበት እየዳበስኩ መብራት ለማብራት ወደ በሩ ሄድኩ:: የሚጣፍጥ ሽታ ሸተተኝ:: እሱን እያነፈነፍኩ መብራቱን አበራሁ:: የግድግዳው ላይ ቢጋር ፎቶውን እንዳቀፈ ሳይወድቅ ይነቃነቃል:: መስታወቱ ላይ የስብራት ሸንተረር ይታየኛል:: አንደኛውኑ ተሰባብሮ አለመውደቁ ገርሞኛል:: ወደ ጠረጴዛዬ ተመልሼ ሻማውን ልለኩስ ክብሪት ለማውጣት የጠረጴዛውን መሳቢያ ሳብኩና ቀና ብዬ ሻማውን አየሁ:: እቀለጠ ሰም ውስጥ አንድ ንብ ትፈራገጣለች:: አንድ ክንፏ የለም:: በዝምታ አየሁዋት:: እያየሁዋት መፈራገጥዋን አቆመች:: ሻማውን አነሳሁና ወደ ቆሻሻ መጣያ ወስጄ ዘንበል አድርጌ ንብዋንና የቀለጠውን ሰም ደፋሁቀቸው:: የሻማውን ሰንደቅ እቦታው መልሼ ስቀመጥ ወንበሬ ጉድጓድ መሰለኝ:: ትራሱን ከወደቀበት እንዳላነሳሁት ትዝ አለኝ:: ተቀምጬ የማረፍ ምኞቴ ሞተ:: ትራሱን ከወደቀበት ሻላንላ በር ዘግቼ ወጣሁ:: ዋናውን የሆቴሉን በር ስቆልፍ ዳገቱን ተከታተለው እያዘገሙ በቀስታ የሚሄዱ ሰዎች ጋር ተያየን:: ማን እንደሆኑ አላውቅም:: ተራ በተራ ሰላም ሰላም አሉኝ:: ሰላምታ ለማለት ሞከርኩ:: ከአፌ የወጣ አይመስለኝም:: በችኮላ እየተራመድኩ ቤቴ ልገባ እለፋለሁ:: አልማዝ ቤት ጫጫታ ነው:: ግቢው ተዘግቷል:: ለአፍታ ንብ ገድዬ እንደማላውቅ ትዝ አለኝ:: ገድዬ ሊሆን ይችላል፣ ግን እንደዚህ ድራማ አልነበረውም:: ትዝ የማይለኝም ድራማ ስላልነበረው ይሆናል:: ንቡ ያለቦታው ለምን መጣ? ቀፎው ውስጥ እያለ

ብገለው ኖሮ ወንጀለኛ እሆን ነበር። እኔ በማርፍበት ቦታ መጥቶ ለመንዛዛት ማን ፈቀደለት? አስገራሚ የሆነብኝስ ንቡ በራሱ ልጅ መገደሉ ነው። ንቡ ሰምና ማር ይሰራል። የእሱ ውላጆች ናቸው። በቀለጠ ሰም ውስጥ ገብቶ መሞት ራሱን ከራሱ መከላከል አለመቻሉ ውጤት ነው እንጂ የእኔ ትራስ ገሎት አይደለም። ሽፍጠኛ ክርክሬን እያሰላሰልኩ ቤቴ ገባሁ። ትርጉም አለው? ትርጉም ካሌለው ለምን አብሰለሰለኝ? ከግማሽ ሰአት በፊት ሰላማዊ አሁን ገዳይ ከሆንኩበት ሁኔታ ምን ልማር ነው? ምን ሊታየኝ ነው?

•

•

•

ማታ ከተኛሁ በሁዋላ ድንገት ሰው የጠራኝ መሰሎኝ ስባንን ለጥቂት ጊዜ ቤቴ በማዕበል ተመቶ ያገኘሁት መሰለኝ። ፀጥታው ጥልቅ ነው። በዚህ ፀጥታ ውስጥ የስሜ የመጨረሻዋ የማሚቶ ሽራፊ ሞት ወለል ላይ እንዳረፈ እሳት ራት ስትላወስ እሰማታለሁ። ከወገቤ በላይ አልጋዬ ውስጥ በጨለማ ቁጭ አልኩ። ትራሴ ስር ያስቀመጥኩትን ማከዳ የገዛችልኝን ከራቫት ዳብሼ አወጣሁ። የማከዳን ቆዳ የምነካ ይመስለኛል። ፈሪምባዋ ላይ ያለውን ለስላሴ። ጠረኗ ጨርቁ ላይ ቀርቶ እንደሆነ ብዬ ወደ አፍንጫዬ እወስደዋለሁ። እንዲህ ጎንበስ ብዬ ሳሸት ድምፅዋን የሰማሁ ይመስለኛል። የእግር ዱካ እንደሚከታተል ሰው የራስጌ መብራት አበራሁ። ለረጅም ጊዜ ከድምፁ ጋር ቀጠሮ እንዳለኝ ሁሉ ጆሮዎቼን ከፍቼ ጠበቅሁ። በሌሊቱ ቅዝቃዜ መጠናቸው የሚጨማደድ ቁሶች ሲንጣጡ እሰማለሁ። መብራቱን ቀጭ አድርጌ ሳጠፋ ልክ ከቀጭታው ጋር ማከዳ ተደርባ ስትጠራኝ የሰማሁዋት ይመስለኛል። የእጄ ጣቶች በማብሪያና ማጥፊያው ቂንጥር እየተጫወቱ ጨለማ ውስጥ ደግሜ ጆሮዬን አቆምኩ። የተሰማኝ ድምፅ ስለአልነበረ በድካም አልጋዬ ላይ ተንጋልዬ ተከናነብኩ። *ማከዳ የት ነሽ? የእኔ መረቅ የት ነሽ?*

ተርብ ቻቻን በመኪ። ተቀ፦ር ፈር ጀማባሴ።

# ማከዳ፡ 'ሰዶ ማሳደድ ሲያምረኝ'



ጥርሶቻችን በመከ[illegible] ጥቁር [illegible] ይሞላሉ።

## የእውጥ ልጅ

የእግዜር መዳፍ ሰፋት አንድ አገር ያክላል:: ባላየውም ልገምት (ለሰው ልጆች የሰጠን አንዱ ስጦታ መገመት ነውና እሱን ራሱን ብገምተው ይከ'ፋ'ብኛል?):: ከዕለታት አንድ ቀን ገነት መሃል ሲዘዋወር አደናቅፎት ይወድቅና በሁለቱም እጆቹ እንስሳት፣ አፈርና ተክሎች ጧጠና ጨብጦ ይነሳል:: በልብሱም ተንቀሳቃሾችና በራሪ ነፍሳት ይሰበሰባል:: ቤተመንግስቱ ከመግባቱ በፊት እጆቹንና ልብሱን ለማፅዳት ሲያራግፍ፣ የሰበሰባቸው ነፍሳትና ግኡዛን ነገሮች የወደቁት እወዲህ ነው:: ዛሬ ሰፈሬ ናት:: ሰፈሬ የገነት እርጋፊ ናት:: ባላገር በመሆኗ የማታፍር፣ ከተማ ከተማ በመሽተቷም ጉራ የማትነፋ አመቱን ሙሉ በአረንጓዴ የተሸፈነች፣ በመተ'በይ የሚነገርላት፣ እንደ ጣእትም ብትመለከ ቅር የማይል......ለዚህ ነው እንደዛ እንደተወለድኩባትና እንዳደግሁባት ያለ የሚያምር ቦታ ቢኖርም ያለ የማይመስለኝ......ግራና ቀኝ የሚተላለፉት እግረኞችና ባለመኪኖች ቸል ብለው ሲያልፉዋት፣ በልቤ *ከዚህ የበለጠ ምርቃት የት አለና የት ይሄዳሉ?* እል ነበር::

......ወንዛችን ሲጠራ ጥል'ቆሽ ከምንጫወትበት ከአሂራቱ ገደል ላይ ከሚንቦገቦጉት ነጫጭ ጥዋማ አበቦች ወሰላ ባይጠቡ......ከተንዠረገገ ቅርንጫፍ ላይ ተንጠላጥለው ከተፈጥሮ ኮሽም ባይዘረፉ......የረግረግ ቄጤማ እየኮረኮራቸው ቀልቃላ እግሮቻቸውን ባያበርዱ.....

ፈራጅ አይደለሁምና አልፈርድባቸውም::

......ከጊላዎች ጥላ ስር እሽቅድድሞሽ ባይሮጡ......የምሽታችን መንገድ ዳር በትላበራ መንቆጥቆጡን ባያዩ......(በልጅነትም ድፍረት እነሱን ከጥሻ ውስጥ ለቅመው መዳፋቸው ላይ አስቀምጠው በሚያምር አረንጓዴ ቢጫ ፍማቸው ባይመሰጡ......የብብታችን ዲአዶራንት የመስቀል ወፎች ግሳት መሆኑን ባይደርሱበት......ከደረቅ የባሕር ዛፍ ቅጠሎች የቀመርናቸውን የፉርቴዎቻችንን እንጉርጉሮ ባይሰሙ......

አልኖሩበትምና አልፈርድባቸውም::

......ሽንሽን ቀሚሴ ላይ አለማየሁ (ዛሬ የት እንዳለ እንጃ)፣ ቴዲ (እሱም የት እንዳለ እንጃ)፣ ኢዮብ ቦርዴ (ብሄራዊ ውትድርና ዘምቶ ቦርድ ሆኖ እያነከሰ አራት ኪሎ የሚዞር) እና መድህን (የቸርነት ትንሽ ወንድም) በአይኖቻቸው፣ በልፊያቸውና በቃላቸው፣ በጭቃና በአፈር የፃፉዋቸውን ለእኔ ብቻ የሚገቡኝን የመውደድ ሆሄያትን ባያነቡ......እስራ ምንትስ በጋ የሞላቸውን ጡቶቼን ሳፋፋ፣ ገደል ወርጄ በቀበጥባጣ የውሃ እናት የእነሱን ፍንጭ ሳስነክስ ባያዩ......

ፈራጅ አይደለሁምና አልፈርድባቸውም::

......ነጫጭ እንጉዳዮች እፈኩበት ቀልዛም ረባዳ እግሮቻችንን እንፈራጠን ያታችንን ስናወዳድር አብረውን ባይፎካከሩ......በቀዝቃዛ ጎሕ፣ ዋኖሶች ቤቴ ቆርቆሮ ጣሪያ ስር ካደፈጡበት ኩኩ መለኮቴ ኩኩ መለኮቴ ሲሉ ባይሰሙአቸው......እናቴ ባማረች ትንሽ ዕውቀቷ ከሰራችልኝ የቀበሌ ፓስታ ጋር አውጦች ደብቄ ስበላ......አፌ ውስጥ በጉንጉኖቹ መሃል እየፈረሱ ሲያስቁኝ ባይታዘቡ ('አውጥ አስገብተሻል እዛ፣ ይህቺ ጥጋበኛ?' እያለችኝ እማማ)......የሌሊቱ የሚያሳዝን አርምሞ በጅቦች እሙኝ (እሙኛቸውም ያሳዝነኝ ነበር) ሲታመስ፣ እናቴ ዘልዛላ ጡቶች ስር ይህቺ የአስር አመት ልጅ ስትሰበሰብ ባያዩ......

አልኖሩበትምና አልፈርድባቸውም::

......በቀጭን አልቃሻ ሐምሌ ልብሶቼን በዝናብ ሳበሰብስ፣ አገውኛ ባልረሳ፣ ጆሮ በሚከብድ ጎጃሜ አፉዋ: 'ነግሬሻለሁ፣ የደረቀ ጨርቅ የለሽም በሁዋላ አሪቅሽን እንዳትሆኚ' እናቴ ስትለኝ ባይሰሙ......ቤቴ ፊት ለፊት ካለ መስክ እንደ ዕንቁ በፈሰሰ የጤዛ ባሕር ላይ ስሜን በእግሮቼ እየፃፍኩ......የቅጠሎችንም ወዝ እያራገፍኩ ስፈነጥዝ ባይታዘቡ ......በግቢዬ የአጥር ደርዝ ታከው ከፈነዱት ፅጌሬዳዎች ንብ ከሳመው ማዕከላቸው የፀደይ ዱቄት ሲቦንብኝ ባያዩ......

ፈራጅ አይደለሁምና አልፈርድባቸውም::

......በትንንሽ እጆቼ ጥሬ ሽምብራ ይገፔ ለሜዳ አደር ቡላል መጋበዜን ባይመሰክሩ......በመንገዳችን ዳር ዳር የበቀሉ ሳሮች መሃል ተቀምጠን እየተንጫጫን 'ሻ' ብቻችን' እየተጫወትን......ከሰማይ ጠንፍ የፍቅር ጨረር ስንሰበስብ ባይመዘግቡ......(በተፈጥሮ ውበት ውስጥ መቅለጥ......በዘራችን የመጣ ሳይሆን ይቀራል?)......በመጸው የነፋስ ስረገላ ተሳፍረው ከኮረብታው የወረዱ፣ ለጎፈሪያችን ኮኮብ የሆኑ በራሪ እፉዬዎችን፣ በአስፋልታችን ጥቁር ድግ ላይ የሚንከረባበቱን የቅጠሎች ሹክሹክታ ባይሰሙ......

አልኖሩበትምና አልፈርድባቸውም::

ግን

እዛ ቤታችን ከተሰራበት አምባ ዝቅ ብሎ ካለው ቁልቁለት ደረት ላይ ተጎልቼ በመስኮት መኪና ውስጥ ተቀምጠው በጨረፍታ የማያቸው ምኞት ያሳመራቸው ቀይ ዳማ ልጃገረዶች ነበሩ:: እንዲህ ሳያቸው እነሱን ለመሆን ተመኘሁ:: በዛላቸው ቀናሁ:: ቀለማቸው አማረኝ:: ስመኝና ስቀና የራሴን ትንፋሽ ስንቅ......አስራ አምስት ያልሞላት ደረቴን ተባዕቶች ሽተው የምበስልበትን ቀን ላለመርሳት አብዮታዊ ካሌንደራቸውን ዘርግተው በልቦናቸው እያሰላሰሉ አሴሩ......

እነሆ

እንዲህ ሲሆን......እግዜር በሰጠኝ አውጥ የሚቀኑ እንዳሉ አልገባኝም ......በጨረሬ ንጣት፣ በሳሬ ቀለም፣ የሚበሳጩ እንዳሉ አላወቅሁም...... መንገዳቸው ጠመዝማዛ አይኖቻቸው ፈጣጣ፣ ቀጣፊ ምላሶቻቸው እንደ ስኳር የጣፈጡ፣ እግሮቻቸው ቀልጣፎች እንደሆኑ መች ገባኝ......የተነፈ-ስኩትንና የጠጣሁትን ዘነጋሁ፣ ያቀፍኩትንና ያረጠበኝን ረሳሁ፤ ውበቱንና ጥቅሙን ካድኩ......

እናም

እንደተመኙት ደረስኩላቸውና......ሆ! አሉ:: *ሆ! ብለው መጡ ሆ! ብለው ማከዳ አለች ብለው......*

እንዳሰላሰሉት ሆነላቸው......የሰፈሬን ማር ማር የሚል አየር በሰበሰብኩበት ማሕፀኔ እንቅፋታቸው ደረቅ ግንቡን ሰራ......

ምናለ ያሳለፍኩትን ለሚሰማኝ ከ 'ሀ' እስከምንትስ በአጭሩ *እነሆ* ብል?......

ሳጋንን አይደለም......ነገር ነገር ብሎኝ አይደለም......

## የጀመርኩት

እንግዲህ ራሳቸው ሲነግሩኝ ነው:

አባቴ ወንድወሰን ሞጆ እና እናቴ ማልደያ መሳከ የተዋወቁት እሷ አንድ ትልቅ የተባለ ዛሬ አብዮት የበላውና በሕይወት የሌለ ሻለቃ አለማየሁ የተባለ ሰውዬ ጋ ማድቤት ሰራተኛ እያለች ነበር:: እሱ ከላይ ከሉሉልታ ከሚመጡ ገበሬዎች እንጨት በርካሽ እየገዛ እዚሁ ሽሮሜዳ፣ ስድስት ኪሎና አራት ኪሎ በየቤቱና በየንግድቤቱ በአህያ ጭኖ እያዞረ ይሸጣል:: እግረ መንገዱን ወይም ሰበብ እየፈጠረ እማማ አለችበት ቤት እየተመላለሰ እረፍት አሳጥቶ አባበላት:

«አንቺ የራስሽን እንጀራ ትጋግሪያለሽ፣ እኔ ደሞ የምትጋግሪበትን እንጨት አመጣለሁ:: ለምን ለሰው ትሰሪያለሽ? ለሰው መስራት አይጠቅምም:: ባርነት እኮ ነው» ብሎ ማርኮ ከዛ ቤት ያወጣታል:: አፍ አለው:: አሁንም አፉ ጥሬ ይቆላል::

ትዳር መሠረቱ::

እንደ ተማከሩት ጠዋት ማታ ሰሩ፣ ለፉ፣ ሰሩ፣ ለፉ፣ የጠበቁት ዓይነት ሃብት ግን አላገኙም:: ይሰራሉ ከሆድ አያልፍም:: ቢያዩ ቢያዩ ያሰቡት ሁሉ አልሆነላቸውም:: ምን እንዳሰቡ እንጃ:: እኔ ከተስፋቸው ዘመን ነው የተወለድኩት:: እንደገናም እንደ ማንም ማጠፊያው እንደ ጠፋቸው አባትና እናት ተስፋቸውን እኔ ላይ ነበር የጣሉት:: 66 ላይ አብዮት ሲነሳ ቀን ያልፍልኛል በሚል መሰለኝ ወይም ምናልባት ሃብታም ላይ ቂም በመያዙ፣ አባቴ የሆነ ጊዜ አብዮት ጠባቂ ሆኑ:: የማውቃቸው አብዮት ጠባቂዎች ሁሉ ደሃ ነበሩ::

ችግር አይቼአለሁ:: በእግዜር እንድኖረው የተሰጠኝ የማልከራከረው ስጦታ እንጂ. ችግር እርግማን አይመስለኝም ነበር:: በለጋ ዕድሜዬ ጠራራ ፀሐይ ውስጥ ተቀምጬ፣ ሞርሙሮኝ ምን እንደምሰራ ጠፍቶኝ ያለቀሰኩበት ጊዜ አለ:: ዶፍ ዝናብ መሃል እግሮቼን ዘርግቼ ተቀምጬ የቆሸሸ ገላዬን እያከከሁ በማላውቀው ምክንያት 'እሪ' ያልኩበት ጊዜ አለ:: እናቴ አንዳንዴ እንደምትለኝ ፀባዬ የማይታወቅ ጠዋት የምስቅ ማታ

ማታ የማለቅስ ነጭናጫ ነበርኩ፡፡ ነው? የጠላ እህል ስታነኩር አፈር ጨምሬባታለሁ፡፡ አብሬአት መንገድ ዳር ቂጣና እንጀራ ለመሸጥ ስቀመጥ ወዲያ ወዲህ ማለቴ ለመኪና አደጋ የሚያጋልጠኝ ሲመስላትና ወደ እሷ እንድመጣ ስትጠራኝ በቁጣ ቂጣዋን አንስቼ ወደ መንገድ መሃል ወርውሬባታለሁ፡፡ እሱንም ማንም ስለማይገዛት ማታ ቤት ስንመጣ እንድበላው ታስገድደኛለች፡፡ ይሄ ችግር አይደለም? ለእንጀራ መጋገሪያ ቅጠል ጠረጋ እንጠጠ ስንወጣ እጅንያዋ ልትከት ያዘጋጀችውን የቅጠል ክምር ግራና ቀኝ በትኜባታለሁ፡፡ በዚህ ድርጊቴ እግሮቼንና ሌላውን ሁለመናዬን በልምጭ ተገርፌአለሁ፡፡ የእነዚህም ትዝታና የሚያስፈራራ ተስፋ ከንፈሮቼ ላይ እንደ ምራቅ ለጥፌ የምዞረውን አልቃሻነቴን ቀስቅሰውታል፡፡ ደሞም ይዞርብኛል፡፡ ከመቱኝ በኋላ ያቅፉኛል፡፡ ከመቱኝ በኋላ ሳጌን የምጨርሰው እማማ ጭን ላይ ነበር፡፡ አንዳንድ ጊዜ አባት እና እናቴን አስማምቶ ያስቀመጣቸው እኔን የመደብደብ የጋራ ፍላጎት ሳይመስለኝ አልቀረም፡፡ ከተመታሁ በኋላ የቦንዳ አልጋዬ ላይ ተጋድሜ ወደየት እንደሆነ ግን ባላውቅም፣ ከቤት መጥፋት የምመኝበት ጊዜ ነበር፡፡ ገና ስለመጥፋት ሳስብ እናቴ ትናፍቀኛለች፣ አባቴ ይናፍቀኛል፡፡ ከአልጋዬ ተነስቼ ራቁቴን እተኙበት እሄዳለሁ፡፡ ግራና ቀኝ ፈቀቅ ብለውልኝ ከመሃላቸው እጋደማለሁ፡፡

የአንደበት እጥረት እንደሆነ የገባኝ ከርሞ ከርሞ ነው፡፡ 'ጥሩ ልጅ እንድትሆኚ'፣ 'ባለጌ እንዳትሆኚ' ሲሉኝ ትርጉሙ አይገባኝም፡፡ ምን ሊሉ እንደ ፈለጉ ግልፅ አልነበረም ለእኔ፡፡ ሲነጋ ትናንት የተደረገው ይረሳኛል፡፡ እነሱም እንደ ረሱት ሁሉ ፊቴን ያጥቡኛል፣ ያለብሱኛል፣ ደብተሬን አዘገጃጅተው ትምህርት ቤት ይልኩኛል፡፡

ዕድሜዬ ከፍ ሲል ድብደባው ቢቀርም አፋቸው ተባብኝ፡፡

«የት ሄድሽ?» «እስከ አሁን የት ነበርሽ?» «ማነው ያ አብሮሽ የነበረው?» «ትምህርት ቤቱ የሚነበብም አይሰጥም? የምን ዙረት ነው?»

አንድ ቀን እንደተለመደው እማማና እኔ ጉልት ተቀምጠን ስንሸጥ ወንዶች በሙሉ ወደ እኔ እንደሚመጡ አየች፡፡ እሷ ትቁነጠነጣለች፣ አናቷን ታካለች፡፡ እኔ አልገባኝም፡፡ ብዙ እንደሸጥኩ በኩራት ሳወራት አልተደሰተችም፡፡ ከመሻሽ አንዳንድ ጎረምሳ ሰራተኞች ቆመው ጥቢኞቻቸውን እየገመጡ ወሬ ሊያዋሩኝ ሲቆሙ 'ወንድሞቼ ምን ፈለጋችሁ? ቂጣችሁን ይዛችሁ የለም?' እያለች አስደንግጣ አባረረቻቸው፡፡ ይሄ ሁሉ አልገባኝም፡፡ ማታ ቤት ራት ለመብላት ተቀምጬ እያለሁ ከኋላዬ መጥታ አንገቴን አቅፋ እናቴ መሃል ሳመችኝ፡፡ ድምፅዋን ዝቅ አድርጋ ከነገ ጀምሮ እሷ ብቻ ቂጣ እንደምትሸጥ ነገረችኝ፡፡ 'እምቢ' አልኩ፡፡

«ለምን?» አለችኝ

«ብቻሽን አይሆንም፣ እኔ ካለሁ ቶሎ ጨርሰን እንመጣለን»

«አትሂጂም፣ ትምህርትሽን ብቻ አጥኚ። ነገርኩሽ ስሚ!»

«እነቅሽኝ»

ስትለቀኝ ዞር ብዬ አየኋት። አይኖቿ እንባ አቅርረዋል።(አንዳንዴ ከመታችኝ በኋላ አይኖቿ እንዲህ ይሆኑ ነበር)

«ማሰብሽ ጥሩ ነው። ግን የማይገባሽ ነገር አለ። አሁን አድገሻል። እኔ አሮጊት ነኝ። ገባሽ?»

«አሪፍ እሸጣለሁ አደለ?»

«ስሚኝ! መጋገር ትረጂኛለሽ። እሱም አንድ ነገር ነው»

አተኩሬ አየኋት። ምክንያቷ ባይገባኝም ማምረሯን ግን ተረዳሁ። ውሳኔዋ ደስ ባይለኝም፣ አልተከራከርኩም።

እዚህ እድሜዬ ስደርስ በረኸኛ የልማድ ሂደት (እንዲዛ ነው የሚባለው አይደል?) ምክንያቱን ባልረዳም፣ ብጠራጠርም፣ የተነገረኝን ማዳመጥ፣ ማመንና መከተል ደንቤ ነበር። ቆይቶ ነው ከእናቴና ከአባቴ የተሻሉ ወላጆች ያላቸው ጓደኞች ሳገኝ በደንብ [redacted]ማልለብስ የገባኝ። በደንብ እንደማልበላም የገባኝ። በደንብ እንደማልጠጣም። በአለም ላይ ያሉ ብዙ ነገሮች፣ በገንዘብ የሚገኙት መልካም ነገሮች፣ የራቁኝ ፍጡር እንደሆንኩ ያወቅሁት በኋላ ነው። ግን አላማረረኝም። ገላዬን ቅዳሜ ቅዳሜ የምታጥበኝ እናት፣ ፀጉሬን የሚሰሩኝ ጎረቤቶቼ፣ በአስደንጋጭ መልኬ ተማርከው ወዳጅ የሚሆኑኝ ወንዶችና ሴቶች ብዙ ነበሩ። ከአስተማሪዎቼ አንድ እንኳን በክፉ የሚያየኝ አልነበረም።

አባቴ ኑሮው እንደፈለገው አልሆነለትም። ለእናቴም ባሏ እንደ ተመኘችው አልሆነላትም። እናቴ ተስፋ መቁረጥዋን ወይም ያልጠበቀችው ሁኔታ ውስጥ መውደቅዋን፣ እሱ እንዳይሰማትና እንደለመደው ክፉ እንዳይመኝ ተማራ ተናግራ አታውቅም (ይሄ ይሄ የሚገባኝ በሁዋላ ነው)። ቡና አፍልተው ትይዩ ተቀምጠው እየጠጡ አንዲት ቃል አይለዋወጡም። ምናልባት *ወዶኝ ነበር? አታሎኝ ነበር?* እያለች ሳታስብ አትቀርም። እሱም *ነዝንዝ ነዝንዝ አምጥቼአት ዕድልዋን አበላሸሁባት* ይል ይሆናል። የኑሮ ውጣ ውረድ የሚዋደዱትን በልባቸው እንዲተማሙና እንዲጠራጠሩ ሳያደርጋቸው አይቀርም። ገንዘብ *አብሰንት*[15] ከሆነ ፍቅርም ግራ በሚያጋባ መልክ ሊሻከር ይችላል። *ሰው ቤት ገረድ ሆኜ ብቀር ኖሮ ይሻለኝ ነበር* ያለችበት ጊዜ ይኖራል። የካሽ እጥረት አርቆ አሳቢነትን ሊሰ[redacted] ይችላል።

አባቴ ይቀናባት እንደነበረ ይወራል። እንደሚጠረጥራት ግን አልነበረችም። እናቴ በጣም ጨዋ ሴት እንደነበረች የማይመሰክር የለም።

---

[15] ባይኖር (Absent)

(ሁሉ በመስካሪ እኮ ነው። እንኩዋን በምድር በሰማይ ቤትም በመስካሪ ነው። ልብንና አእምሮን የሚመረምረው አምላክ እንኩዋን የሚፈርደው ከአቃጣሪ ሰምቶ ነው) እንጀራና ቂጣዋን የምትሸጥበት መንገድ ዳር ብዙ ወንዶች ከንግድዋ ሌላ ወሬ ሲያመጡባት አትናገርም። አትመልስላቸውም። ያኔ አይገባኝምና ጨዋ ያልሆነች ይመስለኝ ነበር።

በሌሊት ተነስታ ሽሎጦዋንና እንጀራዋን ትጋግራለች (ዕድሜዬ ከፍ ሲልና ገላዬ ትንሽ ሲበረታ ማምረቱ ውስጥ እኔም ገባሁበት)። ሊመሽ አካባቢ የጋገረችውን ለመሸጥ ታች መስቀለኛ መንገዱ ጋ ትቀመጣለች። ከከተማ መሃል በርተው የሚመለሱ ወንደላጤ የቀን ሰራተኞችና ከአዲስ አበባ ወደ ሱሉልታ የሚመለሱ ገበሬዎች በገፍ ይገዙአታል። ከአባቴ መከራረፋቸው የጀመረው 'ጠላ ቤት ልክፈት' ብላ የምትጠምቀው ጠላና ፊልቴር በአንድ ጊዜ ተወዳጅ ሆኖ ቤታችን ማለፊያ፣ መቀመጫ፣ መቆሚያ ሲጠፋ ነው። ሃብታም መሆን ጀምረው ነበር። አሁን ያለንበትን ቤት የሰሩት ከዛ በተገኘ ገንዘብ ነው (እሱ 'የመሸታ ቤት ብር' የሚለው)። ለአባቴ ይኼ የጠላ ቤት ነገር አልጣመውም። አለ አይደለ እንደሚባለው በቅናት የዕውነት ታመመ። እሷን ለማየት፣ እሷ ስታወራ ለመስማት ምናምን ወንዶች ሁሉ ሲመጡላት ደሙ ፈላ።

ትዝ ይለኛል፣ ያኔ ነፍስ አውቃለሁ። አንዳንድ ነገሮችም ይገቡኛል። ቢያንስ ስድብ ይገባኛል። አንድ ዕለት ተጣልተው። ስለ ጠላ ቤቱ ጉዳይ፣ ስለማላውቃቸው ወንዶች ሲነታረኩ ቆይተው፣ ከመሃል እጇን ጠምዞ ይዞ እየጮኸ መጥፎ መጥፎ ስድብ ሰደባት።

በድንጋጤና በፍርሃት ተይዤ አልጋ ስር ስወሸቅ፣ እሷ እጇን ከእጁ አላቃ (አባቴ ቀጫጫ ነው) አቅፋው አለቀሰች። እኔ ከአልጋ ስር ሆኜ እነሱ ከአልጋ ላይ ሁሉን ነገር ሰማሁ። የእናቴን ለቅሶ፣ የአባቴን ፋከራና ማስፈራራት፣ የሚያሳዝንና የሚያስፈራውን፣ የሚገርመውን የሚያደናግረውን የተባለውን ሁሉ፡ አባቴን 'ሽንኮራዬ' ስትል ሰማሁዋት። እንደዛ ስትጠራው ከዛ በፊት አልሰማሁዋትም። ከዛም በሁዋላ አልሰማሁዋትም። የሚገርመኝ ቃል ነበር። አባቴ 'ወዬ' ሲላት። እንደዛ በልስላሴ የተነገረ 'ወዬ' ከዛም በፊትም ከዛም በሁዋላ አልሰማሁም። አድጌ የገባኝ ነገር ኑሮ ፍቅርን መዘረር መቻሏ ነው። ከአልጋ ስር ከወጣሁ በሁዋላ፣ አይኖቼ ግራ በገባው መልክ ግራ ያጋባኝ አለም ማየት ጀመሩ። ሲቆይ ደቃቃ በሆነ ስልት፣ ቢያንስ በቃላት ደረጃ እኔ ሕይወት ላይ የተሰነዘረ ንግርት መሰለኝ። የአንዱ ሕይወት ለሌላው ንግርት ሊሆን አይችልም? የዛሬው ዘመን ባለፈው ዘመን አይዘረዘርም? የዛሬዋ ቅኔ በትናንቱ ስልት አትፈታም? ቀሮው ተለያይቶ ልቡ ተመሳስሎ አይሆንም? ታዲያ በልጅነቴ የራሴን መስመር ስጀምር እዛ አልጋ ስር ሆኜ የሰማሁትን ቀላል የመሰለ ነገር የምደግመው ይመስለኝ ነበር።

እናቴ ጠላ መጥመቋን አቁማ ቂጣና እንጀራ ወደ መሸጥ ተመለሰች:: ይሄ ንግድ ብዙ አልጠቀማቸውም:: ግን ቤታችን ከረብሻ ፀዳ::

ከ'መወለድ' የበለጠ ቁልፍ ጉዳይ የለም:: ሕይወቴ የጀመረው ከወንድ ወሰንና ከማልደዶ ስወለድ ነው:: አንዳንድ ቁልፍ ነገር ነው የሁሉን ነገር መስመር ጠመዝዞ፣ ጎዳናችንን ቀይሶ፣ ጣፈጠም አልጣፈጠም 'ሕይወታችን' የሚባለውን የብዙ ሁኔታዎችን ጥርቅም የሚፈጥርልን:: ከመወለድ በሁዋላ ልጅነት ይመጣል፣ ከልጅነት ኋላ ብዙ ነገር ይመጣል:: መወለድ መጀመሪያዋ እንጂ ሁሉን የምትወክል መደምደሚያ ምክንያት አትሆንም:: የሁሉ ሰበብ መወለድ ብቻ ቢሆን ኖሮ ብዙዎቻችን ጠባዮችን አንድ ይሆን ነበር:: *ነው እንዴ?*

አዎ ደሃነት የራሷ ጉዳት አላት:: ይሄም የሚታረም ይሆናል:: የሚታረም ጉዳት ማስበርገግ አለበት? ግን ደካሞች ነንና እንበረግጋለን:: በጥቂት አመታት ቆራጥነት የሚሸነፈውን እባብ በቀሽምነታችን ዘንዶ እናደርገዋለን......ልቁስቁስ ዕናትና ትክክለኛ ጥናት ያጠረው አተረጓጎም ብዙ ብዙ ያጠፋል:: እኔና መሰሎቼ የምንጋራው ከዚህ መስክ ላይ የበቀለ አቅመ ቢስነትን ነው:: ወጣ ገባው የሰጠን እርግጠኛው ስጦታ በሌሎች ሰዎች ሃሳብ በቀላሉ ተዘልዝለን ሁሉ ሊበላን የሚያስጎመጅ አይነት ጥብስ መሆን ነው:: 'ሌሎች' ብዙ ናቸው:: ይሄም ያም አለ:: በየቦታው በየጊዜው አሉ:: ከሳምንቱ በሰባቱም ቀኖች፣ በአስራ ሶስቱም ወሮች፣ በመአልቱም በሌሊቱም አሉ:: በተራራው፣ በሜዳው፣ በየጎጆውና በየፎቁ:: የተበላሸበት ተንገዋ ጎዳናውና ሽግግሩ ከአንዱ እንቅፋት ወደ ሌላው ነው:: የእሳት አይነት የመምረጥ ነው::

## [redacted]……መኪናና አንዳንድ ነገሮች

ገና እንዳሽኮረኮርኩ (እንደሚሉት) ገና አስራ ስድስተኛዬን [redacted]ያዝኩ (ስታቲስቲክስ) ገና ምንም ሳላውቅ (ስዶች) 71 አም ውስጥ ዘጠኛ ክፍል እያለሁ፣ 'አልማዜ' የምትባል የጉርጉሱም ቡና ቤት ባለቤትና ብዙ ሰው ይወዳታል የምትባል (ስምዋ አልማዝ ነው፣ ታዲያ ለምን 'አልማዜ' ይሏታል? ካልወደድዋት?) ሴትዮ ጋር ተዋወቅሁ:: የተዋወቅንበት አጋጣሚ እንዲህ ነው……

[redacted] ክረምት ከስድስት ኪሎ ወደ ሰፈር በእግሬ እመጣለሁ:: ዝናብ ይወርዳል:: ፀጉሬ ረጥቦ አናቴ ላይ ተጣብቆአል:: ያደረግሁት የፌስታል ባርኔጣ አላዳነኝም:: ነጠላ ጫማዎቼ በ[redacted]ና በጭቃ ረጥበው እየተንሸራተቱ ስላስቸገሩኝ አውልቄ በእጄ ይዤአቸዋለሁ:: ከላያቸው ጭቃ የቀላቀለ ውሃ ይንጠባጠባል:: ግራና ቀኝ መኖሪያቤትና ቦይ እንጂ መጠለያ የለም:: ብዙ ዝናብ ስለመታኝ ሁለመናዬ ፈጥቶ ወጥቶአል:: ቀሚሴ ውሃ [redacted] ይካበዳል:: ቀሚሴ የትልቅ ሴት ነው:: ደሞ የሱፍ ጨርቅ ነው:: የአባቴ ጓደኛ ዋሕድ የተባለ ሰው፣ እዛው ሰፈሬ የሚኖሩ ሮዛ የሚባሉ ሴትዮ ሲያርፉ ሰራተኛቸው 'ለምትሰጠው ስጥ' ብላ የሚቺቷን ልብስ አመጣችለት:: እሱ ደሞ ለእኔና ለእማማ አመጣልን:: ሌሎቹ [redacted]ሶቿ በጣም ስለሰፉኝ አልተስማሙኝም:: [redacted] ልክ የሆነኝ ደሞ ላውንደሪ መታጠብ የሚገባው ሱፍ ነው:: ገበር ያለው አረንጉዋዴ ነፍስ ይማር ቀሚስ ነው:: ከወገቤ ላጠበው የተጠቀምኩበት መርፌ ቁልፍ አልቻለውም:: እና ጠቅላላ ውሃ ተሸክሞ ተንሸራቶ ወደ መሬት ሊወደቅ ያስባል:: ከላይ ያደረግኹት አንድ ተራ ካናቴራ ነው:: ከገላዬ ተጣብቋል:: ደረቴ እውጭ ያለ ይመስለኛል:: የሚያየኝ ሰው ካለ ጡቶቼን ለመከለል እጆቼን ደረቴ ላይ አጣምሬአለሁ:: ውሃ በቂጤና በምንትፍረቴ ይወርዳል:: ባዶ እግሬን ስለሆንኩ ኮረኮንቹ እየቆረቆረ ስላስቸገረኝ ለስላሳ የአስፋልት ጠርዝ ይዤ በቀስታ ወደ ቤቴ ጉዞዬን ቀጥዬአለሁ:: በዚህች ከተማ፣ በዚህች በተወለድኩባትና ባደግሁባት ከተማ ለአውቶቡስ የምከፍለው ገንዘብ የለኝም:: ይሄ ትንሽ አማሮኛል:: ብርድ እየገባኝ በመጠኑ መንዘፍዘፍ ስጀምር፣ ከሁዋላዬ ክላክስ ሰማሁ:: (አልፎ አልፎ በደህና የፀሐይ ቀን አለባበሴን የናቁ፣ መልኬ የሳባቸው አትኳሪ ወንዶች

ክላከስ ያደርጉልኛል) ዞር ብዬ ሳላይ ውሃ በዝምታ በእግሬ እየመታሁ መንገዴን ቀጠልኩ:: ክላክሱ ተደገመ:: ዞር አላልኩም:: ከዚያ መኪናው ትንሽ አልፎኝ ፊት ለፊቴ ቆመና አየሁት:: አልማዜ ነበረች:: ሴት በመሆንዋ ተንፈስ አልኩ:: የመኪናዋን የመስታወት መስኮት ዝቅ አድርጋ:

«በይ ቶሎ ግቢ!» አለች:: ልክ በደንብ እንደምንተዋወቅ ሁሉ:: በሰፈር ዝም ብሎ መተያየት እንደመተዋወቅ ይቆጠራል:: ይመስለኛል:: በዐይን የለመድኩት ሰው በቃ ብዙ የማውቀው ይመስለኛል:: ልክ ያ ዛፍ አለ ሰላም አልለውም ምክንያቱም እንደበት የለውምና መልስ አይሰጠኝም፣ ግን አውቀዋለሁ አይነት:: እንደዛ::

አልማዝ (በሁዋላ በደንብ ሳውቃት ከ'አትዬ አልማዝ' ወደ 'አልማዜ' እሸጋገራለሁ) ብቻዬን ስሄድ ስታገኘኝ አተኩራ አይታኝ ከማለፍ፣ ወይም በመንገድ ከአባቴ ጋ ወይም ከእናቴ ጋ ስሄድ እሱን ወይም እሷን ሰላም ስትላቸው ከማየትና ከመስማት በተቀር አናግራኝ አታውቅም:: በዚያን ዕለት የሚያምር ሁኔታ ላይ ስላልነበርኩ፣ በሰው መኪና መሳፈር ቀርቶ ሰው በአጠገቤ እንዲያልፍ አልፈለኩም:: ግን በዝናብ በስብሼአለሁ:: ብርድ ያንዘረዝረኛል:: ቤቴ ለመድረስ ቢያንስ ሩብ ሰዓት በእግር መጓዝ አለብኝ:: በመንገዱ ጠርዝ ላይ ስለምራመድ ወደ ታች የሚያልፍ መኪና ውሃ ረጭቶኝ ሊያልፍም ይችላል:: ብዙ ብዙ ነገር አለ በዚያ ዓይነት ቀን፣ በዚህች በተወለድኩባትና ባደኩባት ከተማ፣ እዛች የማውቃት ክረምት ያረጠባት እንጀት ውስጥ:: 'ከአንድ ወንዝ ጠጥተን' እንደሚባል 'በአንድ ዝናብ ተመተን' ይባላል? ከቀመሩት ማለቴ ነው:: እናውቀዋለን::

መኪናው ውስጥ ገባሁ:: የግል መኪና ውስጥ ስገባ የመጀመሪያ ጊዜዬ ነው:: ይሞቃል:: ትዝ ይለኛል መኪናው መሞቅ ብቻ ሳይሆን ደስ የማይል የሽቶ ጠረን ነበረው::

እንደገባሁ ስለዞረብኝ በእጄ ያንጠለጠልኳቸውን ነጠላ ጫማዎች የት እንደማስቀምጣቸው ግራ ገባኝ:: አንቀርቅፌ እንደያዝኳቸው:

«አስቀምጪው ታች ምንም አይደል፣ በስብሰሽ የለም» አለችኝ በሐዘንተኛ ድምፅ::

ነጠላ ጫማዎቼን መኪናው ወለል ላይ በቀስታ ቁጭ አደረኳቸው:: መኪናው ወለል ላይ የተነጠፈው እግሬ የሚረግጠው የስፖንጅ ላስቲክ ደርዙ ነጭና አረንጉዋዴ ነው:: በውሃ የራሰ ልብሴን አስተካክዬ ቀና ብዬ ሳያት አልማዜ ፈዛ ታየኛለች::

«እ» አልኳት('ምን አጠፋሁ?' ማለቴ ነበር)

«እንዲህ በስብሰሽ......ደሞ ብቻሽን» አለች አፏን ሸርመም አድርጋ::

«ምን እሆናለሁ» አልኩ በመሽኮርመም (በመፍራትም)

«ብርድ ቢመታሽስ? ጥሩ አይደለም» መኪናዋ ተነሳች።

አልማዜ በአስፋልት ላይ፣ በሚፈሱ ጎርፎች ላይ፣ ካልጠፉ ቦታ በአስፋልቱ ደርዝ በሚሄዱ አንዳንድ አሀዮች ላይ ውሃ እየረጨችና እየነዳች ሄደች። ወደ ቤቴ በሚወስደው መንገድ በኩል ሆቴሏ ዝቅ አድርጋ ታወርደኛለች ብዬ ሳስብ፡

«ቆይ ልብስሽን አድርቀሽ፣ ሞቅ ብሎሽ ነው ቤት የምልክሽ። ወንድወሰን አባትሽ ባለውለታዬ ነው። ቀበሌ ውስጥ ካሉት ሰዎች እሱ ይሻለኛል። ደግ ሰው ነው። የሽሮሜዳ ሰው ይተሳሰባል፣ ባሕላችን እኮ ነው። አሁን ቤቴ እንሄድና ሞቅ ብሎሽ ልብስሽን ለውጠሽ ትሄጃለሽ። እንዲህ ሆነሽማ ብትሄጂ ተከልዬ ይፈርዱብኛል»

አባቴን ስትጠራ የአባቴ ጓደኛ ሽንኩራ ነጋዴው ዋሕድ ትዝ አለኝ። ዋሕድ ዝናብ ስለሆነ መንገድ ላይ የለም። ዕጣ ክፍል ያቀናጀውን ማን ሊያጥፍ ይችላል? የሚያውቀኝ ሰው ይኖር አይኖር በፍጥነት መንገዱን ቀላውጬ፡

«ኸረ ግድ የለም» ምናምን ብዬ ተግደረደርኩ።

እንደ ብዙው ደሃ ከቤቴ ጋር የበረታ ባይሆንም ጥል አለኝ። አለ አይደለ የሚያስደንቅ ነገር አያጋጥመኝም።

ግቢዋ ገባን። ሞቆኝ ስለ ነበር ከመኪናው መውጣት አልፈለግሁም። ሌላው ምክንያት ደሞ በሩን መክፈት ስለማላውቅ ነው። መውረዴ ስለማይቀር ዝቅ ብዬ እያየሁ መስታወት፣ እጀታና ብሎን ሳስስ፡

«ቆይ ዣንጥላ ይመጣልናል አትውጪ» አለችኝ

ያኔውኑ ከመኪናው ማቆሚያ ፊት ለፊት ከተደረደሩት ክፍሎች ከአንዱ ዣንጥላ የያዘች፣ አንዳንዴ በመንገድ የማያት ሰራተኛ (ስሟ 'ረድኤት' የተባለ) ወጣችና አልማዜ ወደ ተቀመጠችበት የመኪናው ጎን ሄደች። አልማዝ በደረቷ እላዬ ላይ ተንበልብላ በሩን የሆነ ነገር አድርጋ ከፈተችውና፡

«እንደውም ዘለል ብለሽ በረንዳው ላይ ሁኚ» አለችኝ። ነጠላ ጫማዬን በእጇ አንጠልጥዬ ወጣሁ፡ ቀዝቃዛው ነፋስ ሲመታኝ በብርዱ መንቀጥቀጥ ጀመርኩ። ዣንጥላው ወደ እኔ አልመጣም።

«ነይ በእዚህ!......ነይ በእዚህ!» አለች አልማዜ ወደ እሷ እጇን እያራገበች።

ዝናብ ሳይሆን ክርሳሴ ከሰማይ የሚወርድ ይመስላል። ክርሳሴ የሚዘንብ። እየተንዘፈዘፍኩ ሮጥ ብዬ በረንዳው ላይ ሳይሆን አልማዝ ዣንጥላ ስር ገባሁ። ወደ ግራ አቀናች። በመጠኑ ለእግሬ የሚመቹ ጠፍጣፋ ድንጋዮች የተነጠፉበትን እየመረጥኩ በቀስታ እየተራመድኩ

ተከተልኳት:: ትንሽ እንደሄድን በረንዳ ላይ ወጣን:: ዝናቡን እየተራገመች፣ ዣንጥላውን የበረንዳ ምሰሶ አስደግፋ አቆመችው:: በሁዋላ የእሷ መኝታ ቤት መሆኑን ያወቅሁት ሳሎን የሚያክል ሰፊ ክፍል በር ከፍታ ገባን:: ከመግባቷ ወንበር ላይ ተቀምጣ ቶሎ ቦት ጫማዋን አውልቃ ዝናቡን ደግማ ተራገመች:: ከዛ እዛው ከተቀመጠችበት ዞር ብላ በችኮላ አየችኝ::

«እስኪ ነይ» አለችና ልክ ጥፋት እንዳጠፋሁ ሁሉ በዝናብ እረጥባ ከትከሻዬ የተጣበቀች፣ በመታጠብ ብዛት ቡላ የሆነች ሲጀመር ግን ጥቁር የነበረችዋን ካናቴራዬን (እንደ መናቅና እንደ መጠየፍ) በአመልካችና በአውራጣቷ ይዛ፡

«በይ ልጂ እዛ ቁጭ በይና ይሄን ነገር አውልቂ፣ እኔ የሚስማማሽን አመጣልሻለሁ» አለች::

የምዘንጥባትን ካናቴራዬን 'ነገር' ስትላት ትንሽ ቅር አለኝ:: ለመለወጥ ግን አላንገራገርኩም:: ግን እንዴት ነው እንግዳ ሰው ቤት፣ እንግዳ ሴትዮ ፊት ልብሴን የምቀይረው? ዙሪያዬን ተገላምጬ አየሁ::

«አትፍሪ ግድግዳ ውስጥ የተደበቀ ሰው አለ መሰለሽ? በሩን ገርበብ አድርጊው ማንም አይመጣም» ብላኝ ወጣች:: መጀመሪያ እንግዳ ሰው አልፈራሁም:: ምክንያቱም እራሷ እንግዳ ናት:: እንደሚያስፈራኝ የነገረችኝ እራሷን ሳይሆን የማይታየውንና ያሌለውን ነው:: በርዶኛል እናም ዞሮብኛል:: እንኳዋን መቀመጥ መቆም ራሱ አስፈራኝ:: በሩን ሳልነካ፣ ልብሴንም ሳላወልቅ ከሄደችበት እስክትመጣ ጠበቅሁዋት:: ከአስር ደቂቃ በሁዋላ አንድ ካናቴራ አንድ ሹራብና አንድ የሚያምር ጉርድ ቀሚስ ይዛ መጣች::

«አላወለቅሽም? ሳልወፍር በፊት የእኔ ነበር» አለችኝ ልብሶቹን አልጋ ላይ እየወረወረች

«ለመሆኑ መታጠብ ትፈልጊያለሽ?» ቀጥላ

«ምን?»

«ገላሽን መታጠብ»

«አልፈልግም» ለማድረግ የሚከብዱ ነገሮች ስለበዙብኝ ብቻ ሳይሆን፣ ውለታ ስለበዛብኝ የተግደረደርኩ እንዲመስል አድርጌ::

«እሺ ለእግርሽ መታጠቢያ ውሃ ይሞቅልሻል»

በመገረምና ባለማመን አየሁዋት::

«ገረመሽ? የአንቺ አባት ያደረገልኝ ውለታ ቀላል አይደለም:: እሱ ላይመስለው ይችላል:: የሰራውን ውለታ የማይቆጥር ሰው እኮ ክርስቲያን ነው»

በጉጉት ታጤነኛለች:: ፊቴን አዞሬ ካናቴራዬን አወለቅሁና ዞር ብዬ አየሁዋት:: ግራ እየገባኝ የሰጠችኝን ካናቴራ ከአልጋ ላይ ቶሎ አነሳሁና ለበስኩ::

«የከተማ ልጅ አይደለሽም እንዴ? ውይ እቴ:: ግድ የለም:: በይ እኔ ውሃ እንዲያሞቁ ልንገራቸው» አለችኝና በር ጋ ቆማ:

«ረድኤት! ውሃ አሙቂልኝ እስኪ! እና የሚበላ ትኩስ ነገር አዘጋጂ»

ቀሚሴን ማውለቅና በውስጥ ሱሪ እሷ ባለችበት መቆም ከበደኝ::

«ምንዋ ዓይነ አፋር ነሽ? በይ ዞር እልልሻለሁ» አለች ሳቅ ብላ::

በረንዳ ላይ ወጣች:: ወዲያ ወዲህ ስትል አዲስ ያጠለቀችውን የቆዳ ጫማዋን ዳና እሰማለሁ:: ቀሚሴን ቶሎ አወለቅሁና (በስብሶ ክብደቱ አራት አምስት ኪሎ ሳይሆን አይቀርም) የሰጠችኝን ለመልበስ ጎንበስ ስል እክፍሉ ገባች:: ፊት ለፊቴ ተደንቅራ ከላይ እስከ ታች አየችኝ::

«ውይ! ስታምሪ» አለችና በወርቅ አምባር በተሸፈነ እጇ፣ ቀለበት ባደመቃቸው ጣቶቿ አፏን ያዘች::

ቀሚሱን ፊት ለፊቴ ይዤ ራሴን ጋረድኩ

«ላልብሰሽ» አለች

«ግድ የለም እለብሳለሁ» አልኩ::

ሳልጠብቀው ተጠግታኝ ቀሚሱን ከእጄ ነጠቀች:: እጆቼን እግሮቼ መሃል አደረግሁ:: አይኖቼን ተከትላ የምሰልለውን የምትሰልል መሰለኝ:: ከባድ ፈተና ላይ ነበርኩ:: የውስጥ ሱሪዬ በዝናብ እርሳ ከላዬ ተጣብቃለች፣ ከጭኖቼ መሃል ጨርቁ በውሃ ከብዶ ተንጠልጥሎ ቅዝቃዜው ይሰማኛል:: አጎንብሼ ራሴን ማየት ፈርቼአለሁ::

«የውስጥ ሱሪ ላምጣልሽ? ካናቴራው ትንሽ ሰፋሽ አይደል:: ሴት ለሴት አይተፋፈርም» አለች እየሳቀች:: ቀሚሱን እንደ መወርመር አድርጋ ወደ ደረቴ መለሰችልኝና ትታኝ ወደ ውጭ ወጣች:: ከላይ ሞቆኝ ከታች ከርስሶኛል:: ውስጥ ሱሪዬን ሳላወልቅ ቶሎ ቶሎ ለበስኩ:: ጎንበስ ብዬ እሱን እያስተካከልኩ እያለሁ ዘው ብላ ገባች::

«አምሮብሻል:: ትንሽ ሰፋሽ? ግድ የለም ለዛሬ ይሆናል:: ምሳ እንበላለን:: ቡና ትጠጪና ትሄጃለሽ» አለችና እንድከተላት ጠርታኝ ከክፍሏ ወጣን:: ሌላ ጠበብ ያለ ክፍል ተያይዘን ገባንና ቀይ ወጥና ድቡልቡል ጎመን በሰርገኛ እንጀራ በልተን ቡና ለመጠጣት ወደ ክፍሏ ተመለስን:: ይሞቃል የተባለው ውሃ አልመጣም:: ከመሃል ያደረግሁትን ነጠላ ጫማዬን አይታ:

«ቆይ ጫማ እገዛልሻለሁ» አለችኝ

ምን አገባት? አልኩ በልቤ ከዛ 'ምን ቸገረኝ' አልኩ

«ልብስሽን እዚህ ተይው ይታጠብልሽና ነገ ከነገ ወዲያ ትወስጂዋለሽ:: አትፈሪኝ:: የአንድ ሰፈር ሰዎች አይደለንም እንዴ? የዘመኑ ልጆች እኮ ስታድጉ አያድርስ ነው:: ይገርማል:: ምን እየበላችሁ ይሆን? ፋፋው ነው? ሂሂሂ......»

እንክርት መጣና እላዩ ላይ የሸከላ ጀበና ተደርጎ ቡና ማፍላት ተጀመረ::

«ሙዚቃ ልክፈት ማንን ዘፋኝ ትወጂያለሽ?» አለችኝ

«እንጃ» አልኳዋት(ባውቅም መናገር አፈርኩ)

«እንዴ ከጊዜው ጋ ሂጂ እንጂ:: ጊዜውን መምሰል አለብሽ:: ልክ የአንቺ ዕድሜ የምትሆን ልጅ አለች:: ዘመዴ ናት:: በጣም ደስ የምትል ልጅ:: 'ዕዮን' ነው ስምዋ:: የማይወዳት ሰው የለም:: ተግባቢነቷስ:: ግንባር አላት:: ሳርና ቅጠሉ ነው የሚወዳት:: ስትዘፍን ስታንጎራጉር ሌላ ናት:: ስትደንስስ:: ልቅም ያለች ቆንጆ፣ ከፀባይ ጋር:: ካንቺ እንኳን አታምርም ግን የማያስቸግራት ጎረምሳ የለም:: ሁሉን 'ዞር በሉ' ትላለች:: ጨዋ:: ትምህርቷስ? ጎበዝ:: የምትውለው ከትልልቅ ሰዎች ጋር ነው:: አሷን ማወቅ አለብሽ:: ሙች:: በከተማው የተደረገ ነገር አያመልጣትም:: አለባበስ መጣ ቀለብ ነው የምታደርገው:: ስልጡን የስልጡን ስልጡን:: ወተት ትፈልጊያለሽ በቡናሽ?»

«አይ ጥቁር ነው የምጠጣው»

አረፍ አልኩና ድምፄን ዝቅ አድርጌ:

«ጥላሁንን እወዳለሁ» አልኳት እኔስ ምን አንሳለሁ ዓይነት ነገር::

«ጥላሁን ይጮሃል:: ሙሐሙድስ? ሙሐሙድ ጥሩ ነው» አለች ሳቅ ብላ:: ትከሻዬን 'ምን ቸገረኝ' አይነት ነቀነቅሁ:: ከተቀመጠችበት ተነስታ ብዙ ካሴቶች እንኳኩታ የሙሐሙድን ነገር አደረገች:: ዘፈኑ ከመሃል ጀመረ::

«ሪወይንድ[152] አደርገዋለሁ» አለች ወደ ወንበሯ እየተመለሰች:: ቡናውን ቀዳችና ወተት በችንሹ የተከለሰበትን በእሷ አባባል 'ዓይኖቼን የመሰለውን' ለእኔ መድባ:

«በሚቀጥለው ጊዜ ዝናብ አይምታሽ አሺ? እዛ አካባቢ በመንገዱ ዳር፣ ትንሽ ገባ ብሎም የማውቃቸው ሰዎች አሉ:: አስተዋውቅሻለሁ:: ከዘነበብሽ፣ ከቸገረሽ አንኳኩተሽ መግባት ነው (ታየኝ በየሰው ቤት እያንኳኳኩዋሁ 'ጠልሉኝ' ስል):: አዲስ አባ የሰው አገር ነው......» ብዙ

---

[152] ወደ ኋላ መጠምጠም

አወራችኝ:: ከመሃልም እየለመድኳት በምታላግጥባቸው ሰዎች ስስቅና አባቴንና እናቴን ስታመሰግን እየሰማሁዋት ቆየሁ:: አባትና እናቴን ለምን እንደምታመሰግናቸው ግን በትክክል አልገባኝም:: ምክንያቱንም አልነገረችኝም:: ክርስቲያን ስለሆኑ? ጨዋ? ደግ? ባለውለታ? ምን ውለታ? ምንድነው 'ውለታ'? ይሄ ሁሉ ካልተተረተረ (ፈርሶ ካልታየ ቃሉ) መግባባት ፍዝ አይሆንም?

ምናልባት ከአንድ ሰዓት ተኩል ወይም ከሁለት ሰዓቶች በሁዋላ ቡናዬን ጨርሼ፣ የረጠቡ ልብሶቼን እንደ ሳንቡሳ ሊጥ ጠቅልዬ፣ ዝናቡ አባርቶ ቤት ስገባ እናቴ አይታኝ አላወቀችኝም::

«እህ......የዳንግላው ሚካኤል ድረስ ሌላ ሰው መሰልሽኝ:: ምንድነው የለበስሽው? ከየት አመጣሽ?» አለች እንደ መደንገጥ ብላ::

ያሉኝ ሁላችንም የምናውቃቸው ቀሚሶች ሶስትና የተጎዱ ናቸው:: ሲተረተሩና ደጋግሜ በመርፌ ስጠቁማቸው አሪፍ ስላልሆንኩ በሚገናኙበት መስመር የሚስቁ ይመስላሉ::

ለመጀመሪያ ጊዜ ዋሸሁዋት:: የመጀመሪያ ውሸቴ ነበር:: ግን ይሄ የመጀመሪያ ውሸቴ ከአፌ ሲወጣ ገዜ ላይ ጉልህ ቅሬታ አልነበረም:: አላስጠጣሁም:: 'አልማዝ ሰጠችኝ' ብል ከቡና ቤትና ከምኑም ጋር የሚያያዝ መሰለኝና ፈራሁ::

«ከእምነት»

እምነት የቅርብ ጓደኛዬ ናት:: ስሟ አያናደድም? ለእንደ እኔ አይነት ውሸታም 'እምነት' የምትባል ጓደኛ በስሟ ብቻ ፈተና ናት::

«ደሞ እምነት የዚህ ዓይነት ዘበናይ ነገር ለብሳ አይቼአት አላውቅም» አለች::

ከዚህ በላይ እንዴት ትንቃብኝ? ሴት ልባልግ ካለች እንኳን በምድረ አዲስ አባ ውሻውም ዛፉም በሚቆምበት፣ በገዳምም አትቻል:: ይሄ የተገነዘብኩት ትክክል ነገር ነው:: እማማ ብዙ ተናጋሪ አይደለችም:: የሚረጋገጥ እውነት ትናገራለች እንጂ የመሰላትን ይዛ አትከራከርም:: አተኩራ አየችኝ:: ሴቶች የት ዕድሜ ላይ ሲደርሱ እንደሚተኮርባቸው እናቶቻችን ስለሚያውቁ 'ገብቶኛል' ልትል ብቻ ነበር:: 'ሕዝበ አዳም ከቤቱ ሲወጣ የሚያድነው ቆንጆ ሔዋንና ገንዘብ ነው፣ ሚዳቅዋና ቀጭኔ አይደለም' እዝራ ነው ያለኝ እንዲህ::

«እምነት አይደለችም......መንበረ ማለቴ»

«ዘባረቅሽ ምነው? ለምን እቴ?......እም»

«ዝናብ አበስብሶኝ»

ከዛ ዝም አለች:: ደስ የማይል አይነት ዝም ነው:: እንዲህ አይነት ዝም ደስ አይልም:: ወላጆችንን እንደማታለል ቀላል ነገር የለም:: ምክንያቱም ያምኑናል:: ባያምኑንም ቅር እንዳይለን ችላ ይሉናል:: እና ወላጆችን ማታለል ብሩህነት አይጠይቅም:: የእማማ ዝምታ ነገር ስትችል፣ ነገር ስትውጥ ነው:: ከጥርጣሬዋ በላይ ምን ትበል::

እተቀመጠችበት እያሰበች አልፎ አልፎ በገባሁ በወጣሁ ቁጥር ቀሚሴን አተኩራ ታያለች:: ተረት አለ:: አንድ ልጅ በሬ ሰርቆ ይያዝና አባትዬው እጅ እግሩን ታስሮ ሲሄድ ያገኘዋል:: እያለቀሰ 'ልጄ ምን አደረግሁህ? እንዲህ የምታዋርደኝ' ቢለው፣ 'አይ አባቴ አሁን ሁሉ ነገር አለቀ እኮ ገና ከመጀመሪያው ዕንቁላል ስሰርቅ ብትቆጣኝ ኖሮ እዚህ አልደርስም ነበር' አለው አሉ:: እዛ አልማዝ ቤት የዚያ የዝናብ ዕለት ነበር እኔ እንቁላል የሰረቅሁት:: አልማዜ ጎን ለአፍታ ቆምኩና ጎዳናዬ ተለወጠ:: ቀላል የዝናብ ቀን ይመስላል ግን ለኃኔቴ ለሚፈራ ነገር እጇን ሰጠች::

በሁለተኛው ቀን የአልማዝን ልብስ ለመመለስ ስሄድ፣ አቅፋ ስማ ተቀበለችኝ (ልክ እንደ አብሮ አደጌ ወይም ወልዳ እዚህ እንዳደረሰችኝ ሁሉ)::

«ካልኩሽ ዘመዴ ጋ ላስተዋውቅሽ፣ ብዙ አንቆይም ደርሰን መመለስ ነው:: ግን ከዛ በፊት ለአንቺ የምሰጥሽ ስጦታ አለኝ» አለችና አንዲት ባለጥልፍ ጉርድ ሹራብ፣ ደስ ከምትል ፓሪ ቀሚስና ትንሽ ታኮ ያላት ቆዳ ጫማ ሰጠችኝ:: እዛው አለችበት ሁሉን ለበስኩና መስታወት ፊት ለፊት እሷ ከሁዋላዬ እኔ ከፊት ለፊት ቆምን:: ልኬን እንዴት እንዳወቀች ተገርሜ አይኖቼን ስበለጥጥ:

«እንዴ ካየሁ የሰው መጠን አውቃለሁ» አለችና እየሳቀች ትከሻዬን፣ ደረቴን፣ ወገቤን እናም ሌላም ሌላም ቦታ ደባበሰችኝ:: የገላዬ አይገርመኝም:: ከብዙ ሴቶች ጋር ስለምትገናኝ አወዳድራ፣ አወቅሁ ማለት ትችላለች፣ አእምሮዬን ግን በቀላሉ ማንበቧ ገረመኝ:: አተኩራ ሳያት ይሄ ትኩረቴ የልቤን አንብባ በመገረሚ እንደሆነ እንደሚገባት እየገባኝ፣ ይኼም እንደ ገባት አይነት ሳቅ አለችና:

«እዛው ጓደኛዬ ሰ.ጋ ምሳ እንበላለን፣ አንቆይም:: አታውልቂው ልበሺው» አለችኝና (ልክ ምሳ ለመብላት እንደፈለኩ ሁሉ) አሮጌውን ልብሴን በፌስታል ከትቼ ወደ ምትወስደኝ ቦታ ተከታትለን ወጣን::

መናኸሪያ ሆቴልን አለፍ ብለን ወደ ግራ በሚወስደው መንገድ ለመግባት አልማዝ የአትጣጫ መብራት ስታበራ ብርሃን መስቀል የተባሉ የሰፈራችን ሰውዬ የሚያደነቁር ክላክስ ነፍተውብን አለፉ:: ክላክሱ ያስፈልግ አያስፈልግ አላውቅም::

«ይሄ ደደብ። የማናውቀው መሰለው? በዚህ ከርካሳ መኪና ምን ሰላማዊ ሰው ይረብሻል? አይገርምሽም?» አለች አልማዝ። እንደተበደለች ሁሉ ራሷን በትዝብት ነቀነቀች። እኔም መኪናዋ ውስጥ ስላለሁ፣ ማዳላት ያለብኝ መስሎኝ ከንፈሬን መጠጥኩ፤ እሱም ላይ አጭር ክት ክት ጨመርኩ። እነዚህ ትንንሽ የመሰሉ ድርጊቶች (ቢረቡም ባይረቡም)፣ በእሷ ቁጥጥር ስር መውደቄን የሚያሳዩ ምልክቶች ነበሩ። እኔ ማንኛ ነው በዓላዛር አባት የምስቀው? በምንስ በልጩው ነው ወደ መሳቂያ የለወጥኩት?

የአዲሱ ልብሴ ጠረን ሽቶ አለበት። ግና መልበሴ ስለሆነ ገላዬ በትክክል የተቀበለው አልመሰለኝም። ይመስለኛል ብቻ። ልብሴን ደሞ አልማዝ 'ብርቅ ሆነባት' እንዳትለኝ እዛው መኪናው ውስጥ ለማስተካከል እንኳን አልደፈርኩም። ወይም ዝቅ ብዬ እግሮቼን ወይ የቀሚሴ ደርዝ ጭኖቼ ላይ እንዴት እንዳረፈ ደግሜ አላየሁም (መድገም መደጋገም ደንብ ነው)።

«በጣም ነው የምታምሪው» አለችኝ ኮረኮንች መንገድ እንደገባን። ተሽኮረመምኩ። እናቴ እንዲህ እንዳለችኝ አውቃለሁ። አባቴ እንደሚለኝ አውቃለሁ። የዘጠነኛ ክፍል ልጆች ማለት ናይን ኤፍ የነበሩት ልጆች በጨዋታ መሃል እንዲህ ይላሉ። ከእኔ የዐይን ፍቅር የያዛቸው ሺህ ጢም የለሽ ጎረምሶች ትምህርት ቤት አሉ። አዲስ አባባል አይደለም። አዲስ አባባል ማን መሰለኝ። ጉቦ ስለከበበው ነው?

ከመናኸሪያ ሆቴል ጀርባ አንድ ሁለት ደቂቃ እንደነዳች በጣም ሰፊ የብረት በር ያለው ቤት ጋ ስንደርስ ቆመችና ሶስቴ ክላክስ አደረገች። ፑፕ/ፑፕ/ፑፕ። ሁልጊዜም እንደዛ እንደምታደርግ በሁዋላ ገባኝ። እንደ ምልክት ነበር። አናቷ ላይ ባርኔጣ የመሰለ ጉንጉን ያላት ልጅ-እግር ሴት አንዴ ብቻ ቀና ብላ አይታን ማን እንደሆንን ካረጋገጠች በሁዋላ በሩን ወለል አድርጋ ከፈተች። ከፊት ለፊታችን በጣም የሚያምር ቪላ አለ። ሰፈራችን አለ ከሚባለው በደንብ ከማውቀው ከነዓላዛር ቤት ይበልጣል። የግቢው ፊት ለፊት በአስፋልት የተነጠፈ ነው። የማን እንደሆነ አላውቅም። ሲወርሸትም ጃልሰማሁም።

«የሐይለሥላሴ ጊዜ የነበሩ ባለስልጣን ሰውዬ ቤት ነው» አለችኝ አልማዝ እየሳቀች። ሳልጠይቃት። ድንቁርናዬንና መገረሜን ከአይኖቼ አንብባ? ከተከፈተው አፌ ውስጥ ለቅማ?

ወደ ሁዋላዬ ሳይ የአጥሩ በር ተዘግቶአል። ባለጉንጉንዋ ልጅ በጎን እያየችን ፈገግ ብላ አንገትዋን ሰብራ ሰላም ብላን ወደ ቤቱ ጀርባ አለፈች። ያጎነበሰችው ለእኔ እንዳልሆነ ቢገባኝም፣ ቢያንስ ደረጃዬ ከፍ እንዳለ ገብቶኛል። ደረጃ ከራስ ወይ አብረው ከሚውሉት ይመጣል።

ገረድ ባልሆንም እናቴ ገረድ ነበረች:: አሁን ያለው የኑሮ ደረጃዬ ከልጅቷ ይበልጣል ብዬ አላምንም:: አሁን ያለው በእኔና በእሷ መሃል የተፈጠረው ልዩነት ዋናው ሰበብ በቁንጅናዬ (ይሄ ግን ምን ማለት ነው? ከመሃል ራሴን በዝምታ እጠይቃለሁ) መመረጤና ከአልማዝ ጋር በመዋሌ ነው::

ከበስተቀኛችን የዚሁ ግቢ ተቀጥላ አለ:: ይሄ ተቀጥላ እኛ ከቆምንበት በዛፎች የተከለለ ነው:: እዛ ጥላ ስር ጥንዝዛ የመሰሉ ሁለት መኪናዎች ቆመዋል:: አንዱ ይሄ ደርጎች ምናምን ብዙ ጊዜ ይነዱታል የሚባለው ሬንጅሮቨር ነው (ያኔ ስሙን አላውቀውም):: ከመኪናው ወጥተን አልማዝን ከሁዋላ ከሁዋላ ተከትዬ ቤት ገባሁ:: በማፈር ብዘገይባትም ባልዘገይባትም ዞር እያለች:

«ነይ እንጂ......አይዞሽ» ትላለች::

'አይዞሽ' ማበረታቻና ማባበያ ነው:: አልማዝ ስትናገረው ሁለቱን ትርጉም በአንዴ አምቆ ይይዛል:: የአስራ ስድስት አመት ኮረዳ በሆርሞኗ መሸከም የማትችለው ሃሳብ ይሆናል:: የተንቀራፈፍኩ መስሎኝ የወንጀለኛነት ስሜት ይሰማኛል:: በመፍራቴ ስላደፋፈረችኝ የወደደችኝ ይመስለኛል:: ሁል ጊዜ 'አይዞሽ' የምትለው ቃል ከአፏ አትጠፋም (ቃሉን ዛሬ እጠላዋለሁ)::

ቤቱ ውስጥ እንደገባን ጨርቅና እርጥብ ስጋ ሸተተኝ::

(ዛሬ ድረስ ጥሬ ስጋ አልወድም:: ከትፎ ካልተጠበሰ አልበላም)

ከጀርባ በማድ ቤት በኩል ስለገባን ይሆን? ከዚያም በሁዋላ እዚያ ቤት አንዳንዴ ስመጣ የሚሸተኝ የመጀመሪያው ዕለት የሰነፈጠኝ ጥሬ ስጋና ያልታጠበ ጨርቅ ነው:: ፀጥ ያለ ኮሪዶር ውስጥ ስንገባ፣ ከፊት ለፊታችን በስተግራ ሰዎች ሲያወሩ ሰማሁ:: ይሄን ስሰማ እንደምፈራ ጠብቃ ነው መሰለኝ አልማዝ ዞር ብላ:

«አይዞሽ» አለችኝ:: ወደ ሳሎን በተጠጋን ቁጥር እምግ ጠረን ይሸታል:: የጨርቁና የእርጥብ ስጋው ጠረን ጠፍቶ እንዲህ የሚሸት አይመስልም:: ከውጭ ሲያዩት የሚያምረው ግንብ ቤት ከውስጡ ይሄ ጠረን ያለው አይመስልም::

«ነይ አይዞሽ» አለች ደገመችና

ኮሪዶሩን ጨርሰን ወደ ግራ ስንዞር የተንጣለለ የእኛን ቤት የሚያክል ሳሎን አየሁ:: ግድግዳዎቹ በመስታወትና በሚያምሩ ጥቁዋቁር እንጨቶች የተለበጡ ናቸው:: እዛ ውስጥ አራት አዛውንቶች እስከ ደረታቸው ሰፋዎች ውስጥ ሰምጠው ይስቃሉ:: ሳቃቸው እንግዳ፣ ገርዳፋ፣ የሚያስፈራ፣ ኮረኮንች፣ ሚዳና ገደል ነው::

(በልጅነቴ......እነዚህን ሰዎች ከማወቄ በፊት፣ የዚያ ዓይነት ሳቅ በሕልሜ ደጋግሜ አይና እሰማ ነበር:: የዚያ ዓይነት ሳቅ ሳልም፣ ደብዘዝ ያለ ግን ለማየት የሚያዳግት ዓይነት ጨለማ ውስጥ ቆሜ ነው:: እዚህ ጨለማ ውስጥ ልለያቸውና ልሰይማቸው የማልችል ነገሮች አሉ:: ቅጠል፣ ዛፍና የቤት ቁሳቁስ ያለ ይመስለኛል:: የት እንዳለሁ አላውቅም:: ታዲያ በዚህ ጨለማ ለማየት እለፋለሁ:: ግን ምንም አይታየኝም:: ግን ሳቆች እሰማ ነበር:: የተቆራረጡ ግን ሳቅ እንደሆኑ የምረዳቸው ብዙ ሳቆች እሰማ ነበር:: የሚገርመኝ እነዛ ሳቆች የሚተዋወቁ ይመስለኛል:: ሳቁ የሃሳብ ልውውጥ ይመስላል:: እለ አይደለ በአንደበት ሳይሆን የሚነጋገሩት በሳቅ ነበር:: ታዲያ እንዲህ ሲሆን ሴራ ያለ ይመስለኛል:: በመታወሬና ግራ በመጋባቴም የሚያሾፉ ይመስለኛል፡ እና ከጨለማው የበለጠ በዛ ሕልሜ ውስጥ የምፈራው ሳቁን ነበር......)

ሳሎኑ ደጃፍ እንደ ደረስን፣ አልማዝ አንገቷን ሰገግ አድርጋ ባልጠበቅሁት ትህትናና ቦቅቧቃነት:

«እንደ ምን ዋላችሁ?!» አለች

ሁሉም ከአንዱ በስተቀር (በሁዋላ 'ፍፁም' ብለው የተዋወቁኝ ሰውዬ) ዞር ብለው አዩን:: 'ሰላም' ከማለታቸው በፊት ማሰብ እንደነበረባቸው ሁሉ ተያዩ:: ከዛ:

«እንዴ አልማዜ! አልማዜ የእኔ እመቤት!» አሉና ከአንዱ ሰውዬ በስተቀር ሁሉም ተከታትለው ከተቀመጡበት ተነሱ::

ያኔ ዞር አለችና ወደ እኔ፣ ድምፅዋን ዝቅ አድርጋ:

«አይዞሽ አትፈሪ» አለችኝ

እሷ ፈጠን ብላ፣ በዚህም ላይ ትንሽ ጎንበስ ብላ ልትጨብጣቸው ስትሄድ ፍፁም የተባሉት ሰው:

«ይህቺ ቆንጆ ምን ፈርታ ትሸሻለች?» አሉና ከቆሙበት መጥተው ሊጨብጡኝ እጃቸውን ዘረጉ:: ዓይኖቻቸው ዓይኖቼ ውስጥ ተተክለው አዩኝ:: እኔም በመደናገርና በመሽኮርመም፣ ለሰላምታ እጄን ዘረጋሁ:: ክንዴን በግራ እጃቸው ይዘው፣ እጄን በሰፊ እጃቸው እየነቀነቁ የትም እንዳልሄድ ዓይነት አፍነው ይዘው:

«ማን ትባያለሽ?» አሉ::

«ምምማከዳ» አልኩዋቸው

«ስማችሁ ወዳጆቼ ላስተዋውቃችሁ:: እዚህ የምታይዋት መልከመልካም ልጅ 'ማከዳ' ትባላለች» አሉ:: ፍጥነቱ ቢቀንስም እጄን መነቅነቃቸውን አላቆሙም:: ፊታቸው ተላጭቶ ገና በሚበቅል ሽበት ተሞልቶአል::

ከመወፈራቸው የተነሳ መሰለኝ  ጆሮ ደግፍ የመሰለ ነገር አላቸው:: እጄን እየነቀነቁ ቁመናዬን በግ ምናምን ከብት እንደሚያዩ ቃኙኝ:: በማፈር ፊቴን አዙሬ አልማዝን አያለሁ:: አልማዝ ወጥዋ እንዳማረላት ሁሉ ትፍነከነካለች:: አቶ ፍፁም እኔን ከድሮ ጀምረው የሚያውቁኝ አይነት፣ እየተንከባከቡ ወሰዱኝና ለሁሉም ተራ በተራ አስተዋወቁኝ:: እንዴት ነው የማያውቁትን ማስተዋወቅ?

መሃከለኛ ዕድሜ ላይ ያሉ 'ወርቅነህ' የተባሉ ወታደር የመሰሉ ሰውዬ ከበስተግራዬ አሉ:: አንገታቸውን ብቻ ሰበር አድርገው ሰላምታ ሰጡኝ:: ስማቸውን አልነገሩኝም:: አልማዝ አቶ ይሁን ዶክተር፣ ወይም ሻለቃ፣ ወይም ሌላ የሹመት ቃል ጨምራ ስማቸውን ነገረችኝ:: ሶስተኛው ሰው ፊት ለፊቴ ከከቡ ጠረጴዛ ወዲያ የነበሩ ናቸው:: በጣም አጭር ይመስላሉ:: በግራ ጎናቸው ሶፋውን ተደግፎ የቆመ ከዘራ አለ:: አካለ ስንኩል መሆናቸውን ሊያሳዩኝ አይነት ሰላምታ አሉኝና ከተቀመጡበት ተነሱ:: ባይሆኑም ባይመስሉም:: ስማቸው 'ነቢየ ልኡል' እንደሚባል አልማዝ ነገረችኝ:: ከሳቸው ጎን የማይጤስ ፒፓ ይዞ በፈዘዘ ፈገግታ የሚያየኝ ወጣት የሆነ ሰውዬ 'አስመሮም' እባላለሁ አለና ፈገግታውን ሰፋ አደረገ:: የሚያምር ጥርስ አለው:: የፈገገው ጥርሱን ሊያሳየኝ እንደሆነ እንጃ:: አንገቴን እየሰበርኩ ሰላምታ ሰጠሁ:: ሰላምታውና ትውውቁ እንዳለቀ በተባበረ ቃል እንድቀመጥ ጋበዙኝ::

በር በከፈተችልን ልጅ ኮካ ኮላ ጠረጴዛ ላይ ፊቴ መጥቶ ተቀመጠ:: ኮካው ይበላኝ ይመስል እቆመበት እንደ ሰው አየሁት:: ያኔውኑ ወርቅነህ የተባሉት ሰውዬ ኮስተር ባለ ቃል:

«ፅዮን አልነበረችም እንዴ እዚህ?» አሉና ተናገሩ(ድምፁን የሆነ ቦታ የሰማሁት ይመስለኛል)

አልማዝ እኔ ወደ ተቀመጥኩበት መጥታ ከጆርባዬ በኩል ሚስጢር የምታንሾካሹክልኝ ዓይነት ተጠግታኝ፣ ግን ከእኔ ጆሮ አልፎ በሚሰማ ከፍ ባለ ድምፅ(ለምን ታዲያ ቀረበችኝ እንዲያ?)

«አይዞሽ ተጫወቺ፣ ጠጪ» አለችኝ

ለእሱ እንደመጣሁ ሁሉ ችኩል ብዬ ኮካውን ያዝኩት:: ለስ ያለ ነው:: ጠርሙሱ ትንሽ ባይሻክረኝ፣ ያለ አይመስልም:: እሱን አንስቼ ስጠጣ ከሌላ ክፍል አንዲት ልጅ ፀጉሯን እያመቻቸች አለንበት ክፍል ገባች::

«ስሚ ፅዮንዬ ተዋወቂያት!» ኮካዬን ወደ ነበረበት መለስኩት:: ፅዮን የተባለችው ልጅ በጣም ዘንጣ ለብሳለች:: ደርባባ ናት:: ታምራለች:: ከንፈሮቿ ተቀብተዋል:: ጥቁር ጉርድ ቀሚስ ለብሳለች:: ወገቧ በሰፊ ቀይ ቀበቶ ታስሯል:: ትከሻዎቹ አበጥ አበጥ ያሉ አጭር ኮት ለብሳለች:: እየሳቀች መጥታ ጨበጠችኝ:: ፅዮን አልማዝ የነገረችኝ አይነት ወጣት

አልነበረችም:: ልጅ ብትሆንም በዕድሜ ብዙ እንደምትበልጠኝ ሳይታይ በመዳበስ ብቻ ይረጋገጣል:: ትንሽ ደበረኝ::

«እም……የምንቾትና……» ያልሰማሁትን ነገር ተናግራ ዞር ብላ በትከሻዋ ላይ ፈገግ ብላ ስታየኝ፣ ግራ የሚያጋባ፣ ትርጉሙን ያልተረዳሁት ፀጥታ በአካባቢዬ ነገሠ::

«እዚህ ነይ ፅዮን» አሉ ወርቅነህ የተባሉት ሰውዬ፣ በፍጥነት:

እኔን የሚመለከት ጥሩ ያልሆነ ነገር ትናገር እርግጠኛ ባልሆንም፣ ከሰዎቹ ሁኔታ መጠርጠሬ አልቀረም:: ግን ደሞ አላውቃትም ስለዚህ ምን እኔ ላይ ክፉ ያናግራታል? ብዬ አሰብኩ:: ዝም ብሎ ስላማያውቀው ሰው ክፉ የሚናገር ጤነኛ አለ? እንዳለ የገባኝ ቆይቶ ነው:: እንዳለ የገባኝ ዛሬ ነው:: እኔ በእሷ ልብስና አዘናነጥ ስቀና እሷ በልጅነቴና በመልኬ የመቅናት፣ አልፎም የመመቅኘት እርፍና እንዳላት አልገባኝም::

የፅዮን ቂጥ የትልቅ ሴት ነው:: ከእማማ ይበልጣል:: ገና ከእኔ ዞር ስትል ፊቴ የተገተረውና እዛ የተቀመጡትን ትላልቅ ሰዎች የከለለኝ ከብ ጨለማ የለበሰ ቂጥዋ ነው:: ማርያምን:: ከጀርባ ካለው የቀሚሷ ተካፋች፣ የውስጥ ልብሷን ደርዝ የኪሮሽ ስራ አየሁ:: የዛ አይነት ውስጥ ልብስ ደስ ይለኛል:: የተተኮሰ ፀጉሯ ማጅራቷ ላይ ደስ በሚል መልክ ይነቃነቃል:: ታኮ ጫማዋ ይሰብቃታል::

«ጠጪው እንጂ……» አለች አልማዝ ጎንበስ ብላ ጆሮዬን ለመሳም ወይ ለመንከስ ትንሽ አስኪቀራት ተጠግታኝ::

ኮካውን አንስታ በእጄ ሰጠችኝ:: አይኖቼን ከብርጭቆው ወደ ፅዮን መለስኩ:: ፅዮን የፈጠረችው የፀጥታ ቅኔ ግን አልተፈታም:: ልቤን ግራ እንደገባው ኮካውን ተቀብዬ መጠጣት ቀጠልኩ:: ምናልባት አልማዜ ስለ ፅዮን የነገረችኝና የማየው ስለአልተጣጣመልኝ ይሆናል::

አንድ ግማሽ ሰዓት ያህል ወሬ እየተወራ ሳፈጥና ቁንጅናዬ በወንዶቹም በሴቶቹም እየተወሳ ስሽኮረመም ከቆየሁ በሁዋላ ምሳ ቀረበ:: ክትፎ በአረንጉዋዴ አይብ (እሱን አፍጥጬ ሳይ አልማዜ ቀረብ ብላ 'አይብ በጎመን' ብላ ያስተዋወቀችኝ) (ጤና ይስጥልኝ አይብ በጎመን! የሚያገግም ያገግምህ):: የበግ አልጫ ፍርፍር (የሚለጭልጭ ይለጭ ልጨው):: በደቃቁ የተከተፈ ሰላጣና ቃርያ(የሚሰጠስጥ ይሰጥስጠው ደሞም የሚቀርቅር ይቀረቅረው):: የድንችና የካሮት የስጋ ወጥ(የሚከርት ይከርተው፣ ሰግሳጊም ይሰግስገው):: ጥቁር ቆሎ(የሚጨቀጭቅ ይጨቅጭቀው) ቀረበ:: መብላት ብጀምርም፣ ሆዳም እንዳልባል ፈርቼ በመግ ደርደር ልተወው ነበር:: ከመሃልም ፅዮን ሙጢነቷ የሚያሳፍር፣ ማለቴ በቃ ድርቅ ድርቅርቅ ያለች ነገር፣ ወርቅነህ የተባለው ሰውዬ ጭን ላይ ተቀምጣ እንደጨዋታ እንደቀልድ እያደረገች ጉንጨን መሳም ጀመረች:: ማናችንንም ሳታፍር እንጀራ ባልጠቀለለ፣ ወጥ ባልነካው እጇ ፀጉሩን

ትዳብሳለች፣ መላጣውን ታካለች:: እንደዛ ስታደርግ ወንዶቹ ተያይዘው ይስቃሉ:: መሞላፈጧ እያስፈራኝና እያሳፈረኝ፣ ከእሷ ድርጊት ዐይኔን ላሸሽ፣ ትኩረቴን ከእሷ ሳርቅ ብለፋም አልቻልኩም:: ሳላውቀው የሞቀ ኮካዬን ከግማሽ በላይ ጠጣሁት::

ፍፁም: «ማክዳ አልበላችም፣ ባኅርሳት ደስ ይለኛል» እያሉ ሲናገሩ

አልማዝ: «አጉርሳት እንጂ ምን አለበት? ጉረሽለት»

«ኅርሳ አታውቅም?» አሉ አንደኛው

«ኸረ እማማ ሁሌ ታኅርሰኛለች» ምናምን ስላቸው በየዋሕነቴ፣ ሽበታቸው በዙርያችን በኖ እስኪያልቅ ይስቃሉ ምናምን::

ሆዴ ውስጥ የቀረችውን ትንሽ ባዶ ቦታ እሱ/እሳቸው እያኅረሰኝ/እያኅረሱኝ ሞላሁ:: በዚህ ድርጊቴ ወንዶቹና አልማዝ ኮድ እንደተለዋወጡ አልገባኝም:: እኔ ለእሳቸው መመደቤ አልተገለፀልኝም ነበር:: አስመሮም የተባለው ዘናጭ ሰውዬ ቁም ነገረኛ ለመምሰል ነው መሰለኝ:

«ትምህርት እንዴት ነው? አገሪቷን የሚረከቡ ወጣቶች ዛሬ ነው መዘጋጀት ያለባቸው እኮ:: መንግስቱ ጠዋት ማታ የሚናገረው ይሄንን ነው:: የልጁን ስም አለ ነገር 'ትምህርት' አላሳትም:: መማር ጥሩ ነው:: ፅዮንዬ እስኪ ከዛ ከውስኪ ጨምሪ እሱ ነው የሰው መጠጥ......» አለ::

ሌሎች ጉዋደኞቹ እንደተስማሙ ሁሉ ራሳቸውን ነቀነቁና ለመጨረሻ አባባሉ መሰለኝ ኅላ አድርገው ሃሃሂሆሃሃ አስነኩ:: ወይ በልባቸው 'ዝም በል እባክህ' እያሉት ይሆናል:: አልማዝ እኔን ከልጅነቴ ጀምሮ እንደምታውቀኝ፣ አባቴ ለአብዮቱ ብዙ የሰራና በጣም ስነስርዓተኛ(እናቴን ለምን እንደማታነሳ አይገባኝም) እንደሆነ ብዙ አወራች:: ቤተኛ እንደሆንኩ ሊያሳዩኝ ሌላ ቀን እዚህ ቤት ብመጣ ያለ ምንም ችግር እንድገባ በር ከፋቿ ጉንጉናሟ ሰራተኛ ተጠርታ እንድንተዋወቅ ተደረገ::

ቡና ተፈልቶ ስንጠጣ፣ አልማዝ እኔን እንዴት መንገድ ላይ አግኝታኝ በመኪናዋ ሊፍት ሰጥታ ክብርድና ከመከራ (ልክ ልሞት እንደ ደረስኩ ሁሉ) እንዳዳነችኝ ስትነግራቸው፣ እነሱ ወንዶቹ በማዘን (አዲስ አባ ለመጀመሪያ ጊዜ ዶፍ የጣለ አስመስላ፣ እነሱም መስሎአቸው) መኪና የሚገዛልኝ ጥሩ ባል አግብቼ ነፃ እንደምወጣ ተስፋ ሲያደርጉልኝ (ትንሽ አፈር እንኳን አይሉም) 'ከተመኙት ምንም ነገር ይሆናል' 'ምኞት አይከለከልም' ሲሉ(ምኞት ያልተመኘሁ ዓይነት) ምሽት ቀረበ......

በመጨረሻም ሁሉን ሰው ተሰናብተን እንደወጣን፣ አልማዝ ሌላ ቀን ብታገኘኝ ደስ እንደሚላት አሞካሽታኝ ተናግራ ('አንቺ አታሳፍሪም፣ ዕውነትም የአዲስ አባ ልጅ ነሽ')፣ ከአንድ ሳምንት በሁዋላ እሁድ ቀን

አስር ሰአት ላይ ታዚና ሆቴል ወረድ ብዬ እንድጠብቃት ነግራኝ (ለምን እዛ ቦታ እንደ ቀጠረችኝ ሳልጠይቃት) ለታክሲ ለምናምን የሚሆን ብላ ሃምሳ ብር ሰጠችኝና፣ ሰፈሬ ከመድረሴ በፊት ብዙ ሰው ያሌለበት መንገድ ዳር ከመኪናዋ ልታወርደኝ ቆመች:: ግን መንገድ ዳር መቆም እንደሚደብረኝ፣ እንደሚያስፈራኝ፣ እቤቷ መምጣት እንደሚሻለኝ ነግሬአት ተለያየን::

በዚያ ሃምሳ ብር ለአንድ ሳምንት እንደ እኔና እንደ ጉዋደኞቼ የተዝናና አልነበረም:: ሐሩርና ዝናብ አይንካኝ፣ በአውቶቡስ አልጋፋ ምናምን:: ግን ለዚህ ምቾት የምከፍለው ነገር እንዳለ አልገባኝም:: ወይም ተጠራጠርኩ:: *እንዴ? አይሆንም፣ ሊሆን አይችልም* እያልኩ:: ለምሳሌ ለጉዋደኛዬ ለእምነት የነገርኳት አንዲት በቅርብ ያወቅሁዋት ዘመዴ በድንገት ልትጠይቀን መጥታ ገንዘቡን እንደ ሰጠችኝ ነበር:: እንዲህ የዋሸኋት ከአልማዝ ጋር የነበረኝ ግኑኝነት የማያምር ሚስጢር ይኖረዋል ብዬ በመጠርጠሬ ይሆናል:: ለምን አልጠረጥርም? እጠረጥራለሁ ግን አልዋሽም ደስ የሚል ነገር ነበረው:: ምንም ሳታደርግ ምሳ በልታ በመኪና ተንሸራሽራ ሃምሳ ብር ብታገኝ ማን ትጠላለች?

......በሚቀጥለው ሳምንት እሁድ አልማዝን ሳገኛት አዲስ ሹራብ፣ ሁሌ ገበያ መሃል ወይ ሰው አድርጓት ሳይ የምታምረኝን አዲስ ልጥፍ ቆዳ ጫማ ገዝቼ ነበር:: ውድ አይደሉም::

ለብሼ ስታየኝ:

«ለምን ገንዘቡን ደህና ነገር አታደርጊበትም? ልትዝናኚበት ነው የሰጠሁሽ በይ እንኪ ይሄን» ብላ ሌላ ሃምሳ ብር ከቤቷ ልንወጣ ስንል በእጄ አስጨበጠችኝ:: መለስ ብላ:

«ውይ ሳልዘጋጅ» ብላ እዛው አለሁበት ሳታፍር እኔ እያለሁ በችኮላ ልብሷን መቀየር ጀመረች:: ወላ መለመላዋን ሆነች:: ለመጀመሪያ የሴት አፍረት አየሁ:: የአልማዝ የሚያስጠላ ባለ አፍሮ ነው:: ስደነግጥ ታዝባ 'ሴት ለሴት አይተፋፈርም አንቺዬ! ስንቴ ልንገርሽ?' ምናምን አለችኝ (ስንቴ ነግራኝ ይሆን እያልኩ ተመስጬ ስቆጥር፣ አንዴ ብቻ መሆኑን ደረስኩበት):: ወላ ለምን አያሳፍርም? ይሄ ድርጊቷ እኔን ከሀይን አፋርነት ማውጫ አንዱ ቴክኒኳ እንደሆነ የገባኝ መዓት ጊዜ አልፎ ነው:: መልዕክቷ *ፉቁትሽን ብትሆኚ መሰልጠን እንጂ ብልግና አይደለም* ልትለኝ ነበር::

## ወደ ጓሮ ዞሬ ድባቅ......

አዲሱ አመት መስከረም ወር መጀመሪያ፣ አልማዝ እንቁጣጣሽን ለምን አብረን አናከብርም ወይም አንውልም ብላኝ ከቤት ሰበብ ፈጥሬ ('በበአል ምን የሚሉት ነው ወዲያ ወዲህ ማለት!' እያለችኝ እማማ) ተያይዘን መናኸሪያ ጀርባ ሄድን:: የዛ ቤት ግቢ የበግ፣ የጨንራና በቅቤ የተጠመቀ ክትፎ ክትፎ ሲሸት ደረስንበት:: ሳሎን ስንገባ የተቀበለን ይሄ ጠረንና የድሮ ሙዚቃ ነው:: የሆነ ስሙን የማላስታውሰው ዘፋኝ:: እዛ ቤት የእውነት ሙዚቃ ሰምቼ አላውቅም:: ወይም ልብ አላልኩም:: ወይም የዛን ዕለት በአሉን በሆሆና በቻቻ ለማሳለፍ ያቀዱ ሰዎች አሉ:: ብዙ እንግዶች ይኖራሉ ብዬ ጠብቄ ነበር:: እኔ፣ አልማዝ፣ ያቺ ሰራተኛ የምትመስል ልጅ፣ ፍፁም አንድ ሌላ ከዚህ ቀደም ያላየሁት ሰውዬና ዕዮን ብቻ ነበርን:: አቶ ፍፁም በለመድነው አድናቆትና የፍቅር ቃላት ተቀበሉንና እንድንቀመጥ የተደላደለ ሶፋ አሳዩን:: እኔን እጄን ይዘው እየጎተቱ ወሰዱና ነብይ የተባሉት ሰውዬ ይቀመጡበት የነበረው ሶፋ ላይ አመቻችተው 'በይ እዚህ ሁኚ' አሉና የለበስኩትን ሹራቤን እንዳወልቅ ገፋፍተው በመጠኑ የተራቆተ ትንሽ ያላበው ጀርባዬን በቀስታ ዳበስ ዳበስ አደረጉት:: ማውለቅ የረዱኝ ይህቺን ዳበሳ ለማካሄድ ብቻ ይመስላል:: ማን ነካኩኝ ብሎ ጠየቃቸው? ማን ማውለቅ አቃተኝ ብሎ ነጨነጫቸው? በሁለገብ እንክብካቤ ከሌሎቹ ለእኔ የበለጠ ያዳሉልኝ ይመስላል:: 'በይ አንቺ ለበአል የተዘጋጀው ነገር ሁሉ ይምጣ እንጂ' ብለው ወደ ጨለማው ወደ ኮሪዶሩ ዞረው ሲናገሩ በደቂቃ ውስጥ፣ የእጅ መታጠቢያ ጊዜ እንኳን ሳናገኝ በነጭ እንጀራ ላይ የተዘረገፈ ደማሪ ጥሬ ዱለት መጣ:: አየር ውስጥ የተወው የጠረኑ ዳና የራበው ሆዴ ውስጥ ሚጢጢ የመሬት መንቀጥቀጥ ቀሰቀሰ:: አፌ ውሃ ሞልቶ እሱን እየዋጥኩ እጄን ለመታጠብ ወደ ጓዳ ሳልፍ አቶ ፍፁም 'ረሙና ኮካው የት ሄደ?' ሲሉ ሰማሁዋቸው:: ታጥቤ ስመለስ ለእኔም ለአልማዝም ለፍፁምም ለሌሎቹም በሚያማምር ብርጭቆ ረም በኮካ ተቀድቶልን የምንቀመጥባቸው ሶፋዎች ፊት ለፊት ተደርደረው ደረስኩ:: አቶ ፍፁም በሚያውቁበት ፉገራ 'እኔ ማክዳን ሳላበላ አልበላም' ብለው የመጀመሪያ ጉርሻዬን ሁለተኛውንም ሶስተኛውንም አራተኛውንም እየተግደረደርኩ ደሞ አምስተኛውንም

አጎረሱኝና 'በይ ከዛች እየጠጣሽ' ብለው በኮካ የቀላ ረም እንድጠጣ የነጠረ ቅቤ በተነከረ እጃቸው አመለከቱኝ:: በእሱ እያወራረድኩ ዱለቴን ስበላ ከመሃል በቁጣ 'ተይ እንጂ የእኔ ቆንጆ ክትፎው የት ሊቀመጥ ነው? ሳይሽ እንኩዋን ሆድሽ ማስቀመጫ የቀረው አትመስይም' ብለው ምን እንዳሳቃቸው አላውቅም አልማዝና ጽዩን እተቀመጡበት በሳቅ ተንፈራፈሩ:: ያኔውኑ የሳቸውን ጥሪ ይጠብቅ እንደነበረ ሁሉ ሞቅ ያለ፣ ቅቤው የጠፈፈ ክትፎ ከነሽክላው እንደ ድቡልቡል አይሮፕላን በአየር ላይ በዛች ልጅ (ፓይለት መሆንዋ ነው) እየተንሳፈፈ መጥቶ ከፊቴ ቆመ:: እየተከታተለ ለሌሎችም መጣላቸው:: በግማሽ ሰአት ውስጥ በእርግጥ ያለሁት ለእንቁጣጣሽ ጊዜ እንደሆነና ይሄም በትክክል በአል እንደሚመስል እያሰብኩ ሳለሁ በጥጋብና በመጠጥ እንደተዳከምኩ ገባኝ:: በአልጠበቅሁት ድፍረት ረሙ እየጣፈጠኝ ጠጣሁና ስክሬ ስለማላውቅ ደበተኝ:: ሞቅ ሳይለኝ እንዳልቀረ በደከመ ድምፅ ስናገር ሁሉም እተቀመጡበት ያሳበው ግንባራቸውን እያከኩ በሳቅና በፌዝ ተቀበሉኝ:: ቡናና ሻይ ጠጥተን አንጉል ሆዳችንን ከምንነፋ ከዚሁ ከረሙ እንጨምር ተብሎ ለሌላ አንድ ሰአት እነሱ ሲያወሩ፣ እኔ እየሰማሁ ቆየን:: ሞቅ ሲለኝና ይሄም የሞቅታ ስሜት ሊያስፈራኝ ሲጀምር በምሰማው ነገር ቀልድም ይሁን አይሁን ብቻ ስስቅና ስንተከተክ አቶ ፍፁምም በላብ በሚያዳልጥ እጃቸው እየዳበሱኝና እያዳነቁኝ ምሽት ሆነ:: ምሽቱን በመስታወት መስኮት በኩል አያለሁ:: በሁሉ ነገር ስለደከመኝ ግን መነሳት አልፈለኩም:: 'በሉ ቤቴ ልሂድ' ብሎ የመናገር አቅም አልነበረኝም:: ከመሃልም ቤተሰብ ያለኝ አይመስለኝም:: ከመሃልም ከመጣሁ ገና አንድ ሰአት እንኩዋን ያልሞላ ይመስለኛል:: እማማ ልታውቅብኝ እንደማትችል አምናለሁ:: እንዲህ እያሰብኩ ሳላውቀው የሚቀዳልኝን ረም ሳላቋርጥ እጠጣለሁ:: ከመሃል ፅዮንና ወዳጇ አንድ ቦታ እንደርሳለን ግብዣ አለብን ብለው ተሰናብተውን ሲወጡ፣ እኔ፣ አልማዝና (እሷ ልታግባባኝ እንደሆነ በሁዋላ ተረዳሁ) አቶ ፍፁም ብቻ ሳሎን ተጎልተን ቀረን:: በጨዋታ መሃል አቶ ፍፁም ሳል ሳሉና ኮስተር ብለው ሁለታችንን እያቀያየሩ እያዩ:

«አንድ ቁም ነገር ሳሳያችሁ፣ ለእንቁጣጣሽ ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ» አሉንና ሳቁ:: አልማዝም?

'ምን አስቀምጠሃል? ያንተ ነገር......ለምን እዚህ አታመጣውም ከምንነሳ' እያለችና ይሄን አባባሏንም 'እስኪ እንይለት እሱ እኮ የማያደርገው ነገር የለም ሂሂሂ' በሚል ተቃራኒ አባባል እየሰረዘች፣ ወደ ቤቱ ጀርባ 'እንሂድ' ብላ ከተቀመጥንበት ተነሳን:: ከተቀመጥኩበት ስነሳ አዞረኝ:: እንዳዞረኝ መናገር አልፈለኩም:: አልማዝ 'ለሁለታችንም ነው የገዛህልን ወይስ ለእሷ አዳላህላት:: ለእሷ ካዳላህ ፍፁም ሙት አላናግርህም ሂሂሂ' እያለች ከእኔ ቀደም ቀደም ብላ ኮሪዶር ውስጥ ገባች:: ሽሚያ ላይ ያለች ትመስላለች:: መስከሬ አሳፍሮኝና እንግዳ

ልምድ ሆኖብኝ በቀስታ እየተራመድኩ ስከተላት፣ ቆም ብላ 'ለሁለታችንም ነው? ለሁለታችንም ነው?' እያለች ስትናገር አቶ ፍፁም ያልሰሟት መስለው ራመድ ራመድ እያሉ እየመሩን አንድ ክፍል ውስጥ ተከታትለን ገባን:: ልታበረታታኝ ከኋላዬ የነበረችው አልማዝ ቶሎ መለስ ብላ ከክፍሉ ወጣች:: የት ሄደች ብዬ ዞር ስል እንዲህ እያየሁ በሩ በቁልፍ ከውጭ ተዘጋ:: ያኔ ገባኝ:: የዚያ የቁልፍ ድምፅ እስከዛሬ ጆሮዬ ውስጥ ያቃጭላል:: ሰማይና መሬት ዝም ቢሉና እግዜር ከንፈሩን አንዴ ብቻ ሲመጥ ብንሰማ:: የዛ አይነት ነፃነት አለው:: የዛ አይነት ብቸኛ ድምፅ::

አቶ ፍፁም ትልቅ ሰው ናቸው:: በዕድሜም ይሁን በአካል:: በፍርሃት እየተርበደበድኩ፣ እየተጨነቅሁ:

«አልፈልግም ልውጣ!» ስላቸው

«ነይ የእኔ ሸንኩርት»

(የዕውነቴን ነው የምለው ዛሬ ድረስ ሸንኩርት ያለበት ነገር ማለቴ ምግብ አልበላም፣ ከበላሁ ሸንኩርቱ በመቁላላት መጥፋት አለበት:: ባይታየኝ እንኳዋን "አለው' ከተባልኩ ቋቅ ይለኛል)

ተጠግተው ወገቤን በሁለት እጆቻቸው ጠፍረው ያዙኝ:: መተንፈስ ሁሉ አልቻልኩም:: መነቃነቅማ አይታሰብም:: ያን ያህል ትንሽና ቀጫጫ ነበርኩ:: (የደሃ ደርባባ የለውም:: ምን በልቼ ወገብና ትከሻ ላውጣ) ከመሬት አንስተው እንደ ቀላል ዕቃ ግድግዳ ተጠግቶ የተዘረጋ አልጋ ላይ ጣሉኝ:: ብዙ ለፈለፍኩ......

«ልጅ የለዎትም ወይ!» «ሴት ልጅ የለዎትም ወይ!» ምንም ነገር አላቆማቸውም::

ብገለባበጥ፣ ብፍጨረጨር አይኖቻቸው ፈጠው ሊገሉኝ ደረሱ:: ልምድ ሳይጠይቅ አይቀርም:: የመገለባበጥ የመፍጨርጨር ልምድ የለኝም:: ይሄ ችሎታ እንዳነሰኝ ሲገባኝ አለቀስኩ:: እንደ ዛን ዕለት ለማንም ሰው ጮኬ አልተናገርኩም

(ዛሬ እጠላለሁ፣ እጉልቁን መናገር)

በትልቅ እጃቸው ፊቴ ላይ አንዴ ሲያጮሉኝ፣ ቀና ካልሁበት አልጋ ላይ ራሴን ስቼ ተመልሼ ወደቅሁ(እንደዛ ጉልቤ ተጠቅሞ ያላደረገ ወንድ ቀሽም ሴታ ሴት ነው......እያሉ ሲያወሩ ሰምቼአለሁ:: ይሄ ስሙ በሁለት ቃላት 'ደሞ መለማመጥ' ይባላል):: ከመሃል ባነንኩ:: በጀርባዬ ነኝ:: ሰባንን በመጀመሪያ የተሰማኝ ታች ጋ የሚያቃጥለኝ እሳት ነበር:: እግሮቼ ዝለው ግራና ቀኝ ተከፍተዋል (እግሮቼ እንደዛ ቀጫጫ አይመስሉኝም ነበር:: እንዲህ ተንጋልዬ ራቁቴን ያየሁት ለመጀመሪያ ጊዜ ስለሆነ ይሆናል) ዳሌዬ ላይ ግራና ቀኝ ይወጋኛል:: ብሽሽቴ የቆሰለ ይመስለኛል::

ከቂጤ ስር የሚሞቅ እርጥበት ይሰማኛል:: እክፍሉ ውስጥ ማንም የለም:: ቀና ብዬ በከሬል እያቃሰትኩ ተቀምጬ እግሮቼ መሃል አየሁ:: እንሶላው ደም ተንጠባጥቦበታል:: እንደ ገና እራሴን ሳትኩ......ለሁለተኛ ጊዜ ስባንን አቶ ፍፁም የተጠረማመሰ ቲ ሸርት ለብሰው፣ እስከ አንገታቸው የበቀለ ሽበት የተዘራበት ደረታቸውን አራቁተው፣ አልጋው ጎን ወንበር ስበው፣ አተኩሁብት ተጠግተው እያዩኝ ተቀምጠዋል:: የተጣጠፈ ውሃ አረንጉዋዴ እንሶላ እላዬ ላይ ተጥሎአል:: ያን አንሶላ አልረሳውም::

(ውሃ አረንጓዴ ቀለም ላይ ወደ ላይ ይለኛል፣ ሰላጣ አልበላም ዛሬ)

ስነቃነቅ ከአንሶላዬ እንደ መጀመሪያው አይነት እርጥበት አልተሰማኝም:: ከዛ ስር የፈሰሰው ክብርናዬ፣ ለሁለመናዬ ምን ልበል እለ አይደለ ትምክህት የሰጠኝ ቦታ ነበር:: ብቻ እንደዛ ዓይነት ስሜት፣ ሁልጊዜ አዲስ የመሆን ስሜት:: አንዱ 'ሃብት አለኝ' ሲል፣ አንዱ 'ትምሕርት አለኝ' ሲል አለ አይደለ እኔም 'ድንግልና አለኝ' ምናምን ለማለት ሳይሆን አይቀርም:: እሳቸው እንደተቀመጡ እኔ በጀርባዬ ተኝቼ በዝምታ ብዙ ቆየን መሰለኝ:: ያ ዝምታና ያ የቅርብ ዕርቀት የሚረሳኝ አይደለም::

«ይቅርታ አድርጊልኝ የእኔ እመቤት እንዲህ አልመሰለኝም» አሉ ፍፁም ከርመው፣ እንደሚያለቅስ ሁሉ እጆቻቸውን ለልመና ዘርግተው:: አልመለስኩላቸውም:: ገልጬ ደግሜ ራሴን ማየት አፍሬአለሁ:: ጡቶቼ እኮ ገና ከደረቴ አጥንት አልተለያዩም:: ልጅ ነኝ:: አዘንኩ:: አሰብኩ:: እንግዳ ዓይነት ሃሳብ:: ለምሳሌ ያ የክፍሌ ልጅ እዛ ጥግ ዴስክ ከግድግዳ ተለጥፎ 'ታዲያስ' የሚለኝን ስንቴ በማላውቀው ዓይነት ባልተረዳሁት ስሜት በሕልሜ አይቼው ነበረ? ያ አስተማሪዬ ሲስቅ የጥርሱ ትልቅነት የሚስበኝ ሳየው የሚያስደነግጠኝ:: እሱን ለምን ደግሜ ደጋግሜ አሰብኩት? ከፋይ ኮቱ በጣም ያምርበት ነበር:: እነዚህ ሁሉ አሁን የሌላ አገር ሰዎች መሰሉኝ:: በምንም በምንም ከእነሱ የማያገናኘኝ የሆነ ሌላ የስሜት ጎሳ ውስጥ እንደገባሁ ቆጠርኩት......አቅደዋልና ከመጀመሪያው በር ቀርቅረው ከልጃገረድነቴ ሕልም ለያይተው ሊወጉኝ፣ ሲጀመር ለራሳቸው ምለዋልና እንደምንም ብለው ሊገሥሡኝ......ግራ እጄን ይዘው እየዳበሱ ያባብሉኝ ጀመር:: ያዘኑ ይመስላሉ(ያዘነ የመሰለ ፊት ዛሬም አልወድም:: ከጀርባ የደበቀው ነገር ያለ ይመስለኛል)

### የምጠላቸው ነገሮች

### እየበዙ የመጡ

### አይመስልሽም?

ከደቂቃዎች በፊት የደፈሩኝ ሰው አይመስሉም:: ፍፁም እጄን ለቀው ተነሱና መኝታ ቤቱ ጎን ያለ መታጠቢያ ክፍል ገብተው በር ዘጉ::

ያኔውኑ አንሶላ ገልጬ አየሁ። ደም የለም። ግራ ጭኑ ከውስጥ ዝቅ ብሎ ሲጠረግ የቀረ የደም ልስን አለ። ራሴን በእጄ ልፈትሽ አልፈትሽ እያልኩ በፍርሃት የማደርገው ጠፍቶኝ ሳለ፣ ፍፁም ከመታጠቢያ ቤት ወጡ። ቶሎ ጉልበቴን አጥፌ በጎኔ ተኛሁ። እንዴት ነው እንትኑን መደበቅ የምችለው? ፊት ለፊቴ መጥተው ወገባቸውን ግራና ቀኝ ይዘው ቆሙ። በውስጥ ሱሪ ናቸው። ፈገግ ይላሉ(ይሄ ፈገግታቸውን ሳይ ሁል ጊዜ ነገር እንዳሰቡ ይገባኛል) በጆርባዬ ዞረው ተጠግተውኝ ጋደም አሉ፡

«ተውኝ በእግዜር ተውኝ» ምናምን ስላቸው ይግረምሽ ብለው እላዬ ላይ ወጡ።

ሲጀመር በድንጋጤ ፊልጌ ያላገኘሁትን ለቅሶዬን ቀጠልኩ።

«አይዞሽ የእኔ እመቤት» አሉ። (ይሄ 'አይዞሽ' ይሄ ሳንፈልግ እያደረጉን 'አይዞሽ'። 'አንዴ ከጀመረች ሳብ አድርጎ ተም ካደረጓት ሴት ሴት ናት' ነገር። አልገባቸውም ደሃነቴ እንደ ሆነ። ወይስ ሴትነቴ ነው? አባቴ ጠንካራ ቢሆን እዚህስ እመጣ ነበር? ጠንካራ ማለት መቼም ሃብትና ፖለቲካ ነው)

'አይዞሽ' እየተባልኩ ጎዳና ወጣብኝ......በእርጉም ተጀምሬአለሁና እግረኛ ሆንኩ።

**እሳቸው በፈጠሩት መንገድ ያልተመላለስኩ**

**እስኪ እጅህን አውጣ......**

## አንዳንዶቹ የሚስቁት ጋለል ብለው ነው

......እንደዛ አይነት ነገር ካጋጠመኝ በሁዋላ አልማዝን ማየት ፈራሁ:: አልማዝን ማየት ጠላሁ:: አንድ ቀን እናቴ አንድ ቦታ ልካኝ እዛ ደርሼ ስመለስ ቤቴ ልገባ መንገድ እያቋረጥኩ ሳለሁ፣ አንድ ልጅ እየሮጠ መጥቶ 'ሰው ይፈልግሻል' አለኝ:: ብጉዋጉዋም፣ የሚፈልገኝ ሁሉ የሚያባልገኝ እየመሰለኝ 'ማነው የፈለገኝ?' ስለው፣ እንደማያውቅ ሁሉ 'እንጃ አንዲት ሴትዮ ናት እዛ ጋ ቆማለች' አለኝ:: በወሬ ጉጉት 'እሺ' ብዬው ወደ ኋላ ተመልሼ እየተከተልኩት ስሄድ መንገድ ዳር አልማዝን በረዶ የመሰለ ኩታዋን ለብሳ ቆማ አገኘሁዋት:: በአእምሮዬ ቶሎ የመጣው እኔ የለበስኩት እሷ የሰጠችኝን ልብስ መሆኑ ነበር:: ገና ሳላናግራት ቀደም ብላ ያሰብኩትን እንዳነበበች ሁሉ:

«የለበስሽው ያምራል! ጥሩ እመርጣለሁ አይደለ?!» አለችኝ:: ያላስጨነቀኝን::

ልጁ አተኩሮ አየኝ::

«በል አንተ! ሂድ! መልዕክት አድርሰሃል» አለችው

ልጁ እየተገላመጠ እያየን ትንሽ እንደራቀን፣ አልማዝ ድምፅዋን እንደማባበል ዓይነት ዝቅ አድርጋ:

«አይዞሽ......እኔ እንደገዛሁልሽ ማንም አያውቅም፣ እሁድ ይመችሽ እንደሆነ እዛ ቦታ ላግኝሽ:: ደስ ካላለሽ......»

*ስለ ልብሱ ሰወራሁ?* ዞር ብዬ ወደ ቤቴ መንገዴን ስጀምር:

«እቤትሽ ሰው እልካለሁ ድንገት ካልመጣሽ:: እናትሽ ይቆጡኛል ብለሽ ነው?» አለችኝ:: ደነገጥኩ:: 'የምፈራ መሰለሽ?' አልኩ ለራሴ:: እሷ እንድትሰማኝ ማድረግ ፈርቼ::

«አትፍሪ አይዞሽ:: የሚያስፈራ ነገር የለውም:: የምነግርሽ ሚስጢር አለ......» አለች:: ሌላ ነገር ልሰማ አልፈለግሁም:: መንገዴን ቀጠልኩ:: በሚቀጥለው ቀን ጠዋት አራት ሰዓት አካባቢ ቤቴ ግቢ እፍንጫው

የተሸነቆረ የአባቴን ካልሲ እያጠብኩ ከእማማ ጋር ሳወራ፣ ትናንት ከመንገድ ላይ የጠራኝ ልጅ የግቢያችንን በር ከፍቶ ገባና እኔንና እማማን እያቀያየረ እያየ በዝምታ ቆመ::

«ምነው ልጄ? ምነው?» አለች እማማ በመገረም::

«ለማክዳ መልዕክት ላደርስ ነው የመጣሁት» አለ::

«የምን መልዕክት ነው?» ስትል ገና ለገና ይነግራታል ብዬ ፈርቼ ልጁን ገፋፍቼ ከግቢው አስወጣሁና ስጠይቀው:

«አልማዝ ድንገት ወደ ታች ካለፍሽ በዚህ ብቅ በይ ብላሻለች» አለኝ::

ወላ አቦ ብደበርም፣ ለቤተሰቦቼ በተለየ ቄንጥ አሳብቃ ልታስጠምደኝ ያሰበች መስሎኝ 'እንደምመጣ ንገራት' ብዬው ልጁን መለስኩት:: እኔን ወደ አልማዝ አባረረኝ ልበል እንጂ:: ወይም አልማዝ ወደ አልማዝ አባረረችኝ አይነት:: ተመልሼ ቤት ስገባ እናቴ:

«ምን ይፈልጋል ልጄ?» ስትለኝ ምንም መልስ ስላልነበረኝ ብቻ

«የማውቃት የሰፈሬ ልጅ ብርድ መቶአት ተኝታ ክሊኒክ አብሬአት እንድሄድ ነው:: እዚሁ ሽሮሜዳ» አልኩና ዋሸሁዋት::

የረጠበ ካልሲዬን አጥቤ ለመጨረስ ቁጢጥ አልኩ:: እናቴ ምን ትላለች? ምንም ልትል አትችልም:: በቀላሉ ውሸት መፍጠር መቻሌ ትንሽ ሳያስደስተኝ አልቀረም:: ታዲያ የማጥበውን አጥቤ ስጨርስ በግምት ከሁለት ሰዓት በሁዋላ ጉርጉሱም ሄድኩ:: አልማዝ ገና ስታየኝ ተንኮል እንዳልሰራችና እኔ በፈቃዴ እንደመጣሁ ሁሉ ሳቅ ሳቅ እያለች:

«ቀልጣፋ መጣሽ? እንዴት እንደናፈቅሽኝ የዕውነት:: በማርያም ነይ ቁጭ ብለን የማሳይሽ አለኝ» ጠሬ በመላኪ ስለተበሳጨሁ የማባበያዋ አማርኛ አላስደሰተኝም::

«ለምን እንደዚህ ታደርጊያለሽ? ወላጆቼ ቢሰሙስ?» ስላት፣ አልጋዋ ጻር ተቀምጣ፣ ፊቷን በሐዘን አኮማትራ፣ አንድ እጅዋን በጡቷ አቅጣጫ ደረቷ ላይ አስቀምጣ፣ በሚያምር ዜማ:

«ውይ የእኔ እመቤት የማስጨንቅሽ አልመሰለኝም......ውይ! አንዳንዴ እኮ ልብ ቢስ ነኝ......ማርያምን......እንቺን ብቻ ሳይሆን በቃ......ውይ አትቀየሚኝ» አለች፤ 'ውይ አትቀየሚኝ' ስትል ማዘንና ቁጭት የተቀላቀለበት ሁኔታዋን ቀንሳ ሳቀች:: የፈለገችኝ የኪስ ገንዘብ እንድትሰጠኝ እንጂ ለሌላ እንዳልሆነ፣ ለማንኛውም ፍፁም የሆነ ዕቃ እንደላኩልኝ ነገረችኝና ገና ምን እንደሆነ ሳልጠይቃት በፖስታ የታሸገ ነገር ሰጠችኝ:: እሱን ሳልከፍት እያገላበጥኩ ሳይ:

«ክፈቺውና እንየው:: ምንድነው?» አለችኝ

መክፈት ከብዶኝ ስልፈስፈስ፣ ከእጄ ነጠቀችና ከጠባቡ በኩል በአንድ ጊዜ ትርር አድርጋ ቀደደችው:: የተቀደደውን ፖስታ ስትዘቀዝቀው ከውስጡ ሁለት ድፍን መቶ ብሮች እንደ ቅጠል እየረገፉ ወጡ:: በመገረም አፏን ከፈተች:: እውነቴን ነው ብሮቹን ለቅማ ቁና ቁና እየተነፈሰች በእጄ ስትሰጠኝ ልቤ ተሰበረ:: (ያኔ ቲያትር መሆኑን አላውቅም) ግን ብዙ መዋሸት ማንንም አይጠቅምምና የመጀመሪያ ሕመሜ እየጠፋ ከዛ ስር ስር ግን አምልጣ የመጣች የስጋ ደስታ ሳትናፍቀኝ አልቀረችም:: እንኳን እንደዛ እንደዛ ተደርገን ቀርቶ ጀርባችንን ሲያኩን ደስ ደስ ይለን የለ::

በበነጋታው እሁድ ከአልማዝ ጋር መናኸሪያ ሆቴል ጀርባ ያለው ቪላ ሄድንና ሚካኤልን፣ ማርያምንና ጠቅላላ አለምን በሚያስገርም መግደርደር ከፍፁም ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ በፈቃዴ ልብሴን አወለቅሁ......አልማዝ እዛች ክፍሏ እንደተኛች ሳትስቅ አልቀረም('እኔ በትክክል የማስበውና በደንብ የምስቀው ማታ አልጋዬ ላይ ሆኜ ነው' ብላ ያለችው ትዝ ይለኛል)::

## የወጣ ገባው ርዕዮት

የሆነ ቀን ከአልማዝ ጋር እዛው ቪላ ቤት ተገናኝተን (ያለ እሷ በቀጥታ እዛ ቤት መሄድ ጀምሬአለሁ) ምሳ በልተን እጆቻችንን ለመተጣጠብ ተያይዘን ባኞ ስንገባ የተፈጥሮ ነገር የእግዜር ስራ እንደሆነና ማፈር እንደማይገባ መከራኝ የምታወልቀውን አውልቃ አጠገቤ ሽንቷን ማንፎልፎል ጀመረች:: እዛው እያማጠች ፍፁምና ጓደኞቻቸው የታወቁ ሃብታሞችና አገር መሪዎች እንደሆኑ አውርታ ስሜቴን ስትጠይቀኝ ግልፅነቷን ላሳፍረው አልፈለኩምና ደስ እንደሚለኝ ነገርኳት:: ግን እሷ ዘርዝራ ያልጠየቀችኝ እኔም ደፍሬ ከአፌ ያላወጣሁት (እንዴት በቃላት ይቀናበራል?) ነገር ነበር:: ከፍፁም ቀድሜ መኝታ ቤት ገብቼ አንሶላ መሃል ተኝቼ ስጠብቃቸው ወደ ተኛሁበት መጥተው ጎንበስ ብለው ሊስሙኝ ሲያሞጠሙጡ ቅር ይለኛል:: ከቀበቶአቸው ላይ በቸልታ ዘንበል ያለውን የቦርጫቸውን የስብ ድራቶ ሳይ፣ የሰፊ ቡናማ የቆዳ ቀበቶአቸውን ዘለበት እያንካኩ ሲፈቱ ስሰማ፣ አልጋ ላይ ለመቀመጥ ሲያምጡ ስሰማ፣ ቢወረወር ሽሮሜዳን የሚሸፍን ውስጥ ሱሪያቸው ስር መኮማተር በጀመረ ቆዳ የተሸፈኑ ቀጫጫ እግሮቻቸውን ሳይ፣ ጡቶቻቸው ዙሪያ ያሉትን የግራጫ ፀጉሮችን ሚኒ ጎፈሬ ሳይ፣ የአራዳ አፍ መስማት የለመዱ ጆሮዎቼ፣ የሽማግሌ አማርኛ ሲያዳምጡ ቅር ይለኛል……ልብሳቸውን አወላልቀው ጎኔ ጋደም ብለው ሲነካኩኝ፣ በወሬ አዘናግተው አጫዋውተው ከስራቸው አስተኝተው በከባድ ገላቸው ሲሸፍኑኝ ደስ ይለኛል:: ሁሉ ነገር አልቆ ልብሴን ለመልበስ ስነሳ ወይ ደክሞኝ ተንጋልዬ በሰመመን ውስጥ ሁኔታዬን ሳስበው ያስጠላኛል:: ይኼን ይኼን ዘርዝሬ አልነገርኳትም:: ለአልማዝ ባልነግራትም ልምዱ ስላላት ብቻ የማስበውን ጠርጥራ የውስጥ ሱሪዋን ወደ ላይ ጎትታ ቀሚሷን እየመለሰች:

«ቂል አትሁኚ፣ ሌላም ማውጣት ትችያለሽ:: አንዳንዴ ሽውጂ አቸው» አለችኝና አቅፋኝ በሳቅ ጦሽ አለች:: እንዲህ አይነት ምክር ባትመክረኝም፣ መሆኑ አይቀርም ነበር:: ሲሆንም አልነገርኳትም:: ሰይጣንን ለመሸወድ ከራሱ ከሰይጣን ብልጠት መማር አለብን መሰለኝ:: እንዲህ የሚሆንበት ምክንያት ለምንድነው? የተፈጥሮ ሕግ ስለሆነ ነው? ግን ሁሉ ሆኖ ቤቴ ተመልሼ ለብቻዬ የሚሰማኝ፣ አልማዝ ራሷ እንደ

ሌላው ጉዳይ ያልገባት ወይም ገብቷት ያልነገረችኝ ስሜት ነበር:: ምን እንደሚባል አላውቅም......የሆነ ነገር ከውስጤ የተሰደደ መሰለኝ:: መሂዱ ትዝ ሲለኝ ብርድ ልብስ ደራርቤ እንኳን ቢሆን የሚያንቀጠቅጠኝ......አለ አይደለ......እንደ ብርድ......ግን ብርድ ያልሆነ......ስሜት ይሰማኛል......

ቀስ በቀስ በየቦታው ከፍፁምና ከሌሎች ጋር ስዞር አዲስ አባ ውስጥ ወጣት ሴቶች እየተመለመሉ በሽሮሜዳ 'የሚማግጡባቸው' (ነው የሚባለው?) አራት ቦታዎች እንዳሉ አወቅሁ:: ያለ ራሴ እቅድ ልጃገረድነቴ መሰበሩ አንዳንዴ ስለሚቆጨኝ፣ እንደእኔ ያሉ ገና ሃይ ስኩል ያልጨረሱ ወይም ያልደረሱ ልጃገረዶች ሲበላሹ፣ በሽማግሌዎች፣ በባለስልጣኖች፣ በፀረአብዮተኞች፣ ሶሻሊስት ነን በሚሉ ፖለቲከኞችና ሃብታሞች እንደ አልማዝ ባሉ አቃጣሪ ተለቅመው ይሁን ተጠብሰው፣ አለሁበት ቪላ ተነድተው ገብተው፣ ለሰጡት፣ ምናልባትም ላገኙት ደስታ የተሸለሙትን ሳንቲም ግድግዳ ተከልለው ቦርሳቸው ሲጨምሩ፣ የሆነ እርካታ ይሰማኛል:: የሆነ *'ዋጋሽን ነው'*:: እንዲህ ማሰቤን አያውቁትም:: ብናገረውስ እኔ ማን ነኝ? ስንገናኝ የምናወራው ስላለንበት ሁኔታ አይደለም:: ለሚያየን ከአዘናጋችን የታደልን ይመስለዋል:: በቀፈልነው እቃ እንፎካከራለን:: በአንዱ ወዳጅ የመኪና አይነት ራሳችንን እናወዳድራለን:: ባይሆኑላትም ደግ እንደሆኑላት የምታወራ አለች:: እያወቅንባት ራሳችንም እንሰራዋለንና እንከራከራትም:: ልቦቻችንን በቲያትር እንሰብራለን:: የራስን እምነት ደብቆ ለሌላ ሰው ትልቅ መስሎ ለመታየት መዋሸት ራስን ከማጥፋት ምን ለየው? ከብቸኝነት ግን ያወጣናል:: በልቤ ብታረብም ብቻዬን እንዳልሆንኩ አውቃለሁ:: ስንገናኝ በድፍረት እንገባበዛለን ግን ያሳለፍነውን ዘርዝረን አናወራም:: አንዳንዴ ልጅ ስለሆንኩባቸው ነው እላለሁ:: የሚገባኝ ግን ፉክክር ውስጥ እንዳለን ነው:: ተበልጠንም እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ በማናያቸው የአዛዦቻችን ግንባር እንገዛለን:: እነሱ ባይኖሩም እነሱ አብረውን እንዳሉ ሁሉ ለመልካምነታቸውና ለቸርነታቸው እንከራከራለን:: የተበለጥኩ መስሎኝም ትንሽነት የተሰማኝ ጊዜ አለ:: በመንገድ ስንገናኝ ሰላምታችን የሞቀ ነው:: ስሞቻችን እንኳ ስንጠራራ እንዲፈጥን ያጠረ ነው:: ለሌላ ለምን ሊጠቅም? አዛለች (አዚ)፣ ዐይንአለም (ዐይንሽ)፣ ማክዳ (ማኪ)፣ ሮማን (ሮሚ)፣ አሰፉ (አሲ)፣ መንበረ (ሜቢ) የመሳሰለ:: ሲፈለግ ለሽንገላ ይሁን ለምን አላውቅም እነዚህ ስያሜዎች መጨረሻ ላይ 'ዬ' ይቀጠላል:: ለፍጥነት ካልሆነ ለማሳመር ነው ይሄ ሁሉ? ዛሬ ስም መጨረሻ ላይ 'ዬ' መቀጠል ሲቀጥሉም መስማት አልወድም:: አደገኛ ቃል ይሆንብኛል:: ሆዴን እየቦረቦርኩ ልቤን እየቆፈርኩ ትክክለኛ አጠቃቀም እንደሆነ ስልዬ መልስ ለማግኘት ጊዜ ይፈጀብኛል:: ግን ሁላችንም በዚህ ቲያትር ውስጥ በታኮ ጫማ እንመላለሳለን:: የሲአል ትልቁ ምኞት የብዙ ሰዎች እዛ መሰብሰብ ይመስለኛል:: ብዙ ጨዋታ አለ:: *'ዋጋሽን ነው'* ስል ታዲያ ራሴንም በቃል እንደ መቅጣት ነው:: ዋናው መደጋገፊያችን የምቀኛው

ብዛቱ አይደለ:: አልማዝ የገባትና የተራቀቀችው፣ ብዙ ያየችውና አንጠርጥራ ያወቀችኝ (እሷ እንደምትለው)፣ የተከዘኩና የተደበርኩ ከመሰላት:

«ስንቷ ትቀናብሽ መሰለሽ፣ ዘና በይ» ትለኛለች::

እግሬ መሃል ያለችው፣ ጥጥ በርትቶ ያላቀጠቀጠባት ነገር እንዲህ አይነት ወጣ ገባ ትከተኛለች ብዬ አላሰብኩም:: ማናችንስ?

## ዕጣ ፈንታ

እንዴ ፍፁምንና ሌሎችን ሰዎች ለሆነ ጉዳይ እፈልጋቸዋለሁ ብላ ከአልማዝ ጋር ተያይዘን መጀመሪያ የሄድኩበት ቤት ሄድን:: እዛው እንዳለን ለአንዳቸው ስልክ ደውላ 'ትንሽ እንቆያለን' ስላሏት ካርታ እየተጫወትን እንጠብቃቸው ብላኝ ካርታ መጫወት ጀመርን:: (ሁለት አይነት ካርታ ጨዋታ አስተማረችኝ) አንድ ሰአት ያህል እንደተቀመጥን ፍፁምም ይሁን ሌሎቹ ወንዶች በስራ ብዛት (አንዳንዴ የውሸት የሚሰሩ ይመስለኛል) ሳይመጡ ሲቀሩ፣ 'እርቦኛል እራት እንብላ' ብላ ያቺን ባለጉንጉን ሰራተኛ ቀይ ወጥ እንድታመጣልን ነገረቻት:: (እስከዛ ቀን ድረስ ቤቱ ከመኪኖቶች ከተወረሰ በሁዋላ ባለቤቱ ማን እንደሆነ አላውቅም) ልጅቷ እንጀራ በትንሽ ትሪ፣ ወጥ በጎድጓዳ ሰሃን ይዛ መጣች:: እንጀራ የተዘረጋበትን ትሪና የወጡን ሰሃን ሶፋ መሃል ያለው ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠች:: ከአልማዝ ጋር እጃችንን ልንተጣጠብ ወደ ሽንት ቤት ሄድን:: እየታጥበን እያለን:

«ማክድዬ አንቺ ብዪ: አትጠብቂኝ እኔ እዚህ እቆያለሁ» አለችኝና ሽንቷን ለመሽናት ቀሚሷን ከፍ አድርጋ፣ ውስጥ ሱሪዋን እዛው ማውለቅ ጀመረች:: ለምን ደጋግማ እንዲህ እንደምታደርግ እንጃ::

ቶሎ ወጥቼ ወደሳሎን ስመለስ ከእንጀራና ከወጡ ጎን የጎርዶን ጂን ጠርሙስ፣ ከእሱ ጎን ደሞ ቤቢ ጠርሙስ የመሰሉ መለኪያዎችና የተከፈተ አምቦ ውሃ ተቀምጠው ደረስኩ:: ወደ ነበርኩበት ሶፋ ተመልሼ ጠርሙሱን አንገቱ ላይ ይዤ በቀስታ እያሽከረከርኩ ሳይ:

«ጋሼ ፍፁም 'ማክዳ ከመጣች አቅርቡላት ብሎን ነው» አለችኝ ሶፋው ዙርያ እንደ እሳት እራት ወዲያ ወዲህ የምትለው ሰራተኛ ልጅ::

ምንም ሳልግደረደር ጂን ለራሴ ስቀዳ ልጅቷ ትሪው ላይ ያለውን እንጀራ መዘረጋጋት ጀመረች:: በደንብ ካነጠፈችው በሁዋላ ምንም ሳልጠይቃት ቀይ ወጡን እላዩ ላይ አፈሰሰችው::

*ምን ሆንሽ?* አይነት አየሁዋት:: አስተያየቴ ገብቷት:

«እንዲህ ነው ለአልማዝ የማደርግላት:: እንግዲህ አብረሻት ከበላሽ ......» አለች ፈገግ ብላ:: አነጋገሯ ሰልጠን አለብኝ:: ያላስለመደችኝ አይነት ወይም ያልጠበቅሁት አይነት በመቀላጠፏ ግራ ቢገባኝም፣ ችላ ብዬ፣ አልኮሌን ቀዳሁና እንዴ ተጎንጭቼ መብላት ጀመርኩ::

በጣም የሚጣፍጥ መረቁ በዛ ያለ ቀይ የስጋ ወጥ ነው:: ከቀለሙ ቅቤው፣ ከቅቤው የበርበሬው ልክ መሆን:: እንጀራው ለምለም ከመሆኑ የተነሳ ግማሹን በቶሎ ጨረስኩ:: አልፎ አልፎ አልማዝ ትመጣ እንደሆን እያልኩ እየተንጠራራሁ ወደ ኮሪደሩ እያለሁ:: ወዲያ ወዲህ እያለች፣ ሳሎን እየገባችና እየወጣች የምታየኝ ወይም የምትጠብቀኝ ሰራተኛ ከገፅዋ ላይ ለአፍታ እንኳን የማይጠፋ ድምቀቱ ከፍና ዝቅ የማይል ቀጥ ያለ ስዕላዊ ፈገግታ ስታሳየኝ ቆይታ:

«ለአልማዝ ሌላ እንጀራ አመጣላታለሁ አንቺ ብዪ» አለችኝ:: ፈገግ ስትል ልጅ፣ ዝም ስትል ሴትዮ ትሆናለች:: ትከሻዬን በምንቸገረኝነት ነቅንቄ መብላቴን ቀጠልኩ:: የመጨረሻውን ልበላ የጉርሻዬን ሙልሙል ሳሰናዳ:

«ቆዪ! ቆዪ! ልጨምርልሽ ትሪ አትጥረጊ» አለችኝ

የጀመርኩትን ጉርሻ አለበት ተውኩና በመገረም ቀና ብዬ አየሁዋት::

«ሌላ እንጀራ አመጣለሁ! እንዲህ ሲጠረግ ቃቃትም ያስመስላል! እንጀራ ሞልቶ!» አለች ፈገግ ብላ::

በጨኸት የሚያናግር ምን ነገር እንዳጋጠማት እያሰብኩና እሷ ቆማ እያፈጠጠችብኝ ወጥ የተነከሩ ጣቶቼን አንከርፍፌ ተቀመጥኩ:: ትሪውን አንስታ ትሄዳለች ብዬ ስጠብቅ ያኔውኑ አልማዝ ፈንጠር ፈንጠር እያለች መጣች::

«ጥሩ በላሽ?» አለች ትሪውን እያየች

ልጅቷን ቀና ብዬ አየሁዋት:: የሚያምሩ ደቃቃ ጥርሶቿን አሳየችኝ:: 'ይኼውልሽ ጥርሴ፣ ፈልገሽው ነበር?' የምትል ትመስላለች::

«ሌላ እንጀራ የለም?» አልኩ አፍሬ:: ልጅቷ የነገረችኝን መናገር አልፈለኩም:: ማቃጠር መሰለኝ::

«አይ የማሳይሽ አለ» አለችና አልማዝ ገና እንደተቀመጠች ትሪውን ወደ እሷ ሳበችውና ከመሀል የቀረችውን አንዷን ጉርሻ እንድበላት በአመልካች ጣትዋ አሳየችኝ:: ጉርሻዋን ከተጎለተችበት አነሳሁና እየጎረስኩ ቀና ብዬ ያቺን ልጅ አየሁዋት:: ታየኛለች ደሞ አታየኝም:: (ስምዋን ለምን አላውቀውም?) አልማዝ የሆነ ነገር እንደሚፈልግ ሁሉ ትሪውን በትኩረት መመልከት ጀመረች:: ግራ ገባኝ:: ልጅቷ ፈገግታ ከውስጥዋ የሚወጣ አይመስልም:: ልክ እንደወረቀት ገፅዋ ላይ የተለጠፈ ነው::

ሁኔታዎች እንዳሻቸው ቢለዋወጡም ፊቷ ላይ ያለው የዜሮ ሻማ ብርሃን ወጋገን አይጠፋም:: እኔን ስታይ፣ እያየሁዋት እንደሆነ አውቃ አይኖቿን ወደ አልማዝ መለሰች

«ምን እያደረግሽ ነው?» አልኩዋት አልማዝን::

ፈገግ ብላ እያየችኝ፣ ልንገራት አልንገራት እያሰበች መሰለኝ:

«ዕጣ ፈንታሽን እያለሁ»

«የምን እጣ ፈንታ?»

«መረቅ አነባለሁ»

«የምን? እንዴት?» አልኩ በመገረም

ትሪውን በእሷ አባባል እያነበበች በየመሃሉ 'ማንበብ' ማለት ምን እንደሆነ፣ እንዴት እንደሚደረግ ቀስ እያለች ኮስተር ብላ አብራራች:: እንደ ማስጠንቀቂያም ሳይሆን አይቀርም ወይ ራሷን ስታቆለጳጵስ ለማንበብ የተፈጥሮ ስጦታ እንደሚጠይቅ፣ ብዙ ልምድም እንደሚያስፈልግ፣ በየሄደችበት አገር ይሄ ዕውቀቷን በተለያየ መልክ ስታዳብርና ስትራቀቅበት እንደኖረችና ለሺህ ሰዎች አንብባ ሺዎቹ እንደተደሰቱ ነገረችኝና በጥልቅ ተንፍሳ ትሪውን ጠረጴዛ ላይ መለሰች:: ለደቂቃዎች አፍዋን ስትጠርግ፣ አይኖቿን ስታሽ፣ ስታዛጋ ቆየችና:

«አንቺ አስገራሚ ነሽ» አለች

«በምን? እንዴት?» አልኩ በወጥ የተነከረ እጄን አንቀርፌ:: (ማንቀራፈፍ የሚያምርበት ሰው አለ:: እኔ አያምርብኝም:: ሲያንቀራፍፉ ዳንስ ለመጀመር የተሰናዱ ወይም ያገኙትን ለመዳበስ የቃጡ ይመስላሉ)

«ልዩ ዕድል አለሽ፣ ሃብት ይመጣልሻል:: ሰው ይሰማሻል:: ሰው ይወድሻል፤ ግን ምቀኛ ይበዛብሻል:: እንዲህ ምቀኛ የሚበዛበት ሰው አላጋጠመኝም:: ሕይወትሽ ምቀኛ ይበዛዋል:: ይታይሻል እዚህ ደመቅ ደመቅ ብለው የሚታዩት ቀያይ ወጦች፣ ደሞ እነሱ የከበቡት ጣትሽ የነካው ቦታ?»

«እ»

«እዚህ ጋ ያሉ ነጠብጣቦች ምቀኞች ናቸው: እዛ ፊት ለፊት ያለው የጣትሽ ምልክት ያለበት አንቺ ነሽ:: ገና አልቀረቡሽም ግን አይ አለመታደል! ተወረሻል የእኔ እመቤት:: ቆንጆ መሆን እንዲህ ያስደርጋል? በቁንጅና መታደልና በአለም መፈለግ እንዲህ ያስወርራል? አይዞሽ እንድታውቂውና እንድትጠነቀቂ ነው ያሳየሁሽ»

ልጅትዋን ቀና ብዬ አየሁዋት:: ዝም እንድል በእጅዋ አፍዋን ተመተመች:: ግራ እንደገባኝ አይታ ቸኩል ብላ መጥታ እነበርኩበት ሶፋ ክንድ ማስደገፊያው ላይ ተቀመጠችና ወደ ጆሮዬ ቀርባ በሹክሹክታ:

«ምንም አትበይ፣ ሌላ ድምፅ ይረብሻታል» አለች

ይህቺን ልጅ ዛሬ ድረስ የማስታውሳት በነዚህ አምስት ቃላት ነው:: እንደዚህ ግልፅ ሆኖ የሚሰማ አረፍተነገር ስትናገር አልሰማሁዋትም:: እንደበቷ ሙልጭ ያለ ከተሜ ነው:: የተማረች ብዙ ነገር የምታውቅ የመሰለች ናት:: ደንግጬ ቀና ብዬ አየሁዋት:: በቀኝ እጅዋ አገጬ ላይ ይዛ፣ እንደማንሾካሾክ አይነት ንግግር

«የሀይን ክረሚላ የሆንሽ ነገር» አለች

እየሰለቸኝ የመጣ ነገር ተነገረኝ:: ሙከሻ ሲደጋገም ልብ ይሰብራል:: ***ፍቅሬ ፍቅሬ በዛ እኔ ለሳማረኝም*** እንዳለው አይነት *ማነው እቴ?* ጥላሁን::

ልጅቷ እንዲህ ቀርባኝ አታውቅም:: እንዲህ ደፍራ ተግባብታኝና ተጠግታኝ ገላዬን ነክታ የምታዋራኝ አትመስልም ነበር:: ያቺ ገረድ የመሰለችኝ ግን አቀላጥፋ የምትናገር፣ ዐይነአፋር መስላ የምትሞጣሞጥ ልጅ ጉንጬን ልትስመኝ አይነት ሁሉ ወደ ፊቴ ቀርባ በቀለጠ የከተሜ አማርኛ ያለችኝን ስሰማ ዞር አለብኝ:: የዕውነት ፈራሁዋት:: በትክክል የማላውቀው አካባቢ የመጣሁ መሰለኝ:: በአእምሮዬ *የት ነው ያለሁት?* ማለት ስጀምር ሳቅ ሰማሁ:: ከሃሳቤ ቀስ በቀስ ስወጣ የልጅቷ እጅ ከአገጬ ላይ ተነሳ፣ (አገጬን እንደያዘችኝ ሁሉ ረስቼአለሁ) ጀልጃላ ቀሚሷ ዙሪያዬን የበተነው የማድ ቤት ሳይሆን መዐዛው የሚያምር የሽቶ ጠረን ነው:: አልማዝ ነበር የምትስቀው:: አልማዝ አይኖቿን ከትሪው ላይ አላነሳችም::

«አይዞሽ ሁሉ ይቀራል:: እዚህ አየሽ በስተግራ እነዚህ ነገሮች ያሉበት ምቀኞቹ ቆይቶ ሲሸሹሽ ነው:: ትሪው ተለቅ ቢል ኖሮ እናየው ነበር:: ለሚቀጥለው ጊዜ ትሪውን ትልቅ እናድርገው እይደል?» አለች ቀና ብላ ወደ ልጅትዋ እያየች:: ባለጉዳይዋ እኔ ሆኜ የምታዋራው ግን የማይመለከታትን ነው:: ልጅትዋን ቀድሞ አይቼአት በማላውቀው አይነት አተኩሬ አየሁዋት:: ባላገር አለባበሷ ጀርባ የሆነ የደበቀችው ነገር አለ::

«ሌላስ?» አልኩ አፌ እንዳመጣልኝ ወደ አልማዝ ዞር ብዬ::

«በቃ እሱ ችግር አለብሽ ሌላው ፍክ ነው»

«ምቀኞቹ ወንዶች ናቸው?»

«ወንድ ሴት አይለይም:: ብቻ ተጠንቀቂ፣ አይዞሽ»

አልማዝ ሌላ ጨዋታ አመጣች:: ከረሙ ቶሎ ቶሎ ጠጣሁ:: የሚያስፈራ አይነት ፀጥታ መስፈን ጀመረ:: ከአልማዝ፣ ልጅቷ *ሰሚ ማነው??* የሌላ አገር ሰዎች......እሌላ አገር......ክፍለ *ሃገር*......አውራጃ ......ወረዳ......ከተማ......ከፍተኛ......ቀበሌ......መንደር......አይቼው የማላውቀው ቤት ውስጥ ከማላውቃቸው ሰዎች ጋር ባዕድ ቤት ውስጥ ያለሁ መሰለኝ:: ልብ ሳልለው ሞቅ አለኝ:: አልኮል ባለሰለሰው አንጎሌ የነገረችኝን ሳወጣ ሳወርድ ቆየሁ:: ከመሃል መፍዘዜን አየች መሰለኝ አልማዝ *አታስቢ* ትለኛለች:: *አታስቢ* ስትለኝ *ምን እያሰብኩ ነው?* እያልኩ የበለጠ ስለ አወራችኝ የማላውቃቸው ምቀኞች ብዛት አሰላስላለሁ:: የማውቃቸውን ሰዎች በአእምሮዬ አጠናለሁ:: *አታስቢ* እያለች ታሳስበኛለች::

ከዛ ቀን በሁዋላ ለብዙ ጊዜ በዚህ *ንባብ* እየተብሰለሰልኩ ያየኝ ሁሉ ምቀኛ እየመሰለኝ ሰላም አጣሁ:: ቀስ በቀስ ያደኩበት ቸልተኛነቴ እያታለለኝ የሚያየኝንና የሚያዩኝን ሁሉ አድናቂዎቼ ማድረጌን ቀጠልኩ፣ ግን አንዳንዴ የአልማዝ *ሰበብ* ይመጣብኛል:: *እንጀራ ገለጣዎ* ትዝ ይለኝና የማያዳምጡኝ፣ የሚከራከሩኝ ጓደኞቼ ነጭናጫ መሆናቸው አቁሞ ምቀኞች ይሆኑብኛል:: በሆነ መልክ ልቀበለው በሚያስፈራኝ ግን ድክመቴን ሁሉ የሚሸፍንልኝ ቀላል ምክንያት ሆኖ የሚያገለግል *የምቀኛ ፍልስፍና* አስተናጋጅ ሆንኩ:: ለምሳሌ ብባልግና ቢተቹኝ ተቺዎች *ተመቅኝተውኝ ነው* የመሰለ::

## ምንሞቹ ማንሞቹ

ይሄ ስጋና ይህቺ ነፍሴ የእኔ ናቸው:: አይነጣጠሉም::

እንዴት መልካም ስበላ ለምን ብሎ ገላዬ ይንሰራፋል????

ፍስሐ በልቤና በገጼ ላይ ይጨፍራል????

ሕልሜ ፀአዳ ይሆናል????

ለምን????

ተኝቼ ስነሳ ሆዴ ገብቶ ያደረው የበግ ቅቅል የጠዋት አካሄዴን ያሳምራል????

መልካም ወይን ገጭ ሳደርግ በቆዳዬ ስር ደም ግባትን ያሰፍራል????

ለምን????

ጥሬ ክትፎ የዋጥኩ ዕለት የጻሊዬ ንቅናቄ አምሮ ይበረታል????

ለምን????

ኤልሳቤጥ አርደን የሊፕስቲክ ሰም፣ በማክስ ፋክተር ሊፕ ግሎስ የፀዳ በቅቤ ያበጠ ከንፈሬ ይርበተበታል????

የፀጉሬ ወዝስ ይፈልቃል????

ሳላቅፈው ያቀፈኝ አህዛብ ይቀልጣል????

ለምን????

ቀን አድርገውኝ፣ ለማታ ተኝቼ፣ ጠዋት ስነሳ ለምን ፊቴ ይጠራል????

ስለምን ሁለመናዬ ከእኔ ፈቃድ ውጭ ሳሙኝ ሳሙኝ አባልጉኝ አባልጉኝ ይላል????

የቱ ነው የሚቀድመው????

ባለጌነቴ ቢመቸኝም መባለጊያዬ የእኔ አይደለም:: የሃራምቤ ሆቴል ዋሻዎች፣ የሬንዴቩ ሶስት ፎቅ ኬክ፣ ጠረን በማሳመሪያ ምናምን የታጠኑ ላዳ ታክሲዎች፣ ኮልጌት ሚንቶል፣ የአርባ ዶላር ሽቶ፣ ሆስተሶች

የሚያመጡዋቸው እና ቢሉአቸው መንሳፈፍ የሚጀምሩ ፓንቶች፣ ዘመኑን አልወድም ከዘመኑ አልቀርብም ለማለት መኪናቸው መስኮት የገብሬልን ፎቶ የለጠፉ፣ ከደንበኛ መርጠው የሚያሳፍሩ አዳዲስ ቶዮታ ውይይት ታክሲዎች፣ ለእኔ ፈገግታ የሚታዘዙ አሳላፊዎች፣ እግሬን ሰቅዬ የምቀመጥባቸው ሶፋዎች፣ እነሱ ሁሉ ያሉበት ሕንፃዎቹ የእኔ አይደሉም:: መጠጫዎችና መተኛዎች የእኔ አይደሉም:: እነዚህ ምንሞች ናቸው:: ምንም ናቸው::

በነዚህ ቦታዎች በብርሃንና በጨለማ (በተመቸና ባልተመቸ ጊዜ) አቶ ፍፁም፣ (የተቀናበረ እስኪመስለኝ ድረስ)፣ ነጋ ጠባ ሳያፍሩ፣ ጉልበቴን ጨመቅ ጨመቅ እያደረጉ፣ ሽሽግና ጨለም ካለላቸው ደሞ እስከ ጭኔ ግማሽ እጃቸውን እየሰደዱ፣ ይሂ ይሂ ካልተመቻቸው ጀርባዬን በቀስታ እየዳበሱ:

'የአበሻ ሴቶች እኮ ውብ ናቸው፣ የእኛ ልጆች ምን ይጎላቸዋል? 'አንቺን የምታይ ሴት በቅናት ትቃጠላለች:: ታስቀኚያለሽ' ይሉኛል:: እንደዚያ ሲሉኝ አንዳንዴ *ብዙ አይተዋል* በሚል ያማረብኝ ይመስለኛል:: ምቀኛዋ የበዛ ውብ ነኝና እለሰልሳለሁ:: በከፊል ልቤ ድለላ እንዳለበት ቢገባኝም፣ በከፊል ልቤ ደሞ የተከላከሉኝ ይመስለኛል:: የተከበርኩ ይመስለኛል:: ምናልባት የአዛውንት አንደበትና ገፃቸው እንዳምናቸው እየሳበኝ ይሆናል:: አንዳንዴ እንደውም ተኮሳትረው ስለሚናገሩ የሚያውቁት ነገር ቢኖር ነው ብዬ ትክክል ይመስሉኛል:: አልማዝ የፈጠረችልኝ የምናብ ምቀኞች በሃሳቤ ሲያፍሩ አያለሁ:: ግን ልጅነቴ በነፍሳቸው ገመድ በየሆቴሉ እየታነቀ ይሰቀላል::

(ቤቴ መጥቼ እናቴን ሳያት ከማንም የምታምረዋን መጥቆር መጀመርዋን ልብ እላለሁ:: ማድያቷ ሽፍ እያለ አይወጣም:: ከስር በደም ስሯ እንደ ወንዝ የሚፈስ ነው:: ጨለማ የምትመስልበት ጊዜ እሩቅ አይደለም:: እውነቱ እሱ ነው)

ብዙ እንዲገባኝ ብዙ ማሳለፍ አለብኝ:: የፍፁም ጓደኞች ብዙዎቹ ቡና ነጋዴዎች፣ ደርጎች፣ ምሁሮች፣ ምናምንኖች ነበሩ:: እንደ እነሱ ሰዎች አብዮትና አገር የሚጠላ የለም:: በተለይ ፍፁም ኢትዮጵያን ማንቋሸሽና ማሽሙዋጠጥ ይወዳሉ:: እግሬን እየሰደቡ እኔን ሲያሙቀሙቁ አይምታታባቸውም? የሚበሉት ዳቦ ከእጃቸው ተስፈንጥሮ አይወጣም? በሁሉም ነገር ውስጥ ስድብ ያገኛሉ:: አንድ ትንሽ ጉዳይ ማስፈፀም ከቸገራቸው፣ 'ይኼ አገር እንደ ድንጋይ ተጎልቶ አይንቃነቅም እኮ' ይላሉ:: የሆነላቸው ጊዜ ደሞ 'ይሄ አገር እኮ ተበላሸ ያለጉቦ አይሆንም፣ ለአንዱ ካድሬ ደህና ሰጠሁት ተደስቶ ሰራልኝ' ይላሉ:: ካድሬ ለካድሬ ጉቦ እየተሰጣጣ:: ካድሬ ምንድነው? እናቴ ቴትሮን ቀሚሷ በቀትር ፀሐይ እስኪቀልጥ ቀበሌ ሱቅ ለዘይት የሚያሰልፋት አይደለ? እዛ ተቀምጠን ሲያወሩ የገባኝ ነገር አባቴ ለአብዮቱ ለፋሁ የሚለው ነገር ሁሉ ውሸት እንደሆነ ነው:: እየለመድኩ

ስሄድ በተለይ ትንሽ ጠጥቼ ሞቅ ሲለኝ፣ ፍፁም ሁኔታዬን ስልለው ማንም ባለበት (አዋቂዎቹና ወሽሞቻቸው) እየጎተቱ አንዱ መኝታ ቤት ያስገቡኛል:: ከዛ ደርጎችም ሌሎችም እዛ ያሉት በየራሳቸው በየመኝታ ክፍል ይገቡና ቪላው በልጃገረዶች የወሲብ ዋይታ ይሞላል:: ውድድር ይመስላል::

አብዮቱ መሬታችንን ቢወስድ......

አብዮቱ ፋብሪካውን ቢወስድ......

አብዮቱ መሠረተ ትምህርት እያለ ቢጮህ......

አብዮቱ ሰሜን ቢዋጋ......ምናምን

እኛ የሚያሳድጋቸውን እዚህ በአጭር እናስቀራለን ይመስላል::

በውይይት ክበብና በሬድዮ ከሚዘረዘረው ግን ይሄ የማየው አይበልጥም? በመንፈስም በአካልም የሚቀጠቅጡኝ ፍፁምና የመሳሰሉት አይደሉ? 'በቃ ነፃነት እኮ ጠፋ ትላለች' ፅዮን በሰዓት እላፊ ሳስት ዊክ[153] ስድስት ኪሎ ያስቆሟቸውን ፖሊስ ወይም ጠባቂ አስታውሳ:: ምን ለማለት እንደሆነ አይገባኝም:; የመጠለዣ ጊዜ አነሰኝ ነው? እንዲህ የምለው ከአብዮት ጥቅም ስላገኘሁ አይደለም:: አልጎዳኝም:: ስላልጎዳኝ ለመሳደብ ይከብደኛል:: እነሱስ ምን ተጎዱ? አብዮቱንና መሪውን እየሰደቡ ሚሊየነር አይደሉ? አባቴ ለአብዮቱ ተከሶ 'ወጣት ገለሃል' ተብሎ ታምቶ ለእሱና ለእኔ መሰደቢያ ሆኖ ያገኘው ነገር ክሊኒክ ጥበቃ አይደለ? እኔስ ያገኘሁት ነገር አባቴን በሚሰድቡት መሰረር አይደለ? አብሬአቸው እንደ ፅዮን ፖለቲካ እያወራሁ፣ ለመምሰል ብዬ ብሳደብ አልችልም:: ምን ብዬ ልስደበው? ሞክሬአለሁ አለ አይደለ 'ቀበሌ ያስጠላኛል' ምናምን ብዬ:: እንዲህ አኪያኪስና በሃሳቤ የሚመጣው አባቴ ነው:: አላምር ይላል:: የአብዮት ሰልፍ፣ ብቻ የሆነ ሰልፍ አለ ተብሎ ቤቶች መፈክር ተሸክመው ሲንዘላዘሉ ሳይ በሆዴ ሺህ አይነት ሳቅ እስቃለሁ:: ሕዝብ እንኩዋን አይደሉም 'ምንም' ናቸው::

አንዳንድ ነገሮች እየገቡኝ በየመሃሉ ውስጤ ድክም እያለ የሆነ የባዶነት ስሜት እየነዳኝ ስድ የመሰሉና የሆኑ ነገሮችን ወደድኩ:: ግራና ቀኝ መሽቫ ያለ አይመስልም:: በጣም ከባድ ማኖ ነው የነካሁት:: አልቢትሮው ፊሽካውን ሳያቋርጥ ይነፋል:: የሚነፋ ይንፋው:: ላመልጠው በማልችል ነገር የተቀፈደድኩ መሰለኝ:: ከጥላ ሞት ማምለጥ ይቻላል? ከደበረኝ አኗኗር መጎዳቴን እየዋጥኩ ደስታ ማፍረጥረጥ ሞከርኩ--ያቺን ጠብታ ልቤን ዘግቼ ለመላስ:: የአልማዘ በሳቅ የታጀበ ትንቢት እንደ ሰመረ አየሁ:: እሷ ልቤን ሳይሆን ሕይወቴንም ማንበብ የቻለች መሰለኝ:: ዛሬ ድረስ እፈራታለሁ:: ታዲያ ያ ባዶነት ሲሰማኝ፣ መንገዴ በወራዳነት

[153] ያለፈው ሳምንት(እንግሊዘኛ)

የተዘጋብኝ ሲመስለኝ፣ ባጋጠመኝ ቦታ ያለቅሬታ ፊቴን ወንድ አንገት ስር ቀብሬ መዳሰስን ወደድኩ:: ከፍፁም ስጋ ግንኙነት ፍፁም ደስታ ለማግኘት ለፋሁ:: አለመወደድና ከፍት ማደር ተመሳሳይ ሆኑ:: አንገት የተሰራው ሀብል ወይ ክራቫት ቢኖር አይደል እንዴ? እምባር የተሰራው እጅ ቢኖር አይደል እንዴ? ሴት ሆኜ በሽንቁር የተሞላሁት በወንድ መደፈን ቢኖር አይደለ እንዴ? ትንሽ ቅሌት ቢኖረውም፣ የተፈጥሮ ሕግ ይሰረዛል? ከንዴ ላይ ትንሽ ቁስል ቢኖር መራመድ ያቆመኛል? አይነት:: መዳበስን ስተኛና ስራመድ አሰብኳት:: እንደ መልካም ዘፈንም ማረከችኝ ......እንደ መጠጣትም አረካችኝ::

ከወንጂ ምድር አንሳለሁ የተተከለብኝ ሽንኮራ ቢቆጠር? መዝገብ ተይዞ ቢሰላ? ያም ሲዘረዘር የሳዳቢዬ ቁጥር ነው:: ከአንዱ ሽንኮራ ስያያዝ ከስሩም ስፈራገጥ አጀማመሬ ትዝ ይለኛል: በልቤ ገብቶ ትንሽነት የሰጠኝ ፍፁም የለገሱኝ ታሪኬ:: ይሄን አጀማመሬን ሁሉም የሚያውቁ ይመስለኛል:: መዝነውኝ የቀረቡኝ ይመስለኛል:: ሚዛኑ ላይ ኀፍረትና ትንሽነት ይቀመጥና ......ከዛ ዝቅተኛነትና ቂልነት ታይረው እንደ ጨው ከላዩ ይነሰንሱበታል:: 'ማንም የተጫወተባት' ሆኜ ነው የሚያገኙኝ:: የተሰናዳሁ ነኝ:: የምደረገው እኔ ብቻ አይደለሁም ታሪኬም ነው:: የሕሊና ቁስል አይኖርባቸውም:: ከዛ 'ማንም' ሂሳብ ውስጥ ራሳቸው ይገባሉ:: በአንዱና በሌሎቹ መሃል ልዩነት ይጠፋል:: 'ማንም' መሆናቸውን ግን ልብ አይሉም:: ማንም የተጫወተብኝ ምንም በመሆኔ እኔን ግን ይከብደኛል:: ለመሆኑ ማናቸው እነዚህ ***ማንሞቹ?***

※ *አራጋው* ባለቶዮታ ፒክ አፕ ጤፍ ነጋዴ:: ሁለቴ በፈረሱላ ጤፍ የጫነልኝ (ሲመጣበት የሚፎክር) ※ *ሃይሌ* ከተማ ልማት የሚሰራ:: 'ስሜን ካላስጠራሁሽ ሃይሌ አይደለሁም' የሚለኝ--እየሳቀ:: 'ስም ጠፋ?' እላለሁ በልቤ:: *ይልቁን ቱቦውን አሳምር ማለቴ--የከተማውን* ※ *ሻለቃ ተካ* አላማው ግልፅ የሆነ ዝምተኛ ተከታኪ (ከእኔ ጋር አይነጋገርም ከዘውገ ጋር ግን አፍ ለአፍ ነው) ※ *አሉላ* ካድሬው:: ሽጉጡን እወገቡ የሚሸጉጥ፣ ሊተኛ ሲል ኮቱ ኪስ የሚከት:: ማድረግ ካልሆነለት 'ፀረ አብዮተኞች አስደገሙብኝ እንዴ?' የሚል ※ *ፀጋይ* ሁሌ ሲጀምር 'እሰይ' ማለት የሚወድ:: ትኩሳታም:: ቶሎ ፈልቶ ቶሎ የሚበርድ:: የደስታው እርዝመት ሶስት ሆሄ:: ግልግል ※ *ካሳሁን ቲቸር* ሁሌም የምወደው:: እያከበርኩ የምወደው:: እርካሽ ቤርጎዎች የት እንዳሉ የሚያውቅ:: ሻይ እየጠጣን ሲፈልግ 'ላባልግሽ' ይለኛል ※ *ወልዴ* ባለጋራጅ:: አማረልኝ ብሎ ያለ ውስጥ ሱሪ ወዲያ ወዲህ የሚል:: ኮዳ ያንጠለጠለ የመሰለ ቆለጣም:: ስድነት አራዳነት የሚመስለው ※ *አያሌው* የፎገርኩትን ሁሉ የሚያምን:: 'ኸረ ቀልዴን ነው' ብለው እንኩዋን የሚቀየም:: 'አንቺ ቁም ነገር የለሽም' የሚል:: ስምን እግዜር ያወጣዋል:: እና ጅል:: እንኩዋን ዘፈኑበት ※ *ዘውገ* የምግብ ቤት ባለቤትና ቡና ነጋዴ:: ዝም ብሎ ካሸ:: 'የፈለግሽውን' ማለት የሚወድ:: ይሁን ብለው ቢለቁት እናትን በካሽ መግዛት የሚቻል የሚመስለው፣ እያንሾካሾከ የሚናገር ከሻለቃ ተካ ጋር አገር ላይ የሚያሴር

※ *ፍስሐ* እያረገኝ አገር የሚያማርር:: ምን ፈለክ አንተ ጭርታም? መንግስቱ ሃይለማርያም ቢሰማህ ፔጆህን ይወስድብሃል:: አገር ላይ ከኪሩቤል ጋር የሚያሴር (ያልሰማሁዋቸው መስሎአቸዋል) ※ *አስመሮም* ፋርማሲስት 'አስመራን የሚያክል ከተማ የትም የለ' የሚል:: 'ሚሊያኖች እንኩዋን አዲስ ሚላን' ይሉዋታል:: ምን ያደርግልኛል እሱ:: ያቦንንክብኝን እንዷን የጭገር ፀጉሬን የሚላጭ ፍቅርህ ይተካልኛል? ለምን የሮማ ምንቸት አታባልግም? ※ *ዘሰራት* ሁልጊዜ 'ባስረግዝሽ' የሚል:: አልሆነለት:: ግን ይዝታል ※ *ገመቹ* በቆምኩ ቁጥር ከፍ ዝቅ አድርጎ የሚያየኝ:: ይወደኛል ግን መናገር አይችልም:: ዝምተኛ ሳይሆን ድዳ ነገር ※ *ዳንኤል* ሲኒማ ወይም ሞት:: አይገባኝም ሲኒማ:: ለምቦጫም:: ፈረንጆቹ ሊስሙኝ ይፈልጋሉ:: ፈረንጅ ግን ለምቦጭ የለውም:: ፈረንጆቹ በለምቦጭ መሳም እንዴት ነው? ※ *ወንድሙ* እንደ እህቱ የሚያቅፈኝ:: ወንደላጤ. ገንዘብ ሚኒስቴር ምናምን የሚሰራ:: ደመወዙን ይዞ እኔ ጋ ※ *ዶ/ር ኪሩቤል* በስሙ የሚኮራ:: 'ጂሰስ' ማለት የሚወድ:: ጺንጢ. ግን አይደለም:: ቀልቃላ:: ረጋ በል ※ *አብዱሰላም* አብረሽኝ ሶላት አድርጊ ሊለኝ ምንም አይቀረው:: ዘራፍ! የአቡነ አረጋዊ ልጅ ※ *መሐሪ* ክትፎ ካላበላሁሽ ሞቼ ልገኝ ባይ:: የዳሌዬ አንድ አራተኛው የእሱ ስጋ ነው:: በቅቤ የረሰረሰ ክትፎ ምንድነው ለመሆኑ? ወጥ ነው ምንድነው? ግን እንጀራ ካልረጠበ አበበ ካልጠገበ ※ *አበበ* 'መጀመሪያ እንብላ' የሚል:: መብላት ፒሽአፕ:: እንደ እናቴ 'አረቅ' የሚል:: ያንቃቃህ እቴ:: ምንድነው ማንቃቃት? ※ *ሃይለ ኢየሱስ* የአራት ኪሎ ዩንቨርሲቲ አስተማሪ:: ምን እንደሚያስተምር አላውቅም:: ማርያምን ግድ የለኝም:: እስኪ አንድ ቀን ያለ ውስጥ ሱሪ ነይ የሚል:: እንዴ? ጉንዳን እፈራለሁ ※ *ብርሃኑ* ብርሽ:: ማማ የለሽ:: ማማ የማያበዛ:: የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሰራተኛ:: መሰለኝ:: እዛ ብሄራዊ ጋ ያለው:: ቦርሳዬ ውስጥ እሱ የሰጠኝ ሃያ የአሜሪካ ዶላር:: ብርቅ መስሎኝ ነበር ያን ሰሞን ※ *ሰለሞን* በጣም ግዙፍ ሰውዬ፣ 'እኔ ጋን ነኝ፣ አንቺ ምንቸት ነሽ፤ ራቁትሽን እስኪ ቁሚ' እያለ የሚሰቅ:: ምናባቱን ራቁቴን ከተኛሁለት አይበቃውም? በሞጆና በደብረዘይት መሃል የሆነ ሜዳ ላይ መኪናውን አቁሞ፣ ግራር ስር እናድርግ አለኝ:: ግራር እሾህ አለው:: እሾህም ይዋጋል:: ቦርበል:: ※ *ለገሰ* 'ለጊ' በይኝ የሚል:: 'እስኪ ልለጋ' ይላል:: የሚለጋ ይለጋው:: ቃሉ ያስጠላል:: ይሄን ቃል ካለ በሁዋላ ሳገኘው አልፈለኩም:: አሪቻ ኪሎ አይጠፋም:: ሐውልት ጠባቂ ነው? በል ጠብቅ:: አባቴ ብቻ ነው ጠባቂ? ※ *ዮሴፍ* ሳሚ ስምሳሚ:: አፌ ላይ ዘሎ ልለጎም የሚል:: የንግግር ነፃነቴን መንፈግ ደስ ሲለው:: ትንፋሹ አደንዛዥ እፅ ነበር:: እወደዋለሁ:: ከካስሽ ቀጥዬ:: ትንፋሽ ሲወደድ አይገርምም? ※ *ማህደር* ማሂዬ:: ልሳለምሽ የሚል:: ቸርችህን ፈልግ አቦ:: ኩርማን መሳም:: ግንባሩ እንደ አርጊት አርማጎን ሰፊ ነው ※ *በርሔ* ጨቅጫቃ:: ለጋስ:: ይለግሳል:: ይጨቃጨቃል:: ይለግሳል:: ምናለበት በሆነው ባልሆነው ባትነዛነዝ ※ *ገርማሜ* ኢንጂነየር ከሚተኛኝ የበለጠ የሚረዳኝ:: ጥርሶቹ ደስ

የሚሉ፡፡ ፀጉሩ ደስ የሚል፡፡ ላይሽ ነው ይላል፡፡ 'ልቀይስሽ' ብሎ ቀጥሮኝ አይችልበትም፡፡ ተባረክ ጂሚ፡፡ ሽሮሜዳ ዘመድ አለው አጎቱ ምናምን፡፡ የት እንደምኖር አያውቅም፡፡ ደሞ አልነግረውም፡፡ ሃሃሃሃ ※ ጌታሁን ጌቾ ገቻቻ፡፡ የናቀኝ የመሰለኝ፡፡ አልረሳውም የናቀኝ ስለመሰለኝ ※ ነሰሩ ቅርናታም ካልሲ ※ ፅናት የወንድ ላም፡፡ አብሮኝ መታየት የሚወድ ፉንጋ፡፡ ሳልበው ቅር የማይለው፡፡ አይ አንዳንዱ! ※ አድማሱ ከመብላቱ በፊት አቡነዘበሰማያት የሚል፡፡ 'የኔታ' እለዋለሁ ※ ሙላት ፈጣኑ፡፡ የሆነ ካድሬ፡፡ ነገሩ የሚያስፈራኝ ※ ሃፍቶም ሃፍትሽ፡፡ ደግ፣ ግን ከንፈሩን እየመጠጠ የሚያማርር ※ ገበየሁ ጌቢ፡፡ የቅቤ ነጋዴ ልጅ፡፡ ጥርሱ በበርጫ ቁጥቋጦ የመሰለ፡፡ ቅጠሉን በጉንጩ ከያዘ፣ ቦርሳው ቢቀልጥ የማያይ፡፡ ቾልታውን ስወደው ※ ለሜሳ 'ላፈንዳሽ እንደሳንቡሳ' የሚል ልቅ አፍ፡፡ ሳንቡሳ ይፈነዳል እንዴ? ※ ...........ስሙ ጠፋኝ ገላው ላይ ፀጉር የሌለ ዙሪያዬን እንደ እባብ የሚጠቀለል፡፡ ቆዳው እንደ ጥጥ ※ ፋሲል ከእስር ቤት ገና የወጣ፡፡ ባለ ዲግሪ የኮሌጅ አስተማሪ፡፡ አቃጣሪዬ አለም አንተ እንደነገረኝ፡፡ ብልጭ ብሎ የጠፋ፡፡ ግድ እንደሌለኝ አያውቅም፡፡ ሲያየኝ የሚያደርገውን የሚያሳጣው፡፡ እንደሚያሳጣው ግን ሲነግረኝ ያፍራል፡፡ ጡቶቼን በቀስታ እየሳመ 'ቱቱ' እያለ ይጠራቸዋል፡፡ እሱ ሲቀጥረኝ 'ቱቱ ጋ ልሂድ' ብዬ ለራሴ እነግራታለሁ፡፡ ሲብስበት ደረቴ ላይ ከተለጎመ የሚላቀቀው በእርግማንና በመሰቅሰቂያ ነው፡፡ ※ አለም አንተ የፍፁም ጓደኛ ልጅ እዛው በዛው ፍፁምን መድፈሬን ለመለማመድ ያወጣሁት፡፡ ራሱን ይወዳል ※ አቶ ፍፁም ሙጭጭ ሙጭጭ እንደ ቬልክሮ መቀነት፡፡ አልተዋቸው፣ ያስራል ካሻቸው፡፡ ልድገመው፡ አልተዋቸው ያስራል ካሻቸው ※

## ለአንገቱ

አንድ ከሰአት ከዋልኩበት ውዬ ቤት ገብቼ ልብሴን ለውጬ ምሳ ለመብላት ሳንጎዳጉድ በሽሮ አቅም እንኩዋን የተሰራ ወጥ ስላላገኘሁ፣ ትንሽ ገንዘብ ስለነበረኝ ማድ ቤት ከመርመጥመጥ ብዬ ታዚና ቤት ጥብስ ልበላ ሄድኩ:: በስሎ የተጠበሰ ዝልዝል አዝገቼ ገና ከመቀመጤ እዝራ ማዕዱን ይዞት መጣ:: እዝራ እንደማንኛውም ሰው ምግብ ቤት ውስጥ ይሰራል:: ባለቤቱ እንደሆነ ለማያውቀው ሰው የታዚና ተቀጣሪ ምናምን ነው የሚመስለው:: በልቼ ሳልጨርስ፤ ጌታቸው የተባለው አሳላፊ መጥቶ፣ የምግቤ ሂሳብ 'በቤቱ ይከፈላል' ብሎ ነገረኝ:: በልቼ ከጨረስኩ በሁዋላ፣ በሙሉ ልቤ እንኳን ሳይሆን የምሄድበት ስለአልነበረኝ እዝራን ላመስግነው ቢሮው ሄድኩ:: ገና ሲያየኝ ተርበተበተ:: መናገር ተሳነው:: በልቡ እንደፈለገኝ ገባኝ (ይህቺ ይህቺን አውቃለሁ):: እዝራ መልኩ ትንሽ ያስፈራል:: ማለት ከመልከ ጥፉነት በላይ ነው:: አንገቱ አጭር ነው፣ ሃብል ማስገቢያ ቦታ ያለው አይመስለኝም:: ሁልጊዜ ይሄ የአንገቱ መጥፋት ራሱን ለመደበቅ የሚለፋ ያስመስለዋል:: ግንባሩ ፈጣጣ ነው:: ፈጣጣ ስል ያበጠ የሚመስል ማለቴ ነው:: እግሮቹ ቀጭን ናቸው፣ ኮምፓስ ላይ የቆመ ይመስላል:: ደረቱ እንደ እብጠት ወደ ፊት ወጣ ያለ ነው:: እዝራ ፊቱ እንደ ቴስ ፊት ባለሪዝ ነው:: የማወጣቸው ሰዎች ብዙዎቹ የሚዘንጡና የሚላጩ ናቸው:: መርበትበቱን ሳይና ጨይባነቱ ሲገባኝ በልቤ *ካሽ የሚታለብ ሰው መጣ እንዴ?* እያልኩ ነበር:: ይሄ አሳቤ ግን አላማረኝም:: በሆነ መልክ መንተባተቡና መጨነቁ የሚያሳዝን ነገር ነበረው፤ ልጅ ይመስላል:: እዝራ መልክ ባይኖረውም፣ ገጣጣነቱና ዝም ሲል ገፁ ላይ የተከመረው ፀረ ኪነትነት በሚያምር አሳሳቁ ይጠፉል:: ሳቅ በጥርስ ብቻ እንደማይሰራ በእዝራ ይታወቃል:: ሳቅ የሁሉና አንድ የማይታወቅ ነገር ቅንብር ነው:: እሱን በእዝራ አየሁ:: ያን ቀን ይሄን ይሄን ከማየቴና ሴራ ከማሴሬ ሌላ ምን ነገር እንዳወራን ትዝ አይለኝም::

ከዚያ ቀን በሁዋላ (ብዙም አልቆየም) አራት ኪሎ አካባቢ መንገድ ላይ አገኘኝና መኪና አቆመልኝ:: ወደ መርካቶ ስለሚሄድ እኔም የምገባው

እቃ ስለነበረኝ ወደዛው ሊፍት ሰጠኝ:: የእውነት ያን ቀን ፀሐይ ሳትሆን ፍም ነበር የወጣው መርካቶ ሰማይ ላይ:: ፊቴ ላይ ትኩሳት አለ:: ብብቴ ምንጭ ሆኗል:: እንደ ደከመኝ ተገንዝቦ፣ ከእሱ ጋር እንዳልንከራተት 'የምገዛውን ገዝቼ እመጣለሁ እንቺን አላድክምሽ እዚህ ጠብቂኝ' ምናምን ብሎ እንደ ቀላል ነገር ሁለት መቶ ሃምሳ አምስት ብር ሰጠኝና ማርስ ሆቴል ፊት ለፊት ትቶኝ ሄደ:: በመገረም እሱን ይገፔ ገበያ ውስጥ የጥፍር ቀለም መሰለኝ እሱን ብቻ ገዝቼ ሌላ ምንም ነገር ሳላደርግበት ስንከረፈፍ ቆየሁና፣ *ከመሬት ተነስቶ (ባይሆንም ይችላል) ይሄን ያህል ብር ከበጠሰልኝ፣ እኔ ደሞ ስጦታ ብገዛለት ማን ይጎዳል?* ብዬ አሰብኩና አንድ ሶስት ሱቆች ዞሬ የሚያምር የመሰለኝን ክራቫት ገዛሁለት:: ለማንም ወንድ ስጦታ ገዝቼ አላውቅም:: ማርስ ሆቴል ተመልሼ ፓፓያ ጭማቂ አዝዤ እስኪመጣ መጠበቅ ጀመርኩ:: አድካሚና አሰልቺ የመሰለኝ ያህል ጊዜ ቆየሁ:: የማውቀውን የመርካቶ ሰማይና አቧራማ አየር አያለሁ:: ካለሁበት ሆቴል በረንዳ ፊት ለፊት መተላለፊያ መንገድ ላይ አሮጌ መፃሕፍት ደርድረው የሚሸጡት ጎረምሶች ሳቅና ልፊያ ያስጠላል:: ለብዙ ጊዜ በድፍን ቆዳ ጫማ ውስጥ የታሰሩት እግሮቼ አብጠዋል:: የሚታየኝን አቧራ አያለሁ:: የማይታየኝንም እተነፍሳለሁ:: የምሰራው ሳጣ ከጠረጴዛ ላይ በሻይ፣ ወይ በቡና ወይ በወተት ረጥቦ ከማይካ ጋር የተጣበቀ የዳቦና የኬክ ፍርፋሪ እጠርጋለሁ:: ልቤ ውስጥ በማላውቀው ምክንያት ከምጠጣው ፓፓያ ጭማቂ የቀዘቀዘ ሐዘን ነበር:: ብቻ መንገዴ በተወሰኑ ፕላን አውጪዎች ተቀይሶ ያልሆነ ቦታ የቆምኩ ይመስለኛል:: የመጀመሪያ ልምድ ከራስ ሲያጣላ ከባድ ነው:: የከበደኝ ለዚህ ሳይሆን ይቀራል? ይሄ ክብደት ተለምዶ ሳያቋርጥ የራስ ሲደረግ ጎዳናው ባርነት ነው:: ሁሉ ነገር ይገለበጣል:: ስለምን የተጎዳሁ ይመስለኛል? እነዛ በዛ በኩል የሚያልፉት ሴቶች ታሪኬን ቢሰሙ 'ብርቅ አይደለም' ይሉኝ ይሆን? ራሴ ውስጥ የሚሰማኝን ማድረግን መሰለኝ የሳትኩት:: ክራቫቱን ለእዝራ ስገዛ በራሱ ካሽ እንኩዋን ቢሆን በዛ የቀላል የስጦታ ልውውጥ ያለሁበትን ሁኔታ በደማቅ ቀለም አሳየኝ:: ለእቃው ከፍዬ ስወጣ ላመልጥ የምችለው ቀላል ጣጣ ውስጥ እንደገባሁ ሳውቅ አዘንኩ:: ከመጎዳቴ ተምሬ ሳይሆን ገና ሳልጎዳና እልማዝን ሳላውቅ ሁሉ ቢገባኝ እድነት:: ለዚህ የመጥፋቴ መሠረቱ የሌሎችን ሃሳብ በማመኔ ነው:: 'ቆንጆ ነሽ' እያሉ ሊያመልኩኝ ከደረሱ ለምን አያገቡኝም? ለምን ንግድ አይከፍቱልኝም? ለምን ሃይለኛ ትምህርት ቤት አስገብተው ከፍለው አያስተምሩኝም? ጥሩ አድርገው አይጠቅሙኝም? ይሄ የሚደብር ነገር አለው:: ተራ የወሲብ ስታድዮም ነበርኩ:: የተቃጠርኩና በሌሎች መዝገበ ቃላት የተለካሁ ነበርኩ:: አጎንብሺ ሲሉኝ የማጎነብስ፣ ዝፈኚ ሲሉኝ የምዘፍን:: የቀኑን ሙቀት እያማረርኩ ስለራሴ የገባኝ ነገር ደደብ መሆኔ ነው:: ደደብነቴ አሳዘነኝ::

ቅመም ቅመም የሚሸት ነፋስ በሆቴሉ በር ሲገባ ያስለኛል:: ራት ብዬ ወደ ውስጥ እቀመጣለሁ እያልኩ እስብና ከአሁን አሁን እዝራ ይመጣል እያልኩ እዛው:: እዛው ጠረጴዛ የተደገፍኩበት ክርኔን ያመኛል:: እሱን እየጠበቅሁ ሰዓቴን አሁንም አሁንም እያለሁ:: ጠረጴዛው ላይ ቦርሳዬና (ነጭ ዚፕ ያለው ጥቁር ቆዳ) በካኪ ወረቀት የተጠቀለለ የገዛሁለት ክራቫት አለ:: እዛ ተቀምጬ *ምን ይለኛል?* እላለሁ:: አለ አይደለ በራሱ ገንዘብ በድርቅና የምጣበሰው ይመስለው ይሆን? *በራሴ ገንዘብ ገዝታ ሸርክ ልትሆነኝ ነው?* ምናምን የሚል:: የገዛሁትን ለሱቁ መመለስ ብችል ልመልሰው አስባለሁ፣ ግን መነሳት ደክሞኛል:: ግን ከራሱ ገንዘብ ደግ ሆኖ ከሰጠኝ የራሴው አይሆንም?......ካኪውን ተርትሬ ከፍቼ (እንደ ነገሩ ነው የተጠቀለለው) ክራቫቱን እያለሁ:: ጥቁር ሰማያዊ ሆኖ ቢጫ መስመሮች አሉት:: መስመሮቹ እንደ ወርቅ ይፈልቃሉ:: እቶ ፍፁም የሚያደርጉት ዓይነት::

ከአንድ ሰአት ተኩል በሁዋላ መጣ::

«አስጠበቅሁሽ አይደለ?» አለ

«ምንም አይደለም» አልኩት:: ልቤ ለሁለት ተከፍሎ ነበር::

«ምን ገዛሽ?» ብሎ እንደ ጨዋታ ካኪ ወረቀቱን ሲነካካ ተበረታታሁ:: እንዲቀመጥ ነገርኩትና ሲቀመጥ፣ የተጠቀለለውን ወረቀት ፈትቶ ውስጡ ያለውን ነገር እንዲያይ ጠየቅሁት:: የእሱ ክራቫት እንደሆነ ስነግረው ዓይኖቹ ውስጥ ያየሁትን ብርሃን ማንም ዓይን ውስጥ አላየሁት:: ቀሚሴ ሰፊ መሆኑ አላስበላም እንጂ ከእሱ ስር በደስታ ትንሽ ተንቀጠቀጥኩ:: አቅፎ የሆነ ቦታ ቢስመኝ ግድ አልነበረኝም:: ድምፁን ዝቅ አድርጎ (ጎላ አድርጎ እንዳይናገር የከለከለው እንዳለ ሁሉ) 'እግዜር ይስጥልኝ' አለና በዝምታ እቃውን መዳበሱን ቀጠለ:: ለምን እንደሆነ እንጃ:: ይሄን ያህል አልጉም (እማማ እንደዛ ትላለች) አይመስለኝም ነበር:: ሲያወራ ቀልጣፋ እንደሆነ አይቼአለሁ:: የአሁኑ ዝምታውን የተረጎምኩት የሆነ ነገር እንደደበቀኝ አድርጌ ነው:: ይሄ ሚስጢሩ አጓጓኝ፤ ግን ልጠይቀው አልፈለኩም:: የተገባበዝነውና የተወዳጀነውን ያህል ብዙ ሳናወራ ሰፈር ተመለስን::

መርካቶ የሆነውን ቀላል የመሰለውን ነገር ማታ በጀርባዬ ተኝቼ ሳስብ እሱ እንደወደደኝ፣ መውደጃ መንገዱም ከሌሎች ወንዶች የተለየ መሆኑ ሲገባኝ ደስ አለኝ:: ያልለመድኩት ዓይነት ስለሆነ ግራ ገባኝ፣ ትንሽ ተገረምኩ:: *ለምን ገረመኝ? ምን ግራ ያጋባል?*

የእናቴ ወዳጅ ጎረቤታችን እልጣሽ የተባሉ ሴትዮ የስፌት ስራ እየሰሩ እየሸጡ በእሱ ይተዳደራሉ:: 'እልዬ' 'እልይ' 'እልጣሽዬ' እንላቸዋለን:: እጃቸው በርሂ ቆርፍዶም ማንንም የሚያስገርም ጥልፍ ስራና የሳር ስፌት ይሰራሉ:: ከሁለት ዓመታት በፊት ለእኔ 'ልጄ ሚስጢሯን

የምትደብቅበት ጊዜ ደርሶአል' ብለውኝ እናቴ ሳታይ ('ሚስጥር' ማለታቸው በሁዋላ ነው የገባኝ) በሁለት እጆቼ መሃል ማረፍ የምትችል ሙዳይ ሰጡኝ:: በሁዋላ ኮረዳ ሆኜ ስገባ ስወጣ፣ ወንድ ስር ስወድቅና ስነሳ ለምን እንደምትጠቅም አወቅሁ:: ቤተሰቦቼ ሊገዙልኝ ለማይችሉ ለትንንሽ ጌጦች (ሎቲ፣ አምባር፣ ሀብል) ማስቀመጫና ወላጆቼ ሊያዩዋቸው የማይገባቸውን ነገሮች ማስቀመጫ አደረኳት:: ብዙ ጊዜ የወሊድ መከላከያ ኪኒን የምደብቅባት፣ በዛ ያለ ገንዘብ ካገኘሁ ደሞ ከማንም የማሸሽባት ነበረች::

ታዲያ ያን ቀን ማታ የምሰራው ጠፍቶኝ ሳንጎዳጉድ ልብ ሳልለው እጇ ገብታ ከፍቼ ሳያት ውስጥዋ፣ ሁሉን ነገር ጨምሮ ሳሩንም የሕይወቴ መስታወት መሰለችኝ:: የማውቃቸው ዕቃዎች ሁሉ አሉ:: በአንጎሌ ውስጥ የአመጣጥ ታሪካቸው እንደ ቦይ ውሃ ይፈሳል:: ለምሳሌ አንድ የላሊበላ መስቀል ያለበት ሃብል አለችኝ--ዘውገ የሰጠኝ:: ዘውገ በቅርብ የታወቀችዋ ዘፋኝ የአስቴር በቀለ ባል ወይም እጮኛ ነው:: አንድ የብር ቀለበት አለችኝ እሷንም ከአንዱ አብረን እንደተኛን ልኬ በመሆኑ ነጥቄ ያስቀረሁበት:: አንድ ሰፊ የብር አምባር--ከፖስታ ቤት አካባቢ ራሴ በገንዘቤ የገዛሁት(የተሰጠኝ ገንዘብ ያኔውኑ የራሴ ይሆን የለ?) ከዚያ በሁዋላ በቀለም የተዝጎረጎሩ የክር ብጣሾች (ከየትና እንዴት ገቡ?) አቧራና የሰበዝ ወለል ነው:: ወደ አፍንጫዬ ስወስዳት የሽቶ ጠረን አላት:: እዝራ ከሰጠኝ ገንዘብ የቀረውን ሙዳዬ ውስጥ አስቀመጥኩ:: ብሮቹ የሆነ ልዩ ነገር ነበራቸው:: ከእነሱ በስተቀር ሙዳዬ ውስጥ ያሉት ሌሎች ዕቃዎች ከወሲብ ጋር የተያያዙ ነበሩ:: ወሲብ ላያቸው ላይ አብሮአቸው እንደተወለደ ካንሰር የተጣበቀባቸው ናቸው:: ቁስ ማስቀመጫ ሙዳዬን ስለምን የሕይወቴ ምሳሌ አደረግሁዋት? እንዴት ይሄ ነገር ተከሰተልኝ? እንዲህ ተንጋልዬ ትናንት ከትናንት ወዲያ ወይም በመሳሰሉ የቆዩ ጊዜያት አስብ የነበረው፣ በቅርብና በሩቅ ያሳለፍኩትን ስድነት ነበር:: ስለእንትና ስለእንትናና ስለእንትና እንትን:: የጠገበና ያልጠገበ ስድነታቸውን፤ የሆኑትንና ሊሆኑ የሚችሉትን:: ያወራሁትንና ያወሩትን:: ያን ማታ ግን በፀጥታ፣ ጋቢ የጋረደው፣ የታመመ ሁሉ ነገር የበቃው የመሰለ ገላዬ የሆነ ጭጋግ ውስጥ ነበር የሚመቸውን ቦታ ሲፈልግ......የሆነ የሚሰማኝ ልሸሸው የማልችል ነገር እንደ ጉም ከቦኛል:: እና በጀርባዬ አልጋ ላይ ተጋድሜ ሙዳዬን ከፍቼ ሳይ፣ በትንሽ ሕይወቴ በጣት በሚቆጠሩ አመታት፣ ብዙ እንዳሳለፍኩ ገባኝ:: ስሜና ልጅነቴ ከነዚህ አይመዝኑም? ለመሆኑ እነዚህን የሰጡኝ ሰዎች እዚህ ሙዳዬን ከፍቼ ሳይና ሳስባቸው እነሱም እዛ ባሉበት የትም ይሁን--ተቀምጠው ይሁን ተኝተው ያስቡኛል? ያስቡልኛል? ወይስ እኔ ነኝ ከራሴ ሰአትና ደቂቃ ልጅነቴን እየቸረቸርኩ ትዝ የማልላቸው ትዝ የሚሉኝ?

ከሁለት ቀኖች በሁዋላ ትምህርት ቤት ስመለስ ለማንም በሚታይ መንገድ ተለውጬአለሁ:: አንድ===አላወራም (እፌን ምን ያዘው? እራሴንም መልሶ ይገርመኛል):: ሁለት==ባወራም ድሮ ግንፍል ግንፍል

የሚለው ተረቤ የለም (በሰዎች የማሾፈው ሁሉ በራሴ ላይ መሰለኝ):: ፍሬንዴ እምነት 'ምን ሆንሽ?' ትለኛለች:: እምነት ደጋግማ 'ምን ሆንሽ?' ትለኛለች:: አስተማሪዬ ካሳሁን/ካስሽ ክፍል ሲያልቅ ጠብቆ ስለሁኔታዬ ሲጠይቀኝና 'ደህና ነኝ' ስለው 'ወደ ማታ እንድንገናኝ ጠየቀኝ':: 'አይመቸኝም' ስለው አፌን አልያዘኝም:: ለቡናና ለሻይ ሊሆን ይችላል ግን:: ካስሽን ደሞ ልቤ ባይጠፋለትም እወደዋለሁ:: ፊቱ ሲለወጥ ታየኝ:: በልቤ *አስተማሪ የለኝም* አልኩ:: ሽፍቴ ካለቀ በሁዋላ ከጉዋደኞቼ ጋር ከመቆየት ይልቅ በቀጥታ ሰፈሬ ሄድኩ:: እግሬም ሳላስባት ታዚና ቤት ወሰደችኝና ሕይወቴን የለወጠችዋን አረፍተነገር ተናገርኩ:

«እዝራ አለ?» አሁን ይሄ ቃል ምን አቅም ኖሮት በር ይከፍታል?

እዝራ አልነበረም:: አፌ ስላመለጠኝ ተበሳጭቼ ለራሴ 'የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል' ብዬ ተርቼ ቤቴ ገባሁ:: አንድ ሰዓት እንደቆየሁ እዝራ ከነመኪናው ቤቴ ፊት ለፊት መጥቶ ሲቆም አየሁት:: በዝባዝንኬ የቤት ልብስ ነበርኩ:: ሊወድቅ የደረሰውን የአጥሬን በር ቀስ ብሎ ከፍቶ ገና ሲያየኝ:

«ደህና ዋልሽ? ፈልገሽኝ ነበር አሉ?» አለ

ምን አልኩት?

«ሰላም ልልህ ነበር»

«ደህና ከሆንሽ ምንም አይደል:: ራት ልጋብዝሽ?»

እጁን ሲያፋትግ ሲያሳዝን:: 'ድሮ' ወንድ እንዲህ ሲያደርግ ባይ እታረብ ነበር: 'ጤባ'

«በልቼአለሁ ግን ከተጋበዝኩ ምን አደርጋለሁ? ሂሂሂ»

«ቤት ማን አለ?»

«ለቡና ወጥተዋል»

«ትመጫለሽ?»

«አዎ»

*እንክት አድርጌ ነዋ(በልቤ)*

## ከፊል ቻው

አቶ ፍፁምን የማገኝበት ቦታ ከሰፈሬ የራቀና የተደበቀ ስለሆነ የሚያውቀኝ ሰው ሊያየኝ አይችልም:: የቅርብ ጉዋደኛዬ እምነት እንኳን ከእሳቸው ጋር ስላለኝ ግንኙነት አታውቅም:: የማልከደው ዕውነት አለ:: ኑሮዬን ቀለል ያደርጉልኛል:: በልቤ የያዝኩትን ይገፔ ምንም እንዳልተፈጠረ ሁሉ በአደባባይ ዘና እላለሁ:: አንድ ቀን ለማታለያ ከፈጠርኳቸው ጓደኞቼ አንዷን ሰበብ አድርጌ ወደ አስመራ መንገድ ለቀጠሮዬ ወጥቼአለሁ:: በውይይት ታክሲ ነኝ:: ከእንጦጦ አጠቃላይ ወረድ ብለን ወደ መነን ትምህርት ቤት የሚወስደውን መታጠፊያ አለፍ እንዳልን የነበርኩባት ታክሲ ተበላሽታ ቆምን:: ጋቢና ውስጥ ነበርኩ:: ወደ ቀኝ ዞር ስል ወንድና ሴት ወጣቶች አየሁ:: ሴቷ ከእኔ በስተግራ ልጁ ደሞ ከእኔ በስተቀኝ ከተቀመጥኩባት ታክሲ ምናልባት አስር ሜትሮች ያህል እርቀው የዩንቨርሲቲውን አጥር ግንብ ተደግፈው ተቀምጠዋል:: ልጁ ጂንስ ጃኬትና ቴትሮን ሱሪ፣ ልጅቷ ነጭ ሹራብና ጥቁር ቀሚስ ለብሳለች:: አካባቢው ሳር ስለነበር ጫማቸው አይታየኝም:: አቀማመጣቸው አሻሚ ነው:: የሚተዋወቁ ግን በዛች ደቂቃ የተኮራረፉ ይመስላሉ:: መልከመልካም አይደሉም ግን ገላቸው የጤነኛ ወጣት ነው:: ሁለቱም ፈዘው እኔ ባለሁበት አቅጣጫ ያያሉ:: እንደማያዩኝ አውቃለሁ:: ገፃቸው ልሙጥ የተከዘ ነው:: ምናልባት የኮሌጅ ተማሪዎች ናቸው:: ልጁ ልጅቷን ለአፍታ ዞር ብሎ አያት:: እንዳያት ያወቀች አይነት ፊቷን ለአመል ወደ ግራ ዞር አደረገች:: ከዛ መለስ አለች:: ልጁ ፊት ለፊት አተኮረ:: እንዲህ ሆነው ምናልባት ለአምስት ደቂቃ ይህል ተቀመጡ:: ሐውልት ሊመስሉ ምንም አልቀራቸው:: ከዛ ልጁ ቀኝ እጁን የተቀመጡበት ግንብ ላይ በቀስታ አስቀመጠ:: ከጥቂት ደቂቃዎች በሁዋላ እጁ ሲነቃነቅ አየሁት:: ደረጃ በደረጃ እየዘረጋ ዳሌዋ ላይ በጣቶቹ ነካት:: ለአፍታ ዞር ብሎ እጁ ያለበትን አየ:: ከዛ እጁን ሳይሰበስብ ፊቱን መለሰ:: ልጅቷ ይሄን ሁሉ የማታይና የማታውቅ አይነት ፊት ለፊቷ ታያለች:: ጥቂት ደቂቃዎች አለፉ:: ልጅቷ ከወገቧ በላይ ትንሽ ተነቃነቀች:: በጉልበቶቿ መሃል ይዛቸው የነበሩ እጆቿን አወጣችና ፊቷን ዳበሰች:: ግራ እጅዋ ወደ እግሯ ከመመለስ ይልቅ ጭንዋ

ላይ አረፈ:: ልጁን ሆር ብላም ሳታየው የሚዳብሳት እጁን በቀስታ ያዘችው:: እሱ እንዳያያት እንደፈለገች ሁሉ ፊቷን ወደ ግራ መለስ አድርጋ ፈገግ አለች:: ታክሲው ተነሳ:: ከሆነ ሕልም በግድ ተጎትቼ የወጣሁ መሰለኝ:: ሾፌሩ ላይ መሮጫህ አማረኝ: **ምናባቱን ቀስ አይልም!!**

የገባኝ ነገር ከዚህ አይነት የወጣቶች ቋንቋ የራቅሁ እንደነበርኩ ነው:: ቋንቋችን የተለያየ ነውና የተለያየ ጎሳ ነበርን:: የሁለቱ ልጆች ነገር ቀጠሮ ቦታዬ እስክደርስ፣ ደርሼም የማደርገውን እስካደርግ አንጀቴን በላኝ:: እነዚህ ልጆች የነበሩበት ቦታ አልነበርኩምና እኩል ወጣት ነን? እኩል አለምን እያየን ነው? ዘፈናችን አንድ ነው? ይህቺን የፍቅር መጋቢ ጅረት ሳታይ ባሀር የገባች ተጠላፊ ናት ማከዴ::

ይሄ ቀላል የዐይን ትውስታ ሰበብ ሆኖ መሰለኝ ከፍፁም ጋር ተኝተን ('አይ አንቺ ስኳር' 'አንቺ ከረሜላ' 'አይ የእኔ እመቤት' እያለ--ማለት ይወዳሉ) በየመሃሉ ቀስ እንዲሉልኝ እየለመንኩ ('ኸረ ገደልከኝ!') እያገቡ ከፊቱዋቸው ሶስት ሚስቶቻቸው በለቃቀሙትና ባጠራቀሙት ልምድ ገና ያልገባኝን ልጅ ብዙ አዳከመውኝ በስመመንና በጣመን መናገር እንኳን እንደተሳነኝ፣ ገና 'ጥንት' ከእሳቸው ጋር ይሄ ይሄ ነገር ከመጀመሩ በፊት ማሰብና መጠየቅ የነበረብኝን ማሰብና መጠየቅ ጀመርኩ...... *ሚስቱ እኮ ይሄኔ 'ባሌ ጨዋ ነው' ትላለች......ምናልባትም እኚህ ሰው በሰፈራቸው 'የሚናገሩት ጠብ አይልም' የሚባሉ የዕድር አለቃ ይሆናሉ......ምናልባት በመንግሥትና በመሳሰሉ ድርጅቶች 'ለአገራቸው ግንባታ አስተዋፅዖ ያደርጋሉና ተባበሩዋቸው' የሚባሉ ሰው ይሆናሉ (ይኼው በመተባበር ላይ ነኝ)......ምናልባትም በእኚህ ሰውዬ ድርጊት የሚቀኑ ብዙ ብዙ ሰዎች ይኖራሉ (አንዳንዴ እንደ እሳቸው ዲኢክስ እንዲኖረኝ ሳልመኝ እቀራለሁ ምኞት አይከለከልምና......ለምን ምኞት አይከለከልም?)......ምናልባትም እንደ እሳቸው ለመሆን ብዙ ብዙ ወጣቶች ቀን ከሌት ይለፋ ይሆናል('ገንዘብ ካለ በኩረዶች እግር መሃል መንገድ አለ' አይነት ተረት ሰምተው ያደጉ------ወደ እግዜር ቤት ማስገባት ከቻለ እኔ እከብዳለሁ እንዴ?)......ምናልባትም እሳቸው ሰላምታ ስላሏቸው ብቻ በኩራት የሚንደላቀቁ ብዙ ሰዎች ይኖሩ ይሆናል('አሁን ማን ሰላም እንዳለኝ ታውቂያለሽ? እንትና የሚባለው ሚሊየነር ሂሂ')......እኔ ለእሳቸው ምንድነኝ? ይሄ እዛ ካለው ስፉ መቻርቻፍ ከጀመረው ወንበር እበልጣለሁ? ከዚህ ግድግዳው ቀለም ሲቀባ ካመለጠው የካኪ ወረቀት እመረጣለሁ? እዛ ኮታቸው ኪስ ሊወድቅ ግማሽ ጎኑ ከወጣው ስክሪፕቶ እበልጣለሁ? መኪናቸውን ሲነዱ ከሚረግጡት ፍሬን የበለጠ እጠቅማለሁ? በመንገድ ሲያልፉ ቆሻሻ ሲሸታቸው ከተፉት ምራቅ በምኔ እሻላለሁ? መቼ ዕለት ገበያ ወጥተው ቀበቶ ሲገዙ ጥራቱን ለመፈተሽ ካቅጨለጨሉት የብረት ዘለበት እመረጣለሁ? ጠዋት ጠዋት ፊታቸውን ታጥበው ፂማቸውን ላጭተው ከሚወረውሩት ጂሌት በምኔ ውድ ነኝ? እዛ*

*ጋ አጣጥፈው ካስቀመጡት 'ከውጭ መጣልኝ' ከሚሉት ውስጥ ሱሪ እኔ ተመራጭ ነኝ? ከጫማቸው ማሰሪያና ከእኔ ማን ይበልጣል? ልጃቸው ጉንፋን ከምትታመም እኔ በተስቦ ብሞት አይቀላቸውም? ቆለጣቸው ላይ ተጣማ ከበቀለች አንዲት ሽበት እሻላለሁ?* እንዲህ እንዲህ እያልኩ እርስ በእርሳቸው የተያያዙ እሳቸውንም ሳልጠይቅ እኔው ራሴ በቀላሉ ልመልሳቸው የምችላቸው ጥያቄዎች ከአእምሮዬ አንድ ጎን ወደ ሌላው፣ ከአንዱ ወደ አንዱ ቦታ ተመላለሱ......

......መታጠቢያ ቤት ሲያንጎዳጉዱ እሰማለሁ:: በጎን ላይ መጋረጃ የመሰለ ውስጥ ሱሪያቸው የወንበር መደገፊያ ላይ ከምዕራብ ወደ ምስራቅ ተዘርግቷል:: ሰማያዊና ነጭ ሰንበሮች አሉት:: ከመታጠቢያ ቤት ሲወጡ እንቅልፍ እንደወሰደኝ ሁሉ አይኖቼን ጨፈንኩ:: አልጋ ዳር ተቀመጡና ወገቤ ላይ የቀረውን ብርድልብስ ወደ ታች ሳቡት:: የተኛሁ ስላስመሰልኩ ላስቆመው አልቻልኩም:: ቀዝቃዛ አየር በዳሌዬ ትኩሳት ላይ አለፈ:: አንድ እግሬን በቀስታ ዞር አደረጉና እጃቸውን አፍረቴ ላይ አስቀመጡ:: በጣታቸው ነካኩኝ: *መንቃት* ሲዳዳኝ ሐዘን ባለበት ቅላፄ፣ *'አይ አንቺ አትጠገብ'* አሉ:: አይኖቼን እንደጨፈንኩ ደሜ ፈላ:: ምክንያቱም 'አትጠገብ' የተሰፋዬ ክሬዚ እናት ናቸው:: እንደዛ ሲደባበሱኝ ቆዩ:: ሌላ ቃል ከአፋቸው አልወጣም:: ዝም ስላቸው እንደለገምኩ ጠርጥረው (ባይጠረጥሩም አዝናኚያቸው ነኝና) ከተቀመጡበት ተነስተው በካናቴራ ግድግዳ ተደግፈው የቡጡሌ ቢራቸውን መጠጣት ቀጠሉ:: እየጠጡ፣ ለሌላ ስሪያ ራሳቸውን ሲያደራጁብኝ፣ (የምለምዳቸው አይመስለኝም) በልቤ *እግዜአብሄርዬ አዳክምልኝ* እያልኩ (ግን የሚደክሙት እኔን ፎግለው አይደለም እንዴ? ፀሎቴ ራሱ ወደ ምሸሸው መስዋዕትነት ይወስደኛል) እና ብርድልብሱን ስለተገፈፍኩ በርዶኝ የነቃሁ መስዬ ብርድ ልብሱን ተከናነብኩና ፊቴንም ሳላዞር የማስበውን ሁሉ አሳጥሬ እንዲህ ጠየቅሁዋቸው:

«ጋሼ ፍፁም ሚስትህ ምን ትላለች አሁን?»

«የተኛሽ መስሎኝ......ምን አልሽ? ምን ትላለች ደሞ ስራ ላይ ነኛ!» ከዛ ከት ብለው ሳቁ:: ትንሽ ያደነዘዘኝ ሳቅ:: *ለምን ይስቃሉ? ለመሆኑ* 'ስራ' ምንድነው? ይሄን ቃል መጠቀማቸው ብፍህ እንዳልሆኑ ቢነግረኝም፣ ጉጽቡትና ብልጠት እንዳላቸውም አልጠፋኝም:: ደደብ አባባል በጉልበት ግርማ ሞገስ ያገኛል:: ዘበናይ፣ ያለው፣ ባለአቅም፣ አፉን የሚከፍተው እንዳሻው ነው:: የአቦሬአቸውን እፊያ ሲያነሱ አይጣል ነው:: ከንፈሮቼን ነከስኩ:: እዚህች ጭንቅላቴ ውስጥ የሆነ ብርሃን በፀፀት ፈሰሰ--ምን አይነት ልበል አለ አይደለ ጭርቅርቅ የምትል ነገር:: ገላዬ ከእኔ ፈቃድ ውጭ ተሰበሰበ:: ተኮማትሬ ተኮማትሬ ጭብጥ ማከል ፈለግሁ:: በዚህ የገላዬ መርቀቅ ጎዳና የሚፎግሷት ቀዳዳዬም እንድትጠፋ ተመኘሁ::

«ዛሬ እንደው ያለወትሮሽ ዝም አልሽ? ባሰብሽ?» አሉ:: ተጠጥቶ ያለቀለት የቢራቸውን ጠርሙስ ትራስ አጠገብ ያለች ጠረጴዛ ላይ አስቀምጠው ጎኔ ጋደም አሉ:: ደባብሰው የሚፈትሹትን ፊትሽው፣ ከወገቢ ይዘው ወደ እሳቸው ሳቡኝ:: እንደለመዱት በንግግራቸው ሽንኩራና ከረሜላ ጨማምረው እያሞካሹ ተሳፈሩኝ:: *ምን ብዬ ተነስቼ ምን ምክንያት ሰጥቼ ለዘላለም አልመጣም?*

ገላዬን አጥብቄ ሰበሰብኩ:: ጭኖቼን አከረርኩ:: ለመጀመሪያ ጊዜ አፍንጫቸው ላይ ማድያት አየሁ:: *እንዲህ ቀርበውኝ አያውቁም?*

«የእኔ ቆንጆ ዛሬ ምን ሆንሽ?»

«አመመኝ መሰለኝ»

«ደደደህና ነሽ:: ምንንን ያምሻል......ትትኩሳትም የለሽ»

*መቼ አወራሁ ስለትኩሳት?* ዓይኔ ውስጥ ፍላጎት እንዳሌለኝ ቢያዩም መድፈር በደበቀ ጨዋታ በግራ እጃቸው አልጋ ተደግፈው ተመቻቹ:: የደረታቸው ሽበት ፊቴ ላይ እንደ ፎጣ ወደቀ:: ላባቸው (እስከዛሬ መኖሩን ያልተገነዘብኩት አይነት) የብረት ጠረን አለው:: የቢላ ስለት የማሽት ይመስለኛል:: ፊቴን አዞርኩ:: ፊቴን በአንዱ እጄ ጋረድኩ::

ገላዬን ሁልጊዜ ለሁለት ከፍለው ያዩታል:: ከዕንብርቴ በላይና በታች:: ከላይ ያለው ስለታቹ ሁኔታ መረጃ የመሰብሰቢያ ነው:: መረጃው ከሁለት አንዱ ነው:: *ፈለገችኝ? ወይስ አልፈለገችኝም?* የአንድ ሰው ፊት እንዴት ሁለት መረጃ ብቻ ይኖረዋል? ምላሳቸው ከንፈሮቻቸው መሃል ተወትፈው እያማጡ ሲገፉኝ፣ ብስክሌት በዳገት የሚነዱ ይመስላሉ:: ከአቅሙ በላይ የሚፍጨረጨር ልጅ ይመስላሉ......

......ሁለመናዬ ክሮ፣ ጡቶቼ አገጬ ስር እንደ አረፋ ተዘፍዝፈው፣ በተጣጠፈ ቆዳ የተሞላ ፊታቸው ላይ አዲስ አህጉር ያገኘው ክሪስቶፈር ኮለምበስ ያሳየው አይነት ባዕድ ደስታ ስፈ ፊታቸው ላይ ፈክቶ...... አይኖቻቸው እያዩኝ ግን ሳያዩኝ......በእኔ ውስጥ ጠቅላላ አገሪቷ ላይ ያሉትን ልጃገረዶች እንዳገኙ ዓይነት ወይም ገና ለመወለድ ማሕፀን ውስጥ ያኮበኮቡ ጩቅላዎችን ደምረው በአንዴ እንደሚገቡ......ከአንድ ሰአት በሁዋላ አለም እንደሚያልፍ መረጃ እንደደረሳቸው ሁሉ...... ('አለም ልትጠፋ ነውና ቶሎ ቶሎ እንደራረግ' ምናምን)::

ኮስታራ ባልሆነ ግንኙነት ውስጥ ኮስታራ የሆነ ተራካቢ እንደ እሳቸው አላየሁም......

ከዚያ ከእኔ ቁጥጥር ውጭ ምክንያቱን ብጠየቅ በቃላት ለመመለስ የሚከብደኝ፣ ራሴኑም በረበሸኝ ዓይነት ለቅሶ መንሰቅሰቅ ጀመርኩ:: ድምፅ የለኝም፣ ግን ወደ ውስጥ ሳጌን እንዳይሰማ እየጎተትኩ:: ከዛ

ልጅነቴን አሰብኩ፣ ለምን እንደዛ የራቀ ነገር አሰብኩ? በጣም በጠዋት ይመስለኛል፣ እኔም ሽሮሚዳም አልሞቅንም፣ ጤዛ ገና መስኮች ላይ እንደፈሰሰ ነው:: ጡጦዬ ከእጄ ተፈናጥሮ እዛ ዛሬ ክሊኒኩ የተሰራበት ቦታ ላይ የሰፈር ውሻ እያንከባለለ ሲነካክሰው አለቅሳለሁ---'እማማ! እማማ! እማማ!' ላስቲኩ ከተበሳሳባቸው ቦታዎች ላይ ወተት ፈነንንን ይላል......ውሻው ምላሱን በጉምጅት ይልሳል......'እማማ! እማማ!'...... ፍፁም ስርቅታዬ ራሱን ከሚደብቅበት ከአንጀቴ መሃል ወደ አፌ ይገፋታል፣ በዚህም ታታሪ ይመስላሉ......አይኖቼን አተኩረው እንደ ጥፋተኛ ያዩአቸዋል......'አርፊሽ አትደረጊም' ይመስላል 'ይሄን አግኝተሽ ነው?' ይመስላል 'እሱስ ወደሻል' ይመስላል......መንገዱን አቋርጦ ቀይ ካናቴራ የለበሰ የአስራ ሁለት ወይ የአስራ አራት ዓመት ልጅ ድንጋይ ይዞ ይመጣል......ወደ ውሻው ይወረውራል......ሽማግሌው ወደ ሁዋላ ተወጥረው ጣሪያ ደርሰው ተመለሱ......ከሁለቱም በአፍንጫቸው ቀዳዳ ለአፍታ ከፊሉ በንፍጥ የተነከረ የፀጉር ችቦ ብልጭ ብሎ ጠፋ......ለቅሶዬ ከአፌ ተወርውሮ ወጣ......

«አይዞሽ......አይዞሽ......አለቀ......አይዞሽ አለቀ......» እንደ ማራቶን ሯጭ እየተነፈሱ፣ እንደ ወላይትኛ ደናሽ እየተናጡ፣ ከሰፋት እርጥበት ሳለመውጣት......የታች ጥርሶቻቸው መሃል አያለሁ እዚህ ከመምጣታችን በፊት ከበላነው ሶስት ኮርስ ምሳ (ላዛኛ፣ ስቴክ፣ ቀይ ስርና ስፒናች) የቴርሶው ስፒናች ተሰንቅሮ......ስልጣኔ-ቢስነት እርግማን ነው:: ሀሞተ ቢስነትም እንዲሁ......ለማምለጥ እየቻሉ ማንገራገር ደሞ ከነዚህ የበለጠ እርጉምነት ነው......

ሁለት እጆቼን ፊቴ ላይ......90 ኪሎ የሚከብዱ ሰውዬ አልገለብጣቸው እንደ ጠላት ተሰግስገውብኝ......አፋቸውን ከፍተው ቁና ቁና እየተነፈሱ በጀርባቸው ሲገለበጡና እንደ ውሃ የሚፈስ ቦርጫቸው ተከትሏቸው ሲሄድ......

......ቀጭኑ ድንጋይ የያዘው ልጅ ምናልባት እዝራ ነው......ከእጁ መሃል የሚበር ድንጋይ......ውሻውንና ወተቱን ስቶ......የተነጻደለውን ጡጦ በእጁ ይዞ......አባቴ የት ነበር? እናቴ የት ነበረች? 'እንወድሻለን' የሚሉት የት ነበሩ?......እዝራ ጡጦውን ይዞ......ተጠግቶኝ......ያለቀሰ ፊቴን በሐዘን ሲያይ......ቀላል ሰመመን ሁለመናዬን ወሰደው......

......ይህቺ 'ዐይን ይከላልሽ' የተባለች ማክዳ ኳስ መሰለችኝ አለ አይደለ ይሄ ፓውሎ ሮሲ የነረታት፣ ፎሪ ሳትወጣ ጎል ሳትገባ ሜዳው ውስጥ በማንም እየተጠለዘች (የደከሙት ተጫዋቾች ሲወጡ አዲሶች ይገባሉ) የምትኖር:: *የት ነው መድረሻዬ?* ፊቴን ወደ ግድግዳ አዞሬ የቆሸሸ ቤዥ የሆቴል ግድግዳ እያየሁ......ያረጀ የሆቴል ወንበር ላይ እያፈጠጥኩ...... ወንበሩ ላይ በቁሙ ለሁለት ታጥፎ በስነስርዓት የተቀመጠ ቀሚሴ አለ...... መደገፊያው ላይ ጥቁር ሱፍ ኮትና የውስጥ ሱሪያቸው ተንጠልጥሏል

......ታች መቀመጫው ላይ ሰሪ አለ......ከወንበሩ ስር የሰውዬው ጫማ አለ......በሩ ጎን ጫማዎቼ አሉ(መኝታ ክፍል ገና ስገባ በር ስር ማውለቅ እወዳለሁ)......

ቀና ብዬ ሳያቸው ፍፁም የሚያናውዙ ይመስላሉ:: ቶሎ ከአልጋ ወረድኩና ልብሴን መለባበስ ጀመርኩ::

«የት ነው?......የት ነው?......የት ነው?» አሉ ፍፁም በደከመ ድምፅ:: አልመለስኩም:: ሹራቢ በእጄ ነው:: ከለመድኩት አልቢርጎ ግማሽ እየሮጥኩ ግማሽ እያለቀስኩ ወጣሁ:: *ቆሎዬን በልቼ እሞታታለሁ......* ደብተሬን ከሙሳ ሱቅ(ፎርፌ ስሰጥ እዛ ነበር የማስቀምጠው)......*ያልበሰለ ክሌን (እማማ ብዙ ጊዜ ካልጠፉ እህል ክክ ትሰራለች) በልቼ እወድቃለሁ* ......ጎዳናው የተወሳሰበ ፈተናው የሚያታልል፣ ሁሉ ነገር ሞላጫ ነው:: በቂልነቴና በድንቁርናዬ ባርከፈከፍኩት ዳጥ ላይ ራሴኑ ስፈታተን......እዛ አባብ አለ ዓይኖቹ በላዩ ፍም የሚያፈሱ......በምላዩ ቅጥነት......በቁርሴ ባዶነት......በእራቴ አልባሌነት አሳፍረው ክንዳቸው ላይ እንድተኛ የሚጋብዙኝ......ስራዬንም ብልጠት ብለው የሚያጨበጭቡ የእኔ ቢጤ ደናቁርት......

## ወይም የአንቺ ቢጤ ብልጦች

በሰፈሬ መንገድ ገብቼ ስጉዋዝ መሬት መሬት እያየሁ፣ ጠጠር እየቆጠርኩ ፊቴ ላይ የሚፈሰው ፀጉሬን ወደ እናቴ እየገለብኩ...... ደብተሬን አልጋዬ ላይ ወርውሬ የልብስ ሳሙና ይገፔ ቤቴ ጀርባ ያለ የጉድጉዋድ ሽንት ቤት ገባሁ:: እንደዛ ታጥቤ አላውቅም፣ የተላጥኩ እስኪመስለኝ......ቁጢጥ እንዳልኩ፣ እየበረደኝ ቢሆንም ተሰምቶኝ የማያውቅ መረጋጋት፣ ዝም ብሎ ደስ የሚል ነገር፣ ዝምብሎ መርካት ነገር፣ ዝምብሎ ባላውቀውም ብዙ ተጉገፔ የደረስኩ ሲመስለኝ ነገር......

ከሽንት ቤት ስመለስ እማማ ትኩር ብላ አየችኝ::

«ምን ታይኛለሽ?» አልኩዋት

«አልይሽ እንዴ? ምን ጉድ አመጣች? ደህና ነሽ?»

ያዘመመ ወንበር ላይ ዘምሚ ተቀምጬ በአዘመመ እናት ባዘመመ ምላስ

«ት ቅ ማ ጥ አ መ መ ኝ» አልኩዋት

«እኔም የአመመሽ መሰለኝ እዛ ገብተሽ ስትከርሚ:: ባህል መድሃኒት ልስራልሽ»

«አሁን ተሽሎኛል:: መጥፎ ነገር በልቼ»

«ምን?»

«የሆነ እንጀራ በወጥ»

«የት?»

ውሸቱ ቅጥፈቱ እየሰፋ ድርሰት እያከለ ቢሄድ ማን ግድ አለው? ቀጠልኩ፡

«አንዷ አብረን የምንማር ልጅ ቤቷ ጋብዛኝ»

«አንቺ ተጠንቀቂ»

ሁሌ የምትለኝ ነው።

«ከምግቡ? እንዴት አውቃለሁ። ሁሉም በልቶ እኔ ብቻ ታመምኩ። ከአንድ ማዕድ ነው የበላነው»

«ከምቀኛ»

«የምን?»

«ቆንጆ ልጅ ነሻ። በዕውቀትና በመልክ ነው የእኛ አገር ሰው የሚቀናው። ሴት ደሞ ቅናቷን ታበዛዋለች። ራስሽን በመስታወት አይተሻል? እኩያ የለሽም። አቅም ኖሮን አትለብሽም እንጂ የመኳንንት ዘር ነው የምትመስይው»

«አንቺ መኳንንት አይደለሽ»

«አይ ይህቺ ነገር አሳመርኩ ብለሽ......ብቻ ተጠንቀቂ»

«በምን ይቀናሉ?»

«አይ እንግዲህ ነገርኩሽ። ዐይንሽስ? ጠጉርሽ፣ ከንፈርሽ፣ አቋቋምሽ፣ ባትሽ......እህም......ምን ይጎልሻል? ላንቺ የሚመጥን የዛ የብርሃን ልጅ ነበር። ዓላዛር የሚባለው»

«ልታጋቢኚ? እሱ ፈረንጅ አገር ሄዶ የለ። ደሞ መፈጠሬንም አያውቅ»

«እውነት ድሮ ሳየው አይ መልክ እቴ......ከዛች ቂጣም ጋር ሳየው......አታውቂያትም 'ተባረኪ' የምትባል......አይ እቴ......ደሞ ምላሷ እንደ እናቷ......ሰው ተሰዶ ሊያልቅ ነው እኮ»

«እኔ ቀርቼአለሁ አደለ፣ ደሞ ቦሌ ቆመሽ ቆጠርሽ?»

«አትቀልጂ ሂሂሂ......ነገርሽ እኮ.....»

«አንቺ ነሽ ተወዳዳሪ የሌለሽ ቆንጆ ያልሽኝ እንጂ......»

«ማን ሊልሽ ነው? አገሩ ጣል ጣል አድራጊ ነው......ደሞ......ኩራት እንዲሰማሽ አይደለም፣ ጎራዳ»

«እየሽ 'ጎራዳ' አልሽኝ»

«ይልቁን ትምህርትሽን ቻይበት:: መልክ ታጥቦ አይጠጣ»

በወዲህና በወዲያ ሄደን ከእማማ ጋር ቅጥፈት መስቀለኛ ላይ ተገናኘን

«እናት ልጅዋን 'መልክ ጥፉ' አትልም ለዚህ ነው?»

«እሱስ አዎ»

የእማማ ሃሳብ በትክክል ምንድነው? ቅጥፈት አይሆንም? እማማ እኔ ልጇ በቅጥፈት እንደማስከነዳት አታውቅም:: የቅጥፈት ዲፕሎማዬን በአጭር ጊዜ ከወሰድኩ እንደከረምኩ አልደረሰችበትም::

* *

ይሄ ከሆነ ከሁለት ወይም ሶስት ቀኖች በሁዋላ ደክሞኝ አልጋ ላይ ቀለሙና መልኩ የሚለዋወጥ መምሸት የጀመረ ሰማይ እያየሁ በጀርባዬ ተጋድሚአለሁ:: እማማ የማታ ቡና ልትጠጣ ደቤ እናት ጋ ሄዳለች:: እህቴ ጎሕ ('ጎሒ' ብሎ ብዙ ሰው የሚያቆላምጣት:: እኔ 'ማሚዬ' የምላት:: ጎሕ ያልተጠበሰ ሽክላ ትመስላለች:: እማማ 'የእኔ ምንቸት' ነው ብላ የምትጠራት:: 'ኸረ እባክዎን ምን የሚሉት ማቆላመጫ ነው' እያሉ ጎረቤቶች ቢተርቧትም ማለቷን አልተወችም) ጎሕ ልብስ ማጠቢያ ሳፋ የምናስደግፍበትን ጎማ እየደበደበች *የተ ተወዶ የተ ሊጠላ፣ መላ አካላቴ በውበት ሞላ ምናምን የሚል፣* የሆነ በከተማው የዛን ሰሞን ተወዳጅ የሆነ የማነው የእሱን ዘፈን ትዘፍናለች:: ዘፋኝ ባትሆን ደስ ይለኛል:: የአጥሩ በር ሲከፈት እሰማለሁ:: ከመሃል ድብደባዋን አቋረጠች:: ማሚዬ ለጨዋታ እንደወጣች ጠርጥሬ ትንሽ ተናደድኩ:: እየመሸ ስለሆነ የትም መሄድ የለባትም:: ሁልጊዜ አንድ ነገር የምትሆን ይመስለኛል:: ስትራመድ አንገቷን ሰብራ መሬት መሬት እያየች ነው:: ያዘነች ወይም ነገር ያሰበች ትመስላለች:: የትኛው እንደሆነ እንጃ:: ሁለመናዋ ቀጫጫና የምታሳዝን ናት:: ጎሒ ሳቅዋ ገዳይ ነው:: የአባቴ ፊትና የእናቴ አሳሳቅ አላት:: በግልፅ የሚታይ መልኳ ይሄ ነው:: ጎሕ ስራዋ ማየት እንጂ ማውራት አይደለም:: አልፎ አልፎ ከሳቀች ግን ፈገግታዋ ማማሩ ልብ ያሳምማል:: ብዙ ጊዜ ግን ትይ እንጂ የምታየውን ትረዳ ወይም አትረዳ የምታውቀው እሷ ብቻ ናት:: የሆነ ሹክሹክታ ሰማሁና ቀና ስል በር ጋ ቆማ አየሁዋት:: እውጭ ያሉች ስለመሰለኝ በቅርብ ድምፅ በመስማቴ ደነገጥኩ::

«ምነው ማሚዬ?»

«ሰው ይፈልግሻል» አለች

ቁጣ ይመስላል::

«ምነው? ማነው? እዝራ?»

«አይደለም:: ያ የአልማዝ ተላላኪ»

ለምን እንደተላከ አልጠሩኝም:: አልማዝ ሆነ ብላ እማማ ሳትኖር አጥንቷ ነው የላከችው:: ሕዝብ ደህንነት አላት እንዴ ሴትዮዋ? ደሚ ፈላ::

«የለችም በዪው»

አሁንም ቆማለች

«ምነው?»

«ሁለተኛ አትምጣ ልበለው አደለ?»

«የለችም በይው፤ ሲደክማቸው ይተዋሉ:: ይገባቸዋል»

ፈገግ አለች::

የምትናገረው ውሸት ወይም ዕውነት መሆኑን የምታውቀው እሷ ብቻ ናት:: ልጁ ፊቷን አይቶ ሙሉ በሙሉ እንዳመናት እርግጠኛ ነኝ:: እንዳየሁትና እንደምፈርደው ወደ ፊት ተስፋ ያላት እሷ ናት:: ምክንያቱም ስትፈጠር ቲያትረኛ ናት:: ብልጥነቷ ደስ ብሎኝ እጄን ግራና ቀኝ ዘረጋሁላት:: ይገባታል:: መጣችና አቀፈችኝ:: ሳርና ምሽት ትሸታለች:: አንገቷን ምጥምጥ አደረኩት:: ተስማ ወጣች:: አፌ እንደ ወፍ ተከትሏት ቢሄድ ደስ ይለኛል:: ሃሳቤ እንደሚከተላት አፌና ከንፈሬ እየሳሙዋት እየመጠመጥዋት ብትሄድ......እማማ በድንገት መጥታ *በር ጋ የቆመው ልጅ ምን ይፈልጋል?* ብትለኝ ለመሆኑ ምንም ሳላጎል እውነቱን እነግራታለሁ? ጅልነቴን የዋህነት፣ አለማወቅ፣ ቅንነት፣ ሰው ወዳጅነት የመሳሰለ እያልኩ እየሰየምኩ ራሴን በቃላት እያሽቀረቀርኩና እየሸወድኩ እንዳላረጅ እፈራለሁ......እግሮቼን ፈልቅቄ የግል አለሜን ማስወረር የደረስኩ ሌላ ምን ቀረኝ? ከዚህ የበለጠ መጃጃል አለ?

## የቀጣፊ መዓት

ግራና ቀኝ ያሉ ጎረቤቶቻችን ወደ አስር ሰአት ላይ ለቡና ተሰብስበዋል:: ቡናው ባይደርስም፣ በፈንድሻ የተዥጎረጎረ የሰነፍ ቆሎ ቡና ቁርስ ለመብላት ቁና ይቀባበላሉ:: እማማና አባባ፣ መኘታ፣ ሰውም ክረምትም ሁሉ ደብሮኝ ተጋድሜአለሁ:: ዝም ብሎ መጋደም:: ኢ.ኤስኤልሲ ወድቄ ከወላጆቼ አይኖች እሸሻለሁ:: ከእህቴም እሸሻለሁ:: ከጎረቤቶቼ አይኖች እሸሻለሁ:: ብችል ከእግዚአብሄር ዐይን እሸሻለሁ:: የሚገርመው ግን ማናቸውም በተለያየ ደረጃ ይሁን እንጂ ግድ የሚሰጣቸው አይመስልም:: የፈንድሻው ጠረን እተጋደምኩበት ድረስ ይነሰንሳል:: ፈንድሻ መብላት አልወድም:: ጠረኑን ግን እወዳለሁ:: ታናሼ ቡና አፍዪ ተብላ አዋቂዎቹ መሃል ኩርሲዋ ላይ ተቀምጣለች:: በሚያቆላምጡ አይኖች እያዩ 'ቡና ስታፈላ አቤት ማማሯ' እያሉ የመንደር ሰነፎች ጊዜዋን ይቀሟታል:: ከእኔ ታሪክ ጋር የሚመሳሰል ነገር እየኖረች ነው::

አቦሉ ደረሰና መጥቼ እንድጠጣ ጎሕ ጠራችኝ:: ከእኔ ጋር ካልሆነ ከሌሎች ጋር ምንም አትናገርም:: ምንም ተናጋሪ ናት:: ሰዎቹ ስለ ብዙ ነገር ያወራሉ:: ወደ ሳሎን ሄጄ ከዳር ተቀመጥኩ:: ጎሒን ሳይጨምር ሰባት ሰዎች ነበርን:: አባባ፣ እማማ፣ የቸርነት እናት (እትዬ ምንትዋብ) (ቸሩ እንደ ታላቅ ወንድሜ ነው:: እናቱ ብዙ ጊዜ ስለሚታመሙ እሱ ካልተመቸውና እቤት ካለሁ አስታማሚ የምጠራው እኔ ነኝ:: ቸርነትን እንደ ብራዘር እወደዋለሁ:: እንደ ሲስተር ይወደኛል--መሰለኝ:: አንደኛ ደረጃ ትምህርቴን ያስጨረሰኝ እሱ ነው)፣ እትዬ አልጣሽ፣ የደበበ እናት (ልጃቸው በቀይ ሽብር ከሞተ ስድስት ሰባት አመት ቢያልፈውም፣ አሁንም 'የደበበ እናት' ይሏቸዋል፤ ሕሊናቸው አፋቸው ላይ ነው:: አታድርጉ ቢሉአቸውም የማይሆንላቸው አሉ) ሳውቃቸው ጀምሮ ግራና ቀኝ ጉንጮቻቸው ላይ ሰፋፊ ክርክ የሚያካክሉ ማድያቶች አሉ:: መልካቸው ነው:: ልጃቸው ሰፈር ውስጥ ከተገደለ በሁዋላ ነው አሉ የወጣባቸው(ያኔ አባቴ ገና አብዮት ጠባቂ ስላልነበረ እንጂ እኛንም ይጣሉን ነበር:: ሴት ልጃቸው 'ማሚ' ጬጬ እያለሁ ፀጉሬን ትሰራኝ ነበር:: አሁን አንድ የአፍንጮ በር ልጅ አግብታ ጂዳ ሄዳለች:: አጎንብሳ

ስትታጠብ ፀጉሯ መሬት የሚነካ ከእኔ የማያንስ ፀጉር ነበራት:: ደሞ 'ግርምሽ' የምትለው ቀይ ዳማ ልጅ ቦይ ፍሬንዷ ነበር:: እሱን ካየሁት እንደሚፈልጋት እንኩዋን ሳላውቅ እሮጩ ቤቷ እሄድና እጠራታለሁ)......በውስጥ ልብሴ ላይ *እንትና የገዛልኝን ውድ የአሜሪካን* ጃኬት ደርቤ፣ አዋቂዎቹ በነሲብ ከሰሩት ክብ ትንሽ ፈንገጥ ብዬ ተቀምጬአለሁ......*ማን ነበር ጃኬቱን የሰጠኝ?*

የመጀመሪያው ቡና እጄ ገብቶ አንዴ ፉት እንዳልኩ አባቴ ክሊኒኩ ጋ ስለተፈፀመ ጉዳይ ማውራት ጀመረ:: ልጅ ብሆንም ክሊኒኩ ሲሰራ ትዝ ይለኛል:: አባቴ ሲያወራ ቦታውን የሚቆፍሩት ማሺኖችና የተማሰው ድንጋይና አፈር ትዝ አለኝ:: እየተገረምኩ ከማሺኖቹ ስር አልጠፋም ነበር:: አንድ ጊዜ እንደውም ወደ ሁዋላ የሚመጣ አፈር ዛቂ በላዬ ሊሄድ ሲል የአቶ ብርሃን ልጅ ዓላዛር አድኖኛል:: ዓላዛር ቀጫጫ እጄን እንጠልጥሎ ዞር አድርጎ ተቆጣኝ:: አባቴ ከዓላዛር ተቀብሎ ጆሮዬ እስኪበጠስ ቆነጠጠኝ:: *ዓላዛር እንደኛውኑ ነው የሄደው እንዴ?* እነዚህ ሰዎች፣ ነገሮችና አንድ አጋጣሚ ብቻ ትዝ ይለኛል: **መቆፈሪያ ማሺን፣ ዓላዛር፣ አባቴ፣ ቁንጠጣ**:: እነዚህን ያጀባቸው አውድ የለም:: ዓላዛር እጄን ሲጎተት እጁ ላይ ሰአት ነበረው? ምን አይነት ሸሚዝ ወይም ጃኬት ለብሶ ነበር? አባቴ ያንን ቦቱን አድርጎ ነበር? የቁንጠጣው ስሜት ምን ይመስላል? ከእማማ ቁንጠጣ የተለየ ነው? አይኖቼን ብጨፍን ማስታወስ እችላለሁ? መልካም ሆነ ክፉ ካለፈ በሁዋላ አውዱ በመርሳት ሲፋቅ የሚቀረው ሊያምኑት የሚከብድ የተበጣጠሰ መረጃ ነው:: ክሊኒኩ ሰማያዊ ግድግዳዎችና ቢጫ በሮች አሉት:: ሲጀመር ጀምሮ ቀለሙ እንደዛ ነው:: ለምን ይሄ አይነት ቀለም እንደተመረጠ እንጃ:: ክሊኒክ ሳይሆን የልጆች መጫወቻ ቤት ይመስላል:: 'አሮጌ' ተብሎ መጠራት የሚገባው ክሊኒክ፣ እስከ አሁን 'አዲሱ ክሊኒክ' ይባላል:: አባቴ የክሊኒኩ ዘበኛ ሆኖ ሲሰራ መዓት ጊዜ ሆኖታል::

.................................................................................................................................

«የግድግዳው ቀለም የውስጡም የውጩም ተፋፍቆ አልቆ በፈቃደኞች ለማስቀባት ቀበሌው "ሶስት" ሰዎች" አገኘ፣ ፈቃደኛ ሆነው ከመጡት ደሞ አንዱ ማን መሰለችህ? ያ ስሙም ስራውም ጠማማ የሆነ፣ ያ አስፈሪ እዝራ ነው» ሲል ጆሮዬ ቆመ:: ቀደም ሲል ስለ እዝራ የተናገረውን ስለአልሰማሁት፣ ምን ጉዳይ አንተርሶ ይሄን እንዳለ ዕውቀቱ አልነበረብኝም:: የበለጠ ለመስማት ጆሮዬ ግን ቆመ:: የቸርነት እናት እትዬ አልጣሽና የደቤ እናት ሳል ሳሉ:: ሳሉ የበሽታ ሳይሆን፣ አባቴ የተናገረው ጉዳይ ውስጥ ቅኔ እንዳለ በማወቅና 'አልተመቸኝም' ለማለት መሰለኝ:: ለምን አልተመቻቸውም? ምን የሚያውቁት ነገር አለ? ቸል ያልኩ መስዬ ጆሮዎቼን የበለጠ ከፈትኩ:: የቡናዬ ፉት እንዳይሰማና ቀና

ብለው አይተው የሚገናኝ እንዳያገናኙ እንደ አህያ ሳብ አደርጋለሁ:: አባቴ ሳላቸውን እንዳልሰማ ጨዋታውን ቀጠለ:

«ማከዳ......ሰማሽ? ቁልፍ ትሰጪልኛለሽ ለእሱ» አለ

ካደኩ ጀምሮ አባቴ ብዙ አዞኝ አያውቅም:: የሚያዘኝ ነገርም ስላልነበረ ነው:: በዚህ ዕድሜዬ 'ቁልፍ ስጪልኝ' ብሎ ተራ ነገር አያዘኝም:: ትዕዛዙ አላማረኝም:: ይሄ ትዕዛዝ ካባልቴቶቹ ጉንፋን ጋር ተደርቦ ስብቀት ሆኖ ሲያብጥ ታየኝ:: ነገሩ የገባት የመሰለች እማማ (ወይስ አቦ ሰጡኝ ነው?):

«ለምን ራስህ አትሰጠውም?» አለችው

«በጣም ያስጠላኛል፣ ገብጋባ ሰው ነው» አላት::

«እህ ምን አገባህ? ቢንገበገብ በራሱ ገንዘብ» አለችው::

«አይ እንዴ የቄስ ልጅ ሆኖ እንዲህ አይነት ፀባይ» አለና ከተቀመጠበት ተነሳ:: አባቴ ከተቀመጠበት ከተነሳ ወሬ ማቆም ፈልጓል ማለት ነው:: ተነስቶ ግድግዳ ላይ ከተሰቀለው ካፖርቱ ቁልፍ አወጣ:: ካፖርቱ ወፍራም ብቻ ሳይሆን ከባድ ነው:: ከተሰቀለበት ምስማር ላይ ሁሌ ይወድቃል:: ከሚያሰማው ድምፃ ማንም ኪሎውን (አስር አካባቢ) መገመት ይችላል:: ክሊኒኩን ያቋቋመው ድርጅት የሰጠው ነው:: በውሃ የሚታጠብ ስላልሆነ አቧራና ጉድፍ እየሰበሰበ የበለጠ እንደሚከብድ ተስፋ አለኝ:: ደሞ አብዮት ጠባቂ ሆኖ ለምንድነው በኢምፔሪያሊስት ካፖርቱ የሚኮራው? ቁልፉን እያቅጨለጨለ አየኝ:: ግን የተነሳው ወሬ በቅቶት ነው? ወይስ ቁልፍ ሊሰጠኝ ግድ ሆኖበት ነው? ልቤ አረፍ አለች::

«በሉ እዚህ ከምጨቃጨቅ ዋሕድ ይሰጥልኛል» አለና ወደ መቀመጫው ተመለሰ::

ቁልፍ......እዝራ......ዋሕድ......እኔ......አውዱ እየተዘጋጀልኝ መሰለኝ:: በገዳዳና በቀጥታ ሊዘከዘክ:: ተነስቼ ከሄድኩ አውድ ላዳብር ነው::

«አይ ጥጋብ፣ ነገር የምትፈልገው ነገረኛ ካልሆነ ሰው ነው» አለች እማማ

«የት ታውቂያለሽ?» አለ::

የቸርነት እናት 'የሰው ልቡ የወፍ ወንዱ' አይታወቅም አሉና አዛጉ:: የቸርነት እናት የማይወዱት ነገር ሲመጣ ያዛጋሉ:: ሃሳባቸውንና ወሬውን ወደ ቡና ያዞራሉ:: ቀጠሉና:

«እመቤቴ ሁለተኛው መቼ ይደርሳል?» አሉ እህቴን

እህቴ ፈገግ ብላ አየቻቸው:: ገና አቦል አልተጋባም:: አባቴ ያሉትን የሰማ ሳይመስል:

«እዚህ ሰፈር በጣም ጥሩ ሰው አልማዜ ናት። እንደው ሰዎች የሚያስወሩባት ሁሉ እኔ አውቅ የለ ውሸት ነው። ደግ። ቃልዋን የምትጠብቅ ለአገር የምታስብ። ጥሩ ነጋዴ ናት በዚህ ላይ። ይሄ እዝራ የጠንቋይ ልጅ። ደብተራ አደለ። ስራው እኮ መጠንቆል ነው፣ አልማዝ ግቢ ሶስቴ ጥቁር ዶሮ አስጥሎባታል። እንዲማ ኩታቱ የተቆረጠ ነው አሉ»

«ደሞ ምን አመጣህ? እንዴት እሷ በምንዋ ተሻለች ትላለህ? ትጠንቀላለች ሲባል የምሰማው እሷን ነው»

«አታውቂውማ፣ አሁን እንደው ሰው በጥብስ ብቻ እንዲህ በአጭር ጊዜ መኪና ይገዛል? የተንጣለለ ቪላ ይገነባል? ግብርማ አይከፍልም። የታወቀ ነው። ተደርሶበት በሰው በሰው ነው የዳነው»

«አይ አንተ ደርግ ይለቀዋል ብለህ ነው ቢያገኘው። ያ ባርያ እናቱንም አይምርም» አሉ የቸርነት እናት

«እሱ ብቻ መሰላችሁ? ለስጋ የሚገዛቸው ከብቶች በሙሉ የተዘረፉ ናቸው። አስር በሬ ተደሆበት ሊታሰር ሲል በድግምቱ የፈዘዙ ጉቦኞች ማሩት። ጉቦ ሲሰጥ ደሞ በደንብ ነው አሉ»

«እውነት?»

«ለምን እዋሻለሁ? ምን አገኝ ብዬ። የማውቀውን ነው የምናገረው። ሰው መስሎሻል። ይኼ አልማዝ ላይ ጥንቆላ ብለው የሚያወሩባት ምቀኞች ናቸው። በተለይ ሴት በሴት ከቀናች......»

«አይ እሱ እንኩዋን ከተወራባት ከረመ። ካልሆነ እንዲህ ይጠናል። የእሱ ስራ ወንጀል ከሆነ ቀበሌ ምን ይሰራል ታዲያ?»

'ሰው ነገረኝ' ብዬ ስለጠንቋይነቷ መናገር ዳዳኝ።

«ኸረ እኔ ምን አገባኝ? የፈለገውን ያድርግ። ቢያስደግምብኝስ? አባቱ ሰይጣን ጎታች ነበር። የቀጨኔ ሰው አልነበሩ። ያያቸው አለ ወንዝ ዳር ቆመው ሲደግሙ። በፀባይ ሰላም እለዋለሁ። ከአስማተኛ ጋር ማን ይጋፋል? ጎመን በጤና»

«ዋሕድ አብሮች ይሰራ የለም እንዴ? ዋሕድ አሁን ገንዘብ በገንዘብ ሆኖአል»

«ምን ያገኛል? ትንሽ አዎ ያገኛል። ቀን ያለፈለት አታስመስይው። ዐይነጥላ አስደግሞበት እንደሆነስ? ምን ይታወቃል?»

«ኸረ አንተ ሰው እንደዛ አትበል» አለች እማማ

«ለምን ሚስት አያገባም? ምን ያስፈራዋል?» አለ ቆጣ ብሎ

«ቆሞ ቀረ ልትል ነው? የወንድ ቆሞ ቀር አለው?»

«ሰካራም ነዋ፣ እኔ አውቅልሽ የለ:: በአልማዝ ስለሚቀና እዛ ሰክሮ ቤቷ እየሄደ ይረብሽ ነበር:: አሁን ተወው እንጂ......»

«ምነው እዛ እዛ አልከ ወንጀሉን አበዛህበት? ደሞ ምነው ይሄን አውርተሽኝ አታውቅም?» አለች እማማ

«ምን ይወራል? ደሞ ሰው ላይ ክፉ ማውራት አልወድም:: ወሬው ከተነሳ ብዬ ነው እንጂ:: ልጅ እግሮችን ማባለግ መስሎታል? ትንሽ ሃብት ሲያገኝ ዐይኑ ገለጥ አለ» ያለ እኔ ፈቃድ አንገቴን ሰበርኩ:: ሳለማስጠጣት ቶሎ ቀና አልኩ:: ተነስቼ መሄድ ቢዳዳኝም፣ ጎበጥ ብዬ በመቀመጤ ቀጠልኩ::

«እሱ ይሰክራል? ዛሬ መስማቴ ነው» አሉ የደበበ እናት:: ሳላቸውን ረሱት?

«ወደጄ ጌታቸው ሰክሮ ሲጫወት አምልጦት ተናግሮ ነው የሰማሁት:: ቤቱን ዘግቶ ነው አሉ የሚጠጣው:: ምን አሳፈረው? ጨዋ ለመምሰል ካልሆነ»

ተነስቼ የጠጣሁበትን ሲኒ ስመልስ፣ እትዬ አልጣሽ ፈገግ ብለው አዩኝና:

«ማክዬ እኮ ሁለንተናዋ እናቷን ቁጭ እኮ ናት»

*እኔን ያስቀምጠኝ......እናንተንም......*

ስለ እዝራ ሲያወራ ከእናቴ መመሳሰሌን አልጣሽ ማንሳታቸው አሳፈረኝ:: ምን ይደረጋል? ለመሸሸ ብለፋም፣ ከእዝራ ጋር ወዲያ ወዲህ እንደምል እዚህ የተቀመጡት ሁሉ እንደሚያውቁ አመንኩ:: ፍፁም ላይ አይወራም? ማነው እየመረጠ ወሬ የሚነፋው? ግን የፈሰሰ ውሃ አይታፈስም:: ልፍሰስ ካለስ? ፈሶም አልታፈስ ካለስ? በራሱ ጉዳይ ለምን በተረት ይቀፈድዱታል?

«መልኩ ትንሽ አያስፈራም? ያን ማን ሴት ትስማለች? አሁን ትስሚያለሽ እሱን?» አለ ወደ እማማ ዞሮ

«እንዴት እንዲህ ትለኛለህ? ወይ ጉድ! አያመጣው የለ! አንተ የት ሄደህ ነው? ደሞ እሱ በመልኩ ቢያስከፋ እኛም በደሃነታችን እናስፈራለን:: እግዜር የምንመረቅበትን የምንረገምበትን ገምዶ ነው የሰራን»

«የማታወሪው የለም:: ዘባራቂ»

«ሂሂሂ ጨዋታ መጣ ሂሂሂ» አሉ የቸርነት እናት

«ይሄውልሽ በፊት በፊት የታዚና ጥብስ ሳይመጣ እየሰከረ አልማዝን ሲያስቸግር ነበር የሚያመሸው:: በቀበሌ ነው ያስቀረችው:: ለቀበሌ ብትነግር ውሸት መስሎአቸው አላመኗትም:: 'ሲረብሽ ጥሪን' ብለዋት

አንድ ቀን እንደለመደው ሲረብሽ ጠራቻቸው:: ቶሎራ ያውቃል ይሄንን:: ሊያስሩት ነበር:: ቀበሌ ካስጠነቀቀው በኋላ ቤቷ ስንት ጊዜው፣ ድርሽ ብሎ አያውቅም:: ቢገባም አልኮል አይቀርብለትም፣ ተሳድቦ ይሄዳል:: ኸረ ብዙ ጉድ አለበት! የግርማቸው አባት የሉም? እሳቸው እንዲገደሉ ወሬ ያቀበለ ነው ይባላል:: ደርግ ጠርጥሮት መረጃ ሲያጣ ለቀቀው:: ግን እሱ ነው:: እዝራ ማለት አታውቂውም እንጂ ይሄ መንገድ ላይ የወደቀ ሰው በይው፣ ገና መንገድ አልወደቀም እንጂ»

ሁለተኛው ቡና ደረሰ:: በመጀመሪያ ለእኔ በመስጠቷ ጎሕን እማማ ተረበቻት::

«መጀመሪያ ለአዋቂ ስጪ!»

እህቴ አንገቷን ሰብራ ፈገግ አለች::

«ትስቃለች?»

አባቴ ሁለተኛውን ቡና ቶሎ ጠጥቶ፣ ሲኒውን ጠረጴዛ ላይ ገጭ አደረገና:

«ይበቃኛል፣ ብዙ ጠጣሁ ቀኑን ሙሉ:: ዋሕድን ላግኘውና ቁልፉን ይስጥልኝ»

«ምሳህን አልበላህም እኮ» አለችው እማማ

«ምን አለ?»

«ሆቴል አደረከው? 'ምን አለ ይላል?'»

«በሉ እናንተ ተጨቃጨቁ......ልጄን አትንኩብኝ እንጂ......» አሉና የቸርነት እናት ለመሄድ ሲነሱ እግረ መንገዳቸውን ጉንጩን ቆነጠጡኝ:: ቀና ብዬ ሳቅ አልኩ::

ብዙ ነገር በአግቦ የተነገረኝ መሰለኝ:: ቢሆንም ባይሆንም መሰለኝ:: እኔን የሚመለከት የአግቦ ድርሰት በአባቴ እየተደረሰ ቢሆን፣ የቸርነት እናት ቁንጠጣ እንደ ነጠላ ሰረዝ ናት:: እስከአሁን የተወራው በሙሉ ሳያስጨንቀኝ እንዲሰሚኝ፣ ወይም በየቤታቸው ገብተው ግል ጉዳያቸው ሲሰምጡ፣ እኔ ትዝ ብሎኝ በነገሩ እንድብከነከን ይሆናል:: በዚህች ደቂቃ ያልገባኝ መሰዬአቸው ይሆናል:: እትዬዋ 'ደህና እምሹ' ብለው ወጡ:: እኔም ጎላ አድርጌ 'ደህና አምሹ!' አልኳቸው:: ወገን መሰብሰቤ ነበር::

ቡና ለመጠጣት የተሰባሰብነው በሙሉ ዕውቀት የሌለን ነን:: ሁሉንም በየተራ አየሁዋቸው:: እማማ እዛ ተቀምጣለች:: በየቀኑ ፊቷ ላይ የማድያት ነቁጥ ቀድመው ከወጡት ጋር የስብሰባ ቀጠሮ እንዳለው ሁሉ ይበቅልባታል:: ጠዋት ስትነሳ 'ዛሬም አንድ ወጣ' ትላለች:: እነዚህ

ነቁጦች እየተጠራቀሙ ገፅዋ የተቆጣ ይመስላል:: አንዳንዶቹ ጠንካራ ብረት ይመስላሉ፣ የምር በፊቷ ብትወድቅ የምስማው የምስማር አይነት ቋቋታ ነው:: ከጥቂት አመታት በፊት የነበረው ውበቷ የለም:: ሰው ዞር ብሎ ቢያያት 'እሷ ናት? እንዴት ተለወጠች?' ማለቱ አይቀርም:: መሠረተ ትምህርት ጨርሳ ቁጥር መለየት ትችላለች:: እዛ ጎንዋ ደሞ መመሪያዋን እየተቀበለች የተቀመጠች እህቴ ናት:: ጎሕ ባይገባትም የገባት የምትመስል ናት:: ጉልበት የማይጠይቀውን የቤት ስራ ከእኔም ከእማማም ተቀብላ ትሰራለች:: ገና አምስተኛ ክፍል ናት:: በቤት ስራ ተጠምዳ ትምህርቷን ስትሰራ አላያትም:: አባቴ ሁለተኛ ክፍል የወደቀ የድሮ ተማሪ ነው:: አሁን እንጃ እንጂ አብዮተኛ ነበር:: አሜሪካንን ይሰድባል፣ ግን እኔ ምን እንደደረሰብኝ እንኩዋን የማያውቅ ወይም የሚያውቅ ያልመሰለ ደንቆሮ ነው:: ከዛ የደበበ እናት አሉ:: አእምሮአቸው በቂም የሞላ ነው:: ልጃቸውን ማን እንደገደለ ያውቃሉ አሉ:: 'ቀን ያልፋል ያኔ እንተያያለን' እያሉ ቂጭ ብለዋል:: ይተያዩ አይተያዩ ባላውቅም፣ 'አይ አይ' ይሉና ማሰብ ይጀምራሉ:: ማሰብ ሲጀምሩ አያቆሙም:: ነጠላቸው በየቦታው በጥላሸት ተዥጎርጉሮ ጠፍጣፋ የሚጻ አህያ ይመስላል:: የሁሉም ሴቶች ነጠላዎቻቸው ከጥለታቸው የተዘነተሩ ናቸው:: እያጣፉ ቀዳዳውን ይሸፍናሉ:: አንደኛ ክፍል ደርሰው አቁመዋል:: 'አንብቡ' ሲባሉ 'ተይኝ እባክሽ' ብለው ፊታቸውን ወደ ሰሜን ወደ ደቡብ ወደ ምናምን አቅጣጫ ያዞራሉ:: መሀይም ናቸው:: የቸርነት እናት አሉ:: ቸርዬ አካውንታንት ሆና አሁን ስልጣን ቢሰጠውም አያወሩም:: ከተነሳባቸው ጉራቸው መከራ ነው:: አለም በልጃቸው ስር ያለች ስለሚመስላቸው ራሳቸው ትዝ አይላቸውም:: ይሄም ድንቁርና ነው::

ሁሉም ቡናው አክትሞ ከወጡ በሁዋላ ብቻዬን ቀረሁ:: ስለራበኝ ትንሽ ዳቦ በክክና በሽሮ የተሰራ ወጥ (ጤፍ ስለተወደደ በዚህ ነው ያለነው:: አንዳንዴ ጠቀም ያለ ካሽ ከፈለጥኩ ጤፍ ገዝቼ እመጣ ነበር----'ከየት አመጣሽው አንቺ ሽሽሽ?' ይላል አባቴ---'እሷ እኮ ከሰው ትግባባለች ጎበዝ ናት' ምናምን ይላሉ:: ይሄ ሲባል ቡና ላይ ከሆነ፣ አንገታቸውን ደፍተው እእእእ የሚሉ ጎረቤቶቼ አሉ----መሽሩሞጤን እያመኑ የውሸት አናምንም ሊሉ (እያመኑ አልማመን ይችላሉ----ብቻ ብዙ ነገር አለ) በትሪ አድርጌ ወደ ነበርኩበት ተመለስኩ:: በቀስታ እበላለሁ:: የጃኬቴ እጀታ እየወረደብኝ ወደ ክርኔ አሁንም አሁንም እሰበስባለሁ:: ደርዙ ላይ የወጥ ሊፕስቲክ አለ:: በሁዋላ አጥበዋለሁ እያልኩ ለራሴ እነግራለሁ:: በቂጤ የሞቀ ኩርሲ የበለጠ እያሞቅሁ ወደ ውጭ እያየሁ መብላቴን ቀጠልኩ:: በመስኮት የማየው ከዝናብ ለማምለጥ የሚሮጡ ሰዎችን ነው:: ጎበጥ ጎበጥ እያሉ በችኮላ ያልፋሉ:: እቤታቸው ሲደርሱ ወይም የሚደርሱበት ደርሰው 'ዝናብ አባረረኝ' ይሉ ይሆናል:: መባ'ረር የሚከተል ሲኖር አይደለ እንዴ?......ሰማይ

ጥቁር ጠይም ሆኗል:: የተቀመጥኩበት ቤቴ ውስጡ በጋዜጣ ወረቀት የተለበጠ ስለሆነ ምሽት ውስጥ የተጎለትኩ ይመስላል:: የቤቱ ጣሪያ ቆርቆሮ ጩኸቱ ያደነቁራል:: በአባራ ሽሮ የመሰለው መንገድ በአንድ ጊዜ በሚረግፈው ዝናብ ጠቆረ:: በመስኮቴ የአፈር ጠረን ይገባል:: ደስ የሚል ነገር አለው......መብላቴን አቁሜ ፊቴን ወደ ላይ ቀና አድርጌ ማንም የረገጠውን የአፈር ጠረን በጥልቅ ተነፈስኩ:: ገላዬ ይገባዋል......ያደገበት:: በመስኮት ቀዳዳ ከታዚና ሆቴል ጀርባ እኔ ስወለድ የተተከሉት ዛፎች በዝናብና በነፋስ እየተገረፉ መከራቸውን ሲያዩ ይታዩኛል:: እየታጠፉ ሲነሱ:: ዓለምን ዞሮ የመጣ ያረጀ ነፋስ ደረቅ ቅጠላቸውን እየገፈፈ......ቅጠሎች እንደ ወረቀት ወደ መሬት ይወርዳሉ......ከሆቴሉ ማድ ቤት የሚወጣው ጪስ ትንሽ ከፍ ብሎ ይታጠፍና ሆቴሉ ጣርያ ላይ በእናቱ ይደፋል......ቆሻሻ ወተት ነው......ከዚያ ደሞ ቀጥኖ ይበተናል:: በልቼ ብጨርስም፣ ጭኔ ላይ የምሳ ሳህኔን አስቀምጬ አስባለሁ:: ወጡ እጄ ላይ ሳይደርቅ ትሪዬን ጓዳ መልሼ ተጣጥቤ ስመለስ አባቴ ከውጭ መጥቶ ካፖርቱን ሲሰቅል አገኘሁት::

«ምነው?!» አልኩት:: 'ለምን ተመለስክ?' አይነት:: ቃሉ አመለጠኝ ብል ይሻላል

«እዚሁ ልብላ ያለውን አምጪልኝ......ሻይም»

ሌላ ነገር ሳልናገር የናፍጣ ምድጃ ለኮስኩና ለእሱ የሚበቃ የሻይ ውሃ ጣድኩ:: *ለምን አሁን ሄዶ አሁን መጣ?* ሁሉን አቀናብሬ በአስር ደቂቃዎች ውስጥ እኔ የበላሁትን አይነት ምግብ በሚወደው ሳህን፣ ሻይውን ደሞ በብርጭቆ አድርጌ ፊቱ አስቀመጥኩለትና በዝምታ ወደ መኝታ ቤቴ ልገባ ስል:

«የት ልትሄጂ ነው?» አለኝ

«መኝታ ቤቴ»

«ትሸሺያለሽ»

«ምን?»

«አጠገቤ መሆን አትፈልጊም»

«ለምን?»

«እንጃ»

እንዲህ ብሎኝ አያውቅም:: ነገር እንዳያመጣ ወደ ኩርሲዬ ተመለስኩና እግሮቼን ገጥሜ በስርቆሽ እያየሁት ተቀመጥኩ:: ደጋግሜ ሳየው፣ የአባቴ ፊት እየተረሳኝ እንደመጣ ገባኝ:: የሌላ ሰው ፊት መሰለኝ:: እዚሁ አጠገቤ ጠዋት ማታ እያየሁት፣ እንዴት ፊቱ ይረሳኛል? እንዴት አላውቀውም?

ቶሎ ቶሎ ይበሳል:: ከመሃል ጉንጩ በጉርሻ እንዳበጠ ጎንበስ ብሎ ብርጭቆዋን አነሳትና ፈገግ ብሎ ትኩስ ሻይውን ሳበ:: እንዳቃጠለው ሁሉ እርጥብ ከንፈሮቹን በፍጥነት መጠጠ:: ከትንሽ፣ ከማይረባ፣ ነጋ ጠባ ከማየው ከዚህ ድርጊቱ አባቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ውሽታም መሰለኝ:: ትኩስ ሻይና መዋሸት ምን አገናኛቸው? ምሳና ውሽትስ? ከክና ውሽትስ? ምናልባት የአባቴ ከንፈሮች የውሽታም ከንፈሮች ይመስሉ ይሆናል:: ምሁር መልክ፣ እናት መልክ፣ ጤይባ መልክ፣ ቁሊታም መልክ፣ ገበሬ መልክ እንደሚባለው ውሽታም መልክ ይኖረው ይሆን? በጊዜ ዕርቀት ራሴን ለአፍታ አግልዬ የታዘብኩት፣ ቀደም ሲል እዚህ ተሰብስበው ቡና ሲጠጡ የነበሩት መሃይማን ስብሰባና የቡና እናንቃር ጉባኤ፣ ከምሁራኑና ከሃብታሞቹ ከእነ አቶ ፍፁም ማህበር የሚለይ እንዳልሆነ ነበር:: ሁለቱም የተለያየ ቀለም የተቀቡ ውሽት ማጠራቀሚያ ፈረሱላዎች ናቸው:: ጎዳናዬ በመህይምነትና በድንቁርና የተጥለቀለቀ ነው:: ማስረጃዬ እነዚህን ከእነዛ ልምዴ እነዛን ከነዚህ ልምዴ አነፃዕሬ በቀላሉ ሊመሳሰሉልኝና ልረዳቸው መቻሌ ነው:: ግራ ያጋባሉ ደሞ ግራ አያጋቡምም:: ያሳዝናሉ አያሳዘኑምም:: ያስፈራሉ ደሞ አያስፈሩም::

### ልዩነታቸውን ለማወቅ ከፈለጉ

### ይጋጩአቸው

ከሚያወጡኝ ወንዳ ወንዶች ጋር አብሬ ሆኜ የሚናገሩት ካልገባኝ ውሽትነት ያንሰዋል? ቀጣፊነት ልኩ አይሆንም? ለመሆኑ ምን ማለታቸው ነበር......

ጉምሩክ ✱ ግብር ✱ ኮሚኒስት ✱ ያ ሰውዬ ✱ ምን ይደረጋል? ✱ እንገናኝ ነገ ✱ ጉዳይ አለኝ ✱ ዶክተር ✱ እዛ ቦታ ✱ እናት አገር ጥሪ ጊዜ✱ ምሁር እኮ ነው ✱ ደቡብ ✱ እዛ አሩሲ ✱ ጐርዶን ✱ አክሲደንት ✱ ኰንትሮባንድ ✱ ድሬዳዋ ✱ አሰብ ✱ አይ ላቭ ዚስ ✱ ኮሎኔሉ ✱ ኬንያ ናይሮቢ ✱መብቱን የጠበቀ ✱ ፕሮሰስ ✱ መብት ብሎ ነገር ✱ ሴክሲ ✱ ሚ ✱ አ ሎርድ ✱ ሻለቃው ✱ ኢምፖሲብል ✱ አን ቢሊቭበል ✱ ዲክቴተር ሺፕ ✱ ሞርደረር ✱ መኒ ኢዝ ኢምፖርታንት ✱ አፍሪካን ብሮብሌም ✱ ሳይንሳዊ ✱ ኤጁኬትድ ✱ ሰሜን ✱ ዲሞክራሲ ✱ አፕረስድ ፒፕል ✱ ጎድ ክርኤትድ ጁስ ✱ ዌስተርን ✱ ኤስተርን ✱ ኔሽንስ ✱ ብሄር ✱ ራሽያ ✱ ቱቱቱቱ ✱ ብሄራዊ ✱ ራሊ ✱ በዛ በወለጋ በኩል ✱ ፋክ ዜም ✱ ካፒታል ✱ ሀሀሀሀ ✱ ኢኮኖሚው ✱ በጠዋት ✱ ሆሆሆሆ ✱ የብሄረሰቦች ትግል ✱ ይገርማል ✱ ኪሲንግ ✱ ዌስት ይግድለኝ ✱ ካም ሂር ነይ እዚህ ✱ አ ✱ አአአአ ስሎው ✱ ያያያያያ ✱ በገብሬል ✱ ሁፍ ሁፍ ✱ ጁውሲ ነሽ ✱ ሽኮሪና ✱ ሂሂሂሂሂሂሂ ✱ ፓስፖርት ✱ ከቴም እድገት ✱ ዩ ላይክ ዚስ ✱ አ ዩ

ላይክ ዚ.ስ ✱ አሳህ ያውቃል ✱ ቴክ ዚ.ስ ✱ ተክተክተክተክተክ ✱ ፊንገር ኢ.ዝ ጉድ ✱ ቴክ ዚ.ስ ✱ ሰልፍ ዲ.ተርሚኔሽን ✱ ቴክ ✱ ተክ ✱ እ ጉድ ✱ እ ጉድ ✱ ድሆች እኮ ናቸው ✱ ዘ ቤስት ✱ የተክለሃይማኖት ክትፎ ✱ ዩኤስ ✱ አንቺ ማር ✱ አልጋቸው ጥሩ ነው ✱ ዚ.ስ ✱ አይ ሶሻሊ.ዝም ✱ የተረገመች አገር ✱ ጅቡ.ቲ ወደብ ✱ ይሄ ያንሰሻል? ✱ አምስት መቶ ሺ.ህ ✱ አበዛሽው አልማዝ ✱ መረገም ነው እንጂ ✱ ሌላ ነው ✱ ኪንጅ ጆርጅ ጊዜ ✱ ካስቴሊ. ✱ እሱ? ✱ እሷ? ✱ አውቀው የለ? ✱ ሽርሙጣ ✱ የሽርሙጣ ልጅ ✱ ሽርሙጣ የሽርሙጣ ልጅ ✱ ልቤን ልታቆሚው ✱ ኡፍ ✱ ስትራግል ✱ ሀሀሀ ምምምም ✱ ሮስትድ ኮፊ ✱ ቪዛ ✱ ምን ያስቸኩላል ✱ ጅማ ✱ ዌስት ✱ ኸረ እባክህ ✱ የጉድ አገር ✱ ጉድ አያልቅ ✱ ኢ.ፒ.ኤል ኤፍ ✱ ሰውዬው መስሎታል ✱ አደረገ? ✱ ዌይት ዌይት ቆዪ ✱ ይህቺን ጨርስና ✱ ሊ.ሙ ✱ ሲ.ዳሞ ✱ ኢ.ዲ.ዩ ✱ ይርጋ ጨፌ ✱ ኤክስፖርት ✱ መኒ ኢ.ዝ ✱ ሽንኩርት ✱ ገንዘብ ካለ በሰማይ መንገድ አለ ✱ ካፒታሊ.ዝም ✱ መብት ✱ ሆሆሆ ✱ ኪኪኪኪ ✱ ሀሀሀሀምመመመም ✱ ✱ ✱ ✱ ✱ ✱ ✱ ✱ ✱ ✱ ✱ ✱ ✱ ✱ ✱ ✱ ✱ ✱ ✱ ✱ ✱ ✱ ✱ ✱ ✱ ✱ ✱ ✱ ✱ ✱ ✱ ✱ ✱ ✱

ሲ.ሉኝ?

ይሄ ሁሉ የዘረዘርኩት በሰኮንዶች የሚነገር አንድ አረፍተ ነገር ቢ.ሆን ለእኔ የሚተርፈኝ:

'ነይ እዚህ አፕረስድ ፒፕል ፋክ አይ ላቭ ጁውሲ ነሽ ዚ.ስ ዩ ላይክ ዚ.ስ አ! እሷ? ሎርድ! ልቤን ልታቆሚው ነበር አንብሊቨብል ኡፍ ሀሀሀምተመመም'

የተሰኘው ነው::

ከነዚ.ህ ቁርጥራጭ ነገሮች ባይገቡኝም አንዳንዶቹን እየለቃቀምኩ እንደገባኝ ሁሉ ባወራ ቀጣፊ ሆንኩ ማለት አይደለም?

ነኝ:: ማርያምን::

ታዲያ ሁላችን በሆነ ጎዳና ቅጥፈት አደባባይ ተገናኘን ማለት አይደለ?

ቀለም ተቀባ አልተቀባ ጥፍር ጥፍር ነው:: መቧ'ጨርም መቦ'ጨርም መቧጨርም መቦጨርም::

## የመጨረሻው ሸንኮራ

ከእዝራ ጋር መሻረካችን በሰፈር መወራት ከጀመረ ከረመ:: አዎ በመጠኑ ቅር ይለኛል:: እሱ መልከ-ስንኩል ሲባል እኔ ኪስ-ወይም ቦርሳ--ስንኩል በመሆኔም አይደለም:: ግን ለምን ቅር ይለኛል? ብዙ ነገር የሚተረጎም ነው:: አተረጓጎምና ትርጉም እንደ ባለቤቱ ነውና፣ በእኔ አተረጓጎም የሶስተኛ ደረጃ **መናቅ** በሕይወቴ ማስገባቴ ነው:: ምን ማለቴ ነው? እስኪ ልተርጉም:

***ከአንደኛው ደረጃ*** ልጀምር:: በደሃነቴ ተንቄአለሁ: ደርዙ በመርፌ የተዘመዘመ ዱልዱም ቀሚስ ለብሼአለሁ፣ የፀጉር መሰብሰቢያዬ ተራ ላስቲክ ለእኔ ብርቅ ነበረች፣ አተር አጥቤ፣ እስጥቼ፣ አድርቄና ከክቼ የሽሮ እህል ሰርቼአለሁ:: ያሳፍራል? በእንጦጦ የዛፍ ቅጠል በጢስ እየታፈንኩ እንጀራ ጋግሬአለሁ:: ውርደት ነው? አንድዋን የውስጥ ሱሪዬን አጥቤ እሷ እስክትደርቅልኝ ቤቴ ግቢ ወዲያ ወዲህ እያልኩ የጓደኞቼን ጨዋታ ናፍቄአለሁ:: ያሳዝናል? እርሳስ ተውሼ በስርቆት አስቀርቼአለሁ--እንዳልወሰድኩም በማርያም ስም ምዬአለሁ:: ያስከስሳል? ዛሬ ዛሬ ከወንዶች እጅ የምቀበላት ገንዘብ አጥግባኝ ይሄን ይሄን እንዳላሳለፍኩ ሁሉ እዋሻለሁ:: ይሄስ ብልግና ነው? መሰልጠን ነው? መሻሻል ነው? ወይስ እከኩን በጨርቅ መጋረድ ነው? ይሄ የዘረዘርኩት በዚህ ሕብረተሰብ ያለኝ ቦታ፣ በዚሁ ሕብረተሰብ አስንቆኛል:: እራሮት፣ ክስ፣ ብልግናና የመሳሰሉት የማይገቡበት ቦታ የተለያየ ቀለም ያላት ንቀት ሰተት ብላ ትገባለች::

***ሁለተኛ ደረጃ*** በአባቴ አብዮት ጠባቂ መሆንና መባል በንቀት ተገልዬአለሁ:: አብዮት ጠባቂነቱን የሚጠቀሙበት ግን እኔን ሊያገሉበት እንደሆን ይገባኛል:: በትምህርት ቤትም ይሁን በሰፈር አንዳንድ ልጆች ወይም ብዙ ልጆች (እንደቆጣሪው ይለያያል) በአባቴ አብዮት ጠባቂነት በሽሙጥ ያበሽቁኛል፤ ወይም አርቲ ቡርቲ ሲያወሩ ከደረስኩ፣ እንደፈሩ ሁሉ (ባይፈሩም) ልክ እንደማቃጥርባቸው ሁሉ (ይኼንንም እንደማላደርግ ያውቃሉ--ያውም የሚቃጠር ካላቸው) ተያይተው ጨዋታቸውን ያቆማሉ::

በእርግጥ እንዲህ የሚሰሩኝ አብዮት ጠባቂ አባቴን ፈርተው አይደለም:: ይገባኛል (ደስ ባይለኝም)፣ አጠገባቸው ስቆም ጎራዳዋን ጎራዳ እንደ ማደር ጋት፣ አስቀያሚዋ አስቀያሚ እንደምትሆን:: አጠገባቸው ስቆም ውበቴ አስደንግጠአቸው ራሳቸውን እንደሚጠሉ አውቃለሁ:: ልክ እንደ በደልኳቸው ሁሉ ግን 'ቀይ ሽብር አልፎአል' ቢባልም (ቀይ፣ ነጭ ሽብር ሲባል ብዙ የማይገባኝ ልጅ ነበርኩ:: ይኼንንም ያውቃሉ) ፣ ልክ አባቴ ነገ ተነስቶ ሁለተኛውን ክፍል እንደሚጀምረው ሁሉ 'ይህቺ ጥቤ መጣች' ይሉኛል:: አላማቸው የሚገባው ጥቂት ንቁ ነው:: አንዳንዴም እንዲህ ሲያርቁኝ፣ አእምሮአቸው ያልበሰለ ነገር ነውና፣ ክፍት ያለኝ ዕለት፣ 'እግዜር ሌላ ቀይ ሽብር አምጥተህ የቀረውን ነገረኛ አጥፋልኝ' እላለሁ::

ከቀናቸው (ማለት ለአግቦ የሚመች ሁኔታ ከተፈጠረ) ያሽሙዋጥ ጡኛል:: ግን ደሞ ባይቀናቸውም እንደምንም ብለው ለሽሙጥ የሚሆን ሁኔታ ይፈጥራሉ:: *'ብዙ አታውሪ* ነገር *ቢበዛ በአሀያ አይጫንም'* ይባባላሉ:: ቅኔው ሁለት ነው:: አባቴ ይሰራ የነበረውን የአህያ ነጂነት ስራ በጎን ጠቅሰው እንደገና በድራቢ 'ነገር' የሚለው ቃል ወደ ፖለቲካ ይመነዘርና 'የአህያ ነጂው ልጅ ካድሬዋ ወይም አብዮተኛዋ መጥታለችና ፖለቲካ አታውሩ' ይሆናል:: ደሜ ቢፈላ ይፈረድብኛል? አልተዋቸው አብረን የቆየን የዕድሜ ጓደኞቼ፡ አብሬአቸው አልዞር ሽሙጣቸው:: ይሄን ይሄን ትምህርት ይቅርና የመንጌ ጥይት አይመልሰውም:: ሆን ብለው ካማሰሉት እንኳን አገር ድስት አይረጋም:: ማርያምን:: ድብልቅልቁ የፖለቲካ ነገር የሚያልፍ አይመስልም:: ከዚህም ጋር መገለሌ አያልቅም:: በትክክል የሚያልፈው ሌላ አይነት ሽብር መጥቶ ሲቀንሳቸው፣ ወይ የሆነ አደጋ ደርሶብኝ ፊቴ በእሳት ሲቃጠል፣ ወይ አውቶብስ ተገልብጦ እግሬና እጄ ተቆርጦ አካለ ስንኩልና አስቀያሚ ስሆን፣ ወይም ይሄ አገር ከምድረ ገፅ ለማንም ሳትሆን ስትጠፋ ነው:: አንዳንዴ ከሁሉ አንዱ ቢሆን ግድ የለኝም:: ከመሰል እኩያዬ ልጆች ጋር አለ አይደለ መጫወት እወዳለሁ፣ መላከፍ፣ መተራረብ፣ ያሰኘኝን ማውራት እወዳለሁ:: ይሄ ስህተት አይደለም:: ግን ትንሽ የበልጥኳቸው ወይም የተቀናቀንኳቸው ከመሰላቸው 'ይቺ ጥቤ ጠገበች'ምናምን ይሉኛል።

አባቴ (ለሌሎች ሲያወራ እንደሰማሁት) በብዙ ሰዎች ተሳዷል:: ሃብት ያላቸው ሳይጎዳቸውና ሳይደርስባቸው፣ የለፉበትን እቃ አቃለው፣ የተሸከመውን እንጨት ጥራትና ክብደት ተርበው፣ ዋጋውን አርክሰውበታል:: ቃል የተገባለትን የዱቤ ገንዘብ በማጭበርበር ነጥቀውታል:: ታዲያ ቀን ተለውጦ ቂሙ አብቦ እንደዛ ዓይነት ሰዎችን አብዮት ጠባቂ ሆኖ ቢያንተሸትሻቸው ሊፈረድበት ነው? ቂም ይዘሩና እንድንረሳው ይፈልጋሉ:: ይደቁንና እንድንዘነጋላቸው በሰው ልጅ

ወንድማማችነት፣ በሁሉን አዋቂ አምላክና በመላዕክት ስም ያባብሉናል:: አባቴ አልዘነጋም:: መዋረዱን አልዘነጋም:: በየቀኑ ሲቀበቀብበት እንዴት ይዘነጋል? ጊዜ ሳይሰጡ በንቀት ሲያርሱት እንዴት ልቡ ይለስልስ? ተሳስቶ ቢዘነጋ ቂል ሊባል ነው? ቅዱስ?

**እርስዎ ከበደሉት**

**ቀን ጠብቆ**

**ልክ ቢያስገባዎት--**

**አይቀየሙ::**

**በልብዎ 'ይገባ'ኛል' በሉ**

**እንደውም 'ሲያንሰኝ ነው' በሉ**

ትክክለኛው ድርጊት ንስሐ መግባት እንጂ ምንም የማላውቀውን ልጃን ማንጓጠጥና ማዋረድ አይደለም:: ይሄንንም የሚሉኝንን ሁሉ መዝግቤ፣ ቀን ሲመጣ፣ አባቴ ብቻውን አይሆንምና እኔም ከእሱ ተደርቤ ባቀምሳቸው ይገርማቸው ይሆን? አሁን እንዲህ ስል ቢሰሙኝ 'ማሪያምዬ ምን አይነቷ ጨካኝ ናት!' ማለታቸው አይቀርም:: ማርያም ታንሳቸውና::

እኔ ግን እነሱን በመሰሉና በሌሎች የማግለል ክፋት ተማርሬ፣ ልቦናዬ ተጎሳቅሎ፣ እንደ አባቴ በሰቀቀን ተሞልቼ፣ ቂም በሆዴ አርግዤ፣ ቀን እስኪለወጥ ጠብቄ፣ ሰው ማመስ አልፈልግም:: ግን ደደብ ናቸውና አይገባቸውም:: ቢሉአቸው ቢሉአቸው አይገባቸውም:: እነዚህ ከአባቶቻቸው ያልተሻሉ፣ ክፋትን አራዳነት ያደረጉ፣ ደናቁርት ሆነው እንደ አዋቂ የሚሰራቸው፣ ደርግንም ሆነ የደርግን ጠላት እንደ ፋሽን የሚጥሉና የሚያነሱ፣ ሰው ላይ ለመፍረድ ራሳቸውን በግድ መልካም ያደረጉ ናቸው:: ልማድ ቶሎ ይተዋል? (ያውም አለም ያደነቀው)

በአጠቃላይ ሳስበው አፌ ላይ የሚመጣልኝ የተከበረ አጭር ቃል 'ደደብ' የሚለው ነው:: ደደብ 'ደደብ' ሲባል ይጠላል፡ ብልህ 'ደደብ' ቢባል 'ለምን ተባልኩ?' ብሎ ያስባል፤ ከሆነም እሱን ለማረም ይለፋል:: ደደብነት ያለብን ግን እናፍራለን፣ እንቆጣለን:: ደደብ መሆን የማችለው ሰው እንጂ ሌላ ፍጡር እንዳልሆነ እንረሳለን:: ማለቴ በሆነ መልክ ሂሂሂ ደደብ መሆን ምርቃት ነው::

*ሶስተኛ ደረጃ* ከዚህ ከአባቴ ሕይወት ጋር የተያያዘው ሶስተኛው ምክንያት ደሞ መውጫ መግቢያ እንደሌለኝና የተሻለ ወንድ ማግኘት እንዳቃተኝ ሁሉ 'ለገንዘብ ብላ ማንም ሴት ከዘጋችው አስቀያሚ ጋር ወጣች' ተብዬ ስሜ መነሳቱ ነው:: እንዴት በሶስት ትርያንግል ዕርግማን መሃል ሳላብድ በጤና መቆም እችላለሁ? 'የፍቅር ትሪያንግል' እንደሚሉት የእርግማንም ይኖረዋል::

ቀስ በቀስ አንዳንድ ጥያቄ መጠየቅ ጀመርኩ:: የሆነ ርጣቱ[154] ስረፀብኝ---(እዝራ እንዳዛ ይል ነበር በምን ቁዋንቁዋ እንደሆነ አላውቅም) በችኮላ በዓይኖቼ ገርፌ የማልፋቸውን ነገሮች በቀስታና በጥርጣሬ ማጤን ጀመርኩ:: የሚከነክነኝ እውነት እያየለብኝ መሰለኝ ረጋ አልኩ:: የማየው ነገር በዕርግጥ የማየው ካልሆነስ? ከማየው ስር የተደበቀ ነገር አለ? ወይስ ሁሉ ሲጀመር እንደዛ ነበር? አለም ስትፈጠር ከውሃና ከድንጋይ ጋር ከብርሃንና ከጨለማ ጋር አምላክ ራሱ 'ቅጥፈት ሁኚ!' ብሎ ቅጥፈትን ሰራት? ውርደትን ከምናምን ፈትሎ 'እፍ' ብሎ ጠርቷታል? መቅለልን ድካምን ምንምን ምኑምን ሁሉ ሲጀመር ሰርቶአቸዋል? አዳም ያደረገው ነገር እዛ ውስጥ እየተራመደ መግባት ብቻ ነበር? በልቤም ማሰቡና ማመዛዘኑ ሲከብደኝ፣ በሃሳብ ተጉገሬ ተጉገሬ 'ሁሉ ከልኩ ሳያልፍ ምን አስጨነቀኝ?' እላለሁ::

......እዝራ ለመጀመሪያ ጊዜ ያወጣኝ ከሰፈሬ ውጭ ነው:: እዛው ታዚና ሬስቶራንት አቢሮው የሚያስተናግደኝ መስሎኝ ነበር:: መጀመሪያ ታዚና ገብቶ ለሰራተኞቹ መሰራት የሚገባውን ነገር ነግሮ የተደረገውንም ተቆጣጥሮና 'አመራር ሰጥቶ' (እሱ ሲለው ግን......ቃሉ ቀልድ ይመስላል) እስኪመለስ ድረስ መኪናው ውስጥ እንድጠብቀው ነግሮኝ ሄደ:: እዛ ውስጥ ተቀምጬ ካልለመድኩት አቅጣጫ የሰፈሬን ስፋትና ጥበት ስመለከት፣ የመኪናውን የጋለ ብረትና የሞቀ የላስቲክ ሽፋን ሳሽት፣ እዛ ውስጥ የረገፉትን የአምስትና የአስር ሳንቲሞች ብዛት ስቆጥር፣ መሳቢያ ውስጥ ያገኘሁትን ትልቅ የፀሐይ መነፅር ሳገላብጥና ስለካ፣ አንድ ተስፋዬ የተባለ የሰፈሩ የእኔ ቢጤ ዕብድ መጥቶ የመኪናውን መስኮት አንኳኳ:: ተስፋዬ ዕብድ የሆነው በፖለቲካ ነው ይባላል:: 'ተስፋዬ ክሬዚ' ይባላል::

«እስኪ አንድ ስሙኒ አለሽ?» አለኝ:: ሳልከራከር ከቦርሳዬ (ፍፁም የገዙልኝ) ሌላ ቦርሳ አወጣሁና *ማነው እቴ እሱ የገዛልኝ?* ስሙኒ ሰጠሁት:: ስሙኒዋን ተቀብሎኝ እሷንም እንደ ልዩ ዕቃ አገላብጦ አያትና ምንም ሳይናገር ትቶኝ ፊት ለፊቴ ታዚና መግቢያ ድልድይ ላይ ለተቀመጠች አንዲት ሴትዮ ገንዘቡን ሰጣት:: ቆሞ አወራትና በቀስታ እየተራመደ በመኪናዬ ቂጥ አቅጣጫ ወደ ላይ ወጣ:: ተነፈስኩ::

ሁለት ሰዎች እፈራለሁ:: ተስፋዬን እፈራዋለሁ:: ተስፋዬ የእናቸርነት ጓደኛ የነበረ በፖለቲካ ምክንያት ያበደ ልጅ ነው:: አንዱ 'ባንዳ' ሲለው፣ አንዱ 'ኢሕአፓ' ሲለው፣ አንዱ 'ተገንጣይ' ሲለው፣ ጓደኞቹ ሁሉ በተሰጠው ስያሜ ምክንያት ሲሸሹት (ማን እንደሰየመው ባይታወቅም)፣ አንድ ሌሊት ከቤቱ ወጥቶ እዚህ መንገድ ላይ ቀረ:: አሁን አሁን ተወ እንጂ በመንገድ ላይ 'የለሁበትም!!' እያለ እየጮኸ ይሮጥ ነበር አሉ:: አላጋጠመኝም:: ማንም ቤት ሄዶ የሚበላ ሲጠይቅ የሚነፍገው የለም::

---

[154] የደመ ነፍስ ጥርጣሬ (ምክንያቱ ግልፅ ያልሆነ)

እንደውም ይንከባከቡታል:: አሳብደው ይንከባከቡታል:: ብዙ ሰው የማያውን ስለሚያይ ዕብደቱ የባሰበት ዕለት እየጮኸ ይናገራል:: ይሄኑ ስለ ፍጹምና ስለ እኔ ያውቃል:: ከተስፋዬ ሌላ እዛ ታዜና ሆቴል ስመጣ የምፈራው ዋሕድን ነው:: ከአባቱና ከእናቱ ጋር በደንብ ይተዋወቃል:: ድሮ እማማ ጠላ ቤት ያላት ጊዜ የማይቀር ደንበኛዋ ነበር:: እማማ እንጀራና ቂጣ በምትነግድበት ጊዜም ከምትሸጠው ሁለት እንጀራ ትቀንስና 'ይሄ ለዋሕድ ነው እንዳትሸጪው' ትለኛለች:: ሰርተን ወደ ቤት ስንመለስ እግረመንገድዋን እንጀራውን ለእሱ ሰጥታው ሂሳቧን ተቀብላ ስትሄድ አንድ የሽንኩራ መለኪያ ይሰጠኛል:: ምንም እንኳዋን አንድ ሁለት ቀን ሞቅ ብሎኝ ከአለም አንተ ጋር ታዜና ሆቴል ለመጸራት መጥቼ ቢያየኝም፣ ልበላ የመጣሁ እንጂ ለሌላ እንዳልሆነ እንዲረዳ ማድረግ ለፍቼአለሁ:: ያን ጊዜ ደሞ እሱ መንገድ ዳር ሽንኩራ እየቆረጠ ይሸጥ ነበር እንጂ የታዜና ሽንኩራ ጨማቂ አልነበረም:: ሆቴሉ ስገባ ቢያየኝም ቢርቃ እንደያዝኩ አያውቅም:: ግን ሊያውቅ ይችላል እያልኩ እፈራዋለሁ:: ግን እኮ በሰፈሬ ለመታማት መታየት አስፈላጊ አይደለም:: በባዶ መታማትም እንደ ልብ ነው:: ይሄንን ደሞ የሚታማውም፣ አሚውም፣ ሃሚት ሰሚውም ያውቃል:: እያወቁም ግን ያምናሉ:: ይሄ አይነት ፀባይ ስሙ 'በሽታ' ይባላል::

በእንግሊዘኛ 'ዲዚዝ'[155]::

የሚታማም ሃሚቱ ትክክለኛ እንኳዋን ቢሆን በቀላሉ ለማርከስ ይጥራል:: 'የእኛ ሰው ዝም ብሎ ያወራል......ወሬኛ' ብሎ ማምለጥም ይሞክራል:: ከታደለ ይሆንለታል፣ ካልታደለ......

መኪና ውስጥ ተቀምጬ እዝራን ስጠብቅ ለከበቡት ሰዎች ሽንኩራ ይሸጥ የነበረውን ዋሕድን እያየሁ *ለመሆኑ እዚህ መኪና ውስጥ በመቀመጤ የዘየድኩ ይመስለዋል? ወይስ የተሸራሞጥኩ? እኔን ማየቱን ለአባባ ለእማማ ዛሬውኑ ሄዶ ይነግራል ወይስ በዝምታ ይታዘባል?* እያልኩ አስባለሁ::

ደፍሬ ባናግረውና ባውቅ ደስ ይለኝ ነበር::

እዝራ ከሆቴሉ ፌስታል አንጠልጥሎ እየሮጠ ወጣና መኪና ውስጥ ገባ:: ፌስታሉን ወደ ጀርባ አስቀመጠና:

«አስጠበቅሁሽ?» አለ ቁና ቁና እየተነፈሰ:: ማን ሮጠልኝ እንደዚህ? ማን አከበረኝ? በዝምታ በልቦናዬ ፃፍኩ::

«......ኸረ እንደ......ምንም:: መኪና ውስጥ እኮ ነኝ ሂሂሂ»

[155] በሽታ ( Disease )

መርካቶ እስክንደርስ ሶስቴ 'ታዴያስ ማክዳ' አለኝ:: ሶስቴ 'አለሁ' አልኩት:: ቀስ ብሎ እየነዳ በመርካቶ በኩል አድርጎ በሆለታ መንገድ በመድሃኒያለም ትምህርትቤት በኩል እዛ የአዲስ አባ ውሃ ከሚመጣበት ገፈርሳ የተባለው ሃይቁ እማላውቅበት ቦታ ወሰደኝ:: ከሰው ዓይን ሊያርቀኝ ነው? 'ዱርዬ' ስለምባል አፍሮብኝ ነው? ብዙ ጠማማ ነገር አሰብኩ::

እውነቱን ነው ታሪኬን ፈራሁት:: የሰፈሬ ሰው ስለሆነ ፀባዬ በወሬ አያመልጠውም:: ደሞስ እሱ ቤት ከሰዎች ጋ እየመጣሁ ስሄድ ያየኝ አልነበረም? ምናልባት ልብ ካለ? ልብስ ላይል ይችላል?

መኪናውን በአፈርና በኮረኮንች መንገድ ላይ ሲነዳ ቆየና ገፈርሳ ሐይቅ ዳር ትልቅ ዛፍ ስር አቆመ:: ዛፍ እፈራለሁ:: የዛፍ ጥላና ቅዝቃዜ ያባባኛል::

«ቦታው ደስ ስለሚል ነው ያመጣሁሽ:: ከተማ ጥሩ አይደለም:: ደሞ ያሰለቻል:: አይሰለችም ከተማው?» አለ::

«አስቢው አላቅም» ደሞ አዲስ አባ ሲመሠረት የተወለድክ ትሆን ይሆናል አልኩና በልቤ፣ ሳቅ አልኩ::

«ምን አሳቀሽ?» አለ

«እንደዚህ ከከተማ ወጥቼ አላውቅም»

«እዚህ ደስ ካላለሽ ወደ ከተማ እንመለስ»

«አይ......ደስ ይላል፡ ምንም አይደለም»

«'ምንም አይደለም' ማለት እኮ 'ከሆነ ምን ላድርግ?' ማለት ነው»

«አይደለም......እዝራ ደስ ይላል፣ የምር»

«እውነት?»

«እማማ ትሙት» እንዲህ ለማንም ወንድ ምዬ አላውቅም:: ግን ጨዋ ያስመስላል::

ልፉቴ አያባባም? ለመሆኑ አዲስ አባ ከተማ የት ጀምሮ የት ያልቃል? የምንጠጣው ውሃና የምንጋግርበት ገፈርሳ ራሱ አዲስ አባ አይደለ? ገፈርሳ በሬ የሸናው አይደለ ቤቴ መንግስት ቧንቧ ቁጭ ያለው? ሂልተን ውስጥ የሰርጂታ ሰጪ ድርጅት ተወካዮች ገላቸውን የሚታጠቡበት ወይ ቢራውን የሚጠጡት? ለመሆኑ አዲስ አባ የሚረግዙ ፈረንጆች በርግጥ ፈረንጅ ናቸው? የውስጣቸው ቅመም ጠቅላላ የአዲስ አባ አፈርና ኩበት አይደለ እንዴ? እኔ ራሴ አሜሪካን ባልሄድ በተለየ መልክ እዛ እሆን ይሆናል:: ይሄኔ አሜሪካ ባልሆንም የዋሽንግተን ዲሲ ኑዋሪ ነኝ ሂሂ......'ወደ ውጭ እንሂድ' እያሉ የሚያስቸግሩት 'ኢሚግሬሽን አስቸገረን' የሚሉት ውጭ ከሄዱ ከርመዋል:: የሚጠጡት ውሃ ውስጥ የአሜሪካ ኮካ ሲብስ ደሞ የአምባሳደሩ ጢም አለ:: ታዲያ ሁልጊዜ

ፎቶው ላይ እንዴት ያለጢም እየዋለሁ? እዚህ ገፈርሳ እየዶለው ካልሆነ በሚስጢር ምናምን?

«ምን አሳቀሽ?»

«እያሰብኩ»

«ምን እያሰብሽ?»

«አሁን ይሄ ሁሉ ውሃ አዲስ አባ ሆድ ይገባል:: ግን እያንዳንዷ ጠብታ ከየት እንደመጣች የሚያውቀው የለም:: ሊያውቅም አይችልም»

«ጥሩ አስተያየት ነው:: ለምን አይገባንም መሰለሽ? ሲመስለኝ ርጣቂ የለንም:: 'ርጣቂ' አተኩሮ ማጥናት ነው:: እኛ አተኩረን ያጋጠመንን እናወራለን እንጂ አናጠናም:: አእምሮአችን ሰነፍ ስለሆነ ከሌላ ሰው ምላስ ነው ዕውነትን የምንቀበለው:: ከጠላታችንም ምላስ:: ከሚያጠፋንም ምላስ:: ርጣቂ ያስፈልጋል:: እስኪ እንረጥቅ ሃሃሃ»

«እም» አልኩ ለራሴ:: *ምን ማለቴ ነው ነበር??*

«በአጠቃላይ ሰሙ 'ገፈርሳ' ይባላል:: እያንዳንዷ ጠብታ ከየት እንደመጣች አምላኬ ብቻ ነው የሚያውቀው:: መኪና እየነዳን ገላምጠነው ያለፍነው እረኛ ሽንቱ እዚህ ነው:: ከአውቶቡስ ወርዶ እናቱ እየሰደበችው የሚፀዳዳው ልጅ ከገላው ያወጣው ቆሻሻ ላይ ያበበ ሰላጣ እንበላለን»

«ምነው በእናትህ! ሌላ ጨዋታ አምጣ»

«እውነት ከባድ ናት»

«ታዲያ......»

«ትንሽ በርግጊ.»

«ምነው በእማማ ሞት አስጨነቅሽኝ»

«ይቅርታ ሃሃሃ»

ከመኪና ተከታትለን ወረድንና እሱ ከጋቢና ሁዋላ ያስቀመጠውን ፌስታል ሲያወጣ፣ እኔ ዙሪያ ገባዬን ማየት ጀመርኩ:: እዝራ አንድ ዛፍ መርጦ ከስሩ ሳርማ ቦታ ላይ ፌስታሉን አስቀመጠ:: ራቅ ብሎ ካለ የድንጋይ ጉብታና የቄጠማ ደን መሃል መምጣታችንን የሰሙ ዳክዬዎች ተደናግጠው እያስካኩና እየተንደፋደፉ ተነሱ::

«ውይ!! ዳክዬ!» ስል በድንጋጤ:

«ዳኪዎች አይደሉም ዝዮች ናቸው» አለኝ::

*ምን አገባኝ አልኩ በሆዴ::* ካስደነገጠኝ በሁዋላ *ዞሮ ደክሮ ምን አገባኝ::* ፌስታሉን ከፍቶ ባለሰንበር አረንጉዋዴ የበዛው፣ ብርድልብስ የሚያክል ፎጣ አወጣና መሬት ላይ አነጠፈ:: ከዛ አንድ ሰታቴ ድስት የሚያክል

አገልግልና አንድ የአልኮል ጠርሙስ በግራና በቀኝ እጁ አወጣ:: ቀና ብሎ አየኝ እየሳቀ::

«ነይ ተቀመጪ ፌሽታ እናደርጋለን:: አልኮል ካልፈለግሽ ኮካ አለ» አለ እየሳቀ

«ግድ የለም ትንሽ እጠጣለሁ»

«ረም ይባላል:: ታዚና የሚመጡ የጃማይካ ልጆች አሉ:: እነሱ አመጡልኝ»

«እነሱ ሰዎች እጠፋርስ ምናምን ያጤሳሉ አደለ?»

«እኔ አላጤስም:: ተጠራጥረሽ እንደሆነ:: እነሱ ከፈለጉ ምን አገባኝ:: ደሞ ሃይማኖታቸው ነው»

«ነው እውነት?»

«አዎ:: ማንም ይሁን፣ ምንም ይብላ አገሬን ከወደደ ወዳጄ ነው:: አይመስልሽም?»

ምን እንደምመልስለት አላወቅሁም:: *ዕፅና አገር: ዕፅና ረም ምን አገናኛቸው?* እያልኩ ሳስብ ከት ብሎ ሳቀ:: ምን አሳቀህ አይነት አየሁት::

«ላስጨንቅሽ አይደለም:: ለመዝናናት ነው የመጣሁት:: ባጭሩ አንቺን ከወደድኩ ከነሁለመናሽ ነው የምወደው ማለት ነው»

ለመልስ ፈገግ አልኩ:: *ፈገግ መልስ ይሆናል?* 'ሁለመናሽ' ከባድ ቃል ነው:: እንደገና ሳቀ:: እንዴት ነው አስቀያሚ ገጣጣ የተበላሸ ጥርስ ያለው ሳቁ የሚያምረው? ሊያበረታታኝ ነው መሰል ተቀመጠና ሐይቁ ላይ አተኮረ:: *ምን ያስባል?* ልጠይቀው አልፈለግሁም:: ከተቀመጠበት ተነስቶ እጄን እየጎተተ አጠገባችን የነበረ ከፍ ያለ ቦታ ላይ አወጣና አቆመኝ:: የዛ ከፍታ ሙቀትና ነፋስ ደስ ይላል:: የአየር ውበት በቆዳዬ መለካት ካቆምኩ ቆይቼአለሁ:: በትንሹ ወደ ልጅነቴ ሄድኩ:: ፊቴን እዝራ ወደ ሚያየበት አቅጣጫ መለስኩ:: እንዲህ በስፋት የቆመ ብዙ ውሃ አዲስአባ አካባቢ ይኖራል ብዬ ገምቼ አላውቅም:: በከተማው የሚጠጣ ውሃ መሆኑ ምንም ምልክት አያሳይም:: እንዴት ያሳያል? ባሕሩ ላይ ነጫጭና ጥቋቁር ወፎች ከፍ ዝቅ ይላሉ፤ ከውስጥ ዘለው ተነስተው ወደ ባሕሩ የሚጠፉ አሶች አሉ::

ኮቱን አወለቀና አንድ አጭር ዛፍ ቅርንጫፍ ላይ አስቀመጠ::

«ነይ» አለና እጄን እየጎተተ ቁልቁለት ይዞኝ ወረደ::

አጭር ጊዜ እንደተንደረደርን ከፊት ለፊታችን ቀደም ብሎ ያልታዩኝ ረግረግ መሬት ላይ የበቀሉ ጥዋ የመሰሉ ብዙ ነጫጭ አበቦች የበቀሉበት መስክ ጋ ደረስን:: አበቦቹ በወፋፍራም ወዛም ዘንግ ላይ የበቀሉ ናቸው::

ከስራቸው በተኛና በቆመ ቄጤማ ተወረዋል:: ቄጤማው በተለያየ አቅጣጫ በሚዶ የተበጠረ ይመስላል::

«አንድ ነገር ልጋብዝሽ» አለና የያዘኝን እጄን ለቆ ወደ አበቦቹ ሄደ:: አንድ አራት የሚሆኑ አበቦችን ከግንዳቸው ላይ በቀስታ ነቀላቸው:: አንዱን አዞረና በቂጡ በኩል ጠባው:: አጣጣመና የቀሩትን ደረቱ ላይ እንደ ሕፃናት አቅፎ አመጣና ከታች ሆኖ አንዱን አበባ ሰጠኝ::

«ሞክሪ» አለ

«ይሄን ሳይሆን ሌላ አይነት አበባ እንደዚህ አድርጌአለሁ» አልኩት ሳልቀበለው::

«በጣም ደስ ይላል» አለና አዞሮ ወደ አፌ አስጠጋው:: መጠጥኩ:: አፌ ውስጥ የሚጥም ወለላ ፈሰሰ:: የአድናቆት ድምፅ አወጣሁ:: አቅፎ የያዛቸውን አበቦች ሰጠኝና ሌላ ሊያመጣ ተመለሰ:: የተቀበልኩትን አበቦች ፋታ ሳልሰጥ እያከታተልኩ ጠባሁ:: አይኖቼ ልዩ መድሃኒት እንደ ወሰድኩ ሁሉ ቦግ አሉ::

«ብዙ ላምጣ?» አለ ዞር ብሎ

«ምናለበት»

«አምስት አምስት ይበቃናል» አለ

አበቦቹን ይዞ ከመጣ በሁዋላ፣ በሙሉ ለእኔ ሰጥቶኝ ኮቱን ከሰቀለበት ዛፍ ላይ አውርዶ ለበሰ:: ከአበቦቹ ልሰጠው ስል፣ በእጁ የበቃኝ ምልክት አሳየኝ::

«እንኩዋን ተውክልኝ» አልኩ እየሳቅሁ::

«ሌላ ላሳይሽ?» አለ

«ምን ሌላ ሚስጢር አለ? እንየዋ!» አልኩ ከት ብዬ:: ይሄ ሁሉ የምታዪው ባህር ዛፍ ማገዶና ጥላ ብቻ ይመስላል:: አይደለም:: እንደ አገዳ ቁጠሪው:: ለብዙ ነገር ደንቆሮ ነን:: ይሄ ሁሉ ዛፍ ወለላ ነው»

«እንዴት? የማላውቀው የለም» አልኩት በጉራ

«የተከለከለ ወግ አፍርሰሻል? ልክ ሎም እንደማፍረስ?»

አልገባኝም::

«ይሄ ሁሉ ዛፍ መረቅ አለው:: ላሳይሽ......» አለና ሱሪ ኪሱን በረበረ:: በእጁ ሳንቲሞችና ሴንጢ ይዞ ወጣ:: ሳንቲሞቹን ኪሱ መልሶ ሴንጢውን ዘረጋጋና አጠገቡ የነበረውን ዛፍ ከፍ ዝቅ አድርጎ ልክ እንደ ሰው አየው:: እንደ ሰው ሳይሆን እንደ ሽንኮራ:: ከዛ ወገቡ ላይ በፍጥነት በሴንጢው ቆረጠው:: ከአፍታ በኋላ ስለቱ ባለፈበት ቀጭን መስመር ላይ ደቃቃ የዉሃ ኳሶች ብቅ አሉ:: ጎንበስ ብሎ እነዛን የውሃ ኳሶች በምላሱ

ላሳቸው:: እንደገና ከዛ ትንሽ ከፍ አድርጎ ሌላ ሽንትር አበጀና ዞር ብሎ አበባ የያዘ እጄን እየጎተተ ወደ ዛፉ አስጠጋኝ::

«በይ»

ምን ማለቱ እንደሆነ ገባኝና ፍጭጭ ብሎ የወጣውን የባህር ዛፍ ወለላ እያፈርኩ በምላሴ ጫፍ በቀስታ ላስኩት:: ከሴንጢው ጨካኝነት ስር ይሄ የሚያምር ጣፋጭ የሚፈልቅ አይመስልም:: እንዲህ አድርጌ አላውቅም:: እንግዳነቱ እንዳስደሰተኝ ፊቴ ላይ አየ መሰለኝ እዝራ ከመጀመሪያው ስንጥቅ ከፍ አድርጎ ሌላ ስንጥቅ ቀደደ:: እሱንም ላስኩ:: ለጋ ዛፍ ነው:: ዛፉን እንደ ፍቅረኛ ከላይ እስከታች አየሁት::

«እንዴት ነው?» አለ

«አሪፍ ነው»

«አበባ በይው ዛፍ የወለላዎች ጣዕም ይመሳሰላል አይደለ?»

«እ......»

ዕድሜዬን ሙሉ ሰፈር ውስጥ ስኖር ይሄን የባህርዛፍ ጉዳይ ባለማወቁ ተበሳጨሁ::

«ሽሮሜዳ ሌላ ናት አደለ ለዚህ:: ከባህር ዛፍ ሽንኮራ ይፈጥራል ሃሃሀ፣ ብዙ ወለላ ከጠጣሽ አፒታይትሽ ይዘጋል፣ አገልግላችንን ለማን እንተወው:: ሃሃሃሀ ወደ መኪናችን እንሂድ» አለ

በእቅፌ የያዝኩዋቸውን የቀሩትን አበቦች በየተራ በመምጠጥ ላይ እያለሁ ወደ መኪናው ከመሄድ ይልቅ ቆም ብሎ የጠራው ሰማይ ላይ የሚሄደውን አንድ ጭስ የሚተፋ አየር መርማሪ አተኩሮ ሲያይ ቆየ:: ሲያተኩር የብልጥ ግንባር እንዳለው አየሁ:: ግንባሩን ሳይ ፈራሁት:: ልፈላሰፍ ከሚለው ለስላሳ እንደበቱ ጀርባ፣ ከቂላቂል ገፁ ጀርባ፣ እንዲህ ሲያተኩር ምንም ነገር የማይሳተው ብልጥ ይመስላል:: እንደዛ ሲያይ ከአይሮፕላን የተለየ ሌላ የማይገባኝ ነገር የሚያይ ይመስላል:: በተለይ ምግብ ቤት፣ ከሰራተኞቹ ጋር ሲያወራና ወዲያ ወዲህ ሲል፣ ምንም የማይገባው ካሽ ብቻ የሚሰበስብ፣ ማንም ሊያታልለው የሚችል የዋህ ይመስላል:: እንዲህ እያየሁት ጥርሶቹ ወደ ድዱ ልክ እንደ አንቴና እየተሰበሰቡ ገቡ:: እንዲህ እያየሁት የተስተካከለ ነጭ ጥርስና ጠቆር ያለ ድድ እንደ ገና በቀለ:: አባባኝ:: እየፈራሁ እጄን ሰድጄ እጁን ያዝኩት:: ዝቅ ብሎ የያዝኩበት እጄን አይቶ ጠበቅ አድርጎ ያዘኝ:: ነጭ ዋዲያት አለው:: የማውቃቸውን ሰዎች መዳፍ ማስታወስ ሞከርኩ:: የማንንም አላየሁም:: ባይም ትዝ አይለኝም:: ምክንያቱም እጄና እጃቸው አልተገናኙም:: ቀና ብዬ አየሁት:: እኔን ይሁን የማረከውን ሰማይ እያሰበ እንደሆነ አላውቅም:

«አገራችን ልዩ ናት። የማስበው ልዩ መሆንዋን ነው። ይገርመኛል። 'እንዴት ነው ሌላ አገር ሳታይ ልዩ መሆኑን ያወቅሽው?' አትበይኝ። አንድን ግመል በረሃ መሃል ብትጥይው በቀጥታ ይፈነጥዛል፣ አያቅማማም። ዕድሜ ልኬን በደስታ አልኖርኩም፣ ግን አይኖቼን ገልጬ ተራራዎቼን ሳይ ትክክል ቦታ እንዳለሁ አውቃለሁ።»

«ለምን?»

«ሁልጊዜ ድንግል ናት። ሁልጊዜ ትደፈራለች፣ ግን ሁልጊዜ አዲስ ናት። እየወደቀች መነሳት»

*ምን አመጣው ይሄን ወሬ* እዚህ አልኩ በልቤ። *እንደዚህች አገር መሆን እችልበታለሁ?*

ውሃ ጠማኝ።

«ይሄን ውሃ ሳይ፣ ውሃ ይጠማኛል» አለ እዝራ።

ደነገጥኩ። እኔም 'ጠማኝ' ልል አልፈለግሁም። እጄን ይዞኝ ከጉብታው ላይ ወረድንና መኪናው አጠገብ የተነጠፈው ፎጣ ጎን ሄድን። ምን ላድርግ? እጁን ለቅቄ ቦርሳዬ ጎን ሳር ላይ በቀስታ ተቀመጥኩ። ባዶ ከመሰለው ፌስታል ውስጥ ሌላ ፌስታል አወጣ። ከዚያም ውስጥ ሁለት ብርጭቆዎችና አንድ ድፍን ሎሚ አወጣ። አንዱን ብርጭቆ እኔ ፊት ሌላውን እሱ ፊት አስቀመጠ።

«ረም እወዳለሁ። አይገርምም? ረም እየወደድኩ ፊልቴር ስሸጥ?»

ፈገግ አልኩ

«አገልግሉን ከፈቺው»

«ምንድነው?»

«ጥብስ ስፔሻል ወይም ጥብስ ማከዳ»

«ሂሂሂ መታጠብ ያስፈልጋል። ደሞ አሁን አልራበኝም»

«ሞክሪ የምትችይውን ያህል»

«እጄን እዚህ ልታጠብ?»

«የምታቆሽሺው መስለሽ የምንጠጣው ነው ስላልኩ? *የገፈርሳ ልጅ እጁ ቆሻሻ ነው* እንባል እንዴ? *የላጪን ልጅ ቅማል በላው* አይነት። የዚህን ሐይቅ ውስጡን ብታዪ የአዲስ አባን ውሃ አትጠጪም»

«ምነው?»

«ወይስ ቆሻሻ ነው ብለሽ ነው? የዕውነት ግን በጣም ቆሻሻ ነው። የሞተ ከብት፣ የሞተ ጅብ፣ የሞተ ሰው አይጠፋም። በሞተ ነገር የተሞላ ነው»

«በስማብ»

«እዎ:: ግን ይፀጻል»

«ለምን ለገፈርሳ አልተዘፈነለትም?» ምን ማለቱ ነው?

«ምን አልሽ?»

«የአዲስአባ ዘፋኞች ለካዛንቺስ፣ ለፒያሳ፣ ለመርካቶ ምናምን ግን ለሚያሳድራቸው ገፈርሳ አልዘፈኑም»

«ለምን እንደዚህ አሰብሽ?»

«ለምን እንዳሰብኩት እንጃ:: ምናልባት እዚሁ ተወልጄ እዚሁ አድጌ የምጠጣው ውሃ ምን ይመስል እንደ ነበረ ባለማወቄ ቀሽምነት ተሰምቶኝ ይሆናል:: ብዙ ጊዜ ቀሽም የሆንኩ ይመስለኛል (ድምጼን አኮስሼ)»

«ብዙዎቻችን እንደዛ ነን:: አዎ ቀሽምነት ነው:: ብሩህ መሆን እኮ ያለሽበትን ሁኔታ ማወቅ ነው:: ደሞም ይከብዳል:: ለመጠየቅም ለመመለስም ድፍረት ይጠይቃል:: ዮት ነኝ? ቀላል ጥያቄ ይመስላል:: ግን ይሄን ካስተካከልሽ በሁዋላ፣ ምን አለ አካባቢዬ? ትያለሽ:: ከዛ ትክክለኛ መስመር ላይ እንዳለሽ ይገባሻል:: አሁን ኤኤስኤልሲ ብታልፊም ብትወድቂም አዋቂ አያደርግሽም:: ገፈርሳን ስላላወቅሽ በትክክል አላወቅሽም:: ድሮ መዝናናት እወድ ነበር:: ከእነ ዓላዛር፣ ደቤ፣ ቸርነት፣ ገርማሜ፣ አማን፣ ተስፋ ጋ---ብዙ ልጆች ነበሩ......መኪና ከቤተሰብ ሰርቀን በአንድ መኪና አንዳንዴ ስድስት ሰባት ሆነን እዚህ እንመጣለን:: ታውቂያለሽ ይሄ ይሄንን ላይ እዚህ ስሆን በቃ ትክክል ይመስለኛል:: እኔ ነኝ:: ያሳለፍኩት የእውነት የምወዳቸው የነበሩ ልጆች ትዝ ይሉኛል:: ይሄን ሃይቅ ላይ ከአሁን በሁዋላ አብረሽኝ ባትኖሪም አንቺንም አብሬ አያለሁ:: በዚህ በተራራ በተጋረደ ውሃ ሰበብ ብዙ አያለሁ»

ዝምታ:: ለምን ዝምታ? የገርማሜ ስም ሲነሳ ተበሳጨሁ:: በስሙ መጠራት ተደናግሬና ተበሳጭቼ እጄ እንዳመጣው አገልግሉን በግራ እጄ ከፈትኩት:: በእንጀራ ተጠቅጥቋል::

«ምሳዬንም አልበላሁም ነበር» አለ

ከእነ ገርማሜና ከገርማሜ መሸሹ ደስ አለኝ:: እንጀራው መሃል ከሳህኑ እፊያ ስር ተልባ የመሰለ ዝልዝል ጥብስ እንደ እባብ ተጠቅሎ ተኝቷል:: ውፍረቱና መልኩ የሚያሳፍር ነገር አለው:: የእንጀራው ንጣት ወተት ይመስላል:: የእሱን ብርጭቆ በረም ሞላና ለእኔ ግን ትንሽ አድርጎ የቀረውን ኮካ አደረገው:: የእኔን እንድጠጣ አንስቶ ሰጠኝ:: ተቀበልኩ::

«አሁን ካልራበሽ እኔ እበላለሁ» አለና ባልታጠበ እጁ ስጋ በጥሶ ወደ አፉ ወሰደ:: ሁለት አስፈሪ የፊት ጥርሶቹ ስጋው ላይ እንደ መሮ ተተከሉ:: ረም ኮካዬን መጠጣት ጀመርኩ::

«ሬም እወዳለሁ። ለምን የሀበሻ አረቄ አትጠጣም?»

«እንደምትወጂ አላውቅም(እየበላ) ትወጂ ነበር? የምወደው ከስኳር ስለተሰራ ነው»

«እዚህ ትመጣለህ ብዙ ጊዜ? ማለቴ አሁን»

«አንዳንድ እሁድ ከነጋዴ ጉዋደኞቼ ጋር እመጣለሁ። እዚህ ጋ መኪናችንን አቁመን እናወራለን»

ስጋ ባልነካ እጁ ዳበሰኝ እጄን። አየሁት። እጁን መለሰ።

*ምን አስፈራህ?*

አቶ ፍፁም ቢሆኑ ኖሮ ባና ሬሚን እንደ ቀመስኩ(እሱንም መቅዳታቸውንም እንጃ) ወደ ሆነ ጥሻ ነድተው ተምትመው ይመልሱኝ ነበር። ያንንም አልከራከርም ነበር። ምናልባት፡

«ሳሩ ርጥብ ነው፣

ቅጠሉ ይጮኻል፣

ያቺ ወፍ ታየኛለች፣

ተዘቅዝቄ አለሁ፣

እግሬን ገነጠሉት፣

ጡቴን አይጫኑኝ፣

ቀስ በሉ አሳመሙኝ፣

ሰፍት ረስቼአለሁ»

ምናምን የመሳሰለ ነገር እል ይሆናል። እዝራን ከቅንጥ የሚገድበው ምን ነበር? አንዳንዴም 'ልጃገረዶችን አባለጉዋቸው' ሲባል በልቤ እጠይቃለሁ። መጀመሪያ ተደፍሬአለሁ። ከዛ በኋላ ግን ፈቃደኛ ተሳታፊ ነኝ። ግን ይሄ መልሴ ውስብስብ እንደሆነ አውቃለሁ። የሚያበሽቀኝ 'አባለጓት' እያለ ከርሞ የአፉን ቀለም ለውጦ ሲያሰኘው ደሞ 'ባለገች' የሚለኝ ሰው ነው። እለ አይደለ በራሴ እንዳልተማመን ዝቅተኝነት እንዲገባኝ ብዙ ሲዘባዝብ ከርሟል። በደሃ አገር ውስጥ ደሃ መሆን ምን የሚያሳፈር ነገር አለው? ማነው በዚህ ብዙዎቻችን የምንጋራውን ሁኔታ ማፈሪያ አድርጎ በልቦናዬ የመከተት ስልጣንና ዕውቀት የሰጠው። ከዚያ መሄጃ ይጠፋኛል። በአጭሩ እንድንደፈር ያዘጋጁኝና፣ ካደረግሁት በሁዋላ በነገሩ ፊዕመው እንዳሌሉበት ሁሉ ስህተቱን እኔ ላይ ይዘፈዝፋሉ። ካሰኛቸውም እንደ ፍፁም ዓይነቱ ከሚስታቸው የበለጠ እየተኙኝ 'ደርግ እኮ የወጣቱን ሞራል ሰበረው' ይላሉ። አይገርምም? 'ሁሉ ነገር በምርምር ይፈረዳል'። ብዙ ሰዎች ግን መመራመር ይጠላሉ። 'እርጣቄ' አያደርጉም።

እዝራ ሲያጫውተኝ የሌላ አለም ልምድ ውስጥ ያለሁ መሰለኝ:: እንግዳነቱ ሳበኝ:: ሌላ ማክዳ የሆንኩ መሰለኝ:: ሌላ ሴት:: አለ አይደለ ለምንድነው---የየሁት ነው---'ሽርሙጣ ነሽ' ብለው ከማያከብሩኝ፣ የሚያከብሩኝን ሽሺ ሽሺ የሚለኝ? በማክበር ሲለማመጡን እንን-ቃቸዋለን:: ሲንቁን ሲያጣጥሉን እንለማመጣቸዋለን:: ምናልባት ክብር አንወድም:: ምናልባት ወራዳነት በደማችን አለ:: ድሃ ስንሆን ደሞ ድህም ይረግጠናል:: አስገራሚው ይሄ ነው:: ሴት ከመደብ ትግል ውጭ ነች? ለደሃ እናስባለን የሚሉትም 'ቁሌታም' 'ሰጤ' ምናምን ብለው ይተኙናል:: በሁሉ አቅጣጫ ያጣፉናል::

ከሁለት ሰአት በላይ ቆይተን ሰፈር ስንደርስ መምሸት ጀምሯል:: ከቤቴ ትንሽ ሸሸት አድርጎ ጨለም ያለ ቦታ መኪናውን አቆመ:: ሌላ ነገር አልጠየቀኝም:: ጠበቅሁ:: ቤቱ እዛ ሁለት ደቂቃ ቢነዳ እንደርሳለን:: በጨለማ ከመኪናው ወርደን ማንም ሳያየን መግባት እንችላለን:: በምትኩ ምን አደረገ?

«ስሚ ማክዳ»

«ምን?»

በቀኝ እጁ ከደረት ኪሱ ገብቶ ቦርሳ አወጣ:: ባልጠበቅሁት ፍጥነት ሻሻሻ አድርጎ ብሮች ቆጥሮ እጁን ወደ እኔ ዘረጋ::

«ምነው?»

«ለትራንስፖርት ምናምን ይሆንሻል»

«አለኝ» አልኩ ኮስተር ብዬ::

የለኝም:: ግን ከእኔነቴ የበለጠ ደሃነቴ የታየው መሰለኝ:: እዚህ አጠገቡ ቆልቶኝ ተቀምጬአለሁ እሱ ስለ ትራንስፖርት ችግር ያስባል:: ያጣጣለኝ መሰለኝ:: ከዚህ ቀጥሎ የሚኖረው ሩካቤ ስጋ እንጂ ሩካቤ ካሽ አይደለም:: ገንዘቡን አጣጥፎ ጭኖቼ ላይ ጣለው:: ገንዘቡ እየተተረተረ ሳይበታተን በፊት ያዝኩት::

«ደህና እደሪ» አለና ሊጨብጠኝ እጁን ዘረጋ-

«ደህና እደር» ይሄ ቃል የወጣው 'ምናባትክን' ከሚለው ቀድሞ ነው:: ግን የእሱ ቸርነትና ወሲብ መንፈግ ሁለት ስለት ያለው ቢላ ነው:: 'ቺስታ ነሽ ደሞ እዛና እዚህ የምትዪ አይነት ነሽና ለዛ ነገር አልፈልግሽም' ምናምን:: 'ምናባትክን' ከአፌ አልወጣችም፣ አፌ ውስጥ ከምራቂ ጋር ትገላበጣለች::

ለእሱ ባልናገረውም (ምኑን ተናገርኩት) ለራሴም ሆን ብዬ ገላልጬ ባላስሰውም ታሪኬ ያስፈራኛል:: ያስፈራራኛል:: 'እሙኝ' ምናምን

ይለኛል:: የሰውነት ገንዘቡን መቀበል አልነበረብኝም:: ጭኔ ላይ እንደ ወረወረው መልሼ ወደ እሱ መወርወር ነበረብኝ:: እውነታና ምኞት ግን ሽርክ ሆነው አያውቁም ማለት እኔ ሰፈር:: ገንዘብ ያስፈልገኛል:: ብቻም ሳይሆን፣ የገንዘብ ፍላጎቴ ዳብሯል:: ብሩን በእጄ ጨምድጄ ይገባ ከሚቃጠለው ሆዴ እሳት ሲነድ እሰማለሁ:: ከመኪናው ወረድኩና ገንዘብ ያልያዘ እጄን አንስቼ ለሁለተኛ ጊዜ ሰላም አልኩት::

## ነዲዶ ገራኒ[156]

ልቤ በፍርሃት ቢርድም፣ የ75 አመተምሕረቱን ኢ ኤስ ኤል ሲ ቤት አጥንቼ አልፋለሁ እያልኩ እጎርራለሁ:: እማማ እያዘነችም ቢሆን ልታበረታታኝ ትሞክራለች: *ዋናው ልጄ ጤንነት ነው፣ ትደርሺያለሽ::* የምር ግን እማማ ተስፋ አለመቁረጥን ኪነት ታደርገዋለች:: ከቀበሌ እስክስታ አውራጅ፣ ከባህል እስክስታ አውራጅ ከሌላም አይነት ዘፋኝ የተለየች አይደለችም:: የሚገርመው ግን ምኑን ከምን ማያያዝ እንዳለብኝ አላውቅም:: ትንሽ ቢረዳኝና ደደብነቴን ቢያስታግስልኝ ብዬ መስከረም ላይ ተፈሪ መኮንን የማታ ሺፍት መማር ጀመርኩ::

ያለፈ ታሪኬ አልለቅሽ ብሎኛልና አንድ ቀን ዘውገ የተባለው የፍፁም ዘመድ ቤቴ ድረስ መጣ:: የእሳቸውን የላንድሮቨር መኪና እየነዳ ነበር:: ላንድሮቨሩን ሳይ ሁሉን ነገር ጠላሁ:: ቢያንስ መተንፈስ ጠላሁ:: ከጎኑ ቀለሙ ተፍቆ የተፃፈው፣ ሁልጊዜ አየው የነበረ ኪ ሜ ወይም ኬ ሜ ወይም ኬ ማ ወይም ኩ ም ምናምን የሚለው ፅሁፍ ራስ ምታት ቀሰቀሰብኝ:: መኪናው ውስጥ እሱና ሌላ 'አለምአንተ ሁሴን' የተባለ የአንድ የቡና ነጋዴ ልጅ ነበሩ:: ከአለምአንተ ጋር ወጥቼአለሁ:: 'የቡና ነጋዴ ልጅ ነኝ' ብሎ ትንሽ ሲያነጅብ *እስኪ የአብዮት ጠባቂ ልጅ ጋር ኩሺ ብታደርግ ምን ይመስልሃል?* ልለው ይሆናል፣ በኢኮኖሚም ያጣሁትን የበላይነት በሴትነቴ ለመተካከል:: ምንም አልመሰለውም:: ማኖ ካስነካሁት ይበቃል:: አሁን እሱ ፀረ አብዮተኛ ነኝ ማለት ይችላል? የሴቶች አፍረት ከታሪክ ውጭ ጥት? ፍፁም ከእሱ ጋር እንደወጣሁ ጠርጥረዋል:: ማልዕ አድርገው ያልነገሩኝ ሊጣሉኝ ስላልፈለጉ ነው:: ግን ሊጣሉኝ አይፈልጉም ምክንያቱም አይወዱኝም:: እንትኔ እስካልጠፋ ድረስ ከማንም ሴት እኩል ነኝ:: ዘውገ ያለፍርሃት የቤቴን በር መጥቶ አንኳኳ:: በዕድሌ ከጎሐ በስተቀር ቤት ማንም አልነበረም:: ሚጢን ከግቢ እንዳትወጣ ነገርኳት::

[156] ሆዶ ይቃጠላል(ኦሮምኛ)

«ታዲያስ የጠፋችው ልጅ......ፍፁም በአንቺ ናፍቆት በመሳሰለ ነገር ታሞአል አንቺ እዚህ ተቀርቅረሻል» አለ

«ምን ፈለግህ?!» አልኩት:: ደነገጠ:: ከአፌ ከወጣ በሁዋላ በፍጥነትና በቁጣ እንደተናገርኩ ልብ አልኩ::

«ምን ሆንሽ? ጨዋ አልነበርሽም?» አለ ዘውገ:: 'ምን ሆንኩ' ብዬ ልንገረው? ልመልስለት አልቻልኩም:: እንደዛ አጥብቄ ተናግሬ አላውቅም:: የተናገርኩትን በሃሳቤ ስደግመው፣ የሆነ የሚጣፍጥ ነገር አለው:: ዕውነትን በልቤ ባውቃት ግን፣ ስራ ላይ ካላዋልኩዋት ምን ትጠቅመኛለች? ተማረ'ውና ተበሳጭተው ጥይት ሲታኮሱ፣ ላልተማረረው ወንጀል የሚመስለው ለዚህ ይሆናል:: ልመልስላቸው የማስበው አፌ ላይ የሚያንዣብበው ነገር ሁሉ ጨዋነት የሚጎለው ነው፤ ለምንድነው ተበዳይ ጨዋ የመሆን ግዴታ የሚጣልባት? በዳዮች ለምን ጨዋ አይሆኑም? ቢሆኑ ኖሮ ከመጀመሪያው በዳይ አይሆኑም ነበር:: የልብን ሰርተው መልስ እንዳይሰነዝርባቸው 'ጨዋ ሁኑ' 'ክርስቲያን እንዲህ አያደርግም' ይሉናል:: በስድነት ጎዳና አይተውኛል:: ጨዋ ነኝ? ደጀሰላም አይተውኛል? ስፆም ስፀልይ አይተውኛል? ለእነሱ እንጂ ለክርስቶስ አጎንብሼአለሁ? ክርስቲያን አይደለሁም:: ምን ዓይነት ብልጠት ነው ያልሆንኩትን እንደሆንኩ ሁሉ ማባበያ የሚያደርጉት? እነሱስ አብረውኝ ሐጢያት ተራ እንዳልነበሩ ጨዋነትንና ሃይማኖትን በሸንጦ የሚከቱት? የልብን ሰርተው 'እግዜር ያውቃል' ይሉናል:: እግዜር ያውቃል? ፍርድ እዚህ ይሁን......ፍርድ እዚህ ምድር ላይ......

ብድር በምድር ትሁን......

«ፍፁም ይፈልግሻል» አለ ፈገግ ብሎ:: እንዲህ ሲለኝ አለምአንተ እጁን በመኪና መስኮት አውጥቶ እየተዝናና ነበር::

«ከስንት ጊዜ በሁዋላ መጥተህ ፍፁም ምናምን ትለኛለህ? የቀረ ነገር»

«እንዴ ምነው ያ ሁሉ ነገር ተረሳ?» አለኝ ዘውገ:: አለምአንተ የተናገረውን ይስማው አይስማው አላውቅም:: እየተዝናና ምንም ነገር ወደ ጆሮው እንዳልደረሰ ሁሉ የእኔንና የዘውገን ፊት እያቀያየረ ያያል::

«ታመዋል» አለ ዘውገ

«ዶክተር ናት አሉህ?»

«ምነው ከመቼ ወዲህ አፍ ለቀቀብሽ ጥሩ ልጅ አልነበርሽም?»

'ጥሩ?' ምን ማለት ነው 'ጥሩ?' ስትደረጊ ባትወጂም በዝምታ ትደረጊያለሽ ማለት ነው? 'ጥሩ' ማለት ባሳየሁሽ ትሄጃለሽ ማለት ነው? ሳስፈራሽ ትፈሪያለሽ ማለት ነው? የማውቀው ቃል ለአፍታ እንግዳ ሆነብኝ:

«እኔ ሕክምና አላውቅም» አልኩት

«አይ......ሊያዩሽ ይፈልጋሉ»

«የሚያወርሰኝ ነገር አለ ሲጥ ሲል? ወይስ ቆለጠበት?»

ሁለቱም ተያዩ:: 'ምን ሆነች?' ዓይነት:: በልቤም *ጨዋነቴን ምን ነካት?* እላለሁ:: ባለጌዎች የተማረሩ ናቸው? በአሁኑ አባባሌ ትንሽ ባፍርም እምቢታዬን ከአፌ ስሰማው እርካታ ሰጥቶኛል:: ራሴን ልክ እነሱ እንዳዩኝ ዓይነት እንግዳ አድርጌ አየሁት:: አለምአንተ ማባበል፣ እዛው በዛው ሽወዳ ይችልበታልና:

«ምን ሆንሽ? ሲቀልድ አይደለም:: ታሞአል:: ሊያይሽ ይፈልጋል:: እውነቴን ነው»

መቀለዱ እንዳልሆነ እውቃለሁ:: ወደዛ እንድታጠፍለት መሰለኝ......

ውሸቱን ዓይኖቹ ውስጥ እንዳላይ ሳይሆን አይቀርም ፊቱን ዞር አደረገና:

«ስኳርና ጉበት» አለ አለምአንተ

«ጉበቱ ነው መጥፎ ሁኔታ ውስጥ ያደረሳቸው» አለ ዘውገ

ግን በባህርዬ ተልፈስፍሼ መጠቀሚያ በመሆኔ ለፈጠርኩት አለም ሃላፊ አይደለሁም? ብልጦች እንዲኖሩ ቂሎች መኖር አለባቸው:: ብልጦች ብቻቸውን ብልጥ አይሆኑም:: ውሸታሞች እንዲኖሩ የሚዋሽ'ለት መኖር አለበት:: ብልጦች ከቂሎች ጋር ሆነው ጥፋት ቢያጠፉ ብልጦችን ብቻ ወንጀለኛ ቂሎችን ሰማዕታት የሚያደርጋቸው ምንድነው? ፍፁም ታመው ቢሆንም ወይ በሌላ ሕመም አሳበው ቢፈልጉኝ፣ ነገሩን በትክክል ለመጨረሻ መዝጋት የለብኝም?

«የት ነው ያለው?»

«ኮከብ ሬስቶራንት ይጠብቅሻል»

«ከታመመ እዛ ምን ይሰራል?»

«ትንሽ ተሽሎት 'ከእሷ ጋር እሄድበት የነበረው ቦታ ውሰደኝ' አለኝ ወሰድኩት:: ያሳዝናል ሰውዬው:: ስትዪኝ ታምኚኝያለሽ» አለና ዘውገ ሲጋራ ለማጤስ የሮዝማን ፓኮውን አወጣ:: አለምአንተን አመንኩት:: ምክንያቱም አለምአንተን አቅምሼዋለሁ:: ለምን ይዋሸኛል?

«በዚህ በኩል እንሄዳለን»

«በየት?»

«በዚህ»

«በዚህ በኮረኮንች? ያስኬዳል? ለምን በአስፋልቱ አንሄድም?»

«እኔ ያልኩት በዚህ ነው:: ካልሆነ አልሄድም»

ተያዩ::

«እሺ የሰውዬው ነፍስ ከዳኑ» አለ አለምአንተ እየሳቀ:: በእኔ ይሳቅ በፍፁም እንጃ::

ከመኪናው ሁዋላ ገባሁ:: መኪናው እንደተነሳ ሰምቼው የማላውቀው ዘፋኝ ሙዚቃ ተከፈተ:: ዘውገ በየቀኑ አንዳንድ ሙዚቀኛ ይተዋወቃል:: 'ከእንትና ጋ ተዋወቅሁ' ምናምን ማለት ይወዳል::

«ማነው ይሄ ዘፋኝ?» አልኩ አፌ ዝም ከሚል::

«ይሄን አታውቅም ቴዲ እኮ ነው»

«አላውቅም»

«የወጋየሁ ጉዋደኛ»

«ማነው ወጋየሁ?»

«ረሳሽው እንዴ? አስተዋውቄአችሁ ነበር»

«ስሚ ማክድሽ ዘውገ ዘፋኝ ሚስት ይዞ መጣ» አለ አለምአንተ አቋረጠውና::

«ከየት?»

«ከጅማ»

«እ»

«ሰማሽ? ዛሬ ልብሽ የት ነው?»

«ሃሳብ»

«ልጆቹ በዕድላቸው ያድጋሉ»

የሚያስጠላኝ ተረት:: ስድስት ኪሎን ልናልፍ ስንል ጎማው የፈነዳ መኪና ከፊት ለፊታችን ቀስ እያለ ቆሞ ተደነቀረ::

«ናዓል ኡመክ!!» አለ አለምአንተ

ዘውገ ሳቀ:: ጆለምን ሳውቀው ሽድቡ ያስደስተኝ ነበር:: ከስር የመጣ ቱግ ይመስላል::

«አልጨርስክልኝም»

«ስለ ምኑ?»

«ስለ ዘውገ ሚስት»

«እሱ አይነግርሽም? ምን የመሰለች ጥሩሬ ባርያ ይዞ መጣ:: የመንጌ እህት መስላኝ ነበር:: ድምፅዋ ግን አሪፍ ነው»

ዘውገ ይስቃል:: ስትሰደብ እየሰማ ሚስቱ ያደርጋታል?

«ካሽ እሰራባታለሁ:: ፖስቸሯ ደሞ አሪፍ ነው:: ምንም እንደ ማከዳ ባትሆንም»

«ጥሩ የቅዠት መድሃኒት አምጥተሻል» አለ አለም

«ለምን እንደዛ ትላላችሁ? ካልወደድካት ደሞ በምኔው አገባህ? እንዴት ይዞአት መጣ?» አልኩት

«አታሎ ነዋ»

«ቤተሰብ የላትም? ትልቅ ሴት ናት?»

«አንቺን ብታክል ነው»

«ቤተሰብ አላት ወይ?»

«አዎ:: ዘፋኝ መሆን ትፈልጋለች:: አሪፍ ድምፅ አላት»

አራት ኪሎን መውረድ ስንጀምር:

«ይሄ የምንነጋገረው ሊያሳስረን ይችላል ዝም እንበል» አለ አለም:: ሁለቱም ተያይዘው ሳቁ:: የአገሪቷን ቡና እየነገደ ማን ነው የሚያስረው? ተስማምቶ እያደረ ያማል? ብልጠት ነው ገብጋባነት?

«ይሄ ባርያ ሂልተን አጥር ላይ የተሰቀለውን ስዕሉን አየህ? ቀልቶ ሌላ ሰው መስሎአል»

«መጥቆር መጥፎ ነው?» አልኩ

«ዘውገን ልታስከፊ ነው?» አለ አለም እየተገላመጠ

«ካሹን በሁዋላ ሳመጣ አፍሽን ትዘጊያለሽ» አለ ዘውገ ሁለተኛ ሲጋራ እየለኮሰ::

«በእናታችሁ አታጧሱ» ዘውገ ተገላምጦ አየኝ

«ምን ሆንሽ?......»

ፊቴ ላይ የሰፈረውን ቁጣ አይቶ ዘውገ ሲጋራውን በመስኮት ወረወረ:: አቶ ፍፁም በእርግጥ የታመሙ መሰለኝ:: ያደረገው እኔን ለማባበልና እንዳልሸፍትበት ለማድረግ አልመሰል አለኝ:: ይህቺ ውርደቱን ለማጠፋፋት 'ቀልድ ላውራችሁ' አለ:: ቀልዱን አልፈለኩም:: ሁሉም ከያኒያን ናቸው:: በሆነ ጥበባቸው እኔን ከገላዬ መለያየት ይችላሉ:: ሁለት ማንነት ይሰጡኛል:: ሊበዛም ይችላል:: ሃብታሞች ሁሉ ብሩህ ከሆኑ ብሩህ አይደለሁምና አእምሮዬ አይፈለግም:: በድርቆሽ ማንፍልፍል ያደገ አንጎል ምን ስለት አለው? የሚፈለገውና ለጨዋታ ገበያ የማቀርበው ስጋዬ ነው:: ሳልወልድ ጡቴን እያሹ ያረዝሙታል፣ ሳልወልድ እናቴን አክላለሁ:: ከገላዬ ደሞ የተመረጠው ቀዳዳዬ ነው:: እሱም ዕድሜው ሲጨምር ወይም ምን እንደሚሆን ባላውቅም ከተወሰነ ጊዜ በሁዋላ እንደ

መድሃኒት ኤክስፖየር ያደርጋል:: ጎረቤቶች እንኩዋን ማለት ጀምረዋል: 'በእንዴ አደገች ማኪ':: ቅኔው ይገባኛል:: 'እየተሰጣት ነው' ማለት ነው::

«የእውነት ምን ያደርጋል ኮኮብ ሬስቶራንት?» አልኩ:: ገና እንደገረመኝ ነው::

«ማን? እ? ፍፁም?»

«ፍቅር ፍቅር ፍቅር» በዚያው በቀልድ የአስቴር አወቀን ዘፈን ለመዝፈን ሞከረ አለምአንተ::

«ስማ አንተ ለገርልህ ዕፈህላት ታውቃለህ?» አለ አለም ወደ ዘውገ ዞር ብሎ

«ቆየሁ»

«አሜሪካ እንዴት ያደርጋታል?»

«ተስማምቶአታል፡ ምን ትሆናለች......እኛ እዚህ እንደርቃለን እንጂ» አለ ዘውገ

«ምን ነደለብህ?» አልኩት

«ምን ነደለብህ?»

«አዎ»

«ይህቺ ልጅ ትንሽ አፍ አለቀቀባትም?» አለ ዘውገ

«ይመስላል:: ከፍፁም ሲርቁ እንደዚህ ነው» አለም ዞር ብሎ ጠቀሰኝ:: 'ውሸቴን ነው' ሊለኝ ነው:: ለእኔ ግን ውሸቱም እውነቱም ውሸት ናቸው:: ልብ ሲዘጋ አዳሜ ደጃፍ ላይ ራቁቱን ይሰለፋል:: ልብ ሲዘጋ ተግለጥልጦ ማየት እንዲያመቸው ተበዳይ እንኩዋን ገለልተኛ ይሆናል::

«ዕውነት ምን ያማርራል? ወይስ ሊላውን አባራችሁት እንዲሰፋችሁ ነው?»

«አንድ ሃሳብ ነው ይሄ» አለና አለምአንተ ከት ብሎ ሳቀ

«ለእኛ ሕዝብ ወሬና ጤፍ ከጫንክለት ግድ የለውም» አለ ዘውገ

ልክ ከሆነስ እሱ የሚለው? ራሴን ብቻ ካፀዳሁ አይበቃም? ከተማ ልማትን ትንሽ አልፈን ወደ ቀኝ ስንታጠፍ ሲጋራ ልግዛ ብሎ አለም ከመኪና ወረደ:: እሱ እንደሄደ ሚስጢር እንደሆነ ሁሉ:

«ፍፁም 'ማክዳ! ማክዳ!' ሲሉ ነበር:: ቀልዴን መሰለሽ» አለ ዘውገ

«አዎ ሰማሁ»

ፊቴን እንደተሰላቸሁ ሁሉ ወደ ውጭ አዞርኩ:: አለም ያቀጣጠለውን ሲጋራ እያጤሰ መጣና መኪናውን ተደገፈ:

«እዛ እኔ ፍፁም እያስጠሉኝም እዚህ ላጢስና እንሂዳለን» ብሎ ቆመ:: እዛ ጋ ኮከብ ሆቴል ነው:: ወርጄ መሄድ ፈለግሁ:: ከፊቴ ላይ መግረሬን እየ መሰለኝ አለም ያላለቀውን ሲጋራ ወርውሮ መኪና ውስጥ ገባና ወደ ኮከብ ሆቴል መንገዳችንን ቀጠልን:: የሬስቶራንቱ ሊፍት ቀድሞ ብርቄ እንዳልነበር፣ 'እዛ ሄድኩ' እያልኩ እንዳልጎረርኩ፣ ወደ ላይ እየጎተተኝ ሲወጣ ባር ባር አለኝ:: ሬስቶራንቱ ስንገባ አንድ ጠረጴዛ ዙርያ ሁለት ሰዎች ተቀምጠዋል:: ፍፁም ገና ሲያዩኝ አንገታቸውን እንደ ቡችላ ሰበር አድርገው አጤኑኝ::

«አንቺ! አንቺ! ነይ እስኪ!» አሉኝና ፈገግታ በፈገግታ ሆነው ከተቀመጡበት ተነሱ:: ከሁኔታቸው በፍፁም አልታመሙም:: ተናደድኩ ግን ደሞ አሳዘኑኝ:: ለምን አዝናለሁ? እንዲህ እያሰብኩ ልጨብጣቸው ስጠጋ ሳብ አድርገው ሊስሙኝ ሲሉ ጉንጬን ልሰጣቸው ሞከርኩ:: አፋቸው ጉላሽ ጉላሽ ይሸታል:: ጉላሽ ይወዳሉ:: እዛ ጋ አንዲት መላላ ከወገብ ብቻ የተሰራች የመሰለች የደስ ደስ ያላት ጥቁር ልጅ ተቀምጣለች:: የዘውገ ዘፋኝ እንደሆነች ገባኝ:: ወንበር ስቦ ጎኗ ተቀምጦ አንሾካሾከ:: ከደቂቃ በሁዋላ ጎትቶ እነበርኩበት አመጣትና አስተዋወቀኝ:: ልጅትዋን ሰላምታ አልኳትና ስሜን ነገርኳት:: 'አስቴር' ብላ ስሟን ስትነግረኝ በድምፅዋ ማማር ብቻ ዘፋኝ መሆኗ አልጠፋኝም:: እኩልነት በሌለበት ቦታ ትውውቅ ትስስር ብቻ ነው:: ተዋረዱ ካልፈረሰ:: ዘውገን ወይም አለምን ባላውቅ ኖሮ ፍፁም ማንን አማላጅ ይልኩ ነበር? ፍፁም ትከሻዬን አቅፈው ወደ ትከሻቸው እየሳቡ:

«ምን ትበያለሽ? አሁን ጨረስን» አሉኝ:: የምመጣ አልመሰላቸውም ነበር:: ይህቺ ይህቺን የፋገራ ባህላቸውን ያውቁባታል:: አውቅባቸዋለሁ:: 'ድንገት ካልመጣሽ ብዬ ብቻዬን በላሁ' ብለው ጥርጣሬአቸውን አይናገሩም:: ከውስጡ መራራቃችንን ያመኑ ሊሆንባቸው ነው::

«ቤት በላሁ፣ ኮካ ብቻ» አልኳቸው

«ኮካ በበረዶ!!» አሉ አሳቸው:: ሲያዙ ለቅምጥል የሚያዙ ይመስላሉ:: 'ኮካ በበረዶ' ሲሉ፣ ልዩ የሚጠጣ ነገር ያስመስሉታል:: ወደ ጆሮአቸው ጠጋ አልኩና፣ በእሳቸው ስልት:

«አሞህ ነበር አላሉም አንተ ተንኮለኛ» ('አንቱ ባትይኝ እወዳለሁ፡ ልጅ ነኝ ስለ ሸበትኩ ነው?' ስላሉኝ ነው:: ከእንግዳ ጋር ከሆነማ......)

አንድ እጁን ቦርጩ ላይ አድርጎ እንዳይወድቅበት እንደፈራ ሁሉ ሁሁሂሀ አለና ሳቀ:: ኮካዬን ቶሎ አጋመስኩና ጆሮው ጠጋ ብዬ:

«የት እንሂድ?» አልኳቸው:: ሳያመነቱ መገረምም ሳያሳዩ:

«የው እዛ ቤት» አሉ

«እንሂድ» አልኳቸው

ዘውግ አስቴርን የሆነ ነገር ሹክ ይላታል:: አፏን ይዛ ትንተከተካለች:: ምናልባት በእኔ እያሳቀብኝ ነው:: 'ፍፁም ቦይ ፍሬንዲ ናቸው' ምናምን እያለ:: በዚህ ድርጊት ልጅትዋ የተሳካላት፣ እኔን ሲያጣጥልላት የትም ባትደርስም ከፍ ያለች እንዲመስላት......ዘውግ ብዙ አዳዲስ ሙዚቀኛ ጠልፎ የሚያመጣ ነው:: ነክተውት የሄዱ ሁሉ ያማርሩታል:: አዲስ ይመጣሉ፣ ያዘፍናቸዋል፣ ይነካቸዋል፣ ይዘርፋቸዋል ከዛ ያማርሩታል......ቂሎች ሲጠቁ እንደዚህ ነው: ድምፁ፣ ካሹና እንትኑ የእሷ::

እነ ዘውግን እንደተቀመጡ ተሰናብቼአቸው ወጣን:: ሊፍቱን ስንወርድ ፍፁም ሊያቅፉኝ እጃቸውን ዘረጉ:: እጁን ከአየር ላይ ቀለብኩና እውር እንደሚመራ ያዝኳቸው:: ከሆቴሉ ወርደን ወደ መኪናቸው እየሄድን:

«አቶ ፍፁም ከሆቴሉ እንድንወጣና ብቻችንን እንድንሆን ፈልጌ ነው እንጂ የትም መሄድ አላሰኘኝም:: ሰዎች ባሉበት ማውራት ደስ አይልም ብዬ ነው:: ሳስበው ሁሉ ነገር ልክ አይመስልም»

«ምን? ምኑ?»

«የእኔና የአንተ ነገር»

«ምኑ?»

«ይሄ:: ልጅህ እሆናለሁ:: እኔን ታስተምረኛለህ እንጂ እንዲህ ማድረግ አልነበረብህም»

«የመቼ ሃሳብ ነው? እ? ተዋደን ጨርሰን......ግድ የለም...... የምንሄድበት ሄደን ስናርፍ እናወራለን»

«የትም አንሄድም»

«ታዲያ እንዴት ላግኝሽ?»

«በቃን:: ከታመምክም እግዜር ይማርህ:: አሁን ቤቴ መሄድ አለብኝ» ('አንተ' የምለው ትንሽ ዝቅ ላደርገው እንጂ፣ እንደ ወጣት ጠርቼ ላስደስታቸው አልነበረም)

«ምን?»

«ከፈለግህ ወደ ሬስቶራንቱ ተመለስ፣ እኔ ቤቴ እሄዳለሁ»

«ብልግና ነው:: ምን ለማለት ነው ና እንሂድ ብለሽ......»

«እዚህ መንገድ ላይ አናውራ......ለስምህ አይበጅም:: ትልቅ ሰው ነዎት» 'አንተ' እና 'አንቱ' ን በመዘባረቄ በርትቼአለሁ::

«እና በቃ?»

«አዎ»

«እንከፍ!......የዞረባት!»

«አዎ ልክ ነዎት:: ሌላስ?» ስድባቸው ቢያስደነግጠኝም ምሕፃር መሰለኝ:: እኔን ካስጀመሩኝ ጀምሮ አሁን እዚህ እምቢ እስከላቸው ድረስ ከእሳቸው ጋር ያሳለፍኩት ጊዜ ተሰብስቦና ተጨምቆ አንድ ቃል ቢሆን ይሄ ነው:: የሚሰሩትን ያውቃሉ:: የምሰራውን ነው የማላውቀው:: ከደፋሪዬ ጋር ይሄን ሁሉ መርሳት ጀምሬ ነበር:: ይሄ በትክክል የዞረባት ሴት ልጅ ስራ ነው:: የእንከፍም::

«ባለጌ!»

አተኩሬ አየኋቸው::

«አሁን እዛ ከዛ አስቀያሚ ስጋ ነጋዴ ጋር ጥብስና ጠላ ማሳለፍ ጀመርሽና መኩራትሽ ነው?» አሉ::

«ማን አለ?»

«ያመለጥሽኝ ይመስልሻል? ብዙ ሰው አውቃለሁ:: ከፈለግሁም ለእዝራ ለራሱ ማን እንደሆንሽ እነግረዋለሁ:: አታሳይ:: ቀጣፊ:: ለምነሽ ትሰጭኛለሽ» ጉንጫቸው በንዴት ይንቀጠቀጣል:: ስለፈራሁዋቸው አንድ ሁለት ሜትር ራቅ ብዬ:

«አትችልም»

«እንዲህ ቀልደሽብኝ አትቀሪም:: መውደቂያ ቢስ፣ የሸርሙጣ ልጅ ሁሉ......»

እሳቸው ሲደነፉ፣ እጃቸውን እየጠፉ ወዲያ ወዲህ ሲሉና ምራቃቸውን ሲተፉ ጉዞዬን ቀጠልኩ:: በልቤ *በራሴ ቀዳዳ ይሄ ሁሉ ዕዳ?* እላለሁ:: መንገድ ተሻግሬ ቃክሲ ስጠብቅ መኪናቸው ጎን ቆመው ሲንጎራደዱ አያለሁ:: *የሚገባኝ ነኝ እከካም መባል? አዎ እከካም ነኝ::* ከላይ ሳይሆን ከውስጥ:: ነፍሴ እከካም ናት:: ቆዳዬ ባይሆንም:: ለምን ይጠሉኛል? እንዲህ መባል አለብኝ? ቆሜ ብሰማቸው ኖሮ ከሆዳቸው ገና ያልወጣ ስንት ዓይነት ስድብ ይኖራል? ያኔ በጆርባዬ ሆኜ አይናቸው ተጎልጉሎ ያዩኝ የነበሩ ሰውዬ እንዲህ ሲሰድቡኝ የሰማ *'ይሄን ሁሉ ጠላትነታቸውን ምናቸው ውስጥ ደብቀውት ነበር?'* ቢል አይደንቅም:: እንዴት ያ አይነት መንደባለልና ይሄ አይነት አማርኛ ጎን ለጎን ሳይሰራረዙ ይቀመጣሉ? እንዴት ቻሉበት?

ዕንባዬ ይተናነቀኛል:: ሆዴ በንዴት ይቀጣጠላል:: ግን ማልቀስ አልፈለግሁም:: ምራቄን እውጣለሁ:: ቁና ቁና እተነፍሳለሁ:: ራሴን ለማጣጣል ከእሳቸው ጋር ተዳብዬአለሁ:: በትክክል ልክ በዚህ አይነት ስድብ ራሴን ቀድሜ መልከፍ ነበረብኝ:: በድንገት ብቸኛ ሆንኩ:: ቆሜ መንገድ ዳር ሳስብ ጥቂት ታክሲዎች አመለጡኝ:: ይሄ ሽማግሌ ሳያፍር ቅር ሳይለው ሽርሙጣና ጎረምሳ አስተባብሮ እኔን ከነበርኩበት ጉድጉዋድ ጎልጉሎ አውጥቶ እዚህ ድረስ ካመጣኝ፣ እኔ ለምንድነው እዝራን ከገባበት ጉድጉዋድ ከተደበቀበት ሆቴል ጎትቼ የማላመጣው? ድል የማደርገው ፍፁምን ብቻ ሳይሆን አጨብጫቢያቸውንም ነው:: እየቃዠሁ ሰፈር ደረስኩ፡ ቤቴ ገብቼ ሳርፍ ጭንቀቴ ነው መሰል ወንድ አሰኘኝ:: በቃ ወንድ:: ገላዬ ሳይነካካ ወንድ ፈልጌ አላውቅም:: ሳይዳብሱኝ አልነቃም:: ግን ያን ማታ ወንድ አሰኘኝ:: ሁለት እኔዎች አልጋ ላይ ነበሩ፤ እንቅልፍ ሊጥላቸው:: የተለከፈው አንዱ አልጋ ላይ አንሶላ አቅፎ ሲቀር፣ ሌላው ንፁህ ለመሆን የሚዳክረው ደሞ ወደ ሕልም አለም ተነሳ:: ብዙ ያልተቀያየምኩትን የመጨረሻ ሽንኮራዬን እዝራን በሃሳቤ ጠራሁ፣ እዝራ በሕልሜ ቀጭን አጭር ነበር......

# ባክቴርያና ዕድል

ሙሉ ቀን ቤት ስለምውል፣ እዝራ 'ሲመችሽ ታዚና መጥተሽ ስራ እርጂኝ' ስላለኝ ናይት ስኩል ማታ ማታ፣ ቀን ደሞ ጥናት ከሌለኝ እሱ ጋ እሄዳለሁ። ብዙ ጊዜ ለእኔ የሚሆን ስራ የለውም። ሰራተኞቹ ተፈ ነገር ስለሆኑ ዳተኝነቴ አላረካቸውም። እና ብዙ ጊዜ የምቀመጠው እሱ ቢሮ ነው። አልፎ አልፎ ደንበኛ በዝቶ አሳላፊ ሲያጥር ከቢሮ ወጥቼ አሳላፊ እሆናለሁ። መኪናው ማቆሚያ ሲጨናነቅ ባለቤቶቹን ጠርቼ ማድረግ ያለባቸውን እነግራለሁ፣ ስልክ እመልሳለሁ። ብዙ ጊዜ ግን ደብተሬን ወስጄ አጠናለሁ።

እንደዚህ ሆኖ እዝራ እየደፈረኝ ቢሄድም (እጄን መያዝ፣ ትከሻዬን መነካካት፣ ሹራቤን ማስተካከል፣ ሹሩባዬን ማድነቅ) እንጂ አንድ ቀን ተስቶት እንኳን ሌላ ነገር አልጠየቀኝም። ሲመስለኝ ፍርሃቱን በጨዋታ ይደብቃል። አንዳንዴ መዝናናት ሲያሰኘኝ ድሮ ትምህርት ቤቴ ሄጄ ከካስሽ ጋር እውላለሁ። ወይ ውል ያሉኝ ጋ እደውላለሁ። እዝራ እየወደደኝ እያወቅሁ ግን በእሱ ስሜት ላይ ሌላ ሳወጣ የወንጀለኛነት ስሜት ይቆነጥጠኛል። ገላ ነው የሚቀድመው ልብ? የገላ ከሆነ እዝራ ላይ እያወጣሁ ነው። የልብ ከሆነ ካስሽ ላይ እያወጣሁ ነው። ከወደደኝ ግን ለምን አይገፋፋም? ምን እስፈራለሁ? ችግሩ *መውደድን* አላውቅም። መውደድ የራሷ ውስብስብ ደረጃ እንዳላት አላውቅም። ያወጣሁዋቸው ደስ ይሉኛል እንጂ አልወዳቸውም። ካስሽን የቀረብኩት ለመዋረድ በመድፈሩና እንደብቱ ነው። በጣም እንደፈለገኝ ስለገባኝ ነው።

በዝምታ የሚሆነውን ከማየት፣ ፍላጎታችን ሁሉ የተረጋገጠ መስመር እንዲይዝ ከድሮ ልምዴ ትንሽ ጥበብ መዋስ ነበረብኝ። እና አንድ ቀን እስከ ዘጠኝ ሰአት ድረስ ታዚና ቆይቼ እዛ እዛ ስል ደክሞኝ ቢሮ እንደ ተቀመጥኩ፣ እዝራም እንደ እኔው ደክሞት እነበርኩበት ፊቱን እያሻሸ ገባ። ወንበሩ ላይ ተቀምጦ በጣም እንደደከመው ሲያወራ:

«ማጅራትህን ልሽህ፣ እኔ ብዙ አልደከመኝም» አልኩት። ዓይኖቹ ውስጥ እንደፈራ አየሁ።

በድፍረት ተነሳሁና ከወንበሩ ጀርባ ቆምኩ:: ፀጉሩ ከሁዋላ መሳሳት ጀምሮአል:: አልፎ አልፎ ሽበት አለ:: ጆሮ ቀራፋ ነው:: ግራና ቀኝ ትከሻውን ስይዘው ገላው በፍርሃት ተሰበሰበ::

«እንዴት ነው የማታ ትምህርት?» አለ

«ገና ካሁኑ ከብዶኛል»

«መሠረት ያስፈልጋል:: ለዚህ ነው»

«እንዴት?»

«ዘጠኝ......አስር......አስራ አንድ......በደንብ እየተማርሽ ካልመጣሽ ይከብዳል:: ለማንም ነው»

«ታዲያ ሁሉን ክፍል ልማር?»

«ለመሆኑ ምንድነው የምትማሪው? አልነገርሽኝም»

«ሳይንስ»

«ይስተካከላል፣ ጠንክረሽ መስራት ነው፤ ሸብቻለሁ አይደል?» አለ እየተንቀጠቀጠ:: ጥምዝምዝ ያለው የአካሉ ክብደትና ግዝፈት መዳፌ ላይ ይሰማኛል:: እያሸሁት እየዳበስኩት......

«ሶስት አራት ቢሆኑ ነው ምናልባት ሰላሳ»

ሳቀና፤

«በይ አፅናኚኝ......ሰው በር ከፍቶ ቢመጣስ?» አለ

«ሰው በግምት ብዙ ነገር አስቦ ጨርሶአል» አልኩት ውሸቴን::

«ዋሕድ ያውቃል:: ዋሕድ ካወቀ አባትሽ ያውቃል»

«ያሳሰበውን አታስብ:: የምሰራ ነው የምመስለው:: አልስራ እንዴ?»

አዎ ባይንቁኝም ቢያንስ በአፋቸው እንደሚንቁኝ ይገባኛል:: በአሉባልታቸው ይንቁኛል:: ትንሽ ሳዋራኝ፣ ደስ ሳለኝ፣ ትንሽ ተለማምጠ ለጠየቀኝ፣ ሽልማት ብሆንም፣ እንደ ውለታ አይቆጠርልኝም:: የሂያጂነት ኪሳራ ይሂ ነው:: ሁሉን እናውቃቸውና ግን አያውቁንም:: ከመደበር ጉድጓድ በጭገራችን ትትተን እውጥተናቸው ካልደረሳቸው እኩል ያሙናል:: እዝሬ ግን አዲስ ነው:: 'ሰው እፈራለሁ' ሲለኝ ለእኔ ያሰበ መሰለኝ:: የግብዝነት ትራፊክ እንደ እኔ አይነቱን እንደማያሳልፍ ገብቶት ይሆናል::

«ወሬ አልወድም» አለ:: 'አየር አልወድም' እንደማለት ነው::

ከአንድ ሰዓት በላይ ቢሮው በር ዘግተን የሚያስቅ የማያስቀውን፣ ስለገበያ፣ ስለ ጥብስ፣ ስለጠላ፣ ስለ ገንዘብ፣ ስለ ሰፈር ሰዎች ስናወራ፣ ከመሃል ስልክ ሲመልስና ሰዎች ሲያነጋግር ቆየን:: የትምህርት ጊዜዬ

ስለደረሰ 'አደርስሻለሁ' ብሎኝ መኪናው ውስጥ ሳንነጋገር ገብተን ሳንነጋገር እንጦጦ አጠቃላይ ደረስን:: ለመውረድ ደብተሮቼን ስሰበስብ፣

«ነገ የት ነሽ?» አለ

«እንዴት?»

«ታዚና ትመጪያለሽ ወይስ ቤት ነሽ?»

«ነገ ቤት ነኝ.....»

«ጠዋት ላይ መርካቶ እሄዳለሁ:: አንድ ነገር አመጣልሻለሁ»

«ምን? አይነገረኝም?»

«አይ አይነገርም:: በባስ ትመጪያለሽ ወይስ ልምጣልሽ?»

«አይ ባስ እወስዳለሁ፣ ስራህን ስራ......ከጓደኞቼ ጋር ትንሽ ወሬ አወራለሁ ደሞ:: ካላወራንማ እንሞታለን:: ወይም የመንፈስ አደጋ ይደርስብናል ሂሂ......ምን ማለት ነው የመንፈስ አደጋ? ......እንጃ ሂሂ»

«ሃሃሃሃ በቃ ነገ እንገናኛለን»

«እቤት ነው የምታመጣልኝ?»

«አይ ታዚና መጥተሽ ውሰጂ:: ታውቂያለሽ ቤት አይመችም»

«ይሁን እሺ:: በር ጋ መጥቶ መስጠት ማንን ገደለ?»

«የአባትሽ ግልምጫ መከራ ያሳየኛል:: ፈርቼው ሳይሆን......ለሰላም ሂጂ ግልምጫ ቢሰፈርልኝስ? ሃሃሃሃ»

«በቃ እመጣለሁ ታዚና......ቻው»

በር ከፍቼ ወጣሁ:: ዞር ብዬ አላየሁትም:: በጆሮዬ የመኪናውን ዳና አዳምጣለሁ:: ከማማሰል ዝቅ አድርጌ ቂጤን ሰበቅ አድርጌአለሁ:: የእውነት እንዲፈልገኝ:: ተረከዝ ያለው ጫማ ላይ ብቆም ከአራት ኪሎ ሊያየኝ ይችላል:: ተነስቶ የሄደው መንገድ ካቋረጥኩ በሁዋላ ነበር:: ሳላየው ያየኝ እንደነበር አውቃለሁ:: ግራና ቀኝ ሳልገላመጥ እሱ ሲያቅፈኝ እያሰብኩ ክፍሌ ገባሁ::

በበነጋታው ሳነብ አምሽቼ ከአልጋዬ የተነሳሁት ዘግይቼ ነው:: 'የሀሊና ደወል' የተባለ ልብወለድ አንዷ ጓደኛዬ አውሳኝ እሱ አስደስቶኝ መተኛት አልቻልኩም:: ቤት ማንም አልነበረም:: ፊቴን ታጥቤ ቁርስ ልበላ ስል ምንም የተዘጋጀ ነገር አላገኘሁም:: መስራት ስለደበረኝ ልብሴን ለውጬ ታዚና ሄድኩ:: ምሳ ሰአት መጀመሪያው ነው:: ማድ ቤት በቀጥታ ሄጄ ጌታቸውን ትንሽ እንጀራና ድልህ አድርጎ እንዲሰጠኝ ጠየቅሁትና እዝራን እንደምፈልገው ስናገር፡

«ራሱን አሞት ቤት ሄደ» አለኝ

አንድ ሶስቴ ጎርሼ ሳልጨርሰው ተነሳሁ:: እዝራ ታሞ እኔ ስበላ ሆዳም የሆንኩ መሰለኝ:: እንዲህ አይነት ስሜት የሚሰማኝ ለቸሩ ነበር:: እንጀራውን ቢሮው ትቼ ከሆቴሉ ስወጣ እዝራን በእርግጥ እንደምወደው ገባኝ:: ስሜቱ ደስ አለኝ:: በዐይኔ ቂጥ ጌታቸውን ሲያጤነኝ አየሁት:: በፍጥነት ከሰውና ከመኪና እየተጋፋሁ ያን አውራ መንገድ ሳልፍ ዋሕድ የሸንኮራ ጁስ እንድጠጣ ጠራኝ::

«አልፈልግም!» አልኩት

«ጥጋበኛ!» ሲል እሰማዋለሁ

«ሂድዛ!» አልኩ እንዳይሰማኝ አድርጌ

የእዝራ ቤት በጉርጉሱም ሆቴል አቅጣጫ ከዋናው አስፋልት አስር ደቂቃ ያህል የሚወስድ የእግር መንገድ መጨረሻ ላይ ነው:: አባቱ ለሞቱ ጊዜ የለቅሶ እራት ይገፔ መጥቼ እንደነበረ ትዝ ይለኛል:: ከውጪ በዕድ ዛፎች የተከበበ፣ ተራ ሲሚንቶ የተገረፈ ጭቃ ቤት ነበር:: ውስጡን ብዙ አላስታውስም:: ሳሎኑ አንድ ፍሎረሰንት የተመደበለት ብርሃን ያነሰው፣ የታመገ ጠረን እንደነበረው ብቻ ትዝ ይለኛል:: የአልማዝን ሆቴል ሳላየው እንዳለፍኩት ልብ ያልኩት እዝራ ግቢ በር ፊት ለፊት ስቆም ነው:: መጀመሪያ ቤቱ ስደርስ የማደርገው መስኮትና በር መክፈት ነው እያልኩ ሳስብ፣ የአጥሩ በር ገርበብ ብሎ ደረስኩ:: በስተግራ መኪናው ቆማለች:: አንድ ነገር የሆነ መሰለኝ:: ወንድሜ ወይ ፍቅረኛዬ ብቻ የምወደው ሰው እንደተጎዳ ሁሉ ደነገጥኩ:: ቶሎ ቶሎ እያልኩ ግራና ቀኝ እንኩዋን ሳላይ ሄጄ የቤቱን በር አንኩዋኩዋሁ:: ብዙ ሳይቆይ እዝራ ከፈተ:: ሲያየኝ ደነገጠ:: መደንገጡን ያላየሁ ወይም ያልገባኝ መሰልኩ:: በካናቴራ ነው: እንደዚህ በከፊል ተራቁቶ አይቼው አላውቅም:: የታመመ አይመስልም::

«ጌታቸው አሞሃል ብሎኝ ላይህ ነው የመጣሁት»

«ያጋንናል፣ ትንሽ ራስ ምታት ይዞኝ ነው»

ገና ሲያየኝ መፍራት እንደጀመረ አልጠፋኝም:: ለብሶ ሲያዩት ቀጫጫ ይመስላል እንጂ ደህና ጡንቻ አለው:: በር ላይ አቁሞ ያፋጥብኛል::

«እንዴ?......ግቢ አትልም እንዴ?» አልኩ ሳቅ ብዬ:: ልቤ ድም ድም ትላለች::

«እንዴ ግቢ እንደውም ጥሩ ጊዜ መጣሽ»

ቤቱ ይቀዘቅዛል:: ገና ስገባ ውስጡ የተለወጠ መሆኑ ቢሰማኝም፣ እንዲህ ፀአዳ ይሆናል ብዬ አልጠበቅሁም:: አዲስ ኮርኒስ ገብቶለታል፡ ሁለት የፍሎረሰንት መብራቶችና አንድ የጠረጴዛ መብራት አለ:: ሳሎኑ

ስፊ ነው፣ ግን ቲቪ ወይም ሬድዮ የለውም:: ወይም አይታየኝም:: ውስጡ አልፌው እንደመጣሁት ግቢ ይሸታል:: እርጎ በዳቦ ሊበላ እያዘጋጀ ስለሆነ፣ እንዴት እንደሚሰራ አሳይሻለሁ ብሎኝ እየጎተተ ወደ ማድቤት ይዞኝ ሄደ:: ለራሱ ምግብ የሚሰራ ወንድ ሲያጋጥመኝ መጀመሪያ ጊዜዬ ነው:: የሆነ አይነት ጉድለት ይመስላል:: ትንሽ የወንድነት እጥረት:: አባቱ ከሞቱ ጀምሮ ሰራተኛ እንዳልቀጠረ፣ ሆቴሉ እንደሚበላ፣ ልብሱንም እዛ እንደሚያሳጥብ፣ ሲነግረኝ ትንሽ ተሻለኝ:: 'ዐዞ' ብሎ የጠራውን የእርጎ አይነት ብዙ ባልወደውም ስለራበኝ ብቻ አንድ ሶስት ጉርሻ በዳቦ በላሁና በቃኝ አልኩ:: ትንሽ የወየበ የመሰለ እርጎ የሚያስፈራ ነገር አለው:: የቆሸሸ ጨርቅ ይመስላል:: እሱን 'እርጎ' ማለት ይደብራል::

«በሁዋላ ሄደሽ ታዚና ብዬ» አለ እንደተውኩት ሲያይ

«ከዛ ነው የመጣሁት»

«ይቅርታ ቃል የገባሁልሽን ዕቃ ትንሽ ራሴን ስላመመኝ መኪና ውስጥ ትቼዋለሁ:: ላምጣልሽ:: እንጀራ ሆኖብኝ እንጂ የመርካቶ ጫጫታ ሁሌ እንዳሳመመኝ ነው» አለና ከተቀመጠበት ተነሳ::

«እኔ አመጣዋለሁ ንገረኝ የት ጋ እንዳለ:: ደሞ ለእቃው አልመጣሁም»

«እንዴ ግድየለም፣ አንቺ አሁን እንግዳ ነሽ» አለና በችኮላ ከቤት ወጣ::

ሲመለስ ፌስታል አንጠልጥሎ ነበር:: እውስጡ ዕቃ አለ:: ከውጭ እዛ ውስጥ ምን እንደያዘ አይለይም:: ፌስታሉን ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠና:

«ይጠቅምሻል ብዬ ነው» አለ ፈገግ ብሎ

«ምንድነው?»

ከፌስታሉ ውስጥ አንድ ወፍራም ላስቲክ ወገባቸው ላይ እንደመቀነት ያቀፋቸው የተጠረዙ ሺቶችና አንድ ትልቅ መጽሐፍ አወጣ::

«እዩው» አለ:: ስድስት ከዘጠነኛ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች የተዘጋጁ የሳይንስ፣ የኬሚስትሪና የፊዚክስ ኖት ጥራዞችና ፍቅር እስከ መቃብር" የተባለ መጽሐፍ" ነው::

«የሂሳቡን ላገኝ አልቻልኩም:: ሌላ ቀን ሲገኝ እንገዛለን......ፍቅር እስከ መቃብርን አላነበብሽም?» አለ

«በሬድዮ ትንሽ ሲተረክ ሰምቼአለሁ:: ሰብለ ምናምን በዛብህ ምናምን የሚባሉ አሉበት አይደለ? አላነበብኩትም»

ፈገግ ብሎ አየኝና:

«ይደርሳል» አለ

«በጣም አመሰግናለሁ፣ እግዜር ይስጥልኝ» አልኩት ኖቶቹን እያገላበጥኩ።

«በዚህ አመት ማትሪክን ማለፍ አለብሽ። ባለሱቁ እነዚህ የታወቁ ተማሪ የሚወዷቸው ናቸው ብሉኝ ነው የገዛሁዋቸው»

«አመሰግናለሁ በጣም»

«ችሬ ግድየለም። እንደ ውለታ አትቁጠሪው። እኔም አንቺም ለሌላ ሰው እናውራው። ቀላል ነገር ነው። በይ አሁን በሁዋላ በደንብ ታይዋለሽ። ሻይ ላፈላ ነበር ምን ይመስልሻል?»

«ምንም አልፈልግም......»

«እርጎው አበሳጨሽ? ተቀመጪ»

ኖቶቹን ይገቼ ሶፋ ላይ ተቀመጥኩ። ጭኔ ላይ አስቀመጥኩአቸው። ይከብዳሉ። በቃል የሰጠሁት ምስጋና የሚበቃው አልመሰለኝም። ኖቶቹን ፊት ለፊቴ ያለው ጠረጴዛ ላይ አስቀመጥኩና ቀና አልኩ። ሲያየኝ አየሁት። ወይም ሲያየኝ ያዝኩት።

«ትምህርት ማንንም አይጎዳም። ሁሉ ነገር ያለ ትምህርት አይሆንም። ይገባሻል አደል። ባለፈው ስጠይቅሽ ብዙ ግድ የሰጠሽ አትመስይም። ግድ እንዲሰጥሽ ያስፈልጋል። ከአባቶቻችንና ከእናቶቻችን በብዙ የተሻልን መሆን አለብን። አሁን ትምህርት ብታቆሚ ማነው የሚጎዳው? አንቺና ቤተሰብሽ። አሳድገው ቁምነገር ሊያደርሱሽ ሲያስቡ አንቺም ከልብሽ ቆራጥ መሆን አለብሽ። አደለም? ብሩህ ልጅ ነሽ፣ ግን የሚረዳሽ ያስፈልጋል። አውቃለሁ፣ ሳይገባሽ ቀርቶ አይደለም። ወጣትነት ከባድ ነው። ወጣት መሆን ስለሚገባኝ ነው። ነበርኩ አንድ ጊዜ ሃሃሃ። የሚከብድሽ ከመሰለሽ አንዳንዴ የሚያስተምርሽ መቅጠር እንችላለን። እዚህ ታች የማውቃቸው ሰዎች አሉ። በሳምንት አንዴ ለአንድ ሰአት ምናምን ይቸገሩልናል። ስርአት ያለው ልጅ አውቃለሁ»

ለመመለስ ጥቂት ጊዜ ወሰደብኝ።

«አይመስልሽም?» አለ መልሴን ሳይጠብቅ

«ትክክል ነህ። ይገርምሃል ስለ ትምህርት ያወራኸኝ አንተ ብቻ ነህ። አንዳንዴ እንደውም ተማሪ መሆኔን እረሳ ነበር። ትምህርት ቤት ሄጄ እመጣለሁ እንጂ በትክክል ምን እያደረኩ እንደሆነ አላውቅም»

«ቀላል ነው። *መማር አለብኝ* በይ»

«መማር አለብኝ ሂሂሂ»

«ትምህርት ቤት ሳይሆን የምትሄጂው ለመማር ከሆነ አያዳግትሽም። ካልሽስ መማር አይደለም የሚያዳግተው የተማሩትን ስራ ላይ ማዋል ነው የሚያዳግተው። ለዛ ደሞ ብሩህነት አለሽ። ስዋሽሽ አይደለም። በእቅድ በጥላን ከስራሽ አያቅትሽም። ሳትሞክሪና ሳትለፊ ግን ቀድሞ ማማት ጥሩ አይደለም»

«ተምረሃል?»

«እስከ አስር ድረስ:: ቤተክህነት ተምሬአለሁ:: መቀደስ እችላለሁ»

«ሂድዛ! የምትቀድስ አትመስልም»

«ለምን አልመስልም? ጠምጥሜ መሄድ አለብኝ?»

«እኔ እንጃ ብቻ አትመስልም»

«ሰው እንደ ነገር፣ እንደ ሃሳብ ነው:: ገለባብጠሽ፣ ገላልጠሽ መመርመር አለብሽ ማን እንደሆነ ከማወቅሽ በፊት፣ ካልሆነ ግን አይቻልም»

«ለምን አቆምክ ታዲያ?»

«አልወድም ትምህርት:: የአባቴ ሆቴል ስላለ በቃ እዛ ንግድ እገባለሁም ብዬ ነው:: ትንሽ እያለሁ ጎበዝ ተማሪ ነበርኩ፣ በሁዋላ ሰነፍኩ»

«አንተ ታዲያ መማር ደብሮህ......»

«ለእኔ ታዚና አለኝ፤ አንቺ ምን መውደቂያ አለሽ?»

«እሱስ አዎ»

«አገሪቷም እንደዛ ናት፣ ያንቺ የተለየ ችግር አይደለም»

«አንተ ምንድነው *አገር አገር* አበዛህ?»

«እላለሁ?»

«መዓት ጊዜ፣ አትመስልም ግን»

«እንዴት?»

«ካድሬ ምናምን ብቻ ነው *አገር አገር* የሚለው:: አብዮት ጠባቂው አባቴ እንኩዋን......»

«አባትሽ ስለአብዮት ሊያወራ ይችላል፤ እኔ ደሞ ስለ አገር ነው:: የኢትዮጵያ ጠላቶች አብዮት አይፈሩም፣ የአገሪቷን ማደግ ነው:: የሚያሻሽላትን ነገር ነው የሚጠሉት»

«ደሞ ኢትዮጵያ ምንዋ ያስፈራል?»

«ዛሬ አታስፈራም፤ ግን ከበረታች ለምን አታስፈራም? አንቺ በዚህ ቁንጅናሽ ላይ ዕውቀት ብትጨምሪ ተአምር ይሆናል:: ግን ጠላቶቿ ብልጦች ስለሆኑ ወደ ፊት የሚመጣ እርፍናዋን ነው ዛሬ የሚያበላሹት:: አገርን ወራሽ በማሳጣት:: እኔ የአባቴ ሃብት ወራሽ ነኝ:: አደለ ደስ ይለኛል:: አገርም እንደዚሁ ወራሽ ያስፈልጋታል:: ወራሹ የሚዘጋጀው ትምህርት ቤት ነው:: አንቺ ወራሽ ነሽ:: ራስሽን ስታሻሺዪ አገርሽም፣

እንቺም፣ እኔም ከማፈር እንድናለን::......ስለዚህ......የሚሳቡን ሌላ ጊዜ እንገዛለን እንቺ ብቻ በደንብ አጥኚ:: አትፍሪ የምትፈልጊውን ምንም ነገር ጠይቂኝ»

«እ እሺ.»

«ምነው 'እ' አልሽ»

«ሌላ ነገር እያሰብኩ ነበር»

«አላዋጣሽም:: በነገራችን ላይ ቤቱ አሪፍ ነው አይደል?»

ለእዝራ ቤቱ ድሮ መጥቼ እንደነበረ ግን ብዙ ነገር ትዝ እንደማይለኝ ስነግረው፣ ሊያወራ እንዳሰበ ሁሉ ቅንጅ ተከዘና፣ እየሳቀ 'አሁን በደንብ እዩው፣ እንዳይረሳሽ' አለኝና ነጠላዬን ወርውሬ ቤቱን ለማየት ወደ ጓዳ ሳልፍ፣ በድርቅናዬ እንደተመሰጠ ሁሉ ከተቀመጠበት ፈገግ ብሎ ያየኛል:: እወዳለ ጥምጥም የተሸከሙ የሚመስሉ፣ ስልካካ ፊትና የሾለ ጢም ያላቸው ቄስ ትልቅ ፎቶ አለ:: ደረታቸው መሃል ትልቅ መስቀል ተንጠልጥሏል:: እኔን አተኩረው የሚያዩኝ ይመስለኛል:: እንደዚህ አይነት አዛውንት ያስፈሩኛል:: የሚተቹ፣ ባይናገሩም ማን እንደሆንኩ የሚያወቁ ይመስለኛል::

«አባቴ ነው»

«አውቃቸዋለሁ» አልኩና ቶሎ አለፍኩ::

አንድ ክፍል ልገባ ስል ጨልሞ አጋጠመኝ:: ዐዞ ባልንካ እጄ መብራት ለማብራት ግድግዳ ብዳብስም ማብሪያና ማጥፊያውን ማግኘት አቃተኝ::

«ጨለማ ነው! ማብሪያና ማጥፊያው የት ጋ ነው!?» አልኩ::

ከተቀመጠበት ተመንጥቶ ሲነሳ ሶፋው ሲንጫጫ ይሰማኛል::

«መጣሁ አሳይሻለሁ!»

በቸልታ ግድግዳ መዳበሴን ቀጠልኩ:: ማብሪያና ማጥፊያውን አገኘሁት::

'የት ነሽ?' ብሎ እዝራ ከወደ ሁዋላዬ ሲመጣ ዞር አልኩ:: በምኑው እንደደረሰ እንጃ ፊት ለፊት ተገጣጠምን:: ደነገጥኩ:: ደረቱ ስር ነበርኩ:: ትንፋሹ ግንባሬን ይፈጀኛል (ከምቾ ገሽታው ነው የመጣበት ከድንጋጤው?) ከቦሊ እንደሚነሳ አይሮፕላን ማፋዋጨት ነው የቀረው:: ቁጣም ይመስላል::

«መስኮቱን ለምን አትከፍተውም፣ ያስፈራል» ብዬ የምወድቅ መስሎኝ ደረቱን ስደገፍ በምንተፍረቱ አቀፈኝ:: ከእግሮቹ መሃል የሆነ ነገር በሆዴ አቅጣጫ ሲነሳ እሰማለሁ:: እንደደረስኩ አወቅሁ:: ተንጠራርቼ አይኖቼን እንዲያይ አድርጌ አንገቱን አቀፍኩት:: ጎንበስ ብሎ ፊቱን አንገቴ ጋ አደረገና ለሁለት እስኪታጠፍ አቀፈኝ:: በማተብ የተከበበ አንገቱ ይፋጃል:: እንደ አፍርንጅ ጉም ይሸታል:: ቀና ብዬ ዘርፈፍ ያለ

ለምቦጬን በትህትና ሳምኩት:: እርጋታዬ ትህትና ይመስላል:: ከንፈሩን ከንፈሬ ላይ አስቀመጠና እቶን መተንፈስ ጀመረ::

«እስኪ አንሳኝ፣ ትችለኛለህ?» አልኩት እንደልመና:: ጎንበስ ብሎ ከእንገቴና ከእግሮቼ ይዞ ክንዱ ላይ አስተኛኝ:: ለእሱ ወረቀት ነበርኩ:: ፍቅር እላዬ ላይ የሚፃፍ:: እንደ ደረቅ ቅጠል የቀለልኩ፣ ለመውማገድም እሺ ያልኩ:: ወደ ቤት ጣሪያ እንዲህ ተጠግቼ አላውቅም:: ወደ መኝታ ቤት ሲወስደኝ አይኖቼ ፈጠው......በሀፍረት ሳቅ ተንተከተኩ:: ሳቄ ጫፍ ሰጠው መሰለኝ ክንዱ ላይ እንደተጋደምኩ አናቱን ሆዴ ላይ አድርጎ ባልገባኝ ግን እሱን በሚያስቀው ነገር ሳቀ:: ባይገባኝም አልጠየቅሁትም:: አልጋ ላይ ሲያስቀምጠኝ ሰባዊ ሴት ሳልሆን ተተኩሶ በስርአት የታጠፈ የሃር ሸሚዝ ነበርኩ:: የተረበሸ ቀሚሴን አልሰበሰብኩም:: ቆሞ አየኝ:: ከላይ እስከ ታች ቆሞ አየኝ:: በዐይኑ ማንኪያ፣ ጭልፋ እዛና እዛ አደረገኝ:: ተፈቅሮ እንደመፈለግ እንደ መፈለግ:: ያቺን የቀመሰች የትም አትሄድ:: ሊያለቅስ የደረሰ ይመስላል:: ሁለመናዬ ይፈላል:: እንደ ስዕል ሳልነቃነቅ ጠበቅሁት:: ሁሉ ነገር ከብዶኝ አይኖቼን ጨፈንኩ:: አይኖቼን ከገለጥኩ የልቤ ምት የሚቆም መሰለኝ:: *ይሄን ልጅ ይሄን ሰውዬ አለመድኩትም:: የዕውነት እወደዋለሁ::*

ጎኔ በቀስታ ጋደም አለ:: በቀስታ በቀኝ እጁ ወደ ደረቱ ጎተተና አቀፈኝ:: ምንም የማያውቅ ይመስላል፣ ግን እውቀታም ነበር:: 'ብዙ ሴት አወጣን' የሚሉ አይችሉበትም እንደዛ:: ፍቅር ድንቁርናን ያጠፉል:: ያፈቀሩ እንዴት መሀይም ይሆናሉ? እዛ ደመነፍስ ውስጥ ያልተፈታ ሚስጢር አለ:: ተገልቦ ያልበቃው ቀሚሴን በቀስታ ከፍ ሲያደርግ እንደማልከለክለው ገብቶት ነው:: ራሴን በፈቃዴ በመስጠቴ ውስጥ ባይገባኝም፣ እሱ ያልተቀበለው ሕገወጥ የመሰለው ነገር አለ:: ሁሉ አልቆ እንግዳ የሆነ ጥልቅ እርጋታ ተሰማኝ:: የሆነውን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ አስባለሁ......የአይኖቹን አጨፋፈን......አንዳንዴ ስግብግብ ወንድ ነቱ አቅጣጫው ጠፍቶት ሲባዝን......ጨዋነትንና አመንዝራነትን ሳላም ታታ በትንንሹ ሳስተምረው ሲዳዳኝ......በስሜት የምትርገበገብ ሰልቅቱ ......ክብ ዕንብርቢጣው......

ውስጤን የነካኝ ፀሊእሱ የማልፈሳው ባሲብኩት ቂጥር አንጀቴን የሚበላኝን የሚያባብሼን ነገር አደረገ:: አንገቱን አንገቴ ስር ቀብሮ በለሆሳስ፡

«ራጉኤል ምስክሬ ነው እወድሻለሁ» አለኝ

አድርጌ የማላውቀውን አቃሰትኩ:: አፌን መግጠም አልቻልኩም:: ከሆዴ የሚወጣውን የአየር ጎርፍ ላቆመው አልቻልኩም:: ከአፌ የወጣው ዜማ የራሴ አልመሰለኝም:: እንዲህ በመሰለ የየዋህ አፍ ማንም እንዲህ ብሎኝ አያውቅም:: የምፈቀር አልነበርኩም:: ከአፉ የወጡት ቃሎች እውነተኛነት ተሰምቶኝ ውስጤ እየተንቀጠቀጠ (ዕውነት ውስጣችን

እንዳንዴ ይንቀጠቀጣል) ከተንዠረገገ ከታቡ ጋር የትም እንዳይሄድብኝ አይነት አቀፍኩት......

......ከተኛሁበት መነሳት አልፈለኩም......መነቃነቅ አልፈለኩም...... ብርድልብስ ስር እንደተከናነብኩ መሽቶ እንዲነጋ ፈለኩ:: ነግቶ እንዲ-መሽም:: ከዛ እንዲሁ ለዘላለም:: ሚስቱ ሆኜ የመቅረት አይደለም ......በቃ እንዲሁ......ደከሞት ሲያርፍ ለአጭር ጊዜ እንቅልፍ ሲወስደው ነጭ ካናቴራውን በቀስታ ገልቤ በላቡ የቀዘቀዘ ዝንጉርጉር ቆዳውን (እንደ ኤሊ ድንጋይ ያዘለ የሚያስመስለው) ሳምኩለት......እጄን ጨምድዶ መስመጥ እንደፈራ ሁሉ በምችልበት ጥበብ እንዳድነው መሰለኝ በእንቅልፍ ልቡ ሲያጉተመትም......ከአልጋው ተነስቶ ከመኝታ ቤት ሲወጣ እንዳይቀሰቅሰኝ (እንቅልፍ ባይወስደኝም) የዳናው ቀሰስተኛነት ......ተመልሶ መጥቶ ከጀርባዬ ቆሞ ሲያየኝ......እተጋደምኩበት መጥቶ ፊትለፊቴ ቆሞ ቆሞ ቆሞ ቆሞ ሲያየኝ......ወደ ፊቴ ቀርቦ ሲያየኝ ሲያየኝ ሲያየኝ......እንዳንቀሳፋሁ ሁሉ ስሜን ሲጠራ ሲጠራ በመደሰት ሳዳምጠው ሳዳምጠው......ያለፈው ሳምንት ያወጣሁት ካስሽ፣ በለከፋ የሚያስቸግሩኝ ለአፍታ የተመኘሁዋቸው ኀረምሶች ያልነበሩ ያህል ሲሰረዙ ተሰማኝ::

......ሲመሽ ተያይዘን ወጣን......ሁለመናዬ ቀሎኛል......ከገደል ብዘል አልወድቅም፣ እንደ ላባ ሰማይ ላይ እቀራለሁ:: ወደ ቤቴ ሲሸኘኝ ሰው ያየኛል ብዬ አልፈራሁም:: ጎን ጎኔን ሲሄድ እጁን ያዝኩት:: የዕውነት እጁን መያዝ አይደለም የፈለኩት:: በትክክል የፈለኩት ከንዱን ተደግፌ መንገድ ዳር ቆሞ ማናወዝ ነው......

......ከጀርባዬ ሐሜት መሽመኑን ቀጠለ:: ቆሞ ከተሄደ ሐሜት፣ አየር፣ ሞትና ቆሎ አይጠፉም:: ሐሜቱ እንዲህ ይላል: 'ይህቺ አራዳ ዘየደች'::

ለጥቂት ሳምንታት ከእዝራ ጋር ወጣሁ::

ደስተኛ ነበርኩ ግን:: በአራድነት፣ በዝየዳ አልነበረም: በፍቅር::

ከእሱ ጋር ያሳለፍኩአቸው ሰአታት ለዘላለም የሚደገሙ አይመስሉም:: አልተደገሙምም::


ለምን?......ለምን?

***በባከቴርያ ተለከፍኩ::***

'ከአንድ ወንዝ የተቀዳን ነን' የተባለ ምሳሌ አስደግፌ እንዲህ ልጠይቃችሁ: ***ለምንድነው ያልበደሉንን መበደል የሚቀናን?***

ተርበኞችን በሠኩ። ተቀ።ር ፈር ደምነሉ።

# መዋዕለ አየር ጤና



......አንድ ሌሊት ነው እንዳመመኝ ያወቅሁት:: ከቤቴ ጀርባ ወጥቼ ሽንቴን ስሸና ገና ውጋት የታች ገላዬን ሲዘነትረኝ፣ ሲቆራርጠኝ፣ ሲያስጮኸኝ እናም ሲያስለቅሰኝ ነገሩ ምን እንደሆነ ገባኝ:: ከእዝራ አልተጋባብኝም:: ከሌላ እኔን ከመሰለ የማይረባ ጋር ነበርኩ:: ብነግረው አውቃለሁ 'ከየት ሰበሰብሽው?' እንደሚለኝ:: *ለምንድነው ያልበደሉንን መበደል የሚቀናን?*

አዛኝ ወደ መሰለኝ ካስሽ ጋ ሄድኩ:: አይኖቼ ውስጥ የተፃፈውን የመደናገጤን ግጥም አንብቦ መሰለኝ......'ላብራቶሪ ሄደሽ ምን እንደታመመሽ እወቂ......ከዛ ......'አለኝ:: ደመወዝ እስኪያገኝ ምናልባት ስድስት ቀን ወይም የበለጠ መጠበቅ ነበረብኝ:: አልተከራከርኩትም፣ አልተለማመጥኩትም:: ያለችውን ትንሽ ገንዘብ ቢሰጠኝም አልወሰድኩበትም:: አፍረት ፊቱ ላይ ነበር:: እንዲጨነቅ አልፈለኩም:: በልቤ ቅር አለኝ:: በበነጋታው ከየትም ከየትም (ያው የእዝራ ገንዘብና በእሱ ገንዘብ ካዝናናሁዋቸው ሰዎች) ለቃቅሜ ፒያሳ የሚወራለት ክሊኒክ ወጣሁና ተመርምሬ (ከሌሎች በሽተኞች ጋር ተደርድሬ ያፈርኩትን እፍረት እንኳን ላወራው ቀርቶ ላስበው ይከብደኛል) ጨብጥ እንደታመምኩ ተነገረኝ:: ('ጨብጥ' የሚለው ቃል አያስጠላም?) መድሃኒቴን ተወግቼ ቤቴ ተመልሼ ተኛሁ::

የአለመታደል ወይም የመረገም ስሜት ወሮኛል:: አሁን እዝራን ምን እለዋለሁ? ለመሆኑ እዝራ ፈልጎኝ ይመጣል? እሱ የሚታመመው ከአስራ አምስት ቀን በሁዋላ ቢሆንም አሁን ከግንባሬ እስከ እግር ጥፍሬ በብስጭት አመድ መሰልኩ::

በሕይወቴ ለመጀመሪያ ብተኩስ ጥይቴ ኢላማዋን ስታ ፈነዳች:: አነጣጥሬአለሁ? የእዝራን ልብ ሰበርኩ:: የራሴንም ሰበርኩ:: *አነጣጣሪ ልብ ሰባሪ*:: የጅሎች ስራ ወዳጆቻቸውንም መጉዳት ነው:: ቢያነጣጥሩ አንድ አይናቸውን ጨፈኑ እንጂ የትም አይደርስም:: ሲተኩሱ እግራቸውን ይመታሉ:: ለምን የአራዳ ልጅ ትባልኩ? ለምን 'ያቺ እሳት የላሰች' አሉኝ?

•

•

•

መዳፌ መሃል ሞላላ መድሃኒት አለ:: 500 ግራም ቴትራሳይክሊን:: የሞተ ሚጢጢ እንበሳ አውቶቡስ ይመስላል:: በእጄ ጨብጬ ስይዘው ሊቀልጥ ይዳዳዋል:: ከመዳፌ ሰንበሮች ላይ እንደ ልዩ ቅምቡርስ ከቆዳዬ

ተጣብቆ ይተኛል። ግራና ቀኝ ይገፔ ስከፍተው የሚወጣው መርሳት የሚከብድ ቢጫ ስለት ያለው ትዝታ ነው። ለአስራ አምስት ቀን እሱን ስውጥ ነበር።

•

•

•

**ትውስታን የሚያሟሟ ድንገተኛ ማን አለው?**

**ወሬ አልሰማሽም ወይ?**

**ወሬኛዬ ሆይ!**

•

•

•

......አልጋ ላይ ተጋድሜ በር ሲከፈትና ሰው ሲጠራኝ አስባለሁ። በር በር እያለሁ። ከአሁን አሁን እዝራ መጥቶ የሚሰድበኝ ይመስለኛል። ከመዋረዴ ጋር ያልተቆረጠ ቀጠሮ ይገፔአለሁ። ቢጨንቀኝ ያለሁበትን ነገር የማወራውና የሚመክረኝ ሰው ስላሌለ ብሸሻትም ልሸሻት አልቻልኩምና አልማዝ ሳትጠራኝ ድርቅ ብዬ መሽቶ ዐይን ሲይዝ ጉርጉሱም ሄድኩ......

ነጠላ ለብሼአለሁ። አረማመዴ ኮሳሳ ነው። በዛ ጨለማ ማንም ሊያውቀኝ ባይችልም፣ እየተገላመጥኩ አንገቴን ሰብሬ በመኪና መግቢያ በኩል ገባሁ። ሁልጊዜ ጠባብ ሱሪ አድርጋ ልዘንጥ የምትለው ረድኤት አቆመችኝና፣ ሳቅ ወይም ፈገግታ ቅልቅል፣ መበልጠጥና መንበላጠጥ በመሰለ ስልት እያየችኝ......

«ተቀመጪ የእኔ እመቤት» አለችና እጅዋን ዘረጋች......ጨበጥኳት።

«እዚህ ሁኚ» አለችና እጄን ይዛ ጎትታ ያመለከተችኝ ወንበር ላይ አስቀመጠችኝና ሄደች።

አልማዝ ብዙ ሳትቆይ መጣች።

«ምነው? አኩርፈሽ መጥፋትሽ ነው? እህትሽ አልነገረችሽም? አትዋሺኝ። ፍፁምን ነግሬዋለሁ፣ አትጨክንም ብዬ። ሶስት ቀን ሆነው ከናይሮቢ ሲገባ፣ ገና ሳያርፍ ነው የአንቺን ነገር የጠየቀኝ ሂሂ» አለችኝ ከእግር እስከ ራሴ እያየችኝ። ምክንያቱም አልዘነጥኩም። ምክንያቱም ከሁኔታዬ የሆነ የጎደለ ነገር እንዳለ ሳይገባት አልቀረም። ቲያትረኛ ናትና ስለጥርጣሬዋ ምንም አልተናገረችም።

«በግል የማወራሽ አለ:: ክፍልሽ እንሂድ» አልኳት ድምፄን የለማኝ አድርጌ

ገና እንደገባን ለመቀመጥ ጊዜ ሳትሰጠኝ፡

«ምነው? ምን ሆንሽ?» አለች

ቶሎ መመለስ አልቻልኩም:: በትክክል ገና ልጅ ነኝ:: ከአዋቂዎች ጋር መዋል ማለት አንጉል ጥምዝዝ ያለ ማርጀት ነው::

«አመመኝ» አልኳት

«ምን?» አለች የሚያስብ መስላ፣ አይኖቿ ውስጥ እንደገባት ገብቶኛል:: ይሄ ሁኔታዋ ግን ያሳፈረኝ እኔኑ ነው:: አንገቴን ሰበር አደረኩ:: አንገቴን እንደሰበርኩ በአይኖቼ ግንባር ፈገግ ስትል አየሁዋት:: ቀና አልኩና፡

«የምትረጂኝ ይመስልሻል?» አልኩዋት

«አልነገርሽኝም እኮ......ስራ አለብኝ ልጅቷ ምን ሆነች?» አለች::

እንደገባትና እንደገባኝ ገብቷታል

«ከፍፁም መሰለኝ የአባለዘር በሽታ......»

«ፍፁም?!» አለች አባባሌ እንዳስጠላት ሁሉ ፊቷን ከስክሳ፣ አፏን አስቀያሚ ነገር እንደነካች ሁሉ ወደ ታች ቀልብሳ:: እንዲህ ስታደርግ ከዚህ በፊት አላየሁዋትም:: ዛሬ ብቻ ክፉ ነገር ያጋጠማት ትመስላለች::

«ኬንያ አልነበረም...ነበር እንዴ እሱ? ወይ ድርቅና:: አሰልጥነን ልትሰለጥንብን:: ‘ደህና ሰው ሲበላሽ ቅራሪ የለውም’ አሉ:: የማላውቅ መሰለሽ ከማንም ጋር እዛ እዛ እንደምትይ:: ፍፁም የልጆች አባት ነው:: ንፁህ ነው:: በአስር ጣቴ እፈርማለሁ:: ደሞ ከተለያያችሁ ስንት ጊዜአችሁ፣ የማላውቅ መሰለሽ? አለምአንተ ሁሴን ነግሮኛል» አየሁዋት:: ፈገግ አለች:: ምን ለማለት እንደፈለገች ገብቶኛል፣ ልጁንም አትምሪም እንደማለት ነው:: እንጻፍር ነው:: አላቆመችም::

«ማንሽና ነው የሰው ስም የምታጠፊ:: እሳቸውን? እሕ ፊት ሲያሳዩት የዚህ አገር እከካም ነገር ያበዛል:: ወገኛ ምን ታደርጊ በሕልምሽ የማታገኚውን ቀመስሽ ጠገብሽ:: ስራ አለብኝ ልሂድ:: ደሞ ተመርመሪ ......ቀላል ነው:: ፍፁም ይሄ አይነት ነገር......» ከዛ ቀጠለች ፋታ ሳትሰጠኝ::

«ከታመምሽ አልማዝ ጋ አይደለም የምትመጪው ሃኪም ቤት ነው:: ፒያሳ ሞልቷል:: በአገሩ ያለ በሽታ ነው:: አገሩ እኮ ቂጥኛም ነው:: ቂጥኝ ከያዘሽ......» እወዲያ ተሻግሮ ቡና ቤቱ እንዲሰማ አይነት ጮክ ብላ::

ራሴን ደፍቼ ቶሎ ከክፍሏ ወጣሁ:: ለስማትም ላየትም አልፈለኩም:: ቤቴ ገብቼ ስጋደምና ያሳለፍኩትን ሁሉ በልቦናዬ ሳመላልስ ......በአልማዝ ሂሳብ መረቄ የተበላሽ፣ ስኳሬ ያለቀ ሴት ሆኛለሁ ማለት ነው:: ባይሆን አልማዝ ፈውሳ፣ አጣጥባና አሳምራ ወደ ምናውቀው ባህር ወደ አሳ ነባሪዎቹ ትመልሰኝ ነበር:: ፍፁም 'አንቺ ስኳር' ይሉኝ ነበር:: ደሞ ያ ማነው 'አንቺ መረቅ' ይል ነበር:: ያላሉኝ ነገር አለ ሲያደርጉኝ? አሁን ያለቀ ጫማ፣ ካልሲ፣ ምናምን የተቀደደ ስቶኪንግ ነኝ:: አለቀስኩ ......እንዲህ ሆኖ ከነእርግማኔ ለማን ደረስኩት? ምንም ላልበደለኝ ሰው:: ማንን አሳመምኩ? ምንም ያልበደለኝን ሰው:: ምን ይባላል? ለብሺም የምስደብ፣ አውልቄላቸውም የምሰደብ:: ይሄ የአለመታደል ስልጣን ነው ወይስ የደደብነት ጉድጓድ?

•

•

•

እንደታመምኩ ባወቅሁ በሶስተኛው ቀን ከአዝራ ጋር ወጣን:: ገና ደዌው አልተሰማውም:: 'ምን ሆነሻል?' እንዳይለኝ ብቻ እየሳቅሁ እየተጫወትኩ አብሬው ቆየሁ:: ያቺን ነገር ፈልጎ ጻር ጻር ሲል፣ ብዙ እንዳያስብ ወር አበባዬ ላይ እንደሆንኩ ነገርኩት:: ቅር አለው:: መዓት የሚያስቅ ጨዋታ ቢያመጣም በደንብ አልሳቅሁለትም:: ኮሚክ ነው ግን ያን ቀን ኮሚክ አላደረኩትም:: እንደለመደውና እንደለመድኩት ገንዘብ ሰጠኝ:: ለመድሃኒት ስለሚያስፈልገኝ እንጂ አልወስድም ነበር:: ከእሱ እንደተለያየሁ ቶሎ ፒያሳ ሄድኩና ፋርማሲ ጀርባ ግራና ቀኝ ቂጤ ላይ በድጋሚ መርፌ ተወግቼ ቤቴ ተመለስኩ......

•

•

•

ይረገም ከንፈሬ የማይሆን የሳመው

ይረገም ይህ ክንዴ የማይሆን ያቀፈው

ይረገም ይህ ልቤ ለማይሆን ያሰበው

ይረገም ይህ እግሬ አይሆን ቦታ የሄደው

የነገማን ጉዳይ የነገማን ጉዳይ

ገና መቼ አየነው

(ለምን ዝምብዬ ስትዘፍን ብቻ ልስማህ ሙሉቀን? አንተ በእንጥልህ ስትለው፣ እኔ በወረቀት ስርጌ ልግባብህ)

•

•

•

እስከመጨረሻው ያጋባሁበት በሽታ እስኪያመው እና እስኪዘጋኝ ድረስ አብሬው ላይና ታች እላለሁ:: ከእዝራ ጋር ስፔሻል ክትፎ ልንበላ ተክለሃይማኖት ሄድንና በቃ በሆነ ነገር ተደበርኩ:: ልቤ ይባክናል:: በየሰከንዱ *ምን ሊለኝ ነው?* እያልኩ እሰጋለሁ:: 'በሽታ ያዘኝ፣ አንቺ የተረገምሽ እንዲህ አደረግሽኝ' የሚለኝ እየመሰለኝ:: ግን ያን ዕለት ስናወራ የሆኑ ሰዎች አንድ ጊዜ መጥተው ንግዱን ሊያዘጉበት እንደነበረ ሲነግረኝ ከእኔ ሕይወት ጋር የተገናኘ መስሎኝ ደነገጥኩ::

«ምነው ደነገጥሽ?» አለ

«አይ በቃ ሰዎች እኮ ሰው ሲለፋ ሲያዩ አይወዱም:: ምቀኛ ሁሉ» አልኩት

«ከሕግ ውጭ ነው»

«ምን አይነት ሰዎች ናቸው?» አልኩት

«ከማዘጋጃ ቤት ነዋ»

አሰብኩ:: የእውነት ደሚ ፈላ:: ፍፁምና ጓደኞቻቸው ያደረጉት መሰለኝ:: እሱ ወሬውን ትቶ እንድበላ ይነዘንዘኛል: 'በይ እንጂ በላ በላ አድርጊ እንዴ?' የመሳሰለ::

ፍፁምና ጓደኞቻቸው ቢሆኑስ? ፍፁም የዛቱብኝን ልነግረው ፈለኩ:: ግን ከማን እንደተጣላ ማንን እንዳስቀና አውቃለሁ? ፍፁም ዛቱ ማለት አደረጉት ማለት ነው? ዝተውስ ሳያደርጉት ቢቀሩስ? ማስረጃ እንኳዋን ቢኖረኝ፣ ለእዝራ ብነግረው አያምርብኝም:: 'የት ታውቂያቸዋለሽ?' ቢለኝስ? 'ልጃቸው ወዳጄ ነበር? የሆነ ሰውዬ ሲያስቸግረኝ አይተው ገላገሉኝ?' ለውለታ:: የሆነ ቦታ ከጓደኞቼ ጋር ምግብ ስንበላ ገንዘብ ቢያንሰን ከፈሉልን? 'ደሞ ተጠንቅቃችሁ ሆቴል ግቡ ብለው መከሩን?' ውሸቴ ቀዳዳ አለው:: የማይጠ'ፋ:: ልጣፍህ ብለው እንኳዋን የማይጣፍ:: ቢያንስ ለእኔ:: በዋደቁ ላይ ጥያቄ ቢያመጣብኝስ? ልክ በእኔ አቅጣጫ ድፍን ሆኖ የሚታየኝን ጉዳይ እዝራ ወንፊታም ሆኖ ቢያገኘው? አሁን መታመሙን ሲደርስበት፣ በራሴ በገላዬ ያልታመንኩ እንዴት የሌላ ሰው ባህርይ በመገምገም ችሎታዬ ያምነኛል?

ቢሆንም ግን በብልግና ልምድ አለኝ:: ቁጭ ብዬ የዘመኔን ጮሌዎች አይቼአለሁ:: ማን አደባባይ የወርቅ ካባ ለብሶ እንደሚታይ፣ ማታ ላይ ደረቱን በአቡጀዲ እንደሚፍቅ አይቼአለሁ:: ራቁቱንም ሲሆን የሰበሰበውን ጉድፍ አይቼአለሁ:: ይሄ ዱርዬነቴ የሰጠኝ ምሁርነት ነው:: የሚያምር የጣሊያን ጫማ አድርገው ካልሲያቸው የሚሸት አውቃለሁ::

የተለያየ አይነት ምግብ፣ የተለያዩ አይነት ፍራሾችና አንሶላዎች፣ የተለያየ አይነት ፖለቲካ፣ የተለያየ አይነት ቆዳ፣ የተለያየ አይነት ሰው፣ የተለያየ አፍ፣ የተለያየ አይነት ቲያትር፣ የተለያየ አይነት ቀለም ያላቸው ግብዝነቶችን አይቼአለሁ:: በ16 አመቴ ሸበት ያወጣ የዳበረ የወንድ ብልት ማየት ራሱን የቻለ አብዮት ነው:: የዛ ብልት ወዝና ቁጣ፣ ጡንቻና ደም ስር፣ ከዛም የሚወጣው ፈሳሽ እርጅና አልከተበኝም? የሆነ ብስለት አይሰጠኝም? ዕድሜዬ የግልገል ቢሆን ውስጤ ማቱሳላ አይደለ?

ሊያደናቅፉት ስለተነሱት ሰዎች አቃሉ በመናገሩ፣ ቀላልነቱን ተገን አድርጌ ከማውራት ሸሽሁ:: 'ብዪ' 'ብዪ' 'ብዪ' የሚል ንዝንዛውን ላለመስማት መብላት ባያሰኘኝም አፌን ለመያዝ ያህል ሆዴ ላይ አተኮርኩ:: ቢሆንም ገና በትክክል በማስመሰል አልሰለጠንኩምና:

«ምን ሆንሽ ዛሬ?» አለኝ

«ፀሐዩ......ማለት ሙቀቱ»

ያን ቀን ፀሐይ አልነበረም፣ ሞቃት ይሁን አይሁን እዝራ የቀኑን አየር ፀባይ ልብ አላለም:: ስህተቴን ያወቀብኝ መስሎኝ ቀና ብዬ አየሁትና አፍሮ ሊሆን ትንሽ የቀረው የአናቱ ፀጉር መሳጨቱን ገና አሁን ልብ እንዳልኩ ሁሉ ስለ ፀጉሩ ወሬ ጀመርኩ:: ልቡ እኔን ከመፈተሽ እንዲሸሽ (ለፍተሻ ባይነሳሳም) አናቱን በቀስታ እየዳበስኩ:

«ተላጨህ? ምንድነው ይሄ......ሂሂሂ......ተወው ይደግ......»

•

•

•

**ቀሚሴን ከኋላ ይዞ ሲጎትተኝ**

**ወዳንተ መምጣቴ መጮኹ ቢያቅተኝ**

**ባቴን ተረከዜን ስሄድ ተመልከተኝ**

*(አንዱ አስተማሪ ያበደረኝ ግጥም:: የገጣሚው ስም ጠፍቶኛል)*

ግን ጎታቼ ራሴው ነኝ:: ራሴን በራሴ አፌን በምላሴ ካላበጣበጥኩት ማን ያበጣብጥልኛል......እ?......ጅሉ እኔ ነኝ:: ፈንጂው የእኔ ነው:: አፍረቴ ውስጥ አመቻችቼ ያስገባሁት እኔ ነኝ:: ቦንቡ ከፈነዳ ቆየ:: የተበታተነው ገላዬ በቀስታ አየር ውስጥ እንደ እፉዬ ይቦናል:: ገና መሬት አልነካም::

•

•

•

እዝራን ካየሁት ብዙ ጊዜ አለፈኝ:: ሳንነጋገር፣ ሳንተያይ ሁለታችንም ተግባብተናል:: እንዲህ ሲሆን ግራ በሆነ መልክ ወደድኩት:: ሲጀመር እንዳልናቅሁት አሳቀለኝ:: የማስበው እሱን፣ ትምህርቴንና ልክ እንደፍጡር ቁጭቴን ነው:: ቁጭት እንደ ፍጡር እንዳረገዝኩት ሁሉ ሆዴ ውስጥ ያድጋል:: ሲያብጥ ይታወቀኛል:: ከዕንብርቴ ዝቅ ብሎ ከጭገሬ ማለቂያ ከፍ ብሎ:: የሆነ አባጣ አለ:: አንዳንዴ ያሳክከኛል:: አንዳንዴ ይመዘምዘኛል:: አንዳንዴ ሆዴን ይነፋኛል:: ሽንት ቤት ሆኜ ሳምጥ በጥፍሩ ተተክሎ አይወጣም:: ሳምጥ አመሻለሁ:: የሚወጣኝ አውሎ ነፋስ ብቻ ነው::

«አንቺ እዛ ጨለማ ሽንት ቤት ተጎልተሽ......ሆድሽ *ታመመ? ሃኪም* ማየት ያባት ነው» ትላለች *እማማ*

አዎ እማምላክን ቁጭቴን አርግዤአለሁ እሱንም አስባለሁ:: አንጀቴ ሲቃጠል፣ ደም ስሬ ሲወጣጠር፣ ሁለመናዬን ሲያልበኝ፣ መዳፌንም ሲያልበኝ:: *መቆጨት* እንዲህ ነው:: ምን አደረጉኝ ሁሉ? እማማ 'ምነው ቤት አበዛሽ? ወጣ ብለሽ ተጫወቺ እንጂ:: ነፋስ መቀበል ጥሩ ነው' ትላለች:: *እማማ ዝምበይ*

ይሄ አባባሏ እንደማይሰራ አታውቅም:: ምን እንዳሳለፍኩ አታውቅም:: ምስክሬ እኔው ብቻ ነኝ:: ራሴ ላይ እንደፈረድኩ አይገባትም:: *አይቻልም መኖር ለማንም ሳይሆኑ......?*

•

•

•

*መቼ* ደስተኛ ነበርኩ? ጊዜዎቼን ተራ በተራ እየደረደርኩ እህ እህ እህ እህ እያልኩ እቆጥራለሁ:: ከገላዬ የወሲብ ከረሜላው ወይ ውጋቱ (አሁን አሁን የትኛው እንደሆነ እንጃ) ከጠፉ በሁዋላ አፌ ሲደርቅ፣ ጡንቻዬ ሲዝናና፣ በቀኝ ጎኔ የተጋደመው ሰው ትንፋሽ ሲረጋጋ-- ትንግርት የመሰለው ነገር ሁሉ ይተናል:: የስጋ እሳት ጠስ ሲል እውነት በግራ ጎኔ መጥታ ትጋደማለች:: ያልሄድኩበት ሌላው መንገድ ከፊት ለፊቴ ተከፍቶ አያለሁ:: ከግራውም......ከቀኙም......ከፊቱም......ለመሸሽ ወደ ሁዋላ እምቢቻለሁ:: 'የት ትሄጂያለሽ?' 'አይኖችሽ የኒያላ ይመስላሉ'፣ 'ፀጉርሽን ተሰርተሽው ነው?' 'ለቆዳሽ ምን ክሬም ትጠቀሚያለሽ?' 'ጥርስሽን በምን ተፋቅሺው?' ቢሉኝ እንጃ:: የሽሽቴ መስመር የተቆራረጠና የተዛነቀ ነው:: ዛሬ ትናንት......ከትናንት ወዲያ......ዛሬ ......ያለፈው አመት......የሆነ ሰው ፊት......የሆነ መንገድ......የሆነ አስተ- ናጋጅ......አባቴ......ትናንት.....ያለፈው ወር......ሰኔ......ፍለሰታ......እንቁ- ጣጣሽ.....ራቴን ሰበላ.....ከዛ ዛሬ......ከዛ በልጅነቴ......ከዛ በልጅነቴ

......አውጥ ሳፈርጥ......ቃሞ ስቅም......ትል የወጋው ኮክ ሳገላብጥ......ከዛ ሽንኩራ ስልጥ......ልጣጩ ቆርጦኝ አመልካች ጣቴን ስጠባ:: ደሞ የሆነ ጊዜ ብዬ ብዬ የምደርሰው እዝራ ጋ ነው:: እሱ ጎባጣው ባለልማሙ:: ስወደው::

•

•

•

ብለፋ ብለፋ እዝራን በሕልሜ ማየት አልቻልኩም:: አስራ አምስት ጊዜ ቆጥሬአለሁ:: አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ጉዳይ አለ አይደለ በእግዜርና በሰይጣን ትብብር የሚሰራ የሚመስል:: 'እኔ ላደናቅፋት እንዲህ ሳደርግ፣ አንተ አይኗን ያዝልኝ' የመሳሰለ ሴራ ያለበት::

**አይሆንም ብለሽ ነው?**

•

•

•

የስፌሬ ደመና የሚነቃነቅ ጠባሳ ነው:: ከቤት ጀርባ ተቀምጩ ሳር እየበጠስኩ እጫወታለሁ:: እበጥሳለሁ እጥላለሁ:: ይሄ ቀላል ይመስላል እንጂ ውስብስብ ነው:: ተበጥሶ የወደቀውን አያለሁ እንጂ እንዴት እንደተበጠሰ አላይም:: የማየው እዝራን ነው:: ለጋስ እጁን:: የተደበቀ የተሸሙዋጠጠ ግን የጣመኝ ገላውን:: ያላቀድኩትን ማድረጌን (ደሞ ማቀድ እንደማቅበት):: ገላዬ አሁን ንፁህ ነው:: በየሳምንቱ ፍልውሃ እሄዳለሁ:: አእምሮዬ ግን ጉድፍ ውስጥ ይዋኛል::

•

•

•

አንድ ማታ ላይ አልማዝ ጋር መንገድ ላይ ተገጣጠምን:: ገላምጫት አለፍኩ:: እየሰማሁዋት:

«እከካም» አለች፡

*ምን ልበላት?*

ልሰድባት ያሰብኩት ስድብ ራሴ የምሰደብበት ሆነብኝ:: ችሎታዋን ልደርስበት አልቻልኩም:: ድክመቷ ምን እንደሆነ እንኩዋን አላውቅም:: ለእኔ የማይበጅኝን ነገር አስርታኝ እንደ እቃ ተጠቅማብኝ ቄንጠኛ አጣጣል ጥላኛለች:: ትታኝ ስትሄድ ከአረማመዷ መግቢያ እንዳሌለኝ እንደገባት ያስታውቃል:: ይሄን ሁሉ እንዴት ቻለችበት? ጥርሴን ነክሼ

አፌ ተሳስሮ እያየሁዋት ቆምኩ:: ዞር ብላ እንኳዋን አላየችኝም:: ብተውሽም አልተውሽም ያለች ይመስላል:: በእግሮቼ መሃል ድንባዜ እንደ ነፋስ አለፈ::

•

•

•

ቅዳሜም እሁድም ከቤት አልወጣም:: 'ስዕል ለጀማሪዎች' የሚል መፅሃፍ ይገፔአለሁ:: 'ተክለብርሃን' የተባለ ፊቱ በፂም የተሸፈነ ሰውዬ የሣለው ነው:: የመፅሐፉ ልባስ ላይ የብሩሽ ስዕልና ተስሎ ያላለቀ የሴት ፊት አለ:: እኔ ብሩሽ የለኝም:: ባለመስመር ወረቀት ላይ የመጣልኝን በእርሳስ እስላለሁ:: መስመር ያለው ባይሆን የበለጠ ደስ ይለኝ ነበር:: የምስለው የልብ ስዕል ነው:: ቀላል ነው:: ከባድም ነው:: ልብ አይቼ አላውቅም:: እንኳዋን የሰው የእንስሳ አላየሁም:: እና የምስለው የምንድነው? ለምን በማየው አላምንም? ከምስለው ልብ በአይኖቼ የማየው የእናቴ ስፌት አይበልጥም?

«አንቺ ልጅ እቤት ታስረሽ ልትውይ ነው? ቀድሞ ለምን እግሬን ያዛችሁት፣ አሁን ደሞ ከርቸሌ ትገቢ? የጤና ነው?»

እንዲህ ያለ ፀባይ ዳንግላም አላየች::

•

•

•

አባቴ አዲስ ስራ ምዕራብ አዲስአባ አየር ጤና ተስፋ ድርጅት አካባቢ አገኘ:: የድሮውን ቤታችንን በብዙ ገንዘብ ሸጦ ሌላ ርካሽ ቤት ገዛ:: እማማ ደሞ 'አካባቢው ሳር አለበት አሉ ስፌት እየሰራሁ እሸጣለሁ' ብላ ጉራ ትነፋለች:: እዛ ስንደርስ ሳር አልነበረም:: አጠገባችን ያለው ሸለቆ ደኑ ተቆርጦ ያለቀ ነው:: ሃምራዊ ማር የሚያንጠባጥቡ የሽሮሜዳ አይነት የአጋም ጫካዎች የሉም:: ከገደል ገደል የሚሳቡት ሃረጎች ሳይሆኑ ቁልቁለቶችና ዳገቶች ናቸው:: አሞሮቹ የረዷ ቆሼ ፂላዎች ናቸው:: የመንገዶች ዳር ባቦዶ የተቆራረጠ በአፈር መሸርሸር ያገጠጠ:: ማታ ስወጣ ትላበራ የሌለበት አፈር አፈር የሚሸት አየር:: ጥሻዎች በጉርጥ የተወረሩ:: እዛ ያሉት እኔና ሃሳቤ ነን:: ግን ከሽሮሜዳ መራቄን እንደ ትልቅ ግልግል ቆጠርኩት:: ከታሪኬ በአካል ብርቅም ከላይ እስከ ታች እውስጤ ይገፔው እዞራለሁ፣ ልክ እንደሙጫ በደም ስሬ ግድግዳ ተጣብቆ:: ብበጣ የሚፈስኝ ደምና ጥላዝማ ብቻ አይደለም፣ ታሪክም ነው::: 'ወላ ታሪክ እንዴት ይፈሳል?' አልባል:: ባይፈስም ይሄው ያውም እንደ ፈንጣጣ ሲወጣ:

•

•

•

አንድ ምሽት የድሮ ጎረቤቶቼን ለመጠየቅ ሽሮሜዳ ቆይቼ ወደ አየር ጤና ልመለስ ስል እዝራ አውቶቡስ ስሳፈር እንዳያየኝ በታች በኩል እየሄድኩ ኢያለሁ፣ ተባረኪ የተባለችውን የእትዬ ትደነቂያለሽን ልጅ በደንብ ከማውቀው ፋሲል ከተባለ ሰውዬ ጋር አየሁዋት:: ፋሲል የአለምአንተ ዘመድ ነው:: ፋሲልን የማውቀው አለምአንተ አስተዋውቆኝ ነው:: ምናልባት ከሶስት አመታት በፊት:: በአጠገባቸው ሳልፍ ከፋሲል ጋር ፊት ለፊት ተገጣጠምን:: ተባረኪ አታውቀኝም:: ፋሲል አየኝና ደንግጦ እንዳላየኝ ሁሉ እስር እስሩ ዱብዱብ የምትል አንዷት ትንሽ ቀይ ልጅ ተጣራ: 'መስኪ ነይ እንጂ! አስቸገርሽ አሁንስ!' እየሮጠች መጣችለት:: በዐይኑ ቂጥ ያየኛል:: አነሳና አቀፋት:: ሲያቅፋት ፊቱ ተጋረደ:: አይደብርም? ከተባረኪ ጋር እንዳለ አመንኩ:: መስኪ የተባለችው ልጅ ደሞ ተባረኪ ከዓላዛር የወለደቻት መሆን አለባት:: እኔ ስዳራቸው ስም ያበዙብኛል፣ እንዳንዷ ደቅላም ፕሮፌሰር ታገባለች:: ስነ ምግባር ነው? ስነ ምንድነው?......

አለምአንተ ፋሲልን ሲያስተዋውቀኝ 'ከእስር ቤት ገና ስለወጣ ትስ ያስፈልገዋል ተቸገሪለት' አለኝ:: እምቢ ልለው ፈልጌ ነበር:: አለ አይደለ ብቻ አጠያየቁ ደስ አላለኝም ነበር:: 'የአባትሽ አብዮት ጠባቂነት ተጋጋብሽ መሰለኝ' ምናምን የሚለኝ መሰለኝ:: ችግር ነው:: መታመን እፈልጋለሁ ደሞ:: ደሞ ከኮሌጅ አስተማሪ ጋር መውጣት ኮሌጅ ባይሄዱም ትንሽ ክብር ሳይኖረው አይቀርም:: አለምአንተ ፎግሮኝ እኔም ተፎገርኩለት:: አንጎሌ ማሕፀኔ ውስጥ ነበር:: ምናልባት ለሶስት ወሮች ወይ ሁለት ወሮች ወዳጅ ሆንን (የጊዜውን እርዝመት እርግጠኛ አይደለሁም):: ከፋሲል ጋር ስወጣ አንዳንድ ወዳጆቼን ናቅሁ:: አለ አይደለ 'በአሪፍ ሰው እየተደረኩ ነውና ከእናንተ ምን አዳረቀኝ' አይነት:: ሶስት ወይም ሁለት ወር ሲያልቅ 'ማስተማር ስለምጀምር፣ አለማያ እሄዳለሁ' ብሎኝ ጠፋ:: በስርአት እንኳን አልተሰናበተኝም:: 'ለማስተማር መሄዱ ነው ምን አይነት ስንብት ነው? ከፈነገለኝ በሁዋላ መጎዳቴን በሆዴ ይዤ የረሳሁት መሰልኩ:: አለምአንተ ሊፎግረኝ 'ፋሲል መቼ እለት ደውሎ ሰላም ብሎሻል' ምናምን ይለኛል:: በሆዴ ከቴም እልና ከዛ ግን 'ኸረ እባክህ በእናትህ ሰው አይናፈቅህም ወይ? ሰላም ብለሃለች በልልኝ' እለዋለሁ:: እንዲህ እየዋሸኝም አለምአንተ ዱቅ ያደርገኛል:: ፋሲል ግድ እንደማይሰጠው እየገባኝም ቢሆን፣ እንዲህ ሳደርግ ፋሲልን የተበቀልኩ ይመስለኛል:: አለምአንተ ግን ፋሲልን እየተበቀልኩ ሳይሆን እየተቆላሁ ይመስለዋል:: አንዳንዴም አለምአንተ ፋሲልን የሸወድነው እንዲመስልለት ይፈልጋል:: እኔም እንደዛ

እንዲመስልልኝ፣ አለ አደለ አደጋው ራሴን እንዲያስደስተኝ። ግን እኔም አለምአንተ ፋሲልን እንደሸወድኩት እንዲቆጥርልኝ እፈልጋለሁ። ምንም ሸወዳ ሊሆን እንደማይችል አውቃለሁ። ተንጋልዬም አጎንብሼም የቡና ነጋዴ ዘር እሰበስባለሁ። እያንዳንዱ ድርጊቴ እየቆየ ተናቂ አደረገኝ። መሸነፌን ሌላ ሳልነገር ጉብጠቴን በሚያምር መልኬና በወሲብ ጉቦ እየሸፋፈንኩ እኖራለሁ። ስለመሸነፌ ልነግረው የምችል እዝራ የተባለ ሰው ሲመጣ……ወሬ ቢበዛ በአህያ አይጫንም……

……ፋሲል ልጅቷን እንደተሸከመ ዳገቱን ወጣ። ወደ ቀኝ ወደ ተባረኪ ቤት ለማለፍ መንገዱን ሲሻገር ዞር ብሎ ወደ አውቶቡሱ መቆሚያ አየ። መኖሬን እንዳረጋገጠ ፊቱን ከእኔ ቶሎ መለሰ። ከሰፈር ለመራቅ የሚቀጥለው ፌርማታ ጋ አውቶቡስ ለመያዝ ቶሎቶሎ መራመድ ጀመርኩ። አውቶቡሱ በፍጥነት እንዲመጣልኝ ፀለይኩ። ድንገት እዝራ በዚያ ቢያልፍና አይቶኝም ከሚበሳጭ መሬት ተከፍታ ብትውጠኝ ደስ ይለኛል።

•

•

•

በጀርባዬ ተኝቼ ጎኔን ሳክ አልማዝ ባበጀችልኝ ቀዳዳ መረቄ ወደ ባዕድ መሬት ይፈሳል። የጥንቆላ ውጤቷ ትክክለኛነት የወለፈንድ ቢሆንም ትክክል ነው። ***የምቀኛዬ ብዛቱ፡*** ከራሴ በላይ ምቀኛ አለኝ? ራሴን ብቆጥረው ስንት ሺህ እሆናለሁ?

•

•

•

አልረሳሁትም።

«እና ምን መሰለሽ?» አለኝ፡ አንድ ቀን እዝራ። ያወራኝን ሁሉ እያሰብኩ እያጠናሁት ነው። የሆነ ሰባኪ ይመስላል፣ ግን ሰባኪ ሳይባል።

«የራሳችን መጉጂያ ይዘን እንዞራለን። ሕጻድ ነገር ሲበላሽ ራስሽን ጠይቂ። 'ምን አጥድፎኜ?' ነው ብለሽ። ሁላችንም በውስጣችን መደሻና መስፍ ይዘን እንዞራለን»

«ምንድነው መስፍ?» አልኩት

«ማስደገፊያ። ብረት የምንቀርፅበት ብረት። ወይም የምናፈርስበት። ካልፈረሰ አይቀረፅም። ራስሽ ውስጥ የጥፋትሽ መነሻ ይኖር እንደሆነ ጠይቂ። በትህትና ጠይቅሽ ከጨረስሽ በሁዋላ ልታገኚው ካልቻልሽ የጥፋቱን መነሻ ሌላ ቦታ ፈልጊ»

«እኔ የአንቺ፣ አንቺ የእኔ መስፍ ካልሆንን እንደ ተፈጥረናልና መዶሻ መሆናችን አይቀርም:: መዶሻ ለመዶሻ»

•

•

•

'ያቺ ደባሪ ነገር' ስል አባቴ ሰማኝና ተቆጣኝ:: 'ደባሪ' በአዲስአባ ስድብ አይደለም:: ግን አባቴ በልፋት አጋኖ አጋኖ ስድብ አደረገው

'ምን አደረገችሽ ስርታ ባደረች?'

'ደባሪ ናት!' አልኩት ለእሷ ወገቡን ይዞ መከራከሩ ቢያበሳጨኝ

'እሷን የመሰለ ሰው ጥቂት ነው እዛ ሰፈር ያለው:: እስኪ ጥሪ እንደ እሷ ሁነኛ ሰው:: የታዚናውም አስቀያሚ ስራው ድግምትና ሰይጣን መጥራት ነው:: ደብተራ ደሞ ሆቴል የት ያውቃል:: ጥብሱን ለሙያተኞች ለሚያውቁበት አይተወውም? የእውነት አልማዝ ጥሩ ሴት ናት:: ለስንት ሰው ችግር ደርሳለች:: ዋሕድ እንኳዋን ገብቶታል፣ እያበላው:: አልማዝን በክፉ አታንሺ'

'እንሳለሁ!'

'ከመቼ አንቺ ከአባትሽ እኩል ትናገሪያለሽ?' አለች እማማ::

*ሰፈሩን ትቶላት መጥቶ ምን አሁን አከራከረው?* እማማና አባባ አንድ ከሆኑ በቃ እኔ የት ልድረስ? ራሺያና አሜሪካ ተመሳጠሩ ማለት ነው::

•

•

•

የተለያየ ዓይነት እውቀት አለ:: እና የተምታታብኝ ይሄ ነው:: ቤታችን ፊት ለፊት ጥቁር አፈር፣ ጥቂት ሳር፣ ጥቂት ድንጋዮች ያሉባት ባዶ የመሬት ቁራጭ አለች:: ሰኔ ላይ ስትረጥብ ቆፈርኩዋት:: እየቆፈርኩ የማስበው የምተክለውን በቆሎ፣ ሽሮሜዳና ምሕረትን ነው:: ከአየር ጤና መሄድ ግን እጠላለሁ::

«አንቺ ጤነኛ ነሽ? ጉድ! ገበሬ ሆንሽ» ትላለች እማማ

እማማ ሰፌት ስትይዝ ታምራለች:: እኔ ዶማ ስይዝ አላምርም:: ግን የአፈሩ ሽታና ጭቃው ልጅነቴን ያስታውሰኛል:: መኮትኮትና ማረስ ብቻ ሳይሆን ልብሴን በየሳምንቱ አጥባለሁ:: ብዙ ቢኖሩኝም፣ አበክሬ የምለብሳቸው ቀሚሶች ሁለት ብቻ ናቸው:: አንዷ አረንጉዋዴ ናት:: ልጅ እያለሁ ዋሕድ ነፍስ ይማር ያመጣልኝ አይነት ትመስላለች:: ግን ገበር

የላትም:: ግን ያለመርፌ ቁልፍ ወገቤ ላይ ትገጥማለች:: ግን ቴትሮን ናት:: ግን ረገም ናት:: በግራ ጎንዋ በዚፕና በአንድ ጥቁር ቁልፍ ትዘጋለች:: ደሞ በሰበብ በአስባቡ ገላዬን እታጠባለሁ:: በየቀኑ አፍረቴን እታጠባለሁ:: ጠዋት ከስአት ማታ:: ማሕፀኔ መጨረሻ ድረስ የምሸተው እንደ ላክስ ነው:: ብብቴንና አፍረቴን ምላስ አስኪመስሉ እላጫቸዋለሁ:: ራሴን በመስታወት የማየው ጠዋት ከአልጋዬ ስነሳ ብቻ ነው:: ጌጦቼን በሙሉ ሙዳዬ ውስጥ ከትቼአቸዋለሁ:: ሙዳዩዋን ሳጥን ውስጥ ከተተኳት:: ሳጥኑ አልጋ ስር ነው:: የአልጋው ስር ደሞ አይጥ በአይጥ ነው:: እንደ ጨርቅ ቢያራግፉኝ ከላዬ የከበረ ነገር አይረግፍም:: እማማ:

«እየር ጤና ፀባይዋን ለወጠው» ትላለች

ሰፈር መድረክ መሆኑን ትረሳለች:: የእኔ የመድረክ ተዋናዮች ቁጥራቸው ጥቂት ሆኗል: ተራራ፣ ሜዳ፣ አፈር፣ ድንጋይና እንደ ጅራት የሚከተለኝ ትናንትና:: እማማ ዞር ስትልልኝ እንደ ልጅነቴ ብይ የሚያክል የመረሬ አፈር ጓል በአፌ አስገባሁ:: የብረት ጣዕም አለው:: ያኔውኑ ወደ ታንክ ብለወጥ ደስ ይለኛል::

•

•

•

እናቴ ፀሐይ ውስጥ ኩርሲዋን ታወጣለች፣ ኩርሲዋ ላይ ትራስ ታስቀምጣለች:: ትራሷ ላይ እሷ ቂብ ትላለች:: ጭንዋ ላይ የተጀመረ ስፌት:: እግርዋ ስር የቀለም እስር:: እኔ ራቅ ብዬ ሳር ላይ እግሮቼን ዘርግቼ:: እዛ ዛፍ ስር ቁጭ ስል በእርግጥ ቁጭ ነው:: ቂጤ መሬት ይነካል:: ጭኔ ላይ የማጠናው መፅሃፍ:: በአስቴር አወቀ ጅንኑ ስጀነጀን:: አንጎሌ ውስጥ ጅንኑ:: የሚያምር ሽፋን አለኝ:: የሚያስጮህ ነገር ሲኖር መጮህ ደንብ አይደለም? ምን በዘፈን አስጀነጀነኝ? ግራ ክንዴ ጡንቻው ላይ እንደዚህ የተኸርጎረጎረ ነገር ወጥቶብኛል::



በሽታ መሰለኝ: ከሆነ ሰውዬ የተጋባብኝ:: እማማን ልጠይቃት አሰብኩና

«እማ እማ» አልኩዋትና ቀና ተውኩት:: 'ይሄማ......ይሄማ...... እእም......ይሄማ የአባለዝር በሽታ ምልክት ነው' ብትለኝስ:: የማይፈልጥ የማይቆርጥ ብልጥ በሽታ ዝም ብሎ ምልክት ትቶ ቢሄድስ? ልደብራት ካለ እግዜርን ማን ይችለዋል::

«ምን» አለች

«ዶሮ ማርባት እፈልጋለሁ»

«ምን»

«ዶሮ»

«ኸረ ነገር አመጣች» አተኩራ እንደ አበድኩ ሁሉ አየችኝ፡፡ ወስፌዋን ከቁናዋ ላይ እንደተከለች፡፡

«ምናለበት፡፡ ደህና ዶሮ ጉልት ሄደን እንመርጣለን፡፡ ወደ ሰበታ ሄደን»

እናቴ ናት፡፡ የልቤን ብደብቅ ብልጥ አያደርገኝም፡፡ ቂል አያደርጋትም፡፡ ምክንያቱም የልብን የሚያውቅ አምላክ ብቻ ነው፡፡ እማማ እማማ እንጂ አብ፣ ወልድ ወይም መንፈስ ቅዱስ አይደለችም፡፡ በቃ እማማ ናት፡፡ እኔ ግን ቀጣፊ፣ አታላይ፣ ልቧ የማይገኝ ምናምን ነኝ፡፡ እኔ እከካም ነኝ፡፡ እንደዚህ እጄ ላይ የሚወጣብኝ ነገር ሁሉ ውስጥ በምደብቀው የሚወዱኝን በማታልልበት መርዝ ሰበብ ነው፡፡ የምጋለጠው እንዲህ እየወጣ ነው፡፡

•

•

•

በልጅነቴ 'አንቺ ቆንጆ ልጅ' ሲሉኝ አባባላቸው ያኮራኝ ነበር፡፡ 'የፀጉሯ ብዛት፣ የአይኖቿ ነገር፣ እይልኝ አካሄዷን' ቅብርጥሴ ምናምን፡፡ ታዲያ 'ማክዳ' ሲሉ 'ቁንጅና' ብቻ ይመስለኛል፡፡ ቃሉ ሲዘረዘርና ወደ ድርጊት ሲተረጎም ምን ማለት እንደሆነ አላውቅም ነበር፡፡ ምኑንም ባላውቅም፣ አባባሉ መድረሻዬ እሱ ብቻ እንደሆነ ሁሉ እኮራለሁ፡፡ ምኑም ባይገባኝም እንዲህ የሚሉኝን ሰዎች ብዙ ሳልመራመር እወዳለሁ፡፡ ከፍ ሲልም ብሩህ መሆኔ አይደለም የተነገረኝ፣ ቆንጆ መሆኔ ነው፡፡ በመሀይም አባቴ፣ በመሀይም ጎረቤቶቼና የሰለጠነ በሚመስለው ምናምንቴ መሃል ልዩነት አልነበረም፡፡ ለአቅመ ሔዋን ስደርስ በረታ፡፡ ቃሉ መቅድም አይመስለኝም ነበር፡፡ ልክ መጽሐፍ መጀመሪያ ላይ እንዳለው ነገር፡፡ ዋናው ጉዳያቸው እኔ ሳልሆን እግዜር ከሰራው ኪነቴ ነው፡፡ እኔ ማክዳ የእግዜር ኪነት ወይም ስዕል ተሸካሚ ሸራ ነኝ፡፡ እኔ ማክዳ ግን ከኪነቱ የተለየሁ ነኝ፡፡ እንዲህ ለሁለት ሲሰነጥቁኝ ልማዳቸው ነውና እንደገደሉኝ አልገባቸውም፡፡ እኔም እንደተገደልኩ አልገባኝም፡፡ 'ቆንጆ' ማለት ከርሞ ሲገባኝ በጀርባዋ ስትንጋለል ሆዷ ላይ ተንበለብሎ አይኖቿን ማየት ደስ የሚል' ማለት ናት፡፡ 'ቆንጆ' ሲሉ እግዜር አስቦ የላከላቸው ደስ ብሎአቸው የሚያደርጉኝ ኪነት ተሸካሚ ሰብ ማለታቸው ነው፡፡ የዋህነቴ

ቁንጅና አይደለም:: አንጎሉ ቁንጅና አይደለም:: አነጋገሩና የቃላት አመራረጡ ቁንጅና አይደለም:: እኔ ማክዳ የማይነገረውና ያልተነገረው የወንዶች የሩካቤ ስጋ ተስፋ ነኝ:: የሚገርመኝ እዝራ ወደዚህ ክልል አልሄደም:: ወደዚህ ባለመሄዱ ለአጭር ጊዜ ለእሱ ባልነግረውም አጥላላሁት:: 'ወንድ አይደለም' አይነት ናቅሁት:: ቂል አደረኩት:: የተሳሳተ ደደብ ሆነብኝ:: ያደኩት እንደዛ ነው:: ካአደኩበት አለም አሯሩጠው ተነጫንጨው 'እናድርግሽ' ካላሉኝ የናቁኝ ይመስለኝ ነበር:: የምጠላውን እንደሆንኩ የገባኝ እዝራን ሳገኝ ነው:: አግኝቼ ብቻ ሳይሆን አግኝቼ ሳጣው ነው:: እወዲያ ተቀምጦ እያየኝ ልቡ ሲመታ ይሰማኛል:: በዚህ ማዕበል ሽሚዙ ከፍ ዝቅ ሲል አያለሁ:: ያን ማንም አያይም:: አይኖቹን ጨፍኖ ክንዴ ላይ ሲጋደም፣ እንቅልፍም የመሰለ ነገር ሲወስደው በዛ የቤቱ ፀጥታ በዛ ድንግዝግዝ ውስጥ እንደ ትንሽ ደብተር አነበብኩት:: ግን መታገስ አቃተኝ:: የሰለጠንኩበት አሸነፈኝ::

በተረትሽ ተገዛሁ፣

ወሬሽ ግሜን ወሰደ::

•

•

•

ውጩ ቀዝቃዛ ነው:: በጥርሶቼ እርሳስ ነክሼአለሁ:: ከነከስኩት ብዙ ጊዜዬ ነው:: ምራቁ ውስጥ የሚመር የላጲሱ ጣዕም አለ:: እርሳሱን ከአፌ ማውጣት አልፈለኩም:: ፊት ለፊቴ የተከፈተ መስኮት ነው:: ቀሚሴን ሰበሰቤ እፍረቴን እላጫለሁ:: ከንፈሮቹ እየተልቆሰቆሱ አዕድቶ ለመቁረጥ አይመችም:: መቀሱ በደንብ አይቆርጥም: ቆዳዬን ይነክሰኛል:: ጎኔ እዝራ ከገዛልኝ የሂሳብ ሺት ጀርባ ላይ ተሰርቶ ያላለቀ የአልጋ ስዕል አለ:: አልጋዬ እንደዚህ ነው: *ሱፉ ገና ረግፎ ያላለቀ ብርድልብስ ከላዩ አለ:: ሽሮ መልክ ያለው የአቡጀዲ አንሶላ ከራስጌ በኩል ታጥፎ ብርድልብሱ ላይ ነው:: አልጋዬ ቢትልስ ሹራብ የለበሰ ይመስላል:: ራሴ በጠለፍኩት ልብስ የተሸፈነ አንድ ትራስ ራስጌ ላይ አለ::*

ዋሕድ ሰላምታ ሲል እሰማዋለሁ:: ቆዳዬ ላይ የተለጠፉትን ደቃቃ ፀጉሮች አረጋግፌ......*ማኪዬ ዋሕድ መጣ!*......እማማ ትጣራለች:: ምላጬን የሚቀመጥበት አስቀምጬ ቶሎ ወጣሁ:: ዋሕድ የአጥር በር ግራና ቀኝ ከፍቶ ቆሞአል:: ግራ ገብቶኝ አየሁት:: እማማ ጎኑ ቆማ ክንዱን ይዛለች:: አያያዟ አያምርም:: ልትደገፈው ትንሽ ነው የቀራት ......ዋሕድ ከሉንቺና ላይ አልጋ ሊያወርድ ሄደ......እሱን እያማጠ ተሸክሞ አልፎኝ ገባ:: ብዙ ጊዜ ዋሕድ አየር ጤና ብቅ ሲል የሆነ ነገር ይዞልኝ ይመጣል:: እማማ በፍቅር ዐይን ታየዋለች:: እስተያየት አውቃለሁ::

እማማ ግን የማውቅ አይመስላትም:: እሱን በነፃነት የምታየው ደንቆሮ ስለምመስላት ነው::

የመጣውን አልጋ ከዋሕድ ጋር በብልት በብልት እያወላለቅን ቤት እያስገባን ነው:: እማማ ቡና ማፍላት ጀምራለች:: እዛ የዋሕድ አይኖች ከእማማ ላይ አይነሱም:: አይኖቹ እሷን ከማየት ሲያርፉ፣ ላለማስጠጣት ሊተርበኝ ይሞክራል: 'ጓደኞቼ አሁንም የሽሮሜዳ ልጆች ናቸው? ወይስ የ[redacted]?' ምናምን የመሳሰለ:: እያወቀ ግን እንዳላወቀ:: እማማም እያወቀች እንዳላወቀች:: ሁላችንም በማስመሰል እንቃለዳለን:: እሷ ሳታየኝ እገላምጠዋለሁ:: ደጋግሜ ገላመጥኩት:: የዚያ አይነት ወሬ እንዲያቆም: 'ከኮረዳ አይሚገቱም' አለ እየሳቀ::

«ነገ እሷ ትዘርጋው፣ አሁን እረፍ:: ጭንህ አምጥተህ ደሞ እዚህ ትቸገር» ትላለች እማማ::

ወደ ግቢው ፊት ለፊት የቡና ጠረን ይመጣል:: ቡና ሲሸተኝ ይርበኛል:: ቡና ሲሸተኝ ቡና አይጠማኝም:: ቡና ሲሸተኝ ሽንብራ ያምረኛል::

'አልጋውን እዝራ ሲጥለው ሲል እፈልገዋለሁ ብዬ ለእንቺ አመጣሁት' ሲል አላመንኩትም:: ላምን አልፈለኩም:: ሳስበው ከእዝራ ጋር ንግድ ስለሚሰራ እዝራ ውሰድላት ብሎት ቢሆንስ? እዝራ 'አልጋው ተስማማሽ ወይ?' ሊል ቢመጣ ሁሉን ዘክዝኬ ነግሬው የመጣው ይመጣ ነበር:: አልጋውን ምናልባት ተኝቼበት ይሆናል:: ከአለምአንተ ጋር አንዳንዴ እዛ ሲመሽ እሄድ ነበር:: በሶስት ቢራ ሞቅ ሲለኝ:: ይሄ ሁሉ ሆኖ ግን 'ጎበዝ ተማሪ' መባል አልፈለኩም:: ያለፈው ሃጢያት እንዴት ይሰረዛል? ኢኤስኤልሲ በሁለት ነጥብ ስምንት ማለፍ፣ ('እሷም ትላ ዩንቨርሲቲ ገባች?' እየተባልኩ) እሱ ጀብድ ሆኖ ያ ያ ያ ያለፈው ሁሉ ይሰረዛል?

«ይሄ አልጋ አይደለም፣ ሲመች [redacted] ዙፋን ነው» አለኝ::

ዙፋን አይደለም:: አይመስለኝም:: የአውቶቡስ ጣቢያ ነው:: አሁን አሁን ወደ እዝራ ለመሳፈር የምጠብቅበት:: ለመሆኑ እዝራ ግን ያውቃል ለእኔ ከሁሉ ወንዶች እንደሚበልጥብኝ? ደሞስ ሃሜት እንደምደፍር ፊት ለፊት መናገርን እንደምፈራት? አባቴ የተናገረው ትዝ ብሎኝ ዋሕድን ስለ እዝራ ልጠይቀው አልደፈርኩም::

«እንዴት ነው ታዚና? ጥብሱ ናፈቀኝ ለምን ጥብስ አታመጣልኝም?» አልኩት ሳቅ ብዬ

«ሊዘጉበት ነበር እኮ ሃሃ»

«ምን?»

«ከማዘጋጃ ቤት መጥተው ሊዘጉበት ነበር» አለ ፈገግ ብሎ::

«ታዲያ ያስቃል?»

«ለምን አያስቅም? ጉራው እኮ ሊገለን ነበር:: እሱ ወገን አለው እንጂ የሌላ ሰው ቢሆን ይዘጋ ነበር»

«ምን አደረገ?»

«ምነው አንቺ ተከራከርሽለት ነገር አለሽ?» አለ ዋሕድ:: ነገር እንዳለኝ ያውቃል ግን እንዲህ እማማ ፊት ይናገራል? ምን ሆንክ? አይነት አተኩሬ አየሁት:: አካሄዱ ስለ እዝራ ለማወቅ እንደሆነ ገብቶታል:: ከገባው ያልገባው አይመስልም? ዘሎ እንዲህ ምን አናገረው? የተለያየንበትን ምክንያት ባያውቅም፣ እንደተለያየን ያውቃል:: ዋሕድ የሚወራውን እንጂ ልብን የማወቅ ችሎታ የለውም::

«እኔ ምን አገባኝ ነገሩን ነው እንጂ»

«ታዲያስ:: ስጋውን ከየት እንደሚያመጣው አታውቂም:: ከየት እንደሚመጣ እሱን ለእግዚአብሄር እንተወውና፣ ማድቤቱ በሙሉ በአይጥ የተወረረ ነው:: አንድ ቀን እንደውም ሽንኩራ ላመጣ ስሄድ ከአገዳው ክምር እባብ ተሽሎክሉኮ ወጣ:: ስጋው የእውነት ከሆነ ለምን እንደዛ ርካሽ አድርጎ ይሸጣል? መመራመር» አለ:: የመጨረሻውን ቃል ሲናገር በአመልካች ጣቱ ግንባሩን እየወጋ::

«እርካሽ ነው?»

«ድልሁ ብቻ ሶስት ብር አያወጣም? ስጋውን ጨምሪ»

«እኔ አላውቅም»

«ጠማቂ ስትነግረን ጠላው ውስጥ የሚያስገባው ነገር አለ:: ብቻ ሰራተኞች ሳይገቡ በጠዋት ይመጣና በጠርሙስ የሆነ ነገር ድፍድፉ ውስጥ ይከታል:: የተደገመበት ውሃ ይሆናል»

«እንጃ፣ ሰው ካልገባ ማን ሰው አየው?»

«አይ ይህቺ ልጅ ኮሌጅ መግባት ማወቅ መስሏታል:: ብዙ ተንኮል አለ አለም ላይ:: ትደርሺበታለሽ»

«ጋሼ ዋሕድ ቤቱ ቢዘጋ አንተ ስራ ታጣለህ» አልኩት ላስፈራራው

«ያው ሽንኮራ መሸጤ እመለሳለሁዋ:: ያው እኮ ነው»

«ገንዘቡ ያው ነው?»

«ያው ነው:: እንደበዘበዘኝ እኮ ነው:: ለማን ይነገራል እንጂ:: ሊያዘጉበት መጥተው ሳይመለሱ ቀሩ:: ሰው አለው አሉ እላይ ድረስ» በአመልካች ጣቱ ወደ ሰማይ እያሳየ::

«እኔ አንተን ብሆን እንዲህ የሚያስመርረኝ ቢሆን በታውን እለቃለሁ» አልኩት ልፈትሸው

አተኩሮ አየኝና፣ እየሳቀ

«ለምን? እንዴ ሚስጢር አውቆ ሊናገርብኝ ነው ብሎ በሰፈሩ ሰው ቢያስደበድበኝስ? አንቺ የማያውቀው አይነት ሰው የለም»

«ብዙ ገንዘብ አይከፍልህም አይደል? አንተንም ያሳማሃል ጠላውን እንደዛ ካደረገው»

«ስሙኒስ ብትሆን ገንዘብ አይደለች»

«ለስሙኒ ብለህ»

«ስሙኒ ስልሽ……ይህቺ ልጅሽ ምን ሆነች?! ነገር ነገር አላት!» አለ ለእማማ

እማማ መልሳ:

«እቤት ተቀርቅራ፣ እኔ ለሰፈሩ አዲስ የሆነች መስሎኝ ነበር:: ከሰው የምትግባባዋ ልጅት ተጋድማ ትውላለች:: ምላሷስ ደሞ»

«ለእሷ ብዬ አልጋ ከሽሮሜዳ ተሸክሜ አምጥቼ ነዘነዘችኝ»

«ስለ አልጋ መቼ አወራን» አልኩት

«ያው ነው ምን:: ካልፈለግሽው እወስደዋለሁ»

«እንዴ ምነው እስከዚህ ውሰደዋ!» አልኩት የእውን ተበሳጭቼ

«ምን አንቺ ቀልማዳ:: አፏ እኮ ነው» አለች እማማ

እዛ መቀመጥ አልነበረብኝም:: አስመርረው ሊያስወጡኝ እንደሆነ ገባኝ::

«እማማ ሳልረሳው አንድ ልጅ ጋ ደርሼ መጣሁ:: ሆምወርክ እርጂኝ ብላ ነበር:: እቆይ ይሆናል» አልኩ ወዲያ ወዲያ እያየሁ:: ዋሕድ በፍጥነት እማማን አያት:: በዐይኔ ቂጥ አየዋለሁ:: በዐይኔ ብቻ ሳይሆን፣ በዐይኔ ቂጥ ማየት እንደምችልበት አያውቁም::

«አይ አንቺ……» አለች

ምንም አልቀጠለችም 'አይ አንቺ' ብላ:: ምን ማለት ነው? አፍራ ነው?

«እውነቴን ነው እማማ ረሳሁት»

«በይ ሂጂ» አለችና ጀበና አንስታ ቡና እየቀዳች ዋሕድን ቶሎ አየችው::

እንደ አየሁዋት አላየችም:: እሱ እግሮቹ ተነቃነቁ:: ጉርሻ ሊሰጡት ከተቀመጠበት እንደጠሩት ልጅ:: ከንፈሮቹን ላሰ:: ከንፈሮቹን ሲልስ

እንዳየሁት አላየም። እማማም አላየችውም። መኝታ ቤት ገብቼ መፅሃፌን ይዤ ልወጣ ስል:

«ካላገኘሁህ ደህና ሰንብት እንገናኛለን» አልኩትና አቅፌ አንድ ጉንጩን ሳምኩት።

«ብቅ በይ ሽርሜዳ፣ ከስድስት ኪሎ አይርቅም አይደል። ታዚና ሳይዘጋ ጥብስ ጥገቢ» አለ

በታዚና ከሚቀልድ ከእናቴ ጋር ቢቀልድ አይሻለውም?

ከቤት ደብተሬን ይዤ ወጥቼ አጥር በር ልደርስ ስል ዋሕድ ሲጠራኝ ሰማሁት። ለማጣራት ዞር ስል ከቤት ብቅ ብሎ:

«እንዴ ሳነጋግርሽ ቆይኝ» አለና ቸኮል እያለ መጣ።

[redacted]ቀረበኝ ወደኋላው ዞር ብሎ አየና:

«ለመሆኑ ከዛ ሰውዬ ጋር ትገናኛለሽ?» አለ

«ማን?» አልኩት ማንን ማለቱ እንደሆነ ቢገባኝም

«አይ አንቺ......ሃሃ እዝራ ነዋ»

«አይቼው አላውቅም»

«የእውነት?»

«አዎ»

«አሪፍ ነሽ። አሁን በታሽን አወቅሽ። ይሄ ውሻ በጨው የማትነካው የመሰለ። ከገንዘብ ሌላ ምንም የማያውቅ። የገባት ብልህ ልጅ ነሽ የእውነት። አሁን ኮሌጅ ገብተሻል አይደል፣ ትምህርትሽን ጠበቅ አድርጊ። ከእሱ አይነት ሰው ጋር ሲጀመርም መገናኘትሽ። እውነት። ተስፋ ቆርጦ ሴት እንደከብት ማንጋጋት ጀምሯል። ጨዋ ነበር እኮ። ሞራሉ ተነካ። ወንድ ሞራሉ ከተነካ በቃው። ስንት አይነት አስቀያሚ ሴት አለ አቦ። ማከዴን አላዩ። እኔ ያኔም ላናግርሽ ያልፈለኩት ይገባሻል ብዬ ነበር። ያለፈ አልፏል.....»

«ትቼዋለሁ። እኔ ትምህርቴን ነው»

«እኮ እኮ ገባኝ። ቀጥዪ በዚህ»

ትከሻዬን በፍቅር ደባበሰኝና ተመለሰ።

የሄድኩት የሆነ ፈፋ ዳር ነው። ታች ጅረት የነበረ ሸጥ፣ በድንጋይ የተሞላ፣ ቀበጥባጣ ውሃ እናቶች አገር ፍለጋ ስንቅና ትጥቃቸውን ይዘው የሸሹት። ጠረኑ የአልባብ አይደለም። አየርና እበት ነው። እናሳው ተክል

ሁሉ ችፍርግ ነው። አመጻም በላሎች ከመላጣ መሬት ወደ መላጣ መሬት ይበራሉ።

ብቻዬን ተቀምጬ ሁሉን ረስቼ ማጥናቴን ጀመርኩ።

•

•

•

ፍሬሽ ማን (የመጀመሪያ አመት የኮሌጅ) መዓት 101 ኮርሶች እወስዳለሁ። መዓት ትዝታዎችም አላምጣለሁ። አንድ አመት ተኩል የከረመ ፍቅር፣ ሊናገሩት የሚከብድ፣ ሊያብራሩት የሚያቅት በሁለመናዬ ይገኛለሁ። ቅዳሜና እሁድ ሰፈሬ አየር ጤና እሄዳለሁ። አየር ጤና ጥሩ ሆና በካውያ የተተኮሰች ሽሮሚዳ ናት። እዛ ወጪጫ፣ እዛ ረጲ፣ እዛ መናገሻ። በነዚህ ተጋርጄአለሁ። ማን እዝራን ሳሰብ ይበርደኛል። ከአውቶቡስ ማቆሚያው እስከ ቤቴ በር ድረስ በየመንገዱ ዳር ፉጭቶች እንደ እሾህ በቅለዋል። የአየር ጤና ሰፈር ኅረምሶች ፉጨት የጣጣ ቅርፅ አለው። በየሄድኩበት እንደ አየር እንደ ነፋስ ይከተለኛል። ከላዬ ላይ እንደ አቧራ እራግፋቸዋለሁ። ስድስት ኪሎ የተማሪ ካፌቴርያ ሰልፍ ላይ የሚገፋኝ ትከሻ ብዛቱ። ይህቺን ልጅ አብዮቱ፣ ፀረ አብዮቱ አያድናትም። ምን አይነት ሽብር ብታፋጭም እንደምትድን አታውቅም......የቅንነት ባርያ መሆን ይሻላል የዓብዝነት ጌታ ከመሆን። ማለት ባርነት ካልቀረ......

•

•

•

'ሕይወት' ሲሉ ከእኔ ተነጥሎ የሚንሳፈፍ ስሙቸው እንደ መንፈስ ዘሎ የሚይዘኝ፣ ሳልመቸው ለቆኝ የሚሰደድ ጉድ ነገር ያስመስሉታል። የነበረውና ያለው ነው። 'ይሄውና' 'ያውና' ተብሎ ከእኔ ውጭ ባይታይም እውስጤ አለ። ከሱንቃፎቼ ውስጥ የቅንድቦቼ ፀጉር ውስጥ በልጅነቴ የበላሁዋት ቂጣ አለች። የእንድዋን ቅንድቤን ግራና ቀኝ ይዘን ብንጠመዝዛት ገብሷ ይወጣል። የአፍረቴ መሬት (አዳሜ የወደዳት) በልጅነቴ የበላሁት የአውጥ ወዝ ነው። ትናንት አትሞትም።

**ሕይወት እኔና አንተ**

**ያ ወንዙና አፈሩ**

**ተራራውና ወሬአችን አይደለ እንዴ?**

ውዝግብሩ እንዲህ ነው:: ይበድሉንና ወይ ራሳችንን እንበድልና የምናማው እንፈልጋለን:: ለዚህ ሳይሆን ይቀራል ከጊዜና ከቦታ የተለየች ቁስ ለመሆን ትንሽ የቀራት 'ሕይወት' የተባለች ነገር የፈጠርነው? ከዛ እናማታለን እናማዋለን:: በትክክል ግን እኔ ቆሻሻ ከሆንኩ እኔ ነኝ ቆሻሻ? እኔ ከሆንኩ መልካም፣ እኔ ነኝ መልካም:: እዚህ ድረስ እየገባኝ ነው::

•

•

•

የስድስት ኪሎ ካምፓስ ያፅናናኛል:: የመኝታ ክፍላችንን ጠረን እወደዋለሁ:: የስድስት ኪሎ ጫጫታ መድሃኒት ነው:: ከጓደኞቼ ጋር ወደ ሚሄዱበት እሄዳለሁ:: መዓት ናቸው:: ስድስት ምናምን፣ አይበልጡም እንዴንዴ? ይላሉ፣ ትላለች ቤላም: ከሁሉ የምወዳት:

«አንቺ አታወሪም? በዝምታሽ ገደልሽን»

ሳላይሽ የምትባለው ደሞ:

«ስትደበር እኮ አይጣል ነው» ትላለች የሚያምር ነገሯን እየሰበቀች:: ማለት ቂጥዋን:: ሳላይሽ አራዳ ለመሆን የምትጥር የባህር ዳር ባላገር ናት:: ባህርዳር ማለት መዓት ባላገሮች አንድ ላይ ተሰብስበው ማለት ነው:: ከቤላ ጋር የቅርብ ወዳጆች ናቸው:: ቤላ ሲፒኤ የተባለ መስሪያ ቤት ትሰራለች:: ሳላይሽን ለማየት ስትመጣ ተዋወቅሁዋት:: ከሳላይሽ ጋር አንድ ዶርም ነን:: ቤላ ብዙ ጊዜ ቅዳሜ ከሰአት ካምፓስ ትመጣለች::

«እንዳታወሩ ከለከልኳችሁ?»

ዙሪያዬን ባዶ ይመስለኛል:: እኔ ለብቻዬ በምድር ላይ የተፈጠርኩ:: ሁልጊዜ ቅዳሜ ከሰአት ቤቴ ብሄድም ባልሄድም ገላዬን እታጠባለሁ:: ሻወር ስወስድ በአጋጣሚ ዶርም ካለች ጀርባዬን የምታጥበኝ ቤላ ናት:: እሷ ስትታጠብ ጀርባዋን የማሻት እኔ ነኝ:: ቤላ ጀርባዬን አጥባ ስትጨርስ ማጅራቴ ላይ ትስመኛለች:: ቤላ ልጅ ባይኖራትም፣ የገላ ቅርፅዋ እንደ እማማ ነው:: ወላድ ትመስላለች:: ፀጉሯ ያምራል:: የምትሄድበት ከሌሳት አራተኛ ብሎክ ጀርባ አፍንጮ በርን እያየን እንነጉናታለሁ:: ትልቅ እህት ያለኝ ይመስለኛል:: የምትናደደው 'ሊትሬቸር እማራለሁ' ስላት ነው:: እሷ የሳይኮሎጂ ምሩቅ ናት:: ስነፅሁፍ ለልቤ ቅርብ እንደሆነ እነግራታለሁ:: ከዚህ ሌላ ምክንያት የለኝም:: 'ደርግ በአዲስ ዘመን' ይደብርኛል ትለኛለች:: ልብ ወለድ ሳነብ፣ ግጥም ሲነበብ ስሰማ እንደ ሴክስ ደስ ይለኛል:: የሴክሱን አልነግራትም:: ጋዜጠኛ ለመሆን አላስብም:: የማልመው ደራሲ ለመሆን ነው::

«ችግር ካለ አውሪን»

«ምንም ችግር የለም»

«በቃ አትደብሪና፣ መጀመሪያውኑ አለመምጣት»

‘ስንት ጊዜ ያለፈው ያረጀው ነገር ይቆጨኛል’ ብላቸው በሳቅ ይፈርሳሉ:: በመሳቂያቸው ይስቁብኛል:: መሳቂያቸው መዓት ነው:: መሳቂያቸው አልሆንም:: የሕይወቴ ቀረጢት ውስጥ እንደ ባልጩት የሚብለጨለጩ ገበናዎች አሉብኝ:: ነገ ብጣላቸው ዛሬ የነገርኩዋቸውን ገመናዬን ‘አይገርምሽም?’ እየተባባሉ ያወሩብኛል:: ሴቶችን አውቃቸዋለሁ::

ሌላ ቀን:

«ደብሮኛል እናንተ ሂዱ»

«ምን ዛሬ ብቻ ስትወለጂ ጀምሮ መሰለኝ የተደበርሽው:: ፍቅር ጠፈነገሽ?»

«ሌላ የሚያሳስብ ነገር ጠፋ አሉዋችሁ እንዴ በዚህ አገር?»

ምን ማለቴ ነው? ከፍቅር ተንሸራቶ ነገሬ ፖለቲካ ሆነ? ራሴን በራሴ ሳሳድድ የምገባው ፖለቲካ ሰፈር ነው?

•

•

•

በጣም በጣም እነባለሁ:: ደራሲ ለመሆን ብቻ አይደለም:: እዝራን የምለምንበት የሚያምር ቃል ፍለጋ:: በሕልሜ ይመጣላ:: አፌን ይስማል ግንባሬን ይስማል:: የሆነ ነገር አድርግ እለዋለሁ:: ትቶኝ ሻንጥላ ዘርግቶ ወደ እንጦጦ ይወጣል:: ይቅርታ ልጠይቀው ስል አፌ በመርፌና ክር እንደ ተሰፋ ይታወቀኛል:: ለቅሶዬን የተለሰነው አፌ ውስጥ እተነፍሳለሁ:: በሕልማችን ወደዚህች ከተማ ጎዳና መውጣት እንችላለን? ተደፋፍረን አውርተን የልባችንን ስጦታ የሞቁ መዳፎቻችን ላይ ልናስቀምጥ?

•

•

•

ዋሕድ አንድ እሁድ አየር ጤና መጥቶ አምሳ ብር ሰጠኝ:: እማማ ‘ደህና ስትማር ገንዘብ ለምን ታስለምዳታለህ?’ አለችው:: ‘ስቁብ ደርሶኝ ነው’ አላት:: ድሮ ሳንቲም ይሰጠኝ ነበር:: ጋዜጠኛ ወይም እንደ በዓሉ ግርማ ልብወለድ ደራሲ ለመሆን እንደምፈልግ ስናገር አፉን በእጁ ጋርዶ ሳቀ:: እንዲህ ሲስቅብኝ በእጄ የያዝኩት ብር ከወረቀት አነሰብኝ::

ያኔውኑ ልመልስለት አማረኝ:: ግን ጓደኞቼ ብዙ ጊዜ ስለሚጋብዙኝ ለብድር መመለሻ ያዝኩት:: የተማርኩት ይሄንን ነው፡ ደግ ልስራ ተብሎ ክፉ ይደረሳል፣ ወይም በክፉ መንገድ ይኬዳል:: መምረጥ ይከብደናል:: ስለ እዝራ ያወራል፡

«አሁን ምን ለመከፈት እንደፈለገ ታውቂያለሽ? ሸሮና በርበሬ ወደ ፈረንጅ አገር ለዘመዶቻቸው ለሚልኩ ሰዎች የሚያዘጋጅበት ባልትና ቤት:: በሰው ቁስል እንጨት ይሰዳል»

ግድ አለኝ?

ማታ ተኝቼ ለእዝራ ደብዳቤ ልፅፍ አሰብኩ:: ፈሪ የሆንኩ ደሞ መሰለኝ:: ፈሪነት ነው:: እዚህ በአንድ አውቶቡስ ብሄድ ለማገኘው ሰው......

•

•

•

ብዙ ጊዜ እንደማደርገው ብቻዬን ለመናፈስ ከስድስት ኪሎ ካምፓስ በአራት ኪሎ በኩል ወደ ፒያሳ በእግሬ ሳቀና ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ፊት ለፊት ለምለምን (ሌሚ ወይም ሊሊ የምንላት) ወደ ካዛንቺስ ለመሄድ ታክሲ ስትጠብቅ አገኘሁዋት:: ሊሊ (እኔም ሲኳት ስምቼ እንጂ 'ሊሊ' ቁልምጫ ብቻ ሳይሆን በእንግሊዘኛ የአበባ ስም መሆኑን ያወቅሁት በቅርብ ነው) አንዳንድ ጊዜ በቅሎ ቤት አካባቢ ያለ ተከርቸም ከፍፁምና ከወዳጆቻቸው ጋር አብረን የምናመሽ ልጅ ነበረች:: እዛ ብቻ ስለማገኛት ለበቅሎ ቤት የተመደበች ይመስለኝ ነበር:: ቋሚ ወዳጇ መከላከያ ሚኒስቴር የሚሰራ መሳቅ የሚወድ ረጋሳ (በቁልምጫ 'ረጌ') የተባለ ረዥም ሰውዬና ዘረአብሩክ የተባሉ ሁለት ዚታዎ ያላቸው ሰውዬ ናቸው:: ስለ ረጌ ከዚህ በላይ አላውቅም:: እንደለመደችው ዘንጣ ለብሳለች:: ምናልባት ምሽቱ ነው:: ምናልባት ወረቀት ላይ ተደፍተው የዋሉት አይኖቼ የሚያምር የሰው ፊት በማየታቸው ሳላውቀው ተደስቼ ይሆናል:: ለምን ደስ እንዳለኝ ምክንያት ጨደርድር ጓንጂ በትክክል አልገባኝም:: ሊሊ ጸቋቋመ መልካም ናት:: ግራና ቀኝ ዳሌዋ ሽጉጥ የታጠቀች ያስመስላታል:: ይሄ የተፈጥሮ ስጦታዋ እንዲታይ ሱሪ ወይም ጠባብ ቀሚስ መልበስ ትወዳለች:: እንደተለመደው ተሳሳምን:: እዛ አይነት ቦታ የምንገናኝ ሴቶች አሳሳማችን ስፊና ጥልቅ ነው:: መሳሳም አሪፍ ነን:: መነጋገር የአፍ እላፊ ስለሚያመጣ አፍረታችንን መሸፈኛ ይሆናል:: ብቻ አይገባኝም:: ለምን እንሳሳማለን?

እ?

«ምነው ጠፋሽ አንቺ?» አለች ሳቅ ብላ:: ለምን እንደጠፋሁ ታውቃለች:: 'ከፍፁም ብትለያዪ ሌላ ወንድ ጠፋ አሉሽ' አይነት ነው:: ከምናውቀው ስርአት እንደተፋታሁ ቢገባትም ያልገባት ትመስላለች:: እናም የተውኩትን ጉዳይ የምታነሳሳው አንዴ ማኖ ነክተሻል ......አድራሻ ለወጥሽ እንጂ የትም አልሸሸሽ......አጉል ጨዋ አትምሰይ ማለት እንደሆነ አጠረጥራለሁ:: *የሚሰምጥ ሰው እጁን ቢሰድ ሰላምታ መስሎህ አትጨብጠው* ይላሉ የፈረንጅ ተራቾች::

«ትምህርቴ ይሻለኛል» አልኩዋት::

«የዘመኑ ትምህርት የት ይደርሳል ብለሽ ነው?......ሳልነግርሽ እኔ አሁን ፕሮሰስ እያደረኩ ነው:: አስመሮም ነው ጉዳዬን የሚከታተልልኝ:: አስመሮምን ታውቂዋለሽ አደል:: አደርጋለሁ ያለውን ያደርጋል:: በቅርብ ከተሳካልኝ ፈረንሳይ እሄዳለሁ:: ለምን ግን አንገናኝም?»

አስመሮም የጀመረውን ጨራሽ ይሁን አላውቅም:: ያድርግላት አላውቅም:: የማላውቀውን ለምን 'እንደምታውቂው' ትለኛለች? 'ቪዛ ማስመቻ አይደለሁም' ልላት ፈለኩ:: በቢሮክራሲው መጫወቻ እንድሆን ነው? ያጋጠማቸው አውቃለሁ:: ፓስፖርት ለማግኘት አንድ አራት ሰው፣ ቪዛ ለማግኘት አንድ አራት ሰው፣ በጥቂቱ ስምንትና አስር ወንድ ያወጡ አውቃለሁ:: እንዲህ ሆኖም የማይሆንላቸውም መዓት ናቸው:: ያሳለፉት ባይናገሩም ወይም ቢቀንሱም የሰማ ላልሰማ......የሰማ ላልሰማ......ወሬው ይተላለፋል:: ሁልጊዜ ከወንዶች የምንወጣው ለጥቅም ስለሆነ ለምደነው አቅልለን እናየዋለን:: ያ ሁሉ ለእኔ ታሪክ ነው:: ባልኖረውም የራሴ ነው:: ምክንያቱም *ለምን?* እያልኩ አስበው ነበር:: እየተፎገርኩም ተፎግሬ እየወጣሁም ሙቅ ጀርባዬ ቀዝቃዛ እንሶላ እየሳመ *ለምን?* እል ነበር:: ልቤ ውስጥ ምንም የለም እና *ለምን?* እላለሁ:: ግን አደረጋለሁ......

«ዩንቨርሲቲ ገብቼአለሁ» አልኩዋት

«እውነትሽን ነው?»

ፈንጂ አጠገቧ እንደወደቀ ሁሉ ስትደናገጥ አየሁዋት--በጨለማ አይኖቿ ፈጠዋል። ግን ላለማስበላት ገፅዋን ፈጣን ፈገግታ አለበሰችው:: ግን ከዚህ የፈገግታ ኩታ ስር የሚንሳፈፈውን ድንጋጤ ማባረር አልቻለችም::

«ለምን ተቀምጠን አናወራም?» አለች ወደ ቱሪስት ሆቴል እያየች

«ጓደኞቼ ይጠብቁኛል» አልኩዋት::

«እዚህ ነሽ?» በአገጭዋ የአራት ኪሎ ዩንቨርሲቲን እያሳየችኝ

«አዎ» አልኩዋት እሷን የመሰለች ስድስት ኪሎ የምትማር ካለች ወሬ አቀነባብረው ቢያጣድፉኝስ::

«ማንን አውቃለሁ እዛ?» አለች እያሰበች

ምቀኝነቷን የምታስፈፅምላት ስም አጥፊ እየፈለገች እንደሆነ አልጠፋኝም::

«ሌላ ቀን ተገናኝተን እናወራለን»

«ስልክ አለሽ?......» አለች በጉጉት:: ገፅዋ ችኩል ያለ ነው::

«የለኝም ስልክ» አልኩዋት

«ሙሊ ስልክ አስገባልኝ» አለች

ሙሊ የመከላከያው ረጌ ጦር ሜዳ ከሄደ......ወይ ከተደበረ......ወይ ዘረአብሩክ ከደከመ......ወይ በራሱ ምክንያት ካልተገኘ......የሚያወጣት ሰውዬ ነው:: እንግሊዘኛ መናገር ይቀናዋል:: ሙሊ ኢንግሊሽ ነው የምንለው:: አሁን ያኔ ከእኔ ጋር ምን በጉራማይሌ አስቀባጠረው?

«ጥሩ» አልኩ:: ልሂድ ሊሊዬ (ያቆላመጥኳት ቶሎ እንድትለቀኝ ብዬ ነው:: የሁለት ደረጃ ማቆላመጥ ግድ ነው: ለምለም......ሊሊ.......ሊሊዬ) ልጆቹ ይጠብቁኛል አልኩ:: ስለ እኔ ብዙ ለማወቅ እንደምትፈልግ ይገባኛል:: አሁን የምትሄድበት በእርግጥ የማውቀው አይነት ቀጠሮ ከሆነ በጋራ የምናውቃቸውንም ይሁን የማላውቃቸውን ልጆች ስታገኝ ስለዛሬ ትንሽ ታወራለች እንጂ፣ ወደድሮው ወደሚያውቁት ወደማይተማመኑበት ቶሎ መግባት አትፈልግም:: ሁሌም አዲስ ወሬ አስፈላጊ ነው:: የጨዋታችን መሠረት ወሬ ነው:: በወሬ ስልታችን እዛው ተቀምጠን በሃሳብና በአንደበት ሊያያዝ ወደማይችሉ እዛና እዛዎች እንሰደዳለን:: ቢያንስ የተሰደድን ይመስለናል::

«በቃ ኮሌጅ ገባሽ......ኮራሽ» አለች በጥልቅ ተንፍሳ:: ቦርሳዋን ከአንዱ ወደ ሌላው ትከሻዋ አሸጋገረች

«እንዴት?» አልኩዋት:: ቅናቷ በፍጥነት ብቅ ይላል ብዬ አልጠበቅሁም እንደዚህ:

«በቃ ዩንቨርሲቲ ገባሽ የዕውነት?»

«ብኮራ ለምን ሰላም አልኩሽ» አልኩዋት ንዴቴን ውጬ እየሳቅሁ:: አታናድደኝም ነበር በፊት:: እንደውም በዳሌዋ ማማር እቀና ነበር:: አሁን አናደደችኝ::

«ስቀልድ ነው እባክሽ» እንዳልቀለደች አውቃለሁ:: ልሰናበታት ላቅፋት ስጠጋት:

«ሳልነግርሽ እረሳሁት ሮሚ ጣሊያን ሄደች እኮ»

«ይቅናት» አልኩ ባጭሩ:: 'ኸረ ባክሽ!' 'ውይ!' 'ታድላ!' 'እኛ እዚህ ስንርመጠመጥ አንዳንዱ ሲቀናው እኮ!' 'አንዳንዱን እግዚአብሄር ያዳላለታል!' 'እግዚአብሄር ምን እንደሚሰጥሽ አይታወቅም:: ዋናው ትዕግስት ነው' የመሳሰለ እንድዘበዝብ ነው::

«ደስ አይልም?» አለች:: ልክ እሷ ራሷ ሮም እንደገባች ሁሉ:: አንዷ እንደምንም ይቀናትና ሰላሳዎቹ ለሃጫቸው ይዝረበረባል::

«ደስ ይላል» አልኩ ቀለል አድርጌ፣ ግድ እንዳልሰጠኝ ይታወቃል:: እንዲህ ማሰቤ እንደ ወንጀል እንደሚቆጠር እጠረጥራለሁ:: ወንጀል ባይደረግም፣ 'የሀበሻ ነገር ምቀኛ' እንደሚባል አውቃለሁ:: እውነቶች እኔ ጋ ቢሆኑም እውነት ያለ አይመስልም:: እውነት በጫጫታ ነው:: የእኛ ሴቶች ሰይጣን ጫጫታችን ነው::

«በይ ሊሊዬ እደውልልሻለሁ»

«ስልኬን ልስጥሽ»

ቦርሳዋን በርብራ ወረቀትና እስክሪፕቶ አውጥታ በትኩረት መቸክቸክ ጀመረች:: ቁጥሩ የተጻፈበትን ወረቀት ተቀበልኩዋትና:

«ልጆቹን ሰላም በይልኝ» አልኩ

«ማንን?»

«ሁሉንም በቃ»

«አትጥፊ የዕውነት:: ብዙ ምሁርነት አይጠቅምም:: ሁሉ ከልኩ አያልፍም» አለች እንደ ቀልድ:: ለምን እንደምትል ይገባኛል

«በይ ሊሊ ልሂድ»

ተሳስመን ተለያየን:: ይህቺ የዘመናች ልጅ፣ ሲያዩዋት ፈረንጅነት የነካካት ከእማማ ያልተሻለች ነበረች:: እማማም አላት አሁን ድረስ 'ከልኩ አያልፍም' የምትለው ሊገባኝ ያልቻለ አማርኛ:: ሰባ ደረጃ ስደርስ በእጄ የያዝኩትን ወረቀት ጨመዳድጄ አስፋልት ዳር ያለ ቦይ ውስጥ ወረወርኩት::

•

•

•

አንድ ቀን ማታ ሁለት ሰአት ላይ ከቤላ፣ ከሳላይሽና ከሌሎች ሁለት ጓደኞቼ ጋር የካፌቴርያ ምግብ ስላመለጠን ራታችንን ልንበላ እላይ ተፈሪ መኮንን ኢ.ደ.ዩ የተባለ ሬስቶራንት ሄድን:: ያን ቀን ትንሽ ደስ ብሎኝ ነበር:: አስታውሳለሁ:: ጎረምሶች እየነጀሱን ያልፋሉ:: የሆቴሉን መግቢያ ተሰልፈን እንደ አለፍን ፊት ለፊት ያለው ጎጆ ውስጥ ፍፁምንና በሀይን

የማውቃቸውን ሌሎች ሁለት ሰዎች ጠረጴዛ ከበው የሆነ ነገር ሲበሉ አየሁ:: ያኔውኑ በደመነፍስ:

«በቃኝ ልመለስ» አልኩ:: ሳላወላውል ፊቴን አዙሬ መመለስ ጀመርኩ::

«አንቺ! ምን ሆንሽ? ነይ!» እያሉ ቢጠሩኝም አልሰማሁም:: ሳላይሽ ገመድ አፍ ተከትላኝ መጣች::

«ምን ሆንሽ አንቺዬ?!»

«ሲሸተኝ አመመኝ»

«ምኑ?»

«በቃ ምግብ ቤቱ»

«ኸረ ይህቺስ አበዛቺው፣ በይ ነይ»

«በዚሁ ባህርዳር አገርሽ ብገባ ይቀለኛል»

«ሂጂዛ! አማረልኝ ብላ ነው!?»

«ነገርኩሽ ሂጂ እኔ እዛ አሴ ቤት የሆነ ነገር እየበላሁ እጠብቃችሁዋለሁ»

«አይ ይህቺ ምኗ የዞረባት ናት እቴ!»

መልስ ሳልሰጥ ቶሎ ቶሎ እያልኩ ወደ ታች ወረድኩ:: ይኼ ፅናት ይባላል::

•

•

•

የሆነ ቅዳሜ ወይም እሁድ (ሌላ ቀን መቼም አይሆንም)፣ ከቤላ ጋር ሴቶች ዶርም ጀርባ ጠፍጣፋ ድንጋይ ላይ ተቀምጬ እሷ ቆማ ፀጉሬን ትሰራኛለች:: ከእኔ ጋር ሳይሆን ከሌሎች ጋር ትነጫነጫለች:: ተረቧ ሃይለኛና አስቂኝ ነው፡ ያን ቀን ደምትሄድበት ቢኖርም ልገላገልሽ ብላ እየተነጫነጨች በሚያማምሩ ጣቶቿ ትጎነጉነኛለች:: መጎንጎንዋን እንዳጋመሰች:

«እውነት በይ ፍሬንድ የለሽም?» አለችኝ:: የምትናገረው ስለሌላት የተናገረችው ይመስላል:: [redacted] አሰብኩና ለምን ዛሬ ጠየቀችኝ አይነት፣ ወይም ምን ልዋሻት አይነት:

«የለኝም» አልኩዋት

«በእማማ ሞት አትደብቂኝ»

«እውነት»

«ወይስ ምንም ነገር አታውቂም?»

«አይ እንደሱ ሳይሆን»

«አንድ ነገር ነው ይሄም ሂሂሂ»

«ምንም ነገር አልፈልግም ለዚህ ነው»

«ለምን አትፈልጊም?»

ትንሽ አሰብኩና ብዙ ውሸትን በጥቂት እውነት ለመዝጋት ሳይሆን አይቀርም፣ ስለመደፈሬ ነገርኳት። ስነግራት ግን ራሴን ከሃጢያቱ አፅድቼ ነው። የመሰላት ከተደፈርኩ በሁዋላ ምንም ነገር እንዳላደረኩ ነው። ስነግራት ያበላሸኝ ሰው ሽምትር እንደሆነ አልነገርኳትም። በመጠኑ መደፈሬ ከመወደዴ የመጣ እንዲመስልልኝ ወይም በወጣት መሰራቱ ክብር የሚሰጠው መሰለኝ።

«ወንዶች በስባሳ አይደሉ» አለችኝ። መሳንጎንዋን አቁማ በዝምታ ትንሽ ቆየች። ታሪኬ ያሳዘናት መሰለኝ። ነገሩን እንደረሳሁት፣ በቀልድ ደም 'ለማይቀር ነገር ምን አስጨነቀኝ' ልላት ሳስብ፡

«እኔም መጀመሪያ እንደዛ ነው የሆንኩት» አለችኝ

ሳላስበው በድንጋጤ ዞር ብዬ አየሁዋት። የጀመረችውን ጉንጉን ሳትጨርስ ከጎኔ ተቀመጠች። ወደ አፍንጮ በር እያየች 'ወንዶች በስባሳ ናቸው' የምትለዋን ደገመች። የመጨረሻ ስድቧ መሆኑ ነው። ያቺ ምላሷ የማያቆም ነገረኛ ቤላ በዚህ አጭር አባባል የምትገላገል አልመሰለኝም ነበር።

«የምትወጂው ማንም የለም?» አለችኝ ኮስተር ብላ

«አልፈልግም» ይሄም ውሸት ነው። መደፈርን መናገር ይቀላል ወይስ እንዲህ መዋሸት? የተዘበራረቀ ነገር ነው።

«ከዛ በሁዋላ ወድጄአለሁ ግን አልቀጠለም። መደበር አልፈልግም። መርሳት እፈልጋለሁ። ብዚህ አንብቤያለን። ብትክክል የአበሻን ወንድ የሚገልፀው የፍቄድ ፍልስፍና ነው። man's sexual organization and his social organization are so deeply interconnected ይላል። ይቅርታ ጋዜጠኛ አይገባውም ሂሂ» አለች።

ሳቋ ለበጣ አለበት።

«በእናትሽ ስንቴ ልንገርሽ ጋዜጠኛ መሆን አልፈልግም» አልኳት

«ኢትዮጵያን ሊትሬቸር እየተማርሽ ምን ትጠብቂያለሽ» አተኩሬ አየሁዋት።

«ስቀልድ ነው የእኔ ቆንጆ» አጎንብሳ እናቴ መሃል ሳመችኝ

ለምን ከሌሎቹ ሴቶች ለእኔ እንደምታዳላ ገባኝ:: አይኖቿ ውስጥ ጥላቻ አለ:: ይሄ ጥላቻ የሚያየው ወደ ውስጥ ነው:: የሚጠላው ነገር ውስጡ ነው ያለው:: የምታስታውሰውን ነው የምትጠላው:: አይኖቿ ውስጥ አይኖቼን አየሁ::

«ጠርጥረሻል አደለ በዚህ ነገር እንደተደበርኩ?»

«ይመስለኛል:: ሰው የጎዳሽ ይመስለኛል:: እኛ አገር ሴት የምትጎዳው በምንድነው? ይሄ ስላለን ብቻ አይደለ?» ወደ እግሯ መሃል እያሳየችኝ:: በማፈር ዙሪያዬን አየሁ::

«እርሻቸው:: አንዳንዴ ወንዶች ሲጠጉሽ በጥላቻ አይነት ዞር ትያለሽ:: ትሸሺያለሽ:: ከገላሽ ቅርፅ ወንድ እንደምታውቂ አውቃለሁ:: ይታይሽ ሁለመናሽ ሲያምር:: ስለዚህ አንድ ነገር ሆነሻል አልኩ:: እንደዚህ እንደነገርሽኝ አይነት ገጠመኝ አልጠበቅሁም:: አጀማመሩም ይሁን አካሄዱ ከተበላሽ ተበላሽ ነው:: አይደለ?»

«በቃ አናውራ በእናትሽ» አልኩዋት:: ይሄም ውሸት ነው:: ሳስበው የምውለውን ነገር ሳስብ የማድረውን ነገር::

«የነገርኩሽ ሚስጢር ትጠብቂያለሽ ብዬ ብቻ አይደለም:: ብዙ ልጃገረዶች አሉ እንዲህ ያጋጠማቸው:: ስለሚደበቅ ነው:: ያበሳጫል አደል? የደፈረንን ሁሉ ብናጋልጠው ልክ ነበር:: ዝም ብሎ መሸሽ ትክክል አይደለም»

አላደርገውም:: ለምን? የራሴ ስፍራ የራሴ ተሳታፊነት ፈጦ ይወጣብኛል:: ከተደፈርኩ በሁዋላ የተደሰትኩባቸው ጊዜያት እኔን ለመወንጀል ይሰለፋሉ:: ከአጀማመሬ ስህተት ጋር ተደርበው ያሴሩብኛል:: ራሴ ከወንጀሉ ጋር ነኝ:: የእኔ ብቻ ሳይሆን የአገር ታሪክ በማሳበብ አይፃፍም? ቢፃፍስ? አቶ 'ሀ' ያደረገው ነገር አቶ 'ለ' አደረገው እየተባለ:: ጥፋቴና መበደሌ አብረው ተጎንጉነዋል::

«በጣም ያበሳጫል» *ካበሳጨኝ ለምን ቀጠልኩበት?*

«ትምህርትሽን በጀንብ መከታተል ነው:: አንዳንዴ ኀባብሽን ትተሽ ስታስቢ አይሻለሁ:: ራስሽን መቻል አለብሽ መጀመሪያ»

«ልክ ነው እሱስ:: ደሞ ከብዶኛል:: የመጀመሪያ ሴሚስተር በግድ ነው ያለፍኩት»

«ከባዱ እሱ ነው:: የሚቸግርሽ ከሆነ......»

ከተቀመጠችበት ተነስታ የተወችውን ጉንጉን ጀመረች::

«ሰው ላገናኝሽ እንዳትይ»

«ምናባቷን፡፡ አሁን እየነገርሽኝ፡፡ ሴቶች ናቸው፡፡ ምነው አንቺ እስከዚሀ፡፡ አትፍሪ»

«ታዲያ ነጨሽኝ»

«ስታበሽቂኝስ......ይበቃል፡፡ እዪው፡፡ ምናለበት ደህና መስታወት ቢኖረን፡፡ ሳላይሽ የሰበረችውን አልተካችም፡፡ እሷ ልጅ፡፡ ችግሩ ወንዶቹ የነፃነታቸውን መጠን አያውቁትም፡፡ የሴት ደስታ በወንድ ደስታ የሚገዛ ይመስላቸዋል፡፡ መሠረቱ አየሽ አቅመቢስነት ነው» አባባሏ እውነት ቢኖርበትም የተሟላ አይደለም፡፡ አልጣመኝም፡፡ እኔስ? ግን አላልኩዋትም፡፡

«እንዴት እንደ ደከመኝ ታውቂያለሽ፣ ደሞ ራበኝ»

«ቤት እንሂድ»

«አልፈልግም»

«ቆይ ከመሄዴ በፊት የሚበላ አመጣልሻለሁ፡፡ ረሳሁት፡፡ ካፕቦርድ ውስጥ አስቀምጬዋለሁ»

ተያይዘን ወደ ዶርም ሄድን፡፡ እንቅልፍ ሊጥለኝ ያዛጋኛል፡፡ ፀሐዩ ብቻ አይደለም፡፡ እንደገባሁ አልጋ ላይ በጀርባዬ ተጋደምኩ፡፡ አይኖቼን እንደጨፈንኩ፣ ቤላ ቁምሳጥን ውስጥ ስታንጋጋ ቆይታ ሆዴ ላይ ትንሽ የክርታስ ሳጥን አስቀመጠች፡፡

«ምንድነው?»

«ግሪሲኒ ነዋ»

ከሆዴ ላይ ሳጥኑን አንስታ ከፈተችና ቀጭን የዳቦ ዘንግ አውጥታ አልጋዬ ላይ ከግርጌ ቁጭ አለች፡፡ ሰብራ ከበላችለት ዳቦ የቀረውን ወደ እኔ ገፋችው፡፡ አንድ መዝገቤ አወጣሁ፡፡ እሷ ቁጭ ብላ እኔ ተንጋልዬ የዳቦ ድርቆሽ መከሽከሽ ጀመርን፡፡ ከአፍታ በሁዋላ እንደተስማማኝ አይታ ክርታሱን ደረቴ ላይ ትታ ግንባሬን ስማ ለመውጣት መዘገጃጀት ጀመረች፡፡

«ማክዬ አውሬ አትሁኚ፡፡ ራስሽን ነው የምትጎጂው፡፡ እኬ? ስላመንሽኝ በጣም ደስ ብሎኛል፡፡ ሲተርፍሽ ቁምሳጥኑ ውስጥ መልሺው፡፡ እንደውም ሳላይሽ አምጪልኝ ብላ ነበር እና ትንሽ አስቀሪላት»

ሊፕስቲክዋን ተቀብታ፣ ቦርሳዋን አንግታ ወጣች፡፡

ገመናችንን ከተወያየን ጀምሮ ቤላ እኔ ጋ ድምፅዋ ዝቅ ያለ ተጫዋችና አባባይ ይሆናል፡፡ ቤላ በሆነ መልክ እህቴ ናት፡፡ በየቀኑ የምታሳየኝ መልካምነቷን በየቀኑ አስበዋለሁ፡፡ ይሄ ስለድካሜቴ

የምብሰለሰልበትን ጊዜ ቀነሰልኝ:: የልቦናዬ ቦታ ጨለማ ብቻ አልነበረም:: ግራው ነገር በልቤ ደስታ እንዲሞላ ሌላው [redacted] እኔ የተበደለ መሆኑን ማወቅ አለብኝ? ይሄ ይገርመኛል::

•

•

•

ሁሉ ነገር ስህተት ሊሆን ይችላል እየተቹ ሲያዩት:: አይደለም? እያንዳንዱ ስህተት ግን አስተምሮ ሊያሳድገን ይችላል:: መታደልም አለው አንዳንዴ ዕጣ ፈንታ 'ፎርቱና' እንደ ምትለው እናቴ--ትንሽ ተሳስቶ ማምለጥ:: ዱርዬነት፣ ብኩንነት፣ ባለጌነት፣ ስድነት፣ ሲጠቀሱ ጨዋ ከተባለ [redacted] ጋር ያላቸውን ቅርበት ሰዎች ይዘነጉታል:: ዕውቀት አለው:: ከሃያ ወንዶች ጋር ስወጣ የማገኘው የሃያ ሰዎችን የተዘባረቀ ገላ ብቻ አይደለም:: ማስመሰላቸውን፣ ፍቅራቸውን፣ ስሜታቸውንና፣ የስሜታቸውን መለዋወጥ፣ የአካላቸውን ንቅናቄ፣ ሃብታቸውንና አወጣጣቸውን፣ ገንዘብ ሳይኖረው ያለው የሚመስለውን፣ ቆንጆ ለመሆን የሚለፋውን፣ ትንሽ ተምሮ ብዙ ያወቀ የሚመስለውን፣ በሚያገባው የሚገባውን፣ በማያገባው የሚፈተፍተውንም ነው:: በነዚህ ተራ ከመሰሉ የስጋ ሩካቤን ከበው ካሉ ድርጊቶች ግለሰቦችን ብቻ ሳይሆን የሕብረተሰቡን አለዋወጥ መማር እችላለሁ:: ከአነጋገራቸው ከአካላቸው ንቅናቄ መገንዘብ እችላለሁ:: 'እሷ ምን ታውቃለች' ከብልግና ሌላ' በሚሉ እገረማለሁ:: ምክንያቱም፣ የማውቀውን አውቃለሁ::

•

•

•

***አልቦ መቀነት አልቦ እልበም:*** ቅዳሜንና እሁድ ቀኑን እቤት ቆይቼ ማታ ወደ ትምህርት ቤት ለመመለስ ስነሳ ሱሪዬን ልለብስ ስል ቀበቶውን አጣሁት:: ከሌላ ሱሪዬ ጋር ካምፓስ ረስቼዋለሁ:: አባባ ስራ ቦታው አዳር ለመሄድ ራቱን ይበላል፤ ወዲያ ወዲህ እያልኩ ክፉሴ ስነሣረክ:

«ምን ሆነሻል?» አለኝ::

«ቀበቶዬን ትምህርት ቤት ረስቼው፣ ቀሚሴን እንዳለብስ ደሞ አልታጠበም» አልኩት::

«የእኔ ቀበቶ ከሆነሽ አለልሽ:: [redacted] ያረጀ ነው»

«የፈለገ ይሁን ሹራቤን እለብሰዋለሁ» የት እንዳለ እንዲነግረኝ ቆሜ ጠበቅሁት::

«ሳጥኑ ውስጥ እዪው» አለኝ:: ሳጥኑ የሚባለው የእሱ ልብስና እቃ የሚቀመጥበት ነው:: ያረጀ ሳጥን ቢሆንም አባቴ እንደ ወርቅ ሉል ይጠብቀዋል:: መኝታ ቤት ገባሁ:: እናቴ አልጋ ላይ ተጋድማለች::

«መሄድሽ ነው?» አለች በሚያናውዝ ድምፅ

«አዎ:: ቀበቶዩ ጠፍቶ የአባባን ላደርግ ነበር»

«እህትሽን ጠዋት ስትለካው አይቼአታለሁ» አለች

«ካምፓስ የረሳሁት መስለኝ:: ምናባቷን ምን ሊያደርግላት»

«አደገች እኮ በቃ:: እንዳንቺ ቀጫጫ አይደለች:: እዛ ኮሌጅ ምንም አያበሉሽም? እሱስ ከድሮም ሰናና ነበርሽ»

«የአባባን ቀበቶ ልወስድ ነው»

«ደሞ የወንድ»

«ታዲያ ሱሪዬ እየወረደ»

«ሌላ የሚለበስ የለሽም?»

«አልታጠበም:: ደሞ ትምህርት ቤት ትቼዋለሁ»

ቀና ብላ አየችኝ:: ለምን ቀና ብላ እንዳየችኝ እንጃ:: ለመናገር የፈለገች ግን ደሞ ላለመናገር የወሰነች ትመስላለች:: ከአልጋ ስር ሳጥኑን ስቤ አወጣሁ:: ቁልፍ የለውም:: ከፈትኩትና ቀበቶውን እስካገኝ ያጋጠመኝን ጨርቃ ጨርቅ መገለባበጥ ጀመርኩ:: ከወደ ጥግ እጄ ጠንካራ ነገር ነካ:: የጋረደውን ልብስ ገለል ሳደርግ የሆነ አልበም አገኘሁ::

«ምንድነው?» አልኩና አወጣሁት

«ምን አገኘሽ?» አለች እማማ እንደተከናነበች

ቀበቶ መፈለጌን ትቼ አልበሙን ገለጥኩት:: ፎቶ ይኖረዋል ብዬ ነበር:: ያጋጠመኝ አስደነገጠኝ:: ወደ ሃምሳ የሚደርሱት የአልበሙ ገፆች በሙሉ ቅጠላ ቅጠል የተለጠፈባቸው ናቸው::

«አባባ ይሄ አልዋ እንዴ?» አልኩ

እማማ ክንብንብዋን ገልጣ የማየውን አየች......

«ስንት ጊዜው እዚህ ሳጥን ከሽሮሜዳ ያመጣው ነው:: ከየት እንዳገኘው» አለች

አልበሙን እየገለጥኩ አባባ ራቱን ወደሚበላበት ሄድኩ:: ገና ሳላናግረው አየኝና:

«እሰጥሻለሁ እያልኩ ረሳሁት» አለኝ:: ፊቱ ደስ ያለው አይመስልም:: ከአልበሙ መጀመሪያ ገፅ ላይ በእስክሪፕቶ የጠፋ ነገር አለ::

«ከየት አገኘሽው?» አልኩት

«ፈረንጆች ወርውረውት ከስራ ቦታ» አለ:: አያየኝም:: ሽሮውን በሰፋፊ እንጀራ ይጠቀልላል::

በእያንዳንዱ ገፅ ላይ አመተምህረት ቀንና ወር እና የተገኘበት ቦታ ሳይሆን አይቀርም **እንጦጦ** ተራራ ይላል::

«ፈረንጅ እንጦጦ ምን ይሰራል፣ ደሞ እማማ ከሽሮሜዳ ጀምሮ ነበር ትላለች» አልኩት

«ፈረንጅ የማይገባበት አለ:: ስትዘባርቅ ነው» አለ ሳያየኝ

ከዛ ቀጠለና:

«ወድቆ ሳየው እስኪ ይጠቅም እንደሆን ብዬ አመጣሁት:: ካልፈለግሽው ጣይው» አለ

እንደምፈልገው ወይም እንደማልፈልገው ሳልመልስለት ወደ መኝታ ቤት ሄድኩና እናቴ ጎን አልጋ ላይ አስቀመጥኩት:: ብዙ ሳልለፋ ቀበቶውን አገኘሁት:: ማርጀት የጀመረ ጥቁር ቀበቶ ነው:: ሁለት ቦታ ቀዳዳዎቹ በተሰነጣጣቀ የነጣ ሰንበር ተከበዋል:: አያምርም:: እነበረበት መለስኩና ካምፓስ እስክደርስ ብቻ የሚረዳኝ ቃጫ ነገር ፈልጌ ከሁዋላ የሱሪዬን ቀበቶ ማስገቢያ ቀዳዳዎች አጣግቼ ቋጠርኩበት:: ለእማማ ሳሳያት:

«ነካ አደረገሽ» አለች

ግን ደስ አለኝ:: አልበሙን ከአልጋ ላይ አንስቼ ወጣሁ:: አውቶቡስ ውስጥ እያየሁት ለመሄድ ቦርሳዬ ውስጥ ላስገባው ስል ቦታ አልበቃኝም:: ቦርሳው ትልቅ ቢሆንም:: ሳነግተው እርዝመቱ ከጡቴ ስር እስከ ጉልበቴ ይደርሳል:: ግን ጠባብ ነው:: ከውስጥ ሶስት ክፍሎች አሉት:: ከላይ ደሞ አንድ ትልቅ ኪስ አለው:: አልበሙን ኪሱ ውስጥ ከተትኩት:: ከዚህ ኪስ ስር ያስቀመጥኳቸው የሊፕስቲክና የጥፍር ቀለም ብልቃጦች ትንሽ አስቸገሩኝ:: አባቴ ደህና እደሩ ብሎ ሲወጣ አልሰማሁትም::

ልሰናበተው ስጠራው

«ጆሮሽ ተደፍኗል ደህና እደሩ ሲል አልሰማሽውም?» አለች እማማ

አልመለስኩላትም:: እተጋደመችበት ሳምኩዋትና ወጣሁ:: ትንሽ በእግሬ ሄጄ 26 ቁጥር አውቶቡስን ጠበቅሁ:: ብታቆየኝም አልቀረችም:: አንዳንዴ ሜዳ ላይ አንድ ሰአት ያህል ታቆመኛለች:: ሃያ ደቂቃ መጠለያው ስቆም ጥፍሬን ቀለም ተቀባሁ፣ ሊፕስቲኬን አደረኩ:: እዛ ለካፊ ወንድ አልነበረም:: ሁሌ እንደተለከፍኩ ነው:: ገና ቆመው ሳያቸው ነው ከሁኔታቸው እንደሚለክፉኝ የማውቀው......

አውቶቡሱ ሙሉ ነው:: መርካቶ ደርሼ ወደ ስድስት ኪሎ ውይይት ለመያዝ ማርስ ሆቴል ፊት ለፊት ስቆም፣ በርሳዬን እንዳሁ ዳበስኩ:: አልበሚ አልነበረም:: ወይም አልበሙ አልነበረም:: የነበረበትን ቦታ በጥፊ መታሁት:: ደሚ ለትንሽ ጊዜ ፈሳ:: ታክሲ ውስጥ ስገባ የማርስ ሆቴል በር ፊት ለፊቴ ተከፍቶ አያለሁ:: የእዝራንና የቁሊታምነት ዘመኔን አስታወስኩ:: የጠጣሁት ወፍራም ፓፓያ:: ወይም ከእሱ ጋር እቃ ለመግዛት ስንሄድ ሁልጊዜ የምጠጣው የቡና በወተት ጠረን:: የዳቦና የኬክ ጠረን::

ታክሲው ተነስቶ ሲሄድ ልክ እንደማገኘው ሁሉ አልበሙ የነበረበትን ቦታ ዳበስኩ::

•

•

•

የረጺ ተራራ አረንጓዴ ዝንቦች (ዝንቦች ለምን አረንጓዎዴ ይሆናሉ?) የወረሩት ያበጠ ኩበት:: ፈቀቅ ብዬ እንደ ሳም ተቀምጬአለሁ:: ቂጤማ ያላጀበው ቀላል ጅረት በታች ያልፋል:: አንድ ክረምት አይቼዋለሁ:: ደንፍቶ ይሰወራል:: አፈር ይዞ ደን ይዞ ምናምን ይዞ......እንደ በረገገ ሁሉ......የተሸከምኩት ሃሳቤ ግን ጉንጉኔ ውስጥ ይቀራል:: ብዙ እንቁራሪት አለ:: እሱን አይቼአለሁ:: መረሬ መሬቱ በየአቅጣጫው የተተረተረ ነው:: ክረምቱ መጥቶ በዝናቡ እስኪሰፋው:: የጅረቱ ወለልና ግድግዳ አጋም የለውም:: የሚንጠባጠበው ጥቁር አፈርና የጥቁር አፈር ምራቅ ነው:: ወንዙ የደለል መኖሪያ ነው:: አጥንታቸው የወጣ የኮሽም ዛፎች ጥፍራቸው ተንዠርገጎ......የቂጤማ መብቀያ መረሬዎች በክረምትም ነፍስ የላቸው:: በሂላ ጥላ ስር ደቃቃ እንቅልፍ እተኛለሁ:: ያ አፍታ አይበቃኝም:: ቀሚሴ ላይ የጎረምሶች ምኞት፣ የቁሊታቸው እሳት የቀደደውን ጥጥ አያለሁ:: ቃላቸው አይጥመኝም:: እንደበታቸው አያሻፍደኝም:: የዘሬ አያንዘረዘረኝም :: እዚህ ሜዳ ላይ በቀዝቃዛ አክርማ ቀዳዳውን እጠቀማለሁ:: እናቴ በትንሽ ሰውቀቷ በሳልሳ የሰራችልኝ የቀበሌ ፓስታ ጠረኑ አፌ ውስጥ አለ:: መረሬ አፈር በአፌ አስገብቼ ሳስላሳ ብረቷንቱን እምጣለሁ:: እርምሞ በሞላው ገጠር የነጠላ ጅብ እሙኝ ሰማዩን በሐዘን ያምሳል......በመጸው ፈገግታ የደረቁ ቅጠሎች ወደ ረባዳው ይሰደዳሉ:: ጆሮዎቼን ከፍቼ የቅጠሎቹን ሻሻታ እሰማለሁ:: አይኖቼ ውስጥ ጤዛ ይሰበሰባል:: 77 ገፆች አንብቤ ሰባት ቀን እተኛለሁ:: ዘመኔ አሁን ደግ ነው:: ይሄ ይሄ ነው:: ያ ያ ነው:: እሱም እሱ፣ እሷም እሷ ናት:: ማለት እችላለሁ እንደዛ:: ቲያትር የማያውቅ እኔ ቲያትር ወድጄ:: ከአልማዝ የተማርኩት መደፈርን ብቻ ሳይሆን ማስመሰልንም ነው:: ቲያትርን ነው:: እንዲህ የማምታታት ቲያትርን በሳቅ አቅልሎ ማሳለፍን ነው:: አልሚና ያስለጠነችኝ ብላክቦርድ

ዘርግታ አይደለም:: ይህቺ አፍ ጋርዶ፣ ትንሽ ሳቅ ስቆ፣ ተጠጋግቶ ማንሾካሾክ:: ይህቺ አይነት ትንሽ ንቅናቄ ከፕሮፌሰር እንደምትበልጥ አየሁ::

•

•

•

ስለት ያላት የሕይወት ሴንጢ በሆዴ ላይ ከግራ ወደ ቀኝ ቀጭን ስንጥቅ ሰርታ ሄደች:: ወደ ታች ሳይ በቀዳዳው የሚወጣኝ ውሃ የመሰለ ነገር ነው:: ለሁለት ታጥፌ ላስኩት:: ወለላም ነው ሬትም ነው::

•

•

•

ከዕለታት አንድ ቀን ከቤት ስወጣ ወይም ከስድስት ኪሎ ግቢ......እዛ እዛ ስዞር......ከዕለታት አንድ ቀን እንደ እናቴ የቀይ ዳማ ነኝና ዕጌ መስዬው ንብ ቢነድፈኝ......ከዕለታት አንድ ቀን በር ከፍቼ ወጥቼ ኀሕን በልጅነት ፊቴ ቆፍሬ፣ በእግሬም ብዕር፣ በጤዛም ቀለም፣ በሳር ብራና ለሁሉና ለእሱ ያለኝን ፍቅሬን ብፅፍ......ከዕለታት አንድ ቀን አዳልጦ የጣለኝ የሰበታ ጠፍጣፋ ላይ የሐምሌን ሙሉ ዝናብ በማሕፀኔ ግድብ ብሰበስብ......ከዕለታት አንድ ቀን ጥቁር አፈር መሃል በጀርባዬ ተኝቼ በጨረር ጉንጬን ብላም......ድርሰቴም ይሄ ነው:: አለም ፊት ለፊቴ ተከፍታለች:: የምፈልገውን አውቃለሁ:: መድረሻዬን አውቃለሁ:: ግን ወደዛ መሄጃ ኀዳናውን እንጃ:: ስንት አቅጣጫ አለ? ያም ይሄም ያም ያም ያም ኀርባጣ ይመስላል:: ለመሆኑ የሚያዋጣው የቱ ነው?

•

•

•

***የልዋጭ ልዋጭ፣ ሕይወት አሸዋ እኔም አሸዋ:*** ወደ ሰፈሬ ወንዝ ወረድኩ:: በትክክል ወንዝ መባል የለበትም:: ክረምት ቢሆንም የወንዙ አብዛኛው ውሃ ዝናብ የጣለ ዕለት እየቸኮለና እየጮኸ ወደ አዋሽ ወርዷል:: ግራና ቀኝ በድንጋይ የተወረረ ነው:: *ፍቅር እስከመቃብር* የተባለ መፅሃፍ ይገኜ አለሁ:: ሶስተኛ ላነበው ጀምሬዋለሁ:: የገፅ እልባት የሰራሁባቸው ጣቶቼ ደክመዋል:: ከማንበብ ይልቅ እሱን ይገኜ ወንዙን ተከትዬ ላይና ታች ስወጣ ስወርድ ቆየሁ:: ማንበብ ስጀምር ሃሳብ ይይዘኛል:: ማሰብ ስጀምር ማንበብ ያሰኘኛል:: መንከራተቴን አቁሜ ወደ ወንዙ ገባሁና አንድ ንፁህ ጥቁር ድንጋይ ላይ ተቀመጥኩ:: ድንጋዩ እኔን ሊያስተኛ የሚችል ስፋት አለው:: ገና ስቀመጥ ጭኔንና ቂጤን ደስ የሚል ቅዝቃዜ ተሰማኝ:: ፊት ለፊቴ ከወደ ላይ የደፈረሰ ውሃ ያቋረ

ጎድጓዳ አለ:: ላዩ ላይ ተስፋ ያልቆረጡ ደቃቃ በራሪዎች ገበያ ሰርተዋል:: ከውሃው የሚወጣና ወደ ውሃው የሚገባው የቆለጮች ጀርባ የረጠበ ባልጩት ይመስላል:: የተቀመጥኩበትን ድንጋይ የከበበ እንደ ወረቀት የለሰለሰ የአሸዋ ምንጣፍ አለ:: ድንጋዩ ላይ ተንበልብዬና ተንጠራርቼ በአመልካች ጣቴ ነካሁት:: ገና እርጥብ ነው:: ጣቶቼ ያረፉበት ቦታ ክብ ደቂቅ ረባዳ ሆነ:: ከተንበለበልኩበት ተነሳሁና ግራና ቀኝ አየሁ:: ባላ ሊሆን ሞክሮ በአጭሩ የቀረ የደረቀ የዛፍ ቅርንጫፍ አገኘሁ:: ነጠላ ጫማዬን አውልቄ አሸዋው ላይ ቆምኩ:: ልስላሴውና ቅዝቃዜው ሁለመናዬን በእርካታ ወረረኝ:: አይኖቼን ጨፈንኩ:: ለአፍታ ከሰፈሬ እርቄ ከቤቴ እርቄ ሌላ የማላውቀው ቦታ ያለሁ መሰለኝ:: በዛች ጠባብ ሸለቆ ማንም ጆሮ ያለው እስኪሰማ አሁአሁአሁው!!! አልኩ:: ሁለትና ሶስት ማሚቶዎች ተጨዋጨኸው ቀድሞ የነበረው ፀጥታ ተመለሰ:: ከጀርባ ያለው ገደል ወደ እኔ የሚፈስ ይመስላል:: በትኩረቴ ሃያልነት መፍሰሱን እንደሚያቆም ሁሉ አተኮርኩበት......ይሄን አሸዋ ሰጥቶኛል:: ጭራሮዬን ይዤ ወደ መቀመጪያዬ ድንጋይ ልሄድ ስል ሶስት ማዕዘን ስዕል ወይም ትሪያንግል ለስላሳው አሸዋ ውስጥ ሳልኩ:: አሸዋው የሰራሁትን መስመር ተከትሎ ግራና ቀኝ የተከፈተ መሰለኝ:: የጠርዞቹ እርጥበትና ጥቁረት እንደ መከፈት ነው:: በጥቂት ደቂቃዎች እያከታተልኩ ይሄን ሰራሁ::



ይሄን ለምን ሳልኩ?



ከሶስቱ ማዕዘን በር ካሬ አስገባሁ:: ለምን ካሬ ቀጠልኩ??



ልክ ማለቅ የሚገባው ነገር እንዳለ ሁሉ ከትከሻዬ እስከ ጣቶቼ ባለው የገላዬ ቀበሌ፣ በደመ ነፍስ ንቅናቄ መስኮቶችና በር ሳልኩ:: ለምን መስኮቶችና በር ሰራሁ?



መንገድም አበጀሁለት:: መንገዱ ወደ ቤት ብቻ አይወስድም:: ራሱ በር ይሆናል::



እዚህ ስደርስ እንዲህ አልኩ: አራተኛው ቁራጭ የአንደኛው ትዝታ አለው? ማስታወስ ይችላል? ለምሳሌ ትሪያንግሉ የመጀመሪያዋን ትሪያንግል ነጥሎ ያስታውሳታል? እንድስ ናቸው?

ወደ ጠፍጣፋው አለት ሂጄ ተቀምጬ ሳነብ ቆየሁና አካባቢው መቀዝቀዝ ሲጀምር ወደ ቤቴ ሄድኩ:: ካነበብኩት ትዝ የሚለኝ ብዙ ዝርዝር የለም……

አልጋዬ ላይ ጋደም እንዳልኩ እንቅልፍ ጣለኝ:: በሕልሜ ወይም በቅዠቴ አሸዋ ላይ የሳልኩዋትን ቤት ከነመንገዱ አየሁዋት:: የመንገዱ ግራና ቀኝ ሳርና ቄጤማ ነው:: በየቄጤማው መሃል መዓት ትልበራዎች ይንቦገቦጋሉ:: መንገዱን ተከትሎ እስከ ትከሻዬ ከፍታ የሚያምርና የሚያስፈራ አረንጉዋዴ ወጋገን አለ:: ወደ ቤቱ ልገባ እሄዳለሁ:: የማያቋርጥ የማያልቅ መንገድ ነው:: የምደርስ ይመስለኛል ግን አልደርስም:: ቤቱን አየዋለሁ ግን አልደርስም:: ልንካው ያህል ስጠጋው ይሸሸኛል:: እየለከለኩ ባነንኩ:: እማማ ትከሻዬን እየናጠችኝ ነበር……

«ምነው አንቺ ቀን በቀን ቅዠት:: በይ ተነሽ!»

ደክሞኛል:: ልክ ብዙ እንደተጓዝኩ ሁሉ ደክሞኛል:: በጀርባዬ እንደተንጋለልኩ በመስኮት ወደ ውጭ አየሁ:: ምሽት ጀምሯል:: ማር የመሰለች ፀሐይ ረጺ ተራራ ጉንጭ ስትገባ:: ሁሉ ነገር ተፃራሪ አለው ይላሉ:: አይደለ:: ለሰማይ መሬት፣ ለወንድ ሴት፣ ለረዠም አጭር:: የመሳሰለ……

«እራት አለ እማ?!»

……እና ፀሐይ ጠዋት ስትወጣ አውራ ዶሮ ይጮሃል:: ግን አሁን ስትጠልቅ የሚጮህላት ማነው? አውራዶሮዎች ለምን ፀሐይን መሸኚያ ዜማ ይዘው አይመጡም? የሆነ የኩኩሉ ተቃራኒ:: አለ አይደለ ሉኩኩሉ ኩኩሉኩኩ……ስትጠልቅ ሁሉ የሆነ ባዶነት አለው:: ምናልባት ይሄን ባዶነት ለመሙላት ይሆናል ጅቦች የሚጮሁት……

«እማ እርቦኛል!»

«ጥጋበኛ ተጋድማ እርቦኛል ትላለች:: ይልቁን ለቅዠትሽ የአቡነ አረጋዊ ጠበል አለኝ ዛሬ ጠዋት ያመጣሁት:: ሲያዝ:: እሱን ጠጪ:: ጥሩ ነው»

እንደዚህ ፀምታምር ፀሐይ እስከዛሬ አላየሁም……

•

•

•

ማታ ላይ መብራት ጠፍቶ ስንተኛ ከዚህ አሮጌ ቤት ስር አይጦች ይወጣሉ:: ምን እንደሚያደርጉ እንጃ:: እያንዳንዷን እንቅስቃሴአቸውን በመቁጠር ብዛታቸውን ለማወቅ ስሞክር……አንድ አይጥ……ሁለት አይጥ

......ሶስት አይጥ......ይቻላል? መርጦህ ያምረኛል:: በዛ ጨለማ አፌን እስከመጨረሻው ከፍቼ: እዝራ!

•

•

•

አድማስን ለመያዝ አይሮጡም:: አድማስን ለመያዝ ከሮጥን የምንደርሰው የጀመርንበት ነው (አለም እኮ ክብ ናት):: ቆም ብዬ ጥቅስ ተበድሬ እንዲህ ካልኩ አነሰኝ?:

«ፀሐይዋ ጠልቃ ቀኑ እስኪጨልም ድረስ: 'ነገም ሌላ ቀን ነው'» ከአድማስ ባሻገር (በዓሉ ግርማ)

[illegible]

ቀርቦቻቸውን [illegible] ዘመኑ። [illegible] ቀጥር [illegible] ሌር ይሞቁሉ።

[illegible]

# ክፍል ፫

ተርቦቻችን በመኪና ተቀብር ፊር ደምባለ።

## እንቅና መለልታ

| | |
|---|---|
| **እንቅ:** ማገጃ፣ መታገጃ:: |
| **መለልታ:** ቀጥታ እርዝማኔ፣ ውጤታው ያማረ:: |

ተርቦቻችን በመኪ. ተቀር ፈር
ይሞላሉ·

`ሕይወት እንደ ሸንኮራ አገዳ` ነው ማን አለ?
ተክሉ አሳድጎ ከሕይወቱ ወጣ ገባ ያስተያየ?
…………ስንዋደድ በመረቅ የሞላ የሸንኮራው መለሉታ ነው።
ከዕለታት አንድ ቀን አገዳው ይዘጋል (በእንጓ)።

…………የሕይወታችን ሽንኮራ አገዳ በግል ፍላጎታችን ብቻ በቀለ?…………ከነጠላ ልብ በፈሰሰ ወለላ ብቻ ጠጥቶ ለመለመ?…………በራሳችን ትክሳት ብቻ በሰለ?

............ዋሽንግተን እንጱ በረደኝ ሲል እንጦጦ ጋራ ስር የጋቢ ገበያ ይሞቃል፡፡ አዋሳ የፀሐይ እሳት ሲነድ......................አየር ጤና በሐምሌ ዝናብ ድርቆሽ ይሰጣል....................................

..........አንደበታችን በደስታ ወለላ ይሞላል (መለልታ)

..............በድብርት ጥቁር እንዝ ይቆለፋል......(እንዝ)

የሁላችንም ሌሊት ተቆፍሮ ቢታይ የምናልመው በእርግጥ አፈር ነው

የምንቸትና የሕይወት ቅንሽ የለውም፡፡

# ስለ እንጀራ ገለጣ፡ መግቢያ

እንጀራ ገለጣ ጥንት ይደረግ እንደነበረ አጥብቀው የሚወሸከቱ አሉ:: ማስረጃቸው ወሬ ብቻ ነው:: ትክክሉን እንዳወቁ ሁሉ በእምነትና በድፍረት ለመመስከር ሲዳዳቸውና አለቅጥ ሲሙዋዘዙ 'እንዴ?' እንላለን:: ግን መቼ ነው ቀጣፊን 'እንዴ?' ወደ ሕሊናው የመለሰው? ከአሰስ ገሰሱ ረገብ ከጥርጣሬው ጠበቅ አድርገን ስለ ጉዳዩ ጥቂት እናውጋ::

ነገን በሚፈራ አለም እንዲህ አይነት የጥንቆላ ወይም የአጉል እምልኮ ብልጥነቶች ያለብዙ ውዝግብ በራሳቸው በተታላዮች ቦታ ይሰጣቸዋል:: እንጀራ ገለጣ በአፈ ታሪክ እንደሚወራው ከሆነ ጥንት ሽምብራ ኩሬ ዛሬ ሞጆ የተባለው አካባቢ እንደተጀመረ ይነገራል:: የማይጨበጥ ነገርን የሚጨበጥ ቦታ መስጠት፣ ባይኖርም እንዳለ ሁሉ ኮስተር ብሎ ማውራት፣ ቢረባም ባይረባም ለሃሳቡ ተሰሚነት ያስጠዋል ይባላል:: ለዚህ ደንቆሮ ትውፊት በቂላቂልነት ከልባቸው ትንሽ ቦታ ቆርሰው የመሩ ከተሜዎች አንድ ሰሞን ቁምነገር እንዳገኙ ሁሉ ሲያወሩለትና፣ ማውራት ብቻ ሳይሆን፣ አልፈው ተርፈውም ***መቼም ካልጠቀመ አይፈለሰፍ*** በሚል የሰነፍ ዘይቤ የዋሃንን ስለ ጉዳዩ እንዳይረዱ አግተዋቸዋል:: ጠላታችን ሰይጣን ሳይሆን ወሬ እንደሆነ ሳይታለም የተፈታ ነው:: ደህና ቢታለምም የሚፈታው በወሬ ነው:: ሕልሙን አሳምረን ፈታነው ብንልም ያም ፍቺ ወሬ ነው:: የቡና አተላው ከተነበበ (tasseomancy)፣ ሆድቃ ከተነበበ (extispicy)፣ እሳት ከተነበበ (pyromancy)፣ የሚቀልጥ ሻማ (ceromancy) ከተነበበና ትንበያው ሁሉ ከታመነ፣ ወጥና እንጀራስ በመረቃቸው (mereqmancy እንበለውና በእንግሊዘኛ) 'ለምን ይቅርባቸው?' ብለው ያሉ ብልጦች የሰሯት ጥበብ ናት:: አንድን ነገር ግን በጭፍኑ ካዱ ከማለት ቢያንስ ማጃጃያው ምን እንደሚመስል አጠር አድርጎ ማሳየት ተገቢ መስሎኝ ይሄን አቅርቤአለሁ:: እምነት ሳይውጣችሁ ተጫወቱበት......

**መረቅ ንባብ(እንጀራ መግለጥ)**

*መረቅና እንጀራን በመጠቀም ጥንቆላ ለማኪያሄድ(እንደ ብዙዎቹ ሰገሎች አሰራር) ከዚህ በታች ያሉ ነገሮች ያስፈልጋሉ:*

*አንደኛ መረቁ የበዛ (ባለቅባት) ቀይ ወጥ*

*ሁለተኛ ንፁሕ ነጭ ሳህን*

*ሦስተኛ የተረጋጋ አእምሮ*

**አሰራር:**

አነባበቡ ሁለት ዘዴዎች አሉት ይላሉ ገላጮያን(ገላጮች)::

አንደኛው *የቅርብ ንባብ* ሲባል ሁለተኛው *የርቀት ንባብ* ይባላል:: የሚጠነቆልለት ሰው እንጀራውን ሳህኑ ላይ ያነጥፋል:: እንጀራውም ይሁን ወጡ ከልቡ በሚያቀርባቸው ሰዎች ቢጋገርና ቢወጠወጥ የበለጠ ይሰምራል:: በትክክለኛ አሰራር የሚጠነቆልለት ሰው 'አዋቂው' ጋ ሲሄድ የራሱን እንጀራና ቀይ መረቃም የስጋ ወጥ ይዞ (መረቁ አጉል ዠራራ መሆን የለበትም) ቢሄድ የተሻለ ነው:: (ይሄን አይነት ወጥ መስራት ብዙ ጊዜ ስለማይሳካ፣ ይሄንንም ችግር የተገነዘቡ ሁለት ወይዘሮዎች በትዕዛዝ እንደሚሰሩ ማሳወቅ ግድ ይሆንብኛል:: አንደኛዋ ስድስት ኪሎ አካባቢ ከሐውልቱ ጀርባ የምትኖርና የባህል ምግብ የምትሸጥ ስትሆን፣ ሁለተኛዋ ደሞ ራስ ደስታ ሆስፒታል አካባቢ የባህል መድሐኒት በመሸጥ የምትተዳደር ናት) ወጡ እንጀራው ላይ ከፈሰሰ በሁዋላ ቡና ይፈላል:: ቡናው ተጠጥቶና እንጀራው ተበልቶ ሲያበቃ ሳህኑ ላይ በአይኖቹ ስርጎ ሳህኑ ላይ የሚታየው በበላተኛው በከፊል የተጠረገው መረቅ ይነበባል:: ይሄ አሰራር *የቅርብ ንባብ* ይባላል:: ይሄኛው የበለጠ የተስተካከለ ትርጉዋሜ ይሰጣል:: ሁለተኛው *የእርቀት ንባብ* ይባላል:: በዚህ ስልት የሚጠነቆልለት ሰው የተገኘውን እንጀራና ወጥ ጨርሶ ይበላና ሳህኑ ላይ የቀረው መረቅ ይነበባል:: ሁለተኛው ፈጣን፣ ቸልታ ያለበትና ቡና የለሽ ነው::

በሁለቱም መንገድ ቢሆን መረቅ ማንበቡ ከተጠናቀቀ በሁዋላ ንባቡን ካልወደደው (መጥፎ የትንቢት ይዘት ካለው) የበላበትን ሳህን ቢያጥበው ይደርስበት የነበረው ትንቢት ይከሽፋል ይባላል:: ንባቡ ለተገለጠለት ሰው ሲነገር *ትርጉም ማፍሰስ* ወይም *ትርጉም መጨለፍ* ይባላል::

**ለመሆኑ ምን ምንና እንዴትስ ይነበባል?**

አንደኛ መረቁ ሳህኑ ላይ የፈሰሰበት ቦታ ስፋት

ሁለተኛ መረቁ በፈሰሰበት ክልል ውስጥ ምን ያህል የሳህኑ ቦታ መረቁ በእንጀራ የተጠረገና ያልተጠረገ መሆኑ

ሦስተኛ የመረቁ ድምቀትና አሰረጫጨት

አራተኛ መረት ያልነካውና የነካው ቦታ ስፋትና ጥበት

አምስተኛ የመረቁ ከፊኛ ቅርፅ ልሙጥ ነው ወይስ ችርችፍ የበዛው እንደሆነ መመልከት

ከነዚህ ሁሉ በተጨማሪ መረቅ አሩት ሲገልፅ የተለያዩ ዓይነት ቃላቶችና ጠልሰሞች የመፍታት አገልግሎት ላይ ይውላሉ:: ጠልሰሞቹ ከገለጣ ጋር የተያያዙ ብቻ ናቸው:: በመጀመሪያ ብዙ ጊዜ መጠቀሚያ የሆኑትን ቃላቶች ልጥቀስ::

**ደመቁ:** ቀዩ(በርበሬው የደመቀ ወጥ)

**ልሻዎ:** ለስለስ ያለ ወጥ

ርዛ፡ ብዙ ወጥ የሌለውና መተርጎም የሚከብድ ወጥ

ርግ፡ ወጥ የበዛበት ትርጎማ

ኾራሮ፡ ውሃው የበዛ በርበሬው ያነሰ በዚህ ምክንያት ማንበብ የሚከብድ

ሙጥ፡ በላተኛው ባለማተኮሩ ሲበዛ በእንጀራ የተጠረገ መረቅ (ጠቅላላ መጠረግ የለበትም)

ወይባ፡ (የወጥ ሌላ ስሙ) ማወየቢያ (ማቅለሚያ)

ሐመር፡ ምግብ የሚቀርብበት ትሪ

ሕመት፡ ለመጠንቆያ የተመረጠው ወጥ ከተሰራበት የሚነድ እንጨት ወይም ከሰል የሚቀር አመድ፡፡ የሚጠነቆልለት ሰው ግንባር ላይ በመስቀልና በጨረቃ መልክ ይሳላል 'ንባብ አበርታ' እየተባለ፡፡ ይኼ ከንባቡ ቀድሞ የሚደረግ ነው፡፡

ጣቢታ፡ ዓይናማ እንጀራ

እንሶስላ፡ እጅ ላይ የሚቀረው(በላተኛው እጅ ላይ የሚቀረው መረቅ)

ወጌመት፡ ባዶ(ወጥ ያልነካው ቦታ)

ለምሳሌ እንጀራና ወጡ በአንድ ሆነው የሚሰፍሩበትና እየተነሱ የሚበሉበት እቃ ምን እንኳን ነጭ የቆርቆሮ ወይም የመስታወት ሳህን ቢሆን *ሳር ምድር* ይባላል፡፡ አባባሉ የመጣው የብረትና የቆርቆሮ መብያዎች አገሪቷ ውስጥ ከመግባታቸው በፊት ከሳር በተሰሩ መብያዎች ሰዎች ይመገቡ ስለ ነበር ነው፡፡

በትውፊት እንዲህ ይባላል:

**ጎራዳ ብለሽኝ፣ ድካካ ብለሽኝ**
**ጠዋት ማታ አሳቅለሽ አጣጥለሽኛል፣**
**የማይቀር የማይቀር የማይቀር ተነግሯል**
**ሳር ምድሬን አየሁት እንቺን እቦልኛል፡፡**

በአጠቃላይ የተበላበት ሐመር ታይቶ የሚሰጥ የችኩል ትርጉም አለ፡፡ ***ጅምሉ*** ይባላል፡፡ ይኼ የደካማ ትርጉም ስራ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ዝርዝር ስለሚጎለው የመታመኑ ነገር ጠባብ ነው፡፡ ጅምሉ የእሩቅ ትርጉም አንዱ መልክ ነው፡፡

በተጨማሪም በቀጥታ ከትርጉም ጋር የተያያዙና ለፍቺ የሚረዱ መረቁ በበላተኛ ሲጠረግ የሚሰሩ ቅርፆች ወይም ጠልሰሞች ይኖራሉ፡፡ እነዚህም ከላይኛው ነጥቦች ጋር በመሆን ለትርጉም ይስለፋሉ፡፡

**ነጩ ሳህን ላይ የሚቀሩት የመረቅ ቅርፆች (ጠልሰሞች) ስማቸውና ትርጉማቸው ከዚህ የሚከተለው ነው**

*ጥንጌ (ክብ)*: ሕያው ነህ፡ አትሞትም:: ዘር ይኖርሃል ወይም መልካም ስራ ሰርተህ ታልፋለህ:: ያልገጠመ ክብ ከሆነ ሃሳብህ ግብ አይደርስም፣ ያለመግጠሙ ስፋትና ጥበት ይሄን ይጠቁማል::



*እመጫቴ(እመጫት የመሰለ ቅርፅ ያለው የተጠረገ ዳና)*: አላማህ ሁልጊዜ ወደ ላይ ነው:: ጠፍጣፋነቱ ከገነነ ዕቅድህ ግብ አይደርስም፣ ባትለፋ ጥሩ ነው:: ምቀኞች ባያቆሙህም በልቡናህ ተስፋ መቁረጥ አለ:: ሾል ካለ ልፋቱ ይበዛብሃል እንጂ ይሳካልሃል::



*ደጋኔ(ቅንፍ የመሰለ ጠረጋ የተሰራበት ዳና)*: ቀስ እያልክ ተስፋ እየቆረጥክ ነው:: ቀና በል:: ነቃ በል::

አራት አይነቶች አሉ:: እነዚህ የየራሳቸው ትርጉም አላቸው:: ('አዋቂ' ያማክሩ)

ቆሬ ደጋኔና(ወደ ላይ የተከፈተ)



ደረት ደጋኔ(ወደ ታች የተከፈተ)



አፍ ደጋኔ(በምስራቅ በኩል የተከፈተ)



ጨንበር ደጋኔ(በምዕራብ በኩል የተከፈተ)::



መስመር፦ ያገኙትን መርቆ መኖር:: ቀላል ጎዳና ነው:: ተመችቶሃል



*ጭረት(ወደ ግራ/ቀኝ/ላይና ታች/ አግድም የተሰራ የጠረጋ ቅርፅ)*:

*ክንፌ(የክንፍ ቅርፅ ያለው የመረት ዳና)*: ቤትህ ዳመናዎች ላይ ነው:: መሬት ለቀህ ትኖራለህ:: አለምን የምታየው ከሰማይ ነው:: ሃሳበ ትልቅ ነህ:: አስተዳደር አይሆንህም:: ግጥም መግጠም ቤትህ ነው:: ዘፋኝም መሆን ትችላለህ:: በተለምዶ ክንፌ ከርፋፌ ይባላል:: ይሄ ሁለት ክፍሎች አሉት፡ *ሰጣጢ እና ምላሶ*

መልከመልካም ብዬ ነካክቼ ሞላ
የማይረባ ነገር አደረገኝላ::
አንድ አመት ባገባው ከእናቱ ጠልፌ
በሮ ተሰወረ ክንፍዬ ከርፋፌ::

('ክንፉ' የተባለ ወጣት የወደደች ሴት በመቆጨት የገጠመችው)




*ሰንድል (የጫማ ቅርፅ የሚታይበት ዳና)*: መንገድ ታበዛለህ:: ሴሰኛ ነህ:: ቋሚ መኖርያ የለህም:: እንደዘላን ኖረህ እንደ ዘላን ትሞታለህ::



*ፈንጣጣ(የወጥ ነጠብጣብ የበዛበት ዳና)*: ልጅ ትወልዳለህ:: ፈንጣጣዎቹ ከተቀራረቡ የምትወልደው ከአንድ ሴት ነው:: ከተራራቁ ከአንድ በላይ ሴቶች የልጆችህ እናቶች ናቸው:: ሴት ከሆነችም ልጆቿን የምትወልደው ከተለያዩ ወንዶች ነው:: ወይም መከራህ ይበዛል:: በመከራህ ብዛት ልብህ ቂመኛ ሆኗል::

ጨዋ ናት እያልኩኝ እላት የነበረ
በተክሊል ላገባት አስብ የነበረ
ፈንጣጣ ወጣባት የተደራረበ



*ነጭ(ሳር ምድሩ በደንብ የሚታይ ዳና)*: (ጠርጎ የበላ) ስጋህን ትወዳለህ:: ቢረባም ባይረባም መኖር ትወዳለህ:: አንዲት የአንተን ደስታ ለአላማና ለወዳጅ አሳልፈህ አትሰጥም::

*ቀይ(ብዙ ወጥ ሳር ምድር ላይ የቀረበት ዳና)*: ለሰው ይታደጋል:: ተካፍሎ በይ ነው::


*ነጭና ቀይ(ሻኜ/ መረቅና ሳር ምድር አቻ ለአቻ የሚታይበት ዳና)*: የሚፈልገውንና የማይፈልገውን አያውቅም፣ ወረተኛ ነው:: እዛና እዚህ ይረግጣል

*እምቢልታ(ይሄን የመሰለ ዳና)*: መልካም ወሬ ነጋሪ



*ጎጂ ት:(ጎጆ የመሰለ ዳና)* ቤቱን ወዳጅ፣ ትዳሩን የሚወድ


ጎምሻሏ ጎምለል የሚል ያለ ትራሷ ወድጄ
ከሌላ ላሸሸው ላገባው ፈርጄ
ተከዬው ነበረ እራዳ እደጃፌ
መቼ ገብቶኝ ጎጂት አመለጠኝ ካፌ



*አረንዛ:(የእንጀራ ፍርፋሪ የቀረበት ዳና)*: ልበ ሸካራ:: እንቅፋት መሆን የሚወድ

**ወይ ጥላ ወይ ውደድ፣ ወይ ውደድ ወይ ጥላ**
**አረንዛ መሆን ነው አለበለዛማ**

*እሻራ (የመመሳለስ ዳና)*: ብኩን ትሆናለህ ከዛ ይቀናሃል:: ከዛ ብኩን ትሆናለህ:: ከዛ ይቀናሃል:: አካሄድህ ሕይወትህ እንዲህ ነው:: ብትሄድም ይመስልሃል እንጂ እዛው ነህ::



ምልክቶቹ ወይም ጠልሰሞቹ በቁጥር ሰባ ይደርሳሉ:: ንዑስ ክፍሎችና የንዑስ ንዑስ ክፍሎችም አሉት:: አንባቢ ይሄን በሚመለከት ወደ ደብረዘይት ወይም ሞጆ ቢወርድና ከአዋቂ ቢጠይቅ የበለጠ ዕውቀቱ ይኖረዋል ተብሎ ይገመታል::

—— // ——

## መውጫ

የዚህ ልብወለድ አጨራረስ ሁለት የተረክ ዘዬዎች አጣምሮ ይይዛል:: አንደኛው የትውፊት ተረክ ስልት ሲሆን ሁለተኛው ሕፀናዊነት ነው:: በባህላዊው ተረት ብዙ ጊዜ ትረካው ሲጠናቀቅ የትረካውን መልዕክት አጠቃሎ በጥቂት መስመሮች ወይም በምሳሌዎች የማቅረብ ልማድ አለ:: መሰረታዊ አገልግሎቱ ማስተማር ስለሆነ::

አራቱ ምዕራፎች በሁለት ጉች ጉች (ክፍሎች) የተከፈሉ ናቸው:: የነዚህን ግኑኝነት ለመግለፅ ከየታሪኮቹ ሂደት ቃላት 'ፈሰው' ይወርዱና (እንደ መረቅ) የመጨረሻውን የአንጓና መለልታ ምዕራፍ ይሆናሉ:: ይሄ ምዕራፍ በተረትና ምሳሌዎች አጨራረስ ላይ የሚቀመጡትን ምክሮች ይመስላል፣ ምክር ግን አይደለም:: ሕፀናዊነት ያሳያል እንጂ አይሰብክም::

### ስለ ጠልሰሙ

በሕፀናዊነት አመለካከት በሰው ልጆች መሃል ያለው የግኑኝነት መስመር ቀጥተኛ ብቻ ሳይሆን በአብዛኛው በግልፅም ይሁን በሕቡዕ መረባዊ መሆኑን ማንሳት ነው:: የሕፀናዊነት ጎኑ ደሞ እንዲህ ነው: እንደ መረቅ ወይም ወለላ ተጨምቀው የሚወጡት ቃላት የሚፈሱት በድርሳኑ አይኖች ነው:: ከሁሉም ክፍሎች የሚረግፉ ናቸው:: ቃሎቹ በመረቅ ወይም በወለላ ሊመሰሉ ይችላሉ:: ግራጫ ቀለም ባለው የሪጋ ምልክትነት ፈሰሳቸው ይታያል:: እነዚህ ምዕራፎቹን የሚያገናኙ ፈሰሶች ጠልሰም ሆነው የመጨረሻው ምዕራፍ መግቢያ ወይም የመፅሐፉ ሽፋን ላይ የሚታየውን ምስል ይሰጣሉ:: ደራሲው ይሄን ጠልሰም ለመስሪያ የተጠቀመባቸው ቃላቶች አንጓ፣ መለልታና መረቅ የተባሉትን ብቻ ነው:: ስዕሉ 'መረቅ' የተባለውን ይሄን ልብወለድ 'ወካይ' ነው::

የሁለንተናው(የጠቅላላ መፅሐፉ ጠልሰም አሰራር እንዲህ ነው: የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ያሉ ቃሎች በሙሉ ለእያንዳንዳቸው ቁጥር ይሰጣቸዋል:: መፅሐፉ ዋና ገላ ውስጥ ያሉበት ገፅ ይፈለጋል:: ሁለት ዛቢያዎች ግራና ቀኝ አራርቀን እንስላለን:: አንዱ ዛቢያ 'ሀ' ፣ ሁለተኛው 'ለ' ነው:: በ 'ሀ' ዛቢያ ወደ ላይ የቃሎቹ ተራ ቁጥር ከዝቅተኛው ወደ ከፍተኛው ይፃፉሉ፣ በ 'ለ' ዛቢያ እንዲሁ ከዜሮ እስከ 595 (የመፅሐፉ ገፅ ብዛት) ይፃፉል:: ለቃሉ የገፅ አሴት ይፈለግና ቁጥሮቹ የሚገናኙበት ቦታ የነጥብ ምልክት ይደረጋል:: አንዱ ቃል ያለባቸው ገፆች በሙሉ ከተነጠቡ በሁዋላ በመስመር ይገናኛሉ:: ይሄ መስመር ካሉት የግኑኝነት መስመሮች አንዱ ነው:: ከዚህ

ድርስት በስተመጨረሻ ሁሉም የቃሎቹ እሴት ተነጥበው ይያያዙና ጠልሰም ይሰራሉ::


ከተፈለገም ከእያንዳንዱ መስመር ሁለት ጥንድ እሴቶች በመውሰድ የመስመር ኢኩዌሽን በመስራት 'የተጠና ሕፅን' ማቀናበር ወይም መቀመር ይቻላል:: 'የተጠና ሕፅን' ማለት የኢኮሺኑ መስመርና የእውነታው መስመር የሚዛነቁበትን ባዶ እሴት ወይም ዋጋ በሚፈልጉት አይነት ቃላት ድርሰቱ ውስጥ ሞልቶ የተስተካከለ መስመር ማምጣት ማለት ነው::

## የጉርሻ መስመሮች

በአንዳንድ ገፆች ላይ ያሉ በደማቅ እንደ ግጥም ወደ ታች የተሰተሩ ግን ግጥም ያልሆኑ አንድና ሁለት ወይም ከዛ በላይ መስመሮች አሉ:: እነዚህ በሙሉ እንደ ጉርሻ የሚቆጠሩ ናቸው:: ቅርጻቸውም ወደዛ የቀረበ ነው:: ባለታሪኩ ለአንባቢው በቀጥታ የሚናገራቸው ስለሆኑ ጉርሻ እንደማቅረብ/ማጉረስ ይቆጠራሉ:: ጉርሻ ተሻጋሪ ነው (ከእቴሜቴ ሎሚሽታ ልብወለድ: 2002)::

የማንበብ ሂደቱ እንጀራውን የመዘርጋት፣ እንጀራው ላይ ወጥ/መረቅ የማፍሰስ፣ በሂደቱም መጎራረስ፣ በስተመጨረሻም የቀረውን አንድ ገፅ የመረቅ ቅሬት ጠርጎ መብላትን ያካትታል:: 'የመጽሐፍ ቀበኛ' አለነገር አላሉም አበው::

— // —



ፎቶ በሙሉቀን አስራት

አዳም የድህረ ዘመናዊ ልብወለድ መገለጫዎችን በስፋት በመጠቀም፣ በእውነታ፣ በህይወት እና በልብወለድ መካከል ያሉ ጉዳዮችን በሂስ ለጥያቄ በማቅረብ በታሪክ እና በእውቀት መስክ አይነኬ የሆኑትን ጉዳዮች እንዲነኩ፣ የተሰቀሉ እንዲወርዱ እና እንዲጠየቁ፣ ከሌላ አቅጣጫ እንዲታዩ፣ በዚህ ውስጥም ማህበራዊ ህፀፆች ጎልተው እንዲወጡ በማድረግ ረገድ አዲስ የልብወለድ አፃፃፍ ፈር ቀዷል፡፡ በኢትዮጵያ ስነፅሁፍ ታሪክም ሌላ ደማቅ አሻራ ጥሏል ወይም አኑሯል ማለት እችላለሁ፡፡

ሀይሉ ወንድሙ፣ ሐምሌ 9፣ 2003፣ በሃገር ፍቅር ቴአትር በተደረገው ውይይት የተወሰደ

ርኆቦት አታሚዎች

ዋጋ፡ 250 (ሁለት መቶ አምሳ ብር ብቻ)